መስከረም

STANFORD LIBRARIES
HOOVER INSTITUTION
1985

- ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት
  - የወል የእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ መሣሪያ
- ህጋዊ ምርምሮችና አመለካከቶች
- በቀይ ካባ ሽፋን የሚከናወን ፀረ-ማርክሲስት ደባ
  - የመንግሊ. ሪቪውና የበረከተአብ ፀረ-ኢትዮጵያ አብዮት ኅብረት
- ድንበርዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና የኋላቀር አገሮች ሁኔታ
- ባህልና አብዮታችን

DT
371
M469
1975

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት
ቅጽ 3 ቁጥር 10
መስከረም 1975

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem
no. 10
ETa844KP
9

መስከረም

ቅጽ 3 ቁጥር 10
መስከረም 1975

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገጽ 3
- ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF)—የወል የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ መሣሪያ 11
  —ለገሠ ለማ (ዶ/ር)
- ሕጋዊ ምርምርችና አመለካከቶች ሕግና ዕድገት (ክፍል ፩) 35
  —ለማ ጉተማ
- በቀይ ካባ ሽፋን የሚከናወን ፀረ ማርክሲስት ደባ የመንዝሊ ሪቪውና የበረከተአብ ሀብተሥላሴ ፀረ ኢትዮጵያ አብዮት ኅብረት 48
  —አምኃ መለሰ
- ድኅበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና (ባንኮች) የኋላቀር አገሮች ሁኔታ 64
  —ላቀው ዓለሙ (ዶ/ር)
- ባህልና አብዮታችን.... 80
  —አያልነህ ሙላት
- በሶሻሊስት አገሮች ላይ የሚካሔድ የኢምፔሪያሊዝም ደባ —አንዳንድ ገጽታዎች 90
  —ጳውሎስ ደኪን

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቍጥር — 80001
የስልክ ቍጥር — 113000

Digitized by Google

ያለ አብዮቲዊ ንድፈ ሃሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም !

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የርዕዮተዓለም ሚና

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት አድሃሪውንና አስከፊውን የፊውዳል ሥርዓት በማስወገድ በእኩልነትና በወል ብልፅግና ላይ የተመሠረተ አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት ሁኔታዎችን የማመቻቸትና መሠረት የመጣል ሂደቱን ከጀመረ እነሆ ዛሬ ስምንተኛውን ዓመት ይዞ ይገኛል። ዛሬ ከደረስንበት የእድገት ምዕራፍ ወደኋላ መለስ ብለን የሕዝባዊ አብዮት የተግባር መመሪያ ከሆነው የወዝአደሩ ርዕዮተዓለም አንጻር ከስምንት ዓመት በፊት የነበርንበትን፣ በዚህ አብዮታዊ ወቀት የተካሄዱትን ውስብስብ ትግሎችና የተመዘገቡትን ድሎች ስንገመግምና ከሌሎቹም የሶሻሊስት አገሮች ልምድ ጋር ስናገናዝበው፣ የማሌን ሳይንስ ለሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ማስታጠቅ የግንባታውን ተግባር በድል ለመደምደም አማራጭ የሌለው ግደታ ሆኖ እናገኘዋለን።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ርዕዮተዓለም የመደቦች ፍላጐት ወይም ጥቅም ማንፀባረቂያ፣ ማራመጃና መግለጫ ነው። በዝባዥና ጨቋኝ መደቦች ርዕዮተዓለማቸውን የሚያንፀባርቁት ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ በላዕላይ መዋቅር ዘርፎችና በንቃተ ህሊና ፈርጆች በተለይም በሃይማኖት በፍልስፍና በፖለቲካ ወዘተ...አማካይነት ነው። በዝባዥ መደቦች ርዕዮተዓለማቸውን የሚያራምዱት ገዥነትና ተገዥነት፣ የበላይነትና የበታችነት፣ ጌትነትና ድህነት ወዘተ...ከላይ ከፈጣሪ ወይም ከእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው፤ ሁሉም በአርባ ቀን ዕድሉ ይመራል፤ ከዚህ ውጭ ምንም ነገር ለማድረግ አይቻልም ወዘተ ... በማለት የበዝባዛውንና የጭቁናውን ሥርዓት ዘላለማዊነት ለማሳመን ይጥራሉ። በአንጻሩ የማሌ ሳይንስ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ማናቸውም የላዕላይ መዋቅር ዘርፍ የመደብ ባህሪይ ያለውና ለዚሁ የሚያገለግል መሆኑን ተንትኖ ያስረዳል። ምዝበርችና ጭቁናች በአጠቃላይ የኅብረተሰብን የእድገት ህግጋት ምንነትና አሠራር የሚተነትነውንና የሚያብራራውን፣ ሰው በሰው የማይበዘበዝበትንና የማይጨቆንበትን፣ በጋራ ብልፅግና ላይ የተገነባውን፣ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነበት የሶሻሊስትና የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የሚገነባበትን ታክቲክና ስትራተጂ የሚያስጨብጣቸውን የወዝአደሩን ርዕዮተዓለም በይፋ አውጀው ጠንቅቀው በማጥናት የተግባራቸው መመሪያ ያደርጉታል።

ከዚህ አጠቃላይ አባባል ወደ ኢትዮጵያ ሁኔታ ስንመለስ አብዮቱ በየካቲት 1966 ሲፈነዳ የሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ደረጃ በአጠቃላይ አነጋገር ለውጥን በመፈለግ ደረጃ ላይ የተወሰነ ነበር ለማለት ይቻላል። እርግጥ በወቀቱ የነበረው የንቃተ ህሊና ደረጃ የፊውዳሉን አድሃሪና አስከፊ ሥርዓት በማስወገድ ሥር ነቀል ለውጥን በማስገኘት ላይ ያተኰረ ቢሆንም፣ እንዴት በምን ወይም በማን አመራር ይህ ሊረጋገጥ እንደሚችል ግን ግልፅ የሆነ አመለካከት አልነበረውም፤ ሊኖረውም አይችልም ነበር። ምክንያቱም በማናቸውም የሕዝባዊ ትግሎች ታሪክ ውስጥ የጭቁን

Digitized by Google

ሕዝቦችና መደቦች የንቃተ ህሊና ደረጃ ለለአንድ መደብ፣ ለለ መደብ የፖለቲካ ድር
ጅት ወይም ፓርቲ የርዕዮተዓለም እና የፖለቲካ አመራር እንደዚሁ ጭቆናና ብዝበዛ
ስለደረሰባቸው ብቻ የሚዳብርና አቅጣጫውን በሚገባ የሚተልም ሊሆን አይችልም።

በኢትዮጵያ የየካቲቱ ሕዝባዊ አብዮት ሰፊው ሕዝብ የፊውዳሉ ሥርዓት ባደረ
ሰበት ጭቆና፣ ብዝበዛ፣ ረሐብ፣ ችግር፣ ገፍና በደል ተንገፍገፎ በገብታዊነት የተቀ
ጣጠለና የተቀሰቀሰ ቢሆንም፣ ከመጀመሪያውም በይዘቱ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ቢሮክራ
ቲክ ካፒታሊስትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ነበር። ይሁንና በአድሃሪው የፊውዳል ሥርዓት
ውስጥ የተለያዩ መደቦች በፖለቲካ ሊደራጁ የሚችሉበት ሁኔታ ጨርሶ ስለአልነበረ፣
አብዮቱ ሲፈነዳ አመራር ሊሰጥ የሚችል የማሌ ድርጅት አልነበረም። በመሆኑም
ከመለዮ ለባሹ የተውጣጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይኸን ጉድለት
በማስወገድ የሕዝባዊውን አብዮት አመራር ለመስጠት ታሪካዊ ሃላፊነት ተቀበለ ።
የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግም የዘውድ አገዛዙን በመገርሰስ የመንግሥት
ሥልጣን ከያዘበት ከመስከረም ወር 1967 ጀምር የኢትዮጵያ አብዮት ከገብታዊነት
ወደ ተደራጀ አመራር የሚያደርገውን የትግል ሂደት ተያያዘው ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የኢትዮጵያ አብዮት መመሪያ ሶሻሊዝም
መሆኑን ካበሰረበት ጊዜ ጀምር ለአብዮቱ የወደፊት ገስጋሴና ገብ መምታት ዋንኛ
መሣሪያ የሆነውን የማሌ ርዕዮተዓለም በሕዝቡ ውስጥ እንዲሰራጭ ወሳኝና ተከታ
ታይ እርምጃዎችን ወስዷል። በቀድሞው የአድሃሪ ሥርዓት ወደ አገር ውስጥ እንዳይ
ገቡ ታግደውና ተከልክለው የነበሩ የማሌ መጻሕፍት በብዛት እንዲገቡና እንዲነበቡ፣
ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችም እንዲተረጐሙ፣ የሶሻሊዝም ምንነትና ፅንሰሃሳብ በሕዝብ
መገናኛ ዘደዎች ለሰፊው ሕዝብ እንዲብራራ ወዘተ ... በማድረግ የአዲሱ ኅብረተ
ሰብ መገንቢያ የሆነው የማሌ ርዕዮተዓለም በሰፊው እንዲሠራጭ አመች ሁኔታን
ፈጥሯል። የማሌ ርእዮተዓለም የማርክሲስቶች የዓላማ አንድነት መሠረት፣ የሕዝባዊ
አብዮት የአሸናፊነት ምንጭ እንደመሆኑ፣ የጊ.ወ.አ.ደርግ በወቅቱ በሀገር ውስጥና
በውጭ አገሮች አድሃሪውን ሥርዓት ይታገሉ የነበሩ አብዮታውያንን በማሰባሰብና
በአብዮቱ ጐን በማሰለፍ፣ ርዕዮተዓለሙን በሚገባ ለማሰራጨትና ሰፊውን ሕዝብ
በየደረጃው ለማደራጀት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትንና የየካቲት 66
የፖለቲካ ት/ቤትን አቋቋመ። እነዚህ ተቋሞች ሰፊውን ሕዝብ ሊያነቁና ሊያደራጁ
የሚችሉ ካድሬዎችን በማሰልጠንና በማሰማራት፣ የማሌን ርዕዮተዓለም በማሰራጨ
ትና የአድህርት ሃይሎችን ርእዮተዓለም በመዋጋት፣ በአጠቃላይ አብዮቱ ወደፊት
እንዲገፋ በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የማሌን ርዕዮተዓለም በስፋት ለማሠራጨት
ሰፊውንም ሕዝብ በየዘርፉና በየደረጃው የማደራጀቱና የማሰባሰቡ ተግባር ውስብስ
ብና መራራ ትግል የተካሄደበት፣ ከፍተኛ መስዋዕትነትንም የጠየቀ ቢሆንም፣ በአብዮ
ታዊ መንግሥት ቀራጥ አመራር አብዮቱ ገስጋሴውን ሊቀጥል ችሏል። ሰፊው ሕዝብ
በሥራ ስምሪትና በመኖሪያ ክልል ከመሰባሰቡም ሌላ በማናቸውም የመንግሥት ተቋሞ
ች፣ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች ውስጥ የውይይት ክበቦች መቋቋም ቀጥተኛና
ሰፊ ሕዝባዊ መድረክ በመፍጠሩ የርእዮተዓለም ሥርጭቱ እየተስፋፋ እንዲሄድ
አድርጓል ።

ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ ፀረ አብዮት ሃይሎች እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀ
መጡም ። ከአብዮቱ ጐን የተሰለፉት ማርክሲስቶችና ተራማጅ ኃይሎች ሳይንሳዊ

Digitized by Google

ውን ርዕዮተዓለም በማሰራጨት ሰፊውን ሕዝብ ሲያነቁና ሲያደራጁ፥ በማርክሲዝም ሌኒንዝም ካባ ተሸፋፍና የቀረበው የሥርዓተ አልበኞችና ቀጥረኞች ጥርቅም የሆነው ኢህአፓ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ስም ሥልጣን ለመያዝ የነበረውን ፍላጐት የአብዮቱ ሃይሎች ባካሄዱት የርዕዮተዓለም ትግል ስለአከሸፉበት ፥ ሀቀኛ አብዮታውያንን በመግደል በርዕዮተዓለምና በፖለቲካ ትግሉ የደረሰበትን ሽንፈት ለመወጣት ነጭ ሽብሩን ማፋፋሙን ጀመረ ። ይሁንና ይህ ሙከራው በቀይ ሽብር በመመታቱና በመሀል አገር ፀረ አብዮት ሃይሎች የማሊ ርዕዮተዓለም ሥርጭትን ለማሰናከል ያደረጉት መፍጨርጨር ሁሉ በመክሸፉ ፥ ለርዕዮተዓለሙ በስፋት መሠራጨት የበለጠ አመች ሁኔታ ተፈጠረ ። ከዚህ ወቀት በኋላ በውይይት ክበቦች አካባቢ የተከሰተው የፀረ አብዮት ደባ በአሉባልታና በፌዝ ፥ እንዲሁም በዳተኝነት መልክ ቢቀርብም፥ የርዕዮተዓለሙን ሥርጭት ሊገታው አልቻለም ።

በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የማሌ ርዕዮተዓለም ተቀባይነት እንዲያገኝ ካደረጉት ነገሮች መካከል በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው የጊ.ወ.አ.ደ. በተከታታይ ያወጣቸው አብዮታዊ አዋጆች ተግባራዊ ክንዋኔ ነው ። ከቃል ይልቀ ተግባር ብዙ ስለሚናገር የአብዮታዊ አዋጆች ተግባራዊነት እራሱ ርዕዮተዓለሙ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ በቀላሉ ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የተጫወተው ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ አብዮት በተለያየ መንገድ ጥቅማቸውን የነካባቸው ፀረ አብዮት ኃይሎች አብዮቱን ከመጀመሪያው አንስተ የታገሉት፥ አሁንም የሚታገሉት ብቻቸውን ቆመው አይደለም ። እንዲያውም የፀረ አብዮት ሴራቸውን በበላይነት የሚመራውና የሚያቀነባብረው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ነው ። ይህም በኢትዮጵያ አብዮት ብቻ ሣይሆን በሁሉም አብዮቶች ታሪክ የተከሰተ ነው ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በአብዮቱ የመጀመሪያ ወቀት የውስጥ አድኅርት ኃይሎች በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በመደገፍ ኢትዮጵያን ከፋፍሉ ለማዳከምና አብዮቱን ለመቀልበስ ካካሄዱት የተጥቀ ትግል ጉን ለጉን፥ ሰፊውን ሕዝብ በመርዘኛ ፕሮፓጋንዳ ለመበከል ያደርጉት የነበረውን ጥረት በማጋለጥና የአድኅርት ኃይሎችን የርዕዮተዓለም ትግል በማክሸፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት የርዕዮተዓለም ሥርጭት ዘርፎች መካከል የሕዝብ መገናኛ ዘደዎች ማለትም ራዲዮ ፥ ቴሌቪዥን ፥ ጋዜጣ ወዘተ ... ይገኙበታል ።

በተለይም የኢትዮጵያን አብዮት የቀርብና የረዥም ጊዜ ዓላማ ጠቋሚ የሆነው የዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከወጣ በኋላ፥ የሕዝብ መገናኛ ዘደዎች ሥርነቀል የሆኑ አዋጆች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ በማብራራት ፥ ሰፌው ሕዝብ ከአድሃሪው ሥርዓተ ርዕዮተዓለም እንዲላቀቀ፥ አብዮቱንና የአብዮታዊት እናት ሀገሩን ነጻነትና ህልውና እንዲንከባከብ በማድረግ፥ ኢምፔርያሊዝምና የውስጥ ፀረ አብዮት ሃይሎች አብዮቱንና ሶሺያሊዝምን የማጥላላት ፕሮፓጋንዳቸውን በማክሸፍ፥ በአጠቃላይ የሶሻሊዝምን ብሩህ ገጽታ በማንጸባረቁና የአድኃሪያን ሤራ እንዲከሽፍ በማድረጉ ረገድ ሰፊ ሚና ተጫውተዋል ።

ፀረ-አብዮት ኃይሎች አብዮቱን ለማንቋሸሽ ያደረጉትን ጥረት በመዋጋቱና በማክሸፉ ረገድ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የአብዮቱን ፈር በመከተል የወጡ ቲያትሮች ፥ ስነ ጽሑፎች ፥ ሌሎችም የኪነጥበብ ዘርፎች የተጫወቱት ሚና በቀላሉ

Digitized by Google

የሚገመት አይደለም ። የአድሃሪውን ሥርዓት ኋላቀርና ኢሣይንሳዊ አመለካከቶ በመዋጋትና የማሊን ርዕዮተዓለም በማሰራጨቱ ረገድ የጣሁሉ ዘርፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ።

ሰፊውን ሕዝብ ከመሀይምነት በማላቀቅ መጻፍና ማንበብ እንዲችል በማድረግ፣ ብሎም በመላ ኢትዮጵያ የማሊ ርዕዮተዓለም ሊስፋፋ የሚችልበትን አመቺ ሁኔታ በማዘጋጀቱ ረገድ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነው ። ሌኒን መሀይም ሰው ከፖለቲካ ውጭ ነው ያለውን አባባል ስናስታውስ፣ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻው የማሊ ርዕዮተዓለም በሠርተአደሩ ሕዝብ ዘንድ ሰርጾ ሊገባ የሚችልበትን ቀድመ ሁኔታ በማመቻቸቱ አንፃር ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳደረገ ለመገንዘብ አያዳግተም ።

ሌላው በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው የኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ ድክመት ሆኖ የቀየውን የግንባር ቀደም ፓርቲ አለመኖር ምክንያት በማድረግ ይህንን ጥያቄ ለማሟላት ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምር እስከ ኢሠፓአኮ መመሥረት ድረስ ሲካሄድ የቀየው የርዕዮተዓለም ትግል ነው ።

እንደሚታወሰው በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ አብዮቱን እስከ ዘለቄታ ግቡ ድረስ ለማድረስ የሚችል አንድ ወጥ የሆነ የማሊ ፓርቲ እንደት ሊመሠረት ይችላል የሚለው ጥያቄ ዛሬ ኢሠፓአኮ ከተመሠረተ፣ የተደረሰበትም የርዕዮተዓለም ግንዛቤ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ዕድገት ካሣየ በኋላ ቀላል መስሉ ቢታይም፣ በወቀቱ ከፍተኛ የሆነ የርዕዮተዓለም ትግልን አስከትሉ እንደነበር አይዘነጋም ። በጊዜው በነበረው የርዕዮተዓለም ግንዛቤ በፐሮግራማቸውና በታክቲካቸው አንዳንድ ልዩነቶች የነበሩአቸው የህቡእ ድርጅቶች ቀደም ሲል በግንባር፣ ከኢማሌድህ መቋቋም በኋላም በውህደተ ቲዎሪ አማካይነት ድርጅቶችን ሚካኒካዊ በሆነ መንገድ በጅምላ በማዋሀድ አንድ ወጥ ፓርቲ ለመመሥረት ታስቦ ነበር ። ሆኖም ይህ ዘዴ በድርጅቶች መሀከል የነበረውን የጠባብ ቡድን ስሜት ሊገታ የማይችል፣ ለፀረ አብዮት ኃይሉች የመከፋፈል ሴራ የተጋለጠና እንዲያውም ከሌኒን የአዲሱ ዓይነት ፓርቲ አመሠራረት ልምድ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው በመሆኑ፣ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ይህ ዓይነት የፓርቲ ምስረታ «ዘደ» ፍጹም የተሳሳተ ዘዴ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ ወደሆነው የፓርቲ አመሠራረት፣ ማለትም ኢሠፓአኮ ላይ እስኪደርስ ድረስ የተካሄደው የርዕዮተዓለም ትግል ፀረ አብዮት ኃይሉች በየደረጃው እንዲተፋ ከማድረጉም በላይ፣ በአብዮቱ ኃይሉች ዘንድም የርዕዮተዓለም ግንዛቤ ደረጃ እንዲዳብር በማድረግ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይገመታል ።

በአጠቃላይ ለነጋገር እስከ ኢሠፓአኮ መመሥረት ድረስ የነበረው የርዕዮተዓለም ሥርጭት ሲገመገም፣ በወቀቱ በአብዮቱና በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ በተፈጠረው ያገጠጠ የውስጥና የውጭ አድህርት ኃይላት ጥቃትና ጥቃቱም በፈጠረው ውጥረት ሳቢያ፣ ቀንጅት የሌለውና በአብዛኛውም በቀስቀሳ ላይ ያተኮረ ነበር ለማለት ይቻላል ።

በኢሠፓአኮ መከሰተ ርዕዮተዓለሙን በስፋት ከአንድ ማዕከል ለማሠራጨት ከመ

Digitized by Google

ቻሉም በላይ የርዕዮተዓለም ስርጭት ይበልጥ ጥራት ባለውና በተቀነባበረ መንገድ ሊከናወን የሚችልበተ ለመች ሁኔታ ተፈጥሯል ።

የኢሠፓአኮ ዋና ዋና ዓላማዎች በማሌ ርዕዮተዓለም የታነፀ የሠርተአደሩን ፓርቲ መመሥረትና የማሌን ርዕዮተዓለም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ማሰራጨት እንደ መሆናቸው ፡ እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ የማድረጉ ሂደት ከማሌ ርዕዮተዓለም መስፋፋት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው ።

በመሆኑም ኢሠፓአኮ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በአባላቱም ውስጥ ሆነ በሰፊው ሕዝብ መሀከል የማሌን ርዕዮተዓለም ለማሰራጨት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ። ኢሠፓአኮ በሣይንሳዊ ሶሻሊዝም ቲዎሪ የታነፀ የሠርተአደሩን ፓርቲ የማዋቀር ታሪካዊ ኃላፊነት የተጣለበተ በመሆኑ ፡ ይህን ታላቅ ተግባር በሚገባ ለማከናወን በአባላቱ መካከል የሚካሄደው የርዕዮተዓለም ሥራ ስፋትና ጥንካሬ ወሳኝ ነው ።

ኢሠፓአኮ ፓርቲ ባይሆንም በአንድ በኩል ፓርቲውን የሚያዋቀር ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፓርቲን አሠራር በመለማመድ እንደ ፓርቲ የሚሠራ የፖለቲካ አካል እንደ መሆኑ ፡ የአባላቱን የርዕዮተዓለም ትጥቅ ለማዳበር ቋሚ በሆነ መንገድ በመሠረታዊ ድርጅቶቹ ውስጥ በሚካሄድ የፖለቲካ ጥናት ፡ በልሣኑ በ«ሠርተአደር» እና በንድፈሃሳብ መጽሔቱ በ«መስከረም» ይጠቀማል ። ከዚህም በተጨማሪ በየካቲት 66 የፖለቲካ ትምህርት ቤት እና ወደሶሻያሊስት ለገሮች በመላክ አባላቱ መደበኛ የንድፈሀሳብ ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል ።

በሠርተአደሩ ሕዝብ መካከል የማሌ ርዕዮተዓለምን ማስፋፋትና በኢሠፓአኮ ለመራር ሥር ማሰለፍ ፡ ሠራተኛው ሕዝብ በተለይም የሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ተልዕኮውን በሚገባ እንዲገነዘብ ማድረግ ሌላው የኢሠፓአኮ መሠረታዊ ዓላማ እንደመሆኑ ፡ በዚህም ረገድ ኢሠፓአኮ በሰፊው ሕዝብ መሀከል ለሚካሄደው የርዕዮተዓለም ሥርጭትና የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል ፤ በመስጠቱም ላይ ነው ። ከዚህ አንጻር የርዕዮተዓለም ሥራው ያተኮረባቸው መስኮች ሠርተአደሩን ሕዝብ ከኢሠፓአኮ ዓላማ ጋር በማስተዋወቅ ለፓርቲው ምሥረታ ማነሣሣት ፡ ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆነውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣልና የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ለማዳበር በሚደረገው ትግል ሠርተአደሩ ሕዝብ ተሳትፎውን በይበልጥ እንዲያጠናክር ማድረግ ፡ ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትንና ሶሻሊስት አርበኝነትን የማጠናከር ኃላፊነትን ማስገንዘብ ፡ የሥራ ዲስፕሊን ማክበር ፡ የሥራ ምርታማነትን ማሣደግና ወዝአደራዊ ባህል እንዲሰፍን መታገል ፡ የሕዝቦችንና የብሔረሰቦችን እኩልነትና ወንድማማችነት ማራመድ ፡ በየጊዜው የሚከሰቱ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮችን መንስኤና መፍትሔ መጠቆም ፡ በባህሉም መስክ ብኩንነትን ምዝበራንና የመሳሰሉትን የአድሃሪውን ሥርዓት ቀሪቶች የመዋጋት አስፈላጊነቱን ፡ በውጭ ፖሊሲም ለሰላም ፡ ለዕድገትና ለሶሻሊዝም የሚካሄዱ ትግሎችን የመደገፍና በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲን የማራመድ አስፈላጊነትን የሚያጠቃልሉ ናቸው ።

በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ኢሠፓአኮ የርዕዮተዓለሙን ሥርጭትና የፕሮፓጋንዳ ሥራውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገለገልባቸው በማናቸውም መንግሥታዊ ተቋሞች ውስጥ የተቋቋሙት የውይይት ክበቦች ፡ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ፡ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ልሳን «ሠርተአደር» እና የንድፈሃሳብ መጽሔቱ «መስከረም» ናቸው ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሊጠቀስ የሚገባው ሣይንሳዊ ሶሻሊዝምን ዘላቂ በሆነ መን

Digitized by Google

ገድ ለማሠራጨት በሚደረገው ትግል የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጻሕፍትን ወደ ኢት
ዮጵያ ቋንቋዎች ለመተርጐምና ለማሠራጨት የሚደረገው ጥረት ነው ።

በተለይም የካድሬዎች አጥረት ጉልቶ በሚታይበት ፣ አብዛኛው ሕዝብ አሁንም
ቢሆን ከመሀይምነት ባልተላቀቀበት በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ፣ የሕዝብ መገናኛ
ዘዴዎች የማሌን ርዕዮተዓለም በስፋት በሠርቶአደሩ ሕዝብ ውስጥ በማሠራጨቱ
ረገድ ዓይነተኛ ሚና ይኖራቸዋል ። ራዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች የአብ
ዮታዊ መንግሥትንና የኢሠፓአኮን መመሪያዎች በማብራራትና ሠርቶአደሩም ሕዝብ
የተገባር መመሪያው እንዲያደርጋቸው በማነሳሳቱ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ
ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። ከመንግሥታዊ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በተጨ
ማሪ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በሙያ ማኅበራት የሚወጡ ጋዜጦችና መጽሔቶችም አሉ ።
እነዚህ ጋዜጦችና መጽሔቶች በአሁኑ ወቀት አሠራራቸው ሙሉ በሙሉ የተቀናጀና
የተጠናከረ ነው ባይባልም ፣ የልዩ ልዩ ማኅበራዊ ክፍሎችን ባህሪ ከማንፀባረቅና ተል
ዕኮዎቻቸውንም ከማብራራት ባሻገር የማሌን ርዕዮተዓለም በማሠራጨቱ ረገድ ከፍ
ተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው ። የማሌን ርዕዮተዓለም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ
በማሠራጨቱ ረገድ ቲያትር ፣ ስነ ጽሑፍና ሌሎችም የኪነ ጥበብ ዘርፎች ሠርቶአ
ደሩን ሕዝብ ለኢኮኖሚ ግንባታ ፣ ለሀገር ነጻነትና ሐልውና እንዲነሳሳ ፣ እንዲሁም
የሶሻሊስት ባህልን እንዲያዳብር በማድረግ አብዮቱ ለቀመለት የሶሻሊስት ሥርዓት
ግንባታ ሐሊናዊ ሁኔታዎችን ለማሟላት የሚያደርጉት ጥረት በቀላሉ የሚገመት
አይደለም ።

የሶሻሊስት ግንባታ የተወሳሰበና የረዥም ጊዜ ጥረትን የሚጠይቅ እንደመሆኑ ፣
አዲሱ ትውልድ ከሥር ጀምሮ በየደረጃው በማሌ ርዕዮተዓለም ታንጾ እንዲያድግ የማ
ድረጉ ትግል ወሳኝነት ያለው ነው ። ከዚህ አንጻር ቀደም ሲል ከዝቅተኛ ጀምሮ እስከ
ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ድረስ ያለው ሥርዓተ ትምህርት ከአብዮቱ ሂደት ጋር
ሊራመድ የሚችልበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ከተደረገው ሙከራ በተጨማሪ ፣ በአንደኛ
ደረጃ ፣ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ በማሌ ርዕዮተዓለም
ላይ የተመሠረተ ፣ ቋሚ የሆነ የፖለቲካ ትምህርትና የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ ለመ
ስጠት የሚደረገውና በመደረግ ላይ ያለው ጥረት ለርዕዮተዓለም ሥርጭቱ ዘላቂነት
ዋስትና ነው ። በሌላ በኩል በክፍለ ሀገር ፣ በአውራጃ ፣ በወረዳና በከተሞች ውስጥ
የተለያዩ ሴሚናሮች በማካሄድ የአብዮቱን ሂደት ለማብራራት የሚደረገው ጥረት
የሠርቶአደሩን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ለማዳበር እንደሚረዳ አይጠረጠርም ።

በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው ዋንኛ ነጥብ የርዕዮተዓለም ሥርጭት
ሥራ ሠርቶአደሩን ሕዝብ ከማደራጀቱ ተግባር ጋር ዲያሌክቲካዊ የሆነ ግንኙነት
ያለው መሆኑ ነው ። ሰፊው ሕዝብ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በሙያ ማኅበራት ካልተ
ደራጀ የማሌን ርዕዮተዓለም በስፋትና በጥልቀት ለማሠራጨትና ሠራተኛውን ሕዝብ
ለሶሻሊዝም ግንባታ ለማሰለፍ አይቻልም ። በመሆኑም በቅርቡ አንጋፋ የሆኑትን ሕዝ
ባዊ ድርጅቶች ማለትም መኢሠማንና መኢገማን ከኢሠፓአኮና ወደፊትም ከሚመ
ሠረተው ፓርቲ የአደረጃጀት መርህ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በአዲስ መልክ እንዲዋ
ቀሩና እንዲደራጁ ለማድረግ የተወሰደው እርምጃ ፣ ለሠርቶአደሩ ፓርቲ አስፈላጊ የሆነ
ውን ማኅበራዊ መሠረት ከመጣሉም ባሻገር ፣ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ የማሌን ርዕዮተ
ዓለም በስፋት ለማሠራጨት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ።

Digitized by Google

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ አብዮታዊ መንግሥት ለማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሣይንስ መስፋፋት ለመች ሁኔታ በመፍጠሩ፣ የማሌን ርዕዮተዓለም የማስፋፋቱ ጥረት ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል። ይህም ለመሆኑ በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ የዲሞክራሲያዊና የሶሻሊስት አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መምጣቱ ቋሚ ምስክር ነው። በተለይም ከኢሠፓአኮ መመሥረት በኋላ የርዕዮተዓለም ሥርጭት ቀደም ሲል ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ጥራትና ቀንጅት እያገኘ በመምጣቱ፣ በተለያዩ የሀገርና የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ትክክለኛ አቋም ለመያዝ ተችሏል። በዚህም አንጻር የሠርቶአደሩ ሕዝብ የፖለቲካ ንቃትህሊና በይበልጥ እየዳበረ መጥቷል።

ከዚህ በላይ ጠቅለል ባለመልክ ለመጠቀም የተሞከረው በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የርዕዮተዓለምን ሥርጭት ሚናና ሥርጭቱም የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ነው። እንደተባለውም እስካሁን ድረስ ርዕዮተዓለሙን ለማሠራጨት የተደረገው ጥረት በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም፣ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችንን አገባድደን የሶሺያሊስት አብዮቱን ለመያያዝ፣ የጀመርነውንም የፓርቲ ምሥረታ ለማከናወን፣ ለሶሺያሊዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት ለመጣል የተያያዝነውን የረዥም ጊዜ ትግል አግቡ ለማድረስ ከሚቀረን ከባድና ውስብስብ ትግል አንጻር የርዕዮተዓለም በተለይም ደግሞ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራችንን በአጥፍ ድርብ የማጠናከር ኃላፊነት እንደሚጠብቀን አያጠራጥርም።

ለወደፊቱ የኢሠፓአኮን የርዕዮተዓለም፣ በተለይም የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሥራዎች በይበልጥ እንዲሰምሩ ለማድረግ የኢሠፓአኮን ልሣንና የንድፈሃሳብ መጽሔት ማጠናከር፣ የመንግሥት የመገናኛ ዘዴዎች ማለትም የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የጋዜጦችና የመጽሔቶች፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲሁም የባህል ተቋሞች በይበልጥ ሊጠናከሩና አሠራራቸውም ሊቀናጅ የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። በመደበኛ ት/ቤቶች ውስጥ የፖለቲካ ትምህርትን አሰጣጥ በማጠናከር አዲሱን ትውልድ በማሌ ሣይንስ ለማነጽ የሚደረገውን ጥረት በይበልጥ ማፋፋም አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ፣ አብዮቱ አሁን ባለበት ደረጃ የገጠመውን የካድሬዎች እጥረት በአጭር ጊዜ ለማሟላት ከፍተኛ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል።

ሌኒን ያለ አብዮታዊ ንድፈ ሃሳብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም ሲል፣ የሰው በሰው መበዝበዝ የሌለበት የሶሺያሊስት ሥርዓት ለመመሥረት የማሌ ርዕዮተዓለም ሥርጭትና ሥርጸት አማራጭ የማይገኝለት ነው ማለቱ ነው። በተለይም አሁን ባለንበት የሽግግር ወቅት የርዕዮተዓለም ሥራችንን ከምን ጊዜውም ይበልጥ ማጠናከር በአብዮቱ ሂደት ላይ ወሣኝነት ያለው ነው። አብዮቱ ወደፊት እየገፋና እየተጠናከረ በሄደ መጠን ፀረ አብዮት ኃይሎች አብዮቱን በከፍተኛ ደረጃ የሚፈታተኑት በአብዛኛው በርዕዮተዓለሙ ትግል መስክ ነው። ሌኒን ይህን በአብዮቶች የመጀመሪያው ምዕራፍ የሚካሄደውን የፖለቲካ ትግል አስመልክቶ፣ <u>በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ዘመን ስለአለው ኢኮኖሚና ፖለቲካ</u> በተሰኘው ዝነኛው ጽሑፉ ውስጥ ሲጽፍ፣ «...በዝባዦች ክፉኛ ተመተዋል፣ ጨርሰው ግን አልጠፉም። እነሱ ቀርንሟፍ የሆኑለት የዓለም አቀፍ ካፒታል እንደ መሠረት ሆኖ ያገለግላቸዋል። አሁንም ቢሆን ይነስ እንጂ በከፊል የምርት መገልገያ ባለቤትነት አላቸው፣ ገንዘብ አላቸው፣ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውም በጣም የሰፋ ነው። በመሸነፋቸው አልሞት ባይ ተጋዳይነታቸው በመቶ

Digitized by Google

በሺህ እጥፍ ጨምሯል። ቁጥራቸው ካጠቃላዩ የሕዝብ ብዛት ጋር ሲመጣጠን በጣም ትንሽ ቢሆንም የመንግሥታዊ፣ የወታደራዊና የኢኮኖሚያዊ የአስተዳደር ልምዳቸው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ተፅዕኗቸው ከቁጥራቸው ጋር ተመጣጣኝ አይደለም። በመሆኑም ስልጣናቸው በተገፈፈው በዝባዦችና በአሸናፊነት በወጣው ወዝአደር መካከል የሚካሄደው የመደብ ትግል የበለጠ የተካረረ ይሆናል። የመደብ ትግል ጽንሰ ሀሳብ በጥገናዊ ቀዝቀዝ እስካልተለወጠ ድረስና ስለ አብዮት እስካወራን ድረስ ሌላ ምንም መልክ ሊይዝ አይችልም፤» ያለው የሽግግር ወቀት ተጨባጭ ሁኔታ የግድታ ወደ ተካረረ የርዕዮተዓለምና የፖለቲካ ትግል የሚያመራ መሆኑን ለመጠቆም ነው።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት በደረሰበት የእድገት ደረጃ ቀደም ሲል በአብዮቱ ላይ ተሰንዝሮ የነበረው የትጥቅ ትግል አብቅቷል የሚባልበት ሁኔታ ላይ ባይደረስም፣ የአብዮቱን የወደፊት እርምጃ የሚወስኑት የማሌ ፓርቲ ምሥረታና ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሠረት የመጣሉ ትግል በተጠናከረ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገኛል። ሆኖም ይህ ትግል ውስብስብና ረቂቅ የሆነ የውስጥና የውጭ አድሀርት ኃይሎችን የርዕዮተዓለም ትግል የሚያስከትልና በማስከተልም ላይ ያለ በመሆኑ፣ የማሌን ሳይንስ የተመረኮዙ አንዳንድ መፈክሮችንና ፅንሰሐሳቦችን ብቻ መጨበጥ ከትግሉ በአሸናፊነት ለመውጣት አያስችለንም። ወቅቱ ከሚጠይቀው ውስብስብ ትግል በአሸናፊነት ለመውጣት የሚቻለው ሳንዘናጋ የማሌን ሳይንስ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር በማገናዘብ በጥልቀትና በስፋት ስንጨብጥ ብቻ ነው።

ለአብዮታዊ ተግባራችን ገብ መምታት ብሎም ለአብዮቱ መሳካት ወሳኙ የርዕዮተዓለም ጥንካሬያችንና ርዕዮተዓለሙንም ከግል ሕይወታችን ጋር በማዋሀድ ወደ ተግባር ለመተርጐም የምናደርገው ጥረት በመሆኑ፣ የርዕዮተዓለም ብቃትን በየጊዜው ከፍ ማድረግ የአብዮታውያን ሁሉ መሠረታዊ ኃላፊነት ነው። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ በሕይወት ለከፈሉት መስዋዕትነት በሕይወት የሚገኙ አብዮታውያን ማድረግ የሚገባቸው በአብዮቱ ዓላማ እስከ መጨረሻው ጸንተው እንዲቆሙ የሚያስችላቸውን የርዕዮተዓለም ጥንካሬያቸውንና የድርጅት ብቃታቸውን ማዳበር ነው።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በአራተኛው የኢሠፓአኮ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባቀረቡት ሪፖርት ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው ሲናገሩ፣ «ኮሚኒስቶች ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የሚያንቀሳቅሱት በርዕዮተዓለም ጥንካሬያቸው ነው። ኮሚኒስቶች ሠርቶአደሩን ሕዝብ የሚያንቀሳቅሱት በማደራጀትና በመምራት ብቃታቸው ነው። ኮሚኒስቶች ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የሚያንቀሳቅሱት በአርአያነታቸው ነው። በማናቸውም መስክ በምናደርገው እንቅስቃሴ ልንገነዘባቸው የሚገቡ መርሆዎች እነዚህ ናቸው፤» ያሉትን የኢትዮጵያ አብዮታውያን የተግባራቸው መመሪያ ማድረጋቸውን በየጊዜው መገምገም ይኖርባቸዋል።

Digitized by Google

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF)

—የወል የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሣሪያ

—ለገሠ ለማ (ዶ/ር)

የዘመኑ ኢምፔሪያሊዝም አንድ ዋና ገጽታ ከኢምፔሪያሊስቱ ሥርዓት የተላቀቀውን የዓለም ክፍል መልሶ ለመያዝና በኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ መረብ ውስጥ የሚገኘውን የዓለም ክፍል ደግሞ በዚሁ አኳኋን እንዲቆይ ለማድረግ ያለው ከፍተኛ ፍላጐት ነው ። ለዚህ ዓላማውና በተለይም በኋላ ቀር አገሮች ሕዝቦች ላይ የሚያካሂደውን ብዝበዛ ለመቀጠል ፤ ኢምፔሪያሊዝም የዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ሥርዓትን እንደመሣሪያ ይጠቀምበታል ። ጃክ ውዲስ ስለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በጻፈው መጽሐፉ ውስጥ እንደገለጸው እንደዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (International Monetary Fund – IMF) ዓለም ባንክ (IBRD)፣ ዓለም አቀፍ የዕድገት ድርጅት (IDA) እና ዓለም አቀፍ የፊናንስ ኮርፖሬሽን (IFC) የመሳሰሉት ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ተቋሞች የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች «ታዳጊ አገሮችን በአንድነት እንዲበዘብዙ የሚረዱ «የወል ቅኝ አገዛዝ» ናቸው ። ከዋሚ ንክሩማህም እንደዚሁ በእነዚህ ተቋሞች ለታዳጊ አገሮች የሚሰጠውን እርዳታ «የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ኢኮኖሚያዊ ወጥመድ» በማለት ገልጾታል ።[1] ስለዚህ ባንድ በኩል ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ባላቸው መተሳሰር ምክንያት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአብዛኞዎቹ ኋላቀር አገሮች (የሶሻሊስት የእድገት ፈለግን የሚከተሉትንም ጭምር) ጋር በአላቸው ግንኙነት የተነሣ ስለ እነዚህና እነዚህን ስለመሳሰሉት ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ድርጅቶች የበለጠ ማወቅ ከኢምፔሪያሊዝም ወጥመድ ላለመግባት ለሚደረግ ጥረት አስፈላጊነቱ አያጠራጥርም ።

የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ሥርዓትን የማቀነባበር ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበትና በአንዳንድ አካ

ባቢዎች የብሔራዊ መንግሥታት የበላይ «መንግሥት» እየተባለ የሚነገርለት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ነው። ጽሑፉ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን አመሠራረት፣ ዓላማና ተግባር ከገለጸ በኋላ የገንዘብ ድርጅቱ ከውጥኑ ጀምሮ እንዴት የኢምፔሪያሊዝምን፣ በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ሲንከባከብና ከኋላቀር አገሮች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሣሪያነት ሲያገለግል እንደቆየ ለማሳየት ሙከራ ያደርጋል። በመጨረሻም ጽሑፉ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ሥርዓትን በአጠቃላይ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን በተለይ በሚመለከት ረገድ ምን መደረግ እንዳለበት ይጠቁማል።

አመሠራረት

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የተመሠረተው ከዓለም ባንክ (IBRD) ጋር ባንድ ወቅት ሲሆን ይኸውም እ. ኤ. አ. በ1944* በአሜሪካ፣ ብሬተን ውድስ በተባለው ሥፍራ በተደረገው ጉባኤ ነበር። በዚህ ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ጉባኤ የተሰበሰቡት የአርባ አራት መንግሥታት ተወካዮች ነበሩ። የጉባኤው ዓላማ በኢኮኖሚ ዝቅጠት እና በጦርነት ሳቢያ ተንኮታኩቶ የነበረውን የዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ሥርዓት መልሶ መገንባት መሆኑ ተገልጾ ነበር።

አሜሪካና እንግሊዝ በጉባኤው የተሳተፉ ሲሆን፣ ጉባኤው በተካሄደበት ወቅት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በመካሄድ ላይ ስለነበረ እንደ ፈረንሳይ ያሉ ሌሎች የአውሮፓ አገሮች መንግሥታት ተወካዮቻቸውን የላኩት በስደት ላይ ሆነው ነበር።

ከኋላ ቀር አገሮች መካከል 19 የላቲን አሜሪካ አገሮች በጉባኤው ሲገኙ፣ በተጨማሪም አምስት የእሲያና ሶስት የአፍሪቃ አገሮች ተገኝተዋል። በዚህ ጉባኤ ላይ ተወካዮች የነበሩዋቸው ሶስቱ የአፍሪቃ አገሮች ግብጽ፣ ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ናቸው። በጉባኤው ላይ የተካፈሉት ኋላቀር አገሮች በኢምፔሪያሊስት አገሮች ቀጥተኛም ሆነ እጅ አዙር ቁጥጥር ሥር ስለነበሩ የጉባኤውን ሂደት ለመወሰን ሙሉ ነጻነት አልነበራቸውም። ሌሎች ቅኝ ግዛት የነበሩት የአፍሪቃ፣ የእስያና የካሪቢያን አገሮች ደግሞ በጉባኤው ላይ ጨርሶ ምንም ዓይነት ቦታ አልተሰጠቸውም ነበር።

በብሬተን ውድስ ጉባኤ ላይ አራት የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ማለትም ሶቭዬት ኅብረት፣ ፖላንድ፣ ቼኮዝሎቫኪያ እና ዩጎዝላቪያ ተሳትፈው ነበር። ሆኖም ሶቭዬት ኅብረት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል ላለመሆን ስትወስን፣ ፖላንድ ደግሞ በ1950 በገዛ ፍቃዷ ከድርጅቱ ወጣች። ቼኮዝሎቫኪያም እንዲሁ በ1954 ከድርጅቱ ለቃ ወጣች። አሁን በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ውስጥ በአባልነት የሚገኙት የምሥራቅ አውሮፓ ሶሺያሊስት አገሮች መሥራች አባል የሆነችው ዩጎዝላቪያ፣ በ1972 ድርጅቱ ውስጥ የገባችው ሩማንያ እና ከጥቂት ወራት በፊት አባል የሆነችው ሀንጋሪ ብቻ ናቸው። ቻይና የድርጅቱ መሥራች አባል ብትሆንም በድርጅቱ ውስጥ የነበራትን መቀመጫ ከ1949 እስከ 1980 የያዘው የታይዋን መንግሥት ተወካይ ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን የቻይና ሕዝባዊት ሪፐብሊክ በድርጅቱ ውስጥ ታይዋንን ተክታለች። የሶሻሊስት አገሮች በድርጅቱ ውስጥ ላለመሳተፍ የሚያቀርቡት አንድ ዋና ምክንያት የድምጽ አሰጣጡ ሥርዓት አባላት ባላቸው ኮታ መጠን ላይ የተመሠረተና የተዛባ በመሆኑ እና ይህም የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት በተለይ ዋና ዋና ውሳኔዎችን በሚመለከት ለአሜሪካ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት የሚሰጥ በመሆኑ ነው። ከሌሎች ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ደግሞ አባላት ማንኛውንም ድርጅቱ የሚጠይቃቸውን የኢኮኖሚ መረጃዎች፣ ያላቸውን

---

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው።

Digitized by Google

የወርቅና የውጪ ምንዛሪ መጠንም ሳይቀር፣ በየጊዜው ለድርጅቱ የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው መሆኑና የወርቅና የውጪ ምንዛሪ መጠጮም በአሜሪካ እንዲቀመጥ ግዴታ መኖሩ፣ እንዲሁም አባል አገሮች ከድርጅቱ ብድር ለማግኘት ከቡርዧ የኢኮኖሚ አመለካከት የሚመነጩ ግዴታዎችን እንዲያሟሉ መጠየቃቸው ይገኙባቸዋል ።[2] በአጠቃላይ ድርጅቱ በኢምፔሪያሊዝም ኃይሎች ቁጥጥር ሥር የወደቀ በመሆኑ ሶሻሊስት አገሮች በድርጅቱ እንቅስቃሴ ሙሉ ተሳትፎ ሊኖራቸው አልቻለም ። ይህን ጉዳይ ወደፊት የምንመለስበት ይሆናል ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሥራውን የጀመረው በ1947 ሲሆን በወቅቱ 49 አባል አገሮች ነበሩት ። ካፒታሉም ስምንት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያህል ነበር። በ1981 የድርጅቱ አባል አገሮች ቁጥር 141 ሲሆን ፤ ከነዚሁ በመዋጮ ያገኘው ገንዘብ ብቻ ድርጅቱ ሥራውን ሲጀምር ከነበረው ካፒታል ጋር ሲነጻጸር አሥር እጅ ያህል አድጓል ።[3]

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል ባለመሆናቸው በጉልህ የሚታወሱ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ኩባ፣ አንጐላና ሞዛምቢክ ናቸው ። ኩባ የድርጅቱ መሥራች አባል ብትሆንም በ1964 በገዛ ፈቃዱ ከድርጅቱ ተገለለች ። አንጐላና ሞዛምቢክ ግን ነጻነታቸውን ከተቀዳጁ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ ጭራሹንም አልገቡም ። በሌላ በኩል የቪየትናም ሶሻሊስት ሪፑብሊክ ቀድሞ በድርጅቱ ውስጥ በደቡብ ቪየትናም ተይዞ የነበረውን ሥፍራ ስትወስድ ሌሎች እንደ አፍጋኒስታን፣ ኢትዮጵያ፣ ካምፑቺያ፣ ላኦስ፣ ግሬናዳ እና ኒካራጉዋ ያሉ ሥርነቀል የፖለቲካ ለውጥ የተካሔደባቸው አገሮች ግን አባልነታቸው እንደጸና ቆይቷል ።[4] አንድ አገር በሌሎች በኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር ሥር በሚገኙ ሁለት ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፊናንስ ተቋሞች ፤ ማለትም በዓለም ባንክና በዓለም አቀፍ የዕድገት ድርጅት ውስጥ ለመሳተፍ በቅድሚያ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል መሆን ይኖርባታል ። ስለዚህ እንደኩባ፣ አንጐላና ሞዛምቢክ ያሉ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል ያልሆኑ አገሮች የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የዕድገት ድርጅትም አባል አይደሉም ።

ዓላማና ተግባር

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሁለት ዓበይት ተግባራትን እንደሚያካሂድ ይገልጻል ። የመጀመሪያው ተግባር የውጪ ምንዛሪ ዋጋንና ክፍያን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣትና የወጡትን መመሪያዎች አባል አገሮች በተግባር መተርጐማቸውን መከታተልና መቆጣጠር ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ አባል አገሮች እነዚህኑ መመሪያዎች ለመከተል ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ዕርዳታ መስጠት ነው። ለዚህ የሚያስፈልገው የገንዘብ ምንጭም ባብዛኛው የሚገኘው ከአባል አገሮች መዋጮ ነው። ድርጅቱ እነዚህን ተግባራት በማካሔድ ሲቋቋም በጸደቀው ስምምነት ላይ የተገለጹት ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ለማድረግ ይቻላል በማለት ይለፍፋል። ድርጅቱ ሲቋቋም በጸደቀው ስምምነት ውስጥ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ዓላማዎችም መካከል ዓለም አቀፍ የገንዘብ ነክ ስምምነትና የአጭር ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ሥርዓት እንዲኖር ፣ የዓለም አቀፍ ንግድ እንዲስፋፋና የተመጣጠነ ዕድገት እንዲያሳይ፣ የውጪ ምንዛሪ ዋጋ መዋዠቅ እንዲገታና አባል አገሮች የውጪ ምንዛሪ ችግር ሲያጋጥማቸው ችግሩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ከማስከተሉ በፊት መፍትሔ እንዲገኝለት ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል ።[5] በተግባር እንደሚታየው ከሆነ ግን የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዋና ተግባር ዝቅ ብለን በዝርዝር እንደምንመለከተውና ድርጅቱን በቁጥጥራቸው ሥር ባዋሉት የኢምፔሪያሊ

Digitized by Google

ሉት ኃይሎች አመለካከት ካፒታሊዝምን ከውድቀት ማዳን ፣ የካፒታሊስት ይዞታ በየአገሩ እንደየሁኔታው እንዲያቆጠቁጥና እንዲጠናከር ማድረግ ፣ እንዲሁም የሞኖፖል ካፒታል በውጪ ምንዛሬና በውጪ ንግድ ላይ ያለውን የበላይነት ማጠናከር ነው ።[6]

በብሬተንውድስ የተመሠረተው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ሥርዓት ዋና ዋና መርሆዎችና የሥርዓቱ መንኮታኮት

በ1944 በብሬተን ውድስ ስምምነት የተደረሰበት ሥርዓት በአንድ በኩል በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል በነበረው በታላቁ የኢኮኖሚ ዝቅጠት ጊዜ እንደታየው ዓይነት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ዋጋ መዋዠቅ እንዳይኖርና በሌላ በኩል ደግሞ የውጪ ምንዛሬ ዋጋ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተወሰነ ለውጥ እንዲያሳይ የማያስችል በወርቅ ላይ ሙሉ በሙሉ የተመሠረተ የገንዘብ ሥርዓት (GOLD STANDARD) ከሚያስከትለው ችግር እንዲያድን የታቀደ እንደነበር ይነገራል ። እያንዳንዱ የድርጅቱ አባል የገንዘቡን ዋጋ በወርቅ ወይንም በአሜሪካ ዶላር እንዲወስንና የገንዘቡም የምንዛሬ ዋጋ ከ1% በላይ ከፍ ወይም ዝቅ እንዳይል ስምምነት ተደረገ ። ቀደም ሲል ዋጋው ከ5.52 ግሬይንስ የተጣራ ወርቅ ጋር እንዲመዛዘን ተደርጐ የነበረው የኢትዮጵያ ብር ከ40.25 የአሜሪካ ዶላር ሳንቲም ጋርም እኩል እንዲሆን የተደረገው በዚያን ጊዜ ነበር ። አንድ የድርጅቱ አባል አገር የገንዘቡን ዋጋ ሊለውጥ የሚችለው ከፍተኛ የሆነና ለረጅም ጊዜ የቆየ የውጪ ምንዛሬ ገቢ እና ወጪ መጠን አለመጣጣም ችግር ሲደርስበትና ድርጅቱም ይህንኑ ችግር ተገንዝቦ ሲፈቅድለት መሆኑ ስምምነት ተደረሰበት ። ሆኖም አባል አገሩ በተከታታይ የሚያደርገው የገንዘብ ዋጋ ለውጥ ስምምነት ከተደረሰበት የገንዘቡ ዋጋ ከአሥር እጅ በመቶ በላይ ካልሆነ የድርጅቱን ፈቃድ የማግኘት ግዴታ ውስጥ እንዲገባ አልተደረገም ነበር ። በስምምነቱ መሠረት የአሜሪካ ዶላር ይህን ከፍተኛ ሚና እንዲጫወት ሲደረግ ፣ አሜሪካ ለብሔራዊ ባንኳ ለሚቀርብ ለእያንዳንዱ ዶላር በቋሚነት አንዱን አውንስ ወርቅ በሰላሳ አምስት ዶላር ሂሳብ ለመቀየር ቃል ኪዳን እንድትገባ ተደርጐ ነበር ።

ይህ ቃል ኪዳን ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በዓለም በጥንካሬ እጅግ የላቀ ኢኮኖሚና ከካፒታሊስቱ ዓለም ጠቅላላ የወርቅ ክምችት 75 በመቶ ያህል ያላት አገር ከመሆንዋ ጋር ተዳምሮ የአሜሪካን ዶላር ልክ እንደወርቅ እንዲቆጠር አስቻለው ። ስለዚህ ሌሎች አገሮች በአሜሪካ ዶላር ክፍያ ሲደረግላቸው ያለማቅማማት በመቀበል የውጪ ምንዛሬም በአሜሪካ ዶላር ያከማቹ ጀመር ። በዚህ አኳኋን አሜሪካ ዶላሯን እያተመች በዓለም ላይ በማሰራጨት ከሌሎች አገሮች ጋር በምታደርገው የገንዘብ ክፍያ ግንኙነት አማካኝነት የሚደርስባትን ዴፊሲት ስትሸፍን ቆየች ። እጅግ በጣም ብዙ ዶላሮችን በማሳተም በኩሪያና በቬየትናም የተደረጉትን ዓይነት ኢምፔሪያሊስት ጦርነቶች አካሄደች ። በሌሎች አገሮች የጦር ሠፈሮችን መሠረተች ። ወደ ሌሎች አገሮች ካፒታል በማጓጓዝ ሕዝቦችን በዘበዘች ። ከሌሎች አገሮች ጥሬ ዕቃዎችንና ሌሎችንም ሸቀጦች በብዛት ወደ አገሯ ውስጥ አስገባች ። በየአገሩ ለሚገኙ አድኃሪና አጋሯ ለሆኑ ኃይሎችም የወታደራዊ እና የኢኮኖሚ ድጋፍ ሰጠች ። አሜሪካ ይህን ሁሉ በማድረጓ ለምሳሌ በ1970 የነበራት የወርቅ ክምችት ጠቅላላ ዋጋ 11 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ሲሆን ፣ በገፍ

Digitized by Google

ካተመችው ገንዘቧ ውስጥ ከአሜሪካ ውጪ
የተከማቸው ጠቅላላ መጠን 53 ቢሊዮን
ዶላር ደረሰ ።

በዚህ አኳኋን በአንድ በኩል በዓለም ተ
ቀባይነት ላለው ገንዘብ ያለው ፍላጐት በአ
ፋጣኝ እያደገ ሲመጣ ፥ በሌላ በኩል ደግሞ
በወርቅ ያልተደገፈ የአሜሪካን ዶላር በገፍ
አትሞ ማሰራጨቱ ከቀጠለ የአሜሪካ ዶላ
ር ከፍተኛ ቀውስ ያጋጥመዋል የሚል መ
ሠረት ያለው ፍርሀት ተፈጠረ ። ስለዚህ በ
አንድ በኩል ይህን ቀውስ ለማስቀረት፥በ
ሌላ በኩል ደግሞ በዓለም ተቀባይነትያለ
ው የገንዘብ እጥረት ለመቋቋም እርምጃ
መውሰድ አስፈለገ።ለዚህ ነበር ቀደም ሲል
በ1969 ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ስፔ
ሻል ድሮዊንግ ራይት (ኤስ.ዲ.አር.) በተ
ሰኘ ሰነድ አማካኝነት ገንዘብ የማግኛ ልዩ
መብት እንዲፈጥር ሥልጣን የተሰጠው ።
በዚህ ሥልጣን መሠረት ድርጅቱ ዋጋቸው
በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመቱ ኤስ.
ዲ. አር. በልዩ ልዩ ወቅቶች በመፍጠር
ተሳታፊ ለሆኑ የድርጅቱ አባል አገሮች
ለድርጅቱ በሚያደርጉት መዋጮ መጠን
መሠረት ሲያድል ቆይቷል ። በአሁኑ ጊዜ
የኤስ. ዲ. አር. ዋጋ የሚመሠረተው በአባ
ላት አገሮች ዋና ዋና ገንዘቦች ዋጋዎች አ
ማካይ ዋጋ ላይ ነው ። በዚህ አኳኋን የሚ
ተመነው ዋጋ ከቀን ወደቀን ልዩነት የሚ
ያሳይ ቢሆንም ፥ በአሁኑ ጊዜ የአንድ ኤስ
ዲ. አር. ዋጋ 1.3 የአሜሪካ ዶላር አካ
ባቢ እንደሚዋዥቅ ይታወቃል ። [7]

ይህም ሆኖ አሜሪካ ከሌሎች አገሮችጋር
ያላት የገንዘብ ክፍያ ችግር እያደር እየተባ
ባሰ መሔዱን ሳያቆም ቀረ ። በዚህ ምክን
ያት በ1971 ሶስት ትናንሽ የአውሮፓ ብሔ
ራዊ ባንኮች በአሜሪካ የኢኮኖሚ ሁኔታ
እምነት በማጣታቸው በዶላር መልክ አከ
ማችተውት ከነበረው የውጪ ምንዛሪ በከ
ፊል ወደወርቅ እንዲለወጥላቸው ለአሜሪካ
ብሔራዊ ባንክ ጥያቄአቸውን አቀረቡ ። ነ
ገር ግን ከአሜሪካ ውጪ የነበረው የዶላር
ክምችት አገሪቷ ከነበራት የወርቅ ተቀማ
ጭ እጅግ የበዛ መሆኑን የተገነዘበው የአ
ሜሪካ መንግሥት የተጠቀሱት ብሔራዊ
ባንኮች ያቀረቡትን የዶላር ክምችት ወደ
ወርቅ ለመለወጥ ከተስማማ ሌሎችም ብሔ
ራዊ ባንኮች የወርቅ ክምችቱ ከማለቁ በፊ
ት ያላቸውን የዶላር ክምችት ወደ ወርቅ ለ
መለወጥ ይንጋጋሉ በማለት በፍርሀት ተዋ
ጠ ። በዚሁ ሳቢያ በጥቂት ቀናት ውስጥ ማ
ለትም በነሐሴ 1971 ዩናይትድ ስቴትስ
በዶላር ለውጥ ወርቅ ላለመስጠት መወሰ
ኗን አሳወቀች ።

በዚህ ዓይነት አሜሪካ ከሌሎች አገሮች
የሚቀርብላትን ዶላር ወደ ወርቅ ለመቀየር
የገባችውን ቃል ኪዳን በማፍረስ በብሪቶን
ውድስ የተመሠረተው ዓለም አቀፍ የገን
ዘብ ሥርዓት እንዲንኮታኮት አደረገች።በዶ
ላር ላይ የደረሰውን ቀውስ ለማስታገስ ይረ
ዳል በማለትም አሜሪካ የገንዘቧን ዋጋ በዚ
ያው ዓመት በ8.6%፥ ዳግመኛም በ1973
በ10% ዝቅ እንዲል አደረገች ። በዚህ
መሠረት በ1971 35 ዶላር የነበረው የአ
ንድ አውንስ ወርቅ ዋጋ በ1973 ወደ
42.22 ዶላር ከፍ አለ ። በዚሁ ወቅት ግን
ዶላርን ወደወርቅ ላለመለወጥ የተጣለው
እገዳ እንደፀና ቆየ ። [8]

በገንዘቦች መካከል የነበረው ቋሚ የም
ንዛሪ ዋጋ ሥርዓት እንደፀና ሊቆይ እንደማ
ይችልም ወዲያውኑ ግልጽ እየሆነ መጣ ።
አሜሪካና ሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች
ቋሚ የምንዛሪ ዋጋ ሥርዓትን በማውገዝ
የምንዛሪ ዋጋቸው የገበያን ውጣ ውረድ
ተከትሎ እንዲለዋወጥ አደረጉ ። ኋላም
በ1978 በፀደቀ የድርጅቱ ስምምነት ማሻ
ሻያ መሠረት ማንኛውም አባል አገር የሚ
ስማማውን የምንዛሪ ዋጋ ተመን ሊደነግግ
እንደሚችል ተገለጸ ። ይሁ ማሻሻያ የአባል
አገሮች የምንዛሪ ዋጋ ፖሊሲ የድርጅቱን
አላማዎች አለመጻረሩን የመከታተልና የመ
ቆጣጠር መብት ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድር
ጅት ቢሰጥም ፥ በብሪቶን ውድስ ተመስርቶ

የነበረው ቋሚ የምንዛሬ ዋጋ ሥርዓት በዚህ አኳኋን ተሰረዘ ። በአዲሱ ማሻሻያ መሠረት አንድ አባል አገር የገንዘቡን የምንዛሬ ዋጋ በሌላ አገር ገንዘብ የምንዛሬ ዋጋ ላይ ፣ ወይንም ቁጥራቸው በርከት ባሉ አገሮች ገንዘቦች (ኤስ. ዲ. አርንም ጨምሮ) የምንዛሬ ዋጋዎች አማካይ ዋጋ ላይ ሊመሠርት፣ ወይንም የገበያን ውጣ ውረድ በመከተል ሊለዋወጥ እንዲችል ተደረገ ። ማሻሻያው በተጨማሪም የወርቅን ኦፊሴላዊ ዋጋ ከመሠረዙም ሌላ አባል አገሮች ለድርጅቱ የሚያደርጉትን መዋጮ በወርቅ እንዲከፍሉ የማይጠየቁ መሆናቸውን አሳወቀ ።[9] በብሬቶን ውድስ የተመሠረተው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ሥርዓት በዚህ ዓይነት ሲንኮታኮት ፣ የካፒታሊስቱ ዓለም የገንዘብ ቀውስና ወደፊት በሰፋት የምንመለከተው የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የኢምፔሪያሊዝም ጥቅም አስከባሪነት እንደቀጠለ ይገኛል ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስም ስለመገልገሉ

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደ አንድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ አካል የሚታወቅ ሲሆን ፣ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ያለው ግንኙነትም በ1948 በተፈረመ ውል ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህ ስምምነት መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተወካዮች (ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው) በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች የመሳተፍ መብት አላቸው ። በአንጻሩም የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተወካዮች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤና የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ምክር ቤት ስብሰባዎች የመሳተፍ መብት ተሰጥቷቸዋል ። ሆኖም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንቅስቃሴ ወይም ፖሊሲ ውስጥ ጣልቃ ሊገባ አይችልም ። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እራሱን የቻለ ድርጅት መሆኑ በስምምነቱ ውስጥ ተገልጿል ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት መካከል የተደረገው ስምምነት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ምንም ዓይነት ግዴታ ውስጥ የማያስገባው ከመሆኑም በላይ የገንዘብ ድርጅቱን በቁጥጥራቸው ሥር ላዋሉት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቶላቸዋል ። ይኸውም በዓለም አቀፍ ድርጅት አማካኝነት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ስምና ሥልጣን እንደሽፋን ሊገለገሉበት በመቻላቸው የሚያገኙት ጥቅም ነው ።[10]

አባላት ለድርጅቱ የሚያደርጉት መዋጮ በድምጽ አሰጣጥ ላይ ያለው ወሳኝነት ድርጅቱ በኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር ሥር እንዲውል ስለማድረጉ

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በብድር መልክ ከአባል አገሮች የሚያገኝ ቢሆንም ዋንኛው የገንዘብ ምንጩ አባል አገሮች በተወሰነላቸው ኮታ መጠን መሠረት የሚያዋጡት መዋጮ ነው ። ለአንድ አገር የሚደለደለውን ፣ ኮታ (መዋጮ) መጠን የሚወስነውም የአገሩ ብሔራዊ ገቢ መጠን ፣ የውጭ ምንዛሬ ክምችት መጠን ፣ የውጪ ንግድ ሁኔታ ፣ በተለይም የንግዱ ሚዛንና ሌሎችም የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በአንድነት ታይተው ነው ።[11] አንድ አባል አገር ለድርጅቱ የሚከፍለው መዋጮ መጠን ደግሞ አባል አገሩ በድርጅቱ ውስጥ ያለውን የድምጽ ጥንካሬ ፣ ከድርጅቱ ሊያገኝ የሚችለውን የብድር መጠንና ድርጅቱ በየጊዜው ከሚያድለው ኤስ.ዲ. አር ከተሰኘው ገንዘብ ማግኛ ልዩ መብት የሚያገኘውን ድርሻ ይወስናል ። ድርጅቱ ካከማቸው ወርቅ በከፊል እንዲሸጥ በተወ

ስንበትም ጊዜ ከወርቁ ሽያጭ የተገኘው ትርፍ ለአባል አገሮች በኮታ መጠን መሠረት እንዲከፋፈል ተደርጓል ። [12]

በ1981 የድርጅቱ ጠቅላላ ኮታ መጠን 59.6 ቢሊዮን ኤስ. ዲ. አር. ፣ ወይንም 77 ቢሊዮን ያህል የአሜሪካ ዶላር ነበር። የኮታ መጠን በአባል አገሮች መካከል ከፍተኛ ልዩነትን ያሳያል ። ለምሳሌ የአሜሪካ ኮታ 12.6 ቢሊዮን ኤስ.ዲ.አር. (ከጠቅላላው 21.2%)ሲሆን የማልዲቭ ደሴቶች ኮታ ግን 1.4 ሚሊዮን ብቻ ነው ። ከአሜሪካ በተጨማሪ መጠኑ ከአንድ ቢሊዮን በላይ የሆነ ኮታ ያላቸው ሌሎች አገሮች የሚከተሉት ናቸው ፣ እንግሊዝ 4.4 ፣ ጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ 3.2 ፣ ፈረንሳይ 2.9 ፣ ሕዝባዊት ሪፑብሊክ ቻይና 1.8 ፣ ሕንድ 1.7 ፤ ሆላንድ 1.4 ፣ ቤልጂየም 1.3 ፣ አውስትራሊያ 1.2 ፣ ሳውዲ አረቢያ 1.04። እራሳቸውን «አሥሩ ታላላቅ አባላት» እያሉ የሚጠሩት የበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች (ማለትም ፣ አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ ምዕራብ ጀርመን፣ፈረንሣይ፣ ጃፓን ፣ ካናዳ ፣ጣሊያን ፣ ሆላንድ ፣ ቤልጂየምና ስዊድን).ድርሻ ከጠቅላላው ኮታ መጠን 55% ነው ። ይህ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ቡድን በገንዘብ ድርጅቱ ላይ ወሳኝ የሆነ ተጽእና የሚያደርግ ነው ። የገንዘብ ድርጅቱ አባል የሆኑት ሃያ አምስቱ የበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ከጠቅላላው ኮታ 65% በመካከላቸው ሲከፋፈሉ ፣ የቀሩት 116 አባል አገሮች ድርሻ የተረፈው 35% ነው ። የድርጅቱ አባላት የሆኑት 48 የአፍሪካ አገሮች (ደቡብ አፍሪካን ሳይጨምር) በአንድነት ያላቸው ድርሻ ከጠቅላላው 7% ብቻ ነው ። ኢትዮጵያ ያላት ድርሻ 54 ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር ሲሆን ይህም ከጠቅላላው 0.09% ይሆናል።

እያንዳንዱ አባል አገር በድርጅቱ ውስጥ የሚኖረውን የድምጽ ጥንካሬ የሚወስነው የኮታው መጠን መሆኑ የድርጅቱ የገዥዎች ቦርድ እና የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ቁጥጥር ሥር እንዲውል አድርጎታል ። በመሠረቱ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የበላይ አካል የእያንዳንዱ አባል አገር አንድ ገዥና አንድ ተለዋጭ ገዥ የሚወከሉበት የገዥዎች ቦርድ ነው። እያንዳንዱ የገዥዎች ቦርድ አባል ያለው የድምጽ ጥንካሬ የሚወከለው አባል ቃገር በድርጅቱ ውስጥ ከያዘው ኮታ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። እያንዳንዱ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል አገር በድርጅቱ ውስጥ 250 መደበኛ ድምጽና ፣ በተጨማሪም ለኮታው ለእያንዳንዱ 100,000 ኤስ ዲ. አር. አንድ ድምጽ አለው ። በዚህ መሠረት ለምሳሌ አሜሪካ 126,326 ወይም ከጠቅላላው 20.10 % ድምጽ አላት ። «አሥሩ ታላላቅ አባላት» የሚባሉት ኢምፔሪያሊስት አገሮች ብቻ በአንድነት ሆነው ከጠቅላላው 51.4% ድምጽ አላቸው ። በዚህ መሠረት በአጠቃላይ በገንዘብ ድርጅቱ የገዥዎች ቦርድ ውስጥ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን በኢምፔሪያሊስት አገሮች እጅ ገብቷል ። [13]

በየዓመቱ አንዴ የሚሰበሰበው የገዥዎች ቦርድ ሥልጣኑን በአብዛኛው ለሥራ አፈጻሚ ዲሬክተሮች በውክልና መስጠቱ ይነገራል ። እንዲያውም እውነተኛ ሥልጣን ባብዛኛው ያለው በሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች እጅ ነው ። የገንዘብ ድርጅቱን የዕለት ተዕለት ተግባሮች የማካሔድ ኃላፊነት ያለበትና 22 አባላት ያሉት የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች ቦርድ በድርጅቱ የሥራ አመራር ዲሬክተር ሊቀ መንበርነት በዋሽንግተን ከተማ በየጊዜው እየተሰበሰበ ተግባሩን ያካሂዳል ። በገንዘብ ድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛውን ኮታ የያዙት አምስት አባላት ማለትም አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ ምዕራብ ጀርመን ፣ ፈረንሣይ እና ጃፓን እያንዳንዳቸው አንድ የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር ይሾማሉ ። በድርጅቱ ውስጥ በአንደኛ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ አበዳሪ የሆነው አባል አገር (ከላይ ከተጠቀሱት «ከአምስቱ ኃያላን» አንዱ ካልሆነ) አንድ የ

Digitized by Google

ሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር ሊሾም ይችላል። በዚህ ደንብ መሠረት ሳውዲ ዓረቢያም አንድ የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር ሾማለች። ይህ ለሁለት ዓመታት የሚቆይ ሲሆን ሳውዲ ዓረቢያ ከፍተኛ አበዳሪነቱን በአንደኛ ወይንም በሁለተኛ ደ/ጃ ከቀጠለች ከዚያም በኋላ የሚ[illegible]ስ [illegible]ሆናል። ሕዝባዊ ሪፑብሊክ ቻይናም በግዷ አንድ የሥራ አስጸሚ ዲሬክተር የመሰየም ሥልጣን ተሰጥቷታል። የተቀሩትን 15 የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች ተመሳሳይ ፍላጐት ያላቸው አባል አገሮች በቡድን በመሰባሰብ ለ2 ዓመት ይመርጣሉ። ልክ እንደገዥዎች ቦርድ ሁሉ በሥራ አስፈጻሚ ቦርድም ውስጥ እያንዳንዱ አባል ያለው የድምጽ ጥንካሬ በገንዘብ ድርጅቱ ውስጥ ካለው ኮታ ጋር የተያያዘ ነው። [14] በየመንግሥታት የተመረጡት የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች እያንዳንዳቸው 250 ድምጽና በተጨማሪም አገሮቻቸው በድርጅቱ ውስጥ ላላቸው ኮታ ለእያንዳንዱ 100,000 ኤስ.ዲ. አር አንድ ድምጽ አላቸው። ተመሳሳይ ፍላጐት ያላቸው አባል አገሮች በቡድን በመሰባሰብ የመረጧቸው የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮች ደግሞ 250 መደበኛ ድምጽና በቡድን ለመረጡት አገሮች አጠቃላይ ኮታ ለእያንዳንዱ 100,000 ኤስ. ዲ. አር. አንድ ድምጽ አላቸው። [15]

የድምጽ አሰጣጥን በሚመለከት፣ ባጠቃላይ አብዛኛውን ድምጽ ያገኘው ሐሳብ ተቀባይነት እንደሚያገኝ የተገለጸ ቢሆንም፣ በጣም ከፍተኛ ውሳኔዎችን በሚመለከት ግን ከጠቅላላው 75% ወይም 85% የድምጽ ብልጫ ማግኘት ያስፈልጋል። 85 % የድምጽ ብልጫ የሚያስፈልጋቸው የኮታ መጠን ለውጥን፣ የውጪ ምንዛሪ ልውውጥን፣ ለአንድ አባል አገር የተሰጠ የብድር የክፍያ ጊዜ ከገደቡ በላይ እንዲቀጥል ማድረግን፣ የገንዘብ ድርጅቱን የወርቅ ክምችት አጠቃቀም፣ የሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተሮችን ቁጥር ማሳደግን፣ ድርጅቱ የሚፈጥረውን ኤስ.ዲ.አር ዋጋ መወሰንና በአባላት መካከል ማከፋፈልን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች ናቸው። የ85% የድምጽ ብልጫ ሕግ ዋነኛ ባሕርይ ከጠቅላላው ድምጽ ከ20% በላይ ያላት አሜሪካ በተናጠል ወሳኝ ጉዳዮችን በሚመለከት ረገድ ድምጽን በድምጽ ለመሻር መቻሏ ነው። [16]

እስካሁን ድረስ የገንዘብ ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በመሆን የሚሠሩት የምዕራብ አውሮፓ ዜጎች መሆናቸውና በዚሁ አኳያ የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት በመሆን ደግሞ የሚሠሩት የአሜሪካ ዜጎች መሆናቸው በቋሚነት ሲሠራበት ቆይቷል። እስካሁን ድረስ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በመሆን የሠሩት የቤልጂጉ ካሚይጊት (1946—51)፣ የስዊድኑ ኢቫር ሩት (1951—56)፣ እሁንም የስዊድኑ ፔር ያኮብሰን (1956—63)፣ የፈረንሣዩ ፒየር ፓውል ሽቫይትሠር (1963—73) የሆላንዱ የሃንስ ቪተፈን (1973—78) እና የፈረንሣዩ ዣክ ደ ላሮዚየር (ከ1978 ጀምሮ እስካሁን ድረስ) ናቸው። የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆና የሚሠራው ሰው ደግሞ ሁልጊዜም የአሜሪካ ዜጋ መሆኑ ድርጅቱ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር ሥር መዋሉን በበለጠ ያረጋግጣል። [17]

የድርጅቱ የብድር አሰጣጥ ሁኔታና የሚያስከትላቸው ከቡርዧ ርዕዮተ ዓለም ጋር የተገናዘቡ ግዴታዎች

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በሚሰጠው የብድር ዓይነት ብዛት የታወቀ ሲሆን፣ ተበዳሪዎችን ከሚያስገባቸው ግዴታዎች አንጻር የሚከተላቸው አጠቃላይ መርሆች እንዳሉት ይገልጻል። አንድ አባል አገር ከድርጅቱ የሚወስደው ብድር ለድርጅቱ ካዋጣው መዋጮ ከ25% እስካልበለጠ ድረስ ምንም ዓይነት ግዴታ እንዲገባ አይወየ

Digitized by Google

ትም ። ሌላ ተዉጣሪ የኮታዉን 25% ያህል ብድር ለማግኘት የፈለገ አገር ግን ከሌሎች አገሮች ጋር ያለዉን የገንዘብ ክፍያ ሚዛን መዛባት ችግር ለመወጣት«በቂ ጥረት»እንደሚያደርግ የሚያሳይ የኢኮኖሚ መርሐ ግብር (ፕሮግራም) ለገንዘብ ድርጅቱ ማቅረብ አለበት ።

ከዚህ ውጭ የሚገኙ ብድሮች ግን የተወሰኑ ግዴታዎችን ያስከትላሉ ። ይህም ማለት አንድ አባል አገር ብድሩን ሊያገኝ ይችል ዘንድ በድርጅቱ ተቀባይነት ያለው የአንድ ወይንም የሁለት ዓመት «የማስተካከያ» ፕሮግራም ("Stabilization" Programme) እና ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሔድ የ«ተግባር መመዘኛ » («performance Criteria») ወጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ። በብድር ጠያቂውና በገንዘብ ድርጅቱ መካከል የዚህ ዓይነት ስምምነት የሚደረሰው ከብዙ መደራደር በኋላ ሲሆን ፣ የገንዘብ ድርጅቱ በስምምነቱ አግባብነት በተበዳሪው አገር ላይ የሚያደርገው ተጽዕኖ ጥንካሬ ተበዳሪው አገር ካለበት ችግር ጋር የሚመጣጠን ይሆናል ። ይህም ማለት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ችግር ደርሶበት የገንዘብ ድርጅቱን ብድር ከተኛ የሚፈልግ አገር የራሱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነድፍ በተግባር ከመተርጐም መብቱ አብዛኛውን ወይንም ሙሉ በሙሉ ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አሳልፎ ለመስጠት ይገደዳል ማለት ነው። ተበዳሪው አባል አገር በተግባር ለመተርጐም የተስማማባቸው ፖሊሲዎች በመርሐ ግብር ደብዳቤ (Letter of Intent) ውስጥ በዝርዝር እንዲገለጹ ይደረጋል ። ስምምነት ላይ እንደተደረሰም የተፈቀደው ብድር የሚሰጠው ባንድነት ተጠቃልሎ ሳይሆን በተጠባባቂነት አሠራር (Stand by Arrangement) መሠረት በየጊዜው ተከፋፍሎ ይሆናል ። የገንዘብ ድርጅቱ ወደተበዳሪው አገር በየጊዜው የኤክስፐርቶቹን ቡድን በመላክ ስምምነት ላይ የተደረሰበት የተግባር መመዘኛ መሟላት አለመሟላቱን ያረጋግጣል ። በቡድኑ አስተሳሰብ ተበዳሪው አገር የተግባር መመዘኛውን ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለአባል አገሩ ሊሰጥ የተስማማውን ብድር ሰጥቶ ሳይጨርስ በመሀል እንዲቋረጥ ያደርገና ፣ ብድሩ እንዲቀጥልለት ከፈለገ ሌላ የ«ማስተካከያ» ፕሮግራም መደራደር የሚያስፈልገ መሆኑን ለአባል አገሩ ይገልጽለታል ። አዲሱ«ማስተካከያ» ፕሮግራምም ተደም ሲል ስምምነት ተደርሶበት ከነበረው ይልቅ የአባል አገሩን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መብት ለገንዘብ ድርጅቱ በይበልጥ አሳልፎ የሚያስጥ ይሆናል ። [18]

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በክፍያ ሚዛናቸው ላይ ዴፊሲት ለደረሰባቸው አገሮች መፍትሔ ይሆናል ብሎ የሚያቀርበው የ«ማስተካከያ» ፕሮግራም ከአገር ወደ አገር የሚለያይ ቢሆንም በአጠቃላይ የሚከተሉትን ያቅፋል ።

— የዋጋ ንረት መከላከያ (Anti-Inflaitionary) ፕሮግራም ፤

ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል

- የባንክ ብድርን መጠን መገታት ፣ የወለድ መጠንን ማሳደግ ፤
- የመንግሥት ዴፊሲት መጠንን መገታት (በተለይም ለማኅበራዊ አገልግሎት የሚውል የመንግሥት ወጪን መቀነስ)
- መንግሥታዊ የኢኮኖሚ ቁጥጥርን ማላላትና የመንግሥት ድርጅቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጨመር ፤
- በፍጆታ ሸቀጦች ላይ የሚደረገውን የዋጋ ድጎማ ማስቀረት ፤
- በመንግሥት ሥልጣን ሥር እስከሆነ ድረስ ምንዳ እንዳይጨምር ቁጥጥር ማድረግ ፤
- የዋጋ ቁጥጥርን ማስቀረት ።

— ለውጪ ካፒታሊስቶች አመቺ ሁኔታን መፍጠር ፤

Digitized by Google

—የውጪ ምንዛሪንና የገቢ ንግድን ቁጥጥር ማስቀረት ወይም ቁጥጥሩን ማላላት ፣
—የገንዘብን የምንዛሪ ዋጋ መቀነስ ።[19]

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መፍትሔ ብሎ የሚያቀርበውን ፕሮግራም «ሳይንሳዊ» መሠረት እንዳለውና እራሱንም ለአባል አገሮች የቴክኒክ ዕርዳታ በማበርከት ተግባር ላይ ብቻ የተሰማራ ፣ የማያዳላና ገለልተኛ እንደሆነ አድርጐ ያቀርባል። ሆኖም የድርጅቱ እንቅስቃሴ በሚገመገምበት ጊዜ በግልጽ የሚታየው የዚህ ተቃራኒ ነው ። በ1980 በአሩሻ ታንዛኒያ ፣ ስለ «ዓለም አቀፍ የገንዘብ ሥርዓትና ስለአዲሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት»ተደርጐ የነበረው ጉባኤ ያሳለፈው ውሳኔ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ኢሳይንሳዊነት ፣ አድልዎ አድራጊነትና ገለልተኛ አለመሆን በጠንካራ ቃላቶች በትክክል ያመለክታል ።

እንደ ጉባኤው ትክክለኛ አስተያየት የገንዘብ ድርጅቱ ሳይንሳዊ አይደለም ። ኋላቀር አገሮችን በዕድገት ሂደታቸው ውስጥ የገንዘብ ክፍያ ችግር ማጋጠሙ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው የኢኮኖሚ ልዩ ልዩ ክፍሎች አደረጃጀት አንጻር ሲታይ የማይቀር መሆኑ ግልጽ ነው ። ነገር ግን የገንዘብ ድርጅቱ እንደመፍትሔ አድርጐ የሚያቀርባቸው ሐሳቦች ኋላቀር አገሮች በዕድገት ሂደታቸው ውስጥ የሚያጋጥማቸውንም ሆነ የገቢ ንግዳቸው ዋጋ በመናሩና ከወጪ ንግዳቸው የሚያገኙት ገቢ በመቀነሱ ምክንያት የሚደርስባቸውን ያልታሰበና ድንገተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ዴፊሲት ችግር ለመቋቋም የታቀዱ አይደሉም ። እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከቱ አሁን ያሉት ሁኔታዎች የገንዘብ ድርጅቱ ሲቋቋም ከነበሩት ሁኔታዎች ጋር ሲነጻጸሩ ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው ሆነው ሳለ ፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የኋላቀር አገሮችን የኢኮኖሚ ችግሮች በገንዘብ ነክ ፖሊሲ ብቻ ሊቃለሉ እንደሚችሉ ፣ ጊዜአዊ ሁኔታዎች አድርጐ መቁጠሩን እንደቀጠለ ነው ።[20] የኋላቀር አገሮች ችግር የውጪ ምንዛሪ እጥረትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ከዚያም በላይ መሠረታዊ የሆኑ ዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነቶችን ፣ የቴክኖሎጂ ስርጭትን ፣ ወዘተ ... የሚጨምር መሆኑን ለመገንዘብ ያለመፈለግ የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ትልቁና ዋናው ድክመቱ ነው ።

የገንዘብ ድርጅቱ ገለልተኛ ስላለመሆኑና በቡርዧ ርዕዮተዓለም ስለመበከሉ የአሩሻው ጉባኤ የሰጠውን አስተያየት ከማየት በፊት ድርጅቱ መፍትሔ ለሚላቸው አንዳንድ ሃሳቦች ሳይንሳዊ መሠረት ብሎ የሚያቀርባቸውን አስተሳሰቦች መመልከት አስፈላጊ ነው፡ በአንድ አገር ውስጥ የዋጋ ንረት መናር የወጪ ንግድን የሚያዳክምና የገቢ ንግድን የሚያበረታታ በመሆኑ የአገሩን የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ችግር የማባባስ አዝማሚያ ያለው መሆኑ የታወቀ ነው ። ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትም የውጪ ምንዛሪ ክፍያ ችግርን ለማቃለል ያስችላል በሚል ሳቢያ ፀረ ዋጋ ንረት ብሎ የሚያቀርበው ፕሮግራም አለ ። የዚህ ፕሮግራምም መሠረት ፣ የዋጋ ንረት መንስኤ በአገር ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠን ለገበያ ከሚቀርቡ ሸቀጣሸቀጦች መጠን ጋር በማይመጣጠን አኳኋን ከፍተኛ ሆኖ መገኘት መሆኑን ድርጅቱ ይለፍፋል ። ድርጅቱ ከዚህም በመነሳት በአንድ አገር ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠን ሊያድግ የሚችለው የመንግሥት ወጪ አድጎ የበጀት ዴፊሲት ሲያጋጥምና ባንኮችም የሚሰጡት ብድር ሲያድግ በመሆኑ እነዚህ መገታት አለባቸው ይላል ። እንዲሁም እንደድርጅቱ አባባል የመንግሥት ቀረጥንና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለዕቃና ለአገልግሎት የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጨመር በሕዝብ እጅ የሚገኘው ገንዘብ ወደ መንግሥት እጅ እንዲገባ በማድረግ የዋጋ ንረትን ለመቋቋም ያስችላል ። የወለድ መጣኔንም ማሳደግ ሕዝቡ የተቀማጭ ገንዘቡን መጠን እንዲያሳድግና ከባንክ የሚበ

ደረውን ብድር መጠን እንዲቀንስ በማድ
ረግ በአገሩ ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ
መጠን እንዲቀንስ በመርዳት የዋጋ ንረትን
ለመከላከል ይረዳል ብሎ የገንዘብ ድርጅቱ
ያምናል ። በአንድ አገር ውስጥ የወለድ መ
ጣኔ ግደግ በተጨማሪም የውጭ አገር ዜጐ
ችና ኩባንያዎች ከፍተኛ ወለድ ለማግኘት
ሲሉ ገንዘባቸውን ወደዚሁ አገር ስለሚያ
ዛውሩ የውጭ ምንዛሬ ችግርን ለማቃለል
ይረዳል የሚል ሀሳብም ከድርጅቱ ይሰነዘ
ራል ። ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዋጋ
በገበያ ውስጥ ከብዙ መዋዠቅ በኋላ በራሱ
ሊስተካከል ስለሚችል ይህም በሂደቱ በተ
ለያዩ ክፍላተ ኤኮኖሚ መካከል የሚኖረውን
የሰው ኃይልና የማቴሬያል ስርጭት ባልተ
ዛባ መንገድ እንዲካሄድ ሊያደርገው ይች
ላል የሚል አመለካከት ስለአለው ፣ የመንግ
ሥት የዋጋ ቁጥጥርን በጥብቅ ይቃወማል ።
በአጠቃላይ መንግሥት በኤኮኖሚው ውስጥ
የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ግደግ ኤኮና
ሚው በበለጠ እንዲዛባ ከማድረጉም በላይ
ግለሰቦችና ድርጅቶች ገንዘባቸውን ወደ
ውጪ እንዲያሸሹ በመገፋፋት የአገሪቱ
የውጪ ምንዛሪ ችግር እንዲባባስ ያደርጋል
ብሎ ስለሚያምን ፣ የዓለም አቀፍ የገንዘብ
ድርጅት መሪ መፈክር መንግሥት በኢኮ
ኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ እጁን ከማስገባት
ይቆጠብ የሚል ነው ።

የውጪ ምንዛሪንና የገቢ ንግድን ቁጥጥር
ማስቀረት ወይንም ማላላት ፣ ሸቀጣ ሸቀጦ
ችና ካፒታል ነፃ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው
በማድረግ በልዩ ልዩ ክፍላተ ኤኮኖሚ መካ
ከል የሚኖረው የሰው ኃይልና የማቴሪያል
ስርጭት ባልተዛባ መንገድ እንዲካሄድ ይረ
ዳል የሚል አስተሳሰብም ከድርጅቱ በተደ
ጋጋሚ ሲሰነዘር ይሰማል ። የአንድ አገር
ገንዘብ የምንዛሪ ዋጋ እንዲቀንስ ሲደረግ የሌ
ላው አገር ገንዘብ የምንዛሪ ዋጋ አንጻራዊ
ዕድገትን ስለሚያሳይ በውጭ ምንዛሪ ከውጪ
የሚገዙ ሸቀጣሸቀጦች እንዲወደዱና ወደ
ውጪ የሚላኩ ሸቀጣ ሸቀጦች በአገሩ ገን
ዘብ ሲተመኑ እንዲረክሱ በማድረግ የገቢ
ንግድን በማዳከምና የወጪ ንግድን በማጠ
ናከር የውጪ ምንዛሪ ችግርን ለማቃለል ይረ
ዳል በማለት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት
የገንዘብ የምንዛሪ ዋጋ ቅነሣን በየጊዜው
እንደ መፍትሄ አድርጐ ያቀርባል ። የውጭ
ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ያስች
ላል በሚልም ሳቢያ የገንዘብ ድርጅት
ለውጪ ካፒታሊስቶች አመቺ ሁኔታ እንዲ
ፈጠር ይጠይቃል ።[21]

እዚህ ላይ በቅድሚያ መገንዘብ የሚያስ
ፈልገው እንደዋጋ ንረት ፤ የመንግሥት ወጪ
ከገቢ በልጦ መገኘትና በልዩ ልዩ ክፍላተ
ኤኮኖሚ መካከል የሰው ኃይልና የማቴሪያል
ስርጭት መዛባትና የመሳሰሉ ሁኔታዎች በቁ
ጥጥር ሥር መዋል የለባቸውም ማለት አለ
መሆኑን ነው ። ይሁንና ዓለምአቀፍ የገንዘብ
ድርጅት ለነዚህ ችግሮች መፍትሔ ብሎ
የሚያቀርባቸው ሀሳቦች በእርግጥ ለችግሮቹ
መፍትሔ ሊሆኑ እንደማይችሉ ደግሞ መገ
ንዘብ ያስፈልጋል ። በዚህ አጋጣሚ የድር
ጅቱ የ« መፍትሄ » ሃሳቦች ከቡርዧ ርዕዮተ
ዓለም ጋር ምን ያህል የተቆራኙ ናቸው ?በእ
ነዚህ ሀሳቦች ላይ የተመረኮዙ እርምጃዎች
መውሰድስ ያልታሰቡና ተፈላጊ ያልሆኑ ምን
ምን ሁኔታዎችን ያስከትላሉ ? የሚሉትን
ጥያቄዎች መሠንዘር እጅግ አስፈላጊ ነው ።
ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደመፍ
ትሔ አድርጐ የሚያቀርባቸው ሀሳቦች የተ
መሠረቱት በቡርዧ የኤኮኖሚ ንድፈ ሀሳ
ቦች ላይ ሲሆን ፣ በእነዚሁ ንድፈ ሀሳቦች መሠ
ረት የሚወሰዱ እርምጃዎች እንኳን የኋላ
ቀር አገሮችን ችግሮች ሊያቃልሉ ይቅርና
በቅድሚያ ያንጸባርቃሉ የሚባለውን የዳ
በሩ ካፒታሊስት አገሮች ሁኔታ የማያንጸ
ባርቁና የእነዚህኑ አገሮች ችግሮች ለመረ
ዳትና ለችግሮቹ መፍትሄ ለማግኘት የማያስ
ችሉ ለመሆናቸው ኢምፔሪያሊስት አገሮች
በየጊዜው ከሚያጋጥሟቸው የኤኮኖሚ ቀው
ሶች ፣ በተለይም ከዋጋ ንረትና ከሥራ አጥ
ነት ችግሮች መባባስ የበለጠ መረጃ ሊገኝ
አይችልም ።

Digitized by Google

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እራሱን ገለልተኛና ከርዕዮተዓለም ነጻ የሆነ ድርጅት ለማስመሰል ልፈፋ ማካሄዱ የታወቀ ነው። ሆኖም ይህ ልፈፋ ድርጅቱ የቡርዧ ርዕዮተዓለም ተገዥ መሆኑንና የሚያቀርባቸው ሀሳቦች በቡርዧ ርዕዮተዓለም ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ሊያሸር አይችልም። ድርጅቱ የሚያቀርባቸው ሀሳቦች ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆነ ገበያ ለችግሮች ሁሉ መፍትሔ ሊያስገኝ ይችላል የሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ የአገር ውስጥና የውጪ ካፒታሊስቶች በኤኮኖሚው ውስጥ እንደልብ እንዲፈነጩ የሚያስችሉ ናቸው። ከዚህም አመለካከቱ በመነሳት ድርጅቱ በአንድ አገር ኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ እንዳይኖር አለዚያም እጅግ አነስተኛ በሆነ ደረጃ እንዲወሰን ጥረት ከማድረግ የተቆጠበበት ጊዜ የለም።

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት በመሠረቱ የፖለቲካ ተቋም መሆኑን በተግባር አረጋግጧል። በኋላቀር አገሮች ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅሙ መሠረታዊ የሆኑ መዋቅራዊ ለውጦችን ለማምጣት የሚደረጉ ብሔራዊ ጥረቶችን በማፈን ካፒታሊስታዊ ግንኙነት እንዲስፋፉ ያደርጋል። ከወዛደሮች ይልቅ ለካፒታሊስቶች፣ ከመንግሥታዊ የኢኮኖሚ ዘርፍ ይልቅ ለግል የኢኮኖሚ ዘርፍ ያደላል። ድርጅቱ የሚከተለው ፖሊሲ በመሠረቱ በመደቦች መካከል የሚገኝ የኑሮ ደረጃ ልዩነትን ለማጥበብ ከሚያስችል ለውጥ፣ እራስን በራስ ከመቻልና ከማናቸውም ተጽዕኖ ነጻ ከሆነ ዕድገት ጋር የማይጣጣም ነው። ኋላቀር አገሮችን በሚመለከት የገንዘብ ድርጅቱ የሚያቀርባቸው ሐሳቦች በተቀነባበረ መንገድ በነዚህ አገሮች ውስጥ ያሉ ወግ አጥባቂና የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ኃይሎችን የሚደግፉ ናቸው። በተለይም ደግሞ የሶሺያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅ በሚታገሉ አገሮች ውስጥ፣ ለሶሻሊዝም በቆሙና ሶሻሊዝምን በተለያየ መንገድ በሚጻረሩ ኃይሎች መካከል ከሚካሔደው ትግል አንጻር፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ጋር የሚመሠረተው ግንኙነት በከፍተኛ ጥንቃቄ እስካልተያዘ ድረስ የመንግሥት ይዞታውን በማዳከም የግል የኢኮኖሚ ይዞታውን የሚያጠናክር፣ በዚህም የአብዮትን ማኅበራዊ መሠረት በማጥበብ ፀረ ሶሻሊስት ኃይሎችን የሚያጠናክርና ለአብዮት ቡርቦራና ቅልበሳ ሴራቸው ሁኔታዎችን የሚያመቻች በመሆኑ፣ ሁኔታው እጅግ በጣም በጥሞና ሊጤን የሚገባው ነው።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የራሱን መመሪያዎች በማስፈጸምም በኩል በአባል አገሮች መካከል ልዩነት ያደርጋል። ኢምፔሪያሊስት አገሮችና የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች ጠንካራ ግዴታዎችን እንዲያሟሉ አይጠየቁም። ኢምፔሪያሊስት አገሮች የድርጅቱን መሠረታዊ መርሆች ባፈረሱበት ጊዜ እንኳን ድርጅቱ አይቶ እንዳላየ ማለፉ የታወቀ ነው። ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች ላይ ግን በተለይ የውጭ ምንዛሪ ችግራቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ሲገኝ እጅግ አስቸጋሪ ግዴታዎችን ይጭንባቸዋል።[22] ሆኖም ድርጅቱ ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮችን ቀስ በቀስ አግባብቶ በኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ መረብ ውስጥ ለመመለስ በሚያደርገው ጥረት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠንካራ ግዴታዎች ውስጥ ባለማስገባት ቀስ በቀስ ግን ወጥመዱን እያመቻቸ ሊያዘናጋ የሚፈልግ መሆኑንም በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

Digitized by Google

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት—ኃይለኛው አዞ ። ስውርና ምሥጢራዊ ፣ እጅግ በጣም ጠንካራ የሆኑ ጥርሶች ያሉት ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉትን አድብቶ የሚይዝ

Digitized by Google

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለኋላቀር አገሮች«መድኃኒት» ብሎ የሚያቀርባቸው ሐሳቦች ፋይዳ ቢስ ብቻ ሳይሆኑ መራራም ናቸው ። ይህን ለማብራራት አንዳንድ ምሳሌዎችን እንውሰድ ። ድርጅቱ የዋጋ ንረትን በመግታት የውጭ ምንዛሪ ችግርን ያቃልላሉ በሚል ሳቢያ የመንግሥት ወጪ፣ ባንኮች የሚሰጡት ብድርና የገንዘብ የምንዛሬ ዋጋ ፣ እንዲሁም ምንዳ እንዲቀንሱ ይጠይቃል ። ሆኖም የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ችግር በአገር ውስጥ በመነጨ የዋጋ ንረት ቢሳበብም ፣ በገቢ ንግድ አማካኝነት ወደኋላቀር አገሮች የሚዛመተው የዋጋ ንረት በድርጅቱ አይነሳም ። በተጨማሪም ችግሩ በወጪ ንግድ ዝቅተኛነት ቢሳበብም ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከኋላቀር አገሮች በሚላኩ ሸቀጦች ላይ የሚጥሉት የኮታ ገደብና ከፍተኛ የቀረጥ ክፍያ ከቶውንም አይወሳም ።

የመንግሥት ወጪ ሲቀንስ ግን በተለይ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰቡን ክፍሎች ለሚጠቅሙ ፕሮግራሞች የሚመደበው ወጪ ይቀንሳል ። እንደ ምግብ ላሉ መሠረታዊ ዕቃዎች ፣ ወይንም እንደ መጓጓዣ ላሉ አስፈላጊ አገልግሎቶች ከመንግሥት ይደረግ የነበረ የዋጋ ድጎማ ሲቋረጥ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰቡ አባላት አሁንም በይበልጥ ጉዳት ይደርስባቸዋል ። ባንኮች የሚሰጡት ብድር እንዲቀንስ ሲደረግ በይበልጥ የሚጐዱት የአገር ውስጥ ትንንሽ አምራቾችና ካፒታሊስቶች ናቸው ። ትልልቆቹ የአገር ውስጥ እና የውጭ ኩባንያዎች የብድር ቅድሚያ እንዲያውም በአነስተኛ ወለድ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ አድራጎት ትልልቅ ካፒታሊስቶች ትንንሽ ካፒታሊስቶችን በመዋጥ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይላቸውን እንዲያጠናክሩ ከመርዳቱም በላይ ፣ የሥራ ፈቱን ቁጥር ያበዛዋል ። ይህም የመንግሥት ወጪ በመቀነሱ አዲስ ከሚፈጠረው ሥራ አጥነት ጋር ሲደመር ችግሩን የተባባሰ ያደርገዋል። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የአንድን አገር መንግሥት ወጪውን እንዲቀንስ ፣ ወይንም ባንኮች የሚሰጡትን ብድር እንዲቀንሱ ሲጠይቅ ግን እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ችግሮች እንደሚፈጠሩ ባለማወቁ ሳይሆን ዓላማው ያተኮረው በጋራ የእጅ አዙር የቅኝ አገዛዝ መሣሪያነቱ የተሰጠውን ተልዕኮ ከመወጣቱ ላይ በመሆኑ ነው ። ይህንንም ለማለት የሚያስችለው እንደተጠበቀው ችግሮች በሚነሱበት ጊዜ መፍትሔ በመሻቱ ረገድ ለመተባበር ፈቃደኛ ሁኖ አለመገኘቱ ነው ።

አንድ ኋላቀር አገር የገንዘቡን የምንዛሬ ዋጋ በመቀነስ የውጭ ምንዛሪ ችግሩን ለማስወገድ አይችልም ። እንዲያውም የከፋ ማድረግ ጉዳቱ አመዝኖ ይገኛል ። አንድ ኋላቀር አገር ከውጭ የሚገዛቸው ሸቀጣ ሸቀጦች በአብዛኛው የገንዘቡ የምንዛሪ ዋጋ ቀነሰም አልቀነሰም የግድ መግዛት ያለባቸው ናቸው ። ልዩነቱ የገንዘቡ የምንዛሪ ዋጋ ከቀነሰ በኋላ ከውጭ የሚገዙት ዕቃዎች የበለጠ ውድ መሆናቸው ብቻ ነው ። እንዲሁም የገንዘብ የምንዛሪ ዋጋ መቀነስ የተባለው አገር ያለበትን የውጭ ዕዳ ያሳድገዋል ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የአገሩ ገንዘብ ዋጋ ከውጭ ምንዛሪ ጋር ሲነጻጸር ስለሚቀንስ ብድሩን በውጭ ምንዛሪ ለመክፈል መጠኑ የበዛ የአገር ውስጥ ገንዘብ ስለሚያስፈልግ ነው ። በተጨማሪም አንድ ኋላቀር አገር በገንዘቡ የምንዛሪ ዋጋ ቅነሳ አማካኝነትም ሆነ በሌላ ምክንያት ወደውጭ የሚልካቸው ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ መቀነስ ከወጪ ንግድ የሚያገኘውን ገቢ ብዙውን ጊዜ ላያሳድገው ፣ እንዲያውም ሊያሳንሰው ይችላል ።

ለዚህም ሁለት ምክንያቶችን ለመጥቀስ ይቻላል። አንደኛው ምክንያት የአንድ ኋላቀር አገር ዋና ችግር ለወጪ ንግዱ ገበያ ማጣት ሳይሆን ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚችለው ምርት መጠን አነስተኛነት መሆኑ ነው ። ሁለተኛው ምክንያት ኋላቀር አገሮች ለውጪ ገበያ የሚያቀርቧቸው

Digitized by Google

በተለይም የእርሻ ምርቶች ዋጋቸው ስለቀ
ነሰ ከቀድሞው ከፍተኛ በሆነ መጠን ሊሸ
ጡ የሚችሉ አለመሆናቸው ነው ። ሁለተ
ኛውን ምክንያት በይበልጥ ለማብራራት
ያህል ለምሳሌ የቡና ዋጋ እንበል በ15 በመ
ቶ ቢቀነስ ብዙ ሰዎች ከበፊቱ የበለጠ ቡና
አይጠጡም ። አንድ ኋላቀር አገር ወደ
ውጭ የሚልካቸውን ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ
በመቀነስ የወጪ ንግዱን እስከተወሰነ
ደረጃ ሊያሳድግ ይችላል ቢባልም እን
ኳ ፣ ኋላቀር አገሮች ለውጭ ገበያ የሚያቀ
ርቧቸው ሸቀጣ ሸቀጦች በአብዛኛው ተመ
ሳሳይ በመሆናቸው የሌሎቹን ኋላቀር አገ
ሮች ገቢያ በመጋፋት የሚያድግ ስለሚሆን
የኋላቀር አገሮችን ችግር በአጠቃላይ ለማ
ሻሻል የሚያስችል እርምጃ አይሆንም ።[23]

የገንዘብ የምንዛሪ ዋጋን መቀነስ የሚያ
ስከትለው ችግር ከዚህ በላይ በተጠቀሱት
ብቻ የሚወሰን አይደለም ። የገንዘብ ምን
ዛሪ ዋጋን መቀነስ ከውጪ የሚገዙ ሸቀጣ
ሸቀጦችን ዋጋ ስለሚያንረው በተለይ በገቢ
ንግድ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ በሆኑ ኋላ
ቀር አገሮች ውስጥ የኑሮ ሁኔታ እንዲወደድ
ያደርጋል ። ይህም በተለይ የሚጐዳው ከም
ንዳ በስተቀር ሌላ ገቢ የሌላቸውን ሰዎች
ሲሆን ባለመሬቶችና ካፒታሊስቶች ፣ በተ
ለይም የውጭ ሞኖፖሎች በሁኔታው በመ
ጠቀም ብዝበዛቸውን ያባብሱታል ። የገን
ዘቡን የምንዛሪ ዋጋ በቀነሰው አገር ውስጥ
ቅርንጫፍ ያቋቋሙ የውጭ ሞኖፖሎች ለአ
ገሬው ወዝ አደር የሚከፍሉት ምንዳ በውጭ
ምንዛሪ ሲተመን ከበፊቱ ስለሚያንስ ትር
ፋቸው ያድጋል ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የዋጋ ንረ
ትን ለመከላከል በሚል ሳቢያ የምንዳ ጭማሪ
እንዳይደረግ አጥብቆ ይወተውታል ። እዚህ
ላይ በተለይ በገቢ ንግድ ላይ በከፍተኛ ደረጃ
ጥገኛ ለሆኑ አገሮች ድርጅቱ እንደዋና መፍ
ትሄ አድርጐ የሚያቀርበው የገንዘብ ምንዛሪ
ዋጋ ቅነሳ ለዋጋ መናር አንድ ዋና ምክንያት
መሆኑን መገንዘብ ያሻል ። ይህ ከሆነ ታዲያ
የምንዳ ጭማሪ እገዳ እንዲደረግ ጉትጐታው
ለምን ይሆን ? የዚህ ምክንያት ዓለም አቀፍ
የገንዘብ ድርጅት ገለልተኛ አለመሆኑ ነው።
ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የምንዳ ጭማሪ
እገዳ እንዲደረግ የሚወተውተው ከሁሉ አስ
ቀድሞ ካፒታሊስቶች ፣ በተለይም የውጭ
ሞኖፖሎች በዋጋ ንረት ሁኔታ በመጠቀም
የሠራተኛውን ሕዝብ ብዝበዛ በማባባስ ከፍ
ተኛ ትርፍ ለማጋበስ እንዲችሉ ለማድረግ
ነው ።[24]

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚያቀ
ርባቸው ሀሳቦች በተለይ ለኋላቀር አገሮች
ፋይዳቢስ ብቻ ሳይሆኑ ጐጂም መሆናቸው
በየጊዜው መነገሩ አልቀረም ። ለምሳሌ
የታንዛኒያው መሪ ፕሬዚዳንት ኒየሬሬ በ19
80 ባደረጉት ንግግር ከገንዘብ ድርጅቱ
ጋር አገራቸው ታደርግ የነበረውን ድርድር
ይፋ በማውጣት የገንዘብ ድርጅቱ ከርዕዮተ
ዓለም ነፃ አለመሆኑን ካስረዱ በኋላ አገ
ራቸው ለዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት
(IMF) ለማጐብደድ ያልተዘጋጀች መሆ
ኗን እንደሚከተለው ገልጸው ነበር ።

ለቃማችን በሚገባ ሳይጤን የነፃ ገበያ
መርህን መከተል ለማንኛውም ነገር እንደ
መፍትሄ አድርገው የሚያቀርቡት በመሆኑ
ብቻ ታንዛኒያ የገንዘቧን ዋጋ ለመቀነስ አል
ተዘጋጀችም። ለመኳኳያ ከሚያገለግሉ ሸቀ
ጦች ይልቅ ኪኒን ፣ ለጥቂት ግለሰቦች ከሚ
ሆኑ አውቶሞቢሎች ይልቅ የሕዝብ ማመ
ላለሻ አውቶብሶችን ከውጭ ለማስመጣት
በሚያስችል መልክ በቀየሰችው የገቢ ንግዱ
ላይ ያላትን የመቆጣጠር መብት አሳልፋ አት
ሰጥም ።

ማንኛውም ሕፃን የአንደኛ ደረጃ ትምህ
ርት እንዲቀስምና መላው ሕዝብም መሠረ
ታዊ የሕክምና አገልግሎትና ንጹህ ውሀ እን
ዲያገኝ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የም
ናካሂደውን ጥረት ለማቋረጥ መንግሥታችን
አልተዘጋጀም ። ብሔራዊ ወጪአችንን መቀ
ነስ ይኖርብን ይሆናል ፣ ነገር ግን ቀነሳው
የሚደረገው ከመንግሥት ወጪ ወይም ከግል

Digitized by Google

ወጪ መሆን እንደሚገባው እኛው እንወስናለን ። የዋጋ ንረትንና የምርት እጥረትን ችግር ለማስወገድ የምንከተለው ፖሊሲ የበለጠ ጉዳት ላይ የሚጥለው ደሀውን ወይስ ሀብታሙን የሚለውን ጥያቄ ወደኋላ ገሸሽ በማድረግ ገንዘብ ነክ ብቻ እንዲሆንም አንፈልግም ።

የዋጋ ቁጥጥራችን ገቡን ከመምታቱ አንፃር በዓለም ውስጥ ከሚካሄዱት ሁሉ የበለጠ ፍሬያማ ላይሆን ይችላል ፣ ሆኖም የበለጠ ገቡን እንዲመታ ያልተቆጠበ ጥረት እናደርጋለንእንጂየዋጋ መቆጣጠሩን ተግባር ፈጽሞ አንተውም ። ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የመገንባቱን ተግባር እንገፋበታለን ።

አንድ ዓለምአቀፍ ድርጅት ብሔራዊ ፖሊሲ የማመንጨት መብታችንን አሳልፈን ካልሰጠነው በስተቀር፣ መስጠት የሚገባውን ዓለምአቀፍ ብድር የማይሰጠን ከሆነ ብድሩን አንጠይቅም ። ምርጫው የነሱ ብቻ ሣይሆን የኛም ጭምር ነው ።

ፕሬዚዳንቱ ይኸንኑ በመቀጠል ሲናገሩ፥

ነገር ግን ይህ ድርጊት የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስተዳደራዊ መዋቀር ለውጥ እንዲደረግ የሦስተኛው ዓለም አገሮች የሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረታዊ ስለመሆኑ ያለንን እምነት ያጠናክረዋል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ድርጅቱ በሀብታም አገሮች ውስጥ የሚገኙ ጠንካራ የኢኮናሚ ኃይሎች በደሀ አገሮች ላይ ያላቸውን የበላይነት ማጠናከሪያ መሣሪያ ከመሆን ተላቆ በእርግጥ ዓለምአቀፋዊ ፣ በእርግጥም የሁሉም አባል አገሮች መሣሪያ ሆኖ ማገልገል ይገባዋል ።[25] ብለው ነበር ።

የጃማይካ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ማይክል ማንሊ ፣ በ1979 ስለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሲናገሩ እንደዚህ ብለው ነበር ፤

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለኢኮኖሚ ችግሮች መፍትሄ አድርጐ የሚያቀርባቸው ሀሳቦች በለሙ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የዳበሩና ለእነርሱ እንዲያገለግሉ የታቀዱ እንጂ ለማንኛውም በመልማት ላይ ላለ አገር የሚስማሙ አይደሉም ።

በመልማት ላይ ያሉ ኅብረተሰቦች ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች በሥራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ ችግራቸው ሲባባስ እንጂ ሲሻሻል አይታይም ። የድርጅቱ ሀሳቦች በተግባር በሚተረጐሙበት ጊዜ የሚፈጠሩ ችግሮችንም ለመቋቋም የሚያስችሉ ሌሎች መፍትሄ ሀሳቦች ለማመንጨት ድርጅቱ አይችልም ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለአንድ አገር ብድር ለመስጠት ተስማምቶ የተባለው አገር ድርጅቱየሚያቀርባቸውን ሀሳቦች በሥራላይ ካዋለ በኋ የተወሰዱት እርምጃዎች ድርጅቱ ያስገኛሉ ብሎ የሚጠብቀውን ውጤት ሊያስገኙ ሣይችሉ ሲቀሩ ደግሞ ቀደም ሲል ሊሰጥ የተስማማውን ብድር ስለሚያቋርጥ በመጀመሪያ ጣልቃ ሲገባ አቃልላሁ ያለውን የተበዳሪውን አገር የውጭ ምንዛሪ ችግር እንዲባባስ ያደርገዋል ።[26]

በአጠቃላይ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለው ዓላማ የአገሬውን ሕዝብ ፍላጐት በማፈን የውጭ ንግድና ሌሎችም የውጭ ዕዳዎች መክፈላቸውን ማረጋገጥ ፣ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የመንግሥት ሚና እንዲመነምንና የወዝአደሩ ምንዳ ቀርቁ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የካፒታሊስቶች የትርፍ መጠን እንዲያድግ ማድረግ ነው ። ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለኢኮኖሚ ችግሮች መፍትሄ ብሎ በሚያቀርባቸው የ« ማስተካከያ » ፕሮግራሞች አማካኝነት በኋላቀር አገሮች ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያደርግ ለዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የሆኑትን ኢምፔሪያሊስት አገሮች ግን እምብዛም አይቆጣጠራቸውም። ከኋላቀር አገሮች መካከልም የገንዘብ ድር

ጅቱ ተጽዕኖውን የሚያጠናክረው የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ በሚከተሉት ላይ መሆኑም አጋጣሚ ጉዳይ አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል ። [27]

የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የወል የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሣሪያነት አንዳንድ ምሳሌዎች

በጃማይካና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መካከል ከ1974—80 የነበረው ግንኙነት ይህ የገንዘብ ድርጅት በኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሕይወት ላይ የሚያደርገውን ተጽእና ለመመርመር ጥሩ ምሳሌ ይሆናል ።

የገንዘብ ድርጅቱ ጃማይካን የገንዘብ ክፍያ ሚዛን ችግር ያጋጠማት በአገሪቷ ውስጥ የደመወዝ ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ የወጪ ንግድ በመዳከሙ ፣ በአገሪቷ ውስጥ ከፍተኛ የመግዛት ኃይል በመኖሩ የገቢ ንግድ ግደት እና መንግሥት በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ ከመጠን በላይ ጣልቃ በመግባቱ ፣ በልዩ ልዩ የኢኮኖሚው ክፍሎች መካከል ያለው ግንኙነት በመዛባቱና ግለሰቦችና ኩባንያዎች ካፒታላቸውን ከአገሪቷ በማሸሻቸው ነው የሚል አስተሳሰብ ላይ ደረሰ ።

እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባባል የችግሩ መሠረት ካፒታሊስቶችን በሚጎዳ መንገድ ለሠርቶአደሩ እድልዎ መደረጉና የመንግሥት ይዞታን ለማዳበር ሲባል የግል ይዞታ እንዲቀጭጭ መደረጉ ነው ። ስለዚህ የገንዘብ ድርጅቱ ለአገሪቷ የኢኮኖሚ ችግር መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያቀረበውን ፕሮግራም የማይክል ማንሌን ተራማጅ መንግሥት ለመቃወም እንደሽፋን የተገለገለበት መሆኑ ግልጽ ነው ።

በጃማይካ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ችግር በደረሰና መንግሥቱ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር ድርድር ባካሔደ መጠን በሥልጣን ላይ በነበረው በሕዝባዊ ብሔራዊ ፓርቲ (People's National party) እና በመንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛ የርዕዮተ ዓለም ትግል ይካሔድ ጀመር ። በዚያ ሁኔታ በሥልጣን ላይ የነበረው ፓርቲ ግልጽ የሆነ የዕድገት ጉዳና ለመቀየስ ባለመቻሉ ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ኢኮኖሚውን ለመምራት ተሳነው ። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትም በጃማይካ ኢኮኖሚ ላይ የነበረውን ተጽዕና ይበልጥ ለማጠናከር ዕድል አገኘ ።

ጃማይካ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ያቀረበውን ሐሳቦች ለጥቂት ጊዜ ሳትቀበል ከቆየች በኋላ በነሐሴ 1977 በተጠባባቂነት በሁለት ዓመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሚገኝ ብድር ውል በመፈራረም በገንዘብ ድርጅቱ እጅ ወደቀች ። በታኅሣሥ 1977 ከተፈቀደላት ብድር ውስጥ 30% የሚሆነውን ብቻ እንደወሰደች ቀደም ሲል ስምምነት በተደረሰበት የ«ተግባር» መመዘኛ መሠረት ጃማይካ የገንዘብ ድርጅቱ የሚፈልገባትን ለውጥ ሙሉ በሙሉ ሳታሟላ ቀረች ። በዚህ የተነሳም ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የብድሩን ፕሮግራም አቋርጦ በአገሪቱ ላይ ከበፊቱ የበለጠ ተጽዕና ሊያሳድር የሚችል ሌላ የ«ተግባር» ፕሮግራም ላይ የሚያደርስ አዲስ ድርድር እንዲካሔድ አጥብቆ አሳሰበ ። በሰኔ ወር 1978 በተደረገው አዲስ ስምምነት መሠረትም የጃማይካ ዶላር ዋጋ በ49% ዝቅ እንዲል ተወሰነ ። እንዲሁም ተጨማሪ 180 ሚሊዮን የጃማይካ ዶላር ቀጥታ ባልሆነ ቀረጥ አማካኝነት ከሕዝቡ እንዲሰበሰብና የዋጋ ቁጥጥር እገዳ እንዲነሳ ተደረገ ። በብድር ፕሮግራሙ የመጀመሪያ ዓመት ውስጥም የዋጋ መጠን በ45 በመቶ እንዲጨምርና የምንዳ ጭማሪም ከ15% በላይ እንዳይዘል ዕቅድ ወጣ ።

ሆኖም የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት «የማስተካከያ» ፕሮግራም የሕዝቡ የኑሮ

Digitized by Google

በጃማይካ የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተፅእኖ ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ አስነስቶ ነበር

Digitized by Google

ሁኔታ ይበልጥ እያሽቆለቆለ እንዲሔድ ከማ
ድረግ በቀር የኢኮኖሚው ሁኔታ ምንም
ዓይነት የመሻሻል ምልክት እንዲያሳይ አል
ረዳም ። በ1978 እርግጠኛ ምንዳ በ35%
አቆለቆለ ። የሠራተኛው ገቢ ከብሔራዊ
ገቢ አንጻር ከ55.2 ወደ 52.3 ዝቅ አለ ፤
አማካይ እርግጠኛ የነፍስ ወከፍ ፍጆታም
በ13% ቀነሰ ። በሚቀጥለው ዓመት የኑ
ሮው ሁኔታ ማሽቆልቆሉን ሲቀጥል ፣ በሕ
ዝባዊ ግልጋሎት በተለይም በትምህርትና
በጤና በኩል የነበረው ችግር በመባባሱ አ
ስጊ ሁኔታ ተፈጠረ ። በሌላ በኩል ደግሞ
ለውጭ ዕዳ ክፍያ የሚወጣው ወጪ እየጨ
መረ በመሔዱ የክፍያ ሚዛን ዴፊሲት እየ
ሰፋ ሔደ ። ምንም እንኳ ከፍተኛ የገንዘብ
ዋጋ ቅነሳ የተደረገ ቢሆንም የወጭ ንግድ
መጠን ዕድገት በጣም አዝጋሚ በሆነ መን
ገድ ሲያንሰራራ የገቢ ንግድንም ለመቀነስ
የተቻለው እጅግ ጥብቅ የሆነ የገቢ ንግድ
ቁጥጥር ዘዴን በመጠቀም ነበር ።የግል ን
ግድ ዘርፍ ትርፍ ቢያድግም እንኳ የግል
መዋዕለንዋይ ጭማሪ አላሳየም ። እርግ
ጠኛ ብሔራዊ ገቢም በ1978 እና በ1979
በ2% አቆለቆለ ።

ጃማይካ ምንም እንኳ የ«ተግባር» መመ
ዘኛውን ለማሟላት ጥረት ብታደርግም ከ
ቁጥጥሯ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ሳታሟላ
ቀረች ። ካጋጠሟትም ዋና ዋና ችግሮች
መካከል የነዳጅ ዋጋ ከተገመተው በላይ
መናር ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋጋና የወ
ለድ መጣኔ ከታሰበው በላይ መጨመር ፣
እንዲሁም የእርሻ ምርትና ወጪ ንግድን
ሊቀንስ የቻለ የጐርፍ መጥለቅለቅ ይገ
ኙባቸዋል ።. ሆኖም በ1979 መጨረሻ
ላይ የሁለተኛውን ዓመት ፕሮግራም የ«ተ
ግባር» መመዘኛ ለማሟላት አልቻለችም
በሚል ሳቢያ የገንዘብ ድርጅቱ ሊሰጥ የተ
ስማማውን ብድር እንደገና አቋረጠባት ።

ከዚያም በኋላ የጃማይካ መንግሥት አ
ዲስ የብድር ፕሮግራም መደራደር ከፈለገ
ወጪውን በ20% ለመቀነስ በቅድሚያ
ቃል እንዲገባ የገንዘብ ድርጅቱ ጠየቀ።ድ
ርጅቱ በዚህ ዓይነት ጃማይካን በመዳፉ
ውስጥ ለማስገባት ሲጥር በ1980 የማ
ንሊ መንግሥት ከዚሁ ድርጅት ጋር የጀ
መረውን ድርድር አቋርጦ በዚያው ዓመ
ት አጠቃላይ ምርጫ እንደሚደረግ አስታ
ወቀ።መሪው ፓርቲም በምርጫው ውድድር
ወቅት የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ሴራ
እንደዋነኛ ጉዳይ አድርጐ ለማቅረብ ጥረት
አደረገ ። ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ፣
የፓርላማው ተቃዋሚ ወገንና ጠንካራ የኢ
ኮኖሚ የነበረው የግል የኢኰኖሚ ይዞታ
ዘርፍም በመተባበር የማንሊን መንግሥት
ለመጣል ተባበሩ ። የማንሊ መንግሥትም
በአጠቃላይ ምርጫው ተሸናፊ ሆነ ። በም
ትኩም በኤድዋርድ ሲአጋ የሚመራው ወግ
አጥባቂውና የኢምፔሪያሊዝም ደጋፊ የሆ
ነው የጃማይካ ሌበር ፓርቲ ሥልጣን ያዘ ።
ከዚህ የመንግሥት ለውጥም በኋላ፣ ሳይውል
ሳያድር አዲሱ መንግሥትና ዓለም አቀፍ
የገንዘብ ድርጅት ድርድሩን ቀጥለው አዲ
ስ ስምምነት ላይ ተደረሰ ።

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት በጃማይ
ካ ሕዝብ ላይ የፈጸመውን ሴራ በሚተነትን
አንድ ጽሑፍ ውስጥ ጊርሻንና ቤርናል የተ
ባሉት ጸሐፊዎች ለሌሎች ኋላቀር አገሮች
ም ጠቃሚ ትምህርት ይሆናሉ የሚሏቸው
ን ነጥቦች ጠቁመዋል ። ከነዚህም መካከል
የሚከተሉት ይገኛሉ ።

1/ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅተ ሆን ብሎ
ሶስተኛው ዓለም አገሮች ለመከተል የሚ
ፈቸውን አንዳንድ የዕድገት አቀጣጫዎ
ችና ፈለጐች ማደናቀፍንና እነዚሁ አገ
ሮች ሌሎች የተለመዱ የዕድገት ስትራቴ
ጂዎች እንዲከተሉ ተጽእና ማድረግን ሆን
ብሎ የሚከተለው ተግባር አድርጐታል።
ድርጅቱም ይህን ሚና የሚጫወተው የዓ
ለም አቀፍ የባንክ ሥርዓትን ፣ የዓለም
አቀፍ ኩባንያዎችንና የቀንደኛ ካፒታሊ
ስተ አገሮችን ጥቅም በመወከል ነው ፤

Digitized by Google

2/ ይህንንም ለማድረግ ይችል ዘንድ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በሶስተኛ ዓለም አገሮች ፖለቲካና ኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ግደታ ይሆናል ። በዚህም አዲስ ዓይነት የዕድገት ፈለግ የሚደገፉ የኅብረተሰቡ ኃይሎች የፖለቲካ አቋማቸው የሚዳከምበትንና የገንዘብ ድርጅቱ የመረጠውን የኢኮኖሚ አቀጣጫ የሚደገፉ የኅብረተሰቡ ኃይሎችና የፖለቲካ ተወካዮቻቸው ሥልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ ያመቻቻል ።

3/ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለአሠራሩ እንዲያመቸው የፖለቲካና የርዕዮተዓለም አድልዎ የሌላቸው አስመስሎ በሚያቀርባቸው ቴክኒካዊና ሳይንሳዊ በሚላቸው ትንተናዎች መጋረጃ በመጠቀም ሥውር የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም አላማዎቹን ተግባራዊ ያደርጋል ።

4/ ከዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር ግንኙነት ባለው በማንኛዋም የሶስተኛ ዓለም አገር ውስጥ በመንግሥትና በመሪው ፓርቲ ውስጥ ቀራኒዎች ካሉ ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፍልስፍናን ፣ የኢኮኖሚ አመራርንና ሕዝባዊ ተሳትፎን የሚያቀናጅ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ከሌለ ሁኔታው ለዚያ መንግሥት በፖለቲካ ሥልጣን ላይ መቆየት እጅግ አስጊ ሊሆን ይችላል ።[28]

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከብዙ ሌሎች ኋላቀር አባል አገሮች ጋር ያለው ግንኙነትም ከሞላ ጎደል በጃማይካ ከደረሰው ሁኔታ ጋር በጣም ይመሳሰላል ። ለምሳሌ በ1978 ፔሩ የነበረባትን የተጠራቀመ የውጭ እዳ ቀስ በቀስ ለመክፈል ያስችላታል በሚል ሳቢያ «የማስተካከያ» ፕሮግራም ወጥቶላት በተግባር እንድትተረጉመው ተደረገ ። በዚህ መሠረት የመንግሥቱ በጀት ከዴፊሲት እንዲወጣ ይረዳል በማለት ለሕዝቡ ይደረግ የነበረው የዋጋ ድጐማና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በጣም ቀነሱ ። በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበሩ የማምረቻ ድርጅቶችም ተመልሰው ለግል ባለይዞታዎች እንዲሸጡ ተደረገ ። ይህ አልበቃ ብሎ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተወካዮች የገንዘብ ሚኒስቴሩን በቀጥታ ቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ ። በዚህም ሳቢያ ከሠራተኛው ሕዝብ መሀል 45% በመቶ ያህሉ ሥራ አጥና ከፊል ሥራ አጥ ሆነ ። ተመጣጣኝ የምንዳ ዕድገት በሌለበት ሁኔታም የዋጋ ንረት በዓመት 75% ደረሰ ። ይህም ኢኮኖሚውን ያሽመደመዱትን ተከታታይ የሥራ ማቆም አድማዎች አስከተለ ።

ዛየር በ1978 የውጭ እዳዋን ለመክፈል ከባድ ችግር በገጠማት ወቅት ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የአገሪቷን አበዳሪዎች በመወከል ጣልቃ ከገባ በኋላ ኢኮኖሚውን በቁጥጥሩ ሥር አስገባ ። አንድ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ተወካይ የዛየርን ማዕከላዊ ባንክ እንዲመራ ሲላክ ፣ ሌላው ደግሞ የአገሪቱን የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያስተዳድር ተደረገ ። እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት በዛየር ላይ የወሰዳቸው የኢኮኖሚ እርምጃዎች ውጤት በሌሎች አገሮች ከታዩት የተለየ ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ፣ አገሪቱ እራሷን በራሷ የማስተዳደር መብቷን ማጣቷ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አለመሆኑንም ጭምር ነው ።[29]

በሱዳንና በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት መካከል በቅርቡ በ1982 መጀመሪያ አካባቢ በተደረገ ስምምነት መሠረት የ «ተግባር» ፕሮግራም በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል ። በዚህ ፕሮግራም መሠረት ምንም ዓይነት ተመጣጣኝ የምንዳ ጭማሪ ሳይኖር የስኳር ፣ የስንዴና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ እንዲደረግ ተወስኗል ። በተጨማሪም የመንግሥት ወጪ እጅግ እንዲቀንስ ተደርጓል ። ይህንኑ ፕሮግራም በመቃወም በተደረጉ ሕዝባዊ አመፆች ሳቢያም በሀገሪቱ

Digitized by Google

የተለያዩ ክፍሎች የሕይወትና የንብረት መጥፋት ደርሷል ። [30]

ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የታንዛንያን ኢኮኖሚም በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ እንዲሁ ጥረት ማድረጉን አላቋረጠም ። ሁኔታው ያስቆጣቸው ፕሬዚዳንት ኒየሬሬ በ1980 ታንዛኒያ ለሚገኙ ዲፕሎማቶች ባስተላለፉት የአዲስ ዓመት መልዕክት ውስጥ « ለመሆኑ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሚኒስቴር የሆነው ከመቼ ወዲህ ነው ? መንግሥታትስ ውሳኔ የመስጠት መብታቸውን ለሱ አሳልፈው ለመስጠት የተስማሙት መቼ ነው ? » [31] ብለው ነበር ። ብዙ ኋላቀር አገሮችም እነዚህን የፕሬዚዳንት ኒየሬሬ ጥያቄዎች በአሁኑ ወቅት ማንሳት ይኖርባቸዋል ።

የአዲሱ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓት አስፈላጊነት

ከዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ልምድ ግምገማ እንደምንረዳው ኋላቀር አገሮች የዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓት በአዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መሠረት ባጠቃላይ እንዲለወጥና ለጊዜው አጣዳፊ የሆኑ ችግሮችን ለማስወገድ ደግሞ የአጭር ጊዜ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግፊት ማድረግ አለባቸው ። ይህ በረጅም ጊዜ ትግል ወደፊት መቋቋም የሚኖርበት አዲሱ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ሥርዓት ሊኖሩት ከሚገባ ዋና ዋና ገጽታዎች መካከል ዲሞክራሲያዊ ሥራ አመራርና ቁጥጥር ፣ ሁለንታዊነት እና አባላት በውጭ የገንዘብ ግንኙነታቸው ሊገለገሉበት የሚችሉ የራሱ የሆነ ጠንካራ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዓይነት ማውጣት ይገኙበታል ። አዲሱ የገንዘብ ሥርዓት የአብዛኞችን የዓለም ሕዝቦች ጥቅም በቅድሚያ ሊንከባከብና ሊያዳብር የሚችለው ፣ አባላት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሥራውን ሊመሩትና ቁጥጥር ሊያደርጉበት ሲችሉ ብቻ ነው ።

እንደ አሜሪካ ባሉ ጥቂት ሀያላን ኢምፔሪያሊስት አገሮች ቁጥጥር ሥር ያለ ዓለም አቀፍ ድርጅት የአብዛኛውን የዓለም ሕዝቦች ጥቅም ሊንከባከብ ይችላል ማለት ዘበት ነው ። አዲስ የሚቋቋመው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሁለንታዊ መሆን የሚገባው የንግድና የሌሎች አይነቶች የገንዘብ ግንኙነቶችም ይበልጥ ዓለምአቀፋዊ እየሆኑ መምጣታቸው ነው ። ስለዚህ በዚህ ዓለም አቀፍ የሆነ መተሳሰር ምክንያት ሁሉም የዓለም አገሮች በአዲሱ የገንዘብ ሥርዓት መሳተፋቸው የግድ ይሆናል ። በአሁኑ አሠራር ለምሳሌ የሶቭዬት ኅብረትና የሌሎችም የአብዛኛዎቹ የሶሻሊስት አገሮች አባል አለመሆን ዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ዓለም አቀፍነት የተሟላ እንደማያደርገው አያጠራጥርም ። አዲሱ ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓት ለዓለምአቀፍ ልውውጥና እንደተቀማጭነት የሚያገለግል በእርግጥም ዓለምአቀፋዊ የሆነ ጠንካራ ገንዘብ ማስገኘት ይኖርበታል ። ይህም ዓለም አቀፋዊ ገንዘብ አንድ አገር ከሌሎች አገሮች ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ አሳትሞ የሚያሰራጨውንና ዋጋውን በግሉ የሚወስነውን የራሱን ገንዘብ ይህን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ባለማስቻል በአሁኑ ጊዜ ከሚታየው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ቀውስ ለመውጣት የሚያስፈልግ አንድ ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት ይረዳል ።

አዲሱን ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓት የመመሥረቱ ሂደት ያለ ጥርጥር እጅግ አድካሚና ረጅም ጊዜን የሚወስድ በመሆኑ ፣ ኋላቀር አባል አገሮች ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር ባላቸው ግንኙነት በአንድነት ተባብረው ድርጅቱ ከዚህ እንደሚከተሉት ያሉ የአጭር ጊዜ እርምጃዎችንም እንዲወስድ መገፋፋት አለባቸው ። አንደኛ ፣ የገንዘብ ድርጅቱ ዲሲፕሊን በተሞላው መንገድ ለኢኮኖሚያቸው ዕድገት ከፍተኛ ጥረት በማድረጋቸው ምክንያት የውጭ ምንዛሬ ችግር ለሚያጋጥማቸው ኋላቀር

Digitized by Google

አባል አገሮች ተገቢውን ዕርዳታ ለማድረ
ግ ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት ። የዚህ ዓይ
ነቱ ዕርዳታ በሚደረግበትም ጊዜ ተበዳሪ
ዎች እንዲገቡ የሚጠየቁት ግዴታ የፈለጉ
ትን የዕድገት ፈለግ የመከተል መብታቸው
ን በምንም ዓይነት መጻረር የለበትም።በተ
ለይም ሥር ነቀል ለውጥ ፣ ብሔራዊ የኢኮ
ኖሚ ዕቅድና በኢኮኖሚው መስክ ለማኅበ
ራዊና ለመንግሥት ይዞታዎች ከፍተኛ ቦታ
መስጠት ላይ የሚያተኩር ስትራቴጂ የሚ
ከተሉ አገሮች ላይ ምንም ዓይነት የቅጣት
እርምጃ መውሰድ የለበትም ። እንዲያውም
እነዚህ አገሮች እንዲህ ዓይነቱ የዕድገት ስ
ትራቴጂ የሚያስከትላቸውን ችግሮችና እ
ንቅፋቶች ለመወጣት ይችሉ ዘንድ ዕርዳታ
ሊደረግላቸው ይገባል ።

ሁለተኛ ፣ ኋላቀር አባል አገሮች ከገንዘ
ብ ድርጅቱ ብድር ሲሰጣቸው እነዚህ አገ
ሮች በአብዛኛው የሚደርስባቸው የክፍያ
ሚዛን ዴፊሲት ችግር እራሳቸው ሊቆጣጠ
ሯቸው ከማይችሉአቸው ሁኔታዎች የሚ
መነጭ መሆኑ በማያሻማ መንገድ መታወ
ቅ አለበት ። ከእነዚህ ሁኔታዎችም መካከ
ል ከፍተኛ ዓለምአቀፋዊ የዋጋ ንረት ፣ ዝ
ቅተኛና ዋዣቂ የሆነ የኋላቀር አገሮች የወ
ጪ ንግድ ዋጋ፣ ኋላቀር አገሮች ለውጭ ገበ
ያ የሚያቀርቧቸው ሸቀጣ ሸቀጦች ተፈ
ላጊነት ዝቅተኛነት ፣ የኋላቀር አገሮች የወ
ጪ ንግድ ዋጋ ከገቢ ንግዳቸው ዋጋ ጋር ሲ
ነጻጸር ማሽቆልቆልና ከፍተኛ የዓለም አቀ
ፍ ወለድ መጣኔ ይገኛሉ ። እነዚህ ሁኔታ
ዎች በሞላ ፣ የአሁኑ ዓለምአቀፍ የገንዘብ
ቀውስ በአጠቃላይም ፍትሕ የጎደለው የ
አሁኑ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ነጸ
ብራቅ መሆናቸው አሌ ሊባል አይችልም።
በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት የሚፈጠሩ
የውጭ ምንዛሪ ችግሮችን ለመቋቋም የሚ
ረዳ ብድር የገንዘብ ድርጅቱ በሚሰጥበት
ጊዜ ብዙ ግዴታዎችን ማጓላት የማያስጠ
ይቅና ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ባጭር ጊዜ ው
ስጥ ሊወሰንና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል
መሆን አለበት ።[32]

ሶስተኛ ፣ በዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅ
ት የኢኮኖሚ ትንታኔና መፍትሔ ብሎ የ
ሚያቀርባቸው ሐሳቦች ኢሳይንሳዊነት በ
ሚገባ መጋለጥ ይኖርበታል ። የዚህ ዓላማ
ም የገንዘብ ድርጅቱ እስካለ ድረስ የክፍያ
ሚዛን መዛባት ችግርን ለመወጣት ብልሃ
ት የተመላባቸውና የተሻሉ ዘዴዎች መኖ
ራቸውን ተገንዝቦ የማንኛውንም አባል አ
ገር መብት በማይጻረር አኳኋን ግንኙነቱን
እንዲያካሂድ ማስቻል ይሆናል ። በገንዘብ
ድርጅቱ አሠራር በኩል ያለው አደናጋሪ
የሚስጥር ሽፋንም በይፋ እንዲገለጥ ግፊት
መደረግ አለበት ። በዓለም አቀፍ የገንዘብ
ድርጅትና በአባል አገሮች መካከል የሚካ
ሔዱ ድርድሮችና ስምምነቶች ታትመው
በይፋ መውጣት ይኖርባቸዋል ። ተበዳሪ አ
ገሮችም ከዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅትጋር
ያላቸውን ግንኙነት በሚመለከት በመካከ
ላቸው የሐሳብ ልውውጥ ማድረግ አለባቸ
ው ። አራተኛ ፣ እንደ የ«ማስተካከያ» ፕሮ
ግራም ባሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በአባል አ
ገሮችና በገንዘብ ድርጅቱ መካከል ከፍተ
ኛ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ፣ በጉ
ዳዩ ጣልቃ ገብቶ የሚያስማማ አንድ ገለል
ተኛ የሆነ አካል መፍጠር መወሰድ ያለበ
ት አንድ የአጭር ጊዜ እርምጃ ሊሆን ይገ
ባዋል ።

ለማጠቃለል ያህል ፣ ዓለም አቀፍ የገን
ዘብ ድርጅት አሁን ባለበት ሁኔታ በቅድ
ሚያ የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝምን ጥቅም
እንደሚያስጠብቅ አያጠራጥርም ። ስለዚ
ህም ሥርነቀል ለውጥ በማካሔድ ላይ ያሉ
ና ለማካሔድ የሚሹ ኋላቀር አገሮች ካለፉ
ልምዶች በመማር ፣ በአንድ በኩል ለአዲሱ
ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እየታገሉ
በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ዋነኛ ዓላማው የተያያ
ዙትን የለውጥ ሂደት መግታት በሆነው በዓ
ለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መዳፍ ውስጥ

Digitized by Google

ላለመግባት ነቅተው መጠበቅ አለባቸው ። ይህን ለማድረግ እነዚህ አገሮች በገቢ ንግድ ላይ ወቅታዊና ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግና ለአገር ውስጥ ምርት ዕድገት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ። ኋላቀር አገሮች ፥ በተለይም የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ፥ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ያላቸውን የኢኮኖሚ ግንኙነት የገድ ማጠናከር ይኖርባቸዋል ። በተጨማሪም የኋላ ቀር አገሮች መንግሥታት ወርቶአደር ችን በኢኮኖሚ ዕድገት ሂደት ትግሉ ለሚጠይቀው መስዋዕትነት ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ ፥ የትምህርት ሥርዓትና የማደራጀት ተግባር ማካሔድ ይኖርባቸዋል ።[33] የተሻለ ኑሮ እንደሚያስገኝላቸው ከተገነዘቡ ፥ ወርቶአደር ሕዝቦች በሙላ መስዋዕትነትን በፈቃደኝነት ለመክፈል ዝግጁ ሆነው እንደሚገኙ አያጠራጥርም ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Jack Woddis, *Introduction to Neo-Colonialism*, the New Imperialism in Asia, Africa and Latin America (New York; International Publishers, 1967). P. 93; Kwame Nkrumah, *Neo-Colonialism* — The Last Stage of Imperialism (New York: International Publishers, 1965), pp. 242-43.
2. "Background Notes on the International Monetary Fund," *Development Dialogue*, No. 2 (1980), pp. 95-96.
3. A.W. Hooke., *The International Monetary Fund*: Its Evolution, Organization and Activities (Washington, D.C.: IMF, 1981), pp. 71-75.
4. Ismail — Sabri Abdalla, "Bretton Woods and the Dollar Standard," *Development Dialogue*, No. 2 (1980), pp. 27-30, 54. Norman Girvan, "Swallowing the IMF Medicine in the Seventies", *Development Dialogue*, No. 2 (1980), p. 60.
5. Hooke, p. 2.
6. Vasily Vakhrushev, *Neo-Colonialism: Methods ond Manoeuvres*, (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 208.
7. *Europa Yearbook*, 1981 Vol. I, p. 56; Hooke; p. 59.
8. Dominick Salvatore, *Theory and Problems of International Economics* (New York: McGraw Hill, 1975), pp. 163-69, 176-77.
9. Hooke, pp. 5-7.
10. *Neo-Colonialism*: *Methods and Manoeuvres*, p. 203.
11. *Europa Yearbook*, 1981, Vol. I, p. 55.
12. *Development Dialogue*, No. 2, (1980), pp. 96-97.
13. *Development Dialogue*, No. 2, (1980), pp. 98-99: *Europa Yearbook*, 1981, p. 59.
14. Hooke, pp. 71-75; *Europa Yearbook*, 1981, p. 55.
15. *Neo-Colonialism*: *Methods and Manoeavres*, pp. 203-4; Hooke, pp. 11-13.
16. *Development Dialogue*, No. 2, (1980), p. 100.
17. *Ibid.*, 102.

Digitized by Google

18. *Ibid.*, pp. 107-9; Hooks, pp. 40-55.

19. Cheryl Payer, *Debt Trap* (New York: Monthly Review Press, 1974), p. 33.

20. "The Arusha Initiative," *Development Dialogue*, No. 2, (1980), pp. 13-14.

21. *Debt Trap*, pp. 36-37; *Development Dialogue*, No. 2, (1980), p. 66; *Theory and Problems of International Economics*, p. 155.

22. "The Arusha Initiative," *Development Dialogue*, No. 2, (1980), pp. 13-14.

23. New Internationalist, Leicester (U.K.), No. 69 (Nov. 1978), p. 6.

24. *Neo-Colonialism: Methods and Manoeuvres*, p. 229.

25. "No to IMF Medding. Extract From President Nyerere's New Year Message 1980 to the Diplomats accredited to Tanzania," *Development Dialogue*, No. 2 (1980), pp. 7-9.

26. "Message from the Prime Minister of Jamaica. Hon. Michael Manley, to the South-North Conference on the International Monetary System and the New International Order," *Development Dialogue*, No. 2 (1980), pp. 5-6.

27. "The Terra Nova Statement on the International Monetary System and the Third World," *Development Dialogue*, No. 1 (1980), p. 31.

28. Norman Girvan and Rechard Bernal, "The IMF and the Foreclosure of Development Options: The Case of Jamaica," *Monthly Review*, No. 9, (1982), pp. 34-38.

29. Jeff Frieden, "Borrowing from Commercial Banks by the Less Developed Countries: Past, Present and Future," *Appeal to Reason*, No. 1 (Summer 1980), pp. 68-69.

30. *Keesing's Contemporary Archives*, April 16, 1982, p. 31443.

31. *Development Dialogue*, No. 2 (1980), p. 8.

32. *Ibid.*, pp. 19-20.

33. *Development Dialogue*, No. 1, (1980), p. 33.

Digitized by Google

ሕጋዊ ምርምሮችና አመለካከቶች

ሕግና እድገት
(ክፍል 1)

ለማ ጉተማ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ተብትቦት የነበረውን የብዝበዛና የጭቆና መረብ መበጣጠስና ፍትህ ፣ እኩልነት ፣ ነጻነት ፣ ብልፅግና የሰፈነበት ህብረተሰብ የመገንባቱን ትግል ከተያያዘው የስምንት ዓመታት ጊዜ ሆኖታል ። በነዚህ ጊዜያት ሰፊው ሕዝብ የነበረውን ሥርዓት ፈጽሞ ለማንኮታኮትና አዲሱን ሥርዓት ለመገንባት ያደረገው ትግልና የከፈለው መስዋእትነት እጅግ የከበደ ነው ። ሆኖም ሰፊው ሕዝብ በብዙ አቅጣጫ የላቁ ድሎችን እየተጎናጸፈ ነው ። ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ሊከተለው የሚፈልገው የፖለቲካ መስመርና መርህ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሆኑን በይፋ አውጆ በግልፅ መድረክ እያጠናውና ተግባሩን እያዳበረው ይገኛል ።

ሰፊው ሕዝብ የሚገኝበትን የዕድገት ደረጃና ታሪክ ከሚከተለው ሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለም ጋር በማገናዘብ ፣ በማጤንና የትግሉ ግብ የትና ፤ አቅጣጫውም ወዴት እንደሚሆን ለይቶ ለማየት ጥረቱን እያፋፋመ ፣ በዚሁም ሂደት ውስጥ ተፃ የትግል ምዕራፎችን እየገመገመ የመሸጋገሪያውን ወቅት ለማገባደድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን እያሟላ ይገኛል ። ከፓርቲ ምሥረታ ፤ ለሶሻሊዝም አስተማማኝ መሠረት ከመጣልና ራሱን ለመከላከል የሚያስችል ሕዝባዊ ኃይል ከማጽጽም ባሻገር ያሉትን የትግል መስኮች በዓይነ ሕሊናው እየቃኘ ነው ።

የኢትዮጵያ አብዮት የነበረውን የገዥ መደብ ገርስሶአል ። ርዝራዦቹንም በሰከነ የትግል ዘዴ እንዲያከት ምላቸው እያደረገ ነው ። ዛሬም በሽግግሩ ወቅት ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ መምጣት መሠረቶችን እየጣለ ፣ በዚህም ሠራተኛው

Digitized by Google

ሕዝብ ተገቢውን' የዲሞክራሲ መብቶች ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ እያደረገ ነው ።

ተገቢውን የዲሞክራሲ መብቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ሥልጣናዊ የበላይነትን ፣ የበላይነትን ለማረጋገጥ ደግሞ የማስፈጸሚያ መሣሪያና ዋስትናው የሆነውን «ሕግ» እና የሕግ ንድፈሃሳቦችን ፣ የሕግን ታሪካዊ አመጣጥ ፣ ዕድገትና (የወደፊት) የሂደት አቅጣጫውን ኅብረተሰባችን ደረጃ በደረጃ መገንዘብ ይኖርበታል ። በተለይም የዛሬው የኢትዮጵያ ሠራተኛ ሕዝብ የትግል ዓላማና ዘዴ ፣ ይዘቱ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ኢትዮጵያዊ የሕግ አስተሳሰብ የላቀና የመጠቀ በመሆኑ ፣ የሕግ መሠረታዊ ፍቺውና የፍትሕ አስተዳደር መንፈስ ለኅብረተሰቡ ያለጥርጥር ግልፅ መሆን አለበት ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም በዚህ ረገድ አንዳንድ ሃሳቦችን ለመሰንዘር ነው ።

ሕግና ትርጉሙ

ሕግና ፍትሕን ፣ የሕግ ሙያተኞችና የሕግና የፍትሕ አስተዳደር ሠራተኞች የእውቀት ዘርፍና ብቸኛ ሠፈር አድርገው የሚያዩ ኃይሎች በቁጥር በርከት ያሉ ናቸው ። ይህን የተሳሳተ አመለካከት እንዲሰፍን የሚያደርጉት ደግሞ ይበልጡኑ የቡርዧ አመለካከት ያላቸው የሕግ ሙያተኞች ናቸው ። ይህ አመለካከት የተሳተሳና አደገኛም ነው ። ሕግ ፣ ሕተታዎችና ሥርዓቶች ለብዙሀኑ ባዕድ ፣ ለሕግ ምሁራን ግን ክህነት እንደሆኑ ማቅረቡና እንደሆኑም እንዲቆዩ መመኘትና መስበክ ኢሳይንሳዊ ነው ።

ሕግ ከጊዜና ከቦታ ወይም ከአንድ ኅብረተሰብ ታሪካዊ የዕድገት ሂደትና ከስተቶች ትንታኔ ማለትም ከሁኔታዎች የግንኙነትና የተቃዋሚነት ሳይንስ ውጭ የሚታይ ጉዳይ ሊሆን አይችልም ። ይህም የሚባልበት ምክንያት የኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት የሚመራው በነባራዊ ሕግጋት ስለሆነ ነው ።

ሕግ ፣ የከስተቶችን ዝምድና የሚደነግገውም ሆነ የአንድን ሕብረተሰብ መብትና ግዴታ የሚያውጀው ፣ የአንድ አገር ሕዝብ ግለሰብአዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን የሚነካ ፣ ማናቸውም ዜጋ ከአካባቢውና ከባቢው ማኅበረሰብ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ሥርዓት የሚደነግግ መሣሪያ ነው ። በአጠቃላይ አነጋገር ሕግ «በከስተቶች መካከል ያለ ውስጣዊ እውነታ ላይ የተመሠረተ ግንኙነትና ተደጋጋፊነት ነው ።»[1] ይህ ማይንሳዊ የሕግ ፍቺ ፣ ውስን ከሆኑ ግንኙነቶች አንስቶ ሁለንተናዊ ገጽታ እስካላቸው የሂደትና የከስተት የዝምድና ሁኔታዎች ድረስ ያሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ፣ ይህ ጽሑፍ የሚያተኩርበት የሕግ ፍቺ ግን ከላይ በተመለከተው አጠቃላይ ትርጉም ሥር ፣ በተለይ በተወሰነ ኅብረተሰብ ውስጥ ሥልጣንን ከማረጋገጥ አንስቶ በመንግሥታዊ ሥርዓት ሥር ያሉትን የግንኙነት ቅርጾችና ይዘቶች ፣ እንዲሁም መሠረተ ሃሳቦች በሚመለከት ይሆናል ።

ለዚህም አቀራረብ ሕግ «በተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዲሁም የአንድን ኅብረተሰብ የዕድገት ሥነ ባሕርይ የሚመጥን መንግሥታዊ መለኪያና የግንኙነቶች መደንገጊያ መሣሪያ ነው የሚለውን ፍቺ ይይዛል ።

በመደብ የተከፋፈለ ኅብረተሰብ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው ። ከላይ እንደተመለከተው ሕግም የኅብረተሰብን መብትና ግዴታ የሚለካና የፍትሕን አስተዳደር የሚደነግግ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው የሥልጣን መሣሪያ ስለሆነ ፣ ከኅብረተሰብ የታሪክ ሂደት ውጭ የሚታይ አይደለም ። የሕግ ታሪካዊ አመጣጥና ሂደት

Digitized by Google

ከመደብ ትግል ታሪክ ጋር በቀጥታ የተዛ
መደ ነው ።

የኅብረተሰብ የመደብ ትግል ታሪክ ዲያ
ሌክቲካዊ ሂደት የኅብረተሰብ የዕድገት ታ
ሪክ ነው ። የአንድ ኅብረተሰብ ዕድገት የሚ
ወሰነው ኅብረተሰቡ በአንድ ወቅት በሚና
ረው የኢኮኖሚ ሥርዓትና ይኸም የኢኮ
ኖሚ ሥርዓት ከሌሎች ማኅበራዊ ክስተ
ቶች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ወይም
ዝምድና ነው ። የኢኮኖሚ ሥርዓት በአ
ንድ ወቅት የሚገኝ ስልተ ምርት ፥ ብሎም
የምርት ግንኙነት ውጤት ስለሚሆን ፥
በሌላ አነጋገር የአንድን ኅብረተሰብ የዕ
ድገት ሥነ—ባሕርይ የሚደነግግ ግንኙ
ነት ኅብረተሰቡ ካለበት ወይም ከነበረ
በት መደባዊ ሥርዓት ነጥለን ልናየው አን
ችልም ። ማርክስና ኤንግልስ ሕግን ፥
በይዘቱ ፥ ዓላማውና ተፈጥሮው በኢኮኖሚ
ሚዛን እንደሚለካ የኅብረተሰብ ላዕላይ መዋ
ቅር፤[2] አርገው የተመለከቱትም ለዚህ ነው።
በላዕላይ መዋቅርነቱም ሕግ ተጻራሪ መደ
ቦች ባሉበት ሥርዓት የሚፈጠር፥ የሥርዓቱ
ገዥ መደብ ራሱን በሥልጣን ላይ ለማስ
ቀመጥ ፥ እንዲሁም ለማቆየት የሚጠቀም
በት መሣሪያ ነው ።[3] መሠረቱም የተከፋ
ፈለና የማይታረቅ ቅራኔ ያላቸው መደቦች
መፈጠር ነው ። በዚህ ገጽታው ሕግ ሙሉ
በሙሉ ፖለቲካዊ ቅርጽና ይዘት አለው ።

በኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ሕግ በፖ
ለቲካ መሣሪያነቱ የተለያየ ወገናዊነትን
እያሳየ መጥቶአል ። ወገናዊነቱም ከበላ
ይ ገዥነት ጋር ተጣምሮ የታየ ወይም የሚ
ታይ ነው ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ተጻ
ራሪ መደቦቹ የባሪያው አሳዳሪና በዕቃነ
ት ደረጃ የሚታየው ባሪያው ሆነው ፥ የሚ
ኖረው የበላይ ገዥነት የባሪያ አሳዳሪው ስለ
ሚሆን በዚህ ሥርዓት የሚፈጠረውና የሚ
ሰፍነው ሕግ ወገናዊነቱ ሙሉ በሙሉ ለባ
ሪያ አሳዳሪው ነው ። ለምሳሌ በዚህ ሥር
ዓት ውስጥ የነበረውን የእርሻ አካባቢ የም
ርት መገልገያ መሣሪያዎች ሕጋዊ አከፋ
ፈል ብናይ በሶስት የተከፈለ ሆኖ እናገኘዋ
ለን ።

እነዚህም ፡—

—ግኡዝ የሆኑ የእርሻ መሣሪያዎች ፥

—ፍቺ የሌላቸው ድምጾች የሚያሰሙ
የእርሻ መሣሪያዎች ፥

—መናገር የሚችሉ የእርሻ መሣሪያዎች
ናቸው ።[4] በዚህ ሕጋዊ አከፋፈል ሥር የመ
ጀመሪያው አካፋ ፥ ዶማና ፥ ጋሪ የመሳሰ
ሉትን ፥ ሁለተኛው በሬና ላም የመሳሰሉ
ትን የሚይዝ ሲሆን ፥ ሶስተኛው ክፍል ባሪ
ያዎቹን የሚመለከት ነበረ ።

በፊውዳሉ ሥርዓት የሚኖረው የበላይ
ገዥነት ደግሞ የፊውዳሉ አምባገነንነት ስለ
ሚሆን ፥ በዚህ ሥርዓት ማኅበር የሚኖረው
ሕግ የፊውዳሉን ሥልጣን የሚያስጠብቅ
ይሆናል ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት የካፒታ
ሊስቱን፥ በሶሻሊስቱ ኅብረተሰብ የሠራተኛ
ውን መደብ የበላይነት ማስጠበቂያ ስለሆነ
ወገናዊነቱ ለገዢው መደቦች ይሆናል ።

በተለይም በባሪያ አሳዳሪው ፥ በፊው
ዳሉና በካፒታሊስቱ ሥርዓት ማኅበሮች ብ
ዙሀኑ ሙሉ በሙሉ የገዥ መደቦች ሕጐች
ተገዥዎች ስለሚሆኑና ሕግ ራሱ ከንትርጓ
ሜው ከግል ባለሀብትነት ጋር የተጣመረ የ
ገቢ ማስገኛ ሙያም ስለሚሆን ለብዙኃኑ
የበደል ምንጭና ሸክም ይሆናል ።

Digitized by Google



በካፒታሊስት ሥርዓት አለ የሚባለው እኩልነት የውሸት ፈጠራ ነው

Digitized by Google

በተቃራኒው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የበላይነት የሚይዘው ሰፊው ሠራተኛ ሕዝብ ስለሚሆንና የሕግ መደባዊ ባህርይ ሕዝባዊ ስለሚሆን ፥ የኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ግንኙነቶች የሚደነገጉት ፥ የሚሠራጩት ፥ የሚከበሩትና የሚፈጸሙት በራሱ በሠርቶአደሩ ሕዝብ ይሆናል ። አመንጭውም ፥ ፈጻሚውም ፥ አስፈጻሚውም ፥ በአጠቃላይ ባለቤቱ ራሱ ሰፊው ሕዝብ ስለሚሆን የሕግ ንድፈሃሳብ ፥ የተደነገጉት ሕጎችና አፈጻጸማቸው በግልጽ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ መታወቅ ይኖርባቸዋል ።

ሕግ በሽግግር ወቅት

በማርክሲስት ሌኒኒስት መሠረተ ሃሳቦች ላይ የተመሠረተ አብዮት የተለያዩ የትግል ክፍሎች አሉት ። እነዚህም የትግል ክፍሎች በማፍረስና በመገንባት ተግባራት የተከፋፈሉ ናቸው ።

የማፍረስ ተግባር ፥ ለእድገት ዕንቅፋት የሆኑትን የማህበራዊ ፥ የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች የማንኰታኰት ተግባር ሲሆን ፥ የመገንባቱ ተግባር ደግሞ ኅብረተሰቡን ወደ ሶሻሊዝም ለማሸጋገር የሚያስችሉትን መሠረቶች የመጣል ተግባር ነው። በሽግግር ወቅት የማፍረሱና የመገንባቱ ውስብስብ ተግባራት የሚካሄዱበት ወቅት በመሆኑ አስቸጋሪ የትግል ወቅት ነው ።

በሽግግር ወቅት ሊኖር የሚችል ሕግና የአስተዳደር ሥርዓት በመሸጋገሪያ ጊዜ ከሚኖሩት ሌሎች ተግሳሮችና የአሰራር ሥርዓቶች ገጽታ ተለይቶ ሊታይ አይችልም ።

በአጠቃላይ አነጋገር የመጀመሪያው የማፍረስ ምዕራፍ እንቅስቃሴ ግብታዊነት ያጠቃዋል ። ለለውጥ በጓጉትና በስሜት በተነሳሱ ጭቁን መደቦችና የፈራሹ ሥርዓት ተጠቃሚ መደቦች መካከል በሚካሄደው የተጧጧፈ ፍልሚያ ምክንያት ለጊዜውም ቢሆን ማዕከላዊነት ሥፍራውን ያጣል ። ሥልጣንም ከሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች ፥ ማለትም ከሚወድመውና ለማውደም ከሚፈልገው ፥ በአንዱ እጅ ገና ሙሉ በሙሉ ተጠናክሮ ስለማይገባ ማዕከላዊነቱ ይጣሰል ። ይሁንና ወደ ኋላ የተቀነባበረና የተጠናከረ ኃይል ያለው ወገን የሥልጣን የበላይነት ይኖረዋል ።

ሕግና ሥርዓት በሕሊና ታስበው ፥ ታውቀው ፥ በዘልማድ ወይም በባሕል የሚከበሩ መሆናቸው ቀርቶ በጠብመንጃ አፈሙዝ የሚከበሩ ይሆናሉ ። ወቅቱም አመጽ ፥ የሞትና የሽረት ትግል የሚፋፋምበት ፥ አንዱ ወገን የግድ በአሸናፊነት መውጣት የሚኖርበት ወቅት ስለሚሆን፥ ሕግ የሁለቱም ተጻራሪ መደቦች ትርጉሞች ተገዥ ይሆናል። ስለዚህም ከአብዮቱ መፈንዳት በፊት የነበረውን ይዘትና ቅርጽ ያጣል ።

ኃይል ሕግ ፥ ሕግም ኃይል ፥ ስለዚህም ኃይል በሕግነቱ የሥልጣን ማፍረሻ ወይም የሥልጣን ማረጋገጫ መሣሪያ ይሆናል ። ፍትሕም የሚመሠረተው በተወሰነ ሕግና አስተዳደር ላይ ሳይሆን በመደባዊ ፥ ተፈጥሮአዊ ስሜት (Class instinct) ላይ ይሆናል ።[5]

በሶቭየት ኅብረት በተለይም በአፍላዎቹ የአብዮት ዓመታት እንደታየው ፥ የአንድ ድርጊት ሕጋዊነት ወይም ሕጋዊ አለመሆን የሚመዘነው በጽሑፍ በሠፈሩ የሕግ አንቀጾች መጠበቅ ወይም መጣስ ሳይሆን ፥ ድርጊቱ የአብዮቱን እንቅስቃሴ የሚመራውን ኃይል (ፓርቲ) ፖሊሲ በመጣሱ ወይም ባለመጣሱ ይሆናል ።[6] ይህ ፖሊሲ በሕግ መልክ የተቀረጸ ወይም ያልተቀረጸ ሊሆን ይችላል። የጥፋትም ከባድነት (ቅጣት) የሚታየው በድርጊቱ ትንሽነት ወይም ትልቅነት ሳይሆን የመደብ ትግሉን በአሸናፊነት መውጣት ለማረጋገጥ በሚኖረው ግምትና ቦታ ነው ።

በነዚህም ጊዜያት የሚፈጠረው ዋነኛ ጥያቄ የመኖር ወይም ያለመኖር ፥ የማሸነፍ ወይም የመሸነፍ ፥ በአጠቃላይ የመደብ የበላይነትን የማረጋገጡ ስለሚሆን ፍትሕ በሰከነ አመለካከት አይመራም ። ወቅቱ የአብዮት እንቅስቃሴ የሚጧጧፍበት ስለሆነ ሕግ መንጭ

Digitized by Google

ቶና ጸድቶ የሚፈጸም አይሆንም ። ለምን ቢባል ይኸንን የሚሠሩ አካሎች ሕልውና ራሱ ጥያቄ ላይ ነውና ።

ሕጉቹም (መመሪያዎችን ጨምሮ) እንደ ጊዜውና እንደወቅቱ ታክቲክ ፣ እንደ ሁኔታዎችም መለዋወጥ ስለሚኖርባቸው ከአብዮት ማግስት ጀምሮ በየደረጃው ከኃይል ሕጋዊነት በመግለጫ መልክ ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅነት መልክ እስከሚወጡ ሕጎች እና ከዚያም በኋላ በሕግ አውጪ አካሎች እስከሚደነገጉ ሕጎች ድረስ፣ እያደጉ ይሔዳሉ ።

ለምሳሌ ፣ በሶቭየት ኅብረት ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት (እ.አ.አ. 1917) ጀምሮ እስከ «ጦር ኮሙኒዝም» 1921 ድረስ) ያለውን የሕግ ሁኔታ ብንመለከት የሚከተሉትን እናያለን ።[7]

—በመጀመሪያው የአብዮት ዓመታት በ ቦልሼቪክ ፓርቲ የሚመራው መንግሥት ያወጣቸው የነበሩት ድንጋጌዎች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅነት ወይም ፍጹም በመግለጫ መልክ ብቻ የሚወጡ ነበሩ ፣

—የሕግ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን ሥልጣን እና የሥነ ሥርዓት ደንቦችን የሚደነግጉትም ሕጎች በአጠቃላይ ልል ሆነው የተቂረጹ ነበሩ ፣

—አብዮታዊ ሸንጎዎች ፍትሕን በማስፈን ረገድ ወሳኝ አካሎች እንደሆኑ ተደርጐ ነበረ ። በዚህም ረገድ እነዚህ ሸንጎዎች ከማናቸውም የገደብ ዓይነቶች ነጻ ነበሩ ፣

—ከአብዮቱ መፈንዳት ጀምሮ እስከ ኅዳር 1918 እ.አ.አ. ማናቸውም ዜጋ እንደ አቃቤ ሕግ ሕግን የማስከበር ሥልጣን ነበረው ። እንዲያውም በ1919 እ. አ. አ. በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መርህ መሠረት ጽኃይልን ለመቀጠብ ፣ የተበታተኑ እርምጃዎችን ለማስተባበርና ለመቆጣጠር መራተኛው የመደብ ጠላቶቹን እንቅስቃሴዎች የሚገደብበት መመሪያዎችን መንደፍ ፣ ከጠላቶቹ ጋር ለሚኖረው ትግል ዘዴዎችን መፍጠር እና እነርሱንም በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ መግርጋነበረበት ።

በትድሚያም ይህ ተግባር «በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት የመሸጋገሪያ ጊዜ ቅርጽ የሚይዘውን አዲሱን የኅብረት ኑሮ ሁኔታ ከሚጻረሩት ወገኖች መታገል ከሆነው ከወንጀለኛ መቅጫ ጋር መዛመድ» እንዳለበት ተገልጾ ነበር ።[8]

የዚህ ዓይነት ተፈጥሮ ያላቸው ሕጎች በአብዛኛው የማፍረሱን ተግባር የሚረዱ የሠራተኛውን ገንባር ቀደም ተዋጊነት የሚያጠናክሩና የመደብ ትግሉን በአሸናፊነት መወጣት የሚያረጋግጡ ሕጎች ነበሩ።

በሶሻሊስት አብዮት የማፍረሱ ተግባር በአብዛኛው ከተከናወነም በኋላ የአድኃሪያንን ፀረ—አብዮት ተልዕኮ መቋቋም እጅግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል ። ይኸም ከሁኔታዎች ጋር በተገናዘበ ፍጥነት ካልተከናወነ በስተቀር በልምድ ፣ በገንዘብና በግንኙነት የላቀው አድኃሪ ፣ ሶሻሊስት አብዮቱን በቀላሉ ሊያጨናግፈው ይችላል ። ይኸንን ለመከላከል የአድኃሪው ርዝራዦች በለመደውና በሚያምኑበት የገደብ ስልት(በሕግ) መገደብ ይኖርበታል ። ከዚህም በተጨማሪ ሕግ ያለፉትን የብዝበዛ ልምዶች አስወጋጅና አዲሱን ሥርዓት አስተዋዋቂ መሆን ይገባዋል ።

በአንድ ዓይነተኛ አብዮት ፣ ሕግ ከኃይል ሕግነት አልፎና ተጠናክሮ የሚገኘው የማፍረሱ ተግባር ከሞላ ጐደል ተሳክቶ በሚገኝበት ጊዜ ነው ። ይኸም ቢሆን ከማፍረሱ ጥረት ውጤቶች ይልቅ ሕግ በኢኮኖሚ ራሱን ከመቻል ትልምና ውጤት ጋር ይበልጥ የተቃረበና የተዛመደ ይሆናል ። ለምሳሌ፣ በሶቪየት አብዮት ሕግ በመደበኛ የሕግ ፍ

Digitized by Google

ቺንቱ ለዕድገት ያኮበኮበው ከ1921—1928 ባሉት ጊዜያት ነበረ ። ይኸም ወቅት እንደ ሚታወቀው የሶሻሊስት ግንባታ ሥራዎች የተቀየሱበትና አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ የሆነበት ወቅት (N.E.P.) ነበረ። በነዚህም ዓመታት ውስጥ የሚከተሉት የሕግ ማውጣት ሥራዎች ተሠርተዋል ።[9]

ከ1922—23 (እ.አ.አ.)

—አዲሱ የሕግ አውጪው ድንጋጌ ፤
—የፍትሐ ብሔር ሕግ ፤
—ያወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤
—የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ
—የመሬት ሕግ ፤
—የሠራተኛ ሕግ ፤

በ1924 (እ.አ.አ.)

—የተሻሻለው የሠራተኛ ሕግ ፤

በ1926 (እ. አ. አ.)

—ተሻሽሎ የወጣው የቤተሰብ ሕግ ፤
—ተሻሽሎ የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤

በአዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዘመናት የወጡት ሕጐችና ደንቦች በሙሉ ፥ በተለይም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጾች መነሻ ያደረጉት መመዘኛ የአዲሱን ኅብረተሰብ ደኅንነትና የፍትሕ ዋስትና ነበረ ።

እ. አ. አ. ከ1921—28 የነበረውን የሶቪየት የሕግ ዕድገት አንዳንድ ኃይሎች እንደ ርዕዮተዓለም ግፈግፊግ አድርገው ወስደውት ነበረ ። እውነቱ ግን ከቅርጽ ግደግ ጋር ሳይሆን ከይዘት ዕድገት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይኸ አልነበረም ። አብዮት እየሰከነ ሲመጣ የሠራተኛው የበላይነትን ለማስፈንና ብሎም ወደ መደብ አልባው ሥርዓት ለመሸጋገር የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ለመፍጠር ከተራ ኃይል ይልቅ ሕግ የተሻለ መግሪያ ይሆናልና ነው ።

ሕግ በአዲሱ ኅብረተሰብ

ከላይ እንደ ተመለከተው ሕግና ፍትሕ ፍጹም የማይወጡ ነገሮች አይደሉም ። በሁሉም የዕድገት ደረጃው የሰው ልጅ በየጊዜው የሚያስፈልገውን ሕግ እየሻረና አዳዲስ ሕጐችን እየአመነጨ መጥቶአል ። በጠቅላላው አነጋገር እነዚህ ሕጐች በአንድ የዕድገት ደረጃ ያሉትን ሕዝቦች ድርጅታዊ ጠባይ የሚያሳዩ መለኪያዎች ሲሆኑ እነዚህ ጠባዮች በተለምዶ እንደ መመዘኛ ነጥቦች ተወስደው ወደ መብትና ግዴታ ይለወጣሉ ። የኅብረተሰብ አባላትም መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩባቸውና ግዴታቸውን እንዲወጡባቸው ይጠበቃሉ ። መንግሥት የዚህ ሕጋዊ ሥርዓት አስፈጻሚ መግሪያ ይሆናል ።

የዕድገት ደረጃቸው ላቅ ባለ አካባቢዎች ሕግ ሰፊ አድማስ ይኖረዋል ። ይኸም የሕግ አድማስ የማምረትን የማሰራጨትንና የልውውጥ ሥራዎችን ግንኙነትና ዝምድናን ያጠቃልላል ፥ የንብረት ባለቤትነት ዝምድናዎችን ፥ በኅብረተሰቡ አካላት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የሥራና የምርት ስርጭትን ፥ የአስተዳደር ቅርጽንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን ይይዛል ፥ የዜጋዎችን ሕጋዊ ሥልጣን ይደነግጋል ። በተጨማሪ ሕግ በወቅቱ በሚኖረው መንግሥት ማኅበራዊ ግንኙነቶች ላይ የሚነሱትን ደባዎች ለመዋጋት የሚያስችሉ ደንቦችን ያወጣል ። በማርክሲስቶች አስተሳሰብ ከላይ የተመለከቱት የሕግ ዝርዝር ተግባራት የሚያተኩሩትም በቅርጽ ላይ ብቻ ነው ። ለማርኪሲስቶች የሕግ መሠረተ—ባሕርይ እና ምንጭ ፥ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው ፥ በአንድ ወቅት ያለ የኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው ። ሕግ ከአካባቢው ሶሲዮ—ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ኑሮ ተነጥሎ መሠረተ—ባሕርይም ፥ መነ

Digitized by Google

ሻም ፥ ዕድገትም ሊኖረው አይችልም ።[10] በማርክሲስቶች አመለካከት ሕግ በሚከተሉት ቁም ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው ።

1/ በመጀመሪያ ሕግ በአንድ አካባቢ ከሚሰፍን ከፖለቲካ ከኢኮኖሚና ከማኅበራዊ ሁኔታዎች ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ።

2/ ሐሳባውያን የሕግ ሊቆች ሊያስረዱን እንደሚሞክሩት የሕግ ምንጮች አማልክታዊ መርሆዎች ወይም ፥ ሌሎች አስቀድመው የነበሩ ሐሳቦች (a Priorideas) ሳይሆኑ የየወቅቱ ሁኔታዎችና ቁሳዊ አስተሳሰቦች ናቸው ።

3/ የሕግ ፍጥረትና የረዥም ጊዜ ዕድገት ከመደብ ቅራኔዎች ከሶስዮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አለመመጣጠንና ውጤቱ ከሆነው ፖለቲካዊ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው ።

4/ የመንግሥት ሆነ የሕግ ታሪካዊ መነሻቸው አንድ ነው ። መነሻቸው ከሰማይ የወረደ ጽላተ—ሙሴ መሳይ ነገር አይደለም ። መንግሥትም ፥ ሕግም ምንጫቸው ተመሳሳይ የሶስዮ ኢኮኖሚ ሂደት ፥ ማለትም የሥራ ክፍፍሎሽ መፈጠር ፥ የግል ሀብት መምጣትና የኅብረተሰብ በማይታረቁ መደቦች መከፋፈል ናቸው ።

5/ ሕግና ርዕዮተዓለም የተደጋጋፊነት ገጽታ አላቸው ። ሕግ በሰው ልጆች የተፈጠረ ስለሆነ የተወሰነን ርእዮተዓለም የሚያንፀባርቅ መግሪያ ወይም በሥልጣን ላይ ያለው መደብ መንግሥት በሚከተለው ርእዮተዓለም መሠረት የሚደነገግ መግሪያ ነው። በአንጻሩ ሕግ የሕብረተሰብና የግለሰብ ንቃተ ሀሊናን ለማነጽ ከፍተኛ ሚናን የሚጫወት ፤ ስለዚህም ለአንድ ርዕዮተዓለም መጠናከር መሠረትን የሚጥል መግሪያ ነው ።

6/በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለሕግ ዕድገት ፓርቲው የሚጫወተው ሚና ወሳኝ ነው ።

7/በመጨረሻም ፥ ሕግ ከመደብ ጋራ የተያያዘ ክስተት በመሆኑ፥ መደብ አልባውና መንግሥት አልባው ሥርዓት ሲሰፍን እንደ መንግሥት ሁሉ የሚከስም ክስተት ነው ።

እነዚህም ቁም ነገሮች በመሠረቱ ማርክሲስቶችና የቡርዧው የሕግ አዋቂዎች የሚለያዩባቸው ናቸው ።

አዲስ ትውልድ ፥ አዲስ ኅብረተሰብ አዲስ ሕግ ያስፈልገዋል ። ሕግ በአዲሱ ኅብረተሰብ ምን እንደሚመስል ለማየት አዲስ ኅብረተሰብ ምን ዓይነት ኅብረተሰብ እንደሆነ ማወቅን ያሻል ።

አዲሱ ኅብረተሰብ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ነው ። ሶሻሊዝም ቁስ አካላዊ መነሻ አለው ። በሶሻሊዝም ሕግ ፤ ቁስአካላዊ መሠረት ስላለው አዲስ ቁስአካላዊ አመለካከትን ይጠይቃል ። ለዚህም ነው ፤ ዛሬ በኢትዮጵያችን ሕግና ፍቺው የላቀና የመጠቀ አመለካከት አለው ተብሎ አስቀድሞ የተገለጸው ።

በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ በተካሔዱ አብዮታዊ ለውጦች መነሻ በሕግ አካባቢ ከፍተኛ ለውጦች ተካሂደዋል ። በአገራችንም እንደዚሁ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ያለው አብዮት የራሱን ሕዝባዊ ሕግ እያወጣና እያስተዳደረ ነው ። በሚያመነጨውና በሚያስተዳድረውም ሕግ የሠራተኛውን ጥቅም የሚያስከብር ፥ የሠራተኛውን የትግል ውጤቶች የሚያስጠብቅና በማናቸውም የማኅበራዊ የዕድገት ጥረቶች የሠራተኛውን ሕዝብ ድል የሚያፋፍም ሕግ እየሆነ እየመጣ ነው ። ይህ የሕግ ለውጥ መነሻ ቢሆንም ገና ብዙ የሚቀረን ነገር ይኖራል ። የሚቀሩንን ምዕራፎች ለማወቅና ለማገባደድ ግን የሰ

Digitized by Google

ሻሊስትን ሕግ ዓላማዎች በሚገባ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል ። የሶሻሊስት ሕግ ዋንኛ ተግባር « ለኢኮኖሚና ለሌሎችም ብሔራዊ የኑሮ መስኮች ዕቅድና አተዳደር ፣ በንግድ ድርጅቶችና በአስተዳደራዊ መዋቅሮች ያሉትን የአመራር ጉዳዮች ለማስተካከልና ሥራና የሠራተኛ ግንኙነቶችን ሥርዓት ለማስያዝ ሲሆን ፣ አስተሳሰቡም ሕዝቡ የጋራ ንብረቱን በሚገባ እንዲጠቀምበት ፣ የተገቢ ዋጋ መርህ ሙሉ በሙሉ በተግባር እንዲተረጎም ፣ በኢኮኖሚውና ማኅበራዊ ፖሊሲ መካከል ያለው አንድነት ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ ነው። ሶሻሊስት ሕግ ኅብረተሰቡ በሕዝባዊና ኢኮኖሚ በትምህርትና በባህል ጉዳዮች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፍ» [11] የሚያበረታታ መሣሪያ መሆን ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕግ በሕግነቱ የሚወሰድና የሚሰፍን አይደለም ። ሕግ ተቀባይነትን የሚያገኘው በሚጫወተው ሚና እና በአስፈላጊነቱ ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሕግን መኖር የሚወስኑት በወቅቱ የሚኖሩት ማኅበራዊ ምክንያታዊ ነጥቦች ናቸው። ከነዚህም ምክንያቶች ዋነኛው የኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ ሥርዓት ባሕርይ ነው ። [12]

የሶሻሊት ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ሥርዓት ባሕርይ በሁለት ዋና ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው ። እነዚህም የምርት መሣሪያዎች ባለቤትነትና የሥርዓቱ በአንድ ፕላን ሥር መከናወን ሲሆኑ ፣ ከባለቤትነት ሁኔታዎች እስከ ማዕከላዊ ዕቅድ ፣ አልፎም እስከ ዝርዝር ድርጊት ፕሮግራምና እስከ ተግባራዊነቱ ፣ ከምርት መሰባሰብና መስራጨት እስከ ሠራተኛው አሰላለፍ ፣ እነዚህንም የሚመለከት አስተዳደር እስከ ማስፈን ያለውን ሁሉ በሥርዓቱ መምራት ስለሚኖርበት ሕግ በዚህ ገጽታው በቅድሚያ አስፈላጊነቱን ይረጋገጣል ።

ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓትን ለማስፈን የሚሰለፉ ድርጅቶች ማለትም ፣ ፓርቲው ፣ መንግሥትና ብዙኃን ድርጅቶች የሚመሩበት መርህ መደንገግ ስለሚኖርበት ለዚህና የዜጎችን ዲሞክራሲያዊ መብትና ግዴታ ለመግለጽ አስፈላጊ ይሆናል ። ሶሻሊስት ባህልን ለማወቅ ፣ ለመመዘንና ለማዳበርም በተገቢው ርዕዮተ ዓለም ላይ የተመሠረተ ወቅታዊ መመሪያ መኖር ስለሚገባው ፣ ይኸም ሕጋዊ ቅርጽ ይዞ መገኘቱ የሚታይ ይሆናል ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሕጉን መኖር ለመወሰን አስፈላጊነቱን ማረጋገጥ አንድ መልኩ ሲሆን ከዚህ ጋር ተዛምዶ የሚታየው ሌላ ከፍተኛ ጉዳይ ደግሞ የሚኖረውን ሕግ በሶሻሊስት መርህ ላይ መመሥረቱን የማረጋገጡ ጉዳይ ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት ሲጀመር ፣ በቅርጹ ፣ በይዘቱ ፣ በዓላማውና በተግባራዊነቱ አዲስ የሆነ የፍትሕ ሥርዓት የመፍጠሩ አስፈላጊነት ግልጽ ሲሆን በመጀመሪያዎቹ የትግል ዓመታት ይኸን ተግባራዊ ለማድረግ ስለማይቻል ከአሮጌዎቹ የሕግ ዓይነቶች አንዳንዶቹ እንዲቀጥሉ ይደረጋል ። የነዚህ ሕጎች መነሻና የድንጋጌአቸውም ዓላማ የተለየ ስለሚሆን ከአዲሱ የሶሻሊስት አብዮት ፍላጎቶች ጋር ተጣምረው ለመጓዝ የማይችሉ ይሆናሉ ። ይኸም ለሶሻሊስት አብዮት ሂደትና ኋላም ለሶሻሊዝም ዕድገት ዕንቅፋት ይሆናል ። ስለዚህም በየወቅቱ ያስፈልጋሉ ተብለው የሚወጡ ሕጎችም ሆኑ በሁኔታ አስገዳጅነት የሚወረሱ ሕጎች በሶሻሊስት መርህ ላይ የተመሠረቱ ወይም የሶሻሊስትን መርህ የማያፋልሱ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል ። ይህ ጉዳይ በሶቢየት ኅብረት ከ1917ቱ የጥቅምት አብዮት ማግስት ጀምሮ የተከሰተ ነበረ ። [13] በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ከሕግ አስፈላጊነት ጋር ትኩረት የሚሰጠው ሌላው ቁም ነገር በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ በብዙኃን ድርጅቶችና በማናቸውም ዜጋ የሕግ

Digitized by Google

ያለግወላወል መጠበቅና መፈጸም ነው ።
ይህ ቁም ነገር ከሶሻሊስት ሕጋዊነት
(socialist legality) መርህ የሚመነጭ ፥
ነገር ግን የቡርዧ የሕግ ሰዎች እንደሚሉት
የሶሻሊስት ሕጋዊነት ብቸኛ ነጥብ ያልሆነ
ነው ።

የሶሻሊስት ሕጋዊነት የመንግሥት የኅ
ብረተሰብ አመራር ዘዴ ሆኖ የሕዝብን
ሶሻላዊና መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲሁም
ሶሻሊስታዊ የማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነቶችን
ለማሳደግ የሚረዳ ዋነኛ መሣሪያ ነው ። [14]

ከሁሉ አስቀድሞ ሶሻሊስት ሕጋዊነት
በሳይንሳዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ፥ የሕዝ
ቦችን ማኅበራዊና መንግሥታዊ ሥርዓት ፥
የዜጎችን መብቶች ፥ ነፃነቶችና ጥቅሞች
የሚቀርጽ እና ማኅበራዊ ዕድገቶችን የሚ
ገዛ ሕግ ማኖርን ይጠይቃል ። ይህምሕግ
ቢያንስ የሚከተሉትን ነጥቦች ማለትም፤

1/ በሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብ
ቶችና ማኅበራዊ ፍላጐቶች ላይ ከተ
መሠረተ ሕገ መንግሥት የመነጨ
መሆንን ፥

2/ በማናቸም መንፈሱ ለሶሻሊዝም
ግንባታና ብሎም ለኮሚኒዝም መም
ጣት መንገድ የሚከፍቱ ንድፈ ሐሳ
ቦችን ያዘለና ለሳይንሳዊ ኮሚኒዝም
ርዕዮተ ዓለም ስርጭት አመቺ ሁኔ
ታን የሚፈጥር መሆንን ፥

3/ የሰው በሰው መበዝበዝን ፥ የመደቦች
ተጻራሪነትንና የብሔሮች ቅራኔን ለማ
ስወገድ የሚያግዝ መሆ ንን ፥

4/ የግለሰቦችን ሥነ—ምግባራዊ ግዴታ
የሚደነግግ ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካ ድ
ሎች የሚያደርሱ ዘላቂ መርሆዎች
ላይ በበማመርኮዝ ጠቅላላ መመሪያ
የሚሰጥ መሆንን ፥

5/ የዜጎችን የማኅበራዊ ፥ የኢኮኖሚ ፥
የፖለቲካና ሌሎችም መብቶችና ነፃ
ነቶችን የሚያስጠብቅ ፥ (ሕግ የማኅበ
ራዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መብቶችና
ነፃነቶች ዋስትና ነው ሲባል ዋስትና
ው የማቴሪያልንና የሕግን ውህደት
ያዘለ ዋስትና ይሆናል ።)ማለትም እነ
ዚህን ነፃነቶች ለማስጠበቅ ቁስ አካ
ላዊ ሁኔታዎችን ለመዘርጋት የሚያ
ግዝ መሆንን ፥

6/ ዓለም አቀፍ ሶሻሊዝምን ለማጠናከር
ለሶሻሊስት ሕጋዊ ሥርዓት ዕድገት
አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑን [15]
ማጠቃለል ይኖርበታል ።

በአጠቃላይ ይህ ሕግ ከላይ የተመለከቱ
ትን አበይት ነጥቦች፥ንመያዝ የሚገባው ቢ
ሆንም ዋነኛ መመዘኛው ዲሞክራሲያዊ ገ
ጽታው ነው።ይህም ፥ ሕጉ በማን ወጣ ወይ
ም ሕጉን ማን አወጣው የሚለውን ጥያቄ
ይጋብዛል ።

ሐቀኛ ዲሞክራሲያዊ ሕጋዊነት ፥ የአን
ድ አገር ሕግ አውጭ አካል በዲሞክራሲ
ያዊ መንገድ እንዲመሠረት ፥ ከተመሠረ
ተም በኋላ የሕዝቡን ፍላጐቶች እንዲገለጽ
እና የኅብረተሰቡን ተራማጅ ዕድገቶችን
እንዲያከብር ይጠይቃል ። ይኸም በአጭሩ
የሶሻሊስት ሕግ አውጭ ሥርዓት መፈጠ
ርን መጠየቅ ማለት ስለሚሆን ሶሻሊስት
ሕጋዊነት ከዚህ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ
ጉዳይ ይሆናል ።

አንድን ሕግ ሕግ የሚያሰኘው፥በአዋጅ የ
መነገሩ ጉዳይ ሳይሆን ተቀባይነት አግ
ኝቶ የመፈጸሙ ፥ የአስገዳጅነት ባሕርይ
ኖሮት የመጠበቁ ነው ። ሕግ ሕግ ለመ
ሆን በሁሉም ዘንድ ተፈጻሚ መሆን አለ
በት ። ለዚህም አስፈጻሚ ሥርዓትን ይፈ
ልጋል ። ሆኖም አሁንም ዲሞክራሲያዊ

Digitized by Google

ሕጋዊነት እንዲኖር የሕግ ተርጓሚና አስፈጻሚው አካል በምርጫው መውጣቱን ሶሻሊስት ሕጋዊነት ይጠይቃል ። [16]

ለመደምደም ያህል ሶሻሊስት ሕጋዊነት በሶሻሊስት ዲሞክራሲ መሠረት የተመሠረተን ሕግ አውጪ ፣ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ፍላጐቶች ላይ የተመሠረተን ሕግ እና በሶሻሊስት ዲሞክራሲ መሠረት የተመረጠን ተርጓሚና አስፈጻሚን መኖርን የሚጠይቅ ሕጋዊነት ነው ። (እዚህ ላይ የዲሞክራሲና የሕጋዊነት ዝምድና በሚገባ ይታያል ።) የሶሻሊስት ሕጋዊነት መሠረተ ሐሳቦች ከላይ የተመለከቱት ናቸው ። እነዚህ ዝርዝር የሶሻሊስት ሕጋዊነት መሠረተ ሐሳቦች በአንድ የኅብረተሰብ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ተሟልተው ሲገኙ በዚያ ኅብረተሰብ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ሶሻሊስታዊ ሕጋዊነት እንደሰፈነ ተደርጐ ሊወሰድ ይቻላል ። ከላይ የተመለከቱትን መሠረተ—ሐሳቦች በተናጠል ወይም በቁንጽል በመውሰድ ወይም ፣ ከነዚህ መሠረተ—ሐሳቦች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ በመስፈናቸው ሶሻሊስት ሕጋዊነት አለ ለማለት አይቻልም ።

ከዚህም በተጨማሪ ሶሻሊስት ሕጋዊነት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው ተፈላጊው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው ። ይኸም ውስስብ ሁኔታዎችን መወጣትን ከመጠየቁም ሌላ ፣ የሶሻሊስት ሕጋዊነትን ሙሉ በሙሉ ግንዛቤና ይኸንን ለማስፈን መንግሥት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ (የሶሻሊስት ሕጋዊነትን ሕጋዊ ዋስትና ጥምር) ከፍተኛነት ጠይቃል ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲን የጠራ አመራርና ከፍተኛ ጥረትም ይጠይቃል ።

ፓርቲና ሕግ

የሶሻሊስትን ኅብረተሰብ የሚመራው ፣ የዕድገት አቅጣጫውና የፖለቲካ ሥርዓቱ የሚቀየሰው ፣ ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን ጠንቅቆ የሚያውቀው የማሌ ፓርቲ ነው ። ፓርቲው የኅብረተሰቡን ዕድገት ጠቅላላ ዕቅድ የሚነድፍ ፣ ኅብረተሰቡ የሚከተለውን የውስጥ እና የውጭ የፖለቲካ መሥመር የሚጠቁም ፣ ሕዝቡን የሚያንቃቃ ታላላቅ ተግባሮችን የሚመራ እና ኮሙኒዝምን ለመመሥረት የሚያስፈልገውን ሳይንሳዊ ምርምር ወደ ዕድገት ዕቅድ የሚለውጥ አካል ነው ። ለዚህም አላማው መንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ለማሰለፍ የሚችለው ፓርቲው ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ፓርቲው ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ ኃይል ነው ።

የአንድ ማሌ ፓርቲ ከፍተኛ የትግል ዓላማ ሥልጣን የሠራተኛው ሕዝብ እንዲሆን የመጣሩ ፣ ለዚህም ሰፊው ሕዝብ በመንግሥትና በማኅበራዊ ጉዳዮች አመራር ውስጥ እንዲሳተፍ የማስቻሉና የማብቃቱ ነው ። ይህ በሌላ አነጋገር የሠራተኛው ሕዝብ የዲሞክራሲ መብቶች መስፈን በመሆኑ ፣ ፓርቲው በሁሉም መስኮች ለዚህ ዓላማ ግብ መምታት የሚሰለፍ ከፍተኛውና የመጨረሻው አካል ነው ። ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው ደግሞ የሰፊውን ሕዝብ እውነተኛ ጥቅም ሊያስጠብቅ የሚችል ሕግና ሕጋዊነት ሊኖር የሚችለው ሰፊው ሕዝብ በእርግጥ የሥልጣን ባለቤት በሆነበት ኅብረተሰብ ብቻ ነው ። ይኸም በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ስለሚሆን ፣ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲዎች ሕግና ሕጋዊነት ከፖሊሲአቸው ጋር የተዛመደ መሆኑን ይቆጣጠራሉ ፣ አመራርም ይሰጣሉ ። [17]

ይህም ስለተባለ ፓርቲው ሕግ አውጪ አካል ነው ማለት አይደለም ። ሕግ አውጪ አካሉን ተክቶ አይሠራም ። ሆኖም ከላይ

Digitized by Google

እንደተጠቀሰው ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልገው የሕግ ሥርዓትና አጠቃላይ ዕድገቱ እንዴት መሆንና መካሔድ እንደሚገባው መመሪያ የሚያወጣው ፓርቲው ነው ።

ፓርቲው የሚወጡትን ሕጎች ከፖሊሲው ጋር መዛመዳቸውን ከማየት ባሻገር የሕጎችን መከበር በጥብቅ ይከታተላል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕግ በግድና በቅጣት ፍራቻ የሚከበር ሳይሆን በንቃት ላይ በተመሠረተ ፈቃደኝነት የሚከበር ነው ። ይኸም የሚደረስበት በፓርቲው ጥብቅና የማያቋርጥ የርዕዮተዓለም ስርጭት ስለሚሆን ፓርቲው ለርዕዮተ ዓለም ስርጭትና ሥርጸቱም ጭምር ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል ።[18]

ሕዝብና ሕግ

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ግለሰቦች ራሳቸውን ከኅብረተሰቡ አግልለው የሚጠበቁባቸው መግሪያዎች ሳይሆኑ ፣ በማኅበራዊና መንግሥታዊ ጉዳዮች ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለግለሰቦች አስፈላጊውን ሁኔታ የሚያመቻቹ መብቶችና ነፃነቶች ናቸው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሰው ልጅ መብት ሶሻሊዝምን ለመገንባት ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የሚገለገልበት ዋነኛ መብት ነው ። ይኸም የሌሎቹ መብቶች ሁሉ መሠረትና ዋስትና ነው ። [19] በአዲሱ ኅብረተሰብ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብት በማናቸውም የመንግሥት ጉዳዮች የመሳተፍና የራሱን መብቶችና ፍላጐቶች ከሰፊው ሕዝብ መብቶችና ፍላጐቶች ጋር የማዋሐዱ ነው ።

ይኸም ሲባል በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የግለሰቦች ሲቪል መብቶችና ነፃነቶች የሉም ማለት አይደለም ። ግን እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ግለሰቦችን ከኅብረተሰቡ መብቶች ውጭ አርገው እያስቀምጧቸው ለማለት ነው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሰፊው ሕዝብ ሥልጣን በሕግና ፍትሕ አካባቢ ያለውንም ሥልጣን ያጠቃልላል ። ከላይ በሶሻሊስት ሕጋዊነት ሐተታ ውስጥ እንደተመለከተው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕግ አውጪው አካል የሕዝቡ ተወካይ ስለሆነ፣ በዚህ አካል የሚወጣው ሕግ በኅብረተሰቡ ፍላጐት ላይ የተመሠረተና የኅብረተሰቡ ሕግ ይሆናል ። ስለዚህም የራሱን ሕግ ራሱ ያከብረዋል ፤ ያስከብረዋል ማለት ነው ።

የሕግ ከማሚነት

ከላይ በተመለከቱት መሥመሮች የሕግን አመጣጥና የዕድት አቅጣጫ በአጭሩ ለማመልከት ተሞክሯል ። ሕግ መደባዊ ክስተት በመሆኑ በመደብ መፈጠር ወቅት ተወልዶ በልዩ ልዩ ሥርዓተ ማኅበራት ልዩ ልዩ ይዘትና ቅርጽ ይዞ መምጣቱ ታይቶአል ። ሕግ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሚኖረውአስፈላጊነትና ፍቺ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶታል ። የሕግ መጨረሻው ግን አልተመለከተምና ፣ በአጭሩ ይኸንን ማሳየቱ ተገቢ ይሆናል ።

ሕግ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የሚደርሰው በሶሻሊስት ስርዓት ውስጥ ነው ። ይኸም የሚሆነው ሶሻሊስት ሕጋዊነት ሲሰፍን ነው ። ሶሻሊስት ሕጋዊነት የሚሰፍነው ደግሞ የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ሁኔታዎች ለዚህ አመቺ መድረኮችን ሲፈጥሩ ነው ።

የሶሻሊስት ግንባታ ጥረት ኮሚኒዝምን እውን ማድረግ ነው ። ይኸም ጥረት የኢኮኖሚው ፣ የፖለቲካውና የማኅበራዊ ጉዳዮች ዕድገት ጥረት ስለሚሆን፣ በነዚህ መስኮች የሚደርስበት እያንዳንዱ የዕድገት ምዕራፍ የሕግ የዕድገት ምዕራፍ ይሆናል ።

በሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ዕድገት ወደ በለጠ ማኅበራዊ ዕድገት ያመራል ። በኮሚኒስት ኅብረተሰብም «ከእያንዳንዱ እንደ

Digitized by Google

ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጐቱ» በሚለው መርህ ይገዛል ። [20] በዚህ ከፍተኛ የሶሻሊዝም የዕድገት ደረጃ ሶሻሊስት ዲሞክራሲ እንደ ፖለቲካዊ ክስተትነቱ መክሰም ደረጃ ላይ ይደርሳል ። «ሰዎች ለእያሌ ምዕተ ዓመታት ያወቋቸውንና ለብዙ ሺህ ዓመታት የከላለሱአቸውን ማኀበራዊ ግንኙነቶችንና የተለመዱ ደንቦችን ቀስ በቀስ ከራሳቸው ሕይወት ጋር ያዋህዳሉ ። ያለ ኃይል፣ያለ ተጽዕኖ፣ያለ ቁጥጥር፣ያለ መንግሥት ፖለቲካዊ ገጽታ በሌላቸው ደንቦች ይመራሉ ።» [21] ስለዚህም ሕግ በዚህ የዕድገት ደረጃ እንደ መንግሥትና እንደ ዲሞክራሲ ሁሉ ይከስማል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. *The Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy,* (Moscow, Prog. Pub., 1974), p. 128.
2. *Robert Conquest, Justice and the Legal System in the USSR,* (London, 1968), p. 13.
3. *Ibid.*
4. *The Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy,* p. 360.
5. Conquest, p. 7.
6. *Ibid.*
7. *Ibid.,* p. 14.
8. *Ibid.*
9. *Ibid.,* p. 15.
10. *The Soviet State and Law,* (Moscow Prog. Pub., 1969), p. 186.
11. Tord Riemann, *Law and Justice in a Socialist Society,* (Berlin, 1976), p. 9.
12. *The Soviet State and Law,* p. 189
13. V. Terebelov, *The Soviet Court,* (Moscow, Prog. Pub., 1978), p. 34.
14. *The Soviet State and Law,* p. 266.
15. A.KH. Makhnenked, *The State Law of The Socialist Countries,* (Moscow, Prog. Pub., 1978), p. 15.
16. Terebelov, pp. 34-35.
17. Conquest, p. 110.
18. *The Soviet State and Law,* p. 206.
19. G. Gurdeau, *Traite de Science Politique,* Vol. VII. (Paris, 1957), p. 493.
20. V.I. Lenin, *On Soviet Socialist Democracy,* (Moscow, Prog. Pub., 1979), p. 23.
21. V.I. Lenin, *Col. Works,* Vol. 25, (Moscow, Prog. Pub., 1974), p. 467.

Digitized by Google

በቀይ ካባ ሽፋን የሚከናወን ፀረ ማርክሲስት ደባ

—የመንዝሊ ሪቪውና የበረከተአብ ሀብተሥላሴ ፀረ ኢትዮጵያ አብዮት ኅብረት

አምሃ መለሰ

አንዳንድ የምዕራባውያን ጋዜጦች ፣ መጽሔቶችና መጽሐፎች ኢምፔሪያሊዝም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ በአፍሪካ ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ የሚያካሂደውን ፀረ ሕዝብ እንቅስቃሴ በማጋለጥ ረገድ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። እነዚህ እትሞች ለአብዮታዊና ብሔራዊ የአርነት እንቅስቃሴዎች የዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማስገኘት ሞክረዋል። ለምሳሌ በ1960ዎቹ ለኩባ አብዮትና ፣ በ1970ዎቹ ደግሞ ለቬዬትናም አብዮት በራሱ በኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ውስጥ ወገናዊ የሆነ ድጋፍ ለማስገኘት ጥሩ መሣሪያ ነበሩ ። እግረ መንገዳቸውንም ዓለምአቀፋዊ የሆነ የፖለቲካ ግንዛቤን በማስፋፋትም ረገድ የተጫወቱት ሚና የሚናቅ አልነበረም ።

እንደዚህ ካሉት እትሞች መካከል __መንዝሊ ሪቪው ፣ አን ኢንዲፔንደንት ሶሻሊስት ጆርናል__ የሚባለው መጽሔት አንዱ ነበር ።ከአዘጋጆቹ አንዱ የሆነው ሟቹ ሊዮ ሁበርማን ያወጣቸው አጫጭር ጽሑፎችና መጻሕፍቱ ብዙ ተራማጅ ትውልዶችን ቀስቅሰዋል ። ከሊዮ ሁበርማን ጋር በመሆን የዜና መጽሔቱ መሥራች ፖል ስዊዚ አሁንም ከሀሪ ማግዶፍ ጋር በመሆን አዘጋጅነቱን ቀጥሏል ። ሀሪ ማግዶፍ የዳበረ ካፒታሊዝምን ባሕርይንና የዘመኑን ኢምፔሪያሊዝም በሚመለከት ዕውቅ ደራሲ ነው። ፖል ስዊዚ ፣ በማርክሲስቶችም ሆነ ማርክሲስት ባልሆኑ ክፍሎች ዘንድ ካለፉት 30 እና 40 ዓመታት ጀምሮ ተራማጅ ከሚባሉት ኢኮኖሚስቶች መካከል አንዱ ሆኖ ቆይቷል ። ሌሎች የዚሁ መጽሔት ጸሐፊዎችና መንዝሊ ሪቪው የሚያሳትማቸው መጻሕፍት

Digitized by Google

ዶራሲያንም በምዕራቡ ዓለም ውስጥ በጣም የታወቁ ግራ ክንፍ ምሁራን ከሚባሉት መካከል ነበሩ ።

ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ፣ ቀደም ሲል ተራማጅ ሆኖ የቆየው የመንዝሊ ሪቪው መጽሔት በተለይ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ እያሽቆለቆለና ጨርሶ ውዥንብር ውስጥ እየገባ ሲሔድ ማየቱ የሚያሳዝን ነው ። አንደኛው የዝቅጠቱ ምልክት የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ለፀረ ኢትዮጵያ አብዮት ኃይሎች በመድረክነት ማገልገሉ ነው ። አለበለዚያ በዛሬይቱ አፍሪካ ታሪክ ውስጥ ፍጹም ሥርነቀል በሚባለው በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ያልተቋረጠ የማጥላላት ዘመቻ ማካሔዱን እንዴት ለመግለጽ ይቻላል ? ።

<u>መንዝሊ ሪቪው</u> የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከት ትርትስካይት ከሆነውና * በአሜሪካ አገር እየታተመ ከሚወጣው <u>ዘ ጋርርዲያን ኤ ራዲካል ኒውስዊክሊ</u> ከሚባለው ጋዜጣ እኩል ለመዝቀጡ ጳሚ ምስክር የሚሆነው የመንዝሊ ሪቪው መጽሔት በቅጽ 32 ፣ ቁጥር 3 ፣ 1980 እትሙ ላይ የኢምፔሪያሊዝም ቡችላና በቀድሞው የኃይለ ሥላሴ የፊውዶ ቡርዧ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆኖ ይሠራ የነበረው በረከተአብ ሀብተሥላሴ የኢትዮጵያን አብዮት ለማንቋሸሽ በመሞከር ያቀረበውን ጽሑፍ [1] ማውጣቱ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወደ መንዝሊ ሪቪው አጠቃላይ አቋም ወደ ኋላ የምንመለስበት ሲሆን ፣ በመጀመሪያ ግን የበረከተአብን ጽሑፍ ይዘት እንመረምራለን ።

በረከተአብ ሀብተሥላሴ በዚህ ጽሑፍ ተራማጅና አልፎ አልፎም ማርክሲስት ለመምሰል ስለ አብዮትና ስለአብዮታዊ ሂደት አንዳንድ ነገሮችን ሰንዝሯል ። ይሁንና አመለካከቱ ከቡርዧ ሶሻል ሳይንስ ክልል አለማለፉን የሚያሳየው ገና በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ አብዮት የሚፈነዳው ከ«አመራር ቀውስ» [2] (Management Crisis) ነው የሚል ሐሳብ ስፍር መገኘቱ ነው። ይኸ «የአመራር ቀውስ» ቲዎሪ በቡርዧ ሶሻል ሳይንስ ዘንድ ተወዳጅነት ያለው፣ ማርክሳዊ ከሆነው ከታሪካዊ ቁስአካልነት ትንተና ጋር የሚጻረር ጭልጥ ያለ የቡርዧ ቲዎሪ ነው ። እንደበረከተአብ አባባል አንድ አብዮት የሚነሳው (የሚፈነዳው) በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ መሠረታዊ ቅራኔዎች የማይፃፉበት ደረጃ ላይ ደርሰው ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች ተመቻችተው ፣ አብዮታዊ ሁኔታ ሲኗላ ሳይሆን ፣ የገዥው መደብ ጥቅሙን የሚያናጉ ቀውሶችን በብልሃት ለመቆጣጠርና ለማረቅ ካለመቻሉ የተነሳ ነው። እንደ በረከተአብ አመለካከት ፣ ከ1966 ጀምሮ ኢትዮጵያን ያጥለቀለቀው አብዮት መንስኤው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ታክቲክን ያለመቀያየርና ጥንቃቄን ያለመውሰድ ፣ እንዲሁም በወሎ ለ200,000 ሰዎች መሞት ምክንያት ለሆነው ረሀብ «ቅድሚያ ትኩረት ለመስጠት ያለ መዘጋጀት» ኃይለ ሥላሴም «ታዋቂ መሰሪነቱን ሊጫወት ሲችል መደናገጡ» ናቸው ። በረከተአብ ሁኔታውን «(የኃይለ ሥላሴ) ያረጁ ነርቮች መሥራት አልቻሉም ። በመሰሪነቱ እንደተለመደው ለመደለል ተሳነው ። አገሪቱንም ሆነ የውጭውን ዓለም እንደበፊቱ ለማታለል

---

* ለጋርዲያን ጋዜጣ ለብዙ ዓመታት የብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ታዋቂ ሪፖርተር (ዘገበኛ) የሆነው ዊልፍሬድ ቡርቺት ጽሑፍ ከሚያቀርቡት ሰዎች አንዱ ነበር ። ለብዙ ዓመታት ለፀረ አብዮትና ለኢትዮጵያ ትርትስካይት ስደተኛ ቡድኖች እንደዋና ልሣን ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ይህ ሣምንታዊ ጋዜጣ ከቡርቺት ጋር ግንኙነት ያቋረጠው ፣ ቡርቺት የካምፑቺያና የኢትዮጵያን አብዮት ትክክለኛ ገጽታ በመመርኮዝ ባቀረበው ጽሑፍ ምክንያት እንደሆነ የታወቀ ነው ።

Digitized by Google

አልተቻለም ፤ » [3] በማለት ያስቀምጠዋል።
ስለሆነም እንደበረከት አባባል ሁልጊዜም
ሥርነቀል ወደ ሆነ የፖለቲካ ለውጥ የሚያ
መራው በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች የአመ
ራር ዘዴ ወይም ችሎታ ማጣት ነው ። ይህ
ም ማለት አንድ የገዥ መደብ በፖለቲካ ሥ
ልጣን ላይ ያስቀመጣቸው መሪዎች ችሎ
ታና ብቃት ካላቸው ተበዝባዥ መደቦች
ዝንተ ዓለም ቢበዘበዙም ሁኔታውን ለመ
ለወጥ አይቻላቸውም ማለት ነው ። የቡር
ዧው መደብ የካፒታሊስቱን ሥርዓት ያማ
ረ ቀለም በመቀባት ዘላለማዊ እንደሆነ አድ
ርጐ የሚቀጥርና እንዲቀጠርም የሚፈልግ
ስለሆነ ፣ ለዚሁ በዝባዥ መደብ ያደሩ ምሁ
ራን በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ ይኸንኑ
ሁኔታ ሊያሳምኑን ቢሞክሩ አይደንቀንም።

እዚህ ላይ የአብዮቶችን አነሳስ በማስመ
ልከት ኤንግልስ ፣ «አብዮቶች ታስበው የሚ
ደረጉ ወይንም ደግሞ በዘፈቀደ የሚደረጉ
እንዳይደሉ ኮሚኒስቶች ጠንቅቀው ያውቃ
ሉ ፤ በማናቸውም ጊዜና ቦታ (ሁኔታ) አብ
ዮቶች ከተወሰኑ ፓርቲዎች አመራርም ሆነ
ከአጠቃላይ ከመደቦች ፍላጐት ውጭ በሆኑ
ሁኔታዎች የሚከሰቱ ናቸው ፤ » [4] ያለውን
ለበረከተአብ ለማስታወስ በወደድን ነበር።
በረከተአብ ሀብተሥላሴ በዚህ ጽሑፉ ው
ስጥ ከዚህም በተጨማሪ ሌሎችን ነጥቦች
አንስቷል ። ይሁንና ማርክሲዝምን እንደ
ፈለገ ለመረዳትና ለመተርጐም የተነሳ በመ
ሆኑ ፣ ማርክሲስት ሊሆን ቀርቶ የተራማጅ
ነት ብልጭታ እንኳ ከማይታይበት ግለሰብ
ጋር የማርክሲዝምን በኩረ ሐሳብ መሠረት
በማድረግ ክርክር ማንሳቱ ፋይዳ አይኖረ
ውም ። ይኸን እዚህ ላይ በማቆም ስለበረ
ከት የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካና ታሪክ ትን
ተና ደግሞ ያሉንን አንዳንድ አስተያየቶች
ለመግለጽ እንሻለን ።

በመንዝሊ ሪቪው መጽሔት ላይ ቀደም
ሲል የተጠቀሰው ጽሑፍ ከወጣ በኋላ የበረ
ከተአብና የመንዝሊ ሪቪው ሰዎች ትብብር
ቀጥሎ በቅርቡ ደግሞ «ግጭትና ጣልቃ
ገብነት በአፍሪካ ቀንድ» (Conflict and
Intervention in the Horn of Africa)
በሚል ርዕስ በረከተአብ የጻፈውን መጽሐ
ፍ የመንዝሊ ሪቪው አሳታሚ ድርጅት አት
ሞ አውጥቶታል ። በረከተአብ በዚህ መጽ
ሐፉ ውስጥ እንደገና እንደ ማርክሲስትና
እንደታሪክ አዋቂ ሆኖ ለመቅረብ ሞክሯል።
እየታበዩ ፣ አገራቸውንና ወገናቸውን ከደ
ው ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮች መዲናዎች
በመቀመጥ ለኢምፔሪያሊዝም ስትራቴጂ
ያዊ ገብ ሙያቸውን ለሸጡ ፣ በክህደትና
በቅጥፈት ብዕር ለሚበሉ እንደ በረከተአብ
ላሉ ሐሳዊ መሲህ ምሁራን ፣ ማርክስ ፣
አስራ ስምንትኛው ብሩሜር በተሰኘው ታ
ዋቂ ጽሑፍ ውስጥ ፣ «ሰዎች ታሪክን እን
ደፈለጉ አድርገው ለመሥራት አይቻላቸ
ውም» ያለውን በዚህ አጋጣሚ ማስታወሱ
አስፈላጊ ይመስላል ።

በረከተአብ ወደ ጻፈው ጽሑፍ ስንመ
ለስ ፣ በጽሑፉ ውስጥ ስለ ብሔረሰብ ጥያቄ
ስለኢትዮጵያ ታሪክ ከማርክሲዝምና ከእው
ነተኛ ታሪክ የራቀ የተምታታ የሐሳብ ክም
ችት እናገኛለን። የብሔርና የብሔረሰብ ጥያ
ቄን በሚመለከት በረከተአብ ከነአካቴው
በብሔርና በብሔረሰብ ፣ በባለብዙ ብሔረሰ
ብቦች አገርና በህዳጣን ብሔረሰቦች መካከል
ያለውን ልዩነት ጨርሶ እንዳልተገነዘበ እን
ረዳለን። በመሆኑም ዘጠኝ የሚሆኑ የተለያዩ
ብሔረሰቦች የሚኖሩባትን ኤርትራን እንደ
አንድ ብሔር ፣ በጐሣዊ ስሜትና በቅጥረኝ
ነት የተነሳውን የኤርትራ ከሐዲ ተገንጣ
ዮች እንቅስቃሴ እንደ ብሔራዊ አርነት እን
ቅስቃሴ አድርጐ ይወስደዋል ።

በረከተአብ ይኸን መጽሐፍ ሲጽፍ ዓላ
ማው «የአካባቢ ፍላጐቱን ለማርካት ሳይ
ሆን ከዚያም በላይ እንደሆነ» እንዲያውም
«ዕልቂት በተሞላበት ጦርነት ውስጥ የተማ
ገደ ሕዝብ ችግርና ሰቆቃ ስሜቱን ስላስቃ
ዩኝ ነው፤ » [5] በማለት ሲመጻደቅ ይታያል።
ለመሆኑ በረከተአብ ሀብተሥላሴ ለኃይለ
ሥላሴ መንግሥት የሕግ አማካሪና ጠቅላይ
አቃቤ ሕግ በመሆን ለብዙ ዓመታት ይኸ

Digitized by Google

ንኑ አሁን በመጽሐፉ ውስጥ የሚነቅፈውን የፊውዳል መንግሥት በከፍተኛ ደረጃ ሲያ ገለግል የቆየ መሆኑን ዘንግቶት ይሆን ? ወ ይስ የመጽሐፉ አንባብያን የማስታወስ ችሎ ታቸው ውስን ነው ብሎ ገምቶ ይሆን ? በኤ ርትራ ውስጥ የመገንጠል እንቅስቃሴ የተ ጀመረው በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ሆኖ በዚያው ሥርዓት ውስጥ ለብዙ ዓመታት የቆየ መሆኑ የሚታወስ ነው ። የመገንጠሉ እንቅስቃሴ ከአብዮቱ በፊት የተነሳ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ፣ የሚገርመው ነገር በረከተ አብ የፊውዳሉ ሥርዓት ዋና አቀንቃኝና ባለሟሉ ሆኖ ለብዙ ጊዜ ሲያገለግል ፣ ባገ ለገለበት በዛ ያለ ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ው ስጥ ሲካሔድ የኖረው ጦርነት አንድም ቀን እንኳ ስሜቱን ሳያስጨንቀው ፣ በአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት በድንገት ሊያስጨንቀው መቻሉ ነው ። ማንም ሰው ሊያስተውለው እንደሚችለው በረከተአብን ያስጨነቀው «የኤርትራ ሕዝብ ሰቆቃና ችግር» ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት መፈንዳቱና በ ተለይም በአብዮቱ ሂደት «የቅርብ ጓደኛ ዬ» የሚለው የአማን አንዶም ሴራ መጋለ ጡና መክሸፉ ነው ።

በረከተአብ ጭልጥ ያለ አድርባይ እንደመ ሆኑ በአብዮቱ የመጀመሪያ ወቅት ምስቅል ቅል ሁኔታ ስለነበር በዚያ ምስቅልቅል ው ስጥ እራሱን ለማስተዋወቅና ከፍተኛ ሥል ጣን ለማግኘት ሙከራ አድርጐ ነበር ። በዚ ህም ፍላጐቱ መሠረት መርማሪ ኮሚሽን ውስጥ ሰርጐ ለመግባት ችሎ ነበር ። ከዘ ውዱ ሥርዓት መገርሰስ በኋላ በረከተአብ በኢትዮጵያ ውስጥ የቡርዧ ጠጋኝ መንግ ሥት ይቋቋማል በሚል ግምት በወቅቱ የ ደርጉ የመጀመሪያ ሊቀ መንበር የነበረውን አማን አንዶምን «ምክር በመስጠት» የሥ ልጣን ጥቅሙን ለማርካት ተነሳ ። ለአማን አንዶም ከሰጠው ምክር ውስጥ ኤርትራ ከ እናት አገሯ በሰላማዊ መንገድ የምትገነጠ ልበትን መንገድ የሚጠቁም ምክርም እን ደነበረበት ይገመታል ። ይኸም ለመሆኑ በበ ረከትአብ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሷል ። በረ ከት ስለአማን አንዶም ሞት ሲያትት አማን የሞተው «በኤርትራ ምክንያት» እንደሆነ ከጠቀሰ በኋላ ወደዝርዝሩ ሲገባ «ሰላማዊ በሆነ መንገድ» ኤርትራ የምትገነጠልበ ትን መንገድ በማቅረቡና «በደርግ ውስጥ በመንግሥቱ በሚመራው አብዛኛው ክፍል እጅግ ኃይለኛና የመረረ ተቃውሞ»[6] ስለደ ረሰበት መሆኑን ያብራራል ። በረከተአብ የአማን አንዶም «የቅርብ ጓደኛና አማካሪ» ነበርኩ ስለሚል ከሉም በላይ ያወቀ ላማር ነው በማለት ብቻ ይህን ጉዳይ እዚህ ላይ እንደመድመዋለን ።

ወደ በረከተአብ « የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ተመራማሪነት» መለስ ስንል ፣ በረከተ አብ በመጽሐፉ ውስጥ «በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በብዙ ቦታ እንደኖረና እንደሠራ»[7] ፣ በመ ሆኑም ይኸን መጽሐፉን ሲጽፍ ዓላማው ፣ አካባቢውን በደንብ ስለሚያውቀው «ከታ ሪካዊ አግባብነቱ አንጻር አካባቢውን ለማ ጥናት አዲስ ሙከራ» ለማድረግ እንደሆነ በከፍተኛ መመጻደቅ ይገልጻል ።

መመጻደቅ ከአንድ አድርባይ ምሁር የሚጠበቅ ቢሆንም ፣ የበረከተአብ«የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ አዋቂነት» ግን እንዲሁ እሱ ስላለ ብቻ ተቀባይነት አያገኝም ። እንዲህ ከማለታችን በፊት ግን ሁኔታው ግልጽ እን ዲሆን በረከተአብ ስለአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያስፈረውን «ታሪክ»እንመረምራለን ። በ መጀመሪያ ፣ በረከተአብ በመጽሐፉ ውስጥ «ጥንታዊ ታሪክ» በሚለው ክፍል ውስጥ «የኤርትራን» ታሪክ ሲያወሳ ፣ የኢትዮጵ ያን ታሪክ ጨርሶ ከሥዕልም ውስጥ ሳያስገ ባው ይቀራል ። ከነአካቴውም የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያ የሚባለው «ነገር» አሁ ን በቅርቡ «በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተመሠረተ ስርወ መንግሥት»[8] አማካይነ ት የተከሰተ እንደሆነ አድርጐ አቅርቦታል። በረከተአብ በዚህ ብቻ አልተገታም ። ጣሊ ያኖች ቀደም ሲል ባሕረነጋሽ እየተባለ ይ ታወቅ የነበረውን መላውን የመረብ ምላሽ

Digitized by Google

«ኤርትራ» ብለው የሰየሙት እ· እ· አ· በ 1890 መሆኑ ሊፋቅ የማይችል ታሪክ ሆኖ ሳለ ፣ በረከተአብ ስለኤርትራ «ጥንታዊ» ታሪክ ሲጽፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 1000 ምዕተ ዓመት ’ ድረስ ይሔዳል ። እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው አሁን ኤርትራ በሚባለው የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል የሚኖረው ሕዝብ ጥንታዊ ታሪክ የለውም ለማለት ሳይሆን ፣ ኤርትራ የሚለው መጠሪያ በረከተአብ ለማቅረብ እንደሚሞክረው ጥንታዊ ታሪክ የለውም ለማለት ነው ።

በዚህ ሁኔታ በ«ታሪክ» ሽፋን በረከተአብ ራሱ የፈጠረውን አፈታሪክ ከአንዳንድ የታሪክ እውነታዎች ጋር በማቀላቀል ብዙ ካተተ በኋላ እስከ አክሱም ስርወ መንግሥት መውደቅ ማለትም እስከ 9ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ድረስ ይመጣል ። ከዚያም አንድ አፈታሪክ ሌላ አፈታሪክን ሲወልድ ይቀይና ወደመካከለኛው ዘመን ታሪክ ስንመጣ ፣ እንደ በረከተአብ «ታሪካዊ» አቀራረብ ከየት እንደመጡ የማይታወቁ አግራዎች ወይም እሱ እንደሚጠራቸው አቢሲያኖች ከ12ኛው እስከ 14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ ተከስተው ከዚያ በኋላ ኤርትራ ለምትባለዋ «ብሔር» ምንጊዜም የማይተኙ የውጭ ጠላቶች ሆነው ይገኛሉ ። ይኸን አስመልክቶ በረከተአብ በመጽሐፉ ውስጥ ሲጽፍ

> ለማርች ወይም አቢሲያናች በመባል የሚታወቁት በኤርትራ ደጋማ አካባቢዎች ያልተረጋጋ አገዛዛቸውን የመሠረቱት ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ነው ። ያልተረጋጋ ያልነበተም ምክንያት የኤርትራ ሕዝቦች በጂኦግራፊ ክልላቸው የተለዩና የውጭ አገዛዝ ያለመዱ ፣ እንዲሁም ከፍተኛ የብሔርተኝነት ስሜት ያላቸው በመሆናቸው አቢሲያናች ሊገዙአቸው ያደረጉትን ሙከራ ባለማስለስ በመቋቋማቸው ነው ፣ [10]

ይላል ።

የበረከተአብ ታሪክ አዋቂነት ይኸን ሲመስል ፣ እስቲ ለጊዜው ታሪኩን ተወት አድርገን እንደገና ወደ በረከተአብ «ማርክሳዊነት» እንመለስ ። አሁን በያዝነው ዘመን ስለብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴና ትግል ሲወሳ የግዴታ ስለኢምፔሪያሊዝም መወሳት እንዳለበትና ፣ ሳይወሳ ማለፍ እንደማይቻል በረከተአብ የተገነዘበ ይመስላል። በመሆኑም እሱ አሁን ቀሚለታለሁ ፣ እታገልለታለሁ ስለሚለው ስለ «የኤርትራ ብሔራዊ አርነት» ሲያወሳ ፣ የግዴታ አንድ ይኸን «የኤርትራ ብሔራዊ እንቅስቃሴ» የሚያፍንና የሚጻረር የሆነ ኢምፔሪያሊዝም ማግኘት አለበት ። በረከተአብ ጥረቱ «በከንቱ»አልቀረም፤«የኢትዮጵያን ኢምፔሪያሊዝም» አገኘ ።

በረከተአብ ስለኢምፔሪያሊዝም ያለው ግንዛቤ የጨቅላነት ግንዛቤ ከመሆኑ የተነሳ በተለይ ከምኒልክ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ያሉትን የኢትዮጵያ መንግሥታት የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ብሎ በመልካም ፈቃዱ ሰይሟል ። ኢምፔሪያሊዝም የሚባለው ነገር ከ1870ዎቹ በኋላ የመጣ ክስተት ነው የሚለውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሐቅ መጋፋት ላያስኬድ ይችላል የሚል ግምት ቢያድርበት ፣ (ቀደም ሲል አቢሲኒያ «ኤርትራን» ለመግዛት ጥረት ማድረግ የጀመረችው ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው ብሎ ስለነበር) ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ መንግሥታት በሙሉ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ነበሩ ይላቸው እንደነበረ መገመቱ እምብዛም ከትክክለኛ ግምት የሚርቅ አይሆንም ።

በረከተአብ አሁንም በዚህ ብቻ ሳይገታ በኢትዮጵያ ውስጥ አለ የሚለውን ኢምፔሪያሊዝምና ቅኝ አገዛዝ ከፖርቱጋል ኢምፔሪያሊዝምና ቅኝ አገዛዝ ጋር በማነጻጸር፣ ፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶቿን ነፃ በመልቀቋ ፣ «አብዮቷ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ ሲሄድ» ኢትዮጵያ ግን «ቅኝ ግዛቶቿን ባለ

Digitized by Google

መልቀቋ የኢትዮጵያ አብዮት ተቀልብሶ በተሳሳተ አቅጣጫ ወደ ኋላ በመሄድ ላይ ነው ! » [11] በማለት በመጽሐፉ ውስጥ አስፍሯል ። የፖርቱጋልን አብዮት መጢጢፍ በሚመለከት ሁኔታው ይኸን ዓይነት መልክ አልያዘም እንጂ ፣ በመሠረቱ በፖርቱጋል ውስጥ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ቢጢጢፍ በኢትዮጵያም ሆነ በየትም ቦታ ያሉ አብዮታውያን የሚደሰቱበትና የሚበረታቱበት እንጂ የሚከፉበት አይደለም ። ይሁንና ይኸ ሌላ ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ላይ እናቆመዋለን ። ኢትዮጵያን በሚመለከት ግን በረከተአብ የሚለው ነገር በአጭሩ ሲጠቃለል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ካልተገነጠለች በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም ነው ። የበረከተአብ ክህደት አሁንም በዚህ ብቻ አያቆምም ። የሲያድ ባሬ ጠበቃ በመሆን የሲያድ ባሬ መንግሥት ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ቆርሶ ለመውሰድ የሚያደርገውንም ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ይደግፋል ። በረከተአብ በሶማሊያ ውስጥ አለ የሚለውን «ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም» ወደጐን ተወት አድርገን ፣ ኦጋዴንን በሚመለከት በረከተአብ ባለፈው የኦጋዴን ጦርነት ላይ የሲያድ ባሬ መንግሥት ቢሸነፍና «የሶማሊያ ብሔራዊ ስሜት ቢነካም» [12] የሶማሊያን ብሔራዊ ክብር ለማስመለስ ሲያድ ባሬና ጓደኞቹ « እንደገና ወደጦርነት ለመሔድ ይገደዳሉ» [13] ሲል ያለአንዳች ሐፍረት ጽፎ እናገኘዋለን ።

በረከተአብ መጽሐፉ ውስጥ ያሰፈረውን «ታሪክ» ኢ ታሪካዊነት ፣ ጭልጥ ያለ ቅጥፈትና ክህደት መሆኑን በማስመልከት ብዙ ማለት ይቻል ነበር ። አለፍ አለፍ ብለን ለመዳሰስ እንደሞከርነው ፣ ጽሑፉ ከአንድ «የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ አዋቂና ተመራማሪ» ነኝ ከሚል ግለሰብ ፣ «የአካባቢውን ታሪክ በአዲስ መልክ ለማቅረብ» የተደረገ «አዲስ» ሙከራ ሊሆን ቀርቶ ፣ የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኛ የሆኑት ተገንጣዮችና ሌሎችም ከሐዲዎች ምንም ሳይመራመሩ ፣ ቅጥረኝነታቸው ብቻ አስገድዷቸው ሲያላዝኑት ከቆዩትና አሁንም በማላዘን ላይ ከሚገኙት አባባል ጋር ጨርሶ ያልተለየና ፣ የተለመደ የክህደት ሰቆቃ ነው ። ባጭሩ በረከተአብ ሀብተሥላሴ «ተራማጅ ነኝ» እያለ በመመጻደቅ ሊወጣ ከማይችለው የክህደት አዘቅት ውስጥ የገባ ከሐዲ ምሁር ነው ። ኧረ ለመሆኑ «ተራማጅ ነኝ» ሊል የቻለው ከምን ቅድመ ታሪክ ተነስቶ ይሆን ? አበው ሲተርቱ «ጅብ ከማያውቁት አገር ሔደና ቁርበት አንጥፉልኝ አለ» እንዳሉት ፣ በረከተአብ ሀብተሥላሴ ከአብዮቱ በፊት በጠቅላይ አቃቤ ሕግነቱ የፊውዶ ቡርዧው የኃይለሥላሴ መንግሥት ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ (በኤርትራና በኦጋዴን የሚኖሩትን ጨምሮ) ሲወነጅል ፣ ሲያሳስር ፣ ሲያስገርፍና ሲያስገድል እንዳልኖረ ሁሉ ፣ አሁን አሜሪካ ገብቶ «ተራማጅ ነኝ» ለጭቁን ሕዝቦችና ብሔረሰቦች በተለይም ደግሞ «ለኤርትራ ነፃነት ለ30 ዓመታት ያሀል ታግያለሁ» መዘተ...ሲል መስማቱ እጅግ አድርጐ የሚያስገርምና የሚያስተዛዝብ ነው ።

ከአብዮቱ በኋላ ተራማጅ ሊሆን ይችላል እንዳይባል ከአብዮቱም በኋላ ተራማጅ ሊያሰኘው የሚችል ነገር አልሠራም ። እንዲያውም በዚህ አጋጣሚ በአብዮቱ የመጀመሪያ ወቅት ተቋቁሞ በነበረው የመርማሪ ኮሚሲዮን ውስጥ ከበረከተአብ ጋር በዚሁ ኮሚሲዮን ውስጥ ይሠሩ የነበሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ምሁር በረከተአብን በማስመልከት ያሉትን ለመጥቀስ እንገደዳለን ።

> በረከተአብ እንደት ያለ ቀናተኛ ኢትዮጵያዊ እንደነበረ ፣ ከፍተኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣን እንደነበረ ፣ በ1966 ለመርማሪ ኮሚሲዮን አባልነት ሲመረጥ የእናት አገር ጥሪ አክባሪ ነው ብሎ ሲንደረደር ከአሚሪካ መምጣቱን ብዙ ሰዎች ያውቃሉ።«ህመምተኛ ልጄን ትቼ የእናት አገር ጥሪ አክባሪ መጥቻለሁና ለልጄ ማስታመሚያ ገን

ዘብ ያስፈልገኛል» በማለት ወጥር በመከራከር በኢትዮጵያ መንግሥት የደመወዝ እርከን ውስጥ የሌለ በወር ከአራት ሺህ በላይ እንዲያገኝና ከዚህም ውስጥ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ያህል በውጭ ምንዛሪ እንደተፈቀደለት ብዙ ሰዎች አያውቁም ። ይህ ጎበዝ ዛሬ ከኢትዮጵያዊነቱ የተረፉት መልኩና ስሙ ፣ ኢትዮጵያውያን ዘመዶቹ ናቸው ። እነዚህን ለመካድ አስቸጋሪ ነው ። ዛሬ በረከተአብ ለኢትዮጵያ ያለውን ፍጹምና ሙሉ ጥላቻ ትናንትና ለኢትዮጵያ ከነበረው የአገር ፍቅር ቀናት ጋር ስናስተያየውና ኢትዮጵያ ተገነጣጥላ እንድትጠፋ የሚያደርገውን ጥረት ስንመለከት የምንገነዘበው የክህደት ጎዳና የሚያመራው ወደ አስጠያፊ የመንፈስ ለዘቀት መሆኑ ነው ።[14]

በረከተአብ በኋላም እራሱ በመጽሐፉ ውስጥም እንዳሰፈረው የአማን አንዶም «የቅርብ አማካሪ» እና «ጓደኛ» ሆኖ በኢትዮጵያ ጠጋኝ የሆነ የቡርዧ መንግሥት እንዲቋቋምና እሱም (በረከተአብ) ከፍተኛ ሥልጣን ሊሰጠው እንደሚገባው ፣ «ካልሆነም ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል «የአብዮቱ ስትራቴጂ ነዳፊ» እያለ ለሚያሞካሸው ለአማን አንዶም ምክር ሲለግስ ቆየ ። በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮቱ እየገፋ ሲሔድ ፣ በረከተአብ እንዳሰበውም ጠጋኝ የሆነ የቡርዧ መንግሥት ሳይቋቋም በመቅረቱ ፣ የአማን አንዶምም አብዮት ቅልበሳ ሴራ በመጋለጡ ለሥልጣን የነበረው ምኞት እንደሟሸሸበት ሲገነዘብ አገር ጥሎ ወደአሜሪካ የፈረጠጠ ግለሰብ ነው ። የበረከተአብ የ«ተራማጅነት» ታሪክና ቅድመ ታሪክ እንግዲህ ይኸ ነው ። በመሆኑም ጥቅሙ የተነካበት ሰው ያልሆነውን ሆንኩ ብሎ ቢል እምብዛም የሚገርም አይደለም።

በረከተአብ እምነት የሌለውና በምንም ዓይነት መርህ የማይመራ ከሁሉም ይበልጥ የራሱን ጥቅም የሚያሳድድና የለየለት አድርባይ ነው ። አሁንም አሜሪካ ተቀምጦ ፀረ ኢትዮጵያ ጽሑፎች የሚያወጣው የሌሎች አገሮች ከሐዲ ስደተኞችን (የንሾቬሊስቲን ወዘተ ....) ምሳሌነት በመከተል ፀረ አብዮት ጽሑፍ ባወጣ ቁጥር በመጽሐፉ ሽያጭ ስም ከኢምፔሪያሊዝም የሚሰጠውን የገንዘብ ድጎማ ለማግኘት ሲል መሆኑ አያጠራጥርም ። ከሐዲዎችና ቅጥረኞች የትድረስ ለመዝቀጥ እንደሚችሉ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ብዙ ጊዜ የታየ በመሆኑ ፣ የበረከተአብም ተግባር ከዚህ አጠቃላይ ሥዕል ውጭ የሚታይ አይደለም ።

የበረከተአብን ታሪካዊ ክህደት በሚመለከት በዚሁ ለማጠቃለል ስንሻ ፣ የበረከተአብና የመሰሎቹ ፀረ አብዮትና ርካሽ ጽሑፎች በመንዝሊ ሪቪው መጽሔት ላይ ማውጣትና መጽሐፎቻቸውም በመንዝሊ ሪቪው አሳታሚ ድርጅት እየታተሙ መሰራጨት ግን ሌላ መሠረታዊ ጥያቄ እንድናነሳና መልሱንም ለመሻት እንድንሞክር ያስገድደናል ።

«ነፃ» እና «ሶሻሊስት» ነኝ የሚለው የመንዝሊ ሪቪው መጽሔት በረከተአብና መሰሎቹ የሚጽፉትን ፀረ አብዮት ጽሑፍ ማውጣቱ ምንን ያመለክታል ? ምናልባት የመጽሔቱ «ነፃ» የመሆን አቋም ፣ የመጽሔቱ አዘጋጆች የማያምኑበትንም የፖለቲካ መሥመር የሚያራምድ ጽሑፍ ቢሆን እንዲያወጡ አስገድዷቸው ይሆን ? ወይንስ የአመለካከት አንድነት ስለተፈጠረ ይሆን ? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ያስፈልጋል ።

ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ከሶሻሊዝምና ከብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴዎች ጋር በሚያደርገው ትግል የተለያዩ ታክቲኮችን ይጠቀማል ። ይህ ትግል በተለያየ ዘዴ ከሚካሔድ የፕሮፓጋንዳና በአጠቃላይም ከርዕዮተ ዓለም ትግል ጀምሮ እስከ ቀጥተኛ ጦርነት ድረስ ያለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ካፒ

Digitized by Google

ታሊስቱ በርዕዮተዓለሙ መስክ የመደብ
ጥቅሙን ከሚያራምድባቸው በዛ ያሉ መ
ሣሪያዎች ማለትም ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣
ሲኒማ ፣ ቲያትር ወዘተ . . . መካከል ጋዜጦ
ችና መጽሔቶች ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ና
ቸው ። ለምሳሌ ቀዝቃዛው ጦርነት በመባ
ል ይታወቅ በነበረው ጦርነት አማካይነት
የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም በዓለም አቀፍ ሶሻ
ሊዝም ላይ ርዕዮተዓለማዊ ፣ ኢኮኖሚያ
ዊና ሥነ ልቦናዊ ጦርነት ያካሂድ በነበረበ
ት እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ ዓመታት ውስጥ ፣
በአሜሪካም ሆነ በምዕራብ አውሮፓ እራ
ሳቸውን «ነፃ» እና «ተራማጅ» አድርገው
ይቆጥሩ የነበሩ ጋዜጦችም ሆነ መጽሔቶች
ተገንዝበውትም ሆነ ሳይገነዘቡት ፣ በተጨ
ባጭ ያወጧቸው የነበሩ ጽሑፎች በሚያስ
ራጩት ርዕዮተ ዓለማዊ መልእክት አንጻር
ለኢምፔሪያሊስቱ ዓለም በአፈቀላጤነት
ያገለግሉ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም ።
በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ያሉ ፣ አንዳንድ
ኢምፔሪያሊስቱ ዓለም እራሱ በሚያደር
ሰው ተጽዕኖ ምክንያት የሚነሱ ችግሮችን
ከሶሻሊዝም ከራሱ የሚመነጩ እንደሆኑ
አድርገው በማቅረብ ፣ ሶሻሊዝም የኢኮኖ
ሚ ዕድገትን በማፋጠን ረገድ በተግባር ያሳ
የውን ከፍተኛ ችሎታ በማድበስበስና በዚ
ህ ሂደት ውስጥ የሚነሱ ፣ ግን በየደረጃው
ም በመወገድ ላይ ያሉ አንዳንድ አነስተኛ
ችግሮችን አጉልቶ በማቅረብ ፣ ከመደብ ጥቅ
ም ጋር ባልተቆራኘ ሁኔታ ስለ «ሰብአዊ መ
ብት» ስለ «ዲሞክራሲ» ስለ «ነፃነት» በማ
ናፈስ ፣ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም «ነፃ»
እና «ተራማጅ» ጋዜጦችና መጽሔቶች በ
ተጨባጭ የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ሲያካ
ሂድ ለነበረውና ለሚያካሂደው ፀረ አብዮት
ትግል ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መን
ገድ ፣ ሲተባበሩ መገኘታቸው በገሐድ የታ
የ ሐቅ ነበር ።

አሁን በያዝነው ታሪካዊ ወቅትም በኢ
ምፔሪያሊስቱና በሶሻሊስቱ ዓለም መካከ
ል የሚካሔደው የርዕዮተዓለምና የፖለቲ
ካ ትግል በተፋፋመ ሁኔታ ላይ ይገኛል ።
እንዲያውም ከ1970ዎቹ ዓመታት መጨ
ረሻ ገደማ አንስቶ የብሔራዊ አርነት እንቅ
ስቃሴዎች በከፍተኛ ደረጃ መጠናከርና የ
ሶሻሊስቱን የእድገት ፈለግ የሚከተሉት
አገሮች ቁጥር እየተበራከተ መምጣት ፣ ከ
1960ዎቹ ዓመታት ጀምሮ እስከ 1970
ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ገደማ ድረስ በሁ
ለቱ ተጻራሪ ሥርዓቶች መካከል በዴታን
ትና በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ ላይ ተፈ
ጥሮ የነበረው ግንኙነት ከፍተኛ አደጋ ላይ
እንዲወድቅ አድርጎታል ።

እንደሚታወሰው በ1960ዎቹ ዓመታት
ውስጥ በምዕራቡ ዓለም በተለይም በአሜ
ሪካ ውስጥ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በ
ቪየትናም ውስጥ ያካሂድ የነበረውን አጸ
ያፊ ጦርነት በመቃወም «ማርክሲስት ነን፣»
«ተራማጅ ነን» «የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝ
ምን እንታገላለን» የሚሉ መጽሔቶችና ጋ
ዜጦች እንደአሸን የፈሉበት ወቅት ነበር ።
ያን ወቅት የዴታንት ወቅት እንደመሆኑ
በሁለቱ ተጻራሪ ሥርዓቶች መካከል የነበ
ረው ውጥረት አንጻራዊ ርግበት ያሳየበት
ወቅት ስለነበር ፣ በዚያን ጊዜ በምዕራቡ ዓ
ለም ውስጥ እንደአሸን ፈልተው የነበሩት
«ማርክሲስት» እና «ተራማጅ» መጽሔቶ
ችና ጋዜጦች በውል ማርክሲስትና ተራማ
ጅ ለመሆናቸው የሚፈተኑበት አመች ሁኔ
ታ አልነበረም ። በተለይም ደግሞ በአሜ
ሪካ ውስጥ ወደመጨረሻው ግድም የቬዬ
ትናምን ጦርነት መቃወም ፣ በአሜሪካ ኢም
ፔሪያሊዝም የጦረኝነት ባሕሪና ለዚህም
ባሕሪው የኢኮኖሚ መንስኤ በሆነው ሞኖ
ፖል ካፒታሊዝም ላይ የግራ ክንፍ ሒስ ማ
ቅረብ ብቻውን አንድን ሃያሲ ማርክሲስት
ሊያሰኝ እንደሚያስችል ይገመት ፣ መገመ
ትም ብቻ ሳይሆን ይወሰድ የነበረበት ወቅ
ት ነበር ።

ይሁንና ከማርክሲዝም አንጻር አንድ
ግራ ክንፍ ሃያሲ በኢምፔሪያሊዝም ላይ

Digitized by Google

የተወሰነ ሂስ በማቅረቡ ብቻ ማርክሲስት
ሊባል አይችልም ። ማርክሲዝም የተዋሐ
ዱ ክፍሎች ያሉት ሳይንስ ነው ። ይህ ሳይ
ንስ በካፒታሊዝም ላይ ሂስ በማቅረብ ብቻ
የሚወሰን ሳይሆን ፥ የሶሻሊስት ብሎም የኮ
ሚኒስት ሥርዓትን ለመገንባት መታገልና
በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት በዚሁ አ
ቅጣጫ ከፍተኛ ክንዋኔ ላይ የደረሰውን የሶ
ሻሊስት ማኅበረሰብ ማወቅና መደገፍን የ
ሚያጠቃልል ነው ። ከዚህም በተጨማሪ
ማርክሲስት ለመሆን ቲዎሪንና ተግባርን
ማጣጣም ያስፈልጋል ። በቲዎሪ ከተግባር
ውጭ የሆነ ተምኔታዊ ሶሻሊዝምን እየደገ
ፉ በተጨባጭ ግን በተግባር ለኢምፔሪያ
ሊዝም በጣም አነስተኛ የሆነ ድጋፍ እንኳ
መስጠት ተላላነት ብቻ ሳይሆን ፥ ከኢምፔሪ
ያሊዝም ጋር ማበር ማለት ነው ። ከማርክ
ሲዝም የተቆነጸሉ አንዳንድ ሐሳቦችን መ
ቀበል ፥ ሌሎችን ግን አለመቀበል ፥ ወይም
በቡርዧ ሐሳቦች መተካት ሌኒን እንዳስተ
ተማረው የአድርባይነት ትክክለኛ ገጽታ
ነው ።

በዚህ አጋጣሚ ግልጽ ሊሆን የሚገባው
የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ከነፃነት ፥ ከዲሞ
ክራሲ ፥ ከሰላምና ከሶሻሊዝም ኃይላት ጋር
በሚያደርገው የተካረረ የርዕዮተዓለምና
የፖለቲካ ትግል የተለያየ ዘዴና ከዘዴው
ጋር የሚሔድ የተለያየ መሣሪያ የሚጠቀ
ም መሆኑን ነው ። ግልጽ ለሆነው የፀረ ኮ
ሚኒዝም የፕሮፓጋንዳ ዘመቻው በቁጥጥሩ
ሥር ባሉት የመገናኛ ዘዴዎችና በግልጽ አ
ቋማቸውን ሳይደብቁ የካፒታሊስቱን ሥር
ዓት የሚያወድሱ አፈቀላጤዎቹ በሚደር
ሱአቸው መጻሕፍት ፥ በሚያወጡአቸው
መጽሔቶችና ጋዜጦች ሲጠቀም ፥ የረቀቀና
ሥውር የሆነ ታክቲኩን እግቡ ለማድረስ
ደግሞ ማርክሲስቶች ነን ባዮች የምዕራቡ
ዓለም «የአዲሱ ግራ» (New Left)ታዋ
ቂ ምሁራን (እነሲዊዝን ፥ ቤተልሔምንና
መሰሎቻቸውን መጥቀስ ይቻላል) በሚያ
ራምዱት ፀረ የሶሻሊስት ማኅበረሰብ ትግ
ል ይጠቀማል ። እነዚህ የ«አዲሱ ግራ ማ
ርክሲስቶች» የሚያራምዱት መሥመር በ
ተጨባጭ በአሁኑ ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ
ለዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ድጋፍ እየሰ
ጠ መሆኑ የተሰወረ ነገር ሊሆን አይችልም።

የምዕራቡ ዓለም «የአዲሱ ግራ» ታዋቂ
ምሁራን የሆኑት እነ ስዊዚና መሰሎቻቸ
ው «ማርክሳዊ» ሂሳቸውን የሰነዘሩት አን
ዳንድ የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከ
ተል ላይ ባሉ አገሮችና በሶሻሊስት ማኅበ
ረሰብ አገሮች ላይ ብቻ አይደለም ። እንዲያ
ውም ይኸን «ማርክሳዊ» ሂሳቸውን መሠ
ረት ለማስያዝ ሲሉ የማርክሲስት ሌኒኒስት
ንድፈ ሐሳብ ራሱ እንዲከለስ (እንዲበረ
ዝ) የተደጋገመ ጥሪ በማድረግ ላይ ናቸው።

ለምሳሌ፥—ፖል ስዊዚ «የማርክሲስት ቲ
ዎሪ ቀውስ»(A Crisis in Marxian Theo-
ry) በሚል ርዕስ እ. አ. አ. በሰኔ 1969
በመንዝሊ ሪቪው መጽሔት ላይ ያወጣውን
ጽሑፍ ስንመለከት «ድህረ አብዮት ኅብረ
ሰቦችን የሚመለከተው የማርክሲዝም አካል
አዲስ መሠረት ሊጣልለት ይገባል፥...»[15]
የሚል ነገር ሰፍሮ እናገኛለን ። ፖል ስዊዚ
ይኸንኑ አባባሉን በመቀጠል ፥ በዚሁ «የ
ማርክሲዝም ቲዎሪ ቀውስ» በሚለው ጽሑ
ፉ ውስጥ «. . . የዓለምአቀፍ ካፒታሊዝ
ምን ዕድገትና ቀውስ ለመረዳት ካሉት ቲ
ዎሪዎች ሁሉ የማርክሳዊ ቲዎሪ የተሻለ ሆኖ
ባይገኝ ኖሮ » «ማርክሲዝምን መተው»[16]
እንደ አንድ አማራጭ ሊወሰድ እንደሚች
ልም ይጠቁማል ። ለፖል ስዊዚ ማርክሲ
ዝም ካፒታሊዝምን ለመረዳት ዓይነተኛ
መሣሪያ ባይሆን ኖሮ (የተቀረው የማርክሲ
ዝም አካል ለፖል ስዊዚ ተቀባይነት ስለሌ
ለው) ከነአካቴው ሊተው የሚችል ቲዎሪ
ነው ማለት ነው ።

እንደስዊዚ አመለካከት ከማርክሲዝም
ቲዎሪ ውስጥ ተቀባይነት ያለው በካፒታሊ
ዝም ላይ እንደ ሂስ ሆኖ የቀረበው ክፍል ሲ
ሆን ፥ የተቀረው የማርክሲዝም አካል ፥ግ

Digitized by Google

ለትም የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ፣ የሽግግር ወቅትን ፣ የአዲሱን የሶሻሊስት ኅብረተሰብና ብሎም የኮሚኒዝም ግንባታን በሚመለከት የማርክሲዝም ቲዎሪ የሚያስተምረው ሁሉ ግን ተቀባይነት የለውም ። እዚህ ላይ ስዊዚ ተቀባይነት የለውም ሲል እሱና መሰሎቹን በሚመለከት መሆን ይኖርበታል ። ምክንያቱም በገሐድ እንደሚታየው 1/3ኛ በሆነው የዓለም ክፍል ውስጥ በሶሻሊዝም ጥላ ሥር ለሚኖሩ በብዙ መቶ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሕዝቦች ፣ በሌላውም የዓለም ክፍል ውስጥ ቢሆን በካፒታል በመበዝበዝ ላይ ካሉ ጭቁን ሕዝቦች መካከል የማይናቅ ቁጥር ላላቸው ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማካሔድ ላይ ላሉ በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ የኋላቀር አገሮች ጭቁን ሕዝቦች ግን ማርክሲዝም በቁንጽሉ ሳይሆን እንዳለ መላውን ተቀባይነት አለው።

ስዊዚ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ ሕያው የሆነ ሶሻሊዝም እንዳለ አይቀበልም ። እንደ ሲዊዚ አባባል አሁን ባሉት ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ « ... መደብ የለሽ ኅብረተሰብና መንግሥት የለሽ ኅብረተሰብ ያልተመሠረተበት ፣ በብሔረሰቦች ፣ በዘሮች በጾታዎችና በግለሰቦች መካከል ያለው እኩልነት የይስሙላ (FORMAL) እንጂ እውነተኛ (GENUINE) እኩልነት ያልሆነበት ... » [17] ሁኔታ ስለአለ ፣ ስዊዚ በአሁኑ ጊዜ እውነተኛ ሶሻሊዝም አለ ብሎ አያምንም ። ይኸ መቸም ጭልጥ ያለ የመደብ መንሸራተትና ከላሽነት ካልሆ በስተቀር ለብዙ ጊዜ ማርክሲስት ነኝ ሲል ለቆየ ግለሰብ የሚያዋጣ አቋም አይደለም።

ማርክስ ፣ ኤንግልስም ሆነ ሌኒን የኮሚኒዝም የመጀመሪያው የዕድገት ደረጃ በሆነው በሶሻሊዝም ውስጥ መደቦችም ሆኑ መንግሥት እንደማይጠፉ አስተምረዋል ። ሌኒን የመደቦችን መጥፋት በማስመልከት ሲጽፍ «መደቦች ከኮሚኒዝም በፊት ይጠፋሉ የሚለውን ሐሳብ ማርክስና ኤንግልስ ይሳለቁበት ነበር ፣ እንደነሱ አባባል መደቦች የሚጠፉት በኮሚኒዝም ደረጃ ብቻ ነው» [18] ያለውንና ፣ የመንግሥትንም መጥፋት በማስመልከት «ለመንግሥት ጨርሶ መክሰም ኢኮኖሚያዊ መሠረት የሚሟላው በኮሚኒዝም ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ባለንበት ዘመን ውስጥ ለማኅበራዊ እኩልነት ዋናና መሠረታዊ ዕንቅፋት የሆነው በአእምሮና በጉልበት ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ሲጠፋ ነው ። ይህ ሁኔታ ግን የምርት መገልገያዎች ወደ ሕዝብ ንብረትነት እንደተዛወሩና ካፒታሊስቶች እንደተወረሱ ወዲያውኑ የሚሟላ አይደለም ። ... ስለዚህም ስለ መንግሥት ቀስ በቀስ እየከሰመ መሔድ በምንናገርበት ጊዜ የምናተኩርበት ነገር የመክሰሙ ሁኔታ ውስብስብና ጊዜ የሚፈጅ መሆኑንና ፣ የሚወሰነውም በከፍተኛ የኮሚኒዝም የዕድገት ደረጃ ላይ መሆኑን ነው ... ፤ » [19] በማለት ሌኒን ያሰፈረውን ቁም ነገር ማርክሲስቶች በቀላሉ የሚዘነጉት ነገር አይደለም ። ታዲያ ሶሻሊስት አገሮች በአሁኑ ወቅት የኮሚኒዝም የዕድገት ደረጃ ካልደረሱና ፣ ደርሰናልም ብለው ካልተናገሩ ፣ ያሉበት የሶሻሊዝም የዕድገት ደረጃ መደቦችም ሆነ መንግሥት የሚጠፉበት ደረጃ ካልሆነ ፣ መደቦችንና መንግሥትን አላጠፉምና የሶሻሊት ሥርዓት አልገነቡም ብሎ ከሎጂክም ሆነ ከተራ ግንዛቤ ውጭ የሆነ ክርክር እንዴት መክፈት ይቻላል ?

ሌላው በአሁኑ ጊዜ እነ ፖል ስዊዚና መሰሎቹ ሕያው የሆነውን ሶሻሊዝም እንደሌለ አድርገው ሊመለከቱ የቻሉበት ነጥብ በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ያለው እኩልነት የይስሙላ እንጂ እውነተኛ እኩልነት አይደለም የሚለው ነጥብ ነው ። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ የምዕራቡ ዓለም «የአዲሱ ግራ» «ማርክሲስቶች» ስለ እኩልነት ያላቸው አመለካከት ከቡርዧው የእኩልነት አመለካከት ጋር የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር ፣ ለሐቀኛ ማርክሲስቶች እኩልነት ሲባል በቅድሚያ ሰዎች ከምርት መገልገያ

Digitized by Google

ዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት
መሆኑን ይዘነጉታል ለማለት ያዳግታል ።
ከዚህም በተጨማሪም እኩልነት ሲባል ፣
ማርክሲስቶች እንደሚገነዘቡትና በሶሻሊ
ስት አገሮች በተግባር በመተርጐም ላይ እ
ንዳለው ፣ ሠራተኛው ሕዝብ በየዘርፉ ተደ
ራጅቶ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራ
ዊ መስክ የሚያደርገው ተሳትፎ ከፍተኛ
ነት ነው። ከዚህ ውጭ የግል ሀብት ባለበት
ሁኔታ ፣ ስለዲሞክራሲና ስለ እኩልነት የሚ
ለፈፈው ሁሉ የሚያመለክተው የቡርዧ
ርዕዮተዓለም ተገዥ መሆንን ብቻ ነው ።
በሌላ በኩል በሶሻሊዝም የምርት መገልገ
ያዎች የግል ባለቤትነት ባለመኖሩ ይዞታን
በሚመለከት የሰዎች ግንኙነት በእኩልነት
ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ፣ በዚህ ደረጃ
ክፍያ «ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእ
ያንዳንዱ እንደሥራው» በሚለው መርህ
ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፣ የእያንዳንዱ ሰው
ችሎታም የሚለያይ በመሆኑ ፣ የሁሉም ሰ
ዎች የወር ገቢ እኩል ነው ለማለት አይቻ
ልም ፤ ሊሆንም አይችልም ። በሌላ አነጋ
ገር በሶሻሊዝም የዕድገት ደረጃ የገቢ ልዩ
ት ይኖራል ማለት ነው ። በዚህ ደረጃ የሚ
ኖረው የሰዎች እኩልነት በካፒታሊስቱ ሥ
ርዓት ካለው አፍአዊ እኩልነት እጅግ በጣ
ም የበለጠ ቢሆንም ፣ በኮሚኒስት ደረጃ ከ
ሚደረስበት የሰዎች እኩልነት ጋር ግን የሚ
ነጻጸር አይሆንም ። ስለዚህ ጉዳይ ማርክስና
ኤንግልስ በታዋቂው የጐታ ፕሮግራም ሂስ
በተሰኘው ጽሑፋቸው ላይ በሰፊው ያብ
ራሩት ነው ። ሌኒንም ይኸን አስመል
ክቶ ሲናገር «መደቦች በማይኖሩበት ፣ «የ
መንግሥት ሕልውና በሚከስምበት»...ስለ
ነፃነት ለመናገር በሚቻልበት... በኮሚ
ኒስት ሥርዓት ብቻ ነው ፣ የእውነተኛ ዲሞ
ክራሲ ፣ ምንም ዓይነት እንከንና ገደብ የሌ
ለው ዲሞክራሲ ሕልውና ሊከሰት የሚች
ለው ... ፤ »[20] ብሎአል ። በመሆኑም በአ
ሁኑ ጊዜ በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ያለው
እኩልነት ፍጹም የሆነውና በኮሚኒስት
የዕድገት ደረጃ ላይ ያለው ዓይነት እኩ
ልነት ካልሆነ ፣ እውነተኛ ሶሻሊዝም
የለም ማለት ነው የሚለው የነፖል ስዊዚ
አመለካከት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ቲዎ
ሪን ካለማወቅ ሳይሆን ፣ ቲዎሪውን ለመከ
ለስና ለመበረዝ የሚደረግ ሙከራ መሆኑ
ግልጽ ነው ። ይህ ዓይነት የከላሽነት አቋ
ም ደግሞ በሆነ ባልሆነው የሶሻሊስት አገ
ሮችን በማንቋሸሽ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢም
ፔሪያሊዝም በሚያካሂደው ፀረ ሶሻሊስት
አገሮች የርዕዮተዓለም ትግል ውስጥ በመ
ሳተፍ ከካፒታሊስቱ መደብ ጋር የመደብ
አጋርነት መፍጠር ማለት ነው ።

እነ ፖል ስዊዚና ጓደኞቹ ይኸን ዓይነት
የፀረ ሶሻሊስት አገሮች አቋም ይዘው በመ
ነሳታቸው ፣ እልም ወደአለ ፀረ ማርክሲስ
ት መድረሻ ላይ ደርሰዋል ። በተለይ ፖል
ስዊዚ በማርክሳዊ ቲዎሪ ውስጥ በታሪካዊ
ቁስ አካልነት ክፍል በማርክስና በኤንግ
ልስ ያልተጠቀሰ አዲስ ዓይነት ሥርዓተ ማ
ኅበር ፈጥሯል ። ይኸውም «ካፒታሊስታ
ዊም ሆነ ሶሻሊስታዊ ያልሆነ ሥርዓተ ማኅ
በር»[21] የሚለው ነው ። ፖል ስዊዚ በአ
ሁኑ ጊዜ ባሉት ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ
ያለው ሥርዓት ፣ «ካፒታሊስታዊም ሆነ ሶ
ሻሊስታዊ ያልሆነ አዲስ ዓይነት ሥርዓት»
ነው በማለት በዚሁ «የማርክሲስት ቲ
ዎሪ ቀውስ» በተሰኘው ጽሑፉ ውስጥ አቅር
ቧል ። ምናልባት ይኸ አዲስ ዓይነት ሥር
ዓተ ማኅበር ፖል ስዊዚ ለማርክሲስት ቲ
ዎሪ ያበረከተው አዲስ«አስተዋጽኦ»ይሆን?
አይመስለንም ። አስተዋጽኦው የሚሆነው
ለማርክሲዝም ሳይሆን ማርክሲዝምን ለመ
ከለስ ፣ ለመበረዝና ብሎም ከከበርቴው መደ
ብ ጋር የመደብ አጋርነት ለመፍጠር ከፍ
ተኛ ጥረት ለሚያደርገው ለምዕራቡ ዓለም
የ«አዲሱ ግራ» ፀረ—ማርክሲስት ቲዎሪ
ነው ።

በምዕራቡ ዓለም ውስጥ በተለይ እ.አ.አ.
ከ1970ዎቹ ዓመታት ጀምሮ በምሁራኑ አ
ካባቢ ተስፋፍቶ የሚገኘው የ«አዲሱ ግራ»

Digitized by Google

ማርክሲዝምን» በርዕዮተዓለም ይዘቱ ለካ ፒታሊስቱ መደብ ጥቅም ከቆሙና ፣ አለ ምንም ሽፋን የቡርዧ አድኃሪ ቲዎሪያቸውን ከሚያናፍሱት ከነ ኪሲንጀር ፣ ብሬዥንሲኪና መሰሎቻቸው ጋር የቅርጽ ልዩነት ቢኖረውም የይዘት አንድነት አለው። ሁለቱም ቢሆን በአቀራረብ ይለያዩ እንጂ የቲዎሪያቸው አልፋና ኦሜጋ ፀረ ሶቭየትነት ነው ። ፀረ ሶቭየትነት ደግሞ ከዚህ በፊት በመስከረም ፣ ቅጽ 2 ፣ ቁጥር 6 ላይ በሰፈው እንደ ተብራራው ሥረ መሠረቱ ፀረ ኮሚኒዝም ነው ። ይኸ ደግሞ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምር በተግባር የታየ ነገር ነው ።

ቀደም ሲል እውቅ ማርክሲስቶች የነበሩ እነ በርንስታይን ፣ ካውትስኪ እና መሰሎቻቸው ከማርክሳዊ መሥመር ማፈንገጥ ሲታጣቸው የማርክሲዝምን ቲዎሪ «በአዲስ ዓይነት ሁኔታ ለማሻሻል» እና «ለመከለስ» ጥረት እንዳደረጉ ይታወሳል ። በኋላም የማርክሲዝምን ቲዎሪ የመከለሱ ሂደት ከፀረ ሶቭየት አቋም ጋር በተዋሐደበት ወቅት ይኸን መሥመር ሲያራምዱ የነበሩ ኃይሎች ወደዱም ጠሉም ፣ በተጨባጭ በየአገራቸው የሚካሔደውን የሠራተኛውን እንቅስቃሴ እንዲኮላሽ በማድረግ ፣ ለኢምፔሪያሊዝም በመሣሪያነት እንዳገለገሉ ይታወቃል የነዚሁ የቀደምት በራዦች (በርንስታይን ካውትስኪና ሚሊራንድ ወዘተ...) ተከታዮች የሆኑት እነ ትሮትስኪ ፣ ጀላስና መሰሎቻቸው በያዙት የፀረ ሶቭየት አቋም ከአብዮት ካምፕ ደረጃ በደረጃ በማሽግሸግ በኋላም ጨርሰው በመውጣት ፣ ከነአካቴው የፋሽስቶች ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን የማይረሳ ታሪካዊ ክህደት መፈጸማቸውን ታሪክ ሲያስታውሰው የሚኖር ነው ።

የነበርንስታይን ፣ ካውትስኪ ፣ ትሮትስኪ ወዘተ ... የአሁኖቹ ደቀመዛሙርት የሆኑት ማኦይስቶችና የምዕራቡ ዓለም «አዲሶቹ ግራዎች» ደግሞ ፣ ቀደምት አስተማሪዎቻቸው ያሳዩአቸውን ፈለግ በመከተል በፀረ ሶቭየት አቋማቸው ገፍተውበታል ። እዚህ ላይ አንድ መታወስ ያለበት ነገር አለ ። ይኸውም ታሪክ እርግጥ ያለፈውን ነገር የማተትና የማገናዘብ ባሕሪ ቢኖረውም ፣ አሁን በመሆን ላይ ባለውና ወደፊትም በሚሆነው ላይ ደግሞ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው መሆኑን ነው ።

የ «አዲሱ ግራ» ቲዎሪ ህያው የሆነ ሶሻሊዝም የለም ከሚል መነሻ የሚነሳ ስለሆነ (እግረ መንገዱን በካፒታሊዝም ላይ አንዳንድ ሂሶችን ቢያቀርብና የፈለገውን ያህል በማርክሲዝም ካባ ቢሸፋፈንም) ማርክሳዊ ሊሆን አይችልም ። ሐቀኛ ማርክሲስቶች እንደሚገነዘቡት ፣ እራሳቸውም የሶሻሊስት አገሮች ኮሚኒስት ፓርቲዎች በግሃድ እንደሚገልጹት ፣ በሚያካሂዱት የሶሻሊስት ግንባታ አንዳንድ ችግሮች እንዳሏቸውና እነርሱንም ለማስወገድ ጥረት በማድረግ ላይ እንዳሉ የተደበቀ ነገር አይደለም ። ማርክሲስቶች በሶሻሊስት ግንባታ ወቅት ምንም ዓይነት ችግር የለም በሚል መነሻ ተነስተው አያውቁም ፣ ወደፊትም አይነሱም ። ይሁንና በሶሻሊስት ግንባታ ወቅት የሚነሱ አንዳንድ ችግሮች ተጨባጭ የሆኑ ፣ ከኢኮኖሚ ግንባታው ጋር የተያያዙ ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገት ፣ በሠራተኛው ሕዝብ ታታሪነት ፣ የፈጠራ ችሎታና ብርታት የሚፈቱና በመፈታትም ላይ ያሉ ናቸው ። እዚህ ላይ የሶሻሊዝምን ኃያልነትና ህያውነት ከተቀበሉ በኋላ በግንባታው ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቅን መንፈስ በማንሳት ውይይት መክፈትና የሥርዓቱን ህያውነት በመካድ ህልውናውን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ሁለት በጣም የተለያዩና ተጻራሪ የሆኑ መስመሮች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው የሶሻሊስቱን ዓለም ይበልጥ የሚያጠናክር ሲሆን የኋለኛው ግን ፣ በቀይ ካባ ተሸፍና ቢቀርብም ፣ በተጨባጭ የኢምፔሪያሊስቱን ካምፕ የሚያጠናክር ነው።

ሐቀኛ ማርክሲስቶች አሁን ያሉ የሶሻሊስት አገሮች (በተለይም ሶቭየት ኅብረት)

Digitized by Google

ከኅብረተሰብ ዕድገት አንጻር እጅግ በጣም
አነስተኛ በሆነ ጊዜ (65 ዓመት ከአንድ
ሰው ዕድሜ የማይበልጥ ጊዜ ነው) ውስጥ
በአብዛኛው ኋላቀር ከሆነ ደረጃ ተነስተው
ምን ታአምር እንዳሳዩ ስለሚገነዘቡ ፣ የሶሻ
ሊስት አገሮች በደረሱበት ከፍተኛ የዕድ
ገት ደረጃ ይኩራራሉ ። ሐቀኛ ማርክሲስ
ቶች ሶሻሊስት አገሮች በሚያካሂዱት እጅግ
አስቸጋሪ የሆነ የኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ
አንዳንድ ችግሮች ሊገጥሙ እንደሚችሉ
ይገነዘባሉ ፣ ሆኖም ግን ማናቸውም ችግር
በሠርቶአደሩ ሕዝብ ታታሪነትና በፓርቲ
ዎቹ ትክክለኛ አመራር እንደሚፈታና
በመፈታትም ላይ እንዳለ ያምናሉ ።

አስመሳይ ማርክሲስቶችና ከላሾች (ፖል
ስዊዚና መሰሎች) የሚያራምዱት ቲዎሪ
በኩረ ሃሳብ ግን የዓለምአቀፍ ሶሻሊዝምን
ሕልውና ከነአካቴው በመካድ ላይ የተመ
ሠረተ ነው ። የወንበር ላይ ማርክሲስቶች
ወንበራቸው ላይ ቁጭ ብለው በአሁኑ ጊዜ
ያሉት ሶሻሊስት አገሮች « ካፒታሊስትም
ሶሻሊስትም» አይደሉም በማለት አዲስ ዓይ
ነት ሥርዓት ማኅበር በመፍጠር ለመመጻደ
ቅ ቢሞክሩም ፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር
ሕዝብ የተሰዋለትን የዓለም አቀፍ የሶሻሊስ
ት ሥርዓት ሕልውና ለማሳጣት ከቶውንም
አይቻላቸውም። ከላሾችና የፖለቲካ ደላሎች
የመጨረሻው እጣቸው, በቡርዧ ርዕዮተዓለ
ም ውስጥ በመዘፈቅ የዚሁ ርዕዮተዓለም
አራማጅና ተገዥ መሆን ነው ። ይኸም በመ
ሆኑ ነው ተጨባጭ የሆነውንና ማቴሪያላዊ
መሠረት ያለውን ዓለም አቀፍ ሥርዓት ከአ
እምሮ ጅምናስቲክ በሚመነጭና ከቅዠት
ጋር በተቀላቀለ አስተሳሰብ ብቻ ኒዮርክና
ለንደን ወዘተ... ቁጭ ብለው ህልውናውን
ለማጥፋት ሙከራ የሚያደርጉት ። ታዲያ
ይኸ የቡርዧ ሃሳባዊነት ካልሆነ ምን ሊሆን
ይችላል ? ዓለም አቀፍ ሶሻሊዝም እንኳን
በጥቂት አድርባይ ምሁራንና አስመሳይ ማር
ክሲስቶች « ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ » ሊጠፋ
ቀርቶ ፣ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ባለው

እጅግ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ወታደ
ራዊ ኃይል በመጠቀም በተደጋጋሚ የሞ
ፋት እጁን ቢሰነዝርበትም እንኳ ሊያጠ
ፋው አልቻለም ፤ አይችልምም ።

እንኳን ማርክሲስት ነኝ የሚል ይቅርና
ማርክሲስትም ባይሆን ፣ ማንም ነገሮችን
በቅን ልቡና የሚመለከት ሁሉ ፣ በአሁኑ
ጊዜ የምንኖርባት ዓለም በሁለት ተጻራሪ
ዓለም አቀፋዊ ሥርዓቶች የተከፈለች መሆ
ኑዋን አይክድም ። ይኸ ሐቅ ገሀድ የሆነ
ሐቅና ለማንም የሚታይ ሆኖ ሳለ ፣ የሚያሳ
ዝነው ነገር « ካፒታሊስታዊም ሆነ ሶሻ
ሊስታዊ ያልሆነ ሥርዓተ ማኅበር » እን
ዳለ ፣ ኮሚኒዝምም ቢሆን በየአህጉሩ ሊለ
ያይ እንደሚችል (ዩሮ ኮሚኒዝምን፣ ሶስተኛ
መንገድን ወዘተ...) የሚያናፍሱ በራዦች
ሁሉ ፣ ይኸን ፀረ—ማርክሲስት አቋማቸ
ውን በማርክሲዝም ካባ ሸፍነው ለማቅ
ረብ የሚያደርጉት ጥረት ነው ።

ሌኒን በነበረበት ወቅት እንደነዚህ ያሉ
አስመሳይ ማርክሲስቶችን በማስመልከት
ከፍተኛ ትግል ማካሄዱ ይታወሳል ። ሌኒን
በወዝአደሩና በካፒታሊስቱ መካከል ፣ በሶ
ሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል በሚ
ካሄደው ትግል ውስጥ ፣ በተዘዋዋሪ መን
ገድ ለካፒታሊስቱ መደብ ርእዮተዓለማዊ
ድጋፍ መስጠት ቀርቶ ፣ የገለልተኛነት
አቋም መውሰድ ማለት እንኳ ለአድኃሪው
መደብና ሥርዓት ጥቅም መቆምና ታዳጊው
ንና ተራማጁን መጻረር ማለት እንደሆነ በግ
ልጽ አስተምሯል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደትም የኢትዮጵያ
አብዮታውያን መንዝሊ ሪቪው እና መሰሎቹ
የሚያራምዱትን የ‘ አዲሱን ግራ’ የከላሽነ
ት መስመር መታገል እንደሚያስፈልግ የተ
ገነዘቡት አሁን አብዮቱ ስምንተኛውን
ዓመት በተያዘበት ወቅት አይደለም ።
ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዮትና
በፀረ አብዮት ኃይሎች መካከል በዳር ድን
በር ብቻ ሳይሆን በመሀል አገር ጭምር የጦ

ትና የሽረት ትግል ይካሄድ በነበረበት
በ1969 ፣ በኢትዮጵያ አብዮት ማዕከ
ላዊ የዜና ማሠራጫ ተዘጋጅቶ በወጣ ብር
ሽር ውስጥ መንዝሊ ሪቪው እና መሰሎቹን
በማስመልከት ፣

> በኢትዮጵያ ውስጥ ለሶሻሊስት ንድፈ
> ሃሳብ መስፋፋትና እድገት መሰናክል
> ከሆኑት ነገሮች መካከል ዋንኛው፣ለኢት
> ዮጵያ ፋራማጅ ምሁራን ለረዥም ጊዜ
> የፖለቲካ አስተሳሰብ መሠረት የነበረው
> የአንግሎ—አሚሪካን አስመሳይ ማርክ
> ሲስት ሥነጽሑፍ ነው ። በ« መንዝሊ
> ሪቪውና » በ «ኒው ሊፍት ሪቪው »
> ወዘተ... ዘይቤ የማርክሲስት ቲዎሪ
> መዛባት ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአብ
> ዮት በፊት ሥርዓት ያለው የሶሻሊስት
> አመለካከት እንዳይዳብርና ሥር እንዳ
> ይሰድ በማድረግ የበኩሉን ሚና ተጫ
> ውቷል ። ... በመሆኑም ሐቀኛ የኢት
> ዮጵያ ማርክሲስት—ሌኒኒስቶች የአን
> ግሎ አሚሪካን አስመሳይ ማርክሲስቶ
> ችምሆኑሌሎች በራዦችየማርክሲዝም
> ን ቲዎሪ ለመበረዝ የሚያደርጉትን ጥረ
> ት በፅኑ መዋጋት ብቻ ሣይሆን፣ትክክለ
> ኛው የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ቲዎሪ በኢ
> ትዮጵያ የሠራተኛ እንቅስቃሴ ውስጥ
> ሰርጾ እንዲገባ መታገል አለባቸው ፤

የሚል ነገር ሠፍሮ እናገኛለን ። ይኸ አባ
ባል በኢትዮጵያም ውስጥ ከምዕራቡ ዓለም
« የአዲሱ ግራ» ፀረ—ማርክሲስት መስመር
ጋር ይካሄድ የነበረው ትግል የቆየ መሆኑን
ያመለክታል ።

በኅዳር ወር 1974 ጓድ ሊቀ መንበር
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕ
ከላዊ ኮሚቴ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀ
ረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ «...የ«ግራ»
እና የቀኝ አድርባይ መሥመሮች በራዥᎉ
ትዋ ቀናናዊነት በኢትዮጵያችንም ለጥቂት
ጊዜ ውዥንብር ሲፈጥሩ ቆይተዋል ። ከዚ
ህም ውስጥ ማኦይዝምና«የአዲሱ ግራ» ዝን
ባሌዎች በጊዜው ለነበረው የርዕዮተ ዓለም
ሥርጭት ዕንቅፋት ሆነዋል፤» ብለው ነበር።
የምዕራቡን ዓለም « የአዲሱን ግራ» ፀረ
ማርክሲስትነትን በሚመለከት ብዙ ለማ
ለት ይቻላል ። ይሁንና ነገሩን ላለማንዛዛት
ዋና ዋና ነገሮችን በማንሳት ብቻ ለማጠቃ
ለል እንፈልጋለን ።

የምዕራቡ ዓለም የ «አዲሱ ግራ» ፀረ ሶሻ
ሊስት ማኅበረሰብ ትግል ይዘቱ ፀረ ኮሚኒ
ዝም ነው ። ይኸ ዓይነት ቀስ በቀስ እየተን
ኛቀቀ የመጣ ከላሽነት ደግሞ አሁን በተጨ
ባጭ በመታየት ላይ እንዳለው ፣ በዓለም
አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአንድ አገርም
ደረጃ የመደብ ትግልን አስፈላጊነትና ወሳ
ኝነት እስከመካድ ድረስ የደረሰ ነው ። ከላ
ሽነት ደግሞ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይ
ንስ እንደሚያስተምረን የአድርባይነት ዋን
ኛው ገጽታ ነው ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የመዝአደ
ሩን መደብ የትግል ታሪክ መለስ ብለን ስን
መለከት ፣ የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ
አጠቃላይ ገጽታ ከአድርባይነት ጋር የተ
ደረገ የሚያኩራና ጠንካራ የሆነ የትግል
ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን።በአገርአቀፍም ሆነ
በዓለምአቀፍ ደረጃ አድርባይነት የመዝ
አደሩን መደብትግል የሚያኩላሽና የሠራተ
ኛውን መደብ ጥቅም ለካፒታሊስቱ መደብ
አሳልፎ የሚሰጥ ፣ በተራማጅ ቃላቶች ያሸ
በረቀ የክህደትና የሽንፈት መንገድ ነው ።

አድርባይነት በፈለገው ዓይነት ካባ ተሸ
ፋፍኖና ተደብቆ ቢቀርብም ፣ ተጨባጭ
ከሆነው ፣ በአገር ውስጥና በዓለምአቀፍ
ደረጃ በመካሄድ ላይ ካለው የመደብ ትግል
የተንሸራተተ ፣ ከኅሊና በሚመነጭ ትዠት
የሚመራ ፣ በመጨረሻም በተጨባጭ በሚያ
ራምደው መስመር የአገር ውስጥና የዓለም
አቀፍ አድኅርትን ጥቅም የሚደግፍ ነው ።
ሌኒን የአድርባይነትን ይዘት በግልጽ
ካስቀመጠ በኋላ ፣ ከአድርባይነት ጋር የሚ

Digitized by Google

ደረገው ትግል ያለማሰለስ መቀጠል ያለበት መሆኑን አስመልክቶ ሲጽፍ ፤

የፓርቲያችን አጠቃላይ ትግል (አጠቃላዩን የአውሮፓ የሠራተኛ እንቅስቃሴ ጨምሮ) በአድርባይነት ላይ የታለመ መሆን አለበት ። አድርባይነት አንድ ዓይነት አመለካከት ወይም አዝማሚያ አይደለም ፤ አድርባይነት ከዚያም አልፎ በአሁኑ ወቅት በሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ውስጥ የቡርዧው ዓይነተኛና የተደራጀ መሣሪያ ሆኗል ፤ [22]

ብሎ ነበር ።

በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት በምዕራቡ ዓለም ውስጥ እንደ ፋሽን ተይዞ ያለው « የአዲሱ ግራ » አድርባይነት ከሁለቱ ዓለምአቀፍ ሥርዓቶች ውጭ ሆኖ በሁለቱም ላይ « ማርክሳዊ» ሂሱን በማቅረብ «ነፃ » ኃይል ሆኖ ለመቅረብ ቢሞክርም ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአንድ በኩል ለዕድገት ፣ ለሰላምና ለእኩልነት ፣ በሌላ በኩል እድገትን ፣ እኩልነትንና ሰላምን በመጻረር ከሚካሄደው ትግል ውጭ ለመሆን ከቶውንም አይቻለውም ።

የ«አዲሱ ግራ» የርዕዮተዓለም መሠረት የሆነው ፀረ ሶቭየትነት የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የፀረ ኮሚኒስት ትግል አካል ነው ። በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት የተከሰተ «አዲሱ ዓይነት » አድርባይነት ነው ።

የ « አዲሱ ግራ » «ማርክሲዝም» ፀረ ሶቭየትነትና ማርክሲዝም አንድ ላይ ሊሄዱ እንደሚችሉ ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ፣ ጥረቱ ከበራዦች ኅሊና የመነጨና ተጨባጭ ሁኔታው የማይደግፈው በመሆኑ የትም ሊደርስ አልቻለም ። በፀረ ሶቭየት አቋማቸው የገፉ ቀደም ሲል ግን ማርክሲስቶች ነን ሲሉ የነበሩ ፓርቲዎች አሁን ከማን ጋር እንደተሰለፉ በገሃድ የሚታይ ነው ። ለእንደነዚህ ዓይነት ፓርቲዎች ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ነው ። የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር ለብዙ ጊዜ ሲከተለው የነበረው የቀኝ አድርባይ መስመር አሁን ከኢምፔሪያሊዝም ጋር እንዳሰለፈው የሚታወቅ ነው ። እነ ፖል ስዊዚ ፣ ቻርልስ ቤተልሔምና የምዕራቡ ዓለም « አዲሱ ግራ» በአጠቃላይ ፣ ለብዙ ጊዜ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አድኃሪ አመራር ደጋፊዎች ሁነው መቆየታቸው የሚታወስ ነው ። የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲከተለው የነበረው መስመር ፀረ ማርክሲስት መሆኑ የታወቀ ሲሆን ፣ እነ ፖል ስዊዚና መሰሎች የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አመራር የብዙ ጊዜ ደጋፊ ሆነው መገኘታቸው ፣ ለፀረ ማርክሲስት አቋማቸው ሌላው ተጨማሪ ማስረጃ ነው ።

በዚህ አጋጣሚ በዓለም አቀፍ የሠራተኛ ትግል ውስጥ ታዋቂ የሆነው ማርክሳዊውና ዓለም አቀፋዊው ታጋይ ጆርጅ ዲሚትሮቭ ማርክሲዝምና ፀረ ሶቭየትነት ጨርሰው ሊጣጣሙ እንደማይችሉ በማስገንዘብ፣

የሶሻሊዝምና የእውነተኛ ብሔራዊ ዲሞክራሲ አገር ከሆነችው ከታላቋ ሶቭየት ህብረት ጋር በቁርጠኝነትና በልበሙሉነት ያልቆመ ማናቸውም ሰው ሶሻሊስት ሊሆን ቀርቶ ሐቀኛ ዲሞክራት እንኳ ሊሆን አይችልም ፤ [23]

ያለውን ለማስታወስ እንወዳለን ።

በመጨረሻም በምዕራቡ ዓለም ውስጥ ያሉ የ «አዲሱ ግራ» አስመሳይ ማርክሲስቶች እንዲገነዘቡት የሚያስፈልግ አንድ ቁም ነገር አለ ። አድርባይነት ከእውነትና ከተጨባጭ እውነታ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ ዕድሉ እየወደቀ በመሄድ ላይ ካለው

Digitized by Google

ከካፒታሊዝም ዕድል ጋር የተቆራኘ ነው ። ካፒታሊዝም ጠፊ የሆነ ሥርዓት እንደመሆኑ ከሱ ጋር የተያያዘም ሆነ የተቆራኘ ሁሉ አላፊና ጠፊ ነው ። በአንጻሩ ግን ከዓለም አቀፍ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ፡ ከሶሻሊዝም ግንባታ ፡ ከሠራተኛው መደብ ትግልና ከብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች ጋር የተቆራኘ ሁሉ ሕያውነትና ዘላቂነት ያለው ነው ። «የአዲሱ ግራ» አድርባዮች ይኸን እውነታ አሌ ቢሉ ፡ ከታሪክ የበለጠ ግስረኛ ስለማይገኝ ፡ ታሪክን ዞር ብለው መመልከት ይችላሉ ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Bereket Habte Selassie, "The Dergue's Dilemma: The legacies of a Feudal Empire," *Monthly Review*, Vol. 32, No. 3, July-August 1980, pp 1-23.
2. *Ibid.*, P. 1.
3. *Ibid.*, P. 2..
4. K. Marx & F. Engles, *Selected Works*, Vol. 1, p. 89.
5. Bereket Habte Selassie, *Conflict and Intervention In the Horn of Africa*, (New York & London: Monthly Review Press, 1980) P. IX.
6. *Ibid.*, p. 30.
7. *Ibid.*, p. IX.
8. *Ibid.*, p. 11.
9. *Ibid.*, p. 49.
10. *Ibid.*
11. *Ibid.*, p. 162.
12. *Ibid.*, p. 5.
13. *Ibid.*
14. መሥፍን ወልደ ማርያም ፤ *የኢትዮጵያ ሰሜን ክፍላተ ሀገር በአፍሪካ ቀንድ የትግል ታሪክ ውስጥ* (አሥመራ፥ መስከረም 3 1974) ገጽ 69—70
15. Paul Sweezy, "A Crisis in Marxian Theory," Monthly Review, Vol. 31, No. 2, June 1979, p. 24.
16. *Ibid.*, p. 23.
17. *Ibid.*, p. 22.
18. Lenin, *CW*. Vol. 32, p. 250.
19. Lenin, "The State and Revolution," *CW*, Vol. 25, pp. 67-70.
20. Lenin, pp. 462-463.
21. Sweezy, p. 24.
22. Lenin, *CW*, Vol. 35, p. 197.
23. "Dimitrov: Hero of the Comintern," *The New Worker*, 18 June 1982, pp. 4-5.

Digitized by Google

ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና (ባንኮች) የኋላቀር አገሮች ሁኔታ

ላቀው ዓለሙ (ዶ/ር)

ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ወደ ኋላቀር አገሮች የገባው የግል ካፒታል መጠን በጣም እየጨመረ መምጣቱ ይታወቃል ። ከዚሁም ጋር የትላልቅ የኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽኖችና የድንበር ዘለል ገንዘብ ድርጅቶችም ሚና በእነዚህ አገሮች ውስጥ እየጐላ በመምጣት ላይ ይገኛል። ድንበር ዘለል ባንኮች ከኋላቀር አገሮች ጋር የሚያደርጉት የኢኮኖሚ ግንኙነት የተለያዩ ገጽታዎች አሉት ። ከእነዚህ የግንኙነት ገጽታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፣ የውጭ ምንዛሪ ብድርችን መስጠት ፣ ቅርንጫፍ ባንኮቻቸውን በእነዚህ አገሮች ውስጥ በማቋቋም ብሔራዊ የገንዘብ ገበያቸውን (National /money Market) በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል ፣ በግል ባንኮች ዘንድ ያለ የአውሮፓ አገሮችን ገንዘብ ፣ (Euro-currency) ከዘይት ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ (Petro- Dollar) ከምችቶችን በእነዚህ አገሮች ውስጥ በብድር መልክ በሰፊው ማንቀሳቀስና የመሳሰሉት ይገኙበታል ።

በድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና በኋላቀር አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ሌላ አንድ በጣም ልዩ የሆነ ገጽታ አለው ። ይኸውም እነዚህ የገንዘብ ድርጅቶች ለኋላቀር አገሮች የሚሰጡት ብድር ያስከተለው ችግር ነው ። በ1981 * ከኋላቀር አገሮች የሚፈለው የግል ባንኮች ብድር ከ200 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነ ተገምቷል ። ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ለኋላቀር አገሮች የሚሰጡት የግል ብድር እየጨመረ መምጣት በሁለቱም ወገኖች (አበዳሪና ተበዳሪ) ላይ አንዳንድ ችግሮችን ማስከተሉ እንዳልቀረ ተረጋግጧል ። ታዳጊ አገሮች ብድሩን

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመተ ምሕረቶች ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

መልሶ ለመክፈል የሚያደርጉት ጥረት በብሔራዊ የኢኮኖሚ ዕድገታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው የሚያጠያይቅ አይሆንም ። በአበዳሪ ባንኮች ላይ ሊደርሱ የሚችሉትም ችግሮች ቢሆኑ በተለያዩ መልኩዎቻቸው በመከሰት ላይ ይገኛሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ አበዳሪ የገንዘብ ድርጅቶች ሆነ ብለው የያዙት ሌላ ተግባር ኋላ ቀር አገሮች ለዕዳቸው መክፈያ የሚውል ተጨማሪ ብድር እንዲወስዱ መገፋፋት ነው ። የዚህ ዓይነቱ አዝማሚያ እነዚህ አገሮች በምዕራባውያን ላይ ያላቸውን ጥገኝነት በማጠናከር ከዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ጋር በዕኩልነት ላይ ያልተመሠረቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስምምነቶችን (Concessions) እንዲያደርጉ ያስገድዷቸዋል ።

በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው ዕዳ እየጨመረ ስለመምጣቱ

ከኋላቀር አገሮች የሚፈለገው የምዕራባውያን ጠቅላላ ዕዳ ከ1971 እስከ 1980 ባለው ጊዜ ውስጥ ከ87 ቢሊዮን ዶላር ወደ 450 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ብሏል ። ይህንንም ዕዳ ለማወራረድ የሚደረገው ክፍያ (ወለዱን ጨምር) በየዓመቱ ከዕዳው በበለጠ መጠን እያደገ መጥቷል ። በዚህም መሠረት ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ የዚህ ክፍያ መጠን ከ10.2 ቢሊዮን ወደ 88 ቢሊዮን ዶላር አድጓል ። ለኋላቀር አገሮች ዕዳ መናር ዋነኛው ምክንያት የወለድ መጣኔ (ሬት) እያሻቀበ መሔድ ነው ። ከፍተኛውንም የአበዳሪነቱን ሥፍራ የግል ባንኮች እያየዙት ነው ። በ1971 ከግል የገንዘብ ድርጅቶች የተገኘው ብድር ከኋላቀር አገሮች ጠቅላላ ዕዳ ውስጥ25% ብቻ ሲሆን በ1980 ግን ወደ 50% ከፍ ማለቱ ተረጋግጧል ።[1]

ከአውሮፓ የገንዘብ ገበያ (Euro Currency Market) የተገኙ የመካከለኛ ጊዜ ብድሮች ፣
(በዓመቱ መጨረሻ እና በቢሊዮን ዶላር) [2]

ሠ-1

ዓ. ም.	ተበዳሪ ከገሮች በአጠቃላይ (1)	ዘይት የሌላቸው ኋላ ቀር አገሮች (2)	ዘይት ላኪ ታዳጊ አገሮች (3)	2/1 X100
1972	6.9	1.6	0.9	23.2
1973	21.9	4.6	2.7	21.0
1974	29.3	6.3	0.8	21.5
1975	20.8	8.6	3.0	41.3
1976	28.9	11.0	4.0	38.1
1977	41.8	13.5	7.5	32.3
1978	70.2	26.9	10.4	38.3
1979	82.3	35.4	13.0	43.0
1980	77.4	24.0	11.0	31.0
1981	132.3	33.1	11.7	25.0

Digitized by Google

በዓለምአቀፍ ደረጃ የተንሰራፋው የድንበር ዘለል የፋይናንስ ድርጅቶች የብዝበዛ ሰንሰ
ለት ሠርቶአደር ሕዝቦች ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ በሚያካሂዱት ትግል ይበጠሳል

Digitized by Google

ኋላቀር አገሮች ከምዕራባውያን የገንዘብ ድርጅቶች የሚወስዱት የብድር መጠን ከፍተኛ መሆኑን ከሠንጠረዥ 1 ለመረዳት ይቻላል ። ብድሩን ከሚሰጡት የገንዘብ ድርጅቶች መካከል የአሜሪካ ባንኮች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ ። በእርግጥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የምዕራብ አውሮፓ አገሮችና የጃፓን ባንኮች እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እየሠፉ በመምጣቱ ፣ ለኋላቀር አገሮች ከተሰጠው ጠቅላላ ብድር ውስጥ ንም ። አሜሪካ ለኋላቀር አገሮች ከምትሰጠው ጠቅላላ የብድር መጠን ውስጥ ¼ ኛውን ድርሻ የያዙትን የአሥር ታላላቅ የአሜሪካ የገንዘብ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ፣ በዝርዝር ከሠንጠረዥ 2 መመልከቱ ለዚሁ በቂ ግረጋገጫ ሊሆን ይችላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለኋላቀር አገሮች ከታሰጠው የምዕራባውያን ባንኮች የብድር መጠን ውስጥ የጥቂት ተበዳሪ አገሮች ድርሻ

በታላላቆቹ አሥር የአሜሪካ የገንዘብ ድርጅቶች የተሰጡ ዓለም አቀፍ ብድሮች

(በ1979 መጨረሻ) [3]

ሠ 2

የባንክ ስም	ዓለም አቀፍ ብድሮች	ለታዳጊ አገሮች የተሰጡ ብድሮች		ከዓለም አቀፍ የብድር አገልግሎት የሚገኝ ትርፍ	
		በሚሊዮን ብር	ከጠቅ. በ%	በሚሊዮን ብር	ጠቅላላ የትርፍ መጠን በ%
ሲቲ ኮርፖሬሽን	38,927	15,587	40.0	352	64.7
ቸስ ማንሃተን	21,773	6,828	31.4	146	46.9
ባንክ ኦፍ አሜሪካ	22,804*	8,804*	36.3	226	37.7
ማኑፋክቸርስ ሃኖቨር	13,266	4,864	36.7	103	48.8
ኬሚካል ኒውዮርክ	8,697	3,011	34.6	50	35.1
ጄ.ፒ. ሞርጋንና ኩባንያ	11,971	2,272	19.0	150	52.0
ባንከርስ ትረስት ኒውዮርክ	7,814	2,698	34.5	59	51.5
ፈርስት ቺጋጐ	5,454	1,819	33.4	4	3.5
ኮንቲኔንታል ኢሊኖይስ	6,816	1,953	28.7	36	18.5
ሴኩሪቲ ፓስፊክ	3,585	1,725	48.1	17	10.4

የአሜሪካ ያገንዘብ ድርጅቶች ድርሻ በጣም ዝቅ እያለ መጥቷል ። ሆኖም ግን ይህ ድርሻ በአጠቃላይ ሲታይ ዝቅተኛ ይምሰል እንጂ በነጠላ ሲወሰድ በቀላሉ የሚገመት አይሆ በጣም ጉልቶ ይታያል ። በአሁኑ ወቅት ብራዚል ፣ ሜክሲኮ ፣ ፊሊፕንስ ፣ አርጀንቲና ፣ ወዘተ...የመሳሰሉት ጥቂት አገሮች ከሚሰጠው ጠቅላላ የብድር መጠን ውስጥ

* ድምሩ ሰነዶችንና ወንዶችን ያጠቃልላል ።

Digitized by Google

80% የሚሆነውን ድርሻ ይወስዳሉ ። እነዚህ አገሮች በተለይ በፍጥነት በማደግ ላይ በነበረው የኢንዱስትሪና የውጭ ንግድ ኢኮኖሚያቸው ሳቢያ በ1960ዎቹ ዓመታት መጨረሻ የመጀመሪያዎቹ የምዕራባውያን የግል ባንኮች ብድር ተቀባዮች እንደነበሩ ይታወሳል ። በ1950 እና 60ዎቹ ዓመታት ውስጥ ታዳጊ አገሮች ለኢኮኖሚያቸው ዕድገት የሚውለውን የካፒታል ክምችት በአብዛኛው ከግል መዋዕለ ንዋይ ፣ ዕቃዎችን ከውጭ እንዲገዙ በግል ድርጅቶች ከሚሰጥ ብድር ፣ ከሌሎች መንግሥታት ከሚገኙ ብድሮችና እርዳታዎች ፣ ወዘተ ... ከመሳሰሉት ምንጮች ያገኙ ነበር ። በዚህን ወቅት የግል የገንዘብ ድርጅቶች እስከዚህም ጉላ ብሎ የሚታይ ሚና አልነበራቸውም ። በመጠኑም ቢሆን ለውጭ ንግድ የሚውሉ ብድሮችን (Export-Credit) ለኋላቀርአገሮች በመስጠትና በእነዚህ አገሮች ውስጥ የመንግሥት ዋስትና ያላቸውን የልማት ፕሮጀክቶች በከፊል ፋይናንስ በማድረግ ላይ ብቻ ያተኩሩ ነበር ። እነዚህ የግል ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች በወቅቱ ኋላቀር አገሮች ለግል የባንክ ብድር ብቁ ሆነው አልተገኙም የሚል አመለካከት ነበራቸው ።

በ1970ዎቹ ዓመታት ውስጥ በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የግል የድንበር ዘለል ባንኮች እጃ በጣም እያደገ መምጣቱ ይታወቃል ። ለዚህም መሠረታዊ ምክንያቱ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በኋላቀር አገሮች ውስጥ የታየው የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሆነ ይገመታል ። ድንበር—ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ፣ ቅርንጫፍ ባንኮቻቸውን በመጠኑም ቢሆን በኢኮኖሚ ጠንከር ብለው በሚታዩት ታዳጊ አገሮች ውስጥ ማቋቋምን መርጣሉ።አብዛኛዎቹ የእነዚህ የገንዘብ ድርጅቶች ቅርንጫፍ ባንኮች በላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ ተከማችተው ይገኛሉ ። ከላቲን አሜሪካ አገሮች ሁሉ በሰፋቱ በታወቀው በብራዚል ውስጥ ብቻ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከ160 በላይ የሚሆኑ የውጭ ታላላቅ ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ቅርንጫፎች ይገኙ ነበር ። በሩቅ ምሥራቅ አገሮችም ውስጥ ቢሆን የአሜሪካና የጃፓን ታላላቅ ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ቅርንጫፍ ባንኮቻቸውን በሰፊው በማስፋፋት ላይ ናቸው ። የአፍሪካ አገሮችን በሚመለከት በአብዛኛዎቹ በብሔራዊ ደረጃ የገንዘብ ኢኮኖሚ በበቂ ካለመዳበሩም በላይ፥ የግል ባንኮችን እንቅስቃሴ በሚመለከት ያሉት የመንግሥት ሕጎች ጠበቅ ያሉ በመሆናቸው ታላላቅ ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችን ትኩረት የሚጋብዝ ምቹ ሁኔታ እምብዛም ነው ። ከዚህም የተነሣ በእነዚህ አገሮች ውስጥ የድንበር ዘለል የግል ባንኮች ቅርንጫፎች በብዛት ተስፋፍተው አይገኙም ። በአጠቃላይ ግን በ1976 በኋላቀር አገሮች ውስጥ የነበሩት የድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ቅርንጫፍ ባንኮች 1573 እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል ።[5]

ለኋላቀር አገሮች የሚሰጠው የድንበር ዘለል ባንኮች የብድር ሁኔታ ከድንበር ዘለል የሞኖፖሊ ኩባንያዎች ወደ እነዚህ አገሮች ሰርጎ መግባት ጋር በጥብቅ የተያያዘና የተቀናጀ ነው ። እንደ ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ሁሉ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ውስጥ ካላቸው የመዋዕለ ንዋይ መጠን አብዛኛው እጅ በኢኮኖሚያቸው ገፋ ብለው በሚታዩት ታዳጊ አገሮች ውስጥ ይገኛል ። ከዚህም ሌላ የምዕራብ ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያላቸውን የንግድና የመዋዕለ ንዋይ እንቅስቃሴ ባሳደጉ መጠን ፣ ለውጭ የግል ድንበር ዘለል ባንኮች እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ እንደሚፈጥሩ ለመገንዘብ ይቻላል ። ያንዱ ድርጅት ተግባር ለሌላው ዕድገትና ሕልውና በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ፣ የሁለቱም ዓለም አቀፍና ድንበር ዘለል ተቋሞች ዓላማና እንቅስቃሴ በቅርብ የተዛመደ ሆኖ ይገኛል ። በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚገኙት ቅርንጫፍ ባንኮች ለድንበር ዘለል ኩባን

Digitized by Google

ያዎች ብድር በመስጠት የምዕራባውያን ሸቀጦች በገፍ ወደ እነዚህ አገሮች እንዲገባ ያደርጋሉ። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ካፒታላቸውን ወደ ኋላቀር አገሮች በብዛት በማዝመቱ ረገድ የእነዚህን የገንዘብ ድርጅቶች ዕርዳታና ትብብር በከፍተኛ ደረጃ እያገኙ ነው።

ለድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖችና ባንኮች እንቅስቃሴ በኋላቀር አገሮች ውስጥ እየሰፋ መምጣት አንዳንድ የኢምፔሪያሊስት አገሮች (በተለይ አሜሪካ) የሚከተሉት የውጭ ንግድ ፖሊሲ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ አልቀረም። በመንግሥታት መካከል ከሚደረጉት ቀጥታ የፋይናንስ ብድሮች ይልቅ በግል ካፒታል አማካይነት የሚደረገው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ለብዝበዛ ዓላማቸው የበለጠ ጠቀሜታ እንዳለው ኢምፔሪያሊስቶች ስለተረዱ፣ በኋላቀር አገሮች ውስጥ የግል ካፒታል ይዞታን በማጠናከር በብሔራዊ የኢኮኖሚ ዕድገታቸውና በፖለቲካ ነፃነታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማድረግ ችለዋል።

አንዳንድ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታዎችም ለዚሁ የኋላቀር አገሮች ችግር መባባስ ምክንያት መሆናቸው አይካድም። በምዕራባውያን አገሮች የታየው የኢኮኖሚና የኃይል ቀውስ ዘይት አምራች ባልሆኑ ኋላቀር አገሮች ላይ የክፍያ ሚዛን (Balance of Payment) መዛባትን ማስከተሉ ይታወቃል። ይህ ሁኔታ ደግሞ እነዚሁ አገሮች ለውጭ ካፒታል ያላቸውን ፍላጎት በጣም ከፍ እንዲያደርጉ አስገድቸዋል። ከ1970ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ከምዕራብ የግል ድንበር ዘለል ባንኮች ብድር የሚጠይቁ ኋላቀር አገሮች ቁጥር እየበዛ መምጣቱ ለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። ከ1977 ወዲህ በማዕከላዊ ግምት 54 ኋላቀር አገሮች ከአውሮፓ የገንዘብ ገበያ በየዓመቱ ብድር ወስደዋል። ከተሰጡት የግል ባንኮች ብድር ውስጥ በግምት 90% የሚሆነው የተሰጠው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃቸው ከተቀሩት ሻል ብለው ለሚታዩት ኋላቀር አገሮች ነው።[6] በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የድንበር ዘለል ባንኮች ዕዳ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እየጨመረ መምጣት፣ እነዚህ ባንኮች የብድር ደንበኞቻቸውን ለማብዛት የጀመሩትን ጥረት የበለጠ ከፍ እንዲያደርጉ ረድቷቸዋል። የዚህ ጥረት ውጤት ደግሞ ለሚሰጠው የባንክ ብድር የተጠየቀውን ከፍተኛ የወለድ መጠን ለመክፈል የሚገደዱ ኋላቀር አገሮች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣት መሆኑ በገሀድ ታይቷል።

በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የካፒታሊስት ባንኮች ዕዳ በፍጥነት እንዲጨምር ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የራሳቸው የባንኮቹ ገፊት የሚገኝበት መሆኑን አንዳንድ የእነዚህ አገሮች ተወካዮች በይፋ ይናገራሉ። አንድ የላቲን አሜሪካ የፋይናንስ አዋቂ ይህን ሁኔታ በማስመልከት፣ «የውጭ ባንኮች እኛ ከመጠየቃችን በፊት ብድር እንስጣችሁ በማለት ይቀርቡናል። እኛ ለምገንባው ግድብ ኢጣሊያኖች «ሊሬ» እንስጣችሁ ይሉናል። ፈረንሳዮችም ለምንሠራው ፋብሪካ «ፍራንካቸውን» እንስጣችሁ ይሉናል።»[7] ሲሉ የተናገሩትን ማስታወስ፣ ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች በኋላቀር አገሮች ላይ በገንዘባቸው አማካይነት የሚያደርጉትን ገፊትና ተጽእኖ ለመረዳት ያስችላል። በዓለም ላይ ያለው የኢኮኖሚ ቀውስ እየተባባሰ በሄደ መጠን አያሌ ኋላቀር አገሮች (በተለይ ዘይት አምራች ያልሆኑ) የምዕራብ ባንኮች ጽኑ ደንበኞች ወደ መሆን ላይ ናቸው። ከዚህም የተነሣ እነዚሁ የግል ባንኮች በእነዚሁ አገሮች ላይ ከፍተኛ ትኩረትና ተስፋ መጣላቸው አያስደንቅም። ከ1970ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ጀምሮ በምዕራብ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እየተዳከመ በመምጣቱ ኋላቀር አገሮች ለአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ብቸኛ የብዝበዛ ክልል የሆኑትም በዚሁ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ካለው የዓለም የኢኮኖሚ ሁኔታ አንፃር በኋ ላቀር አገሮች

Digitized by Google

ላይ ያለው የምዕራብ ባንኮች ዕዳ መጨመር ሁለት መሠረታዊ ግላግዎች አሉት። በመጀመሪያ ደረጃ ከዘይት ሽያጭ የተገኘውንና መጠኑ በጣም ከፍተኛ የሆነውን ገንዘብ መልሶ ሥራ ላይ ለማዋል የሚረዳ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሕልውና አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች እንደ አንዱ ሆኖ መቅረቡ ነው። ዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ስርዓት በከፍተኛ የኢኮኖሚና የፋይናንስ ቀውስ ውስጥ ባለበት በአሁኑ ጊዜ፣ በተለይ የፋይናንስ ቀውሱን ለማቃለል ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንደኛው ለኋላቀር አገሮች የሚሄደውን የብር መጠን በማብዛትና ወለድንም በመጨመር ከፍተኛ ትርፍ ማጋበስ መሆኑን መገመት አያዳግትም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት የፋይናንስ ገበያ ውስጥ ለተከሰቱት ችግሮች ይህ መንገድ እንደ አንድ መፍትሔ ሆኖ የቀረበ መሆኑ አያጠራጥርም።

በተበዳሪ አገሮች ላይ የደረሱ ችግሮች

የባንኮችን የግል ብድር (Private Bank Credits) የማስፋፋት እንቅስቃሴ የኢምፔሪያሊዝም የውጭ ኢኮኖሚ እስትራቴጂ አንዱ ገጽታ ሲሆን፣ ዓላማውም ኋላቀር አገሮችን በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ሥርዓት ማነቆ ሥር ለማቆየት ነው። በምዕራብ ባንኮች ከሚሰጡት የግል ብድሮች መካከል አብዛኛው በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶችንና የጥሬ ዕቃዎችን ለመጠቀም እንዲያስችል ታስቦ የሚሰጥ ስለሆነ፣ ካፒታሊስት አገሮች ለጥሬ ዕቃ ያላቸውን ከፍተኛ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር የታቀደ መሆኑ ግልጽ ነው። በምዕራባውያን የፋይናንስ ጠበብቶች አመለካከት የዚህ ዓይነቱ የብድር አሰጣጥ ሁኔታ ከፍተኛ የትርፍ መጠን ለማስገኘት የሚችል ስለሆነ፣ ለግል ካፒታሊስቶች ጥሩ የእንቅስቃሴ መስክ ነው የሚል ዕምነት አለ። ዳሩ ግን እዚህ ላይ በግልጽ መገንዘብ የሚያስፈልገው በዚህ ዓይ

ዘይት አምራች ላልሆኑ አገሮች የተዛባ የክፍያ ሚዛን ማስተካከያ የተሰጠ የብድር መጠን (በቢሊዮን ዶላር)[7]

(በዓመቱ መጨረሻ)

ሠ 3

	1973	1974	1975	1976	1977	1978	1979
በተንቀሳቃሽ የንግድ ሂሣብ ላይ የደረሰ መዛባት፣	6	24	32	20	14	26	39
የረዥም ጊዜ የመንግሥት ብድሮች (የተጣራ)	5	7	11	9	11	12	14
ከግል ባንኮች የተገኘ ብድር (የተጣራ)	9	16	19	18	18	23	32
ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ካፒታል	1	4	3	4	3	3	1
መጠባበቂያ — ሪዘርቭ	9	3	1	11	12	12	8

Digitized by Google

ድንበር ዘለል የፋይናንስ ኩባንያዎች በጭቁን ሕዝቦች ምዝበራ ያበጡና የደለቡ የፋይናንስ
ካፒታል አይነተኛ ገጽታ ናቸው

Digitized by Google

ነት መንገድ የሚገኘው ትርፍ ለምዕራብ ሞኖፖሊስቶች ጥቅም እንጂ ለኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ዕድገት የማይውል መሆኑን ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር አገሮች (በተለይ ዘይት አምራች ያልሆኑ) የክፍያ ሚዛናቸው የበለጠ በመዛባት ላይ እያለ ከምዕራብ ባንኮች የሚወስዱትን የግል ብድር ምርታማ በሆነ የሥራ መስክ ላይ በአብዛኛው እንደማያውሉት የሚታወቅ ነው። በእርግጥ እነዚህ ብድሮች ከቅርብ ዓላማ አንፃር ሲታዩ የተዛባውን የክፍያ ሚዛን ለማስተካከል እንደሚረዱ ይታመናል ። ሆኖም ግን ለወደፊት ዕዳውን መልሶ ለመክፈል ያለውን ችግር የበለጠ እንደሚያባብሱት አይጠረጠርም ።

በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የግል ባንኮች ብድር እየጨመረ መምጣት የእነዚህን አገሮች የዕዳ ዘመን እንደሚያራዝመው የሚታወቅ ነው ። ከግል ባንኮች የሚገኙት ብድሮች መንግሥታት ከሚሰጡት ብድሮች ጋር ሲነፃጸሩ ውድ ከመሆናቸውም ሌላ ፣ ረዘም ላሉ የጊዜ ገደቦች የሚሰጡ አይደሉም ። ዓለም አቀፍ የልማትና የዕድገት ባንክ (IBRD) ባጠናቀረው መረጃ መሠረት እስከ 1977 መጨረሻ ድረስ በኋላቀር አገሮች ላይ ካለው የግል ባንኮች ዕዳ ውስጥ 70% የሚሆነው እስከ 1982 ድረስ ተከፍሎ ማለቅ ያለበት ዕዳ ሲሆን ፣ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ ከመንግሥታት የተገኘ ብድር ግን 25% ብቻ እንደነበር ተገልጿል ። [8]

የምዕራብ ባንኮች ብድር ተጠቃሚ የሆኑት ኋላቀር አገሮች በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት የገንዘብ ገበያ ላይ ያላቸው ጥገኝነት በጣም ሥር እየሰደደ በመምጣት ላይ ይገኛል ። በካፒታሊስት የገንዘብ ገበያ ውስጥ የሚታየው የወለድ መጣኔ የማሳደግ አዝማሚያ ኋላቀር አገሮች ለወለድ የሚያወጡትን ክፍያ በጣም እያናረው በመሄድ ላይ ይገኛል ። የምዕራብ ባንኮችን የግል ብድር ከወሰዱት መካከል የአሥራ ሁለት ዘይት አምራች ያልሆኑ አገሮች የወለድ ክፍያ መጠን ከ1970—80 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ11 ወደ 16 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ብሎ ተገኝቷል ። በተለይም ደግሞ ከአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ለሚገኘው የመካከለኛ 2ዜ ብድር የሚከፈለውን ወለድ ወደፊት ለሚሰጡት ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ለተሰጡትም ብድሮች የሚከፈለውን የወለድ መጣኔ በማናር የተበዳሪ አገሮች ችግር እንደ ሚያባብስ ብስ ለማወቅ ተችሏል ። በወለድ መጣኔ ላይ የሚደረገው የአንድ በመቶ ለውጥ ተበዳሪ አገሮች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚከፍሉትን የወለድ ክፍያ በ400 ሚሊዮን ብር እንደሚያሳድገው ተረጋግጧል ። [9]

ለባንክ ብድር በአንድ በተወሰነ ወቅት የሚከፈለውን የዕዳ መጠንና የተበዳሪ አገሮችን ብድር የመክፈል ችሎታ ፣ ዓመታዊ የዕዳ ክፍያ መጠንን ከውጭ ንግድ ከሚገኝ ገቢ ጋር በማነፃፀር ለማወቅ ይቻላል። በዚህም መሠረት ዘይት አምራች ላልሆኑ አገሮች በአጠቃላይ የዚህ ዓይነቱ መለኪያ እየተዛባ በመምጣት ላይ ይገኛል ። በ1974 መጠኑ 9% የነበረው በ1979 ወደ 17.5% ከፍ ብሎ መገኘቱ የእነዚህ አገሮች የኢኮኖሚ አቅም ምን ያህል እንደተዳከመ ለመገመት ይቻላል ። በ1970ዎቹ ውስጥ ምንም እንኳ ዘይት አምራች ያልሆኑ ኋላቀር አገሮች ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡአቸው ያንዳንድ ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ በመጠኑ ቢጨምርም ፣ በተንቀሳቃሽ የንግድ ሚዛናቸው (Balance on current trade account) ላይ የነበረው የክፍያ መዛባት እየተባባሰ ከመምጣት አልዳነም ። ስለሆነም የውጭ ብድር ክፍያ አብዛኛውን ጊዜ ተጨማሪ ብድሮችን በመውሰድ ይከናወናል ማለት ነው ። በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የብድር ዕዳ አሁን ባለው ዓመታዊ ግምት እየጨመረ ከሄደ በ1985 ብድሩን ለመክፈል ከሚደረገው የክፍያ መጠን ውስጥ 88% የሚሆነውን አዲስ በሚወስድ ተጨማሪ ብድር ብቻ ለመሸፈን እንደሚቻል ይገመታል ። ይህ ከሆነ በትክክል ወደ ኋላቀር አገሮች ገብቶ ሥራ ላይ ሊውል

Digitized by Google

የሚችለው የገንዘብ መጠን በጣም እየቀነሰ እንደሚመጣ ለመገመት አያዳግትም። የምዕራባውያን ዕዳ በኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ችግር በማስመልከት «ዓለም አቀፍ ዕዳና ታዳጊ አገሮች» የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲ «የታዳጊ አገሮች ዕዳ እየጨመረ በሄደ መጠን ፣ ለልማት ሊውል የሚችለው ሀብት እየቀነሰ ይሄዳል ። ይህ ደግሞ በበኩሉ የኢኮኖሚን የዕድገት መጠን ከመቀነሱም በላይ ለመዋዕለ ንዋይና ለውጭ ዕዳ መክፈያ ሊውል የሚችለውን የአገር ውስጥ ክምችት ያመነምናል»[10] በማለት ሁኔታውን በትክክል ገልጾታል ።

አንዳንድ የቡርዧ ምሁራን ከምዕራብ ባንኮች የሚገኘውን የግል ብድር ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ ተጽዕኖ ውጪ የሆነ አስመስለው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ዳሩ ግን ሁኔታው የተገላቢጦሽ መሆኑን በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል ። አበዳሪ ባንኮች አብዛኛውን ጊዜ ለብድር ብቁ ናቸው በማለት የሚቀበሉዋቸው አገሮች የኢምፔሪያሊዝምን ፖሊሲ የሚደግፉትን ወይም ደግሞ በረዥሙ ሂደት በወጥመዳቸው ውስጥ እንዲገቡ የሚፈልጉትን ብቻ መሆኑ ይታወቃል ። በመሆኑም ከምዕራብ የግል ባንኮች ብድር ከሚሰጣቸው አብዛኞቹ የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮችና የወታደራዊና የሌሎች ዕርዳታዎች ተቀባይ የሆኑ አገሮች መሆናቸው የሚታወቅ ነው ።

በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የምዕራብ አገሮች የግል ባንኮች ዕዳ እየጨመረ መምጣት እነዚህ ድንበር ዘለል ባንኮች በተበዳሪ አገሮች የብሔራዊ ኢኮኖሚ የዕድገት አቅጣጫና አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዲኖራቸው አድርጓል። «ሲቲ ባንክ» እና «ሞርጋን ጋራንቲ ትረስት» የተባሉት በአሜሪካ የሚገኙ የግል ባንኮች ፣ ተበዳሪ አገሮች ወደፊት ብሔራዊ የፍጆታ መጠንን በመግታትና የሕዝባቸውን የኑሮ ደረጃ ዝቅ በማድረግ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ፖሊሲን እንዲከተሉ ለማስገደድ ያላቸውን ፍላጐት በይፋ ገልጸውታል ። ስለዚህ ከግል የምዕራብ ባንኮች የተገኘውን ብድር ሁሉ በገፍ ለመቀበል መሞከር የአንዳንድ ታዳጊ አገሮች መንግሥታት እንደሚሉት ጥገኝነትን የሚቀንስ ሳይሆን መልኩን ብቻ ቀይሮ የቀረበ ሌላ ጥገኝነትን መሻት ለመሆኑ ቅንጣት ያክል አያጠራጥርም ።

የምዕራብ የግል ባንኮች ለኋላቀር አገሮች የሚሰጡትን ብድር ከአንዳንድ ለራሳቸው ከሚስማማ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ጋር አያይዘው ያቀርባሉ ።የዚህ የኢኮኖሚ ጥያቄ መሠረታዊ ዓላማ የተበዳሪ አገሮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ የብድር መክፈል ችሎታ ለማረጋገጥ የታለመ ሊመስል ይችላል ። ሆኖም ይህ የፋይናንስ ሞኖፖሊስቶች አቀራረብ ተራማጅና የሶሺያሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች ለኤኮኖሚና ለማኅበራዊ ዕድገታቸው የቀየሱትን ዘላቂ ዓላማ በጽኑ እንደሚፃረር በግልጽ መገንዘብ ያስፈልጋል ። ከዚህም ጋር በአንዳንድ ኋላቀር አገሮች ውስጥ በአማካሪነት ደረጃ የሚያገለግሉ የምዕራባውያን ኤክስፐርቶች የግል ባንኮች የሚያቀርቡትን ይህን ጥያቄ በኤኮኖሚው ውስጥ የግል የኢኮኖሚ ይዞታው እንዲጠናከር ለማድረግ ካላቸው ዓላማ አንፃር በሚገባ እንደሚጠቀሙበት ለአንዳፍታ እንኳን መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው ።

በሌላ አንፃር ደግሞ እያደገ የመጣው የምዕራብ ባንኮች ዕዳ በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለውን የሀብት ሥርጭት የሚያዛባ መሆኑ ተረጋግጧል ። ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ያለባቸው ኋላቀር አገሮች በብዛት እያሉ ፣ የገንዘብ ክምችቱ በአብዛኛው ወደ ዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች እንዲጐርፍ መደረጉ ለዚህ በቂ ማረጋገጫ ነው ። የዚህ ሁሉ ድምር ሁኔታ የሚያረጋግጥልን መሠረታዊ ሀቅ

Digitized by Google

ቢኖር ፣ ከምዕራብ የግል የገንዘብ ድርጅቶች የሚገኝ ብድር በምንም ዓይነት መንገድ የኋላቀር አገሮችን የገንዘብ ችግር ሊያቃልል የማይችል መሆኑን ነው ። ከዚህም የተነሣ ዛሬ አያሌ ኋላቀር አገሮች ለብሔራዊ ነፃነትና ለማኅበራዊ ዕድገት የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ መሥዋዕትነትንና መራራ ትግልን የሚጠይቅ ለመሆኑ ጥርጣሬ አይኖርም ።

ሊፈታ ያልቻለ የአበዳሪዎች ችግር

በዓለም አቀፍ የባንክ ሥርዓት አሠራር ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከታዩት ከስተቶች መካከል ዋናው የኋላቀር አገሮች የውጭ ምንዛሪ ይዞታ እየከፋ መምጣት መሆኑ ይታወቃል ። የዚህ ዓይነቱን ችግር ሊያስከትሉ ከሚችሉት መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል አብዛኛውን ጊዜ በምዕራባውያን ዘንድ የሚጠቀሰው በኋላቀር አገሮች ላይ ያለው የግል ባንኮች ዕዳ እየጨመረ መምጣት ነው የሚለው ሲሆን ፣ ይህንንም አባባል አፋቸውን ሞልተው የሚናገሩት ራሳቸው አበዳሪ ባንኮች ሳይሆኑ የአንዳንድ ካፒታሊስት አገሮች የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊዎች ናቸው። አንድ የአሜሪካ ምክር ቤት የባንክ ኰሚቴ የቀድሞ ሊቀመንበር የግል ባንኮች ለኋላቀር አገሮች ሊሰጡ የሚችሉት ከፍተኛው የብድር መጠን ላይ ተቃርበዋል በማለት ሀሳብ መሠንዘራቸው ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። በእርግጥ ለእንደዚህ ዓይነቱ ፍራቻ ተጨባጭ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ከ1974 እስከ 80 ባለው ጊዜ ውስጥ ዕዳቸውን መክፈል ስላቃታቸው የዓለምአቀፍ ድርጅቶችን ዕርዳታ የተማጠኑት ኋላቀር አገሮች ቁጥር ከ3 ወደ 18 ከፍ ማለቱ ከዚህ ሁኔታ ጋር የተዛመደ ነው ።[11] በአንድ ወቅት በምዕራብ ባንኰች ዘንድ ተመራጭነት የነበራቸው አገሮች ሁሉ ከዚህ ሁኔታ ሊያመልጡ እንዳልቻሉ ተረጋግጧል ። ለዚህም ሁኔታ በተፈጥሮ ሀብት የታወቀችውን ዛየር ከምዕራብባን ኰች የወሰደችውን እስከ 500 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ብድር በ1975 አካባቢ በተፈጠረው የጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ቀውስ ምክንያት መክፈል ተስኗት እንደነበር በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ።[12]

ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት የምዕራብ የገንዘብ ድርጅቶች ፍራቻ ከሚያጠናክሩት ሁኔታዎች ሌላው ደግሞ ፣ ከአበዳሪዎችም ሆነ ከተበዳሪዎች አንፃር ሲታይ የብድሩ ዕዳ በአንድ አካባቢ ተከማችቶ መገኘት ነው ። በ1979 ከአሥር አገሮች ላይ አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ ባንኰች ብቻ ከ1 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕዳ ይፈለግባቸው ነበር ። የአሜሪካ ባንኮች ለአንድ አገር ሊሰጡ የሚችሉትን የብድር ጣራ ቀደም ሲልወስነው ነበር ። ከዚህ የብድር መጠን በላይ ለኋላቀር አገሮች በአሁኑ ጊዜ ምንም መስጠት እንደማያስፈልግ ከተለያዩ አካባቢዎች ይነገራል። ይህን ሁኔታ በማስመልከት «የቡንደስ ባንክ» ሊቀመንበር የነበረው ኦ.ኤሚንገር «እኛ አደገኛ ሁኔታ ላይ ልንወድቅ እንችላለን ። በባንኮች እጅ የሚገኘውን ትርፍ ገንዘብ በብድር የምንሰጣቸው ደንበኞች ይበቁናል»[13] ሲል መናገሩ ይታወሳል ። ከዚህ ሁኔታ ለመረዳት የምንችለው ፣ በ1980ዎቹ ውስጥ ዓለም አቀፍ የባንክ ሥርዓት ጥንቃቄ የተሞላበት እንቅስቃሴ ለማድረግ ማቀዱን ነው ። የኋላቀር አገሮችን የፋይናንስ ሁኔታ ለማሻሻል ውስን የሆነ የኢኰኖሚ ፖሊሲን መከተል እንደሚያስፈልግ በአንዳንድ የምዕራብ ምሁራን ዘንድ ተደጋግሞ መነገሩ ይታወሳል ። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ እርምጃ በምዕራብ የካፒታሊስት አገሮች ላይም ቢሆን የማይፈለግ ተጽእኖ ማስከተሉ አይቀርም ። የኋላቀር አገሮች የኢኰኖሚ ዕድገት መጠን በማዕከላዊ የዓመት ግምት በ3% በቀነሰ ቁጥር ፣ የአንዳንድ ምዕራብ አገሮችን የኢኰኖሚ ዕድገት መጠን በ1% መቀነስን እንደሚያስከትል አንዳንድ ግምቶች ይጠቁማሉ ።[14]

ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች አንዳንድ ምዕራባውያን የፋይናንስ ጠበብቶች የራሳቸውን

Digitized by Google

«መፍትሔ» ከመስጠት አልተቆጠቡም ። በዚህም መሠረት በግል ባንኮች ብድር አማካይነት የሚደረገውን የካፒታል እንቅስቃሴ በመቀነስ በመንግሥታት መካከል ባሉት የግንኙነት አካሎች በኩል ካፒታል ወደ ሌሎች አገሮች የመላኩ ተግባር መጠናከር ይኖርበታል የሚል እምነት አላቸው። በሌላ አነጋገር እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ፣ ዓለም አቀፍ የልማትና የእድገት ባንክ (IBRD) ወዘተ... ፣ በመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አማካይነት ወደ ኋላቀር አገሮች ካፒታል የማስገባቱ ተግባር መጠናከር አለበት ባዮች ናቸው ። በሌላ ወገን ደግሞ ሁኔታውን ከተለየ አንፃር የሚመለከቱ ወገኖችም አልታጡም ። አንዳንድ የአሜሪካ ባንኮች ተጠሪዎች ባንኮቻቸው ለኋላቀር አገሮች በሚሰጡት የግል ብድር ላይ ከፍተኛ የወለድ ክፍያ እስከገኙ ድረስ ፣ ብድሩ ለማን ፣ ምን ያህል ? ተሰጠ የሚለው ጥያቄ ብዙ እንደሚያስጨንቃቸው በይፋ አስታውቀዋል ።

በአጠቃላይ ሲታይ የአሜሪካ የፋይናንስ ሞኖፖሊስቶች በዚህ ጥያቄ ላይ ስላላቸው አቋም ፍሬድማን የተባለው ኢኮኖሚስት እንደሚከተለው አብራርቷል ። በእርሱ አባባል «የጥንቃቄ እርምጃዎች» በሚገባ ሥራ ላይ ከዋሉ ለኋላቀር አገሮች ብድር የመስጠቱ ሁኔታ ከሌሎች የባንክ ተግባሮች የበለጠ አደጋ የለውም የሚል ነው ። ፍሬድማን «የጥንቃቄ እርምጃዎች» በማለት የሚጠቅሳቸው ፤

—የተበዳሪ አገሮችን ብድር የመመለስ ችሎታ በሚገባ ማጥናትና ማረጋገጥ ፤

—በአበዳሪና በተበዳሪ አገሮች ውስጥ ያሉትን የመንግሥት አካሎች ዋስትና ለማግኘት ሰፊ ሙከራ ማድረግ ፤

—በተበዳሪ አገሮች ውስጥ ያሉ የድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖች ትርንጫፍ ድርጅቶችን ዋስትና ማግኘት (በተለይ ብድሩ ዉእነርሱ በኩል ሥራ ላይ የሚውል ከሆነ)

—ለሚጠረጠሩ ኪሣራዎች መሸፈኛ የሚውል የባንክ መጠባበቂያን ከፍ ማድረግ፣

—ያለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችንና የአካባቢ ባንኮችን ድጋፍና ትብብር ማግኘት የመሳሰሉት ናቸው ። [15]

የዚህ ዓይነቱ የታላላቅ ድንበር ዘለል የባንክ ሞኖፖሊስቶች አቋም ለኋላቀር አገሮች ብድር የመስጠቱ ተግባር ከፍተኛ የትርፍ መጠን ያስገኛል በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነው ። በ1980 የሁለተኛው ሩብ ወቅት በአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ብድር ከኋላቀር አገሮች የተገኘው ትርፍ በማዕከላዊ ግምት 1.2% መሆኑ [16] ፣ ይህን ዕምነት የሚያጠናክረው ይሆናል ።

በተጨማሪም ደግሞ በዓለምአቀፍ የገንዘብ ገበያ ላይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ውስብስብ እየሆነ የመጣውን ሌላ ሁኔታ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል ። የምዕራብ አገሮች የፋይናንስ አቋም እየተናጋና የዋጋ መናርም እየከፋ በመጣበት በአሁኑ ወቅት በግል ባንኮች ውስጥ ለአጭር ጊዜ የተቀመጠ የገንዘብ መጠን (Short Term Deposits) በጣም እየጨመረ በመምጣት ላይ ይገኛል። የዚህ ዓይነቱ የባንክ ተቀማጭ ገንዘብ በአብዛኛው የዘይት ገንዘብ (Petro-Dollar) መሆኑ የታወቀ ነው ። በ1980 ብቻ በአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ዘንድ የተከማቸው የዘይት ገንዘብ መጠን 41.5 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር ። [17] ከዚህም ሌላ በአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ውስጥ ባሉት ባንኩች ዘንድ ለተፈጠረው ተቀማጭን ወዲያውኑ ወደ ጥሬ ገንዘብ ለመለወጥ ያለው ችግር (Liquidity Problem) ፣ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ቀውስና በዚህም ሳቢያ ለባንክ ብድር ያለው ፍላጐት መቀዝቀዝ በተዘዋዋሪ መንገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከታቸው አይካድም ።

ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶች ምንም እንኳ በአመቺ ሁኔታ ውስጥ ባይሆኑም የቅ

ርብ ደንበኞቻቸው ለሆኑት ኋላቀር አገሮች ብድር የመስጠቱን ተግባር አላቋረጡትም ። ይህን በማድረጋቸውም ሊደርስባቸው የሚችለውን አደጋ በቸልተኝነት አይመለከቱትም ። የተበዳሪ አገሮችን የብድር መመለስ ችሎታ በጥንቃቄ የሚመረምሩበትን መንገዶች በሚገባ ከማዘጋጀታቸውም በላይ ፣ ለመጠባበቂያ ሊውል የሚችለውን የገንዘብ መጠን በበቂ መያዝ ጀምረዋል ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የቡርዧውን መንግሥትና ተቋሞቹን በመጠቀም ለራሳቸው ጥቅም የዋስትና ጥላ ለመዘርጋት መሞከራቸው ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ።

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችና የድንበር ዘለል ባንኮች ሕብረት

በድንበር ዘለል ባንኮች አማካይነት የሚሰጠው የግል ብድር በአንድ በኩል እየጨመረ ሲሄድ በሌላ በኩል ደግሞ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለኋላቀር አገሮች የሚሰጡት የገንዘብ መጠን እየቀነሰ በመምጣት ላይ ይገኛል ። ከ1974—78 ባለው ጊዜ ውስጥ የዘይት አምራችና ላኪ አገሮች ማኅበር (OPEC) አባል አገሮች «በልማት ዕርዳታ» ስም ለሌሎች የሰጡት የገንዘብ መጠን ከአጠቃላይ ብሔራዊ ምርታቸው (GDP) በአማካይ ግምት 5.7% ብቻ እንደነበር ይታወቃል ።[18]

ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የሚገኘው የገንዘብ መጠንም ቢሆን ፣ ከግል ባንክ ብድሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ መሆኑ ይታወቃል ። በ1974—79 ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF)ለኋላቀር አገሮች የሰጠው ብድር 11 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ሲሆን ፣ እነዚህ አገሮች በ1979 ብቻ ከኤውሮፓ የገንዘብ ገበያ የወሰዱት የግል ብድር ግን ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደነበር ይገመታል ። በተጨማሪም ዘ ኢኮኖሚስት የተባለው መጽሔት ባጠናቀረው መረጃ መሠረት ከ1974—79 ባለው ጊዜ ውስጥ ኋላቀር አገሮች ከነበረባቸው የተዛባ የክፍያ ሚዛን (Deficit) ውስጥ 3% የሚሆነው ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በተገኘ ብድር የተሸፈነ ሲሆን ፣ በተመሳሳይ ወቅት በግል ባንኮች ብድር የተሸፈነው ደግሞ 80% ገደማ መሆኑ ለተጠቀሰው አዝማሚያ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ።[19]

ብዙውን ጊዜ ዘይት አምራች ባልሆኑ ኋላቀር አገሮች ላይ ስላለው የዕዳ ጉዳይ ተገናኝቶ መወያየት በምዕራባውያን ዘንድ የተለመደ ነገር ሆኖአል ። የዚህ ዓይነቱ ውይይት አብዛኛውን ጊዜ በዓለምአቀፍ የፊናንስ ድርጅቶች አማካይነት እንዲካሄድ የግል ባንኮች አጥብቀው ይፈልጋሉ ። ለምሳሌ ያህል በ1976 «የፓሪስ ክለብ»* በተባለው የውይይት መድረክ ላይ ዛየር ያለባትን ዕዳ በሚመለከት አስተያየት እንዲደረግ ውሳኔ ተላለፈ ። በውሳኔውም መሠረት ዛየር ያለባትን የውጭ ዕዳ ከፍሎ ለመጨረስ የ10 ዓመታት የጊዜ ጭማሪ ተሰጣት ። በሌላ በኩል ደግሞ በለንደኑ የ1976 መግለጫ መሠረት ዛየር ሌላ የውጭ ብድር በግል ለማግኘት ከፈለገች እስከ ኅዳር 1976 ድረስ ያለባትን የግል ባንኮች የወለድ ክፍያ በዚያው ወር ውስጥ ከፍላ እንድታጠናቅቅ ፣ እስከ መጋቢት ወር 1977 ድረስ ደግሞ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ብድር ለማግኘት እንድትችል ፣ ከዚህ ድርጅት ጋር ድርድር እንድታደርግና ፣ በተጨማሪም ካለባት የግል ባንኮች ዕዳ ውስጥ 50ሚሊዮን ዶላር ያህሉን እስከ የካቲት 1977

* «የፓሪስ ክለብ» ከ1965 ጀምሮ የውጭ ምንዛሪ ችግር የደረሰባቸውን አገሮች የዕዳ ሁኔታ ለመመርመር ኦፊሴላዊ ባልሆነ መንገድ የተቋቋመ ድርጅት ነው

Digitized by Google

መጨረሻ ድረስ እንድታጠናቅቅ ከፍያውን ቶሎ መጀመር እንዳለባት ተወሰነ ።

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር የተደረገው ድርድር ዛየር አበዳሪ ባንኮች የሚፈልጉትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመከተሏ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋስትና ሆኖ መቅረቡንና ከግል ባንኩች የወሰደችውን ዕዳ ለመመለሷ የቅድሚያ ትኩረት የተሰጠ መሆኑን ነው ። ይህ ደግሞ በበኩሉ የቡርዥዋ መንግሥታት የግል ባንኩችን ጥቅምና ፍላጐት ለማስጠበቅ የቆሙና ከዚህ አቋማቸው ምንጊዜም ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ይሆናል ።

በድንበር ዘለል የግል ባንኩችና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መካከል ሊኖር ስለሚችለው ትብብር «ሞርጋን ጋራንቲ ትረስት» የተባለው ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1977 ማውሳቱ ይታወሳል ። ይህ ድርጅት በሚያስትመው አንድ መጽሔት ውስጥ እንደተጠቀሰው የአበዳሪ ባንኩችን እምነት ለመጠበቅ የገንዘብ አቋማቸው አስተማማኝ ያልሆነ ተበዳሪዎችን በመቆጣጠር በኩል ከምንጊዜውም የበለጠ የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ንቁ ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል ።[20] በዚህ ድርጅት አመለካከት በሁለቱ ተቋሞች መካከል የሚደረገው ትብብር ለሁለቱም ወገኖች ጠቃሚ የሚሆኑትን መረጃዎች ለመለዋወጥ ይረዳል የሚል ነው ። ከዚህም በመነሳት ሊደረጉ ስለሚችሉት የትብብር ቅርፆች ላይ በሁለቱ ወገኖች መካከል ውይይት ተጀመረ ። በዚህም መሠረት በ1977 በግንቦት ወር ቶኪዮ ላይ ተደርጎ በነበረው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ጉባኤ ላይ በዚያን ወቅት የአሜሪካ የገንዘብ ሚኒስትር የነበረው ኤም.ብሉሜንታል ያቀረባቸው ሀሳቦች ፤

—ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የግል ባንኩች ብድር በጋራ ሊሰጡ የሚያስችላቸውን መንገድ መቀየስ ፤

—ይህ ብድር በጋራ የመስጠቱ ሁኔታ መረጃዎችን በመለዋወጥ በተለይም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የተበዳሪ አገሮችን የፋይናንስና የኢኩኖሚ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን ለአበዳሪ ባንኩች በመስጠት ላይ እንዲያተኩር ወዘተ ... የሚሉ ነበሩ ።

ዳሩ ግን በዚህ የትብብር ጥያቄ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች በመከሰታቸው በቀረቡት ሀሳቦች ላይ ጉባኤው ስምምነት ሳያደርግ ቀረ ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ድንበር ዘለል የግል ባንኩች የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅትን አገልግሎት ከማግኘትና በእነርሱም በኩል በተበዳሪ አገሮች የኢኩኖሚ ፖሊሲ ላይ ተጽእና ከማሳደር ሊገታቸው አልቻለም ።

በሌላ በኩል ድንበር ዘለል ባንኩች ለኋላቀር አገሮች ብድር በሚሰጡበት ወቅት እንደ ዓለም አቀፍ የልማትና የዕድገት ባንክ (IBRD) ከመሳሰሉት ተቋሞች ጋር በተወሰነ ደረጃ ትብብር ሲያደርጉ ቆይተዋል። ከ1975 ጀምሮ ሁለቱም ወገኖች ብድር በጋራ የመስጠት ተግባር ጀምረው ነበር ። በዚህም መሠረት ዓለም አቀፍ የልማትና የዕድገት ባንክ የራሱ ደንበኞች በተመሳሳይ ወቅት ከግል ባንኩች ብድር ሊወስዱ የሚችሉባቸውን መንገዶች በማዘጋጀት ሲተባበር ቆይቷል ። በ1975 አጋማሽ ገደማ በዚህ ዓይነት መንገድ በጋራ ከተሰጠው ከ3.2 ቢሊዮን ዶላር የብድር ገንዘብ ውስጥ 550 ሚሊዮን ዶላር ያክሉ የግል ባንኩች ድርሻ እንደነበር ይታወቃል ።[21] የዚህ ዓይነቱን ከግል ባንኩች ጋር በጋራ ብድር የመስጠቱን ተግባር ሌሎችም የአካባቢ ባንኩች (የአሜሪካ የልማት ባንክ) እንደሚያከናውኑ ተረጋግጧል ።

በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችና በድንበር ዘለል የግል ባንኩች መካከል የሚደረገው ትብብር የብድር ውሎችን ለማጠናቀር

Digitized by Google

የኢኮኖሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ፣ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ ወዘተ... ለመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚረዳ በመሆኑ በግል ባንኩች ዘንድ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል ። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችም ቢሆኑ በዚህ ዓይነቱ ትብብር አማካይነት የገንዘብ አቅማቸውን ሊያጠናክሩና በተበዳሪ አገሮች ላይ የሚያደርጉትን ተጽእኖ የበለጠ ሊያሰፉ እንደሚችሉ ዕምነት አድርባቸዋል ።

የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በብድር አሰጣጥ ሁኔታ ላይ ከላይ ከተጠቀሰው የትብብር ደረጃ በማለፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ድንበር ዘለል የግል ባንኩች በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዋስትና የሚያገኙበትን መንገድ ለመፍጠር በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ ። በብዙዎቹ የምዕራብ አገሮች የፋይናንስ ባለስልጣናት አስተሳሰብ የድንበር ዘለል ባንኩችን የብድር እንቅስቃሴ የሚያስናክሉ ፣ ደንበኞች የሆኑት አገሮች ዕዳቸውን በጊዜው ባለመክፈላቸው ወይም ተቀማጭ ገንዘባቸውን ከእነዚህ ባንኩች ውስጥ በማውጣታቸው ሳቢያ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ የሚቀንሱ እርምጃዎችን አስቀድሞ መወጠን ያስፈልጋል የሚል እምነት አለ ። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በተለይም ከዘይት ሽያጭ የተገኘውን ከፍተኛ ገንዘብ ሥራ ላይ የማዋሉ ችግር እየጐላ በመጣበት በአሁኑ ወቅት ሰፊ ተቀባይነትን ያገኘ ይመስላል ።

በ1980 በተካሄደው «የቡድን አሥር» ማዕከላዊ ባንኩች ስብሰባ ላይ በአሁኑ ወቅት የዓለም አቀፍ የባንክ ሥራ በጣም እየተስፋፋ ስለመጣ ፣ አስተማማኝነቱንና ጥንካሬውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል የሚል ማስገንዘቢያ መሰንዘሩ ይታወቃል ። ለዚህም ዓላማ ተግባራዊነት ሲባል ተበዳሪ አገሮችንና የግል ባንኩችን እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎችን በተሻለ መንገድ ማጠናቀር ፣ ድንበር ዘለል ባንኩች የሌሎች የብሔራዊ ባንኩችን መረጃ በጊዜ እንዲያገኙ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠናቀሩትን የባንክ እስታትስቲክስ የማዘጋጀቱን ሁኔታ ማሻሻል እንደሚያስፈልግ በመጠቆም ውሳኔዎች አልፈው ነበር ። የዚህ ሁሉ ጥረት መሠረታዊ ይዘት የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ዓለምአቀፋዊ የባንክ እንቅስቃሴን በመቆጣጠሩ በኩል የገጠማቸው ችግር ፣ ዞር ዞር ለግል የፋይናንስ ካፒታል እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከሚደረግ ጥረት ተለይቶ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው ።

ለኋላቀር አገሮች የሚሰጠው የድንበር ዘለል ባንኩች ብድር እየጨመረ መምጣት የግል ካፒታል በነዚህ አገሮች የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ውስጥ እያደገ ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ ነው ። ይህም ሆኖ ግን የግል ካፒታል እንቅስቃሴ በምዕራባውያን አገሮች ውስጥ ያለውን የሀብት ክምችት በተስተካከለ መንገድ ለማከፋፈል እንደማይችል ከብዙ ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ለማረጋገጥ ተችሏል ። ከዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በመነሣት የኋላቀር አገሮችን የውጭ ፋይናንስ ችግር በማቃለሉ ተግባር ውስጥ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ተሣትፎ ያስፈልጋል የሚል ዕምነት ሊኖር ይችላል ። ዳሩ ግን ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው የኃይል አሰላለፍ አንፃር ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የኋላቀር አገሮችን ብሔራዊ ጥቅምና መሠረታዊ ፍላጐት ተከትለው እንደማይሰሩ ደግሞ የታወቀ ነገር ነው ። በ1981 በጥቅምት ወር በተደረገው የ22 መንግሥታት ባለሥልጣኖች ስብሰባ ላይ የንግድ ፣ የኤኮኖሚና የፋይናንስ ሁኔታዎችን በሚመለከት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ደረጃ አንድ ዓለምአቀፍ ውይይት እንዲካሄድ የተጠየቀው በነዚህ ምክንያቶች የተነሣ ነበር ። ከዚህም በተጨማሪ ዛሬ ኋላቀር አገሮች በአንድነት በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ በዕኩልነት ላይ ለተመሠረቱ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች የሚያካሂዱት ውስብስብ ትግል ከኢምፔሪያሊዝምና ከጥቅም ተካፋዮቹ የተጽእኖ ክልል ለመውጣት መሆኑ በገሀድ የሚታይ ነው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. Taken from OECD data.
2. "International Currency Review," Vol. 12, No. 3, 1980, p. 29 and "World Financial Markets", December, 1981, p. 14.
3. "International Currency Review," Vol. 12, No. 3, 1980, pp. 31-32.
4. "Transnational Corporations in World Development : A Re-examination," U.N., N.Y. 1978, p. 215.
5. According to IBRD, these are countries with per capita annual income of 550-2500 US dollars.
6. "CEPAL Review", No. 6, 1978, p. 94.
7. "International Currency Review," Vol. 12, No. 2, 1980, p. 12.
8. "Financial Times", June 16, 1979.
9. *Ibid.*, January 7 ,1981.
10. G.C. Abbot. "International Indebtdness and developing countries". (New-Delhi, N.P., 1980), p. 7.
11. "Far Eastern Economic Review", Oct. 19, 1979, p. 57.
12. R. Weston, "Domestic and Multinational Banking," London, 1980.
13. "US News and World Report", Nov. 18, 1980, pp. 93-94.
14. "Foreign Policy," Spring 1978, p. 134.
15. I.S. Freidman, *The Emerging Role of Private Banks in the Developing World*, N.Y., 1977.
16. "Financial Market Trends", Nov., 1981, p. 24.
17. Bank for International Settlements, Annual Report, 1981, p. 110.
18. "World Bank" 1980 Annual Report, p. 20.
19. The Economist, January 12, 1980, p. 67.
20. "The World Economy", May 1979, p. 232.
21. "The Banker", Nov., 1979, p. 46.

Digitized by Google

ባሕልና አብዮታችን

እያልነህ ሙላት

ባህል የሰው ልጅ በመላው ታሪኩ በማኅበራዊ ተግባሩ. ወቅት የፈጠረውና ያከማቸው የቁስ አካላዊና የመንፈሳዊ ቅርሶች አጠቃላይ ድምር ነው። [1] ባሕል የኅብረተሰብ እንቅስቃሴና ዕድገት ውጤት ነው። የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ከታላላቆቹ የቁስ አካላዊ ቅርሶች አንዱ ናቸው። ስልተ ምርት በአጠቃላይ የባህል ወሳኝ መሠረት ነው።

የባህል ቁስአካላዊ እሴቶች ከስልተምርት ውስጥ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ ፤ የምርት የቴክኒክ ደረጃ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ እርምጃዎች በምርቱ ውስጥ ያላቸውን ስፋትና ጥልቀት፣ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ሰዎች ያላቸው ችሎታና ዕውቀት፣ ሳይንሳዊ የሥራ ቅንብርና መልኮች (በጉልበትና በአዕምሮ ሥራ፣ በከተማና በገጠር መሀከል ያለው ልዩነት ወይም አንድነት፣ የግለሰብ ጠባብ ወይም ሁለገብ የሙያ ትምህርት ዕድገት ወዘተ...)፣ በኢንዱስትሪ ውስጥ የሳይንሳዊ ሥራ ቅንብር፣ ከዘመናዊ የቴክኖሎጂ እርምጃዎች ደረጃ ጋር በመጣጣም በቀን ተቀን ኑሮአቸው ውስጥ የሰዎችን ቁስ አካላዊ ፍላጐቶች የማርካት፣ በኅብረተሰብ በተደነገጉ ደረጃዎችና ልማዶች አንፃር ሰዎች በየዕለት ኑሮአቸው የሚያሳዩት ባህሪያት፣ በኢንዱስትሪ ውስጥ አዲስ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ የቴክኒክ እርምጃዎች መጠቀም (ኤሌክትሪፊኬሽን፣ አቶሚሽን፣ ራዲዮ ቴክኖሎጂ ወዘተ...)። እነዚህ ሁሉ በቁስ አካላዊ መስክ የሚገኙ የባህል ቅርጾች ናቸው።

የኅብረተሰብ የተለያየ የንቃተ ህሊና ቅርጾች (ለምሳሌ ሐይማኖት፣ ህግ፣ ሳይንስ ኪነጥበብ፣ ግብረገብነት፣ ወዘተ...) የሰው ልጅ በመንፈሳዊ፣ (በሕሊናዊ) ሥራው የሚያመርታቸው መንፈሳዊ (ሕሊናዊ) ባሕል

Digitized by Google

ናቸው ። የመንፈሳዊ ባህሎች በሙሉ ከምርት መገልገያዎች ፣ ከመለዋወጫና ከመጠቀሚያ እቃዎች ጋር የተያያዙ የሰው ልጅ የሥራ ውጤቶች ናቸው ። ይህም ጠቀሜታ ያለው የመንፈስ ጥበብ ከኅብረተሰብ አጠቃላይ ዕድገት ጋር ፣ ከምርት ኃይሎች መዳበር ጋር እያደገ የሚሄድ ነው ።

የሰው ልጅ የምርት ተግባር ሁለት መሠረታዊ መልኮች (ክፍሎች) አሉት ። የቁሳዊና ሕሊናዊ ምርቶች ባህልም እንዲሁ ከምርት ክፍፍል ጋር የሚጣጣሙ ሁለት መልኮች አሉት ። እነሱም ቁሳዊ ባህልና ሕሊናዊ ባህል ናቸው ። ቁሳዊ ባህል የምንለው ቁሳዊ ክንውንና ውጤቱን ፣ ለምሳሌ የቴክኒክ መሣሪያዎች ፣ መኖሪያ ቤቶች የቤት ዕቃዎች የመገናኛ መሣሪያዎች እና የመሳሰሉትን ፣ ያጠቃልላል ። ሕሊናዊ ባህል የሚባለው የንቃተ ሕሊናንና የአእምሮ ውጤቶችን የሚጠቀልል ነው ። ለሕሊናዊ ባህል ምሳሌ የሚሆኑት ዕውቀት ፣ ትምህርት ፣ ሳይንስ ፣ ኪነጥበብ ፣ ሕግ ፣ ፍልስፍና ፣ ፖለቲካ ፣ ኃይማኖት እና የመሳሰሉት የሕሊና ክንውን ናቸው ።

በመሠረቱ ባህል መንፈሳዊና ቁሳዊ ተብሎ ቢከፈልም ፣ በማቴሪያል ባህል ውስጥ ለመንፈሳዊ ባህል ሚና የለውም ማለት አይደለም ። የመንፈሳዊ ባህል ዕድገት የቁሳዊ ባህልን ዕድገት ያዳብራል ። የቁሳዊ ባህል ዕድገትም የመንፈሳዊ ባህል እድገትን ያራምዳል ። ለምሳሌ የቁሳዊ ባህል ውጤት የሆነው የቴሌቪዥን መዳበር የመንፈሳዊ ውጤት የሆነውን ቲያትርን ፣ ሲኒማን ወዘተ... ያጐለምሳል ። በአንፃሩ ደግሞ ጥልቀት ያላቸው የሥነ ጽሑፍ የፈጠራ ሥራዎች ሲፈልቁለ እነሱ ሥራ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤች እንዲፈለሰፉ ይረዳሉ ።

በተጨማሪ ባህልን በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ማለት ቁሳዊና መንፈሳዊ ብለን ስንከፍል ቢያንስ ሁለት አበይት ነገሮችን ማጤን ይኖርብናል ። አንደኛው ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል በአንድነት ተዋህደው ሊከሰቱ መቻላቸው ነው ። ለምሳሌ በአንድ መጽሐፍ ወይም በቴሌቪዥን ፣ ወይም በአንድ ሙዚቃ ወዘተ... ውስጥ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች በአንድ ላይ ተዋህደው እናገኛቸዋለን። የመጽሐፉ ወረቀት የማቴሪያል ባህል ውጤት ሲሆን፣ በመጽሐፉ ላይ የሰፈረው ሀሳብ ግን መንፈሳዊ ነው ። የሙዚቃው ዜማ መንፈሳዊ ሲሆን የሙዚቃ መሣሪያው ቁሳዊ ባህል ነው። የቴሌቪዥን መሣሪያው ቁሳዊ ሲሆን በውስጡ የሚተላለፈው ቲያትር ፣ ሲኒማ፣ ወዘተ...ግን መንፈሳዊ ነው።ሁለተኛ፣ ቁሳዊ የሆነው ባህል(ለምሳሌ የምርት መገልገያን) ለማምረት ያለሰው አስተሳሰብ፣ ያለሰው ዕቅድና ተግባር ፣ ያለ ህሊናዊ ባህል ሚና የማይቻል መሆኑ ነው ። [2] ስለሆነም ባህልን ቁሳዊና ህሊናዊ ብለን ስንከፍል ሁለቱ ክፍሎች ያላቸውን ግንኙነት ባለመርሳት ነው።

በአጠቃላይ ባህል በታሪክ የተወሰነ የሕዝብ ችሎታዎች ፣ ዕውቀቶች ፣ አመለካከቶች ፣ አስተሳሰቦችና ስሜቶች አጠቃላይ ድምር ሲሆን ፣ ዓላማውም እነዚህ በምርት ቴክኒክና በሕዝባዊ አገልግሎቶች ፣ በሕዝቡ የትምህርት ደረጃ ፣ ማኅበራዊ ኑሮን በሚያደራጁ ፣ የማኅበራዊ ተቋሞችን በሚቆጣጠሩ ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዕድገቶች ፣ በኪነጥበብና በሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ መሠረት መጣልና ቁስ አካላዊ ማድረግ ነው። የባህል ንጥረ ነገሮች ሁሉ በመሠረቱ የተያያዙና የቀረበ መስተጋብር ያላቸው ናቸው ። እነዚህ በአንድ በኩል ለኅብረተሰቡና ለግለሰቦች መንፈሳዊ ፍላጐቶች ሲጠቅሙ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በቁስ አካላዊ ባህርያቸው የየዕለቱን የኑሮ ሁኔታዎች ፣ የምርት ዕድገትንና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ያገለግላሉ።

የሕዝቡ የቀን ተቀን (የየዕለቱ) ኑሮ ማለት ሕይወትን ለመጠበቅና የሕዝቡን ፍላጐቶች ለማሟላት በቤተሰብና በኅብረተሰብ ውስጥ ከቁሳዊ ሀብት መጠቀም ጋር የተያያዙ ልማዶች (ወጐች) በቅደም ተከተል

Digitized by Google

የሚከናወኑ ተግባራትና ዘዴዎች አጠቃላይ ድምር ነው ። መጠለያ ልብስና ምግብ የሕዝቡ የኑሮ ዋስትዋ ናቸው ። የሚፈጠሩትም በማምረት ሂደት ከቁሳዊ ሀብት ሲሆን፣ ተፈጥሮአቸውም (የተሰሩበት ነገር ፣ ተግባራቸው ወዘተ...) ደግሞ የሚወሰነው በምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ነው ። የሕዝቡ የቀን ተቀን ኑሮ የሚወሰነው በምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ላይ ብቻ ሳይሆን በምርት ግንኙነቶች ባህሪ ፣ በኅብረተሰብ የሀብት ክፍፍል ፣ ፍጆታ ወዘተ ... ላይም ጭምር ነው ።

ሀሳባውያን ፈላስፎች መንፈሳዊ ባህልን መሠረቱ ከሆነው ከምርት ግንኙነት ነጥለው ያቀርቡታል ። በነሱ አስተሳሰብ ለባህል መሠረቱ እራሱ ባህል ፣ ከስልተ ምርትና ከምርት ግንኙነት ተነጥሎ እንጂ የቁስ አካል መሠረት የለውም ። ማርክሲስቶች ግን ለባህል ዕድገት የምርት ግንኙነቶች መሠረት መሆናቸውን ፣ የባህል ዕድገት ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር የተያያዘ መሆኑን ያረጋግጣሉ ። በተጨማሪም ባህል ምንም እንኳን መሠረቱ የሰው ልጅ ቁሳዊ ክንውን ቢሆንም መልሶ በመሠረቱ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል ። በሌላ አነጋገር ባህል ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገት እንደሁኔታው የዕድገት አፋጣኝም እንቅፋትም ሊሆን ይችላል ማለት ነው ።

በመሠረቱ ማንኛውም የቴክኒካዊ ፈጠራ የሚመነጨው ከምርት ፣ ከሕዝቡ የኑሮ ፍላጎቶች ፣ ከሰፊው ሕዝብ የሥራ እንቅስቃሴና ችሎታ ነው።ከቀን ተቀን የሕዝቡ ኑሮ ፣ ከኑሮ ፍላጎቶቹና ከሕዝቡ የሥራ ሁኔታዎች ጋር ይበልጥ የተያያዘ ባህል በይበልጥ ጠቃሚ ነው ። የሕዝቡ ነባራዊ ፍላጎቶችና የባህል መጣጣም ባሕሉም በሚያስተማምን መንገድ እንዲያድግ ፣ እንዲበለጽግ እንዲዳብር ያደርጋል ። ይህ ሁኔታ ከዓለም ታላላቅ የስነጽሑፍ ፣ የኪነ ጥበብ፣ የሙዚቃ ፣ የሥዕል ወዘተ. . .ሰዎች ሥራ አንፃር በግልጽ ሊታይ ይችላል ። እነዚህ የባሕል ሰዎች ታላቅና ዕውቅ ሊሆኑ የቻሉት ስለ ሕዝባቸው የፈጠራ ሥራ እጅግ የላቀ ዕውቀት ስላላቸውና የሕዝቡንም የተከማ ባህላዊ ቅርስ መሠረት ስላደረጉ ነው ።

ባህል ፈጣሪው ሰፊው ሕዝብ ነው። ታዲያ እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ነገር ምንም እንኳን ባህል በሠራተኛው ሕዝብ የሚሠራ፣ የሚፈጠር ቢሆንም በመደብ ስርዓተ ማኅበራት መልሶ ይህንኑ ፈጣሪውን ማለትም ሠርቶ አደሩን ለመጨቆኛ ሊውል የሚችል መሆኑን ነው ። በባሪያ ፣ በፊውዳልና በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ የታየውና የሚታየው ይኸው ሀቅ ነው ። የቡርዧው ኅብረተሰብ ባህል በይበልጥ የቡርዧውን መደብ ጥቅም ያስከብራል ፤ ይህ ባህል ለምዝብሮች መጨቆኛ ፣ ማደናገሪያ ፣ ሆኖ ያገለግላል ። በዚያው አንፃር ደግሞ በዚሁ በቡርዧው ኅብረተሰብ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ይዘት ያላቸው የሰፊው ሕዝብ ባህል የሆኑ የባህል መልኮች ይከሰታሉ ፤ እስከወሰነም ደረጃ ያድጋሉ ። የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ባህል የሚያብበውና የበላይነቱን የሚጎናጸፈው የሶሻሊስት አብዮት ድል ሲቀዳጅ ነው ። በባህል አብዮት አማካይነት የሶሻሊስት ባህል ሲገነባ እያንዳንዱ ሠራተኛ ሕዝብ የባህል ፈጣሪ ብቻ ግይሆን በባሕል ተሳታፊም ይሆናል ። በባሕል ውጤቶች ይገለገላል ፤ መንፈሱን ያድሳል ፤ አእምሮውን ያበለጽጋል ። የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ፣ የመንፈሳዊ ባህል ሚና ከመቼውም የበለጠ የሚዳብርበት ኅብረተሰብ ነው ። ሥነ ጽሑፍ ፣ ኪነት ፣ ሕዝባዊ ፈጠራና የመሳሰሉት የሚበለጽጉበትና ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱበት በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ። እነዚህን የባሕል ገጾች ማዳበር የሶሻስት ኅብረተሰብን መንፈሳዊ ሀብት ማበልጸግ ማለት ነው ።

የሶሻሊስት ባሕል በሰፊው ሕዝብየ ሚፈጠር ሲሆን የሚያድገውም ከሰው ልጅ የተከማቸውን ቁስ አካላዊና መንፈሳዊ ቅርሶች ሁሉ በቁጥጥሩ ስር በማዋልና እነር

Digitized by Google

ሱንም መሠረት በማድረግ ነው ። በዚህም የሶሻሊስት ባህል ከዓለም ሥልጣኔ የዕድገት አቅጣጫ ያፈነገጠ አንድ ነገር ሳይሆን ለአርጌው የባሕል ቅርስ ሕጋዊ ወራሽ መሆኑን ያረጋግጣል ። የወዝአደሩን ባህል ፣ ከጥንቱ ሳይያያዝ ፣ ከምንም ተነስቶ ማዳበር አይቻልም ። የወዝአደሩ ባህል ከምን ተነስቶ እንደሚያድግ ሌኒን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፣ «ወዝአደራዊ ባሕል የሰው ልጅ በካፒታሊስት ፣ በፊውዳልና በቢሮክራሲ ኅብረተሰብ ቀንበር ስር ከተከማቸው የዕውቀት መጋዘን ተነስቶ የሚያድግ መሆን አለበት።» [3] በተጨማሪም ፣ ሌኒን «እኛ ካፒታሊዝም ያፈራውን ባሕል መውሰድ አለብን ። የዚህን ሥርዓተ ማኅበር ሳይንስ ፣ ቴክኖሎጂ ዕውቀትና ሥነ ጥበብ መውሰድ አለብን ፤ » [4] ብሏል ።ኮሚኒስቶች የሰው ልጅ በረጅም ታሪኩ ያፈራውን ባሕል ለሶሻሊዝም ግንባታ የሚጠቀሙበትና የሚያበለጽጉት ጠቃሚ የሆነውን የባህል ገጽታ ነው ። ተመርጦ እንጂ የተወረሰው ባሕል ሁሉ አይገበሰበስም ። ሌኒን ይህን አስመልክቶ ሲያስገነዝብ ፣ «እኛ የምንወርሰውን እንደ አንድ የታሪክ ቅርሶችን እንደሚንከባከብ ሰው አናየውም ። የተወረሰን ቅርስ መንከባከቢ ማለት ራስን በተወረሰው ወስኖ ማስቀረት ማለት አይደለም» [5] ብሏል። ስለሆነም የሕዝባዊና የሶሻሊስት ባሕል ገንቢዎች ከዱሮው ባሕል የሚወስዱትና የሚያበለጽጉት ለሰፊው ሕዝብ የሚጠቅመውን ሲሆን፣ ለመውሰድና ላለመውሰድ መለኪያውም መደባዊ አመለካከት ነው ። በሁሉም የባሕል መልኮችና ባሕላዊ ግንባታ የቡርዧውን ርዕዮተዓለም በጽኑ መታገል እንደሚያስፈልግ ሌኒኒዝም ጥሪ ያደርጋል። የኮሙኒስትን አመለካከት መሠረት በማድረግ የሶሻሊስት ባሕልን እንዲፈጠር ይጠይቃል።

የሶሻሊስት ባሕል እንደ ቡርዧው ባሕል ብሔራዊ ቅርጽ አለው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በዕኩልነት የየራሳቸውን ባሕል ያዳብራሉ ። በአገሮቻቸው መካከልም የቁሳዊና የመንፈሳዊ ባሕል ውጤቶች ልውውጥ ያደርጋሉ ። በዚህም ልውውጥ የሶሻሊስት ባሕልን በበለጠ ያዳብራሉ ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የእያንዳንዱ ብሔረሰብ ወይም ብሔር ባሕል እኩልነት ስለሚረጋገጥ እያንዳንዱ ብሔረሰብ እና ብሔር የራሱን ባሕል ለምሳሌ ኪነት ፣ ሥነጽሑፍ ፣ ወዘተ... ያዳብራል ፤ በውጤቱም ይኩራል ። እያንዳንዱም ብሔረሰብ እና ብሔር ከራሱ ወይንም ከሌላ ብሔር ባሕል ጠቃሚ የሆነውን መምረጥና ወስዶ የማዳበር መብቱ የተጠበቀ ነው ። በዚህም መልክ የብሔራዊ ባሕል መፈክር ከባሕል ዓለም አቀፋዊ ይዘት ጋር በሁብር የሚዋሀድ እንጂ የሚቃረን አይሆንም። በቅርጹ ብሔራዊ የሆነው ባሕል በይዘቱ ኅብረተሰባዊ ይሆናል ማለት ነው ። ሁሉም ሠራተኛ ሕዝቦችን የሚመለከት የሶሻሊስት ባሕል ነውና ። ስለሆነም የሶሺያሊስት ባሕል የምንለው ባለፈው የሰው ልጅ ተራማጅ የባሕል ቅርሶች ላይ ተመስርቶ በሶሺያሊስት የግንባታ ሒደት ወቅት የሚከሰት አዲስና ከፍተኛው የሆነ የባሕል ደረጃ ነው።

የሶሺያሊስት ባሕል ከዘመናዊ የቡርዧ ባሕል የሚለየው በራሱ በኅብረተሰብ ተፈጥሮውና በሐሳቡ ይዘት ፣ በፈጠራ ዘይቤው፣ በቅርጹና አጠቃቀሙ ወዘተ...ነው። የሶሻሊስት ባሕል ባህርይ በኮሚኒስታዊ ሐሳብ የበለጸገ ነው ። ወገናዊ የሆነ ፣ ሳይንሳዊ አመለካከት ያለው ፣ ሕዝባዊ ፣ ሰብአዊና ሕብረታዊ ነው ። የአገር ፍቅር ስሜት ያለውና ዓለምአቀፋዊ ነው ። ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉትን ፣ ተራማጅ የሆኑትን የሕዝብ ባሕላዊ ቅርሶችን የሚጠብቅ ነው ። በባሕላዊ መስተጋብር ብሔራዊ ባሕልን በጋራ አዳባሪ ነው። እንደሌሎቹ የሶሻሊስት ግንባታ ገጽታዎች የሶሻሊስት ባሕልም የሚገነባው በኮሚኒስት ፓርቲው መሪነት ነው ።

ቁሳዊ ባህልና መንፈሳዊ ባህል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን ፣

Digitized by Google

በአጠቃላይም የአንዱ እድገት የሌላውም እድገት፣ የአንዱ ኋላቀርነት የሌላውም ኋላቀርነት መሆኑን በቅርብ ለማየት የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያን ሁኔታ በአጭሩ እንመለከታለን ።

ባለፈው ስርዓት የፊውዶ ቡርዧው ኢትዮጵያ ገዥ መደብ በሕዝቡ የቀን ተቀን ኑሮ ላይ የመወሰን ሥልጣን ወይም የበላይነት ነበረው።ሥልጣኑን ወይም የበላይነቱን ያረጋገጠው በኢኮኖሚና በፖለቲካዊ መስክ ብቻ ሣይሆን በመሠረቱ የሥርዓቱ ነፀብራቅ በሆነው በባሕልም አካባቢ ጭምር ነበር። ስለ ባሕል ስናነሳ ከአገራችን የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር አንፃር ማየት ያስፈልጋል ። ከብዙ የኅብረተሰብ ግንኙነቶች የኢኮኖሚው ማለትም የምርት ግንኙነቱ ዋናና ወሳኝነት ያለው ነው ። ለዚህም ነው ቁሳዊ ምርትን ለማምረት የሚደረገው ጥረት የታሪካዊ ቁስ አካላዊነት መሠረት የሆነው። የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር በአንድ የምርት ዓይነት ላይ የተመሠረተ የማኅበራዊ ክስተቶችና ሂደቶች (የኢኮኖሚ ግንኙነት ፣ የርዕዮተዓለም ፣ የቤተሰብ ፣ የኑሮ ዘይቤ ወዘተ ...) አጠቃላይ ድምር ነው።አንዱ የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር በሌላ ይበልጥ በተሻሻለው ይተካል ። በዚህ መልክ ኅብረተሰብ ያድጋል ። ታዲያ የፊውዶ ቡርዧው የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር ከኮሚኒስታዊ የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር አንፃር ሲታይ እጅግ ኋላ ቀር ነበር ። ይህ ደግሞ በተራው የኋላ ቀር ሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር ነፀብራቅ የሆነው ባሕል እንደዚሁ ዝቅተኛና የተዥጎረጎረ እንዲሆን አድርጎታል ።

የኢትዮጵያ ባሕል ኋላቀርነት ምክንያት ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅንብር ዝቅተኛነት ውጤት ነው ። ይህም ብቻ አልነበረም ። የባሕሉ ምንጭ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ ሳለ ባሕሉ እንዳያድግ ፣ እንዳይዳብርና እንዳይፋፋ በፈላጭ ቆራጭ የነጋሲ መንግሥት ፖለቲካ የፊጥኝ ታስሮ ነበር ። በዚህ ፖለቲካ አማካይነት ሰፊው ሕዝብ ተገናኝቶ በመወያየት ለችግሮቹ መፍትሔ እንዳያገኝ ተደርጓል ። የፊውዳሉ አመለካከት በዕደ ጥበብ ሥራና በአንዳንድ ሙያ ላይ የተሰማሩትን ሰዎች እንዲናቁና እንዲንቋሸሹ አድርጓል ። እነዚህንም የሙያ ሰዎች ኅብረተሰቡ እንዲያገላቸው አድርጓል ። ለዚህም አድኃሪ ፖለቲካ መሳካት የአመለካከት አንድነት ያላቸው ኃይማኖቶች መማሪያ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ። እንዲያም ሆኖ ታዲያ ንጉሡ ፣ መኳንንቱ ፣ መሣፍንቱ ፣ ጉልተኞቹ በአጠቃላይ የገዥው መደብ አባላት በሚኖሩባቸው ከተሞችና አካባቢዎች አንዳንድ የባሕል ዘርፎች በመጠኑም ቢሆን አንፃራዊ የሆነ ዕድገት አሳይተዋል በእርግጥ የዕድገቱን ዲያሌክቲክስ በምናጤንበት ወቅት የገዥውን መደብ ድሎች ለመጠበቅ ፣ ለባዕድ ባሕል መስፋፋት አካባቢውን ለማመቻቸት ያህል የተደረገ እንጂ በማምረት ሂደት ውስጥ ሰፊው ሕዝብ የምርት መገልገያዎችን እንዲጠግን ፣ ይበልጥ የሚሻሻሉበትን ሁኔታዎች እንዲፈጥር በኢንዱስትሪ ውስጥ የሳይንስና የቴክኒክ ርምጃዎችን የመጠቀም ልምድን እንዲያዳብር ፣ በአጠቃላይ በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ ብዙ ብሔረሰቦች ፣ እንደየዕድገት ደረጃቸው ልዩ ልዩ ባሕሎች የሚገኙባትን አገር ብሔራዊ ባሕል ለመገንባት እንዳልነበረ ግልጽ ነው ። ብሔረሰቦች በልዩ ልዩ የዕድገት ደረጃ ላይ መገኘታቸውና በአንዳንድ አካባቢ የባዕድ ባሕል ሠርጎ መግባቱ ባሕላችንን በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ እንዲገኝና እንዲዥጎረጎር ስላደረገው፣ ከዚህ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን አዲስ ብሔራዊ ባሕልን መገንባት ቀላል አይሆንም ።

የባህል አብዮት ይዘትና አስፈላጊነት

የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ድሎችን በመንከባከብና በማሳደግ ወደ ሶሻሊስት አብዮት በሚደረገው ሽግግር በየፈርጁ የበ

Digitized by Google

ባይነትን ለመተዳደት ትግላችን ለአንድ
አፍታ እንኳ ጋብ የሚል አይሆንም ። ብዙ
አብዮታዊ መስዋዕትነትን ከፍለን አብዮ
ታችንን እዚህ ደረጃ ላይ በማድረሳችን ሳን
ኩራራ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎችንና ጥረ
ቶችን በእጥፍ በመጨመር በሽግግሩ ወቅት
ከሚከናወኑት አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች
መሀከል አንዱ ገጽታ የሆነውን የርዕዮተ
ዓለምና የባሕል አብዮትን ማፋፋም በጣም
አስፈላጊ ነው ። ምክንያቱም አርጌው ባሕል
በአዲሱ ባሕል የሚተካው ፣ አድኃሪው ርዕ
ዮተዓለም በተራማጁ የሚለወጠው በዚህ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ አማካይነት ነው ።
ይህም ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ተስማሚ
በሆነው መሠረት ላይ ላዕላይ መዋቅሩ እን
ዲዘረጋ ድጋፍ ይሰጣል ።

ዛሬ መልክ እያበጀ በመሔድ ላይ የሚገ
ኘው አዲሱ ባህል የአርጌው የፊውዶ ቡር
ዧው ባህል ቀጥተኛ ተቃራኒ የሆነ ፤ ወዝ
አደራዊና ሶሻሊስታዊ ባህል ነው ። በእር
ግጥ ይህን ከመደብ ሥርዓት ባህሎች እጅግ
የላቀውን ባህል መገንባት ለሰፊው ሕዝብ
ቀላል አይሆንም ። ከዝቅተኛ የባህል ደረጃ
ከማሀይምነት ወደ ከፍተኛው የባህል ደረጃ
እመርታ ማድረግ ያስፈልጋል ። እንደዚህ
ዓይነቱ እመርታ ደግሞ በመላው ኅብረተ
ሰብና በሠርቶ አደሩ ሕይወት ውስጥ ከሚ
ከናወን ሐቀኛ የባህል አብዮት ውጭ ሊታ
ይ አይችልም ። ስለሆነም የሶሻሊዝም ግን
ባታ አርጌው ፣ ኋላቀሩ ስልተምርት ወደ አ
ዲስና ተራማጅ የሶሻሊስት ስልተ ምርት
የሚያደርገው አብዮታዊ ሽግግር ብቻ ሳይ
ሆን ፣ የፊውዶ ቡርዧው ባህል ወደ ሶሻሊ
ስት ባህል የሚያደርገው አብዮታዊ ሽግግ
ርም ጭምር ነው ። ይህም ሽግግር ወይም
የባህል ለውጥ በአንዲት ቀን ጀምበር የሚ
ከናወን ሳይሆን ካለፉት ልምዶች በመቅሰ
ም ደረጃ በደረጃ የሚያድግ ነው ።

ባህል መላውን የማኅበራዊ ኑሮ ማለትም
ከምርት ጀምሮ እስከ ርዕዮተዓለም መስ
ኩች ድረስ ያሉትን አቅጣጫዎች እንደሚ
ያቅፍ አይተናል ። ኩሚኒስቶች የባህል ኋላ
ቀርነትን እንደ ቋሚ ክስተት አድርገው አ
ይወስዱትም ። ባህል የምርት ግንኙነት ነጸ
ብራቅ እንደመሆኑ የእርሱ መለወጥ ባህል
ንም ይለውጠዋል። የሶስዮ ኢኮኖሚ ቅን
ብሩ መሻሻል ባህሉን ያሳድገዋል ። በዚ
ያም ላይ ባህል እንደ ማኅበራዊ ኑሮ ብዙ
አቅጣጫዎች ያሉት ስለሆነ ከታህታይና
ከላዕላይ መዋቅሩ ለውጥ አንጻር ከሚሻሻ
ለው የቀን ተቀን ኑሮ ጐን የባህሉ የተ
ለያዩ ዘርፎች በዚያው መጠን ያድጋሉ ።
በተለይም ደግሞ በአብዮቱ አማካይነት
በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከናወኑት ለው
ጦች በሕዝቡ ባሕሪያት ፣ አመለካከቶች ፣
አስተሳሰቦች ፣ ዝንባሌ ፣ ንቃተ ሕሊና ፣ የ
ፈጠራ ችሎታና ቋንቋ ላይ ፈጣን ውጤት
አሉዋቸው ። በዚህ መሠረት ሥር ነቀል
የሆነውና በየካቲት 1966 የፈነዳው አብዮ
ታችን በየጊዜው ሥር ነቀል እርምጃዎችን
በመውሰዱ ከፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት አ
ንጻር ሲታይ ታህታይና ላዕላይ መዋቅሩን
በሚያስተማምን ሁኔታ በመቀየር ላይ ይገ
ኛል ። ይህ ደግሞ ባህል በሁሉም አቅጣጫ
ዎች እንዲያድግ ድጋፍ ይሰጣል ። በአገራ
ችን የማምረቻና የማከፋፈያ ተቋሞች በመ
ንግሥትና በሕዝብ ቁጥጥር ሥር መሆን
ለሕዝባዊ ባሕል ፣ ለወዝ አደራዊ ባሕል
ዕድገት አመች ሁኔታን ፈጥሯል ። የተፈ
ጠረውን ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታ በመጠ
ቀም የባሕል አብዮትን አካሂዶ ኋላቀርና
ጐጂ የሆኑትን የጾታ ጭቆና ፣ ትምክህተ
ኛነትንና ጠባብነትን ፣ ማሃይምነትን ፣ ብኩ
ንነትን ወዘተ... ማጥፋት እጅግ አስፈ
ላጊና መሠረታዊ ነው ።

እንደ አብዮታችን የዕድገት ደረጃ የተ
ወሰዱት አብዮታዊ እርምጃዎች ሰፊው ሕ
ዝብ ጭቆናና ብዝበዛን አስወግዶ ፍትሕና
እኩልነት የሰፈነበት ፣ ብዝበዛ የሌለበት
ኅብረተሰብ መገንባት የሶሻሊስት አብዮ
ትን እስከዛሬ ከታሪክ ከታዩት አብዮቶች

Digitized by Google

ሁሉ ልዩ ከሚያደርጉት ጠባዮቹ ዋንኛው ነው ። ማርክስና ኤንግልስ የጀርመን አይዲዮሎጂ በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዳስቀመጡት ፡

> እስከዛሬ ድረስ በድል የተገኙ መብቶች ውስን በሆኑ የምርት ኃይሎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። እነኝህ የምርት ኃይሎች ሊሰጡ የሚችሉት ምርት ለጠቅላላ ኅብረተሰቡ በቂ አልነበረም ። እናም ዕድገትም የሚቻለው ጥቂት ሰዎች በሌሎች ትከሻ ፍላጐታቸውን ሲያረኩ ነበር ። ስለሆነም ሌሎች—ብዙሀኑ—እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ፍላጐቶቻቸውን ለማርካት የማያቋርጥ ትግል በማድረጋቸው ለጊዜው ማለትም አዲስ የምርት ኃይሎች እስኪወለዱ ድረስ ከማንኛውም ዕድገት ተወግደው ጥቂቶች ግን ዕድገትን በሞኖፖል ይዘውታል ፡፡[6] ብለው ነበር ።

የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ በኢኮኖሚ ግንባታውና በርዕዮተዓለም ትግሉ አማካይነት እራሱን ነፃ ለማውጣትና የተሻለ ኑሮ ለመኖር መራራ ትግሉን በየአቅጣጫው ተያይዞታል ። ባህል ከሰፊው ሕዝብ የሚመነጭ እንደመሆኑ ፡ ሰፊው ሕዝብ በተያያዘው ትግል የባህሉ ተገልጋይ ይሆናል ። ይህን በማስመልከት ሌኒን ፡

> ባለፉት ለርጊ ዘመናት በሰው ልጅ ዕውቀትና ለዕምሮ የተፈጠረው የቴክኖሎጂና የባህል ጥቅሞች ለጥቂቶች ገልጋሎት ብቻ እንዲውል የተደረገ ሲሆን ሌሎችን ግን ከመሠረታዊ ፍላጐቶች፣ ከትምህርትና ከዕድገት ነጥሏቸዋል ። ከዛሬ ጀምር ድንቅ የሣይንሳዊ ፈጠራዎችና የባህል ውጤቶች ሁሉ የአገሪቱ ለንጡራ ሀብት ናቸው ። ከእንግዲህ ወዲያ የሰው የአእምሮ ውጤትና ዕውቀት ለጭቆናና ለብዝበዛ ጨርሶ አይውልም ፡፡[7] ብሏል ። የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችን ፕሮግራም ይዘትም ይህንኑ ያረጋግጣል ።

በተለይም የኢትዮጵያ ሠርቶአደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ከተዘረዘሩት የኢሠፓአኮ ሥልጣንና ተግባር መሐከል «ጠቃሚ የሆኑት የኅብረተሰብ ባህሎች ፡ ወጐችና ልማዶች ሶሻሊስት ኅብረተሰብን መገንባት በሚያስችል ሁኔታ የሚያድጉበትና የሚዳብሩበትን ዘዴ ይፈልጋል ። እንዲሁም አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሕዝቡ ጐታችና ኋላቀር ከሆኑ ባህሎች ፡ ወጐችና ልማዶች እንዲላቀቅ ይደረጋል ፡፡» የሚለው ክፍል ሌኒናዊ የባህል ዕድገት መመሪያ በተግባር የሚተረጐምበትን መዋቅር ለመዘርጋት ጠንካራ ድጋፍ ይሰጣል ።

ይህ ሁሉ አብዮታዊ ጥረት የአዲሱን ባህል ይዘት በይበልጥ ለማበልጸግ የሚረዳ አንድ የባህል ፖሊሲ እንዲወጣ ያበረታታል ። በመሠረቱ የርዕዮተ ዓለምና የባህል አብዮት ማካሔድ የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበርን ለመገንባት ከሚያገለግሉ አጠቃላይ ሕጐች አንዱ ነው ። በዚህም ሕግ ውስጥ ለሠርቶ አደሩ መደብ ታማኝ የሆኑ ሶሻሊስት ምሁራንን በብዛት ማፍራቱ አጣዳፊና አንገብጋቢ ነው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አድኀሪያን ከየአቅጣጫው ከከፈቱበት ጦርነት በአሸናፊነት በመውጣት በምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ አማካይነት ወደ ግንባታ መስክ ተሸጋግሯል ። የዚህ ዘመቻ አካል የሆነው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ማይምነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት በየአቅጣጫው የተፋፋመ እንቅስቃሴ በመካሔድ ላይ ይገኛል ። የዚህ ዘመቻ የመጨረሻ ዓላማ ማይምነትን ከአገራችን አስወግዶ የትምህርት ስርጭት ለሁሉም በእኩልነት እንዲዳረስ ማድረግ ይሆናል ። ይህም ሰፊው ሕዝብ የራሱን የባህል ደረጃ እንዲያሳድግ ዋስትና ያለው ድል እ

Digitized by Google

ንዲጐናጸፍ ይረዳዋል ። በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የትምህርት ስርጭት ፣ የዕውቀት መስፋፋት ፣ ለዚህ ሕዝብ የትግል መግሪያው ነው ። ሌኒን ሠርቶ አደሩ ለምን ትምህርትን እንደሚፈልግ ሲናገር ፣ «ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዕውቀት ጠምቶታል ፤ ምክንያቱም ድል ለማድረጊያ ይፈልገዋልና ፤» [8] ብሎ ነበር ። የኢትዮጵያም ሠርቶ አደሮች የትምህርት ፍላጐት ሌኒን ካለው የተለየ አይደለም ።

በዘመቻው አማካይነት የሚደረገው እንቅስቃሴ ከቀን ተቀን ሕይወት ጋር የተያያዘውን ዕውቀት ያዳብራል ። ከኅብረተሰቡ ተግባራዊ ሕይወት ጋር የተቆራኙት የሙያ ትምህርት ቤቶች ማለትም የንግድ ሥራ ት/ቤቶች ፣ የሥራና የሁለገብ ሙያ ትምህርት ቤቶች ወዘተ ... የመሳሰሉት በብዛት እንዲቋቋሙ ይረዳል ። በእርሻና በኢንዱስትሪ በአጠቃላይ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ አካባቢ አሁን የተጀመረው የምርት ካድሬዎች የማሰልጠኑ ተግባር ይበልጥ እንዲስፋፋም ያግዛል ። ይህም እርሻውንና ኢንዱስትሪውን ሊመሩ የሚችሉ አዲስ ካድሬዎችን በብዛት ያፈራል ። ይህም ሲሆን አዲስ ሶሻሊስታዊ ምሁራን የማፍራቱ ሂደት ይፋፋማል ።

ዕድሉን ከሠርቶ አደሩ መደብ ዕድል ጋር ያስተሳሰረውን ሕዝባዊ ምሁር ለመፍጠር የአገራችንን ወጣቶች በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም በማነጽ በውስጣቸው አዲስ ባሕርይ መስረጽ በጣም አስፈላጊ ነው ። በቡርዧው ርዕዮተዓለም ተተብትበው ያሉት የአገራችን አብዛኞቹ ምሁራንም እንዲሁ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም ንቃታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ።

በተለይም ወጣቱ ትውልድ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ቲዎሪ መታጠቅ በአገራችን ለኮሙኒዝም መገንባት ዋስትና ነው ።

ሌኒን እ. ኤ. አ. ጥቅምት 2 ቀን 1920 ለሶቪዬት ወጣቶች ስብሰባ ስለወጣቱ ተግባራት ሲናገር ፣

> የኮሙኒስት ኅብረተሰብን የመገንባት ዕውነተኛ ተግባር የሚገጥመው ወጣቱ ነው ። ስለሆነም እነኝህ የወጣቱ ተግባር በአጠቃላይና በተለይ የወጣቱ ኮሚኒስቶችና የሁሉም የሌሎች ድርጅቶች ተግባራት በአንዲት ቃል ሊጠቃለሉ ይችላሉ እላለሁ ፣ ተማሩ ፤ [9] ሲል አስ

ገንዝቦ ነበር ።

ሌኒን በዚህ አላቆመም ። ተማሩ የሚለው ቃል ሰፊ ቃል መሆኑን አስመልክቶ ወጣቱ መማር ያለበት ኮሚኒዝምን መሆኑንም አስገንዝቧል ። ይህ ብቻ አይደለም ፤ ሌኒን ትምህርቱ እንዴት ይካሔዳል ? የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ ትምህርቱ ቲዎሪና ተግባርን በማጣጣም ሁለቱንም ያቀፈ መሆን እንዳለበት አመልክቷል ። በእርግጥም የዚህ ዓይነቱ ትምህርት ብቻ ነው እውነተኛ ታጋዮችን ሊያፈራ የሚችለው ።

የወዝአደራዊ ባህል እጅግ በጣም ጠቃሚ ባህሪው አዲስ የሶሻሊስት ሰው ለመፍጠር መቻሉ ነው ። ይህም አዲስ ሰው አዲስ የሥነ ምግባር ገጽታዎች ይኖሩታል። አዲስ ሰው ለሰፊው ሕዝብና ለኮሚኒዝም በቆራጥነት የቆመ ነው ። የግል ጥቅሙን ለኅብረተሰቡ የማስገዛት ችሎታ አለው።አብሮ የመሥራትንና በጋራ መረዳዳትን አጣምሮ የያዘ ነው ። ዓለም አቀፋዊነትንና ሶሺያሊስት አርበኝነትን ያዋሐደ ነው ። ፍጹም ሰብዓዊ ፣ ታማኝና እውነተኛ ነው ። በኮሚኒዝምና በሠርቶአደሩ ሕዝብ ጠላቶች ላይ የማያወላውል አቋም ያለው ነው።ምንጊዜም ለትግል ዝግጁና ንቁ ነው ። አመለካከቱ ብሩህና ሳይንስን መሠረት ያደረገ ኮሚኒስት ነው ። አንድ የሶቭዬት ኅብረት ጸሐፊ ይህን መሰል ሰው ምን ዓይነት የባ

ሀል ገጽታዎች እንደሚኖሩት እንደሚከተለው አስቀምጦት ነበር ፤

> ከፍተኛ የባህል ደረጃ ያለው ሰው የጊዜውን ተራማጅ አስተሳሰብና ስለዓለም ያለው አመለካከት ዕውነተኛና ሣይንሣዊ የሆነ ፣ የሰፋ የርዕዮተ ዓለምና የባህል አመለካከት ያለው ፣ የኅብረተሰብ የማኅበራዊ የአዕምሮ ዕድገት መሠረታዊ አዝማሚያዎች ሊገባው የሚችልና ፣ ለነኝህ ሀሳቦችና ለኮሚኒስታዊ መርሆች ተገዥ ሆና የሚኖር ነው ። [10]

ስለሆነም በኅብረተሰብ አቋሙ ፣ በእንቅስቃሴው ፣ ባመለካከቱና በሥረ መሠረቱ ለሰፊው ሕዝብ ታማኝ የሆነ ሕዝባዊ ምሁር ማፍራት አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ግልጽ መሆን አለበት ።

በምሁራን ፣ በሠራተኛው መደብና በገበሬው መሐከል አሁን ያለውን ልዩነት በመጀመሪያ ማጥበብ ፣ ብሎም ማስወገድ ተገቢ መሆኑ አያጠያይቅም ። ይህ ሲባል ደግሞ የምሁራንን ዕውቀት ወደቀሩት የሕዝቡ ክፍሎች ዝቅ ማድረግ ወይም ቁጥራቸውንና ሚናቸውን መቀነስ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል ። በተቃራኒው ፣ በሶሻሊዝም ግንባታ ሂደት ውስጥ የመላ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ የዕውቀት ባህል በማዳበር ፣ የምሁራንን ቁጥርና ሚና ይበልጥ በማሳደግና ሠራተኛውን ደረጃ በደረጃ ወደ ምሁርነት በመለወጥ ነው። ያለዚህ የሶሻሊዝም የግንባታ ሥራዎች ሊከናወኑ አይችሉም ። ያለዚህ ዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂን መሠረት አድርጐ ምርትን በሶሻሊስት ፈር ማቀነባበር አዳጋች ይሆናል ። ለዚህ ነው አዲሱን ዲሞክራሲያዊና ዓለም አቀፋዊውን ባህል ለማዳበር የባህል አብዮት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው የሚባለው ። የባህል አብዮቱን ለማፋፋም ፣ በተቀየሰው አጠቃላይ አቅጣጫ እንዲያድግና ተግባራዊ እንዲሆን ደግሞ የባህል ፖሊሲ ማውጣት ያስፈልጋል ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ ንድፈሐሳቦችና ሐቆችን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያን የባህል መመሪያ ወይም የባህል ፖሊሲ /ካልቸራል ፖሊሲ/ መንደፍ እጅግ አስፈላጊ ነው ። የባህል ፖሊሲ ጥያቄ ደግሞ በመሠረቱ የርዕዮተዓለም ጥያቄ ስለሆነ አሮጌውን ባህል በአዲስ ባህል በመተካት ለሶሻሊስት ሥርዓት ተስማሚ የሆነ ላዕላይ መዋቅር ለመዘርጋት ይረዳል ። ለዚህ ነው ባህል ወገናዊ ፣ መደባዊና ሕዝባዊ መሆን አለበት የሚባለው ። በፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት በባህል መስክ የነበረውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ዛሬ ወደ እምንገኝበት የታሪክ ወቅት መምጣቱ ብሩህ አቅጣጫውን ቀይሶ ኅብረተሰባዊ መሠረት ለጣለው ባህል ዕድገት አስተማማኝ ዋስትና ይሰጣል ።

እዚህ ላይ ባህል የበለጠ እንዲዳብር የምርት ኃይሎችና የምርት ዕድገት ከፍ ማለት እንዳለባቸው መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነው። ሌኒን የምርት ኃይሎች ዕድገት ለባህል መበልጸግ አስፈላጊ መሆኑን ሲናገር ፣ « በባህል እንድንበለጽግ የምርት ኃይሎችን ማሳደግ አለብን ፤ የቁስ አካል መሠረት ሊኖረን ይገባል ፤ » [11] ብሏል ። በተለይም የገበሬውን ባህል ከፍ ለማድረግ የምርት ኃይሎችን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ሌኒን አስገንዝቧል ። [12]

የሕዝቡን የባህል ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ መሠረታዊ ነገሮች ሁለት ናቸው ። አንደኛው የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ዕድገት ሲሆን ሌላው ደግሞ የመንፈሳዊ ባህል ዕድገት ነው ። እነዚህ መንፈሳዊና ቁስአካላዊ ባህሎች ከምርት መገልገያ መሣሪያዎች ዕድገት ጋር የተያያዙ ናቸው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሳይንስ ፣ ኪነት ፤ ዕውቀት ፤ እንዲሁም ባህላዊ ቁሳቁሶች ፣ የምርት መገልገያዎች ፣ የባህላዊ ዕቃዎች ፣ የመዝናኛ ፣ የመደሰቻ ቦታዎች ወዘተ... ከኅብረተሰቡ የምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው ። የሶሺያሊስትም የኢኮኖሚ ሕግ

Digitized by Google

ዓላማው የሕዝቡን የቁስ አካላዊና የመንፈሳዊ ፍላጎቱን በማርካትና ከጊዜ ወደጊዜ በማሳደግ ወደከፍተኛው ደረጃ ማድረስ ነው። የሶሺያሊስት የምርት መገልገያዎች ዓላማም ይህንኑ የሕዝቡን የቁስ አካላዊና የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃውን ከፍ ማድረግ ነው። የሲኒማና የቲያትር ቤቶችን ቁጥር መጨመር ፣ ክበቦችን ማቋቋም ፣ ቤተመጽሐፍትን መክፈት ፣ ጋዜጣና መጽሐፎችን በብሳዛት ማሳተም ፣ የሕዝቡን የባህል ደረጃ የማሳደጊያ ዓይነተኛ ዘዴዎች ናቸው ። ወደ ሶሺያሊዝም ለመሸጋገር ኅብረተሰቡ በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በባህልም መዳበር አለበት ።

የሶሺያሊስት የባህል ማዳበሪያ መስኮች ክበቦች ፣ የባህል ማዕከሎች ፣ ቤተ መጻሕፍት ፣ የመወያያ መድረኮች ፣ ሙዚየሞች ዩኒቨርስቲዎች ፣ የሥነ ጽሑፍና የፕሮፓጋንዳ ማዕከሎች ፣ ሲኒማዎች ሙዚቃዎች ፣ የአማተር ኪነቶች ፣ ባህላዊ ፓርኮች ፣ ማረፊያዎች የሳይንሳዊና የቴክኒክ ማዕከሎች ፣ የማገገሚያ ጣቢያዎች ወዘተ . . .ናቸው ። የባህል ማዳበሪያ መስኮች የሰፊውን ሕዝብ ችግር የሚፈቱ ፣ አእምሮውን የሚያድሱ ፣ የፈጠራ ችሎታውን ከፍ የሚያደርጉና የሚያበለጽጉ ፣ የወዝአደሩን ርዕዮተ ዓለም ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የሚያስፋፉና ማንኛውንም አድኃሪ ርዕዮተ ዓለም የሚወጉ መሆን አለባቸው ። ባጭሩ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መገሪያ መሆን አለባቸው ።

የእነኚህ ማዕከሎችን ዕቅዶች መመሪያት ያለበት የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ሲሆን ፣ ዕቅዶቹን ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ግን ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች ናቸው። የባህል ማስፋፊያ መስኮች የሕዝብ መገልገያ መገሪያ መሆን አለባቸው ። በባህል ፈጠራም የሕዝቡ ተሳትፎ በዓይነትም ፣ በመጠንም መጨመር አለበት ፣ ታሪክ ሰሪው ሰፊው ሕዝብ ነውና ።

ስለሆነም በዚህ ረገድ የታለመው ዓላማ ግቡን እንዲመታ ፣ ሕዝባችን ካለበት ችግር እንዲላቀቅና እኩልነት የሰፈነበት ፣ የሠርቶ አደሩ ፍላጎቶች የሚሟሉበትና በሥራ ፍሬው የበለጸገ ኅብረተሰብ ለመገንባት የኢኮኖሚ ግንባታና የባህል አብዮታችንን ማፋፋም አለብን ። በዚህም ሂደት ውስጥ እንደ ዋልጌነት ፣ አባካኝነት ፣ ስግብግብነትና የመሳሰሉትን ከግል ሀብት ይዞታ የሚመነጩ መጥፎ ባህሎችን ማስወገድና ፣ የሥራ ወዳድነትና ፣ የሥራ ዲስፕሊን አክባሪነትን በአጠቃላይ አዲሱን የሶሺያሊስት ባሕል ለመገንባት የተያያዝነውን ትግል ይበልጥ ማፋፋም ይጠበቅብናል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. መሐመድ ሳላ ፣ ባህልና ንድፈሀሳባዊ ግንዛቤው ፣ መስከረም ፣ ቅጽ ፣ 2 ቍ. 7 ፣ ታኅሣሥ ፣ 1974 ፣ ገጽ 68
2. *The Fundamentals of Marxist-Leninist Philosophy*, (Progress Publishers, Moscow, 1975), p. 468.
3. V.I. Lenin, *Col. Works*, Vol. 31, p.287.
4. *Ibid.*, Vol. 26, p. 70.
5. *Ibid.*, Vol. 2, p. 526.
6. K. Marx and F. Engles, *The German Ideology* as quoted by A. ARNOLODOV. *On the Path of Cultural Progress*, (Progress Publishers: Moscow, 1974), p. 41.
7. V.I. Lenin, *Col. Works*, Vol. 28, pp. 171-172.
8. *Ibid.*, pp. 284-285.
9. *Ibid.*, Vol. 31, p. 283.
10. ARNOLODOV, pp. 55-56.
11. V.I. Lenin, *Col. Works*. Vol. 33, p. 475.
12. *Ibid.*, Vol. 32, p. 288.

Digitized by Google

በሶሻሊስት አገሮች ላይ የሚካሄድ የኢምፔሪያሊዝም ደባ–አንዳንድ ገጽታዎች

ጳውሎስ ደኪን

ሶቭዩት ኅብረት ፣ ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፣ ቡልጋሪያ ፣ ቼኮዝሎቫኪያ ፣ ሃንጋሪ ፣ ፖላንድና ሩማኒያ ለዓለም ሰላም ፣ ለዕውነተኛ ዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም በሚደረገው ትግል በአንድነት የግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱ ሶሻሊስት አገሮች ናቸው ። እነዚህ አገሮች በወታደራዊ ወይንም የመከላከልን ተግባር በሚመለከት በዋርሶ የጋራ መከላከያ ድርጅት ፣ በኢኮኖሚ ደግሞ በጋራ የኤኮኖሚ ተራድኦ ምክር ቤት ወይም በእንግሊዝኛ በአጭሩ (CMEA) በመባል በሚታወቀው ኢኮኖሚያዊ ድርጅት ተሳስረው ይገኛሉ ። ኢምፔሪያሊስቶችና ፀረ ሶሻሊስት ኃይሎች ሁሉ ሶሺያሊስት አገሮችን በዓለም ሕዝቦች ፊት ዝቅ አድርጎ ለማሳየት ባላቸው ዓላማ መሠረት በነዚህ አገሮች ላይ የስም ማጥፋት ፕሮፖጋንዳ ከማካሄድ አይቆጠቡም ። ከላይ የተጠቀሱትን የምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮች የሶቭዩት ሕብረት ጥገኛ ወይንም ተቀጽላ (Sattelites) እንደሆኑና ሶቭዩት ሕብረትም የራሷ ጥቅም ማዳበሪያና የራሷ ዓለም አቀፋዊ ገናናነት መጣሪያ እንደምታደርጋቸው አስመስለው ያቀርባሉ ። ይህ የኢምፔሪያሊስቶችና ግብረ አበሮቻቸው የስም ማጥፋትና የማጥላላት ፀረ ሶሻሊስት አገሮች ዘመቻ በጣም በረቀቀ ዘዴ ስለሚካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተደረገ ትን፣ ሐቀኛና ተራማጅ የሆነ ወገን እንኳን ሊወናበድና ሊሳሳት ይችላል ። የሶሻሊስት አገሮችን ሁኔታ ለመግለጽና ለመተንተን ከመሞከር በፊት ፣ ስለነሱ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረን የሚረዱ በካፒታሊስት አገሮች ያሉትን አንዳንድ ነገሮች በቅድሚያ መጥቀስ ጠቃሚ ይሆናል ። እንዲሁም ከዚህ ጋር በማያያዝ በካ

Digitized by Google

ፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል ስለአለው መሠረታዊ ልዩነት በትድግሚያ አጠር ያለ ሐተታ ማቅረብ ያስፈልጋል ።

ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለሚያካሂዱት ፀረ ሶሺያሊስት ፕሮፖጋንዳ ታሪካዊ አመቺ ሁኔታ (Historical Advantage) አላቸው ። ይኸውም በለሙት ካፒታሊስት አገሮችም ሆነ በኋላቀር አገሮች ዜና ፣ ሐተታ ወይንም ትንተና ማዳመጥ ወይንም ማንበብ የሚችሉ ሁሉ በአብዛኛው አመለካከታቸው በቡርዧው ርዕዮተዓለም የተበከለ መሆኑ ነው ።አእምሮአዊና ስነልቦናዊ ምንነታቸው በቡርዧ አስተሳሰብና አመለካከት የተጠቃ ነው ። በለሙት ካፒታሊስት አገሮች የሚገኝ ሠርቶአደር ሕዝብ በጣም ለጠነከሩትና ለተራቀቁት የገዥው ካፒታሊስት መደብ የርዕዮተዓለም ሥርጭት ተጽዎች ፕሮፓጋንዳ የተጋለጠና በእነሱ የሚታነጽ በመሆኑ።እንደተጠቀሰው በአብዛኛው ለቡርዧው ርዕዮተዓለም ተገዥ ሆኖ ይኖራል ። በቡርዧ ርዕዮተዓለም የሚመራ በመሆኑም ርዕዮተዓለም የሚሠራጩና የሚዳብሩ አመለካከቶችን የራሱ አመለካከቶች አድርጎ ይወስዳቸዋል ። ምንም እንኳ ሠራተኛው ሕዝብ በራሱ የሙያ ድርጅቶች ቢደራጅም ድርጅቶቹ በአመለካከታቸውና በፍላጎታቸው ከዚያው ከቡርዧው ርዕዮተዓለም ክልል ውጭ አይሄዱም ። ድርጅቶቹ የአለውን ሥርዓት ለሠርቶአደሩ ሕዝብ ደህንነትና ጥቅም በሚበጅ ለመለወጥ የሚሹና የሚጥሩ ሳይሆን በአብዛኛው ለገዥው ካፒታሊስት መደብ አመለካከቶችና ስልቶች ተገዥ በመሆን ባለው ሥርዓት ውስጥ የተወሰነ ጥቅም ለማግኘት ብቻ ስለሚታገሉ ፣ ተግባራቸው ለአለው ሰውን በሰው የመበዝበዝ ሥርዓት ሕልውናና ጥንካሬ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ይኖራል ።

ዲሞክራሲና ነፃነት የመሳሰሉትን ጽንሰ ሐሳቦች በሚመለከት በቡርዧ ርዕዮተዓለም የሚሰጠውን አተረጓጎም እንደ ሁለንታዊና ዘለዓለማዊ ትርጉም አድርገው ይወስዳሉ ። ከዚህም የተነሳ በሶቭዬት ኅብረትና በሌሎችም ሶሻሊስት አገሮች ዲሞክራሲ የለም ፤ ነፃነት የለም እያሉ ከካፒታሊስት መደብ ፓርቲዎች ጐን በመሰለፍ በጠቅላላው የሠራተኛውን መደብ ያወናብዳሉ ። ስለሆነም በለሙት ካፒታልስት አገሮች ያለው አብዛኛው ሠርቶአደር ሕዝብ ሶሻሊዝምንና ሶሻሊስት አገሮችን በሚመለከት በጣም የተወናበደ ነው።የካፒታሊዝምን ፈር የሚከተሉ ኋላቀር አገሮችን በሚመለከትም ሁኔታው ከዚህ እምብዛም የሚርቅ አይደለም። እነዚህ አገሮች አብዛኛዎቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ቅኝ ግዛቶች የነበሩ ሲሆን ፣ ዘመናዊ ሥልጣኔም ወደ እነዚህ አገሮች መግባት የጀመረው ከቅኝ ገዥዎችና ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ነው ፤ የተስፋፋውም በእነዚህ አገሮች ተጽእና አማካይነት ነው። ዛሬም ቢሆን የካፒታሊስቱን ፈለግ የሚከተሉ ኋላቀር አገሮች ለኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ተጽእና ተገዥነታቸው በገሃድ የሚታይ ነው ። ስለሆነም የእነዚህ አገሮች ዘመናዊው ወገን ሁሉ በጠቅላላው ፣ ማለትም ካፒታሊስቱ ፣ ንዑስ ከበርቴውና ምሁሩ በአመለካከቱና በፍላጎቱ ፣ በዓላማው ከቡርዧው ዓለም ጋር አንድነት ያለው ነው ።

ምንም እንኳ ሶሻሊዝም ለኋላቀር አገሮች እውነተኛ ብሔራዊ ነፃነትና ማኅበራዊ ዕድገት አማራጭ የሌለው ቢሆንም ፣ ከላይ የተጠቀሱት ወገኖች በጠቅላላ ስለ ሶሻሊዝምና ስለሶሻሊስት አገሮች ያላቸው አመለካከት የተወናበደና ከእውነት የራቀ ነው ። አብዛኛው ሠርቶአደርና የምሁሩ ክፍል ጭምር ኢምፔሪያሊስቶች ሆን ብለው ስለ ሶሻሊስት አገሮች የሚነዙት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ እንደ ሐቅ አድርጎ ይቀበላል ።ስለዲሞክራሲ፣ስለነፃነት ፣ ስለመንግሥት ሚና ፣ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ፣ ወዘተ . . . ትክክለኛ አመለካከት ወይንም ትርጉም ነው ብሎ የሚያምነው ያንኑ የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም አመለካ

Digitized by Google

ከት ነው ። ይህም ለፀረ ሶሻሊዝምና ለፀረ
ሶሻሊስት አገሮች ፕሮፓጋንዳ አመቺ ሁኔታ
ይፈጥራል ።

ካፒታሊዝም በመሠረቱ ወይንም በዓይ
ነቱና በባሕርዩ ቀድመውት በሰው ልጅ
ታሪክ ውስጥ ከታዩት ከባሪያ አሳዳሪውና
ከፊውዳላዊ ኅብረተሰቦች ወይንም ማኅበ
ራዊ ሥርዓቶች የተለየ አይደለም ። እንደነ
ዚያ ኅብረተሰቦች ሁሉ ካፒታሊዝምም
ሰውን በሰው በመበዝበዝ ላይ የተመሠረተ
ሥርዓት ነው ። ሰብአዊ ፍልስፍናው ግላዊ
ነው ። የሰው ልጅ ማኅበራዊ እንስሳ ነው
የሚለውን አባባል ባይቃወምም ለዚህ አባ
ባል የራሱን ትርጉም ይሰጠዋል ። በካፒ
ታሊዝም የኅብረተሰቡ ዋና አንቀሳቃሽ
ኃይል ግላዊነት ወይንም የግል ባለ ይዞ
ታነት በመሆኑ ከማኅበራዊ ጥቅም የግል
ጥቅም ተቀዳሚነት ይኖረዋል ። የኅብረ
ተሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅሞች የኅብ
ረተሰቡ ወገኖች ሁሉ በእኩልነት በጋራ
የሚጠቀሙባቸውና የሚገለገሉባቸው ማይ
ሆን ፣ እንደአለፉት በመደብ የተከፋፈሉ
ሥርዓቶች ሁሉ ፣ ተጠቃሚዎችና ተገልጋ
ዮቹ ጥቂት ሰዎች ብቻ ይሆናሉ ። ሶሻሊዝም
ይህን ሁሉ የሚቃረን ሥርዓት ነው ። ዓላ
ማው ሰውን በሰው የመበዝበዝን ሁኔታከዚ
ህች ምድር ጨርሶ በማስወገድ የሰው ልጆ
ችን እኩልነትና የጋራ ብልጽግና ለማረጋ
ገጥ ነው ። «ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ
ነው» ይላል ታላቁ ማርክሳዊ ምሁር ፍሬዴ
ሪክ ኤንግልስ ። ሥራም ትክክለኛ በሆ
ነው ማርክሳዊ ትርጉሙ በመሠረቱ ማኅበ
ራዊ ነው ። ስለሆነም ሰው ሰውነቱ (ሰው
መሆኑ) የሚረጋገጠው ወይንም የሚለካው
በማኅበራዊነቱ ነው ማለት ይቻላል ።
የአንድ ሰው ነፃነትና ብልጽግና ከሌ
ሎች ሰዎች ነፃነትና ብልጽግና ተለይቶ
ሰብአዊ ትርጉም አይኖረውም ። የማርክ
ሲስት ሌኒንስቶች ጥረት በእኩልነትና ፣
በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ፣ የሰዎች
የተሟላ ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና
የሰፈነበት ፣ አዲስ ሥርዓት ወይንም ኩሚ
ኒስታዊ ኅብረተሰብ መገንባት ነው ። ይህን
ዓይነት አዲስ ሥርዓት ለመገንባት መጣር
አዲስ ሰውን ለመፍጠር መጣር ማለት
ነው ፣ የሰውን አእምሮአዊና ስነ ልቦናዊ
ምንነት ማሳደስ ፣ መለወጥ ማለት ነው ።
ይህንንም ለውጥ ማምጣት የማርክሳዊ
ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ዓላማና ተግባር ነው።
ተጨባጭ ሁኔታዎችን በሚገባ በማገናዘብ
የሶሺያሊዝምን ግንባታ ማጠናከርና ማዳ
በር ያስፈልጋል ። በሶሻሊስት ግንባታ
ሂደት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለምና
ተግባር ከፍተኛ አንፃራዊ ግንኙነት አላ
ቸው ። ፍሬያማነታቸው በሙሉ ሊረጋገጥ
የሚችለው ሁለቱ በትክክል አብረው ሲሄ
ዱ ብቻ ነው ። የአንዱ ጥንካሬና ድክመት
በሌላው ላይ በቀጥታ ተጽእና ይኖረዋል ።
ሂደቱም ውስብስብና እጅግ በጣም ከባድ
ነው ። ከአለፉት አድኃሪ ሥርዓቶች የተወ
ረሱ በቀላሉ የማይወገዱ ፀረ ሶሻሊስት
ጉታች ባሕላዊ ቅሪቶች አሉ ። ከዚህም በላይ
ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሶሻ
ሊዝም በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት
እንዳይኖረው ለማድረግና በተለይም በሶ
ሻሊስት አገሮች ሕዝቦች ዘንድ ገና ያል
ጠሩ ሶሻሊዝምን የሚቃረኑ አመለካከቶች
ንና ፍላጐቶችን በማጠናከር የሶሻሊስት
ግንባታን ሂደት ለማዳከም ያለማቋረጥ የሚ
ካሄደው ፣ በጣም የተጠናከረና የተራቀቀ
የዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊስቶች ፀረ ሶሻ
ሊስት ፕሮፓጋንዳ አለ ። ስለዚህም ሶሻ
ሊስት አገሮችን በሚመለከት ትክክለኛ ግን
ዛቤ ይኖረን ዘንድ አገሮቹን ከእነዚህ ከላይ
ከተጠቀሱት ነጥቦች አንፃር መመልከት
መቻል ያስፈልጋል ።

በዚህ አንፃር ሲታዩ ሶቭዬት ኅብረትና
ሌሎችም ሶሻሊስት አገሮች በአጠቃላይ
የተጐናጸፏቸው ድሎች ፣ ማለትም የሶሻሊ
ስት ግንባታ ውጤቶቻቸው እጅግ በጣም
የሚደነቁ ናቸው ። እነዚህ አገሮች በአጠ
ቃላይ ሶሻሊስት አብዮት ማካሄድ ሲጀምሩ

Digitized by Google

ብሔራዊ የዕድገት ደረጃቸው በካፒታሊስት አገሮች ከነበረው ሁኔታ ጋር በተነፃፃሪነት ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነበር ። በ1910 (እ. አ. አ. 1917) አብዛኛው የሶቭዬት ኅብረት ሕዝብ በኋላ ቀር ግብርና የሚተዳደር ነበር ። በአገሪቷ ኢኮኖሚ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው ሚና በጣም አነስተኛ ነበር ። በተጠቀሰው ዓመት አብዮት ሲፈነዳ አገሪቷ ለሶስት ዓመት ያህል በአንደኛው የዓለም ጦርነት ተሳታፊ ከነበሩት አገሮች አንዷ ስለ ነበረች፣ ጦርነቱ ብዙ ጉዳት አድርሶባት ነበር ። ቀጥሎም ከ1918 እስከ 1921 የአውሮፓ ፣ የሰሜን አሜሪካና የጃፓን ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ከሌሎች የውጭና የውስጥ ፀረ አብዮተኞች ጋር በመተባበር አብዮታዊ ሂደቱን ለመቅጨት ከፍተኛ የትጥቅ ትግል አካሂደውበታል ። በመጨረሻም የአብዮቱ ወገኖች በአሸናፊነት ለመወጣት ቢበቁም፣የአገሪቷ ኢኮኖሚ ይህ ነው የማይባል ጥፋት ደርሶበት ነበር ። ከዚህ የተነሣ የነበረው ሁኔታ በምንም ዓይነት ሶሻሊስት ሥርዓት ለመገንባት አመቺ አልነበረም ። ነገር ግን ሌኒንና ሌሎቹም የአብዮቱ መሪዎች በሁሉም ዘርፍ እጅግ የሚደነቅ ቆራጥና ትክክለኛ አመራር መስጠት በመቻላቸው፣በአጭር ጊዜ ውስጥ በፀረ አብዮተኞች አሻጥርና ጦርነት ፈራርሶ የነበረውን ብሔራዊ ኢኮኖሚ መልሶ ለማቋቋም ተችሏል ።

በ1928 አብዮታዊው የሶቭዬት መንግሥት የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ሶሻሊስት የልማት ዕቅድ ነድፎ በሥራ ላይ ማዋል ጀመረ ። ቀደም ሲል ሶሻሊስት ኃይሎች በፖለቲካዊና በወታደራዊ ትግሎች ለማሸነፍ እንደበቁ ሁሉ፣ በ1928 እና በ1938 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ወይንም በመጀመሪያዎቹ ሁለት የአምስት ዓመት ፕላኖች ወቅት ደግሞ በኢኮኖሚውም ትግል የበላይነታቸውን አሳይተዋል ። የኢኮኖሚ ዘርፎችን በሙሉ ማለትም ኢንዱስትሪን ፣ እርሻን ፣ ንግድን ፣ ወዘተ... ሶሻሊስታዊ ቅርጽና ይዘት አስይዘዋል ። ከዚህም በላይ በእነዚህ ዓመታትና ቀጥሎ በወጣው በሶስተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ጊዜ ውስጥ በተለይ ከባድ ኢንዱስትሪን በማስፋፋትና በማሳደግ በኩል አገሪቷ ከፍተኛ ውጤትን ለመጐናፀፍ ቻለች።የሶቭዬት ኅብረት ኰሚዩኒስት ፓርቲ መሪዎች ከዚያን ጊዜ በፊት ታይቶ የማይታወቀውን ሰው በሰው የማይበዘበዝበት ሥርዓት ፣ ሶሻሊስታዊ ኅብረተሰብ ለመገንባት ሲጥሩና በግንባታውም ሂደት ጥሩ ውጤት እያሳዩ ሲሄዱ ፣ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በጠለቀ ጥላቻ ይመለከታቸው እንደነበርና ውሎም አድሮ በቀጥታ ጥቃት ለማንሳት መሞከሩ እንደማይቀር በሚገባ የተገነዘቡ ነበሩ ። ስለሆነም ታላቁ አብዮታዊ መሪ ቭላድሚር ኢሊይች ሌኒን «ራሱን መከላከል የማይችል አብዮት ፋይዳ አይኖረውም» ብሎ የተናገረውን ማይንግዊ አባባል መመሪያቸው በማድረግ፣ በአንድ በኩል በኢኮኖሚው ግንባታ ላይ ሲረባረቡ በሌላ በኩል ደግሞ የመከላከያ ተቋማቸውን የማጠናከሩን ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውት ነበር ። በዚህም ረገድ ከባድ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋትና ለማሳደግ በመብቃታቸው ለብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው ዕድገትና ለሶሻሊስት እናት አገራቸው ደህንነት አስተማማኝ ዋስትና ሊያስገኙ ችለዋል ።

ስለሆነም በሰው ኃይል ፣ በመሣሪያው ብዛትና ጥራት ፣ በሌላውም የጦር ተቋሙ እጅግ በጣም የተጠናከረው የናዚ ጀርመን ጦር እ. አ. አ በ1941 ሶቭዬት ኅብረትን በይፋ መውረር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለአራት ዓመታት ያህል በተደረጉት እጅግ ከባድ ከሆኑ የትጥቅ ትግሎች ሁሉ ሶቭዬት ኅብረት በአሸናፊነት ልትወጣ ችላለች ። ለሰው ልጆች ሰብአዊና ብሔራዊ መብቶች፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በሚደረገው ዓለም አቀፋዊ ትግል አንፃር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመን መሸነፍ ምን ያህል ታሪካዊ ቁም ነገር ያለው ድርጊት እንደሆነ

Digitized by Google

የናዚዎችን ፍልስፍናና ዓላማ ለሚያውቅ ሁሉ ግልጽ ነው ። ለዚህም ፣ ግለትም ለናዚ ጀርመን መሸነፍ ፣ ሶቭዬት ኅብረት ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት በመክፈል ከሁሉም ፀረ ናዚ ኃይሎች ይበልጥ አስተዋጽኦ ማድረጓ አሌ የማይባል ታሪካዊ ሀቅ ነው ። በዚህ ጦርነት አገሪቷ የደረሰባት ጥፋት የቱን ያህል እንደነበር ለማሳየት የሚከተለውን አጭር ስታትስቲካዊ ዘገባ መጥቀሱ ብቻ ይበቃል ። ይኸውም ከሀያ ሚሊዮን የማያንሱ ወገኖቿ በጦር ግንባርና በናዚ ወህኒ ቤቶች የሞቱባት ሲሆን ፣ 1710 ከተሞችና 70 ሺህ መንደሮች ተቃጥለውባታል ። በስንት መራራ ትግልና መስዋዕትነት የተገነቡት የኢኮኖሚ ተቋሞች በአብዛኛው ወድመውባታል ፤ ሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብም አስከፊ የሆነ ሥቃይ ደርሶበታል ። ነገር ግን የሶቭዬት ሕብረት ፓርቲ መንግሥትና ሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብ ከጦርነቱ ማብቂያ ማግሥት ጀምረው ክፉኛ የተጠቃውን ብሔራዊ ኢኮኖሚ መልሶ ለመገንባት ልክ በጦርነቱ ወቅት እንደአሳዩት ሁሉ ከፍተኛ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀነባበረ መረባረብና የግንባታ ትግል በማድረጋቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ አልበገር ባይነታቸውን በተግባር በድጋሚ ሊያስመሰክሩ ችለዋል ። የወደሙትን የኢኮኖሚ ተቋሞቻቸው በጥቂት ዓመታት ውስጥ መልሶ ማቋቋም ብቻ ማይሆን ከጦርነቱ በፊት ከነበራቸው የዕድገት ደረጃ የበለጠ ማሳደግ ችለዋል ። በማይንስ ዕውቀትና በቴክኒክ ጥበብ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አገራቸው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምንም ካለመነካቷም በላይ እንዲያውም ይበልጥ በልጽጋና ተጠናክራ ወጣች ። በዚህ ዕድል በመጠቀም በዓለም ላይ የበላይነትን ቦታ ለመያዝ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዓለምን በሙሉ የራሱ የብዝበዛ መድረክ ለማድረግ ከጦርነቱ ማብቂያ ማግሥት ጀምሮ ፍጹም ፀብ አጫሪ ፣ ገደብ የለሽ ፀረ ተራማጅና ፀረ ሶሺያሊስት ኃይሎች ፖሊሲውን በሁሉም አህጉሮች ማራመዱን ተያያዘው ። በዚህም ድርጊቱ ዓለምን ወደ ሌላና ወደ ባሰ ጦርነት አፋፍ ላይ አቃርቧት ነበር ። በዚህም ወቅት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ወደር የሌለው የኢኮኖሚ ኃይል ብቻ ማይሆን እስከ እ.አ.አ. እስከ 1961 ድረስ በብዛትና በአስተማማኝ ደረጃ የኑክሌር የጦር መሣሪያዎች ብቸኛ ባለቤት በመሆኑም ፣ ጠቅላላ ጦርነት ቢጀመር በአሸናፊነት እንደሚወጣ ሙሉ እምነት ነበረው ። ይሁንና ከ1961 ጀምሮ በዚህ ረገድ ሶቭዬት ሕብረት ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የነበረውን የበላይነት ለማሳጣት በቃች ፤ የኒኩሌር ጦር መሣሪያዎችም ባለቤት ሆነች ።

የቀሩትን የዋርሶ የጋራ መከላከያ ድርጅት አባል ሶሻሊስት አገሮች በሚመለከትም ተመሳሳይ ፍጥነት ያለው ዕድገት ታይቷል። ከላይ የተጠቀሰው የጋራ የኤኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት (CMEA) እ.አ.አ በ1949 ሲቋቋም አብዛኛዎቹ አገሮች በጣም ኋላ ቀር ነበሩ። በኤኮኖሚያቸው የኢንዱስትሪ ድርሻ እጅግ በጣም አነስተኛ ነበር ። እንዲያውም በቡልጋሪያ፣ በሀንጋሪና በሩማንያ ምንም ድርሻ አል ነበረውም ለማለት ይቻላል ፤ ምክንያቱም እነዚህ አገሮች በዚያን ጊዜ ኋላቀር የሆነ ግብርና የተንሰራፋባቸው ነበሩ።ከ1949 ጀምሮ ግን በየዓመቱ ያሳዩት ዕድገት እጅግ የሚያስደንቅ ነው ። እ.አ.አ ከ1949—1974 ባለው ጊዜ ውስጥ ብሔራዊ ምጣኔ ሀብታቸው በስምንት እጥፍ ያደገ ሲሆን ፣ የኢንዱስትሪ ምርታቸው ደግሞ በአሥራ ሁለት እጥፍ ከፍ ብሏል ። ዛሬ እነኚህ አገሮች በሙሉ በኢኮኖሚ የዳበሩ አገሮች ናቸው ። ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው በከባድ ኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ ነው ። በዘመናችን የዚህ ዓይነት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በሶሻሊስት ለውጥ ብቻ ሊገኝ እንደሚችልም ቋሚ ምስክር ሊሆኑ በቅተዋል ።

የሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት (CMEA) አባል አገሮች የሕዝቦቻ

Digitized by Google

ቸው የኑሮ ደረጃ ድርጅቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል ፡፡ እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር አለ ፡፡ ይኸውም ከአብዛኞቹ የኢኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት አባል የሶሺያሊስት አገሮች መካከል አነስተኛው የኑሮ ደረጃ የሶቭዬት ኅብረት እንደሆነ ሲታወቅ ፣ ፀረ ሶሻሊስትና በተለይም ፀረ ሶቭዬት ኃይሎች ሶቭዬት ኅብረት የምሥራቅ አውሮፓን ትናንሽ ሶሻሊስት አገሮች የራሷ ጥቅም መጣሪያ በማድረግ ትጠቀምባቸዋለች እያሉ የሚሰነዝሩት ዘለፋ የቱን ያህል መሠረተ ቢስ መሆኑን ቁልጭ አድርጐ ያሳያል ፡፡ የሶሻሊስት አገሮች የኤኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት አንዱ የሚበዘብዝበት ሌላው የሚበዘበዝበት ሳይሆን የጋራ ጥቅምን አብሮ በጋራ ፣ በሶሻሊስታዊ ወንድማማችነት የማዳበሪያ ድርጅት ነው ፡፡ የድርጅቱ መርሆች ሕግና አሠራር ዲሞክራሲያዊ ናቸው ፡፡ አባሎቹ በሙሉ በድምጽ አሰጣጥ እኩል ናቸው፡፡ ድርጅቱ እንደ አውሮፓ የጋራ ገበያ ድርጅት (EEC) ከመንግሥት በላይ «ሱፐራናሽናል» አይደለም ፤ ማለትም በአባል አገሮች መንግሥታት ላይ ሥልጣን የለውም፡፡ ማንኛውም አባል መንግሥት ያላመነበትን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ አይገደድም ፡፡ በአውሮፓ የጋራ ገበያ ድርጅት ግን ይገደዳል ፡፡ የአውሮፓ የጋራ ገበያ ድርጅት በእኩልነት ላይ ተመሠረተ ድርጅት አይደለም ፡፡ አባሎቹም በድምጽ አሰጣጥ እኩል አይደሉም ፡፡ ትላልቆቹ በትናንሾቹ ላይ የድምጽ ብልጫ አላቸው ፡፡ ይህም የሚያንፀባርቀው የሁለቱን ድርጅቶች አባል አገሮች የውስጥ ሁኔታዎች ነው ፡፡ በካፒታሊስት አገሮች በትላልቅና በትናንሽ ካፒታሊስቶች መካከል እኩልነት የለም ፤ በሥርዓቱም ባሕርይ ሊኖር አይችልም ፡፡ ትላልቆቹ በትናንሾቹ ላይ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት አላቸው፡፡ ሶሻሊስት አገሮች ግን የውስጥ ይዞታቸው በእኩልነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በመካከላቸው ያለው ወይንም የሚኖረው ግንኙነትም ይህን መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ሊሆን አይችልም ፤ አለበለዚያ ሶሻሊስታዊ ግንኙነት አይሆንም ፡፡ በኢኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት ይህ ተግባራዊ ሆኗል ፡፡ በዚህ ድርጅት አማካይነት የተደረገው ትብብር የአባል አገሮችን የጋራ ጥቅም በእኩልነት አዳብሯታል ፡፡ የእያንዳንዱን አባል አገር ኤኮኖሚ ዕድገት በፍጥነት እንዲራመድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ፡፡ በአባል አገሮች መካከል ያለውና ሊኖርም የሚገባውን ሁለንተናዊ የትብብርና ግንኙነት ጠንካራ መሠረት አስይዞታል ፡፡

እርግጥ ነው ፣ ሶሻሊዝም በእነዚህ አገሮች የደረሰበት የዕድገት ደረጃ በማርክስ ፣ በኤንግልስና በሌኒን ከተተለመለት ግብ አንፃር ሲታይ ገና ብዙና ውስብስብ የእድገት ሂደት ይቀረዋል ፡፡ ለወደፊት ረጅም ጉዞ ፣ ብዙ ትግልና መስዋዕትነት ይጠብቀዋል ፡፡ ብዙ ችግሮችና ድክመቶች አሉት ፡፡ የሶሻሊዝም ጽንሰ ሀሳብ በካፒታሊዝም ላይ ያለውን መሠረታዊ ልዕልና ገና ሙሉ በሙሉ አላስመሰከረም ፡፡ በዚህ ረገድ በሶሻሊስት አገሮች ውስጣዊ ሂደቶችና በሶሊስት አገሮች መካከል ያሉ ወይንም የሚከሰቱ ድክመቶችና ችግሮች ወይንም እጥረቶች ትክክለኛ ምንጫቸው ፣ መንስኤያቸው ወይንም ምክንያታቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ሣይንሣዊ በሆነ መንገድ በጥሞና ይጥራሉ ፤ አውቀውም ድክመቶቹና ችግሮቹ እንዲወገዱ በያሉበት በማንኛውም አጋጣሚ በመጠቀም በሣይንሣዊ ስልትና ዘዴ የበኩላቸውን ጥረት ያለማቋረጥ ያደርጋሉ ፡፡ ድክመቶቹንና ችግሮቹን የሶሻሊስት ንድፈ ሀሳብ ኢሳይንሳዊነትን ወይንም መሠረታዊ «ኢተግባራዊነትን» እንደሚያሳዩ አድርጐ መውሰድና ማውራት ግን የፀረ ሶሺያሊስት ኃይሎች ተግባር ነው፡፡ በአንድ በኩል በሶሻሊዝም ግንባታ አንዳንድ ድክመቶችና ችግሮች መኖራቸው የማይካድ ሐቅ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንዲሁ በገሀድ እንደሚታየው፣ በሶሺያሊስት አገሮች የሶሻሊስት ግንባታ ሂደት በፍጥነት እያደገ ፣ አድማሱን እያስፋፋና ጥልቀት እያስያዘ ፣ ጥንካሬውን እየጨመረና

ታሪካዊ ሕልውናውን በማያሻማ ሁኔታ እያረጋገጠ መጥቷል ። በአንፃሩ ደግሞ የኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ መረብ እየተጣበበ በመሄድ ላይ መሆኑ የማይካድ ታሪካዊ ሐቅ ነው ። «ጊዜው የሶሻሊዝም ነው» የሚለው አባባል እንደ አጉል መፈክር የሚጣል አይደለም ። የዓለምን የቅርብ ታሪካዊ ሂደት በጥልቀት ለተመለከተና በትክክል ለተገነዘበ ሁሉ ሂደቱ እያደር ለሶሻሊዝም የሚያመች እየሆነ መምጣቱን ለማስተዋል አያዳግትም። በአሁኑ ወቅት በኢምፔሪያሊስት ዓለም የሚታየው ገደብ የለሽ የጦረኝነት ጠባይና መቅበዝበዝ ለዚህ ታሪካዊ ሐቅ ዓይነተኛ ምስክር ነው ።

ሶሻሊስቱ ማኅበረሰብ ፣ በለሙት ካፒታሊስት አገሮች የሠራተኛው መደብ ትግል በቀጥታና በእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ፣ እነዚህ የጊዜያችን ሶስት አበይት የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ዘርፎች ናቸው ። ሶሻሊስት ማኅበረሰብ ስንልም ሶሻሊስት አገሮች ማለታችን ነው ። ቀደም ሲል እንደተመለከተው ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎቹም የምሥራቅ አውሮፓ የዋርሶ ቃል ኪዳን ድርጅትና የኢኮኖሚ ተራድኦ ድርጅት አባል ሶሻሊስት አገሮች በዓለም አቀፍ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ካፒታሊስት ትግል ውስጥ የግንባር ቀደሙን ሚና ይጫወታሉ ። እነዚህ አገሮች በማቴሪያል ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ መጐናጸፍ ፣ በኢምፔሪያሊስቶች ፀረ ሕዝብ ደባ ላይ ገደብ ፈጥሮበታል ፤ ገትቶታል ። ለእውነተኛ ብሔራዊና ማኅበራዊ ነፃነት፣ ለብልጽግና፣ ለሰላምና ለሰው ልጆች እኩልነት ለሚደረጉ ሕዝባዊ ትግሎች ሶሺያሊስት አገሮች አስተማማኝና የማይበገር መከታ መሆናቸውን በተለያዩ ቦታዎችና በተያዩ ጊዜያት በተግባር አሳይተዋል ። ስለሆነም የእነዚህ አገሮች ይበልጥ መጐልበትና መበልጸግ ፣ በመካከላቸው ያለው ሶሻሊስታዊ የትብብር ግንኙነትም እየተጠናከረ መሄድ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለሶሻሊዝም ፣ ለዓለም ሰላም ፣ ለጋራ ብልጽግናና ዕድገት የቆሙ ኃይሎች ሁሉ ያምኑበታል ።

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BERHANENA SELAM PRINTING PRESS

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER
-6 1985
INSTITUTION

- የማሌ ፓርቲ ንድፈሐሳባዊ መሠረት-ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር
- የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተግባርና በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወቱት ሚና
- ኪነጥበብና ርዕዮተዓለም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት
- የሶሻሊስት ትምህርት ሥርዓት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ
- ዲሞክራሲና የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት
ቅጽ 3 ቁጥር 11
ታህሣሥ 1975

Digitized by Google

መስከረም

ቅጽ 3 ቁጥር 11
ታህሣሥ 1975

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገጽ 3
- የሕዝብ መገናኛ ዘደዎች ተገባርና በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወቱት ሚና 15
- ኪነጥበብና ርዕዮተዓለም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት.... 33
- የሶሻሊስት ትምህርት ሥርዓት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ ... .54
- ዲሞክራሲና የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት 80
- የሐተታ ገጽ 93

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር -- 80001
የስልክ ቁጥር - 113000

Digitized by Google

ኢሠፓአኮ

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የማሌ ፓርቲ ንድፈሃሳባዊ መሠረት-ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር

ሌኒን «ያለ አብዮታዊ ንድፈሃሳብ ጠንካራ የሆነ ሶሻሊስት ፓርቲ ሊኖር አይችልም» *ሲል፣ አንድ አብዮታዊ ፓርቲ በጠንካራ መሠረት ላይ መመስረቱም ሆነ ለሚመራው ሰፊ ሕዝብ ትክክለኛ አመራር በመስጠት ታሪካዊ ተልዕኮውን በሚገባ ለመወጣት መቻሉ የሚወሰነው ፓርቲው በማሌ ርዕዮተዓለም በመታነጹ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ሌኒን የአዲሱን ዓይነት ፓርቲ አሠራር ሲያብራራ ፓርቲው በሳይንሳዊ ኮሚኒዝም ንድፈሃሳብ በመመራቱና ይህንንም ንድፈሃሳብ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር ለማገናዘብ ካለው ብቃት ተነጥሉ ሊታይ እንደማይችል አስተምሯል።

ማናቸውም የማሌ ፓርቲ የሚመሠረተው «የወዝአደሩን መደብ ትግል በማደራጀትና በመምራት የትግሉ የመጨረሻ ዓላማ የሆነው የፖለቲካ ሥልጣን በወዝአደሩ መደብ እንዲያዝ ማድረግና የሶሻሊስት ኅብረተሰብን ለማደራጀት» ** ነው። ይህንን ዓላማ ለማሟላት ፓርቲው ምን ዓይነት ፕሮግራም መንደፍና ምን ተግባር በምንጊዜ ማከናወን እንዳለበት የሚጠቁመው የማሌን ንድፈሃሳብ ነው። የማሌ ንድፈሃሳብ ኮሚኒስቶች መላ አመለካከታቸውን የሚቀርጹበት፣ የትግል ዘዴያቸውንና የአሠራር ስልታቸውን የሚቀይሱበት በአጠቃላይ የአመለካከታቸውና የእምነታቸው የአንድነት መገለጫ ነው።

የአዲሱ ዓይነት የማሌ ፓርቲ የሚመሠረተውም በወዝአደሩ ርዕዮተዓለም ላይ የታነፀ የአመለካከትና የዓላማ አንድነት ባላቸው፣ የፓርቲውን አብዮታዊ ፕሮግራም በተቀበሉና ለፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ እራሳቸውን ባስገዙ፣ የላቀ የመደብ ንቃተ ሕሊናና የንድፈ ሐሳብ ትጥቅ ባላቸው ግለሰቦች ነው። እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ዋና ነጥብ የአንድ የማሌ ፓርቲን ፕሮግራም የትግል መመሪያ አድርጐ ለመቀበልና ለደንቡም እራስን ለማስገዛት፣ በቅድሚያ የማሌ ርዕዮተ ዓለምን የሕይወት መመሪያ አድርጐ መቀበል ማስፈለጉን ነው። የማሌ ርዕዮተዓለምን የሕይወት መመሪያ አድርጐ መቀበል ማለት ደግሞ ከተግባር የተገነጠለ ንድፈሃሳብን ማነብነብ ማለት አይደለም።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለምን ወደ ወዝአደሩ መደብ ንቅናቄ ውስጥ በማስገባት የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ንድፈሃሳብ ከወዝአደሩ መደብ ትግል ጋር የሚያዋህደው የማሌ ፓርቲ በመሆኑ፣ የማሌ ንድፈሃሳብ የመነጨው ከወዝአደሩ መደብ ውጭ ነው ቢባልም ፣ ይህ ንድፈሃሳብ ሳይንሳዊነቱን ሊያረጋግጥ የቻለው ወዝአደሩ በሆር

* Lenin, Col. Works, Vol. 4, p. 211
** *Ibid.*

Digitized by Google

ዡዋው ላይ ያካሄደውን ትግል መሠረት በማድረግና የዚህንም ትግል አቀጣጫ በትክክል ለመግለጽ ስለቻለ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።

ስለዚህ ነው የማሌ ንድፈሃሳብ መሠረቱ ተግባር ነው ፤ የሚዳብረውም ተግባርን በመመርኩዝ ነው የሚባለው ። የማሌ ንድፈሃሳብ ተግባራዊ ክንዋኔ ሊያገኝ የሚችለው ደግሞ በማሌ ፓርቲ አማካይነት በመጀመሪያ በአባላቱ ፣ ለጥቀም በሠርተአደሩ ሕዝብ እንደመሆኑ ፣ የዚህን ዓይነት ፓርቲ ፕሮግራምና ደንብ ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ የማይ ታገል ሰው የማሌን ርዕዮተዓለም እንደሕይወቱ መመሪያው አድርጐ ተቀብሏል ለማለት አይቻልም ።

አንድ የማሌ ፓርቲ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ፣ ተመሳሳይ የሆነ አብዮ ታዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች የአላማና የተግባር አንድነት የሚገለፅበት ፣ እንቅስቃሴያ ቸውም በአንድ ንድፈሃሳባዊ ፣ ድርጅታዊና ታክቲካዊ መርሆዎች የሚመራበት ነው ።

አንድ አብዮታዊ ትግል ግቡ ሶሺያሊዝም መሆኑን ቢያውጅም ፣ አብዮታዊ በሆነው በማሌ ንድፈሃሳብ በታጠቀ ፓርቲ እስካልተመራ ድረስ ትግሉን ከግብታዊነት ለላቀ እገቡ ለማድረስ የሚያስችለውን ሳይንሳዊ ፕሮግራምና ደንብ ፣ እስትራቴጂና ታክቲክ ለመንደፍ አይችልም ። በመሆኑም ይኸ ዓይነቱ ንቅናቄ በቡርዧው ርዕዮተ ዓለም ስር ከመውደቅ አያመልጥም ። ሌኒን « የግንባር ቀደምና የታጋይነት ሚናን ሊያሟላ የሚችለው እጅግ ተራማጅ በሆነው ንድፈሃሳብ የሚመራ ፓርቲ ብቻ ነው ፤ » * ያለውም አንድ ፓርቲ አብዮታዊና ግንባር ቀደም ሊሆን የሚችለው በማር ክሲዝም ንድፈሃሳብ ሲመራ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ነው ።

የማሌ ንድፈሃሳብ ለማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሚያቀ ርብና የተወሳሰቡ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ግልጽልጽ አድርጐ የሚያሳይ በመሆኑ ፣ ኅብ ረተሰቡን በአዲስ መልክ ለማደራጀትና ለመምራት ፍቱን የሆነ መሣሪያ ነው ። የማሌ ንድፈሃሳብ የሠራተኛ ፓርቲዎች ተጨባጭ በሆኑ የኅብረተሰብ የእድገት ሕጎች እውቀት እንዲታጠቁ በማድረግ ፣ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ መርሆዎችን ሳይንሳዊነት የሚያረጋግጥ ነው ።

ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሠራተኛው መደብና መላ ሠርተአደሮች ለሚያካሂዱት ትግል አመራር የመስጠት ታሪካዊ ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ማናቸውም የሠራተ ኛ መደብ ፓርቲ በማሌ ንድፈሃሳብ በሚገባ የታነጸ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው ። በአብዮታዊ ንድፈሃሳብ የታነጸ የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ የሠራተኛውን መደብ ትግል ከግብታዊነት በማላቀቅ በንቃት ላይ ወደተመሠረተ ትግል ፣ ግቡንና ወደ ግቡ ሊደ ርስ የሚችልበትን መንገድ በውል ወደሚያውቅና ወደ ተደራጀ ትግል ያሸጋግረዋል።

በመሆኑም የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ዓይነተኛ ሚና ትክክለኛውን አቀጣጫ የሚ ያመለክተውን ፣ የብርታቱ ምንጭ የሆነውን የማሌን ንድፈሃሳብ ከበራዦችና ከአድርባ ዮች ጥቃት በመከላከል በሀገርና በዓለምአቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ንድፈ ሃሳቡን ማዳበር ነው ። ከዚህ አንፃር የአንድ ፓርቲ አብዮታዊነት የሚወሰነው አጠቃ ላይ የሆኑትን የማሌ መርሆዎች በመቀበሉ ብቻ ሳይሆን ፣ እነዚህን አጠቃላይ መርሆ

* Lenin, Col. Works, Vol. 5, p. 370

Digitized by Google

ዎች ከሀገርና ከዓለምአቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በትክክል ለማዋሃድ ከመቻሉም ጭምር ነው ።

የማሌ ንድፈሃሳብ በግብታዊነት ሊከሰት የሚችል ነገር ያለመሆኑን ያህል በሠራተኛው መደብ ትግል ውስጥም ሆነ በሠርተአደር ሕዝቦች እንቅስቃሴ ውስጥ በአጠቃላይ በግብታዊነት የሚሠራጭና የሚስፋፋ ነገር አይደለም ። ቀደም ሲልም ለመጠቆም እንደተሞከረው የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ መሠረታዊ ተግባር አብዮታዊ የሆነውን የማሌን ንድፈሃሳብ በስፋት በማሠራጨት ፣ የሠራተኛው መደብና የመላ ሠርተአደር ሕዝቦች ንቅናቄ ከሶሻሊዝም ጋር እንዲዋሃድ ማድረግ ነው ።

ማርክስ ይኸንኑ አስመልክቶ ሲጽፍ« ንድፈሃሳብ ቁሳዊ ኃይል ሊሆን የሚችለው ሰፊው ሕዝብ ውስጥ ሠርጾ ሊገባ ሲችል ነው ፤» * ያለውም ፣ ማናቸውም የማሌ ፓርቲ የአብዮታዊነትና የመሪነት ሚናውን በሚገባ ሊወጣ የሚችለው በሰፊው ሕዝብ ውስጥ የማሌ ንድፈሃሳብ እንዲሠረጽ ለማድረግ ሲችል ብቻ መሆኑን ለመጠቆም ነው።

አንድ አብዮታዊ ፓርቲ የሚመራበትን ርዕዮተዓለም ለማስፋፋትና በኅብረተሰቡ ውስጥ የበላይነት እንዲኖረው ለማድረግ በሚያካሂደው የርዕዮተዓለም ትግል ሁልጊዜም ቢሆን ተግባራዊ እንቅስቃሴው በአብዮታዊ ንድፈሃሳብ መመራቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ። እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን የሚገባው ነገር አለ ። በአጠቃላይ አነጋገር ንድፈሃሳብ የሚመነጨው ፣ ትክክለኛነቱም የሚፈተነው ከተግባር ቢሆንም ፣ ተግባርን አቅጣጫ በማስያዝና በመምራቱ ረገድ ንድፈሃሳብ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ለሶሻሊዝም በሚደረግ ትግል ውስጥ ንድፈሃሳብ ታላቅ ኃይል መሆኑ የሚከሰተው ሠርተአደር ሕዝቦች ከሚያካሂዱት አብዮታዊ ትግል ጋር ሲዋሐድ ቢሆንም ፣ ይህን ትግል የሚያካሂደው ሕዝብ በትግሉ ውስብስብነት ግራ እንዳይጋባ ፣ ተስፋ እንዳይቆርጥና በትግሉ አሸናፊነት ሙሉ እምነት እንዲኖረው የሚያደርገው ፣ የተጨባጭ ሁኔታዎች ምንነትና የርስ በርስ ግንኙነትን በማሳየት ትግሉ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዳይስት ለማድረግ የሚችል ሳይንሳዊው የማሌ ንድፈ ሃሳብ ብቻ ነው ። ንድፈሃሳብ በአብዮታዊ የትግል ሂደት ውስጥ በአንድ ወቅት ያሉትን መደቦች ፣ የሚጫወቱትን ሚና ፣ በመካከላቸው ያለውን የኃይል ሚዛን ፣ ለምንና በምን አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳሉ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በመደቦች መካከል የሚካሄደው ትግል ወደየት እንደሚያመራ የሚጠቁም ነው ። ሌኒን« ስለ አብዮታዊ ንድፈሃሳብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም ፤» ** ያለውም ይህንኑ ሁኔታ ለማብራራት ነው ።

ከላይ ወደ ጠቀስነው ነጥብ ለመመለስ ፣ በማናቸውም የአብዮታዊ ሂደት ወቅት አንድ አብዮታዊ ፓርቲ አብዮታዊነቱ የሚለካው በንድፈሃሳብና በተግባር መካከል ያለውን አንድነት በመጠበቁ ቢሆንም ፣ ይህ ሁኔታ ፓርቲው በርዕዮተዓለም ሥራው አብዮታዊ ንድፈሃሳብ ለፓርቲው ተግባራዊ እንቅስቃሴ አመራር ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ ላይ መገኘቱን ማረጋገጥ ከማስፈለጉ ጋር አይቃረንም ። ንድፈሃሳብ ከተግባር ወደኋላ ከቀረ የፓርቲው የዘለቄታ ዓላማ በቀን ተቀን ትግሉ እየተዋጠ ፣ ፓርቲው የቀመለት ዓላማ ብቻ ሣይሆን ፓርቲው እራሱ የማሌ ፓርቲ ፣ አብዮታዊ ፓርቲ ሆና የመ

* Karl Marx, Introduction to The Critique of Hegel's Philosophy of Right,
** Lenin, Col. Works, Vol. 5, p. 369

Digitized by Google

ቀየቱ ሁኔታ አደጋ ላይ ይወድቃል። ንድፈሃሳብ የአንድን ፓርቲ ተግባራዊ እንቅስ ቃሴ የአጭርና የረዥም ጊዜ ግብ በቅድሚያ ለመተለም ካልቻለና እንደጭራ ከፓርቲው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በኋላ የሚጉተተ ከሆነ፣ የፓርቲው ገቢራዊ እንቅስቃሴ ስለሚ ታፈን ፓርቲው የመሪነት ሚናውን ከማጣቱም በላይ፣ ሠራተኛው ሕዝብ ለሶሻሊዝም የሚያደርገው ትግልም ይጨናገፋል።

ማናቸውም አብዮታዊ ፓርቲ በንድፈሃሳብና በተግባር መካከል ያለውን አንድ ነት ሁልጊዜም ቢሆን መጠበቅ አለበት በሚባልበት ጊዜ በፕሮግራሙ፣ በድርጅታ ዊና ታክቲካዊ መርሆዎች መካከል ያለውን አንድነት መጠበቅ አለበት ማለት ነው።

የአንድ ፓርቲ አብዮታዊ ብቃትና ሐቀኛነት በእምነቱና በድርጊቱ መካከል ባለው መጣጣም አንፃር የሚወሰን ነው። ፓርቲው ማቴሪያላዊ ሀልውና የሚያገኘው ደግሞ በአባላቱ አማካይነት እንደመሆኑ፣ የፓርቲው ጥንካሬም ሆነ ድክመት የሚመ ነጨው ከአባላቱ የርዕዮተዓለም ብቃትና ኮምኒስታዊ ሥነምግባር መሆኑ ግልፅ ነው። ማናቸውም አብዮታዊ ፓርቲ ለሠርተአደሩ ሕዝብ አመራር የመስጠት ኃላፊነቱን የሚወጣው እንደዚሁ በአባላቱ አማካይነት ስለሆነ፣ በሕዝባዊ ድርጅቶች፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ በሙያ ማኅበራትና በተለይም ደግሞ በመንግሥታዊ ተቋሞች ውስጥ ፓርቲውን በመወከል በተለያየ የአመራር ደረጃ ላይ የተመደቡ አባላቱን መልካም ሥነ ምግባር፣ የሥራ ብቃትና የንድፈሃሳብ ግንዛቢ ደረጃ በየጊዜው የመገምገምና የእርምትና የማጠናከሪያ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት።

የሶሺያሊዝምን አሸናፊነትና ድል አድራጊነት ለማረጋገጥ በሚካሄድ አብዮታዊ ትግል ውስጥ ሥልጣን የያዘ የማሌ ፓርቲ ይኸንኑ ክቡር ዓላማ ለማስፈጸም ከሚ ጠቀምባቸው፣ በፓርቲውና በሕዝቡ መካከል እንደ ድልድይ ሁነው ከሚያገለግሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ የሙያ ማኅበራት ወዘተ... መካከል ዋንኛውና ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን የሚያገለግለው መንግሥት ነው። በመሆኑም በተለይ በልዩ ልዩ የመንግሥታዊ ተቋሞች ውስጥ ፓርቲውን በመወከል በተለያየ የኃ ላፊነት ደረጃ የተቀመጡ የፓርቲው አባላት፣ በተመደቡበት የሥራ ዘርፍ ሁሉ ሥራ ወዳድነታቸውን፣ አብዮታዊ አመለካከታቸውን፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት በጓዳዊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ግምባር ቀደምነታቸውንና አርአያነታ ቸውን በተግባር ለማስመስከር የሚችሉ መሆን አለባቸው።

በመንግሥታዊ ተቋሞች፣ በሕዝባዊ ድርጅቶች፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራትና በሙያ ማኅበራት ውስጥ ፓርቲውን የሚወክሉ የፓርቲ አባላት በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ለመ ኖር፣ ችግሩንና ብሶቱን፣ ደስታውንና ኀዘኑን ለማወቅ የሚጥሩ ካልሆኑ፣ በየአካባቢው አመራራቸውን የሚጠብቀውን ሕዝብ በማስተማርና ከሱም በመማር ለመርዳትና ለማ ቀረብ ካልቻሉ፣ በአጠቃላይ በመልካም አርአያነታቸው የሕዝቡን ሙሉ እምነት ሊያ ገኙ የሚችሉ ካልሆኑ፣ ሕዝቡ የሚጠላው እነሱን ብቻ ሳይሆን የሚወክሉትን ፓርቲ ውን ጭምር መሆኑን በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል። እንደነዚህ ዓይነት የፓርቲ አባላት ፓርቲውን ከሰፊው ሕዝብ በመገንጠል ማኅበራዊ መሠረቱን የሚያሳጡት በመሆኑ፣ ፓርቲው ከዚህ ዓይነት እጅግ ከፍተኛ አደጋ እራሱን ለመከላከል፣ በአመ ክሮና በሂስ ሊመለሱ የማይችሉ አባላቱን ከፓርቲው በማስወጣት ዘወትር እራሱን የማጽዳት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

Digitized by Google

የፓርቲ አባላት ጥራትና ብቃት የሚወሰነው መጀመሪያ ከአመላመል ላይ ሲሆን፣ ከዚያም በኋላ በአባልነታቸው በፓርቲው ውስጥ በሚያገኙት የንድፈሃሳብ ትምህርትና ይህን ትምህርት የሕይወት መመሪያ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ፓርቲው በሚያደርገው ክትትል ነው። እዚህ ላይ ለአንድ አብዮታዊ ፓርቲ በአባላት አመላመል፣ ከምልመላም በኋላ ንድፈሃሳባዊ እውቀታቸውን በየጊዜው ማሻሻላቸውንና የፓርቲ ዲስፕሊንን መጠበቃቸውን በሚመለከት ልል በመሆን፣ ለፓርቲው ርዕዮተዓለምና ፓርቲው ለቆመለት ዓላማ ጽኑ እምነት የሌላቸውን ግለሰቦች በውስጡ አቅፎ መያዝን ያህል አደገኛ ነገር እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል። ሌኒን «ፓርቲያችን፣ የአብዮታዊው ሠራተኛ መደብ ፓርቲ የአባላትን ቁጥር ከማበራከት ይልቅ ጥራትን በማሻሻል፣ እንዲሁም እራሱን ከራስ ወዳዶች በማጽዳት ላይ የሚያተኩር በዓለም ብቸኛው መንግሥታዊ ፓርቲ ነው።»* ያለው ማናቸውም የማሌ ፓርቲ ለአባላቱ ጥራት እጅግ በጣም ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባው ለማስገንዘብ ነው።

አንድ የማሌ ፓርቲ የአባላቱን ጥራት በሚመለከት ከፍተኛ ትኩረት ቢሰጥም፣ ውስብስብ በሆነ የትግልና የግንባታ ሂደት ውስጥ ለሠራተኛው መደብና ለመላ ሠርቶ አደሮች አመራር የሚሰጥ አካል እንደመሆኑ፣ በአሠራሩ ሂደት አልፎ አልፎ ስህተት አያደርግም ማለት አይቻልም። እንደሚባለውም የማይሳሳት የማይሠራ ብቻ ነው። በመሆኑም አንድ የማሌ ፓርቲ ከሌሎች የቡርዧና የንዑስ ከበርቴ ፓርቲዎች የሚለይበት ዓይነተኛው ነገር ስህተት ሲፈጸም ስህተቱን ወዲያውኑ ተገንዝቦ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ በመሆኑ ነው። ዋንኛው የአብዮታዊነቱና የጥንካሬው መሠረትም ይኸው ቀራጥነቱ ነው።

አንድ የማሌ ፓርቲ ድክመቶቹን ተሉ ብሉ የመገንዘብ፣ ሳይዘገይም የማረም አብዮታዊ ልምድን ካዳበረ፣ ከሚመራው ሕዝብ ጋር በመዋሃድ የሕዝቡን የልብ ትርታ ካዳመጠና ከሕዝብ የመገንጠል አደጋን በፅኑ ከተከላከለ፣ ተጨባጭ ሁኔታውን ከዘለቄታ ግቡ ጋር በማገናዘብ ለየወቅቱ ተስማሚና ትክክለኛ እስትራቴጅና ታክቲክ ከነደፈ፣ ውጣ ውረድ የበዛበትን አብዮታዊ ትግል እስከመጨረሻው ድል-እስከ ሶሽያሊዝምና ኮሚኒዝም አሸናፊነት ድረስ ለመምራት የሚችል ስለመሆኑ ቀንጣት ያህል ጥርጥር አይኖርም።

አንድ የማሌ ፓርቲ በተወሰኑ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈሃሳባዊና ድርጅታዊ መርሆዎች ላይ የተገነባ እንደመሆኑ፣ ከላይ የተጠቀሰውን ክቡርና ታሪካዊ የሆነ ተልእኮውን በሚገባ ሊወጣ የሚችለው በድርጅታዊ አሠራሩ የሌኒኒስት የአዲሱ ዓይነት ፓርቲ ድርጅታዊ መርሆ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን አጥብቆ የተከተለ እንደሆነ ነው። ይህ ማለት በፓርቲው ውስጥ በማናቸውም ደረጃ በንቃት ላይ የተመሠረተ ዲስፕሊን በጥብቅ የተከበረ እንደሆነ፣ በአባላቱ መካከል የሂስና የግለሂስ ልምድ በሚገባ የዳበረ እንደሆነ፣ የአባላቱ አሠራር በፓርቲ ውስጣዊ ዲሞክራሲና የጋራ አሠራር ልምድ የበለጸገ እንደሆነ ብቻ ነው።

እነኚህ የማናቸውም አብዮታዊ ፓርቲ ሌኒናዊ የሆኑ የድርጅታዊ አሠራር መርሆዎች ሲጣሱ ፓርቲው የሠራተኛው መደብ ከፍተኛና የተደራጀ አካል፣ የሠርቶ አደር ሕዝቦች ትግል ግንባር ቀደም መሪ መሆኑን ያቆማል። ልል ወይም፣ ቀርጽ ወደሌለው

---

* Lenin, Col. Works, Vol. 30, p. 63

የሰዎች ከምችት ወይም ከሠራተኛው ሕዝብ ወደተገነጠለ ጠባብና የተገለለ ቡድን ይለወጣል ። ስለሆነም ማናቸውም የማሌ ፓርቲ በአብዮታዊነቱ ጸንቶ ለመቆየት ከላይ የተጠቀሱትን የሌኒኒስት የድርጅታዊ አሠራር መርሆዎች በጥብቅ መከተል ይኖርበታል ።

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር አለ ። ይኸውም አንድ አብዮታዊ ፓርቲ ይህን ስያሜውን እንደያዘ ሊቆይ የሚችለው እራሱን ከአድርባዮችና ከጸረ ሶሽያሊስት ኃይሎች ለማጽዳት የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው ። እንደነዚህ ዓይነት ተባዮችን አዝሎ ለመጓዝ የሚፈልግ ፓርቲ ይዋል ይደር እንጂ ከውድቀትና ከጥፋት ሊያመልጥ አይችልም ።

በአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ውስጥ ለፓርቲው አብዮታዊ አንድነት ጸር የሆነ በተለያየ መልኩ የሚከሰት የጠባብ ቡድን ስሜት ካለ፣ በዚያ ፓርቲ ውስጥ እንደሁኔታው የ« ግራ» ወይም የቀኝ ወይም ሁለቱም ዓይነት አድርባዮች መኖራቸውን ያመለክታል ። ምንጊዜም ቢሆን ድርጅታዊ መርሁ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በሆነ በአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ውስጥ የጠባብ ቡድን ስሜት ፣ የአንጃኝነትና የማንኛውም ዓይነት የከፋፋይነት አዝማሚያ ምንጩ አድርባይነት ነው ። ሌኒን አድርባይነትን በፅኑ መዋጋት ስለማስፈለጉና ስለአድርባይነት ትክክለኛ ገጽታ ሲያወሳ« አሁን በያዝነው ወቀት አድርባይነትን ስለመዋጋት ስንናገር በማናቸውም መስክ የሚከሰተውንና የአድርባይነት ልዩ መለያ የሆነውን ጠባዩን መዘንጋት የለብንም ፤ ይኸውም ግልጽ ያለመሆኑ፣ ነገርችን ቀርጽ አልባ አድርጉና ሸፋፍና ማቅረቡ፣ ለለመጨበጡና ማምታታቱ ነው ። አድርባይ በተፈጥሮው ሁልጊዜም ቢሆን ግልጽና ወሳኝ የሆነ አቋም አይወስድም፣ ሁልጊዜም መሐል መንገድ መውሰድን ይመርጣል፤ ሁልጊዜም እርስ በርሳቸው ተፃራሪ ከሆኑ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች ውስጥ አንዱን ወይም ሌላውን ላለመያዝ እንደ እባብ ይጥመለመላል ፤ » * ብሎ ነበር ።

ሌኒን «አንድ ፓርቲ ሊጠናከር የሚችለው እራሱን ከአድርባዮች ለማጽዳት የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው ፤ » ** ባለው መሠረት፣ ማናቸውም አብዮታዊ ፓርቲ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። አድርባይነትን ለመዋጋት ዋነኛው መሣሪያ የአባላትን የርዕዮተዓለም ብቃት በየጊዜው በማሳደግ ፣ የፓርቲውን መስመር የሚፃረሩ አዝማሚያዎችን አባላት በየደረጃው ሊታገሉና ሊያከሽፉ እንዲችሉ ማድረግ ነው ። ይህም ሊሆን የሚችለው አባላት የማሌ ንድፈ ሃሳብ እውቀታቸውን ለማዳበር ዘወትር ጥረት ሲያደርጉ ነው ። በፓርቲ ውስጥ የአባላት የንድፈሃሳብ ጥናት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር መሆኑን ሌኒን በተደጋጋሚ ያስገነዘበው፣ በየደረጃው በርእዮተዓለም የበሰሉ ካድሬዎች የሌሉት ፓርቲ ወይም እንደነዚህ ዓይነት ካድሬዎች ለማፍራት በጣም ከፍተኛ ጥረት የማያደርግ ፓርቲ የመሪነት ሚናውን ጨርሶ ሊወጣ የማይችል መሆኑን ለማስገንዘብ ነው ። እዚህ ላይ ሌላ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር የአንድ ኮምኒስት የርእዮተዓለም ብቃት ያነበበውንም ሆነ የተማረውን በተግባር ከመተርጐምና ከተግባርም ከመማሩ ተገንጥሎ መታየት እንደሌለበት ነው ። ይህም ማለት አንድ ኮምኒስት የማሌ ንድፈሃሳብ እውቀቱን ያለማሰለስ ለማዳበር የሚችለው ሁልጊዜም በማጥናት፣ በተለያዩ ሙያዎችና መስኮች የእውቀት አድማሱን ለማስፋት ያለመታከት ሁልጊዜም ሲጣጣር ፣ በሰፊው

* Lenin, Col. Works, Vol. 7, p. 404
** See J. Stalin, Foundations of Leninism, p. 123

ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ፣የፓርቲውን መመሪያዎችና ውሳኔዎች በትክክል ተገንዝቦ ለሕዝብ በመግለፅና በማስረዳት፣በሕዝቡና በፓርቲው መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር በማድረግ፣ያለአንዳች ማወላወል ለዘብተኝነትንና ጸረ አብዮት አዝማሚያዎችን፣የአድኅሪ ሥርዓት ሥነ ልቦናዊ ዝይቤዎችንና አመለካከቶችን በመዋጋት ኮምኒስታዊ ሥነ ምግባርን ሲያጉለምስ ነው።

ሌላው ፓርቲው እራሱን ከአድርባዮች ለማፅዳት ከሚያካሂደው ትግል ጋር የተቀራኘው፣ ፓርቲው አባላቱን በማሌ ንድፈሃሳብ ለማስታጠቅ በሚያካሂደው ጥረት ውስጥ ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ለማጠናከርና ብሔረተኝነትን ለመዋጋት መስጠት ስለአለበት ትኩረት ነው። ማናቸውም የማሌ ፓርቲ አባል የሆነ ኮምኒስት ለዓለም ሠርቶአደሮች አንድነትና ኅብረት የቆመ፣ በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ጽኑ እምነት ያለው፣በአገር ፍቅርና የሶሽያሊስት አርበኝነት ስሜት የታነጸ መሆን አለበት። በተለይ ደግሞ የጉሣ፣የሃይማኖት፣የዘር፣የጾታና በመሳሰሉትን ልዩነቶች ማድረግ ለብሔራዊ አንድነት ጸርና እድገትንም ጉታች በመሆኑ፣እነዚህን አደገኛ አዝማሚያዎች መዋጋት ይጠበቅበታል። አንድ ኮምኒስት ከማናቸውም ዓይነት የብሔረተኝነት ስሜት ነፃ ካልሆነ፣ኮምኒስት የሚለውን መጠሪያ ሊይዝ አይችልም። በመሆኑም ፓርቲው ለአባላቱ በተለያየ መንገድ በሚሰጠው የንድፈሃሳብና የፖለቲካ ትምህርት ውስጥም ሆነ በሕዝቡ ውስጥ በስፋት በሚያካሂደው የፕሮፓጋንዳ ሥራ፣የወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ስሜት የማጠናከሩና ብሔረተኝነትን በጽኑ የመዋጋቱ አስፈላጊነት ሊታለፍ የማይችል ነገር ነው።

እንደሚታወቀው ማናቸውም የማሌ ፓርቲ የርዕዮተዓለም ሥራውን የሚያካሂደው በአባላቱ መሐል ብቻ አይደለም። የሠራተኛውን መደብና የሠርቶአደር ሕዝቦችን አብዮታዊ ትግል እስከ ሶሽያሊዝም አሸናፊነት ድረስ ለመምራት ባለው ታሪካዊ ኋላፊነት፣በሰፊው ሕዝብ መካከል የማሌ ርዕዮተዓለምን ለማሠራጨት የሚያካሂደው የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሥራም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

የማሌ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ከቡርዧ ፓርቲዎች ፕሮፓጋንዳ የሚለየው ለጥቂት የኅብረተሰብ በዝባዥ ክፍሎች ጥቅም ሳይሆን ለመላ ሠርቶአደር ሕዝቦች ጥቅም የቆመ በመሆኑ፣ በሐቀኝነቱና በአብዮታዊነቱ ነው። ሐቀኛና አብዮታዊ በመሆኑ ብቻ ግን የአንድ የማሌ ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራ እንዲሁ በራሱ የታለመለትን ግብ ሊመታ አይችልም።

አንድ የማሌ ፓርቲ በሰፊው ሕዝብ መካከል የማሌን ርዕዮተዓለም በማሠራጨት የአድኃሪ መደቦችን የርዕዮተዓለም ትግል ለማክሸፍ የሚችለው ፓርቲው ርዕዮተዓለሙን በሚያሠራጭባቸው ዘርፎች (ማለትም የሕዝብ መገናኛ ዘደዎችን፣የትምህርቱን ዘርፍ፣የኪነጥበቡና የባሕሉ ዘርፍ ወዘተ ...) ሁሉ አባላቱን በአመራር ቦታዎች ላይ በመመደብ አንድ ወጥ የሆነ የርዕዮተዓለም አመራር ለመስጠትና በአባላቱም አማካይነት ሥራውን በቅርብ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ሲችል ብቻ ነው። ይህም ማለት በዚህ ረገድ የሚሰጠው መመሪያ ተግባራዊ መሆኑን በቅርብ መከታተል፣ርዕዮተዓለሙን በሚያሰራጭባቸውና የፕሮፓጋንዳ ሥራ በሚሠራባቸው ዘርፎች መካከል ያለው አሠራር የተቀናጀ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል ማለት ነው። አንድ የማሌ ፓርቲ ይህን ለማድረግ ካልቻለ የፕሮፓጋንዳ ሥራው የተቀላጠፈ እንዲሆን ለማድረግ አይችልም።

Digitized by Google

ስለ ማሌ ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ሲወሳ አንድ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር አለ። ይኸውም፣ የአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ የታለመለትን ግብ ሊመታ የሚችለው ሠርቶአደር ሕዝቦች በቀን ተቀን ኑሮአቸው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች መሠረት በማድረግ የሚያነሱአቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ፣ ችግሮቹ ሊፈቱ የሚችሉበትን መንገድ ለመጠቆም የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው። የፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ከሕዝቡ የንቃተ ሕሊና ደረጃ ቀድሞም ሆነ ወደኋላ ቀርቶ መገኘት የለበትም። ሁልጊዜም ቢሆን በሕዝቡ ውስጥ በወቅቱ ሰፍና የሚገኘውን የንቃተ ሕሊና ደረጃና አመለካከት መሠረት በማድረግ፣ መፈክሮቹን ማብራራትና የመደብ ትግሉ ከደረሰበት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት። ይህንንም ለማድረግ የሚቻለው ፓርቲው ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በይበልጥ በማጥበቅ የሕዝቡን የልብ ትርታ ለማዳመጥ የሚያስችለውን አስፈላጊውን ስልት በመቀየስ ነው።

ሌላው አንድ በሥልጣን ላይ ያለ የማሌ ፓርቲ ርዕዮተዓለሙን በስፋት ለማሠራጨትና ሥር እንዲሰድ ለማድረግ በሚያካሂደው የፕሮፓጋንዳ ሥራ ላይ ከፍተኛ ተጽእና ያለው የሠርቶአደሩን ሕዝብ ቁሳዊ ሕይወት የመሻሻሉ ሁኔታ ነው። በማናቸውም የማሌ ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራ፣ ፓርቲው በነደፈው የኢኮኖሚ ፖሊሲና በመንግሥት አማካይነት በሚካሄደው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጤት መካከል ዳያሌክቲካዊ የሆነ ግንኙነት አለ። እንደሚታወቀው ለብሔራዊ ኢኮኖሚው እድገት የሠርቶአደሩ ሕዝብ የሥራ ምርታማነት መጨመር እጅግ አስፈላጊ ነው። የሥራ ምርታማነት እድገት የሚገኘው ደግሞ የሠርቶአደሩን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት በማዳበርና በምርት መስክ የሳይንስና የቴክኒዎሎጂ እድ፣ገን በማፋጠን ነው። በዚህ ረገድ የሠርቶአደሩን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃት ለማዳበርና ምርታማነቱን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሳድግ በማድረጉ ረገድ የፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ወሳኝ የመሆኑን ያህል፣ በአንፃሩም ለፓርቲው የፕሮፓጋንዳ ሥራ በይበልጥ መስመርና ለርዕዮተዓለም ስርጭቱም ሥር መስደድ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ወሳኝ ነው። በሁለቱ መካከል ዳያሌክቲካዊ ግንኙነት አለ የተባለውም ይኸው ነው። ባጭሩ ሠርቶአደሩ ሕዝብ ለሶሺያሊዝም ያለው ፍቅር እንዳይቀንስና ስሜቱም እንዳይቀዘቀዝ ለሚያደርገው የፓርቲ የርዕዮተዓለም ስርጭትና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ቁሳዊ መሠረት የማስገኘቱ ሁኔታ፣ በሁለቱ መካከል ያለው ዳያሌክቲካዊ ግንኙነት ከእድገቱ አንፃር ተመጣጣኝነቱን የመጠበቁ ሁኔታ የሶሺያሊዝም ድል አድራጊነት የሚወሰንበት ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር ሌኒን በ1921 አዲሱን የኢኩኖሚ ፖሊሲ በነደፈበት ወቀት ሲፅፍ «የሶቭየት መንግሥት በፖለቲካው መስክ ለተቀዳጀቸው ድሎች የኢኩኖሚ መሠረት መጣል አለብን፤ አለበለዚያ ሁሉንም እናጣለን። ይህ መሠረት ደግሞ እስካሁን አልተጣለም፤ በመሆኑም ይህን መሠረት ለመጣል በአፋጣኝ ወደ ሥራ መሰማራት አለብን፤» * ሲል ያስገነዘበው፣ የአብዮቱ ድል አድራጊነት በመጨረሻው ደረጃ የሚወሰነው የኢኩኖሚውን እድገት በማፋጠን የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ሲቻል መሆኑን ለማስገንዘብ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል።

እስካሁን ድረስ ጠቀለል ባለ መልኩም ቢሆን፣ የማሌ ፓርቲዎችን ርእዮተዓለማዊ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር ለማቀረብ ተሞክሯል። ወደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለስ፣ እስካሁን ድረስ የአብዮቱ ከፍተኛ ደካማ ጉን ሆና የቀየው አብዮቱ

* Lenin, *On Public Education*, p. 117

Digitized by Google

ይህን ዓይነት የማሌ ፓርቲ አመራር አለመቀዳጀቱ እንደሆነ ይታወቃል። እንደሚታወቀውም የኢትዮጵያን ሕዝባዊ አብዮት ዘላቂ አመራር ሊሰጥ የሚችል ግንባር ቀደም የማሌ ፓርቲ ለመመሥረት ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ ውስብስብና መራራ ትግል ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህ አንፃር የተካሄደውም ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ የማሌን ርእዮተ ዓለም በስፋት ለማሠራጨትና ጠንካራና አንድ ወጥ የሆነ የማሌ ፓርቲ ለማዋቀር ሁኔታዎችን የሚያመቻቸውን ኢሠፓአኮን ሊያስገኝ ችሏል።

ኢፓሠአኮ እርግጥ ፓርቲ ባይሆንም የአንድ የማሌ ፓርቲን ርእዮተዓለማዊ፣ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር በመለማመድ ላይ የሚገኝ የፖለቲካ ድርጅት ነው። ከዚህ አንፃር ሕልውናው ከተከሰተበት ወቀት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የማሌ ፓርቲን ርእዮተዓለማዊ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር በመለማመዱ ረገድ ምን ያህል ገፍቷል የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው። የአንድ የማሌ ፓርቲን የአሠራር ይዘት በሚመለከት ቀደም ሲል ለማቀረብ ከተሞከረው ንድፈሃሳባዊ ዘገባ ለመገንዘብ የሚቻለው ዋናው ቁምነገር የማናቸውም የማሌ ፓርቲ የሕይወት እስትንፋስ የሚለካውና የሕልውናውም እምብርት የሆነው የርእዮተዓለም ሥራው እንደሆነ ነው። ከዚህ አንፃር የኢሠፓአኮን እንቅስቃሴ ጠቀለል ባለ መልኩም ቢሆን የመገምገሙ አስፈላጊነት ግልፅ ይሆናል።

የብዙ ዓመት የትግልና የግንባታ ልምድ ያላቸው ፓርቲዎች ለአባሎቻቸው የርእዮተዓለም ትጥቅ መዳበር የሚሰጡትን እጅግ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ስንመለከት፣ አብዮቱ የፓርቲ አመራር ባልተቀዳጀበት ሁኔታ፣ለሚደራጀው ፓርቲ የፖለቲካ መስመር ትክክለኛነትና ድርጅታዊ አሠራር መስመር ወሳኝ ለሆነው የርእዮተዓለም ሥራ እጅግ በጣም ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይሆንም። በተለይም ደግሞ የማሌ ርእዮተዓለም ማኅበራዊ መሠረት የሆነው የሠራተኛው መደብ አነስተኛ በሆነበት ፣ ማይምነት በሰፈነበት ፣ አነስተኛ የሸቀጥ ምርትና ከዚህም የመነጩ ኋላቀር አመለካከቶች በሰፈኑበትና የፖለቲካ ባሕል ባልተስፋፋበት ሁኔታ ጠንካራ የማሌ ፓርቲ ለመመሥረት ምን ያህል የርእዮተዓለም ሥራና ትግል እንደሚጠይቅ መገመት አያዳግትም።

ይኸንን ሐቅ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስናገናዝብ በዚች አገር ውስጥ አንድ ጠንካራና የማይበገር የማሌ ፓርቲ ለመመሥረት በመካሄድ ላይ ያለው ትግል እግቡ መድረሱ የሚወሰነው፣ኢሠፓአኮ የአባላቱን የማሌ ርእዮተዓለም ግንዛቤ ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት፣የአባላት አመላመልን በሚመለከት ለጥራት በሚሰጠው ትኩረት፣በተግባራቸው ኢሠፓአኮ ለቀመለተ ክቡር ዓላማና ለሚያራምደው ትክክለኛ መስመር ፅኑ እምነት የሌላቸው መሆናቸውን የሚያንጸባርቁ ግለሰቦችን ለማረቅ በሚወሰደው እርምጃ ፣ አባላት በሚያሳዩት ኮምኒስታዊ ስነምግባር፣የማሌን ንድፈሃሳብ ለማጥናት፣ለማዋሃድና የተግባራቸው መመሪያ ለማድረግ በሚያሳዩት ጥረት፣ አባላቱ በማናቸውም ሥራ የጋራ አሠራር ልምድን ለማበልጸግ በሚያሳዩት ጥረትና ፍላጉት መሆኑ ግልፅ ነው። በተለይ የአባላት ምልመላን በሚመለከት አባላት በሚዘጋጁበትና በሚመለመሉበት ወቀት በርእዮተዓለሙ በኩል ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረትና ለርእዮተዓለሙም ያላቸው ተገዥነት ሊረጋገጥ የሚችልበት መንገድ መቀየስ፣ከዚህም አንፃር አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ድርጅቱ የሚያቀፋቸው አባላት ጥራት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ አቢይ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

Digitized by Google

በሌላ በኩል ደግሞ የኢሠፓአኮ አባላት ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የሕይወት መ መሪያ ማድረግ አለባቸው በሚባልበት ጊዜ ግልፅ ሊሆን የሚገባው የማሌን ርእዮተዓ ለም እንደ ሃይማኖት አምና በመቀበል ብቻ የሕይወት መመሪያ ለማድረግ ያለመቻ ሉን ነው ። የማሌ ንድፈሃሳብ ትክክለኛና አጠቃላይ በሆኑ የኅብረተሰብ የእድገት ሕግ ጋት ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ፣ እንደ ሃይማኖት ለአንደና ለመጨረሻ ጊዜ የተሰጠና የማይለወጥ ሳይሆን ፣ በተጨባጭ አብዮታዊ ትግል ልምድ የሚዳብር ነው ። እንደማ ናቸውም ሳይንስ የማሌ ንድፈሃሳብም ያለማቋረጥ መጠናት ያለበት ሳይንስ ነው የሚ ባለውም ለዚህ ነው ። ከማሌ ንድፈሃሳብ ውስጥ በአንዳንድ ዋና ዋናና መደምደሚያ በኩረሃሳቦች ገንዛቤ ረክቶ መቀመጥም በቂ አይሆንም ። የማሌን ንድፈሃሳብ ማጥና ትና ከተግባር ጋር ማዋሃድ ፣ በተግባር የዳበረ ንድፈሃሳብን ማጠቃለልና ማጥናት ፣ ለሚ ቀጥለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ፈር ቀዳጅና አቀጣጫ ቀያሽ እንዲሆን ማድረግ ፣ ይህ ያለማቋረጥ የሚቀጥል ሂደት መሆኑን ተገንዝቦ ለዚህ ዓይነት የአጠናን ዘዴ እራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ። እንደዚህ ለማድረግ ሲቻል ብቻ ነው ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን የሕይወት መመሪያ ለማድረግ የሚቻለው ። ይኸን በማስመልከት ጓድ ሊቀመንበር መን ግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረ ቡት ማእከላዊ ሪፖርት ላይ « ከችግሮቻችን ለመላቀቅ መሠረታዊው ጉዳይ ለዓላማ ችን ባለን ታማኝነት ላይ የምንጓዝበትን ጉዳና ብሩህ የሚያደርግልንን ርእዮተዓለማዊ ብቃታችንን ያለማቋረጥ ማዳበር ነው ። ለተግባሮቻችን ሁሉ መቃናት መነሻችን ርእ ዮተዓለማዊ ብቃታችን ከፍ ማለት እንደመሆኑ ፣ ይህን ቸል ማለት መሠረታዊ ኃላፊ ነታችንን መዘንጋት ይሆናል ፤ » በማለት አስገንዝበው ነበር ።

የማሌ ንድፈሃሳብ ተፈጥሮንም ሆነ ማኅበራዊ ሕይወትን በትክክል የምናይበት መነፅር እንደመሆኑ ፣ ይህን ሳይንሳዊ ንድፈሃሳብ ማጥናት በምናቆምበት ወይም ቸል በምንልበት ጊዜ ፣ ለብዙ ሺህ ዘመናት የቆየውን ፣ ያልጠፋውን ፣ ወደፊትም ለተወሰነ ጊዜ የሚቆየውን ፣ የግል ሀብት ይዞታ የአስተሳሰብ ቅሪት መሠረት በመጠቀም አሁ ንም በተለያየ መንገድ በስፋት በመሠራጨት ላይ ለሚገኘው የቡርዧ ርእዮተዓለም ተፅእኖ መጋለጣችን የማይቀር ነው ። በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ውስጥ በተፃራሪነት የቆ ሙ ርእዮተዓለሞች የቡርዥዋውና የሠራተኛው መደቦች ርእዮተዓለሞች እንደመሆና ቸው ፣ በአንደኛው ርእዮተዓለም ላይ ያለን ትጥቅ በላላበት መጠን በዚያው መጠን በተ ጻራሪው ርእዮተዓለም ተፅእኖ ስር መውደቃችንን መገንዘብ ይኖርብናል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የማሌ ንድፈሃሳብን የሕይወት መመሪያ አርገን መቀበል አለ ብን በምንልበት ጊዜ ከተግባር የተገነጠለ ንድፈሃሳብን ማነብነብ አለብን ማለት አለ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል ። የተያያዝነው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ መሳካት ፣ የማሌ ንድፈሃሳብ ግንዛቤያችንን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማዋሃድ ካለን ችሎታ ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ነው ። ይህንኑ ጉዳይ በማስመልከት ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማእከላዊ ኮሚቴ አንደኛ መደበኛ ስብሰባ ባደ ረጉት ንግግር ላይ ፤

« የአመራር ሚና አውቀ ማሳወቀ ነው ። በበጉ አስተሳሰብ ብቻ ትክክለኛ አመ ራር መስጠት አዳጋች ነው ። ስለዚህ በቀድሚያ ወደ ግባችን የምንጓዝበትን ብሩህ ጉዳና የሚያመለክተንን መሣሪያ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን አጥብቀ መጨበጥ አማ ራጭ የለውም ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን መሣሪያችን አድርገን የሶሽያሊስት ኅብ ረተሰብን የእድገት ሕግ በሚገባ ለማጤን ካልቻልንና የቀሰምነውንም እውቀት

Digitized by Google

ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ተግባራዊ ለማድረግ ካልበቃን ሶሻሊዝም በዚህ አገር ከምኞት ሊያልፍ አይችልም ።» በማለት በትክክል አስቀምጠውት ነበር ።

ያልተከለሰ የማሌን ሳይንስ በሰፊው ሕዝብ ውስጥ እንዲሰርፅ የማድረግ ኃላፊነቱን መሠረት በማድረግና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በቀየሰው መስመር ፣ ኢሠፓአኮ ከአንደኛ ጉባኤው አንስቶ ሰፊውን ሠርተአደር ሕዝብና አባላቱን በሳይንሳዊው የማሌ ርእዮተዓለም ለማስታጠቅ ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ፣ ደካማ ጐኖችም መከሰታቸው አልቀረም ። አብዮታችንን ለመቀልበስ ፣ አብዮታዊት እናት አገራችንን ለመቀራረስና ለመበታተን ከየአቅጣጫው ተነስተው የነበሩት የኢምፔሪያሊዝም ቀጥረኞች በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደጀንነትና በአብዮታዊ ጦሩ ታሪካዊ ተጋድሎ ድባቅ ተመተው እንዲያፈገፍጉ ሲደረጉ ፣ በአንዳንድ የአብዮቱ ወገኖች ዘንድ የመኩራራትና የመዝናናት አደገኛ አዝማሚያ ተፈጥሮ ነበር ። ይህ ሁኔታ በተፈጥሮ ፣ በወራሪዎችና በተገንጣዮች አፍራሽ ድርጊቶች ሳቢያ ከተፈጠረው ችግር ጋር ሁኖ ፣ሶሻሊዝም የማይዋጥላቸውና የካፒታሊዝም ናፋቂ የሆኑ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በየመንግሥት መዋቅሩ የተሰገሰጉ ኃይሎች ከገል የኢኮኖሚ ይዞታው ጋር በመመሳጠር በምዝበራና በብኩንነት መልክ ከሚያካሂዱት የኢኮኖሚ ቡርቦራ ፣ ዓለምአቀፍ ኢምፔርያሊዝም በአብዮታችን ላይ ከሚያካሂደው ጸረ አብዮት ፕሮፓጋንዳና በቅጥረኞቹ አማካይነት ከሚፈፅመው ደባ ጋር ተዳምሮ ሰፊው ሕዝብ ለማሌ ርእዮተዓለም ያለውን የጋለ ስሜት በመጠኑም ቢሆን ለማቀዝቀዝ ተሞክሯል ።

ለኢሠፓአኮ ማእከላዊ ኮሚቴ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ በቀረበው የርእዮተዓለም ዘርፍ ሪፖርት ላይ በዚህ አንጻር የተከሰቱትን ድክመቶች ጠቀስል ባለ መንገድ ሲጠቁም ፣

—የአባላት የርእዮተዓለምና የንድፈሃሳብ ጥንካሬ ፣ የድርጅታዊ አሠራርና የአመራር ብቃት ከአንድ የማሌ ፓርቲ አባላት የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ያለመገኘት ፣

—አባላት በሰፊው ሕዝብ ሕይወት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛነት ፣

—የሠርተአደሩን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃተህሊና በማዳበር ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎች በቂ አለመሆናቸው ፣

—የፕሮፓጋንዳ ሥራው ቅንጅት የሌለውና ተጨባጭነት የሚያንሰው መሆኑ ፣

—ርእዮተዓለሙን በማሠራጨቱ ረገድ የበኩሉን ሚና የሚጫወተው የትምህርቱ ዘርፍ አዲሱን ትውልድ አብዮታዊ አድርጐ ለማፍራት በሚያስችል ይዘትና መልክ መደራጀቱንና መዋቀሩን ለማረጋገጥ የተወሰደው እርምጃ በቂ አለመሆኑ ፣

—ለርእዮተዓለሙ ሥርጭት የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ በሚገባው በባሕሉ ዘርፍ የተሠማሩትን ባለሙያዎች የርእዮተዓለም ግንዛቤ በማዳበርና በተለያየ መልክ በማበረታታት ለአዲሱ ባሕል ግንባታ የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሳደግና አዳዲስ ባለሙያዎችን ለማፍራት በቂ እርምጃ አለመወሰዱ ፣ ወዘተ...

በማለት አተተ ነበር ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ መደበኛ ስብሰባም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ ድክመቶች ያልተወገዱና ሥር የመስደድ አዝማሚያ የያዙ መሆናች

Digitized by Google

ውን በርእዮተዓለም ዘርፍ ባደረገው ትንተና ለመልከቷል። የአንዳንድ አባላት የርእ
ዮተዓለም ግንዛቤ ደረጃም ሆነ በተለይም የርእዮተዓለም ተገዥነት ጉዳይ ገና ብዙ
እንደሚቀረውና ባንዳንድ ገጽታውም አሳሳቢ መሆኑን በስብሰባው ላይ የቀረበው ሪፖ
ርት ለመልከቷል። የርእዮተዓለም ሥራ ውጤታማነት የሚለካው ሠርቶ አደሩን ሕዝብ
ወደ ድርጅቱ ለመሳብ በተገኘው ውጤት አንጻር እንደመሆኑ፣ በዚህ በኩል ከንውኑ
የሚጠበቀውን ያህል ሁኖ አለመገኘቱ የድክመቱ ነጸብራቅ መሆኑ በአራተኛው የኢ
ሠፓአኮ ማእከላዊ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ሪፖርት ውስጥ ተገልጿል።

ኢሠፓአኮ ከተከሰተ ወዲህ ሶየሌ ተግባራት የተከናወኑ በመሆናቸው በሚያበረ
ታታ ሁኔታ ላይ እንገኛለን ለማለት ቢቻልም፣ የፕሮፓጋንዳ ሥራን ተጨባጭና ውጤ
ታማ ማድረግን በሚመለከት፣ በባሕሉም ዘርፍ የኪነጥበብ ይዘትና የእድገት አቀጣ
ጫን በሚመለከት፣ በትምህርቱም በኩል የተደረገውን የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ተግ
ባራዊ የማድረጉን ሁኔታ በአጠቃላይ አሮጌውን ላዕላይ መዋቅር አፈራርሶ በምትኩ
አዲስ ላዕላይ መዋቅር የመገንባቱን ትግል በማፋፋም ረገድ በተለይም ደግሞ የማሌ
ፓርቲን ንድፈሃሳባዊ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር በተጠናከረ መልክ መለማመ
ድን በሚመለከት ድክመቶች መንጸባረቃቸው የሚታይ ነው። በመሆኑም የሠርቶአደ
ሩን ፓርቲ ሕልውና በአስተማማኝ ለማስገኘት፣ የተያያዝነውን የግንባታ ምዕራፍ
ለማገባደድና በኢትዮጵያ ውስጥ የሶሽያሊዝምን ልዕልና ለማረጋገጥ ኢሠፓአኮ፣
ንድፈሃሳባዊ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራሩን በተጠናከረ ይዘትና መልክ ማካሄድ
ይኖርበታል ።

ከዚህ አንጻር በቀርቡ የሚካሄደው የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ የኢሠፓአኮን የር
እዮተዓለም ስርጭት ሂደትና የድርጅታዊ አሠራር ልምዱ፡የደረሰበትን የእድገት ደረጃ
የሚገመግም፣ ከሁለተኛው ኩንግሬስ ጀምሮ እስከ ፓርቲው ምስረታ ድረስ ባለው ጊዜ
ውስጥ ለኢሠፓአኮ ርእዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አሠራር የተግባር መመሪያ የሚነደ
ፍና የሠርቶአደሩ ፓርቲ የሚመሠረትበትን የጊዜ ገደብ የሚወስን እንደመሆኑ፣ በማሌ
ንድፈሃሳብ የታጠቀ፣ በድርጅታዊ አሠራሩም የሌኒንን የአዲሱን ዓይነት ፓርቲ አሠራር
የተከተለ፣ በሚነድፈውም ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር የኢትዮጵያን አብዮት እስከ
መጨረሻው ግብ — እስከ ሶሺያሊዝም አሸናፊነትና የኩምኒዝም ልዕልና ድረስ ሊመራ
የሚችል ጠንካራና የማይበገር የማርክሲስት-ሌኒኒስት ፓርቲ ለመመስረት በመካ
ሄድ ላይ ያለውን ውስብስብ ትግል በተሳካ ሁኔታ በማገባደዱ ረገድ እጅግ ከፍተኛና
ወሳኝ የሆነ ሚና ይጫወታል።

Digitized by Google

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተግባርና በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወቱት ሚና

የጊዜያችን የሣይንስና የቴክኖሎጂ የተፋጠነ ዕድገት ፣ የዓለምን ኅብረተሰብ ከምን ጊዜውም የበለጠ ባቀራረበበትና ባስተሳሰረበት በአሁኑ ወቅት ፣ የሰዎችን አስተሳሰብና አመለካከት በመቅረጽ ፣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ማለትም ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን፣ እትሞች ፣ (ጋዜጦች ፣ መጽሔት ፣ መጻሕፍት ...) ፊልሞች ፣ ሙዚቃዎች ፣ ቅርጻቅርጾች ስዕሎች ወዘተ... የሚጫወቱት ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐላና እያደገ መጥቷል ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የተፋጠነ ዕድገትና በዓለም ላይ ያስከተለውን ለውጥ በማስመልከት ፣ «ብዙ ድምጾች አንድ ዓለም » (many voices one world) የሚባለው የዩኔስኮ ጥናታዊ እትም ፣ « ማተሚያ ከተፈለሰፈበትና በቅርቡ ደግሞ ቴሌግራፍ ፣ ቴሌፎን ፣ ቴሌክስ ካሜራ እና ፊልም ፣ ፎቶግራፍ ፣ ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን የመሳሉስት ልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች ከተሰሩ ወዲህ ዓለም በእውነት ተለውጣለች ፤ »[1] በማለት አትቷል ።

እነዚህ የሣይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከፍተኛ ተጠቃሚ የሆኑት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በሚሸፍኗቸው የሥራ መስኮች ፣ በሚያዘጋጁዋቸው የተለያዩ ፕሮግራሞች ፣ በአቀራረባቸውና በዘዴዎቻቸው የሰዎችን ሕሊና ለመማረክ በሚያደርጉት ያላሰለሰ እሽቅድምድም የመንግሥታትና የብሔሮች ዳር ድንበር ፣ የሕዝቦች የቋንቋና የባሕል ልዩነት ሊያግዳቸውና ሊያቆማቸው ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ።

በተለይም ደግሞ ዓለም በሁለት ተከፍላ የመደብ ቅራኔው በተካረረበት በአሁኑ ዘመን ፣ እያንዳንዱ አገርና ሕዝብ ስለዓለም ሁኔታ ለማወቅ ያላው ፍላጐት እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህንን በማስመልከት ጂዮርጅ አክዜል ዘ ሪስፖንሲቢሊቲ ኦፍ ዘ ማስ ሚዲያ በሚለው ጽሑፍ«ለማኅበራዊና ለስብዓዊ ነጻነት ዕድሉ እየሰፋ ሲሄድ የሰው ልጅ አስጊ ደረጃ ላይ በደረሰበት የዓለም ሁኔታ ፣ ለማ

Digitized by Google

ንኛውም እርምጃ ቅድመ ሁኔታ ስለሆነው ስለ ድርጊቶች በቅድሚያ መረዳት አንገብጋቢ ሆኗል ፤ »[2] በማለት አስገንዝቧል ።

በዚህ አንጻር የዩኔስኮ ዋና ዲሬክተር ሚስተር እምቦ «መገናኛ የማኅበራዊ ግንኙነት ልብ ነው ። ሰዎች በመካከላቸው መደበኛ ግንኙነት በፈጠሩበት ሁሉ ፣ የመገናኛ ቅንብሮች ባሕርይ፣ የያዟቸው ቅርጾች ፣ የደረሱበት የጠበቀ አሠራር ደረጃ ኅብረተሰቦችን የበለጠ ለማቀራረብና አንድነታቸውን ለማጠናከር ወሳኝ ናቸው ። እንደዚሁም በመካከላቸው የሚነሱትን ውጥረቶች ለማላላት ወይም ግጭቶችን ለማባባስ የሚጫወቱት ሚና የዚያኑ ያህል ወሳኝነት አለው ፤ »[3] በማለት የመገናኛ ዘዴዎች የያዙትን የላቀ ስፍራ ጠቁመዋል ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ብዙ ነገሮችን ይሸፍናሉ ፣ ሁሉን አቀፍና ሁሉን ነክ ናቸው ፤ ስለሆነም በቀላሉና በጠባቡ መታየት የለባቸውም ። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የዩኔስኮ ጥናታዊ እትም ፣ «መገናኛ ዘዴን እንደዜናና መልዕክት ልውውጥ ብቻ ሳይሆን ፣ ሰፋ ባለ ትርጉሙ ሃሳቦችን ፣ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን፣ መረጃዎችን መለዋወጥን እንደሚያጠቃልል ፣ የግልና የኅብረት እንቅስቃሴ የተመለከትን እንደሆነ ፣ በማናቸውም ማኅበራዊ ስሪት አበይት ተግባራቱ፡- ማሳወቅ . . . ማስተባበር (Socialization) ማንቀሳቀስና ማነሳሳት (Mobilization) ... ማከራከርና ማስተማር... ባሕላዊ እድገት ማስገኘት . . . ማዝናናት. . . ውህደት መ ፍ ጠር (Integration) . . . ይሆናሉ ፤ »[4] በማለት ሰፋ አድርጐ አመልክቷል ።

ስላለንበት ዓለም ከተለያዩ ምንጮች መረዳት የሚቻል ቢሆንም ፣ ከሁሉም ይበልጥ ግን በተደራጀ መልክ የዕለት ተዕለት ድርጊቶችን የሚያስራጩልን የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ማለትም ራዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ጋዜጣ ፣ መጽሔቶች ፣ መጻሕፍት... ወዘተ ናቸው ። ለምሳሌ በሶቪየት ኅብረት ውስጥ ታጋንሮግ በምትባል ከተማ ውስጥ ከ1968 እስከ 70 (እ.ኤ.አ) የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ፣ በወቅቱ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ አንዳንድ ጉዳዮችን በሚመለከት ስላገኙት መረጃ ሲጠየቁ፣ከተጠየቁት መካከል 80.3 % መረጃውን ያገኙት ከሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ፣ 5% ከጓደኞቻቸውና አብረው ከሚሠሩ ግለሰቦች ፣ 14.9% ደግሞ ከቤተዘመድ ጋር ካደረጉት ጭውውት መሆኑን ያመለክታል ። ከላይ የተጠቀሰውን አኃዝ አጠቃላይ አድርገን ባንወስደውም እንኳን ካለን ልምድ አንጻር ሲታይ በአሁኑ ወቅት የአብዛኛው ሰው የመረጃ ምንጭ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መሆናቸውን ያስገነዝበናል ።

ከመገናኛ ዘዴዎች መካከል ቀደምትነት ያላቸው በጽሑፍ አማካይነት የሚሠራጩ እንደመጻሕፍት ያሉት ናቸው ። ታሪካዊ አመጣጣቸው ፣ በአውሮፓ የሕትመት ሥራ ከተጀመረበት ከአሥራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት ጋር የተያያዘ ነው ። በዚያን ወቅት የሰውን አስተሳሰብ በመቅረጽ በኩል ከፍተኛ ሚና ትጫወት የነበረችው ቤተክህነት በመሆኗ ፣ በጽሑፍ ይሠራጩ የነበሩት መልዕክቶችም የቤተክህነት ነበሩ ። የሕትመት ሥራ እየተስፋፋ ሲመጣ ከመጻሕፍት አልፎ በጋዜጣ መልክ የሚሠራጩ ጽሑፎችም ተጀመሩ ። ሆኖም መገናኛ ዘዴዎች ዛሬ ያሉበትን የዕድገት ጉዳና የጀመሩት በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ራዲዮ ሲፈለሰፍና ወደ ኋላም ቴሌቪዥን ሲሠራ ነው ። በተለይ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች አካባቢና ከዚያም በኋላ የመገናኛ ዘዴዎች አጠቃቀምም ሆነ እድገት እመርታን በማሳየት በ1960ዎቹ ላይ ሳተላይት መገናኛ ደረጃ ላይ በመደረሱ ያለንበት ወቅት «የኢንፎርሜሽን ፍንዳታ» ዘመን እየተባለ ሊጠራ በቅቷል ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ሁሉን አቀፍና ሁሉን ነክ የሆኑት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች

Digitized by Google

ከፖለቲካ ነጻ ሊሆኑ እንደማይችሉ አንዳ
ንድ የቡርዧ ምሁራን ሳይቀሩ ለመቀበል
ተገድደዋል ። በዚህ አንጻር ሄርቦት ሂማን
<u>« የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችና ፖለቲ
ካዊ ትብብር ፣ የመገናኛ ዘዴዎች ሚና »</u>
(mass media and political socialisat-
i on the role of patterns of communi
cations) በሚለው ድርሰቱ «የሰፈው ዓለም
ዜናዎች አካባቢንና ብሔራዊ ሁኔታዎችን
የሚመለከቱ ጉዳዮች ፣ የፖለቲካ ሃተታ
ዎች ፣ የርዕሰ አንቀጽ ጉዳዮች እነዚህ ሁሉ
በተለያየ የሃይማኖት ፣ የኪነጥበብ ፣ የሳይ
ንስ ፣ የንግድና የመዝናኛ ይዘት ባላቸው
የመገናኛ ዘዴዎች የታቀፉና ባንጸባራቂ
ሽፋኖች ተጠቅልለው ቢቀርቡም፣ የፖለ
ቲካ ማስተማሪያ ናቸው ፤ »[5] በማለት የፖ
ለቲካ ማንጸባረቂያ መሆናቸውን በጥናቱ
ውስጥ አብራርቶታል ። ከፍ ብሎ የተመ
ለከተው የዩኔስኮ ጥናትም በመደብ በተከ
ፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ማናቸውም በመ
ገናኛ ዘዴዎች የሚተላለፍ ነገር ከፖለቲካ
ነጻ ሊሆን የማይችል መሆኑን እንደሚከተ
ለው አብራርቷል ። «መገናኛ በአጠቃላይ
ሲታይ ከፖለቲካ ገፅታው ተለይቶ ሊቀርብ
አይችልም ። ችግሮቹም የፖለቲካ ግንኙነ
ቶችን ሳይመረኮዙ ሊፈቱ አይችሉም ።
ፖለቲካ «ላቅ» ባለው ትርጉሙ መገናኛ
ማለት ስለሆነ መገናኛ ከፖለቲካ ጋር የማ
ይፈርስ ቁርኝት አለው ። »[6] የመገናኛ
ዘዴዎችን ዓላማ በማስመልከት በሌላው
መስክ እንዳለው ሁሉ በቡርዧና በሶሻሊ
ስት ርዕዮተዓለማውያን መካከል የተለያየ
አመለካከት አለ ። የቡርዧ ርዕዮተዓለማው
ያን የመገናኛ ዘዴዎች «እውነተኛ» መል
ዕክት ማስተላለፊያ ፣ ማስተማሪያና ማዝናኛ
በመሆናቸው አመለካከታቸው ወገናዊ አይ
ደለም የሚል አቋም ሲኖራቸው ፣ በማርክ
ሲስቶች አመለካከት ደግሞ የመገናኛ ዘዴ
ዎች ጥንትም ሆነ ዛሬ የገዢው መደብ አመ
ለካከት ማሰራጫ ናቸው ። ከታሪካዊ አመ
ጣጣቸውም ብንነሳ ገና የሕትመት ሥራ
በተጀመረበት ወቅት በአውሮፓ ገና የነበ
ረው የፊውዳል ሥርዓት በመሆኑና የፊው
ዳል አመለካከት ማሠራጫ ደግሞ ቤተክህ
ነት በመሆኗ ፣ የሚተላለፉ ጽሑፎች በሞላ
የዚሁ ነጸብራቅ ነበሩ ። በፊውዳሉ ሥርዓት
ውስጥ ቡርዧው እያቆጠቆጠ ሲመጣ የቡ
ርዧውን አመለካከት ለማሠራጨት ይወጡ
የነበሩ ጽሑፎች በወቅቱ ይታፈኑ ነበር ።
የቤተክህነቱን አመለካከት የሚያናጋ ሳይን
ሳዊ አመለካከት ሲጀምር ይወጡ የነበሩ
ጽሑፎች እንዳይታተሙ ይከለከሉ ነበር ።
እንደአጋጣሚ ቢታተሙም ለአንባቢያን
የተከለከሉ ጽሑፎች በመባል በልዩ ልዩ
ስፍራ ይቀመጡ እንደነበር ከጽሑፎቹ
ታሪክ መረዳት ይቻላል ።

የመገናኛ ዘዴዎች ዓይነተኛ ዓላማ የኅብ
ረተሰብን አስተሳሰብ ለገዢው መደብ በሚ
ስማማ መልክ መቅረጽ ነው ። ይህንን ዓላማ
የቡርዧ ርዕዮተዓለማውያን ለመካድ ቢሞ
ክሩም እውነቱ የሚያሳየን ይህንኑ ከመሆ
ኑም በላይ አንዳንድ የቡርዧ ርዕዮተዓለማ
ውያን ራሳቸው ከሚሰጡት አስተያየት ሐ
ቁን በቀላሉ መረዳት ይቻላል ። ለምሳሌ
ካርል ጂ. ፍሬድሪክ የተባለ አንድ አሜሪ
ካዊ የፖለቲካ ሳይንቲስት «የመገናኛ ዘዴ
ዎች የአገራችንን ሰው ይሁን የውጭ ዜጋ
የኛን ፖለቲካ እንዲደግፍ ካልሆነም እንዳይ
ቃወም ማድረጊያ ዓይነተኛ መሣሪያ ናቸ
ው »[7] በማለት (እ-ኤ-አ) በ1972 ጽፏል ።
አባባሉ የመገናኛ ዘዴዎችን ዓላማ ቁልጭ
አድርጎ ያሳያል ።

ዛሬ በዓለም ላይ በየዕለቱ የሚሠራጩ
ጽሑፎች ፣ የሚተላለፉ ዜናዎች ፣ የሚታዩ
ፊልሞችና በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን የሚ
ተላለፉ መልእክቶች ዓላማቸው የሰውን አስ
ተሳሰብ መቅረጽ ነው ። ቡርዧው በኅብረ
ተሰቡ ዘንድ እንዲሰፍን የሚፈልገው አስ
ተሳሰብ ከመደብ ባሕሪው የመነጨ ነው ።
የቡርዧ ሥርዓት ዘለዓለማዊነት ፣ የቡርዧ
ባሕል ከፍተኛነትና በወዛደሩና በቡርዧው
መካከል ያለው ‘ወንድማማችነት’ ፣ ‘ዕኩ
ልነት’ ፣ ‘ነፃነት’ በየዕለቱና በየሰዓቱ ይሰ

Digitized by Google

በካል ። አንዳንድ በቡርዧ ሥርዓት ውስጥ
ከቁጥጥር ውጭ ሆነው የሚታዩ ደካማ
ጐኖች (ሥራ አጥነት ፣ ወንጀል ፣ ዝሙት፣
ስርቆት ወዘተ —) ከሥርዓቱ ሳይሆን ከሰ
ዎች የተፈጥሮ ባሕሪይ የመነጩ ተደርገው
ይወሰዳሉ ። ይህንንም አስተሳሰብ ሕዝቡ
እንዲቀበል በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አግ
ካይነት በአማረ አቀራረብ ይሰበካል ። ባጭሩ
ቡርዧው በተግባር የመገናኛ ዘዴዎችን ወገ
ናዊነት እያሳየ በቃል ግን በመካድ የመደብ
ጥቅሙን ለማራመድ ይጠቀምባቸዋል ።

ማርክሲስቶች በበኩላቸው እነዚህ ድክ
መቶች ከቡርዧው ሥርዓት መደባዊ ባሕ
ሪይ የመነጩ መሆናቸውን በተጨባጭ የሚ
ያስረዱ መልዕክቶችን በመገናኛ ዘዴዎቻ
ቸው ያስተላልፋሉ ። በቡርዧ ሥርዓት የሚ
ታየው አጠቃላይ ቀውስ የሚወገደው በቡ
ርዧው ሥርዓት መገርሰስና በምትኩ የሠ
ራተኛው መደብ የበላይገዥነት መመሥ
ረት መሆኑን ያስተምራሉ ፣ በዚህም ዓላማ
ጭቁኑን ሕዝብ ለማስተባበር ይጥራሉ ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በመደብ በተ
ከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ ማን
ፀባረቂያ ናቸው ። በልዩ ልዩ መልክና
ቅርፅ የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች
የፖለቲካ ይዘት አላቸው ስንል የመደብ
ትግልን ፣ የርዕዮተዓለም ትግልን የሚያራ
ምዱና የሚያንቀሳቅሱ መሆናቸውን መግ
ለጻችን ነው ። ዛሬ በሁለት ዓበይት ጐራዎች
በተከፈለው ዓለማችን የመደብ ትግሉን በማ
ፋፋሙ በኩል እነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች
ከፍተኛ ስፍራ ይዘው ይገኛሉ ። ኢምፔሪያ
ሊዝም በሞኖፖል የያዘውን የበላይነት በሶ
ሻሊዝም መከሰት ከተነጠቀና ካጣ ወዲህ
በጭፍን ኃይል በመጠቀም ብዝበዛውን ለመ
ቀጠል ባለመቻሉ የሰዎችን ሕሊና ለመያዝ
ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ ተገዷል ። በዚ
ህም ጥረቱ ዓይነተኛ መሣሪያ አርጐ የሚ
ጠቀመው በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ነው።

በመሆኑም ዛሬ የመደብ ጥቅሙን በማስ
ጠበቁ ረገድ ከምንጊዜውም የበለጠ የተሰ
ለፈው መንግሥት በዚህ መስክ ቀጥተኛ
ተሳታፊ ሆኖአል ። በዓለም አቀፍ ደረጃ
ያለው ግንኙነትም ከዚሁ አንፃር የሚታይ
መሆኑን በማስመልከት ጆርጅ ጐርዶን ፣
ኤርቪንግ ፎክና ዊሊያም ሆዳፐ የተባሉት
አሜሪካዊ ተመራማሪዎች «ከዚህ በፊት
ከነበሩ ምዕተ ዓመታት ሁሉ ባለፉት አርባ
ዓመታት የዓለም አቀፍ ግንኙነት ከፍተኛ
ለውጥ አሳይቷል ። በዓለም ታሪክ ውስጥ
ለመጀመሪያ ጊዜ አንድም መንግሥት ሰፊ
ውን ሕዝብ ወደራሱ ዓላማ ሳይገፋፋ መኖር
የማይችልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።» [8] በማ
ለት መጻፋቸውን ጂዮርጂ አርባቶቭ ገል
ጿል ። ይህም በመሆኑ ዛሬ የዜና ማሠራጫ
ዎች በብዛት ፣ በዓይነትና በጥራት ከምንጊ
ዜም በልጠው መገኘታቸው ከዚሁ አኳያ
የሚታይ ነው ። በዓለም በጠቅላላው 400
ሚሊዮን ቴሌቪዥኖች ፣ 25,000 የሬዲዮ ጣ
ጣቢያዎች ፣ 1000 ሚሊዮን ሬድዮኖች ፣ ከአ
ንድ መቶ በላይ የዜና ማሠራጫዎችና በብዙ
ሺህ የሚቆጠሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች [9] በየ
ዕለቱ ለዓለም ሕዝብ መልዕክታቸውን ያስ
ተላልፋሉ በማለት ቪ ራቪዶቭ፣በታሽኬንት
ለተደረገው ዓለምአቀፍ የጋዜጠኞች ሴሚ
ናር ባደረጉት ንግግር አብራርተዋል ።

በዛሬው ወቅት የመደብ ትግሉ ዓይነተኛ
ገፅታ የሆነው የርዕዮተዓለም ትግል ይበልጥ
እየተጠናከረና የበላይነቱን እየያዘ የመጣው
ይበልጥኑ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወ
ዲህ ነው ። ባንድ በኩል እንደ አቶሚክና
ኑክሊዩር ቦምብ ያሉት ብዙሃንን አውዳሚና
አጥፊ የጦር መሣሪያዎች መስፋፋት እና
የሶሻሊስቱም ጐራ በዚህ መታጠቁ ፣ በሌላ
በኩል ኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ መረቡን
ለማጠናከር ወይም ለማቆየት ባካሄዳቸው
የተለያዩ የአካባቢ ጦርነቶች ፣ ለምሳሌ እንደ
ቪየትናም ባሉት፣ ቀንድ ቀንዱን፣ እየተመታ
ወደኋላ እንዲያፈገፍግ መገደዱ የርዕዮተ
ዓለሙ ትግል ብቸኛ አማራጭ ሆኖ እንዲ
ቀርብ አድርጉታል ። ይሁንና ኢምፔሪያ
ሊዝም በርዕዮተዓለሙ መስክ ትግሉን እያ

Digitized by Google

ፋፋመ ቢሆንም በቀቢፀ ተስፋ በኃይል ለመጠቀም የጦር መሣሪያ እሽቅድምድሙን ፣ ወራሪነቱንና ፀብ አጫሪነቱን እርግፍ አድርጐ ትቷል ለማለት አይቻልም ።

የርዕዮተዓለሙ ትግል ባለንበት ወቅት ወደ ወሳኝነት ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ፣ ቬ. ኮርቱኖቭ «የሃሳቦች ጦርነት በዛሬው ዓለም ·» (The Battle of ideas in the modern world) በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ በማለት ገልጾታል ። «ማናቸውም ዘመን ፣ ዳግመልደትን (Renaissance) ብርሃናዊነትን (Enlightenment) የመሳሰሉት ፣ በብሔሮች ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆኑት ወቅቶች እንኳን በሃሳቦች ጦርነት፣ ጥልቀትና ግለት ከዘመናችን ጋር አይወዳደሩም ።»[10]

በአጠቃላይ የዜና ማሠራጫዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩና የሚሰጣቸውም ትኩረት ከፍ እያለ ቢሄድም በሶቭየት ኅብረት የጥቅምት የ1917 አብዮት ድል አድርጐ የወዛደሩ የበላይገዥነት ከተመሠረተ በኋላ በተለይም የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አብቅቶ ኃይሎች ሚዛኑ ወደ ሶሻሊዝም ካጋደለ በኋላ፣ዕድገትና እምርታ አሳይቷል ። ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ከዚያን ወቅት በፊት በአንድ አካባቢ ፀረ ኢምፔሪያሊስት እንቅስቃሴ ሲቀሰቀስ በዛቻና በኃይል እንቅስቃሴውን ሲገቱት የቆዩ ሲሆን ፣ ሶቪየት ኅብረት ጠንካራ ሶሻሊስት ኃይል ሆና ብቅ በማለቷ የኃይሉ እርምጃ እምብዛም እንደማያዋጣቸው ተረዱ ። በዚህም ምክንያት ቀዝቃዛው ጦርነት ማለትም የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ተጀመረ ። ቀደም ሲል የዜና ማሠራጫዎች በሁለት አገሮች መካከል ያለውን ቅራኔ የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም በዚያን ጊዜ የነበረው ቅራኔ በሁለት በዝባዥ መደቦች ማለትም በቡርዧውና በፊውዳሉ ፣ በከፍተኛውና በአነስተኛው ካፒታሊስት ወዘተ ... መካከል የሚታዩ ቅራኔዎች ነበሩ ።

ዓለም በሁለት ካምፕ ከተከፈለች በኋላ የተፈጠረው በሁለቱ የመንግሥት ዓይነቶች መካከል ያለው ቅራኔ በዝባዥ መደቦችን በሚወክሉት በካፒታሊስት አገሮች መንግሥታትና ሠራተኛውን ሕዝብ በሚወክሉት በሶሻሊስት አገሮች መንግሥታት መካከል ያለውን ቅራኔ ነው ። በመሆኑም ቅራኔው የመደብ በመሆኑ ፕሮፓጋንዳውም ከርዕዮተዓለሙ ትግል ተነጥሎ የማይታይ ሆነ።ይኸን ሁኔታ በማስመልከት ጆርጂ አርባቶቭ «ዓለም በሁለት ሥርዓት በመከፈሏ የእያንዳንዱ አገር ሕዝብና መንግሥት ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች በሁለት ተቃራኒ መደቦች ርዕዮተዓለሞች መካከል ትግል የሚካሄድባቸው መድረኮች ሆነዋል ፤» በማለት አስገንዝቧል ።

አካዳሚሺያን ጅዮርጂ አርባቶቭ በዓለም አቀፍ ግንኙነት የርዕዮተዓለምን ትግል ወደ ከፍተኛ ደረጃ መድረስን በማስመልከት ፣ «ዛሬ የርዕዮተዓለም ትግሉ በመንግሥታት የውጭ ግንኙነት ውስጥ ከፍተኛ ግምትና አዲስ ገፅታ አግኝቷል ። ከዚህም የተነሳ የርዕዮተዓለም ተፋላሚዎችን በዓለም አቀፍ ግንኙነቶች በቀላሉ የማይገመት የዓይነት ለውጥ መገኘት ፣ የእነዚህ ግንኙነቶች እንደገና «ርዕዮተዓለማዊ» መሆን ፣ ወይም አንዳንድ የቡርዧ ጠበብቶች እንደሚያስቀምጡት «ስሜታዊ» ስለመሆኑ መናገር ተገድደዋል ፤ »[11] ሲል አስቀምጦታል ።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የፖለቲካ ማንፀባረቂያና የርዕዮተዓለም ትግል ዓይነተኛ መሣሪያ ናቸው ። በዛሬው ወቅት በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ጐራዎች መካከል የሚካሄደው ውስብስብ ፍልሚያ በእነዚህ መሣሪያዎች አማካይነት የሚንቀሳቀስ እንደመሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሁለቱም በኩል ከፍተኛ ጥረት ፣ በቢልዮን ዶላር የሚቆጠር ሀብትና ከፍተኛ ቁጥር ያለው የምሁርና የባለሙያ ሠራዊት ተሰማርቶበታል ።

የመገናኛ ዘዴዎች የርዕዮተዓለም ትግል መሣሪያ ሆነዋል ስንል ኢምፔሪያሊስት አገሮች እነዚህን መሣሪያዎች ለፀረ ኮሚኒዝም ፕሮፓጋንዳ ይጠቀሙባቸዋል ማለታችን

Digitized by Google

ነው ። የኢምፔሪያሊስት አገሮች በመገናኛው መስክ የሚያሳዩትን ዕድገትም የምንመለከተው ከዚሁ አኳያ ነው ። በተለይ የሳተላይት መገናኛ ከተጀመረበት ማለትም አሜሪካ ኢኮ 1 የተባለችውን የመገናኛ ሳተላይት ወደ ጠፈር ካመጠቀችበት እ.አ.አ. ከ1960 ዎቹ መጀመሪያ ወዲህ ለፀረ ኮሚኒዝም ፕሮፓጋንዳ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። የዚህን ጥቅም በማስመልከት የቤል ቴሌፎን ምርምር ጣቢያ ዲሬክተር ጆን ፒርስ «በዋሽንግተን ያሉ በርካታ የፖለቲካ ሰዎች ጠፈር የቀዝቃዛው ጦርነት ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን ፣ የመገናኛ ሳተላይቶችም በሶቪየት ኅብረት ላይ ለሚነዛው ፕሮፓጋንዳ መጠቀም የሚቻልበትን ዘዴ ማጥናት ጀምረዋል ፤»[12] በማለት መጻፉን ጂዮርጂ አርባቶቭ ገልጿል ።

የፀረ ኮሚኒዝም ፕሮፓጋንዳ ዓይነተኛ ዓላማ ኮሚዩኒዝም እንዳይስፋፋ መጣር ፣ በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ስርአቱ የሚቀለበስበትን መንገድ መቀየስና በአጠቃላይ ኮሚዩኒዝም ለሰው ልጆች ደህንነትና ብልጽግና ሳይሆን አጥፊ እንደሆነ አድርጐ ማቅረብ ነው ። ምዕራባውያን ለዚህ ዓላማ የሚጠቀሙበት የቴክኖሎጂን ዕድገት ብቻ ሳይሆን በሰውና በገንዘብ ኃይል በከፍተኛ ድርጅት የተጠናከሩ ፀረ ኮሚኒስት ተቋሞችንም ጭምር ነው ። ከነዚህ ዓይነት ድርጅቶች አንዱ ሬዲዮ ፍሪ ዩሮፕ የተባለው ሲሆን ፣ ድርጅቱ ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት ሃያ ስምንት ከፍተኛ ማስተላለፊያዎች ፣ 1600 ሠራተኞች (1100 በሙኒክ፣100 በኒውዮርክ፣400 በፖርቱጋል) ሲኖሩት በ6ቋንቋዎች ማለትም በቼክ፣ በስሎቫክ ፣ በሀንጋሪ ቋንቋ በፖሊሽ በሩማንኛና በቡልጋሪያ ቋንቋ ፀረ ኮሚንስት ፕሮፓጋንዳ እንደሚያስተላልፍ ጆርጂ አርባቶቭ ጠቅሶታል ።[13] ከዚህ በተጨማሪ «አሜሪካን ኮሚቴ ፎር ሊበሬሽን ፍሮም ቦልሼቪዝም» የተባለ በተለይ በሶቭየት ኅብረት ላይ በ17 ቋንቋዎች ፀረ ኮሚዩኒዝም ፕሮፓጋንዳ የሚነዛ ድርጅት (እ.ኤ.አ) በ1951 ተቋቁሞአል ።

ዋናው የአሜሪካ የፀረ ኮሚዩኒዝም ፕሮፓጋንዳ መሣሪያ የአሜሪካ የመረጃ ተቋም (USIA) የተባለው ድርጅት ነው ። ይህ ተቋም በተራማጅ አገሮች አካባቢ የሬዲዮ ጣቢያዎች በማቋቋምና ካልተቻለም በአካባቢው ባሉ አድሃሪ መንግሥታት ሬዲዮ ጣቢያዎች በመጠቀም አብዮት ለመቀልበስ ቅስቀሳ ያካሂዳል ። ድርጅቱ በ1969 ላይ 186,300,000 ዶላር ባጀት የነበረው ሲሆን፣ በተለይ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት ካርተር ፕሮፓጋንዳ የውጭ ፖሊሲአቸው ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን ከገለጹ ወዲህ ድርጅቱ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ድርጅት (International communication agency) የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ይበልጥ በመጠናከሩ የዓመት በጀቱ ወደ 430 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ብሏል ።[14] ሌላው ቀርቶ 'ፔንታጐን' በመባል የሚታወቀው የአሜሪካን የመከላከያ ተቋም እንኳ ለፕሮፓጋንዳ ሥራ ብቻ በዓመት 190 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር[15] እንደሚያወጣ ታውቋል ።

ፀረ ኮሚዩኒዝም ፕሮፓጋንዳ ለመንዛት ኢምፔሪያሊስት አገሮች በመገናኛ ዘዴዎ እንደሚጠቀሙ ሁሉ ሶሺያሊስት አገሮችም የኢምፔሪያሊዝምን ትክክለኛ ገፅታ ለማጋለጥና ሠርቶ አደሮችን ለሶሺያሊስት ግንባታ ለማነሳሳት በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ይጠቀማሉ ። ለዚህ ዓላማ በ1974 በሶቪዬት ኅብረት የሬዲዮ ፕሮግራም በ70 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ይተላለፍ የነበረ ሲሆን ፣ 8,200 የተለያዩ ዓይነት ጋዜጦች ፣ 7,000 መጽሔቶችና ሌሎች ሕትመቶች ይወጡ ነበር ። ሶቭየት ኅብረት አንጋፋ ሶሻሊስት አገር በመሆኗ አብዮቶች በሚቀሰቀሱበት አካባቢ ሁሉ አብዮታውያንን ለማበረታታትና ሕዝቡን ለአብዮቱ ለማሰለፍ የበኩሏን ጥረት ታደርጋለች ። በዚህም መሠረት በ1913 ፣ 2.7 ሚሊዮን የነበረው የጋዜጦች ስርጭት በ1954 ፣ 44 ሚሊዮን መድረሱ አብዮቱ ለዚህ ዘርፍ የሚሰጠውን ትኩረት ያመለክታል ።[16]

Digitized by Google

አብዮት የሕዝቡ ነው ። በመሆኑም አብዮት ለማካሄድ ሕዝቡን መቀስቀስና ማደራጀት ያስፈልጋል ። ሕዝቡን ማደራጀት ብቻ ሳይሆን አብዮት አስፈላጊ መሆኑን አምኖ እንዲሰለፍ ማድረግ የአብዮት ኃይሎች ተግባር ነው ። ይህን በሚመለከት ሌኒን «የአብዛኛውን የሠራተኛ መደብ አስተሳሰብ ሳይለውጡ አብዮት ማካሄድ አይቻልም። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው በራሱ በሠራተኛው ሕዝብ የፖለቲካ ልምድ ነው፤»[17] በማለት አብራርቷል ። የሰፊውን ሕዝብ አስተያየት ለመቀየር በዕቅድ የሚመራ ከሰፊው ሕዝብ የዕለት ኑሮ ጋር የተያያዘና ለችግሩ መፍትሔ ለመሻት የሚያስችል ትምህርት መስጠት ያሻል ። ከዚህ አኳያ ሲታይ ባለንበት ሁኔታ ወደሰፊው ሕዝብ በቀላሉ ሊደርስ የሚችል በመገናኛ ዘዴዎች የሚተላለፍ መልዕክት መሆኑን እንገነዘባለን ።

የሶሻሊስት አብዮት ዓላማ ሕዝቡን ለኢኮኖሚ ግንባታ ፣ ለባሕል ለውጥና ለአዲስ ኅብረተሰብ ምስረታ መቀስቀስና ማሰለፍ ነው ። ለዚህ ዓላማ መሳካት አጠቃላይ የአስተሳሰብ ለውጥ መምጣት ያስፈልጋል ። ስለዚህ የሶሻሊስት ፕሮፓጋንዳ ዋንኛ ዓላማ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ነው ማለት ይቻላል ። ይህንኑ በማስመልከት ሉቺያን ዊ ፓይ የተባለው ጸሐፊ «ሰፊው ሕዝብ አዲስ አስተሳሰብ ካልመሠረተና አዲስ አሠራርን እንዲከተል አመራር ካላገኘ ለኤኮኖሚ ግንባታ ፣ ለማኅበራዊ ለውጥና ለፖለቲካ ብቃት የሚያደርገው ጥረት ውጤቱ እምብዛም ይሆናል፤»[18] በማለት ገልጿል ።

ሶሻሊዝም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን የሚጠቀመው ባንድ በኩል ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን በእኩልነትና በነፃነት ላይ የተመሠረተ ኅብረተሰብ ለመገንባትና የሰፊውን ሠርቶአደር ሕዝብ ንቃተሕሊና ለማዳበሪያ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊዝምንና የአድሃሪያንን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለማጋለጥ ፣ የጭቁንና ምዝብር ሕዝቦችን ትግል ለማገዝ ነው ። በዚህ አንፃር ወደ መቃብሩ በመሄድ ላይ ያለው ኢምፔሪያሊዝም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን የሚጠቀመው የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ዕድሜውን ለማራዘም ሲሆን ፣ ለዚህም ሥራዬ ብሎ የተያያዘው ሶሻሊዝምንና ኮምኒዝምን ማጥላላትና ማንቋሸሽ ፣ ጭራቅ አስመስሎ በማቅረብ ሕዝቦችን ማስፈራራት ነው ።

በኢትዮጵያ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሚና

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው አሌ የሚባል አይሆንም ። ይሁንና ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ፊውዳል ሥርዓት መለኮታዊና ዘላለማዊ አስመስሎ ለማቅረብ ሲውገረገሩ እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው ። የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የተጫወቱትን ሚና ከመገምገማችን በፊት በቅድሚያ አብዮት ኢትዮጵያ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ታሪክና መደባዊ ሚና በሚመለከት ባጭሩም ቢሆን መቃኘት ያስፈልጋል ።

በኢትዮጵያ በቀድሞ ጊዜ አዋጅና ሕዝቡ ሊሰማው የሚገባ ማናቸውም መልዕክት ለሕዝቡ የሚነገረው አዲስ አበባ ከሚገኘው የቤተመንግሥቱ ሰገነት ላይ እንደነበር ይነገራል ። በመሆኑም ያን በሰገነት ላይ ቆሞ ይናገር የነበረውን አዋጅ ተናጋሪ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀሪያው የሕዝብ መገናኛ ነበር ለማለት ይቻላል ።[19] በኋላም ነጋሪቱና በሰገነት ላይ ቆሞ እንደነጋሪቱ የሚጮኸው ሰው ድምፅ ቀስበቀስ በሌላ የዜና ማሰራጫዎች መተካት ጀመረ ። በዚህ ሂደት ውስጥ በእጅ ይጻፉ ከነበሩ ዜናዎች በመነሳት ዘመናዊ ማተሚያ ቤቶች ሊቋቋሙና የጋዜጣ ፣ የሬዲዮና ሌሎችም የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የተስፋፉበት ሁኔታ ላይ ሊደረስ ተችሏል ።

እስከ አስራ ዘጠነኛው ምእተአመት መጨረሻ ገደማ ድረስ የቤተክህነት ትምህርት የተከታተሉ ሰዎች ጽሑፎቻቸውን የሚ

Digitized by Google

ያስፍሩት በብራና ላይ በእጅ በመጻፍ ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ብለው ስለነበሩት ማተሚያ ቤቶች የተሟላ መረጃ ባይኖርም ፥ ኢሌን ሳንከሪእን የተባሉ አንድ የታሪክ ተመራማሪ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የፖርቱጋል ሚሲዮናውያን በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ያትሙ እንደነበር በመግለጽ ጽፈዋል ። [20]

በኢትዮጵያ ውስጥ በውል በታሪክ ከሚታወቁት የመጀመሪያዎቹ ማተሚያ ቤቶች መካከል በአሥራ ዘጠነኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ አጋማሽ ላይ በምፅዋ ፥ በኋላም በከረን ተቋቁመው የነበሩ ማተሚያ ቤቶች ይገኙበታል ። [21] ከነዚህ ማተሚያ ቤቶች መቋቋም ጋር በ1857 ሎሬንዞ ቢያንኬሪ የተባሉ ሰው ስለ አማርኛ ሰዋስው አንድ መጽሐፍ አሳትመው ሲያወጡ ፥ በ1872 በከረን የላዛሪስት ሚሲዮን ሰዎች የአማርኛ ግእዝ ሰዋስው መጽሐፍ አትመው ነበር ። በኋላም በ1878 የስዊድን ሚሲዮናውያን መንኩሉ ላይ አንድ ትንሽ ማተሚያ ቤት አቋቁመው ነበር ። [22]

ዘመናዊ የመጻሕፍት እትመት ከማተሚያ ቤቶች መቋቋም ጋር የተያያዘ ሲሆን ለመጽሔቶችም ሆነ ለጋዜጦች መከሰት የማተሚያ ቤቶች መመስረት ቅድመ ሁኔታ ነበር ። በዚህ አጋጣሚ መጽሔትን በሚመለከት በዚሁ በ19ኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ ላይ ብላታ ገብረ እግዚአብሔር የተባሉ ሰው ሳምንታዊ መጽሔት በእጅ ጽሑፍ በማዘጋጀት እንዲታደል አድርገው እንደነበር ማስታወሱ በኢትዮጵያ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ታሪክ ምርምር የተሟላ ያደርገዋል ።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አመጣጥ ከአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ጋር የተያያዘ ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ታትመው የወጡ ሁለት መጽሔቶችና «አእምሮ» በመባል የሚታወቀው የመጀመሪያው የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ ጋዜጣ ታትሞ የወጣው በአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ነበር ። 'አእምሮ' በመጀመሪያ ታትሞ የወጣው በ1895 ሲሆን ፥ በመሐሉ አቋርጦ እንደገና መታተም የጀመረው ከ1907—1909 በኋላም በ1917 ነበር ። [23] ከ1905—1908 በምፅዋ የስዊድን ሚሲዮናዊያን 'መልእክተ ሰላም' የተባለ ጋዜጣ በትግሪኛ አትመው ሲያወጡ ፥ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅትም ብላቴን ጌታ ሀሩይ «ጎህ ጽባሀ» የተባለ ስለ ልዩ ልዩ ድርሰቶች የሚያትት መጽሔት አሳትመው ያሰራጩ ነበር ።

ከዚህ ወቅት አንስቶ እስከ ፋሽስት ወረራ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በአማርኛና በትግሪኛ እንዲሁም በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች የተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች እየታተሙ የወጡ ቢሆንም ፥ የማተሚያ መሣሪያዎቹ በእጅ የሚንቀሳቀሱ ስለነበሩ የጋዜጦችና የመጽሔቶች ብዛትና ስርጭት እጅግ በጣም የተወሰነ ነበር ።

ከፋሽስት ወረራ በኋላ ከማተሚያ ቤቶች መስፋፋት ጋር የተለያዩ የእለት፥የሳምንትና የወር ጋዜጦች ፥ በወር ፥ በሶስት ወር፥በዓመትና በሁለት ዓመት የሚወጡ መጽሔቶችና ቡሌቲኖች እንዲሁም የመጻሕፍት እትመት እየተበራከተ መጣ ። በ1934 እለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ፥በ1936 እለታዊው 'ዘኢትዮጵያን ሄራልድ' ጋዜጣ መታተም ጀመሩ ። [25]

በኢትዮጵያ ውስጥ በሬዲዮ መልእክት

Digitized by Google

በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን መንግሥት መውጣት የጀመረው 'አእምሮ' የሚባለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሳምንታዊ ጋዜጣ

ከአእምሮ ቀጥሎ የወጣውና እ.ኢ.አ በ1917 ገደማ መታተም የጀመረው 'ብርሃንና ሰላም' የተባለው ሳምንታዊ ጋዜጣ

መተላለፍ የጀመረው በ1928 ሲሆን ፡ በዘመናዊ የሬዲዮ ስቱዲዮ አማካይነት በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስር የሬዲዮ ፕሮግራም መዘጋጀት የጀመረው በ1940ዎቹ ዓመታት ነው ። የቴሌቪዥን ፕሮግራምም የተጀመረው በ1957 ነው ። ይህ ሁሉ የተዘረዘረበት ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በዘመናዊ መንገድ መዋቀር የጀመሩት ከፋሽስት ወረራ ወዲህ እንደመሆኑ ያሳለፉት ጊዜ አጠር ያለ መሆኑን ለማመልከት ነው ።

በፊውዳሉ ስርዓት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ለነበረው ፈላጭ ቆራጭ የኃይለ ሥላሴ ዘውድ አገዛዝ በመሣሪያነት እንዲያገለግሉ የተዋቀሩ ነበሩ ። እርግጥ በሁሉም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መስክ ይታይ እንደነበረው፥ከሀገሪቱ ኋላቀርነት የተነሳ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች (ጋዜጣ፥ሬዲዮ፥ ቴሌቪዥን ወዘተ,..)ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በሙያው ያልተካኑ ፡ በቴክኒኩም ረገድ መገናኛ ዘዴዎች በድርጅት አለመሟላት ይታይባቸው ነበር ። ያም ሆኖ የነበረው የፈላጭ ቆራጭ ንጉሣዊ አገዛዝ ከቤተክህነት ጋር በነበረው የተቆራኘ ግንኙነት የተነሳ ፡ በቤተክህነት ትምህርት የተካኑ ደብተሮችና ካህናት በፕሮፓጋንዳው መስክ አሰማርቶ እንደነበር ይታወሳል ። ለምሳሌ የሰንደቅ ዓላማ ፡ የአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች የመጀመሪያዎቹ አዘጋጆች ከቤተክህነት የተገኙ እንደነበሩ ይታወቃል ።

የፕሮፓጋንዳ ጽ/ ቤት እየተባለ ይታወቅ የነበረው ድርጅት የተዋቀረበት ፖሊሲ ፡ የዘውድ አገዛዝ የአንድነት ምልክትና ያገሪቱ ምሰሶ እንደሆነ ለሕዝቡ ያለመታከት ማስተጋባት ፡ የንጉሡን መለኮታዊነትና ሁለንተናዊ ተውህቦን ማዳነቅ ፡ በቀጥታ በግጥምና በሐተታ መልክ ማወደስ ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የልማት እንቅስቃሴ አገሪቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መንጥቆ የሚያወጣት እንደሆነ በማስመሰል ፡ «ለሚወዳቸውና ለሚወዱት ሕዝብ» ንጉሠ ነገሥቱ ያለምንም መታከት እየሠሩ ከረሃብ ፡ ከድንቁርና እንዲላቀቅ እንደሚያደርጉት ማሳመን ነበር ።

በኋላም በኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታሊዝም እያቆጠቆጠ ሲመጣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በሰው ኃይልና በድርጅት አንጻራዊ የሆነ መሻሻል ቢታይባቸውም በመሠረቱ የዘውዱን አገዛዝ አዲስ ቀለም በመቀባት ታዳጊውና በማቆጥቆጥ ላይ ከነበረው ከካፒታሊስት ሥርዓት አዳዲስ ስልቶችን በማላበስ ሕዝቡን የማደንቆር ተልእኳቸውን አፋፉሙት ። ከአብዮቱ በፊት ይታተሙ የነበሩትን ጋዜጦች ለአንድ አፍታ ብንመለከት መናኛና ርካሽ ጽሑፎች ይዘወተሩባቸው እንደነበር እናያለን ። ይህም ባገር ውስጥ ለሥርዓቱ የቆሙ ጋዜጠኞች ከሚፈለፍሉት የዜና ምንጭ የተገኘ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም የጊዜው የመገናኛ ዘዴዎች የነበራቸው ግንኙነት ከኢምፔሪያሊስት የዜና አገልግሎት ወኪሎች ብቻ በመሆኑም ጭምር ነበር ። በዓለም አቀፍ ደረጃም የሚነሱትና የሚጻፉት ጽሑፎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኢምፔሪያሊዝምን ገናናነት የሚያንፀባርቁ ነበሩ ። በአጭሩ በነበረው አድኃሪ ሥርዓት የመገናኛ ዘዴዎች በርካሽና በዝቃጭ መስኮች ላይ ያተኮሩ ዜናዎችና ሐተታዎች የሚበዙባቸው ፡ በመሠረቱ ስሜታዊ ወይም 'ሴንሴሽናላይዝ' በማድረግ የወሬ ንግድ የሚካሄዱባቸው የወሬ አክሲዮን ኩባንያዎች ነበሩ ማለት ይቻላል ። ለምሳሌ በመጋቢት 12 ቀን 1966 የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ «ትዝብት» በሚል ርእስ ስር ከወጣው ጽሑፍ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በተለይም በጋዜጣ ላይ እንዳይወጡ ከከለከላቸው ነገሮች መካከል ፡

—ስለ ተማሪዎች መረበሽ ፡ ስለገበያ ውድነትና የኑሮ ውድነት ፡ ስለመሬት ይዞታ ፡ ስለጭሰኛና ስለ መሬት ግብር ፡ ስለመጠጥ ቤቶችና ሴተኛ አዳሪዎች ብዛት ፡ ስለልማት መዋጮ ገንዘብ መባከን ፡ ስለ ማዕድኖች ፡ ስለ እድግ ፡ ስለ ሃሽሽ ፡ ስለ ቁማር መኪና

Digitized by Google

ዎች ፣ ስለ አንበሳ አውቶብስ ማኅበር ፣ ስለ አዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የመታወቂያ ካርድ የሚሉና ... ሌሎችም በአጠቃላይ ሃያ አራት የሆኑ ጉዳዮች ይገኙበታል ።

ከዚህ መገንዘብ የምንችለው የፊውዶ ቡርዧው መደብ ብዝበዛውን የሚያጋልጡ ፣ ጥቅሙን የሚነኩ ፣ የሥርዓቱን አስከፊ ገፅታ የሚጠቁሙ ወዘተ . . . ሁኔታዎች ሁሉ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ላይ እንዳይ ወጡ ሲከላከል ፣ በአንፃሩ ግን የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን የመደብ ጥቅሙን ለማራመድ ይጠቀምባቸው እንደነበር ነው ። በሌላም በኩል የሕዝብ የመብት ጥያቄ እንዳይነሳ የፊውዶ ቡርዧው መንግሥት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በዚህ አቅጣጫ ጆሮ ዳባ ልበስ እንዲሉ አስገድዶአቸው ነበር ።

ባለፈው ሥርዓት ለሥርዓቱ የቆመ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ የሥርዓቱን ገናናነትና የንጉሡ ነገሥቱን መለኮታዊነት በመስበክ ብቻ አልተወሰነም ። ሕዝቡ እንዳያውቅ፣ እንዳይግር ፣ እንዳይነቃ ፣ አገሪቱ የሶስት ሺህ ዓመታት የነፃነት ታሪክ ያላት ናት በሚል ሽፋን በአጉል ኩራትና ድንቁርና እንዲጓዝ ተግጽሯል ። የሕዝቡንም መደራጀት በሚመለከት እንደ እድርና ደብ የመሳሰሉትን ካልሆነ የፖለቲካ ድርጅት የሚባል ግን ስሙም እንዳይጠራ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግ እንደነበር ይታወሳል ።

ከ1953 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወዲህ የመደራጀት ጥያቄ በጣም ስላስ ፈራው በወቅቱ ይነሱ የነበሩትን የገበሬ፣ የወዛደሩና የምሑሩ አመጾች « ወጉዝ ወር ኩስ» በማለት በመገናኛ ዘዴዎች ሲያወግዝ ፣ ሕዝቡንም በማሳሳት በአገሪቱ አንድነት ላይ የመጣ የውጭ እጅ ያለበት ነው እያለ የተማሪዎችን ንቅናቄ ያጥላላ ነበር ። ከዚህም ባሻገር ንጉሡ ለአገሪቱ ዕድገት የሚያደርጉትን 'ጥረት' ለማደናቀፍ የተደረገ ሤራ በማስመሰል ተማሪዎች የሚረብሹት ፈተና ሲቃረብ ነው ፣ ጥጋብ ነው ፣ ባለጌዎች ናቸው በማለት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሕዝቡን እያሳሳቱ ማደናቆርን ተያይዘውት ነበር ።

ምንም እንኳን በመሠረቱ አብዛኞቹ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሠራተኞች ፣ በፊውዳሉ ሥርዓት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ከተዋቀሩበት ዓላማ አንፃር ፣ የፊውዶ ቡርዧውን መደብ ፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲና አድኃሪ ርዕዮተዓለም በሰፊው በሕዝቡ መሃከል እንዲያሰራጩ ቢገደዱም ፣ አልፎ አልፎ በቁጥር በጣም አነስተኛ የሆኑ ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው (ለምሳሌ አንዳንድ ጋዜጠኞች) በዚሁ መስክ የተሰለፉ ሠራተኞች ባገኙት ቀዳዳ በመጠቀም ሥርዓቱን በተዘዋዋሪና ኅቡዕ በሆነ መንገድ የሚቃወሙ እንደነበሩም አይዘነጋም ። እርግጥ ቅዋሚያቸው የመደብ አመለካከት ያልነበረው ቢሆንም ፣ በወቅቱ ከነበረው ሁኔታ አንፃር ሲታይ ለውጥ ፈላጊ በመሆኑ ተራማጅ አቋም እንደነበረው አያከራክርም ።

በአጠቃላይ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ለፊውዶ ቡርዧው መደብ የፖለቲካ መሣሪያ በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተዋል ። ይህም ሁኔታ አብዮቱ ከፈነዳ በኋላም እስከ ሰኔ 1966 ፣ የጦር ኃይሎች የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ እስኪ ተቋቋመበትና የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን በቁጥጥር ስር እስከ አደረገበት ጊዜ ድረስ ቀጥሎ እንደነበር ይታወሳል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ እንቅስቃሴው ስር እየሰደደ መጥቶ በየካቲት 1966 ተማሪዎች ፣ መምህራን ፣ ታክሲ ነጂዎች ወዘተ . . . በተንቀሳቀሱበት ጊዜ ሁኔታው እንዳ ይዛመት በመፍራት በዜና ማሠራጫዎች የሚገለጽ አንድም ነገር አልነበረም ። በወቅቱ የሚተላለፉ መልዕክቶች ቢኖሩ ከተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች የሚሰጡ መግለጫዎች « የውጭ እጅ ያለባቸው አንዳንድ ወሮበሎች በሕዝብ ደህንነትና ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን » የሚገልጹ ሀተታዎችና ይህን «በመቃወም» ከዕድርና ከሰፈር የሚሰጡ የድጋፍ አስተያየቶች ነበሩ ። ሰፊው ሕዝብ በአብዮታዊ ወኔ የአድኃሪ

Digitized by Google

ውን አገዛዝ እውታሮች በማናጋት ላይ በነበረበት ጊዜ በጋዜጣና በሬድዮ ይተላለፍ የነበረው የንጉሡ ጉብኝት ፣ የሕገ መንግሥት መሻሻል መፈቀድ ታሪካዊ ስለመሆኑና ፣ በተደረገው የደመወዝ ጭማሪ የወታደሩ ክፍል መደሰቱ ወዘተ ... የመሳሰሉ ዜናዎች ነበሩ ። በአብዮቱ ሂደት የሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴ አይሎ የኃይል ሚዛኑ ወደ ሕዝቡ ሲያደላ የገዥው መደብም መገዛት አቅቶት ሲንገዳገድ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችም የሚያስተላልፉት መልእክት ሕዝባዊ መልክ እየያዘ መጣ ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ

አብዮታችን በ1966 በግብታዊነት ሲፈነዳ የነበረው ውሱን የድርጅትና የቴክኒክ መሠረት እንዲሁም በጣም ያነሰ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዳለ ስለነበር ከተጽእኖው ለመላቀቅ ጊዜን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ሰፊው ሕዝብ ለአዲሱ ሥርዓት እውን መሆን እንዲቆምና ያርጌውን ሥርዓት የማፈራርስ ተግባሩን በሁሉም መስክ እንዲያከናውን የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ዓይነተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

በአንድ ወቅት በተከሰቱት ልዩ ልዩ የፖለቲካ መስመር አራማጅ ቡድኖች ሳቢያ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችም የዚሁ ጽዋ ቀማሽ ቢሆኑም፣አብዮታዊው መንግሥት የሕዝቡን አስተሳሰብ ለመለወጥና አብዮቱን ለማራመድ ግንባር ቀደም ትኩረት ከሰጠባቸው መስኮች አንዱ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በመሆናቸው በጋራ የመቀስቀስ ፣ የማደራጀትና የማስተማር ተግባራቸውን ያለማሰለስ ለመወጣት ሞክረዋል ። ባለፉት የትግልና የድል ዓመታት የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች አብዮታዊው መንግሥት ያወጣቸውን መመሪያዎችና አዋጆች በተግባር እንዲተረጉሙ ሕዝቡን ቀስቅሰዋል ።

በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ ሰርጾ የነበረውን ንጉሡ መለኮታዊነት እንዳለው አርጐ የመመልከቱን ሁኔታ ለመቀየር የዜና ማሠራጫዎች የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል ። ንጉሡ ከሥልጣን ሊወርድ ዋዜማ የወሎን ረሀብ ከንጉሣውያን ቤተሰብ ኑሮ ጋር በማነጻጸር በተለይ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያቀረበው መልዕክት በማግሥቱ የንጉሡ መውረድ እንደተእምር እንዳይቆጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው ማለት ይቻላል ።

መሬት ላራሹ ሲታወጅ ፣ ዕድገት በኅብረት ሲዘመት ፣ ታላላቅ የኢኮኖሚ ተቋሞች በመንግሥት ሲወረሱ ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ሲሆን ፣ የእናት አገር ጥሪ ሲደረግ ፣ በየወቅቱ ሕዝባዊ ድርጅቶችን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማዋቀርና ለማጠናከር በተደረገው ትግል ፣ በብሔራዊ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ወዘተ . . . ሕዝቡ ለሥራ ፣ ለምርት እድገት ፣ ለትግልና ለትምህርት ታጥቆ እንዲነሳ በማነቃቃት ፣ የማሌን ርዕዮተዓለም በማስራጨት ፣ በሕዝብ ውስጥ የሶሻሊስት አርበኛነትና የወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ስሜት እንዲሰርጽ በማድረግ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሚና ተጫውተዋል ።

ይህም ሆኖ እስከ ኢሠፓአኮ መከሰት ድረስ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በተለይም የማሌን ርዕዮተዓለም ለማሠራጨት የሚያደርጉት ጥረት ፈር የያዘ አልነበረም ።

ኢሠፓአኮ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ ለመመስረት ማከናወን ከሚገባው ተግባሮች አንዱ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ርዕዮተ ዓለም በሰፊው ሕዝብ አእምሮ እንዲሰርጽ ማድረግ ነው ። ይህንን በማስመልከት የኢትዮጵያ ሠርቶአደሮችን ፓርቲ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 174/1971 ምዕራፍ 1 አንቀጽ 6—ለ « በጥናትና በውይይት ክበቦች ፣ በመንግሥታዊና በሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም በዜና ማሠራጫ ዘዴዎች አማካይነት ያልተከለሰ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም በሰፊው ሕዝብ ሕሊና ውስጥ እንዲሠርፅ ያደርጋል ፣ » ይላል ። አንድ የፖለቲካ ድርጅት የራሱን አስተሳሰብ በሕዝብ መካከል ለማሠራጨት የራሱ

Digitized by Google

ልግንና መፅሄቶች ፣ ሌሎችም ዘዴዎች ይኖ
ሩታል ። ይሁንና ኢትዮጵያን በመሰለች በት
ምህርት ኋላቀር በሆነች አገር ከድርጅቱ
በሚወጡ ጽሑፎች አማካይነት ብቻ ሕዝ
ቡን ለማደራጀት የሚደረገው ጥረት የተፈ
ለገውን ያህል ውጤት ሊኖረው አይችልም።
ስለሆነም በተለይ የሬዲዮ መልእክት ከአ
ንድ ማዕከል ተነስቶ ጋራ ሸንተረር ሳይወ
ስነው ወደ ገጠሩ ዘልቆ ሊገባ ስለሚችል
ይህን ዓይነተኛ መሣሪያ ለድርጅቱ ዓላማ
በሚገባ ለመጠቀም መቻል የግድ ይሆናል።
አንድ የፖለቲካ ድርጅት የመገናኛ ዘዴዎ
ችን መጠቀም አለበት ሲባል ተቋሞችን
በድርጅትም ሆነ በሰው ኃይል በማጠናከር
ርዕዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ አመራር በመስ
ጠት ለዓላማው ማሰለፍ መቻል አለበት
ማለት ነው ። በመሆኑም ኢሠፓአኮ ከተቋ
ቋመበት ጊዜ አንስቶ መገናኛ ዘዴዎችን
በአግባቡ ለመጠቀምና ማስተማሪያ ለማ
ድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷቸዋል ፤ በ
መስጠትም ላይ ይገኛል ።

በዚህም መሠረት የኢሠፓአኮ ማዕከ
ላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባሳ
ለፈው ውሳኔ « ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን
ለማስራጨትና የመደብ ትግሉን ለማራመ
ድ ሬድዮ ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች ወዘተ...
ማለትም የሕዝቡ የዜና ማሠራጫ ዘዴዎች
ዓይነተኛ መድረክ እንደመሆናቸው ፕሮግ
ራማቸው የተያያዝነውን የመደብ ትግል
ለማፋፋም ፣ የኢኮኖሚ ግንባታውን በተለ
ይም የምርት ግንኙነቱን ለውጥ ለማፋ
ጠን ፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ምርታማነት
ለማሳደግና የአድሀሮት ኃይላትን ፀረ አብ
ዮት ፕሮፓጋንዳ ለማክሸፍ በሚያስችል
ይዘት ተጠናክሮ እንዲቀየስ » በማለት ለመ
ገናኛ ዘዴዎች ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ
መሆኑን አብራርቷል ።

ይሁንና ኢሠፓአኮ የፓርቲን አሠራር
በመለማመድ ላይ የሚገኝ የፖለቲካ ድር
ጅት እንጂ የማሌ ፓርቲ ባለመሆኑ በሕ
ዝብ መገናኛ ዘዴዎች አያያዝና አጠቃቀም
አንፃር ድክመቶች መከሰታቸው አልቀረ
መ ። እርግጥ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች
ቀላል መሣሪያ አይደሉም ፤ ተግባራቸው ፣
አሠራራቸው ፣ እንቅስቃሴያቸው ወዘተ ...
ውስብስብ ነው ። የተጠናከረ ድርጅት ፣
በርእዮተዓለምና በሙያ የዳበረ ፣ ታማኝነቱ
የማያጠያይቅ የሰው ኃይል ይሻሉ ፣ ከዚህ
በስተጀርባ የገንዘብ አቅም ፣ በቂ ባጀትና
በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የሥራ እንቅሥ
ቃሴ ፣ ሳይንሳዊ ፈር የሚከተል አሠራርንና
የመሳሰሉትን መገኘት ይጠይቃሉ ። እነዚህ
ሁኔታዎች ከነባራዊ እውነታው ጋር በቅርብ
የተያያዙ በመሆናቸው ከጊዜው አቅማችን
በላይ ሁነው ሊታዩ ቢችሉም ጥረቶች ግን
መደረጋቸው አልቀረም ።

ማሌ ሳይንሳዊ የተግባር መመሪያ እንደ
መሆኑ ፣ አብዮታውያንና ሰፊው ሠርቶአደር
ሕዝብ ይሄንን ሳይንስ መመሪያው በማድ
ረግ አሮጌውን ሥርዓት አፈራርሰው አዲሱን
ኅብረተሰብ ይገነቡበታል ። የሕዝብ መገ
ናኛ ዘዴዎች አያያዛችንና አጠቃቀማችን
ከዚህ ግብ አንፃር ፣ ማለትም የማሌን ሳይን
ስ በአጠቃላይ ለአብዮቱ ወገኖች ከማስጨ
በጥና የተግባራቸው መመሪያ ከማድረግ
አኳያ መታየትና መገምገም ይኖርበታል ።
በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴም ሶስተኛና
አራተኛ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ በቀረቡት
የግምገማ ሪፖርቶች እንደተመለከተው በ
ዚህ አንፃር ከፍተኛ ጥረት የተደረገና ከነው
ኖቹም በቀላሉ የማይገመቱ ቢሆንም ደካማ
ጐኖችም ተጠቁመዋል ።

በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የሚሠሩ ሠራ
ተኞች መመሪያቸውን የሆነውን የወዝ አደሩን
ርዕዮተዓለም ምን ያህል ጨብጠዋል ? ምን
ያህልስ ተረድተዋል? የግንዛቤያቸው ደረጃ
እስከምን ድረስ ነው ? ይህ የመጀመሪያው
ጥያቄ ሲሆን ፣ በትክክል ለመመለስ ግን አስ
ቸጋሪነት አለው ። ይሁንና የርዕዮተዓለም
መጻሕፍትና ጽሑፎች ሥርጭትን ፣ በው
ይይት ክበቦች የሚደረገውን ተሳትፎ በአ
ጠቃላይ የአብዮቱ ወገኖች ርዕዮተዓ

Digitized by Google

ለሙን ለማወቅ ፣ ለመረዳትና ለመገንዘብ ከሚያሳዩት ፍላጐትና ዝንባሌ አኳያ ለጥያቄው መልስ ለመፈለግ ይቻላል ። ዛሬ አብዮታችን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር አጠቃላይ ሁኔታው የሚያበረታታ ቢሆንም ፣ የሚገባውንና የምንፈልገውን ያህል አለመሆኑ ግልጽ ነው ። ቀደም ብሎ ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲተያይ የመቀዝቀዝ ፣ ቸል የማለት ፣ የመዳከምና የመሳሰሉት አዝማሚያዎች መኖራቸው ለብዙዎች ግልጽ ነው ።

ከርዕዮተዓለም ግንዛቤ ባሻገር የተግባራዊነት ወይም ለርዕዮተዓለሙ ተገዥ የመሆን ጉዳይ አለ ። የተግባር መመሪያ መሆኑ ከዚህ አንፃር የመገምገም ነውና ። በዕለት ተለት የሥራችን እንቅስቃሴ ውስጥ ርዕዮተዓለሙ ምን ያህል ይንጸባረቃል ? ምን ያህል ሥራ ላይ እናውለዋለን ? በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የርዕዮተዓለም ሥርጭትን በሚመለከት ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው ።

ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ የርዕዮተዓለም ማከናወኛ ዘዴዎች እንደመሆናቸው ግምገማው ከዚህም አንፃር ሊታይ ይገባዋል ። በዚህ በኩል ድክመቶች ከተጨባጭና ከአካባቢ ሁኔታዎች ጋር አለመገናዘብና አጠቃላይ መሆን ፣ ችግሮችና ምንጫቸውን በደንብ ባለመረዳት ጸረ አብዮት እንቅስቃሴዎች በሚያንሰራሩበት ጊዜ በአፋጣኝ ለመምታት አለመቻሉ ከድክመቶቹ መካከል ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በሁሉም ነገሮች ውስጥ የሚገቡ ፣ የማይዳስሱት የማይነኩት መስክ ቢኖር እጅግ በጣም ውስን ነው ። በአንፃሩም የርዕዮተዓለም ማሠራጫና የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ ዓይነተኛ መሣሪያ የመሆናቸውን ያህል ፣ ከላይ በአጭሩ የተጠቀሙት ደካማ ጐኖች ከእነዚህ ይዞታና አጠቃቀም ድክመት የመነጨ መሆናቸው የማያጠራጥር ነው ።

እርግጥ የሰው ኃይል ጉዳይ አለ ፤ ይህ ደግሞ በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን ወሳኝነትም ያለው አቢይ ጉዳይ ነው ። የሰው ኃይል ስንል ሐቀኛ ማርክሲስት ባለሙያዎች ፣ በርዕዮተዓለሙ በሚገባ የታጠቁና ጠንካራ የሙያ መሠረት ያላቸው ፣ እንደዚሁም የበለጸገ ልምድ ያላቸው ማለታችን ነው ። የድርጅታችን በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች በሚገባ አለመሟላት ፣ ተገቢውንና የተጠናከረ አመራር ለመስጠት ያለመቻል የችግራችን ምንጮች ናቸው ። በሌላ በኩል በአፈጻጸም ረገድ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ሲተላለፉ የመጡትና የወረስናቸው ችግሮች የሚፈልቁት ከዚሁ በማሌ ሳይንስ በሚገባ ከታጠቁና በሙያና በልምድ ከዳበሩ አብዮታውያን በበቂ አለመገኘት ነው ቢባል ከዕውነት ብዙ መራቅ አይሆንም ።

ከሰው ኃይል ጋር የተያያዙ ሌሎችም ችግሮች መኖራቸው አያጠራጥርም ። የአሠራር ችግሮች መንስኤዎች በአብዛኛው ከሳይንሳዊ አሠራር ልምድ ማነስ የሚፈልቁ ሲሆን ፣ ከሌላም አንፃር ሲታዩ ይችላሉ።በሰዎች መካከል የሚፈጠሩት ግንኙነቶች በአመራርም ሆነ በአፈጻጸም በኩል ችግሮችን ወይም ቀና ሁኔታዎችን መፍጠር ይችላሉ ። ባለው አቅም፤ባለው የሰውና የማቴሪያል ኃይል የሚገባውን ያህል ተሠርቷል ወይስ አልተሠራም ? በማለት ለሚቀርበው ጥያቄ እነዚህ የአሠራርና የግንኙነት ችግሮች እንደዓቢይ ምክንያት ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ ።

የመገናኛ ዘዴዎችን ለማጠናከር አስፈላጊ የሚሆነው የሰለጠነ የሰው ኃይል ብቻ አይደለም ። ዓለም በደረሰችበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ዘመናዊ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ ። ስለዚህ የመገናኛ መሣሪያዎችን የቴክኒክ ደረጃ ከፍ ማድረግ የጠላቶቻችንን ፕሮፓጋንዳ ለመዋጋት ከሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች አንዱ ነው ።

በፕሮግራም ስርጭትም በኩል ቢሆን ገና ብዙ መሥራት ይኖርበታል ። ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች አገር ስለሆነች ለእ

Digitized by Google

ያንዳንዱ አካባቢ በቋንቋውና በባህሉ የሚተላለፍ ፕሮግራም መዘጋጀት አለበት ። ለዚህም መገናኛ ዘዴዎችን በተለ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን በየአካባቢው ለማዳረስ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ጊዜ ሊሰጠው አይገባም ። በተለይ በጠረፉ አካባቢ ከውጭ ያለው ፕሮፓጋንዳ ቀላል ባለመሆኑ ይህንን ለማዋጋት መገናኛ ዘዴዎችን በጥራትም ሆነ በመጠን ማጠናከርን ይጠይቃል ።

የመገናኛ ዘዴዎች ዕድገትና ጥንካሬ በዓለም ላይ ከሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የሚታይ ነው ። በአጠቃላይ በዓለም ላይ ከሚታየው የፕሮፓጋንዳ ስርጭትና በተለይ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታ አኳያ የመገናኛ ዘዴዎች ሊኖራቸው የሚገባው ቅንጅት ከአንድ የኮሚኒስት ፓርቲ ጋር ሊኖራቸው ከሚገባው የአሠራር ግንኙነት አኳያ እንደገና መገምገምና መታየት ያለበት ነው ።

በሶሻሊስት አገሮች እንደማንኛውም የሙያ ዘርፍ በመገናኛ ዘዴዎች ላይ ቁጥጥር የሚደረገው በሙያ የሠለጠኑ ብቁ የፓርቲ አባላትን በሥራው በቀጥታ በማሠማራት ነው ። ለሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ፣ ለፓርቲ ማተሚያ ቤቶችና አስፈላጊውን ማቴሪያል ለሚያቀርቡ ድርጅቶች አመራር የሚሰጥና የሚቆጣጠር ፓርቲው ነው ። በሶሻሊስት አገሮች በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ውስጥ የሚሠሩ ባለሙያተኞችን አሰልጥነው የሚያወጡ የማሰልጠኛ ተቋሞች በየዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ይገኛሉ ። በአጠቃላይ ከሶሻሊስት አገሮች ልምድ እንደምንገነዘበው ፓርቲዎቹ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን አሠራር የሚመሩትና የሚቆጣጠሩት በአባሉቻቸው አማካይነት ሲሆን ፣ አመራሩና ቁጥጥሩም የሠመረ እንዲሆን በዚህ መስክ የተሠማሩትን ሰዎች የርእዮተዓለም ጥራትና የሙያ ብቃታቸውን በየጊዜው ማሻሻላቸውን ፣ ለፓርቲው መስመር ያላቸው ታማኝነት የማያጠራጥር መሆኑን ያረጋግጣሉ ። በሶሻሊስት አገሮች የመገናኛ ዘዴዎች ካላቸው የዕለት ተዕለት ሥራ አኳያ ፓርቲዎቹ የሚያደርጉት ክትትል ቀጥተኛና ዕለታዊ እንደሆነ እንገነዘባለን ።

በአብዮት ሂደት ውስጥ ሕዝብን አስተምሮና አንቅቶ ለሶሻሊስት ግንባታ ለማዘጋጀት ዓይነተኛው ዘዴ በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መጠቀም ነው ። ሌኒን ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ «. . . የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ኋላቀር የሆኑ አሠራሮችን ለማስቀረትና ፣ የሥራ ወኔን ፣ የሥራ ዲስፕሊንንና ድርጅታዊ ጥንካሬን ከፍ ለማድረግ ዓይነተኛ መሣሪያ ሁነው ማገልገል አለባቸው ፤ »[26] ብሎ ነበር ።

በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መጠቀም ሲባል አጠቃላይና ዝርዝር መመሪያ በመስጠት የመመሪያውን ተግባራዊነት ዕለት በዕለት መቆጣጠርና ስህተቶችን ማረም ፣ ለዚህም መሳካት በቀጥታ በሥራው የሚሳተፉ፣ በሙያው የሠለጠኑና ለአብዮቱ ታማኝ የሆኑ ካድሬዎችን ማፍራት ፣ ማሰማራትና አመራር መስጠት ማለት ነው ። ከዚህ አንፃር የሶሻሊስት አገሮች ልምድ ሲገመገም በፓርቲዎቹና በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መካከል ያለው ግንኙነት ከሌሎች የሥራ ዘርፎች ይበልጥ የተቀራረበና ይበልጥም ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ነው ። ስለሆነም ፓርቲዎቹ በአባሎቻቸውና በአጠቃላይ ፖሊሲያቸው አማካይነት ከሚሰጡት አመራር በተጨማሪ ፣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ልዩ ባሕሪ ማለትም ቀጥተኛ የሆነ ፣ የተፋጠነና የማያቋርጥ ቅርብ ክትትልን የሚጠይቁ መሆናቸውን በመገንዘብ ፣ የዕለት በዕለት ቁጥጥር በማድረግ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የፓርቲዎቹን ዓላማ ለማሳካት የቆሙ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ ለመገንዘብ ይቻላል ።

ማጠቃለያ ፤

በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል በሚካሄደው ረዥምና ውስብስብ ትግል የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ዋንኛ መሣሪያ

Digitized by Google

መሆናቸው ዛሬ በሁለቱም ጎራዎች ዘንድ
አጠቃላይ ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ነው ። ቃላት
ከመድፎች የበለጠ ይጮሃሉ የሚለው አባ
ባል ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ዛሬ እውነ
ትነቱ በመረጋገጡ ዳር ድንበርንና የቋንቋ
ልዩነትን ዘልሎ የሚንቦገቦገው የመደብ
ትግል የሰዎችን አስተሳሰብ ለማግኘትና
ዘላቂ ድልን ለመቀዳጀት ከፍተኛውን ት
ኩረት የሰጠው ለሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች
ሆኖ እናገኘዋለን ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የማይዳስሱት ፥
የማይነኩት ፥ የማይገቡበትና የማይጠቅሱት
ነገር ቢኖር እጅግ በጣም ጥቂት መሆን አለ
በት ። በእትም ፥ በሬዲዮ ፥ በቴሌቪዥን ፥
በስዕል ፥ በቅርጻቅርጽና በመሳሰሉት ምን
የማይተላለፍ ይኖራል ? የኪነጥበብ ልዩ
ልዩ ገፅታዎች ፥ የዕውቀት ልዩ ልዩ ክፍ
ሎች ፥ የሰው አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ፥
ዝንባሌዎችና እምነቶች በተለያዩ መልኮችና
ቅርጾች በእነዚህ መሣሪያዎች ይተላለፋሉ።
ከተራና ወቅታዊ ዜናዎች እስከ ረቂቅ ፍል
ስፍናዎች ፥ ከግልፅና ተጨባጭ ቅስቀሳ
እስከ ውስብስብ የኪነጥበብ ማጠቃለያ
ዎች፥ሁሉም በእነዚህ ዘዴዎች ይሰራጫሉ፤
ይዳረሳሉ ። እነዚህ ሁሉ በመደብ በተከፋ
ፈለ ኅብረተሰብ የመደብ ጥቅምና አመለካ
ከትን የሚያንጸባርቁ እንደመሆናቸው በዛ
ሬው ወቅት በመጪጫፍ ላይ ላለው የርዕ
ዮተ ዓለም ትግል ምርጥ መሳሪያ ሆነው ይቀ
ርባሉ ። የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግስጋሴ
በእነዚህ መስኮች እጅግ ከፍተኛና ውጤ
ታማ በመሆኑ ኃይላቸውም በተፋጠነ መን
ገድ እያደገ በመምጣት ላይ ነው ። በርዕዮ
ተዓለም ትግል የተፈላጊነታቸውና የወሳኝ
ነታቸውም ምንጭ ይህ ነው ለማለት ይቻ
ላል ።

ዛሬ ተፋጠው በሚገኙት ሁለት ተጻ
ራሪ ሥርዓተ ማኅበሮች መካከል በሚደረ
ገው ውስብስብ ፍልሚያ የሕዝብ መገናኛ
ዘዴዎች የላቀ ሚናና ወሳኝነት ከእነዚህ
ከላይ ከተመለከቱት ሁለት ባሕርያት የሚ
መነጩ ናቸው ። በሁለቱም ጐራዎች ውስጥ
በተሰባሰቡት በእያንዳንዱ አገርና አካባቢ
ትግሉን በሚገባ ለማካሄድና በአሸናፊ
ነትም ለመውጣት አለያም ላለመበለጥ
በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ላይ ከፍተኛ ቁሳ
ዊና የሰው ኃይል ይመደባል ፥ በቀጥታና
በተዘዋዋሪ መንገድ በዚህ መስክ ላይ የሚ
ፈሰው ሀብትና የሚደረገው ጥረት በትክክል
ይሄን ያህል ነው ለማለት እጅግ በጣም አስ
ቸጋሪ ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም የበላይነት የሚመራ
ው የአድኅሮት ጐራ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ
ዎችን የሚጠቀመው የብዝበዛና የጭቆና
ሥርዓቱን ዕድሜ ለማራዘም ፥ አድኃሪውንና
ወቅቱ ያለፈበትን ሥርዓት ዘላለማዊ ባሕ
ርይ እንደአለው ፥ ለሰው ልጅ ተስማሚ
እንደሆነ አድርጎ አሸሞንሙኖ በማቅረብ፥
ከፍተኛ ፀረ ኮሚኒስት የሆነ የማስመሰልና
የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ነው ።

በሶሻሊስት ጎራ ውስጥ የተሰባሰቡት አገ
ሮችና ተራማጅ ኃይላትም የሕዝብ መገናኛ
ዘዴዎችን ከፍተኛ ሚና ጠንቅቀው ያው
ቃሉ ። የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሳይንሳዊ
ውን አመለካከትና አስተሳሰብ መቅረጫ
ዓይነተኛ መሳሪያ መሆናቸውን ደህና አድ
ርገው በመገንዘባቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰ
ጧቸዋል ። ኢምፔሪያሊዝምንና የአድኅሮ
ትን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለመምታትና የሰ
ፊውን ሠርቶአደር ሕዝብ ማኅበራዊ ንቃ
ተህሊና ለማዳበርና የአዲሱን ኅብረተሰብ
ግንባታ ለማራመድ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ
ዎች አማራጭ የሌላቸው መሣሪያ መሆና
ቸውን ደህና አድርገው የተገነዘቡ በመሆና
ቸው በቀጥታ በፓርቲው ቁጥጥር ስር ሆነው
ተግባራቸውን ያከናውናሉ ። በሕዝብ መገ
ናኛ ዘዴዎች በኃላፊነት ሥራ ላይ የተመደ
ቡት በአብዛኛው የፓርቲው የማዕከላዊ
ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ ፥ ሠራተኞቹም በርዕ
ዮተዓለምና በሙያ የላቀ ችሎታ ያላቸው
የፓርቲው አባላት ወይም ለርዕዮተዓለሙ
ታማኝነታቸው የማያጠራጥር ሰዎች ናቸው።

Digitized by Google

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት የተካሄደብንን የውስጥ ቡርቦራና የውጭ ወረራ ፣ የተነዛብንን የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ውዥንብር በመቋቋምና በመምታት እንደዚሁም የአዲሱ ኅብረተሰብ መመሪያ የሆነውን የማሌን ርዕዮተዓለም በማሰራጨት በቀላሉ የማይገመት አስተዋፅኦ አድርገዋል ። የማሌ ፓርቲ አለመኖርና የአንድ ጠንካራ ማዕከል መጥፋት ባስከተለው የቡድኖች ሽኩቻ ተፈጥሮ የነበረው ችግር በኢሠፓአኮ መከሰት የተቃለለ ቢሆንም ፣ ዛሬም ቢሆን ድክመቶች መንጸባረቃቸው አልቀረም ። በምንከተለው ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም በሚገባ የታጠቁ ፣ በሙያቸው የዳበሩ ለብቸኛው የፖለቲካ ድርጅታችን ታማኝነታቸው የማያወላውል ሰዎች ለማግኘት አሁንም ችግር ያለ መሆኑ አያጠራጥርም ። የፓርቲ አሠራር ልምድ ማነስ ፣ የእነዚህን መሳሪያዎች ወሳኝ ሚና በሚገባ ተገንዝቦ በሰውና በቁሳቁስ አስፈላጊውን ሁሉ በወቅቱ የማሟላት ችግር ከውጤት አንጻር ሲገመገም የሚንጸባረቅ ሐቅ ነው ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል ያህል ጊዜ ኢሠፓአኮ ማዕከላዊነት ባለው መንገድ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችን ባልተከለለ የማሌ ፍልስፍናና ለሠርቶአደሩ ፓርቲ ምስረታ አገልግሎት ለማዋል ያደረገው ጥረት አበረታችና ገንቢ ቢሆንም ፣ ከላይ እንደተመለከተው ደካማ ጎኖችም ታይተዋል ። እስከአሁን ያለፍንበት የማሌ ፓርቲ አሠራርን በመለማመድ ስለሆነ ድክመቶቹ የሚጠበቁ እንጂ አዲስ ነገር ባይሆኑም ፣ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ህልውና እየተቃረበ በመሄድ ላይ እንደመሆኑ መጠን በዚህ በኩል ያለን አመለካከትና ይዞታ ተሻሽሎ ከማሌ ፓርቲዎች ልምድ ጋር እንዲገናዘብ ያስፈልጋል ።

የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የሰዎችን አመለካከትና አስተሳሰብ በመቅረፅ ፣ በማነፅ በማረቅ ፣ በማባዛት ወዘተ . . .በኩል ያላቸው ኃይል ፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር በቅርብ የተዛመደ ከመሆኑ የሚመነጭ ስለሆነ ፣ በተገቢው የሰለጠነ የሰው ኃይል ፣ በመሳሪያና በድርጅት በኩል ማጠናከርና በሚገባ መጠቀም ፣ ከውስብስቡና ከረዥሙ የግንባታ ትግል በአሸናፊነት ለመወጣት ያስችላል ። የአንጋፋዎቹ የማሌ ፓርቲዎች ልምድ ይሄንኑ ሐቅ ቁልጭ አድርጎ የሚያስገነዝብ እንደመሆኑ እኛም የማሌን ንድፈ ሃሳብ ከተጨባጭ የአገራችንና የአብዮታችን ሁኔታዎች ጋር እያገናዘብን በፓርቲው ምስረታ ረገድ በእነዚህ ዘዴዎች በሚገባ በመጠቀም ፣ የአዲሱን በፍትሕና በወል ብልፅግና ላይ የተመሠረተውን ኅብረተሰብ ግንባታ ማፋጠን የታሪክ ግዴታችን ይሆናል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. "Many Voices, One World", in Communication and society Today and Tomorrow (Kogan Page. London (unipub, Newyork) UNESCO, Paris, 1980), p. 57.
2. Gyorgy Aczel, *The Responsibility of The mass media, The New Hungarian quarterly*; Vol. 22, No. 84, 1981, p. 15,
3. "Many Voices, One World," p. XIII. p. XIII.
4. *Ibid.*, p. 14.
5. Lucian W. Pye, *Communications and Political Development*, /New Jersey: Princeton University Press, 1967/, p. 128.
6. "Many Voices, One World", p. 18.

Digitized by Google

7. Carl J. Fredrick, *The Pathology of Politics*, /New York, n.p. 1972/, p. 176.

8. Georgii Arbatov, *The War of Ideas in Contemporary* International Relations, (Moscow: Prog. Pub., 1973), p. 27.

9. Sh. Rashidar, *International Seminar of Journalists* in Tashkent, *Mass Media and the Struggle for Peace and Social Progress*, (Moscow: Novosti Press Agency, 1980), p. 8.

10. V. Kortunov, *The Battle of Ideas in the Modern World*, /Moscow: Prog. Pub., 1979/, p. 9.

11. Georgi Arbatov, *The War of Ideas in Contemporary International Relations*, /Moscow: Prog. Pub., 1973/, p. 27.

12. *Ibid., p.* 31.

13. *Ibid.*, p. 214.

14. Soviet Mass Media, Novosti Press Agency, 1979, pp. 33-36.

15. B. Pyadyshev, *The Military Industrial Complex of the USA*, /Moscow: Progress Publishers, 1977/, p. 103.

16. Alex Iaketes, *Public Opinion in Soviet Russia*, (Cambridge: Harvard University Press, 1951), p. 144.

17. V. I. Lenin, *"Left-Wing" Communism, An Infantile* Disorder, Quoted in Joseph Stalin, *Problems of Leninism*, /San Francisco, Ca: Proletarian Publishers/, p. 49.

18. Lucian W. Pye, *Communication and Political Development* (New Jersey: Princeton University Press, 1967), p. 13.

19. የዜና ማሰራጫ ዘዴ በኢትዮጵያ ፡ አምስተኛ መጽሐፍ ፣ ማስታወቂያ ሚኒስቴር (አዲስ አበባ ፡ ንግድ ማተሚያ ቤት ፡ 1959) ። ገጽ 3

20. ከላይ ከተጠቀሰው ገጽ 6

21. » » ገጽ 7

22. » »

23. » » ገጽ 8

24. » » ገጽ 9

25. » » ገጽ 17

26. V.I. Lenin, *Coll. Works*, Vol. 30, p. 142.

Digitized by Google

ኪነጥበብና ርዕዮተዓለም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት

የዘመናችን ማኅበራዊ አብዮት በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ መሠረታዊ የሥርዓተ ማኅበርን ለውጥ ያመለክታል ። ይህ የሥርዓተ ማኅበር ለውጥ በኅብረተሰብ ዋና ዋና የኑሮ ፈርጆች ውስጥ በርዕዮተ ዓለም ፣ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በማኅበራዊ ኑሮና በሕሊናዊ ሕይወት ዘርፍ ዓበይት ለውጦች ያስከትላል ። የኢትዮጵያ አብዮትም እነዚህን ሁለንተናዊ የአብዮት ባሕርያት ያቀፈና ማቀፍም የሚገባው ነው ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የኢትዮጵያ አብዮት በኪነጥበብ መስክ ምን ለውጥ እንዳሳየ ፣ በአብዮቱ ሂደት ኪነጥበብ የማሌ ርዕዮተዓለምን በማስፋፋት ረገድ ምን ሚና እንደተጫወተና ምንስ ሚና መጫወት እንዳለበት ለማመልከት ይሞከራል።ጠቅለል ባለ መንገድ በዚህ መስክ ያለውን ጥንካሬና ድክመት በመዳሰስ ምን መደረግ እንዳለበት ይጠቆማል ። ኪነጥበብ ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለምን በማስፋፋት ረገድ ያለውን ቦታ ለመረዳት መንደርደሪያ እንዲሆን ርዕዮተ ዓለምና ኪነጥበብ ምን እንደሆኑ ፣ ያላቸውን ግንኙነትና ልዩነት በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ ይሞከራል ።

እንደሚታወቀው በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ በሰዎች መካከል ያለው ቁሳዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የማኅበራዊ ዕድገት መሠረት ነው ። ይሁንና ማኅበራዊ ዕድገትን በሚገባ ለመገንዘብ ስለ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ያለ ዕውቀት ብቻ በቂ አይሆንም ። ከምርት እንቅስቃሴ በተጨማሪ ሰዎች የሕሊናዊ ሕይወት አላቸው ። ሰዎች በተወሰኑ የፍልስፍና፣ የፖለቲካ ፣ የሥነ ምግባር፣ የስነ ውበት ወዘተ . . . አመለካከቶችና በተወሰኑ ንድፈ ሐሳቦች ይመራሉ ። እነዚህ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ማኅበራዊ ጸባይ ያላቸው እንደመሆናቸው በማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው ።

ማኅበራዊ ንቃተሕሊና የሚባለው የኅብረተሰብ ሕሊናዊ ክስተት እንደመሆኑ የሰዎች አስተሳሰብ ፣ ንድፈሐሳብ ፣ አመለካ

Digitized by Google

ከት ፣ ስሜት ፣ ልምድ ፣ ሥነ ምግባር ድምር ነው ። እነዚህ ሁሉ ተጠቃለው የሚገልጹት የኅብረተሰብንና የተፈጥሮን ተጨባጭ እውነታ ነው ። ባጭሩ ማኅበራዊ ንቃተሕሊና የሰዎች ማኅበራዊ ሕልውና ነጸብራቅ ነው ማለት ነው ።

ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ሁለት ገጽታዎች አሉት ። አንደኛው ማኅበራዊ ሥነ ልቦና የሚባለው ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ ርዕዮተዓለም ነው ። «ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ከሰዎች የቀን ተቀን የኑሮና የሥራ ሁኔታዎች በግብታዊነት የሚመነጩ የአመለካከቶች ፣ የልማዶች ፣ የስሜቶች ፣ የአስተያየቶች ፣ ወዘተ... ድምር » [1] በመሆኑ ፤ ሥርዓት ያለው የአመለካከቶችና የእምነቶች ቅንብር አይደለም ። ብማኅበራዊ ሥነልቦና ደረጃ የሰዎች አመለካከትና አስተያየት በተቀነባበረ የንድፈሐሳብ መልክ የሚቀርብ ሳይሆን የክስተቶችን ውጫዊ ሁኔታ ግርድፍ በሆነ መልኩ ከስሜት ጋር በተቀላቀለ ሁኔታ የሚያቀርብ ነው። በመሆኑም ይህ ዓይነት ንቃተሕሊና በመሠረቱ ተራ የሆነ ንቃተ ሕሊና ፣ እውነታ በዝቅተኛ ደረጃ የሚንጸባረቅበት የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ገጽታ ነው ። በመሆኑም ማኅበራዊ ስነልቦና ወደ ሌሎች የንቃተህሊና ቅርፆች ማለትም ወደ ፖለቲካ ፣ ሕግ ፣ ስነምግባር ፣ ኪነጥበብ ወዘተ ... አይከፋፈልም ።

የማኅበራዊ ሥነልቦና ትክክለኛ ግንዛቤ እውነታን በከፍተኛ ደረጃ የሚያንጸባርቁትን የሳይንስ ዘርፎችና ርዕዮተዓለምን በሚገባ ለመገንዘብ ቅድመ ሁኔታ ነው ። በተለይም ስለ ርዕዮተዓለም ታሪክ ቁስ አካላዊ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን የሚችለው ማኅበራዊ ሥነልቦናን በሚገባ የመረመርን እንደሆነ ነው። ማኅበራዊ ሥነልቦና ኅብረተሰብ በመደብ ከመከፋፈሉ በፊት የነበረ ቢሆንም በመደብ ሥርዓት ማኅበራት ግን የመደቦችንና የማኅበራዊ ክፍሎችን የቀን ተቀን እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ በግብታዊነት ስሜታቸውንና አመለካከታቸውን የሚያንጸባርቅ ነው ።

በሌላ በኩል ርዕዮተዓለም ከተፈጥሮና ከማኅበራዊ ሳይንሶች ጋር በመሆን ከላይ እንደተጠቀሰው እውነታን (እንደ ማኅበራዊ ሥነልቦና በዝቅተኛ ደረጃ ሳይሆን) በከፍተኛ ደረጃ ሳይንሳዊ በሆነና በተቀነባበረ መንገድ የሚያንጸባርቅ ነው ። የአንድ ሰው ተራ የሆነ ንቃተሕሊና ከግለሰቡ የግል ልምድና ይኸው ግለሰብ ስለአለበት አካባቢ ከሚኖረው ጊዜያዊ ከሆነ ግርድፍ አመለካከት አይዘልም ። ርዕዮተዓለም ግን ሰፋ ያለ እና የተጠቃለለን የማኅበረሰብ ልምድ መሠረት በማድረግ ውስብስብ ጽንሰ ሐሳቦችን ከታሪካዊና ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር የሚመለከት ነው ።

በአጠቃላይ « ርዕዮተዓለም የኅብረተሰብን ልዩ የሆኑ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጠባዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያንጸባርቅ ፣ የተወሰኑ መደቦችን ጥቅምና ፍላጐት የሚገልጽ ፣ ያለን ማኅበራዊ ሥርዓት ለማቆየት ወይም ለማፍረስ የሚያልም የአመለካከቶችና የአስተሳሰቦች ሥርዓት ወይም ሲስተም ነው ። » [2] በመደብ ሥርዓተ ማኅበራት ማኅበራዊ ንቃተሕሊና መደባዊ ጸባይ ያለው እንደመሆኑ ርዕዮተዓለምም በማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ከፍተኛ ገጽታነቱ መደባዊ ነው ። ርዕዮተዓለም የተለያዩ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርፆችን ማለትም ፖለቲካን ፣ ሕግን ፣ ሥነምግባርን ፣ ፍልስፍናን፣ኪነጥበብን፣ሃይማኖትን ወዘተ... የሚያጠቃልል ነው ። ማለትም የአንድ መደብ የፖለቲካ ፣ የሕግ ፣ የሥነ ምግባር ፣ የፍልስፍና ፣ የኪነ ጥበብ ፣ የሃይማኖት ወዘተ አመለካከት ተጠቃሎ የዚያ መደብ ርዕዮተዓለም ይሆናል ማለት ነው ።

ርዕዮተዓለም መደባዊ ሊሆን የቻለው ለምንድን ነው ? እያንዳንዱ መደብ የራሱ የሆነ ርዕዮተዓለምን ለመፍጠር ለምን ይገደዳል ? ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ተጻ

Digitized by Google

ራሪ መደቦች ባሉበት ሥርዓተ ማኅበር ሁሉ የመደቦች ማኅበራዊ ቦታ የተለያየ ከመሆኑም በላይ ማኅበራዊ ፍላጐታቸውና ተግባራቸውም እንደዚሁ የተለያየ በመሆኑ ነው። እያንዳንዱ መደብ በኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን ማኅበራዊ ቦታ የሚገልጸውና የሚያረጋግጠው፣ የመደብ ጥቅሙን የሚከላከለው፣ ዓላማውን ለማሳካትና ፍላጐቱን ለማሟላት የሚጥረው በተወሰኑ የአመለካከቶች ትንብር ነው። ይህም በመሆኑ ተጻራሪ መደቦች ባሉባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ሁሉ የተለያዩ ርዕዮተዓለሞች ይኖራሉ። በዚህ ሁኔታ በአንድ ሥርዓተ ማኅበር የበላይነትን የሚይዘው ርዕዮተዓለም የኢኮኖሚና የፖልቲካ ሥልጣኑን የያዘው መደብ ርዕዮተዓለም ይሆናል። ከዚህም የተነሳ በገዢውና በተገዥው መደቦች መካከልም የሚካሔደው የከረረ የመደብ ትግል የሚንጸባረቅበት አንደኛው መስክ የርዕዮተዓለም ትግሉ ይሆናል።

እዚህ ላይ፣ ርዕዮትዓለም ሁልጊዜም የመደብ ጠባይ ያለውና የመደብ ጥቅም ማራመጃ መሣሪያ ነው ከተባለ እውነታን በትክክልና ሳያዛባ እንዴት አድርጐ ለማቅረብ ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይህን ጥያቄ እዚህ ለማንሳት የተገደድንበት ምክንያት ወደኋላ የኪነ ጥበብን ወገናዊነት በምንመለከትበት ጊዜ ይኸው ዓይነት ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር በመሆኑና የሚሰጠውም መልስ (ኪነጥበብ እንደ ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርጽነቱ በርዕዮተዓለም ውስጥየሚታቀፍ በመሆኑ) ለዚህ ከላይ ለተነሳው ጥያቄ ከሚሰጠው መልስ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ነው።

በተለይ አሁን በያዝነው ታሪካዊ ወቅት በኮምኒዝምና በፀረ ኮምኒዝም መካከል የሚካሔደው የርዕዮተዓለም ትግል እየገፋ በመምጣቱና የቡርዣውን ርዕዮተዓለም ትክክለኛ ገጽታ በገሐድ በማሳየቱ የቡርዣው መደብ የርዕዮተዓለም ምሁራን ርዕዮተዓለምን በአጠቃላይ በመንቀፍ የኅብረተሰብ ሕይወት «ከርዕዮተዓለም ነፃ መሆን አለብት» (Deideologisation) እያሉ በማናፈስ ላይ ይገኛሉ። የቡርዧው መደብ የርዕዮተዓለም ምሁራን የቡርዣው የመደብ ጥቅም ከኅብረተሰብ ዕድገት ታሪካዊ ግስጋሴ ጋር የሚጋጭ መሆኑን በሚገባ ስለሚገነዘቡ ርዕዮተዓለም የሚል ነገር ጨርሶ እንዳይነሳ ሁኔታዎችን በሥነልቦና ግምገማ ብቻ ለመሸፋፈን ሲሞክሩ፣ ከላሾችና ከቡርዧው ርዕዮተዓለም ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ ያልተላቀቁ ኃይሎች ደግሞ ርዕዮተ ዓለምና እውነት (Truth) ሊጣጣሙ እንደማይችሉ፣ ርዕዮተዓለም የአንድን መደብ ጥቅም ለማራመድ በሚያደርገው ጥረት እውነትን እንደሚሰዋ አድርገው ይመለከቱታል።

በመደባዊ ኅብረተሰብ የመደቦች የአኗኗር ሁኔታ አንድ ዓይነት አይደለም። አንዱ በዝባዥ ሌላው ተበዝባዥ፣ አንዱ ጨቋኝ ሌላው ተጨቋኝ፣ አንዱ ገዥ ሌላው ተገዥ አንዱ አሠሪ፣ አዛዥ፣ ሌላው ታዛዥ፣ ሰሪ ነው። የገዥው መደብ የተደላደለ ኑሮ ላስገኘለት የምርት ግንኙነት ቆይታ የሚታገል ሲሆን ሌላው ሥርዓቱ ያቆረቆዘው መደብ ደግሞ ለዚያ ሥርዓት የምርት ግንኙነት መፍረስ የሚታገል ነው። ይህ የኑሮ ሁኔታ፣ ይህ በግጭት የተሞላ የኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት በኅብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር እንደመሆኑ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉት ርዕዮተዓለሞች ወይም አመለካከቶች የዚህን ኅብረተሰብ ቁሳዊ ግጭት የሚያመለክቱ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተፋላሚ መደቦችን የአስተያየትና የሐሳብ ቅንብር የሚያንጸባርቁ ወይም የሚያቅፉ ናቸው። እያንዳንዱ መደብ ለመደቡ ጥቅም በሚጠቅም መልክ ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ሁኔታን ይረዳል፣ ይገነዘባል። የዚህ ግንዛቤ ሁኔታ የሥርዓቱ ተጠቃሚ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ለሥርዓቱ ቆይታ የሚጠቅሙትን፣ ሥርዓቱን ከመፍረስ የሚያድኑትን፣ የሚያወድሱትን የሐሳብ ቅንብሮች ወይም ርዕዮተዓለም የሚያመርት ሲሆን፣ የሥርዓቱ ተቃዋ

Digitized by Google

ሚ ደግሞ የሥርዓቱ ዕድሜ የሚያጥርበትን
ሐሳብ የሚያብራራ ፣ ሊተካ የሚገባው ሥር
ዓት ምን እንደሆነና ጥሩም እንደሆነ የሚያ
ብራራ የተቀነባበረ ንድፈ ሐሳብ ያቀርባል ።
ለኅብረተሰብ ዕድገት የቆመውና የተራማጅ
መደቦችን ሐሳብ የሚያንጸባርቀው ርዕዮተ
ዓለም ተራማጅና ሳይንሳዊ እንደመሆኑ ፣
እውነታን በትክክል የመገንዘብ ባሕሪ ሲኖ
ረው ፣ ለአሮጌው ሥርዓት ቆይታ የሚታገለ
ውና የአድኃሪ መደቦችን ጥቅም የሚያንጸ
ባርቀው ርዕዮተዓለም አድኃሪና ኢሳይን
ሳዊ በመሆኑ አድኃሪ ከሆነው የመደብ ጥቅ
ሙ አንጻር በመነሳት እውነታን አጣሞ የመ
ገንዘብ ባሕሪ አለው ።

ለዚህ ነው ከርዕዮተዓለም በኅብረተሰብ
ውስጥ መከሰት ጋር የማኅበራዊ ንቃተሕሊ
ና ዕድገት ሁለት አዝማሚያዎች ያሳያል የ
ሚባለው ። አንደኛው ኅብረተሰብ በእርግጥ
ለመኖር ሲል በተፈጥሮና በማኅበራዊ ሳይ
ንሶች አኳያ ተፈጥሮንና እራሱን በትክክል
የሚረዳበት ፣ ነባራዊ ዕውቀት የማከማቸት
አዝማሚያ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ግን ፣ ከማኅ
በራዊ ጥቅሙ አንጻር ተነስቶ ያለውን የም
ርት ግንኙነት እንዳለ ለማቆየት ወይንም ለ
ማፍረስ የሚያስችለው ርዕዮተዓለማዊ ግን
ዛቤው ነው ።[3]

የመጀመሪያው የዕውቀት ክምችት በይ
በልጥ ስለቁስአካል ፣ ስለተፈጥሮ ፣ ስለአስ
ተሳሰብ ያለውን ነባራዊ ዕውቀት የመገን
ዘብ ፣ የመረዳትና የምርት ኃይሎችን በማሳ
ደግና ተፈጥሮን በማረቅ ለማኅበራዊ ጥቅም
ማዋልን የሚመለከት ይሆናል ። ሁለተኛ
ው ግን እንደ አፍላቂው መደብ ማኅበራዊ
አቋሙ ትክክል ወይም ስህተት ፣ እውነት
ወይም ውሸት ሊሆን ይችላል።* የተራማጅ
መደብ ርዕዮተዓለም ከትክክለኛው ፣ ከነባ
ራዊ የሰው ልጅ የማወቅ ፣ የመረዳት ፍላጎ
ት ጋር የተጣጣመ ሲሆን የአድኃሪው መደ
ብ ርዕዮተዓለም ግን የዚህ ተጻራሪ ይሆናል።
ለምሳሌ የቡርዧው መደብ ከፊውዳሉ መ
ደብ ጋር ይታገል በነበረበት ጊዜ ያስፋፋው
የነበረው ርዕዮተዓለም ተራማጅና ከሞላ
ጎደልም ቢሆን ከሳይንስ ምርምር ጋር የተ
ጣጣመ ነበር ። የቡርዧው መደብ ሥልጣን
ከጨበጠና ከወዝአደሩና ከሌሎችም ሠርቶ
አደር ሕዝቦች ጋር ያለው ቅራኔ ሥር እየሰ
ደደ ሲመጣ የቡርዧው ርዕዮተዓለም የአ
ድኃሪነት ሚና መጫወት ጀመረ ። የካፒታ
ሊስት ሥርዓት መፍረስና በሶሻሊዝም መ
ተካት የታሪክ ዕድገት ሕግ መሆኑን አሌ በ
ማለት የቡርዧው ርዕዮተዓለም የካፒታ
ሊስት ሥርዓት ዘላለማዊ ሥርዓት እንደሆነ
አድርጐ ማቅረቡ ፣ ከዚህም በመነሳት ካፒ
ታሊዝምን በማወደስ ሶሻሊዝምን ለማጥላ
ላት የሚያካሂደው ትግል የታሪክ የወደፊት
ሂደትን እንዲጻረር ስለሚያደርገው የአድኃ
ሪነት ሚናው በግልጽ ይከሰታል ።

የቡርዧውን ርዕዮተዓለም በግንባር ቀደ
ምትነት የሚዋጋው የወዝአደሩ ርዕዮተ
ዓለም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው ። ማርክ
ሲዝም ሌኒኒዝም በአሁኑ ጊዜ የኅብረተሰብ
የዕድገት ሕጎጋት የሚጠይቁትን የሚያሟላ፣
የሰው ልጅ የገጠመውንና ወደፊትም በዕድ
ገት ጐዳናው የሚገጥመውን ችግር ለመፍ
ታት የሚጠቀምበት አስፈላጊ ሕሊናዊ ሁኔ
ታ ነው ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሠርቶአ
ደሮችን የትግል አቅጣጫ የሚያመለክት ፣
የኅብረተሰብን ማኅበራዊና ተፈጥሮአዊ ች
ግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚተነትን፣

---

* ሁለቱ አዝማሚያዎች የተለያዩ ሳይሆኑ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አላቸው ። በርእዮተዓለም የእው
ነታ ግንዛቤ ገጽታ ፣ የትክክለኛ የእውቀት መገብየት ፣ እንዲሁም በትክክለኛ የእውቀት መገብየት
ሂደት ውስጥ የርእዮተዓለም የእውነታ ግንዛቤ ይገኛሉ ። ስለሆነም ልዩነት የሚደረገው ለንድፈ
ሃሳብ ትንተና እንዲያመች እንጂ ሁለቱ አዝማሚያዎች የመደራረብና የመጣመር ጠባይ አላቸው ።
በመሆኑም የሁለቱን ልዩነት ስናወሳ ይህ ሃቅ መታወስ አለበት ።

Digitized by Google

ከኅብረተሰብ ዕድገትና ከሳይንሳዊ ምርምር
ጋር በመጣጣም አብሮ የሚያድግና የሚዳ
ብር ርዕዮተዓለም ነው ።

ማርክሲዝም ፤ ስለ ርዕዮተዓለም ሲናገር የ
ሚገባው አመለካከት ከተጨባጭ የታሪካዊ
ወቅት ትንተና ጋር የተገናዘበ፡ከዚህም አን
ጻር በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት አንድ
የተወሰነ ርዕዮተዓለም የተራማጁን ወይም
የአድኃሪውን መደብ ጥቅም የሚያንጸባርቅ
ከመሆኑ አንጻር መታየት እንዳለበት ያስተ
ምራል ። በአጠቃላይ ከማኅበራዊና ኪታሪ
ካዊ ሂደት አንጻር አንድ መደብ የተራማጅ
ነት ሚና ይዞ እስከተገኘ ድረስ ፤ የዚያ መደ
ብ ጥቅም በወቅቱ ካለው ተጨባጭ እውነ
ታ ጋር ተጣጥሞ እስከ ተገኘ ድረስ ፤ በዚያ
ታሪካዊ ወቅት የዚያ መደብ ርዕዮተ ዓለም
የእውነታ ትክክለኛ ነጸብራቅ ይሆናል።ይሁ
ንና ይኸ መደብ የተራማጅነት ሚናውን ሲ
ያጣ ፤ ጥቅሙም ከተጨባጭ እውነታው ዕ
ድገት ጋር መጋጨት ሲጀምር ርዕዮተ ዓለ
ሙ ትክክለኛ ርዕዮተዓለም መሆኑን ያቆ
ማል ። በመሆኑም ከኅብረተሰብ የዕድገት
ሂደት ጋር የሚጋጭ የመደብ ጥቅሙንም ለ
ማራመድ ሲል እውነታን አጣሞ ለማቅረብ
ይገደዳል ።

አድኃሪ መደቦች ማኅበራዊ ክስተቶች ከ
መደብ ጥቅማቸው ጋር ሲጋጩ ፤ የክስተ
ቶቹ መብራራት ፤ ይፋ መውጣትና ትክክ
ለኛ ግንዛቤ ማግኘት የመደብ ጥቅማቸውን
የሚነካባቸው ከሆነ ነጩ ጥቁር ነው ፤ ጥቁ
ሩ ነጭ ነው ወይም በሬ ወለደ ይወልዳል ብ
ለው ሌሎች ሰዎችን ለማሳመን ከመሞከር
አይመለሱም።«ጥቅም ጥልቅ ኃይል ነው፤ስ
ለሆነም የጂኦሜትሪ መንደርደሪያ የሆኑ የተ
ረጋገጡ ሐሳቦች (axioms or theorems)
ከአንድ ቡድን ጥቅም ጋር የሚቃረኑ ከሆነ
ሰዎች በእርግጥ ሲያስተባብሏቸው ይገ
ኛሉ ። » 4

ለምሳሌ የቡርዧው መደብ የፊውዳሉን
ሥርዓት ለመገልበጥ በተነሳበት ጊዜ የቡር
ዧው ርዕዮተዓለም እውነታን በአብዛኛው
በትክክል የሚያንጸባርቅ ነበር ። ይሁንና
የቡርዧው መደብ የተራማጅነት ሚና ሲያከ
ትም ርዕዮተ ዓለሙም እውነታን በትክክል
ከማንጸባረቅ ተገታ ። በአንጻሩ የሠራተኛው
መደብ በመደብነት እስከሚከስምበት ጊዜ
ድረስ መደባዊ ጥቅሙ ተጨባጭ ከሆነው
የታሪክ ዕድገት ሂደት ጋር የሚጣጣም በመ
ሆኑ ፤ የዚህ መደብ ርዕዮተዓለም የሆነው
ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በሁሉም የዕድገት
ደረጃዎች እውነታን በትክክል ከማንጸባረ
ቅ አይገታም ።

በአጠቃላይ ርዕዮተ ዓለም የአንድ መደ
ብ ጥቅም በተቀናጀና በተቀነባበረ ሁኔታ
የሚንጸባረቅበት የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና
ከፍተኛ የሆነ መገለጫ ሲሆን፤ የሚቀነባበ
ረውና ሥርዓትን በተከተለ መንገድ የሚ
ቀናጀው እንደ ኅብረተሰቡ ዕድገት ደረጃ
የመደቦችን ጥቅምና የፖለቲካ ቡድኖችን
ዕድገት በንቃት ፤ በሚገባና በትክክል የማን
ጸባረቅ ችሎታ » 5 ባላቸው ርዕዮተዓለማ
ውያን ተብለው በሚጠሩ ምሁራን ነው ።

ከዚህ በላይ ስለማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና
ይዘት ፤ በተለይም ደግሞ የዚሁ የማኅበራዊ
ንቃተሕሊና ከፍተኛና የተቀነባበረ መገ
ለጫ ስለሆነው ስለ ርዕዮተዓለም ምንነት
ባጭሩም ቢሆን አንዳንድ አስተያየቶችን
ለመሰንዘር ተሞክሯል ። ቀጥሎ ደግሞ ኪነ
ጥበብ በማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርጽነቱ
የርዕዮተዓለም ተገብር (subject) መ
ሆኑን ለማሳየት ከመሞከራችን በፊት ስለ
ራሱ ስለኪነጥበብ አንዳንድ አስተያየቶችን
ለመሰንዘር እንወዳለን ።

ኪ ነ ጥ በ ብ

ኪነጥበብ እንደ ፖለቲካ ፤ ሥነምግባር
ሃይማኖት ወዘተ --- ከማኅበራዊ ንቃተሕ
ሊና ቅርጾች አንዱ ነው ። በኅብረተሰብ ታ
ሪክ ውስጥ ኪነጥበብ የተፈጠረውና የዳበ
ረው ሰዎች ስለ ሥነ ውበት ያላቸውን ፍላጐ
ት ለማርካት ነው ። ኪነጥበብ የሚንጸባረቅ
ባቸው ክስተቶች ብዙ ናቸው ። ይሁን እንጂ

Digitized by Google

አብዛኛውን ጊዜ የኪነጥበብ ሥራዎች በኅ
ብረተሰብ ላይ በተለይም በምርት ግንኙነ
ቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው ። በተጨማሪም ኪነ
ጥበብ ተፈጥሮን ለምሳሌ ፣ ባሕርን ፣ ሐይ
ቅን ፣ ዛፍን ፣ ተራራን ፣ ወዘተ - - - ጨምሮ
ያንጸባርቃል ። ነገር ግን እነኝህ የተፈጥሮን
ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚያንጸባርቁ የኪነ ጥ
በብ ምርቶችም ቢሆኑ በውስጣቸው ከያኒው
ለዚያ ለተፈጥሮ ገጽታ ያለውን ስሜት ወይ
ንም አስተያየት የሚገልጹ ናቸው ። ለምሳሌ
የአንድን ተራራ ሥዕል ኪነጥበባዊ ምርት
ብንመለከት በሥዕሉ ላይ የተቀረጸው ተራራ
በእውን ያለው ተራራ ቀጥተኛ ግልባጭ
አይደለም ። በሥዕሉ ላይ የተቀረጸው ተራራ
በእውን ያለውን ተራራ ከያኒው ተመልክቶ፣
ተገንዝቦና አጣጥሞ በራሱ አስተያየት በሥ
ዕል የሚገልጸው ነው ። ስለዚሁ ተራራ ለማ
ወቅ የጂኦግራፊ ፣ የጂኦሎጂና የሌሎች ሳይ
ንስ ዘርፎች ትምህርት ይረዳል ። ማለትም
እነኝህ የንቃተሕሊና ዘርፎች ስለተራራው
እንድናውቅና እንድንገነዘብ ለማድረግ ያስ
ችሉናል ። ነገር ግን ስለተራራው ውበት ለ
ማወቅና ለማድነቅ የምንችለው በኪነ ጥበብ
ምርት ፣ ማለትም በተራራው ሥዕል ነው ።
ይህ የኪነጥበብ ምርት ከያኒው ከመጣበት
ኅብረተሰብ ባፈራው ዕውቀት ፣ ከኅብረተ
ሰቡ ባገኘውና ባዳበረው አመለካከት አማ
ካይነት ተራራውን የገለጸበት ነው ። ስለሆ
ነም የኪነጥበብ ምርት ተፈጥሮን የሚገልጽ
ቢሆንም ይኸው ምርት የሰውንም አመለ
ካት የሚያንጸባርቅ መሆኑ መታወቅ ይኖር
በታል ።

ኪነጥበብ እንደሌሎቹ የማኅበራዊ
ንቃተሕሊና ቅርጾች እውነታን የሚያንጸባ
ርቅ ሲሆን ከሌሎቹ የማኅበራዊ ንቃተ ሕ
ሊና ቅርጾች የተለየ የሚያደርገው ደግሞ በ
ኪነጥበብ መስክ እውነታ የሚንጸባርቀው
ኪነታዊ ምስል በሚባለውና ተጨባጭነት
ባለው መልክ መሆኑ ነው ። ለምሳሌ ሳይን
ስ እውነታን የሚያንጸባርቀው በንድፈ ሐሳ
ቦች አቀነባብሮ ነው ። ኪነጥበብ ግን አን
ድን እውነታ የሚገልጸው እንደ ሳይንስ በ
ጽንሰ ሐሳቦች ሳይሆን ተጨባጭ በሆነ ነገር
በህዋሶቻችን ልንገነዘበው በምንችለው
መልክ ፣ በአንድ ተጨባጭ ኪነጥበባዊ ም
ስል ነው ። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የካፒታሊ
ዝምን የከፋ ብዝበዛ በኪነጥበብ ዘርፍ ዓይ
ነተኛ ባሕሪዎቹን ለመግለጽ ከተፈለገ በሥ
ዕል ፣ በድራማ ፣ በቲያትርና በመሳሰሉት የ
ኪነጥበብ ምርቶች በተጨባጭ ለማሳየት
ይቻላል ። ነገር ግን ይህንኑ ብዝበዛ በኢኮ
ኖሚክ ሳይንስ ለማብራራት ከተፈለገ ገለ
ጻው የሚደረገው በጽንስሐሳቦች ቅንብር
ውስጥ ባሕሪውን በመዘርዘር ይሆናል ማለ
ት ነው ።

የኪነ ጥበብ ዓይነተኛባሕሪ የሰው ልጆችን
የሥነውበት ፍላጐት (aesthetic requi-
rement) ማርካት ነው ። ኪነጥበብ ሌሎ
ችም ማኅበራዊ ተግባራት አሉት ። ኪነ
ጥበብ እውነታን እንደ መገንዘቢያ መማሪያ
ነት ፣ ሰዎችን ለማስተማሪያና ልዩ ልዩ
መልክ ያላቸው የአስተሳሰብ ፈርጆችን (ለ
ምሳሌ ፍልስፍናን ፣ ፖለቲካን ፣ ሃይማኖ
ትን ፣ ሥነምግባርን ወዘተ - - -) በሰዎች
አእምሮ ለመስረጽ ያገለግላል ።

ኪነጥበብ ልዩ ልዩ ዘርፎች አሉት።ከነ
ርሱም ውስጥ ሥነ ጽሑፍ ፣ ሙዚቃ ፣ ሥነ
ሥዕል ፣ ቲያትር ፣ ድራማ ፣ ፊልሞችና ቅርጻ
ቅርጽ ወዘተ - - - ይገኙበታል ። ኪነጥበብ
በጋርዮሽ ኅብረተሰብ ነበር ። በዚያ ኅብረተ
ሰብ የኪነ ጥበብ ምርት ከሥራ ክንዋኔ ጋር
በቀጥታ የተያያዘና ምርትን የሚያዳብር
ነበር ። አዳኙ አደኑ እንዲሳካለት የሚያ
ድነውን እንስሳ ቅርጽ ፣ የሚያድንበ
ትን ሜካና የሚኖርበትን የአካባቢ ዛፎች ፣
ድንጋዮችና የሌሎችንም ክስተቶች ባሕሪ
ያት ማወቅ ነበረበትና በሥዕል ይገልጻቸው
ነበር ። ስለሆነም እነኝህና የመሳሰሉት የኅ
ብረተሰብ ፍላጐቶች ለሥዕል የፈጠራ ሥራ
ምንጭ ሆኑ ። የሚታደኑ እንስሳትን አሳዶ
ለመያዝ አዳኙ ልምምድና የሰውነት እንቅ
ስቃሴ በማድረግ እንዴት እንደሚያድን ለሱ

Digitized by Google

መስሎች በማስመሰል ማሳየት ነበረበት ።
ይህ የሰው ልጅ ፍላጐት ለዳንስና ለመሳሰ
ሉት የኪነጥበብ እንቅስቃሴዎች ምንጭ
ሆነ ። ስለሆነም ጥልቀትም ባይኖራቸው የ
እንስሳትን ምስል የሚያሳዩ ምስሎች ፣ ዘፈ
ኖችና ውዝዋዜዎች (ዳንሶች) ተፈጠሩ ። በ
ጋርዮሽ ኅብረተሰብ የኪነጥበብ ምርት ምን
ጩ ኅብረተሰቡ ለሥራ ሂደት ፣ ለአደን ፣ ለፍ
ራፍሬ ለቀማ ፣ ለመሳሰሉት የሚያደርገው
ክንውን እንደነበረ የማሌ ሳይንስ ያስተምረ
ናል ።

የምርት ኃይሎች ሲያድጉና ከዕለት ጉርስ
የበለጠ ማምረት ሲጀምር የሥራ ክፍፍል
ሥር ሲሰድ ፣ ኪነጥበብ ከተግባራዊ የምርት
ክንውን ተለይቶ ልዩ የሕሊናዊ ምርት ፣ ልዩ
የፈጠራ መስክ ሆነ ። ከዚህም ጋር ይህንኑ
የፈጠራ ሥራ የሚያካሂዱና ተግባራቸውም
ይኸው ብቻ የሆኑ የተወሰኑ የኅብረተሰብ
ክፍሎች (ለምሳሌ ሙዚቀኞች ፣ ሠዓሊዎች
ገጣሚዎች ፣ ወዘተ . . .) ተከሰቱ ። ሠርቶ
አደሩ ሕዝብ በቁሳዊ ምርት ብቻ በመጠመ
ድ በፈጠራ ውጤት ከመደሰትና ከመጠቀም
ተወገደ ። ኪነጥበብም በኅብረተሰቡ ውስጥ
የበላይነትን ለያዙትና በቁሳዊ የምርት ተግ
ባር ላልተሠማሩት የበለጠ አገልጋይ ሆነ ።
እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ኪነጥበብ ከቁ
ሳዊ ምርት በመለየት ልዩ የሕሊና ምርትና
የፈጠራ መስክ ሆነ ማለት ፣ ይህ መስክ ከቁ
ሳዊ የኅብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ተጽዕኖ ነፃ
ሆነ ማለት አይደለም ። እንዲያውም የኪነ
ጥበብ ዕድገት በአብዛኛው ከኅብረተሰብ
ቁሳዊ ዕድገት ጋር የመያያዝ ዝንባሌ ነው
የሚታይበት ።

የኪነጥበብና የርዕዮተዓለም ግንኙነት

ርዕዮተዓለም ቀደም ሲል እንደተጠቀ
ሰው ከመደብ ጥቅም አንጻር አንድን ማኅ
በራዊ ክስተት ፣ ለምሳሌ የምርት ግንኙነ
ትን ለማጠናከር ወይም ለማፍረስ በተቀነ
ባበረ መልክና መንገድ ምክንያት የሚሰጥ
በት የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና አንደኛው ገ
ጽታ ነው ። ርዕዮተዓለም ከሚንጸባረቅባ
ቸው ቅርጾችም አንዱ ኪነጥበብ (ማለትም
በሥነ ጽሑፍ ፣ በሥዕል ፣ በድራማ ፣ በቲያ
ትር ፣ በዳንስና በመሳሰሉት የኪነ ጥበብ
ዘርፎች) ነው ።

በርግጥ ኪነጥበብ የሚያረካው የሰውልጅ
ፍላጐት ርዕዮተዓለማዊ ብቻ አይደለም ።
ኪነጥበብ የኅብረተሰብን የሥነውበት ፍላ
ጐት ያረካል ፣ ስሜትን ያስደስታል ፣ ስሜትን
ይቀሰቅሳል ። ይህም ብቻ ሳይሆን በኪነ
ጥበብ አማካይነት ነባራዊ ዕውቀት ፣ ሳይን
ሳዊ ዕውቀት ይገበያል ። ስለሆነም በኪነ
ጥበብ ምርት ሰው ርዕዮተዓለማዊና ሳይን
ሳዊ ዕውቀትን በማጣመር ይገነዘባል ማለት
ይቻላል ።

እላይ ስለ ርዕዮተዓለም መከሰትና ግንዛቤ
ስናወሳ በመደባዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ሁለት
ዓይነት እውነታን የመገንዘብ አዝማሚያ
ዎች ይታያሉ ብለናል ። አንደኛው አዝማሚ
ያ ለሰው ልጅ በእውነተኛ የኑሮ ፍላጐት
የሚወሰነውና ስለተፈጥሮና ስለሰው እው
ነታ ነባራዊ ዕውቀት የማከማቸት አዝማ
ሚያ ሲሆን፣ሁለተኛው ግን የመደቦችን ጥቅ
ም ምርኩዝ በማድረግ የሚካሔደው ርዕ
ዮተዓለማዊ የእውነታ ግንዛቤ ነው ። የመ
ጀመሪያው አዝማሚያ ኅብረተሰብ በአ
ጠቃላይ ለመኖር ሲል መረዳት ፣ ማ
ወቅ ያለበትን ነባራዊ ዕውቀት የመገብ
የት ዝንባሌን ሲያመለክት ፣ ሁለተኛው ዝን
ባሌ ደግሞ ፣ ከመደብ ጥቅም አንጻር ተነ
ስቶ እውነትን የማጣመምም ሆነ በትክክል
የመገንዘብን ሂደት ያቅፋል ። እነዚህ ሁለት
መሠረታዊ የግንዛቤ ዝንባሌዎች በኪነጥበባ
ዊ የእውነታ ግንዛቤም ውስጥ እንዳሉ (መ
ደብ እስካለ ድረስ) ማርክሲስቶች ይገነዘባ
ሉ። ይህንኑ በማስመልከት አቭኔር ዚስ የሚ
ባለው ጸሐፊ ሲያትት ፣ «የማርክሲዝም ሌኒ
ኒዝም ሥነውበት (Aesthetics) መሠ

Digitized by Google

ረታዊ መርህ ፣ ኪነጥበብ ማኅበራዊ ንቃተ
ሕሊና በመሆኑ እላይ የተመለከቱትን ሁለ
ት የግንዛቤ አዝማሚያዎች በዲያሌክቲ
ካዊ ውህድ በግልጽ ያሳያል ። ስለሆነም
ኪነ ጥበብ ሁለቱም ፣ ኪነጥበባዊ ግንዛቤና
ርዕዮተዓለም (Artistic cognition and
ideology) ነው ፤ »[6] ብሏል ። ይኸው ጸሐ
ፊ እነዚህን የማይለያዩ የኪነጥበብ መል
ኮችን መረዳት የኪነጥበብን ማኅበራዊ ባህሪ
ለመረዳት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነ
ዝባል ።

የኪነ ጥበብን ምንነት ለመረዳት ከየማዕ
ዘኑ መመልከትን ይጠይቃል ። ምክንያቱም
ኪነጥበብ በጣም ውስብስብና ብዙ ገጽታ
ያለው ክስተት በመሆኑ ነው ። ይህን የኪነ
ጥበብ ውስብስብነት በበለጠ ለመረዳት ቀለ
ል ካለው ምክንያታዊ አቀራረብ መነሳት
እንደሚያስፈልግ አዋቂዎች ይጠቁማሉ ።
መጽሐፍ ያነበበ ወይም ፊልም ወይም ጨ
ዋታ የተመለከተ ወይንም ሥዕል ያየ ማን
ኛውም ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ እነዚ
ህን የኪነጥበብ ምርቶች ከሶስት ማዕዘናት
አንጻር ይገመግማቸዋል።[7] አንደኛ ፣ በተ
መለከተው ወይም ባየው የተደሰተ ወይም
ያልተደሰተ ፣ የጣመው ወይም ያልጣመው
መሆኑን ፣ ሁለተኛ ፣ ይህ የተመለከተው ወ
ይም ያየው የኪነጥበብ ውጤት የሚገልጸው
ትክክል ወይም ሐሰት መሆኑን ፣ ሶስተኛ ፤
ይህ የተመለከተው የኪነጥበብ ምርት «ምን
ዓይነት አስተሳሰብ ፣ ስሜትና ሃሳብ እንደፈ
ጠረ » ፣ ይገመግማል ። እነዚህ የኪነጥበብ
ውጤቶች የመገንዘብ ፣ የመረዳት መልኮች
በሌላ አባባል ቢቀመጡ ፣ ማንኛውንም
የ ኪ ነ ጥ በ ብ ምርት ከሶስት ማዕዘናት
አንጻር ፣ «ከሥነ ውበታዊ ጠቀሜታው
(aesthetic value) ከትክክለኛነቱና ከር
ዕዮተ ዓለማዊ ይዘቱ » አንጻር ይገመ
ገማል ማለት ነው ። የኪነጥበብ ምሁራን
ኪነጥበብን በነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት
ሁኔታዎች አንጻር ማየቱ ትክክለኛ መሆ
ኑን ለማስገንዘብ ፣ « .,ኪነት በመሠረታዊ
ባሕሪው ይህም ማለት በተጨባጭነቱ የነኝ
ህ የሶስቱ ነገሮች፣ የስነ ውበት ፤ የትክክለኛ
ግንዛቤና የርዕዮተዓለም ውህድ በመሆኑ
ነው »[8] ይላሉ ።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ ላይሆን ይች
ላል ። በአንቬር ዚስ አቀራረብ ኪነጥበብ
ሁለት ነገሮች ማለትም ኪነጥበባዊ ግንዛ
ቤና ርዕዮተ ዓለም ነው ። በሌላ በኩል ደግ
ሞ ኪነጥበብ «የሥነውበት ፣ የትክክለኛነት
ግንዛቤና የርዕዮተ ዓለም ውህደት ነው ። »
የአንደኛው አቀራረብ ለኪነጥበብ (በዚህ
አንጻር)ሁለት ፈርጅ (ሥነውበትን በመተ
ው ይመስላል) አለው ሲል የሁለተኛው አቀ
ራረብ ግን ሶስት ፈርጅ አለው ስለሚል የት
ኛው ነው ትክክል ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።
የሁለቱም አቀራረብ ስህተት የለውም ።ምክ
ንያቱም ኪነጥበብ «የኪነጥበባዊ ግንዛቤና
የርዕዮተ ዓለም » ውህደት ነው ሲባል «ኪነ
ጥበባዊ ግንዛቤ» የሚለው ቃል የኪነጥበብ
ልዩ ባሕሪ የሆነውን ሥነውበትን ፣ ስለሚያ
ቅፍ ነው ። ስለሆነም ኪነጥበብ የነዚህ የሶ
ስት ባሕሪያት ዲያሌክቲካዊ ውህደት መሆ
ኑን ለየት ባለ መንገድ ለማቅረብ ተሞከረ
እንጂ በሁለቱም አቀራረብ የተተወ የኪነ
ጥበብ መሠረታዊ ባህሪይ የለም ።

ስለሆነም የኪነጥበብ ውስጣዊ ባሕሪ ከር
ዕዮተ ዓለም ተጽዕኖ ውጭ ሊሆን አይችል
ም ሲባል እንዲያው በዘፈቀደ ሳይሆን ከማ
ርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈሐሳብ አንጻር
የኪነጥበብ እውነታን በመመርመር ፣ በመ
ረዳትና በተጨባጭም የኪነ ጥበብን ታሪ
ካዊ ዕድገት በመገንዘብ ነው ። ጠቅለል ተደ
ርጎ ሲታይ ኪነጥበብ ከርዕዮተ ዓለም ጋር
በሁለት መንገዶች ግንኙነት አለው ማለት
ይቻላል ። አንደኛ ፣ ኪነጥበብ የተወሰኑ መ
ደቦች ልዩ ልዩ አመለካከቶች ማስተላለፊያ
መሣሪያ ነው ። የልዩ ልዩ መደቦች ፖለቲ
ካዊ ፣ ሥነምግባራዊ ፤ ሥነውበታዊ ፣ ፍል
ስፍናዊና የመሳሰሉት አመለካከቶች ከሚ
ሰራጩበትና ከሚተላለፉበት መድረክ አ
ንዱ ኪነጥበብ ነው ። ሁለተኛ ፣ ኪነጥ
በብ በራሱ ባሕሪም ርዕዮተዓለማዊ ነው ።
ምክንያቱም አንድ የኪነጥበብ ምርት በራ
ሱ እውነታን ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን ይህ
ንኑ እውነታ በሚመለከት የኪያኒውን አስ

Digitized by Google

ተሳሰብ ፣ ስሜት ፣ አመለካከት ፣ ፍላጐት ፣ አቋም ወዘተ ...አጣምሮ የሚገልጽ ነው። [9] በመደብ ሥርዓተ ማኅበራት ግለሰብ የግዴታ የዚህ ወይም የዚያ መደብ ወይም ማኅበራዊ ክፍል አባል እንደመሆኑ አስተሳሰቡ ፣ ስሜቱ ፣ አመለካከቱ ፣ ፍላጐቱ ፣ ዝንባሌው ወዘተ --- ከዚህ ወይም ከዚያ መደብ (ወይም ቅይጥ የመደብ ጠባይ ካላቸው ለምሳሌ ንዑስ ከበርቴ) አመለካከት ፣ አስተሳሰብ ፣ ፍላጐት ፣ ስሜት ወዘተ --- ተጽዕኖ ውጭ ሊሆን ከቶውንም አይቻለውም ።

የኪነጥበብ ሚና

ኪነጥበብ የሥነውበት ፣ የትክክለኛ ግንዛቤና የርዕዮተዓለም ውህደት ስለሆነና በተጨባጭና በሚታይ ምስል የሚቀርብ በመሆኑ የሰዎችን አእምሮ ለማነጽ ፣ ለማስተማር ታላቅ መሣሪያ ነው ። በኪነጥበብ አማካይነት ሰው መጥፎውንና ጥሩውን ፣ የሚበጀውንና የማይበጀውን ሊገነዘብና ሊያውቅ ይችላል። ኪነጥበብ በይዘቱ ርዕዮተዓለምን የሚያቅፍ ፣ የሚያራምድ በመሆኑ በመደቦች ትግል ውስጥ ከፍተኛ መሣሪያ ነው ። እንደሚያራምደው የርዕዮተዓለም ዓይነት ኪነጥበብ የተራማጅነት ወይም የአድኃሪነት ሚና ይጫወታል ።

ኪነጥበብ ወገናዊ ነው ። አንድ የኪነጥበብ ምርት ወይም ዘርፍ ፣ እንበል ሥነ ጽሑፍ የሰዎችን ስሜት ፣ ፍላጐት ፣ ምኞት ፣ ርዕዮተዓለምና ማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ያንጸባርቃል ። በኪነጥበብ ሥራ ውስጥ የሚንጸባረቅ አስተሳሰብ ከተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ፣ ከመደብ ፍላጐትና ዓላማ አንጻር የሚታይ ነው ። ለዚህ ነው ኪነጥበብ መደባዊ ነው ፣ ወገናዊ ነው የሚባለው ። በመደባዊ ኅብረተሰብ አንድ ከያኒ በኪነጥበብ ምርቱ ፣ ሰዎችን ያስተምራል ፣ ሰዎች አንድን ማኅበራዊ ክስተት ጐራ ለይተው (ወገናዊ ሆነው) እንዲያደንቁ ፣ እንዲደግፉ ፣ አለበለዚያ እንዲቃወሙ ፣ እንዲያፈርሱ ይጋብዛል ፣ ይቀሰቅሳል ። ከያኒው በአካባቢው ያለውን ማኅበራዊ እውነታ በሚመለከት የሚወስደው አቋም የሚወሰነው በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው መደባዊ ቦታ ወይም በቆመለት መደብ ጥቅም አኳያ ነው ። በተጨማሪም አንድ ከያኒ የብዙ መደብ ፍላጐቶችንም የሚያቅፉ ዥጉርጉርና የሚጋጩ አስተሳሰቦችንና ርዕዮተዓለሞችን የሚያንጸባርቁ የኪነ ጥበብ ምርቶች ሊያመርት ይችላል ። እዚህ ላይ ፍሬ ነገሩ መደብ እስካለ ድረስ የከያኒው የኪነጥበብ ምርት (ከአንድ በላይ የሆኑ መደቦችን ጥቅም በአንድ ወቅት ለማንጸባረቅ ቢችልም) በጠቅላላው ከመደባዊ አመለካከት ፣ ከወገናዊነት ውጭ ሊሆን አለመቻሉ ነው ። ይኸም ማለት መደብ እስካለ ድረስ የኪነጥበብ ምርት እውነታን የሚገነዘበው በመደብ መነፅር በመመልከት ነው ማለት ነው ። ስለዚህም ነው ኪነጥበብ የርዕዮተዓለም መሣሪያ ነው የሚባለው ።[10]

ኪነጥበብ በመሠረቱ የማኅበራዊ ግንኙነት ነጸብራቅ መሆኑን ከነማርክስ በፊት የነበሩትም ቁስ አካላዊ ፈላስፎች ተገንዝበውታል ። ይሁን እንጂ ማርክስና የማርክሲዝም ተከታዮች ብቻ ናቸው «በኪነጥበብ ውስጥ የሚንጸባረቀው እውነታ ፣ የሚወሰነው በመደቦች ጥቅም ፣ በመንግሥት ፣ በመደቦች የትግል ደረጃና በዚያም ኅብረተሰብ ውስጥ የበላይነት ባለው ርዕዮተዓለም መሆኑን »[11] ያስገነዘቡትና ለማብራራት የቻሉት ። ስለሆነም « በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ኪነጥበብ የርዕዮተዓለም ተሸካሚና አስተላላፊ መሣሪያ ነው የሚለው ሐሳብ የማርክሳዊ ሌኒናዊ የኪነጥበብ ጽንሰ ሐሳብ(conception) መሠረት ነው ። »[12]

« ኪነጥበብ ለኪነጥበብ ሲባል »

«ኪነጥበብ ለኪነጥበብ ሲባል» የሚለው ጽንሰ ሐሳብ «ኪነጥበብ በራሱ ለራሱ» ዓላማ ያለው ፣ ከየትኛውም መደባዊ ጥቅም ፣ የፖለቲካ እውነታ ፣ የርዕዮተዓለም ግጭት

Digitized by Google

«ነፃ» መሆን አለበት የሚል የቡርዧ አመለካከት ነው ። ለሐሳቡ አነሳስ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችልም በአጠቃላይ ሲታይ በአሁኑ ጊዜ አድኃሪ የሆነ የቡርዧ አመለካከት ነው ። ይህ አመለካከት በሥነ ዕውቀት (epistemology) አንፃር ሲታይ የኪነ ጥበብ አንድ ገጽታ የሆነውን ስነ ውበትን ከሌሎች የኪነ ጥበብ ገጽታዎች ነጥሎ በማየትና በማጋነን የሚከሠት ነው ። ታዲያ የኪነ ጥበብን አንድ ገጽታ ብቻ መውሰድና ሌሎችን የኪነ ጥበብ ገጽታዎች አለመገንዘብ ስሕተትና ሳይንሳዊነት የሚጎድለው ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ። ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው ሊያየው የሚችለውን እውነት ያጣመመ ኢሳይንሳዊ አቀራረብ ነው ።

« ኪነ ጥበብ ለኪነ ጥበብ ሲባል » የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ጉድኙነቱ የበለጠ የሚከሠተው በማኅበራዊ አንፃሩ (sociological aspect) ሲታይ ነው ። በዚህ አንጻር ሲታይ «ኪነጥበብ ለኪነጥበብ ሲባል» ማለት ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የኪነጥበብን የትግል መሣሪያነት ተረድቶና ተገንዝቦ እንዳይገለገልበት ማድረግ ነው ። ይህ አቋም በቅድሚያ ነቅቶ ኪነጥበብን ለመደብ ጥቅሙ ማስፋፊያነትና መጠበቂያነት በመጠቀም ላይ ካለው ከአድኃሪው የቡርዧ መደብ ጐን የሚሰለፍ ይሆናል ። ይህም በመሆኑ ነው ዛሬ ብዙ የለየላቸው አድኃሪ የቡርዧ ምሁራን ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብ ማናፈስ ሥራዬ ብለው የተያያዙት ። እነኚህ የቡርዧ ምሁራን ኪነጥበብ ሕዝቡን የማያገለግል ፣ የመደብ ትግልን የማያንጸባርቅ ፣ የጭቁኖችን ተስፋና ምኞት የማያቅፍ፣ ከማንኛውም የመደብ ጥቅም በላይ እንደሆነ አድርገው ያቀርቡታል ። ሐቁ ግን የዚህ ተፃራሪ ነው ።

በመደባዊ ኅብረተሰብ አንድ ከያኒ አወቀም አላወቀም ከመደባዊ አስተሳሰብ ውጭ ሊሆን አይችልም ። እንደሚታወቀው ያለ ሐሳብ ኪነጥበብ የለም ። ያለውስ

ጣዊ እምነትና ሐሳብ ከያኒ ኪነ ጥበብን ሊያመርት አይችልም ። የማናቸውም ከያኒ ሐሳብ ተጨባጭ ሁኔታን ፣ ምኞትን ፣ ፍላጎትን ፣ ሐሳብን ወዘተ - - - የሚገልጽ ሲሆን ፣ በመደብ ኅብረተሰብ እነዚህ ሁሉ መደባዊ ጸባይ አላቸው ። ስለሆነም ከያኒው ያመረተው ኪነጥበብ በባሕሪው የከያኒውን መደባዊ ስሜት ፣ ፍላጎትና ምኞት ማንጸባረቅና ለመደቡ ጥቅም ከመቆም ነፃ ሊሆን አይችልም ። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ከዚህ ውጭ የሆነ አጠቃላይ የኪነ ጥበብ ምርት ዘበት ነው ። ስለሆነም ኪነ ጥበብ በመደባዊ ኅብረተሰብ ከመደብ ውጭ ሊሆን አይችልም ። በተለይም ደግሞ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የመደቦች ትግል በየመስኩ ተፋፍሞ የሠርቶአደሩ ሕዝብ ትግል አሸናፊ እየሆነ በሔደበት በአሁኑ ጊዜ « ኪነ ጥበብ ለኪነ ጥበብ ሲባል » የሚለውም አባባል ትክክለኛ ያልሆነና የአድኃሪ መደብ ፍላጎትን የሚያራምድ ፣ ኪነ ጥበብ ጠንካራ የመደብ ትግል መሣሪያ መሆኑን የሚክድ ነው ።

ኪነጥበብ የመደብ ትግል መሣሪያና ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለምን ለማስፋፋት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በመገንዘብ ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት ለኪነጥበብ መስፋፋት ሰፊ በር ከፍቷል ። ኪነጥበብ አድኃሪን ሥርዓትን ለማፍረስና አዲስ ሥርዓትን ለመገንባት ትልቅ ሚና አለው ። ከዚህ ቀጥሎ ይህንን ሐቅ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለመገምገም እንሞክራለን ።

ኪነጥበብ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ

ጥንታዊ ሥልጣኔ ካበበባቸው አገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደመሆኗ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዥም ዘመን ሕልውናው ያካበተው የባህል ክምችት አለው ። ከዚህም የሕሊናዊ ባህል ክምችት መካከል አንደኛው ኪነጥበብ ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ የረዥም ዘመን ታሪክ ካላቸው የኪነ ጥበብ

Digitized by Google

ዘርፎች መካከል የሥነ ጽሑፍ ፣ የሙዚቃ ፣ የቲያትር ጥበቦች ይገኙበታል ። በተለይም ሥነ ጽሑፍ ከመካከለኛው ዘመንም በፊት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በጥንታዊ ዘመንም ጭምር « ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር የተረጋገጠ ነው ። » [13]

የቲያትር ሙያም እንዲሁ በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ እንዳለው ይነገራል ። ምናልባት በአክሱም ሥልጣኔ ጊዜና ከዚያም በኋላ በላስታ ዘመነ መንግሥትና በጐንደር ዘመነ መንግሥት ጊዜም በሰሜን ኢትዮጵያ የትያትር ጥበብ የታወቀ እንደነበረ የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ ።[14] በጐንደር ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ «ቤተ ቴአትር » ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አዳራሽ በጐንደር እንዳለ የታወቀ ነው ። ይሁንና የጊዜው የቴአትር ጥበብ በአብዛኛው በገዥ መደቦች አካባቢ የተወሰነ ነበር ። ለምሳሌ የጐንደሩ «ቤተ ቴአትር» ከጐንደር ነገሥታት አንዱ የነበረው ሳልሳዊ ዳዊት ራሱ በገና የሚደረድርበት ጭምር እንደነበረ ይነገራል ።[15] በላስታ ዘመነ መንግሥትም ጊዜ የነበሩት ከያንያን በንጉሡ የተደራጁና ለቤተ መንግሥት የሚያገለግሉ እንደነበረ ታሪክ ያወሳል ።

በቅርቡ ባለፈው የፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ እስከጀመረበት እስከ 1940ዎቹ ዓመታትና ከዘመናዊ ትምህርት መከሰት ጋር መጻሕፍት ፣ ሲኒማ ፣ ቲያትር ፣ ሙዚቃ ፣ ወዘተ ----- ከመስፋፋታቸው በፊት ፣ በተለይ ሥነጽሑፍና ሙዚቃ በሃይማኖት ሰዎች አካባቢ ብቻ ይካሔዱ ስለነበር ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የኪነ ጥበብ ዘርፎች በአብዛኛው ሃይማኖታዊና ሃይማኖት ነክ አመለካከቶችን ያዘሉና የፊውዳሉን ርዕዮተዓለም የሚያንጸባርቁ ነበሩ ።

ለምሳሌ ፣ በአብዛኛው በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የነበረው ሥነ ጽሑፍ ከሰፊው ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ የተገነጠለ ነበረ ። የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያን ስነ ጽሑፍ ባሕርያት የገመገመ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያብራራ ፣ «የመጻፍና የማንበብ ጥበብ እንደከፍተኛ ምሥጢር ተቆጥሮ የመላእክትንና የቅዱሳን እንዲያም ሲል የምድራዊ ገዥዎችን ማወደሻ ሆኖ ኖሯል ። ከቤተ ሃይማኖት ውጪ ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የሞከረ ሰው «መጽሐፍ ገላጭ» ወይም አስማተኛ ደብተራ እየተባለ ይጠራል ።» [16] ብሎ ነበር ።

በአጠቃላይ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ የኪነጥበብ ዘርፎች ውስጥ በአብዛኛው ይንጸባረቅ የነበረው የአድኃሪው የፊውዶ ቡርዧ መደብ ርዕዮተ ዓለም ነበር ። እንዲያም ሆኖ አድኃሪው የፊውዶ ቡርዧ መደብ ለኪነጥበብ መስፋፋትና ለከያኒያን እንክብካቤ ያደረገው አጥጋቢ ነገር አልነበረም ። እንዲያውም ለኪነጥበብ መስፋፋት ከፍተኛ ደንቃራ ሆኖ ነበር ። ኅብረተሰቡ ለኪነጥበብ ያለው አመለካከት የተሳሳተ እንዲሆን ፣ የኪነት ባለሙያዎች የተናቁና የተጠሉ እንዲሆኑ ሲያደርግ ቆይቷል ። ብዙ ከያኒያን በሙያቸው ምክንያት ሌላው ቀርቶ ጋብቻን ተነፍገው እንደነበረ ዛሬ በየአጋጣሚው ሁሉ በይፋ የሚናገሩት ሐቅና የቅርብ ትዝታ ነው ። ከያንያን በኪነጥበብ ምርታቸው ከሕዝቡ ጐን ለመቆም ቢሞክሩ የሚደርስባቸው በደልና ሥቃይ ከፍተኛ ነበር ። በፊውዶ ቡርዧ ኢትዮጵያ ሐቀኛ ከያኒያን የፊውዳሉ ሥርዓት ያቀረበላቸው ምርጫ ወይ ከፊውዳሉ ሥርዓት ጋር የሚጣጣም ኪነ ጥበብ ማምረት ፣ አለበለዚያም አርፎ መቀመጥ ነበር ። ከያኒያን እምቢ ብለው የጭቁኑን ሕዝብ የልብ ትርታና ፍላጐቱን የሚያንፀባርቅ ጽሑፍ ፣ ሥዕል ፣ ድራማ ትያትር ወዘተ --- ቢያቀርቡ ግን ወደ እሥር ቤት በመወርወር የቁም ሥቃይ እንዲያዩ ይደረግ ነበር ።

ይህም በመሆኑ በፊውዶ ቡርዧ ኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ዕድገት ታፍኖ የኪነጥ

Digitized by Google

በብ ባለሙያዎች እንዲጠሉ ተደርጓል ። እውነተኛ ኪነ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራ ገሸሽ ተደርጓል ። እንዲስፋፉ በር የተከፈተላት የፊውዶ ቡርዥውና የኢምፔሪያሊስት የኪን ጥበብ ምርት ነበር ።

በወደቀው የፊውዳል ሥርዓት ውስጥ የበላይነቱን ይዞ የነበረው የፊውዳሉ ርዕዮተ ዓለምና ኪነጥበባዊ ግንዛቤ ነው ቢባልም ምንም ዓይነት ሥርዓቱን ተቃዋሚና ተራማጅ ኪነጥበባዊ ምርት አልተከየነም ማለት አይደለም ። የተፈለገውን ያህል ለሰፊው ሕዝብ እንዳይዳረሱ የነበረው አድኃሪ ሥርዓት አፍኗቸው ነው እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ብሶት ፣ የሀገራችንን ኋላቀርነት ወዘተ - - - የሚገልጹ በምሁራን የቀረቡ የኪነ ጥበብ ምርቶች ነበሩ ።[17] ለምሳሌ ፣ ባለሥልጣናትና፣ የነሱም ጀሌዎች በሕዝቡ ላይ የሚያደርሱትን በደል ከሚገልጹ ግጥሞች መካከል አንደኛው ፡—

«ጊዜ ነው እንጂ ቁምነገራም
ባላባትነት አያኮራም» የሚል አንጋገር ነበር ።

በተጨማሪም ሰፊው ሕዝብ ለሀገሩ እየሠራ ፣ ምርት እያመረተና ከጠላት እየተዋጋ በትግሉ የተገኘው የሥራ ፍሬ ለጭቁን ሕዝብ ሳይሆን ለጥቂት መሳፍንትና መኳንንት ብቻ ይውል እንደነበረ በሙዚቃ ጭምር ተንፀባርቆ ነበር ።

«እምዩ ኢትዮጵያ ሞኝነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ ፤» የሚለው ግጥም የሚያመለክተው ይህንኑ ነበር ።

አድኃሪው የፊውዶ ቡርዧ መደብ ኪነጥበብን የርዕዮተ ዓለሙ ማሠራጫ አድርጎ ሲገለገልበት መቆየቱ ፣ የአድኃሪውም የፊውዶ ቡርዧ መደብ ርዕዮተ ዓለም ከታሪክ ሂደት ጋር ጨርሶ የማይጣጣም በመሆኑ ፣ የፊውዳሉ ሥርዓት ኪነጥበብ እውነታን ኪነጥበባዊ በሆነ መልክ ከማንፀባረቅ ፈንታ ፣ በማጣመምና በማደናገር ለአድኃሪው ሥርዓት እንዲያገለግል በማድረጉ የራሱን ውበትና ጣዕም አጥቶ ነበር ።

በአጠቃላይ በወደቀው ሥርዓት በኪነ ጥበብ መስክ ከፍተኛ የመደብ ትግል በግልጽም ሆነ በይፋ ተካሒዷል ። የአድኃሪው የፊውዶ ቡርዧ መደብ ጥቅሙን ለማስከበር ሲል ኪነጥበብ የከንቱ ርዕዮተ ዓለሙ ማስፋፊያ እንዲሆን አድርጓል ። በተለያዩ የኪነጥበብ ዘርፎች እንዲወደስ በማስገደድ እራሱን ሲያታልል ኖሯል ። በዚያውም አንፃር በስፋት ባይሆንም አንዳንድ በየወቅቱ የተነሱ ተራማጅ ግለሰቦች ወዘተ - - - ከፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበርና አቀንቃኞች ጋር የሚያደረገውን ትግል በኪነጥበብ መስከም አካሒደዋል ። ይህም በተውኔት ፣ በግጥም፣ በሙዚቃና በመሳሰሉት የኪነጥበብ ዘርፎች ይንፀባረቅ እንደነበር ይታወሳል ። ይህ ለብዙ ዘመን ታፍኖ ፈራ ተባ በማለት ሲከሰት የነበረው ተራማጅ የነበረ የኪነጥበብ አዝማሚያ ታላቁ የየካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት ሲፈነዳ በይፋ ወጥቶ በአድኃሪው ኪነጥበብ ላይ የበላይነቱን ለማስፈን በመታገል ላይ ይገኛል ።

ኪነጥበብ በአብዮቱ ሂደት

አንድ ማኅበራዊ አብዮት ሥር ነቀልነቱ የሚለካው በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን የምርት ግንኙነት ለማንኮታኮት በመቻሉ ብቻ ሳይሆን ፣ ለዚሁ የምርት ግንኙነት ዕድሜ መራዘም ህሊናዊ ሁኔታዎችን ሲያመቻች የነበረውን አድኃሪ ርዕዮተዓለምና ከዚሁ ርዕዮተዓለም ጋር የተቆራኙ የማኅበራዊ ንቃተ ሕሊና ቅርጾችን ለማዳከምና በምትካቸውም አዲስ ርዕዮተዓለምና አዲስ ፖለቲካ ፣ አዲስ ሥነ ምግባር ፤ አዲስ ኪነጥበብ እንዲያቆጠቁጥና እንዲበለጽግ ለማድረግ በመቻሉም ጭምር ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ሥር ነቀል አብዮት እንደመሆኑ ፣ በቅድመ አብዮት በአብዛኛው የፊውዶ ቡርዧ መደብ ጥቅም አና ፋሽና አራማጅ የነበረውን ኪነጥበብ ነፃ አውጥቶታል ለማለት ይቻላል ። ድኅረ አብ

Digitized by Google

ዮት ኪነጥበብ በሙዚቃው ፣ በቲያትሩ ፣
በሥዕሉ ፣ በሥነጽሑፍ ፣ በቅርፃቅርጽ ፣
ወዘተ - - - ዘርፎች ሁሉ ሰፊው ሕዝብ በፖ
ለቲካ ፣ በወታደራዊ ፣ በኢኮኖሚና በማኅ
በራዊ ትግሎች ያገኛቸውን ድሎች የሚያ
ንፀባርቅ ፣ ሕዝቡን ለበለጠ ትግልና ድል
የሚቀሰቅስ ፣ እግረ መንገዱንም የአብዮቱ
ፈር ቀዳጅ የሆነውን ርዕዮተዓለም በስፋት
በሰፊው ሕዝብ ውስጥ እንዲሠርፅ በማድ
ረጉ በኩል የሚጫወተው ሚና በጣም ከፍ
ተኛ ነው ። በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የኪነ
ጥበብ ምርት የጥቂት በዝባዦች መገልገያ
መሆኑ ቀርቶ ብዙኃኑ የኪነጥበብ ም ር ት
ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ በመፈጠር
ላይ ነው ።

አብዮቱ አሁን በደረሰበት የእድገት ደረጃ፣
ለፓርቲ ምሥረታ ፣ ለኢኮኖሚ ግንባታና
ለሀገር መከላከል በመካሔድ ላይ ባለው
ትግል ሠርቶአደሩ ሕዝብ የርዕዮተዓለም
ትጥቁን በየጊዜው እንዲያጠናክር ፣ የሥራ
ምርታማነቱን እንዲጨምርና አብዮታዊት
እናት አገሩን ከማናቸውም ጥቃት ለመከላ
ከል ዝግጁ ሆኖ እንዲጠባበቅ በማድረጉ
ረገድ የተለያዩ የኪነጥበብ ዘርፎች የሚጫ
ወቱት ሚና ከፍተኛ ነው ። በተለይ ደግሞ
የፊውዳሉን ርዕዮተዓለም ቅሪቶች ደረጃ
በደረጃ ለማጥፋትና ለማሌ ርዕዮተዓለም
መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ለሚፈጥረው ለባ
ህል አብዮት ግብ መምታት የአብዮታዊ ኪነ
ጥበብ መዳበር አስፈላጊ ነው ። አብዮታዊ
ኪነጥበብ ሊዳብር የሚችለው ደግሞ ብቃ
ቱን በማጠናከር ፣ ያለውንና ጉልቶ የሚታ
የውን ደጋግሞ በማቅረብ ሳይሆን ፣ በፈጠራ
ላይ የተመሠረተ የኪነጥበብ ምርትን በማ
ምረት ነው ። በኪነጥበብ ዘርፍ ብቃት የሚ
ለካው ደግሞ « - - - ከያኒው የኑሮን መሠ
ረታዊ መርሆዎችና አዝማሚያዎችን በምን
ያህል ጥልቀትና ስፋት እንዳዳበራቸው ፣ ስሜ
ቱንና አመለካከቱን በምን ያህል ግልጽና
በማያሳምን ሁኔታ በማቅረቡ ነው ።» [18]
አብዮታዊ ኪነጥበብን ለማዳበር ሌላው የሚ
ያስፈልገው ነገር ወገናዊነትን ማጠናከር
ነው ። «የኪነጥበብን ርዕዮተዓለማዊ ገጽታ
መካድ የሁለቱንም-የኪነጥበብንና የርዕዮተ
ዓለምን መስኮች በጣም ማጥበብ ነው ። [19]
ሳያስብ ፣ ሳይወጥን ፣ በርዕዮተዓለም አን
ፃር ነገሮችን ሳይገነዘብ እንዲያው በደፈናው
በመገፋፋት (emotion) የሚጽፍ ደራሲ
ካለ ይህ «ደራሲ» እንደዕብድ ሊቆጠር የሚ
ችል ነው ። [20] ነገሮችን በትክክል ሳይገነዘብ
ሳያብላላና የተወሰነ ርዕዮተዓለማዊ አመለ
ካከት ሳይኖረው እንዲያው በስሜት ብቻ
በመነሣሣት የሚጽፍ (የሚጽፍ ከማለት
ይልቅ የሚለቀልቅ ማለቱ ሳይሻል አይቀ
ርም) ደራሲ ፣ ማኅበራዊንና ሕሊናዊ ክስተ
ቶችን በትክክል ተገንዝቦና በአእምሮው
አጣጥሞ አቋም በመውሰድ በፈጠራ ሥራው
አስተያየቱን ፣ ዳኝነቱንና ፍላጎቱን በሚገባ
ሊያንፀባርቅ አይችልም ።

ኪነጥበብ የርዕዮተዓለም መሣሪያ ስለመ
ሆኑ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ትኩረት በመ
ስጠት ለማብራራት ሞክረናል ። በተጨማ
ሪም ይኸው ሁኔታ በቅድመ አብዮት ኢት
ዮጵያ በገሀድ የታየ ነገር እንደሆነም ለማ
መልከት ተሞክሯል ። ኪነጥበብ ከርዕዮተ
ዓለም ብቻ ሳይሆን ፣ የርዕዮተዓለም ዋንኛ
ዘርፍ ከሆነው ከፖለቲካም ጋር የቀረበ ግን
ኙነት ያለው በመሆኑ ይህን በሚመለከት
አንዳንድ ነጥቦችን በተጨማሪ ማንሣቱ
ጠቃሚ ይመስላል ።

የመደብ ትግል በተፋፋመ ቁጥር የኪነ
ጥበብና የፖለቲካ መቀራረብ ከፍተኛ ነው።
በሀገራችንም ይህ ሀቅ ጉልቶ ታይቷል ።
የመደብ ትግሉ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ፣
በኢምፔሪያሊዝም አነሣሽነት የሱማሌ አድ
ኃሪ መንግሥት አገራችንን በወረረበት ጊዜና
የውስጥ አድኃሪዎች በተለይም ኢድህና ኢሕ
አፓ ነጭ ሽብርንና የኢኮኖሚ አሻጥርን በሰ
ፊው በተያያዙበት ጊዜ ኪነጥበብ በፖለቲ
ካ ሥራ ላይ በይበልጥ በማተኮር የፖለቲካ
ቅስቀሳ ያካሒድ እንደነበር ይታወሳል ።
ታዲያ ከዚህ ሀቅ ተነሥቶ ኪነጥበብ ፖለቲ

Digitized by Google

ካዊ ነው ፣ ወይም ኪነጥበብ በቀጥታ ስለፖለቲካ ብቻ ማውሳት አለበት ከተባለ ደግሞ ስሕተት ይሆናል ። ይሁንና ዛሬ ለነፃነት ፣ ለሰላም ፣ ለፍትሕ የሚደረገው እንቅስቃሴ የማይመለከተው ከመደቦች ጦርነት ነፃ የሆነ ቡድን ወይም ግለሰብ አይገኝም ። ስለሆነም ይህንን ሁለንታዊ እውነታ የማያንፀባርቅ ኪነጥበብ ከኅብረተሰብ ፍላጎትና ምኞት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ያስቸግራል ። ዛሬ «ፖለቲካ» በሚለው ቃል ቅጽል የሚጀመሩ ድራማዎች ፣ ሲኒማዎች ፣ ቲያትሮች ሥዕሎች ፣ ሥነጽሑፎችና የመሳሰሉት የኪነጥበብ ምርቶች በሰፊው እየተመረቱ ነው። ይህ የኪነጥበብንና የፖለቲካን ግንኙነት በግልጽ የሚያሳየን አንድ ምሳሌ ነው።ኪነጥበብና ፖለቲካ ግንኙነት አላቸው ሲባል ግን ከዚህ በላይም ይሔዳል ።

ስለማንኛውም የጊዜያችን አንገብጋቢ ችግሮች የሚያወሳ ኪነጥበብ ፖለቲካዊ ነው ።[21] እዚህ ላይ ፍሬ ነገሩ በቀጥታ ፖለቲካ የሚለውን ቅጽል መያዙ ወይም በቀጥታ ስለፖለቲካ ማውሳቱ አይደለም።ምክንያቱም እነዚህ አንገብጋቢ ችግሮች ከፖለቲካ ማለትም ፣ ከመደቦች ፣ ከብሔረሰቦች፣ ከመንግሥታትና ከመሳሰሉት የማኅበረሰብ ቡድኖች መሠረታዊ ጥቅም ፍጹም ነፃ ሊሆኑ አይችሉምና ። በተጨማሪም የአንድ የኪነጥበብ ምርትን ተራማጅነት ፣(የፖለቲካ ተግባሩን) የሚወስነው ኅብረተሰብ የገጠመውን ችግር በትክክል በመመልከትና የኅበረተሰብን እውነተኛ የእድገት አቅጣጫ በማሳየቱ ነው ።አንድ በዚህ ርእስ ላይ ጥናት ያካሔደ ጸሐፊ እንዳስገነዘበው «የኪነጥበብ ተራማጅነት ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ትርጉም የሚወሰነው በኪነጥበቡ ሀቀኛነት ፣ በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ የሚታዩትን መሪ አዝማሚያዎች በሚያሳምን መልክ በማንፀባረቁና በመግለጹ ነው ። »[22]

ከዚህ አጠቃላይ የኪነጥበብ አመለካከት በመነሣት በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት ከደረሰበት የእድገት ደረጃና ከሚከተለው የእድገት ፈለግ አንፃር ፣ በሕዝባዊ አብዮቱም ውስጥ ከሚጫወተው ከፍተኛ ሚና አንፃር ፣ የኪነጥበብ ፖሊሲውን አቅጣጫን መገምገሙ አስፈላጊ ይሆናል ።

እንደሚታወቀው አሁን ያለንበት ወቅት ለሶሻሊዝም ግንባታ ቁሳዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች የሚዘጋጁበት ቅድመ ሶሻሊስት የሆነ የሽግግር ወቅት ነው ። ስለሆነም ፣ በዚህ ወቅት የኪነጥበብ አቅጣጫን ለመገምገም የሽግግር ወቅቱን አጠናቀው ሶሻሊዝምን በገነቡ አገሮች ውስጥ ኪነጥበብ ከደረሰበት ደረጃ አንፃር የሽግግር ወቅት ኪነጥበብን መዳሰስ ያስፈልጋል ።

ለመንደርደሪያ ያህል ግን በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ የኪነጥበብ መመሪያ የሆነውን የሶሻሊስት እውነታነትን ምንነት ለመገምገም እንሞክራለን ። በኪነጥበብ ዘርፍ እውነታነት(Realism)ሲባል ፅንሰ ሐሳቡ በልዩ ልዩ የኪነጥበብ የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ነባራዊ እውነታን (Objective Reality) በትክክል የማንፀባረቅ ባሕሪን የሚያመለክት ነው ። ኪነጥበባዊ እውነታነት የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን አልፏል ።እነሱም ሮማንቲክ እውነታነት ፣ ሂሳዊ እውነታነትና ሂሳዊ እውነታነትን በመተካት በታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት አማካይነት የተከሰተው ሶሻሊስት እውነታነት ናቸው። እነዚህ ሁሉ የኪነጥበብ እውነታነት ዓይነቶች ተጨባጭ ሁኔታውን ፣ ነባራዊ እውነታን የማንፀባረቅ ባሕሪ ስላላቸው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ፣ የእውነታን ውስጣዊ ይዘት ለመገንዘብ ባላቸው ችሎታ ፣ በኪነጥበባዊ የፈጠራ ዘዴያቸውና በታሪካዊ አመጣጣቸው ይለያያሉ ።

ሮማንቲክ እውነታነት በ1820 እና በ1830ዎቹ አካባቢ በአውሮፓ ውስጥ የተከሰተ የኪነጥበብ የፈጠራ ዘይቤ ሲሆን ፣ በወቅቱ ከፈረንሳይ የቡርዧ አብዮት በኋላ በአውሮፓ

Digitized by Google

ውስጥ ተስፋፍቶ የነበረውን የፀረ ፊውዳል ትግል በማገዝ ፣ ፊውዳሉም ሆነ ቡርዧው በሠርቶአደሩ ሕዝብ ላይ ያደርሱ የነበረውን ግፍ በማጋለጥና የሕዝብን ቅሬታ በማስተጋባት በአውሮፓ አገሮች ውስጥ በወቅቱ የነበረውን የመደብ ቅራኔ በመጠኑም ቢሆን የተረዳ የኪነጥበብ የፈጠራ ዘዴ ነው። ሆኖም ግን ተምኔታዊና የትራጀዲ ባሕርያት ጐልተው የሚታዩበት ፣ በካፒታሊዝም ላይ ያካሔድ የነበረው ሂስ (በወቅቱ የካፒታሊዝምን ተራማጅ ባሕርያት በሚገባ ያልተረዳ በመሆኑ) በፈጠራ ሥራው ወደኋላ ተመልሶ የመካከለኛ ዘመን አስተሳሰቦችን ናፋቂ የነበረ የኪነጥበብ ዘይቤ ነው ።

ሂሳዊ እውነታነት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የተከሰተና በዘመነ ካፒታሊዝም የነበሩ ተራማጅ የኪነጥበብ ሰዎችን ያሰባሰበ የኪነጥበብ ዘይቤ ነው።የዚህ የኪነጥበብ ዘይቤ ዋና ትኩረት የካፒታሊስት ሥርዓትን ማጋለጥ ሲሆን ፣ በተጨማሪም በዚሁ ኅብረተሰብ ውስጥ ያሉት ፊውዳሎች ፣ ቀሳውስትና ቢሮክራቶች በሕዝብ ላይ የሚያደርሱትን ግፍና በደል ያጋለጠ፣ የሕዝብን ተቃውሞ ያንፀባረቀና የሚያንፀባርቅ የኪነጥበብ ዘይቤ ነው ። ይህንን ሚናውን ለመጫወትም ጭቆናን የሚቃወሙ ኃይሎችን ለምሳሌ የሠራተኛውን፣የተራማጅ ምሁሩን ወዘተ - - - ገጸ ባሕሪ በመውሰድ የጭቁኑን ሕዝብ አስቃቂ ኑሮና የሚደርስበትን በደል አንፀባርቋል ። ከሂሳዊ እውነታነት የበለጠ የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ የተረዳና በፈጠራ ዘዴውም ከፍ ያለ ኪነጥበባዊ እውነታነት ሶሻሊስታዊ እውነታነት ነው ።

ሶሻሊስታዊ እውነታነት የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሳይንሳዊ የሆነ የኪነጥበብ መመሪያ ሲሆን ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሟላ መልኩ ህልውናውን ያገኘው በሶቭዬት ኅብረት የሽግግር ወቅት ተከናውና ለሶሻሊዝም ጠንካራ መሠረት በተጣለበት በ1930ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ላይ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የዳበረ ሶሻሊዝም በተገነባባቸው አገሮች ሁሉ ሥር የሰደደ የኪነጥበብ መመሪያ ሲሆን ሶሻሊዝም ዓለምአቀፋዊ ሥርዓት በመሆኑ ሶሻሊስት እውነታነት በሌሎችም አገሮች ውስጥ ለሚገኙ ተራማጅና አብዮታዊ የኪነጥበብ ሰዎች መመሪያ ሊሆን በቅቷል ።

ከሶሻሊስት እውነታነት መርሆዎች መካከል ጥቂቶቹ ፦

—እውነታን በማንፀባረቅ ረገድ የተሟላ መሆኑ ፤

—የጠነከረ ወገናዊነቱና ለሠራተኛው መደብ ጥቅም የቆመ መሆኑን ይፋ በማውጣት በሚያሳየው ሀቀኝነቱ ፤

—የሕይወት ፎቶኮፒ ሳይሆን በሕይወት ሀቅ ላይ የተመሠረተ ለአእምሮና ለስሜት ተቀባይነት ያለው ፣ በይዘቱና በቅርጽ ውበት ፣ ጥራት ፣ ጥልቀት ፣ ወዘተ - - - ሀቀኛ የፈጠራ ሥራ መሆኑ ፤

—የሕይወትን ልዩ ልዩ ገጽታ ሲገመግም አስከፊውንና አሳዛኙን ወይም ደግሞ አስደሳችን ብቻ በማንፀባረቅ የሚወሰን ሳይሆን ፣ የሕይወትን ሀቅ ቁልጭ አድርጎ በማሳየት ለእድገትና ለለውጥ የሚያበቃ መሆኑ ፤

— የሠርቶ አደሩን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት በሥራ ወዳድነትና ምርታማነት፣ በሶሻሊስት አርበኝነትና በወዝአደራዊ አለምአቀፋዊነት ፣ በማሌ ርእዮተዓለምና በኮሚኒስታዊ ስነ ምግባር ወዘተ - - - ለማነጽ የተነሳ መሆኑ ፣

— ብሩህ ተስፋ ፈንጣቂና የሕዝብ አገልጋይ መሆኑ ወዘተ - - ይገኙበታል ።[23]

የሶሻሊስት እውነታነትን መመሪያው ያደረገ ኪነጥበብ የሰው ልጅ በረዥም ጊዜ ታሪኩ ያፈራቸውን ተራማጅ የኪነጥበብ ሥራዎች በቅርስነት የሚወርስና ሁልጊዜም ቢሆን እራሱን በአዲስና ከፍተኛ የፈጠራ ሥራ የሚያበለጽግ ነው ። የሶሻሊስት ኪን

Digitized by Google

ጥበብ የሕዝብና ለሕዝብ የቆመ በመሆኑ ከሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ ከፍተኛ ነው ። ሌኒን ይህንን ሁኔታ ሲገልጽ ፣

> «ኪነጥበብ የሕዝብ ነው ። የኪነጥበብ መሠረት በሕዝብ ውስጥ መጠናከር አለበት ። ኪነጥበብ ሰፊው ሕዝብ የሚረዳውና የሚወደው መሆን አለበት ። ኪነጥበብ የሰፊውን ሕዝብ ስሜት ፣ አስተሳሰብና ምኞት የሚያስተባብርና ከፍ የሚያደርግ መሆን አለበት ፤» [24] ብሎ ነበር ።

ከዚህ በላይ ባጭሩም ለመዳሰስ የተሞከረው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ የኪነጥበብ መመሪያ የሆነውን ሶሻሊስት እውነታነትን ሲሆን ፣ የሶሻሊስቱን የእድገት ፈለግ በሚከተሉና ለሶሻሊዝም ግንባታ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ባሉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የኪነጥበብ አቅጣጫ በሚመለከት ደግሞ አንዳንድ አስተያየቶች መሰንዘር ያስፈልጋል ።

እንደሚታወቀው የሽግግር ወቅት ቅይጥ የኤኮኖሚ ይዞታዎችን ያቀፈ በመሆኑ የቡርዧው መደብ ፣ የሠራተኛው መደብና ፣ የንዑስ ከበርቴው መደብ በአንድ ላይ የሚገኙበት ሁኔታ ነው ። ይህ ቅይጥ የሆነ የሶሺዮ ኤኮኖሚ ይዞታና የእነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መደቦች መኖር ቅይጥ ለሆነ የኅሊናዊ አመለካከት ፣ ከአንድ በላይ ለሆኑ ርዕዮተዓለሞችና ብሎም ወደ ተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ ፣ ቅይጥ ለሆነ ኪነጥበብ መኖር ምክንያት ይሆናል ።

ሌላው የሽግግር ወቅት ዓይነተኛ ጠባይ እነዚህ የተለያዩ ኤኮኖሚያዊ ግንኙነቶች መኖር ብቻ ሳይሆን ፣ በግል ይዞታውና በማኅበራዊ ይዞታው መካከል ፣ በቡርዧው መደብ አድኀሪ ርዕዮተዓለምና በሠራተኛው መደብ አብዮታዊ ርዕዮተዓለም መካከል ለበላይነት የሚካሄደው ትግል የተፋፋመ መሆኑ ነው ። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት የፖለቲካ ሥልጣን የመላ ሠርቶአደር ሕዝቦችን ጥቅም የሚያንፀባርቅ ቢሆንም፣ በኢኮኖሚውም መስክ አብዛኛውን ሕዝብ የሚያቅፍ የአነስተኛ ሸቀጥ ምርት (የንዑስ ከበርቴ ምርት) በስፋት መኖር ፣ የሠርቶአደሩ ሕዝብ ባህል ኋላቀርነት ይህንንም መሠረት በማድረግ የሚነሳው የአድኀሪው ሥርዓት ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት በስፋት መኖር ፣ በሽግግር ወቅት በኪነጥበቡም ዘርፍ አቅጣጫውን በውል ለይቶ የማያውቅ ፣ የተዘበራረቀ ፣ ከአንዱ ርዕዮተ ዓለም ወደሌላው የሚዋልል ባጭሩ ቅይጥ የሆነ ርእዮተ ዓለማዊ አመለካከት መኖሩን ያመለክታል ።

ይህ ደግሞ በኪነጥበቡ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ፣ በፖለቲካውም ዘርፍ ያለ ነገር ነው። አነስተኛ የሸቀጥ ምርት በተንሰራፋበትና በመሆኑም የንዑስ ከበርቴው መደብ በስፋት የሚገኝበት አገር በአብዮት ሂደት ውስጥ ሲገባ፣ለማሌ ርዕዮተዓለም እድገትና መስፋፋት ከፍተኛ እንቅፋት የሚፈጥረው ይኸው ከንዑስ ከበርቴው መደብየሚመነጨው ቅይጥ ርዕዮተዓለም ነው።በተለይ የሶሻሊስት የእድገት ፈለግን የሚከተሉ አገሮች በሚያካሂዱት የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው አነስተኛ ሸቀጥ አምራች የሆነው የንዑስ ከበርቴው መደብ እንደመሆኑ ፣ ይህ መደብ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት ባለው ፀረ ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት አቋም ተራማጅ የሆነ ሚና የሚጫወት ነው። የመደብ ጥቅሙ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚጋጭ መሆኑ ከሠራተኛው መደብ ጥቅም ብሎም ከሠራተኛው መደብ ርዕዮተዓለም ጋር የሚያስማማው ሁኔታ ሲፈጥር ፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እየገፋ በሄደ ቁጥር ደግሞ የዚህ መደብ ሌላው

Digitized by Google

ገጽታ የሆነው አድኃሪና ኋላቀር አመለ
ካከት እየጐላ ይመጣል ። እንደሚታወ
ቀው አብዮትም ሆነ ማናቸውም ነገር ቋሚ
ነገር አይደለም ፣ ይንቀሳቀሳል ። ሌኒንም
እንዳለው በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብ
ዮትና በሶሻሊስት አብዮት መካከል የተገ
ነባ ግንብ ባለመኖሩ ብሔራዊ ዲሞክራሲያ
ዊ አብዮት እየገፋ ሲሄድ የንዑስ ከበርቴው
መደብ ተራማጅነት እየቀነሰ ይመጣል ።

የሶሻሊስትን የእድገት ፈለግ የሚከተሉ
አገሮች በሚያካሂዱት የብሔራዊ ዲሞክ
ራሲያዊ አብዮት ካፒታሊዝምን ዘለው ለሶ
ሻሊዝም ግንባታ ሁኔታዎችን ለማመቻ
ቸት በሚያካሂዱት ከባድ ትግል ከፍተኛ
ና ውስብስብ የሆነ ችግር የሚፈጠረው የአ
ነስተኛ ሸቀጥ ምርትን (የንዑስ ከበርቴ
ውን መደብ) ወደ ሶሻሊስት ምርት የመለ
ወጡ ሂደት ፣ የንዑስ ከበርቴውን መደብ
ወደሠራተኛ መደብ የመለወጡ ሂደት ፣
የንዑስ ከበርቴውን አመለካከት ወደሠራ
ተኛው መደብ አመለካከት የመለወጡ
ሂደት ነው ። ይህ ደግሞ ለረዥም ጊዜ የሚ
ካሄድ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ትግ
ልን የሚጠይቅ ነው ። ሌኒንም እንዳለው
«- - -አነስተኛ የሸቀጥ ምርት ዘይቤ ካፒ
ታሊዝምንና ቡርዧውን በተከታታይ ፣
በየቀኑና በየሰዓቱ ግብታዊ በሆነ መን
ገድ በተስፋፋ ሁኔታ እንዲያቆጠቁጥ »[25]
ስለሚያደርገው ፣ ይህን ሂደት በመግታት
የንኡስ ከበርቴውን መደብ ቁሳዊ ሕይ
ወት መለወጥ ያስፈልጋል ። ይህም ከሆነ
በኋላ የሰዎች አመለካከት ወዲያውኑ ሊጠፋ
የሚችል ስላልሆነ የንዑስ ከበርቴውን
ኋላቀር የሆነ ፣ ለብዙ ጊዜ ከግል ሃብት
ይዞታ ጋር ተጣብቆ ከመኖሩ የሚመነጨውን
የግለሰበኝነት አመለካከት ለማጥፋትና የን
ቃት አድማሱን ለማዳበር ያላሰለሰ የርዕ
ዮተዓለም ትግል ማካሄድን ይጠይቃል ።
ሌኒን ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ ሲጽፍ

«- - ንኡስ ከበርቴው ባጠቃላይ በወ
ዝአደሩ የበላይ ገዥነት ጊዜም በመ
ካከል ላይ የመዋለል ሁኔታ ያሳያል።
በአንድ አንፃር ስናየው ከመሬት ከበር
ቴውና ከካፒታሊስቱ ነፃ ለመውጣት ባ
ለው የአላማ ተመሳሳይነት የተባበረ ፣
በጣም ሰፋ ያለ ፣ ጥሮ ግሮ የሚበላ የሕ
ዝብ ክምችት ነው ። በሌላው አንፃር
ስናየው ደግሞ የተበታተኑ ትናንሽ
ባለሙያዎችና አነስተኛ የሀብት ባለ
ቤትነት ያላቸውን (የገበሬውንና የእደ
ጥበብ ሠራተኛውን) አነስተኛ ነጋ
ዴዎችን ያጠቃልላል ። ይህ ዓይነት
የኤኮኖሚና የኑሮ ሁኔታ በወዝአደ
ሩና በካፒታሊስቱ መካከል እንዲዋ
ልል ያደርገዋል።በነዚህ መደቦች (በወ
ዝአደሩና በካፒታሊስቱ) መካከል
የሚካሄደው ትግል እየከረረ በሚመ
ጣበት ጊዜ ፣ ፈጣን በሆነ መንገድ
ማኅበራዊ ግንኙነቶች እየፈራረሱ
በሚመጡበት ጊዜ ፣ ... ንኡስ ከበ
ርቴው ባጠቃላይ ከድሮው ሁኔታ
በተሉ ያለመላቀቅ ጠባዩን በምንገ
መግምበት ጊዜ ከአንዱ መደብ ወደ
ሌላው መደብ ሲንገዋለል ብናገኘው
የሚያስገርም አይሆንም . . . ይህን
መደብ (ንኡስ ከበርቴውን) በማስመ
ልከት ወዝአደሩ የሚኖረው ተግ
ባር አመራር በመስጠት ተፅዕኖውን
ለማጥበቅ መጣር ነው ፣ »[26] ያለው
ለንኡስ ከበርቴው መደብ ርእዮተ
አለማዊ ግንዛቤ ቅይጥነት መሠረቱ ምን
እንደሆነ ለመጠቆም ነው ። በዚህ ጽሑ
ፍ መጀመሪያ ላይ ማኅበራዊ ንቃተሕሊና
በማኅበራዊ ሕልውና ላይ እንደሚመሰረት
ለማሳየት የተሞከረውም በተለይም የን
ዑስ ከበርቴውን ርዕዮተዓለማዊ ግን
ዛቤ ፣ ርዕዮተዓለማዊ ግንዛቤውም የሚን
ፀባረቅበትን የኪነጥበብ ዘርፍ በሚመ
ለከት ላለው ውዥንብርና መዋለል መሠ
ረቱን ለመጠቆም ነው ።

እርግጥ በኪነጥበቡ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራ
ተኞች በኅብረተሰብ ውስጥ በሌሎችም

Digitized by Google

የአእምሮ ሥራ መስኮች እንደተሰማሩ
ሠራተኞች ሁሉ በመደብ ሳይሆን በማኅ
በራዊ ክፍልነት የሚመደቡ ቢሆንም ፥
በተለይ ኋላቀር በሆኑ አገሮች የዚህ
ማኅበራዊ ክፍል አባላት በአብዛኛው
ከንዑስ ከበርቴው መደብ (ከገበሬው
ከእደጥበብ አምራቹ ፥ ከአነስተኛ ነጋ
ዴው) የሚመነጩ እንደመሆናቸው ሳይ
ንሳዊውን የማሌ ርዕዮተዓለም ተቀብ
ለው የሕይወት መመሪያቸው እስከአላደ
ረጉ ድረስ ፥ የሚኖራቸው ርዕዮተዓለም
ም ሆነ የሚከተሉት ፖለቲካዊ አመለካ
ከት (በኪነጥበብ ዘርፍ የተሰማሩ ከሆኑም
በኪነጥበብ ሥራቸው የሚያንፀባርቁት
ርዕዮተዓለም) ከንዑስ ከበርቴው መደብ
ርእዮተዓለማዊ ተጽዕኖ ነፃ ሊሆን አይ
ችልም ።

በሀገራችንም ተጨባጭ ሁኔታ ከአብ
ዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ለተራማጅና አብዮ
ታዊ ኪነጥበብ መስፋፋት አመች ሁኔታ
በመፈጠሩ ፥ አብዮታዊ ኪነጥበብ የተስ
ፋፋ ቢሆንም ፥ አሁንም ከፊውዳሉ መደብ
አድኃሪ የርዕዮተዓለም ተጽኖ ያልተላቀቀ ፥
በቡርዧው ርዕዮተዓለም የተበከለ ፥ በሠራ
ተኛው መደብ ርዕዮተዓለምና በቡርዧው
መደብ ርዕዮተዓለም መካከል የሚዋልል
ዥጉርጉር የሆነ የኪነጥበብ ምርት አለ ።
ይህ ደግሞ ለምን ሆነ ለማለትም አይቻ
ልም ፥ ምክንያቱም ቀደምሲል እንደተጠ
ቀሰውም ተጨባጩ ሁኔታ የተለያዩ መደቦ
ችንና ርዕዮተዓለሞችን ያቀፈ በመሆኑ ነው።
በመሆኑም ከአብዮቱ ወዲህ የማሌን ርዕዮ
ተዓለም በመቀበል በመጠኑም ቢሆን ሶሻ
ሊስት እውነታነትን መሠረት በማድረግ
የተዘጋጁ የኪነጥበብ ምርቶች የመኖራቸው
ውን ያህል ፥ የተራማጅነት ባህሪ ቢኖራቸ
ውም ከቡርዧው የርዕዮተዓለም ተፅዕኖ
ያልተላቀቁ የኪነጥበብ ምርቶችም አሉ። እን
ነዚህ ያሉ የኪነጥበብ ምርቶችን ለመቀ
ነስ ማኅበራዊ መሠረት ሆኖ የሚያገለ
ግላቸውን አድኃሪ የምርት ግንኙነት ደረጃ
በደረጃ ማዳከምና የዚህም አድኃሪ የም
ርት ግንኙነት ነፀብራቅ የሆነውን አድ
ኃሪ ርዕዮተዓለም በፅኑ በመዋጋት ፥ ማዳ
ከምና ማጥፋት ያስፈልጋል ። ይሁንና በአ
ብዮታዊ ሂደት ውስጥ የቀድሞውና የአድ
ኃሪውን ሥርዓት ርዕዮተ ዓለምና አመለ
ካከት የመለወጥና በአዲስና በተራማጅ ርዕ
ዮተ ዓለም የመተካቱ ሁኔታ አድኃሪውን
የምርት ግንኙነት አፈራርሶ በአዲስና
ተራማጅ የምርት ግንኙነት እንደመተ
ካቱ እንዲህ በቀላሉና በፍጥነት የሚከና
ወን ነገር አይደለም ። ከባድና ውስብስብ
የሆነ የርዕዮተዓለም ትግልን የሚጠይቅና
ረዥም ጊዜም የሚፈጅ ነው ። በኪነጥበ
ቡም ዘርፍ ተራማጅና አንድ ወጥ የሆነ
የኪነጥበብ ምርት በስፋት ለማስገኘት እን
ዲሁ ብዙ ትግል የሚጠይቅ ነው ።

በተለይም ደግሞ ማይምነት በተንሰ
ራፋበት ፥ ኪነጥበብ በሚገባ ባልዳበረበት፥
የኤኮኖሚና የባህል ዕድገቱ ዝቅተኛ በሆ
ነበት ፥ የከያንያን ቁጥር በጣም አነስተኛ
በሆነበት እንደ አገራችን ባለው ሁኔታ የኪ
ነጥበብ መመሪያ ሙሉ ለሙሉ ሶሻሊስ
ታዊ እውነታነት መሆን አለበት ለማለት
አይቻልም ። ይሁንና አብዮታችን በመከ
ተል ላይ ያለው የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ
እንደመሆኑ ፥ የኪነጥበቡም ዘርፍ አቅጣጫ
የኢሠፓአኮን ዓላማ መሠረት በማድረግ
የተነሳና ከአብዮቱ እድገት ጋር የሚራ
መድ ሕዝባዊና አብዮታዊ የሆነ ፥ ባጭሩ
የሶሻሊስት እውነታነትን ፈለግ የተከተለ
መሆን እንዳለበት ለመገመት አያስቸግርም።
ይህም ማለት አብዮቱ እየገፋ ሲሄድና
የተያያዝነው ለሶሻሊዝም ግንባታ ቅድመ
ሁኔታዎችን የማዘጋጀቱ ትግል እየሰመረ
ሲሄድ እያደር የበላይነትን የሚይዘው
ኪነጥበባዊ የፈጠራ ዘይቤ የሶሻሊስት
እውነታነት ይሆናል ማለት ነው ።

ከሶሻሊስት አገሮች ልምድ ለመገንዘብ
እንደሚቻለው በነዚህ አገሮች ውስጥ የሚ
ገኙ የማሌ ፓርቲዎች ከያንያን የሠራተ
ኛውን መደብ ጥቅም እንዲያራምዱ ፥ በኪ

ነጥበብ ሥራቸው የኮምንዝምን ግንባታ እንዲያግዙ ያበረታታሉ ፣ ከያንያንንም ለዚህ ታላቅ ተግባር ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን የርዕዮተዓለም ትጥቅ እንዲያገኙ ያደርጋሉ ።

የሀገራችን ኪነጥበብም የሶሻሊስት እውነታነትን ፈለግ ሊከተል የሚገባው ስለመሆኑ ቀደም ሲል ተጠቁሟል ። በዚህ ረገድ ለአብዮቱ የቆሙ ከያንያን ሶሻሊዝምን በኢትዮጵያ እውን ለማድረግ በመካሄድ ላይ ባለው ከባድ ትግል የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ የሚችሉት ፣ ኪነጥበብ የሶሻሊስት እውነታነትን ፈለግ በመከተል ሕዝባዊነቱንና አብዮታዊነቱን ለማጠናከር የሚወስደውን እርምጃ ለማፋጠን በሚያደርጉት ጥረት ነው ። ለዚህም የኪነጥበብ ዘርፍ የመንግሥትን ያላሰለሰ ድጋፍና የኢሠፓአኮን ርዕዮተ ዓለማዊ አመራር ማግኘት ይኖርበታል ።

የኪነጥበብን ዕድገት መምራት በሚባልበት ጊዜ አቅጣጫን ከመጠቆም ባሻገር ወደ ዝርዝር ሁኔታዎች መግባት አስቸጋሪ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል ። የኪነጥበብ ዕድገት በአጠቃላይ ሲታይ በዕቅድ ሊመራ የሚችል ቢሆንም ፣ ምን ያህልና ምን ዓይነት የኪነጥበብ ምርት እንደሚመረት አስቀድሞ ዝርዝር ዕቅድ ለማውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ምክንያቱም የኪነጥበብ ምርት የሚወሰነው በመጀመሪያ ደረጃ በከያኒው ግላዊ ችሎታዎች ፣ በተሰጥኦው ፣ ለሥራ ባለው ችሎታ ፣ ውስጣዊ ስሜት ወዘተ . . . ነው ። ለዚህ ነው በብዙ አንጻር የኪነጥበብና የባህል አመራር በከያኒው ሕሊናዊ ባህርያት ጠባይ ፣ ፍላጐት ወዘተ. . . ይወሰናል የሚባለው ። [27] ሁለተኛ፣ በኪነጥበብ አመራር ውስጥ ለከያኒው የፈጠራ ሥራ ፣ አስተሳሰብና መነቃቃት የበለጠ ቦታ መስጠት አለበት ። ኪነጥበብ ሊያድግና ሊዳብር የሚችለው ከያንያን ሰፊ ነጻነት ሲሰጣቸውና የነፃ ውይይት መድረክ ሲያገኙ ነው።ሶስተኛ ፣ በኪነጥበብ አመራር ውስጥ ሌላ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ቁሳዊ መሠረቱን የማጠናከሩና የማስፋፋቱ ጉዳይ ነው ። በሌላም በኩል በሰፊው ሕዝብ መሃል የባህል ሥራዎች የሚታወቁበትን ዘዴ ማሻሻልና ብቃት ያላቸው ካድሬዎችን በማሰልጠንና በማሰማራት በኩል ከፍተኛና የተቀነባበረ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ። [28]

ሌላው በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ በኪነጥበብ መስክ የማሌ ፓርቲ አመራርና የከያንያን ነፃነት በሚመለከት ነው ። ለሶሻሊስት የኪነጥበብ እድገት የማሌ ፓርቲ አመራር ይሰጣል ሲባል « ከያንያን የሕዝቡን ፍላጐት የሚያራምዱ የኪነጥበብ ሥራዎች እንዲያመርቱ ያበረታታል » [29] ማለት ነው ። ስለሆነም ፣ የማሌ ፓርቲ የከያንያንን መብት የሚገፍ ሳይሆን ኪነጥበባዊ መብታቸውን እንዲጠቀሙበት የበለጠ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል ማለት ነው ።

እዚህ ላይ ስለከያንያን መብትና ነፃነት ሲወሳ ከቡርዧው የኪነጥበብ ነፃነት ወይም «ኪነጥበብ ለኪነጥበብ ሲባል» ከሚለው የቡርዧው አመለካከት ጋር እንዳይደባለቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በማርክሲዚም ሳይንስ የኪነጥበብ ነፃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ መሆን አለበት ። ከማርክሲዝም አንፃር የኪነጥበብ ነፃነት ማለት፣

> ... ዓለምን የመረዳት ችሎታ፣ የሕይወትን ፍች ማወቅ ፣ ዓለምን በትክክል ለመረዳትና የማይቀለበስ የዕድገት ግሥጋሴውንም ለመግለፅ አእምሮን በሰፊው መክፈት ማለት ነው ። [30]

የማሌ ፓርቲም ፣ ከያንያን ይህንን ሀቅ ተረድተው ለሰፊው ሕዝብ የሚያገለግል ኪነጥበብ እንዲያመርቱ ማድረግ የሁልጊዜ ጥረቱ ይሆናል ።

Digitized by Google

ኢሠፓአኮ የግሉ ርዕዮተዓለምን በሰራው ሕዝብ ውስጥ በማስራጨትና ፓርቲውን በማዋቀር ተግባሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ለአብዮታዊ ኪነጥበብ መስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ላይ ይገኛል ። የአብዮታችን ግላግ የሆነውን የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት ፣ አብዮቱም አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ኪነጥበብ የመደብ ትግል ማፋፋሚያ ፣ የሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለም ማስፋፊያና ለግሉ ፓርቲ ምሥረታ አስተዋፅኦውን በይበልጥ ከፍ ለማድረግ እንዲችል ፣ ለኪነጥበብ ሥራ እድገት እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች በተቻለ መጠን ማስወገድና ለእድገቱም ሁኔታዎችን በይበልጥ ማመቻቸቱ አስፈላጊ የመሆኑ ያህል ፣ ከየንያንም ከአብዮቱ ዕድገት ጋር በመራመድ ለአብዮቱ የወደፊት ገፊት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በይበልጥ ለማሳደግ የርዕዮተዓለም ትጥቃቸውን ባለማሰለስ ማዳበር ፣ ኅብረተሰቡን በበለጠ መርዳት ፣ ሙያቸውን በየጊዜው በማሻሻልና ጥራቱን በማሳደግ የኪነጥበብ ሥራቸውን ከሕዝቡ ጉን ለማስለፍ በይበልጥ መጣር ይገባቸዋል ።

<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>

1. V.G. Afanasyev, *Marxist Philosophy*, (Moscow: Prog. Pub., 1980), p.361.
2. *Fundamental of Marxist Leninist Philosophy*, (Moscow: Prog. Pub. 1974), p. 475.
3. V. Kalle and M. Kovalson, *Historicol Materialism; An Outline of Marxist Theory of Society*, (Moscow: Prog. Pub., 1973), p. 228.
4. *Ibid.*, p. 23.
5. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 7, p. 45.
6. Avner Zis, *Foundations of Marxist Aesthetics*, (Moscow: Prog. Pub., 1977), p. 31.
7. Kalle & Kovalson, p. 256.
8. *Ibid.*
9. *Ibid.*, p. 258.
10. *Avner Zis*, p. 60.
11. *Ibid.*, p. 283.
12. *Ibid.*, p. 59.
13. ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የግዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ የባህል ዘርፍ የ10 ዓመት ጠቋሚ እቅድ «1» ፣ ረቂቅ ፣ ሰኔ ፣ 1974(ያልታተመ)
14. ተስፋዬ ገሠሠ ፣ <u>የኢትዮጵያ ቲያትር አጭር ቅኝት</u> (ለኪነጥበባት ሴሚናር የተዘጋጀ) አዲስ አበባ ፣ ነሐሴ 1974 (ያልታተመ)
15. ከላይ የተጠቀሰው
16. ጠቋሚ እቅድ «1» ረቂቅ ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 2
17. ደበበ ሰይፉ ፣ <u>ቅድመ አብዮት የኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ታሪክ</u> (ለኪነጥበባት ሴሚናር የተዘጋጀ) አዲስ አበባ ፣ ነሐሴ 1974 (ያልታተመ)
18. M.K. Khropchenko, "Literature and Art in Today's World," *Social Science*, No. 3, 1979, p. 92.

Digitized by Google

19. Khropchenko, *The Writer's Creative Individuality and The Development of Literature,* (Moscow; Prog. Pub., 1977), p. 8.

20. *Ibid.*

21. Avner Zis, p. 65.

22. *Ibid.*, p. 66.

23. እያልነህ ሙላት፡ አሰፋ ገ/ማርያም ተሰማ፡ ርእዮተዓለምና ኪነጥበብ (ለኪነጥበባት ሴሚናር የተዘጋጀ) አዲስ አበባ፡ ነሐሴ 1974 (ያልታተመ)

24. V.I. Lenin, *On Art and Literature,* (Moscow: Prog. Pub., 1975), p. 230.

25. Lenin, *Collected Works,* Vol. 25, p. 173.

26. Lenin, *Economics and Politics in the Era of the Dictatorship of the Proletariat,* pp. 12-13.

27. Stefan Ganeve, *Guidance of Bulgaria's Socialist Culture,* (N.P. Sofia Press, 1976), p. 36.

28. *Ibid.*

29. Avner Zis, p. 291.

30. *Ibid.*

Digitized by Google

የሶሻሊስት ትምህርት ሥርዓት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ

ለርዕዮተዓለም ሥርጭት የትምህርት አገልጋይነት

እንደሚያገለግለው የመደብ አቋም ትምህርት የአድኃሪነት ወይንም የተራማጅነት ሚና ሊኖረው ይችላል ። ትምህርት በአንድ በተወሰነ ሥርዓት ማኅበር ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን የጨበጠውን መደብ ርዕዮተዓለምና እምነት አንጸባራቂ ወይም መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን በዚህ አንጻር ትምህርት የአድኃሪ መደብ መሣሪያ ከሆነ የአድኃሪነት ባሕሪይ ይኖረዋል ፤ የተራማጅ መደብ መሣሪያ ከሆነ የተራማጅነት ሚና ይኖረዋል ። ትምህርትን ከአንድ ሥርዓተ ማኅበር አድኃሪም ሆነ ተራማጅ ገጽታ ነጥሎ ማየት አይቻልም ። ምንጊዜም ቢሆን ፤ ትምህርት የገኘው መደብ የራሱን አመለካከት ፤ አስተሳሰብ ፤ ሥነ ምግባር ፤ ልምድና ባህል ለወጣቱ ትውልድ የሚያስተላልፍበት መሣሪያ ነው ።[1]

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ትምህርት ባላዕላይ መዋቅር ዘርፍነቱ የምርት መገልገያዎችን በቁጥጥሩ ሥር ባዋለ መደብ ሥር ይውላል ። ይሁንና ከተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በኋላ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ቅራኔ እየሰፉ ሂዶ ማኅበራዊ አብዮት ሲካሄድ የምርት ግንኙነቱ (የታህታይ መዋቅር) ፈርሶ አዲስ የምርት ግንኙነት ይተካል ። አሮጌውን የምርት ግንኙነት እንዳይፈርስ ሲከላከል የነበረው ላዕላይ መዋቅርም መሠረቱ በመናጋቱና አዲስ መሠረትም በመዘርጋቱ እየተለወጠና ከአዲሱ የምርት ግንኙነት ጋር በሚጣጣምና እርሱንም በሚያጠናክር አዲስ ላዕላይ መዋቅር እየተተካ ይሄዳል ።

በአንጻሩም የአዲሱ ላዕላይ መዋቅር ዘርፍና የዚህም ሥርዓተ ማኅበር ርዕዮተዓለም እውነተኛ መሣሪያ የሆነው ትምህርት የአዲሱ ሥርዓተ ማኅበር መገልገያ ይሆናል ። ቢሆንም ትምህርት ያለፈው ሥርዓት ርዕ

Digitized by Google

ዮተዓለም ማሠራጫና መገልገያ ስለነበር
በቅጽበት ተለውጦ የአዲሱ ሥርዓተ ርዕ
ዮተ ዓለም መማሪያ ሊሆን አይችልም ።
ይህን ተግባር ለማከናወን በራሱ በትምህ
ርት ላይ አብዮት መካሄድ አለበት ። ይህም
የባህል አብዮት ነው ። « የባህል አብዮት
በአንድ ቀን ሳይሆን በረጂም ጊዜ የሚካ
ሄድ ነው ፣ ዓይነተኛ ተግባሩም ጐልማሶ
ቹን ከማይምነት ማላቀቅ ፣ ዕድሜው ለት/
ቤት የደረሰ ሕፃን ሁሉ ትምህርት በወቅቱ
እንዲአገኝ ማድረግ ፣ የሁሉንም ብሔረሰሕ
ሠራተኛ ሕዝብ ባህል ማሳደግና ሐቀኛ ህዝ
ባዊ ምሁርን ማፍራት ነው » ። [2]

ይህ ዓይነቱ የባህል አብዮት ግን ሊካሄድ
የሚችለው ሥርነቀል በሆነ አብዮት ሂደት
ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ። በሌላም
በኩል « የባህል አብዮት አካል የሆነው የት
ምህርት አብዮት የሚከናወነውም ከመቅጽበ
ትና በግብታዊነት ሳይሆን ያለማቋረጥ በተ
ከታታይና በዕቅድ መሆን ይኖርበታል ። » [3]

የትምህርት፣ የርዕዮተዓለም መሣሪያ
ነትም ለማመቻቸት የመዋቅርና የይዘት
ለውጥ ማድረግ የግድ ከማስፈለጉም ሌላ
ከላዕላይ መዋቅሩ ጋር የሚኖረውን ትክክ
ለኛ መጣጣም ወይም አንፃባራቂነት በጥ
ሞና ማከናወን ያስፈልጋል ። የትምህርቱ
ይዘት አይነተኛ ምንጭና አቅጣጫ ሰጪ
የሆነው ርዕዮተዓለም የምርት ግንኙነቱን
የሚአጠናክር በመሆን በየሥርዓተ ማኅበሩ
በተለያየ ቅርጽና አይነት ይቀርባል ። ለዚ
ህም የፊውዳልን ፣ የካፒታሊስትንና የሶሻ
ሊስት ሥርዓተ ማኅበራትን የትምህርት አሰ
ጣጥ መመልከቱ ይጠቅማል ።

በፊውዳል ኅብረተሰብ ርዕዮተዓለማ
ዊና መንፈሳዊ አመለካከቱን የምትቀርጸው፣
ነገሥታቱን ቀብታ ለማንገሥ መለኮታዊ
ሥልጣን ያላቸውና በምድር ላይ የእግዚአ
ብሔር ምርጥ ሹሞች አድርጋ የምትቆጥረው
ቤተክህነት ናት ። የንጉሡም የፈላጭ ቆራ
ጭነት ሥልጣን በቤተክርስቲያን ላይ የተ
ዘረጋ በመሆኑ የሃይማኖት የበላይ ጠባቂ
ነው ።

ስለዚህ በፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር መን
ግሥትና ቤተክህነት የተሳሰሩ በመሆናቸው
ቤተ ክህነት በምትሰጠው ትምህርት ሁሉ
« ለንጉሡ ጠላቶቹን በእግሩ እርግጥ ፤ በእ
ጁ ጭብጥ አድርገህ አስገዛለት » « ለተሾ
መ ሁሉ ተገዙ » በማለት ስለሆነ ፣ የንጉ
ሥን ትዕዛዝ መጣስ የእግዚአብሔርን ቃል
መጣስ እንደሆነ አድርጋ በትምህርት ቤቶ
ችና በየመድረኩ ታስተምራለች ።

ይልቁንም የፊውዳሉ ርዕዮተዓለም ከእ
ምነቱ ጋር የተወራረሰ በመሆኑ ቤተክህነት
እምነቷን ለማስፋፋት የምታደርገው እንቅ
ስቃሴ ሁሉ የፊውዳሉ ርዕዮተዓለም መስ
ፋፋት መሆኑ ግልጽ ነው ። ከዚህ አንፃር
የቤተክህነት ት/ ቤቶች ሁሉ የፊውዳሉ ርዕ
ዮተዓለም ማስፋፊያ ተቋሞች ከመሆናቸ
ውም በላይ የቤተክህነት ትምህርት መዋቅ
ርም የርዕዮተዓለም ስርጭት ማስፋፊያና
መሳሪያ መሆኑን መረዳት አያዳግትም ።

በዚህም መንፈስ የፊውዳሉ ሥርዓተ
ማኅበር የትምህርት አቅጣጫ የሚተለመው
የተጨቆነው ኅብረተሰብ የኅብረተሰቡንና
የምርትን አወቃቀር እንዳይረዳ ለማድረግ
ሲሆን ፣ ለሃይማኖት ትምህርት የሚሰጠው
ከፍተኛ ትኩረት የኅብረተሰቡ ዕድገትና
ጥፋት ከእግዚአብሔር በጐ ፈቃድ ጋር የተ
ያያዘና የፊውዳሉም መንግሥት «የሰማዩ
መንግሥት» ትክክለኛ ግልባጭ መሆኑን
እንዲያምን በማድረግ ነው ። [4] ይህ በሃይ
ማኖት ትምህርት መልክ የሚስፋፋው የፊ
ውዳል ርዕዮተዓለም ምርምርና ጥናትን
ገሸሽ የሚያደርግና የሳይንስና የቴክኖሎ
ጂን እድገትን የሚያፍን ነው ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የትምህ
ርት ዓይነተኛ ዓላማ የካፒታሊስቱን ጥቅም
ማዳበርና ማስከበር ነው ። በመሠረቱ የቡር
ዧው መደብ የትምህርት ቅየሳ የካፒታሊስ
ቶችን የብዝበዛ ፍላጐት ለማሟላት እንጂ
የሰፊውን ሕዝብ ልጆች ለማስተማር አለ

Digitized by Google

መሆኑ ግልጽ ነው ፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር
በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የትምህርት
ዓይነተኛ ዓላማ በመሠረቱ ለካፒታሊስቱ
መደብና ሥርዓት አገልጋይ የሚሆን የሰለ
ጠነ የሰው ኃይል ማስገኘት ነው ፡፡ በሌላ
አነጋገር ካፒታሊዝም በቡርዧው አመለካ
ከት የታነጹ ምሁራን በማፍራት ፣ ለሥር
ዓቱ ጠበቃና አገልጋይ እንዲሆኑ ሲያደርግ
በሌላ በኩል ደግሞ በዘመናዊ የሳይንስና
የቴክኖሎጂ ዕድገት አስገዳጅነት ወዝአደሩ
ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችለውን ያ
ህል መጠነኛ ትምህርት አግኝቶ ለካፒታል
ባርያና መሣሪያ ወይም ታማኝና ብቁ አገል
ጋይ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው ፡፡ [5]
ቡርዡዋው ትምህርትን ከራሱ ርዕዮተዓ
ለም ውጭ የሆነውን የርዕዮተዓለም
እንቅስቃሴ ሁሉ መቆጣጠሪያ መሣሪያ
ያደርገዋል ፡፡ ለዚህም ነው በካፒታሊዝም
ት/ ቤት የእኩልነት መብት ማግኛ ሳይሆን
የርዕዮተዓለም ቁጥጥር ዓይነተኛ መሣሪያ
ነው የሚባለው ፡፡ የቡርዧው ትምህርት
ይዘት የቡርዧውን ርዕዮተዓለም እንዲያ
ሰራጭ ሆኖ ስለሚዘጋጅ ካፒታሊዝምን
አወድሶ ኮሚኒዝምን አጥላልቶ በማቅረብ
በትምህርት ገበታ ላይ ካለው የኅብረተሰብ
ክፍል እውነትን ለመደበቅ ሙከራ ያደር
ጋል ፡፡

በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ትምህርት የቡር
ዧው መደብ ርዕዮተዓለሙን የሚያስፋ
ፋበት አንደኛውና ዓይነተኛው መሣሪያ
በመሆኑ ፣ በዚህ ገፅታው በፊውዳሉ ሥር
ዓት ውስጥ ከሚሰጠው የሃይማኖት ትምህ
ርት ሚና ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም ፣
በካፒታሊዝም መንግሥትና ቤተክህነት
የተለያዩ በመሆናቸው ፣ የካፒታሊስት የት
ምህርት ሥርዓት የቡርዧውን ርዕዮተዓ
ለም የሚያስፋፋው እንደፊውዳሉ በቀጥተኛ
የሃይማኖት ትምህርት ሳይሆን በተዘዋዋሪና
በረቀቀ መንገድ ነው ፡፡

በዘመነ ተሃድሶ ወቅት በአውሮፓ የፊ
ውዳሉ ሥርዓት ርዕዮተዓለም የነበረውን
የካቶሊክ ሃይማኖት በመቃረን የተነሳው
« ጥሮ ግሮ እስካገኝ ድረስ » በሚል ሽፋን
የግለሰብ ብልፅግናን የሚደግፈው የፕሮ
ቲስታንት ሃይማኖት ከካፒታሊዝም ማቆ
ጥቆጥ ጋር የቡርዧው መደብ ሃይማኖት ሁኖ
የተስፋፋውም ያለ ምክንያት አይደለም ፡፡
ቡርዧው ብዝበዛውን የሚሸፍንበት ርዕዮ
ተዓለም ስለ አስፈለገው ነው ፡፡ የቡርዧው
ሥርዓተ ምህርት (በተለይም ማኅበራዊ
ሳይንስን በሚመለከት) የቡርዧው ርዕዮተ
ዓለም ዓይነተኛ መግለጫ የሆነውን ሃሳባ
ዊነት መሠረት አድርጎ የሚነሳ በመሆኑ ፣
ከሃይማኖት ጋር ሙሉ በሙሉ ሊላቀቅ አል
ቻለም፡፡በመሆኑም ኢሳይንሳዊ በሆነ አመለ
ካከት ጭቁን ሕዝቦችን በማደንዘዝ በኅብረ
ተሰብ ውስጥ የበዝባዥና የተበዝባዥ መኖር
ፊውዳሉ እንደሚለው የእግዚአብሔር ትእ
ዛዝ ሳይሆን የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ አድ
ርገው እንዲቀበሉ የሚገፋፋ ነው ፡፡

በቡርዧው ሥርዓት በአንድ በኩል የሳ
ይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት በጣም ከፍተኛ
የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን ፣ በሌላ
በኩል የብርዧው መደብ ማኅበራዊ አመለካ
ከት ደግሞ ከሃይማኖት ተፅዕኖ ጨርሶ ያል
ተላቀቀ በመሆኑ በሥርዓተ ትምህርቱ ሁለ
ት ዋና ዋና አካሎች መካከል ከፍተኛ ቅራኔ
አለ ፡፡ የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፉ በሳይንስ ላይ
የተገነባ በመሆኑ ቡርዧው ወደደም ጠላም
ለቁሳአካላዊ አመለካከት መስፋፋት ጥር
ጊያ መንገዱን ሲያመቻች ፣ የማኅበራዊ
ሳይንስ ዘርፉ ግን ሃሳባዊነትን እንደመመ
ሪያ አድርጎ ሙጭጭ አድርጎ በመያዙ
የቡርዧው ሥርዓተ ትምህርት አጠቃላይ
ይዘት በቅራኔ የተወጠረ ለመሆኑ ቋሚ ምስ
ክር ነው ፡፡

ቡርዧው በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ከሃ
ሳባዊነት ጋር የተቆራኘ ጭልጥ ያለ የፖለ
ቲካ ትምህርት እየሰጠ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ
ትምህርት ከፖለቲካ ነፃ መሆን አለበት እያ
ለ ለመስበክ የተገደደውም ከላይ ከተጠቀ
ሰው ቅራኔ ሊወጣ የሚችልበት መንገድ

Digitized by Google

በማጣቱ ነው ። መንገድ አጣ በሚባልበት ጊዜ እውነቱን ቢያወጣ በኅብረተሰብ ውስጥ የአንዱ መከበርና የሌላው መደህየት ቡርዧው እንደሚለው የተፈጥሮ ሕግ ሳይሆን ሰው ሠራሽ መሆኑ ስለሚገለጥበት የራሱን መቃብር ለመቆፈር ስለሚገደድ ነው ።

ቡርዧው የትምህርትን መሣሪያነት በሚገባ በመገንዘብ የከፍተኛ ት/ቤቶችን የትምህርት መርሃ ግብር ከፍላጐቱ ውጭ እንዳይሆን በተለያየ መንገድ እጁን አስገብቶ ይቆጣጠራል ። የመቆጣጠሪያ ዘዴው ዩኒቨርሲቲዎችን በገንዘብ በመደጐም ፣ የገዥዎች ቦርድ አባል በመሆን ወይም የዩኒቨርስቲዎችን ባለሥልጣኖችና ፕሮፌሰሮች የራሱ ድርጅቶች ፣ ማለትም የባንኩ ፣ የኮርፖሬሽኑ ፣ የፋብሪካ ወዘተ--- አማካሪዎች ፣ የቦርድ አባሎች ባለአክሲዮኖች ወዘተ --- አድርጎ ከጥቅሙ በማካፈል የትምህርቱን አቅጣጫ በፍላጐቱ ሥር ያውላል ። እንዲሁም ዩኒቨርስቲዎችን የከበርቴ ልጆች ማስተማሪያ በማድረግ ብቻ ሳይወሰን ከጭቁን መደቦች የሚወጡ ወጣቶችን መርጦ በማስተማር የጥቅሙና የፍላጐቱ ተገዥ የሆነ የምሁር ክፍል እንዲፈጠር ያደርጋል ። በዚህ ማኅበራዊ ክፍል አማካይነት ብዝበዛው ይበልጥ ሊቀላጠፍ የሚችልበትን አመች መንገድ ይቀይሳል ። በካፒታሊዝም ዩኒቨርስቲዎችም ሆነ ሌሎች ዝቅተኛ የትምህርት ተቋሞች የቡርዧውን ርዕዮተዓለም በሚገባ የሚገልጸውን « እያንዳንዱ ለራሱ እግዚአብሔር ግን ለሁላችን » የሚለውን አባባል እንደ ፀጋ አድርገው የሚቀበሉ በመሆናቸው፣ ለብዝበዛው ሥርዓት መጠናከር የቆሙ ዓይነተኛ የቡርዧ ርዕዮተዓለም መሣሪያዎቹ ናቸው ።

በካፒታሊስት አገሮች ያሉ የትምህርት ተቋሞች የቡርዧውን ርዕዮተዓለም በትክክል ማንፀባረቃቸውን ካፒታሊስቶቹ በተለያዩ ዘዴዎች ይቆጣጠራሉ ። ለምሳሌ በአሜሪካ በ1971 የካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ የገዥዎች ቦርድ አባላት ከነበሩት መካከል የዛሬው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን ፣ በዓመት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ያለው የኖርተን ሲመን ኩባንያ ባለቤት የሆነው ኖርተን ሲመን ፣ በዓመት የ12—15 ሚሊዮን ዶላር ገቢ የሚያስገኘው የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ኩባንያ የሆነው « የዋትንኪስን ጆንስን » ኩባንያ ባለቤት ሽርኮች ከሆኑት አንዱ ዱን ዊትኪንስ ይገኙበታል ።[6]

ከዚህም በስተቀር የአሜሪካን ከፍተኛ ትምህርት በመሃል እጃቸው አስገብተው እያደገና እየሰፋ የሚሄደውን የሞኖፖል ካፒታሊዝምን ፍላጐትና ምኞት የሚያስፈጽሙትን እንደ ካርኒጅና ሮክፌለር ያሉትን «የበጐ አድራጐት» ድርጅቶች[7] መጥቀሱ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የትምህርት ሥርዓት አቅጣጫ ቀያሽ ራሱ ቡርዧው ይልቁንም ጥቂት ሞኖፖሊስቶች መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል ።

ትምህርት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ

የሶሻሊስት የትምህርት ሥርዓት የተፈጥሮውም ሆነ የማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፉ በሳይንሳዊ የቁስአካላዊ አመለካከት ላይ የተዋቀረ ፣ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ገንቢ የሆነውን አዲሱን ትውልድ በሳይንሳዊ አመለካከት የሚያንጹ ፣ የሀገር ወዳድነት ስሜቱና ወዝአደራዊ አመለካከቱን የሚያዳብርና በአካልና በመንፈስ የጠነከረ እንዲሆን የሚያደርግ የትምህርት ዓይነት ነው ። ከዚህም በቀር የሶሻሊስት ትምህርት ዓይነተኛ ተግባር ከኅብረተሰቡና ከተፈጥሮ ሳይንሶች አጠቃላይ እውቀት የገበየ ፣ ነፃ አስተሳሰብ፣ ትክክለኛና የፀና እምነት ፣ በአካል የዳበረ፣ በስነምግባር የጸናና በጐ ፈቃድ ያለው አዲስ ትውልድ ማፍራት ነው ። ይህ ትውልድ የኅብረተሰብን የዕድገት ሕግጋት ተከትሎ ለኅብረተሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት የሚታገል ፣ ለመላው የኅብረተሰብ ጥቅም የቆመና በለውጥና በዕድገት አምኖ ለለውጡ

ያልተቆጠበ ጥረት የሚያደርግ እንዲሆን የሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ትምህርት ያስፈልገዋል ።

በሶሻሊዝም ግንባታ ሂደት ወሳኝና ግንባር ቀደም ኃላፊነት የሚወድቅበትን የአዲሱን ትውልድ ማነጽን አስመልክቶ ሌኒን ሲናገር « የኮሚኒስትን ኅብረተሰብ የሚፈጥረውን የአዲሱ ትውልድ ኩትኮታ ፣ ስልጠናና ትምህርት በአሮጌው የአሠራር ዘዴ መመራት የለበትም ። ይሁን እንጂ አሮጌው ኅብረተሰብ ከተወልን ቁስ ተነስተን ነው አዲስ ነገር መፍጠር የምንችለው ። አለብን ። ኮሚኒዝምን መመሥረት የምንችለው ከአሮጌው ኅብረተሰብ ያካበትነውን ጠቅላላ ዕውቀት ፣ ድርጅትና ልምድ መሠረት አድርገን ስንነሳ ነው ። በዚህ መሠረት ላይ የአዲሱን ትውልድ ትምህርት ስልጠናና እንዲሁም ድርጅት በአዲስ መልክ አዋቅረን ጉዞ መጀመር አለብን፤ »[8] ያለውን ማስታወስ ያስፈልጋል ።

እርግጥ በአንድ ጊዜ የትምህርቱን ሥርዓት እንለውጣለን ማለት አይደለም ። ብንሞክርም ትልቅ ስህተት እንሠራለን ። ምክንያቱም አስፈላጊው መሠረት ፣ ልምድ ፣ ሙያና ገንዘብ በብቃት የለምና ነው ። ሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ከጨበጠ እንኳ በኋላ በትምህርቱ ዘርፍ አስቸጋሪ ሁኔታዎች መከሰታቸው አልቀረም። ምክንያቱም የመንግሥት ሥልጣን መጨበጥ ለአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እርምጃ አይደለም ። በመሆኑም የትምህርት አቅጣጫን መለወጥ ከባድ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።[9] ይህ ሐቅ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላ ቀር አገሮች አስቸጋሪነቱ ይበልጥ ጉልቶ ይታያል ። ሌኒን እንዳለው ከአሮጌው ኅብረተሰብ የምንወስደው የዳበረ ልምድ ባለመኖሩ ፣ በአንጻሩ ግን የወረስነው ችግር በብዙ መልኩ ፊውዳላዊና ውስብስብ በመሆኑ የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ ቀላል ሆኖ አናገኘውም ። በዚህ ሁኔታ ላይ የችግሩ ስፋት የሚታየው የትምህርቱን ይዘትና ዓላማ ሶሻሊስት ፈር በማስያዝ ብቻ ሳይሆን የትምህርቱን መዋቅር እስከ እያንዳንዱ የገጠር መንደር ድረስ ዘርግቶ መላውን መማር ያለበትን የኅብረተሰብ ክፍል በትምህርቱ ማሳተፍ ከማስቻሉም አንፃር ነው። ይህ ደግሞ በየሥራ ዘርፉ የሚያስፈልገውን ቁሳዊ አቅም ፣ የሰለጠነና የማሌ ርዕዮተ ዓለም ትጥቅ ያለውን የሰው ኃይልና የራሱ የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ክፍል ተሳታፊነትን ይጠይቃል ።

ከዚህም የምንገነዘበው « - - - ትምህርት የአንድ ግለሰብ የግል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ኃላፊነት » እንደሆነ ነው ።[10] በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ግለሰቡን ከኅብረተሰቡ ፣ ኅብረተሰቡን ከግለሰቡ ነጥሎ ማየት አይቻልም ። በመሆኑም ግለሰቡ ለኅብረተሰቡ ዕድገት ማበርከት ያለበትን የሥራ ድርሻ ለመወጣት የሚያስችለው አስፈላጊ ፣ ማኅበራዊና ሳይንሳዊ ዕውቀት በትምህርት የዕድሜ ዘመኑ የሚአገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ማግኘቱንም ማረጋገጥ የኅብረተሰቡ ዓይነተኛ ኃላፊነት ይሆናል ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው የሶሻሊስት ብሎም የኮሚኒስትን ኅብረተሰብ እውን የማድረግ ኃላፊነት የሚጣልበትን ወጣት ትውልድ ማፍራት የሚቻለው ።[11] ስለሆነም አዲሱን ትውልድ መኮትኮት ለአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ቅድመ ሁኔታ መፍጠር መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

የሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ግንዛቤ ደግሞ የሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ አንደኛው ገጽታ ነው ። ይህም ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው መደብ ለጨበጠው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥልጣን ድል አድራጊነትና ዘላቂነት አማራጭ የሌለው ዋስትና ነው ።

የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ትኩረት በትምህርት ገበታ ላይ ያለውን አዲስ የሰው ኃይል በፖለቲካና ማኅበራዊ ግንዛቤ ከፍ አድርጎ የሚቀስመውንና የቀሰመውን ዕውቀት እንዴትና ለምን እንደሆነ ማስተዋል እንዳለበት ጭብጥ ለመስጠት ነው ። የማስተዋሉ ው

Digitized by Google

ጨት ደግሞ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ክስ
ተቶችን ግንዛቤና የችግሮችንም የመፍ
ትሔ ችሎታ መጨበጥ ይሆናል ።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትጥቅ ያለው
አዲስ ትውልድ ሳይፈጥሩ ኮሚኒስት ኅብረ
ተሰብ መገንባት ፈጽሞ አይቻልም ። ለተ
ፈጥሮና ለማኅበራዊ ክስተቶች ሳይንሳዊ
ትንታኔ መስጠትና በተግባርም ማዋል የሚ
ችል ትውልድ ማግኘት የሚቻለው ማርክሲ
ዝም ሌኒኒዝምን አጥንቶ የተረዳና ሌሎች
ንም የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ሳይንሶች
ከዚህ ሳይንስ ጋር አገናዝቦና አጣጥሞ የቀ
ሰመ የወጣት ኃይል ሲገኝ ነው ።

በዚህ መንፈስ የተማሪው ዓላማ ንድፈ
ሃሳባዊ ትምህርትን አጥንቶ መገኘት ብቻ
ሳይሆን ፣ ንድፈሃሳቡ ከተግባር ጋር ምን
ያህል ውህደትና ትክክለኛነትም እንዳለ
ውና ለፈጠራ ችሎታውም ሥራ በር ከፋች
መሆኑን በተጨባጭ ማጤን ይገባዋል ።
ሌኒን « ኤሌክትሪክሲቲ ምን እንደሆነ መረ
ዳቱ በቂ አይደለም ፤ የሚፈለገው ኤሌክት
ሪክሲቲውን በእንዱስትሪና በእርሻ ውስጥ
በቴክኒካዊ ተግባር ላይ የማዋሉ እውቀት
ነው ፤ »[12] እንዳለው ንድፈሃሳብን ከተግ
ባር ነጥሎ ማየት ኢሳይንሳዊ ነው ።

በሌላም በኩል ትምህርትን በመደብ መ
ሣሪያነቱ በምናይበት ጊዜ በመደብ ትግሉ
ውስጥ የሚጫወተውን አይነተኛ ሚና እን
ገነዘባለን ። በዚህ አቅጣጫ የሶቭዬት ኅብ
ረት ኮሚኒስት ፓርቲ 7ኛው ጠቅላላ ጉባኤ
ትምህርት በመደብ ትግሉ ውስጥ የሚጫ
ወተውን ሚና አስመልክቶ ካሳለፈው የፖ
ሊሲ ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው ፣ ፓር
ቲው ትኩረት የሰጠው ት/ ቤት ከቡርዧ
መደብ መሣሪያነት በኅብረተሰብ ውስጥ የመ
የመደብን ልዩነት ወደ ማጥፊያ መሣሪያ
ነት ፣ ወይም ኅብረተሰብን ወደ ኮሚኒስት
ኅብረተሰብ ለመለወጥ ወደሚያገለግል መ
ሣሪያነት መለወጡ ሲሆን ፣ ይህ ሂደት የሠ
ራተኛውን መደብ የርዕዮተዓለም ፣ የድርጅ

ትና የትምህርት ጽንሰ ሀሳቦችንም መላው
ሠርቶ አደር ሕዝብ ተቀብሎ ተግባራዊ ማድ
ረጉንም ያጠቃልላል ። የኮሚኒስት ትምህ
ርት ማለት ማንኛውንም ጥናት (ትምህር
ት) ሠራተኛው ሕዝብ ከአሮጌው ኅብረተ
ሰብ ጋር ከሚያደርገው ትግል ጋር ማያያዝ
ማለት ነው ። የትምህርቱ ይዘት ሠርቶ አደ
ሩ ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ የሚያውቅበትንና
እነርሱንም የሚወጋበትን ስልት መቀየስ
የሚያስችል ግንዛቤ እስከ አላስጨበጠው
ድረስ ፣ የትምህርቱ አቅጣጫ ከሠራተ
ኛውና ከአጠቃላይ ጭቁኑ ሕዝብ ፍላጐት
አንፃር ተቀይሷል ማለት አይቻልም ። በዚ
ህ መሠረት ትምህርት ለመደብ ትግሉ ፈር
ቀዳጅ መሆን ይኖርበታል ።

ትምህርት በየትኛውም ሥርዓተ ማኅበር
ለማኅበራዊ ለውጥ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆ
ኑንና ማኅበራዊ ለውጥ ደግሞ ለምርት ኃይ
ሎች ዕድገት ወሳኝ መሆኑ መረሳት የሌለ
በት ጉዳይ ነው ። ሰው በምርት ኃይሎች እን
ቅስቃሴ ሁሉ የወሳኝነት ሚና አለው ። ለወ
ሳኝ እንቅስቃሴ መርህ የሚሆነው በትምህር
ት የሚገኘውና በተግባር የተፈተነው ንድ
ፈሃሳብ ወይም ንቃተህሊና ነው።ከዚህም
በቀር « ማይምነት ካልተወገደ ፣ የመግር
ዕድል ካልተዳረሰ ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ
ካልተስፋፉና የሠርቶ አደሩ ሕዝብ አጠቃ
ላይ እውቀትና የቴክኒክ ችሎታ ካልዳበረ ፣
የምርት ኃይሎች እድገት ሊፋጠን አይች
ልም» ።[13] ለነዚህ ሁሉ መሠረታቸው ትም
ህርት ነው ። የምርት ኃይሎች ሞተር የሆነ
ው ሰው በትምህርት አማካይነት ለኅብረተ
ሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት ለመታገል
የሚያበቃውን የንድፈ ሃሳብና የተግባር
ዕውቀት መቅሰም ይኖርበታል። ይህ ሲሆን
ነው ሰው የሰለጠነ ጉልበቱን ለሰፊው
ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም አውሎ አመርታና
ጠቀሜታ ያለው የኅብረተሰብ ዕድገት
ማስገኘት የሚችለው ።

የሶሻሊስት ትምህርት ለሳይንስና ቴክ
ኖሎጂ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደ

Digitized by Google

ርጋል ። ይህ እውነታ በብዙ ሶሻሊስት አገ
ሮች ውስጥ በተጨባጭ የታየ ነው ። ይህም
ሠርቶአደሩ ሕዝብ ከብዝበዛ ነፃ የሆነውን
የፈጠራ ችሎታውን በሚገባ ስለሚጠቀም
ነው ። የፈጠራ ችሎታው አዳባሪ ሳይንስ
እንደመሆኑ መጠን ሶሻሊስት ትምህርት
ለሳይንስ እጅግ በጣም ከፍተኛ ትኩረት ይሰ
ጣል ። በዚህ አንፃር በሳይንስና በትምህ
ርት ሥርዓቱ መካከል ቁርኝት አለ ። ሳይ
ንስ ለሶሻሊስት የትምህርት ሥርዓት
አዲስ ዕውቀት ሲያበረክት የትምህርት ስር
ዓት ደግሞ ለሳይንስ የሰለጠነና የተማረ
የሰው ኃይል ያበረክታል ።

ሳይንስ ፣ ሰው ተፈጥሮን እንዲለውጥ ይረ
ዳዋል ። ይሁንና ተፈጥሮን በመለወጥ ረገድ
ሳይንስ ያስገኘው ችሎታ ተግባራዊ የሚ
ሆነው በቁሳዊ ምርት ላይ የተሰማሩ ሰዎች
የሳይንስ ዕውቀታቸውን ሲያዳብሩ ነው ።
ይህም በተግባር ሊከናወን የሚችለው በት
ምህርት ነው ። በመሆኑም ትምህርት ሳይ
ንሳዊ ሀሳቦችን ወደ ቁሳዊ ኃይል የመለ
ወጥ ችሎታ ያለው ነው ።[14] በዚህም አን
ፃር የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት የምር
ምርና የጥናት ውጤት ነው ። ከነዚህ አጠ
ቃላይ የትምህርት ዓላማና ጭብጦች በመነ
ሣት የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያን የትም
ህርት ይዘት ምንነትና በድኅረ አብዮት ኢት
ዮጵያ የትምህርት ስርዓት ምን ያህል ከሶሻ
ሊስት የትምህርት ዘይቤ ጋር እንደተገና
ዘበ በመጠኑም ቢሆን መገምገም ያስፈ
ልጋል ።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የትምህ ርት ሥርዓት

ዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገ
ባው በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መ
ጨረሻ ገደማ ላይ የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ኃይ
ሎች በአካባቢው ተጽዕኖ ማድረግ ብጀመ
ሩበት ጊዜ ነበር ።[15] በዚህም ወቅት በአ
ንድ በኩል የአውሮፓ ሚሲዮናውያኖች ሃይ
ማኖታቸውን ለማስፋፋትና የቅኝ ገዥዎችን
ጥቅም ለማራመድ ት/ ቤቶችን መክፈት
ሲጀምሩ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵ
እየተጠናከረ የመጣው ማዕከላዊው ፊው
ዳል መንግሥት በአከባቢው በማስፍሰፍ
ላይ ከነበሩት የቅኝ ገዥ ኃይሎች ጋር ለሚ
ኖረው ግንኙነት የዘመናዊ የትምህርት አስ
ፈላጊነትን በመገንዘብ ዘመናዊ ት/ ቤቶ
ችን ከፈተ ። ኢትዮጵያውያንንም ለትምህ
ርት ወደ ውጭ መላክ ጀመረ ።

የትምህርቱም ዓላማ አስተጋርጓሚዎች
ንና በማቆጥቆጥ ላይ ለነበረው ካፒታሊዝ
ም አገልጋዮችን ለማፍራት ሲሆን ፣ በይዘቱ
በይበልጥ በቋንቋ ትምህርት ላይ ያተኮረ
ነበረ ። በዚሁ ሁኔታ ተጀምሮ የነበረው
የፊውዳሉ የትምህርት ሥርዓት በኢጣሊያ
ወረራ ተቋረጠ ። በምትኩም የፋሽስት ኢጣ
ሊያ የትምህርት ሥርዓት ከኤርትራ ወደ
መሀል ኢትዮጵያ በተለይም ወደ አዲስ
አበባ መዘርጋት ተጀመረ ። የትምህርቱም
ዓላማ ለቅኝ አገዛዝ አመቺ ሁኔታ ለመፍ
ጠር በመሆኑ የጣሊያንኛ ቋንቋን በማስተ
ማር ላይ ያተኮረና እስከ አራተኛ ክፍል
ብቻ የተወሰነ ነበር ።

ከፋሺስት ኢጣሊያ ሽንፈት በኋላ የኢት
ዮጵያ የትምህርት ሂደት ለተወሰነ ጊዜ
ም ቢሆን በእንግሊዞች ተጽዕኖ ሥር ወደቀ።
የትምህርቱ አቅጣጫም ከእንግሊዞች የባ
ህል መስፋፋትና ኢምፔሪያሊስት ጥቅም
ጋር የተያያዘ እንደነበረ መገመት አያዳግ
ትም ።

አሜሪካም ቢሆን እንግሊዝን በመተካት
«ፖይንት ፎር» የበሚለው ፕሮግራም አሜ
ካይነት የኢትዮጵያን የትምህርት አቅጣጫ
መቀየስ ጀመረ ። በኋላም አሜሪካ « የሰላም
ጓድ » በሚል ስያሜ ተጨማሪ ልዩ ተል
ዕኮ የነበራቸውን መምህራን ሲልክ ኢትዮ
ጵያ ከፍተኛ ብዛት ያላቸውን «የሰላም ጓድ
ልዑላን » በማስተናገድ ባፍሪካ ውስጥ ከፍ
ተኛውን ደረጃ ከያዙት መካከል ትገኝ
ነበር። በአንድ ወቅትም በኢትዮጵያ ውስጥ

Digitized by Google

የነበሩት የሰላም ጓድ ልዑካን 550 ደርሰው እንደነበረ የታወቀ ነው ። [16]

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የትምህርት ይዘት በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮረ ፣ ከምርት ተግባር ጋር ያልተያያዘና በተማሪዎቹም ላይ የተግባር ሥራን ጥላቻ ያሳደረ የፊውዳልና የኢምፔሪያሊዝም ባህል ተጽዕኖ የነበረበት ከመሆኑም በላይ ፣ ተማሪዎቹ በስሜታዊ ዝንባሌዎች ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ እንደነበረ ከዓላማዎቹና ከዲሲፕሊኖቹ ይዘት መረዳት ይቻላል ። [17]

በቅድመ አብዮት ይሰጡ የነበሩት የትምህርት ዓይነቶች ከሚጠቁሙት አንዱ ቁም ነገር ፣ የፊውዳሉ ሥርዓተ ትምህርት የተማሪውን የተሟላ የሰብዕና እድገት የማይፈልግና ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ፍላጐት ጋር የማይጣጣም መሆኑን ነው ። በይበልጥ የሚፈለገው የተማረ የሰው ኃይልና የቴክኒክ እውቀት ያለው ሳይሆን ፣ ለቢሮክራሲው አሠራር የሚያገለግል ነበር ።

የትምህርት ዓይነቶችን ዝርዝር ይዘት ብንመለከት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፊውዳሉ ገዥ መደብ ጥቅምና ሕልውና ጋር የተያያዘ ፣ የተማሪውን አእምሮ ከሕይወቱና ከአካባቢው ኅብረተሰብ ዕድገትና ፍላጐት ጋር ባልተያያዘ የቀለም ትምህርት የሚአደነዝዝ ነበር ። ይህንን ለመገንዘብ ያህል የታሪክ ትምህርትን ሲለበስ ብንመረምር ዓላማው ሃሳባዊ አመለካከቶችን ለማስፈን የሚጥርና የኅብረተሰቡን የዕድገት ግሥጋሴ የሚወስኑት ጠንካራና ብልህ መሪዎች እንደሆኑ አድርጐ የሚቀርብ ነበር ። [18] ይህንንም በዝርዝር ይዘቱ ስንመለከተው የአፄዎችን መነሳትና መውደቅ ፣ የግዛታቸውን መስፋፋትና መጥበብ ፣ የነገሥታቱን ልደትና ዕድገት ፣ የሃይማኖት መሪዎችን ቅድስና እና ከነገሥታቱ ጋር በመሆን የተጫወቱትን ሚና ወዘተ ... አድምቆ የሚያሳይ ነበር ። [19]

በተጨማሪም ከ1-12 ክፍሎች ይሰጡ ከነበሩት የትምህርት ዓይነቶች መካከል ለፊውዳሉ ርዕዮተዓለም መስፋፋት ዓይነተኛ አስተዋጽኦ የነበረው የግብረገብ ትምህርት ነበር። ይህም በአብዛኛው የቤተክህነት ሰዎችና ለፊውዳሉም ሥርዓት ፍጹም ተገዥዎች በነበሩት ካህናት መሰጠቱ ደግሞ ሌላው ለፊውዳሉ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ አመለካከት መስፋፋት ሁኔታዎችን አመቻችቶ ነበር ። በዚህ ትምህርት አማካይነት የንጉሡን ትእዛዝና ፈቃድ አለመፈጸም ውጤቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትዕዛዝ እንደ መስበር እንደሚቆጠርና በነፍስ በሥጋ የሚአስቀጣ እንደሆነ ተደርጐ ለተማሪው ይነገረው እንደነበር ይታወሳል ።

በዚህ ዓይነት ይካሄድ የነበረው የፊውዳሉ ትምህርት ስርጭትና ይዘቱ በጣም ውሱንና ጠባብ በመሆኑ ከ 1966 በፊት በአገሪቱ ውስጥ መማር ከነበረባቸው ሕፃናት በአንደኛ ደረጃ 18% ፣ በ2ኛ ደረጃ 6% ብቻ በትምህርት ገበታ ላይ ነበሩ ። [20] የትምህርት በርም ለሰፊው ሕዝብ ልጆች እየተዘጋ በመሄዱ ፣ ዕድል አግኝተው የገቡትም በልዩ ልዩ ምክንያቶች በትምህርታቸው ሳይገፉ ከዝቅተኛ የትምህርት ደረጃዎች እየተጠንጠባጠቡ ይቀሩ ነበር ። ይህም ችግር ከሌሎች የኅብረተሰቡ ችግሮች ጋር በመደመር የሕዝቡን ተቃውሞ እያባሰው መጣ። በዚህ ሁኔታ የተደናገጠው የኃይለ ሥላሴ መንግሥትም መፍትሄ ነው ብሎ በ «ተሴክተር ሪቪው » አማካይነት የትምህርት መስፋፋትን ለመግታት የሚችል መመሪያ አወጣ ። ይሁንና በሽታው የሴክተር ሪቪው ብቻ ሳይሆን ራሱ ሥርዓቱ በመሆኑ ፣ የሥርዓቱ መበስበስ የሕዝቡ ተቃውሞ ወደ ማኅበራዊ አብዮት እንዲለወጥ አደረገው።

የፊውዳሉ ትምህርት ሌላም ደካማ ጐን ነበረው ። የትምህርቱ አስተዳደር በቢሮክራሲያዊ ማዕከላዊነት የታነቀና ሕዝባዊ ተሳትፎንም ያገለለ ነበር ። በተጨማሪም በአንደኛ ደረጃ ከነበሩት ተማ

Digitized by Google

ሪዎች ከመቶ ሃያ አምስት እጁ የግል ት/ቤቶች ለነበራቸው ነጋዴዎችና ድርጅቶች ብዝበዛ የተዳረጉ እንደነበረ ይታወሳል ፡፡ [21]

በተለይም የሰፊው ሕዝብ መሃይምነት እንደፖለቲካ ጥቅም በመቆጠሩ ማን በብና መጻፍ ያልሞከረው የሕዝብ ክፍል 93% ነበር ፡፡ የእነዚህን መሳይ ሁኔታዎች ድምር በፊውዶ ቡርዧው የትምህርት ሂደት ላይ ከፍተኛ ቀውስ እያደረሰ በመምጣቱ ይኸው ሁኔታ ለየካቲት 66 አብዮት ፍንዳታ አይነተኛ መንስኤዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው ለማለት ይቻላል ፡፡

በድህረ አብዮት ሥርዓተ ትምህርቱን ለመለወጥ የተደረገ ጥረት

የኢትዮጵያ አብዮት የፊውዳሉን ሥርዓት ሽሮ የሶሻሊስትን የዕድገት ፈለግ ተከትሎ መጓዝ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ከአስፈለጉት በተለይም ከላዕላይ መዋቅር ዘርፎች አንዱ ትምህርት ነበር ፡፡ የትምህርቱ ሥርዓት ከአብዮቱ ሂደት ጋር እንዲራመድ አድርጎ መቀየስና የማሌ ርዕዮተዓለምን እንዲያንጸባርቅና እንዲያሰራጭ አቅጣጫ መስጠትም አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ፡፡

አብዮቱ ጥራት እያገኘ ሲሄድ የትምህርቱ ሥርዓት ይበልጥ ሶሻሊስት ይዘት እንዲኖረው ሙከራ ማድረግ ተጀመረ ፡፡ የተማሪውን ሁለንተናዊ ሶሻሊስት ስብዕና ለማሟላት እንዲያስችል « ትምህርት ለምርት ፣ ለሣይንሳዊ ምርምርና ለሶሻሊስት ንቃተ ኅሊና » የሚል መሠረታዊና ብሔራዊ መርህ ይዞ የሥርዓተ ትምህርቱ ለውጥ ቀጠለ ፡፡ [22] የነዚህ ሦስት መሠረታዊ መርሆዎች የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አቅጣጫ ሆኖ መነደፍም በአብዛኛው በቀለም ትምህርትና ፊውዳላዊ አመለካከት ላይ ተቀይሶ የነበረውን ሥርዓተ ትምህርት ሥረ መሠረቱን እናግቶታል ፡፡

በሶሻሊስት መርህ መሠረት ፣ ሥርዓተ ትምህርቱን ለመለወጥ የተደረገው ሙከራ ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጥያቄና ፍላጐት እንዲሁም ከአገሪቷ የሽግግር ወቅት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታ በመነሳት የትምህርቱን አጠቃላይ ዓላማ ፣ ቅርጽ ፣ ድርጅትና የማስተማር—መማር ጥበብ ለመንደፍ ጥረቱ ተጀምሯል ፡፡ ለእየደረጃው ያስፈልጋሉ ተብለው የተወሰኑት የትምህርት ዓይነቶችም መዘርዘር ይዘት ከሞላ ጐደል ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሎአል ፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱም ማዕከላዊነቱን ጠብቆ እንደ የአካባቢው ልዩነትና አስፈላጊነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታም ለመፍጠር ሙከራ ተደርጓል ፡፡

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በሚመለከት በ1966—1968 የተደረገው የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ በቅድመ አብዮት የነበረውን ሥርዓተ ትምህርትና መጻሕፍት ለመተካት ያህል የተደረገ ስለነበር ፣ የይዘቱና የአቀራረቡ ጥራት በጣም ዝቅተኛ ነበር ማለት ይቻላል ፡፡ ከ1968—1974 የተደረገው ጥረት ግን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ይዘትን ለማንጸባረቅና በይበልጥም የፖሊቴክኒክን ትምህርት አጠቃላይ ባህርይ ለማቀፍ የተሞከረ በመሆኑ ጥራቱ በተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በየትምህርቱ ዓይነት ለክፍሉ ደረጃ ተመጣጣኝ የሆኑ ከ250 ያላነሱ አርዕስቶች ያዘለ ሥርዓተ ትምህርት ፣ ለተማሪዎች የሚያገለግሉ መጽሐፍት ፣ የመምህራን መመሪያና ሌሎችም ጽሑፎች ተዘጋጅተዋል ፡፡ ለምሳሌ ፣ የእርሻ ትምህርት ይዘት በእርሻ የአስተሳሰብ ለውጥና ዝንባሌ በማሳደር የሥራውን ክቡር

Digitized by Google

ነት በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ ለመገን ባት ፣ ተማሪው አካባቢውን በመመልከት የማጥናት ልምድ እንዲኖረው ሆኖ በተ ለያዩ የእርሻ ዘርፎች በቂ እውቀትና የማ ምረት ችሎታ እንዲኖር ለማድረግ የተ ዘጋጀ መሆኑን ሙከራው ያሳያል ። ሌሎ ችም ትምህርቶች በዚሁ ዓይነት የተዘጋጁ ሲሆኑ በቅርቡ የማሌን መሠረተ ሃሣቦች የሚአስጨብጥ ሥርዓተ ትምህርትና መጻሕ ፍት አዘጋጅቶ በሥራ ላይ ለማዋል ዝግ ጅት እየተደረገ ነው ።

ሌላው የሥርዓተ ትምህርቱ አንዱ ገጽታ የመማር — ማስተማር አገልግሎት የሚ ሰጡና ከአዲሱ ሥርዓት ትምህርት ዓላማ፣ ይዘትና የማስተማር—መማር ጥበብ አንፃር መጻሕፍትን የማዘጋጀት ጉዳይ ነው ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ አብዛኞቹ የመማር — ማስተማር መጻሕፍት ከኢም ፔሪያሊስት አገሮች የመጡ በመሆና ቸው ፣ የቡርዧውን ርካሽ ባህልና ጥቅም የሚአስፋፉና ከሰፊው ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጐት ውጭ የሆኑ ነበሩ ። ይህንን ሁኔ ታም በመለወጥ በተቻለ መጠን ከአብ ዮቱ ጋር የማዛመድ ሙከራ የታየባቸው መጻሕፍት በየጊዜው ተዘጋጅተው በሥ ራላይ ውለዋል ። በዚህም መሠረት ከ1967—1974 ለመደበኛ ትምህርት 36,316,490 እና ለመሠረተ ትምህርት 21,715,000 መጻሕፍት ታትመዋል ። [23]

ይሁንና የተዘጋጁት መጻሕፍት በዓይነ ትና በመጠን ፣ በተማሪዎች ዕድሜና ደረጃ እንዲሁም በየትምህርት ቤቱ ካለው የሣ ይንስ መረጃ ቁሳቁሶችና ሌሎች የማስተ ማሪያ መሣሪያዎች እንዲሁም ጥራት ካላ ቸው መምህራን እጥረት አንፃር ሲገመ ገም ተመጣጣኝ ናቸው ለማለት አይቻ ልም ።

ለመሠረተ ትምህርትና ለድኅረ መሠ ረተ ትምህርት የሚዘጋጁትን መጻሕፍት በሚመለከት ረገድ (በአገራችን ሰፍኖ የነ በረውን ማይምነት እስከ ስድስተኛ ዙር ድረስ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ወደ 55.2% ዝቅ ያለና [24] በተለይም በመካሄድ ላይ ያለው የስምንተኛው ዙር ተጠናቆ ከሰ ባተኛው ዙር ውጤት ጋር ተዳምሮ ሊጠቃ ለል ከማይምነት የሚላቀቀው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ቁጥር ከ50% በላይ የሚሆን በት ጊዜም ቅርብ በመሆኑ) በመጠንም ሆነ በዓይነት በቂ ሊሆኑ አይችሉም ። በአሁኑ ጊዜ በ4271 የንባብ ቤቶች የሚሰጠው ግል ጋሎትም ስፋት እያገኘ ካልሄደ የችግሩ መባባስ በቅርብ ጊዜ የሚከሰት ይመስላል ።

ሌላው በመማር — ማስተማር ሂደት ውስጥ ወሳኝነት ያለው የመምህራን ሚና ነው ። ይህንኑ ሀቅ በመረዳት በስምንት የአ ብዮቱ ዓመታት ውስጥ የአንደኛ ደረጃ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች እድገት በ200% ከፍ ለማድረግ ተችሏል ። በዚሁ ደረጃ ያለው የመምህራን ቁጥር ከ1966 ጋር ሲነፃፀር በ1974 በ102% እድገት አሳይ ቷል ። በተጨማሪም ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ አንድ የአፀደ ሕፃናት መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም በመከፈት እስከአሁን ድረስ ከ650 መምህራን በላይ ማሰልጠን ተችሎአል ። በአጠቃላይ ከአንደኛ እስከ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር (በቴክኒክ ሙያ የሚያስተምሩትን ጨምሮ) ከ1966 ጋር ሲነፃፀር በ1974 በ95.4% ጨምሯል ። በየትምህርቱ ደረጃ የመምህራን ብዛት በየዓመቱ ቢያድግም በማንኛውም ደረጃ የመምህራን ዕድገት ከተማሪዎች ብዛት ጋር ተመጣጣኝ አይደ ለም ።

Digitized by Google

የሥርዓተ ትምህርቱንና የመሕጻፍቱን ይዘትና ዝግጅት ለማሻሻልና ለማፋጠን የተደረገ ሙከራ ብቻ ለአንድ የትምህርት ሥርዓት ሂደት መሟላት በቂ አይሆንም ። የማስተማር — መማር ሞተር የሆነው መምህር የመጠንና የዓይነት እድገት ማሳየትና በአንፃሩም እውቀቱን ለማስተላለፍ የሚያደርገው ታታሪነት ወሳኝነት አለው። ይህም የሙያ ብቃትንና የርዕዮተዓለም ግንዛቤን ይጠይቃል ። እዚህ ላይ ሌኒን የመምህራንን ወሳኝ ሚና በማስመልከት ፤

> በት/ቤት ውስጥ በጣም ተፈላጊ ሰው መምህሩ ነው ። ከአጠቃላይ የማስተማርና የማስልጠን ሂደት ወሳኝ የሆኑት ነገሮች የመምህሩ የርዕዮተዓለም እምነት ፣ ልምድና የማስተማር ችሎታ ናቸው ። የት/ቤቱ እውነተኛ ጠባይና አቅጣጫ የሚወስነው በአካባቢው ባሉ ድርጅቶች በጎ ፈቃድ ወይም በተማሪዎች ማኅበር ውሣኔዎች ወይም በሥርዓተ ትምህርቱ ሳይሆን ትምህርቱን በሚሰጡ ሰዎች ነው።» [25]

ያለውን ማስታወስ ጠቃሚ ነው ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በተለይ የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የሙያ ብቃትንም በሚመለከት የተፈለገውን ያህል ነው ለማለት አይቻልም። ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት በውጭ መምህራንና የነበረውንም የአሰለጣጠን ፍልስፍና በመከተል ሰልጥነው በነበሩት ኢትዮጵያውያን መምህራን ይካሄድ የነበረው የትምህርት ሂደት የይዘትም ሆነ የመዋቅር ለውጥ ሲደረስበት የመምህራን እጥረት ታይቷል ። ለዚህ እጥረት ዋና ዋና ምክንያቶች ከካፒታሊስት አገሮች የመጡ መምህራን ወደ አገራቸው መመለስ ፣ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን መምህራን፣ህ/የማስተማር ሥራቸውን እየለቀቁ ወደሌሎች መሥሪያ ቤቶች መዛወር ፣ ለ/የአንዳንዶቹ በፀረ ሕዝብ ሴራ መሠማራት ፣ ሐ/የተቀሩትም መምህራን ሕዝባዊ ተሳትፎ ከፍ ማለት ይገኙበታል ። ሌላው ችግር መምህራን አዲስ ስለተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት በቂ እውቀት የሌላቸው መሆኑና ፣ እጩ መምህራንም በተለያዩ ምክንያቶች ለማስተማር በቂ እውቀት አለማግኘታቸው ነው ። በአጠቃላይ እነዚህና የመሳሰሉት ችግሮች ለትምህርት ጥራት እንቅፋት ሆነዋል ። ችግሮቹንም ለመፍታት ልዩ ልዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው። ከተወሰዱት እርምጃዎች በአጠቃላይና በከፍተኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ኢትዮጵያውያን መምህራን በብዛት ማሰልጠንና መቅጠር፣ ከሶሺያሊስት አገሮች መምህራን ለተወሰነ ጊዜ ማስመጣት ይገኙበታል። ይሁንና ችግሩን ለመቋቋም በየትምህርት ደረጃው የሚያስተምሩ መምህራን በገፍ መቅጠር የሚፈለገውን የመምህራን ጥራት ለመጠበቅ አላስቻለም ። ይህን ችግር ለመወጣት አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል ። ከዚህ ጋር የተጀመረው የድኅረ ምረቃ ፕሮግራም በሰው ኃይልም ሆነ በቁሳዊ መሰናዶዎች ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው ።

ሌላው እርምጃ የመምህራንን ርዕዮተዓለማዊ ግንዛቤ በተቻለ መጠን ከፍ ማድረግ ነው።መምህራንን የማሌ ርዕዮተዓለም ለማስታጠቅና ሙያቸውን ለማሻሻል ከ1969—1971 ድረስ ለ24686 በአጠቃላይ ትምህርት ፣ ለነባርና አዲስ መምህራን የተሃድሶ ትምህርት ተሰጥቷል ። [26] ቁጥራቸው በርካታ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት መምህራንም በየክረምቱ ወራት የርዕዮተዓለም ትምህርት በአገርም ሆነ በሶሺያሊስት አገሮች ውስጥ እየቀሰሙ ናቸው። ይህ ጥረት ያለማቋረጥ ይበልጥ በተጠናከረ መንገድ መቀጠል አለበት ። ከዚህ አንፃር ፣

> ... የመምህራኑ የርዕዮተዓለም ጥራት የሙያ ብቃትና የመምህርነት ሙያ ሊናረው የሚገባው ተወዳጅነት ተፈላጊውን

Digitized by Google

ደረጃ ካላገኘ ሶሻሊስታዊ የትምህርት ሥርዓት ለመገንባት ስለማይቻል ለመምህራን ተከታታይ የሆነ የርዕዮተ ዓለም ትምህርት እንዲሰጥ ወደ መምህርነት የሚገቡትን የሰፊውን ሕዝብ ወገናዊነት የተቀበሉ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ፤ [27]

በማለት የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የሰጠውን ወቅታዊ መመሪያ መጥቀሱ ተገቢ ነው ። የማሌ ርዕዮተዓለም ግንዛቤ የሌለው መምህር የማሌ ርዕዮተዓለም ጽንሰ ሀሳቦችን አገናዝቦና አጣጥሞ የተዘጋጁትን ሥርዓተ ትምህርትና የማስተማሪያ መጻሕፍት በትክክል ያስተምራል ለማለት አይቻልም ። ይህ ዓይነቱ መምህር አገሪቷ የገጠሟትን የኢኮኖሚና ፤ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች በሚገባ አጢኖ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ከራሱ የግል ጥቅምና ፍላጐት ለማስቀደም እንደሚያስቸግረውም መገመት ይቻላል ።

ይህ ሁኔታ በአብዛኞቹም ባይሆን ዛሬ በኢትዮጵያ ት/ቤቶች ውስጥ እየተከሰተ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህ አይነቱ አዝማሚያ በአስቸኳይ የሚታረምበት ዘዴ ተቀይሶ የማሌ ርዕዮተዓለም ግንዛቤ የመምህራንን አመለካከትና አስተሳሰብ ካልሰረጸ በቀር በትምህርት ጥራትም ሆነ ግብ መምታት የሚያበረታታ ሁኔታ ለመፍጠር ያዳግታል ። ለዚህም መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉት እርምጃዎች፣ ሀ/ በመምህራን የስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የማሌ ርዕዮተዓለምን ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ ማስያዝና ፣ ለ/ አሁን በሥራ ላይ የተሰማሩት መምህራንን በሞላ በተከታታይ ሰፋ ያለ የማሌ ጥናት የሚአገኙበት ሁኔታ እንዲጠናከር ማድረግ ይገኙበታል ። በግለ ሰብ ደረጃም መምህራን የማሌ ርዕዮተ ዓለም ግንዛቤአቸውን ከፍ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ማሳየት ይኖርባቸዋል ። ሣይንሣዊ ትምህርት መስጠትና ሳይንሣዊ ምርምር ማድረግ የሚቻለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በትምህርቱ ዘርፍ የሚታየው እንቅስቃሴ

በሶሻሊስት መርህ ላይ ተመሥርቶ የተቀየሰው የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ፣ የመምህራንን በሳይንሳዊ ርዕዮተዓለም ማነጽ ፣ ተፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎችን ለምሳሌ መጻሕፍትን የመሳሰሉትን ማዘጋጀት በአጠቃላይ የነበረውን አድኃሪ የትምህርት ሥርዓት በማፈራረስና በምትኩ አዲሱን የትምህርት ሥርዓት መቀየስ የሚጠይቅ ነው ። በዚህ መሠረት ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ በትምህርት ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ከፍ ብሏል ። የአጸደ ሕፃናት ትምህርት ፣ የመሠረተ ትምህርት ፣ የገጠር ጐልማሶች የሙያ ትምህርት፤ የተልዕኮና በአጠቃላይም የልዩ ልዩ የከፍተኛ ትምህርት አውታሮች ተዘርግተዋል ። የተማሪዎች ተሳትፎም በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል ።

አምራች ፣ ተመራማሪና የላቀ ዜጋን ለማፍራት ተማሪው በሙያው የሚኖረው የንድፈሃሣብና የተግባር ችሎታ ወሳኝነት አለው። የተወሰኑ አዳዲስ ነገሮችን ለመቅሰምም ሆነ የፈጠራ ችሎታውን ለማዳበር የሚረዱ መጻሕፍትና ሌሎችም የማስተማር—መማር አጋዥ የትምህርት መሣሪያዎች በት/ቤቶች ተሟልተው መቅረብ አለባቸው ። ይህንን ለማሟላት የትምህርት ማዕከላት ዛሬ በየአውራጃውና በየአካባቢው እየተቋቋሙ ናቸው።

እነዚህ ማዕከላት በሥርዐተ ትምህርቱ ለውጥና መሻሻል ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። የአዳዲስ ፈጠራዎች ማስታወቂያና መፍለቂያም ከመሆናቸው በላይ መምህራን ፣ የት/ቤቶች ሥራ መሪዎች ፣ የትምህርት ባለሥልጣኖችና ተቆጣጣሪዎች በአንድነት ሆነው በሚመለከታቸው አካባቢ ስለሚካሄደው ትምህርት

Digitized by Google

ግብ መምታት ፥ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስለአለው ተዛማጅነት ፥ ስለትምህርቱ አሰጣጥና በተግባር ላይ ሲውል ስለተከሰተው ችግር ወይም ውጤት ስለ ልምድ መለዋወጥና በየጊዜው ስለሚወጡ አዳዲስ መመሪያዎችና ፈጠራዎች የሚ ወያዩባቸው ትምህርታዊ መድረኮች መሆናቸው በተግባር እየታየ ነው ።

የእነዚህ የትምህርት ማዕከላት መጠናከርና ይበልጡንም እየተስፋፋ መሄድ የሥርዓተ ትምህርቱን ሶሻሊስት ይዘት ለማ ጠናከርና በአንፃሩም የመምህሩንም ሆነ የተማሪውን የፈጠራ ችሎታ ለማበረታታት ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ።

ትምህርትን በዲሞክራሲያዊነት ለማ ዳረስ አብዮታዊው መንግሥት ልዩ ልዩ እርምጃዎችን ወስዷል ። ከእነዚህም እርም ጃዎች መካከል የመንግሥትንና የሰፊውን ሕዝብ ጥረት ለማስተባበርና በትምህርቱ ሂደት የሕዝቡን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የግል ት/ቤቶችን የሕዝብ ያደረገው አዋጅ 54/68 እና ለመንግሥት ት/ ቤቶች ሕዝ ባዊ አመራር ለመስጠት የወጣው አዋጅ 103/69 ይገኙበታል ። እነዚህ አዋጆች ሕዝባዊ ተሳትፎን በማጠናከር ለትምህ ርቱ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድ ርገዋል።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የትምህ ርት ጥቅም ባልታወቀባቸው ኋላቀር አካ ባቢዎችም ት/ቤቶችን በመሥራት የትም ህርትን ስርጭት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሦ ስት እጅ በላይ ለማሳደግ ተችሎአል ። የት ምህርትን ዕድልም ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ለማሠራጨት የሚደረገው ሙከራ አዝ ማሚያው የሚያበረታታ ሆኖ ይገኛል ። ለዚህም አንዱ ምሣሌ የአጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ነው። በመ ዋቅር ረገድ ቀድሞ በመደበኛ ትምህርት ብቻ ተወስኖ የነበረው ትምህርት በአሁኑ

በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ አራት ክልል ውስጥ የሚገኘውና በአካባቢው ህዝብ በመሠራት ላይ ያለው « ካራማራ » የህዝብ ት/ቤት

Digitized by Google

ወቅት አጸደ ሕፃናትንም አቅፎ ይገኛል። አስተባባሪም የሚሆን መንግሥታዊ ድር ጅትም ተቋቁሞአል።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በመጠነኛ ደረጃ የአጸደ ሕፃናት ትምህርት ይሰጥ የነበረው በቤተክርስቲያናትና በመስጊዶች ብቻ ስለነበረ ሕፃናት በለጋ አእምሮአቸ ውና ከፍተኛ ጥንቃቄ በሚያስፈልጋቸው ዕድሜ ወቅት መቅሰም የሚገባቸውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተግባር ግንዛቤ ከማግኘት ይልቅ አንዳንድ የሃይ ማኖት ግንዛቤዎችን በአእምሮአቸው ውስጥ ስለሚቀርጹ በፈጠራ ችሎታቸው ላይ አፍራሽ የሆነ ተጽዕኖ ነበረው ።

በሕዝባዊ ድርጅቶች ትብብርና በመን ግሥት ድጋፍ ከአብዮቱ ወዲህ በማበብ ላይ የሚገኙት የዓፀደ ሕፃናት ዕድገት ከምንጊዜውም የበለጠ ተስፋፍቷል ። በ1974 በ505 ዓፀደ ሕፃናት 50,400 ሕፃናት ትምህርትና እንክብካቤ እንዲያገኙ ተደ ርጓል ። በዚህ መሠረት ሕፃናት ከተለያዩ ኋላቀር የባህል ተጽዕኖዎች ተላቀው እንዲ ያድጉ አስፈላጊውን እንክብካቤና ጥንቃቄ ለማድረግ እየተሞከረ ነው ። ሥርጭቱንም በሚመለከት ረገድ በ1966 በዓፀደ ሕፃ ናት ከታቀፉት ሕፃናት 70 በመቶ በአዲስ አበባና በአሥመራ የነበሩ ሲሆን ፣ በክ ፍላተ ሀገር በሚገኙ ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ዓፀደ ሕፃናት እየተስፋፉ በመ ምጣታቸው በ1972 የአዲስ አበባና የአ ሥመራ የሥርጭት ድርሻ ከጠቅላላው ሕፃናት ብዛት ጋር ሲነፃፀር 39በመቶ ሊሆን ችሏል ። ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት ምንም ዓይነት የዓፀደ ሕፃናት አገልግሎት ያልነ በራቸው የአርሲ ፣ የባሌና ፣ የኢሉባቦር ክፍላተ ሀገሮችም በ1972 ከጠቅላላው ሥርጭት 10 በመቶ ያህል ሕፃናትን ያስ ተናግዳሉ ።

ሌላው ከፍተኛ ሕዝባዊ ተሳትፎና የአብ ዮታዊ መንግሥት ጥረት የሚታይበት የት ምህርት መስክ መሠረተ ትምህርት ነው።

በአምስት የመግሪያ ቋንቋዎች ይሰጥ የነ በረው መሠረተ ትምህርት በአሁኑ ጊዜ 90 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚሸፍኑ በ15 ብሔረሰብ ቋንቋዎች እየ ተሰጠ መሆኑንና አጥጋቢ ውጤትም መታ የቱ የታለመውን ዘመቻ ግብ በማቃረብ ላይ ይገኛል ።

ሌላው የጉልማሶቹ የድኅረ መሠረተ ትምህርት ሁኔታ ነው ። ዓላማው ጉልማ ሳውን ማንበብና መጻፍ ማስቻሉ ብቻ ሳይ ሆን የማሌ ርዕዮተ ዓለም ግን ግንዛቤውን ከፍ ለማድረግና በዕለት ከዕለት ተግባሩ የሚከሰቱትን ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች እንዲቋቋም መፍት ሔም ለመስጠት እንዲሞከር ለማድረግ ነው ። ከዚህ አኳያ በኢሠፓአኮ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ መሠረት ለድኅረ መሠ ረተ ትምህርት ጉልማሳው በደረጃው የሚያስፈልገውን የርዕዮተዓለም ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ትምህርት እንዲዘጋጅና የሙያ ትምህርት እንዲሰጥ በወሰነው መ ሠረት እርምጃዎች ተወስደዋል ። ስለሆነም ለጉልማሶች የፖለቲካ ትምህርት የሚያገ ገለግሉ መጻሕፍት በ9 ብሔረብሰብ ቋን ቋዎች ተዘጋጅተዋል ። በየወረዳው የገጠር ጉልማሶች ማሠልጠኛ ጣቢያ ለማዳረስ የተ ጀመረውም ጥረት ቀጥሎአል ። እስካሁን በተቋቋሙት 386 ጣቢያዎች 284,000 ገበሬዎችን በተለያዩ ሙያዎች ለማሰል ጠን ተችሎአል ። ይህ ጥረት ዛሬ የአብዮ ታችን ዕድገት በደረሰበት ደረጃ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የቴክኖሎጂን አጠቃቀም ለማስፋፋት ከሚደረገው ጥረት ማለትም ከገበሬዎች ሁለገብ ትምህርት ጋር ሊቀ ናጅ ይገባል ። በኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩ 2,400 [28] ጉልማሶች የልዩ ልዩ ሙያ ማሻያና የቀ ለም ትምህርት ያቀፈ የተልዕኮ ትምህርት እየተሰጠ ነው ።

ከዚህም በላይ ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ሰፊው ሕዝብ ለመማር የሚአደረገውን

Digitized by Google

ሴቶች በመሠረተ ትምህርት ላይ

ከበ—ቡ ወደ ንባብ ከዚያም ወደ . . .

Digitized by Google

ጥረት ለማሟላት በማታ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ፕሮግራም እስከ 1973 ድረስ በ6615 መምህራን አማካኝነት 206,479 ጐልማሶች ትምህርቱን መከታተል ችለዋል ።[29] በአጠቃላይና በከፍተኛ ትምህርትም ከፍተኛ የዓይነትና የመጠን ለውጥ ተደርጓል ።

በቅድመ አብዮት የነበረው የአጠቃላይ ትምህርት ስርጭት በጣም ኋላቀር ከመሆኑም በላይ በቀጠና ስርጭቱ ያልተመጣጠነና አዝጋሚ ፣ እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ ለይስሙላ በአንዳንድ አካባቢዎች ት/ቤት እየተከፈተ በተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ተወስኖ የሚቀር እንደነበረ ግልጽ ነው ።

ለምሳሌ ስርጭቱ ምን ያህል አዝጋሚ እንደነበረ ለመረዳት ዘመናዊ ትምህርት በአገራችን ከተመሠረተ ከ70 ዓመታት በኋላ በ1966 የነበረውንና በስምንት የአብዮት ዓመታት ውስጥ የተደረሰበትን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤት ከሚከተለው ሰንጠረዥ ለማየት ይቻላል ።

መሳተፍ ችለዋል ።

በ1966 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መሳተፍ ከሚገባቸው ወጣቶች የተሳትፎ ዕድል ያገኙት 3.1 በመቶ ብቻ ሲሆን ፣ በ1974 የትምህርት ዕድል ያገኙት 9 በመቶ ነበሩ ። ይህ እንግዲህ በስምንት ዓመታት ውስጥ የተገኘ ድል ነው ። ከ1966—1974 የታየው ዓመታዊው አማካይ ዕድገት 14.4 በመቶ ነው ። ይህ ደግሞ ከመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ዓመታዊ አማካይ ዕድገት (11.9 በመቶ) ጋር ሲነጻጸር በጣም ፈጣን ሆኖ እናገኘዋለን ። በተጨማሪም ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት ተረስተው በነበሩት ክፍለ ሀገራት ለምሳሌ ጋሞ ጐፋ ፣ ባሌ ፣ ከፋና ለመሳሰሉት በትምህርት ስርጭት ረገድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ።

በአንደኛ ፣ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከፍ ብሏል ። ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የወጣት ሴቶችን ተሳትፎ ብንወስድ በ1966 32 በመቶ የነበረው በ1974 36 በመቶ

በአንደኛ ደረጃ (1—6) የት/ቤቶች ፣ የተማሪዎችና የመምህራን ቁጥር

1966			1974		
ት/ ቤት	ተማሪዎች	መምህራን	ት/ ቤት	ተማሪዎች	መምህራን
2,754	856,831	18,646	6,208	2,374,362	37,844

ምንጭ፣—አጠቃላይ የትምህርት ሥርጭት ፣ ት/ ሚ ፣ ገጽ 9 (ያልታተመ)

በተጨማሪም በ1966 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት ከሚገባቸው ጠቅላላ የአገሪቷ ሕፃናት መካከል (7—12) ትምህርት ያገኙት 19 በመቶ ሲሆን ፣ የቀሩት 81 በመቶ ግን ተመሳሳይ ዕድል ተነፍጐአቸው ነበር ። ከስምንት ዓመታት አብዮታዊ ትግል በኋላ ግን በ1974 ትምህርት ማግኘት ከሚገባቸው ሕፃናት መካከል 47.1 በመቶ መድረሱ አብዮታችን የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደጉ ብቻ ሳይሆን ያለፈው ሥርዓት የጣለባቸውን ድርብ ጭቆናን ለማስወገድ የተደረገውንም የትግል ውጤት ያመለክታል ።

በሌላም በኩል በከፍተኛ ተቋሞች የማታ ትምህርትን ብንመለከት ዛሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ ከ8,000 የሚበልጡ የማታ ተማሪዎች አሉ ። ይህ ሁሉ አብዮታዊው መን

Digitized by Google

ግሥት ለትምህርቱ ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የተገኘ ድል ነው ።

የፊውዳሉ ሥርዓት የሚገባውን ትኩረት ከነሳቸው የሙያ የትምህርት ዘርፎች አንዱ የቴክኒክ ትምህርት ነበር ። የፊውዳሉ ሥር ዓት ለቴክኒክ ሙያ ከነበረው ጥላቻና ንቀት የተነሳ ሙያው ተወዳጅነት አልነበረውም። የእጅ ሙያ እንደስድብ ከመቆጠሩም በላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከበሬታና ተቀባይነት አልነበረውም ። በ1966 በከፊልና ሙሉ ለሙሉ የቴክኒክ ትምህርት በሚሰጡ መደ በኛ ት/ቤቶችና በተለያዩ ድርጅቶች አማካ ኝነት ይሰጡ በነበሩት የቴክኒክ ሙያ ትም ህርት ተካፋይ የነበሩት ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት 1,533 ነበር ። ከአብዮቱ ፍንዳ ታ ወዲህ ግን ሁኔታውን በመለወጥና ፕሮ ግራሙንም በተጠናከረ አኳኋን ለመስጠት በመታቀዱ የተጠናከረ የቴክኒክ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ቁጥር በ1974 ፣ 5119 ደርሰዋል ። ከዚህም በቀር በተ ለያዩ ክፍላተ ሀገር በሚገኙ 28 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሰው ኃይልም ሆነ በ መሣሪያ የተሟላና በተጠናከረ መንገድ የቴ ክኒክና የሙያ ትምህርት ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው ።

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ት/ቤቶች ከአብ ዮቱ ፍንዳታ በፊት የነበራቸው ዓላማ የኢ ትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጐት በማ ራመድ ላይ ያተኮረ መርሀ ግብር ነድፎ በሥራ ላይ ማዋልና ማስፈጸም አልነበረም። በአንፃሩ በዕርዳታ ስም እጃቸውን አስገብ ተው በአስተዳደሩና በትምህርት አመራሩ ላይ ተጽዕኖ ያደረጉ የነበሩትን የኢምፔሪ ያሊስቶች ፍላጐትና ጥቅም በማስፈጸም ላይ ያተኮረ ነበር ለማለት ይቻላል ። ከእ ርሱን ፈቃድ ውጭ የሆነመርሀ ግብር ለመንደፍ ቢሞከር ደግሞ የሚሰጡትን ርዳታ ያቋርጣሉ ። በዚህም ምክንያት የፊውዳሉ ገዥ መደብ የአገሪቷን ነባራዊ ፍላጐት ለውጭ ርዳታ ሰጪ ካፒታሊ ስት አገሮች ሸጦት ነበር ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም ።

በከፍተኛ ትምህርት ቤቶችም ሲሰጥ የነ በረው ትምህርት በዓላማና በይዘት ሲገመ ገም ተማሪው በመረጠው መስክ በቂ ሥል ጠና የማያስገኝለትና በአጠቃላይ ዕውቀት ላይ ያተኮረ ነበር ። በተለይ በማኅበራዊ ሳይ ንስ የሚሰጠው ትምህርት ውስጣዊ ውህደ ትን ባለማጤኑ በሥራ ስምሪቱና በማኅበራ ዊ ግንኙነቱ የሚገጥሙትን ሙያ ነክና ውስ ብስብ ማኅበራዊ ችግሮች ለመቋቋምና መ ፍትሔም ለመስጠት ከሚአዳግትበት ደረጃ ተደርሶ እንደነበር እንገነዘባለን ። በከፍተኛ ት/ኮሚሽን አስተባባሪነትም በሳይንስና ቴ ክኖሎጂ ፣ በማሌ ትምህርትና በሶሻል ሳይ ንስ ወዘተ - - - የመማክርት ጉባኤዎች ተቋ ቁመው አስፈላጊውን የሥርዓተ ትምህርትና የሰው ኃይል አሰለጣጠን በማሌ ርዕዮተዓ ለም ግንዛቤ አንጻር ለማስተካከል ሙከራ እየተደረገ ነው ። ከ1975 ወዲህም የማሌ ትምህርት መሰጠት መጀመሩም ከዚሁ አን ጻር በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው ።

በተጨማሪም ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ከወዳጅ ሶሻሊስት ሀገሮች ዩኒቨርስቲዎች ጋር ባደረጉት የፕሮቶኮል ስምምነት መሠ ረት እንቅስቃሴያቸውን የሚያዳብሩና ለወ ደፊቱም ብሩህ ተስፋ የሚሰጡ ሁኔታዎች መፈጠር ችለዋል ። የከፍተኛ ትምህርት ኮ ሚሽንም ከሶቪዬት ኅብረት ፣ ከቼኮዝላቫ ኪያ ፣ ከጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ፣ ከዩጐዝላቪያ ፣ ከሐንጋሪ ፣ ከኩባ፣ ከቡልጋ ሪያና ከሌሎችም ሶሻሊስትና ተራማጅ ሀገ ሮችጋር የፕሮቶኮል ስምምነት በማድረግ የነፃ ትምህርት ፣ የመምህራንና የትምህርት መሣሪያዎች ወዘተ- - - እርዳታ እያገኘ ከመ ሆኑም በላይ የምርምርና ጥናት ውጤቶች ንና የትምህርት ባለሙያዎችን ልውውጥ እያካሔደ ነው ። [30] ከዚህም በላይ የሶሻሊ ስት አገሮች በርካታ የነፃ ትምህርት ዕድል ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ ተማሪዎች በመስጠ ታቸው በየዓመቱ እስከ 1000 ድረስ የሚሆኑ ተማሪዎች ወደ ሶሻሊስት ሀገሮች ይሔዳሉ።

Digitized by Google

በውጭ አገር በትምህርት ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያን

(ይኸ ሰንጠረዥ በታዳጊ አገሮች ውስጥ በትምህርት ላይ ያሉ ኢትዮጵያውያንን አይጨምርም ፤ ከዚህም በላይ በየዓመቱ የተጠቀሰው የተማሪዎች ቁጥር ከዚያ ዓመት በፊት የሄዱትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ።)

	በካፒታሊስት አገሮች*	በሶሻሊስት አገሮች
1965	2215	625
1666	2264	636
1967	2694	360
1972	3133	2885
1973	3600	4098
1974	4264	4733

ምንጭ ፦ የኢትዮጵያ አመታዊ የእስታቲስቲክስ መጽሔት ፣ 1967 ፣ 1968 ፣ 1969 ፣ 1970 ፣ 1972 ፣ እና የከፍተኛ ትምህርት ኰሚሽን የውጭ እርዳታና የነፃ ትምህርት ዋና ክፍል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት አጠቃላይ ዕድገት ቢያሳይም ልዩ ልዩ ችግሮች የሉበትም ማለት አይደለም ። ዛሬ በከፍተኛ ት/ቤቶች እጅግ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የትምህርት ጥራት ጉዳይ ነው ። ለዚህም ከሚጠቀሱት ›ክንያቶች መካከል የመማሪያ መሣሪያዎችና የገንዘብ እጥረት ፣ ወደ ከፍተኛት/ቤቶች የሚገቡት ተማሪዎች የተፈለገውን ያህል ችሎታና የትምህርት ጥራት የሌላቸው መሆኑ ፣ በሌላ አነጋገር የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት ማቆልቆሉ ፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የከፍተኛ ት/ቤቶች መምህራን የትምህርት ደረጃ ዝቅ ያለ በመሆኑና ያላቸውም ችሎታ ላሉበት ደረጃ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ የሚሉት ይገኙበታል ።

እነዚህ ችግሮች በቀላሉና በፍጥነት የሚፈቱ ናቸው ለማለት ባይቻልም ፣ የትምህርቱን ዘርፍ የሶሻሊስት ፈር አስይዞ ለመገንባት በሚካሔደው ትግል መፈታት ይኖርባቸዋል ።

ከፍተኛ ት/ቤቶች በተለይም አ.አ. ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች መምህራንንም ሆነ የአገሪቱን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት ለማርካት የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በተለያዩ የትምህርት መስኮች ከፍቶ በማካሔድ ላይ ይገኛል። ወደፊትም በቀሩት የትምህርት መስኮች ይህ ዓይነቱን መርሐ ግብር ይበልጥ ለማጠናከርና ለማስፋፋት ዕቅድ አለ። የዕቅዱ በሥራ መዋል አሁን የሚታየውን የመምህራን እጥረት ሊያስወግድ ይችላል ።

ባለፈው ሥርዓት ከፍተኛ ትምህርትን በሚመለከት የነበረው የተማሪ አቀባበል ፖሊሲ ከገጠሬው ተማሪ ለከተሜው ተማሪ የበለጠ ዕድል የሚሰጥ ነበር ። ከ1961—1962 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን አቀባበል በማስመልከት የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፣ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት37በመቶ ብቻ ከሆኑት ከሐረርጌ ፣ ከሸዋበተለይም ከአዲስ አበባና ከኤርትራ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይገቡ የነበሩት ከጠቅላላው ተማሪ 89 በመቶ ሲሆኑ ፣ የሕዝብ ብዛታቸው 63 በመቶ ከሆኑት ከሌሎች ክፍላተ ሀገር ደግሞ የገቡት 11 በመቶ ነበሩ።ይህ የሚያሳየው በአማካይ ቁጥር አንድ የሸዋ ወይም የኤርትራ የ

* ከአብዮቱ ወዲህ ወደ ካፒታሊስት አገሮች የሄዱት ተማሪዎች ቁጥር በዝቶ የታየው በገል ለትምህርት እያሉ የሄዱትን ሁሉ የጨመረ በመሆኑ ነው ።

Digitized by Google

12ኛ ክፍል ተማሪ ወደ ዩኒቨርስቲ ለመግባት የነበረው ዕድል ከኤሉባቦር የ12ኛ ክፍል ጋር ሲነጻጸር በ14 እጅ የበለጠ እንደነበረ ነው። ከዚህም በቀር በ1960ከሀገሪቷ ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት 3.5 በመቶ ከነበረው ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የገቡት ተማሪዎች ብዛት ከጠቅላላው 48.8 በመቶ እንደነበረ ጥናቶቹ ይጠቁማሉ ።

ከላይ ከተጠቀሱት አሐዞች እንደምንረዳው በፊውዳል ኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት የተዘረጋው በከተማ የተደላደለ ኑሮ ለሚኖሩ ለጥቂት ሰዎች ልጆች እንደነበረና ፣ በአጠቃላይ አርሶ አደሩ ከከፍተኛ ትምህርት የተገለለ እንደነበረ ነው ። ይህንን የተሳሳተ አሠራር ለማስተካከል ከ1971 ጀምር ወደከፍተኛ ት/ቤቶች የሚገቡትን ተማሪዎች ለየክፍለ ሀገሩ የተተመነ ድርሻ(ኮታ) በመስጠት የተሞከረው ሙከራ ለአርሶ አደሩና በዝቅተኛ ደረጃ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ልጆች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል መስጠቱ አያጠራጥርም። ሆኖም ይህ አሠራር የትምህርቱን ጥራት እንዳይጐዳ በጥንቃቄና ስልት ባለው ሁኔታ ተጣጥሞ የሚቀጥልበት መንገድ አሁንም መፈለግ አለበት ።

የአዲስ ተማሪዎችን አቀባበል በሚመለከት ረገድም ከፍተኛ ት/ቤቶች የመቀበል ችሎታቸውን ለማሳደግ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም፣ ይህ ጥረት እንዲሳካ ከመኝታ ቤትና የመማሪያ ክፍሎች መጨመር ፣ ለዚህ ደረጃ ብቃት ያላቸው መምህራን ፣ የቤተ መጻሕፍት በታና የመጻሕፍት ፣ የላቦራቶሪና የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ሌሎችም ለማስተማር—መማር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ከመሟላታቸው ጋር መገናዘብ አለበት ።

ዛሬ ከፍተኛ ት/ቤቶች የሚቀበሏቸው ተማሪዎች ቁጥር በቅድመ አብዮት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል ። ለምሳሌ በ1966 በከፍተኛ ት/ቤቶች ውስጥ ይሳተፉ የነበሩ የተማሪዎች ቁጥር 8151 ሲሆን ይኸው ቁጥር 1974፣14,985 ደርሷል ።

የከፍተኛ ት/ቤቶች ምሩቃንም ከዓመት ወደ ዓመት ዕድገት እያሳየ ነው ። በዚህ ረገድ በ1965 ፣ 1506 የነበረው የምሩቃን ቁጥር በ1974 ወደ 4,659 አድጓል ።[31] በመሆኑም በስምንት የአብዮት ዓመታት ውስጥ ከውስጥና ከውጭ አድኅሮት ኃይላት በደረሱብን የኢኮኖሚ ውድቀትና አሁንም ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ የደረስንበት በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል የማስመረቅ ዕድገት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

ማጠቃለያ

ትምህርት ከርዕዮተዓለም አንጻር ሲታይ በማንኛውም በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ እንዲያገለግል የሚታቀደውና በተቀዳሚም የሚያገለግለው የገዥውን መደብ ጥቅምና ፍላጐት ነው ። ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ አንጻር ትምህርት የላዕላይ መዋቅር አካል ቢሆንም ፣ ታህታይ መዋቅሩን የሚያንጸባርቀውና በታህታይ መዋቅሩም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው በዚያ ኅብረተሰብ ውስጥ የገዥውን መደብ ጥቅምና ፍላጐት የሚያገለግል በመሆኑ ነው ።

ነገር ግን የትምህርት ዕድገት እንደማንኛውም ዕድገት ዲያሌክቲካዊ በመሆኑ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የገዥውን መደብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጐት ለማስከበሪያና ለማዳበሪያ ብቻ የሚውል አይደለም ። የብዝበዛ ሥርዓትን ለመገርሰስ ፣ ተጨቋኝ መደቦች ለሚያደርጉት ጥረት አጋዥነቱ እንደየሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ ይሔዳል ። ስለዚህ ምንም እንኳ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ የትምህርት ተቀዳሚ ተግባር የገዥውን መደብ ጥቅም ማስከበርና ማዳበር ቢሆንም በአጠቃላይ ትምህርት የመደብ ትግል መድረክ ነው ።

እነዚህን ሁለት ትምህርት ነክ ቁም ነገሮች ማለትም ትምህርት የላዕላይ መዋቅር አካል መሆኑንና ትምህርት የመደብ ትግል መድረክ መሆኑን በወደቀው አድኃሪ ሥርዓት የነበረው የአገራችን ዘመናዊ ትምህርት ዕድገት አረጋግጦልናል ። እንደሚታወቀው

Digitized by Google

ትምህርት በአገራችን በአንድ በኩል የፊው
ዳሉን ገዥ መደብና የተባባሪውን የኢምፔ
ሪያሊዝምን ጥቅም አስከባሪና አዳባሪ እን
ዲሆን ታቅዶ ይህንኑ ሚና ተጫውቷል ።
በሌላ በኩል ደግሞ አድኃሪውን ሥርዓት ለ
መገርሰስ በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ለምሳሌ ፣
በተማሪዎች ንቅናቄና በአስተማሪዎች ንቅ
ናቄ ያደረገው አስተዋጽኦ የማይናቅ መሆኑ
የታወቀ ነው ።

ትምህርት የላዕላይ መዋቅር አካልና
የትግል መድረክ መሆኑን መገንዘብ
አሁን ለተያያዝነው የሶሺያሊስት ትምህ
ርት ግንባታ ተግባር እጅግ አስፈላጊ መሆ
ኑን መረዳት ያስፈልጋል ። በአንድ ኅብረ
ተሰብ ውስጥ አብዮት ፈንድቶ የታህታይ
መዋቅር (የምርት ግንኙነቶች) ለውጥ ሲደ
ረግ የላዕላይ መዋቅሩም ይለወጣል ። ይህም
የሚሆነው የላዕላይ መዋቅሩ የታህታይ መዋ
ቅሩ ነጸብራቅ በመሆኑ ነው ። ሆኖም የላዕ
ላይ መዋቅሩ ለውጥ የታህታይ መዋቅሩን
ለውጥ ብቻ ተከትሎ ከመቅጽበትና ያለ ዕቅ
ድ የሚከናወን አይደለም ። አብዮቱ በታህ
ታይ መዋቅሩ በኩል መሠረታዊ ድሎችን
ከተጐናጸፈ በኋላም እንደ ትምህርት ያሉት
የላዕላይ መዋቅሩ ልዩ ልዩ ክፍሎች የትግል
መድረክነታቸውን ይቀጥላሉ ። በተለይም
በታኅታይ መዋቅሩ (በኢኮኖሚው) ውስጥ
ሽንፈት የደረሰባቸው ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ
ክፍሎች በላዕላይ መዋቅሩ ልዩ ልዩ ክፍሎ
ች (ፖለቲካ ፣ ትምህርት ፣ ኪነጥበብ ፣ ሕግ
ወዘተ . . .) ውስጥ በመሰግሰግ አድኃሪ ዓላ
ማቸውን ለማሳካት የመጨረሻ የሞትሽረት
ትግል ያካሂዳሉ ።ስለዚህ በታህታይ መዋ
ቅሩ በኩል የተገኙትን የአብዮቱን ድሎች
እንደገና እንዳይነጠቁ ለማድረግ ፣ ለማጠና
ከርና ተጨማሪ ድሎችም ለመጐናጸፍ በአ
ፋጣኝ የላዕላይ መዋቅር አብዮትን ማቀድና
ማራመድ ያስፈልጋል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት አድኃሪውን
ሥርዓት አፈራርሶ አዲሱንና ተራማጁንሥር
ዓት በመገንባቱ ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ
ከሚታይባቸው መስኮች መካከል የትምህ
ርቱ መስክ አንዱ ነው ። አብዮታችን ለሶሺ
ያሊዝም ግንባታ ቅድመ ሁኔታዎችን በማ
መቻቸት ላይ የሚገኝ አብዮት እንደመሆኑ ፣
የትምህርት አስፈላጊነት ከምንጊዜውም ይበ
ልጥ አብዮቱ አሁን በደረሰበት የዕድገት ደ
ረጃ ጐልቶ በመታየት ላይ መገኘቱም የአ
ጋጣሚ አይደለም ። ሌኒን በአንድ አብዮት
ሂደት የትምህርትን አስፈላጊነት ሲያብራራ

> ሠርተአደሮች ዕውቀት እየጠማ
> ቸው ነው፣ ምክንያቱም ለማሸነፍ ይፈ
> ልጉታልና ። ከሠርተአደሩ ሕዝብ ከአ
> ስሩ እጅ መካከል ዘጠኙ ነፃ ለመው
> ጣት በሚያካሂዱት ትግል ትምህርት
> ዓይነተኛ መሠሪያቸው መሆኑን ተገ
> ንዘበዋል ። በዚህ ረገድ ለሚያጋጥማ
> ቸው ሽንፈት ምክንያቱ የትምህርት
> ማጣት መሆኑን ስለተረዱ ትምህርት
> ለሁሉም ሊዳረስ የሚችልበትን ሁኔታ
> መፍጠር የነሱ ኃላፊነት ነው ።[32]

ያለውም ፍትሕ ፣ እኩልነት ዕድገትና ሶሺ
ያሊዝምን ዓላማው አድርጐ የተነሳ አብዮት
ትምህርትን በማስፋፋት በመደብ ትግል መ
ሣሪያነት ካልተጠቀመበት ግቡን ሊመታ
እንደማይችል ለመጠቆም ነው ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ የትምህርት አብ
ዮት ማቀድና ማካሔድ የሚኖርባትም ስለ
ዚህ ነው ። የባህል አብዮት አካል የሆነው
የትምህርት አብዮት የሚከናወነውም በግብ
ታዊነትና ሙሉ በሙሉ ከመቅጽበት ሳይ
ሆን በዕቅድና ያለማቋረጥ በተከታታይ መ
ሆን እንደሚገባው ማስታወስ ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ የኢሠፓአኮ መመሥረት በ
ኢትዮጵያ የትምህርቱን መስክ ሶሺያሊስ
ታዊ ፈር በማስያዙ ረገድ ቅድመ ሁኔታ የሆ
ነውን ለትምህርቱ ዘርፍ ርዕዮተዓለማዊ አ
መራር ሊሰጥ የሚችለውን አስተማማኝ የሆነ
ድርጅታዊ ማዕከል አስገኝቷል።ከኢሠፓአኮ
ዋና ዋና ተግባሮች መካከል አንደኛው ማር
ክሲዝም ሌኒኒዝምን በስፋት በሰፊው ሕዝብ

Digitized by Google

ውስጥ ማስራጨት መሆኑ የታወቀ ነው ። የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ የሚሰራጭበት አንዱ ዋንኛው መድረክ ደግሞ መደበኛ ትምህርት መሆኑ ግልፅ ነው ። በዚህም መሠረት ከአብዮቱ ወዲህ ትምህርትን በሰፋት ለማዳረስ የተደረገው ትግልና የተገኘው ውጤት የሚያበረታታ ነው ። «ትምህርት ለምርት ፥ ለሳይንሳዊ ምርምርና ለሶሺያሊስት ንቃተ ሕሊና» በሚለው መርህ መሠረት ፥ ትምህርት ቤቶችን በብዛት በመክፈት የትምህርትን ሥርጭት ለማስፋፋት ፥ የማሌ ሳይንስ ትምህርቶችን በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ለማስተዋወቅና በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችም የማሌን ትምህርቶች ለማስተዋወቅ ቅድመ ዝግጅቱን በማሟላት፥ አጸደ ሕፃናትን በማስፋፋት ፥ ለሙያ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና የልዩልዩ የሙያ ት/ቤቶችን ቁጥር በማበራከት ረገድ የማይናቅ ብዙ ሥራ ተሠርቷል ። በተለይም ሰፊው ሕዝብ በንቃት ላይ ተመስርቶ በሚያደርገው ትግል ታሪክ ሰሪነቱን በውል ሊያረጋግጥ የሚችለውና በፖለቲካውም ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ሊኖረው የሚችለው በመጀመሪያ ከማይምነት ሲላቀቅ በመሆኑ ፥ በዚህ አንጻር በተከታታይ በተካሔደው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ እስከ ስምንተኛው ዙር መጨረሻ ድረስ ፥ አብዮቱ ሲፈነዳ 93 በመቶ የነበረውን የማይማን ቁጥር ወደ 50 በመቶ ገድም ዝቅ ለማድረግ መቻሉ ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደናቂነትን ማትረፉ የሚያስደስት ነው ።

በመሆኑም ነው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በትምህርቱ መስክ የታየው እንቅስቃሴ የማይናቅ መሆኑን የጠቆመው ። ይህ ስብሰባ በተለይ አዳዲስና ከአብዮቱ ጋር የሚራመዱ ለአብዮቱ ግፊት አስተዋጽኦ ያላቸውን ሥርዓተ ትምህርቶች በመንደፍ ፥ ይህንንም ተመርኩዞ አዳዲስ መጻሕፍትን በማዘጋጀትና ለመምህራን የርዕዮተዓለም ተሐድሶ በመስጠት በኩል የተደረጉ ጥረቶች የሚያበረታቱ መሆናቸውን ከመግለጹም በላይ ፥ የመማርን ዕድል ለማስፋፋት በተለይም ማይምነትን ለማጥፋት ለሚደረገው ጥረት ታላቅ ግምት ሰጥቶታል ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በትምህርቱ መስክ ለተከናወኑት ተግባራት ታላቅ ግምት በመስጠት ብቻ ሳይቆጠብ ፥ የትምህርቱን ዘርፍ ሶሺያሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የሚደረገው ትግል እንዲፋፋም ለማድረግ ልዩ ልዩ ትምህርት ነክ ውሳኔዎችን አሳልፏል ። ውሳኔዎቹም የፖለቲካና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርት በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ይበልጥ በተጠናከረ አኳኋን የመሰጠቱን አስፈላጊነት ፥ የመምህራን የርዕዮተዓለም ጥራትና የሙያ ብቃት ተፈላጊው ደረጃ ላይ እንዲደርስ ለመምህራን ተከታታይ የሆነ የርዕዮተ ዓለም ትምህርት የመስጠቱና ወደ መምህርነት የሚገቡትንም ወገናዊነታቸውን የማረጋገጡን አስፈላጊነት ፥ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትምህርት ተጠናክሮ የመሰጠቱን አስፈላጊነት፥ ትምህርት ቤቶች(በተለይም በ2ኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች)ትምህርትን ከምርት ጋር አገናዝበ የማካሔዱን አስፈላጊነት ፥ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻው በማያወላውል አኳኋን ግቡን እንዲመታ የተከታታይና የድህረ መሠረተ ትምህርት ፕሮግራሞችን የማጠናከር አስፈላጊነት ፥ ዕድሜያቸው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለደረሱ ሕፃናት በሞላ በአፋጣኝ ትምህርት ለመስጠት የመቻሉን አስፈላጊነት የሚመለከቱ ናቸው ።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ተግባራዊ የማድረጉ ጥረት በየዘርፉ የቀጠለ ቢሆንም ፥ ለነዚህ ውሳኔዎች ተግባራዊነት መፋጠን በመደረግ ላይ ያለውን ጥረት በይበልጥ ማፋፋም ያስፈልጋል ።

በዚህ ሂደት በተለይ በትምህርቱ መስክ ከሚካሔደው የርዕዮተዓለም ትግል አንጻር

Digitized by Google

ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦች
አሉ ። በመጀመሪያ ትምህርትን ለማሌ ርዕ
ዮተዓለም ማስገዛት በማካሔድ ላይ የምን
ገኘው የትምህርት አብዮት አንድ ዋና ገጽታ
እንደመሆኑ ፥ የሶሺያሊስት ትምህርት ለርዕ
ዮተዓለምና ለፖለቲካ ትምህርት ልዩ ትኩ
ረት የሚሰጠው ለምን እንደሆነ ግልጽ ሊሆ
ን ይገባል ። የማሌን ርዕዮተዓለም የሚከተ
ል ኅብረተሰብ ትምህርትን የሚያውለው ለ
ሠርቶአደሩ ጥቅም ነው ። ወጣቱ ትውልድ
ከሥር ጀምሮ በምንከተለው ርዕዮተዓለም
በመኮትኮት የኮምዩኒስት አመለካከት ተቀር
ጾበት እንዲያድግ ማድረግ ከሶሺያሊስት ት
ምህርት የሚጠበቅ ዋና ተግባር ነው ። ስለ
ዚህ እንደ «ትምህርት ለትምህርት ሲባል»
እና «ዕውቀት ለዕውቀት ሲባል» ን የመሳ
ሰሉ የቡርዧ አመለካከቶችን በጥብቅ መታ
ገል ያስፈልጋል ። ከወደቀው አድኃሪ ሥር
ዓት የተወረሱ ኢ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችንና
አሠራሮችን ጨርሶ ለማስወገድና ከኢምፔ
ሪያሊዝም የሚቃጣብንን ትኩስ ርዕዮተዓለ
ማዊና ባህላዊ ወረራ ለማክሸፍ አስተማማኙ
መንገድ ትምህርት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም
ን ፈር ተከትሎ እንዲስፋፋ ማድረግ ነው ።
የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደ
በኛ ስብሰባ ካሳለፋቸው ትምህርት ነክ ውሳ
ኔዎች መካከል በየደረጃው የሚሰጠውን የፖ
ለቲካና የማሌ ትምህርት በተጀመረበት ደረ
ጃ የማጠናከሩ ፥ ባልተጀመረበት ደረጃም በ
አፋጣኝ የመጀመሩ አስፈላጊነት በቅድሚያ
የተጠቀሰውም በዚሁ ምክንያት ነው ።

ሌላው ልዩ ትኩረት የሚጠይቀው ጉዳይ
መምህራንን በርዕዮተዓለሙና በሙያው የ
ማሰልጠኑ ጉዳይ ነው ። የተፈለገው ካሪኩ
ለም ተነድፎና ተስማሚ መጻሕፍት ተዘጋ
ጅተው ቢገኙም እንኳ ፥ (ይህንንም ለማጠና
ቀቅ ገና ብዙ ጥረት፥ድካምና ጥንቃቄ ይጠይ
ቃል) ትምህርቱን ከማሌ ርዕዮተዓለምና ከ
አገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጐት ጋር አገ
ናዝበው ለማቅረብ የተዘጋጁ ብቁ (በመጠ
ንም ሆነ በዓይነት) መምህራን ካልተገኙ የ
ምናካሂደው የትምህርት አብዮት ግቡን ሊ
መታ እንደማይችል የታወቀ ነው ። ይህን
በሚመለከት ቀደም ሲልም በጽሑፉ ውስጥ
በስፋት የተጠቀሰ ቢሆንም ፥ ከጉዳዩ አሳሳ
ቢነት የተነሳ እዚህም ላይ መድገሙ አስፈ
ላጊ ነው ። መምህራን ወጣቶችን በምንከተ
ለው ርዕዮተዓለም ከሥር ጀምሮ በመኮት
ኮት የማሳደግ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።ይህ
ን ኃላፊነት ለመወጣት የሚችሉት ደግሞ
የራሳቸው የርዕዮተዓለም ጥራት ተፈላጊ
ውን ደረጃ ሲይዝ ነው ።

ሌኒን መምህራን የርዕዮተዓለም ብቃት
ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑን በማስመል
ከት ሲጽፍ ፥ «በማናቸውም ትምህርት
ቤት ወሳኙና ትልቁ ቁምነገር የመምህ
ራኑ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ዝንባሌ
ነው ። »[33] ብሎ ነበር ።

በዚህ ረገድ በየትምህርት ደረጃው የሚ
ያስተምሩ፥ ብቃትን ከጥራት ጋር ያዋሐዱ ፥
ቁጥራቸው በቂ የሆነ የማሌ መምህራን በአ
ገር ውስጥና በሶሺያሊስት አገሮች በስፋት
ማሰልጠን ይኖርብናል ። ላሉትም መምህ
ራን በየደረጃው ተከታታይ የሆነ የርዕዮተ
ዓለም ተሐድሶ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈ
ልጋል ።

ከዚህ አንጻር በከፍተኛ ትምህርት ተቋ
ሞች ውስጥ በተለይ የሶሺያል ሳይንስ ዘር
ፍን በሚመለከት ፥ እስካሁን በዚህ ዘርፍ
ለተሰማሩ መምህራን የተሰጠው የርዕዮተ
ዓለም ተሐድሶ በቂ ባለመሆኑ ፥ ለወደፊቱ
በዚህ ዘርፍ ለተሰማሩ መምህራን ተከታታይ
በሆነ መንገድ የርዕዮተዓለም ተሐድሶ የመ
ስጠቱ አስፈላጊነት ከፍተኛ ግንዛቤ ሊያገኝ
ይገባል ። በዚህ ረገድ ከወደቀው የፊውዶ
ቡርዧ ሥርዓት የተወረሱና ከኢምፔሪያሊ
ስቶች አገሮች የተግበሰበሱ የቢርዧ ንድፈ
ሐሳቦችና አመለካከቶች ከማሌ ንድፈሐሳብ

Digitized by Google

የሳቱ ናቸው የሚል አድኅሪ ብቻ ሳይሆን የ
ተሳሳተ አስተሳሰብና በአጠቃላይም ለማሌ
ርዕዮተ ዓለም ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት
ከመምህራን አእምሮ ውስጥ እንዲጠፋ ካል
ተደረገ ፣ የካሪኩለምና የመጻሕፍት ለውጥ
ብቻውን ትምህርቱን የሶሺያሊስት ፈር እን
ዲይዝ ሊያደርገው ስለማይችል ፣ በዚህ በኩ
ል የርዕዮተዓለም ትግሉን ማፋፋም ይኖር
ብናል ።

ይህ ሲባል ባለፉት የትግል ዓመታት ለት
ምህርት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረ
ጉና የማሌን ርዕዮተዓለም የተቀበሉ መም
ህራን የሉም ማለት አይደለም ። እንዲያው
ም የዚህ ዓይነት መምህራን ቁጥር የማይና
ቅና ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ የሚሔድ
እንደሆነ ይገመታል ። ሆኖም ከምናካሂደው
አብዮት አንጻር ሲታይ ከፍተኛ የሆነ የአብ
ዮታውያን ምሁራን እጥረት ያለብን መሆኑ
ግልጽ ነው ።

ከአገራችን ምሁራን መካከል የማሌን ርዕ
ዮተዓለም የተቀበሉና አስፈላጊው ዕርዳታ
ከተደረገላቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ የርዕዮተ
ዓለም ተሐድሶ ሊያገኙ የሚችሉ አብዛኞቹ
እንደሚሆኑ ይታመናል ። ሌሎች ደግሞ
የርዕዮተዓለም ተሐድሶ ለማግኘት ረዘም
ያለጊዜ ሊወስድባቸው ይችል ይሆናል ።
አሁንም ጥቂቶቹ ደግሞ የማሌ ርዕዮተዓለም
ሳይዋጥላቸው የሚቀሩ አሉ ። ይህ የመደብ
ትግል ሕግ በመሆኑ የሚጠበቅ ነው ። ለእ
ንደነዚህ ዓይነቶቹን ምሁራን የማርክሲዝም
ሌኒኒዝምን ርዕዮተዓለም ተቀበሉ ብሎ የሚ
ያስገድዳቸው ኃይል ባይኖርም፣ ይህን ርዕዮ
ተዓለም መመሪያው አድርጐ በተቀበለ መን
ግሥታዊ የትምህርት ተቋም ውስጥ እያስተ
ማሩ ከራሳቸው አልፈው ተዘዋዋሪ በሆነ መ
ንገድ ተማሪዎቻቸው በቡርዧው ርዕዮተዓ
ለም ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁ የሚያደርጉ ፣
የሚሰጣቸውን ትምህርት ከማሌ ርዕዮተዓለ
ም ጋር ለማገናዘብ ጥረት ለሚያደርጉ ተማ
ሪዎች መልካም አመለካከት የሌላቸው መም
ህራን በትምህርቱ መስክ ኢሠፓአኮ የማ
ሌን ርዕዮተዓለም ለማሠራጨት የተያያዘ
ውን ትግል ለማዳከም በመጣር ላይ እንደ
መሆናቸው ፣ ይህ ሁኔታ በሚገባ ሊጤን
ይገባል ።

ይህንንም ደባቸውን የሚያካሂዱት በ«አ
ካዳሚክ ነፃነት»(Academic Freedom)
ሽፋን መሆኑ የታወቀ ነው ። ይሁንና በጽ
ሑፉ መጀመሪያ ላይ በሰፋት ለማብራራት
እንደተሞከረውና ሌኒንም በግልጽ እንዳ
ስቀመጠው «. . . ከፖለቲካ የተገነጠለ
ትምህርት አለ ማለት ሐሰትና አስመሳይ
ነት» [34] በመሆኑ ፣ እነዚህ ምሁራን በ'አካ
ዳሚክ ነፃነት' ሽፋን ለቡርዧው ርዕዮተዓ
ለም የበላይነት የሚታገሉ መሆናቸው ለሁ
ሉም ግልጽ ሊሆን ይገባል ። በአጠቃላይ ለ
ሶሻሊዝም ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠ
ረት ለመጣል በምንታገልበት በአሁኑ ወቅት
የሚያስፈልገን የሰለጠነ የሰው ኃይል መጠ
ን ከፍተኛ በመሆኑ ፣ ማንኛውም ምሁር ድ
ርጊቱ የቆምንለትን መሠረታዊ ዓላማ እስካ
ል ተጻረረ ድረስ ግልጋሎት እንዲያበረክት
ማበረታታት ተገቢ ነው ። ሆኖም በዚህ አን
ጻር ልንከተለው የሚገባን ፖሊሲ ሌኒን ይ
ህን በሚመለከት መከተል ያስፈልጋል ያለ
ውን ፖሊሲ ነው። ይኸውም «አንደኛ ኮም
ዩኒስት ያልሆኑ ባለሙያዎች በኮምዩኒስቶች
ቁጥጥር ሥር መሥራት አለባቸው ፤ ሁለተኛ
አጠቃላይ ዕውቀት የሚሰጡ ትምህርቶችን
በተለይም የፍልስፍናን ፣ የማኅበራዊ ሳይን
ስን እና የኮሚኒስት ትምህርትን አስመል
ክቶ የሚወጡ ሥርዓት ትምህርቶችን ይዘት
የሚወስኑ ኮምዩኒስቶች ብቻ መሆን አለባ
ቸው ። » [35]

ትምህርት የላዕላይ መዋቅር አካል ብቻ
ሳይሆን ከምርት ኃይሎች ዕድገትም ጋር በ
ቅርብ የተቆራኘ ነው ። ስለሆነም የምንዘረ
ጋው አዲስ የትምህርት ሥርዓት አካባቢያ
ችንን በቁጥጥር ሥር በማዋል ምርትን ለማ
ሳደግ ታቅዶ በመካሔድ ላይ ላለው ለምር
ትና ለባህል ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ
ለማበርከት መቻል አለበት ። እንደ ኢትዮ

Digitized by Google

ጽያ ባለች በሳይንስና በቴክኒዎሎጂ ኋላቀር
በሆነችና የምርት ኃይሎች ባልዳበሩባት አገ
ር አስፈላጊው ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት
ሳይጣል ሶሺያሊዝምን እንገነባለን ማለት
ዘበት ስለሆነ ፥ በዚህ ረገድ ከቀድሞው ሥር
ዓት የወረስነውና የተዛባውን የትምህርት
ሥርዓት ማቃናት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር
የትምህርቱ ሥርዓት እንደቀድሞው ሥር
ዓት አገልጋይ ቢሮክራቶችን ለማፍራት ሳይ
ሆን ፥ ለሶሺያሊስት ግንባታ የሚያስፈልገ
ውን የማቴሪያልና የቴክኒክ መሠረት ለመ
ጣልና ሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለማሻ
ሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚ
ችል ፥ የተሟላ ዕውቀት ያለው ሕዝባዊ ምሁ
ር መፍጠር መቻል ይኖርበታል። በመሆኑም
የሚዘረጋው የትምህርት ሥርዓት በአንድ
በኩል በትክክለኛው የኅብረተሰብ ሳይንስ ፥
በሌላ በኩል ደግሞ በተፈጥሮ ሳይንስና
በቴክኒዎሎጂ መካከል መኖር የሚገባውን
ሚዛን የጠበቀ ሊሆን ይገባዋል ።

ትምህርትን በስፋት በሰፊው ሕዝብ ውስ
ጥ ለማዳረስ በምናደርገው ጥረት ፥ ይህን ለ
ማድረግ የሚያጋጥመንን የአቅም ማጠር ች
ግር በከፊልም ለመወጣትና ፥ በሌላም በኩል
የቀለም ትምህርትን ከምርት ጋር ለማዋሐድ
ት/ቤቶች ወጭአቸውን በከፊልም ቢሆን
ሊሸፍኑ የሚችሉበት የምርት እንቅስቃሴ
መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ፥ ይህን ለማድረግ
ጥረቱ በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን መጀመር
ይኖርበታል ።

የመሠረተ ትምህርቱ ዘመቻ እየገፋ ሲ
ሔድ በመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝ
ግጅትና ሥርጭት አንጻር እንዲሁም የንባብ
ቤቶችና መጻሕፍት ቤቶችን በማስፋፋቱ
ረገድ ያልተቆጠበ ጥረትን የሚጠይቅ ነው።
ከዚሁ ጋር የተያያዘው ደግሞ ዕድሜያቸው
ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት የደረሰን ሕፃናት
በትምህርት ገበታ ላይ እንዲገኙ የማድረጉ
ሁኔታ ነው ። ዕድሜያቸው ለአንደኛ ደረጃ
ትምህርት ለደረሰ ሕፃናት በመላ ትምህርት
ለመስጠት ካልተቻለ ፥ መሐይምነትን ከሀገ
ራችን ሙሉ ለሙሉ እናጠፋለን ማለት ትር
ጉም ሊኖረው አይችልም ። ስለዚህ እነዚህ
ሁለት ዓላማዎች በአንድነት መታየትና በ
ተቻለ ፍጥነት ተግባራዊ መሆን ይኖርባቸ
ዋል ። ለሶሺያሊስት ግንባታው ቅድመ ሁኔ
ታዎችን ለማሟላት የምናደርገው ጥረት ፍሬ
እያሰየ ሲሔድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
ንም እንደዚሁ ማዳረስ ይቻላል ።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም በሚ
ዳረስበት ጊዜና ከዚያም በፊት ከአንደኛ ደረ
ጃ በላይ የሚሰጠውንና ለሁሉም ለማዳረስ
አቅም የማይፈቅደውን ትምህርት በኅብረ
ተሰቡ መካከል ዲሞክራሲያዊ በሆነ መን
ገድ ማከፋፈል ያስፈልጋል። የወደቀው ንጉ
ሣዊ አገዛዝ ዘርግቶት የነበረው የትምህርት
ሥርዓት ወንዱን ከሴት ፥ አንዱን ብሔረሰብ
ከሌላው ብሔረሰብ ፥ ያንዱን ሃይማኖት ተከ
ታይ ከሌላው ፥ አንዱን ክፍለ ሀገር ከሌላው
ክፍለ ሀገር ፥ ከተማውን ከገጠሩ የሚያበላ
ልጥ ነበር ። አሁን የሚዘረጋው አዲስ የት
ምህርት ሥርዓት ግን ትምህርትን ዲሞክራ
ሲያዊ በሆነ መንገድ ለኅብረተሰቡ አባላት
ለማከፋፈል የሚያስችል ሥርዓት መሆን
አለበት ። ይኸም ማለት የወደቀው አድኃሪ
ሥርዓት ዘርግቶት የነበረው የትምህርት ሥር
ዓት አስከትሎት የነበረውን መዛባት ለማስ
ተካከል ፊት በደል ተፈጽሞባቸው ለነበሩት
ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ
መስጠት ይኖርበታል ማለት ነው ። ይሁንና
ትምህርትን በኅብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራ
ሲያዊ በሆነ መንገድ ለማዳረስ በሚደረገው
ጥረት የትምህርት መደባዊነት መሠረታዊ
መርህ ሊዘነጋ አይገባም ። ይህም ማለት የት
ምህርቱ ሥርዓት በወደቀው አድኃሪ ሥር
ዓት ይጨቆኑና ይመዘበሩ ለነበሩ በተለያዩ
አካባቢዎች ለሚገኙ ሠርቶ አደሮች ቅድሚ
ያ የሚሰጥና የነሱንም ጥቅም እንዲያዳብርና

Digitized by Google

እንዲያስከብር ሁና መዘርጋት ይኖርበታል ማለት ነው ።

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የኢሠፓአኮ ትምህርት ነክ ውሳኔዎች ካተኮሩባቸው ችግሮች በተጨማሪም ሌሎችም እንደ ትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል ያሉ ዋና ዋና ችግሮች መኖራቸው የታወቀ ነው ። በአጠቃላይ ግን የኢሠፓአኮ የትምህርት ነክ ውሳኔዎች ያተኮሩባቸውንና ሌሎችንም ትምህርት ነክ ችግሮች ሙሉ በሙሉ ለመወጣት በትምህርቱ ዘርፍ «ትምህርት ለምርት ፣ ለሳይንሳዊ ምርምርና ለሶሺያሊስታዊ ንቃተ ሕሊና » በሚለው መርህ መሠረት ከፍተኛ ትግል ማካሔድን ይጠይቃል ።

እንደሌሎቹ የላዕላይ መዋቅር ዘርፎች የትምህርቱንም ዘርፍ ሶሺያሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የሚቻለው በፓርቲው ምሥረታ ሂደት የሚዘረጋው የትምህርት ሥርዓት ንድፈ ሐሳብንና ተግባርን ያቀናጀ፣ ከአገራችን የግንባታ ጥረት ጋር የተገናዘበ ፣ በተለይም ለዛሬው፣ለነገና ለተነገወዲያው በዚህ ዘርፍ የሚያስፈልገውን ፣ በርዕዮተዓለሙ የበሰለና በሙያውየሰለጠነ የሰው ኃይል በማዘጋጀት፣ በጥራት ለማሰባሰብ ፣ አስፈላጊውን ርዕዮተዓለማዊ አመራር በመስጠት የትምህርቱን አብዮት በማፋፋም እስከ መጨረሻው ግብ ድረስ ለማድረስ ሲቻል ነው ።

በአጠቃላይ ግን የሶሺያሊስታዊ ትምህርትን በተሟላ ሁኔታ ለመዘርጋት ጠንካራ የሆነ የማሌ ፓርቲን አመራር የሚጠይቅ በመሆኑ ፣ በኢትዮጵያ የትምህርትን አቅጣጫ ሶሺያሊስታዊ ፈር በማስያዝ ለመገንባት የሚደረገው ትግል ፣ ፓርቲያችንን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማዋቀር ከምናካሂደው ትግል ጋር የተቆራኘ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃ/ማ ለአ.አ. ዩኒቨርስቲ ምሩቃን ሐምሌ 10 ቀን 1974 እና ሐምሌ 12 ቀን 1973 ያደረጉት ንግግር ፣ ከ.ት.ኮ ፣ አ.አ. 1974 ፣ ገጽ 5
2. V.I. Lenin, *On Public Education,* (Moscow: Prog. Pub., 1976), p. 10.
3. አሥረኛው የትምህርት አመራርና አስተዳደር ጉባኤ ፣ ት/ሚ ፣ አ.አ. 1973 ገጽ 21

4, መጽሐፈ ቅዳሴ

5. *On Public Education,* p. 66.
6. D.N. Smith, *Who Rules the Universities; An Essay in Class Analysis,* (New York: Monthly Review, 1974), pp. 19-20.
7. *Ibid.,* pp. 94-109.
8. *On Public Education,* p. 83.
9. Plenum of the CC of Bulgarian Communist Party on problems of education, p. 12.
10. V. Turchenko, *Ibid.,* p. 32.
11. *On Public Education,* p. 83.
12. *Ibid.,* p. 89.
13. ለኢሠፓአኮ ማ/ኮ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ ፤ የርዕዮተዓለም ዘርፍ ሪፖርት ፣ የርዕዮተዓለም ስርጭት ፣ ኢሠፓአኮ፣ አ ፣ አ 1973 ፣ ገጽ 25
14. Turchenko, p. 44.
15. *Ethiopia Observer,* Vol. II, No. 4 1958, p. 130.
16. *Ethiopia Observer,* Vol. IX, No. 1, pp. 11-48.

Digitized by Google

17. Curriculum Change and Development in Ethiopia after the 1974 Revolutionary upheaval, Min. Ed., A.A., 1981, p. 1.

18. የታሪክ ሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ሂደት/ በሥርዓተ ትምህርት መምሪያ የተባዛ ጽሑፍ/ ገጽ 5

19. ከዚሁ ጽሁፍ፣ ገጽ 5

20. Curriculum Change and..., *Ibid.*

21. የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ የአጠቃላይ ትምህርት ግምገማ ዓላማና ስልቶች፣ አ. አ. ፤ 1974፣ ገጽ 28

22. ከሥርዓተ ትምህርት መምሪያ የተገኘ ጽሑፍ ፤ ገጾች 7—8

23. ከትምህርት መገሪያዎች ማደራጃና ማከፋፈያ ድርጅት የተገኘ መረጃ

24. የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ፣ ገጽ 44

25. Lenin, CW, Vol. 15, p. 474.

26. ከመምህራን ትምህርት መምሪያ የተገኘ መረጃ

27. የኢሠፓአኮ ማ/ኮ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች፣ ገጽ 7

28. የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ፣ ገጽ 45

29. ከዚሁ ጽሑፍ፣ ገጽ 45

30. ስለውጭ ግንኙነቶች ፤ ፕሮቶኮሎችና ሥራ አጥር መግለጫ ከፍተኛ ት/ኮሚሽን፣ 1975፣ ገጾች 4—5

31. Facts and figures; Commission for Higher Education, A.A., 1982, p. 55.

32. Lenin, *Collected Works.*, Vol. 28, p. 88.

33. Lenin, Vol. 15, p. 472.

34. *On Public Education, pp.* 10-11.

35. *Ibid.*, p. 115.

Digitized by Google

ዲሞክራሲና የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት

ሕዝቦች ምንጊዜም መብታቸው ከተገፈፈ፣ ነፃነታቸውና ሕልውናቸው ከተደፈረ፣ ከብዝበዛና ከባርነት ቀንበር ለመላቀቅ አቅምና ሁኔታ በፈቀደላቸው መሠረት ይታገላሉ። ትግሉም ብዙ መስዋዕትነትንና ጊዜን ይጠይቅ እንጂ፣ ለአርነትና ለነፃነት የሚደረግ ትግል እውነተኛና ትክክለኛ በመሆኑ፣ የማታ ማታ አሸናፊነቱ አጠያያቂ አይሆንም። ይህም ሐቅ ጭቁን ሕዝቦች በበዝባዥና በጨቋኝ መደቦች ላይ በየጊዜው በሚቀዳጁዋቸው ድሎች እየተንፀባረቀ ነው። ባለንበት የታሪክ ዘመን ኋላ ቀርነትን፣ ጭቆናንና ብዝበዛን ደምስሶ ብልጽግና፣ ነፃነትና ፍትህን ለማስፈን ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ያለው የተራማጆችና የአዲስ ኅብረተሰብ ገንቢዎች ንቅናቄ አካል የሆነው የኢትዮጵያ አብዮት የዘረጋው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ለሰፊው ሕዝብ ጠለቅና ሰፋ ያሉ ድሎች እንዳጐናጸፈ በግልጽ የሚታይ ነው።

የብሔረሰቦችን ጥያቄ በሚመለከትም፣ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ተግባራዊነት፣ ወይንም ሰፊው ሕዝብ በአድኃሪያን ላይ ባገኘው የበላይነት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በሶሻል ጉዳዮች የራሱን ዕድል በራሱ በመወሰኑ ረገድ ያለው ተሳትፎም፣ ካለንበት ጠቅላላ የዕድገት ደረጃ ጋር ሲመጣጠን፣ ከሩቅ ለሚታየን ኮሚኒስታዊ ግብ ተጨባጭና የሚያደፋፍር መንደርደሪያ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንንም ዘርዘር አድርጎ ለመገንዘብ የብሔረሰብ ጥያቄን ታሪካዊ አመጣጥ በአጠቃላይ፣ እንዲሁም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የጥያቄውን አነሳስና በድኅረ አብዮት ኢትዮጵያም የተወሰዱትን ተጨባጭ እርምጃዎች በተለይ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ጠቅላላ አመለካከት

ሰዎች መሠረታዊ ፍላጐታቸውን ለማ

Digitized by Google

ሟላት ለብዙ ዘመናት ከተፈጥሮ ጋር ባደ
ረጉት ትግል ፥ የህልውናቸው መሠረት በሆ
ነው የቁሳዊ ምርት ክንዋኔ ፥ የተለያዩ የዕ
ድገት ደረጃዎችና ስልተ ምርቶች ላይ ደር
ሰው እናገኛቸዋለን ። ከመደቦች መከሰት
በፊት የነበረውን የጥንታዊውን የጋርዮሽ
ሥርዓተ ማኅበርን ስንመረምር ፥ በታሪክ
ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተውን ዝቅ
ተኛ አምራቾች ቡድን የሆነውን በደም ፥
በቋንቋና በተመሳሳይ እምነት የተሳሳሰረ
ውን የቤተዘመድ ማኅበረሰብን እናገኛለን።
ከዚያ ቀጥሎ ከቤተዘመድ ሰፋ ያለና በደም
ግንኙነቱ ላላ ያለ ፥ ግን የጋራ ማደኛ ቦታ
የሚይዝ የጐሣ ወይንም የነገድ ማኅበረሰብ
ይመጣል ።

የምርት ኃይሎች እያደጉ ፥ የሥራ ክፍፍ
ልና የምርት ልውውጥ እየተስፋፋ ፥ እንዲ
ሁም ሀብት በጥቂቶች ዘንድ እየተካበተ
ሲሄድ ፥ ኅብረተሰብም በመደብ መከፋፈል
ይጀምራል ። በዚህ አኳኋን በተለያየ የሀብት
መጠንና የማምረቻ መሣሪያዎች በግል ይዞታ
ሥር ከመሆናቸው የተነሣ የመደብ ልዩነት
እየሰፋ ሲሄድ ፥ የኢኮኖሚ የበላይነት ያገ
ኘው ሌላውን አስገድዶ የሚያሠራበት፥ጥቅ
ሙን የሚያስጠብቅበትና ተገዥውን የሚ
ጨቁንበት መንግሥታዊ መሣሪያ ይከሰ
ታል። ኅብረተሰብ በመደብ እንደተከፋፈለ፥
በቀዳሚነት የታየው የማኅበረሰብ ዕድገት
ደረጃ ብሔረሰብ ነው ። ብሔረሰብ በባሪያ
አሳዳሪና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ሊኖር የሚ
ችል የማኅበረሰብ የተለየ የእድገት ደረጃ ሆኖ፥
ግን ኙነቱ በአንድ አካባቢ ኑሮ ፥ አንድ ቋንቋ
በመናገር ፥ በተመሳሳይ አመለካከትና ባህል
የተቀናጀ ቢሆንም ፥ ከዘር ግንኙነት ይልቅ
በይበልጥ በዝቅተኛ ኢኮኖሚ ላይ የተመሠ
ረተ ነው ።

ቀጥሎ ያለው ደረጃ ብሔር ሲሆን ፥ እሱ
ም የተከሰተው የፊውዳሊዝም የምርት ግን
ኙነት አክትሞ በካፒታሊስት የምርት ግን
ኙነት ፥ የብሔረሰቦች ግድግዳ ሲፈራርስ
ነው ። ማኅበረሰቡ አንድ የኑሮ አካባቢ ፥
አንድ የመግባቢያ ቋንቋና ተመሳሳይ ሥነ
ልቡናዊ ዘይቤ ያለውና በረጅም ጊዜ ታሪክ
የጸና ፥ ከመሆኑም በላይ ግንኙነቱ በከፍተኛ
ኢኮኖሚ የተቀናጀ ነው ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ፥ በሰዎች መካከል
የመደብ ቅራኔና ጭቆና የመጣው ፥ የማም
ረቻ መሣሪያዎች በግል ይዞታ ሥር መዋል
ከጀመሩበት ወቅት አንስቶ ነው ። ከዚሁ
ጋር የብሔረሰቦችም ጭቆና አብሮ መጥ
ቷል ። ላቅ ባለው ብሔረሰብ ወይንም ብሔ
ር የሚገኝ የገዥ መደብ ፥ አነስ ያሉትን በኢ
ኮኖሚ ፥ በፖለቲካና በሶሻል ጭቆናዎች እን
ዲማቀቁ ያደርጋል ። በዚህም በጨቋኝና
ተጨቋኝ ወገኖች መካከል ቅራኔ ይነሳል ፤
ብሔራዊ ንቅናቄም በዚሁ ይወለዳል ።

እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ፥ የትልቁ
ብሔረሰብ ወይንም ብሔር የገዥ መደቦች
ዋናው ዓላማ ፥ መሠረታዊ የሆነውን የግል
ኢኮኖሚ ጥቅማቸውን መጠበቅ ሲሆን ፥
ይህንን ሽፍነው ፥ በመደብ የሚበዘብዙት
ንና የሚጨቁኑትን የራሳቸውን ብሔረሰብ
ወይም ብሔር ምዝብር መደቦች በቋንቋና
በባህል ልዩነት በመጠቀም ፥ በትምክተኝ
ነት ስሜት በክለው ከጭቁን ብሔረሰቦች
ወይም ብሔሮች ምዝብር መደቦች ጋር አን
ድነት እንዳይፈጥሩ የሚሸርቡት ሴራ ነው።
በተቻለ መጠን የሁለቱ ብሔረሰብ ጭቁ
ኖች በመደብ አኳያ እንዳይሰለፉ ከፋፍለው
ያኖሩዋቸዋል ። በአንፃሩ በታሪክ እንደተረ
ጋገጠው ከተጨቋኙ ብሔረሰብ ወይም
ብሔር የገዥ መደቦች ጋር በጥቅም በመቆ
ራኘትና በመተሳሰር ብዝበዛቸውን ያጠና
ክራሉ ።

በታሪክ የብሔርና የብሔረሰብ ቅራኔዎች
ጐልተው የሚታዩባቸውን ሶስት ወቅቶችን
ለመጥቀስ ይቻላል ፥ እነዚህም በፊውዳል
ፍጹማዊነት ፥ በቡርዧ ዲሞክራቲክ አብ
ዮት ሂደትና በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ይከ
ሰታሉ ።

በፊውዳላዊ ሥርዓት ማዕከላዊ መንግ

Digitized by Google

ሥት የሚመሠረተው ፣ የብሔረሰቦች ልዩነት በካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ኃይል ፈራርሶ ብሔር ቀደም ሲል ተፈጥሮ ሳይሆን ፣ የተለያዩ ብሔረሰቦችን አቅፎ ነው ። ስለሆነም የማዕከላዊውን መንግሥት አመራር የያዙት ብሔረሰቦች የገዥ መደቦች ባላቸው ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካና የባህል የበላይነት በአነስተኞቹ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያደርጉ የብሔረሰብ ንቅናቄዎች ይነሳሉ ።

በታሪክ ሂደት አስቀድሞ በምዕራብ አውሮፓ እንደታየው ፣ የሸቀጥ ምርት ከዕደጥበብ ወደ ፋብሪካ ምርት ደረጃ በማደግ፣ ያረጀው ፊውዳላዊ የምርት ግንኙነት ተበጣጥሶ ፣ በቡርዧ መሪነት አዲስ የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ተመሠረተ ። በአብዮቱ ሂደት « ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት » በሚሉ ማራኪ መፈክሮች ፣ ቡርዧው በፍጹማዊ ፊውዳላዊ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር የተሰባሰቡትን ፣ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ወዛደሮችና ገበሬዎች ፣ እንዲሁም ሌሎችንም በማስተባበር ፣ ፊውዳላዊ ጠባብ ማኅበራዊ ሥነልቡናን ፣ የቋንቋን ፣ የባህልንና የአካባቢ ውስኑነትን በመሰባበር ፣ ለሸቀጥ ምርት ፍጹም የበላይነትን ለማስገኘት ሰፊ ገበያ ለመፍጠር በቃ ። በዚህም የተበታተኑትን ብሔረሰቦች በአንድ ቋንቋ ፣ በተመሳሳይ ሥነ ልቡናዊ ዘይቤና ፣ ከሁሉም በላይ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ግንኙነት አስተባብሮ ብሔራዊ አንድነት ፈጥሮአል ።

ቡርዧው ይህንን ያደረገው ብሔረሰቦችን ነፃ ለማድረግ ሳይሆን ፣ ለራሱ በሚያግበሰብሰው ትርፍ ካፒታሉን ለማሳደግና ፣ የሀገሩን ገበያ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ነበር ። ቡርዧ ከፊውዳላዊ ጠባብነት ጋር ሲታይ አንፃራዊ ተራማጅነት አለውነሆኖም «እኩልነትና ወንድማማችነት ለሁሉም» ፣ የሚሉት መፈክሮች በራሱ ብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ፣ የቡርዧውን ዓለምአቀፋዊነት (ኮስሞፖሊታኒዝም) ለመዘርጋት የታቀደ የቃላት ድላላ እንጂ ፣ ዕውነትም ምዝብሮችንና ጭቁኖችን የሚመለከቱና ፣ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነትን የሚያሰፍኑ አልነበሩም ። ዲሞክራሲን ያወጀው የራሱን ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ የበላይነት ለመጨበጥና በፈጠረው ብሔራዊ መንግሥትም ወዛደሩን ጨቁኖ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ለማስጠበቅ እንጂ ፣ እውነትም ሕዝባዊ ዲሞክራሲን ተግባራዊ ለማድረግ አለመሆኑ በግልጽ በታሪክ ታይቶአል ። ካፒታሊዝም ለብሔር ጥያቄ በተጨባጭ የሰጠው መልስ ቢኖር ፣ ከቶጥ እርሻ ባርነት ወደ አሽከርነት ፣ ከምንዳ ባርነት ወደ ሥራ አጥነት ፣ ከቀጥታ ቅኝ ተገዥነት ወደ እጅ አዙር ቅኝነት መሸጋገርን ነው ።

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የተነሳው ብሔራዊ ንቅናቄ መንስኤው የካፒታሊዝም ዕድገት ወደ ሞኖፖል ደረጃ መሸጋገርና ፣ ከዚያም ካፒታል የሀገሩን ድንበር አልፎ በሌሎች ሀገሮች ፣ ለፋብሪካው ርካሽ ጥሬ ዕቃና ጉልበት ፣ እንዲሁም ለሸቀጥ ማራገፊያ ገበያ ለማግኘት የቅኝ አገዛዝን መመሥረት ነው ። በዚህም የብሔር ጥያቄ የቅኝ አገዛዝ ጥያቄ ሊሆን በቅቷል ። ከዚህ የሞኖፖል የብዝበዛ መረብ ነፃ ለመውጣትና ፣ የታሪካቸው ባለቤት ለመሆን ተጨቋኝ ሕዝቦች ፀረኮሎኒያል ትግል አካሂደዋል ፤ ያካሂዳሉም ። በዚህ ዘመን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ወጥቶ ፣ ብሔራዊ መንግሥት ለመመሥረት የሚደረገው ትግል ኢምፔሪያሊዝምን አዳክሞና አሸንፎ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር ከሚደረገው ትግል ጋር ተቀናጅቶ ይገኛል ።

የብሔረሰብ ቅራኔ በተለያዩ የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃዎች የሚነሳ መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለመፍትሔው ስናስብም የተለያዩ መደቦች ባላቸው የአመለካከት ልዩነት ፣ ከጥቅማቸው ባልተለየ ሁኔታ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ ። የፊውዳሉ የገዥ መደቦች የራሳቸውን ምኞት ሆነ የተገዥዎቻቸውን ጭቆና ተፈጥሮ ለአንዱ የወሰነውና የማይለወጥ እንደሆነ አድርገው በማቅረብ ፣ በተለያዩ

Digitized by Google

ስንክላ ምክንያቶች የብሔረሰብም ሆነ ሌሎች ቅራኔዎች እንዲቀጥሉ ይጥራሉ ። በከፋፍለህ ግዛ ዘዴአቸውም ሰፊውን ሕዝብ ይለያዩታል ። ቡርዧውም ቢሆን አፍአዊና የይስሙላ ነፃነት ፣ ወንድማማችነትና እኩልነት ከማወጅ በስተቀር ለብሔረሰብ ችግሮች መሠረታዊ መፍትሔ አያቀርብም። እንደዚሁም አድርባዮችና የቡርዧ አፈቀላጤዎች ማኅበራዊ ግንኙነትን ፣ ከነገድ ወይም ከዘር ጽንሰ ሃሳብ አቅጣጫ በመመልከትና ፣ በኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ቅርጽ ብቻ በማተኮር ፣ መሠረታዊ የሆነው የይዘትና የውስጣዊ ግንኙነት ጉዳይ እንዲዘነጋ ይጥራሉ ። ከዚህም የተነሳ ማኅበራዊ ግንኙነትን ከመደብ አኳያ ሳይሆን ፣ ከባህል አንፃር በመተንተን ፣ ባህላዊና ብሔራዊ አውቶናሚ ለችግሩ መፍቻ ነው የሚሉ አስተሳሰቦችን የሚሰነዝሩ ጥቂቶች አይደሉም ።

ሳይንሳዊ ግንዛቤው

ማርክሳዊው ሳይንሳዊ አመለካከት ግን ከላይ ከተጠቀሱት ሁሉ ይለያል ። የማኅበራዊ ግንኙነት መሠረት የኢኮኖሚ ግንኙነት መሆኑንና ፣ በመደብ የተከፋፈለ ኅብረተሰብም ዋነኛው ቅራኔ የመደቦች እንደሆነ ያስተምራል ። ጭቆናና ብዝበዛ የሚነሰራፋው ፣ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል፣በአገር ውስጥ ያለም ሆነ ከውጭ የሚመጣ ፣ የማምረቻ መሣሪያዎች በራሱ የግል ይዞታ ስር በማዋሉ እንጂ ፣ አንድ ቋንቋ በመናገሩ ወይም የአንድ ጐሣ(ዘር) አባል በመሆኑ አይደለም። የብሔረሰብም ጥያቄ እንደ አነሳሱ ትኩረት ይሰጠው እንጂ ፣ ከመደብ ትግልና ከኅብረተሰብ ቁሳዊ መሠረት ተገንጥሎ ሊታይ አይችልም ። ስለዚህም ነው የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች ማርክስና ኤንግልስ በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ፣ ኮሚኒስቶች ማንኛውም አድኅሪ ሥርዓት የሚቃወሙትን አብዮታዊ ንቅናቄዎች ሁሉ እንደሚደግፉና ነገር ግን በእነዚህ ንቅናቄዎች ሁሉ ዕድገታቸው በየትኛውም ደረጃ ቢሆን የሀብትንና የንብረትን ጥያቄ ዘወትር ቀዳሚ ጥያቄ አድርገው እንድያነሱ አበክረው ያሳሰቡት ።

እነዚህ ቀደምት የወዛደር መሪዎች ራሳቸውም ሆኑ ሐቀኛ ተከታዮቻቸው በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች ለብሔራዊ ቅራኔዎች ካሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች በመነሳት ተገቢውን አማራጭ ከማቅረብና ለተግባራዊነቱም ከመታገል አልቦዘኑም ። ጥያቄውን የተመለከቱት ግን ራሱን የቻለና ለሁልጊዜም የተወሰነ አድርገው በመውሰድ ሳይሆን ነባሩን የብዝበዛ ሥርዓት ለመለወጥ ካለው አጠቃላይ ትግል ጋር በማዛመድ ነው።ለአብዮታዊ ሂደት እገዛ የሚያደርጉትን ንቅናቄዎች እስከመገንጠል ድረስ ደግፈዋል ፤ ለፀረአብዮት የቆሙትን ግን ያለርህራሄ ታግለዋል ። በቡርዧ አብዮት ወቅት ፊውዳላዊውን ሥርዓት ለማዳከም የተነሱትን ደግፈዋል ። ዛሬም የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ ባላከተመበት ዘመን ለሞኖፖል ካፒታል ውድቀት ፣ ለሰፊው ሕዝብ አብዮት ማበብና መጐልበት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ንቅናቄዎች ይደግፋሉ ። በአንፃሩም የሰፊውን ሕዝብ ጽኑ መደባዊ አንድነትና አብዮታዊ ስሜቱን በብሔረተኝነት ፣ በጠባብነትና ትምክህተኝነት ስሜት የሚበክሉትን ፣ ሰፊው ሕዝብ ለመደባዊ ጥቅሙ ተባብሮ እንዳይታገል እሸክላ የሚዘረጉበትን ሁሉ በጥብቅ ይታገሉአቸዋል ። የማርክሳውያን ፍላጐትና ጽኑ አቋም የሁሉም ብሔሮችና ብሔረሰቦች ፍጹም እኩልነት ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና የሁሉም አገር ሠርቶ አደሮችን የጠነከረ ኅብረት ነው ።

ያለንበት የታሪክ ዘመን ዋናው ይዘት ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር በሆነበትና ብሔራዊ ንቅናቂም ከፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ተለይቶ በማይታይበት ወቅት የኢምፔሪያሊስቱ ጽኑ ፍላጐት የብሔረሰቦች መለያየትና መቋሰል ነው ። በአ

Digitized by Google

ንግሩ ግን የአብዮታውያን ፍላጐት የሠርቶ
አደሮች አንድነት እንደመሆኑ የብሔረሰቦ
ችም ችግር መፍትሄ የሚያገኘው ለኢምፔሪ
ያሊዝምና አድህርት ክማይበጅና እንደት
ራኑው መጠን ከሚለያይ የአንድነት ትርጽ
እንጂ ከመገነጣጠል አይደለም ። ስለዚህም
በትግ ግዛትና በአድኀርት ቀንበር ሥር
የሚማቅቁ ሁሉ ነፃነታቸውን ለመጐናጸፍ
የመደብ አንድነታቸው ጽኑ የትግል መሠ
ረታቸው መሆኑን አበከረው መገንዘብ አስ
ፈላጊ ይሆናል ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮት የወሰዳቸው ዓበይት ርምጃዎች

ወደ ኢትዮጵያ ሁኔታ ስንመለስ ከአብ
ዮቱ በፊት የፊውዳሉ ሥርዓት የፈጠረውን
ሁኔታና ከአብዮቱ በኋላ ለብሔረሰቦች ጥያ
ቄ የተሰጠውን መልስ እንመልከት ። እንደ
ዛሬውም በትድመ አብዮት ኢትዮጵያ የሰ
ፊው ሕዝብ የኢኮኖሚ ዋልታ መሬት ነ
በር ። ነገር ግን ያኔ አብዛኛው ለም መሬት
95% የተያዘው በንጉግዊ ቤተሰቦች ፣ በመ
ሳፍንቱ ፣ በመኳንንቱ ፣ በታላላቅ ካህና
ትና ባላባቶች ነበር ። በዚህም ሰፊው አርሶ
አደር ሕዝብ ይተዳደር የነበረው በጭሰኝ
ነትና በተጠግጅ አራሽነት ነበር ። ከመ
ሬት ባለቤትነት ይዞታ ከመገለሉ የተነሳ
ለፍቶ ፣ ጥሮና ግሮ ከሚያመርተው እስከ
ሶስት አራተኛው ድረስ ለባለመሬቶች እን
ዲያስረክብና የተለያዩ የጉልበት ሥራዎችም
እንዲያከናውን ሥርዓቱ ያስገድደው ነበር።
ስለዚህ ሰፊው አርሶ አደር መሬቱን ተቀ
ምቶ ለጭሰኝነት ከመዳረጉም በላይ ለጉል
ተኞች እጥር ማጠር ፣ ጠብመንጃ ተሸክሞ
የበቅሎ ጭራ መከተል ፣ በሁዳድ ላይ መሥ
ራት ፣ ሚስቱና ልጆቹ እንጨት መስበር ፣
እግር ማጠብ ፣ ወዘተ ... የተለመዱ ግዳ
ጆች ነበሩ ። መሬት በሽያጭም ሆነ በስጦታ
ከአንድ ባለመሬት ወደሌላ ሲዛወር በመ
ሬቱ ላይ ሠፍሮ የነበረው አርሶ አደርም በ
መሬቱ ላይ እንደሚገኝ እንደማንኛውም
ሀብት አብሮ ይተላለፍ ነበር ። በተለይ ከ
1950ዎቹ ጀምሮ እንደታየው በየሥፍራው
የካፒታሊስታዊ አመራረት ወደ ገጠር
በመዛመቱ ሰፋፊ መሬቶች ለማግኘት የአ
ርሶ አደሩ ንብረትና ደሳሳ ጐጆዎች የትራ
ክተርና የግሬደር እራት በመሆናቸው ፣
አርሶ አደሩ በገዛ ሀገሩ ለስደት ፣ ለሥራ አጥ
ነትና ለልመና ተዳረገ ፤ ከዚህም በላይ የመ
ሬቱ መሸንሸን ፣ መበጣጠስና መሸርሸር
ከኋላቀር የምርት መገልገያዎች ጋር ተዳ
ምሮ የምርቱን ውጤት በጣም ዝቅ እንዲል
በማድረጉ አርሶ አደሩ በአንድ በኩል ለረ
ሀብና ለመከራ ሲዳረግ በሌላ በኩል በላቡና
በጉልበቱ የፈጠረው ሀብት ለገዥ መደ
ቦች መንደላቀቂያ ይውል ነበር ። በጣም
አነስተኛ በሆነች የበሬ ግንባር ይዞታው ፣
በኋላ ቀር የማምረቻ መሣሪያዎቹ ጥሮ ከሚ
ያመርተው ሰባ አምስት በመቶ ለባለመሬ
ቱ ከሚከፍለውና ከሚያበረክተውም የጉል
በት ሥራ ሌላ ፣ የተለያዩ ክፍያዎችን እንደ
የዓመት በዓል ፣ የጭቃ ፣ የገደል ፣ የሠንጋ፣
የእጅ መንሻ ፣ የሠርግ መደገሻ ፣ የቀሚስ
ማስመረቂያ ፣ ወዘተ --- የመሳሰሉትን ሲከ
ፍል መኖሩ በቅርብ የሚታወስ ነው ። እን
ዲሁም የትምህርትና የጤና ታክስ የማይቀ
ሩለት ክፍያዎች ቢሆኑም የትምህርትም
ሆነ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ግን
እነዚያው የገዥ መደቦች አባላት እንጂ
ሰፊው ሕዝብ አልነበረም ። ቤተለይ የጭ
ቁን ብሔረሰብ አርሶ አደሮች ከጭሰኝነት
ሌላ በቋንቋ ፣ በባህልና በሃይማኖትም ተጽ
እኖ ስለሚያደርግባቸው ይደርስባቸው የነ
በረው ጭቆና የተደራረበ ነበር ።

የነበሩት እንዱስትሪዎችና የገንዘብ ድር
ጅቶች ለጥቂት ሞኖፖሊስቶች የቡርዧ ወገ
ኖች ጥቅም የሚንቀሳቀሱ ስለነበር የወዛ
ደሩ ጉልበት በከንቱ ከመበዝበዙ በላይ ይደ
ርስበት የነበረው ጭቆና እጅግ የከፋና መ
ራራ ነበር ።

በፖለቲካውም ረገድ ሰፊው ሕዝብ ተደራ
ጅቶ ስለራሱ ጉዳይ የሚወያይበት በአካባቢ

Digitized by Google

ውም ሆነ በአገር አቀፍ ውሳኔዎች የሚካ
ፈልበትና ድምጹን የሚያሰማበት መድረክ
አልነበረውም ። ፓርላማ የተባለውም የቡ
ርዧ ተቋም የገዥ መደቦች መወያያና የጥ
ቅማቸው ማስጠበቂያ እንጂ የሰፊው ሕዝ
ብ ፍላጐትና ብሶት የሚንጸባረቅበት መድ
ረክ አልነበረም ። ከላይ እስከታች የተዘረ
ጉት የአስተዳደር ፣ የፍርድና የፀጥታ መዋ
ቅሮችም የገዥ መደቡን የኢኮኖሚ የበላ
ይነት የሚረጋግጡ ፣ ሰፊውን ሕዝብ ግን
እንዳይናገር ለጉመው እንዳይንቀሳቀስ ቀፍ
ድደው የሚይዙ ተቋሞች ነበሩ ።

በባሕል አቅጣጫም ሰፊው ሕዝብ ታሪክ
እየሠራና ባህል እየፈጠረ ታሪክና ባህል
አልባ ሆኖ መቆየቱ ፣ ያከብር የነበረው የራ
ሱን ታሪክና ባህል ሳይሆን ለገዥ መደቦች
ማሞካሻና ዝና ማስከበሪያ ተብለው የሚቀ
ነባበሩትን መሆኑ ፣ እያንዳንዱ ብሔረሰቡ
በራሱ ቋንቋ የመጠቀምና የማስከበር መ
ብት መነፈጉ ፣ በማይምነት ቀንበር ተጠ
ምዶ በኋላ ቀር ባህልና ልማድ እንዲቆይ
መደረጉ ፣ ከዚህም በላይ አንድ ብሔረሰብ
ሌላውን እንዲንቅ ፣ በጥላቻ ዓይን እንዲተ
ያይ ፣ ትምክተኝነትና በጠባብነት እንዲ
ዳብሩ መደረጉ በቁጭት የምናስታውሳቸ
ፀረ—ሕዝብና ፀረ ዲሞክራሲ ድርጊቶች
ናቸው።ከነዚህም ጋር የሰፊውን ሕዝብ ወኔ
የሚሰልቡ ፣ ዓይኑን የሚጋርዱ ፣ የሻገተ
የጭቆና ሥርዓት ለዘላለም እንደማይገረሰስ
አድርጎ እንዲቀበል ፣ በራሱ የመፍጠር
ችሎታ እንዳይተማመንና ተፈጥሮንም ለ
መቆጣጠር ኃይል እንዳለውም እንዳይረዳ
የሚያደርገው ልፋፈና አደንቁረህ ግዛ
ው ከባድ የመንፈስ ተጽእኖ አሳድሮበት
ነበር ።

ይህ ሁሉ አንገፍግፎት ሰፊው ሕዝብ
ከግለሰብ አቤቱታዎች ፣ ሰላማዊ ሰልፎች
የሥራ ማቆም አድማዎች ፣ ትምህርት ማቋ
ረጥ ፣ ግብር አለመክፈል ፣ እስከ ጫካ መግ
ባትና አመጽ ማካሄድ ድረስ ብሶቱን በመ
ግለጽ መራራ ትግል አካሂዶአል ። ለ1966ቱ

አብዮት ፍንዳታም ምክንያት የሆነው ይኸ
ው በሰፊው ሕዝብና በጣምራ ጠላቶቹ በፊ
ውዶ ቡርዧው የገዥ መደቦችና ኢምፔሪያ
ሊዝም መካከል የነበረው ቅራኔ መካረር
ነበር ።

በድኅረ አብዮት ኢትዮጵያ የብሔረሰቦች
ጥያቄ የተሰጠውን ሥፍራ ከመመልከታችን
አስቀድመን ከላይ የተጠቀሰውን ማርክሳዊ
ቁም ነገር ማስታወሱ ይጠቅማል ። ይኸው
ም ፣ ኮሚኒስቶች በማናቸውም ንቅናቄ መሠ
ረታዊ የሆነውን ዐማኅበራዊ ግንኙነትም
ወሳኝነት ያለውን ፣ የመደብ ትግልም የሚ
ገለጥበትን የኢኮኖሚን ጥያቄ ፍጹም እንደ
ማይዘነጉ ነው ። አብዮት በሚካሄድባት የባ
ለብዙ ብሔረሰቦች ኢትዮጵያም ሰፊው
ሕዝብ አንድነቱ እንዲጠናከር ፣ ተፈቃቅ
ዶና ተፈቃቅሮ እንዲኖር ፣ የጥቅም አንድ
ነቱ እንዲከበር ይሻል ። ይህም አንድነት
የሚረጋገጠው ግንባር ቀደም የወዛደሩ
መደብ አብዮታውያን እንዳስቀመጡት የብ
ዝበዛና የጭቆና መሠረት የሆነው ፣ በግል
ይዞታ ላይ የተመሠረተው የሀብትና የንብ
ረት ግንኙነት ሲለወጥ ብቻ ነው ። ያለዚህ
ስለዲሞክራሲና ነፃነት ፣ ስለእኩልነትና
አንድነት ማውራት የቃላት ጨዋታ ሆኖ
ይቀራል ።

የኢትዮጵያ አብዮት በተግባር እንዳሳየ
ው ሰፊው ሕዝብ የጨቋኞችን የግፍ ቀን
በር በመራራ ትግል ሰባብሮ በመጣል
የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የሶሻል መደባዊ
ድሎችን በተጨባጭ ሁኔታ ተጐናጽፎ በብ
ሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም
ዓላማ እንደተመለከተው ለሕዝባዊ ዲሞክ
ራሲ መስፈን ጽኑ መሠረት እየጣለ ይገ
ኛል ።

በኢኮኖሚ መስክ ፣ ታሪካዊው የገጠር
መሬትን ለሕዝብ ያደረገው አዋጅ ለብዙ
ዘመናት ሰብእናውን እስከሚያጣ በጐልተ
ኞችና በባለመሬቶች ሲረገጥ የኖረውን አር
ሶ አደር ከብዝበዛና ከተደራረበ ጭቆና ነፃ

Digitized by Google

በማድረግ የጉልበቱና የምርቱ ውጤት ባለ
ቤትና ተጠቃሚ ራሱ እንዲሆን አድርጎ
ታል ። ይህ የመሬት አዋጁ ለጠቅላላው
ጭቁን አርሶ አደር ሕዝብ ነፃነትና እኩል
ነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጐናጽፍ ታሪ
ካዊና ሥር ነቀል እርምጃ ስለመሆኑ ፣ ከአ
ዋጁ አስቀድሞ በአብዮታዊ መንግሥት
የተሰጠው መግለጫ « ይህ አዋጅ እከሌ
ከእከሌ ሳይል ፣ ዘር ፣ ጾታ ፣ ጐሣና ሃይማ
ኖት ሳይለይ ፣ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የእ
ኩል መብት የሚሰጥ ፣ ከዚህ ቀደም በገ
ዥው መደብና በአጫፋሪዎቻቸው ተዘርፎ
ከሕዝብ ተወስዶ የነበረውን መሬት ወደ
ጥንት ባለቤቱ ወደሰፊው ሕዝብ የሚመ
ልስ ፣ በአጠቃላይ አነጋገር ሲገፉ ፣ ሲጨቆ
ንና ሲበዘበዝ የኖረውን አርሶ በላ ገበሬ
በሙሉ የሚያጠቃልል አዋጅ በመሆኑ ታ
ላቅ የምሥራች የሚያበስር አዋጅ ነው ፤ »
ሲል በትክክል አስቀምጦታል ።

ዛሬ የአብዮታችን ታሪካዊ ሂደት ቁልጭ
አድርጎ እንደሚያሳየው ይህ አነጋገር ተግ
ባራዊ የሆነና በሰፊው ሕዝብ ሕይወትም
የተዋሃደ ሆኖ እናገኘዋለን ። ዛሬ የገባርነ
ትና የጭሰኝነት ፣ የመዝረፍና የመዘረፍ
ግንኙነት የተቋረጠበት ፣ አንዱ ብዙ ጋሻ
መሬት ይዞ ሌላው መሬት አልባ ያልሆነ
በት ፣ ሠንጋ አደልቦ ፣ ሙክት ሞክቶ እሸት
ሸምጥጦ ለጉልተኞች ማስረከብና ለመተያ
ማቅረብ ያከተመበት ፣ እንዲሁም ሌሎች
አሳፋሪ ፊውዳላዊ ግዳጆች ከታሪክ መዘክ
ርነታቸው አልፎ ሌላ ሥፍራ ያጡበት
ኢትዮጵያ መሆኗን የአብዮታችን ጠላቶች
እንኳን ሳይቀሩ ሊሰውሩት የማይችሉት
ሐቅ ነው ።

የኢኮኖሚ የበላይነት የፖለቲካ የበላይ
ነትን ያስከትላል ። በፊውዳሉ ሥርዓት
መሬት ዋናው የኢኮኖሚ መሠረት ስለሆነ፣
በኢትዮጵያም ዘጠና በመቶ (90%) የሚ
ሆነው ሰፊው ሕዝብ ለፊውዳላዊ አገዛዝና
ጭቆና ተጋልጦ ከመሬት ጋር ተቆራኝቶ
ይገኝ ነበር ። በዚህ ሥርዓት የሰው መብት ፣
ማዕረግና ክብር የሚለካው ከመሬት ይዞታ
ጋር ተገናዝቦ ነበር ። ዛሬ ይህ መሬትና ከላ
ዩም የሚገኘው ምርት የራሱ የአርሶ አደሩ
ሆኗል ። በዚህም ከላይ እንደተገለጸው
አርሶ አደሩ የዘር ፣ የጾታ ፣ የጐሣና የሃይማ
ኖት ገደብ ሳይኖርበት እኩልነቱን ፣ ነፃነ
ቱንና የበላይነቱን አረጋግጦና አስከብሮ
ይገኛል ።

ዘለቄታ ላለው አንድነትና ብልጽግና የተ
በታተነ የመሬት ይዞታና በኋላ ቀር የምርት
ልምድ ጭሮ መኖር የትም እንደማያደርስ
ሰው በመገንዘብ አርሶ አደሩ ያገኘውን ነፃ
ነትና እኩልነት ተጠቅሞ ለሶሻሊዝም መዳ
በር መሠረት የሆነውን የኅብረት ሥራ ማኅ
በራት ንቅናቄን በማፋፋም ላይ ይገኛል ።
በየጊዜው ቅርጹን ለውጦ ከሚከሰት ብዝ
በዛ ነፃ ለመሆን ፣ ከኋላ ቀርነት ለመላቀቅና
ለሶሻሊስት አመራረትም የሚበጅ አስፈላጊ
መሠረት ለመጣል አርሶ አደሩ ከተበጣጠ
ሰና ከግለኛ የእርሻ ይዞታ ተላቅቆ ደረጃ
በደረጃ ወደ ጋርዮሽ ይዞታ ለመሸጋገር
አማራጭ የሌለውን የዕድገት ጐዳናውን
ተያይዞታል ።

የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት
ሰፊውን ሕዝብ በኢኮኖሚ ማጐልበት ብቻ
ሳይሆን ፣ በፖለቲካና በማኅበራዊ ጉዳይም
በመደብ አንድነቱ ተቀራርቦ እንዲታገል
የሚያደርጉ ዲሞክራሲያዊ መድረኮች ስለ
መሆናቸው የገበሬዎች አምራቾች የኅብ
ረት ሥራ ማኅበራት መመሪያ « የአምራቾች
የኅብረት ሥራ ማኅበር በአሠራሩ ዲሞክራ
ሲያዊ ማዕከላዊነትን የተከተለ ሆኖ በማንኛ
ውም ተግባሩ በጾታ ፣ በሃይማኖትና በብሔ
ረሰብ ምክንያት ልዩነት አያደርግም » በማ
ለት አስቀምጦታል ። ትክክለኛነቱም በሥ
ራ እየተተረጐመ ነው ።

ለሰብአዊ ሕልውና መሠረት የሆነውን
የምርት ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልጉ
የሥራ መገልገያዎች የሚሠሩት በተለያዩ
የዕደ ጥበብ ሙያ በተሰማሩ የሰፊው ሕዝብ

Digitized by Google

ወገኖች መሆኑ የታወቀ ነው ። ፊውዳሊስ
ቶች በእነዚህ የሥራ ውጤቶች ለመጠቀምና
ለማጌጥ የመጀመሪያዎቹ እንደመሆናቸው
ሁሉ እነዚህን ዕቃዎችና መገልገያዎችን የፈ
ጠሩትን ሠርቶአደሮች ለማንቋሸሽና የኅ
ብረተሰብ አነስተኛ ክፍል አድርገው ለማ
ቅረብ ቀዳሚ ተዋናይ ናቸው ። ዛሬ እነ
ዚህ አምራች እጆች የሚያፍሩ ሳይሆኑ በሥ
ራ ውጤታቸው የሚኩሩ ለሙያቸውም ተገቢ
ክብርና ትኩረት ተሰጥቶአቸው በኅብረት
ሥራ ማኅበራት እየተደራጁ ወደ ዳበረ የም
ርት ክንዋኔ በመሸጋገር ላይ ይገኛሉ ።

የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን በመንግሥ
ታዊና በሕዝባዊ ቁጥጥር ሥር ያዋለው አዋ
ጅም የፊውዳሉን የመጨረሻ የኢኮኖሚ
ምሽግ አፈራርሶ የሰፊውን ሕዝብ የበላይ
ነት አረጋግጧል ። በዚህም ሰፊው ሕዝብ
የከተማ ቦታን ዋጋ እንዳሻቸው እያናሩ
ከሚበዘብዙት ከበርቴዎች ፥ በየወቅቱ የቤት
ኪራይን ያለቅጥ ከፍ እያደረጉ ከሚያራቁ
ቱት የቤት አከራዮችና ከእነዚህም ጋር ተያ
ይዞ ከሚጧጧፈው የአራጣ ገፈፋ ሊድን
ችሏል ። ዛሬ የከተማ ቦታ የጋራ ሀብት በመ
ሆኑ ማንም ልዩነት ሳይደረግበት ለመኖሪያ
ቤት መሥሪያ ቦታ በነፃ ሊያገኝ እንዲችል
ተደርጓል ።

እንዲሁም ዋና ዋናዎቹ የማምረቻ ፥ የማ
ከፋፈያ ፥ የገንዘብና የአገልግሎት ሰጪ
ተቋሞችም ከግል ይዞታ መውጣታቸው
ወዛደሩ ከኢምፔሪያሊዝምና ከቡርዧ ብዝ
በዛ ወጥመድ ተላቆ ለጋራ ጥቅም እንዲ
ሠራ ከማድረጉም ሌላ ለሶሻሊስታዊ የም
ርት አደረጃጀት አዲስ ጐዳና ከፍቷል ።
በዚህም የማምረቻና ለማከፋፈያ ተቋሞች
ትርፍ ለጥቂት ሞኖፖሊስቶችና ለገብረ
አበሮቻቸው መሆኑ አክትሞ ለሀገሪቱ ዕድ
ገት ፥ ለሰፊው ሕዝብ ማኅበራዊ አገልግሎት
ና ምቾት እንዲውል ተደርጓል ። የገንዘብ
ድርጅቶችም አቅም በፈቀደው መጠን ለገ
በሬና ለዕደ ጥበባት አምራቾች የኅብረት
ሥራ ማኅበራት መጉልበትም ሆነ ሌሎች
የሶሻሊዝምን ዕድገት ለሚያፋጥኑ የኢኮ
ኖሚ መስኮች አስፈላጊውን ዕርዳታ እን
ዲሰጡ ሆነው ተደራጅተዋል ።

በፖለቲካውም ዘርፍ ፥ አሮጌው የዘውድ
አገዛዝና የፊውዶ ቡርዧው መዋቅሮች ተሰ
ባብረው በሳይንሳዊው ሶሻሊዝም መመ
ሪያነት ሰፊው ሕዝብ ነቅቶ ፥ ተደራጅቶና
ታጥቆ የራሱ ዕድል ወሳኝ ራሱ እንዲሆን
በተለያዩ የብዙኃንና የሙያ ድርጅቶች
ውስጥ ራሱን አደራጅቶ በንቃት በመሳተፍ
ጥቅሙን በማስከበር ላይ ይገኛል ። ከቀበሌ
እስከ አገር አቀፍ ድረስ በመኢሠማ ፥ መኢ
ገማ ፥ አኢወማና አኢሴማ ወዘተ - - - እንዲ
ሁም በከተሞች ከቀበሌ እስከ አጠቃላይ
በተዋቀሩት ከነማት መደራጀቱ ሕዝባዊ
ዲሞክራሲን በጥልቀትና በስፋት ተግባ
ራዊ ማድረግ ለሚደረገው ጥረት አስተማ
ማኝ ጅምር መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ለሶ
ሻሊስት ግንባታ አመራር ሰጪነት ሌላ አማ
ራጭ የማይገኝለትን ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖ
ለቲካ ፓርቲ ለማዋቀር በሚደረገው አብዮ
ታዊ ትግልም የኢሠፓአኮ መከሰትና ሥራ
ውንም በማፋፋም ላይ መገኘት አስተማ
ማኝ የግንባታ መሠረት እየጣለ ነው ።

ከአድኃሪው ፊውዳል ሥርዓት የተላለ
ፉትን የብሔረሰቦችን ችግሮች መፍትሔ
በሚመለከት የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብ
ዮት ፕሮግራም «በኢትዮጵያ ውስጥ የሚ
ገኝ ማንኛውም ብሔረሰብ የራሱን ዕድል
በራሱ የመወሰን መብቱ ታውቆለት አንዱ
ከሌላው ሳይበልጥ ታሪኩንና ማንነቱ ፥
ባህልና ልማድ ፥ ቋንቋው ፥ ሃይማኖትና
መብቱ በሶሻሊዝም መንፈስ በእኩልነት
ይከበራል ። የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አን
ድነት የጋራ ጠላቶቻቸውን፥ፊውዳሊዝምን
ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ፥ ኢምፔሪያ
ሊዝምንና ሌሎች አድኃሪ ኃይሎችን
ለመደምሰስ በሚያስፈልጋቸው የትግል
አንድነትና አዲስ ኑሮ ለመገንባት በእኩ

Digitized by Google

ልነት ፣ እርስ በርስ በመረዳዳት ፣ በወንድ ማማችነትና በመፈታቀድ ላይ የተመሠ ረተ ይሆናል » በማለት በማያሻማ ሁኔታ ትክክለኛውን የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀ ምጧል ። እንዲሁም በኢትዮጵያ ተጨ ባጭ ሁኔታ የብሔረሰቦች ቅራኔ ሊፈታ የሚችለው ብሔረሰቦች በአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር (በሪ ጅናል አውቶኖሚ) ያላቸው መብት ሲረ ጋገጥ መሆኑን አስረድቷል ።

ከፍ ብለው የተጠቀሱት መሠረታዊ የአ ብዮቱ ድሎች እነዚህን ዓላማዎች ከፕሮ ግራም ባሻገር በሂደት ተግባራዊ እያደ ረጉ መጥተዋል ። አብዮቱ የብሔረሰብ ጭቆና መሠረት የሆኑትን መንስኤዎች በማስወገድ በኩልም ምን ያህል እንደተ ጓዘ የሚያረጋግጡ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ነው ። በአሁኑ ጊዜ በ15 የተለ ያዩ ቋንቋዎች መሠረተ ትምህርት ተስፋ ፍቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደናቂነት ያተ ረፈ ውጤት መገኘት ፣ በልዩ ልዩ 6 ያህል የብሔረሰብ ቋንቋዎች የሬዲዮ ፕሮግ ራም መጀመር ፣ የመጻሕፍትና የጋዜጦች በልዩ ልዩ ቋንቋዎች መታተም ፣ የኪነ ጥበብ መስፋፋት ፣ የአንዳንድ ቦታዎች በሕዝቡ ፍላጐት በትክክለኛ ስማቸው መጠራትና የሃይማኖት እኩልነት መታ ወጁና ሌሎችም አብዮቱ የብሔረሰቦችን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የወሰ ዳቸው ተጨባጭ እርምጃዎች ናቸው ።

ስለባህል መከበር ስናነሳ መረሳት የሌለ በት ለአብዮቱ ሂደት ማነቆ የሚሆኑትን ጐታች ባህሎችና ልምዶች እየተው ጠቃ ሚዎቹን እያዳበሩ ሶሻሊስታዊ ይዘት እንዲኖራቸው መጣር አስፈላጊ መሆኑ ነው ። የአብዮታችን ፕሮግራም እንዳስ ቀመጠው በሀገሪቱ የተሰበጣጠሩ ባህ ሎች ከኢምፔሪያሊዝም የባህል ወረራና ከቆየ አድኃሪ ይዘታቸው ተላቀው ዘመኑ ካፈራው ዕውቀት ጋር እየተዋሐዱ ፣ በእ ርሱም እየታገዙ እንዲበለጽጉና እንዲራ መድ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ተገቢ ነው ።

ከላይ እንደተጠቀሰው የብሔረሰቦች ቅራኔ የመደብ ትግል አንዱ ገጽታ ነው ። የመደብ ትግሉም መሠረት የምርት መገ ልገያዎች በግል ይዞታ ሥር መዋል ነው። ስለሆነም፣ አብዮታችን ዋና ዋናዎቹን የማ ምረቻ ፣ የአገልግሎትና የማከፋፈያ ድር ጅቶችን በመንግሥታዊና በሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሥር ያደረገው መደባዊና ከዚያም ጋር ብሔራዊ ቅራኔዎች ከመሠረቱ እንዲ ፈቱ መንገድ መቀየሱ ነው ። የሆነ ሆኖ ለብዙ ዘመናት ተንሰራፍተው የቆዩ ፊው ዳላዊና የቡርዧ አመለካከቶችን በአጭር ጊዜ ለማጽዳትና ወዝአደራዊ አመለካከ ትን ለማስፈን ጠለቅ ያለ ትግልና አፋጣኝ የአስተሳሰብ ለውጥም ይጠይቃል ። ይህም ሂደት በተገኙ ተጨባጭ ድሎች መንደር ደሪያነት ለሶሻሊዝም ጽኑ ቁሳዊ መሠረት ከመገንባት ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው ።

አርጌውን አፍርሶ ወደ አዲሱ ሥርዓት ጉዞ ሲደረግ የተነደፉትን ዓላማዎች በአ ፋጣኝ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር የተ ጨባጭ ሁኔታ አቅምን የመወሰን ነገር በመኖሩ እንጂ ከላይ እንደተጠቀሰው የአ ብዮቱ መመሪያ ፕሮግራም ለሰፊው ሕዝብ በሪጅናል አውቶኖሚ ራሱን ለማስተዳደር ያለውን መብት አረጋግጧል ። ፕሮግ ራሙ ተግባራዊ ሲሆን ሕዝቡ በየደረጃው ተደራጅቶ በማከናወን ላይ ያለውን የዲሞ ክራሲ ልምድን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያሸጋ ግርለታል ።

ይህንን መሠረቱ ተንዶ ያለውን የብሔ ረሰቦች ጥያቄ መሸፈኛ በማድረግ የፀረ— አንድነትና ፀረ—አብዮት ወንበዴዎች ከኢምፔሪያሊዝምና አድኅሮት በሚሰጣ ቸው ሙሉ ድጋፍ በኤርትራ ክፍለ ሀገር አብዮታችንን ቢፈታተኑም ችግሩን በሰ ላማዊ መንገድ ለመፍታትም በየወቅቱ አስፈላጊ እርምጃዎች ተወስደዋል ። በነ ዚህም መካከል ለዘላቂ መፍትሔ መሠረት

Digitized by Google

እንዲጥል በአብዮታዊው መንግሥት ወጥ ቶ የነበረው የግንቦት 8 ቀን 1968 ባለዘ ጠኝ ነጥብ የፖሊሲ ውሳኔ ፥ ጓድ ሊቀ መን በር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ግንቦት 30 ቀን 1970 ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ያደረጉት ንግግ ርና ችግሩን ከመደብ ትግል ጋር አገናዝቦ ሐቁን ይፋ ለማድረግ በሰኔና በሐምሌ ወራት 1970 የተደረገው ሴሚናር እንደከ ፍተኛ ምሳሌ ይጠቀሳሉ ።

ዛሬም ከብቸኛ ፖለቲካ ድርጅታችን ከኢሠፓአኮ መመሥረት በኋላ አብዮታ ችን ጥራትና ጥልቀት እያገኘ እንደመም ጣቱ የተወረሱትንም ችግሮች ሁለገብ በሆነ አቀራረብ ለዘለቄታው ለመፍታት ስትራቴጂና ታክቲክ እየቀየሰ ነው ። ፖለ ቲካዊ ፥ ኢኮኖሚያዊ ፥ ማኅበራዊ ፥ ባህላ ዊና ወታደራዊ ገጽታዎች ያሉት የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሁለገብ የቀይ ኮከብ ዘመቻም የዚህ አሠራር አንድ አካል ነው ።

ዘመቻው የተጀመረው ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጥር 17 ቀን 1974 ባደረጉት ከፍተኛ የፖሊሲ ንግግር ተመሥርቶ በወጣው ታሪካዊ የአሥመራ ማኒፌስቶ ነው ።

ማኒፌስቶው ስለብሔረሰቦች ያቀረበ ውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ ትን ተና ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ፥ ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ ለሚገኝ ኅብረተሰብ የብሔረሰቦች የራ ስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት በበዝባዥ ሥርዓት ይደርስባቸው ከነበረው ጭቆና ነፃ መውጣታቸውንና ዳግመኛም ምንም ዓይነት ጭቆና የማይደርስባቸው መሆ ኑን ለማረጋገጥ በውስጥ አስተዳደር የፖለ ቲካ ነፃነት እንደሚኖራቸውና ጭቆናም ጨርሶ የሚያከትመው ሶሻሊዝምን በመ ገንባት መሆኑን አረጋግጧል ።

ለአዲሱ ሥርዓት ምሥረታ ፥ ለዘላቂ እኩልነትና ፍትሕም መስፈን የሰፊውን ሕዝብ ትግል በመምራት ላይ ያለው ኢሠ ፓአኮ ለብሔረሰቦች ጉዳይ ከፍተኛ ትኩ ረት መስጠቱን የሚያሳየው አንድ ተጨ ባጭና ዓቢይ ርምጃ በማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ ቤት አንድ ራሱን የቻለ የብሔረሰቦች ጉዳይ መምሪያ እንዲቋቋም ማድረጉ ነው። ይህንንም የመፍትሔ ፕሮግራም ተግባ ራዊ በማድረግ መምሪያው በብሔራዊ ዲ ሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ለብሔረሰቦች ጥያቄ ዘላቂና ሳይንሳዊ መፍ ትሔ ለመስጠት እንዲያመች አስፈላጊ ውን ዝግጅትና ጥናት በማድረግ ላይ ነው። ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በየአቅጣጫው የሚደረገው የግንባታ ትግል ዘላቂ ዋስትና የሚያገ ኘው የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ከረዥሙ ግባ ችን ጋር የተቀናጁና የተሳሠሩ ሲሆን በመ ሆኑ የብሔረሰቦችም ጥያቄ ትክክለኛ መፍትሔ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱ ትን የአሠራር ስልቶች በመከተል ተጨባ ጭና ትክክለኛ እርምጃ ሲወሰድ ብቻ እንጂ የግለሰቦችን ኩርፊያና የሆደ ባሻዎችን ስሜት ለማስታገስ ሲባል የሚወሰድ የግ ብታዊ እርምጃ ባለመኖሩ የብሔረሰብ ጉዳይ መምሪያ «በዓይነታቸው በሀገራችን ውስጥ የመጀመሪያ የሆኑትን መሠረታዊ ጥናቶች በማካሔድ» ላይ ይገኛል ። ይህም ዝግጅት ከአሁን ቀደም በጥያቄው ላይ የነበሩትን ውዥንብሮች ከማፅዳቱም ባሻ ገር በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ብሔረ ሰቦች የዕድገት ደረጃ ፥ የአኗኗር ሁኔታ ባህልና ታሪክ ትክክለኛውን ገጽታ ያሳ ያል ።

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ መ ደበኛ ስብሰባም በጓድ ሊቀ መንበር መንግ ሥቱ ኃይለ ማርያም ሪፖርት እንደተመለከ ተው ፥ የኢሠፓአኮ ጥረት የብሔረሰቦችን እኩልነት በጊዜያዊነት ሳይሆን ዘላቂነት ባለው መንገድ ፥ ለይስሙላ ሳይሆን ለሕ ዝቦች እውነተኛ ነፃነትና እኩልነት መከ በር ፥ ባለው ፅኑ እምነት መፍትሔ ለመ

Digitized by Google

ስጠት መሆኑ ተገልጿል ። ይህ ቁሳዊ መገለጫ የሚያገኘው የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ፥ ፖለቲካና ማኅበራዊ ኑሮ በተጀመረው በአዲሱ ሶሻሊስታዊ ፈር በመገንባት መሆኑም በግልጽ ቀርቧል ።

ከላይ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ማለትም ሠራተኛው፥ ገበሬው ፥ ወታደሩና ተራማጅ ምሁሩ በትግላቸው በተጐናጸፉቸው መደባዊና ርዕዮተዓለማዊ አንድነታቸው በፊውዶ ቡርዧው መደብና በአድኀሮት ኃይሎች ላይ ድል ተቀዳጅቷል ።

የብሔረሰቦችም ጥያቄ ከዚህ ውጭ የሆነና የራሱን የቻለ ሕልውና የለውም ። የተገኙትን ታሪካዊ ድሎች በመጠቀም አስተማማኝ የሶሻሊስት ቁሳዊ መሠረት መገንባት አማራጭ የሌለው የዕድገት ጉዳናና ለመደባዊና ብሔራዊ ቅራኔዎችም መክሰሚያ ነው ። የኢትዮጵያ አብዮት የመረጠውና የሚያራምደው ይህንኑ ፈር ነው ።

ታላቁ ሕዝባዊ አብዮታችን ከስምንት ዓመታት ወዲህ ለብሔረሰቦች ችግር ተከታታይ ተግባራዊ መፍትሔዎችን እየሰጠ ወደፊት በአስተማማኝ ጉዳና ሲጓዝ የሰፊው ሕዝብና የታሪክ ሂደት የተፋቸው አተላዎች በኢምፔሪያሊዝም ምንደኛነታቸው የብሔረሰብ ጭቆናን በመሣሪያነት በመጠቀም አብዮታዊ ግዕበሉን ለመግታት ባላቸው ከንቱ መፍጨርጨር የተቻላቸውን ከማድረግ አልተቆጠቡም ። በተለይም ዛሬ ብሔረተኝነት ከአካባቢ ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ ድረስ ለቡርዧ ፀረሶሻሊስት ቅስቀሳ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ ባለበት ወቅት ጠባቦች ፥ ገንጣዮችና ትምክህተኞች በአጠቃላይ የአድኀሮት ቡድኖች ይህንኑ በአገራችንም በየመስኩ መቀስቀሳቸውና የመደብ ትግሉን ለማዘናጋት መጣራቸው አልቀረም ።

ፀረ አንድነት ወገኖች ፥ እርስ በርሱ ተጠላልፎ የሚወድቅ ኢሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብና ታሪክ እያዛቡ ማቅረብ መተዳደሪያቸው ያደረጉ አንዳንድ ደጋፊዎቻቸውና የቡርዧ ምሁራን እንደሚያቀርቡት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ረጂምና የተሳሰረ ታሪክ ያለው ነው ። የብዙ አገሮችም ታሪክ እንደሆነ ሁሉ ኢትዮጵያም የተገነባችው ለብዙ ዘመናት ከሰሜን ወደ ደቡብ ፥ ከደቡብ ወደሰሜንና ወደ ሌሎችም አቅጣጫዎች በየምክንያቱ በተደረገው የሕዝቦች መዘዋወርና መስፈር ፥ ጥልና ዕርቅ ፥ ጦርነትና ሰላም ፥ ግጭትና ጋብቻ ፥ - - - ነው። የቡርዧ አንትሮፖሎጂስቶች እንደሚያደርጉት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዘር ወይንም ከጐሳ ፅንስ ሐሳብ አንጻር እንኳን ብንመለከተው ከብዙ ዘመን ግንኙነትና መስተጋብሩ የተነሳ ፀረ አንድነት ቡድኖች እንደሚለፍፉት የተለያየ ሳይሆን ከፍተኛ ተመሳሳይነትና አንድነት ያለው ሕዝብ ሆ ና እናገኘዋለን ።

የኢትዮጵያ አንድነት የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዳይደለና የአገራችን ብሔረሰቦችም በሙሉ ለዛሬው ሕልውናችን በየአቅጣጫው አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑን የምንረዳው የብዙ ምዕተ ዓመታት ታሪካችንን በትክክል ስናገናዝብ ነው ። ከሁሉም በላይ ሰፊውን ሕዝብ የሚያኮራው በቅርቡ የምናስታውሳቸው በአድዋ የኢምፔሪያሊስት ቅኝ ገዥዎችን በአንድነት ክንዱ ማንበርከኩ፥ በኤርትራ ውስጥ ፀረ ኮሎኒያል ትግሎችን ማካሄዱ ፥ የፋሺስትን ወረራ በአንድነት መዋጋቱ ብቻ ሳይሆን ከሰሜን የባሕር ጠረፍ ጀምሮ እስከ ደቡብ ድንበራችን የአለው ሰፊ ሕዝብ በፊውዶ ቡርዧ የጭቆና ቀንበር ሥር በአንድነት ይደርስበት የነበረውን መከራ በመደባዊ አንድነቱ አሽቀንጥሮ በመጣል ለአፍሪካና ለሌሎች ጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ችቦ አብሪ ከመሆን ባሻገር ፥ አዲስና የበለጸገም ሥርዓት ለመገንባት በተያያዘው ትግል አስተማማኝ መሠረት እየጣለ ባለው ምሳሌነቱ ነው ።

Digitized by Google

በዚህም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሺእ ገራፊ ፣ ታሪክና ያለፉት ትውልዶች ያወረሱትን ውድ አገር ተረክቦ ግንኙነቱ ከቤተዘመድ ፣ ከጐሳና ከብሔረሰብ አልፎ ዛሬ ከፍተኛ ወደሆነው በንቃት ላይ ወደተመሠረተ መደባዊ አንድነት በመሸጋገር ላይ ይገኛል ። በዚህ አንድነቱ የበለጸገች ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት የኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ በተጨባጭ ለዓለም አቀፍ አብዮታዊ ትግል በማበርከት ላይ ያለው አስተዋጽኦ ነው። ይህንንም ለመወጣት በሚያደርገው ከፍተኛ ትግል የተራማጅና ሶሻሊስት ኃይሎች ተጨባጭ ድጋፍም እንዳልተለየው በግብር እየታየ ነው ።

በጠንካራ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር ሥር ሶሻሊዝምን መገንባት ለብሔረሰብና ለመደብ ቅራኔዎች ብቸኛ መልስ መሆኑ ተደጋግሞ ተጠቅሷል ። ዛሬ ኢሠፓአኮ ነገም የሠርቶ አደሩ ፓርቲያችን ይህ ከባድና ታሪካዊ ኃላፊነት አለባቸው። በሰፊው ሕዝብ መካከል እኩልነትና ወንድማማችነት እንዲሰፍኑ ያሉን የባህልና የቋንቋ ብዛት የማለያያ ምልክቶች ሳይሆኑ በአካባቢያችን የሰው ልጅ በታሪኩ ያካበታቸው የጋራ መዋጮ ፣ አኩሪ ቅርሶቻችንና ሀብቶቻችን መሆናቸው ታውቆና ተከብሮ ሳይንሳዊ ይዘትን እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ አጅግ አስፈላጊ ነው ።

በተያያዝነው ረጅም የትግል ጉዞአችንም የፓርቲው ተግባር በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የማሌን ትምህርት በጥልቀት ማስፋፋት ፣ ሐቀኛ ካድሬዎችን ማሰለፍና መሠረታዊ ድርጅቶችን ማጠናከር ፣ የመደብ ትግሉን ማፋፋም ፣ በጽኑ መከላከያ የአብዮታዊት እናት ሀገርን አንድነትና ሕልውና መጠበቅና ፣ የጠባቦችንና ትምክህተኞችን ፣ በጠቅላላው በየሥፍራው ተሰግስገው የሚያሾፉና የሚያሴሩ የቀልባሾችን አሻጥር መምታት ፣ በኢኮኖሚና በባህል ኋላ ቀር በሆነ የማኅበረሰብ ደረጃ ላሉት እገዛ ማድረግ ፣ የአካባቢን አስተዳደር በየደረጃው ተግባራዊ ማድረግ ፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፕሮግራም በስፋትና በጥልቀት ተግባራዊ አድርጎ ሶሻሊዝምን መገንባትና ሁሉንም ወደ ኮሚኒዝም መምራት ይሆናል ።

ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)

— Marx and Engels, *Collected Works*, Vs. 6 & 8, Moscow, 1977.

— V.I. Lenin, *Selected Works*, Vol. 1, Moscow, 1975

— J. Stalin, *Marxism and the National Colonial Question:* Proleterian Publishers, San Francisco, 1975.

— *Class Struggle and the Problem in Eritrea*, Addis Ababa, 1979.

— Tarekegn Adebo, *Ethnicity vs Class, Concepts in the Analysis of Ethiopian Revolution*, (A paper presented at the Seventh International Conference of Ethiopian Studies, Lund, Sweden, 1982).

—የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ፣ አዲስ አበባ 1967

—የገጠርና የከተማ መሬቶች ለሕዝብ ያደረጉ ዓዋጆች ፣ አ.አ ፣ 1967

—በኤርትራ ክፍለ ሀገር ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተሰጠ የፖሊሲ ውሳኔ ፣ አ.አ ፣ 1968

—ለኢሠፓአኮ አራተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ የጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ማዕከላዊ ሪፓርት ፣ አ/አ ፣ 1974

—የአሥመራ ማኒፌስቶ ፣ አሥመራ ፣ 1974

Digitized by Google

የሐተታ ገጽ

የኢምፔሪያሊዝም ጠረኝነትና የሰላም ጥያቄ

ቀኑ ነሐሴ 6 ቀን1945 ከጧቱ 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ከ30 ሰኮንድ ላይ ነው ። ጃፓን ካሏት ደሴቶች መካከል የሄሮሺማና የናጋሳኪ ደሴቶች ነዋሪዎች ማለዳ ተነስተው የዘወትር ተግባራቸውን ለማከናወን በንእቅስቃሴ ላይ ናቸው። ሕፃናት ወደ ትምህርት ቤት ፣ ሠራተኛውም ወደ ሥራው ሁሉም በየሥራ መስካቸው በመሰማራት ላይ ናቸው። በወቅቱ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እየተካሄደ ቢሆንም በጃፓን ግዛት ክልል ከባድ አደጋ ይፈጸማል ብሎ ያሰበ ያለ አይመስልም ። ነገር ግን የአሜሪካ አይሮፕላኖች ቦምብ ጭነው የጃፓንን የአየር ክልል ጥሰው ገቡ። ከገቡት አይሮፕላኖች መካከል አንዱ የተሸከመው ቦምብ ከ20 ሺህ ቶንቲ ኤን. ቲ. ኃይል ጋር እኩል የሆነና ከ300,000 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ ሙቀት የሚፈጥር ቦምብ ነበር ። ይህ ቦምብ ከጧቱ በ2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ከ30 ሰኮንድ በሄሮሺማ ደሴት ላይ እንደተጣለ ከተማዋን በሙሉ አዳረሳት ። የደሴቷ ከተማ ነዋሪ ከሆኑት 400,000 ሰዎች መካከል 240,000 የሚሆኑት አለቁ ። 163,000 ሰዎች ከፋኛ ተጐዱ ። የቦምቡ ፍንዳታ አካባቢውን በመመረዙ በአካባቢው የሚኖሩ የጃፓን ዜጐች እስከ ዛሬ ድረስ በካንሰርና በሌሎችም በሽታዎች የሚሰቃዩ ከመሆናቸውም በላይ ፣ ይኸው እልቂት አሰቃቂ በመሆኑ እስከ ዛሬ ከብዙዎች የጃፓን ዜጋዎች አእምሮ አልጠፋም ። ለዚህ አሰቃቂ እልቂት መግለጫ በሄሮሺማ በሚገኘው መቃብር ላይ «በሰላም እረፉ ፣ እንደዚህ ዓይነት ስህተት ዳግም አይፈጸምም» የሚል ጽሑፍ ይገኛል።* ከዚህም ሌላ የሄሮሺማ ከተማ የሰዓት ደወሎች የአደጋ ማስጠንቀቂያ ድምፅ አላቸው። እነዚህ ደወሎች ድምፃቸውን የሚያሰሙት በሌላ ጊዜ ሳይሆን ከጧቱ በ2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ከ30 ሰኮንድ ላይ ነው ። ይህም ከተማዋ ከቀን ወደ ቀን ከዓመት ወደ ዓመት በእሳት የጋየችበትንና በሞት ስቃይ የተጥለቀለቀችበትን ጊዜ ያስታውሳል ።

* ቀስተ ደመና ፣ ሐምሌ—ነሐሴ ፤ ቁ. 7-8 ፣ ገፅ 6.

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በጃፓንም ሆነ በሌሎች አገሮች ላይ ያስከተለው እልቂት ከዚያ በፊት ከተደረጉት ጦርነቶች ሁሉ አሰቃቂና አስከፊ እንደነበረ የታወቀ ነው። በዚህ ጦርነት ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሰው ሕይወት ከመጥፋቱም በላይ በረጅም ዘመናት ውስጥ የተገነቡ የሰው ልጅ የጥበብ ውጤቶች ወድመዋል። ይህ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለውን ጥፋት ያደረሰ ጦርነት ካበቃበት ጊዜ አንስቶ ሌላ ተመሳሳይ ጦርነት እንዳይፈጸም ለሰላም የቆሙ ኃይሎች በሙሉ ትግላቸውን ያለ ማቋረጥ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።

በአንፃሩ በየቦታው የሚካሄደውን የነፃነት ትግል ለማፈን ኢምፔሪያሊስቶች «ፈጣን ጣልቃገብ ጦሮችን» ያዘጋጃሉ፤ በየአካባቢው የጦር ስምምድ ያደርጋሉ፤ በሁሉም አህጉሮች ባሏቸው ጦር ሠፈሮች ውስጥ የመሣሪያ ክምችታቸውን ያጠናክራሉ፤ የሰው ልጅን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት የሚችሉ ስትራቴጅያዊ የጦር መሣሪያዎች በየወቅቱ እየሠሩ ያወጣሉ፤ በየአህጉሩ የአካባቢ ጦርነቶችን ይጭራሉ። በኢምፔሪያሊስት አገሮች የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ የሆነ ሚና የሚጫወቱት፣ በጦርነት መነሳትና በጦርነት ዝግጅት ከፍተኛ ተጠቃሚዎች የሆኑት የጦር ኢንዱስትሪ ሞኖፖሊስቶች በአገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ ማድረግ፣ ለሰው ልጅ ሕይወትና ንብረት ማጥፊያ የሰሯቸውን የጦር መሣሪያዎች በብዛት በማምረት ንግዳቸውን ማጧጧፍ ዋነኛውና ተቀዳሚ ዓላማቸው ሆኗል።

የሰው ልጅ ለዘመናት የገነባው ሥልጣኔና ማኅበራዊ ኑሮ እንዳይናጋበት አጥብቆ ይፈልጋል። ምክንያቱም በዓለም ላይ በተደጋጋሚ ጊዜያት እንደታየው በኢምፔሪያሊዝም ጠብ አጫሪነት በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት በሚገባ ግልፅ ሆኗል። ከዚያም ወዲህ ቢሆን በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጠብ አጫሪነት በቬየትናም፣ በመካከለኛው ምሥራቅ በላቲን አሜሪካና በአፍሪካ የበርካታ ሕዝቦች እልቂት፣ የኑሮ መመሰቃቀልና የማኅበራዊ ኑሮ መቃወስ ምን ያህል እንዳስከተለ በተደጋጋሚ ታይቷል።

ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን ሰላም ለማናጋት የጦር መሣሪያ እሽቅድምድምን፣ ጠብ አጫሪነትንና ወታደራዊ ጀብደኝነትን የዘወትር ተግባሩ አድርጐታል። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የመሰሎቹ ጠብ አጫሪ መሆን፣ ሰላም የሚናፍቀውን የአሜሪካንንና የአውሮፓን ሰፊ ሕዝብ ተቃውሞ አነሳስቷል። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚያካሂደው የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም ዛሬ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሥጋትና ውጥረትን በመፍጠሩ ይኸው ተቃውሞ በዩናይትድ ስቴትስ ብቻ ሳይወሰን ወደሌሎች የኢ ኢምፔሪያሊስት አገሮቹ ተዛምቶ ተመሳሳይ የሆነ ሕዝባዊ ተቃውሞን በማስከተል ላይ ይገኛል።

ዛሬ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን ሰላም ለማደፍረስ የተራቀቁ ጦር መሣሪያዎችን በገፍ ማምረቱን ተያይዞታል። ለጦር መሣሪያ ምርት የሚያወጣው ወጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በአንፃሩም በራሱና ተባባሪዎቹ በሆኑ የኔቶ አባል አገሮች ውስጥ የሥራ አጡ ብዛትና ማኅበራዊ ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል። ቢያዝነው ዓመት በዩናይትድ ስቴትስና በኔቶ አባል አገሮች ውስጥ ከ24 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ሥራ አጦች ይገኛሉ።* ከኔቶ አባል አገሮች ሌላ ተባባሪያቸው በሆኑት በ24 ቀንደኛ የካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ከ30 ሚሊዮን በላይ ሥራ አጦች አሉ።** በነዚህ አገሮች ውስጥ በሥራ አጥነት ከሚንገዋለለው መካከል አብዛኞቹ ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ናቸው። በዛሬ ጊዜ የዋና ዋና ካፒታሊስት አገሮች

---

* *Century and Peace*, 7-83, P. 40

** *Panorama DDR*, 2VI-79/2.2, eg, p. 6.

Digitized by Google

ኢኮኖሚ ዕድገት በማቆልቆል ላይ በመሆኑ
ሥራ አጥነት እየጨመረ በመሄድ ላይ ሲሆን፥
በዚያው ልክ ደግሞ የዋጋ ንረት እያሻቀበና
የኑሮ ውድነት እየተባባሰ በመሄድ ላይ ነው።

የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም የዋጋ
መናርንና ብሎም የኑሮ ውድነት የሚያስከ
ትል በመሆኑ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ
ሠርቶአደሩ ሕዝብ በከፍተኛ የኢኮኖሚያ
ዊና የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ ውስጥ እንዲዘ
ፈቅ ተደርጓል ። ዛሬ በዩናይትድ ስቴትስና
ተባባሪዎቿ በሆኑ በሌሎች ካፒታሊስት አገ
ሮች የሰላም ጥያቄ አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ
የቀረበው፥ በቅድሚያ ሰው በተፈጥሮው ለመ
ጥፋት ሳይሆን ለመኖር ያለው ፍላጐት ከሁ
ሉም ዓይነት ፍላጐት የበለጠ ከመሆኑ የተ
ነሳ ቢሆንም ፥ ከዚህም በተጨማሪ ኢምፔ
ሪያሊስት መንግሥታት ለጦር መሣሪያ ክም
ችት የሚያወጡት ወጭ ኢኮኖሚያዊና ማኅ
በራዊ ቀውስ እያስከተለ መሆኑ በግልጽ ስለ
ሚታይ ነው ። በተለይም የአሜሪካን ኢም
ፔሪያሊዝም ለዚህ ዓላማ ሆን ብሎ በመሰ
ለፍ እስከ 1986 ድረስ የሚሊታሪ ቴክኖሎ
ጂን ለማስፋፋት የ1.6 ትሪሊዮን ዶላር
ባጀት መድቧል ።* የጦር መሣሪያ ኢንዱስ
ትሪዎች በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋታቸው
የሲቪል ኢንዱስትሪ ዘርፉን በማዳከም ላይ
ይገኛሉ ። ዛሬ በዩናይትድ ስቴትስ የጦር
መሣሪያ አምራች በሆኑ ኩባንያዎች ውስጥ
ብቻ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ቁጥር
ከሌሎች የኢንዱስትሪ ዘርፎች ጋር ሲነጻ
ፀር 27.1 በመቶ ደርሷል ። ይህም ማለት
በአሜሪካ ውስጥ ዛሬ ከ50,000,000 ሠራተ
ኞች በላይ የሚሆኑ ወዛደሮች በጦር መሣሪያ
ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ይሠራሉ ማለት
ነው ።** ለጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ የሚው
ለው እያንዳንዱ ሺህ ሚሊዮን ዶላር ለ75,0
00 ሠራተኞች ብቻ ሥራ የሚያስገኝ ሲሆን
በልማት ላይ ቢውል ግን በትምህርት ዘርፍ
ለ178,000፥ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለ100,000
በፍጆታ ዕቃዎች ምርት ላይ ለሚሰማሩ
ለ112,000 ፥ በጤና አገልግሎት መስክ ለሚ
ሰማሩ ለ138,000 ሠራተኞች ሥራ ያስገኛ
ል።*** ይሁንና ኢምፔሪያሊዝም ከዕድገ
ትና ልማት ይልቅ የጦር መሣሪያ እሽቅድ
ምድም እንዲባባስና ዓለምም በከፍተኛ ውጥ
ረት ላይ እንድትወድቅ በማድረግ ላይ ይገ
ኛል ። በዚህ ሁኔታ በመጠቀም የኢምፔሪ
ያሊስት ሞኖፖል ኩባንያዎች የጦር መሣ
ሪያ ክምችታቸውን በማሳደግ እጅግ ከፍ
ተኛ የሆነ የሞኖፖል ትርፍ በማካበት ላይ
ይገኛሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም በተለይ የአሜሪካን ኢም
ፔሪያሊዝም የጦር መሣሪያ እሽቅድምድ
ምን በማፋፋም የሶሻሊዝምን የኢኮኖሚ
ዕድገት ለማቆምና ግስጋሴውንም ለመግ
ታት ቢያስብም ፥ እራሱ ባዘጋጀው ወጥመድ
ውስጥ ተተብትቦ በመያዝ ላይ ይገኛል ።
ዛሬ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚ
ውን ወደ ጦር ኢኮኖሚ በመለወጡ በከፍ
ተኛ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ
ተዘፍቆ ይገኛል ።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኢኮኖሚ
ውን ወደ ጦር ኢኮኖሚ በመለወጡ ምክን
ያት በአሜሪካ ውስጥ ኢኮኖሚያዊና ማኅ
በራዊ ቀውሱ ሥር እየሰደደ ከሬጋን አስተ
ዳደር ቁጥጥር ውጭ በመሆን ላይ ነው። ዛሬ
1.7 ሚሊዮን አሜሪካውያን የሄሮይን ዕፅ
453,000 አሜሪካውያን በመርፌ የሚሰጥ ዕፅ
ሱሰኛ ሆነው በየቀኑ መርፌ ሳይወጉ መንቀ
ሳቀስ አይችሉም። 43,000,000 አሜሪካውያ
ንና በዕድሜ ክልልም ከ12—17 ዓመት መካ
ከል ያሉ 4,000,000 ታዳጊ ወጣቶች በማ
ሪዩዋናና በሃሺሽ ሱስ ተጠምደዋል ። ከ20
እስከ 30,000,000 የሚደርሱ አሜሪካው
ያን ከመንፈስ ጭንቀትና በተለያዩ ማኅበ
ራዊ ችግሮች የተነሳ (የንክብል መድሐኒት)
ሱሰኛ ሆነዋል ። አንድ ሱሰኛ የሆነ የአሜ

* *New Times, June* 1982, *No.* 25, p. 10.
** *Century and Peace*, 7-82, *P.* 40.
*** *Ibid.*

Digitized by Google

ሪካ ዜጋ ሱስ ያስያዘውን መድኃኒትና ዕፅ
መግዣ የሚውል ባመት የ25,000 ዶላር
ወጭ ያስፈልገዋል ። ይህንን ፍላጐቱን ለማ
ርካት ደግሞ ሥራ አጥ በመሆኑ የግድ በወ
ንድጀልርጊት ላይ መሰማራትን ይመርጣ
ል ። ለምሳሌ በ1981 ቁጥራቸው ከ22,000
በላይ የሚሆኑ ሰዎች በተለያዩ የወንጀል
ድርጊቶች እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ሲገደሉ፣
8.8 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ የሚያወጣ ንብረት
ተሠርቋል ።* ዛሬ ቁጥሩ በሚሊዮን የሚቆ
ጠር የሥራ አጥ ብዛት በሚያናውጣት በአ
ሜሪካ የወንጀል ድርጊቶች እጅግ በሚዘገ
ንን ሁኔታ እየተካሄዱ ናቸው ። በአሜሪካ
ውስጥ የሚወጣው የወንጀል እስታቲስቲ
ክስ ከፍተኛ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ የሚወ
ጣን የጦርነት ጊዜ መግለጫ ይመስላል ።
በየ3 ሰኮንድ አንድ ወንጀል ፣ በየ23 ደቂቃ
ው አንድ ግድያ ፣ በየስድስቱ ደቂቃ ሴትን
አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ፣ በየ58ቱ ሰኮ
ንድ በመሣሪያ በማስፈራራት የሚካሄድ
ዝርፊያ ፣ በየ33 ሰኮንድ የመኪና ስርቆት
ይፈጸማል ። በዓመት ከ300,000 በላይ በመ
ሣሪያ በመጠቀም የሚካሄድ ወንጀል ይፈ
ጸማል ። በቬየትናም ጦርነት ወቅት በቬየ
ትናም ውስጥ 40,000 አሜሪካኖች ሲሞቱ ፣
በዚያው ወቅት በአሜሪካ ውስጥ 50,000
የሚሆኑ ሰዎች የግድያ ወንጀል ተፈጽሞባ
ቸዋል ። በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ በዚህ ዓይ
ነት ሁኔታ የተገደሉ የአሜሪካን ዜጐች ቁ
ጥር በውል ባይታወቅም ፣ እጅግ ከፍተኛ
እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም ። የአሜ
ሪካን ፕሬዚዳንቶችን ብቻ እንኳ ብንወስድ
ፕሬዚዳንት አብረሃም ሊንከን ፣ ጀምስ ጋር
ፊልድ ፣ ዊሊያም ማኪንሊና ጆን ኤፍ ኬኔዲ
ግድያ ፈጸመባቸው ሲሆን ፣ በፕሬዚዳ
ንት አ ጉ ጃክሰን ፣ ቲዎዶር ሩዝቬልት፣
ፍራንክሊን ሩዝቬልት ፣ ሃሪ ቱሩማን ፣ ጌራ
ልድ ፎርድ እና በቅርቡም በሮናልድ ሬጋን
ላይ የግድያ ሙከራ ተደርጓል ። በአጠቃላይ
በአሜሪካ ውስጥ በአሁኑ ወቅት በዓመት
ከ20,000 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ይገደላሉ ።
ሰዎች የሚገደሉት ሚሊዮን ዶላር ለማግ
ኘት ብቻ ሳይሆን ለጥቂት ዶላሮችና ሳንቲ
ሞችም ጭምር ነው ። ** የጸጥታ መደፍ
ረስ ጉዳይ ከአገሪቱ የጸጥታ ባለሥልጣኖች
ቁጥጥር ውጭ በመሆን ላይ የሚገኝ ሲሆን፣
ይኸው ድርጊት ዛሬ ራሳቸውን አሜሪካው
ያንን መልሶ ከፍተኛ ሥጋት ላይ ጥሏቸ
ዋል ። ወንጀል በአሜሪካ ውስጥ በከፍተኛ
ደረጃ ከመስፋፋቱ የተነሳ በአንድ ወቅት
<u>ዘ ኒዮርክ ፖስት</u> የተባለ የአሜሪካ ጋዜጣ
ወንጀልን በተለይም ግድያን «የአሜሪካን
ስፖርት» በማለት ሰይሞታል ።

ይህ ዓይነት የተመሰቃቀለ ማኅበራዊ
ችግር ጐልቶ የሚታይበት አሜሪካና መላው
የካፒታሊስቱ ዓለም ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ
እንደሚገኝ በአጭሩ ለማሳየት ተሞክሯል።
በአሁኑ ጊዜ የተደረሰበት የሣይንስና የቴክ
ኖሎጂ የዕድገት ደረጃ በብዙ ሚሊዮን ለሚ
ቆጠር የዓለም ሕዝብ የተደላደለና የተመቻ
ቸ ኑሮ ማስገኘት ሲችል ፣ ኢምፔሪያሊዝም
ግን መልሶ የዓለምን ሕዝብ ለጥፋት ሊዳር
ገው ተነሳስቷል። የዓለም ሕዝብ ግን የጦር
መሣሪያ እሽቅድምድም ቀርቶ በሰላም እን
ዲኖር ፣ የጦር መሣሪያ ክምችት የፈጠረው
ውጥረት እንዲረግብ ይፈልጋል። ለዚህ ዓላማ
የሚታገሉ ሶሻሊስት አገሮችና መላው ሰላም
ወዳድ ሕዝብ ለዓለም ሰላም መስፈን ትግላ
ቸውን በማፋፋም ላይ ናቸው። ዛሬ በዓለማ
ችን 500 ሚሊዮን ሥራ አጦች አሉ፤ 450 ሚ
ሊዮን ሰዎች ይራባሉ፤ 130 ሚሊዮን ሕፃ
ናት የመማር ዕድል አላገኙም፤ 870 ሚሊዮ
ን ማይምናን አሉ ፤ 25 ሚሊዮን ሕፃናት አ
ምስት ዓመት ሳይሞላቸው በችግር ምክን
ያት ይሞታሉ ፤ 280 ሚሊዮን ሕዝብ ለጤ

* *Socialism: Theory and Practice*, No. 6, June 1982, P. 111.
** *New Times*, October 1982, No. 44, P. 24.

Digitized by Google

ንነት አደገኛ በሆነ አኳኋን ይኖራል ።*

እነዚህ ሁሉ ከችግር ለመላቀቅ የዓለምን ሕዝብ ዕርዳታ የሚፈልጉ ናቸው ። ሊወገዱ የሚችሉትም የዓለም ሕዝብ በሚያደርገው የጋራ ትብብር ነው ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ግን ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ጆሮ ዳባ ልበስ በማለትና የጦር መሣሪያ ክምችቱን በማጧጧፍ የወታደራዊ የበላይነትን ለመቀዳጀት በመራወጥ ላይ ይገኛል ። ለዚህም የሠራተኛ ሕዝቦች የሥራ ፍሬ የሆነውን በብዙ ቢሊዮን የሚገመት ሀብትና ገንዘብ ለጦር መሣሪያ ምርት ያውላል ። በኋላቀር አገሮች መካከል አንድነትና መግባባት እንዳይፈጠር በማድረግ ያላቸውን አነስተኛ ሀብት ለጦር መሣሪያ ግዢ እንዲያውሉት ያደርጋል ። በአጠቃላይ ዓለምን ወደ ቀዝቃዛው ጦርነት በመመለስ የዓለም ሕዝቦች ለሰላም ለዕድገትና ለእውነተኛ ነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ለመግታት ብቻ ሳይሆን ፣ በየጊዜው በማሻሻል እየሠራ በሚያወጣቸው ስትራተጂያዊ የጦር መሣሪያዎች አማካይነት በዚች ዓለም የሰውን ሕልውና እራሱ አስጊ የሆነ ሁኔታ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ ላይ ነው ።

የሶሻሊስት አገር ሕዝቦች ፣ የታዳጊ አገሮች ጭቁን ሕዝቦች ፣ የካፒታሊስት አገር ሠርቶአደሮችና ለሰላም የቆሙ ኃይሎች በሞላ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ዛሬ በዓለም ላይ ያለው ውጥረት እንዲላላና የጦር መሣሪያ እሽቅድምድም እንዲቆም ፣ በአጭሩ በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን መታገል አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ተረድተውታል ። በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም የኃይል ሚዛን ወደ ሶሻሊዝም በማድላቱ ለሰላም የሚደረገው ትግል አስተማማኝ የሆነ ደጋፊ አግኝቷል ። ሶቭየት ኅብረትና ሌሎች ሶሻሊስት አገሮች እንዲሁም ሰላም ወዳድ አገሮችና ሕዝቦች ያካሄዱት ትግል ቀዝቃዛውን ጦርነት ለማርገብ ፣ በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲና ዴታንት ሥር እንዲሰዱ ለማድረግ አስችሏል ። በአሁኑ ጊዜ የሰላም ጥያቄ የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ እንደመሆኑ በዓለም ላይ ሰፍና የሚገኘውን እጅግ አሳሳቢ የሆነ የፖለቲካና የወታደራዊ ውጥረት ለማርገብ ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የግብረአበሮቹን የጦረኝነት ፖሊሲ በመቃወም የሚካሄደውን ትግል በይበልጥ ለማፋፋም ፣ ለሰላም የቆሙ ኃይሎች የጋራ ትብብራቸውን በይበልጥ ማስፋትና ማጠናከር ይኖርባቸዋል ።

* *Century and Peace*, 7-82, P. 39.

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER
. 6 1985
INSTITUTION

- ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የማስፋፋት ሂደት በኢትዮጵያ
- የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ
- የባህልና የቴክኒክ መሠረት ግንባታ በአብዮቱ ሂደት
- ኢኮኖሚያዊ የውጭ ግንኙነት ከምንከተለው የእድገት ፈለግ አንጻር
- ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሄያቸው በአብዮቱ ሂደት

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 3 ቁጥር
መጋቢት 1975

12

Digitized by Google

Digitized by Google

መስከረም

ቅጽ 3 ቁጥር 12
መጋቢት 1975

ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

● የዝግጅት ገጽ 3

● ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የማስፋፋት ሂደት በኢትዮጵያ 15
—አስፋ ሃብቴ
—ሞገስ ተ/ሚካኤል

● የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ 31
—ንጉሴብሆ ይፍሩ

● የባህልና የቴክኒክ መሠረት ግንባታ በአብዮቱ ሂደት 50
—ፋሲል ተፈራ
—ከበደ ትኩ
—ዘውዱ ስርባር

● ኢኮኖሚያዊ የውጭ ግንኙነት ከምንከተለው የእድገት ፈለግ አንጻር 74
—ዶ/ር ኣቀው ዓለሙ
—ክብሩ ገ/መድህን

● ማህበራዊ ችግሮችና መፍትሂያቸው በአብዮቱ ሂደት 89
—ንጉሤ ተፈራ
—አለማየሁ ፀጋዬ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ኢሠፓአኮ

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

በሽግግር ወቅት በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት

በተለያዩ የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃዎች (በተለይም ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊ
ዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት) በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል መኖር ስለሚገ
ባው ግንኙነትና ተዛምዶ አያሌ ጥናቶችና ምርምሮች ተካሂደዋል ። የእነዚህ ጥናት
ችና ምርምሮች መሠረታዊ ይዘትና የተሰነዘሩትም የመደምደሚያ ሃሳቦች ጥናቱን
ካከናወኑት ወገኖችና ግለሰቦች ርዕዮተዓለማዊ አመለካከትና እምነት አንጻር የተለ
ያዩ ሆነው ቀርበዋል ። ከነዚህ የተለያዩ አስተሳሰቦች መካከል የቡርዧ አፈቀላጤዎች
የሚያራምዷቸውን ሌሎች አድኀሪ አመለካከቶች ትተን ለወዝአደሩ ርዕዮተዓለም ቀመና
ል የሚሉት ወገኖች ከሚያስተጋቡት መካከል በጉልህ ሊጠቀስ የሚገባው - በአንድ
በኩል በሳይንሳዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ትክክለኛ አመለ
ካከት ሲሆን ፥ በሌላ ወገን ደግሞ የዚሁ ፍጹም ተጻራሪ የሆነው የቀኙና የግራ በራ
ዦች አድኀሪ አስተሳሰብ ነው ።

የቀኝ በራዦች በማኅበራዊ የዕድገት ሂደት ውስጥ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ሚና
በማጉላትና የፖለቲካን ተፅዕና በማንኳሰስ ሲያቀርቡ ፥ የግራ በራዦች ደግሞ የኢኮና
ሚን ሚና ዝቅ በማድረግና ወደ ጐን በመተው ለፖለቲካ መፈክሮችና ውሳኔዎች
ብቻ ከፍተኛውንና ወሳኙን ግምት ይሰጣሉ ። ዳሩ ግን የእነዚህ የሁለቱ ወገኖች
አቀራረብ የተለያየ ይምሰል እንጂ ፥ አስተሳሰባቸው አንድነት ባላቸው የጋራ ኢሳይ
ንሳዊነትና በአድኀሪ አቋማቸው ውጤት ይከሰታል ። የመጀመሪያው ወገኖች አስተሳ
ሰብ « ከሁሉም በላይ ኢኮኖሚ » (Economic Determinism) ለሚለው ፖሊሲ
ንድፈ ሃሳባዊ መሠረት ሲሆን ፥ የሁለተኛው ወገኖች አስተሳሰብ ደግሞ በዕድገት
ፖሊሲ ውስጥ ተጨባጭነት የሌለው ምኞት (Voluntarism) የበላይነት እንዲኖ
ረው እንደ መንደርደሪያ ያገለግላል ።

በእነዚህ አፈንጋጮች ያልተበከለው የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ ከላይ ለቀረበው
መሠረታዊ ጥያቄ ከታሪካዊ የዕድገት ደረጃና ካሉት ልምዶች ጋር የተገናዘቡ አጠቃ
ላይ ሕግጋት ላይ በመመርኮዝ ትክክለኛ መልስ ለማቀረብ ችሏል ። ሐቀኛውን የማሌ
ሳይንስ መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ በአንድ በኩል በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካ
ከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሀሳባዊ ግንዛቤን በመጠ
ኑም ቢሆን ለማብራራት ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ ንድፈ ሃሳብ ከአብዮታዊት
ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ መጠነኛ ግምገማ ለማካሄድ እንሞክ
ራለን ።

በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ቁሳዊና ርዕዮተዓለ
ማዊ ገጽታዎች አሉዋቸው ። የኅብረተሰብ ግንኙነት ገጽታዎች በኅብረተሰቡ የኢኮ
ኖሚ መሠረት ውስጥ ተጠቃለው የሚገኙ ሲሆን ፥ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ
የምርት ግንኙነቶች ናቸው ። ርዕዮተዓለማዊ ገጽታዎች ደግሞ ፖለቲካን ፥ ሕግን ፥

Digitized by Google

ሥነምግባርን ፡ ስነውበትን ፡ ሃይማኖትንና የፍልስፍና አመለካከቶችን የሚያጠቃልሉ፣
ካለው የኢኮኖሚ መሠረት የሚመነጩ የላዕላይ መዋቅር አካሉች ናቸው ።

በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ያሉት አያሌ የግንዛቤ ቀርጾች እርስ በርሳቸውና በኢኮ
ኖሚው መሠረት ፡ ማለትም በታህታይ መዋቅር ውስጥ ካሉት አካሉች ጋር በሚፈ
ጥሩት መስተጋቢራዊ ግንኙነት የአንድን ኅብረተሰብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥር
ዓት ይፈጥራሉ ። ባንድ ወቅት በተወሰነ አገር ውስጥ የሚኖረው ሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ
ሥርዓት በተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙት የታህታይና የላዕላይ መዋቅሮች
መስተጋብራዊ ቀንጅት መሆኑን የሚሌ ሳይንስ ያስገነዝባል ። በተለያዩ አገሮችውስጥ
ያሉትን የኢኮኖሚና የርዕዮተዓለም ቀንጅት ዋና መንጸባረቂያ የሆኑትን የፖለቲካ
ሥርዓቶች ይዘትና ግንኙነቶቻቸውን በትክክል ለመገንዘብ በቅድሚያ የየአገሮቹን የኢ
ኮኖሚ መሠረትና የላዕላይ መዋቅር ተጨባጭ ሁኔታዎችን ማጥናት በጣም አስፈላጊ
የሆነውም ከዚሁ የተነሳ ነው ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ መሠረትና የላዕላይ መዋቅር
ፈርጆች በአጠቃላይ በየጊዜው እያደጉና እየተሻሻሉ የሚሄዱ መሆናቸውና በመካከላ
ቸው ያለው መስተጋቢራዊ ግንኙነትም በዚያው መጠን እያደገ የሚሄድ መሆኑ የማ
ርክሳዊ ሌኒናዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ንድፈሃሳብ የማዕዘን ድንጋይ ነው ። የኢኮና
ሚንና የፖለቲካን መስተጋብራዊ ግንኙነት ትክክለኛ ገጽታና አቀጣጫም በውል ለመ
ረዳት የታህታይና የላዕላይ መዋቅር አካሉችን የዕድገት ጠባይና ዝንባሌ በጥሞና
ማጤንን ይጠይቃል ።

በኢኮኖሚ መሠረትና በላዕላይ መዋቅር ፈርጆች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች
የሚገዙትን የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋት ስናጤን እያንዳንዱ ማኅበራዊ ሥርዓት የባ
ሪያው ፣ የፊውዳሉ ፣ የካፒታሊስቱና የሶሻሊስቱ ለኢኮኖሚ መሠረቱ ተስማሚ የሆነ
ላዕላይ መዋቅር እንዳለው እንገነዘባለን ። የላዕላይ መዋቅሩ ጠባይና የዕድገት አቀጣ
ጫም በአጠቃላይ የሚወሰነው በኢኮኖሚ መሠረቱ እንደሆነ ሕግጋቱ ያስረዳሉ ። ስለ
ሆነም ላዕላይ መዋቅር የተጨባጩ የኢኮኖሚ ዕውነታ ነፀብራቅ ሲሆን ፡ ይህም በኅ
ብረተሰቡ ውስጥ የኢኮኖሚ የበላይነት ያላቸው መደቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ
የፖለቲካውን ስልጣን የያዙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው ።

የላዕላይ መዋቅር ፈርጆች በመሠረቱ የታህታይ መዋቅር ነፀብራቅ ቢሆኑም ፡
እንደየሁኔታው የሚለያይ አንጻራዊ ነጻነት ያላቸውና በበኩላቸውም በታህታይ ዋመ
ቀሩ ላይ ተጽዕና በማድረግ ገቢራዊ ሚና ይጫወታሉ ። የተለያዩ የላዕላይ መዋቅር
አካሉች ከኢኮኖሚው መሠረት ጋር ያላቸው ዝምድናም በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኝ
አይደለም ። የፖለቲካ ግንኙነቶች ፡ መንግሥትና ሕግ የመሳሰሉት ካለው ኢኮናሚ
ያዊ ሁኔታ በቀጥታ ሲመነጩ ፡ እንደ ኃሃይማኖት ፡ ፍልስፍና ፡ ኪነጥበብና ወዘተ…
ያሉት ግን ፡ እንደ ፖለቲካና ሕግ ባሉት አማካኝነት ከኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር በተ
ዘዋዋሪ መንገድ የተቀራኙ ናቸው ። እንደ ሃይማኖት ፡ ፍልስፍና ፡ ኪነጥበብ ፡
ወዘተ . . . የመሳሰሉት የላዕላይ መዋቅር ፈርጆች የዕድገታቸውን ሁኔታና በኅብረተሰ
ብ ውስጥ ያላቸውን ሚና በሚመለከተ ሰፊ አንጻራዊ ነጻነት ሊኖራቸው የቻለውም
በዚሁ ምክንያት ነው ። ሆኖም ፡ ይህ አንጻራዊ ነጻነት ከመደብ ይዘት ውጭ ሊሆን
እንደማይችል የሚሌ ሳይንስ የሚያስገነዝበን ሐቅ ነው ። እነዚህ ሰፋ ያሉ አንጻራዊ
ነጻነት ያላቸው የላዕላይ መዋቅር አካሉችም ቢሆኑ ከመደብ ትግል ውጭ በመሆን በገ

Digitized by Google

ለልተኝነት ሊኖሩ ስለማይችሉ ፈጠነም ዘገየ ቅርጻቸውና ይዘታቸውን በማስተካከል የአዲሱ ሥርዓት አካል ይሆናሉ ።*

በግል ንብረት ይዞታ ላይ በተመሠረተ ኅብረተሰብ ውስጥ በማኅበራዊ አብዮት ብቻ ሊፈታ የሚችል ተጻራሪ የሆነ ቅራኔ መኖሩ የታወቀ ነው ። ይህም መሠረቱ በታኅታይ መዋቅር ውስጥ የሆነ ተጻራሪ ቅራኔ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ይንፀባረቃል ። ይህም በምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ ፥ ባሕርይና በምርት ግንኙነቶች መካከል በሚታይ ከፍተኛ አለመጣጣም አማካይነትም ይከሰታል ። ይህ ቅራኔ በተጨባጭ የሚገለጠው እንደ ዕድገት ደረጃው በልዩ ልዩ ገጽታዎች ሲሆን ለምሳሌ በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ውስጥ በካፒታሊስቱ መደብና በወዝአደሩ መደብ መካከል ፥ እንዲሁም በእነዚህ መደቦች፥ ፖለቲካ ፥ ሥነምግባር ፥ ፍልስፍና ፥ ኪነጥበብና ወዘተ . . . መካከል ውስብስብ ርዕዮተዓለማዊ ትግሎች ይካሄዳሉ ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የቡርዧው የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅር ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነቶችን ሲያንጸባርቅ ፥ በአንጻሩ ደግሞ የወዝአደሩ ርዕዮተዓለምና የወዝአደሩ ድርጅቶች ዓላማ ካፒታሊዝምን በመደምሰስ ሰው በሰው የማይበዘበዝበት የእኩልነትና የነፃነት ሥርዓት መገንባት ይሆናል ። የሶሻሊስቱ ኅብረተሰብ ተጻራሪ ከሆነ ቅራኔ ነፃ በመሆኑ የምርት ግንኙነቱ በተከታታይ የምርት ኃይሎችን ለማሳደግና ለማዳበር ያገለግላል ።

በግል ንብረት ላይ በተመሠረቱ ኅብረተሰቦች ውስጥ በተለያዩ በዝባዥ መደቦች መካከል የሚደረጉት ትግሎች በመጀመሪያ በርዕዮተዓለምና በፖለቲካ መስኮች ይካሄዳሉ ። በመጨረሻም የአሮጌውን ሥርዓት የንብረት ይዞታና ግንኙነቶች በመለወጥ ለተተኪው የብዝበዛ ሥርዓት የኢኮኖሚ ዕድገትና መስፋፋት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ። ስለሆነም ፥ በፖለቲካውና በመንግሥት አካሎች ውስጥ የሚደረጉት ለውጦች በኢኮኖሚው መስክ ከተደረጉት ለውጦች ይዘትና ደረጃ አልፈው የማይሄዱ ከመሆናቸውም በላይ በአጠቃላይ በላዕላይና በታህታይ መዋቅሮች ላይ የሚደረገውም ለውጥ ውሱንና በግል ይዞታ ክልል ውስጥ የሚከናወን ይሆናል።

የግል ይዞታን ወደ ወል ይዞታ የሚለውጠው አብዮታዊ ሂደት ስርነቀልና መሠረታዊ እንደመሆኑ ወሳኞቹ የላዕላይ መዋቅር ክፍሎችና ቁልፍ የሆኑት የኢኮኖሚው አካሎች የአዲሱ ሥርዓት እምብርት በመሆን ለሌሎች ተከታታይ ለውጦች የአንቀሳቃሽ ኃይል ሚና ይጫወታሉ ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ በኢኮኖሚ መሠረትና በፖለቲካዊ የላዕላይ መዋቅር መካከል ያለው ዝምድናና የተደጋጋፊነት ጠባይ በግል ይዞታ ክልል ውስጥ ከሚከናወነው የተለየ የሚሆነውም ለዚህ ነው ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚከናወኑት የግንባታ ተግባራት በግብታዊነት ላይ የተመሠረቱ ሳይሆኑ ፥ በተጨባጭ የማኅበራዊ ዕድገት ሕግጋትና በተቀናጀ የአመራር ዕቅድና ሥልት ፥ እንዲሁም በሠርቶአደሩ ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ አማካይነት የሚካሄዱ ናቸው ። የዚህ ክስተት መንስኤ በአዲሱ ኅብረተሰብ የዕድገት ሂደት ውስጥ የፖለቲካ አመራር ሚና የጉላ መሆኑ ነው ። ለሶሻሊስት ኢኮኖሚና ባህል የተፋጠነና የተመጣጠነ ዕድገት አስፈላጊውን ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ሁኔታዎች በየደረጃው ማዘጋጀት የመንግሥት ተግባር ነው ። የሶ

* Karl Marx & Frederic Engels, Selected Correspondence, 2nd revised and Supplemented ed., Moscow, p. 467.

Digitized by Google

ሻሊስት መንግሥት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ዕቅዶችን በማዘጋጀት ፥ ለተግባራዊነታቸው የአስተዳደርና የአመራር ሥልቶችን በመቀየስ ፥ እንዲሁም ለተሳካ የሥራ ውጤት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳና የትምህርት ተግባሮችን በማካሄድ በየመስኩ የሚያደርገው ጥረት በኢኮኖሚ አመራር ውስጥ ያለው ተሳትፎና ኃላፊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐላና እየሰፋ እንዲሄድ ያደርጋል ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ውስጥ የማንኛውም እንቅስቃሴ ግንባር ቀደም መሪ የኮሚኒስት ፓርቲው ነው ። ፓርቲው ከሚቀይሳቸው የፖለቲካ ተግባሮች መካከል ትልቁና ከፍተኛው ኢኮኖሚውን በሚመለከት የሚነድፈው ስትራቴጂና ለተግባራዊነቱም የሚያወጣው መርሃ ግብር መሆኑ የሚታወቅ ነው ። ፓርቲው በኢኮኖሚ ፖሊሲው አማካይነት ከሚከተለው ዓላማ አንጻር የኅብረተሰቡን አጠቃላይ የዕድገት አቅጣጫ ይቀይሳል ፤ ኅብረተሰቡንም ያደራጃል ፤ ይመራል ፤ በሰፊው ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የግንባታውን ተግባር በምዕራፍና በተከታታይ ያከናውናል ።

ፓርቲው የግንባታውን ስትራቴጂ በሚቀይስበትና በየደረጃውና በተከታታይ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ በሚያመቻችበት ወቀት በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል ያለውን ግንኙነትና የግንኙነቱንም ጠባይ ጠንቅቆ መገንዘብ በተለይ ወደ ሶሻሊዝም ለሚደረግ ሽግግር መሳካት እጅግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠራጥርም ። ፖሊቲካ የአንድ ኅብረተሰብ የላዕላይ መዋቀር ዋና ክፍልና ፥ የኢኮኖሚው መሠረት ነፀብራቅ እንደመሆኑ የአንዱ ወይንም የሌላው መደብ ጥቅም በተሰባሰበ መንገድ በፖለቲካ አማካይነት ይገለጻል ። የፖለቲካንና የኢኮኖሚን መስተጋብራዊ ተዛምዶ ለመረዳት ታላቁ መምህር ሌኒን ፖለቲካ የኢኮኖሚ ስብስብ ነፀብራቅ ነው * ያለውን ማጤን ያሻል። ፖለቲካና ኢኮኖሚ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ በጣም የተሳሠሩና ተነጣጥለው የማይታዩ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን ደህና አድርጎ መገንዘብ በሽግግሩና በግንባታው ሂደት ውስጥ በሚናቸው ለማሰለፍና በትክክል ለመጠቀም ያስችላል ።

ሥር ነቀል አብዮት በማካሄድ ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ በኢኮኖሚው መስክ የሚከናወኑት የሽግግር ወቀት ተግባሮች ከፍተኛ ከመሆናቸውም በላይ በይበልጥ የፖለቲካ ጠባይ ያላቸው ናቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ ለወቅቱ ተስማሚ የሆኑ የፖለቲካ ዓላማዎችንና ሥልቶችን ለመቀየስ ያለውን ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንደ መሠረታዊ የመነሻ ነጥብ አድርጎ መውሰድ የግድ አስፈላጊ ይሆናል ። ከዚህም የተነሳ በእነዚህ በሁለቱ ግንዛቤዎች መካከል ያለው የግንኙነት ጠባይ ከምንጊዜውም የበለጠ ውስብስብ ይዘቶች ይኖሩታል ።

በተለይ በአንድ አገር ውስጥ አብዮት ፈንድቶ ለአገር ዕድገት መሠረት የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሚነደፍበት ወቀት ፖለቲካ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል።ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ወቀት በመደቦችና በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ቅራኔዎች እንደመኖራቸው መንግሥት እነዚህን ልዩነቶችና ቅራኔዎች ከተጨባጭ የዕድገት ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ወደ ተቀየሰው ዓላማ ለመድረስ ትክክለኛና የተሟላ አመራርና አስተዳደር የማስፈን ኃላፊነት አለበት።መንግሥት የሚያከናውናቸው እነዚህ

---

* V.I. Lenin, *Collected Works* /Moscow: 1965/ Vol. 32, p. 83.

Digitized by Google

የፖለቲካ ተግባሮች የገንባታውን ፈር የሚተልሙ የመሆናቸውን ያህል በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርጋሉ ።*

ፖለቲካው በኢኮኖሚው ላይ የበላይነት አለው የሚለውን ዕውነታ በትክክል ለመገንዘብ በቀድሚያ በሁለቱ ገንዛቢዎች መካከል ያሉትን ተገባራዊ መስኮች ለይተ ማወቅ ያስፈልጋል ። የኢኮኖሚ ዕድገት ዓላማዎችንና ሥልተችን አስቀድሞ የመቀየሱ ተገባር በመሠረቱ የመንገሥተ ኃላፊነት ማለትም የፖለቲካ ተገባር ነው ። ነገር ግን ይህም ሲባል አንደኛ ኢኮኖሚ ነክ ውሳኔዎች ያለ በቂ ጥናት የሚወሰዱ፤ ሁለተኛ ተጨባጭና ቴክኒካዊ የሆኑ የኢኮኖሚው ዝርዝር ሥራዎች በፖለቲካ ውሳኔ ብቻ የሚፈቱ አይደሉም ። ባንድ በኩል ውሳኔዎቹ ከተጨባጭ ሁኔታዎች የፈለቁ ጠበቂና ዝርዝር ጥናት ላይ የተመሠረቱ፣በሌላ በኩል ተገባራዊነታቸውም በሚመለከታቸው መሥሪያ ቤተችና ድርጅተች ለማካይነተ መከናወን ያለበተ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው ።

በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል መኖር ስለሚገባው ገንኙነተ በሚወሳበተ ጊዜ በተወሰነ ደረጃ ፖለቲካ በኢኮኖሚው ላይ የበላይነተ አለው የሚባለው፤ በትክክለኛ የዕድገተ ጉዳና ላይ በሚጓዙ አገሮች ውስጥ ሳይንሳዊ አሠራርን የሚከተል የፖለቲካ ድርጅተ ወይም ፓርቲ የኅብረተሰቡ አጠቃላይ ዕድገተ መሪ መሆኑንና፣መንግሥተ ደግሞ የዚህን አመራር ተገባራዊነተ የሚያረጋገጥ መሣሪያ በመሆን የሚያገለግል መሆኑን በማጤን ነው ። ከዚሁ ጋር ደግሞ ጉልህ መሆን ያለበተ ሌላው ቁም ነገር ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅተ ምትክ የማይገኝለተ የኅብረተሰቡ መሪ ለካልበመሆኑ ብቻ፣ ያሉተን ተጨባጭ ሁኔታዎች በመመዝገብና በእነርሱም ላይ ውሳኔዎችን በየጊዜው በማሳለፍ ብቻ ገደታውን እንደተወጣ በመቁጠር ረክቶ ይቀመጣል ማለተ አይደለም ። ተጨባጩን ሁኔታ በትክክለኛው መንገድ ለመለወጥ ፓርቲው ንቁና ገንባር ቀደም ተሳትፎ ማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ይጠበቅበታል ።

በሌላ አንጻር ደግሞ የዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ድርጅተ ገንባር ቀደም የፖለቲካ አመራር ተገባራዊነተ የሚረጋገጠው አድኃሪያን እንደሚሉተ ከጭፍን፣ፍላጉተና ከማንአለብኝነተ ስሜተ የሚመነጩ ትእዛዞችን በማስተላለፍ ሳይሆን ተጨባጩን የዕድገተ ሕገጋተ ከተለዋዋጩ ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ትክክለኛ መመሪያዎችን በማውጣትና እነዚህም መመሪያዎች ተገባራዊ መሆናቸውን በማረጋገጥ ነው ።

የዚህ ዓይነቱ ሳይንሳዊ አቀራረብና ትክክለኛ አሠራር አንድ አብዮታዊ የፖለቲካ ድርጅተ ባለው የፖለቲካ ሥልጣን አማካኝነተ ኢኮኖሚያዊ ገንኙነቶችንና ሁኔታዎችን ለመለወጥና ለማሻሻል ብሎም ደግሞ በእነዚህ ለውጦች ሳቢያ መልሶ የፖለቲካ ሥርዓቱን እንዲያጠናክር ከሚያስችሉተ ሁኔታዎች መካከል ዋንኛውና ወሳኙ ነው ።

በፖለቲካና በኢኮኖሚ መካከል መኖር ስለሚገባው ገንኙነተ በሚወሣበተ ጊዜ ያንዱን በሌላው ላይ ቀዳሚ መሆን ብቻ በማንሳተ ማለፍ ትክክለኛ አመለካከተ አይሆንም ። በሁለቱ ክስተቶች መካከል ስላለው ዲያሌክቲካዊ ገንኙነትና የዝምድና ጠባይ ያለመረዳተ አልፎ አልፎ እንደሚታየው ፖለቲካ ከኢኮኖሚ

* Hannes Horning, "Human Essence of the Policy of Communist Parties of Fraternal Countries", gen. ed., *Interaction of the Economic and Political System of the Socialist Countries of the Present Stage,* (Prague: Peace and Socialism, 1977), p. 17.

ተግባር ነጻ መሆን ስለበት ወደሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ ሊያደርስ ስለሚችል፣ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል ።

በማንኛውም ተራማጅ አገር መንግሥት በኢኮኖሚው መስክ በሚያደርገው ተሳትር ተጨባጩን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ግንኙነት ወደጐን በመተው የፈለገውንና የተመኘውን ነገር ብቻ ሊያከናውን አይችልም ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ፖለቲካ ምንጊዜም ቢሆን የተጨባጩ የኢኮኖሚ ሁኔታ ነፀብራቅ እስከሆነ ድረስ በሚገባ ተገባራዊ ሊሆን የሚበቃውና ግቡን በትክክል ሊመታ የሚችለው ከወቀታዊው የኢኮኖሚ ፍላጐት ወይም ከተጨባጩ የማኅበራዊ ዕድገት ሕገጋት ጋር ሲጣጣም ብቻ ለመሆኑ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አይናርም ። እንዲህም ስለተባለ ደግሞ ፖለቲካና የመንግሥት ተገባራት እንዲሁ በደፈናው የኢኮኖሚ ሁኔታዎችንና እንቅስቃሴዎችን በመከተል ብቻ ተገባራዊ መሆን አለባቸው የሚል ቀዠተ ሊኖር አይችልም ። ማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡ የመደቦች አሰላለፍ፣ የርዕዮተዓለማዊ፣ የፖለቲካዊና የባህላዊ ቅርሶች እንዲሁም የዓለምአቀፍ ሁኔታዎች ድምር ውጤት ነው ።

ከካፒታሊስት አገሮች ጋር ሲወዳደር በታዳጊ አገሮች ውስጥ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በማኅበራዊ ዕድገት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕና ጉላ ብሉ ይታያል ። ይህም የሚሆነው በተለይ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ያሉት መንግሥታት የኢኮኖሚ ሁኔታን ለመለወጥና ዕድገቱንም ለመምራት የሚያስችል ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ ነው ።

ሆኖም፣ ምንም እንኳ በአጠቃላይ በታዳጊ አገሮች ውስጥ መንግሥት ለማኅበራዊ ዕድገት መፋጠን ታላቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ ይችላል ቢባልም፣ የዚህን አስተዋጽኦ ትክክለኛ ሚናና ጠባይ እያንዳንዱ አገር ከሚከተለው የዕድገት ፈለግ አንጻር አገናዝቦ ማየቱ ተገቢ ነው ። በዚህም መሠረት የካፒታሊስት የዕድገት ጉዳናን በመረጡ ታዳጊ አገሮች ውስጥ ያለውን ሁኔታ ብንወስድ፣ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ያለው መንግሥት በሚከተለው የቀረጥ፣ የፋይናንስ፣ የመዋዕለ ንዋይ፣ ወዘተ ... ፖሊሲዎች አማካኝነት ለግል ካፒታል እንቅስቃሴና ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ፣ ያበረታታል ። በተለይም በእነዚህ አገሮች ውስጥ ለካፒታሊዝም ዕድገት አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞችንና አውታርችን በማስፋፋት ረገድ የመንግሥት ሚና ጉልቶ ይታያል ።

በሌላ ወገን ደግሞ በተራማጅ (ሶሻሊስታዊ የዕድገት ጉዳናን በመረጡ) ታዳጊ አገሮች ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከተ የመንግሥት ተግባርና ሚና እነዚህ ታዳጊ አገሮች ከመረጡት የዕድገት ጉዳና አንጻር አያሌ ውስብስብ ችግሮችን መፍታት በመሆኑ ቀላል አይሆንም ። ከነዚህም ችግሮች መካከል ሊጠቀሱ የሚገባቸው በአንድ በኩል ድህነት፣ ማይምነት፣ ረሃብና በሽታ፣ በአጠቃላይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለዕድገትና ለሰላማዊ ግንባታ ጠር የሆኑት የውስጥና የውጭ የመደብ ጠላቶች ሴራና የተቀነባበረ አሻጥር ናቸው ። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ የሚገኘው መንግሥት ማከናወን ካለበት ተግባሮች መካከል ተልቁና ወሳኙ ለተመረጠው የዕድገት ፈር በአስተማማኝ ወደ ዘላቂ ግብ መድረስ የሚያበቃ ትክክለኛ የፖለቲካ መመሪያ የመቀየሱና ይህንንም በተገባር የመተርጐሙ ከባድ ኃላፊነት ነው። አንድ ተራማጅ መንግሥት በዚህ በኩል የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት

Digitized by Google

መቻሉ በሽግግሩ ወቅት በተለይ በፖለቲካና በኢኮኖሚ መካከል የሚኖረው ግንኙነት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት በተረጋገጠበት ሁኔታ ውስጥ ካሉት የግንኙነት ሁኔታዎችና ጠባዮች ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንዲሆን ያደርጋል ።

ከሶቭዬት ኅብረትና ከሌሎች የሶሻሊስት አገሮች ልምድ ለመረዳት እንደሚቻለው የሶሻሊዝምን የኢኮኖሚ መሠረት መገንባት የተቻለው በቀድሚያ የፖለቲካ ሥልጣን ከተያዘና የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ከተመሠረተ በኋላ ነበር ። ይህም ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ አብዮታዊ መንግሥት ፥ እርሱም የሚከተላቸው ፖሊሲዎችና የፖለቲካ መመሪያዎች ወሳኝ ሚና እንዳላቸው የሚጠቁም ነው ። በሌላ አነጋገር አብዮት ከተካሄደ በኋላ አዲሱን የሶሻሊስት ኅብረተሰብ በመገንባቱ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ የወሳኝነት ሚና ይኖረዋል ማለት ነው ።

ይህን በማስመልከት ታላቁ ሌኒን ሲናገር ፤ « ፖለቲካ ከኢኮኖሚ ቀድሞ መገኘት አለበት ። ይህ አይሆንም ብሎ መከራከር የማርክሲዝምን ሁሁ መርሳት ነው »* ብሎ ነበር ። እንዲሁም የሶቭየት ኮሚኒስቶች የፖለቲካ መመሪያቸውን በሚቀይሱበት ጊዜ ከምን መነሣት እንዳለባቸው ሌኒን ሲያስረዳና በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ሲጠቁም ፥ እኛ ሁልጊዜ አቋማችንን የወሰድነው በመጀመሪያና በቀድሚያ ከትክክለኛ የኢኮኖሚ ትንተና በመነሣት ነው » ** ማለቱ የሚታወስ ነው ።

ከነዚህ የሌኒን አባባሎች መረዳት የምንችለው ፍሬ ነገር በተጨባጩና በትክክለኛው የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ የተቀየሰ የፖለቲካ መመሪያ ለኢኮኖሚው የተመጣጠነ ዕድገት ወሳኝና ቀዳሚ ሆኖ መገኘት ያለበት መሆኑን ነው ። ከዚህም በመነሣት ለማኅበራዊ ዕድገት ፥ ለሰዎች የጋራ ብልጽግናና ለሶሻሊዝም የቆመ የማንኛውም ተራማጅ አገር ፓርቲ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጉት በየደረጃው በማሟላት ወደ ታለመው ግብ ለመድረስ የሚያስችሉ የፖለቲካ መመሪያዎችን መቀየስና የፖለቲካ አመራር በሚሰጠው መንግሥት አማካይነት መመሪያዎቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ባለማሰለስ መቆጣጠርና አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት ።

በኢትዮጵያም የሽግግር ወቅት ሂደት በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል መኖር የሚገባው ግንኙነትና የግንኙነቱም መሠረታዊ ይዘት ከላይ ከተሰነዘረው ንድፈ ሃሳብ ውጭ ሊሆን እንደማይችል እሙን ነው ። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሰባተኛው የአብዮት በዓል በተከበረበት ዕለት ባደረጉት ንግግር ፥ «ርዕዮተዓለምና ፖለቲካ የማይመራው የኢኮኖሚ ግንባታ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም የምንጓዝበትን ጉዳና ሳናስተውል ለገባችን ልንበቃ አንችልምና በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ ተግባራችንን ከምንመራበት መስመር ጋር ማጣጣም እንዳለብን መዘንጋት የለበትም ። ምክንያቱም ሶሻሊዝም የተገባርና የንድፈ ሃሳብ ቅንጅት ውጤት ነው »*** በማለት የኢኮኖሚ ግንባታ ተግባሮች ከተቀየሰው የፖለቲካ መሥመር ጋር መዛመድና መጣጣም ያለባቸው መሆኑን በሚገባ አስገንዝበዋል ። ለዘላቂው የፖለቲካ ዓላማችን የማይገዛና በርዕዮተዓለማዊ ግንዛቤ ላይ ተመሥርቶ የማይመራ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለሶሻሊዝም የሚደረገውን ትግል የሚያዳክምና ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ለኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ብዝበዛ የሚዳርግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈል

* V.I. Lenin, *Collected Works*, (Moscow: n.d.), Vol. 32, p. 83.
** *Ibid.*, Vol. 29, p. 192.
*** ሠርቶ አደር ፥ ልዩ እትም ፥ መስከረም 2 1974 ፥ ገጽ 4

Digitized by Google

ጋል ። የኢኮኖሚው ዕድገት ዝርዝር ተግባሮች በሚታቀዱበትና በሚነደፉበት ጊዜ ከፖለቲካ ዓላማ ነጥሎ የማየት አዝማሚያ ለቡርዧው አስተሳሰብና ዓላማ ተገዥ ወደ መሆን ሊያመራ ስለሚችል በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

በሽግግር ሂደት ውስጥ ለኢኮኖሚው ብቻ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ኢኮኖሚው ሶሻሊስታዊ የዕድገት ፈርን ተከትሉ እየተጠናከረ የሚሄድ በሚመስልበት ሁኔታም እንኳ፣የፖለቲካው አመራር ወደኋላ የመጉተት አዝማሚያ ካሣየ፣አሳሳቢ የሆኑ የአብዮት ቀልበሳ፣አዝማሚያዎችና ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።የዚህ ዓይነቱ አዝማሚያ በተለይም አስ ፈጻሚ አካል በሆኑት በመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ በጉልህ ሊታይ ይችላል ። ምክን ያቱም (በብዙዎቹ የታዳጊ አገሮች ፣ የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉትንም ጨምር) የመንግሥት አካሉች ውስጥ ከአድኃሪ የቡርዧ ሥርዓት አስተሳሰቦችና ከኋላቀር ልምዶች ጋር የተቀራኙ ባለሥልጣናትና ኃላፊዎች በብዛት በመኖራቸውና አሠራራቸውም ከሠርተአደሩ ሕዝብ አብዮታዊ ስሜትና ፍላጉት ጋር በቀላሉና በአ ጭር ጊዜ ውስጥ ሊጣጣም ስለማይችል ነው ። ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በታዳ ጊ አገሮች ውስጥ የሚካሂዱትን አብዮቶችና ተራማጅ እንቅስቃሴዎች ለማጨናገፍ በመንግሥት አካሉች ውስጥ የተሰገሰጉትን ፣ ሶሻሊዝም የሚባል ነገር የማይዋጥላቸውን ቢሮክራቶች ለመጠቀም ዘወትር ወደ ኋላ የማይለውም እነዚህ ኃይሉች ለሠርተ አደሩ ሕዝብ ዓላማና ለሶሻሊዝም በቀንነት ያለመቆም አዝማሚያ እንዳላቸው ጠንቀቆ ስለ ሚያውቀ ነው ።

እንደሚታወቀው የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመረጡ ኋላቀር አገሮች ውስጥ በአንድ በኩል የአነስተኛ የሸቀጥ ምርት በስፋት የሚገኝ በመሆኑ ከዚህ የአመራረት ዘይቤ የሚመነጭ ሥር የሰደደ የንዑስ ከበርቴ የግለኝነት አመለካከት አለ ። በሌላ በኩል ይህን ፈለግ የሚከተሉ አገሮች የኢኮኖሚ ኋላቀርነታቸው ካስከተለው ጥገኝነት የተነሳ ኢኮኖሚያቸው ከዓለም የካፒታሊስት የሥራ ክፍፍልና ከኢምፔሪያሊስቱ ገበያ ጋር ያለው መተሳሰር ያልተቋረጠ ከመሆኑም በላይ ፣ ለማቋረጥም የሚያስፈልገው ተጨባጭና ኅሊናዊ ሁኔታ በቀላሉ የሚሟላ አይደለም ። እንዲሁም እነዚህ አገሮች በሚያልፉበት የሽግግር ወቅት የካፒታሊስት ይዞታም የሚገኝ በመሆኑ ፣ የነዚህ ጭብ ጦች ድምር በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ ፣ ሕይወታቸውን ከሶሻሊዝም ጋር ሳይሆን ከካፒታሊዝም ጋር ያስተሳሰሩ ቢሮክራቶች ሁኔታው እንዲሁ ከተለቀቀ ወደ ቢሮክራቲክ ቡርዧነት እንዲያድጉ ሊያደርጋቸው ይችላል ። የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች ውስጥ ያሉ መሪ ፓርቲዎች ያልተጠናከሩ በሆኑበት ሁኔታና በዚህም ምክንያት የፓርቲዎቹ የፖለቲካ ዓላማ አስፈጻሚ የሆነውን መንግሥ ታዊ መዋቅር በሚገባ ለመቆጣጠርና ለመምራት በማይችሉበት ሁኔታ ፣ ፓርቲዎች በመ ንግሥታዊ መዋቅር የመዋጥ ወይም በፀረ አብዮት ኃይሉች የመበከል አደጋ ሊያ ጋጥ ማቸው እንደሚችል አይጠረጠርም ። ይህ ሁኔታ በተጨባጭ ከተከሰተባቸው አገሮች መካከል ግብፅን ከናስር በኋላና ጋናን ከንክሩማ በኋላ በምሳሌነት ለመጥቀስ ይቻላል።

የሶሻሊስቱን የዕድገት ጉዳና መርጠው የጀመሩትን አብዮት ከግቡ ለማድረስ ካል ቻሉት አገሮች ልምድ ኢምፔሪያሊዝም የቀሰመው ትምህርት ፣ ለአብዮት ቀልበሳ ዋንኛ የውስጥ ኃይል በመሆን የሚያገለግለው በነዚህ አገሮች ውስጥ በሚገባ ባልጸዳ ውና ወይም መረን በተለቀቀው የመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በየደረጃው የተሰገሰጉ ፀረሶሻሊስት ኃይሉች በነዚሁ አገሮች ውስጥ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፓርቲዎች

Digitized by Google

ውስጥ ካሉ መሰሎቻቸው ጋር የሚፈጥሩት ኅብረት (ግንባር) መሆኑን ነው ። ዓለም ሰቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እነዚህን ተራማጅ አገሮች በሚመለከት የሚነዛው የፀረ ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ መሠረታዊ ዓላማም ለነዚህ የውስጥ ፀረአብዮት ኃይሎች መጠናከር አስፈላጊ የሆነውን ሀሊናዊ ሁኔታ መሟላት ነው ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ በሚገኝ ተራማጅ አገር ውስጥ ግንባር ቀደሙ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ ነገሩን በለዘብተኛነት በመመልከት በቀራኔዎች እስኪዋጥ ዝም ብሎ መጠበቅ የለበትም ። ለችግሮቹ መንስኤ የሆኑትን ምክንያቶችና ሊፈቱ የሚችሉበትን ትክክለኛ ዘዴ በመቀየስ የእርምት እርምጃዎች በአፋጣኝ መውሰድ ይኖርበታል ። ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ወቅት የሠርቶአደር ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት ሊረጋገጥ የሚችለውና መሠረታዊ የኢኮኖሚ ችግርችም ዘላቂ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በትክክለኛ የፖለቲካ አመራር ጥላ ሥር ሲውል ብቻ መሆኑ ለአንዲት ደቂቃ እንኳ ሊዘነጋ አይገባም ።

በድኅረ አብዮት ኢትዮጵያ በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል ያለውን ግንኙነትና የግንኙነቱንም ጠባይና አቀጣጫ ስንገመግም ፣ አብዮታዊ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ፖለቲካው ኢኮኖሚውን እየመራው እንደመጣ ለመገንዘብ እንችላለን። በተለይም በ1967 መጀመሪያ ላይ ንጉሡን ከሥልጣን በማስወገድ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥልጣኑን ከጨበጠ በኋላ አብዮቱ ላነሳቸው መሠረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ሥር ነቀል የሆነ መልስ ለመስጠት የተቻለው በቀድሚያ አመች የሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ በመፈጠሩ መሆኑ አይዘነጋም ። ይህም ሌኒን የማናቸውም አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ማለትም የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ነው ያለውን አባባል ትክክለኛነት ያስገነዝበናል ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የአንድን መንግሥት ፖለቲካ ትክክለኛነትና ተቀባይነት ከሚወስኑት ሁኔታዎች መካከል ዋናው የፖለቲካ መስመሩ ካለው ነባራዊ የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶች በመነሣት የአብዛኛውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ፍላጐት ማንፀባረቅ ሲችልና ለዚህም ተግባራዊ ምላሽ ሲያቀርብ ብቻ መሆኑን ነው። ከዚህ መሠረታዊ የማሌ ሐቅ ውጪ የሆነ አመለካከትና ተግባር ውድቀትን ከመጋበዝ በስተቀር ድልን አያጐናጽፍም ። በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ በተለያዩ ስሞችና ሽፋኖች የተከሰቱት «አብዮታውያን» የሰፈው ሕዝብ «ተቀርቃሪዎች» ፣ ወዘተ ... ነን ባዮች ፣ በየወቅቱ ጊዜው የፈጠረውን ተራማጅ ቃላት ሁሉ ቢወረውሩና ከሁሉም በላይ ለመስዋዕትነት የቆሙ መስለው ቢታዩም ዞር ዞር ከሰፊው ሕዝብ ጐን ስለመቆማቸው ይፋ ሲወጣቱና ከፖለቲካው መድረክ የዛፍረት ሸማ ተከናንበው መውረዳቸው አልቀረም ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መርሆዎችን ከተቀበለና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ይፋ ካወጣ በኋላ ፣ በተለይም ፀረ አብዮት ኃይሎች ሁሉ በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ ትኩረቱ ወደ ግንባታው መስክ አተኮረ ። በዚህ በኩል ያለበትን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ደግሞ ብቃትና ጥንካሬ ያለው የፖለቲካ አመራር አስፈላጊነት በዚያው መጠን እንገብጋቢ እየሆነ መጣ። ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሥር መስደድና ለአብዮቱ ግብ መምታት በማሌ ንድፈ ሃሳብ የሚመራ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ መመሥረት ወቅታዊ ጥያቄ ሆና በየጊዜውና በየመድረኩ እየተደጋገመ የሚነሳውም ይህንኑ ሐቅ በመገንዘብ ነው ።

Digitized by Google

አብዮታዊው መንግሥት አብዮቱ በፖለቲካው አመራር በኩል ያለበትን ይህንን ድክመት ለማስወገድ ከአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት ጀምሮና በተለይም ከብሔራዊ ዲ ሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መውጣት በኋላ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአብዮቱ ግንባር ቀደም ኃይሎች እንዲሰባሰቡና እንዲደራጁ፣ ብሉም ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አንድነት በመፍጠር ለግንባር ቀደሙ ፓርቲ መፈ ጠር መሠረት እንዲጥሉ የተቻለውን ሁሉ ድጋፍ ሰጥቷል ፤ ሁኔታዎችንም አመቻች ቷል ። ዳሩ ግን በአብዮቱ ሠፈር ውስጥ ከነበሩት ወገኖች የተለያዩ የርዕዮተዓለማዊ ግንዛቤ ደረጃና የተግባራዊ ፖለቲካ ስህተቶች እንዲሁም ከአገሪቱ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃና ካለው ዓለምአቀፍ ሁኔታ በመነጩ ሌሎች አያሌ ምክንያቶች የተነሣ የተ ያዘው ጥረት ወዲያውኑ አጥጋቢ ውጤት ሊሰጥ አልቻለም ነበር ።

በወቅቱ ከተከሰቱት ሁኔታዎች የኢትዮጵያ ሐቀኛ አብዮታውያንና ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ታላቅ ትምህርት ለመቅሰም እንደቻሉ አያጠራጥርም ። ይህንንም « ፓርቲ የሚመሠረተው ለይስሙላ ሳይሆን የታሪክ ግዴታ በመሆኑ ነው » በሚለው ግንዛቤና መፈክራቸው በወቅቱ አስተጋብተውታል ። በእርግጥ በዚህ መፈክር ውስጥ የሚጠቃ ለል አንድ ቁም ነገር አለ ። ይኸውም የማንኛውም ነገር ወይም ክስተት በሰዎች ምኞ ትና ፍላጎት ብቻ ሊሆን እንደማይችል ሁሉ ፣ በሳይንሳዊ ንድፈሃሳብ የሚመራ የማ ሌ ፓርቲም በተወሰነ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረት ላይ ተመሥርቶ የሚፈጠርና ከእነዚህም ሁኔታዎች ዕድገት ጋር እየዳበረና ጥንካሬ እያገኘ የሚሄድ ታሪካዊ ክስተት መሆኑ ነው ። የማንኛውንም ኅብረተሰብ የፖለቲካ ይዘት ተጨባጩ የኢኮኖሚ ሁኔታ ይወስነዋል የተባለውም ግንዛቤ ከዚሁ ጋር የተዛመደ ነው ።

ሐቀኛ አብዮታውያን በአብዮቱ ሂደት ወቅት ከቀሰሙት ልምድና ካዳበሩት ግን ዛቤ በመነሳት ለአብዮቱ ዋስትና ሊሆን የሚችለውን የሠርቶአደሩን ፓርቲ በጠንካራ መሠረት ላይ ለማቋቋም ትክክለኛውን ተግባራዊ ጉዳና መርጠው ትግሉን ቀጠሉ ። ለአብዮቱ ያላቸውን ሐቀኛነት በተግባራቸው ያስመሰከሩትን ፣ ለወዝአደሩ ርዕዮተ ዓለምና ዓላማ በቀራጥነት ሊቆሙ የሚችሉ አብዮታውያንን በአንድ ማዕከል ሥር በማሰባሰብ ለተግባራዊ ተሳትፎ ለማሰለፍ ተቻለ ። የኢሠፓአኮ መቋቋምና ኢሠፓአኮ እስከዛሬ ያከናወናቸው ተግባሮች የዚሁ ጥረት ዓይነተኛ ውጤት መሆናቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

ኢሠፓአኮ ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ ያተኮረባቸው ሁለት መሠረታዊ ዓላማ ዎች ፣ « በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መካከል የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፍልስፍና እንዲ ሰርጽና እንዲሠራጭ ማድረግ » እና የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ « ወደ ሶሻሊዝም ብሎ ም ወደ ኮምዩኒዝም ሥርዓት ማኅበር የመምራት ኃላፊነትና ታሪካዊ ተልዕኮ የሚና ረውን አንድ ብቸኛና ጠንካራ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም መርሆዎች ላይ የተመሠረተ የሠ ርቶአደሮች ፓርቲ እንዲመሠረት ማድረግ » ሲሆን ፣ እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ በማድረግ ረገድ አያሌ ድሎች ተገኝተዋል ። ድርጅታዊ ሥራንና ርዕዮተዓለማዊ ሥር ጭትን በሚመለከት በጥቂት ዓመታት ውስጥ የተከናወኑት ተግባራት ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም ።

ኢሠፓአኮ ከተቋቋመና ይፋ እንቅስቃሴውን ከጀመረበት ከአንደኛ ጉባኤው ጀ ምሮ ራሱን በማዋቀር ፣ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በየፈርጁ በማደራጀትና የፖለቲካ ንቃ

Digitized by Google

ተጓሊናውን በማዳበር ለአብዮቱ አስተማማኝና ዘላቂ የፖለቲካ አመራር ለማስገኘት በየመስኩ ካከናወናቸው ሥራዎች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ምድር ሶሻሊዝምን በጸኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ለተለያዩ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መስኮች ትክክለኛውን የዕድገት ፈር ቀይሷል ። ይህንኑ በማስመልከት የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ፣ «የተያያዝነው የሽግግር ወቅት ለሶሻሊዝም ዕውን መሆን ተፈላጊውን የሚቴሪያል ፣ የቴክኒክና የባህል መሠረት ለማስገኘትና በትርፍ ሳይሆን በፍላጐት የሚመራውን ሶሻሊስት ኢኮኖሚ የምንገነባበት ወቅት ነው ። የሽግግር ወቅት ሶሻሊስት ኢንዱስትሪን በተለይም ከባድ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት እርሻውንና የዕደ ጥበብ ዘርፉን ወደ ከፍተኛ የማኅበራዊ ምርት ደረጃ የምናሸጋግርበት ወቅት ነው፤»* በማለት የኢኮኖሚ ግንባታንና የምርት ግንኙነቶችን ለውጥ በሚመለከት ትክክለኛ የፖለቲካ አቋም ወስዶአል ።

በቅርቡ የተካሄደውና ታሪካዊ የሆነው የኢሠፓአኮ ፪ኛ ጉባኤ ያስተላለፋቸው ውሳኔዎችም አጠቃላይ መንፈስ ፣ የተያያዝነው ለሶሺያሊዝም ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት የመጣሉ ፣ የሶሺሊስት የምርት ግንኙነትን የማስፋፋትና የማጠናከሩ ትግል ሊሰምር የሚችለው ፣ ኢኮኖሚውን በዕቅድ በመምራት የሠርቶአደሩን ሕዝብ መሠረታዊ የሆኑ ማኅበራዊ ችግሮች ለማቃለልና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት የሚሟላው፣በአጠቃላይ የሶሺያሊስት የዕድገት ጉዟችንን በማፋጠን የበለጸገችና ፍትሕ የሰፈነባትን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ዋስትናው ጠንካራ የሠርቶ አደሮች ፓርቲ መመሥረት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ። ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይኸንኑ ጉዳይ በማስመልከት ለዚሁ ታላቅ ጉባኤ ባሰሙት ንግግር ላይ «...እጅግ ውስብስብ የሆነውን ሶሺያሊስት ግንባታ ለማቀነባበር ፣ ማለትም ኢኮኖሚያዊ ፣ አስተዳደራዊ ፣ ወታደራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ፣ እንዲሁም የውጭ ፖሊሲንና የመሳሰሉትን ሁሉ በቀንጅትና በትክክል ለማካሄድ የግንባር ቀደም ፓርቲ አመራር ምትክ አይኖረውም፤» ** በማለት የተለያየ ገፅታ ላለው የሶሻሊስት ግንባታ መሳካት የፓርቲን የፖለቲካ አመራር ወሳኝነት አመልክተዋል ።

ይኸም ሁኔታ ከአብዮቱ ሐቀኛና ዘላቂ ዓላማ አንጻር ፣ ቀደም ሲል በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባና በቅርቡም በኢሠፓአኮ ፪ኛ ጉባኤ ለተቀየሱት የኢኮኖሚና የጣህል ግንባታ ተግባሮች ጠንካራና አስተማማኝ የፖለቲካ አመራር የማስገኘቱ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ሠርቶአደሮች ፓርቲ ሕልውና ማግኘት ጋር በቀርብ የተቆራኘ መሆኑን ያስገነዝበናል።የሠርቶአደሩ ፓርቲ ምሥረታ መሳካት ደግሞ ካልተከለሰ የማሌ ርዕዮተዓለም ስርጭትና በተለይም አባላቱ ከሚኖራቸው የግንዛቤ ደረጃና ተገዥነት ጋር የተቆራኘ ነው ።

በመሆኑም የወቅቱ የአብዮታውያንና የመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ትኩረት ለማሌ ሳይንስ ስርፀት ፣ ለፓርቲያችን ሕልውና ማግኘት፣ለሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ መመሥረትና በመካሄድ ላይ ያለውን ትግል በማፋፋም ለታሪካዊው የኢሠ

---

* የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ 1973፣ገጽ 38

** የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች፣ታኅሣሥ 1975፣አ.አ፣ ገጽ 4—5

Digitized by Google

ፓለኮ ሁለተኛ ጉባኤ ውሳኔዎች ተገባራዊነት አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ መክ
ፈል መሆን ይገባዋል ። በተያያዝነው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ በኢኮኖሚውና በፖ
ለቲካው መካከል መኖር የሚገባው ግንኙነት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊፈታ የሚ
ችለው የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ ውሳኔዎችን ተገባራዊ በማድረግ ጠንካራ የማሌ
ፓርቲ ለማስገኘት በምናደርገው ጥረት መሆኑ አያጠራጥርም ።

Digitized by Google

ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የማስፋፋት ሂደት በኢትዮጵያ

— አሰፋ ሃብቱ

— ሞገስ ተ/ሚካኤል

የምርት ግንኙነት ምንነት

የማምረት ተግባርና ሂደት ምን ጊዜም ማኅበራዊ ግንኙነት ያለው ነው። የምርት ግንኙነት የሚባለውም ሰዎች ቁሳዊ ሀብትን በማምረት፥በማከፋፈልና በመለወጥ ሂደት ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚፈጥሩት የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው። የምርት ግንኙነት ባህርይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ይወሰናል። በመሠረቱ የምርት መገልገያዎች በኅብረተሰቡ አባላት በማኅበር ወይም ከኅብረተሰቡ አባላት መካከል በጥቂቶቹ በግል ሊያዙ ይችላሉ። የይዞታቸው ባህርይ በሰዎች መካከል በምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጠረውን ግንኙነት ባህርይ ይወስናል። ስለሆነም የምርት መገልገያዎች በማኅበር በተያዙባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት በእኩልነትና በጋራ መረዳዳት ላይ የተመሠረተ የጋርዮሽ የምርት ግንኙነት ይሆናል። የምርት መገልገያዎች በጥቂቶች ቁጥጥር ሥር በሆኑባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ ግንኙነቱ የሚመሠረተው በእኩልነት ሳይሆን የምርት መገልገያዎች ባለቤት በሆኑና ከሥራቸው በስተቀር ምንም ዓይነት የምርት መገልገያ በሌላቸው መካከል ስለሚሆን ግንኙነቱ በመደባዊ ጭቆናና በምዝበራ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

እስካሁን እኩልነት የሰፈነባቸው ስልተ ምርቶች የጥንቱ የጋርዮሽ ዘመን እና የወቅቱ የሶሻሊስት ሥርዓት ናቸው። በሁለቱ ሥርዓቶች መካከል ኅብረተሰቡ በመደብ የተከፋፈለባቸው የባሪያ አሳዳሪ፥ የፊውዳል እና የካፒታሊስት ጨቋኝ ሥርዓቶች ተከስተዋል። የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ሰው ሰውን እንደዕቃ አድርጐ የሚጠቀምበት፥ የሚሸጥበትና የሚለውጥበት ሥርዓት ሲሆን፥ በፊውዳል

Digitized by Google

ስልተ ምርት ደግሞ መሬት ዋና የምርት መገልገያ ሆኖ በዝባዥ መሳፍንትና መኳንንት ገባሩን እና ጭሰኛውን የሚበዘብዙበት ሥርዓት ነው ። የካፒታሊስት ሥልተ ምርት የሥራ ኃይል እንደሸቀጥ የሚሸጥበትና የሚለወጥበት በምንዳ ባርነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ነው ። ስለዚህ ከባሪያው አሳዳሪ ሥርዓት ጀምሮ እስከ ካፒታሊስቱ ሥርዓት ድረስ በጨቋኝና በተጨቋኝ መደቦች መካከል ያለው ግንኙነት በቅርጽ እየተለያየ የመጣ ቢሆንም በይዘት ግን የብዝበዛ ግንኙነት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም የተካሄደው ሽግግር የካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ በቅለው ማደጋቸውን ያሳያል ። ይህም ሊሆን የቻለው የሁለቱም ሥርዓቶች ኢኮኖሚ በምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነት ላይ በመመሥረቱ ነው ። በአንፃሩ ፣የሶሻሊስት ሥልተ ምርት የምርት ግንኙነቶች የምርት መገልገያዎች የግል ንብረትነትን በአብዮታዊ ኃይል በመደምሰስ እንጂ ከግል ንብረት ይዞታ በግብታዊነት በቅለው ሊያድጉ አይችሉም። በመሆኑም ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር በአጠቃላይ የሠራተኛው መደብና ገበሬው በጨቋኝና በዝባዥ መደቦች ላይ በሶሻል አብዮት አማካኝነት ድል የሚቀዳጁበት ነው ። [1]

ወደሶሻሊዝም በሚደረገው ሽግግር ወቅት ዋና ዋናዎቹ የንብረት ይዞታዎች ሶሻሊስታዊ የንብረት ይዞታ ፣ ቀላል የሸቀጥ ምርትና የግል ካፒታሊስት ይዞታ ናቸው ። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከእጅ ወደአፍ ብቻ የሆነ ኑሮ ለመኖር የሚያስችል ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚም ይገኛል ። ሶሻሊስታዊ የንብረት ይዞታ የመንግሥትንና የኀብረት ሥራ ማኅበር ይዞታዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን በሽግግሩ ሂደት ውስጥ ሌሎቹን ይዞታዎች ቀስ በቀስ ፣ በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ የሚተካ የይዞታ ዓይነት ነው ።

የ1917 የጥቅምቱ አብዮት በፊውዳሊዝም ፣ እና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ድል ከተቀዳጀበት ጊዜ አንስቶ ዲሞክራሲያዊ እና ሶሻሊስት አብዮቶች በተለያዩ ሀገሮች እየተካሄዱ ድል የመምታቸው ሂደት አንድ ዋና ዓለም አቀፋዊ ክስተት ሆኗል ። በዓለም በመስፋፋት ላይ የሚገኘው የሶሻሊስት ሥልተምርት ሰው ከጭቆናና ከብዝበዛ ነፃ ወጥቶ በእኩልነት ሊኖር የሚችልበት ፣ « ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደሥራው » በተሰኘው መርህ መሠረት ፣ የኀብረተሰቡ ፍላጐት ደረጃ በደረጃ የሚሟላበትና ወደ ኮሚኒዝም ለሚደረግ ሽግግር ቅድመ ሁኔታዎች የሚሟሉበት ሥርዓት መሆኑ የታወቀ ነው።

ወደሶሻሊዝም በሚደረገ ሽግግር መከናወን ካለባቸው ዋና ዋና ተግባሮች መካከል ደግሞ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች ዳብረው የበላይነቱን እንዲይዙ ማድረግ፣ የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ኅብረተሰቡን በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም ማነጽና የጠበቀ የኢኮኖሚና ሌሎችም ግንኙነቶች ከሶሻሊስት አገሮች ጋር መፍጠርን መጥቀስ ይቻላል ።

አገራችንን በሚመለከት ሶሻሊዝም መመሪያችን መሆኑ ከታወጀበት ከታኅሣሥ ወር 1967 ጀምሮ አብዮታዊው መንግሥት ለሶሻሊስት ሥርዓት ምሥረታና ግንባታ አመቺ ቅድመ ሁኔታዊ አዋጆችና መመሪያዎችን አውጥቷል ። በዚህ አኳያ ፣ በአዋጅ ቁጥር 26/1967 የወጣው የሶሻሊዝም መመሪያ ፣ የገጠር መሬትን የሕዝብ ያደረገው አዋጅ ቁጥር 31/1967 ፣ ሐምሌ 1967 የወጣው የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን ለየሕዝብ ያደረገው አዋጅ፣በሚያዝያ ወር 1968 የወጣው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና የኀብረት ሥራ ማኅበራትን ስለማቋቋም በቁጥር 138/1970 የወ

Digitized by Google

ጣው አዋጅ በተለይ የሚጠቀሱ ናቸው ። በነዚህ አዋጆችና መመሪያዎች አማካኝነት የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት፣ ትላልቅ እንዱስትሪዎች ፣ ሰፋፊ እርሻዎች፣ ባንኮች ፣ የፊናንስና የመድን ድርጅቶች ፣ ወዘተ . . . በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሕዝብ መሆናቸው ለሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ግንባታ መሠረት ሊጥሉ ችለዋል ። የዚህ ጽሑፍ የትኩረት መስክም በአብዮታዊት ኢትዮጵያ በመዳበር ላይ የሚገኙትና ሶሻሊስታዊ ይዞታዎች የሆኑት የመንግሥትና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይዞታዎች ናቸው ።

የመንግሥት ይዞታ

ወደሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ሂደት የፖለቲካ ሥልጣንን የተረከበው አብዮታዊ መንግሥት አንድ ዋና ተግባር ማኅበራዊ ምርት በዕቅድ እየተመራ የሚዳብርበትን ሁኔታ መፍጠር መሆኑ የታወቀ ነው ። ይህንንም ተግባር ለማከናወን አብዮታዊው መንግሥት የኤኮኖሚውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ፈር ለማስያዝ የሚያስችሉ ዋና ዋና የኤኮኖሚውን ክፍሎች በንብረትነት በመያዝ በቀጥታ ቁጥጥሩ ሥር ያውላቸዋል ። ይህም የሶሻሊስት ይዞታ ዋና አካል የሆነውን የመንግሥት ይዞታን ለመመሥረት ያስችላል ።

በዚህ አኳኋን አብዮታዊው መንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን ሲጨብጥ በተቀዳሚ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን ፣ ባንኮችንና ሌሎች ገንዘብ ነክ ድርጅቶችን ወደ ራሱ ንብረትነት ይለውጣቸዋል ። ትራንስፖርትና መገናኛን በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል። የውጪ ንግድንና ቢያንስ በአብዛኛው የአገር ውስጥ ንግድን በራሱና በሕዝባዊ ድርጅቶች አማካኝነት እንዲካሄዱ ያደርጋል ። መሬትን ከፊውዳሎችና ከካፒታሊስቶች የግል ንብረትነት አላቆ የሰፊው ሕዝብ ንብረት በማድረግ የመንግሥት እርሻዎችንና የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይመሠርታል ። አብዮታዊው መንግሥት በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ እርምጃዎች አማካኝነት የኤኮኖሚውን መሪ ክፍሎች (commanding heights)በአፋጣኝ ወደ ሕዝብ ንብረትነት በመለወጥ የካፒታሊስቱን ይዞታ መሠረቱን ያፈራርሰዋል። በገጠር የነበሩ ልዩ ልዩ የብዝበዛ ቅርጾችን ይደመስሳል ፤ ሶሻሊስታዊ የኤኮኖሚ ይዞታም እንዲፈጠር ያደርጋል ። [2]

በአገራችን አብዮታዊው መንግሥት እንደተቋቋመ ከላይ በተጠቀሰው መርህ መሠረት የመንግሥት ይዞታን ለመመሥረትና ለማጠናከር በርካታ እርምጃዎችን መውሰዱ የታወቀ ነው ። በዚህ አንፃር መንግሥት ሥልጣን በያዘበት ዓመት መጀመሪያ ላይ ፣ ማለትም ታኅሣሥ 11 ቀን 1967 በወጣው መመሪያ ፣ « . . . ለኅብረተሰቡ የኤኮኖሚ ዕድገት መሠረታዊ የሆኑና ለኅብረተሰቡ ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠት የሚገባቸው ሀብትና ንብረቶች ሁሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን ይገባቸዋል»[3] ማለቱ ይታወሳል ። በዚያው ዓመት በሚቀጥለው ወር የወጣው የኢትዮጵያ የኤኮኖሚ መመሪያም በመሠረቱ መንግሥት የኤኮኖሚውን መሪ አካሎች በቁጥጥሩ ሥር እንዲያውል የሚረዳ ነበር ። [4]

ባለፉት ስምንት ዓመታት አብዮታዊው መንግሥት በኢኮኖሚው መስክ ይዞታውን ለመመሥረትና ለማጠናከር ስለወሰዳቸው እርምጃዎች ፣ ስላጋጠሙት ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት ስለተቀየሱት ስልቶች እንዲሁም ስለተገኙት ውጤቶች በዝርዝር ተንትኖ ለማቅረብ ሰፊ ጥናትን እንደሚጠይቅ ግልጽ ነው ። ሆኖም በመንግሥት ይዞታና ቁጥጥር ስለሚካሄዱት ቁልፍ የኤኮኖሚ ክፍሎች ማለትም በእርሻ ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ ፣ እንዲሁም በንግድ ዘርፎች በዚህ አንፃር ስለተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ከዚህ በታች አጠር ባለ መንገድ ለማቅረብ ተሞክሯል ።

የመንግሥት እርሻዎች የተቋቋሙት የገጠርን መሬት የሰፊው አርሶ አደር ሕዝብ

Digitized by Google

ንብረት ባደረገው አዋጅ መሠረት በቅድመ አብዮት ጥቂት ከበርቴዎች ለብዝበዛና ለግል ሀብት ማከማቻ ሲጠቀሙባቸው የነበሩት ሰፋፊ እርሻዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ እንደተደረገ ነው ። የመንግሥት እርሻዎች ትኩረትም የምግብ እጥረትን ለማቃለል ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ማድረግ ፣ ለኢንዱስትሪ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን ለማሟላት ድጋፍ መስጠትና የውጪ ምንዛሪ የሚያድጉና የሚያዳብሩ የግብርና ውጤቶችን በዓይነትና በመጠን አዳብሮ ማምረት ናቸው ።

መንግሥት በ1967 የተረከባቸው እርሻዎች ጠቅላላ ስፋት 131 ሺህ ሄክታር ቢሆንም አብዛኛዎቹ እርሻዎች የተበታተኑና ለመንግሥት እርሻነት የማያመቹ ሆነው በመገኘታቸው በከፊል ለአካባቢው ገበሬዎችና ለሠፈራ ጣቢያዎች እንዲሰጡ ተደርጎ በ1969 የመንግሥት እርሻ ስፋት 63 ሺህ ሄክታር ሆነ ። በሚቀጥለው ዓመት ወደ 72,700 ሄክታር ከፍ አለ ። በዚያ ዓመት ፣ ማለትም በ1970/71 የመንግሥት እርሻ ስፋት በአገሪቱ ከታረሰው ጠቅላላ ስፋት ጋር ሲነፃጸር 1.4 በመቶ ፣ እንዲሁም በእርሻ ምርት መጠን 1.6 ሚሊዮን ኩንታል እህልና 75 ሺህ ኩንታል አትክልት በማምረት ከአገሪቱ ጠቅላላ የእርሻ ምርት 3 በመቶውን ብቻ ይዞ ነበር ።[5]

የምርትና ባህል ዕድገት ዘመቻ ከተጀመረ ወዲህ የመንግሥት እርሻ ስፋት እያደገ መጥቷል ። በዘመቻው ጠቅላይ መምሪያ ግምገማ መሠረት በ1973 በመንግሥት 224 ሺህ ሄክታር መሬት ታርሶ 3,525,000 ኩንታል ምርት ተገኝቷል ። ይህም በዚያው ዓመት በአገሪቷ በጠቅላላ ታርሷል ተብሎ ከተገመተው የመሬት ስፋት (6,165,000 ሄክታር) እና ተመርቷል ተብሎ ከተገመተው ምርት (62,970,000 ኩንታል) ጋር ሲነፃጸር 3.6% እና 5.6% መሆኑ ነው ።

በዚህ አኳኋን የመንግሥት እርሻዎች የመሬት ስፋትና የምርት ጭማሪ ዕድገት ያሳዩ መሆናቸው ቢታወቅም፣ ይህ ዕድገት ምርታማነት በሄክታር ከማደጉ የመነጨ አለመሆኑ ግልጽ ነው ።

ለዚህም በርካታ ምክንያቶች በየጊዜው ይነሳሉ ። አንዳንድ የመንግሥት እርሻዎች የሚጀመሩት በቂ ጥናት ሳይደረግና አስፈላጊ መረጃዎች በትክክል ሳይሰበሰቡ ነው። ሳይንሳዊ የእርሻ ሥራ ባልመከተል የማረስ የመዝራት ፣ የማረም ፣ የመሰብሰብና የመሳሰሉት ተግባራትን በወቅቱ ያለማከናወን ችግር መኖሩ ታውቋል ። በተጨማሪም የመንግሥት እርሻዎች ከእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩቶች ጋር አጥጋቢ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ተገቢውን የዘር ጊዜ ፣ ቶሎ የሚደርሰውን ዘር ፣ በሽታ የሚቋቋመውን ዘር ፣ ብዙ ፍሬ የሚሰጠውን ዘር ፣ ወዘተ. . . እንደቦታውና እንደአየሩ ጠባይ ለይተው ተግባራቸውን ማካሄድ አይችሉም ። በተለይ በቴክኒክ ፣ በእርሻና በሒሳብ ሥራ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረትም በየመንግሥት እርሻው የሚታይ ችግር ነው ። በሥራ አመራርም በኩል አብዮታዊው መንግሥትና ኢሠፓአኮ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በሚገባ የተገነዘበና የሰፊው ሕዝብ ወገናዊነቱን ያጠናከረ ፣ ተግባሩን በተቀላጠፈ አኳኋን ለማካሄድ የሚያስችሉት የሥራ አመራር ዘዴዎች ዕውቀቱን ያዳበረ የሥራ መሪ እጥረት በተለይ አብዮታዊት ኢትዮጵያ አሁን በምትገኝበት የሽግግር ወቅት መኖሩም የሚካድ አይሆንም ። የጉልበት ሠራተኞችም ቢሆኑ በአንዳንድ የመንግሥት እርሻዎች እጥረት ሲኖር በሌሎች ደግሞ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ መኖራቸው ታውቋል ። የእርሻ መሣሪያዎች እጥረትና አጠቃቀም ችግርም አለ ። አጠቃቀምን በሚመለከት ለምሳሌ በ1973 የመንግሥት እርሻዎች በአጠቃላይ ከነበሯቸው 2,100 ያህል ትራክተሮች በብልሽት የቆሙ 44% ያህል ነበሩ ። ለዚህም ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል

Digitized by Google

የትራክተር ሹፌሮች ጥራት እነስተኛነት፥ የሚካኒኮች እጥረት ፥ የተሟላ የጋራዥ ዕቃ አለመኖር ፥ የመለዋወጫ ዕቃ እጥረትንና የእርሻ መሣሪያዎች ዓይነት በመጠኑም ቢሆን ካለው የአየር ጠባይና ከመሬቱ ጥንካሬ ጋር አለመስማማት ይገኛሉ ። ገንዘብ ንም በሚመለከት የመንግሥት እርሻዎች ከባንክና ከእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ጋር ያላቸው ግንኙነት የእርሻዎቹን እንቅስቃሴ በተቀላጠፈ አኳኋን ለማካሄድ በማገዝ ረገድ አጥጋቢ ነው ለማለት አይቻልም ። ስለዚህ የመንግሥት እርሻዎች እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮች ያሉባቸው በመሆናቸው ምርታማነታቸው የተፈለገውን ያህል ከፍተኛ ሊሆን አልቻለም።[7] ሆኖም እነዚህ ችግሮች በአብዮቱ ሂደት የመንግሥት ይዞታ ልምድ እያካበተ ሲሄድ ደረጃ በደረጃ በዕቅድ መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉና ማግኘትም የሚገባቸው መሆናቸው አያጠራጥርም ። የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ካሳለፋቸው ኤኮኖሚ ነክ ውሳኔዎች መካከልም ፥ «የመንግሥት እርሻዎች ምርታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ እንዲችሉ የአደረጃጀታቸውንና የማኔጅመንታቸውን ጥራት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡትና እንዲሁም ገበሬው በተሻለ ቴክኖሎጂና የእርሻ ዘዴ እየተጠቀመ የተሻለ ውጤት እንዲያስገኝ በተግባራዊ አርአያነት ለማስተማር የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ጥረት እንዲደረግ»[8] የሚል መገኘቱ በመንግሥት እርሻዎች አካባቢ ለሚታዩ ችግሮች ትኩረት መስጠቱን ያሳያል ።

በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚጠቃለሉት ማኑፋክቸሪንግ ፥ ኮንስትራክሽን፥ ማዕድን፥ የውሃ ልማትና የኃይል ምንጭ ልማት ሲሆኑ ፥ ይህ ክፍለ ኤኮኖሚ፥ በተለይም የማኑፋክቸሪንግና የኮንስትራክሽን ክፍሉ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በከበርቴዎች ቁጥጥር ሥር እንደነበር የታወቀ ነው። ኢንዱስትሪ የዕድገት እንቀሳቃሽ ኃይል ብቻ ሳይሆን በሠራተኛ ክምችትም ሆነ በአመራረት ጠባዩ ለሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ይዞታ መስፋፋት ወሳኝነት ያለው በመሆኑ በአብዮታችን ሂደት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል ። ባለፉት ስምንት ዓመታት በተወሰዱት እርምጃዎች አማካኝነት ይህ ክፍለ ኤኮኖሚ የመንግሥት ይዞታ በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበት ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ረገድ የተደረጉ ጥረቶችና የተገኙ ድሎችም ከዚህ በታች ባጭሩ ይገለጻሉ ።

በ1962 አካባቢ በተጠናቀረ መረጃ መሠረት ፥ በዚያን ጊዜ ከነበሩት የፋብሪካ ባለ ንብረቶችና የኩባንያ ዲሬክተሮች ውስጥ 71 በመቶ የውጭ አገር ዜጐች ነበሩ ። በኢትዮጵያ አብዮት ዋዜማ ከጠቅላላው የተከፈለ የኩባንያዎች አክስዮን (paid-up jointstock capital) የውጭ አገር ዜጐች ድርሻ 43.5 በመቶ ፥ የአገር ውስጥ የግል ባለንብረቶች (በአብዛኛው ዜግነታቸውን ለውጠው ኢትዮጵያውያን የሆኑ ግሪኮች ፥ ጣሊያኖች ፥ ሕንዶች ፥ አርመኖችና ሌሎች) ድርሻ ደግሞ 19 በመቶ ነበር። የቀረው 37.5 በመቶ ለስሙ የመንግሥት ይዞታ ድርሻ ቢሆንም በአብዛኛው ንጉሣውያን ቤተሰቦች ፥ ባላባቶችና ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት በስውር በግል ባለቤትነት የያዙት እንደነበር የታወቀ ነው ።[9]

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮት እንደተቀጣጠለ አብዮታዊው መንግሥት ፋብሪካዎችን በሚመለከት በወሰደው ከፍተኛ እርምጃ መሠረት በ1967/72 የማምረቻ ድርጅቶችና ኩባንያዎችን በአዋጅ በመንግሥት ቁጥጥር የሕዝብ ንብረት ሊሆኑ ቻሉ ። አዋጁ በተጨማሪም የ 29ሌሎች የኢንዱስትሪ ድርጅቶች አክስዮን አብዛኛው የመንግሥት እንዲሆን አድርጓል ። የኢንዱስትሪው ክፍለ ኤኮኖሚ የመንግሥት ይዞታ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመሄድ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ አሥርና ከዚያም በላይ የሆነ የሠራተኞች ቁጥር ካላቸው 417 ፋብሪካዎች መካከል በምርት ውጤታቸው በጣም ከፍተኛውን እጅ የያዙ 180

Digitized by Google

ፋብሪካዎች በመንግሥት ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ይገኛሉ ። [10]

በ1969 የበጀት ዓመት ግምቱ 656 ሚሊዮን ብር የነበረው የመንግሥት ፋብሪካዎች የቋሚ ንብረት በ1975 ወደ 1.13 ቢሊዮን ብር ከፍ እንዳለ ይገመታል ። የዚህ ዕድገት ዋና ምክንያት በኢንዱስትሪው መስክ የመንግሥት ይዞታን ለማስፋፋት መንግሥት በየጊዜው በቁጥጥር ሥር የሚያውላቸው ፋብሪካዎች ቁጥር መጨመር ሲሆን፣ በመጠኑም ቢሆን የመዋዕለ ነዋይ ወጪ መደረጉን ያመለክታል ። በ1974 የአገሪቷ ጠቅላላ የማኑፋክቸሪንግ ክፍለ ኤኮኖሚ ምርት ዋጋ (Gross value of Production)

1.9 ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህም ውስጥ የመንግሥት የሆኑ ፋብሪካዎች ድርሻ ከ 85%በላይ መሆኑ ተገምቷል ። በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በጠቅላላ የተሠማሩ ሠራተኞች ብዛትም ከ95,000 በላይ ሲገመት ከእነዚህ ውስጥ በመንግሥት ይዞታ ሥር ባሉ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ከ86% በላይ ናቸው ። [11]

በኢንዱስትሪው መስክ የመንግሥትን ይዞታ ለማስፋፋት የሚችሉ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በተጨማሪም በሥራ ላይ በመዋል ላይ ናቸው ። ለምሳሌ በ1975 የበጀት ዓመት በዝርዝር ከተያዙት ፕሮጀክቶች ዋና ዋናዎቹ የባሕርዳር ምግብ ዘይት ፋብሪካ ፣ የሐረር ቢራ ፋብሪካ ፣ የቢራ ብቅል ፋብሪካ ፣ የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ፣ አራተኛው የሙገርና አምስተኛው የድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች የኮስቲክ ሶዳ ፋብሪካ ፣ የእርሻ ትራክተር መገጣጠሚያ ፋብሪካ እና የመለዋወጫ ዕቃዎች ፋብሪካ ሲሆኑ የእነዚህ ፋብሪካዎች ተጠናቅቀ በሥራ ላይ መዋል ክፍለ ኤኮኖሚውን የሚያጠናክር ብቻ ሳይሆን በምርት አቅርቦት በኩል የሚገኘው ውጤት ከፍተኛ እንደሚሆን ግልጽ ነው ።

የኮንስትራክሽን ክፍለ ኤኮኖሚ የምርት ኃይሎችን ለማሳደግ ለሚወጣ ዕቅድ አፈፃፀምና ፣ በአጠቃላይም በኤኮኖሚና በሶሻል እድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ስለአለው የክፍለ ኤኮኖሚው በቅልጥፍና መንቀሳቀስ ለሌሎች ክፍላተ ኤኮኖሚዎች ዕድገት ወሳኝነት አለው ። በቅድመ አብዮት ይህ ዘርፍ በተበታተነ መልክ በግል ተቋራጮች የሚካሄድና እንቅስቃሴውም ለግል ባለሀብቶች የገቢ ምንጭ የሚሆኑ ሕንፃዎችን በመሥራት ላይ ያተኮረ ነበር።

በአሁኑ ጊዜ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የመንግሥት ይዞታ ድርሻ 55.5 በመቶ የደረሰ ሲሆን ይዞታው የተስፋፋው በመጀመሪያ ደረጃ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው የውጭ አገር የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ባለንብረቶች ከአገር በሚኮበልሉበት ጊዜ መከናወን ያለበትን ተግባር የሚረከቡ ተገቢ ድርጅቶችን በማቋቋም ነው ።

በኮንስትራክሽን ሥራ የተሠማሩ የመንግሥት ከፍተኛ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ፣ የኢትዮጵያ ትራንስፖርትና ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ፣ የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሲሆኑ የአገሪቱን የኮንስትራክሽን ሥራ በበላይነት የሚመራ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተቋቁሟል ። በአሁኑ ጊዜ የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ሥራ የሚያተኩረው እንደቅድመ አብዮት ሁኔታ በትላልቅ ከተሞች ላይ ብቻ ሳይሆን በፕላን መካሄድ ያለበትን የልማት እንቅስቃሴ በማገዝ በመንግሥት እርሻዎች ፣ በትናንሽ ከተሞች የመኖሪያ ቤቶች ሥራ ፣ የትምህርትና የጤና ጣቢያዎች ግንባታ ፣ የገጠር መንገዶችና የገጠር ውሃ ቁፋሮ ሥራዎችና የመሳሰሉትን በመከናወን ላይ ነው ።

የዚህ ክፍለ ኤኮኖሚ ችግር በአጠቃላይ አገሪቱ በልማት ኋላቀር ከመሆን ጋር የተያያዘ ሲሆን በተለይም የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረትና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አቅርቦት ማነስ ዋናዎቹ መሆናቸው ግልጽ ነው ። የኮንስትራክሽን ዕቃዎችንበሚመለ

Digitized by Google

ከት በመገርና በድሬዳዋ በመሠራት ላይ ያሉት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማምረት ሲጀምሩ ችግሩ በአንድ ወሳኝ በሆነ ዕቃ አቅርቦት በኩል እንደሚቃለል ይገመታል ።

የትራንስፖርትና መገናኛ ክፍል ኤኮኖሚ እንደመንገድ ፣ ወደብ ፣ የባቡር ሃዲድ አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ፣ የቴሌፎን መገናኛና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን (ኢንፍራስትራክቸሮችን) መሥራትና መዘርጋትትን ፣ እንዲሁም በየብስ ፣ በባህርና በአየር ተሳፋሪዎችንና ጭነት ማጓጓዝን ፣ የቴሌፎንና የፖስታ አገልግሎት መስጠትን የሚያጠቃልል በመሆኑ የአንድ ኤኮኖሚ «የደም ሥር» እየተባለ ይነገርለታል ።

ይህን ክፍለ ኤኮኖሚ የሚመለከቱ መሠረተ ልማቶች በፊትም እንደነበረው የመንግሥት ንብረት ሲሆኑ ፣ አገልግሎት መስጠትን በሚመለከት ግን ከአብዮታችን ፍንታ ወዲህ ብዙ ለውጦች ተካሂደዋል ።

በአገራችን የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የሕዝብም ሆነ የጭነት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በግለሰቦችና በግል ኩባንያዎች ሲካሄድ ነበር ። በቁጥጥር ፣ በሥምሪት ሥርዓትና በዋጋ ተመን በኩል እንኳን የነበረው የመንግሥት ሚና ውሱን ሆኖ ቆይቷል ።

ባለፉት ስምንት የአብዮት ዓመታት በተወሰዱት እርምጃዎች አማካይነት ባሁኑ ጊዜ ካለው የመንገድ ጠቅላላ የመጫን ችሎታ የመንግሥት ድርሻ በደረቅ ጭነት 25.5 በመቶ ፣ በፈሳሽ ጭነት 32.4 በመቶ በሰው መጓጓዝ ደግሞ 35 በመቶ ሊሆን ችሏል ። የጭነት ማመላለሻ ድርጅት ካፒታል በ1967 ከነበረው ከ750,000 ብር ወደ 50 ሚሊዮን ብር ከፍ ሲል ፣ የሕዝብ ማጓጓዣው ክፍል ደግሞ በነሐሴ 1966 የነበረው አምስት ሚሊዮን ብር ካፒታል ከእጥፍ በላይ አድጓል ። [12] አዳዲስ የመንግሥት አውቶቡሶችና የጭነት መኪናዎች በሥራ ላይ እየተሰማሩ በመሆኑ በዚህ ረገድ እድገት መታየት ወደፊትም እንደሚቀጥል ይጠበቃል ።

የመንገድ ትራንስፖርት በሀገራችን በዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚጠቀመው 96% ያህል ተሳፋሪ የሚያጓጓዝና ከአጠቃላይ ጭነትም 93% ያህል የሚያንቀሳቅስ በመሆኑ ለእድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ግልፅ ነው ። [13] ሌላው የየብስ ትራንስፖርት ዘርፍ ክፍል የባቡር ትራንስፖርት መሆኑ የታወቀ ነው ። ንብረትነቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና የጂቡቲ የሆነው አዲስ አበባ ጂቡቲ የምድር ባቡር የሚያነሳውን ጭነት መጠንና የሚያመላልሰውን ሕዝብ ቁጥር ለማሳደግ፣ ያረጁ መሳሪያዎችን ለመተካትና አገልግሎቱን ለማስፋፋት የሚያስችል ስምምነት በሁለቱ መንግሥታት መካከል በቅርቡ ተፈርሟል ። በመንግሥት ሙሉ ቁጥጥር ሥር ውለው የሚገኙት የባህር ትራንስፖርት አገልግሎትና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥር በሚተዳደሩ 6 ባለሥልጣኖች፣ ኮርፖሬሽኖችና ድርጅቶች አማካኝነት በዕቅድ ለመምራትና ለማስፋፋት የሚያበረታታ እንቅስቃሴ በመታየት ላይ ይገኛል ። የመገናኛ አገልግሎትም በመንግሥት ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ሲሆን፣ የዚሁ ዘርፍ ክፍሎች የሆኑት የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎት በሚመለከት እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኘውን የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት በበለጠ ለማርካት ጥረቱ እንደቀጠለ ነው ።

በንግዱ ክፍለ ኤኮኖሚ ፣ በተለይም በውጪ ንግድና በኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች ያገር ውስጥ ጅምላ ንግድ በአሁኑ ጊዜ የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶች ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ይገኛል ። ዝርዝር ሁኔታውን በዚሁ መጽሔት ስለንግድ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ መመልከት ይቻላል ።

Digitized by Google

ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴና ያሉበት ሁኔታ

የኅብረት ሥራ ማኅበር ይዞታ ከሶሻሊስታዊ የንብረት ይዞታ አንዱ ሲሆን ፣ አባላቱም የሚደራጁት የሌኒንን የኅብረት ሥራ መርሆዎች በመከተል ነው ። እነዚህም መርሆዎች ፣ አባልነት በፈቃደኝነት መሆኑን ፣ ማኅበራት በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መመራታቸውን ፣ ክፍያ የሚከናወነው « ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፣ ለእያንዳንዱ እንደሥራው» መሆኑን ፣ ማኅበራት በማዕከላዊ እቅድ መመራታቸውን ፣ ማይምነት እንዲጠፋና ሙያ እንዲዳብር ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጥ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው ። የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዙ ዓይነቶች ናቸው ። እነዚህም የአገልግሎት ፣ የአምራቾች ፣ የሸማቾች የብድርና የቁጠባ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመባል ይታወቃሉ ። የዚህ ጽሑፍ ትኩረት በተለይ የገበሬዎችና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ነው ።

የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት

የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የጭሰኛና የባለርስት የምርት ግንኙነት በአብዮቱ ተደምስሶ መሬት የሕዝብ ሲሆን እርሶ አደሩ በተፈጠረለት አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ከ1968 ጀምሮ ከከበርቴ በተወረሱ እርሻዎች ላይ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከመመሥረቱም በላይ በቀበሌ ገበሬ ማኅበር በመደራጀት የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራትን እያቋቋመ የሸቀጥ ሥርጭትን አገልግሎት ማግኘት መጀመሩ ይታወሳል ።

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መደራጀት የጀመሩት በዚህ አኳኋን ቀደም ሲል ቢሆንም ፣ ተገቢውን ፈር ይዘው መስፋፋትና መጠናከር የጀመሩት በ1971 ነው ። የግብርና ሚኒስትር በቅርቡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት እንደሚቻለው የአምራቾች የኅብረት ሥራ መመሪያ በአብዮታዊው መንግሥት ከወጣ ፣ ከ1972 ወዲህ ገበሬዎች በፈቃደኝነት በመጀመሪያ መሬታቸውን በማዋሃድ ፣ ከዚያም የንቃተ ሕሊና ደረጃቸው እያደገ ሲሄድ የማምረቻ መሳሪያዎቻቸውን በማኅበሩ አስተዳደር ሥር በማድረግ በማልባና በወልባ ደረጃ በመደራጀት ላይ ይገኛሉ ። እስካሁን ድረስ የተቋቋሙ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጠቅላላ ቁጥር 1,006 ሲሆን ከእነዚህም መካከል 744ቱ በማልባ ደረጃና የተቀሩት 262ቱ በወልባ ደረጃ የተደራጁ ናቸው ። ሕጋዊ ሰውነት ያገኙ የአምራቾች ማኅበራት ቁጥር 150 ደርሷል ። በ1,006ቱ ማኅበራት ውስጥ የተደራጁ አባላት ብዛት 60,058 ሲሆን ፣ የሚያለሙት የመሬት ስፋት 151,759 ሄክታር ነው ። ማኅበራቱ የሚጠቀሙባቸው የእርሻ በሬዎች ብዛት 42,643 የሚደርስ፣ያላቸው ካፒታልም 222,150 ብር ያህል ይገመታል ።ባሁኑ ጊዜ በትራክተር የሚጠቀሙ ማኅበራት ቁጥር 47፣ እንዲሁም መሬታቸውን በመስኖ ሥራ በማልማት የተሰማሩ ማኅበራት ቁጥር 102 መድረሱ ታውቋል ። 130 ማኅበራት የተሻሻለ የእህል መጋዘን ያላቸው ናቸው ። ባሁኑ ጊዜ፡ በባሌ ክፍለ ሀገር በ300 መንደሮች ከተሰባሰቡ ገበሬዎች በተጨማሪ የ61 ገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት በመንደር በመሰባሰባቸው ለምርት እድገትና ለማኅበራዊ አገልግሎት

መስፋፋት አመቺ ሁኔታን በመፈጠር ላይ ይገኛል ። የምርት ግብ ተጥሎላቸው ባእቅድ የሚያመርቱ ማኅበራት ብዛት በ1972/73 42 የነበረው በ1973/74 ወደ 357 ከፍ ሊል ችሏል ።[14]

በቅርቡ የተደረጉ ግምገማዎች እንደሚያሳዩት ፣ የአምራች ማኅበራትን እንቅስቃሴ ለማፋጠን የሚደረገው ጥረት ግቡን እንዳይመታ ከሚያደርጉ ችግሮች አንዱ ያለው የሰው ኃይል የሙያ ብቃት ማነስ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚታየውን ችግር ለማቃለል በተደረገው ጥረት 706 ሙያተኞች ሠልጥነው ወደ ሥራ ተሰማርተዋል ። እንዲሁም እስከ ዛሬ ድረስ 832 የማኅበራት አባላት በኅብረት ሥራ ትምህርት ሠልጥነዋል ።

አምራች ማኅበራት ኃይላቸውን ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በማቀናጀት የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን በማቋቋም አኳያ የማይናቅ አስተዋፅኦ እያደረጉ ናቸው ። ከዋናው መንገድ የሚያገናኝ መንገድ በመሥራት ፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ክሊኒክ በማቋቋም ፣ ትምህርት ቤት በመክፈት ፣ ለመጠጥ ውሀ የሚያገለግል ጉድጓድ በመቆፈር ፣ ወዘተ — ተሳታፊና ከጥቅሙም ተካፋይ የሆኑት አምራች ማኅበራት ቁጥር ድምር ከ331 በላይ ነው ።

ማኅበራቱ ይበልጥ እንዲጠናከሩና ለሌሎች አርአያ ለመሆን እንዲበቁ ፣ ለአብዮቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ፣ ከአካባቢው ገበሬዎች የተሻለ ምርት ያመረቱ፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የምርት ጥራታቸውን ያሻሻሉ ፣ ዕቅዳቸውን በተግባር የተረጐሙ ፣ ወዘተ — 33 የበቁና የነቁ አምራች ማኅበራት በ1973 አሸናፊ ሆነው በጠቅላላ ከ124,000 ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ ሽልማት አግኝተዋል ።

የአካባቢ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ለልማት አመቺ ሆነው ሳለ ድርጅታቸውን ለማንቀሳቀስ አቅም ላነሳቸው አምራች ማኅበራት የአጭርና የረጅም ጊዜ ብድር በአነስተኛ ወለድ ፣ በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ከባንክ አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ፣ ወዘተ ... ምንጮች ብድር የሚጠይቁና የሚያገኙ ማኅበራት ቁጥር በየዓመቱ እያደገ በመሄድ ላይ ነው ። 300 አምራች ማኅበራት 864,713 ብር ከአካባቢአቸው የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በጥሬ ገንዘብ ብድር አግኝተዋል ። ከባንክና ከሌላ ምንጭ ብድር ያገኙ ማኅበራት ብዛትም 34 ይሆናል ።

አምራች ማኅበራት በራሳቸው የሰው ኃይል ሊወጡት ያልቻሉ የሥራ ዘርፍ የሒሳብ አያያዝና የመዛግብት አጠባበቅ በመሆኑ በየጊዜው ጥራት ባለው መንገድ ያልተያዘን ሒሳብ መመርመር ረጅም ጊዜ እና ከፍተኛ የሰው ኃይል የሚጠይቅ ቢሆንም በ1974 ሒሳባቸው የተመረመረላቸው ማኅበራት ቁጥር 107 ደርሶአል ። የምርመራውን ተግባር ለማሻሻል በ1974 ለሒሳብ ሠራተኞች ሴሚናርና የአጭር ጊዜ ትምህርት ተሰጥቷል ።

የአምራች ማኅበራትን እንቅስቃሴና የእንቅስቃሴያቸውን ውጤት ለመገምገም የተደረጉ ጥረቶች እንደሚያመለክቱት የአንድ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር አማካይ ሁኔታ ከዚህ በታች በቀረበው አኳኋን ሊገለጽ ይችላል ።

የማኅበሩ አባላት 37

የማኅበሩ የተጣራ የዓመት ገቢ 47,013 ብር ፣ ከዚህ ውስጥ ለአባላት የደተመ

Digitized by Google

በው 32,909 ብር ፣ ለምርት ሥራ የተመ ደበው ከቀሪው 60% ወይም 8,462 ብር ፣ ለመጠባበቂያ የተመደበው ከቀሪው 25% ወይም 3,526 ብር፣ለማኅበራዊ ኑሮ የተመ ደበው ከቀሪው 13% ወይም 1,833 ብር ፣ ለሽልማት የተመደበው ከቀሪው 2% ወይ ም 282 ብር ፣ የአንድ አባል አማካይ የዓመት ገቢ 889 ብር ይሆናል ።

በዚህ አኳኋን የገበሬዎች አምራቾች ኅብ ረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋፋትና ለማጠ ናከር የሚደረገው ጥረት የሚያበረታታ ቢሆ ንም ፣ በአንፃሩ ደግሞ ጉልህ ድክመቶች የሉም ማለት አይደለም ። ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓአኮ ሁለ ተኛ ጉባዔ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ እንደገለጹ ት ፣ «---ስለ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበ ራት መደራጀት ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመ ሆኑ ገና ቁጥራቸው ይህን ያህል ባልተበራ ከተበት ወቅት ማኅበራቱን በብድር ፣ በቁሳ ቁስና በሌሎችም አስፈላጊ መንገዶች ለመ ደገፍ የሚደረገው ጥረት ለዚህ ተግባር ከተ ሰጠው ተቀዳሚነት ጋር የሚመጣጠን ነው ለማለት ያዳግታል ።»

የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅ በራትን በሚመለከት የሚያጋጥሙ ችግሮች በርካታ ናቸው ። ያንዳንድ አምራች ማኅበ ራት አመሠራረት በጥናት ላይ የተመሠረ ተና መመሪያን የተከተለ አይደለም ። በዚህ አኳያ ፣ አንዳንድ አምራች ማኅበራት ፣ ቁጥር ለማብዛት ሲባል ፣ በተለያዩ ገሬቶች ፣ በገ ብታዊነት በመቋቋማቸው ችግር ስለፈጠሩ እነሱን ለማስተካከል አዲስ ማኅበራትን ከማቋቋም የበለጠ ጥረት የሚጠይቅ ሆኗል።

የአባላት የሥራ ምርታማነት የሚወስነው በሰው ኃይልና በምርት መገልገያዎች ልዩ ልዩ ክፍሎች ትንብር ሲሆን ፣ ከነዚህ የአ ንዱ መጉደል ወይም አለመመጠን የአባላ ትን የሥራ ምርታማነት ውሱን እንደሚያ ደርገው ግልጽ ነው ። በ1974 በተለያዩ ቦታ ዎች ከተካሄዱት የአምራች ማኅበራት ግም ገማዎች ለመረዳት እንደተቻለው ፣ በአንዳ ንድ ማኅበራት የሥራ መስክ የተሰማራው የሰው ኃይል ፣ የበሬ ጉልበት ፣ የእርሻ መሬት ስፋት ትንብር የተዛባ ነው ። ለምሳሌ ፣ በአ ንድ ማኅበር ውስጥ 232 የሰው ኃይል፣ 29 ጥማድ በሬዎችና 318 የእርሻ መሬት እን ደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል ። በአማካይ የአ ካባቢ ሁኔታ በአንድ የሰው ኃይልና በአንድ ጥማድ በሬ ሊከናወን የሚችለው የመሬት ስፋት 2.5 ሄክታር እንደሆነም ይገመታል። ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ከዚህ አንፃር ሲታ ይ የሰው ኃይልና የእርሻ በሬዎች እጥረትም መኖሩ የሚታወቅ ነው ። በዚያ አምራቾች ማኅበር ውስጥ አብዛኛው ሥራ የተከናወነው በኪራይ በትራክተርና ከአካባቢ በተገኘ የጉ ልበት ድጋፍ በመሆኑ አባላቱን ለስንፍና ከመጋበዙም ሌላ እርዳታው በድንገት ቢቋ ረጥ ማኅበሩን አደጋ ላይ እንደሚጥለው መገመት አያስቸግርም ።

በአንዳንድ ሌሎች ማኅበራት ደግሞ የመ ሬት ጥበት ጉልቶ ይታያል ። ለምሳሌ የአ ንድ ማኅበር የአባላት ብዛት 58 ፣ የጥንድ በሬ ብዛት 19.5 ፣የመሬት ስፋት በሄክታር 33 ሆኖ ተገኝቷል ። ይህም የአንድን አባል አማካይ የእርሻ መሬት ድርሻ ወደ ግማሽ ሄክታር ዝቅ ያደርገዋል ።

አሁን ያለውን የአምራች ማኅበራት ብዛ ትና በየጊዜው እንደ እንጉዳይ የሚፈላው ንም የቁጥር እድገት ለመከታተልና ትክክ ለኛ ፈር ለማስጨበጥ ያለው የሰው ኃይል

Digitized by Google

ሊቋቋመው ካለመቻሉም ሌላ ፥ በሌሎች የሥራ መስኮች ያሉትን ቦታዎች ለመሸፈንና ለባለሙያዎችም የደረጃ እድገት ለመጠበቅ ሲባል ችሎታና የሥራ ልምድ ያላቸው የግደራጃ ኤክስፐርቶች የሠለጠኑበትን የሥራ መስክ እየለቀቁ በቦታቸው በቂ ችሎታና የሥራ ልምድ የሌላቸው ሠራተኞች እንዲተኩ በመደረጉ ያለውን የሠራተኞች እጥረትና የጥራት ዝቅተኛነት እያባባሰው በመሄድ ላይ ነው ።

የአምራች ማኅበራት የተጠነሰሱት በአድኃሪው ሥርዓት ጭቁን በነበሩ ገበሬዎች እንደመሆኑ ፥ በክልላቸው ውስጥ ያለውን የሰው ኃይል ከማሰባሰብ በስተቀር የሌላቸውን የማምረቻ መሣሪያዎች ለማሟላትና ሥራውን በትክክል ማካሄድ ከመዋጮ የተገኘው ገቢ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በየዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን ምርት እጅግ ዝቅ ስለሚያደርገው ብዙ ማኅበራት የገድ እርዳታ ጠባቂዎች ይሆናሉ ።

የሥራ አፈጻጸም ድርሻ ለማሟላት ሲባል ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ በግብታዊነት የሚቋቋሙት ማኅበራት ለክትትል አመች ባለመሆናቸው በአደራጆች ላይ ተጽዕኖ ከማድረሱም በላይ የማኅበራትን መሠረተ ሃሳቦች ሊያናጋ የሚችል ነው ።

የተሻለ ዘዴ ተከትለው ማምረት የጀመሩ ጠንካራ ማኅበራት ለረጅም ጊዜ ሊቀመጡ የማይችሉ ምርቶችን ፥ ለምሳሌ አትክልትና ፍራፍሬ የሚያመርቱ ማኅበራት ፥ የእንስሳትና የእንሰሳት ተዋጽኦ አምራች ማኅበራት ወዘተ ... ለምርታቸው ትክክለኛ ዋጋ እና ወቅታዊ ገበያ ባለማግኘታቸው በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ ከመገደዳቸውም አልፎ አንዳንዴ ምርት ለብልሽት ተጋልጦ ይባክናል።

አምራች ማኅበራት የገንዘብና የገንዘብ ነክ የሆኑ ልውውጦች እንደሚያደርጉ ሁሉ ሥራ ለማንቀሳቀስና የተለያዩ ገቢዎችን በሥርዓት ለመያዝ ንብረቶችንም ለመቆጣጠር መደበኛ ሠነዶችና መዛግብት ኖረዋቸው በመዛግብቱና በሠነዶቹ ለመጠቀም በቂ እውቀትና ልምድ ይጠይቃል ። በዚህ አኳያ ገበሬዎች ያላቸው የሥራ ልምድና እውቀት አነስተኛ በመሆኑ በማኅበራት አስተዳደርና አመራር ድክመቶች ይታያሉ።የአምራች ማኅበራት የሥራ አመራር አካላት ጠቅላላ ጉባኤ ፥ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ፥ ቡድን ፥ ወዘተ ... ሲሆኑ ፥ እነዚህ አካላት በተግባር በሚሠማሩበት ጊዜ ከልምድና ከትምህርት ማነስ የተነሳ አንዱ አካል የሌላውን ሥራ አልፎ ሲሠራ በመገኘት ሥራው ሲበደል ይታያል ። ይህ የሥራ ክፍፍል ሥርዓት ባለመያዙ የንብረት መባከንና መዝረክረክ ይታያል ። [16]

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም ችግሮችና ድክመቶች በየጊዜው በሚደረግ የግ ያጽርጥ ጥረትና በሚገኘው የሥራ ልምድ እየታረሙና እየተስተካከሉ ፥ እንደሚሄዱ ይጠበቃል ። ሆኖም ለችግሮቹ መፍትሔ ለማግኘት የሚቻለው የሚመለከታቸው የመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም አብዮታውያን ግለሰቦች ሁሉ በዚህ አንፃር ኃላፊነታቸውን ሲወጡና ጥረታቸውን ሲያጠናክሩ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ጓድ ሊቀመንበር በኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ላይ እንደገለጹት ፥ «በአጠቃላይ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋፋትና ያሉትንም ለማጠናከር ካለፈው ልምዳችን በተጨባጭ የተገነዘብነው ለማኅበራቱ ማበብ በመፈከር ደረጃ የምናሰግውን ድጋፍ ወደቁሳዊ ኃይልነት (ተግባራዊነት) ለመለወጥ በጣም ከፍተኛ የሆነ ትግል የሚጠብቀን መሆኑን ነው ።» [17]

Digitized by Google

መወሰድ ካለባቸው እርምጃዎች መካከል ጥንስስ የሆኑ ወይም የተደራጁ ማኅበራት ሳይንሳዊ ፈር ይዘው እንዲያድጉ ማድረግ አንዱ ነው ። ከዚህ አንፃር ያሉትን አደራጆች በተጨማሪ ማሠልጠን፣ በቂ የኅብረት ሥራ ማኅበር ማሠልጠኛ ተቋሞች በማቋቋም የበቁ የነቁ ሠራተኞችን እያሠለጠኑ ማውጣት ፣ ግብረ ኃይላትን ማጠናከር፣ወዘተ... ያስፈልጋል ። የኅብረት ሥራ ማኅበር ባለሙያዎች ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ተከፍቶ ሥራውን በቅርቡ መጀመሩ በዚህ ረገድ የሚያበረታታ ነው ። በዚህ ትምህርት ቤት የገበሬዎች ፣ የዕደ ጥበብ እና የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ይደረጋል ። ይህም የሰው ኃይል እጥረትንና የጥራትን ችግር ለመፍታት እንደሚረዳ ይጠበቃል ።

አባላት በአብዛኛው ከራሳቸው ጉልበትና መሬት በስተቀር አንድ ጥማድ በሬ እንኳን የሌላቸው በመሆኑ የአነስተኛ ወለድ ብድር ድጋፍ እንዲያገኙ ቢደረግ የማምረቻ መሣሪያቸውን በማሟላት ምርታማነታቸውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሳደግና ወደ ተሻሻለ ቴክኖሎጂ ለመሸጋገር አመቺ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ።

ስለመሬት ምርታማነትና የተፈጥሮ አቀማመጥ ጥናት እየተደረገ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም አመቺ የሆነውን እየከለሉ ማደራጀትና ሲያስፈልግም ሰፊ መሬት ወደ ሚገኝበት ማዛወር ያስፈልጋል ።

ለገበያ ችግር ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት፣ የዋጋ ተመን ቁጥጥርን ማጠናከር፣የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማጠናከር ፣ የነጋዴዎችን ጣልቃ ገብነት እንዲቆም ማድረግ ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት በተለይም በቀላሉ ብልሽት የሚደርስባቸው ምርቶችን—ወተት ፣ ፍራፍሬ ፣ አትክልት ፣ ወዘተ....የሚያመርቱ ማኅበራት የተለየና የቅርብ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል ።

የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ገበሬው በተለይ ምርቱን ለገበያ አቅርቦ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸጥና የሚፈልጋቸውንም ሸቀጣሸቀጦችና ብድር በተቀነባበረ መልክ እንዲያገኝ በማድረግ ሊጫወቱ የሚገባቸው ሚና ከፍተኛ ነው ። በአሁኑ ጊዜ የገበሬዎች አገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት 3,651 ሲሆን እነዚህ ያቀፏቸው የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ብዛት ደግሞ 16,113 ነው ። የተመዘገቡ የገበሬዎች የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት 593 ደርሷል። የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በአጠቃላይ ያላቸው ካፒታል 91,114,981 ሲሆን፣የሚሰጡት አገልግሎት ተጠቃሚ ሕዝብ ብዛት 4,610,426 ነው ። የአገልግሎት ማኅበራቱ ለአምራቾች ማኅበራት የሚሰጡት ከፍተኛ የብድር ድጋፍ ከዚህ በላይ የተጠቀሰ ሲሆን ፣ ለአርሶ አደሩ ሕዝብ በአጠቃላይ የሚሰጡት የሸቀጥ ስርጭት አገልግሎት የማይናቅና እያደገ በመሄድ የሚገኝ ነው ።

ሆኖም እንደ አምራቾች ማኅበራቱ ሁሉ የአገልግሎት ማኅበራቱም ችግሮች ያሉባቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። በተለይ የሂሳብ አያያዝ ችግር እጅግ ጉልቶ የሚታይ ነው ።

የማኅበራት ጥራትና ጥንካሬ አንዱ መመዘኛ የሂሳብና ንብረት አያያዝ ሲሆን ጥናት በተደረገባቸው ማኅበራት የሂሳብ አያያዙ እየተሻሻለ መምጣቱን ቢያመለክትም የገንዘብና የንብረት መባከኑ ሁኔታ ከፍተኛ መሆኑ ታውቋል ። የማኅበራት ሂሳብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መመርመር የሚገባው ቢሆንም፣የአብዛኞቹ ማኅበራት ሂሳብ ለብዙ ዓመታት ሳይመረመር ቆይቷል ። ከ3,603 (ያሁኑ ቁጥር 3,651 ነው) የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ ሂሳባቸው የተመረመረው ማኅበራት ቁጥር 562 ብቻ ነው።በ1973 እና 1974 ሂሳባቸው ከተመረመረላቸው 562 ማኅበራት ውስጥ 1.83 ሚሊዮን ብር ጉድለት መገኘቱ በዚህ አንፃር ከፍተኛ ችግር መኖሩን ይጠቁማል ። [18]

Digitized by Google

የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራት

በሀገራችን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ለኅብረተሰቡ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ፣ ልብሶችን ፣ የእርሻና የጦር መሣሪያዎችን እንዲሁም የጌጣጌጥ እቃዎችን እየሠሩ በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል ። ሆኖም ያለፈው አድኃሪ ሥርዓት በዕደ ጥበብ ሙያ ላይ የተሰማሩትን ሁሉ የሚንቅ ፣ የሚያራክስና የሚያወግዝ ስለነበረ ምንም ዓይነት ድጋፍ አይሰጥም ነበር ።

በአብዮቱ ዓመታት ፣ በተለይም የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር መመሪያ ከወጣ ከ1971 ጀምሮ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ማኅበራት በመቋቋም ላይ ይገኛሉ ። የዕደ ጥበብ አምራች ማኅበራት በተሻሻለ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለምርት ዕድገት አስተዋጽኦ ከማበርከታቸውም በላይ ቀስ በቀስ እያደጉ ወደ አነስተኛ እንዱስትሪዎች በመለወጥ የሶሻሊስት ኤኮኖሚ መሠረት የሆነውን ከባድ እንዱስትሪ ለማቋቋም ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ። የነዚህ ማኅበራት መስፋፋት የከምችትን ማሳደግ ብቻ ሳይንሆ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን መዳበር ለማፋጠን እንደሚረዳ የታወቀ ነው ።

መመሪያው ሥራ ላይ ከዋለ ጀምሮ እስካሁን ድረስ 3,133 አባላትን ያቀፉ55 አምራች ማኅበራት የተመዘገቡ ሲሆን ካፒታላቸውም 56 ሚሊዮን ብር ያህል መድረሱ ታውቋል ። እንዲሁም ባሁኑ ጊዜ ተደራጅተው የሚገኙ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥር 776 ደርሷል ። ቁጥራቸው 831 የሆነው የአምራቾችና የአገልግሎት ማኅበራት በጠቅላላ 48,636 አባላትን ያቀፉ ሲሆን ያላቸው የተጣራ ካፒታልም 24 ሚሊዮን ብር እንደሆነ ታውቋል ።

ማኅበራቱን ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንዱ ካለው አጠቃላይ የቤት እጥረት አንፃር ለምርት ተግባር ተስማሚ የሆኑ ሕንጻዎችን ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱ ነው ። ችግሩን ለመወጣት ማኅበራት የራሳቸውን የማምረቻና የመገበያያ ቤቶች እንዲሠሩ ቅስቀሳና ትምህርት እየተሰጠ ነው ። የማኅበራት ካፒታል ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እያለ ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ በሕንጻ ላይ ማዋሉ ተገቢ ባይመስልም ያለውን የቤት እጥረት ችግር ከመወጣት አንጻር አስፈላጊነቱ አያጠራጥርም ። በመሆኑም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1974 ድረስ 305 አምራች ማኅበራት 7.9 ሚሊዮን ብር በሕንጻዎች ሥራ ላይ ያዋሉ ሲሆን፣ 356 ማኅበራት በዓመት 335,736 ብር በመክፈል በኪራይ ቤቶች ይጠቀማሉ ። የቀሩት 170 ማኅበራት በጥገኝነትና በቤት ችግር ላይ የሚገኙ ናቸው ።

በሂሳብ ረገድ በ1973 እና በ1974 የተካሄደው የሂሳብ ምርመራ ውጤት ማኅበራቱ በአጠቃላይ ካፒታላቸውን እያሳደጉ መምጣታቸውን ያመለክታል ። ማኅበራቱ ገንዘባቸውን ባንክ እንዲያስቀምጡና እንዲያንቀሳቅሱ የማድረጉ ቅስቀሳ እየተካሄደ በመሆኑ ባሁኑ ወቅት 410 ማኅበራት በባንክ አገልግሎት ይጠቀማሉ ።

ምንም እንኳ ማኅበራት ከፍተኛ የፋይናንስ ችግር ቢገጥማቸውም በ1974 ውስጥ 43 ማኅበራት የ2.38 ሚሊዮን ብር ብድር ጠይቀው 34 ማኅበራት 1.5 ሚሊዮን ብር የባንክ ብድር አግኝተዋል ።

በ1973 43 ማኅበራት ባወጡት ዕቅድ መሠረት 9.6 ሚሊዮን ብር ያህል የሚያወጣ ምርት አምርተዋል ። በ1974 ፣ 51 ማኅበራት በእቅድ ታቅፈው 15 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ምርት ተገኝቷል ። ይህም የእቅድ አሠራር እየዳበረ መሄዱን ያመለክታል ። ማኅበራቱ እንቅስቃሴአቸውን ለማጐልበት ይችሉ ዘንድ ለምርት ለገበያ ተስማሚ በሆኑ አካባቢዎች ቦታ እየተመረጠ ሊሰጣቸው ይገባል ። ካፒታላቸው ለምርት ማስፋፊያ ተግባር በማዋል ፈንታ ለቤት መሥሪያ እየ

Digitized by Google



ቦሌ ብረታብረት የእጅ ጥበብ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በሥራ ላይ እንዳሉ

Digitized by Google

ዋለ እድገታቸውን ስለሚገታ ፥ አብዮታዊው መንግሥት ለማኅበራቱ የማምረቻ ቤቶችን እየሠራ የሚያከራይበትና የኢንዱስትሪ መንገዶችንም በማቋቋም ለማኅበራት በረዥም ጊዜ ክፍያ የሚሰጥበት ዘዴ ቢቀየስ ለችግሩ መፍትሔ ይሆናል የሚል ግምት አለ ።

ማኅበራት ካጋጠማቸው ችግሮች አንዱ ጥሬ ዕቃ በሚፈለገው መጠን አለመገኘት በመሆኑ ፥ ቢያንስ ያለውን ወገናዊ በሆነ መንገድ ለማኅበራት በቅድሚያ እንዲከፋፈል ማድረግ ይገባል ።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 1974 የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማስመልከት ባቀረቡት ሪፖርት ፦

—የግብርናው ዘርፍ ጠቅላላ የምርት ውጤት ዝቅተኛነት የሚመነጨው ከሚታረሰው መሬት ጥበት ሳይሆን ከእያንዳንዱ ሄክታር የሚገኘው የምርት ውጤት መጠን ማለትም የገበሬው ምርታማነት ዝቅተኛ መሆኑን ፥

—ገበሬው የሚጠቀምባቸውን እጅግ ኋላ ቀር የሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎችና የአመራረት ዘዴዎች ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ፥

—የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችና የተሻሻሉ የግብርና ዘዴዎችን በማስተዋወቅ የቴክኖሎጂ ለውጥ ማስፈለጉን ፥

—በተበታተኑ ግለሰብ ገበሬዎች ጥረትና በአማካይ ከሁለት ሄክታር በማይበልጥ እርሻ ላይ የቴክኖሎጂን ለውጥ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ፥

—የቴክኖሎጂ አብዮትን ለማራመድና ለኢንዱስትሪ መስፋፋት ጠንካራ መሠረት ለማስገኘት የተበታተነው የገበሬ እርሻ ወደሰፋፊ የኅብረት እርሻ የሚለወጥበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ፥

—በዕደ ጥበቡ ዘርፍም የማምረቻ መሣሪያዎች እጅግ ኋላቀር ከመሆናቸውም በላይ በምርት አደረጃጀት ረገድ በግላዊ ጥረት ላይ የተመሠረተና የተበታተነ በመሆኑ እድገት ለማስገኘት ያለው ዕድል የተወሰነ መሆኑን ፥

—የዕደ ጥበብ ማኅበራት ጥሬ ዕቃ በማግኘት ረገድ ከፍተኛ ችግር ያለባቸው መሆኑን ፥

—ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር የምናደርገው የሰው ኃይል ፥ የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ ለእድገታቸው ወሳኝ በመሆኑና እነሱን ለማቋቋምና ለማጠናከር ያልተቋጠበ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት ስላለብን ፥ ለዚሁ ግብ የፋይናንስ ድጋፍ አሰጣጥ ፖሊሲያችንን ማሻሻል ያለብን መሆኑን ፥

በመግለጽ ችግሮቹንና መፍትሔዎቹን በሚገባ አመልክተዋል ።

በአጠቃላይ ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነቶችን የበላይነት በኢኮኖሚያችን ውስጥ ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስብስብ ችግሮች ያጋጠሙ ቢሆንም እስካሁን የታየው እንቅስቃሴም የሚያበረታታ ነው ለማለት ይቻላል ። ባለፉት የአብዮት ዓመታት ለሶሻሊስት ግንባታ መሠረት የሆኑ ፖለቲካዊ፥ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮችን ለመዘርጋት ከፍተኛ ትግል ተካሂዷል ፤ ከፍተኛ ድሎችንም ተጎናጽፈናል ። ከተገኙት ከፍተኛ ውጤቶችም አንዱ ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ የሠርቶ አደር ፓርቲን የሚያደራጅ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) በታህሣሥ ወር 1972 መከሰቱ ነው ። ኢሠፓአኮ ለሠርቶ አደሮች ፓርቲ ምሥረታ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ከማከናወን ጋር ሐቀኛ ታጋዮችን እያሰባሰበ ወቅታዊ የፖለቲካ አመራር በመስጠት ለሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መስፋፋት ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ነው። በተለይም ኢሠፓአኮ በማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባውና በ2ኛ ጉባኤው አማካኝነት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ፥ ለኢንዱስትሪ እድገትና ለምርት ኃይሎች መዳበር ወሳኝ

Digitized by Google

ነት ያላቸው የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች በኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን መመሪያዎችና ውሳኔዎች አሳልፏል። በመመሪያዎቹና በውሳኔዎቹ መሠረትም የሚታየው እንቅስቃሴ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ።

አብዮታችን ከተቀሰቀሰ ጀምሮ ፣ በአብዮታዊው መንግሥትና በኢሠፓአኮ አመራር የሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ለማስፋፋት በየዘርፉ የተፈጠሩት አመቺ ሁኔታዎች ፣ የተወሰዱት እርምጃዎችና የተከናወኑት ተግባሮች ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታችን የማይናወጽ መሠረት እየጣሉ ነው ። ይህም ሂደት ነገ የማሌ ፓርቲአችን ሲመሠረት በበለጠ እየተጠናከረና እድገቱም እየመጠቀ የሚሄድ መሆኑ አያጠራጥርም ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. *Great Soviet Encyclopedia*, Volume 19, Macmilan, INC., New York 1978, "Transition Period", pp. 709-710.
2. G.A. Kozlov, Gen. ed., *Political Economy: Socialism* (Moscow, 1977), pp. 17-23.
3. ኅብረተሰብአዊነት — የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ፣ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መመሪያ ፣ አዲስ አበባ ፣ ታኅሣሥ 11 ቀን 1967 ፣ ገጽ 10
4. የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኤኮኖሚ መመሪያ ፣ አዲስ አበባ ፣ ጥር 30 1967 ፣ ከገጽ3—6 ካለው የተወሰደ
5. ከብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ለአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ የግብርና ክፍለ ኤኮኖሚን በሚመለከት ከተዘጋጀው ያልታተመ ጽሑፍ ፣ በገጽ 16—17 ካለው የተወሰደ
6. የብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ መመሪያ ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የሦስተኛ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ፣ ክፍል 1 ታኅሣሥ 1974 ፣ ገጽ 90 የዘመቻው የአራተኛው ዓመት ዕቅድ ፣ ገጽ 50
7. <u>የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የሦስተኛ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ፣</u> ክፍል 1 ፣ ታኅሣሥ 1974 ፣ ገጽ 102—107 ፣ 116 — 119
8. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ሠነዶችና ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 130
9. *Georgi Galperin, Ethiopia: Population, Resources, Economy,* (Moscow: Progress Publishesrs,), 1981, p. 203.
10 የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ሠነዶችና ውሳኔዎች ፣ ገጽ 52
11. ከብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባሕል እድገት ዘመቻ በጥር 1975 የተገኘ
12. የትራንስፖርትና የመገናኛ ክፍለ ኤኮኖሚ የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ ፣ የትራንስፖርትና የመገናኛ ግብረ ኃይል ሰኔ 1974 (ያልታተመ) ገጽ 12—42
13. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ሠነዶችና ውሳኔዎች ፣ ገጽ 63
14. አዲስ ዘመን ፣ጥር 8 ቀን 1975 ፣ ገጽ 2
15. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሠነዶችና ሳውኔዎች ፣ ገጽ 49
16. ከግብርና ሚኒስቴር የኅብረት ሥራ ማኅበር መምሪያ የተገኘ ፣ መስከረም 1975 ከተጻፈ ጥናት የተውጣጣ
17. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ሠነዶችና ውሳኔዎች ፣ ገፅ 49
18. የግብርና ልማት 10 ዓመት መሪ ዕቅድ (1976-85) እትም 2 የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዝርዕትና ቋሚ ሰብል እርሻ ልማት ፣ ክፍል 1 ግምገማ ዓላማና ስልት ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ ሐምሌ 1974
19. ከአዕማድ የመስከረም 1975 ሪፖርት የተውጣጣ

Digitized by Google

የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ

— ንሴብሆ ይፍሩ

ንግድ፣ አምራቾች ያመረቱትን ምርት ለገበያ የሚያቀርቡበት ፣ ሸማቹም ለዕለት ኑሮው የሚያስፈልጉትን ሸቀጦች የሚሸምትበት ፣ የሀገር ውስጥ ምርት ፍላጐትን ለመሸፈን ባልተቻለበት የሸቀጥ ዓይነት ከውጭ በማስመጣት ለገበያ የሚቀርብበት መድረክ ሲሆን በአምራችና በሸማች መሀል እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል የኢኰኖሚ መስክ ነው ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ንግድ መደባዊ ባሕሪ አለው ። የምርት መገልገያዎች በግል ይዞታ ሥር በሆኑበት የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ንግድ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ነው ። በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የምርት መገልገያዎች በማኅበራዊ ይዞታ ሥር ስለሆኑ ንግድ የኅብረበሰቡ የዕለት ተዕለት ኑሮው ፍላጐት ማርኪያ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ።

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የምርት መሠረታዊ ዓላማ የሰውን ፍላጐት ለማርካት ሳይሆን ለማምረቻ መሣሪያ ባለቤት ለሆነው የካፒታሊስት መደብ ከፍተኛ የሆነ ትርፍ እንዲያገኝ ማስቻል ነው ። ካፒታሊስቱ ትርፍ ለማግኘት የሚችለው ደግሞ በምርት እንቅስቃሴ ውስጥ በወዝአደሩ የሥራ ኃይል የሚፈጠረውን ተረፈ እሴት በምርት መገልገያ መሣሪያዎች የግል ባለቤትነት በመጠቀም በግል ለማጋበስ በመቻሉ ነው ። እንደሚታወቀው የካፒታሊስቱ መደብ በተለያዩ ክፍሎች የተከፈለ እንደመሆኑ፣ ሸቀጦችን ወደ ገንዘብ በመለወጥ ቀደም ሲል በወዝአደሩ የሥራ ኃይል የተፈጠረውን ተረፈ እሴት ወደ ትርፍ ገንዘብ የመለወጡ ሚና የሚወድቀው በንግድ ካፒታሊስቱ ላይ ነው ።

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር የምርት ተግባር ግብታዊ ስለሆነ የሚመረተው ምርትና የኅብረተሰቡ የሸመታ ፍላጐት እም

Digitized by Google

ብዛም የተጣጣመ አይደለም ። ይህም ብዙ ጊዜ በጠቀሜታ እሴትና በእሴት መካከል ለሚፈጠረው ቅራኔ አንዱ ምንጭ ነው ።

የሶሻሊስት ምርት በዕቅድና በነቃ ተግባር የሚከናወን ስለሆነ በኅብረተሰቡ ወቅታዊና የወደፊት ፍላጐት ላይ የተመሠረተ ነው ። በዚህም ምክንያት ሶሻሊስታዊ ንግድ ከካፒታሊስቱ ንግድ የተለየ ይሆናል ።

በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ማምረት የተለየ ዓላማ አለው ። የማምረት ዓላማ የሰውን ማቴሪያላዊና ባህላዊ ፍላጐቶችን ማሟላት ነው ። ዓላማው በየጊዜው እያደገና እየሰፋ የሚሄደውን የሰውን ልጅ ፍላጐት ለማሟላት መጣር ነው ። የምርት መገልገያዎች የኅብረተሰቡ ስለሚሆኑ ፣ በዝበዥና ተበዝባዥ መደቦች የማይኖሩበት ሥርዓት ስለሚሆንና ምርት የሚመረተው የሰውን ልጅ ፍላጐት ከማርካት አንጻር ስለሚሆን በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚካሄደው ንግድ በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ከሚካሄደው ንግድ በዓይነት ይለያል ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ንግድ የሚካሄደው በመንግሥታዊና በሕዝባዊ ድርጅቶች አማካኝነት ነው ። የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማ የሶሻሊስት ኤኰኖሚ በማጠናከር የሕዝቡን ፍላጐት በተቻለ መጠን ለማሟላት መጣር ስለሆነ በነዚህ ተቋሞች የሚካሄደው ንግድ ተገቢ ያልሆነ ትርፍን የማካበት ዓላማ የለውም ። ከነዚህ ድርጅቶች የሚገኘው ትርፍ የመንግሥት ክምችት አቋምን በማጠናከር መልሶ የኅብረተሰቡን የጋራ ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችል እንጂ የግለሰቦችን ጥቅም የሚያስከብር አይደለም ።

ከሶሻሊስት ኤኰኖሚ ሕግጋት መካከል በዘርፍ ኤኰኖሚዎች መካከል የተመዛዘነና የተጣጣመ ዕድገት መኖር አንዱ ነው። ስለሆነም ሶሻሊስታዊ ንግድ ከሌሎች ክፍለ ኤኮኖሚዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። በኢንዱስትሪና በእርሻ ዘርፍ መደረግ የሚገባውን እንቅስቃሴ ለመወሰን ተጨማሪ መረጃ የሚያስገኝ ፣ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ሊውል የሚችል ክምችትን የሚያስገኝና ማኅበራዊ የሆኑ ችግሮችን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ።

ሶሻሊስታዊ ንግድ ካሉት ዓላማዎችአንዱ የኅብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የተቀራረበ ማድረግ ስለሆነ በከተማውና በገጠሩ ነዋሪ መካከል ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ልዩነት እንዳይኖር ለመቆጣጠር ይረዳል ።

በሀገራችንም አብዮታችን ከፈነዳ ወዲህ አብዮታዊ መንግሥት ሰፊውን ሕዝብ ከብዝበዛ ለማዳንና መብቱን ለማስከበር በወሰዳቸው እርምጃዎች በአንድ በኩል የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ፣ የማከፋፈያና የማምረቻ ድርጅቶች ፣ ባንኮችና የመድን ድርጅቶች ወዘተ ... በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የንግዱን ዘርፍ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በንግዱ ዘርፍ እንዲስፉ አድርጓል ።

በውጭ ንግዱ ዘርፍ ከአሁን በፊት በግል ነጋዴዎች ተይዞ የነበረውን ዕቃ የማስመጣትና የመላክ ተግባር አዲስ የተፈጠሩት መንግሥታዊ ድርጅቶች በሥራው ተሳታፊ በመሆን ደረጃ በደረጃ ያላቸውን የገበያ ድርሻ በማሳደግ እንዲተኩ ተደርጓል ።በሀገር ውስጥ የንግድ ዘርፍም እንዲሁ በሀገር ውስጥ በማምረቻ ድርጅቶች የሚመረተውና ከውጭ ሀገር የሚመጣውን የኢንዱስትሪና የእርሻ ምርት ውጤት በማከፋፈል በግል ነጋዴው ተይዞ የነበረውን የንግድ ሥራ ደረጃ በደረጃ መንግሥታዊ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ነው ። አንድን የምርት ውጤት ለተጠቃሚው ማድረስ መንግሥት ላቋቋማቸው የማከፋፈያ ድርጅቶች ብቻ የሚተው ተግባር ባለመሆኑም በከተማ የቀበሌና በገጠር የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበ

Digitized by Google

ራትን በማደራጀት ከአምራች እስከ ሸማች
የነበረውን የዕቃ ቅብብል ሰንሰለት በማሳ
ጠር በችርቻሮው ሥራ ላይ ሕዝባዊ ድር
ጅቶች እንዲሰማሩ ተደርጓል ። የችርቻሮ
ንግድ እጅግ ሰፊ በመሆኑም ሕዝባዊ ድር
ጅቶች ተጠናክረው ከግል ነጋዴው እጅ
እስከተረከቡት ጊዜ ድረስ የሚከሰተውን
ችግር ለመከላከያ መንግሥት በተለያዩና
በተወሰኑ ቦታዎች የችርቻሮ መደብሮች
በመክፈት አገልግሎት እየሰጠ ነው ። ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ ይቋቋማል ተብሎ ለሚጠበ
ቀው የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር
ጽኑ መሠረት ለመጣል በሚደረገውም
ጥረት የአዲስ አበባ መሠረታዊ ዕቃዎች
አቅራቢ ድርጅት መቋቋም እንደ ምሳሌ
ነት የሚጠቀስ ነው ።

የንግዱ ዘርፍ ሕዝባዊ ይዘት እንዲኖረው
በተወሰደው እርምጃ ጥቅማቸው የተነካባ
ቸው ከበርቴዎች ቀድሞ ሲያገኙት የነበ
ረው ገቢ እንዳይቋረጥባቸው ለማድረግ በን
ግዱ ሥራ ላይ መሰማራታቸው በእህሉም
ሆነ በኢንዱስትሪ ውጤቶች ንግድ ከፍተኛ
ክምችት በመያዝ ሰው ሠራሽ እጥረትን
ፈጥረዋል ። እነዚህ ግለሰቦች ተጠቃሚው
ዕቃዎቹን ለመግዛት በሚፈልግበት ወቅት
የተፈጠረውን እጥረት በመመርኰዝ ሊሸ
ከመው የማይችለውን ዋጋ በመጠየቅ ከገ
ቢው ጋር ሊጣጣም የማይችል ዋጋ እንዲ
ከፍል ያደርጉታል ፤ በአብዮቱ ላይ እንዲ
ያማርር ለማድረግ የሚያካሂዱትንም ፀረ-
አብዮት ትግል ተያይዘውታል ። ሆኖም
አዲስ በተቋቋሙት መንግሥታዊና ሕዝባዊ
ድርጅቶች እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት
በወጡ መመሪያዎች አማካኝነት በግል
ንግድ ላይ ቁጥጥር እንዲደረግ ፣ በዚህም
ሳቢያ በዋጋ በኩል ያለው መዋዠቅ በመ
ጠኑም እንዲረጋጋና ሕገወጥ ክምችት
በመፍጠር የሚፈጸመው ሰው ሠራሽ የም
ርት እጥረት እንዲቀንስ ለማድረግ የሚካ
ሄደው ጥረት እንደቀጠለ ነው ።

ንግድ በፀረ—አብዮተኞችም ሆኑ ጥቅማ
ቸው በተነካባቸው ግለሰቦች ዘንድ ከፍተኛ
የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ፍልሚያ የሚ
ካሄድበት የመጨረሻ የትግል መድረክ
በመሆኑ ፣ እጅግ በጣም የተወሳሰቡና የተ
ሳሰሩ ችግሮች ያሉበት የሥራ መስክ
ሊሆን በቅቷል ።

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የንግድ ሁኔታ

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ይካሄድ የነ
በረው የንግድ ሥራ ዓላማ ትርፍ በማካበት
ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ በአገር ውስጥ የሚ
መረቱትም ሆኑ ከውጭ አገር የሚመጡት
ሸቀጦች በሰፊው ሕዝብ ፍላጐት ላይ የተመ
ሠረቱ ሳይሆኑ በአብዛኛው የባለካፒታሉን
ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያገለግሉ ነበሩ ።
የማከፋፈያ አውታሮችም ገበያ በደራባ
ቸው ከተሞች ብቻ በመቋቋማቸው በገጠር
የሚኖረው ሕዝብ ለኑሮው የሚያስፈልጉ
ትን ሸቀጦች ተነፍጐ ቆይቷል ። ይህም
አሠራር በአንድ በኩል በመሀል አገር የተ
ዛባ የሥርጭት ሁኔታን ሲፈጥር ፣ በሌላ
በኩል ደግሞ የጠረፍ አካባቢ ኗሪዎች በመ
ሀል አገር ይካሄድ ከነበረው የንግድ ልው
ውጥ እንዲገለሉና በጐረቤት አገሮች ሸቀ
ጥና በነዚሁ አገሮች ገንዘብ ላይ እንዲያተ
ኩሩ አድርጓቸዋል ። አብዛኛው የወጪም
ሆነ የገቢ ንግድ የተያዘው በውጭ ሀገር ዜጐ
ችና በኢትዮጵያውያን የግል ነጋዴዎች በ
መሆኑ የመንግሥት ተሳትፎ ነበረበት ለማ
ለት አያስደፍርም ። በወቅቱም በነበረው
አሠራር ከውጭ ሀገር ለሚመጡና ወደ
ውጭ ሀገር ለሚላኩ ዕቃዎች ትክክለኛ ያል
ሆነ ሰነድ በማቅረብ ውድ የሆነውን የሀገሪ
ቱን የውጭ ምንዛሬ ሀብት በሥራው የተሰ
ማሩት ግለሰቦችና ድርጅቶች ያሸሹ እንደ
ነበር የሚታወስ ነው ። ይልቁንም አነስተኛ
የመነገጃ ካፒታል ይዘው ወደ ሀገር ውስጥ
በመግባትና በወቅቱ በነበረው ሁኔታ በመ

Digitized by Google

ጠቀም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች በመሰማራት በውጭ ሀገር ዜጐች ይደረግ የነበረው ብዝበዛ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነበር ።

የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓትን ፥ ግዴታና መብትን አጣምሮ እንዲይዝ ባለመደረጉ የንግድ ፈቃድ የትርፍ ማካበቻና ኅብረተሰቡን የመበዝበዣ መሣሪያ ሆኖ ቆይቷል። በንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ረገድ ግለሰቡ የሚሳተፍበት የንግድ ሥራ ዓይነት ፥ በመጠን ፥ በዘርፍና በካፒታል ገደብ ያልነበረው በመሆኑ ተደራራቢ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ነበር ። በተለይም የውጭ ዜጐችን በሚመለከት የእገዳ ፖሊሲ ስላልነበረ አብዛኛው የውጭ ንግድ ተይዞ የነበረው በውጭ ሀገር ዜጐች ነበር ። ይህ ሁኔታ የፊውዶ ቡርዥዋ አድኃሪ መንግሥት ይከተል ከነበረው የክፍት በር ፖሊሲ ጋር ተዳምሮ ፥ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት የሥራ ክፍፍል ሥር እንዲወድቅና ለኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተጋለጠ እንዲሆን አድርጐታል ። ይህም ከቀድሞው ሥርዓት የተወረሰው የተዛባና ለኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛ የተጋለጠ የንግድ ሁኔታ ፥ አሁን አብዮቱ የተያያዘውን ንግዱን የሶሻሊስት ፈር የማስያዝ ከባድ ትግል ይበልጥ ከባድና ውስብስብ እንዳደረገውና በዚያው ልክ ደግሞ ይህን የኤኮኖሚ ዘርፍ የመጨረሻ የመፋለሚያ ቦታቸው ላደረጉት ፀረ—አብዮት ኃይሎች አመች ሁኔታ እንደፈጠረላቸው የሚታወቅ ነው ።

ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ የንግድ ሁኔታ

ለሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ መሠረት ለመጣል የሚደረገውን ትግል ለማገዝ በሚችልበት መልክ የኢትዮጵያ አብዮት አቅጣጫ ትክክለኛውን ፈር እየያዘ ሲመጣና በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች መሠረታዊ ለውጦች ሲወሰዱ ፥ በንግዱም ዘርፍ በ1967 ቁልፍ የሆኑ የማከፋፈያና አስመጭ ድርጅቶች ወደ መንግሥት እንዲዛወሩ ተደረገ ። ይህ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ሲባል የተወሰደው አብዮታዊ እርምጃ የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሺያሊስታዊ ፈር ለማስያዝ መሠረት ሊሆን ችሏል ።

ለሸማቹ የተሟላና አመቺ የንግድ አገልግሎት ለመስጠትና የምርት ኃይሎችን ለማሳደግ በምርት ምንጮች በኩል ያለውን አሠራር በሶሻሊስታዊ ይዞታ ሥር ማዋል አስፈላጊ ስለሆነ ዋና ዋና የማምረቻ ድርጅቶች የመንግሥት ይዞታ እንዲሆኑ ተደርጓል ። ይህም በመንግሥታዊ ድርጅቶች መካከል ቀጥታ የሆነ የንግድ ግንኙነት ሊፈጥር በመቻሉ ለሶሻሊስት የሸቀጥ ልውውጥ መዳበር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ።

ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ እርምጃዎች በመመርኰዝ የውጭ ንግዱን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ በተደረገው ያላሰለሰ ጥረት በገቢም ሆነ በወጪ ዕቃዎች የመንግሥትን ተሳትፎ በማሳደግ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው በገቢ ንግድ እንደ እ.አ.አ. በ1974% የነበረው የመንግሥት ድርሻ እንደ እ.አ.አ. በ1981ወደ 79% ከፍ ሲል በአንፃሩም ከላይ በተጠቀሰው ወቅት የነበረው የግል አስመጭዎች ድርሻ ከ94% ወደ 21% ዝቅ እንዲል ተደርጓል ። በወጪም ንግድ እንዲሁ ቅድመ አብዮት ማለትም በ1965 መንግሥት ዕቃዎች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተግባር በፍጹም ያልተካፈለ ሲሆን በ1973 ፥ 72% ድርሻ እንዲኖረው ሲደረግ በአንጻሩም በተጠቀሱት ዘመናት የግል ላኪዎች ድርሻ ከ100% ወደ 28% ዝቅ እንዲል ተደርጓል ።

Digitized by Google

በገቢ ዕቃዎች የመንግሥትና የግል የገበያ ድርሻ

ዓመት	መንግሥት		ግል		ጠቅላላ
	ብር	መቶኛ %	ብር	መቶኛ %	
1966/67 /1974/	33,467,530	6	542,530,381	94	575,997,911
1967/68 /1975/	92,587,894	14	555,068,297	86	647,656,191
1968/69 /1976/	250,759,460	30	596,042,475	70	846,801,935
1969/70 /1977/	303,501,339	30	708,823,583	70	1,012,324,922
1970/71 /1978/	384,100,326	38	628,494,075	62	1,012,594,401
1971/72 /1979/	831,967.136	70	361,051,175	30	1,193,018,311
1972/73 /1980/	887,191,836	69	401,209,712	31	1,288,401,548
1973/74 /1981/	1,141,844,565	79	305,313,511	21	1,447,158,076

ምንጭ ፤— ከብሔራዊ ባንክ በተገኘ መረጃ የተዘጋጀ

በወጪ ዕቃዎች የመንግሥትና የግል የገበያ ድርሻ

ዓመት	መንግሥት		ግል		ጠቅላላ
	000 ብር	መቶኛ /%/	000 ብር	መቶኛ /%/	
1965	—	0	494,865	100	494,865
1971	260,166	37	451,899	63	712,065
1972	623,309	66	325,274	34	948,583
1973	582,566	68	268,278	32	850,844
1974	615,600	72	240,330	28	855,930
1975 ዕቅድ	692,264	72	271,861	28	964,125

ምንጭ፤— በብሔራዊ አብዮታዊ ምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ከንግድ መምሪያ ከተገኘ መረጃ የተቀነባበረ ።

Digitized by Google

የሀገር ውስጥ ንግዱን በሚመለከትም እንዲሁ በተደረገው ጥረት የኢንዱስትሪና የእርሻ ውጤቶችን በማከፋፈል ተግባ ላይ የተሰማሩት የኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ማከፋፈያና የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽኖች የሚይዟቸውን ዕቃዎች ዓይነትና መጠን ከዓመት ወደ ዓመት እያሳደጉ በመምጣት ተጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው ዓመታዊ የግዥ መጠናቸውን በመጨመር በገበያው ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዲይዙ ጥረት በመደረግ ላይ ነው ።

ያወጣ የኢንዱስትሪ ውጤት ለገበያ ቀርቧል ። [1]

በአንጻሩ መሰረታዊ ሸቀጦችን ለገበሬው በማቅረብ አገልግሎት የሚሰጡ 3,603 የገበሬዎች የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተቋቋሙ ሲሆን የእነዚህም ማኅበራት ካፒታል 59,731,980 ብር ይደርሳል ። በከተማዎችም እንዲሁ በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ሥር ያሉት የሕዝብ ሱቆች ብዛት 1,072 ሲሆን ካፒታላቸውም የአሰብ አስተዳደርንና የጐጃምን ፣ የሸዋና የአርሲን ክፍላተ ሀገር ሳይ

ዓመት	ሸ ቀ ጥ 000 ብር	እ ህ ል በኩንታል
1969	109,384	1,183,651
1970	174,578	1,072,194
1971	286,185	1,329,006
1972	415,371	2,710,243
1973	517,892	4,369,464
1974	518,774	4,589,269

ምንጭ ፣ የሀገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ይዘት ለማዳበር ሕዝባዊ ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ድርሻ የተዘጋጀ መግለጫ ፣ ግንቦት 16፣1974 /ያልታተመ/

በ1973 መንግሥታዊ የኢንዱስትሪ ውጤት አምራች ድርጅቶች በሽያጭ ዋጋ 1,464,490,000 ብር የሚያወጣ ምርት ያመረቱ ሲሆን በኮርፖሬሽን ሥር ያልተደራጁ የአክሲዮን ኩባንያዎች ደግሞ 77,654,000 ብር የሚያወጣ ምርት አምርተዋል ። በአጠቃላይም ከውጭ ሀገር ከሚመጣውና በሀገር ውስጥ በግል አምራቾች ከሚመረተው ምርት በስተቀር 1,542,141,000 ብር የሚ

ጨምር 19,482,728 ብር ይደርሳል ። [2]

በሀገር ውስጥ ንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ የግል ንግድ ድርጅቶችን ተሳትፎም ስንመለከት በሀገር አቀፍ ደረጃ በችርቻሮ ፣ በጅምላና በአገልግሎት ንግድ 67,893 ነጋዴዎች በመሰማራት ለችርቻሮና ለጅምላ ንግድ 91,460,248 ብር ካፒታል እንዳላቸው ይታወቃል ። (ከላይ የተጠቀሰው የነጋዴ ብዛትም ሆነ የካፒታል መጠን በኢሉባቦር የሚገኙትን የግል ነጋዴዎች የማይጨምር

Digitized by Google

ከመሆኑም በላይ የነጋዴዎች ብዛት በተጨማሪ በአክሱምና በአዋሳ የሚገኙትን በአገልግሎት ሥራ የተሰማሩትን የግል ነጋዴዎችን አይጨምርም)።[3]

ምንም እንኳ ለገበያ የሚቀርበው ምርት የሕዝቡን ፍላጐት የማያረካ ቢሆንም ሕዝባዊ ድርጅቶች ያላቸው ካፒታልና መሠረታዊ ሸቀጦችን ለማከፋፈል ያቋቋሟቸው ድርጅቶች ከግል ነጋዴዎች ጋር የሚመጣጠን አለመሆኑን ያመለክታል። ያም ሆኖ በተለይ በጅምላ ንግድ በ1974 የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ንግድ ድርጅቶች ድርሻ ከ70% በላይ መሆኑ የሚያበረታታ ነው።[4]

በሌላ በኩል የግል ነጋዴዎች፣ በተለይም በችርቻሮው የንግድ ዘርፍ የተሰማሩት፣ የያዙትን ድርሻ በአሀዝ ለማቅረብ ለጊዜው መረጃው ተጠናቆ ባይገኝም፣ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አሁንም ሰው ሠራሽ የሸቀጥ እጥረትን፣ የሥርጭት መዛባትንና የዋጋ መናርን መፍጠራቸው አልቀረም ።

በእርግጥም የሸቀጥ እጥረት መንስኤው ሰው ሠራሽ ብቻ ሳይሆን ራሱን የቻለ የሽግግር ወቅት ችግር በመሆኑ በዕድገት የሚፈታ ነው። ይህን የመሰለው ችግር በአንድ መልኩ የፋብሪካዎችን የማምረት አቅም አነስተኛነት ሲጠቁመን በሌላ በኩል የኅብረተሰቡ የመግዛት ኃይል እየጨመረ መምጣቱን ያመለክታል። ለእጥረቱ መባባስ መንስኤ ከሆኑት ዓበይት ሁኔታዎች ጥቂቶቹን እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል፦

—አብዮታችን ከፈነዳ ወዲህ ሰፊው ሕዝብ ከፊውዳሉች የጭቆና መዳፍ የተላቀቀ ቢሆንም በንግዱ መስክ ተመሳሳይ ድል ገና አልተቀዳጀም። አብዮታዊው መንግሥት ቀድሞ የግል ባለሀብቶች መበዝበዣ የነበሩ ፋብሪካዎችን በቁጥጥር ሥር ካዋለ በሙሉ ኃይላቸው እንዲያመርቱ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፣ ፋብሪካዎቹ ያረጁ በመሆናቸውና በአዲስ ለመተካትም አቅም ባለመፍቀዱ - የምርቱ መጠን በየጊዜው እያደገ ከሚመጣው የኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር ሊገናዘብ አልቻለም ። በተጨማሪም ያረጁት ፋብሪካዎች እንኳን በሙሉ ኃይላቸው እንዳይሠሩ ጸረ አብዮተኞች በዚህ ረገድ ብዙ ደባ እንደፈጸሙ የሚዘነጋ አይደለም ።

—በሌላ በኩል የእንዱስትሪ ሸቀጥን እጥረት ከውጭ በማስመጣት ማቃለል እንዳይቻል የውጭ ምንዛሪ አቅማችን አልፈቀደም ። ያለውን አነስተኛ የውጭ ምንዛሪ በሙሉ በፍጆታ ዕቃዎች ላይ ማዋል ደግሞ ለዘለቄታው ከእጥረት ለመዳንና ለተደላደለ ኑሮ ዋስትና የሆነ አስተማማኝና ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያደርገውን ጥረት የሚያሰናክል ይሆናል ።

— ቀድሞ ለከበርቴው ተርፍ ማካበቻ በሚያመቹ ጥቂት የደሩ ከተሞች ተወስነው የነበሩት የማከፋፈያ አውታሮች ወደ መንግሥት ይዞታነት ሲዛወሩ ለሰፊው ሕዝብ አገልግሎት በጠረፍና በገጠር እንዲስፋፉ መደረጉም ቀድሞ የኢንዱስትሪ ውጤት የማይደርሳቸው አዲስ ሸማች አካሉች በመፍጠሩ ፍላጐቱን ከፍ አድርጎታል ።

— ባለፉት ስምንት ዓመታት አብዮታዊው መንግሥት ለብዙ ሥራ አጦች የሥራ ዕድል እንዲከፈት አድርጓል። በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ አዲስ ሰፋሪዎች አምራች ዜጋዎች ለማድረግ የሠፈራ ፕሮግራሞች አዘጋጅቷል ። ይህም የአኗኗር ለውጥ ወቅታዊ የመሠረታዊ ሸቀጥ እጥረትን ይፈጥራል ።

— ቀድሞ በአርቦና በሲሶ አራሽነት ይኖር የነበረው ጭሰኛ ከታሪካዊው የገጠር መሬት አዋጅ ወዲህ የራሱ የማምረቻ መሣሪያና የምርት ባለቤት በመሆኑ የገበሬው ኅብረተሰብ

Digitized by Google

ገቢ አድጓል ። የገበሬው ገቢ አድገት በአንፃሩ የሸቀጥ ፍላጐት እድገት በማስከተሉ ለእጥረቱ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል ።

— በአጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እየበረከተ ሲሔድ በአንጻሩ ተመጣጣኝ የምርት እድገት ለማስገኘት አለመቻሉ የፍላጐትንና የአቅርቦትን ሚዛን እንደሚያዛባ ግልጽ ነው ።[5]

ዛሬ የምንዘረጋቸው የልማት ተቋሞች ለተያያዝነው የሶሻሊስት ኢኰኖሚ ግንባታ መሠረት የመጣል ትግል አጋዥ እንደመሆናቸው ፣ ይህን ጥረት በማጧጧፍ ለመሠረታዊ ዕቃዎች እጥረት ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት መቻል ይኖርብናል ። እስከዚያው ያለውን ምርት በተቀላጠፈ አሠራርና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለሕዝቡ እንዲከፋፈል ማድረግ ደግሞ አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው ።

ሶሺያሊስታዊ የንግድ ሥርዓት በአንድ በአጭር እመርታ የሚገኝ ድል እንዳልሆነ አብዮት ካካሄዱ አገሮች ታሪክ መረዳት ይቻላል ። እንዲያውም በሽግግር ወቅት ከባዱ ተግባር ንግድን ሶሻያሊስታዊ ፈር የማስያዙ ተግባር እንደመሆኑ ፣ በዚህ አንጻር የሚያበረታታ ውጤት እየተገኘ ነው ።

በቅድመ አብዮት የሸቀጥ ልውውጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚያተኩረው ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በሚኖሩበት ጥቂት ታላላቅ ከተሞች ብቻ እንደነበር ቀደም ሲል ተጠቅሷል ። ይህ የተዛባ አሠራር የሚያተኩረው በበዝባዡ መደብ ጥቅም ላይ ብቻ በመሆኑ ሰፊው ሕዝብ የሀገሪቱ ፍሬ ተቃማሽ ሳይሆን ቆይቷል። ቅድመ አብዮት የነበሩት 19 የሸቀጥ ማከፋፈያ ቅርንጫፎች ወደ 54 ከፍ እንዲሉ መደረጉና አብዛኛዎቹም የተቋቋሙት ከአሁን በፊት ተረስቶና በመሀል ሀገር ከሚደረገው የሸቀጥ ልውውጥ ተገልሎ በነበረው በገጠሩና በጠረፍ አካባቢባሉ ሥፍራዎች በመሆኑ የሰፊውን ሕዝብ የሸቀጥ ፍላጐት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን ያመለክታል ።[6]

በሌላ በኩል በንግዱ ክፍለ ኢኰኖሚ የተገኘው አብዮታዊ ድል በከፊልም ቢሆን በልውውጥ ዋጋና በሸቀጥ ዓይነት በኩል የተገኘው መሻሻል ነው ። በሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት አማካኝነት የሚካሄደው የሥርጭት ተግባር የሸቀጦች ዓይነትን በሚመለከት ከቀድሞው የተለየ ይዘት አለው ። ድርጅቱ በግል ይተዳደር በነበረበት ወቅት ያከፋፍል የነበረው የቅንጦትና ለቡርዧው መደብ አባላት የሚያገለግሉ ዕቃዎች ሲሆኑ ፣ ይህ አሠራር ተለውጦ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የሚያሠራጨው መሠረታዊ የሆኑና ለአብዛኛው ሸማች አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚገመቱትን ዕቃዎች ነው ።

በዋጋ በኩል ያለው ሁኔታ ሲገመገም የግል ነጋዴዎች ዘዴአቸውን እየለዋወጡ የንግድ አሻጥር ስለሚፈጽሙና የተረጋጋ የዋጋ ቁጥጥር ሥርዓት ገና በሰፊው ስላልተዘረጋ ችግሩ ጉልቶ ይታያል ። ሆኖም በሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት በኩልና በአንዳንድ አምራች ድርጅቶች በኩል የሚከፋፈሉ ሸቀጦች በተተመነ ዋጋ ስለሚሸጡ በገበያ ውስጥ ከሚገላበጠው ሸቀጥ ውስጥ ከመንግሥታዊ ማከፋፈያዎች በቀጥታ ለሕዝባዊ ድርጅቶች የሚሸጠው በተረጋጋ ዋጋ ነው ። ይህን የመሰለው የሸቀጥ ልውውጥ ለሸማቹም ሆነ ለመንግሥታዊ ድርጅቶች ጤናማ የንግድ መድረክ የሚፈጥር በመሆኑ ለወደፊት የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶች የገበያ ድርሻ እየዳበረና እያደገ ሲሄድ ጠቅላላው የንግድ ዘርፍ ከብዝበዛ ነፃ እንደሚሆንና ትክክለኛ ኅብረተሰብአዊ ባሕርይ እንደሚኖረው አይጠረጠርም ።

ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ለማገባደድ መከናወን ካለባቸው ተግባሮች መካ

Digitized by Google

ከል አንዱ በንግዱ ዘርፍ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ማጸጸምና በየጊዜው ማጠናከር መሆኑ እሙን ነው ። በንግዱ እንቅስቃሴ ውስጥ ከነዚህ ድርጅቶች ጋር ቀጥታ ግንኙነት ማድረግና ሶሻሊስታዊ የንግድ ሰንሰለት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑም መንግሥታዊው የማከፋፈያ ድርጅቶች በሸቀጥ ስርጭቱ ለመንግሥታዊና ለሕዝባዊ ድርጅቶች ቅድሚያ እንዲሰጡ ተደርጓል ። በዚህ መሠረት በ1973 የበጀት ዘመን ድርጅቱ ካከፋፈለው ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥ ውስጥ 62.3% ያህሉ ለመንግሥታዊና ለሕዝባዊ ድርጅቶች ሲሰራጭ በተለይ መሠረታዊ የሆኑ ሸቀጦችን በሚመለከት ደግሞ በዚሁ በጀት ዘመን ድርጅቱ ካከፋፈለው 70% ያህሉ በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት እንደሆነ ይታወቃል ።[7]

ከላይ የተጠቀሰው ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች በመሠረታዊ ሸቀጦች ስርጭት የያዙት ከፍተኛ የገበያ ድርሻ እንደ ምስማር ፣ ቀርቀሮ ፣ ጨው ፤ ቡና ፣ ጨርቃ ጨርቅ ፣ ሳሙና ፣ ክብሪትና የጽሕፈት መሣሪያዎች ያሉትን ስለሚያቅፍ ኅብረተሰቡ የተጠቀሱትን ሸቀጦች በሚመለከት በተረጋጋ ሁኔታ በማግኘት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። በእህሉም ንግድ እንደዚሁ ቀጥሎ ከተመለከተው ሠንጠረዥ ለመመልከት እንደሚቻለው ለመንግሥታዊ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የገበሬ ማኅበራት ያመረቱትን ምርት በማኅበራቸው አማካኝነት በማሰባሰብና በማቅረብ ላይ እንደ መሆናቸው የእህል ንግዱን ሶሻሊስታዊ አቅጣጫ ለማስያዝ ጥረት እየተደረገ ነው ።

የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት በ1973 እና በ1974 የበጀት ዘመን ከገበሬና ከነጋዴ የገዛው

የእህል መጠን /በኩንታል/

ተራ ቁጥር	ም ን ጭ	1973		1974	
		ብዛት	%	ብዛት	%
1	ገበሬ ማኅበራት	642,549	25.0	149,375	5.0
2	የአምራቾች ማኅበራት	13,242	0.5	82,383	3.0
3	የአገልግሎት ኅ· ሥ· ማ·	252,245	10.0	870,318	28.0
4	የሠፈራ ጣቢያዎች(መንግሥት)	23,232	1.0	73,483	2.0
5	ነጋዴዎች	1,638,271	63.5	1,889,090	62.0
	ድምር	2,569,539	100.0	3,064,649	100.0

ምንጭ ፥ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የ1973 እና 1974 የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት /ያልታተመ/

Digitized by Google

መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶችም በን
ግዱ መስክ የሚያደርጉትን ዕድገት በመ
መልከት ቅንጅት ባለው አሠራር የንግድ
ፈቃድ አሰጣጡም እንዲስተካከል በተደረ
ገው ጥረት የንግድ ፈቃድ በዘርፍ ተለይቶ
አንድ የግል ነጋዴ በአንድ ዘርፍ ብቻ የንግድ
ፈቃድ እንዲያገኝ በመደረግ ላይ ነው ።

በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም በመን
ግሥታዊ አስመጭ ድርጅቶች በኩል ከው
ጭ ሀገር እየመጡ በብቸኝነት መንግሥታዊ
የማከፋፈያ ኰርፖሬሽን በሚያከፋፍላቸው
የንግድ ዕቃዎች የጅምላ ንግድ ፈቃድ ለግ
ል ነጋዴዎች እንዳይሰጥና ከአሁን በፊትም
በዚሁ የንግድ ዘርፍ የጅምላ የንግድ ፈቃድ
ተሰጥቷቸው የነበሩ ነጋዴዎች ባልተከለ
ከሉ የችርቻሮና የአገልግሎት የንግድ ዘር
ፎች እንዲሰማሩ በተወሰደው እርምጃ ቀጥ
ሎ በምሳሌነት የተጠቀሱት የምርት ዓይነ
ቶች በመንግሥታዊ ማከፋፈያዎች ብቻ
በጅምላ እንዲከፋፈሉ ተደርጓል ።

ሀ/ ከናይለን በስተቀር ጨርቃ ጨርቅ ፣
ድርና ማግ ክርና የስፌት ክር ፣
ለ/ አንሶላ ፣ ብርድልብስ ፣ ፎጣና ካኔቴራ
ሐ/ የልብስ ፣ የገላና የዱቄት ሳሙናዎች
መ/ የቲማቲም ድልህ ፣
ሠ/ ሸራና ላስቲክ ጫማ ፣
ረ/ የባትሪ ድንጋይ (የሀገር ውስጥ ምርት)
ሰ/ ክብሪትና ሻማ ፣
ሸ/ ፓስታ ፣ መካሮኒ ፣ ሩዝ (ከውጭ
የመጣ) ፣
ቀ/ የቤት ክዳን ቆርቆሮና ምስማር ፣
በ/ የግድግዳና የወለል ቀለም ወዘተ - -

ቀደም ሲል በቀረበው ሠንጠረዥ እንደ
ተመለከተው ለውጭ አገር ገበያ የሚቀር
በው የሀገር ውስጥ ምርት መጠንና አይ
ነት ቢሆንም ያለውን ዕቃ በመላክም ሆነ
ከውጭ ሀገር በማስመጣቱ ሥራ መንግሥ
ታዊ ላኪና አስመጭ ድርጅቶች ተሳትፎ
አቸውን እየጨመሩ ፤ በሄዱ ቁጥር የግል
ላኪዎች የሚልኩት ዕቃ ባለመገኘትና እን
ዲሁም ለመላክና ለማስመጣት በሚሰጡ
ፈቃዶች ላይ ቁጥጥር በማድረግ የግል ነጋ
ዴው በዚህ መስክ የነበረውን ተሳትፎ ለመ
ቀነስ ተችሏል ።

ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የትራንስፖ
ርት የንግድ ዘርፍ ሙሉ ለሙሉ በግል ነጋ
ዴዎች ተይዞ እንደነበር የሚታወስ ነው ።
በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት ዕቃዎችን በ
ማስተላለፍና የትራንስፖርት ስምሪትን በሚ
መለከት ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ያዋለ
ከመሆኑም በላይ በትራንስፖርት አገልግ
ሎት ተግባር ተሳታፊ መሆን በመጀመሩ ፣
በዚህ መስክ ልቅ የነበረውን የንግድ ሥራ
ሕዝባዊ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት አጠ
ቃላይ የንግድ ክፍለ ኢኰኖሚ ሶሻሊስ
ታዊ ፈር ለማስያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ
እንደሚኖረው አያጠራጥርም ።

በየአካባቢው የአገልግሎት የኅብረት
ሥራ ማኅበራት በመቋቋም ላይ ያሉ እንደ
መሆናቸው መጠን ቀደም ሲል በቀረበው
ሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው በሥራ
ቸው ካሰባሰቧቸው የገበሬ ማኅበራት ያመ
ረቱትን ምርት በመሰብሰብና ለመንግሥ
ታዊ የእህል ንግድ ድርጅት በማቅረብ የሚ
ያሳዩት ትብብር በአሁኑ ወቅት አጥጋቢ
ነው ባይባልም በእህል ንግድ ዘርፍ የሚታ
የውን የግል ነጋዴ ተሳትፎ እንደሚያዳከ
መው ይታመናል ።

ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የምርት ውጤ
ት ሃምሳ በመቶውን ይሸፍናሉ ተብሎ የሚ
ገመተውና በተለያዩ የዕደ ጥበብ ባለሙያ
ዎች በመደራጀት ላይ ያሉትም ማኅበራት
ገና ወጣት በመሆናቸው ፍሬአቸው ያልታየ
ቢሆንም በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች
ለማምረት አቅም ባጡበትና ወይም ባልተ
ቋቋሙበት የምርት ዓይነት አኳያ የማም
ረት ኃይላቸውን በማሰባሰብ የኢንዱስት
ሪው አጋዥ ኃይል ይሆናሉ ተብሎ ይታ
መናል ። የተለያዩ የማከፋፈያ ድርጅቶች
በተለያዩ ባለቤቶች ሥር በነበሩበት ወቅት
ከፍተኛ የሥራ ማስኬጃ ወጭ ያወጡ እን
ደነበርና ወጭውንም ዕቃ ላይ
በመጨመር ተጠቃሚው ለማገዛቸው የፍ

Digitized by Google

ጆታ ዕቃዎች የሚከፍለውን ከፍያ ያን ሩት እንደበር ለመረዳት ይቻላል ። ስለሆ ነም ሁኔታውን ለማሻሻል በተወሰደው እርምጃ ተመሳሳይ ተግባራት የሚያከናወኑ ድርጅቶች በአንድ ላይ ተሰባስበው እንዲ ሠሩ በመደረጉ የተመለከተውን ዓይነት ወጭ ለመቀነስና ለአንድ ዓይነት ዕቃ በተ ለያዩ ድርጅቶች ይጠየቅ የነበረውንም የተ ለያየ ዋጋ ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል ።

በንግዱ ክፍለ ኤኮኖሚ በአሁኑ ወቅት ጉልተው የሚታዩ ችግሮች

ምንም እንኳን የንግዱን ዘርፍ ሶሻሊስ ታዊ ፈር ለማስያዝ ከፍተኛ ጥረት ቢደ ረግም ዛሬም ቢሆን በኢንዱስትሪ ውጤቶ ችም ሆነ በእርሻ ሰብሉ የችርቻሮ ንግድ የግል ነጋዴዎች በስፋት የተሰማሩ በመሆና ቸው አሁንም የገበያ ቀውሶችና ችግሮች ሙሉ ለሙሉ ሊወገዱ አልቻሉም ። ለነ ዚህ ችግሮች ዓይነተኛ መንስኤ ከሆኑት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል ።

—የማምረቻ ድርጅቶች ምርታቸውን ራ ሳቸው ለሕዝባዊና ለመንግሥታዊ ድር ጅቶች ቅድሚያ እየሰጡ እንዲያከፋ ፍሉ የተደረገ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የማምረቻ ድርጅቶች በአገሪቱ ውስጥ በስፋት የተዘረጉ ቅርንጫፎች ስለሌ ኳቸውና ሕዝባዊ ድርጅቶች በርቀት ምክንያት ማምረቻዎቹ ድረስ ሔደው ሽቀጡን መውሰድ ባልቻሉበት አካ ባቢ ለግል ነጋዴዎች እንዲሸጥ መደ ረጉ ፣

—አንዳንድ አካባቢዎች በፀጥታ መደፍ ረስ ፣ የጠረፍ አካባቢ በመሆናቸውና በሌሎችም ምክንያቶች በኅብረት ሥራ ማኅበራት ባለመደራጀታቸውና ባለ መጠናከራቸው ለአካባቢው ሕዝብ በኰታ የተመደበው ሸቀጥ በተወካይ ነጋዴዎች አማካኝነት እንዲከፋፈል ሁኔታው አስገድዶአል ። ስለሆነም በዚህ ሁኔታ የሚሠራጨው ሸቀጥ መጠን በቀላሉ የሚገመት አይደለም ፤

—የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበ ራት በአብዛኛው ክፍላተ ሀገር የተ ቋቋሙ ቢሆንም ብዙዎቹ በገንዘብ አቅም ፣ በአሠራር ልምድ በአመራር ወዘተ . . . ረገድ ባለመጠናከራቸው የግል ነጋዴዎችን ለመተካትና ተሳት ፎአቸውን በሚፈለገው መጠን ለመ ቀነስ አልቻለም ፤

—አንዳንድ ክፍላተ ሀገር በየጊዜው ባዛ ር በማዘጋጀት ለልዩ ልዩ የልማት ሥ ራዎች መዋጮ ለመሰብሰብ የሚያደ ርጉት ጥረት መሠረታዊ የፍጆታ ሸቀ ጦችን በግል ነጋዴዎች እጅ እንዲገቡ መንገድ ስለሚከፍት ነጋዴዎችን ለማ ዳከም የሚደረገው ጥረት የተጠበቀ ውን ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም ፤

—ነጋዴዎች ዕቃ ሲከለከሉ በድርጅታ ቸው ውስጥ የሚሠሩ በርካታ ወዛደ ሮች ሥራ አጥተው ስለሚባረሩ ይህ ሁኔታ በሚያስከትለው ግፊት ዕቃ እንዲሰጣቸው በመደረጉ በነጋዴው እጅ የሚገባውን የሸቀጥ መጠን ሊያ ሳድገው ችሏል ፣

—አንዳንድ ሸቀጦች ወቅታቸውን ጠብ ቀው ካልተሸጡ በመቆየት ምክንያት ከጥቅም ውጭ ስለሚሆኑ ወይም መጠ ናቸው ስለሚቀነስ መንግሥታዊ አከ ፋፋዮች አንዳንድ ጊዜ (ለምሳሌ ባትሪ ድንጋይ ፣ ወጨው ወዘተ . . .) በየአ ካባቢው ለሚገኙ የግል ነጋዴዎች መ ሸጥ ይገደዳሉ ፤

—አንዳንድ ምርቶች ለተጠቃሚው የሚ ቀርቡት በአገልግሎት የንግድ ሥራ ዘርፍ በተሰማሩ ነጋዴዎች አማካይነት

Digitized by Google

በመሆኑ መሠረታዊ ሸቀጦች ነጋዴው እጅ መግባታቸው አልቀረም ፤ (ለምሳሌ ለሻይ ቤት ፣ ለቡና ቤት ፣ ለምግብ ቤቶች ወዘተ . . .)

ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶች የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦች ነጋዴው እጅ ሊገቡ ስለቻሉና ይህም የምርት ኃይሎች ባለመዳበራቸው ምክንያት ከሚያጋጥመው የምርት እጥረት ሁኔታ ጋር ሲዳመር የነጋዴው ድርሻ ከፍ እንዲል ከማድረጉም በላይ ዛሬ የሚታዩትን የገበያ ቀውሶችና ችግሮች ሊያስከትል ችሏል ። ከዚህም በተጨማሪ በሕዝባዊና በመንግሥታዊ ድርጅቶችም በኩል የተከሰቱ ሌሎች ችግሮች አሉ ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፤

—በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ የዕቃ ፍላጐት በዓይነት ፣ በመጠን ፣ በወቅት ተለይቶ ካለመታወቁም በላይ በየአካባቢው በዘልማድ የሚመረቱት የኢንዱስትሪን ውጤቶች ለመተካት የሚችሉ ዕቃዎች ዓይነትና መጠን እንዲሁም አካባቢ የሚያመለክቱ እስታትስቲካዊ መረጃዎች ተጠናቅረውና ተሰባስበው በማዕከላዊ ደረጃ ተቀምጠው ባለመገኘታቸው በሀገር ውስጥ የሚመረተውንም ሆነ ከውጭ ሀገር የሚመጣውን ዕቃ በትክክል ለማከፋፈልም ሆነ ለማዳረስ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮአል ፤

—በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ በየጊዜው መጨመሩና በዚህም ሳቢያ የልማትም ሆነ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ በመጨመሩ በአንጻሩ ደግሞ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የእርሻ ምርት ውጤቶች ዋጋ በተመጣጣኝ መጠን አለመጨመሩ በገቢና ወጪ ንግድ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ለማሳየት በቅቷል ፤

—ስለሆነም በቂ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ባለመቻሉ በሕዝቡ መሰረታዊ ፍላጐት ላይ በተመሠረተ መጠን የፍጆታ ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ለማስገባት አልተቻለም ፤

—በቂ የፍጆታ ዕቃዎች ባለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለማስገባት ባለመቻሉና በእጥረቱ የተነሳ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ በመናሩ የሕገወጥ ንግዱን (Contraband) ሥራ ከምንጊዜውም ይበልጥ አባብሶታል ፤

—በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ የሕገወጥ ንግድ በመደበኛ መንገድ ከሀገር ውስጥ በመውጣት መንግሥት ሊያገኘው የሚችለውን የውጭ ምንዛሪ ከማስቀረቱም በላይ በገቢም ዕቃዎች ላይ መንግሥት ሊያገኘው የሚችለውን የቀረጥ ገቢ በማስቀረት ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ላይ እንደሆነ ይታያል ። ምንም እንኳን በቁጥጥር የሕገወጥ ንግድን ለመግታት እየተሞከረ ቢሆንም ፍላጐትና የምርት መጠን ባልተዛመደበትና በመግዣና በመሸጫ ዋጋ መሀል ከፍተኛ ልዩነት በሚታይበት ሁኔታ የትርፉ መጠን እያሳሳቸው የሚያስከትለውን ጉዳትና ጥቅም የተረዱም ሆነ ያልተረዱ ግለሰቦች በሥራው በሰፊው በመሰማራት በዋጋም በኩል ያለውን ሁኔታ ከፍተኛ ውጣ ውረድ ሊፈጥሩበት ችለዋል ፤

—መንግሥታዊ የማከፋፈያ ድርጅቶች በአቋም ፣ በገንዘብ አቅም ፣ በማከማቻና በማከፋፈያ አውታር አዘረጋግ፣ በሰው ኃይልና በአሠራር ስልት የሚፈለገውን ያህል ባለመጠናከራቸውና ሊይዙ የሚችሉት የሸቀጥ ዓይነትና መጠን የተወሰነ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ንግዱን ሶሻያሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የሚደረገውን ጥረት ለማፋጠን አላስቻሉም ፤

—የሠለጠነና የነቃ እንዲሁም ጥራት ያለው የሰው ኃይል በየሙያ መስኩ በበቂ ሁኔታ ባለመገኘቱ አንዳንድ ሥራዎች የሚገባውን ያህል ባለመራመዳ

Digitized by Google

ቸውና ባለመስራታቸው ያለውን ችግ ር በተገቢው መጠን ለመቀነስ የሚያ ስችል ሁኔታ አልተፈጠረም ።

—ለሕዝብ ሱቆች አመራር መጠናከርና መሟላት ወሳኝነት ያላቸው የሂሳብ አያያዝ ፣ የንብረት አጠባበቅ ፣ የሥ ርጭት ሥርዓትና የመሳሰሉት መመ ሪያዎች ተሟልተው አለመስጠታ ቸው ፣ ለቁጥጥርና ለክትትል የተሰ ጠው ትኩረት በቂ ባለመሆኑ የሕዝብ ሱቆች ለፀረአብዮት ኃይሎች ፣ ለግል ጥቅም አሳዳጆችና የሕዝብ ሱቅን መጠናከር ለማይሹ በዝባዥ ነጋዴ ዎች እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል ።

—በከተማዎችም ሆነ በገጠሩ የተቋቋሙ ትን የሕዝብ ሱቆች በቅርብ እየተከ ታተለ መመሪያ የሚሰጥና አፈጻጸሙን የሚከታተል አካል ባለመኖሩ ትኩ ረት የሚሰጣቸውን ተግባሮች በቅ ደም ተከተል ለማከናወን ካለመቻ ሉም በላይ የኃይል መበታተንን በማ ስከተሉ እንደተጠበቀው ለመራመድ አልቻሉም ።

—በንግዱ መስክ ከተሰማራው የግል ካፒታል ጋር በመመሳጠር በመንግሥ ታዊና ሕዝባዊ የአከፋፋይ ተቋሞች ውስጥ ባሉ ለግል ብልጽግና በቆሙ ፀረአብዮት ኃይሎች በሚፈፀመው ደባ አማካይነት ንግዱን ሶሺያሊስ ታዊ ፈር ለማስያዝ የሚደረገውን ጥረ ት ለማሰናከል የሚደረገው ሙከራ እየ በዛ መምጣቱ አንድ ራሱን የቻለ ትል ህ ችግርና የንግዱንም ዘርፍ ሶሺያሊ ስታዊ ፈር ለማስያዝ የሚደረገውን ጥረት የሚያደናቅፍ ሆኗል ።

—የግል ነጋዴዎች መልካቸውን በመቀ ያየር ገና በመቋቋም ላይ ባሉት ጨ ቅላ ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በመሰ ግስግ ሸቀጦችን በሕዝባዊ ድርጅቶች ስም ከማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅ ቶች እየገዙ ለሕዝቡ በማዳረስ ፈንታ በከፍተኛ ዋጋ እያሳለፉ ለነጋዴዎች በመሸጥ ሕዝቡን ለበለጠ ብዝበዛ እን ዲጋለጥ አድርገውታል ።

ወደፊት መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች

ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ የተሞከረው ባለ ፉት ጥቂት ዓመታት የተደረጉ ትን ጥረቶ ችና የተገኙትን ውጤቶች ሳይሆን በንግዱ ረገድ የምንገኝበትን ሁኔታ በተጨባጭ በመገምገምና ይልቁንም ከፍተኛ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡትን ደካማ ጐኖች በግልጽ በመጠቆም ሊታረሙ የሚችሉብ ትን የመፍትሔ እርምጃ ለመሻት እንዲረዳ በማሰብ ነው ።

ስለሆነም የድክመቶቹ መወገድ ለረዥም ጊዜ ግባችን መሳካት የበለጠ አስተማማኝ መሠረት የሚጥል በመሆኑ በንግዱ ተግ ባር የተሠማሩ መንግሥታዊ ድርጅቶችና ሕዝባዊ አካሎች ሁሉ የሥራ ድርሻና ኃላ ፊነታቸውን እያመዛዘኑ ድክመቶችን ለማ ስወገድ ምን መደረግ አለበት ? የሚለውን ጥያቄ አንስተው ሊወያዩበትና አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል ።

እዚህ ላይ አብዮታዊ መሪያችን ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በአ ንድ ወቅት ሲናገሩ « የአብዮታችን ዋነኛ ትኩረት ከትናንቱ ላይ ሳይሆን በነገው ላይ ነውና ባለፈው ከመኩራራት ለመጭው ጠንከር መሥራት ዓላማውን በማያጠራ ጥር ከግብ ለማድረስ ያስችለዋል ። ወደ ኋላ የቀረንበትን ለማሻሻልና ለማጠናከር ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግም ትግላችንን የበለጠ የሠመረ ግባችንም የቀረበ ያደርገ ዋል ! » ያሉትን ማስታወስ ይጠቅማል ። በዚህ አንጻር የንግዱ ክፍለ ኤኰኖሚ የወደ ፊት ገጽታ እንዲሻሻል ለሶሻሊስት ኤኰ ኖሚ ግንባታ መሠረት ለመጣል ለሚደረ ገው ጥረት ተገቢ ድርሻውን እንዲያበረክ ትና በኤኰኖሚ ዕቅዱ እንዲመራ ለማድ ረግ በመንግሥት ብቻ የሚደረገው ትግል በቂ ስለማይሆን ሕዝባዊ ድርጅቶችም ከመ

Digitized by Google

ንግሥት ጉን በመቆም በንግዱ ክፍለ ኤኮ
ኖሚ የሚደረገውን ትግል ማገዝ ይኖርባቸ
ዋል ። ለዚሁ ነው የኢሠፓአኮ ሁለተኛ
ጉባኤ « የምርት እጥረት በስርጭትና ልው
ውጥ ላይ የሚያሳድረውን ተጨማሪ ተጽ
ዕኖ ለመቋቋም ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድር
ጅቶችን በሰው ኃይልና በገንዘብ በማጠና
ከር ድርሻቸው ከፍ እንዲል » [8] በማለት
ያሳሰበው ።

ድርጅታዊ ጥንካሬን በሚመለከት

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2 ሁለተኛ
መደበኛ ስብሰባ የአገሪቱን ኤኮኖሚያዊ፣የሶሻ
ልና የፖለቲካ ሁኔታ በሚገባ ከገመገመ
በኋላ ፣ የኤኮኖሚ ግንባታን የምርት ግንኙ
ነትንና ልውውጥን በሚመለከት ፣ « የመሠ
ረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች እጥረት ብሎም የእ
ነዚህ ዋጋ መናር የሚመነጨው ከምርት
አነስተኛነት ብቻ ሳይሆን ከምርት አሠረ
ጫጨትና አጠቃቀም ጉድለት በመሆኑ የን
ግዱን ዘርፍ ሶሻሊስታዊ ይዘት በማጠናከር
ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከነጋዴው ብዝበዛ
ለማላቀቅ በምርት ስርጭት መስክ የተሰማ
ሩት መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እን
ዲጠናከሩ » ውሳኔ አስተላልፎአል ።

ይህንንም ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ
አብዮታዊው መንግሥት ሕዝባዊ ድርጅ
ቶችን ለማጠናከር የሚረዱ ልዩ ልዩ እርም
ጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል ። በዚህም
መሠረት መ-ኢ-ሠ-ማ- ፣ መ-ኢ-ገ-ማ- እና
ከ-ነ-ማ-ት በተሻሻለና በተጠናከረ መልክ
እንዲዋቀሩ ለማድረግ የሚያስችሉ አዋጆች
ወጥተው ተግባራዊ መሆናቸው ነው ።

የወጡት የማጠናከሪያ አዋጆች በአንጋፋ
ሕዝባዊ ማኅበራት ውስጥ የሚታዩትን አን
ዳንድ የአሠራር ጉድለቶች ለማስተካከልና
ብቃታቸውን የጠራ ለማድረግ እንደሚረዱ
ይታመናል ። የሠራተኛው መደብና ገበ
ሬው በማናቸውም አገር ውስጥ ከሚገኙት
አምራች ኃይሎች ውስጥ ከፍተኛውን የም
ርት ክንዋኔ የሚያካሂዱ ናቸው ። በአ
ገራችንም ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ እነ
ዚህ ሁለቱ ምርታማ ኃይሎች በማንባ
ታውም ሆነ በፖለቲካው አቅጣጫ ያበረከ
ቱት አሁንም በማበርከት ላይ የሚገኙት
አስተዋጽኦ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሲ
ሆን ፣ በመካከላቸውም ሊኖር የሚገባው
መደባዊ ግንኙነት ይበልጥ እየተጠናከረ
እንዲሄድ በመደረግ ላይ ነው ። ዛሬ በሠራ
ራተኛው መደብና በገበሬው መካከል ያለው
ግንኙነት በዓላማ አንድነት ላይ የተመሠ
ረተ በመሆኑ ፣ ይህ አንድነት ሠርቶ አደሩን
ወደ አዲስ እመርታ እንደሚያሸጋግርና ሁለ
ቱም መደቦች የተጣለባቸውን ከፍተኛ
አብዮታዊ ድርሻ በአጥጋቢ ሁኔታ እንደሚ
ወጡ ይታመናል ።

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ መሠ
ረትም ቀደም ሲል የከተማ ነዋሪዎች ማኅ
በራት ሶስተኛ ዙር ምርጫ በማካሄድ ማኅ
በሩ ገጥሞት ለነበረው አንዳንድ የአሠራር
ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥ መመሪያ በመ
ስጠትና መዋቅሩንም በማጠናከር ለሁለን
ታዊ ትግሉ በብቃት እንዲሰለፍ የሚያስ
ችል እርምጃ መወሰዱ ይታወሳል ። የሕዝ
ባዊ ድርጅቶች ጥንካሬ የሚያበረታታ ቢሆ
ንም መደራጀት ብቻውንና በራሱ የመጨ
ረሻ ግብ ባለመሆኑ የተጠናከሩት ድርጅቶ
ች ለዘለቄታው ግብ የበኩላቸውን አስተዋ
ጽኦ ማበርከት እንዲችሉ ትኩረታቸውና
አሠራራቸው አብዮቱ ከደረሰበት የዕድ
ገት ደረጃና ከወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ጋር
መቀነባበር ይኖርበታል ።

እንደሚታወቀው በከተማ ነዋሪዎችም
ሆነ በገበሬ የአገልግሎት የኅብረት ሥራ
ማኅበራት የተቋቋሙት የሕዝብ ሱቆች በገ
ንዘብ አቅም ፣ በሰው ኃይል ፣ በመገልገያ
ቁሳቁስ ፣ በማከማቻ ወዘተ - - - የተጠናከሩ
ባለመሆናቸው የሚጠበቅባቸውን ያህል አ
ልገሉት ስጥተዋል ለማለት አያስደፍርም።
ስለዚህ ነው የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ
« ዛሬ በምንገኝበት የሽግግር ወቅት በከተ
ማና በገጠር በእርሻ መሃል የሚደረገ

Digitized by Google

ውን ልውውጥ በተለይም የሠራተኛውንና የገበሬውን አጋርነት ቁሳዊ መሠረት ለማጠናከር የንግዱ ክፍለ ኤኮኖሚ ያለውን ድርሻ በትክክል በመረዳት በአመዛኙ በጅምላና በተወሰነ ደረጃም በችርቻሮ የንግድ ሥራ የተሰማሩት መንግሥታዊ ድርጅቶች መዋቅርና አገልግሎት በሚገባ ተጠኖ በአሠራርና በድርጅት እንዲጠናከሩ እንዲደረግ»[9] የሚል ውሳኔ ያስተላለፈው ። ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተጠቀሰው እህል አሰባስቦ ለሸማቹ በማከፋፈሉም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለገበሬው በማሠራጨቱ ተግባር ሕዝባዊ ድርጅቶች በገበያው ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ይዘው ብዝበዛን ለማስወገድ ብዙ ትግል ማካሄድ ፣ አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈልና ያላሰለሰ ጥረታቸውን አጠናክረውና አፋፍመው መቀጠል ይኖርባቸዋል ። ይህንንም እውን ለማድረግ ወደፊት ለምርት ስርጭቱ ተግባር የተለየ ትኩረት የሚሰጡት የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እስኪደራጁ ወደዚያ መሸጋገሪያና አስኳል የሆኑትን የሕዝብ ሱቆችና የአገልግሎት ማኅበራት ማጠናከር አማራጭ የሌለው እርምጃ ነው ።

የንግዱን ሶሻሊስታዊ ይዘት ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት በአመራር ሰጪ አካላት ውስጥ የተመረጡትንና በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን በልዩ ልዩ የሙያ ዘርፍ በማሠልጠን የብዙ ዘመን የአሠራር ልምድና ካፒታል ካካበተው ነጋዴ ጋር ተወዳድረው የበላይነት ለመያዝ በሚያስችላቸው ዕውቀት ማስታጠቁ ዓቢይ ተግባር ነው ። ስለዚህ የእርሻ ሰብል ግዥም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤት ክፍፍል ኮታ ሲደለደል አግባብ ያላቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች በውይይቱ እየተሳተፉ እንዲወሰን ቢደረግ ለተግባራዊነቱ እንዲታገሉ የበለጠ የሚያነቃና የሚያደፋፍራቸው ሁኔታ ይፈጠራል ። በሌላ በኩል ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር የመንግሥታዊ ድርጅቶች መጉልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ግልጽ ነው ።

ምንም እንኳን በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት መንግሥታዊ ድርጅቶች ዕድገታቸው ከዓመት ወደ ዓመት ከፍ እያለ የመሔዱና የሚያበረታታ ብሩህ ተስፋ የሚታይባቸው ቢሆንም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ዛሬ በእህልም ሆነ በኢንዱስትሪ ሸቀጥ ንግድ ውስጥ መንግሥታዊ ድርጅቶች የያዙት የገበያ ድርሻ የነጋዴውን ብዝበዛና ፀረ—ሕዝብ ደባ በሚያስተማምን ሁኔታ ለመቋቋም እሚያስችል ወሳኝ ደረጃ ላይ አለመድረሱ የአብዮቱ ደካማ ጐን መሆኑ ግልጽ ነው ።

እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት መንግሥታዊ የማከፋፈያ ድርጅቶች እንደሕዝባዊ ድርጅቶች ሁሉ በገንዘብ አቅም ፣ በሠለጠነ የሰው ኃይል ፣ በማከማቻ ፣ በትራንስፖርትና በሌሎች መገልገያ ቁሳቁስ ወዘተ ---- የተሟሉ ባለመሆናቸው ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ከፍተኛ የማጠናከሪያ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ።

ስለዚህ መንግሥታዊ የማከፋፈያ ድርጅቶች ኃይላቸውን በማሰባሰብ ፣ የሚይዙት የሸቀጥ ዓይነት በመሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ፣ ከሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር የበለጠ በመቀራረብ የሥርጭት ስልታቸውን ወገናዊ አድርገው ለሕዝባዊ ድርጅቶች ቅድሚያ በመስጠት፣ መሠረታዊ ዕቃ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተጠቃሚው ሚዛናዊ በሆነ ክፍፍል እንዲዳረስ በማድረግ ተጠናክረው በተቀነባበረ መንገድ የሚሠሩበት ዘዴ መቀየስ ይኖርበታል።

አብዮታዊ መሪያችን ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በስድስተኛው የአብዮት በዓል ባሰሙት ንግግር እንዳስገነዘቡት «---ዛሬ በደረስንበት የዕድገት ደረጃ አበይት ከሆኑት ተግባሮቻችን አንዱ ሠርቶ አደሩ የሥራ ፍሬው ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለሰፊው ሕዝብና ለአገር ደንታ

Digitized by Google

የሌላቸውን ግለኞች መቆጣጠር ነው ። » ይህንንም ተጨባጭ ለማድረግ የሚያስችለው ዋነኛው ተግባር ሕዝባዊና መንግሥታዊ የማከፋፈያ ድርጅቶችን አግባብ ካለው የሸቀጦች ዓይነት አንጻር መዘርጋትና የንግዱን መስክ ደረጃ በደረጃ ሶሻሊስታዊ ባሕርይ እንዲኖረው ማድረግ ነው ።

በዚህ ረገድ በተለይ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲያብቡና ሸማቹ ሕዝብ በአንድ ላይ ተሰባስቦ በድርጅቱ አማካኝነት የሚፈልገውን ሸቀጥ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ ወሳኝነት አለው ከዚህም በቀር የምርት ምንጮችንና የገበያ ድርጅቶችን ሶሻሊስታዊ ክልል ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ በአምራችና በአከፋፋይ ድርጅቶች መካከል ቀጥታ ግንኙነት ስለሚፈጥር ለበለጠ የምርት ዕድገትም አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ።

በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ መጠናከር ማለት ፊት ለፊት የሚወጉንንና አብዮታችንን የሚቦረቡሩትን አሻጥረኞች ከዕቃዎች ልውውጥ መድረክ በሥልት በማገለል ለንግዱ ሶሺያሊስታዊ ፈር መያዝ መሠረት መጣል ማለት ነው ።

በሌላ በኩል መንግሥታዊ የንግድ ድርጅቶች በገበያ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ከፍ በማድረግ የምርት ሥርጭቱን ሚዛናዊና አስተማማኝ ለማድረግና ገበያውን ለማረጋጋት እንዲችሉና ለሕዝባዊ ድርጅቶችም ተገቢውን ዕርዳታና ድጋፍ እንዲሰጡ አሁን በሚታይባቸው ድክመትና ከሚገኙባቸው የተወሳሰቡ ሁኔታዎች እንዲላቀቁ ማድረግ የመንግሥትን ትኩረት ይጠይቃል። በዚህ ረገድ ከሚወሰዱት እርምጃዎች የእርሻ ሰብልንም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤትን በማከፋፈል ተግባር ላይ የተሰማሩትን መንግሥታዊ ድርጅቶች የመዋቅር አዘረጋግ ከአምራቾችና ከሸማች ሕዝባዊ ተቋሞች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት ለመመሥረትና የተቀነባበረ አሠራር ለመከተል በሚያስችላቸው ሁኔታ እንዲስተካከል ማድረግ ነው ።

በዚህ አንፃር የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅትም ሆነ የአገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅት መዋቅር ከገበሬ የአምራች ፣ የአገልግሎት ማኅበራትና ከሸማች አካሎች አደረጃጀት ጋር እንዲገናዘብ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህን ዋና ዋና መንግሥታዊ የንግድ ተቋሞች (ማለትም የእህል ሰብል ገበያ ድርጅት ፣ የአገር ውስጥ ማከፋፈያ ድርጅትን ወዘተ - - -) በሚመለከት ቀደም ሲል ከተጠቀሰውና በባጀት ፣ በሰው ኃይልና በመጋዝን ወዘተ - - - ካላቸው ተጨባጭ ድክመት በተጨማሪ በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ የሚገባው ነገር አለ ። ይኸውም ፦

—ግልጽና በመመሪያ ላይ የተመሠረተ የግዥና ስርጭት ሥርዓት አለመኖር፣ የወጭና የገቢ ሰነዶች በሚገባ አለመሰብሰብ ፣

—በቂ ዋስትና የሌላቸውን የግዥም ሆነ የስርጭት ጣቢያ ሠራተኞችን መመደብ ገንዘብ እየያዙ ለሚጠፉ ሰዎች ቀዳዳ መክፈቱ ፣

—ገንዘብ በባንክ መንቀሳቀስ ሲገባው ሠራተኞች በካሽ ስለሚሰጣቸው ሁኔታው ለስርቆሽና ለዝርፍያ አመች መሆኑ ፣

—ግዥ ፣ ሽያጭና ስርጭት በዕቅድና በፕላን የማይከናወን መሆኑንና በአፈጻጸምም ላይ ክትትል የማይደረግ መሆኑ ፣

—ከሌሎች ሕዝባዊና መንግሥታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ማለትም ከትራንስፖርት ፣ ከባሕርና ትራንዚት ፣ ከአስመጭና ላኪ ድርጅት ፣ ከወደቦች አስተዳደር ወዘተ - - - ጋር የተቀናጀ አሠራር አለመኖሩ ፣ የብኩንነትና በአጠቃላይም የአሠራር ድክመት ያለ መሆኑን ይጠቁማሉ ።

Digitized by Google

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ የመንግሥት የንግድ ተቋሞች በግዥ ወይም በሽያጭ ወይም በሁለቱም አንፃር በንግዱ ዘርፍ ውስጥ ከተሰግሰገው የግል ካፒታል ጋር ግንኙነት ስላላቸው ፣ ይኸ ግንኙነት በነዚህ ተቋሞች ውስጥ ለሚሠሩ አንዳንድ የግል ሀብት አምልኩት ላጠቃቸውና የተጣለባቸውን የሕዝብና የመንግሥት አደራ ለዘነጉ ግለሰቦች ምዝበራ አመች ሁኔታ መፍጠሩ በገሃድ የሚታይ ነው ።

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ፣ በንግዱ መስክ የተሰግሰገው የግል ካፒታል በመንግሥት የንግድ ተቋሞች ውስጥ ካሉ አንዳንድ ለግል ጥቅም እራሳቸውን ከሸጡ ግለሰቦች ጋር በጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በሚፈጥርበት ጊዜ ዓላማው ከዚህ ግንኙነት በከፍተኛ ትርፍ መልክ የኤኮኖሚ ጥቅም ማግኘት ብቻ አለመሆኑን ነው ። ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው አብዮቱ አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ፣ የመደብ ትግሉ መልኩን ቢቀይርም ፣ በተፋፋመ ሁኔታ የሚካሄደው በተለይ በዚሁ የኤኮኖሚ ዘርፍ በመሆኑ ፣ በንግዱ መስክ የተሰግሰገው ካፒታል በመንግሥት የንግድ ተቋሞች ውስጥ ከሚሰሩ የጥቅም ተካፋዮቹ ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት የፖለቲካ ዓላማም ያለው ነው ።

የመንግሥት የንግድ ተቋሞች መሠረታዊ ዓላማ ባላቸው አቅም ለሕዝቡ እንዲያሰራጩ የተመደበላቸውን ምርት በተቀላጠፈ አሠራርና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ በማከፋፈል ፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጐት በተቻለ መጠን በማርካት በንግዱም ዘርፍ ለሶሺያሊስት የምርት ግንኙነት መጠናከር መታገል መሆኑ የታወቀ ነው ። በንግዱ መስክ የተሰግሰገው የግል ካፒታል በመንግሥት የንግድ ተቋሞች ውስጥ ከተሰገሰጉ የጥቅም ተካፋዮቹ ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት ፣ የተለያየ መልክ ቢኖረውም ዞር ዞር በግል ጥቅም ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ የመንግሥት የንግድ ተቋሞችን አሠራር የሚያበላሽ ፣ ዕድገታቸውን የሚገታ ፣ ሸማቹ ሕዝብ በመንግሥት ተቋሞች ላይ ያለውን አመለካከት የሚያሻክርና ብሎም ሕዝቡ በሶሺያሊዝምና በአብዮቱ ላይ ያለው እምነት እየቀነሰ እንዲሄድ የሚያደርግ በመሆኑ፣ የዚህ ዓይነት በግል ጥቅም ላይ የተመሠረተና የማኅበራዊ ጥቅምን የሚገረር ግንኙነት የፖለቲካ ዓላማ ግልፅ ሊሆን ይገባል ።

ስለዚህ ከመንግሥታዊ የንግድ ተቋሞች ጉቦን ፣ ምዝበራን ፣ ብኩንነትና የመሳሰሉትን ለማጥፋት የሚካሄደው ትግል በንግዱ ዘርፍ የግል ካፒታል በአብዮቱ ላይ ለሚያካሂደው የመደብ ትግል አጸፋውን ለመመለስ የሚካሄድ የመደብ ትግል — ስለሆነም የፖለቲካ ትግል መሆኑን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል ።

የአሠራር ቅንጅትን በሚመለከት

አብዮታዊ መሪያችን ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በ1974 የሜይ ዴይ በዓል ላይ ባደረጉት ንግግር « የዕድገታችን አንዱና ዋነኛው እክል የአሠራር ቅንብር አለመኖር ነው ። የአሠራር ቅንጅት መታየት ያለበት በተወሰነ ዘርፍ ከላይ ወደታች ባለው የግንኙነት መስመር ብቻ ሳይሆን በተለይ በአንድ በተወሰነ አካባቢ በሚገኙትና የአካባቢውን ሁኔታ በሚገባ በሚያውቁት ልዩ ልዩ መንግሥታዊና ሕዝባዊ አካላት መካከል መሆን ይኖርበታል ። በዚህ መልክ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካሎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ጊዜን ፣ ገንዘብንና ጉልበትን በሚቆጥብ ሁኔታ ካልተወጡ ሕዝባዊ አካሎችም በተመሳሳይ ድርሻቸውን ካላከናወኑና እንዲሁም ሁሉቱም ወገኖች በመደጋገፍ ሕዝቡን ለማገልገል በሚያስችላቸው ሁኔታ ካልተሰለፉ ችግሩ ሊቃለል አይችልም » ያሉትን ስናጤን ለወደፊቱ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ግልጽ ይሆናል ።

በተለይም ፣

— ምርትን በማሳደግ ፣

Digitized by Google

— ለሸቀጦች ሥርጭት ሥርዓት መያዝ የማጓጓዣና የማከፋፈያ ለውታሮችን በመዘርጋትና በማጠናከር ፥

— በቁሳቁስና በሰው ኃይል ለጠቃቀም ቀንጅት እንዲኖር በማድረግ፥

— በጊዜና በአሠራር ቀንብር ረገድ አብዮታዊ ስልት በመቀየስና በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰገሰጉትን የግል ሀብት አምላኪዎች ለመመንጠር ከፍተኛና የተቀነባበረ ጥረት ማድረግ የያንዳንዱ አብዮታዊ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ተቋም ግደታና ኃላፊነት ሊሆን ይገባል ።

በመሠረቱ የመንግሥትና የሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማ የተያያዝነውን ለሶሻሊስታዊ ኢኰኖሚ መሠረት የመጣል ትግል በማፋፋም በተቻለ መጠን የሕዝቡን ፍላጐት ለማሟላት መጣር ስለሆነ ፥ በነዚህ ተቋሞች የሚሰጠው የንግድ አገልግሎት ተገቢ ያልሆነ ትርፍን የማካበት ዓላማ የለውም ። በነዚህ ድርጅቶች የሚገኘው መጠነኛ ትርፍ መልሶ የኅብረተሰቡን የጋራ ኑሮ ለማሻሻል የሚያግዝ እንጂ የግለሰቦችን ጥቅም የሚያዳብር አይሆንም ።

ስለዚህ አግባብ ያላቸው መንግሥታዊና ሕዝባዊ አካሎች ለንግዱ ክፍለ ኤኰኖሚ ሶሺያሊስታዊ ፊር መዳበር በተቀነባበረ ሥልት ከመቸውም የበለጠ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

መመሪያን በሚመለከት ፥

ወደ ሶሻሊስታዊ የንግድ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚደረገውን ጥረት ለማፋጠን ሕዝባዊና መንግሥታዊ ተሳትፎን ማሳደግ ብቻ በቂ አይሆንም ። ሶሻሊስታዊ የሸቀጥ ልውውጥን ለማካሄድ ተራማጅ የሆኑ የሥርጭትና የቁጥጥር መመሪያዎችን አዳዲስና የተጠናከሩ አስፈጻሚ መዋቅሮች የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል ። እነዚህንም በማስፈጸም ረገድ በተለይም የግል አምራቾችና ነጋዴዎች በገበያ ላይ ቀውስ እንዳያደርሱ ለመቆጣጠር የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በመከታተልና በመቆጣጠር ረገድ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ተሳትፎ በተሻለ ጥራትና ቅልጥፍና መቀጠል ይኖርበታል ። በዚህም አንጻር ዋጋ በመቆጣጠር ፥ ሕገወጥ ንግድን በማጥፋት ፥ የሶሻሊስታዊ የንግድ ዕድገት ሂደትን ለማደናቀፍ የተሰማሩትን በመመንጠር፥ ምዝበራንና ብኩንነትን በመዋጋት ወዘተ - - - ጥብቅ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል ።

ሌላው መሥመር ሊይዝ የሚገባው ጉዳይ የዋጋ ተመን ነው ። በአሁኑ ወቅት ዋጋዎች ከሸማቹ ገቢ ጋር ያልተዛመዱና ከአምራቹ ወጪና ምርታማነቱን ከፍ ከማድረግ አኳያ ያልተገመገሙ በመሆናቸው የሸምቶ አዳሪውን ክፍል ፍላጐት ለማርካት አልተቻለም ። ይህ የተዘበራረቀ የዋጋ ሁኔታ ተወግዶ የሸቀጦችና የሰብል ዋጋዎች በማዕከላዊነት መተመን ይኖርባቸዋል ። ሶሻሊስታዊ የዋጋ አሠራርን በመከተል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመሠረታዊ ሸቀጦች ተመን በማውጣት የሚፈለጉትን የምርት ዓይነቶች በሚፈለገው መጠን እንዲመረቱ ማድረግ የሚያስፈልግ ከመሆኑም በላይ ሠራተኛው ለምርት ውጤት ባበረከተው መጠን ሸቀጦችን ለማግኘት የሚችልበት መንገድ ከእቅድ ዝግጅቱ ጋር አብሮ መቀየስ ይኖርበታል ። ይህ በትክክል ሲፈጸም ነው ሶሻሊስታዊ የንግድ ግንኙነት በእርግጥ ሊሰፍን የሚችለው ።

ኢትዮጵያ ለልውውጥ በሚውሉ ሸቀጦች ረገድ ሙሉ በሙሉ ራሷን እስክትችል ድረስ ለፍጆታ የሚውሉና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለምርት ተግባር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከውጭ አገር ማስገባት ይኖርበታል ። ይህ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ የውጭ አገር ሸቀጦች በአገር ውስጥ ገበያ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ ። እንደአስፈላጊነቱም በምርት ተግባር ውስጥ በመቆየት አገልግሎት ስለሚሰጡ በምርቱ መጠን ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ።

Digitized by Google

ስለዚህ በአንድ መንገድ ወይም በሌላ የውጭ ንግድ የውስጥ ንግድን እንቅስቃሴ ይወስናል ። የተጽዕኖው ደረጃ በሚመጣው የዕቃ ዓይነት ፣ ዋጋ ፣ መጠንና በተለይ በም ርት ቅንጅት ውስጥ ምን ሚና እንዳለው የሚወስን ቢሆንም በአጠቃላይ በገቢ ንግድ ሳቢያ አብሮ የሚሰርገውን የዋጋ ቀውስ ለመ ከላከል ፣ በውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለውን ችግር ለመቋቋም ፣ እንዲ ሁም የሚያስፈልጉ የሸቀጥ ዓይነቶችን ከማ ካበት ለመከላከል ፣ በገቢ ንግድ የተጀመረው መንግሥታዊ ይዞታ በ፣ፋጠነ ሁኔታ ማደ ግና በተቻለ ፍጥነት ሙሉ ሞኖፖል ደረጃ መድረስ ይኖርበታል ። ለወደፊቱ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል ። ይሁን እንጂ በአ ጠቃላይ የሶሻሊስት ንግድ ግንኙነት ለመ ፍጠር የሚደረገው ጥረት በሌሎች የኤኮ ኖሚ ዘርፎች ከሚካሄዱት ሶሻሊስታዊ እንቅስቃሴዎችና በፖለቲካና በሶሻል መስ ኰች ከሚደረገው ትግል ተገንጥሎ ለብ ቻው የሚታይ አይደለም ። ስለሆነም በየግ ንባሩ የተያያዝነው ለሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ መሠረት የመጣል ትግል በማያቋ ርጥ ጥረት እየተፋፋመ መቀጠልና በየጊ ዜው የልማቱ ሥራ በተቀነባበረ እቅድ እየታቀፈና እየተመራ ተጠናክሮ መራመ ድ ለንግዱ ክፍለ ኤኰኖሚ መልክና ሥር ዓት መያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በፖለቲካውና በማኅበራዊ ጉዳዮች በኩ ልም በመካሄድ ላይ ያለው የመደብ ትግል መፋፋም ወሳኝነት ያለው ሲሆን ፣ በባህ ልና በቴክኒክ አብዮት የሚደረገውም እርምጃ የበለጠ ድጋፍ እንደሚሰጠው አያ ጠራጥርም ። እነዚህ ሁኔታዎች በሙሉ የተ ያያዙ በመሆናቸው በአንድ አቅጣጫ የተ ገኘው እመርታ የሌላውን ክፍል የዕድገት እንቅስቃሴ መፋጠንና መጠናከር እንደ ሚያግዝ ይታመናል ።

ምርትን አዳብሮ የሥርጭት መዛባትን አስተካክሎ ፍትሕን በተከተለ አሠራር ሸማቹ የሚፈልገውን ሸቀጥ በሚፈለግበት ቦታና ወቅት እንዲሁም ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ በማድረስ ፣ የሰፊውን ሕዝብ ፍላጐት በበለጠ ለማርካት ግለኝነትን አስወግዶ ሕዝ ባዊ አሠራርን ለመተካት ፣ በዝባዥና ተበዝ ባዥ መደቦችን በማጥፋት ሁሉም እንደየ ሥራው የልፋቱና የወዙ ባለቤት እንዲሆን፣ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ አመራር ወሳኝ መሆ ኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ የአገር ውስጥ ክፍለ ኤኮኖሚ ግምገማ ለ10 ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ ፣ 1974 አዲስ አበባ
2. ከላይ የተጠቀሰው
3. ከላይ የቀጠቀሰው
4. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳ ኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ ገጽ 58
5. የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ኢትዮጵያ ፣ ዓመታዊ የስታቲስ ቲክስ መጽሔት 1972 ፣ ገጽ 49
6. ከኢትዮጵያ የሀገር ውስጥ ማከፋፈያ ኰርፖሬሽን ከተገኘ መረጃ የተዘጋጀ 1975
7. ከላይ የተጠቀሰው
8. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳ ኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 131
9. ከላይ የተጠቀሰው

Digitized by Google

የባሕልና የቴክኒክ መሠረት ግንባታ በአብዮቱ ሂደት

— ፋሲል ተፈራ
— ከበደ ትኩ
— ዘውዴ ስርባር

ዘመናችን የሶሻሊስት አብዮት ዘመን ነው ። የሶሻሊስት አብዮት የፖለቲካ ሥልጣንን በሠራተኛው መደብ እጅ በማስገባት የሚጀምር ሲሆን ዋነኛ ተልዕኮውም አዲሱን ማለትም ሶሻሊስት ኤኮኖሚንና ኅብረተሰብን መገንባት ነው ። የሶሻሊስት ኤኮኖሚና ኅብረተሰብ ግንባታ የፖለቲካ ሥልጣንን ጨብጠው ካበቁ በኋላ በማግሥቱ ወይም በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሚከናወን ጉዳይ ሳይሆን እራሱን በቻለ ታሪካዊ የሽግግር ወቅት ውስጥ የሚካሄድ ተግባር ነው ። በዚህ የሽግግር ወቅት ማለፍ ለማንኛውም የሶሻሊዝምን ዕድገት ፈለግ ለተከተለ አገር ሁሉ ሊዘለል የማይችል ታሪካዊና አብዮታዊ ግዴታ ነው ። በየትኛውም አገር ይህንን የሽግግር ወቅት የሚገዙ አጠቃላይ ሕጐች አሉ ። ከእነዚህ አጠቃላይ ሕጐች መካከል አዲሱን ሶሻሊስታዊ ባህል የመገንባቱ ተግባር አንዱ ነው ።

ባህል ሲባል በኅብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ መላውን የሰው ልጅ የፈጠራቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶችና እንዲሁም እነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ የባህል ግንኙነቶች የተፈጠሩበትን ፣ ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትንና የሚተላለፉበትን ዘዴዎች ያጠቃልላል ። ቁሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅን ቁሳዊ ክንውንና ውጤቶችን የሚሸፍን መስክ ሲሆን ይህም የቴክኒክ መገልገያ መሣሪያዎችን ፣ የማምረት ልምድንና ሌሎችንም ቁሳዊ ሀብቶች በማጠቃለል ይይዛል ። መንፈሳዊ ባህል የሚባለው ደግሞ ሰዎች ቁሳዊ ምርትን በማምረት ሂደት የሚያመርቱትን የመንፈሳዊ ምርት መስክ ሲሆን ይህም እንደ ሳይንስ ፣ ትምህርት ፣ ሥነጥበብ ፣ ፍል

Digitized by Google

ስፍና ፥ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ባህላዊ
ቅርሶች ያጠቃልላል ። [1] እነዚህ የቁሳዊና
የመንፈሳዊ ባህል መስኮች የተነጣጠሉ ሳይ
ሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው ።
በመካከላቸው ባለው ግንኙነት ውስጥ
መንፈሳዊው ባህል ከቁሳዊ ባህል የሚመ
ነጭና በሱም የሚወሰን ይሁን እንጂ ፥
መንፈሳዊው በቁሳዊው ላይ ተመልሶ የራ
ሱን ተፅዕኖ ያሳርፋል ። ይኸው የቁሳ
ዊው ባህል ዕድገት ደግሞ ተመልሶ በተራው
የቁሳዊው ባህልን ዕድገት ያዳብራል ።

ከላይ ስለባህል ከቀረበው ሃሳብ ውስጥ
የባህል ፅንሰ—ሃሳብ ሰፊና በውስጡም የኅ
ብረተሰቡን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት
እንደሚያጠቃልል በቀላሉ መገንዘብ ይቻ
ላል ። ባጭሩ ባህል የሰው ልጅ ማኅበራዊ
ተግባር እንቅስቃሴ ውጤት የሆነ ታሪካዊ
ክስተት ነው ። ዕድገቱም የሚወሰነው በሶ
ሲዮ ኤኮኖሚ ቅንብሮች ተከታታይነት ነው።
የሶሲዮ — ኤኮኖሚ ቅንብሮች ተከታታይ
ነት ደግሞ የማኅበራዊ አብዮት ውጤቶች
ናቸው ። በተለይ በሶሻሊስት አብዮት የት
ኛውንም ዓይነት ጭቆናና ብዝበዛ ለአንዴና
ለመጨረሻ ጊዜ በማስወገድ ነፃነትና እኩ
ልነትን ለማስገኘት በዚህም ላይ መመሥ
ረት ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገት ለማስፈን የሚ
ካሄድ በመሆኑ ካለፉት የሶስዮ ኤኮኖሚ ቅን
ብር ለውጦች ሁሉ የተለየ ጥልቀትና ይዘት
ያለው ነው ። ስለዚህም በዚህ አብዮት
ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገትን
ለማስገኘት በኅብረተሰቡ ቁሳዊና ቴክኒ
ካዊ መስኮች ውስጥ ከሚካሄደው ሥር
ነቀል ለውጥ ጋር በባህሉም መስክ ተመ
ሳሳይ ለውጥ መካሄድ ይኖርበታል ።

የባህል አብዮት እንቅስቃሴ የሶሻሊስት
አብዮት አካል ሲሆን ይህም አዲሱን ሶሻሊ
ስት ባህል ለመገንባት በየመስኩ የሚካሄ
ደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚሸፍን
ነው ። የአብዮቱም ዋነኛ ዓላማዎች መላ
ውን የትምህርት ሥርዓት በአጭር ጊዜ
ውስጥ እንደገና ማዋቀርንና ባህላዊ ቅር
ሶች ለሰፊው ሕዝብ ግልጋሎት እንዲውሉ
በማድረግ ሰፊው ሕዝብ ኤኮኖሚያዊ ፥ ባህ
ላዊና ፖለቲካዊ ሕይወቱን በማስተዳደር
በኩል የሚኖረውን ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረ
ጋገጥ ፥ ሶሻሊስት ምሁራንን በጥራትና በብ
ዛት ማፍራትና አዲስ ሶሻሊስት ባህል መገን
ባት ናቸው ።[2] የሶሻሊዝም ግንባታ እንደየ
አገሩ ታሪካዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች መለ
ያየት የተነሳ የተለያዩ ባሕሪያት ሊኖሩት
ቢችልም የእነዚህ ከፍ ሲል የጠቀስናቸው
የባህል አብዮት ዋነኛ ዓላማዎች ተግባራዊ
መሆን በግንባታው ሂደት ውስጥ ለየትኛ
ውም አገር ቢሆን አግባብነት ያላቸው
ግዴታ ናቸው ።

ሶሻሊስት ባህል ያለሶሻሊስት አብዮት
ሊፈጠር አይችልም ። የሶሻሊስት አብዮት
መሠረታዊ መንስኤ በካፒታሊዝም ውስጥ
በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነት መካ
ከል የሚፈጠረው ቅራኔ መካረር ሲሆን የዚ
ህም ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ገጽታ በም
ርት ማኅበራዊ ባሕሪና በክፍፍል ግላዊ ባሕ
ሪ ይገለጻል ። በመሠረቱ የሶሻሊስት አብ
ዮት መሠረታዊ ተልዕኮ የፖለቲካ ሥል
ጣንን ከቡርዧው በመንጠቅ በዚህ ኃይል
መሣሪያነት የምርት ኃይሎችን ዕድገት
አፍኖ በቆየው አሮጌ የምርት ግንኙነት ላይ
አብዮት ማካሄድ ነው ። የምርት ግንኙነቶች
አጠቃላይ ድምር የኅብረተሰቡን የኤኮ
ኖሚ መዋቅር የሚያጠቃልል ስለሆነ በዚህ
መስክ የሚካሄደው ለውጥ ከሞላ ጎደልም
ቢሆን በጠቅላላው በኅብረተሰቡ መንፈሳዊ
ሕይወት ላይ ለውጥ ማስከተሉ የማ
ይቀር ነው ። እዚህ ላይ የለውጡን ጠባይ
በሚመለከት መታወስ የሚገባው አንድ
ነጥብ አለ ። ይኸውም ካርል ማርክስ «ለፖ
ለቲካ ኤኮኖሚ ሂስ አስተዋጽኦ » በሚለው
ጽሑፉ ፥

እነዚህን ለውጦች በሚመለከት ምን
ጊዜም ቢሆን በተፈጥሮ ሳይንስ ትክክ
ለኛ ስሌት ሊወሰኑ በሚችሉት በምርት

Digitized by Google

> ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ቁሳዊ ለውጥና በፖለቲካ፣ በፍልስፍና ፣ በውበት . . . ባጭሩ ሰዎች ያሉትን ግጭቶች ለው ቀው ትግል በሚያካሒዱባቸው ርዕ ዮተዓለማዊ ቅርጾቹ መካከል ልዩነት መደረግ አለበት ፤[3]

በማለት መንፈሳዊ ባህል በቁሳዊ ሁኔታዎች የሚወሰን ይሁን እንጂ በኅብረተሰቡ ቁሳዊ ሕይወት ውስጥ የተካሄደው ለውጥ በመንፈሳዊው ሕይወት ላይ ወዲያውኑ በማከታተል ለውጥን ሊያስገኝ እንደ ማይችል ያስገነዘበው ፍሬ ሃሳብ መዘንጋት የለበትም ።

ስለሆነም ሶሻሊስት ባህል ያለ ሶሻሊስት አብዮት ከቶውንም ሊፈጠር የማይችል መሆን የባህል አብዮቱን የሶሻሊስት አብዮት አስፈላጊ አካል ያደርገዋል ። በተጨማሪም የባህል አብዮት ድንገተኛና ቅጽበተኛ ክንዋኔ ሳይሆን ረዥም ጊዜ ፣ አድካሚና ጥንቃቄ የተመላበት ሥራን እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድርጅትን የሚጠይቅ ተግባር ነው ። ከዚህም በላይ ለአዲሱ ሶሻሊስት ባህል መነሻ መሠረት የሚሆን ሰፊና ጠንካራ ቁሳዊና የቴክኒክ መሠረት ያስፈልጋል ። ይህም መሠረት በኤኮኖሚው የተለያዩ መስኮች ውስጥ ሶሻሊስት የንብረት ይዞታን ለመፍጠር በሚካሄደው የምርት ግንኙነት አብዮት አማካኝነት ይፈጠራል ። በአጠቃላይ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር በተሟላ ሁኔታ ግንባር ቀደም በመሆን ሊያስተባብርና ሊመራ የሚችለው ደግሞ የማሌ ፓርቲ እንደሆነ ግልጽ ነው ።

የምርት ግንኙነት አብዮት በማካሄድም ብዝበዛና ጭቆና ይወገድና በምትኩ እኩልነትና ነፃነት ይሰፍናል ። ይሁንና የሕዝቦች ነፃ መውጣት ብዝበዛንና ጭቆናን በማስወገድና ሕጋዊና ፖለቲካዊ እኩልነትን በማጐናጸፍ ብቻ ሳይወሰን አዲሱን ሶሻሊስት ባህል በመገንባት ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገትን ማስገኘት ይኖርበታል ። ስለዚህም በተደረገው የምርት ግንኙነት ለውጥ ሳቢያ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ከሚካሄደው የተፋጠነ የኤኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጠናከረ የባህል አብዮትን ማካሄድ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ የማይታለፍ ግዴታ ይሆናል ።

ሶሻሊስት ኅብረተሰብን በተሟላ ሁኔታ ለመገንባት እንዲቻል የባህል አብዮትን ማካሄድ አስፈላጊነት ከተመለከትን ዘንዳ ከዚሁ ጋር አያይዘን መመልከት የሚገባን አንድ መሠረታዊ ቁም ነገር አለ ። ይህም የምርት ግንኙነት ለውጥ አሮጌውን የምርት ግንኙነት ሙሉ በሙሉ በጣጥሶ የማስወገድ ጠባይ ያለው ሲሆን የኅብረተሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ግን ከኤኮኖሚ መሠረቱ አንፃራዊ ነፃነት ያለውና ከመለወጥ አንፃርም የዕድገት ተከታታይነት ባሕሪ ያለው መሆኑን መገንዘብ ነው ። የዚህ ፍሬ—ሃሳብ በትክክል መጤን በአዲሱ ሶሻሊስት ባህል ግንባታ አንፃር መወሰድ ያለበትን ትክክለኛ ፖሊሲ ለመንደፍና በተግባራዊ ክንዋኔ ወቅትም ተገቢና ወቅታዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያስችላል ። በተጨማሪም አስፈላጊ ያልሆኑ ስህተቶች እንዳይፈጸሙ በቅድሚያ ለመከላከል እንዲቻል ይረዳል ።

የባህሉን መስክ የተለየ ባሕሪ አስመልክቶ በቅጡ መጤን እንዳለበት የተገለጸው ቁም ነገር ሶሻሊስት የባህል አብዮትን ከማካሄድ እንቅስቃሴ አኳያ የሚኖረውን ትርጉም ተመልክቶ ማለፉ ጠቃሚነት አለው። የሶሻሊስት ባህል ግንባታ በቡርዧው ሥርዓትም ሆነ ከዚያ በፊት የሰው ልጅ በመላው ታሪኩ ውስጥ በማኅበራዊ ተግባሩ አማካኝነት ያከማቻቸውን የባህል ቅርሶች ሙሉ በሙሉ የሚደመስስ ሂደት ሳይሆን ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ይዘቶቻቸውን በሙሉ በመውሰድ አጣጥሞ በማዋሐድ ወደ ከፍተኛ ባህላዊ ዕድገት ደረጃ የማሽጋገር ሂደት ነው ። ሌኒን ይህ ተግባር በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ፣ « ካፒታሊዝም ከኋላ ትቶ ያለፈውን ባህል በሙሉ ወስደን ሶሻሊዝምን እንድንገነባበት ይገባል ። የካፒታ

Digitized by Google

ሊዝምን መላውን የሳይንስ ፣ የቴክኖሎጂ ፣
የዕውቀትና የኪነጥበብ ቅርሶች መውሰድ
አለብን ። ያለእነዚህ ኮሚኒስት ኅብረተሰ
ብን መገንባት አይቻለንም ፤»[4] በማለት
ገልጾታል ። በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ሌኒን
ይህንኑ ፍሬ ሀሳብ በማጠናከር ኮሚኒስቶ
ችን ሲያስጠነቅቅ ፣

> አዲሱን ሥርዓት የቡርዧው ዓለም
> በአተረፈልን ማቴሪያሎች በመጠቀም
> ለመገንባት ካልቻላችሁ ጨርሶ ልትገ
> ነቡት አትችሉም ፤ ኮሚኒስቶች መሆና
> ችሁ ይቀርና ተራ ጥራዝ ነጠቆች ትሆ
> ናላችሁ ። ለዚህም ምክንያቱ ሶሻሊዝ
> ምን የመገንባት ዓላማችን ሳይንሱን ፣
> ቴክኖሎጂውንና ባጠቃላይ ካፒታሊ
> ስት ሩሲያ ያስቀረችልንን ማንኛው
> ንም ቅርሶች በተሟላ ሁኔታ በግልጋ
> ሎት ላይ ማዋል ስላለብን ነው ፤[5]

ብሏል ።

እስከ አሁን ድረስ ሶሻሊስት ባህል ለመገ
ንባት ከዚህ በፊት በነበሩት ባህላዊ ቅርሶች
ላይ መወሰድ ያለበት አጠቃላይ አቋም ተመ
ልክተናል ። ይሁን እንጂ አዲስ የሚገነባው
ሶሻሊስት ባህል በርዕዮተዓለም ይዘቱም ሆነ
በማኅበራዊ ተግባሩ ከቡርዧ ባህል ዓይነተኛ
ልዩነት የለውም ማለት አይደለም ። ባህል
በየትኛውም ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ኅብ
ረተሰብ ውስጥ በርዕዮተዓለማዊ ይዘ
ቱም ሆነ ተግባራዊ ዓላማዎቹ የመደብ ጠ
ባይ አለው ። ስለሆነም የኅብረተሰብ ባህል
ሁለት ባህሎችን ማለትም የበላይነቱን ይዞ
የሚገኘውን የቡርዧ ባህልና የጭቁኑ ሰፊ
ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሶሻሊስት ባህል
ይዘቶች ይገኙበታል ። ይህ በመሆኑም በቡ
ርዧው ኅብረተሰብ ባህልና የቡርዧው
ማለትም የበላይነቱን በያዘው መደብ ባህል
መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ መመልከቱ
በሶሻሊስት የባህል አብዮት እንቅስቃሴ
ሂደት ውስጥ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ
ነው ። አዲሱን ሶሻሊስት ባህል ለመገንባት
የሚካሄደው የባህል አብዮት መሠረታዊ
ይዘትና ሰፊው ሕዝብ የቡርዧውን ኅብረተ
ሰብ ባህል ጠንቅቆ በማወቅ ጠቃሚ የሆኑ
ትን ቅርሶች በሙሉ በመውሰዱ ባህልን ከሰ
ፊው ሕዝብ መጨቆኛ መሣሪያነት ወደ
እራሱ ነፃ መውጫ መሣሪያነት የመለወጥ
ተግባር ነው ። ይህንኑ የባህላዊ ለውጥ እን
ቅስቃሴ አስመልክቶ ታላቁ የወዝ አደር
መሪ ሌኒን ሲጽፍ ፣

> ባለፉት አርጌ ዘመናት በሰው ልጅ
> ዕውቀትና አእምር የተፈጠረው የቴክ
> ኖሎጂና የባህል ጥቅሞች ለጥቂቶች
> ግልጋሎት ብቻ እንዲውሉ የተደረገ
> ሲሆን ፣ ሌሎችን ግን ከመሠረታዊ
> ፍላጉቶች ፣ ከትምህርትና ፣ ከዕድገት
> አገልሏቸው ነበር ። ከዛሬ ጀምሮ ማናቸ
> ውም የሳይንሳዊ ፈጠራዎችና የባህል
> ውጤቶች ባለቤትነት የመላ ሀገሪቷ
> በመሆናቸው ከእንግዲሁ የሰው አእ
> ምር ውጤትና ዕውቀት ዳግም ለጭቆና
> ናና ለብዝበዛ ጨርሶ አይውሉም ፤[6]

በማለት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ
ሂደት ውስጥ የባህል አብዮትን ግብ ግልጽ
አድርጎ አሳይቷል ።

ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር ታሪ
ካዊ ግዴታነት ለካፒታሊስትም ሆነ ለቅ
ድመ—ካፒታሊስት ኅብረተሰቦች በሩሲያ
የተካሄደው ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት
አብዮት በዘመናችን የተከሰተ ዓይነተኛ
ባሕሪ ነው ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው
ባህላዊ ዕድገት የሶስዮ ኤኮኖሚ ቅን
ብር ተከታይነት ውጤት በመሆኑ የባህል
አብዮት መካሄድ ከቅድመ—ካፒታሊስት
የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃዎች ካፒታ
ሊዝምን በብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብ
ዮት ውስጥ በማሳለፍ ወደ ሶሻሊዝም
በመሸጋገር ላይ ላሉ አገሮች ታሪካዊ ግዴ
ታነት ያለው ተግባር ነው ። ይሁንና በዚ
ህም ሁኔታ የባህል አብዮት ማካሄድ
አስፈላጊና ግዴታ ቢሆንም ከካፒታሊ
ዝም ወደ ሶሻሊዝም ከሚደረገው ሽግግር

Digitized by Google

ጋር ሙሉ ፀሙሉ የባሕሪ ተመሳሳይነት የለውም ።

የሶሻሊዝም ግንባታ ከፍተኛ የምርት ኃይሎችን ዕድገት የሚሻ በመሆኑና ይህ ደግሞ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ አስቀድሞ የሚፈጠርና ዳብሮ የሚገኝ በመሆኑ እንደነዚህ ዓይነቶቹ አገሮች ውስጥ ወዝ አደሩ የፖለቲካ ሥልጣን ከቡርዧው ነጥቆ ሲያበቃ የምርት ግንኙነት አብዮትን በማካሄድ ብቻ የባህል አብዮት ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑትን የቁሳዊና የቴክኒክ መሠረቶች በቀላሉ ሊያመቻች ይችላል ። ከቅድመ— ካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ በካፒታሊዝም ዕድገት ደረጃ ውስጥ ሳይታለፍ ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ሽግግር ግን ሁኔታው ከዚህ ለየት ያለ ባሕሪ አለው ። ለዚህም ዋነኛ መንስኤው በእነዚህ አገሮች ፣ መካከል የደረጃ ልዩነት ሊኖር ቢችልም ፣ በአጠቃላይ የምርት ኃይሎች ዕድገት ዝቅተኛና ኋላ ቀር ሆኖ መገኘቱ ነው ። አስቀድመን እንደተመለከትነው የባህል አብዮት ጠንካራ የቁሳዊና የቴክኒክ መሠረት ከመፍጠሩ ተግባር ተነጥሎ ለብቻው የሚካሄድ እንቅስቃሴ አይደለም ። በታዳጊ አገሮች ይህ የቁሳዊና የቴክኒክ መሠረት ደካማ አሊያም ጨርሶ ኋላቀር ነው ። በደካማ የቁሳዊና የቴክኒክ መሠረት ላይ የተካሄደ የምርት ግንኙነት አብዮት ደግሞ ብቻውን በቂ ነው ሊባል አይችልም ። በዚህ አንፃር ጓድ ሊዱዋን በቬየትናም በጊዜው የነበረውን ሁኔታ በማስመልከት ለአዲሱ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የተሟላ ግንባታ ሶስቱ ማለትም የምርት ግንኙነት ፣ የቴክኒክና የባህል አብዮቶች በተደጋጋፊነት ተጣምረው መካሄድ እንዳለባቸው ሲገልጽ ፣ « አዲሱ ኅብረተሰብ ፣ አዲሱ ሰው ፣ አዲስ የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይሎች የአንዱ አብዮት ብቻኛ ውጤቶች ሳይሆኑ የሶስቱም የጋራ ውጤቶች ናቸው፤ »[7] በማለት ሥርነቀልና የተሟላ የኅብረተሰብ ለውጥ በሶስቱም አቅጣጫዎች የሚካሄድ አብዮት አጠቃላይ ድምር መሆኑን አስገንዝቧል ። ስለዚህ ከኋላቀርነት ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ወቅት በቴክኒክ መስክ የሚካሄደው አብዮት ከምርት ግንኙነቱና ከባህሉ አብዮት ጋር እንዴት መቀነባበር አለበት ? ይህስ በምን መንገድ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ያፋጥናል ? የሚሉት ጥያቄዎች ዋነኛነት አላቸው ።[8] በመሆኑም ሰፊው ሕዝብ በቅድሚያ በሚጨብጠው የፖለቲካ ሥልጣን አማካኝነት በሚያካሂደው የምርት ግንኙነት አብዮት የሚፈጥረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የቴክኒክ አብዮትን ማካሄድ ያስፈልጋል ። የቴክኒክ አብዮት ከምርት ግንኙነት አብዮት ጋር የተዛመደ ነው።በመካከላቸውም ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አላቸው ። የምርት ግንኙነት አብዮት ለተፋጠነ የቴክኒክ ዕድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል ። በቴክኒኩ መስክ የሚካሄድ አብዮት ደግሞ ለምርት ግንኙነቱ አብዮት በጠንካራ ማቴሪያላዊ ምሥረታ ላይ መመሥረት የበለጠ ጥንካሬና ጥልቀት ያስገኝለታል ። ለአዲሱ ኅብረተሰብ ጠንካራ የቁሳዊና የቴክኒክ መሠረት ከመጣሉ ሂደት ጋር በማያያዝ የባህል አብዮትን ማካሄዱ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ለግንባታው የበለጠ ፍጥነትና ጥንካሬ ይሰጠዋል።በዚህም የባህል አብዮት ክንውን አማካኝነት በኅብረተሰቡ ውስጥ ተንሠራፍተው የቆዩትን ኋላቀር አድኀሪ አስተሳሰቦችንና ልማዶችን በማስወገድ ሳይንሳዊ አመለካከቶችንና ሃሳቦችን በሕዝቡ ውስጥ በማስራጨትና እንዲሠረጹም በማድረግ ፣ የሕዝቡን የፈጠራ ችሎታ በመቀስቀስ ፣ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲያፈልቅና እንዲያዳብር በማድረግ ወደ ከፍተኛ ባህላዊ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማስቻል ያስፈልጋል ።

እስካሁን ድረስ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከቅድመ ካፒታሊስት የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃዎች በመነሳት ሶሻሊስት ኅብረተሰብን ለመገንባት በሚካሄደው ሽግግር ውስጥ የባህልና የቴክኒክ መሠረት የመ

Digitized by Google

ገንባቱ ተግባር እጅግ ዋነኛነት ያለው ይሁን
እንጂ በቴክኒኩ መስክ የሚካሄድ አብዮት
የመሪነቱን ሥፍራ ይይዛል ። በመሆኑም
በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ለአዲሱ ሶሻሊስት
ኅብረተሰብ ግንባታ የሚያስፈልጉት የቁ
ሳዊና የቴክኒክ መሠረቶችን የመፍጠሩና
የማዳበሩ ተግባር በመሠረቱ የወሳኝነት
ሚና ይኖረዋል ። ይህ ሲደረግ ብቻ ነው
የሠራተኛው ሕዝብ ኅብረተሰብ አመራር
እንዲሁም የሶሻሊስት ኤኮኖሚ ሊጠናከርና
በአስተማማኝ ሊገነባ የሚችለው ። በተጨ
ማሪም ኅብረተሰቡ ጊዜው ካለፈበት ኋላ
ቀር ጉታች አስተሳሰቡና ልምዱ ነፃ ሊሆ
ንና ሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ሊጠናከር የሚ
ችለው ። እንዲሁም ለኅብረተሰቡ በቂ ቁሳ
ዊ ባህል ቀርቦለት የተፈጥሮና የራሱ ባለ
ቤት ሊሆን የሚችለው እራሱን ከባህልና
ቴክኒክ ኋላ ቀርነት በማላቀቅ የአዲሱን ሶሻ
ሊስት ኅብረተሰብ የባህልና የቴክኒክ መሠ
ረት በመጣሉ ሂደት ውስጥ ነው ።

የኢትዮጵያ ሁኔታ ከባህልና ከቴክኒክ መሠረት ግንባታ አንፃር

ከላይ እንደቀረበው ባህል ሰፋ ብሎ ሲታይ
ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸው ቁሳዊ፣ ቴክ
ኒካዊና መንፈሳዊ ይዘቶች አሉት ። ይ
ህም ዘርዘር ብሎ ሲተነተን ባህል የኅብረ
ተሰብ ሕይወታዊ እንቅስቃሴዎችን— ማለ
ትም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ የማመን
ጭነት ፣ የፈጠራ ፣ የማግኘትና የዲዛይን
ማውጣት ችሎታዎችን ፣ የኪነ ጥበባት የዕ
ድገት ደረጃዎችን ፣ የሥራ ምርታማነትና
የአመራረት ዘዴዎች ቅልጥፍናን ፣ የምርት
ውጤቶችና የተፈጥሮ ሀብቶች ክፍፍል ፣
ስርጭትና ልውውጥ ሥርዓቶችን ይይዛል ።
ከዚህም አልፎ ባህል የፖለቲካ ፣ የአስተዳ
ደርና የአኗኗር መዋቅሮች የጊዜ አጠቃቀም
ሥርዓትን ፣ ምኞቶች ፣ ተስፋዎችንና የመ
ሳሰሉትን የኑሮ ውጤቶችን የያዘ ሕይወት
ያለው ስብስብ ነው ። ሲጠቃለል ባህል የሰ
ዎች የሥራ ውጤትና ሰዎች ከሌሎች እንስ
ሶች የሚለዩበት መደበኛና ዓይነተኛ
ምልክታቸው ፣ የየወቅቱ አኗኗራቸው ነፀ
ብራቅ ፣ ድምራዊ የይዘት ክምችት ያለው
ክስተት ነው ። [9]

ባህል ከሚንፀባረቅባቸው ድርጅቶች መካ
ከል ትምህርት፣የጤና አጠባበቅ ፣ የሕዝቦች
አሠፋፈር ፣ የከተሞች አቀራቀርና መስፋ
ፋት ፣ የፖለቲካ መዋቅሮች ፣ ሳይንስና ቴክ
ኖሎጂ ፣ ኢንዱስትሪና እርሻ የትራንስፖር
ትና መገናኛ ዘዴዎች፣ኪነጥበባት ፣ የምርት
ክፍፍል ፣ ስርጭትና ልውውጥ የመሳሰሉት
ይገኙበታል ። የነዚህን ድርጅቶች የዕድ
ገት ሂደትና ደረጃ ማጥናት የተጠቃሚዎቻ
ቸ ውንና የገንቢዎቻቸውን ሕዝቦች የባህል
ሁኔታ ማወቅ ያስችላል። ይህም ማለት የት
ምህርት ሥርዓት ተፈጥሮን በቁጥጥር ሥር
ለማዋልና ለመጠቀም የሚያስችል ዓላማ
ይዘት፣ መዋቅርና የአፈጻጸም ዘዴዎች መያ
ዙን መገምገም ያስፈልጋል ። በጤና
በኩል ኅብረተሰቡ በሽታን ለመከላ
ከል ፣ ከተያዘም ለመዳን ያለው የሰው
ኃይል ፤ የድርጅትና የቁሳቁስ መሟላት
ሁኔታን ማጥናት ይገባል ።ጊዜን ለሥራና
ለዕረፍት ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓ
ትና ልምድ መኖሩን መመልከት ያሻል ።
ለኪነ ጥበባት ፤ ለቴክኒክና ሙያ ዕድገቶች
አስፈላጊ መዋቅሮች መኖራቸውን ማጤን
ይገባል ። የልዩ ልዩ የአገልግሎት ድርጅ
ቶችን ደረጃ መመልከት ያስፈልጋል።ለልዩ
ልዩ የምርት ተቋሞች ተገቢ የአመራረት
ዘዴዎች ፣ የምርት መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች
ድርጅቶችና የሰው ኃይል መገኘቱ መጠናት
አለበት ። በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ የግን
ዛቤ ፣ የአስተሳሰብ ፣ የአመለካከትና የተግ
ባራዊ ችሎታ ደረጃ መገምገም ይኖርበ
ታል ።

ከዚህ በመነሳት አብዮታዊት ኢትዮጵያ
ካለፈው ሥርዓት የወረሰችው የቴክኒክ
ና የባህል ኋላቀርነትና ከአብዮቱ ፍንዳታ
ወዲህ እነዚህን ሁኔታዎች ለመወጣት
የተፈጠሩትን አመቺ ሁኔታዎች ማቅረብ
ተገቢ ይሆናል ።

Digitized by Google

የቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የኅብረተሰብ
ባህል በኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት
የፊውዶ — ቡርዧው ሥርዓት ነፀብራቅ
እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ። ይህም
ሲባል በፊውዳሉ ሥርዓት ማይምነት እጅግ
በጣም የሰፈነበት ፣ ኢሳይንሳዊ እምነት ፣
ልማድና አሠራር የተስፋፉበት ፣ የአገልግ
ሎት ተቋሞች ያልተስፋፉበት፣ የአመራረት
ዘዴዎችና መሣሪያዎች በግብርናም ሆነ
በኢንዱስትሪው በጣም ኋላቀር የሆኑ
በት ፣ ምርት በእርሻ ላይ ያተኮረበት የም
ርት ክፍፍሉ በመኳንንቱና በደጋፊዎቻ
ቸው ላይ በይበልጥ ያተኰረ ነበር ማለት
ነው ። ከሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ
ጀምሮ በደባልነት ሲያድግ የመጣውም የቡ
ርዧው ሥርዓት ገና ያልዳበረ ፤ የትምህርት
የጤና አጠባበቅ ፣ የአመራረት ዘዴዎች ፣
የማምረቻ መሣሪያዎች፣የፖለቲካና የአስተ
ዳደር መዋቅሮች በደንብ ያልተዘረጉበትና
ተሟልተው ያልታዩበት ነበር ። ሆኖም
የፊውዳሉ ሥርዓት እያረጀ ፣ እየሞተና
እየበሰበሰ ሲሄድና የቡርዧው ሥርዓት
መሠረቱን እያጠናከረ ሲመጣ የሳይንስና
ቴክኖሎጂ ባህል አቅጣጫ በመጠኑም
ቢሆን ይህንኑ ፈር የተከተለ እንደነበር
ይታወቃል ። ሆኖም የእርሻ ሥራ በመጠኑ
ሜካናይዝድ እየሆነ መምጣቱ ፣ የጉጂና
ሌሎች እንዱስትሪዎች መቋቋማቸውና ቁጥ
ራቸው መጨመሩ ፣ የንግድ ተቋሞች
መስፋፋታቸውና የአሠራር ውስብስብነታ
ቸው ከፍ ማለቱ ፣ የመድንና የባንክ ድር
ጅቶች በግለሰቦች መቋቋም መደራጀትና
መስፋፋት መጀመራቸው፣ የትምህርት ሥር
ዓትና አገልግሎት ወደዚሁ አቅጣጫ ማም
ራቱ የሚያፈራውም የሠለጠነ የሰው ኃይል
ውስን ሆኖ መቆየቱ የዚሁ ሁኔታ ምልክ
ቶች ነበሩ ።

የምርት ግንኙነቶች በአብዮታዊ ሂደት
በተፋጠነ ሁኔታ እንደሚለወጡ ተደጋግሞ
ተረጋግጧል ። የባሕል ዕድገት ግን አዝ
ጋሚ ይዘት ባለው ላይ መገንባት እንደ
ሚኖርበት ታላቁ ምሁር ሌኒን አስተ
ምሯል ። [10] ይህም እውነታ በድኅረ አብ
ዮት ኢትዮጵያ በትክክል እየታየ ነው ።

ከአብዮታችን ፍንዳታ እስከ ኢ.ሠ.ፓ.
አ.ኮ. መከሰት ድረስ ሥር ነቀል ለውጦች
ብመደረጋቸው ሰፊው ሕዝብ አዲስ አኗኗር
ውስጥ ገብቷል ። የፊውዳል ሥርዓት ከሥሩ
ተመንግሎ ወድቋል ። የአብዮቱ የፖለቲካ
መመሪያ የሆነው ሶሻሊዝም ጉልህ ሆኖ
ወጥቶ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ትግል
በመካሄድ ላይ ነው ። የገጠሩ መሬት ለተገ
ቢው ባለቤት ለገበሬው ተመልሶአል ፤
የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር ተቋ
ቁሞ ከአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበር
ወደ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በመ
ሸጋገር ላይ ይገኛል ። የማምረቻና የማከፋ
ፈያ ፣ የባንክና የመድን ድርጅቶች በመን
ግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነዋል ። ከዚህም ጋራ
የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርና
ሌሎች የሙያ ማኅበሮች ተጠናክረዋል ።
የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በሕዝብና በመ
ንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመሆናቸውም በላይ
የከተማ ነዋሪዎች በከነማት ተደራጅተዋል ።
የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማ
ዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ተቋቁሞ
በተከታታይ በዕቅድ በተካሄዱት የምርትና
የባህል ዘመቻዎች አማካይነት ከፍተኛ
የአሠራር ለውጦች የዕቅድ አዘገጃጀትና አፈ
ጻጸም ስልቶች ፣ አዲስ ልምዶች ተቀስመ
መዋል ። ማይምነትን ለማስወገድ በተወሰ
ዱት ጠቃሚ እርምጃዎች አማካይነት ሰፊ
ው ሕዝብ ማንበብ ፣ መጻፍና ማስላት ከመ
ቻሉም በላይ የፖለቲካና የርዕዮተዓለም
ንቃቱ ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል ። ከኑሮ
ውና ከሥራው ጋራ የተዛመደ የድኅረ መሠ
ረተ ትምህርት ፕሮግራም እንዲከታተል
በመደረጉም የአመራረት ስልቱና ዘዴ
ው ፣ ጤናውና አኗኗሩ መሻሻል እየታየበት
ነው ። የመደበኛ ትምህርትም በአቅጣጫና
በመመሪያ ፣ እንዲሁም በመሣሪያዎች ዝግ
ጅት አማካይነት ንድፈ ሃሳብና ተግባር ያዋ

Digitized by Google

ሃደ ፣ በንቃትና በልማት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ለመተለም ጥረቶች በየአቅጣጫው እየተደረጉ ነው።በኪነጥበባትም በኩል አዲስ የሙዚቃ ፣ የሥዕል የድራማ ፣ የፊልም ፣ የሥነ ጽሑፍ ፣ ሥነድርሰት ይዘቶች አቆጥቁጠዋል ። በአጠቃላይ ሲታይ ለገበሬው ከመሬት ባለቤትነት ጋራ የምርጥ ዘር (አትክልትና እንስሳትን) ማግኘት የማምረቻ መሣሪያዎች ተሻሽለው መቅረብና የንቃት ከፍ ማለት ለቴክኒክ መሠረት ግንባታ የተሻሉ ሁኔታዎች ተፈጥረውለታል ። የኢንዱስትሪ ሠራተኛውም ከሥራ የመወገድ ሥጋትና ጭንቀት ስለቀረለት ፤ ንቃቱም ከፍ ስላለ ፣ የባህልና የቴክኒክ ዕድገቶች አቅጣጫ ይዘዋል ለማለት ይቻላል ።

ከኢሠፓአኮ መቋቋም ወዲህ ከላይ የተዘረዘሩት የሥራ ፕሮግራሞች ተጠናክረው እንዲከናወኑ ከፍተኛ የአመራርና የአፈጻጸም ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል ። አዳዲስ ዕቅዶች እስከ ግብ ደረጃ ተተንትነው በመቅረባቸው ለአፈጻጸምና ለግምገማ አመቺ ሆነዋል ። [11]

የርዕዮተዓለማዊ ሥርጭትም በመመሪያም ሆነ በትምህርት መሣሪያዎች አቀራረብ በጣም ተጠናክሯል ። በድርጅታዊ መዋቅር በኩልም ከነማት መጠናከራቸው ፣ ኢኢሴማና ኢኢወማ መቋቋማቸው ፣ የመኢገማ ሶስተኛና የመኢሠማ ሁለተኛ ጉባኤዎች መካሄዳቸው ለሕዝባዊ ዴሞክራሲና ለሶሻሊዝም ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ መደረጉ በግልጽ ይታያል ። በአሥር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ አማካይነት ከአጭር ጊዜ ዕቅድ ወደሩቅ ግብ መሸጋገር የአብዮታዊት ኢትዮጵያን የምርትና የአገልግሎት ተቋሞች ዕድገት በሳይንሳዊ መንገድ ለመምራት እንደሚቻል ይጠበቃል ።[12] የሠርቶ አደሩን ቁጥጥር ኮሚቴ ያቋቋመው አዋጅና ለቁጥጥር ሥራ የሚያስፈልጉ እርምጃዎች መወሰዳቸው ወደ አዲስ ሕዝባዊ ባህል የሚያሸጋግሩ ሁኔታ መፈጠሩን ያመለክታል ። ይህም ሲጠቃለል ከኢሠፓአኮ መቋቋም ወዲህ ለሶሻሊስታዊ የባህልና ቴክኒክ ግንባታ መሠረቶች መጣላቸው ግልጽ ሆኖ ይታያል ።

የሰፊው ሕዝብ ንቃት ፣ ሳይንሳዊ አመለካከት ፣ የፈጠራና የቴክኒክ ችሎታና የሥራ ወዳድነት ግምገማ

ከላይ የተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች በግልጽ ያስገነዘቡት አድኃሪ በሆኑ የምርት ግንኙነቶች ዕድገታቸው ተጉትቶ የነበሩት የምርት ኃይሎች በሶሻሊስታዊ አመራርና አሠራር በተፋጠነ እርምጃ ወደፊት ለመገስገስ አመቺ ሁኔታ የተፈጠረላቸው መሆኑን ነው ።

በኢትዮጵያ የምርት ኃይሎች የዕድገት መነሻ እስካሁን የተደረሰባቸውን የባህል ለውጦችና ግንባታዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች በማስማማት መጠቀም ነው ። በዚህም በመቀጠል አዲስ ግኙቶችና ፈጠራዎችን ወደ ተግባራዊነት በመለወጥ ሥራ ላይ ማዋል ይሆናል ። ይህም ማለት የመጀመሪያው የምርት ኃይሎች የዕድገት እርምጃ ያደጉና የበለጸጉ አገሮች የተጠቀሙባቸውና ያጠናከሩዋቸው ግንዛቤዎች ፣ አመለካከቶች ፣ ተግባራዊ ችሎታዎችና መሣሪያዎች ለሀገር ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚስማሙ አድርጉ ማቅረብና በጥቅም ላይ ማዋል ይኖርበታል ። ከዚህም ቀጥሎ የዕውቀት አድማስን በማስፋት በምርምር የሚመነጩና የሚፈጠሩ ፣ በስርፀት የሚጠነከሩና ወደ ተግባራዊነት የሚሸጋገሩ ግኝቶች ፣ ዕውቀቶች ፣ መሣሪያዎች በየወቅቱ ለሠርቶ አደሩ ከተስማሚ ዘዴዎች ማለት ሙያና ዕውቀት ፣ ድርጅት ፣ አመራር መሟላታቸውንና በሥራ ላይ መዋላቸውን ከትትል ማድረግ ይሆናል።ይህም ሂደት የሥራ ምርታማነትን ከፍ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው ። [13]

እንግዲህ ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው ከአድኃሪ የምርት ግንኙነቶች ለተላቀቁ የም

Digitized by Google

ርት ኃይሎች ሶሻሊስታዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ባህል ሚና የተሟላ ዕድገት የሚያስከትል መሆኑን ነው ። ስለሆነም ሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ በርዕዮተ ዓለሙ ሥርጭትና ግንዛቤ በአዲስ የትምህርት ሥርዓት በተለይም በመሠረተ ትምህርት ዘመቻና በአዲስ ሕዝባዊ አደረጃጀት አማካይነት የሶሻሊስት ባህል መቅሰም መጀመሩ በመጠኑም ቢሆን እየተከሰተ ነው ። በሌላም በኩል አዲሱ ባህል ሥር ሰድዶ ተጨባጭ ለመሆን ጊዜ ስለሚያስፈልገው ማለትም የአዝጋሚነት ባሕሪ ስላለው ተፈላጊና ተገቢ አዎንታዊ ለውጦች በቅጽበት ለማስገኘት አለመቻሉ እየታዩ ነው ። ከነዚህ ተቃራኒ ሁኔታዎች በመነሳት የባህልና ቴክኒክ መሠረት ግንባታ ኋላቀርና አድኃሪ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ከማስወገድ ፣ ከትምህርትና ከሥነጥበባት መስፋፋት አንፃር ከኢሠፓአኮ መቋቋም ወዲህ የደረሱበት ደረጃ ግምገማ ከዚህ በታች ቀርቦአል ።

ኋላቀር አድሀሪ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ከማስወገድ አንፃር

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢሠፓአኮን መቋቋም በሚመለከት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ንግግር ባደረጉበት ጊዜ «የኢሠፓአኮ ዋነኛ ተልዕኮ በሰፊው ሕዝብ መካከል የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ ይበልጥ ማሠራጨትና ፓርቲውን ማደራጀት ሲሆን አባሎቹ የፓርቲ አሠራርን የሚለማመዱበትም ትምህርት ቤት ነው ፤ » ብለው ነበር ። ይህንኑ መሠረታዊ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛው መደበኛ ስብሰባ «የርዕዮተዓለም ስርጭትን በሚመለከት » የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፎ ነበር ።

1. ኢሠፓአኮ በተጣለበት ታሪካዊ ኃላፊነት መሠረት በመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ መካከል ያልተከለሰና ያልተበረዘ የወዛደሩን ርዕዮተዓለም በስፋትና በጥልቀት ለማሠራጨትና የግንባታውን ምዕራፍ በሚገባ ለማራመድ በሠርቶ አደሩ ' ሕዝብ መካከል የሚካሔደው ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ሥራ እንዲጠናከር ፣
2. ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ለማሠራጨትና የመደብ ትግሉን ለማራመድ ሬዲዮ ቴሌቪዥንና ጋዜጦች - ወዘተ . . . ማለትም የሕዝብ የዜና ማሠራጫ ዘደዎች ዓይነተኛ መድረክ እንደመሆናቸው ፕሮግራማቸው የተያያዝነውን የመደብ ትግል ለማፋፋም የኢኮኖሚ ግንባታውን በተለይም የምርት ግንኙነቱን ለውጥ ለማፋጠን የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ምርታማነት ለማሳደግና የአድህሮት ኃይላትን ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳ ለማከሸፍ በሚያስችል ይዘት ተጠናክሮ እንዲቀየስ ፤ [14]

ይኸው ጉባኤ በትምህርት አማካይነት የርዕዮተዓለም ሥርጭትና ግንዛቤ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጠው ሌላ ውሳኔ አስተላልፎአል ። በተጨማሪም የውይይት ክበብን በሚመለከት ፣

1. ሠርቶ አደሩ ንቃተ ሕሊናውን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም እየዳበረ በየሥራውና በየትግሉ ዘርፍ አብዮታዊ ተሳትፎውን ለማሳደግ እንዲበቃ አስፈላጊው እገዛ እንዲደረግለት ፣
2. የሠርቶ አደሩን ፓርቲ ለመመሥረት በሚደረገው ትግል የኢሠፓአኮ ተልዕኮ እንዲሳካ ተገቢውን እገዛ ለማድረግ አዲስ የውይይት ክበብ አሠራር መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሁሉ ለኢሠፓአኮ አመራር ሙሉ ትብብርና ድጋፍ እንዲያደርግ ፣ [15] የሚል ውሳኔ

አስተላልፎ ነበር ።

ከነዚህ መሠረታዊና ግልጽ መመሪያዎች በመነሳት ልዩ ልዩ ተግባሮች ተከናውነዋል ። የጽሑፍ ዝግጅትና ሥርጭት እየተሟላ መሄድ ፣ የውይይት ክበብ መመሪያ

Digitized by Google

መውጣት ፣ ለውይይት ክበቦች የትምህርት አርእስት በማዕከላዊ ደረጃ ተዘጋጅተው መላክ ፣ የ« ሠርቶ አደር » ጋዜጣ እና የ« መስከረም » መጽሔት በየወቅቱ ለውይይት ክበብ አባሎች መቅረብ ፣ ለመደበኛ ተማሪዎች የሚሆኑ የርዕዮተ ዓለም የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት መደረጉ ፣ ለአዲስ አንባቢያን የሚሆኑ መጽሐፎች ተዘጋጅተው መሠራጨታቸውና በሥራ ላይ መዋላቸው ለርዕዮተ ዓለም ሥርጭትና ግንዛቤ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ። የኩራዝ አሳታሚ ድርጅትም የሚያሳትማቸው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጽሐፎች ብዛትና ዓይነት እየጨመረ እንዲሄድ ፣ በአማርኛ ቋንቋ እንዲቀርቡና በየክፍለ ሀገሩ እንዲሠራጩ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው ይገባል ። በተጨማሪም ልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎችም ለርዕዮተዓለም ሥርጭት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

ከሌላ አንፃር ሲታይ የርዕዮተዓለም ትምህርት አቀራረብና የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በጥንቃቄ መመልከት ያሻል ። ይህም ማለት በውይይት ክበቦች ውስጥ የትምህርቱ አሰጣጥ የሚያመረቃ ሆኖ አባላትን የሚስብ ነው ወይ ? የአባላትን የአመለካከትና የአስተሳሰብ ሁኔታዎች ለመለወጥ ችሏል ወይ ? በተከታታይ ሁለት ሰዓት ማስተማሩ ከፔዳጐጂስ አንፃር ምን ያህል ትክክለኛ ነው ? እስካሁን የተካሄደውን ሥራ ለመገምገም ምን ጥረት ተደርጓል ? የሚሉ ጥያቄዎችን በጥሞና መረዳት ይገባል ።

በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት አማካይነት ሊቀርብ የሚገባው የርዕዮተ ዓለም ሥርጭትና ግንዛቤም በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል ። ይህም ሲባል የተጀመረው የመጻሕፍት ዝግጅትና የመምህራን ሥልጠና ዕቅድ መከናወን እንዳለበት ለማመልከት ነው ። ምክንያቱም የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ያቀፈው የርዕዮተ ዓለም ትምህርት ቀጣይነቱ ፣ ተከታታይነቱና ፔዳጐጂካዊ ዕድገቱ የተሟላ መሆን እንዳለበት ስለሚታወቅ ነው ። ከዚህም በላይ በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉት ወጣቶች ሁለንተናዊ ስብእና ሊኖራቸው ስለሚገባና የርዕዮተዓለም ትምህርት ለዚሁ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል ።

የልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች (ጋዜጦች ፣ ሬድዮ ፣ መጽሔቶች ፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ...) ለርዕዮተዓለም ስርጭትና ግንዛቤ መዋላቸው እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን አያጠራጥርም ። ሆኖም የአቀራረብ ስልትና ዘዴ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል ። በዚሁም ከፍተኛ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መደልደል ተገቢ ይሆናል ።

ት ም ህ ር ት

ትምህርትን ለሰፊው ሕዝብ በማዳረስና ይዘቱን ሶሻሊስት ፈር ማስያዝን በሚመለከት የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ፡—

1 በትምህርት መልክ የማሊ ትምህርት በሁሉም ደረጃ እንዲሰጥ ፣

2 የመምህራን ርዕዮተዓለም ከፍ ማድረግ ወደ መምህርነት የሚገቡ የሰፊውን ሕዝብ ወገናዊነትን የተቀበሉ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ፣

3 የሳይንስና ቴክኖሎጂ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት በተጠናከረ መልክ እንዲሰጥ ፣

4 የሥራ ባሕልን ለማዳበር ት/ ቤቶች የሥራ ማስኪያ ወጭያቸውን ለመሸፈን እንዲችሉ ፍሬያማ በሆኑ የማምረት ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ፣

5 የሚሰጠውን የመሠረተ ትምህርት ርዕዮተዓለም ጥራት በማጠናከር ዘመቻውን ይበልጥ ማጉልበት - የድኅረ መሠረተ ትምህርት ፕሮግራሞች ተጠናክረው እንዲካሔዱ ፣[16] የሚሉ ውሳኔዎችን ማስተላለፉ ይታወሳል ።

በሶሻሊዝም ግንባታ ሂደት ውስጥ የትምህርት ዓላማ ከሀገሪቱ የሠለጠነ የሰው ኃይል

Digitized by Google

ፍላጐት አኳያ በሙያ ሠልጥኖ ሰፊው ሕ
ዝብ ተግባራዊ ችሎታ እንዲጨብጥ የሚያ
ደርግ፣ የተፈጥሮ አካባቢውንና በኅብረተሰ
ውስጥ የሚገኙ ግንኙነቶችን ለመገንዘብና
ለመተንተን እንዲበቃ የአእምሮ ሥልጠና፣
በአካሉ ብቁና ከሥራ ውጪ የሚኖረውን
ጊዜ ለአካሉ ፣ ለአእምሮውና ለመንፈሱ
ርካታ በሚያስገኙ ፕሮግራሞች ላይ ለማሳ
ለፍ የሚቻል በተሟላ መልኩ የሠለጠነ
ሰው እንዲሆን የሚያደርግ መሆን ይኖር
በታል ። ይህም ሲባል ትምህርት በአንድ
በኩል የግለሰብን ሁለንተናዊና የተሟላ
ዕድገትና ሶሻሊስታዊ አመለካከት የሚያ
ንጽ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው ሕ
ዝብ ከሚታገልለት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ
ና የሶሻል ዓላማዎች በመመንጨት በመገን
ባት ላይ ያለውን የሶሻሊስት ኅብረተሰብ
ፍላጐቶች ማሟላት ነው ።

ባጠቃላይ ትምህርት የማኅበራዊ ምርትን
ለማስገኘት የሚችል ሰው ከማፍራት አልፎ
በሁለንተናዊ ዕድገታቸው የዳበሩ ሰብአዊ
ፍጡሮችን ለማስገኘት በሳይንስ ላይ የተ
መሠረተ የምርት ሥራን ፣ የአካል ብቃት
ንና ትልጥፍናን የሚያስገኝ የሥራ ፍቅርን
ለመንግሥትና ለጋራ ሀብት እንክብካቤ ማ
ድረግን የሚያስተምር፣ ወግ አጥባቂ አስተ
ሳሰቦችን በማስወገድ በአዳዲስና ጠቃሚ
አስተሳሰቦች ለመተካት (ይኸውም አርጌ
ነገሮችን ፣ ሥርዓቶችን ፣ ሃሳቦችን ፣ የሥራ
ዘዴዎችንና አርጌ ልምዶችን) የሚያበቃ
መሆን ይገባዋል ። የኮሚኒስት ትምህርት
ዓለማም ጠንካራ ዲሲፕሊንና ሰብአዊ የስ
ነምግባር ጠባዮችን ለማዳበር (ይኸም ወላ
ጆችን፣የትዳር ጓደኛን ፣ ልጆችን ማፍቀር፣
በዕድሜ የገፉትን ማበከርን ያጠቃልላል)
ኑሮን በቀላሉ ለመምራት ፣ በጠባይም
ሁል ጊዜ ትሁት ለመሆን የሚረዳ መሆን
ይኖርበታል ።

የሶሻሊስት ትምህርት አሰጣጥ አጠቃ
ላይ ፖሊቴክኒክ ትምህርትና የትኩረት
መስክ ትምህርት በሚባል በሁለት ይከፈ
ላል ።

በኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ ምክንያት ማይ
ምነትን በማጥፋት ብሎም በንቃትና
ኑሮን በማሻሻል ላይ ያተኮረ መሠረተ ትም
ህርት ይሰጣል ።

አጠቃላይ ፖሊቴክኒክ ትምህርት
ደግሞ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች ማለ
ትም አጠቃላይና ፖሊቴክኒክ የሚባሉ
አሉት ። አጠቃላይ ትምህርት የኅብ
ረተሰብ አባላት በሙሉ የሚሳተፉ
በት፣ ከባህል መስኮችና ከሳይንስና ቴክ
ኖሎጂ የተውጣጡ መሠረታዊ ዕውቀቶ
ችን ፣ አመለካከቶችንና ተግባራዊ ችሎታ
ዎችን ማንኛውም የኅብረተሰብ አካል የሚ
ያገኝበት፣ለሁለንተናዊና ለተሟላ ዕድገት
መሠረት ነው። የአጠቃላይ ትምህርት ፅንሰ
ሃሳብ በቡርዧው ኅብረተሰብ የተጀመረ ቢሆ
ንም ሙሉ በሙሉ በትክክል በተግባር ሊ
ውል የቻለው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ብቻ
ነው ። የፖሊቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና
ዓላማ ተማሪዎችን በምርት ሂደት ውስጥ
በማስገባት በዘመናዊ የአመራረት ስል
ትና ዘዴ ማስታጠቅ ነው ። የፖሊቴክኒክ
ሥልጠና ተማሪውን ስለ ምርት መገልገያ
መሣሪያዎች አጠቃላይ መሠረታዊ ዕውቀ
ቶችንና ችሎታዎችን እንዲያገኝ ሲያስች
ለው ፣ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ደግሞ ለሥ
ራ ትክክለኛ አመለካከት ፣ ሥነ ምግባር ፣
ተራማጅ አስተሳሰብ እንዲኖረውና ትክክ
ለኛ የሶሻሊስት ሰው እንዲሆን ያደርገ
ዋል ። አጠቃላይ ፖሊቴክኒክ ትምህርት
ለልዩ ሙያ ለትኩረት መስክ ትምህርት
መሠረት ነው ። የትኩረት መስክ ትምህ
ርት ዓላማ በአንድ በተወሰነ ትምህርት
መስክ ተፈላጊውን የሠለጠነ የሰው ኃይል
ማፍራት ነው ። ይህም በመለስተኛ ፣ በመ
ካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ሊሆን ይች
ላል ።

Digitized by Google

የሀገሪቱ የትምህርት ይዘት ለምርታማነት ከፍ ማለት ቀጥተኛ ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎች ሊሙሉ በሚችሉ መሠረታዊ የዕውቀትና የሳይንስ ዘርፎች ይኸውም በሶሻል ሳይንስ (ሶስዮሎጂ ፥ አንትሮፖሎጂ፥ ኢኮኖሚክስ ፥ ሶሻል ሳይኮሎጂ ፥ ፖለቲካል ሳይንስ ፥ የማቴሪያሊዝም ፍልስፍና ፥ወዘተ . . . (በተፈጥሮ ሳይንስ) ሚካኒካል ፥ ኬሚካል ፥ ማይንንግ ፥ ኤሌክትሪካልና ሲ ቪ ል ም ህንድስና፥ ጂኦሎጂ ፥ኬሚስትሪ ፥ ባዮሎጂ ፥ የእርሻ ሳይንሶች) የእነዚህ ዘርፎች ተዛምዶ እና የምርት መገልገያ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም (ቴክኒኮች) ላይ ያተኮረ እንዲሆን በየደረጃው ጥረቱ ይበልጥ መቀጠል ይኖርበታል ። የሀገሪቱ የትምህርት ይዘት ስብስብ ባለ አገላለጽ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ብቃትና ቅልጥፍናን ማሻሻል የሚችሉ ቴክኖሎጂስቶችን ፥ መሬትና ከዚህ ጋር አብረው የሚሄዱ የምርት መገልገያዎች ምንነትና ባሕርያት በመተንተንና ሊሙሩ የሚችሉ የእርሻ ኤኮሎጂስቶች ፥ የምርት መገልገያዎችን ተዛምዶንና ትንጅትን ጠንቅቆ በማወቅ ማኅበራዊ ሥራን በማደራጀትና በመምራት የሠርቶ አደሩ ግብ ከሆነው የሶሻሊዝም ግንባታ አኳያ አሻገረው በዓይነ ሕሊናቸው በማየት ደረጃ በደረጃ ውጤት ለማስገኘት ብቁ አመራር መስጠት የሚችሉ ሙያተኞችን ማፍራት ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ። ይህ ደግሞ ትምህርት በሠራተኛው መደብ ከፍተኛ ድርጅት (ፓርቲ) መመራትን ይጠይቃል ። ኅብረተሰቡን ደግሞ ከማይምነት አላቆና የአጠቃላይ ዕውቀት ደረጃው ከፍ እንዲልና ያላወቀውን እንዲያውቅ የአጠቃላዩንና የመሠረተ ትምህርቱን ይዘት መዋቅርና ፕሮግራም ይበልጥ ማጠናከር ይገባል ።

መሠረተ ትምህርት

የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ከሐምሌ 1971 ጀምሮ በዘመቻ በመከፋፈል በሥራ መተርጐም ከተጀመረ ጀምሮ ሦስት ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸው የሥራ ክፍፍሎች እንዲኖሩት ሆኖ ተዋቅሯል። እነዚህም

1. የማይምነት ማጥፋት ፕሮግራም
2. ማይምነት እንዳያገረሽ የማጠናከሪያ ፕሮግራም
3. የድኅረ መሠረተ ትምህርት ፕሮግራም

ናቸው ።

ማይምነትን በማጥፋት በኩል ሰባት የዘመቻ ዙሮች ተፈጽመው ስምንተኛው በመካሄድ ላይ ይገኛል ። እስከ አምስተኛው ዙር መጨረሻ ድረስ 11,787,020 ማይማን ለመማር ተመዝግበው 5,406,395 ፈተናውን በማለፍ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ የማይማን ብዛት ወደ 55.2 % ዝቅ ብሏል።የስድስተኛውና የሰባተኛው ዙር ስታትስቲካዊ መረጃዎች ሲጠናቀሩ ይኸው ቁጥር እንደገና ዝቅ እንደሚልና በሰባት ዓመታት ማይምነት ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት የወጣው ዕቅድ እንደሚፈጸም ተገምቷል ።

ማይምነት እንዳያገረሽ የማጠናከሪያ ፕሮግራም በሚመለከት እስከ አምስተኛው ዙር መጨረሻ 2,800 የንባብ ቤቶች አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸው የሚያበረታታ ሁኔታ ነው ። ከዚህም በላይ በልዩ ልዩ ርዕሶች የተዘጋጁ ጽሑፎች ለንባብ ቤቶች መሠራጨታቸው ፥ ሌሎች ደግሞ ለኅትመት መቅረባቸው የሚነበብ መጽሐፍ ችግር በመጠኑም ቢሆን ያስወገደዋል ። ይኸው ጥረት ግን መቀጠል ይኖርበታል ።

የድኅረ መሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ለማጠናከር በቤተሰብ ኑሮ ፥ በኅብረት ሥራ፥ በጤናና በአፈር ሀብት አጠባበቅ ላይ ያተኮሩ ስድስት መጽሐፎች ተዘጋጅተው ለአዲስ አንባቢያን ቀርበዋል ። ግብርና ፥ ጤናና የቤተሰብ ትምህርቶችን የሚያጠቃልሉ ፕሮግራሞች በትምህርት ሚኒስቴር በሚካሄዱ 11 የሬዲዮ ጣቢያዎች ይተላለፋሉ ። መሠረተ ትምህርትን ያጠናቀቁ ጐልማሶች ወደ መደበኛ ትምህርት በመዛወር በማታና

Digitized by Google



በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ተቋሞች በማበብ ላይ ከሚገኙት የንባብ ቤቶች መካከል አንዱ

በቀን ገብተው እንዲማሩ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው።በየገበሬ ማኅበራት የተመረጡ ጐልማሶችም በጐልማሶች ማሠልጠኛ ጣቢያዎች በልዩ ልዩ ሙያዎች እንዲሠለጥኑ በማድረግ ፣ የሠለጠኑትን ወደ ገበሬ ማኅበራቸው በመመለስ ሌሎችን በማሠልጠንና ሙያቸውን በማራባት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እየተሞከረ ነው ። በቅርብ በተቋቋመው የተስማሚ ቴክኖሎጂ ማዕከል የተሻሻሉ ቁሳቁሶች ለመሥራት ተሞክሯል ።

በሌላ አንፃር መሠረተ ትምህርት ለብቻው የቆመ ፕሮግራም እንዳይደለ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል ። ይህም ማለት ፕሮግራሙ ለወቅታዊ ችግር መፍቻ ሆኖ ለዘለቄታዊ ግን ከመደበኛ ትምህርት ጋር እንዲዋሃድ ማድረግ ጥሩና ዘላቂ መፍትሔ እንደሚሆን አያጠራጥርም ።

መደበኛ ትምህርት

በ6,256 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 2,373,427 ተማሪዎችበ 37,272 መምህራን አማካይነት በትምህርት ገበታ ላይ ለመገኘት ችለዋል ። ይህም ከ1966 ከነበሩት የተማሪዎች ቁጥር ጋራ ሲነፃፀር ዕድሜያቸው ከ7—12 ዓመት ክልል ሆኖ መማር ከሚገባቸው ሕፃናት ከ19% ወደ 47% ከፍ እንዲል አድርጐታል ።

በዕድሜ ክልል ከ13—14 ዓመት መካከል ያሉ 248,652ተማሪዎች ፣ በ813 መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተቋሞች በመማር ላይ ይገኛሉ ። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ወጣቶች 16.4% የትምህርት ዕድል እንዲዳረሳቸው ለማድረግ ተችሏል ማለት ነው ።

በ192 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዕድሜያቸው ከ15—18 ዓመት የሆኑ 237,353 ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ናቸው ። በዚሁ መሠረት ከጠቅላላው በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት

Digitized by Google

8.6% ትምህርት ያገኙ ሲሆን ይህ ከ 1966 ጋር ሲነፃፀር ዕድገት አሳይቷል ።

በቴክኒክ ትምህርት ረገድ ዕድገት በማሳየት 7 ትምህርት ቤቶች በመጨመር በጠቅላላው በ19 ተቋሞች 5,119 ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ ። ለ2,500 መምህራን የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ተሰጥቷል ። የሥራ ትምህርትን ለማስተላለፍ ማለት የዛፍ ተከላ እና የውሃ አጠቃቀም ትምህርት ለመስጠት ተሞክሯል ። የሥርዓተ ትምህርቱን የማርክሲስት ሌኒኒስት የትምህርት ፈር ለማስያዝ ጥረት ተደርጓል ።

በከፍተኛ ትምህርት በኩል በፖሊቴክኒክ ፣ በከብት ሀብት ልማትና በንግድ ሥራ ተቋሞች ፣ በእርሻ መለስተኛ ኮሌጆች ፣ በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ፣ በቅድመና ድኅረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞች 14,985 ተማሪዎችና 1,137 መምህራን ይገኛሉ ።

ይህ ዘርፍ ዕድገት አሳይቷል ። ነገር ግን በአፈጻጸም ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ችግሮች አልተወሱም ። በአጠቃላይ ትምህርት የፖሊቴክኒክ ፅንሰ ሐሳብ መሠረታዊ ሆኖ ቀርቧል ። የዚህ ፅንሰ ሐሳብ ተግባራዊነት የፖሊሲ ድጋፍ ማለትም ዓላማዎችን ፣ ይዘትን ፣ መዋቅርንና የማስፈጸሚያ ሁኔታዎችን ፣ እንዲሁም የመምህራንና የመማሪያዎች መሟላትና የአምራች ድርጅቶች መተባበር ሲገኝ ብቻ ነው ። እነዚህም ሁኔታዎች በአሁኑ ጊዜ ተሟልተው ይገኛሉ ለማለት አያስደፍርም ። በሌላም በኩል የመምህራን ተማሪዎች መጣኔ በመምህራን ቁጥር ማነስ የተዛባና የሥራው ጭነት ከፍተኛ በመሆኑ በትምህርት ጥራት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ እያደረገ ነው ። የከፍተኛ ትምህርትም ቢሆን በመምህራን ጥራትና ብዛት ፣ በትምህርት መማሪያዎች (ሕንፃዎች) መሟላት አጥጋቢ አይደለም ። በሌላም በኩል ለአብዛኛው ሕዝብም የትምህርት ዕድል አልደረሰም ።

ኪነ ጥበብ

ከታሪክ አንፃር ሲታይ ኢትዮጵያ ቀደም ብለው እርሻ ፣ የከብት ርባታና መንደር ቆርቁረው መኖር ከጀመሩት ፣ የከተማ ሥልጣኔ ከመሠረቱት ፣ በመካከለኛው ዘመን በኪነ ጥበባት ፣ በፍልስፍናና በፖለቲካ ከምችት ካሏቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ በመሆንዋ የሀገራችን ባህል የራሳችን ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝብ ባህል ነው ። ሆኖም አድኀሪው ሥርዓተ ማኅበር ይህን ባህል ለማዳበር ባሕሪው የማይፈቅድለት ስለነበር ዕድገቱን አቀጨጨው ።

ከየካቲት 1966 ወዲህ በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ ምቹነት የሶሻሊስት ባህል እንቅስቃሴ በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛል ። የዚህ ባህል ግንባታ አካሄድ ሶስት ገጽታዎች አሉት ። በዲሞክራሲያዊ ገጹ ለኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ባህል እኩል የዕድገት መድረኮችን ያዘጋጃል ፤ በብሔራዊ ገጹ ብሔራዊ ባህል ይገነባል ፤ በሳይንሳዊ ገጽታው ከአሮጌው ተራማጁን በመውሰድና እንደተገቢነቱ አዲስም በመጨመር ዓለም አቀፋዊነትን ያራምዳል ፣ ሰብአዊነትን ያበለጽጋል ፣ የመፍጠር ችሎታን ያዳብራል ፣ ረቂቅ ጥበብን ያንፀባርቃል ።

ኪነጥበብ የአንድ ሀገር ባህል ከሚገለጽባቸው ፈርጆች አንዱ ገጽታ ሲሆን ፣ እሱም ሙዚቃን፣ ሥዕልን ፣ ምስልን፣ ሥነ ጽሑፍን ሥነ ግጥምን ፣ ሥነ ድርሰትን ቲአትርን ፣ ዳንስንና ሲኒማን ወዘተ ... ያጠቃልላል ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ወጣቱን በሚመለከት ካሳለፋቸው ውሳኔዎች አንዱ ፣

> ወጣቱን ከልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ ኃይላት ቲዎሪያዊና ፖለቲካዊ ውኾንብር እንዲሁም ከባሕል ወራሪዎች በመከላከል በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ታንጸ ራሱን ለወዝአደራዊ ሥነ ምግባር እንዲያስገዛ በማድረግ ረገድ የተጠ

Digitized by Google

ናከረ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ እንዲከናወንና ለዚሁም የሚያገለግሉ የንባብ ቤቶች ፣ መጻሕፍት ፣ አብዮታዊ ፊልሞች ፣ ወዘተ ... የመሳሰሉት ሁሉ በተቻለ አቅም የሚገኙበት ዘዴ ሁሉ ተፈልጐ ተግባራዊ እንዲሆን ፣ [17] የሚል ነበር ።

ይህም ተተኪው ትውልድ በሶሻሊስት ባህል ታንጾ እንዲያድግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የኪነጥበባት ሚና ምን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው ።

ለምሳሌ ከኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በኋላ በአዲስ አበባው ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት 167,236 ሰዎች ብቻ ሊስተናገዱ ሲችሉ ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ 12 መጻሕፍት ቤቶች በሰው ኃይልና በመጻሕፍት ለማጠናከር ተሞክሯል ። 179,363 ሰዎች ብቻ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ድራማ ለመመልከት ሲበቁ ፣ 1,106,967 ሰዎች ሲኒማ (ፊልም) በመመልከት ትርፍ ጊዜያቸውን ሊጠቀሙበት ችለዋል ። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በማጥናት ሥነ ጽሑፍን ለማዳበር እንዲቻል በልዩ ልዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ፊደላት ተቀርጸዋል ፣ የልዩ ልዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ሥነ ልሳንም እየተጠና ነው ። በልዩ ልዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎች መዝገበ ቃላት በመዘጋጀት ላይ ናቸው ።

ከላይ እንደተመለከተው በኪነ ጥበባት ዘርፎችም ሆነ መጻሕፍትን በመመርመር የትርፍ ጊዜ በትክክል በመጠቀም ረገድ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ዕድል የራቀ መሆኑን እንገነዘባለን ። በመሠረቱ ይህ በዚህ ሁኔታ ላይ መገኘቱ ራሱ በሀገራችን የሶሻሊዝም ግንባታ ምን ያህል ከባድ መሆኑን የሚያስረዳ ቁም ነገር ነው ። የኪነ ጥበቦቹ የዕድገት ደረጃን ማየቱ ነጥቡን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል ።

በሀገሪቱ ውስጥ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ የሙዚቃ ፣ የዳንስ ፣ የቴያትር ፣ የሥዕልና የመሳሰሉት የኪነጥበብ ምርቶች ታሪካዊ ይዘቶች የኢትዮጵያን አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚመሩ ውስጣዊና የአካባቢ ሁኔታዎች በመቅረጽ በዚህ ትውልድ እየተከናወነ ያለውን ታሪካዊ ድርጊት በመጠኑም ቢሆን እያንጸባረቁ ነው። በባህላዊ ይዘታቸውም ቢሆን የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችን ኪነ ጥበብ ውጤቶች በማቅረብ በይዘቱ ዓለም አቀፋዊ ለሆነው ለብሔራዊ ሶሻሊስት ባህል ግንባታ አስተዋጽኦ እያደረጉ ናቸው። በጥበባዊ ይዘታቸውም ኅብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ቴክኒክ በሥራ ላይ በመተርጐም ላይ ይገኛሉ ።

ባጠቃላይ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ዘርፎች ምንም እንኳ በብዙ መቶ ዘመናት የሚቆጠር ዕድሜ ቢኖራቸውም በሙያውም ሆነ በአማተር ደረጃ ዕድገታቸው የፈካና የተዝናና አይደለም።የዘርፎቹ ዕድገት በሳይንስ ላይ የተመሠረተ ይዘታቸውም የኅብረተሰቡን አጠቃላይ ታሪክ ፣ ባህልና ውበት በሚገባ በማንጸባረቅና በመምራት ሠራተኛው የእረፍት ጊዜው የራሱን የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብርበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይህም በዚህ አብዮታዊ ትውልድ ትከሻ ላይ ያረፈ ሌላው ኃላፊነት ነው ።

የቴክኒክ መሠረት ግንባታ

ከላይ እንደተጠቀሰው ከየካቲት 66 ጀምሮ የምርት ግንኙነቶችን በመለወጥ የተወሰዱ ሥር ነቀል ርምጃዎች ለምርት መገልገያ መሣሪያዎችና ለተፈጥሮ ሀብት ልማት አመቺ ሁኔታዎች እየፈጠሩ ናቸው ። ለዚህም የፊውዶ ቡርዧው ሥርዓተ ማኅበር ያራምዳቸው የነበሩ ኋላቀርና ዕድገት ገቺ አስተሳሰቦች ፣ አመለካከቶችና ተስፋዎች ዕድገትን በሚጋብዙና በሚያራምዱ የሶሻሊስት ባህል ገጽታዎች የመተካቱ ጉዳይ

Digitized by Google

አመለካከቶችና ተስፋዎች ዕድገትን በሚ
ጋብዙና በሚያራምዱ የሶሻሊስት ባህል
ገጽታዎች የመተካቱ ጉዳይ በኢሠፓአኮ
መከሰት ይበልጥ እየተጠናከረ ይገኛል ።
የፊውዶ ቡርዧውን ስልተ ምርት በሶሻሊ
ስት ስልተ ምርት ለመተካት በሚደረግ አጠ
ቃላይ እንቅስቃሴና ዝርዝር ፕሮግራሞች ው
ስጥ ደግሞ በሀገሪቱ የቴክኒክ መሠረት ላይ
አብዮታዊ ድሎችን ማስገኘት ወሳኝ ነው ።
ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከአድኃሪ መደቦችና
ከተፈጥሮ ጋር በሚያደርገው ትግል በአሸ
ናፊነት እንዲወጣ የቴክኒክ ችሎታውን
ማዳበር ይኖርበታል ። ስለዚህ የተጀመረ
ውን ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ መሠ
ረት የመጣል ትግል እንዳይጨናገፍ የካፒ
ታሊዝም አዋላጅ የሆኑ ባለው የሥራ ምር
ታማነት አማካይነት የኅብረተሰባችንን የቁ
ሳዊና መንፈሳዊ ደረጃዎች ዓይነትና ጥረት
የሚጠቁሙ የባህል ሁኔታዎችን ከማስወ
ገድ ጐን አነስተኛ የሸቀጥ ምርት በሶ
ሻሊስት ምርት እንዲተካ የምርት
ግንኙነት ለውጡን ማፋፋም አለብን ። የሶ
ሻሊስት ሥልጣኔ በር ከፋች ሌላው ቁልፉ
ችን ለሆነው ለሀገሪቱ የቴክኒክ መሠረት
ደረጃና ዕድገት ተገቢውን ትኩረት መስ
ጠት የሀገራችን የሶሻሊስት ግንባታ ፍላ
ጐት ነው ። ይህን ፍላጐትና ሐሳብ ወደ
ተጨባጭነት ለመለወጥ ደግሞ የኅብረተ
ሰባችን ታሪክ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘመናት
በምርት መገልገያዎች አኳያ ባጠቃላይ ከፋ
ፍለን የምንገኝበትን የቴክኒክ ደረጃ በቅጡ
ማጤን መቻል ይኖርብናል ።

> ... ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘመናትን
> ለመለየት የሚያበቁን ቁሳቁሶች
> እንደተና በምን መሣሪያዎች እን
> ደተሠሩ እንጂ ቁሳቁሶች ራሳቸው
> ለይደሉም ። የምርት መገልገያ መሣ
> ሪያዎች የሰው ሥራ በምን ዓይነት
> ማኅበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ እየተካ
> ሄደ መሆኑን የሚያስገነዝበን አመል
> ካቾቻችን ነው ፤ [18]

ሲል ታላቁ የወዝ አደር ምሁር ማርክስ
በሥራ ላይ የሚውሉ ቁሶች፥ ትክክለኛው
ማኅበራዊ ድርጅት ከተፈጠረ ፥ በአንድ
ኅብረተሰብ ሕይወት ውስጥ ዩሥራ ምርታ
ማነትን፥ምቾትንና ደስታን በመወሰን ረገድ
የሚጫወቱትን ሚና በግልጽ አስቀም
ጦታል ።

በዚህ አኳያ በሚቀጥሉት ገጾች ሀገራችን
በእርሻ ፥ በከብት ርባታ ፥ በማዕድንና ኃይል
አገኛኘት በኢንዱስትሪና ዕደ ጥበባት ፥ እን
ዲሁም በትራንስፖርት በምን የቴክኒክ ደረ
ጃና ዕድገት ላይ እንደምትገኝ እንመለከታ
ለን ።

እርሻና ከብት ርባታ

የኢሠፓአኮ የማዕከላዊው ኮሚቴ ሁለ
ተኛ መደበኛ ስብሰባ የሽግግሩን ወቅት ኢኮ
ኖሚ ሕግጋትንና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሚገ
ኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመሥረት
የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የጥሪት ክምችት
ምንጭ የመሆኑን ሚና በሚገባ እንዲጫ
ወት ችሎታውን ከፍ እንዲያደርግና የካፒ
ታሊዝም ዕድገትን ለመከላከል የገበሬዎች
አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማቋ
ቋም ፥ የደን ሀብትን ማልማትና የተሻሻሉ
መሣሪያዎችና አገልግሎቶች ማቅረብ እን
ደሚገባ ውሳኔ መስጠቱ ይታወሳል ። [19]

በመሠረቱ የኢትዮጵያ እርሻ የተበጣጠሰ
ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር
በመጣ የእርሻ ዘዴና በከብት ኃይል ተሰቦ

Digitized by Google

ሰው ተጭኖት አፈርን እየሰነጠቀ በሚገለብጥ የብረት ግሬሻና አብረውት በሚሄዱ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ፣ የማገዶ ግልጋሎት ሽሚያ ቢበዛበትም ፍግ በማዳበሪያነት ፣ ዝናብ በውሃ ምንጭነት በመጠቀም ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ።

ይህን ሁኔታ ለውጦ የእርሻ ምርታማነትን ከፍ ለማድረግ በ1974—75 ባለው የሰብል ዘመን የተቋቋሙት የገበሬዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከከለሉት 117,256 ሄክታር መሬት ውስጥ 70,353ሄክታር መሬት ለማረስ የተጠቀሙት በ16,811 ጥማድ በሬዎችና በ37 ትራክተሮች ነው ። [20]

በዚሁ የምርት ዘመን በሽያጭ ለገበሬዎች የቀረበው ከ22,394ኩንታል የማያንስ ምርጥ ዘር ፣15 ,143 ኩንታል ማዳበሪያ 39,096 ኪሎ ግራም ፀረ—ተባይ ዱቄት ፣ 40,703 ሊትር ፈሳሽ፣3,485 ደርዘን እንክብል ነው ። 102 ፀረ ተባይ መርጫ መሣሪያና 57 የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች ሲታደሉ ፣ 321 ኩንታል ምርጥ ዘር ተባዝቷል። በራስ አገዝ ፕሮግራም አማካይነት 85 መጋዘኖች ሲሰሩ፣ 190 የአዝርዕት ሙከራ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል ። እንዲሁም ሌሎች የተወሰኑ ልዩ ልዩ የሙከራ ጣቢያዎች አገልግሎቶች ለማቅረብና 157 ወንዞችን ለመጥለፍና 91 ኩሬዎች ለመቆፈር ተችሏል ። [21]

ገበሬዎችን በማሠልጠን ረገድ በተፈጥሮ ሀብት ፣ በአዝርዕት ፣ በእንስሳት ሀብት ጥበቃና ልማት እንዲሁም በእርሻ አምራቾችና አገልግሎት ኅብረት ሥራ አመራር 41,380 ገበሬዎች እንዲሠለጥኑ ተደርጓል ፤ ከዚህ ውስጥ በእርሻ ነክ ቴክኒክ የሠለጠኑት 22,172 ሲሆኑ የተቀሩት 19,208 በሥራ አመራር የሠለጠኑ ናቸው ።

በደን ልማት ረገድ በመንግሥት ከ39,656 በሕዝብ ከ82,403 ያላነሱ ችግኞች ሲተከሉ በአንፃሩ ደግሞ 55,201 ሜትር ኪዩብ አጠና ፣ 161,639 ሜትር ኪዩብ ማገዶ ፣ 18,992 ሜትር ኪዩብ ሳንቃ ፣ 77,049 ጆንያ ከሰል ተመርቷል ። [22] የደን ውጤት ምርት ከሚለማው ሲወዳደር አጠቃቀሙ ልማቱን እየቀደመው መሆኑ ግልጽ ነው ።

ሀገሪቱ በእንስሳት ሀብት ረገድ የከብት ሀብት ከሕዝብ ብዛት ጋር ተዛምዶ ሲታይ በዓለም ከታወቁት አምስት አገሮች አንዷ ፣ በበግና ፍየል እንዲሁም በዶሮ በአፍሪካ ሁለተኛ ናት ። [23] የዚህን ሀብት (ወተት ፣ ሥጋ ፣ እንቁላል) አገኛኘት ችሎታ በቴክኒክ ረገድ ለማሻሻል በተደረገው ጥረት የውጭ አገር ምርጥ ኮርማዎችን ለገበሬው በማደል ወይም በሰው ሠራሽ ዘዴ ላሞችን በማስጠቃት በከብት ውጤት ብቻ መሻሻል እየታየ ነው ። የከብት መኖም በማዘጋጀት በአዲስ አበባ አካባቢ ብቻ ሥራዎች እየተከናወኑ ናቸው ። የእንስሳትንም ጤንነት ለመንከባከብ የሚያስችለው ቴክኒክ እንስሳቱ ከመታመማቸው በፊት (ክትባት ፣ ከታመሙ በኋላ ሕክምና) መስጠት የበሽታዎች ምርምርና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን መዘርጋት በመሆኑ በ1973 ለ16,337,000 በ1974 ደግሞ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ለ8,829,000 እንስሳት ክትባት ሲሰጥ በ1973 43,590,000 ፣ በ1974 በዘጠኝ ወራት 28,144,000 ዶዝ የመከላከያ ክትባት መድኃኒት ተመርቷል ። [24]

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የቴክኒክ አገልግሎት በሀገሪቱ በእርሻ ከተሰማራው 28,055,400 [25] የገጠር ሕዝብና ከእርሻው መሬት ስፋት ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በምርምር ጣቢያዎች አለመጠናከር ፣ በገበሬው ባህልና የገንዘብ አቅም ዝቅተኛነት ጥቂትም ቢሆኑ የሚቀርቡት ግልጋሎቶች ውጤት እምብዛም ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህ ሌላው ቀርቶ በገጠር የተሰማሩ 6 ሰዎች በከተማ ያለን 1 ሰው የመመገብ አቅማቸው ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል ።

ከዚህ እንደምንረዳው የሀገራችን እርሻ የጥሪት ክምችት ምንጭ የመሆንና የሕዝቡን ፍላጐቶች ለማርካት ያለውን ችሎታ ከፍ እንዲያደርግ በይበልጥ የጠለቀ ለውጥ

Digitized by Google

ሊካሄደበት ይገባል ። ይህ ለውጥ የምርት ግንኙነት ከግል ወደ ማኅበራዊነት ሽግግር ባሻገር የቴክኒክ ለውጥን ባጠቃላይ እርሻን ማሻሻልና የአካባቢ « ኢንቴንሲቭ ስፔሽያላይዜሽን » አስተራረስን ፣ ሰብል ማፈራረቅን ፣ የሚታረሰውን መሬት ማስፋፋትን ፣ የውሃ አገኛኘት ዘዴን አስተማማኝ ማድረግን ፣ የሥራ ፕላን ማዘጋጀትን ፣ የሰው ኃይል ያለማባከንን ፣ ለእያንዳንዱ እንደየ ሥራው የሚለውን መርህ ተግባራዊ ማድረግን ፣ በኅብረት የሚሠራ ማኅበራዊ ሥራ የቡድንና የአባላት ብዛት ለሥራ አመራር በሚያመች ቀልጣፋ ሁኔታ መቅረጽን መረጃ መሰብሰብን ይጠይቃል ።

አዝጋሚና ያልተመጣጠነ የእርሻ ልማት፣ በተለይም በልማት መጀመሪያ ላይ ፣ ለሀገራችን የከባድ ኢንዱስትሪ እንዲያስገኝ ለማድረግ ፣ በማኅበራዊው ርባታ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። ስለዚህ የፋይናንስ ፣ የንግድና እንዲሁም በአሁኑ ደረጃ ከሚያመርታቸው የብረታ ብረት ምርቶች ውስጥ የእርሻና የደን የእጅ መሣሪያዎች (አካፋ ፣ ዶማ ወዘተ - - -) 3% ብቻ የሆነው ፣ ኬሚካሎችን በማምረት ከግብርናው ጋር ግንኙነት የሌለው የኢንዱስትሪው ዘርፍና የወደቁ ብረቶችን በመጠቀም የእርሻ መሣሪያ ፍላጐት ለማርካት የሚጥሩት የሀገረሰብ ቴክኖሎጂስቶችን አቅም ከፍ በማድረግ በሚገባ እርሻን አገልግለው ባጠቃላይ በብሔራዊው ኤኮኖሚ መሠረታዊ ለውጦችን በአፋጣኝ ማስገኘት አለባቸው ።

ስለዚህ እርሻውን ሶሻሊስታዊ በማድረግ ግንባርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእርሻ ምርት ውጤትን ከፍ ፣ የእርሻ ምርትንም አስተማማኝ ለማድረግ የገበሬው የእርሻ ባህልና አመራር ወደ ኢንዱስትሪው እየቀረበ እንዲሄድ ከማሻሻል ጐን ቅልጥፍናውን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የእርሻ መሣሪያዎች (ወደ ሜካናይዜሽን የሚያመራ) የዕጽዋት ዕድገትን ሊያፋጥኑና ሊገቱ የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን (ወደ ኬሚካላይዜሽን የሚወስዱን) እና የውኃ አገኛኘትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ቴክኒኮች በእርሻው ውስጥ ደረጃ በደረጃ በተቀነባበረ ሁኔታ እንዲዘልቁ አመራር የመስጠት ችሎታ ፍላጐት እንዲረካ ማድረግ ሀገሪቷን የገጠማት ሌላው የዕድገት መሰናክል ነው ።

እንዱስትሪና ዕደ ጥበብ

በመሠረቱ የሶሻሊስት ግንባታ ፣ በማኅበራዊ ምርት ሽግግርና በሥርነቀል የብሔራዊ የኤኮኖሚ መዋቅር ለውጦች ላይ ተመሥርቶ የሚገኝ እንጂ በአንድ ወይም በጥቂት ዘርፎች መለወጥ ብቻ የሚከሰት አይደለም ። ሀገራችንን ለዚህ ለማብቃት መከናወን ከሚገባቸው ዓበይት የግንባታ ዘርፎች ለሌሎች ምርታማነት ከፍ ማለት በቀጥታ አስተዋጽኦ የሚያደርገው ከባድ ኢንዱስትሪን የማስፋፋቱ ጉዳይ ወሳኝነት አለው ። በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ላይ በሚገባ እንደተመለከተው ይህን ፍላጐት በሚያመረቃ ሁኔታ ለማሟላት የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ኑሮ ከፍ ከማድረጉ ጐን ለተፈላጊው የኢንዱስትሪ ልማት ካፒታል ምንጭ እንዲሆኑ ፣ እርሻና ቀላል ኢንዱስትሪዎችን ለማዳበር ሀገሪቱ ለምትገኝበት የእንዱስትሪና ዕደ ጥበባት ቴክኒክ ደረጃና ዕድገት ተገቢውን ትኩረት መስጠት እጅግ አገብጋቢ ነው ። አሁን የሀገሪቱን ቁሳዊ ፍላጐቶች ለማርካት ጥረት የሚያደርጉት መፈብረኪያዎች ምርታማነት ማደግ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ «ኰምፖነንትስ » ለማቅረብ የኢኔርጂ ፣ የቁሳቁሶች እና የመሣሪያዎችም ምንጭ መፍጠር ያስፈልጋል ። ስለዚህ የኤሌክትሪክ ኃይል ፣ የሕንፃ መሣሪያዎች ፣ የብረታ ብረት እና የኬሚካል ቅርንጫፎች ዕድገትና ደረጃ ሀገራችን ካለችበት በመነሳት አስተማማኝ የዕድገት እንቅስቃሴ ውስጥ ማስገባት መቻል ይኖርበታል ።[26] ከሁለተኛው መደበኛ ስብሰባ በኋላ ዕድገት እያሳዩ የሚገኙት በመ

Digitized by Google

ንግሥት ቁጥጥር ስር የሆኑ ኢንዱስትሪዎች የቴክኒክ ደረጃው ባጠቃላይ የሚከተለውን ይመስላል ።

የሀገሪቱ ጨርቃ ጨርቅ ቴክኖሎጂ ኋላቀርና አብዛኞቹ መሣሪያዎች በጣም ያረጁ ሲሆኑ በዓለም ደረጃ ቴክኖሎጂው ስለተለወጠ በዚህ መልኩ ብቻ የውጭ ሀገር ጥገኝነት እንዲሻ የሚያደርጉት መለዋወጫ ዕቃዎች በቀላሉ አይገኙም ።

የምግብ ፣ የመጠጥና ትምባሆ መፈብረኪያዎች ባለፉት የዘመቻ ዓመታት ዕድገት አሳይተዋል ። ሆኖም የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ያብዛኞቹ በጣም ያረጁና አንዳንዶቹ በሰው ጉልበት በሚንቀሳቀሱ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች የሚጠቀሙ ናቸው ።

የቆዳና ጫማ አመራረት ቴክኒክን በሚመለከት ለቆዳ ማልፋትና ማለስለስ ሥራ የሚውሉት ኬሚካሎች የዓለም የቆዳ ኢንዱስትሪ የሚጠቀምባቸውና ዘመናዊ ናቸው ። ሆኖም ቆዳውን ሙሉ በሙሉ ወደ ተለፋ ቆዳ ደረጃ ለማሸጋገር ከፍተኛና መካከለኛ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ስለሚታይበት በሙሉ የተለፋ ቆዳና ሌጦ ማምረት እሚቻልበት ደረጃ አልተደረሰም ፣ በጫማ ኢንዱስትሪ ረገድ ከ1940 ወዲህ በተግባር በዋለውና የማጣበቂያ ኬሚካሎችን ከውጭ እያስመጣ ስለሚጠቀም ሻል ያለ ደረጃ ቢገኝም ባጠቃላይ የአሠራሩ ዘዴ በመካከለኛ የቴክኖሎጂ ደረጃ የሚገኝ ነው ።

የብረታ ብረት ማምረት ቴክኒክ ኮንስትራክሽን ሥራ የሚውሉ ቁሳቁሶች ፣ የኤሌክትሪክ ገመድና ቱባ ፣ የእጅ ባትሪ ድንጋይና የመኪና ባትሪ ፣ ቀላልና ሌሎች የመለዋወጫ ዕቃዎችን ያመርታል ፣ የቴክኖሎጂ ደረጃው ዝቅተኛ ነው ፣ በመሠረቱ የብረታ ብረት ምርት ማቅለጥ ፣ ማንጠር ፣ ማርጋት መዳመጥ ፣ መቀጥቀጥን ቢያጠቃልልም በዚህ አኳያ የሀገሪቱ ብረታ ብረት ምርት ተግባር የወዳደቁ ብረታ ብረቶች በመሰብሰብ የማቅለጥና የሮሊንግ ሚል የአርማታ ብረት ሥራ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የላውንደሪ ሥራ በጣም ኋላቀር ደረጃ ላይ ይገኛል። ስለዚህ የብረታ ብረት ምርት እርስ በርሱ የሚደጋገፍበት ደረጃ እንዲደርስ ለማድረግ ብዙ ጥረት መደረግ ይኖርበታል ።

የጎትመት ምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች ከ10 ዓመት ዕድሜ በላይ ያላቸው ሲሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጎትመት ዘርፉን የውጭ ጥገኝነት የሚያጠቃው ነው ። በእንጨት እንዱስትሪም ረገድ መሣሪያዎቹ ከ20—30 ዓመት በፊት የተተከሉ መሣሪያዎች ስለሆኑ የቴክኖሎጂ ደረጃቸውም በዚሁ ደረጃ የሚገኝ ነው ።

ኬሚካልን በሚመመለከት ጨው በፀሐይ ኃይል በማትነን ፣ ፕላስቲክ በዓለም ደረጃ ቴክኖሎጂው ፈጣን በሆነ መንገድ ቢቀያየርም ዘመናዊ መሣሪያ የሚጠቀም ፣ ጉማም እንዲሁ ከሞላ ጎደል ዘመናዊ መሣሪያዎችን የሚጠቀም ፣ ፐልፕና ወረቀት ፣ ወረቀትን ብቻ ለማምረት በነዳጅ የሚሠሩ መሣሪያዎችን የሚያገለገል ፣ ብርጭቆና ጠርሙስ የአዲስ አበባው በነዳጅ ፣ የአሥመራው በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ፣ በሰው ኃይል የሚጠቀም ፣ ሲሆን ቀለማ ቀለምም ጥሬ ዕቃዎቹን ከውጭ በማስመጣት ኬሚካሎችን በተወሰነ ፈሳሽ ደባልቆ ማሸግ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ።

ብረት ነክ ካልሆኑ ማዕድናት የሚሠሩ የእንዱስትሪ ውጤቶች (ጠርሙሶችና ብርጭቆዎች ፣ ሞዛይክስ ፣ ሲሚንቶ ፣ ኖራ ፣ የሲሚንቶ ውጤቶች ፣ የአስቤስቶስ ውጤቶች) የሚከናወኑት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው ። ሆኖም የመሣሪያዎቹ ዕድሜ የገፉ በመሆኑ የመበላሸት ዕድላቸው ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል ። አነስተኛ « ማኑፋክቸሪንግ » (የግል) የምግብ ፣ በመጠጥ ፣ በጨርቃጨርቅ (ሹራብ) በቆዳና ጫማ ፣ በእንጨት ፣ በወረቀትና ማተሚያ ፣ በኬሚካል ፣ ሽቶ ፣ ቅባቶች ፣ የመኪና ባትሪዎች፣ ኩላ ወዘተ... ብረት ባልሆኑ ማዕድናት ፣ በብረታ ብረት (ወንበር ፣ ጠረጴዛ ፣ አልጋ ፣ ቁምሳጥን

Digitized by Google

ወዘተ...) ውጤቶች ላይ በአብዛኛው በሸዋ፣ በኤርትራ ፣ በሐረርጌ ፣ ክፍላተ ሀገር ምርት ይካሄዳል ፣ ይህ አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ የግል ባለንብረቱ የእጅ ሙያተኞችን በአ ንድ ጣሪያ ሥር አሰባስቦ እያንዳንዱ ሙያ ተኛ (ለምሳሌ ልብስ ስፌት) ምርቱን እን ዲያመርት ወይም አንዱ ሠራተኛ አንድን ምርት ከሚያስገኙ ክፍሎች አንድዋን ብቻ እንዲሠራ (ለምሳሌ ጫማ ስፌት) በማድ ረግ የምርት ውጤት ለማስገኘት በኤሌክ ትሪክ ወይም በሰው ኃይል ግፊት ወይም በሁለቱም በሚንቀሳቀሱ የምርት መገል ገያ መሣሪያዎች በመጠቀም ደረጃ ላይ የ ሚገኝ ነው ።

የዕደ ጥበባት እንዱስትሪዎች 50% ምር ት የሚያቀርቡ ናቸው ። የሚጠቀሙበት የሀገረሰብ ቴክኖሎጂ ምርታማነት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ የአምራቾችን የሥራ ክን ውን የሚወስኑ ሌሎች ሁኔታዎች ተደምረ ውበት በማኅበራት የተደራጁ የዕደ ጥበብ ሙያተኞች (ሽመና ፣ ልብስ ስፌት ፣ ብረታ ብረት ፣ እንጨት ሥራ ፣ እንጥረኛ ፣ ቆዳ ሥራ) የነፍስ ወከፍ ምርት አማካይ አስተ ዋጽኦ ከመንግሥትና ከ10 በላይ ሠራተ ኛ ካላቸው የግል ፋብሪካ ሠራተኞች የነፍስ ወከፍ ምርት አማካይ አስተዋጽኦ ጋር ሲወ ዳደር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው ።

በኢንዱስትሪውና በዕደ ጥበባት ላይ ያለ ውን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ባለፉት ሁለት ዓመታት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ላሉት አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ያረጁ መሣሪያዎች ሊለወጥላቸው ተችሏል ። የዕደ ጥበባትንም የቴክኖሎጂ ደረጃ ለማ ሻሻል ባለው ፍላጐት መሠረት በኢትዮ ጵያ ዕደ ጥበብ ማዕከል ልዩ ልዩ የተሻሻሉ የሽመና ፣ የፈትል፣የሸክላ መሣሪያዎች እየ ተሠሩ መጠናቸው (440 ልዩ ልዩ መሣሪያ ዎች ከ1972 ጀምሮ) ዝቅተኛ ቢሆንም ለዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ቀርበዋል ። ካለው ፍላ ጐት አኳያ ሲታይ ይህ በጣም አነስተኛ መ ሆኑ በዚህም ረገድ የሚጠበቀው የግንባታ ሥራ ቀላል አይደለም ።

ኃይልና ማዕድን

ኢንዱስትሪም ሆነ ሌሎች ዘርፎች ዳብ ረው በሀገሪቱ የኤኮኖሚ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ይበልጥ ጥልቀትና ስፋ ት እንዲያገኙ ለማድረግ የኃይልና የማዕ ድን ምርምርና ልማት ቦታ የጐላ ነው ።

የኃይል ምንጭ ጥናትና ምርምርን በሚ መለከት ጥቂቶችም ቢሆኑ አዳዲስ የባዮ ጋዝ ጣቢያዎችን ለማቋቋም ሲቻል የፀሐይ ጨረር ኃይል መለኪያዎችም ተተክለዋል። የዝግ ምድጃዎችና የቤተሰብ የኃይል ፍጆ ታም ጥናት እየተካሄደ ነው። ነዳጅንም በሚ መለከት የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ የኃይል ማመንጫ ተቋምን ለማሻሻል ተጨማሪ ቦይለር ለመትከል ጥናት እየተካሄደ ሲሆን የአዳዲስ ዲፖዎች ሥራም እየተከና ወነ ነው ። ሀገሪቱ ከላት የነዳጅ ኢነርጂ 70% ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ፣ 30% በቋሚ ነት ተተክለው ለሚሠሩ የእንዱስትሪና የኃ ይል ማመንጫዎች ይውላል ።[27] እስከ ዛሬ ያለው የኤሌክትሪክ አመነጫጨትና አሰረጫጨት ቴክኒክ ልምዶች በከፍተኛ ቸልበት የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎ ችን አቋቁሞ ረጃጅም የከፍተኛ ቮልት መስመሮችን በመዘርጋት ወይም ባለ ትና ንሽ ጉልበት ዲዝል ጣቢያዎችን በየቦ ታው በማቋቋም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከባድ መዋዕለ ነዋይ ፣ የውጭ ምንዛሪና ቴክኖሎጂን የሚጠይቅ ነው ። በጠቅላላው ከሀገሪቱ ሕዝብ 6% የኤሌክትሪክ ኃይል ያገኛል ። በአጠቃላይ የኃይል አጠቃቀም ትራንስፖርት 63% ፣ ኢንዱስትሪ 15 %፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ 11% ፣ እርሻና ሌሎች 11% ሆኖ ይገኛል ።[28]

በኢትዮጵያ ከጠቅላላው የኃይል ፍጆታ ውስጥ 93% ያህሉ የሚገኘው ከእንጨት ፣ ከከሰል ፣ ሌሎች ዕፀዋትና ከብት ሲሆን በዓ መት 23 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ እንጨት

Digitized by Google

ለማገዶነት እንደሚቃጠል ይገመታል።
በደን ውጤቶች አጠቃቀምና በደን ልማት
መካከል ያለው የተዛባ ሚዛን ካልተሰተ
ካከለ የሀገሪቱ ደን ከተወሰኑ 10 ዓመታት
በኋላ አልቆ ሀገሪቷ የእርሻ ቴክኖሎጂ
ዋና የኃይል ፍላጐትዋን የምታረካበት ሁኔ
ታ እንደማይኖር የአሁኑ አዝማሚያዎች
ያመለክታሉ ። ስለዚህ አማራጭ የኃይል
ምንጮችን ማጥናትና ማልማት የማይታ
ለፍ ነገር ሆኖ ይገኛል ።

ነፃ የኢንዱስትሪ ግንባታን ካለ ማዕድን
ሀብት ልማት ማሰብ አይቻልም ። ስለዚህ
የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ ሁለተኛ
መደበኛ ጉባኤ ባስተላለፈው መሠረት በአ
ዶላ የወርቅ ልማት፣በዩብዶ የፕላቲኒየም ም
ርት ለማምረት ሙከራ እየተካሄደ ነው ። [29]
በ1888 የተጀመረው የሀገሪቱ ማዕድ
ናት ልማት በሚገባ ተቀነባብሮ ሊያድግ
ባለመቻሉ በአሁኑ ወቅት ልማት የሚካ
ሄድባቸው የአዶላ ወርቅ ፣ የዩብዶ ፕላቲ
ኒየም ፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ጨው ማዕድናት
የሚከተሉት አሠራር በአብዛኛው በሰው
ኃይልና ኋላቀር በሆኑ መሣሪያዎች መጠ
ቀምን ነው ። ባለው የአሠራር ቴክኒክ ደረጃ
የወርቅና የፕላቲኒየም ምርት ውጤት በዶ
ለል ውስጥ ከሚቀረው ሲወዳደር ከ30%
አይዘልም ። [30]

ሰፊ ክልል የጂኦሎጂ ካርታ ሥራ ፣ በድ
ንጋይ ከሰል ፣ በኢንዱስትሪ ማዕድናት
በጅኦሎጅ ፣ በጂኦተርማል እና በሌሎች ፣
የሃይል ምንጮች ጥናቶች ተካሂደዋል። ሀገ
ሪቱ ከወርቅ፣ ብረት ወዘተ ... እስከ ኖራና
ድንጋይ ማዕድናት ድረስ ሀብት ያላት
መሆኑ ቢታወቅም ፣ ጥናት የሚካሄደው
ኃላ ቀር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ስለሆነና
በሌሎቹም ምክንያቶች ውጤት የሚገኝበት
ፍጥነት አዝጋሚ ሆኗል።

ትራንስፖርት

የምርትን ሂደት ለማፋጠንና የክፍላተ
ኤኮኖሚዎች ተደጋጋፊነትን ለማዳበር ትራ
ንስፖርት የሚጫወተው ሚና ጉልህ ነው ።
የትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ከአብዮቱ
በፊት 6,363 ኪ/ ሜትር ብቻ ይሸፍን የነ
በረው በ1974 13,525 ኪ/ ሜትር ሊሸፍን
የቻለበት ደረጃ ደርሷል ። ይህም ሆኖ በአፍ
ሪካም ደረጃ ቢሆን ዝቅተኛ ነው ። [31]
የኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃ ፣ ያረጁና የወደሙ
ኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ሲያጋጥመው
ለመተካት አቅም ያንሰዋል ።

የየብስ ትራንስፖርት የተቋቋመው ከ50
ዓመት ወዲህ ሆኖ ዕድገት ቢያሳይም ተሽ
ከርካሪዎቹ ያረጁ በመሆናቸው ቅልጥፍ
ናቸው ዝቅተኛ እየሆነ መምጣቱ እነርሱን
የመተካቱ አስፈላጊነት ግልጽ እየሆነ ነው።
የባሕር ትራንስፖርት ቴክኒክ ችሎታ
ለማሻሻል እንደ ክሬን ፣ ፎርክሊፍት የመ
ሳሰሉት ልዩ ልዩ የወደብ መሣሪያዎችን
ጉታች ጀልባዎች ፣ እንዲሁም ሁለት እያ
ንዳንዳቸው 4,000 ቶን የመሸከም አቅም
ያላቸው መርከቦች ተገዝተዋል ። የአ
የር ትራንስፖርትንም በሚመለከት በዘ
መናዊ ቦይንግ ጀቶችና የምስል በረራ ትም
ህርት ቤት እንዲቋቋምለት በማድረግ
የቴክኒክ ችሎታውን ከፍ ለማድረግ ርም
ጃዎች ተወስደዋል ። [32]

ማጠቃለያ

ከአብዮቱ በፊት በነበረው የፊውዶ ቡር
ዥዋ ምርት ግንኙነት ምክንያት በሀገሪቱ
ውስጥ ኢሳይንሳዊ አመለካከቶችና አስተ
ሳሰቦች የበላይነት የያዙበት ፣ አብዛኛው
ኢትዮጵያዊ ችሎታውን ከማዳበርና ከዕው
ቀት ርቆ በማይምነት ውስጥ መቆየቱ ገልጽ
ነው ። በኪነጥበባትም ረገድ ምንም እንኳ
ሀገሪቱ የብዙ መቶ ዓመታት የሙዚቃ ፣
የሥነጽሑፍ ፣ የሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ ፣ የዳ
ንስ ፣ ወዘተ . . . ሀብት ክምችት ቢኖራ
ትም ዕድገታቸው ታፍኖና ተይዞ ቆይ
ቷል ።

በቴክኒክ ረገድም በገጠሩ የውኃ ወፍ
ጮ ቴክኒክ የፊውዳል ኅብረተሰብና
ፊውዳሉን ከመፍጠርና በከተማ ጥቂት

Digitized by Google

የኤሌክትሪክ ወፍጮ የቴክኒክ ዕድገቱ
የተሸመደመደ ቡርዥዋ ማቆጥቆጥን
ከመጋበዝ ባሻገር መራመድ ባለመቻሉ
እርሻው በመሠረቱ ኋላ ቀር የምርት መገ
ልገያ መሣሪያዎችና የአስተራረስ ዘዴዎ
ችን የሚጠይቅ ፣ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ
በመካከለኛና በዝቅተኛ ቴክኒክ ደረጃ የሚ
ገኝና የውጭ ጥገኝነት የሚያጠቃው ፣ ዕደ
ጥበባትም ዕድገታቸው ተፋጥኖ ወደ መለ
ስተኛ ፋብሪካዎች ለመሸጋገር ሁኔታው
ሳይፈቅድላቸው ቀርቷል ። የኃይል ምን
ጭም ቢሆን በመሠረቱ እፅዋት ሁነው መቆ
የታቸው በሀገራችን ሶስዮ ኤኮኖሚ ስርዓት
ላይ መዛባትን ማስከተሉ ፣ የማዕድን ልማት
ፍጹም አልነበረም የሚሰኝበት ደረጃ መገ
ኘቱና ትራንስፖርትና መገናኛም የእርሻው
ና የኢንዱስትሪውን ዕድገት ተከትለው የሚ
ሄዱ በመሆኑ አዝጋሚ ሆነው መቆየታቸ
ውና የእነዚህ ሁሉ ስብስብ ውጤት የሕዝ
ቡን ኑሮ ደረጃ ሊያሻሽለው ባለመቻሉ
በ1966 የካቲት የሕዝባዊ እንቅስቃሴ ፍን
ዳታን አስከትሏል ። ይህም ሕዝባዊ አብዮ
ት መሠረታዊና ሥር ነቀል ሁኔታዎችን
አከናውኗል ።

በሌላው ግንባር ደግሞ ሠራተኛው ሕዝብ
ያሉት ዋና ዋና ኃይሎቹን በሚገባ እንዲ
ጠቀምባቸው ተፈጥሮአዊ አካባቢውንና የ
ሚኖርበትን ማኅበራዊ ግንኙነት ለመተ
ንተንና ለመተርጐም ይበልጥ ችሎታውን
ማዳበር ስለሚገባው የባህልና የቴክኒክ ትም
ህርት በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ፣
በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ፣ በሕዝብ መገ
ናኛ ዘዴዎች ፣ በውይይት ክበቦች አማካይ
ነት እንዲደርሰው እንቅስቃሴዎች ተደር
ገው የሚያበረታቱና ተስፋ የሚጣልባቸው
ውጤቶችን ለማግኘት ተችሏል ።

በዚህም ምክንያት እነሆ ዛሬ ሠርቶ አደሩ
ሕዝብ ካለፈው ሥርዓተ ማኅበር የተረከበው
ኋላ ቀርና አዝጋሚ ዕድገት የነበረው ባህ
ልና ቴክኒክ መሠረትን ለመለወጥ ታላቅ
ጥረት እያደረገ ይገኛል ። በአሮጌው ሥር
ዓተ ማኅበር ፍርስራሽ ላይ በተፈጠረው
አመቺ ሁኔታ በመጠቀም የሶሻሊዝምን
ሥልጣኔ ለመገንባት የሚሻው ይህ ሕዝባዊ
ጥረትና ፍላጐት የፊውዶ ቡርዥዋውን
ምርት ግንኙነት ለመሻር የትኛውንም ማኅ
በረሰብ ለመለወጥ በተግባር ላይ ከሚውለው
ከፍተኛ ስሜት ባሻገር ዕውቀት ፣ ሳይንስና
ቴክኒክ እንዲቀነባበሩለት ይጠይቃል ፣
ካለፈው ሥርዓተ ማኅበር ከተወረሰው አስ
ተሳሰብና አመለካከት ፣ ትምህርት ፣ ኪነጥ
በብ ሳይንስና ቴክኒክ በጐ በጐውን መርጦ
አዲሱን በመጨመር አሁን ያለውን ሠርቶ
አደር ሕዝብና የሶሻሊዝም ግንባታን ከዳር
የሚያደርሰው ተተኪ ትውልድ ኑሮው
ምቹና ደስተኛ እንዲሆንለት የባህልና ቴክ
ኒክ መሠረት ግንባታ ጥረቶችን ርስ በርሳ
ቸው በተደጋጋፋና ድምር ውጤታቸው
ሶሻሊዝም በሆነ ፖሊሲዎች መምራት አስ
ፈላጊ ነው ።

ይህ እንዲሆን ደግሞ መሪ የፖለቲካ ድር
ጅት ማግኘት ቀዳሚነት አለው ፤ ሆኖም
ሀገሪቱ ከተረከበችው ዝቅተኛና ኋላቀር የዕ
ድገት ደረጃ የተነሳ ፣ ከሶሻሊዝም በኢትዮ
ጵያችን መስፈን አኳያ በሀገሪቱ ባህልና ቴ
ክኒክ ሁኔታዎች ላይ የጥራት ለውጥ በማስ
ገኘት ሠራተኛውን ሰው በምርታማ እንቅስ
ቃሴዎች ውስጥ በማስገባት ፣ ከሩቅ ጊዜ ግባ
ችን አንፃር ነፃ ማውጣት ቀርቶ ፣ ከምርት
እንቅስቃሴ መፋታቱን በቅጡ እንኳን ሊገቱ
የሚችሉ ማኅበራዊ ድርጅቶች ማግኘት ቀ
ላል ሆኖ አልተገኘም ። ስለዚህ በሀገራችን
ተጨባጭ ሁኔታ የሽግግሩ ሂደት አሮጌ የም
ርት ግንኙነቶችን ከማፍረስ ጐን የሶሻሊስት
ኅብረተሰብን ለመገንባት የፖለቲካ ቁርጠ
ኝነት ባሕርዩ የሆነ ግሌ ድርጅት ለማስገ
ኘት እንቅስቃሴዎችን መጀመሩ የማይታ
ለፍ ፣ አስገዳጅና ዓቢይ ጉዳይ ሆኖ እስከዛሬ
ቆይቷል ። ሆኖም የዚህ የፖለቲካ ድርጅት
ድል አድራጊነት ደግሞ ስለራሱ ባለው
ንቃት ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ወደፊት
የሚከናወኑት የባህልና የቴክኒክ ግንባታ

አብዮታዊ ንድፈ ሀሳቦች በፖሊሲ ፣ አፈጻጸማቸውን ደግሞ በብቁ ካድሬዎች ሊያደራጅ ፣ ሊከታተል ፣ ሊመራና ሊግር የሚችል ግሌ ድርጅት የማግኘቱ ጥያቄ የሀገሪቱ የኤኮኖሚ ዕድገትና የማኅበራዊ ልማት የሚያነሱ ዋቸው ጥያቄዎች እምብርት የመሆኑ ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ መጥቷል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1. M. Rosenthal and P. Yudin (eds). *A Dictionary of Philosophy*, Moscow, 1967 P. 106.
2. *Ibid*.
3. Karl Marx, *Contribution to the Critique of Political Economy*, as quoted by, Raymond Williams in Culture and Society, Chatto and Windows England, 1966, p. 259.
4. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 29, p. 70.
5. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 39, p. 24.
6. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 26, p. 481-82.
7. Le Duan, *The Vietnamese Revolution*, International Publishers, New York, 1971, p. 66.
8. Vo Nguyen Glap. *Essential Tasks of the Scientific and Technological Revolution in Agriculture*, Foreign Language Publishing House, Hanoi, 1979, p. 20.
9. Chesnakov, *Historical Materialism*, first printing, page 431.
10. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 31. P. 287.
11. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶ አደር ፣ ቅጽ 2 ፣ ቁጥር 23 ፣ ገጽ 2—7
12. ከአጭር ጊዜ ዕቅድ ወደ ሩቅ ግብ ፣ ሠርቶ አደር፣ቅጽ 3 ፣ ቁጥር 54 ገጽ 1
14. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ሠርቶ አደር፣ ቅጽ 2፣ቁጥር 23 ፣ ገጽ 2
15. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶ አደር፣ ቅጽ 2፣ቁጥር 23፣ገጽ 5
16. የኢሠፓአ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶአደር ፣ ቅጽ ፣ 2 ቁጥር 23፣ገፅ 2
17. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶ አደር ቅጽ 2፣ቁጥር 23፣ገጽ 2
18. K. Marx, *Capital*, Vol. II, Moscow, 1967, p. 36-37.
19. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶ አደር ቅጽ 2፣ቁጥር 23፣ገጽ 5—6
20. የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዝርዕትና ቋሚ ሰብል እርሻ ልማት ገምገማ ፣ ዓላማና ስልት ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ ሐምሌ 1974
21. የአራተኛው —1974 ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ (የዘጠኝ ወር) የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ኢንስፔክሽን መምሪያ ፣ አዲስ አበባ፣ ሰኔ 1974
22. ከላይ የተጠቀሰው
23. የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ገምገማ ፣ ዓላማና ስልት ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ ሐምሌ 1974
24. ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 79-80
25. *Population Projection of Ethiopia*, 1980-1990 Central Statistical. *Statistical Abstracts* 1980-1990 *Central Statistical Office*.
26. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ ሁለተኛ

Digitized by Google

መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ፣ ሥርቶ አደር፣ ቅጽ 2፣ቁጥር 23 ፣ ገጽ 5

27. የኢነርጂ ክፍለ ኤኮኖሚ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ግምገማ ፣ ዓላማና ስልት ፣ መስከረም 1975፣አዲስ አበባ፣

28. ከላይ የተጠቀሰው ፣

29. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ፣ ሠርቶ አደር ቅጽ 2፣ቁጥር 23፣ገጽ 5

30. በማዕድን ክፍለ ኤኮኖሚ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ግምገማ ፣ ዓላማና ስልት ፣ መስከረም 1975 ፣ አዲስ አበባ

31. የትራንስፖርትና የመገናኛ ክፍለ ኤኮኖሚ የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ (1977-1985) ሰኔ 1970

32. ከላይ የተጠቀሰው

Digitized by Google

ኢኮኖሚያዊ የውጪ ግንኙነት ከምንከተለው የእድገት ፈለግ አንጻር

—ዶ/ር ላቀው አለሙ
—ከብሩ ገ/መድህን

አለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት

በተለያዩ አገሮች መካከል ስላለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ምንነት ለማወቅ በቅድሚያ የዓለም ኢኮኖሚ ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል ። የተለያዩ ኢኮኖሚስቶች በየበኩላቸው የዓለምን ኢኮኖሚ ለመግለጽ ጥረት አድርገዋል ። አንዳንዶቹ «የተለያዩ ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች ጥንቅር ነው» ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ «የዓለም ኢኮኖሚ ግንኙነቶችና የገዥ ሕጐቻቸው ድምር ነው [1]» ብለዋል።የመጀመሪያው አባባል የተለያዩ ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች በዓለም የሥራ ክፍፍል በኩል የሚፈጥሩትን ግንኙነትና መተሳሰርን የሚዘነጋ በመሆኑና ሁለተኛው ደግሞ የዓለም ኢኮኖሚ ሕዋስ የሆኑትን ብሔራዊ ኢኮኖሚዎችን የሚያያይዝ ባለመሆኑ ሳይንሳዊ መሠረት የላቸውም ።

የዓለምና የተለያዩ ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች በዓለም የኢኮኖሚ መዘውር (The World Economic Circuit) እንዲሁም በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍሎች ውስጥ ከመሳተፋቸው የተነሳ ፣ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ የዕድገት ደረጃ የሚከሰቱ ናቸው።በዚህም መሠረት የዓለም ኢኮኖሚ የሚከተሉት መሠረታዊ ዘርፎች ይኖሩታል ።

—የተለያዩ ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች ፣
—ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍሎች ፣
—የዓለም የኢኮኖሚ መዘውርና ግንኙነቶች ፣

ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት የዓለም ኢኮኖሚ አንዱ አካል በመሆኑ ከሌሎች መሠረታዊ ዘርፎች ጋር እንደሁኔታው በመተባበር ፣ በመደጋገፍና በመታረን በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ይሠራል ።

ለዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት መገስኤው በብሔራዊ ደረጃ የተከሰቱ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ምክንያ

ቶች ናቸው ። የዓለም የኢኮኖሚ ግንኙነት ከብሔራዊ ኢኮኖሚዎች ዕድገትና ሁኔታ ውጭ ሊታሰብ አይችልም የሚባለውም ለዚሁ ነው ። ለዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት መከሰት ካሉት ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፣

—የብሔራዊ ገበያ ማደግና መስፋፋት ፣
—የምርት ኃይሎች ዕድገት ፣
—የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ጥልቅ እየሆነና እያደገ መምጣት ፣
—የሸቀጥ ምርት መከሰትና መስፋፋት ሲሆኑ ፣

ከፖለቲካዊ ምክንያቶች ደግሞ የማዕከላዊ መንግሥት መመሥረትና በኋላም የቡርዧው ሥርዓት ማደግና መስፋፋት የመሳሰሉት ይገኙበታል ።

ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት አያሌ መሠረታዊ ዘርፎች አሉት ። ከነዚህም መካከል የንግድ ፣ የፋይናንስ ፣ የመዋዕለ ንዋይ ፣ የትምህርትና የባህል ፣ ወዘተ . . . ዋና ዋናዎቹ ናቸው ። ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ቀደም ሲል መስፋፋት የጀመረው በንግድ ግንኙነት ሳቢያ ነበር ። በጋርዮሽ ሥርዓት ዘመን እያንዳንዱ ቤተሰብ ለራሱ ፍጆታ የሚሆኑትን እንደ ምግብ ፣ ልብስ . . . ወዘተ ያሉትን በራሱ ጉልበት አምርቶ ይጠቀምባቸው ነበር ። ቀስ በቀስ ግን ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በመጀመሩና ትርፍ ምርቶች በመገኘታቸው እነዚህን ትርፍ ምርቶች መለዋወጥ ተጀመረ ። ይህም በየጊዜው እያደገ በመምጣት የተደራጀ የንግድ ልውውጥን አስገኘ ።

ቀደም ሲል በንግድ ሥራ ታዋቂነት የነበራቸው ባቢሎናውያንና ዓረቦች ሲሆኑ እነርሱም በወቅቱ የትራንስፖርት መገልገያዎች ባለመኖራቸው በአህያና በግመል ጀርባ በመጠቀም እየተዘዋወሩ የንግድ ተግባርን ያከናውኑ ነበር ። በኋላም በባሕር በመጓዝ የንግድ ሥራን ማካሄዱ እየተለመደ ሲመጣ ፊንቃውያን የበላይነትን እያገኙ መጡ ። የሮም ስርወ መንግሥት ከወደቀ በኋላ እ. ኤ. አ. ከ476 ጀምሮ መጠነኛ የሆነ የዓለም የንግድ እንቅስቃሴ መታየት ጀመረ ። ከዚያም በ11ኛውና በ12ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ በአገሮች መካከል ያለው ግንኙነት እየተጠናከረና እያደገ በመምጣቱ የንግዱ ግንኙነት የመስፋፋትና የመዳበር አዝማሚያ ይታይበት ጀመር።

እ. ኤ. አ. በ14ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ የባሕር ትራንስፖርትን ይበልጥ በማስፋፋት የዓለም የንግድ ግንኙነትን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ተካሄደ ። በዚህም መሠረት በአውሮፓና በአፍሪካ ፣ በሕንድና በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች መካከል በተዘረጉት የባሕር ላይ መስመሮች አማካይነት ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ ተጀመረ ። ከዚያም በ16ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ የንግድ ሥራን የሚያከናውኑ ወገኖችና ኩባንያዎች የመንግሥቶቻቸውን ፈቃድ በመጠየቅ በአዳዲስ የዓለም አካባቢዎች የንግድ ሥራን ማስፋፋት ተያያዙት ። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የዓለም የንግድ ግንኙነት ቀስ በቀስ እያደገ በመምጣት ዛሬ ካለበት ሰፊና ውስብስብ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ቻለ ።

ባለንበት ዘመን በሳይንስና ቴክኖሎጂ አብዮት የተፋጠነ ዕድገት ሳቢያ እየዳበረና ጥልቀት እያገኘ የመጣው የዓለም የሥራ ክፍፍል ለኢንዱስትሪና ለፍጆታ ሸቀጦች ምርት መስፋፋትና ማደግ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት ዛሬ የተለየ ቅርጽ እንዲኖረው አድርጓል ። የሳይንስና የቴክኖሎጂ አብዮት የተፋጠነ ዕድገት የንግድ ግንኙነትን ቅርጽ ከመለወጡም ባሻገር በማምረቱም ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ለውጥን አድርሷል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊትእንደ ምግብ፣ጥሬ ዕቃዎች ፣ ዘይትና የመሳሰሉት መሠረታዊ ምርቶች በዋጋ አንፃር ሲታዩ ከዓለም የወጪ ምርት ውስጥ 67% ያህል ድርሻ ሲኖራቸው እ. ኤ. አ. በ1971 አካባቢ ግን 32% ብቻ ነበራቸው ።[2] ከዚህም ሌላ ዛሬ የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ

Digitized by Google

በአብዛኛው ወደ ኢንዱስትሪ ኢኮኖሚና ከፍተኛ የሥራ ክፍፍል ደረጃ በተሸጋገረበት ወቅት የምርት ተሐድሶ እጅግ እየተፋጠነ መጥቷል ። በዚሁ መሠረት በአሁኑ ጊዜ የአብዛኞቹ የኢንዱስትሪ ምርቶች መካከለኛ ዕድሜ ከአምስት ዓመት አይበልጥም ። ዛሬ በዓለም ገበያ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት ምርቶች መካከል ከ10 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ምርቶች መጠን በጣም ትንሽ ነው ። ይህ በሳይንስና በቴክኖሎጂ አብዮት አማካይነት የተፈጠረው የተፋጠነ የምርት ተሐድሶ በዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ለውጥና ዕድገት ያስከተለ መሆኑ ግልጽ ነው ።

ዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ እያደገና እየዳበረ የመጣ በመሆኑ በአብዛኛው የዚህን ሥርዓት ልዩ ባሕሪና ገጽታ ይዞ ይገኛል ። ዛሬ በከፍተኛ መጠን ዳብሮ የሚገኘው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ውጤት በአብዛኛው የተከማቸው እኩልነት ባልሰፈነበት የብዝበዛ ሥርዓት ውስጥ በመሆኑ የዓለም አገሮች ሁሉ የዚህ ውጤት እኩል ተጠቃሚዎች ሊሆኑ አልቻሉም ።

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኑነት ሁኔታ

የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነትና አመጣጥ በተለያዩ የማኅበራዊ ዕድገት ደረጃዎች የተለያዩ ይዘቶችና ባሕሪያት እንደነበሩት ለመገንዘብ ተችሏል ። በዚሁ መሠረት በአሁኑ ወቅት በአገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት መሠረታዊ ገጽታዎች ብንመለከት በግንኙነቱ ውስጥ የበላይነት ያላቸው የኢምፔሪያሊስት አገሮች በሌሎች ሕዝቦች ላይ ለሚፈጽሙት ገደብ የለሽ ዘረፋና አሻጥር ዋናው መስክ ሆና እናገኘዋለን ።

ዛሬ ከመቼውም ይበልጥ የዓለም ኢኮኖሚ በአገሮች መካከል የመደጋገፍና የመተሳሰር ጠባይ እንዲኖር አድርጓል ። ከዚሀም ሌላ ከፍተኛ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት አንዱ አገር ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅም ከፍ እያደረገው በመምጣቱ ከዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ውጪ ራሱን አግልሎ ሊኖር የሚችል አገር ፍጹም አይገኝም ። ዳሩ ግን በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ በዓላማቸው የሚለያዩ ሁለት ሥርዓተ ማኅበሮች በመኖራቸው በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ውስጥ የሚታዩት የመደጋገፍና የመተሳሰብ መሠረታዊ ባሕሪያት የተለያዩ ሆነው ተገኝተዋል ።

በዚህም መሠረት በአንድ በኩል በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተና የመደጋገፍ ጠባይ የማይታይበት ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ሲኖር በሌላ በኩል ደግሞ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ የመደጋገፍ ባሕሪ ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት አለ ። የመጀመሪያው ዓይነት በአገሮች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት የካፒታሊስቱ ሥርዓት የሥራ ክፍፍል ውጤት ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ግን የዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት ባስገኘው አዲስ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው ።

በእኩልነትና በአገሮች የጋራ ጥቅም ላይ ያልተመሠረተው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ለጥቂት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ከፍተኛ መብትና ጥቅምን ሲያስገኝ ፣ ለብዙዎቹ ታዳጊ አገሮች ግን መሠረታዊ መብትና ሕጋዊ ጥቅምን የሚነሳ ነው ። ዛሬ አያሌ ታዳጊ አገሮች በንግድ ፣ በፋይናንስ ፣ በባህልና በሌሎችም የኢኮኖሚ መስኮች ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር ሰፊ ግንኙነት አላቸው ። በዚህም ግንኙነት ሳቢያ የብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው የዕድገት ደረጃ እየቀነሰና የሕዝባቸው የኑሮ ሁኔታ እየተዛባ በመሄድ ላይ ይገኛል ። በሌላ በኩል ግን የኢምፔሪያሊስት አገሮች ያላቸውን የኢኮኖሚ የበላይነት በመጠቀም የግንኙነት ዓላማዎችን በራሳቸው የብዝበዛ ፍላጐትና ጥቅም ሥር በማዋል በታዳጊ

Digitized by Google

አገሮች ላይ በሚያደርሱት ዘረፋ የሀብት ክምችታቸውን ከመጠን በላይ እያደለቡ ናቸው ።

በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ የሞኖፖል ኩባንያዎች በታዳጊ አገሮች ውስጥ የመዋዕለ ንዋይ እንቅስቃሴ በማድረግ በየዓመቱ ከፍተኛ ትርፍና የሰነድ ክፍያ ይሰበስባሉ ። በዚህም ተግባራቸው የእነዚህ አገሮች የካፒታል ክምችት እየመነመነ እንዲሄድ ያደርጋሉ ። እ. ኤ. አ. ከ1973—75 ባለው የሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከታዳጊ አገሮች ከ23 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በትርፍና በክፍያ ስም ተወስዷል ። ሌላው ቀርቶ የአሜሪካን የግል ኩባንያዎች ብቻ ከታዳጊ አገሮች በየዓመቱ የሚያገኙት የተጣራ ትርፍ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ሥራ ላይ ከሚውለው ዓመታዊ የመዋዕለንዋይ መጠን ጋር ሲነፃፀር 2 ½ ጊዜ እንደሚበልጥ ለመረዳት ተችሏል ።[3]

በዛሬው የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ሁኔታ ውስጥ የካፒታሊስት አገሮች የታዳጊ አገሮችን ብሔራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያዳክሙበት አንዱ መንገድ የንግድ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል ። በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ የግል ኩባንያዎች ወደ ታዳጊ አገሮች የሚልኳቸውን ዕቃዎች ከፍተኛ የዋጋ ተመን እንዲያገኙ ሲያደርጉ በአንፃሩ ግን ከእነዚህ አገሮች ለሚገዟቸው መሠረታዊ ዕቃዎች ዝቅተኛ ዋጋ በመስጠት ታዳጊ አገሮች ለልማት በሚያውሉት የውጭ ምንዛሪ እጦት የተነሳ ከኋላ ቀርነት እንዳይወጡ ተፅዕኖ ያደርጋሉ ። ዓለም አቀፍ የሞኖፖሊ ድርጅቶች በኢኮኖሚ ግንኙነት እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር እያሳደጉ መምጣት ለዚህ ዓይነቱ ችግር መባባስ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል ።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሁለተኛውን ዓለም አቀፍ የአፍሮ እስያ ሕዝቦች የትግል አንድነት ጉባኤ አዲስ አበባ ላይ ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር «ድንበር ዘለልና ባለብዙ ብሔር ኩባንያዎች የዓለምን የንግድ እንቅስቃሴ በሙሉ ቁጥጥራቸው ሥር አውለዋል ለማለት ያስደፍራል ። በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ካለው የካካዎ ፣ የሻይ ፣ የቡና ፣ የትምባሆ ፣ የስንዴ ፣ የጥጥና የመዳብ ንግድ ከ80—95 የብረትና የቦክሳይት ንግድ ደግሞ ከ90—95% የሚካሄደው በእነርሱ ቁጥጥር ነው ።»[4] ሲሉ ያስገነዘቡት ይህንኑ ዕውነታ የሚያረጋግጥ ነው ።

አብዛኞቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮች በቀጥታም ሆነ በሌሎች ተዘዋዋሪ መንገዶች ለታዳጊ አገሮች «የልማት እርዳታዎችን» እንደሚሰጡ ይታወቃል ። ዳሩ ግን የዚህ ዓይነቱ የምዕራባውያን እርዳታ ሥውር የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትን ለማጠናከር የተቀየሰ በመሆኑ የታዳጊ አገሮችን የኢኮኖሚ ግንኙነት ሁኔታ ከኢምፔሪያሊዝም ተፅዕኖ ለማላቀቅ እንደማይረዳ በገሐድ እየታወቀ መጥቷል ። በእርዳታ መልክ ለሚሰጠው ብድር ከፍተኛ ወለድ በመጠየቅ ፣ ክፍያው በውጭ ምንዛሪ እንዲሰጣቸው በማስገደድና የብድሩን ሁኔታ ከተለያዩ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግዴታዎች ጋር በማያያዝ በታዳጊ አገሮች ዕድገትና ሕልውና ላይ ከፍተኛ ማነቆን እየፈጠሩ ናቸው ። በተለይም በአንዳንድ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አማካይነት የሚሰጠው የብድር እርዳታ ታዳጊ አገሮች የንግድ ፣ የውጭ ምንዛሪና የመዋዕለንዋይ ፖሊሲዎቻቸውን ለግል ካፒታል እንቅስቃሴ በሚያመች መንገድ እንዲቀይሱ የሚያስገድድ በመሆኑ ብሔራዊ ጥቅማቸውንና የሕዝቦቻቸውን መሠረታዊ ፍላጐት የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል ።

የኢምፔሪያሊስት አገሮች የታዳጊ አገሮችን ብሔራዊ ሀብት ባላቸው የተለያዩ የኢኮኖሚ ግንኙነት መስኮች ሳቢያ በመዝረፍ ላይ ብቻ አልተወሰኑም ። እነዚህ አገሮች ለማኅበራዊ ዕድገት መፋጠን አስፈላ

Digitized by Google

ጊው የሠለጠነ የሰው ኃይ ል እንዳይኖራቸው በማድረግ ከፍተኛ ደባ ይፈጽሙባቸዋል ። ታዳጊ አገሮች በየጊዜ ው ከሚያፈሩት አነስተኛ የሠለጠነ የሰ ው ጉልበት ውስጥ አብዛኛውን ከፍተኛ የደመወዝ ክፍያ እየሰጡ በመደለል ለቡርዧ ው የአኗኗር ዘይቤና ፍላጐት ተገዥ እንዲ ሆን በማድረግ እናት አገራቸውንና ጭቁን ወገናቸውን እያስከዱ ያስኮበልሏቸዋል ።

ዛሬ በአብዛኛው በካፒታሊስት ሥ ርዓት ተፅዕኖ ሥር ያለው ዓለም አቀፍ የኢ ኖሚ ግንኙነት ለአያሌ የማኅበራዊና የፖ ለቲካ ቀውሶች መከሰት አንዱ ምክንያት መ ሆኑ የሚታወቅ ነው ። የኢምፔሪያሊስት ኣገሮች በዓለም ላይ ከፍተኛ እጥረት የሚታ ዩባቸውን የጥሬ ዕቃዎች ፣ የኃይል ፣ የፋይና ንስና የቴክኖሎጂ ሀብቶች በጦር መጣሪያ ምርት ላይ በገፍ በማዋላቸው በዓለም ኅብረተሰብ የፍጆታና የጥሪት ክምችት መጠን ላይ ከፍተኛ ችግር እንዲደርስ ለማድረግ ችለዋል ። ከዚህም የተነሳ በአንድ በኩል የኢምፔሪያሊዝም የመስፋፋትና የጠብ አጫሪነት ሤራ እያገጠጠ ሲመጣ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዓለም ሕዝቦች ላይ የሚደርሰው የችግር ፥ የረሃብና የሥራ አጥነት ሁኔታ እስከፊ እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል ።

በአሁኑ ወቅት በአገሮች መካከል ያለው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ጠባዩ ሰፊና ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ በየትኛውም አገር የሚፈጠረው ቀውስና ችግር በዚያው አካባቢ ተወስኖ የሚቀር አይደለም ። ስለ ሆነም ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚ፥የፖለቲካና የወታደራዊ የበላይነት ለማግኘት በሚያደርገው ገደብ የለሽ እሩጫና በዚህም ሳቢያ የሚፈጠሩት ችግሮች የታዳጊ አገሮችን ሁኔታ እያባባሱት መጥተዋል ። ከዚህም የተነሳ ዛሬ አያሌ ታዳጊ አገሮች ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎች ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ጋር በመሆን ለሰላም ፥ ለማኅበራዊ ዕድገትና በእኩልነት ላይ ለተገነባ አዲስ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ግንኙነት ሥርዓት መመሥረት የሚያደርጉት ትግል ሰፋትና ጥልቀት እያገኘ በመምጣት ላይ ይገኛል ።

ሶሻሊስታዊ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት

ታላቁ የጥቅምት አብዮት ሩሲያን ከካፒታሊዝም የብዝበዛ ሰንሰለት ነፃ በማድረግ በዓለም ላይ የመጀመሪያዋ የሶሻሊስት አገር እንድትሆን አድርጓታል ። ከዚያም ወዲህ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ሶሻሊዝም በአያሌ የአውሮፓ፥የእስያና የላቲን አሜሪካ አገሮች ዘንድ ድል እያደረገ በመምጣቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሶሻሊስት ሥርዓት እንዲከሰትና እየዳበረ እንዲመጣ አድርጓል ።

የሶሻሊስት ሥርዓት መከሰት በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት መስክ ውስጥ አዲስ ሁኔታ እንዲታይ አድርጓል ። ይህ አዲስ ሁኔታ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ግንኙነት ባሕሪ በአገሮች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ መታየት ነበር።አዲሱ ሶሻሊስታዊ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት የአገሮችን የግል መብት በመጠበቅ ፥ ብ ሔራዊ ነፃነትንና ሕልውናን በማክበር ፥ በው ስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት እንዲሁም ' በጋራ ትብብርና ጥቅም መርሆዎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለአገሮች ብሔራዊ ዕድገትና ለዓለም ሕዝቦች ሰላምና ደኅንነት ፍቱን መሠረት ነው ።

በሶሻ ሊስት አገሮችና በሌሎች አገሮች መካከል የሚደረገው የኢኮኖሚ ግንኙነት ሁሉ ከላይ በተዘረዘሩት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ የግንኙነቱ ጠባይና ይዘ ት ከሶሻሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚ ዕድገትና ጥንካሬ ጋር እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል ። በዚህም መሠረት በአሁኑ ወቅት በሶሻሊስ ት አገሮችና በታዳጊ አገሮች መካከል ያለ ው የኢኮኖሚ ግንኙነት አያሌ የትብብር መ ስኮች አሉት ። ከነዚህ የትብብር መስኮች ፣ መካከል በረዥም ጊዜ

Digitized by Google

የትብብር ውሎች ላይ የተመሠረቱ የን
ግድ ፡ የእርዳታና የባህል ግንኙነቶች ዋን
ኞቹ ናቸው ።

በፈታደኝነትና በጋራ ስምምነቶች ላይ
በመመሥረት ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የሚ
ደረግ የንግድ ግንኙነት በሁለቱ ወገኖች
መካከል የሚከናወነውን የዕቃዎች ልው
ውጥና ንግድ ፅኑ መሠረት እንዲረናው ከመ
ርዳቱም በላይ መጠኑም በየጊዜው እያደገ
እንዲሄድ ያደርጋል ። ከዚህም በተጨማሪ
በታዳጊ አገሮች የሚቀየሱት የልማት እን
ቅስቃሴዎች በማዕከላዊ ዕቅድ ከሚመራው
የሶሻሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር
ትንጅት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ በዓ
ለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ውስጥ
ከሚታዩት ገብታዊ ሁኔታዎች ተዕዕና
ፅመላቀቅ ታላቅ አስተዋጽኦ አለው ።

በአሁኑ ወቅት እያሌ ታዳጊ አገሮች ከተ
ለያዩ የሶሻሊስት አገሮች የርዳታ ዘርፍ ከፍ
ተኛ ጥቅም በማግኘት ላይ ይገኛሉ።በሶሻሊ
ስት አገሮችና በታዳጊ አገሮች መካከል
ባለው የውጭ እርዳታ ትብብር አማካይነት
በተለያዩ አገሮች ውስጥ እያሌ የኢንዱስ
ትሪና የሌሎች የልማት ተቋሞች ግንባታ
ተከናውኗል ። በሶሻሊስት አገሮች እርዳ
ታና ትብብር የሚቋቋሙት እነዚህ የኢን
ዱስትሪና የልማት ተቋሞች በግል ካፒታ
ሊስቶች ከሚቋቋሙት የመዋዕለ ንዋይ
ፕሮጀክቶች የተለየ ባሕሪይ አላቸው ።
ይኸውም በታዳጊ አገሮች ውስጥ ለሶሻሊ
ስታዊ የዕድገት ጉዳና ቁሳዊ መሠረት የሆ
ነውን የመንግሥትና የኅብረት ይዞታ በማ
ስፋፋትና በማጠናከር እነዚህ አገሮች ከካ
ፒታሊስቱ ሥርዓት የኢኮኖሚ ጥገኝነት
እንዲላቀቁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋ
ቸው ነው ።

የሶሻሊስት አገሮች ከሚያደርጉት የእር
ዳታና የትብብር ዘርፍ አንዱ ዘመናዊ ቴክ
ኖሎጂን በቀላሉ ወደ እነዚህ አገሮች የማ
ስተላለፉ ሁኔታና ለዚህም አስፈላጊ የሆነ
ውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በየመስኩ የማ
ዘጋጀቱ ተግባር ነው ። በዚህ ረገድ ብሔ
ራዊ ካድሬዎችን የማሠልጠኑ ተግባር በራ
ሳቸው በታዳጊ አገሮች ውስጥ የቴክኒክ
ማሠልጠኛና የምርምር ተቋሞች በመመ
ሥረትና በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ በሚ
ገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችና ዩኒቨ
ርስቲዎች ውስጥ ለመማር የሚያስችል
የነፃ ትምህርት ዕድል በብዛት በመስጠት
የሚከናወን ነው ።

ዛሬ በሶሻሊስት አገሮች መካከል ያለ
ውን የዓላማና የተግባር አንድነት የሚያን
ጸባርቀው የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ተዋ
ሕዶ (Socialist Economic Integration)
ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ይታወቃል ።
የዚህ ዓይነቱ በጋራ ዓላማና ዘላቂ
ጥቅም ላይ የተመሠረተው ፅኑ ኅብረት
በሶሻሊስት አገሮችና በታዳጊ አገሮች መካ
ከል ላለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ቀና መን
ገድ መፍጠሩ አያጠራጥርም ። ሶሻሊስት
አገሮች ታዳጊ አገሮችን በተለያዩ መስኮች
ለመርዳት በሚያደርጉት ጥረት ፍላጐታ
ቸውንና ችሎታቸውን በከፍተኛ ደረጃ የሚ
ያስተባብሩት በዚህ ዓይነቱ የጋራ መድረክ
ላይ መሆኑ ለማንኛችንም ግልጽ ነው ።
የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ተዋሕዶ ከአባል አገ
ሮች የጋራ ጥረት የተገኘውን ሀብት አግ
ባብ ባለውና በተቀነባበረ መንገድ በታዳጊ
አገሮች ውስጥ ሥራ ላይ እንዲውል በማድ
ረግ በኩል ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

በተጨማሪም የሶሻሊስት የኢኮኖሚ
ተዋሕዶ በአመሠራረቱና አሠራሩ ስፊ
ዲሞክራሲያዊ ይዘቶች ያሉት በመሆኑ
በሶሻሊስት አገሮች መካከል በተቀየሰው
የረዥም ጊዜ የትብብር ፕሮግራሞች ውስጥ
ታዳጊ አገሮች እንደችሎታቸው መጠን
ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ይፈጥር
ላቸዋል ። በዚህም መሠረት በሶሻሊስትና
በታዳጊ አገሮች መካከል የሚደረገው የኢ
ኮኖሚ ግንኙነት ቅርጽና ይዘት ቀስ በቀስ
እየዳበረ በመሄድ ወደ ሁለገብ የትብብር
ደረጃ የሚሸጋገርበት ሁኔታ ይፈጠራል ።

Digitized by Google

አዲሱ የሶሻሊስት ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት በቋሚና በትክክለኛ መርሆዎች ላይ የተሞረኮዘ በመሆኑ በግንኙነቱ ውስጥ ተሳታፊ በሚሆን በማንኛውም አገር ላይ ተፅዕኖ አያሳድርም ። የግንኙነቱ መሠረታዊ ዓላማና በእያንዳንዱ አገር ውስጥ ያለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን አስቀድሞ በመገምገም ይህንኑ ከእያንዳንዱ አገር ብሔራዊ ፍላጐትና ከአጠቃላዩ የማኅበራዊ ዕድገት ዓላማ ጋር በማገናዘብ በአገሮች መካከል ጤናማ የኢኮኖሚ ትብብርን በማስፈን ላይ ያተኮረ ነው ። ከዚህ ዓይነቱ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ ከተመሠረተ አዲስ የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነት ታዳጊ አገሮች ከፍተኛ ጥቅሞችን ሊያገኙ ይችላሉ ።

ዳሩ ግን ዛሬ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ስንነሳ ታዳጊ አገሮች የሶሻሊስቱ ሥርዓት ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል በፈጠረው ሁኔታ በሚገባ መጠቀም ችለዋል ለማለት አያስደፍርም ። ስለዚህ እነዚህ አገሮች የብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገታቸውን በማፋጠን ከካፒታሊስቱ ዓለም የገበያ ተፅዕኖ ለመላቀቅ በሶሻሊስቱ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ውስጥ ያላቸውን ሚና በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግና ማጠናከር የማይታለፍ አማራጭ ይሆናል ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የተወሰዱ እርምጃዎች የአገሪቷን የውጭ ኢኮኖሚ ግንኙነት በሚመለከት ያስከተሉት ለውጥ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከነበረበት የግፍና የጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ ለብዙ ዓመታት ከፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት የገዥ መደቦችና ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ተወካዮች ጋር ሲታገል ቆይቶ በየካቲት ወር 1966 ምኞቱንና ተስፋውን በተጨባጭ ተግባራዊ አድርጓል ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከምኞቱና ከተስፋዎቹ የመጀመሪያውን ደስታ የተጐናጸፈው በታኅሣሥ ወር 1967 የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሚከተለው የዕድገት ፈለግ ሶሻሊዝም መሆኑን በይፋ ባወጣበትና ከዚያም በማከታተል አያሌ ሥር ነቀል እርምጃዎችን በፖለቲካው ፣ በኢኮኖሚውና በማኅበራዊ መስኮች መውሰድ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነበር ። ከተወሰዱትም አብዮታዊ እርምጃዎች መካከል እንደ ፤

—የማምረቻና የማከፋፈያ ተቋሞች እንዲሁም የባንክና የመድን ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆናቸው፣
—መሬት የሰፊ ሕዝብ ንብረት እንዲሆን መደረጉ ፣
—የዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በይፋ መውጣቱ ፣
—የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋላቸው ፣
—የአብዮቱ መሠረት የሆኑት ሕዝባውያን ድርጅቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ መደረጉ ፣
—የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የፖለቲካ የበላይነት ለማረጋገጥና ለሶሻሊዝም ግንባታ በተጨባጭ ዕውን መሆን የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲን ለማደራጀት ኃላፊነት የተጣለበት ኢሠፓአኮ እንዲቋቋምና ይፋ እንቅስቃሴውን እንዲጀምር መደረጉና የመሳሰሉት በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሱ ናቸው ።

እነዚህና ሌሎችም በየወቅቱ የተወሰዱት አያሌ መሠረታዊ የለውጥ እርምጃዎች የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ከኋላቀርነትና ከጉስቁልና ኑሮ በአፋጣኝ ለማላቀቅ ሰፊ ዕድልን ከመክፈታቸውም በላይ በዓለም አቀፍደረጃ ከዕውነተኛ የመደብ አጋሮቹና ወዳጆቹ ጐን በመቆም ለፍትሕና ለእኩልነት እንዲታገል አብቅተውታል ።

አገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር የምታደርገው የኢኮኖሚ ግንኙነት አያሌ መስኮች ያሉት ሲሆን ከዚህም ውስጥ ጉልህ

ሥፍራ ይዘው የሚገኙት በንግድ ፣ በእር
ዳታና በትምህርት መስኮች የሚደረጉት
ግንኙነቶች ናቸው ።

ከአብዮቱ በፊት የኢትዮጵያ የውጭ
ንግድ ግንኙነት ከካፒታሊስት አገሮች
ጋር በከፍተኛ ደረጃ የተሳሰረ እንደነበረ
ይታወቃል ። አብዮቱ በፈነዳበት ወቅት
ማለትም እ. ኤ. አ. በ1974 ኢትየዮጵያ
ከውጭ ንግድ ካገኘችው 547.3 ሚሊዮን
ብር ውስጥ 349 ሚሊዮን ብር ወይም
63.8% ሲሆን ከገቢ ንግድ ክፍያ 586
ሚሊዮን ብር ውስጥ ደግሞ 396 ሚሊዮን
ወይም 67.6% የካፒታሊስት አገሮች ድርሻ
ነበር ። በአንፃሩ በዚሁ ዓይነት የሶሻሊስት
አገሮች ድርሻ ከውጭ ንግድ 35.3 ሚሊ
ዮን ብር ወይም 6.5% ሲሆን የገቢ
ንግድ ድርሻ ደግሞ 38.6 ሚሊዮን ብር
ወይም 6.6% ነበር ። በዚሁ ወቅት የታዳጊ
አገሮች የውጭ ንግድ ድርሻ 162.4 ሚሊዮን
ብር ወይም 29.7% እና የገቢ ንግድ ደግሞ
103.3 ሚሊዮን ብር ወይም 17.6%
ነበር ። [5] ይህ ሁኔታ ከአብዮቱ ወዲህ
መጠነኛ ለውጥ እያሳየ መጥቷል ። ለምሳሌ
እ. ኤ. አ. በ1980 ከጠቅላላ የወጪ ንግድ
878.5 ሚሊዮን ብር ውስጥ የካፒታሊስት
አገሮች ድርሻ 500.7 ሚሊዮን ብር ወይም
57%ሲሆን ከጠቅላላው የገቢ ንግድ 1439.3
ሚሊዮን ብር ውስጥ 855.7 ሚሊዮን
ወይም 57.3% የነኝሁ አገሮች ሲሆን፣ይህም
የካፒታሊስት አገሮች የወጪና የገቢ ንግድ
መቶኛ ድርሻ እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል ።
በሌላ በኩል እ. ኤ. አ. በ1980 የሶሻሊስት
አገሮች የወጪ ንግድ ድርሻ 146.7 ሚሊ
ዮን ብር ወይም 16.7% ሲሆን በገቢ ንግድ
በኩል ደግሞ 425.6 ሚሊዮን ወይም28.5%
ድርሻ በማሳየት አጠቃላይ ዕድገት አሳይ
ቷል ። በተመሳሳይ ወቅት ከታዳጊ አገሮች
ጋር ያለው የወጪ ንግድ ድርሻ 231 ሚሊ
ዮን ብር ወይም 26.3% ሲሆን በገቢ ንግድ
በኩል ደግሞ 200.1 ሚሊዮን ብር ወይም
13.4% ሆኖ ይገኛል ። [6] በመሆኑም ከታዳጊ
አገሮች ጋር ያለው የንግድ ልውውጥ በመ
ጠኑም ቢሆን ያለው ድርሻ እየቀነሰ መጥ
ቷል ።

ከታዳጊ አገሮች መሐል ከጐረቤት አገ
ሮች ጋር ማለትም ከጅቡቲ ፣ ከኬንያና
ከሱዳን ጋር ኢትዮጵያ የንግድ ልውውጥ
ታደርጋለች ። እ. ኤ. አ. በ1974 ከኢትዮ
ጵያ የወጪ ንግድ ጅቡቲ የ38.5 ሚሊዮን
ብር ኬንያ የ2 ሚሊዮን ብር እና ሱዳን
የ5.6 ሚሊዮን ብር ከገቢ ንግድ ደግሞ
ጅቡቲ የ1.1 ሚሊዮን ብር ፣ ኬንያ የ14.6
ሚሊዮን ብር እና ሱዳን የ2.9 ሚሊዮን ብር
ድርሻ ነበራቸው ። እ. ኤ. አ. በ1980 ከኢ
ትዮጵያ የወጪ ንግድ ጅቡቲ የ100.4 ሚሊ
ዮን ብር፣ ኬንያ የ1.4 ሚሊዮን ብር ድርሻ
ሲኖራቸው ሱዳን ግን ከምላ ጉደል ምንም
ዓይነት ድርሻ አልነበራትም ። በዚሁዓመት
የጐረቤት አገሮች ከገቢ ንግድ ድርሻ ጅቡቲ
የ11.3 ሚሊዮን ብር፣ ኬንያ የ15.6 ሚሊዮን
ብር እና ሱዳን የ10.5 ሚሊዮን ብር ሆኖ
ይገኛል ። [7]

ከላይ እንደታየው የኢትዮጵያ የወጪ
ንግድ እ. ኤ. አ. በ1974 መጨረሻ 547.3
ሚሊዮን ብር የነበረው እ. ኤ. አ. በ1980
ወደ 878.5 ሚሊዮን ብር ከፍ በማለቱ የተ
ገኘው የውጭ ምንዛሪ በ331.2 ሚሊዮን
ብር ወይም በ37.7% አድጓል ። የገቢ ንግድ
ደግሞ ከ586 ሚሊዮን ብር ወደ 1493.3
ሚሊዮን ብር ከፍ በማለቱ አገሪቱ የከፈለች
ው በ907.3 ሚሊዮን ብር ወይም በ60.8%
አድጓል ። ስለሆነም በ1974 የአገሪቱ የሸ
ቀጥ ንግድ ሚዛን በ38.7 ሚሊዮን ብር
ኪሣራ ሲያሳይ እ. ኤ. አ. በ1980 የ614.8
ሚሊዮን ብር ኪሣራ አስመዝግቧል ። [8]

ይህን ሁኔታ ከፈጠሩት ምክንያቶች መካ
ከል በወቅቱ በካፒታሊስቱ ዓለም የደረሰው
የኢኮኖሚ ቀውስና ከዚህም የተነሳ የኢን
ዱስትሪ ሸቀጦችና የነዳጅ ዋጋ ከመጠን
በላይ በመናሩ ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ
የኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና ሐቀኛ የሆነ
ዓላማው የማይዋጥላቸው የካፒታሊስት አገ

Digitized by Google

ሮች ቀደም ሲል ይሰጡት የነበረው የአጭር ጊዜ ብድሮች በመቀነሳቸውና በውጭ ምንዛሪ አማካይነት የሚደረግ የቀጥታ ክፍያ በመጠየቃቸው ነበር።በተጨማሪም በጥራትም ሆነ በመጠን ከውጭ የምናስመጣቸው ሸቀጦችና የማምረቻ መሣሪያዎች በከፍተኛ ደረጃ መጨመራቸውና ዋጋቸውም በጣም እየናረ በመምጣቱ ነው ።

መስከረም 2 ቀን 1975 ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የአብዮታችን የ8ኛ ዓመት በዓል በተከበረበት ዕለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባሰሙት መሪ ቃል ፥ በካፒታሊስቱ ዓለም ውስጥ ካለው የዋጋ መለዋወጥ ሁኔታና ከምዕራባውያን ጋር በሚደረገው የተዛባና በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ የኢኮኖሚ ግንኙነት ሳቢያ በአገራችን ላይ የሚደርሰውን ችግርና ተፅዕኖ ሲገልጹ ፤

«ከ10 ዓመት በፊት ከ50 እስከ 60 ሚሊዮን ብር ብቻ ይፈጅ የነበረውን የሲሚንቶ ፋብሪካ ዛሬ የምንሠራው በ250 ሚሊዮን ብር ነው።ከጥቂት ዓመታት በፊት በ73ሺህ ብር ይገዛ የነበረው የጭነት መኪና ዛሬ በ130 ሺህ ብር ፥ በ100 ሺህ ብር ይገዛ የነበረው አውቶቡስ ዛሬ የሚያወጣው ወደ 250 ሺህ ብር ነው ። ከሶስት ዓመት በፊት ከ22 ሺህ ብር በላይ የሚያወጣው ትራክተር ዛሬ የሚገዛው በ45ሺህ ብር ነው ። በዚሁ ጊዜ ክልል ውስጥ 14 የአሜሪካ ዶላር ያወጣ የነበረው የአንድ በርሜል ድፍድፍ ዘይት ዋጋ ዛሬ ከ30 ዶላር በላይ ንሯል ። ከሦስት ዓመት በፊት በዓለም ገበያ ላይ ወደ አምስት ሺህ ዶላር ይጠጋ የነበረው የአንድ ቶን ቡና ዋጋ ዛሬ ከሦስት ሺህ ዶላር በታች ወርዷል ።ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ዘጠኝ መቶ ዶላር ወርዷል ።ወደ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ዶላር የነበረው የአንድ ቶን ቆዳ ዋጋ ዛሬ ወደ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ዶላር ያህል አዘቅዝቋል ። ከአምሳ ዶላር በላይ ያወጣ የነበረው አንድ ደርዘን ሌጦ ወደ ሰላሳ አምስት ዶላር ግድም አሽቆልቁሏል ፤»[9] ብለው ነበር ።

የንግድ ልውውጣችን በ1974 65.7% ከካፒታሊስት አገሮች ጋር ነበር ። በመሆኑም ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ በአንድ በኩል አገራችን ቀደም ሲል የነበራትን የተዛባ የንግድ ግንኙነት በአንዴ ለመለወጥ የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅምና የንግድ ተቋሞች እንደሌላት በማወቅ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ለሶሻሊዝም ግንባታ ቆርጦ የተነሳ መሆኑን እየተረዱ በመምጣታቸው የካፒታሊስት አገሮች በብሔራዊ የውጭ ንግዳችን ላይ ያላቸውን ከፍተኛ ቁጥጥርና ይዞታ በመጠቀም በዋጋ ፥ በአከፋፈልና በሌላም መንገዶች ተፅዕና ከማድረግ አልተቆጠቡም ። የኢምፔሪያሊስት አገሮች ተቀጥያ የሆኑ አንዳንድ የዘይት ሻጭ ዓረብ አገሮችም በገበያ ዋጋ የሚገዛውን ነዳጅ እንኳ ለኢትዮጵያ አንሸጥም በማለት ለተፈጸመብን የኢኮኖሚ አሻጥር አስተዋጽኦ አድርገው እንደነበረ የማይረሳ ነው ።

ዳሩ ግን «የሁሉም አገር ወዝ አደሮች ተባበሩ» የሚለውን ትክክለኛ መርሆ መሠረት በማድረግ ሐቀኛ የሶሻሊስት አገሮች ከጐናችን በመቆም ለአብዮታችን ድልና ጥንካሬ ሲሉ በኢኮኖሚም ሆነ በሌሎች መስኮች ከፍተኛ እርዳታና ድጋፍ በመስጠት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገውልናል ። የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት ለመግታትና ለአድኃርያን የቅልበሳ ሤራ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ኢምፔሪያሊስቶችና ተከታዮቻቸው ነዳጅ ላለማቅረብ በአቅማሙበት ጊዜ አገሪቷ ሊያጋጥማት ይችል የነበረውን አደገኛ ሁኔታ በመረዳትና በማጤን የሶቭዬት ኅብረት መንግሥት አገራችን የምትፈልገውን ያህል የነዳጅ መጠን በተስማሚ ዋጋ በአስተማማኝ ሁኔታ እንድታገኝ አድርጓል ።

ከውጭ ኢኮኖሚ ግንኙነት መስኮች አንዱ የእርዳታ ዘርፍ ነው ። የውጭ እርዳታ ሁለት መልኮች ያሉት ነው ፤ የመጀመሪያው ነፃ እርዳታ ሲሆን ሌላው ደግሞ ለልማት ሥራ የሚውል የረጅም ጊዜ ብድር ነው ።

Digitized by Google

ባለፉት ፲፩ ዓመታት ማለትም ከ1963—1973 ድረስ የተገኘው ጠቅላላ ዕርዳታ 4,384.9 ሚሊዮን ብር ነው ። ከዚህ ውስጥ ከ1963—1966 ድረስ የተገኘው የውጭ ዕርዳታ መጠን 1,015.2 ሚሊዮን ብር ሲሆን ከ1967-1973 ደግሞ 3,368.39 ሚሊዮን ብር መድረሱ ታውቋል ። ይህም የሚያሳየው በቅድመ አብዮት የተገኘው ዕርዳታ በአማካኝ ዓመታዊ ግምት 252.3 ሚሊዮን ብር በድኅረ አብዮት ደግሞ 398.3 ሚሊዮን ብር፥ መሆኑን ነው ። ከ1963—66 ከተገኘው ጠቅላላ ዕርዳታ ውስጥ የነፃ ዕርዳታ ድርሻ ደግሞ 1,732.9 ሚሊዮን ብር ነው ። ከአብዮቱ በፊት በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ የረጅም ጊዜ የብድር ድርሻ 708.5 ሚሊዮን ብር ሲሆን ከአብዮቱ በኋላ በተጠቀሱት ዓመታት ወቅት የረጅም ጊዜ ብድር ድርሻ 1,636.8 ሚሊዮን ብር ነው ።[10] ይህም የሚያሳየው የተገኘው የዕርዳታ መጠን ከአብዮቱ በኋላ እያደገ መምጣቱን ነው ። ከጠቅላላው ዕርዳታ ውስጥ ከ1963—66 የተገኘው 351.2 ሚሊዮን ብር ወይም 34% ከካፒታሊስት አገሮች ሲሆን በዚሁ ወቅት የሶሻሊስት አገሮች ድርሻ 207.0 ሚሊዮን ወይም 20% ነው ። በድህረ አብዮት ማለትም ከ1967—73 የካፒታሊስት አገሮች ድርሻ 611.2 ሚሊዮን ብር ወይም 18% ሲሆን የሶሻሊስት አገሮች ድርሻ ደግሞ 698.7 ሚሊዮን ብር ወይም 20% ነው ።[11] በመሆኑም እንደ ንግድ ልውውጥ ድርሻ ሁሉ የሶሺያሊስት አገሮች መቶኛ ድርሻ በድኅረ አብዮት በዕርዳታ በኩልም እያደገ መጥቷል ። ከላይ እንደታየው የካፒታሊስት አገሮች የዕርዳታ መቶኛ ድርሻ በድኅረ አብዮት እያሽቆለቆለ መጥቷል ።

ለአንድ አገር ነፃና ጤናማ የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ከሆኑት ውስጥ የተማረ የሰው ኃይል አንዱ ነው ። ኢትዮጵያ ለልማት የዘረጋችውን ዕቅዶች ለማሟላት በልዩ ልዩ መስክ የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲኖራት ማስፈለጉ ግልጽ ነው ። ይህንንም ለማሟላት በተለይ ከአብዮቱ ወዲህ በአገርም ውስጥ ሆነ በውጭ አገር ኢትዮጵያውያንን በየመስኩ ለማሠልጠን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።በኢትዮጵያ ያለውን የተማረ የሰው ኃይል ችግር በመረዳትና የሚደረገውንም ጥረት በመደገፍ የሶሻሊስት አገሮች በከፍተኛ ደረጃ ትብብራቸውን እያሳዩ ነው።በዚህም መሠረት በ1966 ከነኝህ አገሮች የተገኘው ስኮላርሽፕ ከ80 ያነሰ ሲሆን በ1974 ብቻ የተገኘው ደግሞ ከ650 በላይ መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው ። በአንጻሩ የካፒታሊስት አገሮች በ1974 የሰጡት ስኮላርሽፕ ከ150 በታች ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 120 የሚሆነው ከኢጣሊያን መንግሥት የተገኘ ነው ። በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ከ5,000 በላይ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ሶሺያሊስት አገሮች በመሠልጠን ላይ ይገኛሉ ።[12]

አንድ አገር ከሌላው ጋር የሚያደርገው የኢኮኖሚ ትብብር ሚዛናዊነት የሚመዘነው ከትብብሩ በሚገኘው ውጤት ሁለቱም ወገኖች በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ድርሻ ማግኘት ሲችሉ ነው ። በዚህም መሠረት አገራችን በቅርቡ ከወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ጋር የትብብር ውል በማድረግ ለብሔራዊ ኢኮኖሚያችን ነፃ ዕድገትና ለሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ፍላጎቶች በየደረጃው መሟላት ትክክለኛውን እርምጃ መውሰዷ ይታወሳል ። በተደረገውም ውልና ስምምነት መሠረት ከሶቭየት ኅብረት በተገኘው 468.2 ሚሊዮን የኢት. ብር ዕርዳታ አማካይነት የነዳጅና የጋዝ ፍለጋ ፥ በድሬዳዋ የሲሚንቶ ፋብሪካ ሥራ ፥ በመልካ ዋከና የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት ሥራ ፥ በአዶላ የወርቅ ማዕድን ማስፋፋት ሥራ ፥ በናዝሬት የትራክተርና የእርሻ መሣሪያዎች ፋብሪካ ሥራ ፥ በጋምቤላ የእርሻ ልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እየተካሔደ ሲሆን ፥ በተመሳሳይ መንገድ ከምሥራቅ ጀርመን ፥ ከቼኮ

Digitized by Google

በሶቭየት ህብረት እርዳታ በኦጋዴን ለዘይትና ለጋዝ ፍለጋ የሚደረገው የጥልቀት ቁፋሮ



በሙገር በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ትብብር በመሠራት ላይ ያለው የሲሚንቶ ፋብሪካ

Digitized by Google

ዝሎቫኪያ ፣ ከቡልጋሪያና ከሌሎች ወዳጅ አገሮች በተገኘው የ96 ሚሊዮን የኢት. ብር ብድር ደግሞ የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ፣ የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ፣ የዘይት ፋብሪካዎች ፣ የሸክላ ሥራ ፕሮጀክት ፣ የእንስሳት ሀብትና የእርሻ ልማት ፕሮጀክቶችና የመሳሰሉት ሥራዎች በመካሔድ ላይ ይገኛሉ ። ይህ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየው ዛሬ አድኃርያን በሀገር ወዳድነት ካባ ፀመኮፈስ ከሶሺያሊስት አገሮች ጋር የተገነባው የኤኮኖሚ ግንኙነት እየዳበረ እንዳይሔድ በየሥፍራው እንደሚያናፍሱት ፀረ—ሶሺያሊስትና ፀረ—ወዝአደራዊ ዓልም አቀፋዊነት ሰጣካ ሳይሆን፣የታዳጊ አገሮች ሕዝቦች እውነተኛ አጋሮችና የማንኛውም ሐቀኛ አብዮት መከታና አለኝታ የሶሺያሊስት አገሮች መሆናቸውን ነው ። የነዚህ ፀረ—ሶሺያሊስት ኃይሎች ዓላማ ግልጽ የሆነውን የፖለቲካ ዓላማችንን በመፃረር ፣ ጓድ ሊቀ መንበር ለሁለተኛው የኢሠፓአኮ ጉባኤ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ በትክክል እንዳስቀመጡት ፣«አብዮታችን ከሶሺያሊስቱ ማኅበረሰብ ተነጥሎ በብቸኝነት ለጥቃት እንዲጋለጥ ለማድረግ ነው ። »[13]

በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታሊስት አገሮች አገራችን የምትከተልውን ትክክለኛ የዕድገት ፈለግ በመፃረር ቀደም ሲል ይሰጡ የነበረውን የዕርዳታ መጠን በድኅረ አብዮት የባሰውን እየቀነሱ መምጣታቸውን መገንዘብ እንችላለን ። ለምሳሌ ከአብዮቱ በኋላ እ. ኤ. አ. ከ1975 እስከ 1977 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ከካፒታሊስት አገሮች ለልማት ያገኘው ዕርዳታ ከ5.3 ዶላር በነፍስ ወከፍ ወደ 3.7 ዶላር በነፍስ ወከፍ ዝቅ ብሎአል ። [14] ይህ እንግዲህ ከኢምፔሪያሊዝም የኤኮኖሚ አሻጥሮች መካከል አንዱ ነው ። በሌላ በኩል አይ. ኤም. ኤፍ (IMF) ፣ አይ. ቢ.አር.ዲ (IBRD) ፣ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC) ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅትና (IDA) የተለያዩ አካሎች በሚሰጡት ዕርዳታዎች አማካይነት ኢምፔሪያሊዝም በአብዮታዊ ሂደታችን ላይ ተፅዕኖና ችግር ለመፍጠር ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም ። እዚህ ላይ ነገሩን በትክክል ለማስቀመጥ ያህል ከካፒታሊስት አገሮችና በእነዚህ አገሮች ውስጥ ካሉት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ማንኛውንም ዓይነት ዕርዳታ መቀበል ወይም ግንኙነት ማድረግ አያስፈልግም ለማለት ሳይሆን ፣ በምንወስደው ዕርዳታና በምናደርገው ግንኙነት ሳቢያ በምናራምደው የፖለቲካና የኤኮኖሚ ዕድገት ተግባሮች ላይ ደንቃራ በመፍጠር ወደዘላቂው ዓላማችን ከሚያደርሰን ትክክለኛ የዕድገት ጐዳና እንዳንወጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን መሆኑን ለማስገንዘብ ያህል ነው ። በእርግጥ ይህ ሁኔታ ከሠርቶ አደሩ ፓርቲ መመሥረትና ከሕዝባዊ ሥልጣን መጠናከር ጋር እስተማማኝነቱ የሚጎላ ቢሆንም አሁን ባለንበት ሁኔታ በኤኮኖሚው ውስጥ ተግባራዊ የሚሆነው እርምጃ ሁሉ በታቀደው የፖለቲካ ግባችን ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ስለሚኖረው «የሆዱን አይቶ ጀርባውን ተወጋ» እንዲሉ የወቅቱን ችግራችንን ብቻ አጉልቶ በማቅረብ የወደፊቱን ብሩህ ተስፋችንን እንዳናጨልም በጥንቃቄና ከነባራዊው የዕድገት ሕግጋት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ወደ ግባችን መጓዝ ይኖርብናል ።

ኋላቀር አገሮች የበለፀጉ የካፒታሊስት አገሮች የረዥም ጊዜ ብድር ከወለድ ነፃ በሆነ መንገድ ወይም በአነስተኛ የወለድ መጠን እንዲሰጧቸው በተለያዩ የዓለም አቀፍ መድረኮችና ስብሰባዎች ላይ ትክክለኛ ጥያቄ ቢያቀርቡም ይህ ጥያቄያቸው ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ አልቻለም ። ከዚህም ሌላ እነዚህ ታዳጊ አገሮች ቀደም ሲል ያለባቸው የዕዳ መጠን እንዲሠረዝላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢውን መልስ አላገኘም ። አንዳንድ ቀንደኛ የካፒታሊስት አገሮች እነርሱ ለፈለጉት አገሮች ዕዳውን ሲያነሱ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ተራማጅ አገሮች ግን አሻፈረን ብለ

Digitized by Google

ዋል ። ይህም አድራጉታቸው ፀረ ፍትሕና
ማኅበራዊ ዕድገት አቋማቸውን በይበልጥ
አጋልጦታል ።

ላለፉት ስምንት ዓመታት የተካሔደው
ሥር ነቀል አብዮት አገራችንን ከተራማጁ
የዓለም ኅብረተሰብ ጐራ ውስጥ እንድት
ገባ አድርጓታል ። ይህም በመሆኑ በድኅረ
አብዮት የውጭ ኤኮኖሚ ግንኙነቷ ከሶሺያ
ሊስት አገሮች ጋር እያደገ ሲሔድ ከካፒታ
ሊስት አገሮች ጋር በአንዳንድ መልኩ እየ
ቀነሰ መጥቷል ። ለምሳሌ ዕርዳታን ብንወ
ስድ ከሶሻሊስት አገሮች የሚገኘው እየጨ
መረ ሲመጣ የካፒታሊስት አገሮች ቀን
ሷል ። የአንዳንዶቹም ተቋርጧል ። ኢት
ዮጵያ የውጭ ኤኮኖሚ ግንኙነቷን የምታ
ጠናክረው ዓላማችንን ከሚደግፉ ሌሎች
አገሮችም ጋር በመሆኑ በኤኮኖሚ ፣ በሶሺ
ያልና በንግድ ትብብር ከአብዮቱ ወዲህ
ከታዳጊ አገሮች ጋር ስምምነት አድርጋለች።
ከደቡብ የመን ፣ ከሊቢያ ዓረብ ጀማህሪያ
እንዲሁም ከኬንያ ፣ ከጅቡቲና ከሌሎችም
ጋር የተደረጉት የኤኮኖሚ ግንኙነቶችና
የትብብር ስምምነቶች የዚሁ ጥረት ውጤ
ቶች ናቸው ። ለወደፊቱም ቢሆን በዚህ
በኩል ያለው ፍላጐትና ጥረትም እየዳበረ
መምጣት ይኖርበታል ። አገራችን ከካ
ፒታሊስቱ የዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ
ግንኙነት ተፅዕና ለመላቀቅ በምታደርገው
ትግል እ. ኤ. አ. ከ1972—1980 ባለው
ጊዜ ውስጥ ከሶሺያሊስት አገሮች ጋር የተ
መሠረተው የወጪ ንግድ ግንኙነት ከ7.3%
ወደ 17%፣ የገቢ ንግድ ከ4.2% ወደ 28%
ከፍ ሲል ፣ ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር
ያለውም የወጪ ንግድ ግንኙነት 21.8%
ወደ 24% ከፍ ማለቱ ከሶሺያሊስትና ከታ
ዳጊ አገሮች ጋር ያለው የኢኮኖሚ ግንኙ
ነት እየተስፋፋ መሔዱን ያመለክታል።[15]
ይህንኑ በማስመልከት ጓድ ሊቀ መንበር
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓአኮ 1ኛ
ጉባኤ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ፣—

በዓለም የኢኮኖሚ ግንኙነታችን ላይ
ግልጽ ለቋም ሊኖረን ይገባል።የአገራችንን
የውስጥ ግንባታ ተግባር እያጠናከርን የተዛ
ባውን ሁኔታ ለመለወጥ ለሶሻሊስቱ ካምፕ
ገበያና ግንኙነት ይበልጥ መጠናከር አስተዋ
ጽኦዋችን ከፍ ማለት አለበት። የአብዮታ
ችን ዓላማ በኢኮኖሚ ነጻነት ፣ በፍትሕና
በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ዓለምአቀፋ
ዊ ስርዓትን ማስፈን በመሆኑ የትግላችን
አቀጣጫ ይኸው ነው ፤ [16]

በማለት ማስገንዘባቸው የሚታወስ ነው ።

በዚህ ዓይነት መንገድ ከሶሻሊስት አገሮ
ችና ዓላማችንን ከሚደግፉ ሌሎች አገሮች
ጋር ያለው የውጭ ኤኮኖሚ ግንኙነት ከቀ
ጠለ የብሔራዊ ኤኮኖሚ ዕድገታችንም
ከመፋጠኑም በላይ ከኢምፔሪያሊዝም የሚ
ደርስብንን ተፅዕኖ ሁሉ ለመቋቋም ወደ
ፊት ጥንካሬና ብቃት ሊኖረን ይችላል ።

ከአብዮታችን መሠረታዊ ዓላማ አንዱ
የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጐት ማር
ካት በመሆኑ ይህንን ዓላማ እግቡ ለማድረስ
የሚዘጋጀውን የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ
ወደ ተግባር በሚገባ መተርጐም አስፈላጊ
ይሆናል ። ዳሩ ግን በዚህ ጥረታችን አኳያ
በዓለም ላይ ያለው የኤኮኖሚ ቀውስ ከፍ
ተኛ ተፅዕና ሊያደርስብን እንደሚችል መገ
መት አያዳግትም ። ጓድ ሊቀ መንበር መን
ግሥቱ በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለ
ተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባቀረቡት ሪፖ
ርት ይህንኑ ሁኔታ በማስመልከት ፣—

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ይበልጥ
እሳሳቢ እየሆነ የመጣው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ
ከዓለም ገበያ ጋር ባለው ግንኙነት ሳቢያ ከጊ
ዜ ወደ ጊዜ በውጭ ንግዳችንና በገቢ ንግዳ
ችን ላይ የሚደርሰው ቀውስ ነው ። ከሌ
ሎች ታዳጊ አገሮች ጋር ሲነጻጸርም ሆነየሠ
ርቶ አደሩን የማቴሪያልና ማኅበራዊ ሕይ
ወት ለማሻሻል ካለን ዕቀድ አንጻር የመዋ

Digitized by Google

ዕለ ንዋይ ፍላጐታችን እጅግ ከፍተኛ በመ
ሆኑ ከአጠቃላይ የምርት ውጤት ለምርት
ኃይሎች ተከታታይ ዕድገት የምናውለው
መዋዕለ ነዋይ መጠን ድርሻ በጣም አነስተኛ
መሆኑ የሚያዝናና አይደለም ። [17]

ሲሉ መናገራቸው የሚታወስ ነው ።

ስለዚህ አገራችንን ያለፈው ሥርዓት ካወ
ረሳት ኋላቀርነት ለማውጣት ፣ ማኅበራዊ
አመራረትን በአዲስ መልክ ለማደራጀትና
የምርት ኃይሎችን ለማዳበር ከፍተኛ ትግ
ልና ጥረት በየመስኩ ይጠበቅብናል ። ለዚ
ሁም ደግሞ የሠርቶ አደሩን ምርታማነት
በማሳደግ የአገር ውስጥ ቁጠባን ማበረ
ታት ከዚያም አልፎ የውጭ ኤኮኖሚ ግንኙ
ነታችንን በትክክለኛው ፈር ላይ መተለ
ምና ለተግባራዊነቱም አስፈላጊውን እርም
ጃዎች ሁሉ መውሰድ ይኖርብናል ።

የዚህ ዓይነቱ ትክክለኛ የውጭ ኤኮኖሚ
ግንኙነት ፖሊሲ በቅድሚያ ከሶሺያሊስት
አገሮች ጋር ያለውንና ወደፊት ሊኖር የሚ
ችለውን የትብብር መስክ በማስፋፋትና
በማዳበር ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል።
በዚህ በኩል የተወሰዱት እርምጃዎችና የተ
ገኙትም ተግባራዊ ውጤቶች ቀላል ግምት
የሚሰጣቸው ባይሆኑም የጥረቱ የበለጠ
መጠናከርና ሥር መስደድ የአብዮታችንና
የብሔራዊ ነፃነታችን ደኅንነትና ሕልውና
ማስከበሪያ መንገድ መሆኑን በሚገባ መገን
ዘብ ያስፈልጋል ። በሌላ በኩል ደግሞ ዓላ
ማችንን ከሚደግፉና ለትብብር ዝግጁነታ
ቸውን ከሚያሳዩ ታዳጊ አገሮች ጋር ሁሉ
በተለያዩ መስኮች በተለይም በንግድና በጋራ
ትብብር የሚሠሩ ፕሮጀክቶች በማስፋፋት
ላይ ያተኮሩ የኤኮኖሚ ግንኙነቶችን ማስፋ
ፋት በጣም አስፈላጊ ይሆናል ። ዛሬ አያሌ
ታዳጊ አገሮች ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊ
ዝም የሚያደርስባቸው ብዝበዛና ዘረፋ
አስከፊነት የተነሣ የዓላማ አንድነት እየፈ
ጠሩ መምጣታቸው በግልጽ የሚታይ ሆኖ
አል ።

ይህ የዓላማ አንድነት ከካፒታሊስቱ ስር
ዓት የሥራ ክፍፍልና የገበያ ተፅዕኖ ለመላ
ቀቅ በሚያደርጉት ጥረት በመካከላቸው
ሊኖር የሚችለውን የኤኮኖሚ ግንኙነት
መስኮች እያሰፋ በመምጣቱ ሳቢያ የሚከ
ሰት ሆኗል ። ስለዚህ በዚህ በኩል የተፈጠ
ረውን አመቺ ሁኔታ በሚገባ መጠቀም
መቻል ለኢምፔሪያሊዝም መገርሰስ አስ
ተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ በእኩልነትና
በጋራ ጥቅም ላይ ለተመሠረተ ዓለም
አቀፋዊ የኤኮኖሚ ግንኙነት መስፈን አዲስ
መሠረት እንደሚሆን ይታመናል ።

በመጨረሻም ዛሬ ካለው የዓለም አቀፍ
ሁኔታ ስንነሣ ታዳጊ አገሮች ከካፒታሊስቱ
ዓለም ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን አግልለው
መኖር እንደማይችሉ የታወቀ ነው ። ከዓ
ለም ኤኮኖሚ ውስብስብ ጠባይ የተነሣ በአ
ያሌ መስኮች ከዚሁ ሥርዓት ጋር መተሳሰ
ራቸው አልቀረም ። ሆኖም በዚህ ግንኙነ
ትና መተሳሰር ሳቢያ የሚደርስባቸውን ችግ
ርና ተፅዕኖ ለመቋቋምና ለመከላከል ደግሞ
የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።
ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጭ ኤኮኖሚ
ግንኙነቶችን መሻሻልና በጋራ ጥቅም ላይ
መመሥረት አስፈላጊነት በማስመልከት
የሚካሔዱት ክርክሮችና ውይይቶች ሁሉ
የዚሁ ትግል ነፀብራቅ መሆናቸው አያጠ
ያይቅም ።

ስለዚህ በዚህ በኩል ያለውን ሁኔታ ለማ
ሻሻል በቅድሚያ የሶሻሊስት አገሮች በዓ
ለም ላይ ሰላም እንዲሰፍንና የሕዝቦች ሁሉ
መብትና ጥቅም በእኩልነት ታይቶ እንዲከ
በርና የጋራ ትብብር እንዲሰፍን በየወቅቱ
የሚያቀርቧቸው ሐሳቦችና ተጨባጭ መፍ
ትሔዎች በመላው ዓለም በተለይም በካ
ፒታሊስት አገሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዲ
ኖራቸው ያስፈልጋል ።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍ
ንና በእኩልነት ፣ በጋራ ጥቅምና በዲሞክራ
ሲያዊ ይዘት የተመሠረተ የውጭ ኤኮኖሚ
ግንኙነት እንዲስፋፋ አጥብቃ ትደግፋ
ለች ። ይህን በሚመለከት ጓድ ሊቀ መንበር
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በኢሠፓአኮ

Digitized by Google

አንደኛ ጉባኤ ላይ ባቀረቡት ሪፖርት ውስጥ «ለሕዝቦች ብልጽግናና ዕድገት ባለን ጽኑ አቋም መሠረት በዚች አገር የኢኮኖሚ ፍትሕ ለማስፈን ጥረት እያደረገን በአገሮች መካከል ብዝበዛ የሌለበትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ አዲስ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲሰፍን ጥረት ከማድረግ ወደኋላ አንልም»[18] በማለት ይህንኑ አቋማችንን በሚገባ አረጋግጠዋል ።

ታላቁ አብዮታችን በፈጠረልን ሁኔታዎች ሁሉ በመጠቀም የወደፊቱን የውጭ ግንኙነት አቅጣጫንና ትኩረታችንን በትክከለኛው ፈር ላይ ለመቀየስና ለማዳበር እስከዛሬ ድረስ ጥረት ማድረጋችን የሚታወቅ ነው ። ይህ ጥረታችን ይበልጥ ወደፊት እየጐላና ተግባራዊነቱ እየዳበረ የሚመጣው ከአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄ ከሆነው ከሠርቶ አደሩ ፓርቲ መመሥረት ጋር ለመሆኑ ጥርጥር አይኖርም ። ስለሆነም ለአቀድናቸው ሁሉ ውጥኖች ተግባራዊነትና ወደ ሶሻሊዝም ለምናደርገው ጉዞአችን አስተማማኝነት ከሁሉም አስቀድሞ በማሌ መሠረተ ሐሳቦች ላይ ለተመሠረተ የሠርቶ አደር ፓርቲያችን እውን መሆን አስፈላጊውን ሁሉ መሥዋዕትነት መክፈል የወቅቱ ታላቅ አብዮታዊ ጥሪ ይሆናል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. G.S. Maria: World Economy, (Bucharest: 1979), p. 7-10.
2. N. Suta; *World Trade and Policy*, (Bucharest: 1979), p. 25.
3. Money in the System of World Economic Relations, (Moscow: 1979), n. p.
4. «ሠርቶ አደር» ቅጽ 3 ቁ.83 ሚያዝያ 21፣1974
5. ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠ/መምሪያ የአስር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ ፣ የውጭ ንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ ግምገማ ፣ መስከረም 1975
6. ከላ ይከተጠቀሰው የተወሰደ ገጽ 18-22
7. National Bank of Ethiopia: *Quarterly Bulletin*, Vol. 7, No. 4. Dec., 1981.
8. ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠ/መምሪያ የ10 ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ፣የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚ ግምገማ፣መስከረም 1975
9. «አዲስ ዘመን» መስከረም 3/1975
10. ብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠ/መምሪያ የ10 ዓመት ጠቃሚ ዕቅድ ፣የፋይናንስ ክፍለ ኢኮኖሚ ግምገማ መስከረም 1975 ።
11. ከላይ ከተጠቀሰው የተወሰደ
12. ከከፍተኛ የትምህርት ኮሚሽን የተገኘ
13. የኢሠፓአኮ ፪ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 ፣ አዲስ አበባ ፣ ገጽ 32
14. New Times, The Pitfalls of "Equal Partnership", No. 29, July 1980.
15. የጉምሩክና ኤክሳይዝ አስተዳደር ዓመታዊ የውጭ ንግድ እስታቲስቲክስ፣ 1972 እና 1980
16. ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ ላይ ካቀረቡት ሪፖርት የተወሰደ ፣ አ.አ. ፣ ሰኔ 1972
17. «ሠርቶ አደር» ቅጽ 2 ፣ ቁ. 21 ፣ የካቲት 3/1974
18. ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በኢሠፓአኮ 1ኛ ጉባኤ ላይ ካቀረቡት ሪፖርት የተወሰደ ፣ አ.አ. ሰኔ 1972

Digitized by Google

ማኅበራዊ ችግሮችና መፍትሂያቸው በአብዮቱ ሂደት

— ንጉሤ ተፈራ

— አለማየሁ ፀጋዬ

አንድ ኅብረተሰብ ለአባላቱ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እስካላመረተ ድረስ ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ይሆንበታል። የማምረት ተግባር በአንድ በኩል ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርጉትን ትግል ፣ በሌላም በኩል በአንድ ላይ በሚሠሩበት ወቅት በመካከላቸው የሚፈጠሩትን ግንኙነት ያመለክታል ። በምርት ሂደት ውስጥ ሰዎች ቁሳዊ ምርቶችን ብቻ ሳይሆን ፣ የሚፈጠሩት የራሳቸውን ማኅበራዊ ግንኙነቶችም ነው ። ለሰዎች ሕይወት ዋንኛ የሆኑት ግንኙነቶች ከምርትና ከምርት ክፍፍል ጋር የተያያዙት ቁሳዊ ግንኙነቶች ማለትም ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ናቸው ። እነዚህም የምርት ግንኙነቶች ይባላሉ ።

የምርት ግንኙነቶች በምርት መገልገያዎች የባለቤትነት ይዞታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። የባለቤትነት ይዞታ በኅብረተሰብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ማኅበራዊ ክፍሎች በምርት ሂደት ውስጥ ባላቸው ቦታ ይወሰናሉ ። የምርት መገልገያዎች በጋራ ማለትም በሕዝብ ቁጥጥር ሥር ባሉበት ሁኔታ የምርት ግንኙነቱ ከብዝበዛ ነፃ የሆነ በሰዎች መካከል ያለ የትብብርና የመረዳዳት መልክ ይይዛል ። ይህ ዓይነቱ የምርት ግንኙነት የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ዓይነተኛ ባሕርይ ነው ። የምርት መገልገያዎች በግል በተያዙባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ግንኙነቱ በብዝበዛና በጭቆና ላይ የተመሠረተ ነው ፤

የግል ሀብት በሰፈነበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚመረተው ምርት በቀጥታ ለኅብረተሰቡ አባላት ጥቅም ሳይሆን ለገበያ ለሽያጭ ነው ። ካፒታሊስቶች ምርቱን ገበያ ላይ አውጥተው ባገኙት ትርፍ የራሳቸውን ሀብት ከማካበት በስተቀር ለሕዝብ ፍላጎት መሟላት ወይም ለማኅበራዊ አገልግሎት መስፋፋት ደንታ የላቸውም ። የሳ

Digitized by Google

ይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ለምርት ውጤት ከፍተኛነት ዋንኛው ክንዋኔ ቢሆንም ፣ የካፒታሊስት ኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ዕድገቱ በአንድ መልኩ ለቡርዧው ሀብት መከማቸት ምክንያት ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ሠርቶ አደሩን ለችግርና ለኑሮ ዋስትና ማጣት ይዳርገዋል ።

ካፒታሊስቶች በአዳዲስ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች በመጠቀም በቀላሉ ምርት ለማግኘትና ገበያ ላይ ለማውጣት ከቻሉ ሠራተኞችን በመሣሪያዎች በመተካት ከየሥራ ቦታቸው ያባርሯቸዋል ። ሥራ ማጣት ወዝአደሩን ችግር ላይ ይጥለዋል ፤ በድህነት አዘቅት ውስጥ ይዘፍቀዋል ። በዚህም የተነሣ ሊሠራ የሚችለው ሰው በሁኔታዎች ተገዶ የተለያዩ ወንጀሎችን እየፈጸመ ኑሮውን እንዲገፋ ይገደዳል ። ዝሙት አዳሪነት ፣ ልመና ወዘተ . . . የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ገጽታ ሲሆኑ ፣ ይህም በአሁኑ ጊዜ በካፒታሊስት ሀገሮች በግለሰቦች እንጂ በሥርዓተ ማኅበሩ ውስጣዊ ይዘት የሚፈጠሩ አይደሉም ብለው ስለሚያምኑ የሚወስዱቸው እርምጃዎች ሠራተኛውን ሕዝብ ከማጉዳትና ይበልጥ ችግር ላይ ከመጣል በስተቀር ለሠራተኛው ሕዝብ የሚያስገኘው የዘለቄታ መፍትሔ የለም ። ይህ የሚያስገነዝበን የምርት መገልገያዎች በግል ባለቤትነት በተያዙበትና የምርት ግንኙነቱም በብዝበዛና በጭቆና ላይ በተመሠረተበት ሥርዓተ ማኅበር የኅብረተሰቡ ዕድገት በተገቢው ሁኔታ እንዲዳብር የሚያስችል አመቺ ሁኔታ አለመፈጠሩን ነው ።

በአገራችን የነበረው ከፊል ፊውዳልና ከፊል ከበርቴ ሥርዓትም የምርት ኃይሎችን ዕድገት አፍኖ በመያዙ ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚገኘው አጠቃላይ የምርት ውጤት መጠን ዝቅተኛ ነበር ። ሀገሪቱ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራትም በሚገባ የለማና በጥቅም ላይ የዋለ ባለመሆኑ አብዛኛው ሕዝብ በድኅነትና በበሽታ ይማቅቅ ነበረ።

ከዚህ በተጨማሪም ከኢኮኖሚው የሚገኘው መጠነኛ ውጤትም የምርት ኃይሎችን በማልማትና በማዳበር ፋንታ የምርት ውጤት ባለቤቶች ለነበሩት ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎች የቅንጦት ኑሮ መኖሪያ በመሆን ሲከፋፈልና እንዲሁም ፍሬ በማያስገኙ የሥራ መስኮች ላይ ሲባክን ቆይቷል ። በማኅበራዊ አገልግሎቶች ዕድገት ረገድ ይሰጡ የነበሩት አገልግሎቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኙ የነበረ ከመሆኑም በላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ ጉልቶ የሚታዩ የማኅበራዊ ችግሮች እንደዝሙት አዳሪነት፣ ቦዘኔነት ፣ የወጣት አጥፊነት ፣ ልመና ፣አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናትና ጧሪ ያጡ አረጋውያን እንዲሁም የአካለ ሥንኩላን ችግሮች ሥር ሰደውና ተባብሰው ይገኛሉ ።

እነዚህ የሥርዓቱ ውጤት የሆኑ የማኅበራዊ ችግሮች ጉልተው የሚታዩት በከተሞችና በከተሞች አካባቢ ሲሆን ለዚህ ዋናው ምክንያት በሥራ ዕድልና አገልግሎቶች (የጤና ትምህርት ወዘተ) መስፋፋት ረገድ በከተማና በገጠር መካከል የተዛባ ዕድገትና ሥርጭት በመኖሩ ፣ ሥራና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ ይጐርፍ የነበረው የሕዝብ ቁጥር ቀላል አልነበረም። ከገጠር ወደ ከተማ ይፈልሱ ከነበሩት ሰዎች መካከል የተሻለ የአካልና የዕድሜ ሁኔታ የነበራቸው አመች የኑሮ ሁኔታ ሳያገኙ ሲቀሩ ሴቶች በዝሙት አዳሪነት ፣ ወንዶቹ ደግሞ በቦዘኔነት ፣ በልዩ ልዩ የወንጀል ተግባርና በመሳሰሉት የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲሠማሩ፣የተሟላ ጤና የሌላቸውና አቅመ ደካሞች ደግሞ በልመና ሥራ ኑሮአቸውን እንዲገፉ ሁኔታው አስገድዶአቸዋል ።

ማኅበራዊ ችግሮች

ዛሬ አብዮታዊት ኢትዮጵያን ከገጠሟት ማኅበራዊ ችግሮች አንዱ ቦዘኔነት ነው ። ባሁኑ ጊዜ የኅብረተሰቡ ሸክምና ጠንቅ የሆነው የቦዘኔው ሁኔታ አሳሳቢና በተባባሰ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ። በ1971 በሠራት

Digitized by Google

ኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለ ቦዘኔው የኅብረተሰብ ክፍል እንዲያጠና የተቋቋመው ኰሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ለቦዘኔው ክፍል አጠቃላይ ትርጉም ሲሰጥ «— በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ቦዘኔ ሲባል ከፍተኛ የሰው ኃይል አቅር ምርትንና አገልግሎትን ሊያ ሳድጉና ሊያሻሽሉ በሚችሉ ሥራዎች ላይ ሰማሩ የኅብረተሰቡን የምርት ውጤቶች በመሻማት የዕድገት እንቅፋት ሆኖ እየተን ገዋለለና እያወናበደ የሚኖር የኅብረተሰቡ ክፍል ነው» ብሎታል ። [1] ስለዚህ ቦዘኔ ሲባል አብዛኛውን ጊዜ ጉልተው የሚታ ዩት በልመና ፣ በድለላና በልዩ ልዩ ወንጀል ተግባር ተሰማርተው የሚገኙትን ሰዎች ብዙ ቢሆንም ፣ ዝሙት አዳሪዎችም በቅርጽ ካልሆነ በስተቀር በይዘት የዚሁ ኅብረተሰብ ክፍል አባላት መሆናቸው የታወቀ ነው ።

የቦዘኔነት ትርጉም ከዚህ በላይ የተሰጠው ሲሆን ፣ ከሥራ አጥነት ተለይቶ መታየት ይኖርበታል ። ሥራ አጥ ማለት ዕድሜው ለሥራ ብቁ የሆነ ሥራ ለመሥራት ፍላጉት ያለው ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ወቅት ውስጥ በሥራ መሰማራት ያልቻለ የሰው ኃይል ነው ። ይህም ሥራ አጥ ሥራ ለመሥ ራት በሚያስችል የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለምንም የመተዳደሪያ ገቢ የሌለው፣በጥገ ኝነት ወይም በሌሎች እርዳታ የሚኖር፣ሥራ በመፈለግ ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ነው ። ሥራ ፈላጊ ለረዥም ጊዜ ሥራ ካላገኘ ወደ ቦዘኔነት ሊንሸራተት ወይም በወንጀል ተግ ባር ሊሰማራ እንደሚችል ይገመታል ።

ከፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ወደ ቡርዧው ሥርዓተ ማኅበር ሽግግር በተደረገበት ወቅት የገጠሩ ጭቆና ያስመረራቸውና የከተማው ብልጭልጭ ኑሮ የሳባቸው ፣ እንዲሁም ትም ሀርታቸውን በልዩ ልዩ ምክንያት ያቋረጡና በሥራ ላይ ያልተሰማሩ ሰዎች በትላልቅ ከተሞች እንዲከማቹ ተገድደዋል ። ይህን በመሰለ ሁኔታ በየከተሞች የተከማቹት የ ሥራ ዕድል ጠባብ በመሆኑና ለሥራ የሚ ያበቃም ሙያ ስለሌላቸው አብዛኛዎቹ ሴቶች በዝሙት አዳሪነት ተግባር ሲሰማሩ ወንዶች ደግሞ የኅብረተሰቡን መልካም አኗኗር በሚያደናቅፉ እንደ ስርቆት ፣ ኪስ አውላቂነት ፣ አጭበርባሪነት ፣ ድለላ ፣ ል መና በመሳሰሉት ተግባራት ተሰማርተዋል።

ቦዘኔዎችን በሚመለከት ለጊዜው አስተ ማማኝ ጥናት ባይኖርም በ1972 ከአዲስ አበባ ፖሊስ ጽ/ቤት መዛግብት በተገኘው መረጃ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ 27,600 ቦዘኔዎች እንደነበሩ ተገልጧል። [2] እን ዲሁም በ1974 ከአብዮታዊት ፖሊስ ጠቅ ላይ መምሪያ የተገኘው መረጃ እንደሚገል ጸው በአዲስ አበባ ከተማ 21,757 ፣ በሌሎች ክፍላተ ሀገር (ከሲዳሞ ፣ ከወሎ ፣ ከሸዋና ከወለጋ በስተቀር) 22,914 ፣ በድምሩ 44,671 ቦዘኔዎች እንደሚገኙ ይገመታል ። ቦዘ ኔዎችን ከሥራ አጡ ወይም ፈላጊው በትክ ክል ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ በመሆኑ ይህ አኃዝ አንዳንድ ሥራ አጦችንና በልዩ ልዩ ወንጀል ምክንያት የተመዘገቡትንም ሊጨ ምር እንደሚችል ተጠቁሟል ። በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ከቦዘኔው ክፍል አንዱና ትልቁ በዝሙት አዳሪነት የተሰማሩት ሴቶች ናቸው ።

<u>ዝሙት አዳሪነት</u> ፦ የተጀመረበት ቦታና ጊዜ በትክክል ተለይቶ ባይታወቅም ፣ ይህ ጠንቅ በአንድ ጊዜ የተጀመረ ክስተት ሳይ ሆን ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ ከከተሞች መስ ፋፋት ጋር ደረጃውን ጠብቆ የመጣና የራሱ የሆነ ረጅም ታሪክ ያለው ነው ። በኢትዮ ጵያ ስለዝሙት አዳሪነት አመጣጥ እስካሁን የተደረጉት ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚያመ ለክቱት ችግሩ ረጅም ጊዜ የቆየ ሲሆን፣ በተ ለይ ከፋሺስት ኢጣሊያን ወረራ ወዲህ በዓ ይነትና በመጠን እየተስፋፋና እየጨመረ በመሄድ አሁን ከሚገኝበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ።

ዝሙት አዳሪነት ሲባል አንዲት ሴት በገ ንዘብ ወይም በዓይነት ለሚሰጣት ዋጋ ከብዙ ሰዎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድ ረግ የምትፈጽመው ተግባር ነው ። በሠራ

Digitized by Google

ተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በ22 ከተሞች በተካሄደው የዝሙት አዳሪዎች የቆጠራ ጥናት እንደተተረጐመው ዝሙት አዳሪ ማለት ለጥቅም ወይም ለገንዘብ ስትል በዝሙት አዳሪነት ተግባር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሰማርታ የምትገኝ ወይም የምትተዳደር ማለት ሲሆን ፣ ተጠቃሚ ለኑሮ የሚያስፈልጋትን ገቢ ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛውን የምታገኘው የዝሙት ተግባር በመፈጸም የሆነ እንደሆነ ነው ። [3]

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ በዝሙት ተግባር ተሰማርተው የሚገኙት አንደኛ ፣ የዝሙትን ተግባር ብቸኛ የገቢያቸው ምንጭና ይህንኑ ተግባር በይፋ የሚያካሄዱ ፣ ሁለተኛ እስከዚህም ይፋ ባልሆነ ወይም «በኅቡዕ የዝሙት ተግባር ተሰማርተው ይህንን ተግባር የሚያከናውኑ አንዳንድ ሴት ሠራተኞች ፣ ተማሪዎች ፣ ባለትዳሮችና ሥራ ፈላጊዎች» ናቸው ። በሠራተኛው ክፍል የተጠቀሱት ዝሙተኞች ሌላ የኑሮ መደጐሚያና መተዳደሪያ ያላቸው ስለሆነ እነሱም ቢሆኑ ይህ ፀያፍ ተግባራቸው በይፋ እንዲታወቅባቸው የማይፈልጉ በመሆናቸው ገና ለይቶላቸው ወደ ቦዘኔው የኅብረተሰቡ ክፍል ጭልጥ ብለው ያልገቡ ናቸው ። በዚህ ጽሁፍም የምናቀርበው በአንደኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሱትን የዝሙት አዳሪዎች ነው ።

በዝሙት አዳሪነት የተጠመዱት ሴቶች ለመኖር ሲሉ ሰውነታቸውን እንደ ሸቀጥ ሸጠው የሚተዳደሩበት አስከፊ ተግባር ነው ። ዝሙት አዳሪዎች ለልዩ ልዩ በሽታዎች የተጋለጡ ከመሆናቸውም በላይ በተለይ ለአባለዘር በሽታ መራባትና መተላለፍ ዓይነተኛ ምክንያት ናቸው ።

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከአባለዘር በሽታ መከላከያ ክሊኒክ በተገኘው መረጃ መሠረት በ1974 በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ማለትም ከታህሣሥ እስከ ግንቦት ወር ድረስ ተመላላሽ 17,740 ፣ አዲስ 12,523 በድምሩ 30,269 ሴቶች በልዩ ልዩ አባለዘር በሽታ መመዝገባቸው ሲታወቅ ፣ ከነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ በዝሙት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሴቶች መሆናቸው ታውቋል ። [4] በተጨማሪ የሠራተኛና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በ1971 እና በ1972 በ70 ከተሞች ባካሄደው የሥራ አጥ ምዝገባ 127,421 ሥራ ፈላጊ ሴቶች የተመዘገቡ ሲሆን ከነዚሁ መካከል ያላገቡ ፣ የተፋቱ ፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸውና የጋብቻ ሁኔታቸውን ያልገለጹ 71,131 ናቸው ። [5] እነዚህ ሴቶች የሥራ ዕድል ካላገኙ አንዳንዶቹ በቀላሉ ገቢ ወደሚያገኙበት ወደ ዝሙት ተግባር ሊሰማሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል ።

በ1969 በ6 ከተሞች የዝሙት አዳሪነት የቆጠራ ጥናት ተካሂዶ 24,283 ዝሙት አዳሪዎች ተመዝግበዋል ። በ1973 በ22 ከተሞች በተካሄደው የዝሙት አዳሪዎች የቆጠራ ጥናት ለቆጠራው በተሰጠው መሥፍርት መሠረት 37,115 ዝሙት አዳሪዎች ሲመዘገቡ ፣ ከነዚህ ውስጥ 42.8% በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ናቸው ።

በአሁኑ ጊዜ በተለይም በአዲስ አበባ ጉልቶ ለሚታየው የዝሙት መስፋፋት መባባስ ብዙ ምክንያቶች አሉ።ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። [6]

1ኛ/ ይፋ ያልሆነ (የኅቡዕ) ዝሙት አዳሪነት መስፋፋት ፡-

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሀገራችን ባህል ለአንድ ሴት በዝሙት መሰማራት እሷን ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቿና ለወገኖቿ ሁሉ እንደ አሳፋሪ ድርጊት ተደርጐ ይወሰድ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ባህል በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ዋጋ እያጣ ነው ። በመሆኑም ቤተሰቦቻቸው አውቀውም ሆነ ሳያውቁ በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ አንዳንድ ሴት ወጣቶች ፣ ቋሚ ሥራ ያላቸው አንዳንድ ሴት ሠራተኞች ለቁሳዊ ጥቅም በመጓጓት በዝሙት ተግባር ተሰማርተው ይታያሉ ።

2ኛ/ የአገር ጐብኚዎች (ቱሪስቶች) መረን መለቀቅ ፣

በመሠረቱ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የቱሪ

Digitized by Google

ዝም ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ፣ እንዲያድግ
ትፈልጋለች ። በዚያው አንፃር ግን በቱሪ
ዝም ስም ፀረ-አብዮት ተግባርና መጥፎ ባህ
ልን የሚያስፋፉ ድርጊቶችን መዋጋት አለ
ባት ። ታዲያ በአሁኑ ጊዜ ከአካባቢያችን
የዓረብ አገሮች በቱሪዝም ስም የሚመጡ
አብዛኛዎቹ አረቦች በባሕላቸው ገና ዝቅ
ተኛ ከመሆናቸው የተነሳ ወደ አገራችን የሚ
መጡት ታሪካዊ ቦታዎችን ለማየት ሳይሆን
ለዝሙት ተግባርና ለጫት መቃም ሆኗል ።
እነኝህ ሰዎች በቀን ሥራና በመሳሰሉት ሥራ
ዎች ዘይት አምራች ከሆኑት አገሮች የሚያ
ገኙትን ገንዘብ በሀገራችን ለዝሙት ተግባር
በማዋል በአሁኑ ጊዜ ለሚታየው ለዚህ ጠ
ያፍ ተግባር መስፋፋት አስተዋጽኦ አድር
ገዋል ።

3ኛ/ « ባለአረንጓዴ መቀነት » የታክሲ
ነጂዎች ፣ የአስጐብኝዎችና የዝግ ችሎት
ባለንብረቶች ትብብር ፣

በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ወደ 60 የሚ
ጠጋ «ባለ አረንጓዴ መቀነት» ታክሲ ነጅ
ዎች እንዳሉ ይገመታል ። ከነዚህ መካከል
አብዛኞቹ ከአንዳንድ አረቦችና በሀገራችን
ካሉ ዝሙተኞች ጋር በመተባበር ፣ ሀ/
አረቦችን ወደ ታላላቅ የመንግሥት ሆቴ
ሎች ሳይሆን ዝሙቶችና ጫት ወደሚገ
ኝበት ቦታ በመምራት ፣ ለ/ በዝሙት ተግ
ባር የተሰማሩ ሴቶችን ከአረቦች ጋር በማ
ገናኘትና በሌላም ምክንያት ከአረቦቹ የሚ
ገኘውን የውጭ ምንዛሪ ከተቀበሉ በኋላ
በጥቁር ገበያ ውስጥ በመሸጥና የመሳሰሉ
ትን ለአዲስ ባህል ግንባታ ጠንቅ የሆኑ
ድርጊቶችን በመፈጸም በሀገራችን የዝ
ሙት ተግባርን በማስፋፋት ላይ ይገ
ኛሉ ። እራሳቸውን (ጋይድ) አስጐብኝ ብ
ለው የሰየሙ ግለሰቦች የውጭ አገር ወንዶ
ችን በዝሙት ሥራ ከተሰማሩ ኢትዮጵያው
ያን ሴቶች ጋር በማገናኘት ፣ ከአገናኟቸው
ወንዶችም ሆነ ሴቶች ገንዘብ በመቀበል
ይህን ፀያፍ ተግባር በማስፋፋት ላይ ናቸው።
ከዚህም በተጨማሪ «ዝግ ችሎት» በመባል
የሚታወቁ ፈቃድ የለሽ ነጋዴዎች ከሌላው
ህገወጥ ንግዳቸው ጐን የዝሙትን ተግባር
እያስፋፉ ነው ። እነኝህ ባለዝግ ችሎቶች
በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ እንደአሸን
በመፍላት ላይ ሲሆኑ ፣ አይሮፕላን ጣቢያ
ድረስ በመሄድና ቱሪስቶችን በመቀበል ፣
ከቤታቸው በማስተናገድ ፣ የዝሙት ሥራ
ማስፋፋትን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል።

4ኛ/ ዲፕሎማቶችና የዓለምአቀፍ ድርጅ
ቶች ሠራተኞች ፣

በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ አን
ዳንድ ዲፕሎማቶችና የዓለምአቀፍ ድርጅ
ቶች ሠራተኞች ህገ ወጥና ሀየገራችንን ዕድ
ገት የሚያደናቅፉ ተግባራት የሚያከናውኑ
አሉ ። እነኝህ ግለሰቦች ተቀብሉ የሚያስተ
ናግዳቸውን አገር ደንብና ሥነ ሥርዓት ማክ
በር ሲገባቸው ፣ ከአገሬው ሰው ጋር ሲነፃ
ፀር በሚያገኙት ደሞዝና ሊያጠፉ በሚች
ሉት ገንዘብ ከፍተኛነት ፣ እንዲሁም በተጠ
ናወታቸው የላሸቀ የካፒታሊስት ባህል ምክ
ንያት የዝሙት ተግባርን በማስፋፋቱ ረገድ
የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

ልመናን በሚመለከት ፣ ይህ ችግር በሀገ
ራችን ለረዥም ጊዜ የቆየ ሲሆን ፣ በልመና
ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በዕድሜያ
ቸው ፣ በአካላቸው ፣ በፆታቸውና በገቢያ
ቸው የተለያዩ ናቸው ። በልመናና ከልመና
ጋር በተያያዙ ተግባራት ላይ ለተሰማሩት
ቦዘኔዎች መፍትሔ እንዲፈለግ በሠራተኛና
ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋቋመው
የቴክኒክ ኰሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ላይ
«... ልመና ማለት በወዛቸው ፍሬ ሳይሆን
የዕድሜአቸውን ፣ የአካላቸውን የጤናና የኤ
ኰኖሚ ሁኔታዎችን ምክንያት በማድረግ
ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል በወዙ ያመረተ
ውን ለመካፈል የሚጠቀሙበት ዘዴ ሲሆን
በዚሁ ተግባር ላይ የተሰማሩት ሰዎች ለመ
ልካም ኅብረተሰብ የፖለቲካ ፣ የኤኰኖሚና
የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት እንቅፋት የሚሆኑ፣
ናቸው ፤ » ብሎ ተርጉሞታል ።

በተሰጠው ትርጉም ውስጥ እንደተገለ
ጸው በልመና ተግባር የተሰማሩት ሰዎች
በተለያየ ሁኔታ ላይ ያሉ በመሆኑ ፣ በጥናቱ
ውስጥ ትኩረት የተሰጠው አካለ ሙሉ ሆ

Digitized by Google

ነው ሠርተው መተዳደር እየቻሉ በልመና ተግባር ላይ የተሠማሩትን ብቻ ነው ። እነዚህም ግለሰቦች በቦዘኔው ኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ይጠቃለላሉ ።

ልመናን ሽፋን በማድረግ በስርቆት፣ በንጥቂያ፣በኪስ አውላቂነትና በመሳሰሉት ወንጀሎች ላይ የተሰማሩ በርካታ ሥራ ጠል ቦዘኔዎች በዋና ዋና ከተሞች እንደሚገኙ ይታወቃል ። በዚህ ተግባር ላይ ስለተሰማሩት ሰዎች የተደረገ የመስክ ጥናት ባይኖርም ቁጥራቸው ከቦዘኔዎችና ከወንጀለኞች ተለይቶ የማይታይ በመሆኑ ብዛታቸውንና የተወሰዱትን እርምጃዎች ለብቻው ለይቶ ለማቅረብ አዳጋች ሆኖአል ። የወጣት ጥፋተኝነትንም ችግር በሚመለከት መንስኤው በይዘት እንጂ በቅርጹ ከሌሎቹ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች ተለይቶ የማይታይ ቢሆንም፣ ከአንዳንድ ጥናቶች ለማግኘት እንደተቻለው የችግሩ ገፈት ከሆኑት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ የተዛባ የቤተሰብ አቋም ፣ በከተማና በገጠሩ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ፣ የአካባቢ ሁኔታዎች ፣ የቤተሰብ ቁጥጥር መላላት ፣ የመዝናኛና የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ፕሮግራም አለመኖርና የመሳሰሉት ናቸው።

በሀገራችን በ1973 ከ10— 14 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በገጠር 3,324,900 ፣ በከተማ 577,300 በድምሩ 3,902,200 ናቸው ። በዚሁ ዓመት የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱት 276,069 ተማሪዎች መካከል ከ6ኛ ክፍል 18% ከ8ኛ ክፍል 28% ፈተናውን አለማለፋቸው ታውቋል ። ከ1970 እስከ 1973 ድረስ ባሉት አራት ዓመታት ከ6ኛና ከስምንተኛ ክፍል በጠቅላላው 225,500 በላይ የሆኑ ተማሪዎች የብሔራዊ ፈተና ወድቀዋል ። [7]

የወጣት ጥፋተኞች ልዩ ፍ/ቤት የሚገኘው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ በመሆኑ በሌሎች ክፍላተ ሀገር ከተሞች የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ የሚታየው በመደበኛው ፍ/ቤት ነው ። ስለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ስለወጣት ጥፋተኞች የተሰበሰበ መረጃ ለማግኘት ባይቻልም ከአብዮታዊ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሠረት በአዲስ አበባ ፣ በሐረርጌና በኤርትራ የሚከተሉት ወጣት ጥፋተኞች ተመዝግበዋል።

1965	የተመዘገቡ	ወጣት	ጥፋተኞች	496
1970	»	»	»	214
1971	»	»	»	164
1972	»	»	»	189
1973	»	»	»	180

ናቸው ። [8]

ማኅበራዊ አገልግሎትንም በሚመለከት ማለትም እንደ ትምህርት ፣ ጤና ፣ የሥራ ስምሪት ፣ የኑሮ ዋስትናና የመሳሰሉ የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና በጠቅላላው ለሰው ልጅ ደህንነትና መልካም ኑሮ የሚያስፈልጉት ማኅበራዊ አገልግሎቶች የነበራቸው ገጽታ እጅግ አስከፊ ነበር ።

ለምሳሌ የጤና አገልግሎትን ስንመለከት ከጠቅላላው ሕዝብ 85% የሚሆነው ዘመናዊ የጤና አገልግሎት አያገኝም ነበር ። ንጹህ ውሀ የሚያገኘው ሕዝብ ከጠቅላላው ሕዝብ 5% አይሆንም ነበር ። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ሲፈነዳ በአገሪቱ ውስጥ ይገኙ የነበሩት 650 ክሊኒኮች ፣ 93 የጤና ጣቢያዎች ፣ 8624 አልጋ ያሉዋቸው 84 ሆስፒታሎች ሲሆኑ በልዩ ልዩ ሙያ የተሰማሩ የጤና ባለሙያዎች ጠቅላላ ቁጥር ደግሞ ከ 6472 አይበልጥም ነበር ። [9]

ትምህርትን በሚመለከት ደግሞ በተለይም አጠቃላይ ትምህርት ፣ አብዮቱ በፈነዳበት 1966 ከጠቅላላው ሕዝብ 93% የሚሆነው ማንበብና መጻፍ የማይችል ማሀይም ነበር ። የነበረው አጠቃላይ የትምህርት ዓላማና ይዘት የፊውዶ ቡርዧውን ሥርዓት የሚያንጸባርቅ ይሆንንም ሥርዓት ለማገልገል የተቀየሰ ፣ ለምርምርና ለፈጠራ ሥራ የማያበቃ ፣ የሀገሪቷን ችግሮች ለመፍታት የሚችሉ ባለሙያዎችን የማያዘጋጅ ፣ ለተግባራዊ ትምህርት ዝቅተኛ ግምት የሚሰጥና ለሰፊው ሕዝብ ልጆች ያልተዳረሰ ነበር።

Digitized by Google

በ1966 ዕድሜአቸው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከደረሱት ወጣቶች መሀከል የትምህርት ዕድል የደረሰቸው 19 በመቶ ብቻ ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከደረሱት መሀከል ደግሞ የትምህርት እድል የደረሳቸው 6 በመቶ ብቻ ነበሩ ። [10]

በአጠቃላይ ቅድመ አብዮት የነበረው የትምህርት ሁኔታ ምንም ያህል ያልተስፋፋና መሰረቱንም ጠባብ ከመሆኑ በላይ የትምህርት አገልግሎት ስርጭት በከተማና በገጠር ፥ በክፍላተ ሀገር ፥ በአውራጃና በወረዳ እንዲሁም በጾታ አንጻር ሲታይ እጅግ የተዛባና ያልተመጣጠነ ነበር ።

አጠቃላይ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች፥ ማለትም ሥራ አጥነት ፥ ቤተኛ አዳሪነት ፥ ቦዘኔነትና የመሳሰሉትንም በሚመለከት የነበረው ሥርዓት በፈጠረው ማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ የተነሳ እጅግ ተባብሰውና ሥር ሰደው ነበር ። በተለይም ዋና ዋና ከተሞች በሥራ አጦች ፥ በቤተኛ አዳሪዎች በቦዘኔዎችና በልመና ሥራ በተሰማሩ ረዳት የለሽና አካለ ስንኩላን ተሞልተው ይታዩ ነበር ።

በአብዮቱ ሂደት የተወሰዱ እርምጃዎች

ከነበረው ጉልተኛ የመሬት ስሪት ፥ የኤኮኖሚ ኋላቀርነት ፥ የምርት ኃይሎች አለመዳበር ፥ በእርሻና በሌሎች የሥራ ዘርፎች በገጠርና በከተማ መካከል በነበረው ያልተመጣጠነ እድገትና የግል ባለንብረትነት ፥ በከተማ ተመጣጣኝ የሥራ ዕድል አለመገኘት በመሳሰሉት ምክንያቶች ከተባባሰ ደረጃ ላይ ደርሰው የነበሩት የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች ለአብዮቱም መንስኤ ተጨማሪ ምክንያቶች ነበሩ ።

የማኅበራዊ አገልግሎት ሲባል (እስከዛሬ በአገራችን እንደሚታየው የማኅበራዊ ችግር ሆነው ለሚታዩት ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎች በመንግሥትም ሆነ በግል የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ድርጅቶች በበጐ ፈቃድ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት በጠባቡ ሳይታይ) በጠቅላላው የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማዳበር ኅብረተሰቡ ራሱ በብሔራዊውም ሆነ በቀበሌ ደረጃ እንደሁኔታውኔና እንደአስፈላጊነቱ በሚገባ አደራጅቶ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት መዋል የሚገባውን ነው ።

ስለሆነም አብዮታዊው መንግሥት የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊአብዮት ፕሮግራም ግልጽ ዓላማ ከመተለሙም በላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተጠቀሱት ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ ቆራጥ ርምጃዎች ወስዷል። ከርምጃዎቹም ውስጥ የገጠር መሬትን ለሰፊው አርሶ አደር ያደረገው አዋጅ የፈውዳሉን የምርት ግንኙነት በጣጥሷል፤ በአብዛኛው ገበሬ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ የሚሻሻልበትን ፥ ተደራጅቶና በኅብረት እየሠራ ራሱንበራሱ የሚረዳበትን ጉዳና ቀይሶአል ። የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን የመንግሥት ያደረገው አዋጅም በከተማ የነበረውን ማለትም በከተማ ቦታና ቤት ላይ ይደረግ የነበረውን ብዝበዛ ከማስወገዱም በላይ በተደራጀ ኃይል ኅብረተሰቡ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮችን ለማስወገድ ሰፊ ሚና ሊጫወት የሚችልበትን አመቺ ሁኔታ ፈጥርአል ። ከፍተኛ የማምረቻ ድርጅቶችን የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን ሰፋፊ የግል እርሻዎችንና እንዲሁም የገንዘብና የኢንሹራንስ ድርጅቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ያደረገው አዋጅ የነበረውን የብዝበዛ ሥርዓት በአመዛኙ በማስወገድ፥ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ለዘለቄታው ድል አስተማማኝ በሆነ መንገድ እንዲደራጅ ፥ የሥራና የኑሮ ዋስትና እንዲያገኝና በአጠቃላይ ለሶሻሊዝም ግንባታ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲዘጋጁ አድርጉአል ። የተወሰዱት እርምጃዎች የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮችን በመፍታት አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የነበራቸው ከመሆኑም በላይ ለወደፊቱም የግንባታ ተግባር የመነሻ መሠረት ሆነዋል ።

ምንም እንኳን የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች ሥር የሰደዱና የተወሳሰቡ ሆነው ቢገኙም የእያንዳንዱን ጠንቅ ስፋትና ጥልቀት በማ

Digitized by Google

ጤንና በማገናዘብ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመቀየስ አብዮታዊ መንግሥት ችግሮችን ለመፍታት በየጊዜው ሳይጠቀሱ የማይታለፉ እርምጃዎችን ወስዷል ።

ሙሉ በሙሉ የተሟላ መረጃ ለጊዜው ባይኖረንም በልዩልዩ ከፍላተ ኢኮኖሚ በተከፈቱ የሥራ መስኩች እያሉ ቦዘኔዎችና ሥራ አጦች በሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል ። ለምሳሌ ያህል ከ1967 እስከ 1970 ባለው ጊዜ ውስጥ 5199 ቦዘኔዎች በሠፈራ እርሻ እንዲሰማሩ ተደርጓል ። የምርት ዘመቻውንም ተከትሎ በ1971 ከአዲስ አበባ ከተማ ከ5,000 በላይ የሆኑ ቦዘኔዎች ትምህርተ ተሃድሶ ተሰጥቶአቸው በሥራ እንዲሰማሩ ተደርጉአል ።

ሥራ አጥነትንም በሚመለከት ፣ በየምርት ዕድገት ዘመቻው ሂደት በመንግሥት እርሻዎች ብቻ በ1972 ለ21,915 ቋሚና ለ19,615 ጊዜያዊ ሠራተኞች፣በ1973 ለ22,702 ቋሚ ፣ ለ114,742 ጊዜያዊ ሠራተኞች እንዲሁም በ1974 ለ24,011 ቋሚና ለ107,160 ጊዜያዊ ሠራተኞች የተከፈተው የሥራ ዕድል ችግሩን ለመቅረፍ የተደረገውን ጥረት ከፍተኛነት ያመለክታል። [11]

የዝሙት አዳሪነትን ችግር ለመከላከልና ለማስወገድ የነበሩት ሕጐችና ደንቦች በአሁኑ ወቅት በሙሉ በተግባር ተተርጉመዋል ባይባልም ፣ በወጡት ተራማጅ አዋጆችና መመሪያዎች መሠረት ችግሩን ደረጃ በደረጃ ለመቋቋም አስፈላጊው ጥረት በመደረግ ላይ ነው ። ዝሙት አዳሪነትን ለመከላከልና ለማስወገድ በመጀመሪያ ደረጃ የችግሩን መንስኤ ፣ ጠባይ ፣ ስፋትና ጥልቀት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ቀደም ሲል በልዩ ልዩ ምሁራንና ግለሰቦች ስለዚህ ጉዳይ የተደረጉትን ጥናቶችና ጽሑፎች ለማሰባሰብና ለማቀነባበር ተሞክሮአል። ከልዩ ልዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተውጣጡ አባላት የሚገኙባቸው ኰሚቴዎች ተቋቁመው በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል ። ምንም እንኳን የተደረጉት ጥናቶች ውስን ቢመስሉም ስለችግሩ አጠቃላይ ሁኔታና ይዘት ጠቃሚ መረጃዎችንና አንዳንድ መፍትሔ ሃሳቦችን ሊጠቁሙ ችለዋል ።

ዝሙት አዳሪነት የቦዘኔው ኅብረተሰብ አንዱ አካል እንደመሆኑ መጠን በ1972 ቦዘኔዎች በተሐድሶ ፕሮግራም ተሳትፈው አምራች ኃይል እንዲሆኑ ለማድረግ በተደረገው ጥረት ከ5,000ቦዘኔዎች መካከል509ዝሙት አዳሪዎች በምርት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል ። ይሁንና አንዳንዶች የተሰማሩበት የሥራ መስክ ቋሚ ባለመሆኑ ሥራው ሲያልቅም ሆነ ሳያልቅ እንዲሰናበቱ በመደረጉ ፣ ክትትል ባለመኖሩና ሌላ አማራጭ የሥራ ዕድል ባለመዘጋጀቱ ወደነበሩበት ተግባር ተመልሰው ሳይሰማሩ እንዳልቀሩ ይገመታል ።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላም ቢሆን አልፎ አልፎ ሴተኛ አዳሪዎችን፣ ቦዘኔዎችን ፣ ጤናማ ሆነው በልመና ሥራ የተሰማሩትን በተፈጥሮና ሰውሠራሽ አደጋዎች ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉትን በልዩ ልዩ የሠፈራ ፕሮግራም ለማሰማራት ብዙ ከመደከሙም በላይ ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ ተደርጉአል። ይሁን እንጂ የተገኘው ውጤት እስከዚህም አጥጋቢ አይደለም ። ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩትም ዋና ዋናዎቹ ችግሮች ሁለት ናቸው ።

1ኛ/ ጥናቶቹ የተሟሉ ወይም አስተማማኝ አለመሆን ። ብዙውን ጊዜ ለእንደዚህ ዓይነት የሠፈራ ፕሮግራም የሚደረጉ ጥናቶች ችግሩ በተባባሰበት ወቅት ለተፈጠረው አሳሳቢ ሁኔታ በአስቸኳይ መፍትሔ ለመሻት ሲሆን ፣ ይህንንም ተከትለው የሚደረጉት አንዳንድ ጥናቶች ለበሽታው መድኃኒት ፍለጋ እንጂ ለበሽታው መንስኤ መሠረታዊ መፍትሔ የሚሹ አይደሉም ። ለሰፈራው ከሚመለመሉት ወይም እንዲሰባሰቡ ከሚደረጉት ሰዎች አንስቶ እንዲሠፍሩበት እስከተመረጠው ቦታ ተስማሚነት ድረስ ያሉት ዝርዝር

ሁኔታዎች በሚገባ አይገመገሙም ። አን
ዳንዶቹ ጥናቶች መሠረታዊ ከሆኑት ጉዳ
ዮች ጋር ያልተገናዘቡ ፣ ከተጨባጭ
ሁኔታው ጋር ያልተመሳከሩ ናቸው።በመ
ሆኑም በአፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር
ይፈጠራል። ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተጠ
ንቶ በተግባር እንዲተረጐም የተደረገ
ባለመሆኑ የተጠበቀውን ውጤት አያስ
ገኝም ።

2/ በአፈጻጸም ላይ ተገቢው ክትትል አይ
ደረግም ። እንዲሰግሩ ለሚያደርጉት ፣
መስጠት የሚገባው ትኩረት ፣ ማለትም
ይኖሩበት ከነበረው የአንድ አካባቢ ሕይ
ወት ወደ ተለየ ኑሮና ሕይወት በሚያደር
ጉት ሽግግር የቀረበ ክትትልና እንክብ
ካቤ የማያጽርጥ የተሃድሶ ትምህርት እን
ደሚያስፈልጋቸው ሲታመን ፣ ይህ የሚ
ገባውን ያህል አይደረግም። በየዕለቱ የሚ
ፈጠሩትን ችግሮች በሰማበለው ሳይሆን
ከቦታው በመገኘት አብሮ በመወያየት
በወቅቱ መፍትሔ መሻት ሲያስፈልግ
ይህ አብዛኛውን ጊዜ አይደረግም። በመ
ሆኑም ስንት ወጭ የተደረገበትና የተደ
ከመበት ፕሮግራም ለመንግሥትም ሆነ
ለተረጂዎቹ ሳይበጅ ተሰነካክሉ ይደናቀ
ፋል። ያሉብንን ማኅበራዊ ችግሮች በከፊ
ልም ቢሆን ከማስወገዱ አንፃር ከፍተኛ
አስተዋጽኦ ሊኖራቸው የሚችል አንዳን
ድየሠፈራ ፕሮግራሞች ተገቢው እን
ክብካቤናክትትል ሊደረግላቸውና ወቅ
ታዊ መፍትሔ ሊሰጣቸው ባለመቻሉ ው
ጤት አልባሊሆኑ ችለዋል ማለት ነው ።

ላሉብን አንዳንድ አሳሳቢና አጣዳፊ
መፍትሔ ለሚሹ ማኅበራዊ ችግሮቻችን
እንደዓይነተኛ መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ
ተብለው የሚታሰቡት ልዩ ልዩ የሠ
ፈራ እርሻ ፕሮግራም ምርታማነት
ዝቅተኛ ሆኖ መገኘት ከዚሁ ጋር የተ
ያያዘ ችግር ነው ። የሰው ኃይል ፣ የመ
ገሪያዎችና ማሽኖች ፣ የመሬትና የገን
ዘብ ምርታማነት ድምር ውጤት ዝቅ
ተኛ እንዲሆን ፣ የሠፋሪ ገበሬዎች ራስ
መቻል ብቃት ደካማ እንዲሆን ያስገደዱ
ዋና ዋና ምክንያቶች እንደችግሮቹ ወሳኝ
ነት በተራ ቅደም ተከተል የሚከተሉት
ናቸው ። 12

1/ በገምት ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑ
ሠፋሪዎች በገዳጅ ወደ ሰፈራ ጣቢያ
ዎች ተወስደናል ብለው የሚያምኑ
መሆናቸው ፣ ሠፋሪዎች በሙሉ ከመ
ሬትና ከማምረቻ መሣሪያዎች ጋር
ያላቸው ገንኙነቶች ሁኔታ የአስተሳሰባ
ቸው እድገት መለወጥን ሣያጤን ደረ
ጃ ሰልፍ በወል እንዲሆን መደረጉ ሠ
ፋሪውን ከውስጥ ስቦ የሚያስቀር እ
ምነት እንዲኖረውና በዚህም ምክንያ
ት ብቃት ያለው የምርት መንደር ለ
መፍጠር አለመቻሉ ፣ መኮብለልን
ከሚያስከተሉት ሌሎች ችግሮች አን
ዱ መሆን ፣

2/ በከፍተኛ የምርት መሣሪያዎች ቴክኖ
ሎጂ) የሚገለገለው የወል እርሻ ምር
ት ሥራ የሚጠይቀው የሰው ኃይል
ጥራትና ችሎታ ከሠፋሪ ገበሬ
ዎቹ ዘንድ አለመገኘት ፣ የእርሻው ስፋ
ትና በአንድ እርሻ የሚታቀፈው ሠፋሪ
ብዛት ከፍተኛ መሆን ለእርሻው እን
ቅስቃሴ በሚያመች ሁኔታ አለመከፋ
ፈል ፣

3/ ሠፋሪ ገበሬዎቹ የተለያዩ የዕድገት ደረ
ጃዎች ያላቸው በመሆናቸው ማኅበራዊ
ለተደረገው የምርት ሥራ እንቅስቃሴ
ዲስፒሊን በመሪነትም ሆነ በተመሪ
ነት ደረጃ ራሳቸውን አመራረቱ ለሚ
ጠይቀው ባሕርይ ለማስገዛት ያላቸው
ችሎታና ጥራት በቂ አለመሆን ፣

4/ የሠፋሪ ገበሬዎች አደረጃጀትና የሠራ
ተኞች ምደባና ኃላፊነት በዚህም ምክ
ንያት የተፈጠረው ጣምራ ሥራ አመ
ራር እንዲሁም የተመደቡት ሠራተ
ኞች ችሎታ ሠፋሪ ገበሬዎችን ወደ
አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት
የሚወስድ ሆኖ አለመገኘት ፣

Digitized by Google

5/ በባሕሪያቸው ልዩነት ምክንያት የተ
ለያዩ የሥራ አደረጃጀት የሚጠይቁ
የሥራ ዘርፎች በአንድ ድርጅትና መዋ
ቅር ሥር ሆነው ለሻብት ምንጭ/ ለሪ
ሶርስስ/ ሽሚያ ሲያደርጉ የሚጉዳው
የሠፈራው እርሻ መሆኑ፣ ይህም ሆና
የቴክኒክ አገልግሎት ሰጭ መምሪያ
ዎች ከድጋፍ ሰጭ መምሪያዎች በቀ
ጥታና በቀላሉ ሊደገፉ የሚችሉበት
ሁኔታ ባለመፈጠሩ የጉን ግንኙነት
ቀልጣፋና ብቁ ከመሆን መታገድ፣
ከታች ወደላይ ግንኙነትን በሚመለከት
የቀርንጫፍ ጽ/ ቤቶች በዋናው መ/
ቤት ለሚገኙ ለሁለት ኃላፊዎች ተጠ
ሪዎች ከመሆናቸውም በላይ በመሠረ
ቱ በወል ሆነው በአንድ ሰብሳቢ አማ
ካይነት የሠፈራ እርሻ ፕሮግራም አፈ
ጻጸምን እንዲመሩ የሚጠበቅባቸው
የቴክኒክ መምሪያዎች በቀጥታ ብቁና
ተስሚ በሆነ መንገድ ቀ/ ጽ/ ቤቶችን
ሊያገኛቸው አለመቻል፣

6/ የሥራ ክፍፍልና ለምርት የሚደረግ
ክፍያ አባላትን የሚያነቃቃ፣ ለከፍ
ተኛ ውጤትና ገቢ የሚገፋፉ አለመ
ሆን፣

7/ የምርት ማስፋፊያዎች ጠቀሜታ ከፍ
ተኛነት፣ዘመናዊ የእርሻ አሠራር ዘዴን
ካልቸራል ፕራክቲስ በሥርዓት ለመ
ከተል አለመቻል እና የእርሻ መሣሪያ
ዎች ገልጋሎተች በአገባቡ ጥቀም ላይ
አለመዋል -

8/ በሠፈራ እርሻ ጣቢያ ደረጃ ገልጽ ያለና
የታወቀ የፋይናንስ ደንብ አለመኖር፣

9/ የሠፈራ እርሻዎች አጀማመር በመሠረ
ታዊ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ አለመ
ሆን ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚ ሁለቴኛ ተ
መደበኛ ስብሰባ «... ሥራ አጥ ሴቶች በተ
ለይም ዝሙት አዳሪዎች ትምህርት ተሃድሶ
እየተሰጣቸው የሙያ ዕውቀት እያገኙ በጤ
ናማና ውጤታማ የሥራ መስክ እንደየዝን
ባሌአቸው ተሰማርተው ምርታማ ተግባር
ለማከናወን እንዲችሉ የተጀመረው ጥረት
በይበልጥ በተነባበረ ዕቅድና ጥናት እንዲ
ቀጥል» በማለት ባስተላለፈው ውሳኔ መሰ
ረት ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው ።

በአጠቃላይ የቦዘኔዎች አንዱ ባህርይ
ሥራ ጠልነት ነው ። ከጠቅላላ የቦዘኔነት
ባህሪያቸው ለመላቀቅና ሠርተው በሚያገ
ኙት እንዲተዳደሩ ለማድረግ «በአንድ በ
ኩል የአመለካከት ለውጥ» ሊፈጥርባቸው
የሚችል የተሃድሶ ፕሮግራም ማካሄድና
በሌላ በኩልም ከሠርቶ አደርነት የተሻለ
አማራጭ የሌላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ
ላቸው ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ወሳኝ እርም
ጃዎች ናቸው ። [13]

ይህንን የቦዘኔነት ችግርም አላይ እንዶተ
ጠቀሰው በሰፈሩት ምክንያቶችም ለማመ
ልከት ልዩ ልዩ እርምጃዎች መውሰድ፣ ለም
ሳሌ በሀቡዕ የዝሙት ሥራ የተሰማሩትን
ሴት ተማሪዎች፣ ሠራተኞች ወዘተ — ማጋ
ለጥ፣ ማስቀጣት፣ እንደሁኔታው ወደ ቦዘ
ኔዎች የተሃድሶ ማዕከል መውሰድና ማስተ
ማር፣ በቱሪስትነት ስም ዝሙትን በሚያስ
ፋፉት ላይ የጠበቀ ቁጥጥር ማድረግ፣ በዝ
ሙት ተግባር ማስፋፋት የተሰማሩትን ታ
ክሲ ነጂዎች እንደሁኔታው እስከ ንግድ
ፈቃድ መውሰድና በሕግ መቅጣት ጭምር
እርምጃ መውሰድ፣ ባለዝግ ችሎቶችን፣ የቱ
ሪስት መሪ ነን ባዮችንና ገዱታቸውን በማ
ያከብሩ ዲፕሎማቶች፣ የአህጉሩና የዓለምአ
ቀፍ ድርጅት ሠራተኞችም ላይ እንዲሁ አስ
ፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ያስፈል
ጋል ።

ሌላው ትኩረት የተሰጠው ተግባር ደግሞ
የሕፃናት ጉዳይ ሲሆን፣ ሕፃናት የአገሪቱ
አለኝታና የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተረካቢ ዜ
ጎች እንደመሆናቸው መጠን አስተዳደጋ
ቸውም በሁሉም አቅጣጫ የተሟላ እንዲ
ሆን የአብዮቱ ምኞት ነው ። በመሆኑም በተ

Digitized by Google

ፊጥር አደጋና በጦርነት ምክንያት ወላጆቻቸው የሞቱባቸው እስከ 14 ዓመት ዕድሜ ለሚሆናቸው ለ5,000 ሕፃናት መሠረታዊ ፍላጐታቸው ተሟልቶ ፣ ትምህርትና ምርት ሚዛናዊ በሆነ ቅንጅት እያገኙና እያካሄዱ የሚያድጉበት የሕፃናት አምባ ተመስርቶ ሥራ መጀመሩ ባንድ በኩል የሕፃናትን ችግር ለማቃለል የተደረገውን ጥረት በጉልህ ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ ለወደፊት ለሚደረጉት ጥረቶች ከፍተኛ ልምድ የሚያስገኝ ሆኖአል ።

የማኅበራዊ አገልግሎቶችንም በማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቶአል ። ለጤና መሻሻል የተወሰዱትን አንዳንድ እርምጃዎች ስንመለከት ኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ በምታካሂደው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጤናን በሚመለከት ያለው መመሪያ የሠፊው ሕዝብ የተሟላ ኑሮ እንዲረጋገጥ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቂ የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ የሚል ሲሆን በዚህ መሠረት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ቀድሞ ዘመናዊ ሕክምና ከሚያገኘው ወይም በክሊኒኮች በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ለመጠቀም ከሚችለው ጠቅላላ የሀገሪቱ ሕዝብ 15% ብቻ የነበረው ወደ 43% ከፍ በማለቱ ውጤቱ የሚያበረታታ ነው ።

ከአብዮቱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ማለትም በ1965 በየደረጃው ባሉ ልዩ ልዩ የሕክምና ትምህርት ተቋሞች አዲስ የገቡ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር 766 ብቻ ነበር ። ይህ ቁጥር በ1974 ወደ 5721 ከፍ ብሏል ።

ከአብዮቱ ወዲህ የጤና ድርጅቶችን በማስፋፋት የተገኘው ከፍተኛ ውጤት ወደፊት ጤናን ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት ተግባራዊነት ማረጋገጫ ነው ። ለምሳሌ ባለፉት ሰባት ዓመታት በኅብረተሰብ ተሳትፎና በመንግሥት ድጋፍ የተሰሩት ጤና ድርጅቶች ብዛት ቀደም ብለው ከነበሩት ጋር ሲነጻጸር የተገኘው ውጤት ከፍተኛ ነው ። ቅድመ አብዮት ቁጥራቸው 649 የነበሩት ክሊኒኮች በ1974 ከእጥፍ በላይ ጨምረው 1829 ደርሰዋል ። ቅድመ አብዮት 93 የነበረው የጤና ጣቢያዎች ቁጥር በ1974 130 ደርሰዋል። ቅድመ አብዮት ቁጥራቸው 8624 የነበረው የሆስፒታል አልጋዎች ቁጥር በ1974 10,883 ደርሶአል ።

ትምህርትን በሚመለከት ከ1966 በኋላ ተወሰዱት እርምጃዎች በትምህርት ይዘትና አቋም ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስገኝተዋል ። በተለይ መሠረተ ትምህርትን በሚመለከት በተካሄደው ከፍተኛ ዘመቻ ቀድሞ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 93% የሚሆነውን የማይማን ቁጥር ወደ 55% ዝቅ አድርጉታል። በአፀደ ሕፃናት የሚገኙትን ህፃናት በሚመለከት በ1966 ቁጥራቸው 7573 የነበረው በ1974፥ 50,400 ደርሶአል። በአንደኛ ደረጃ በ1966 ፣ 859,831 የነበረው የተማሪዎች ቁጥር በ1974 ከፍተኛ እድገት በማሳየት 2,376,887 ደርሶአል ። በ1966 101,739 የነበረው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት በ1974 ወደ 249,424 ሊያድግ ችሏል ። ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃንም በሚመለከት በ1966 የነበሩት ተማሪዎች ቁጥር 81,296 ሲሆን በ1974 ላይ ደግሞ ይህ ቁጥር ወደ 238,722 አድጉአል ።

ምንም እንኳን ማኅበራዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት እነዚህን የመሳሰሉ አበይት ክንውኖች ቢደረጉም ፣ ችግሮቻችን ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል ለማለት አይቻልም ። ይህ ደግሞ ያለ ምክንያት አይደለም ።

የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዋነኛ ከሆኑት ተግባራት አንዱ ከአሮጌው ሥርዓት ማኅበር የተወረሱትን እነ

Digitized by Google

ዚህን ሥር የሰደዱ ማኅበራዊ ችግሮች ማለትም ሥራ አጥነትንና ሴተኛ አዳሪነትን ደረጃ በደረጃ ጨርሶ ማስወገድ ሲሆን፣ በተጨማሪም ሰፊውን ሕዝብ ለዘመናት ሲያሰቃዩት ከቆዩ ልዩ ልዩ በሽታዎች ነፃ እንዲሆን ፣ ከማይምነት እንዲላቀቅ ፣ ከአድኃሪ ባህሎች ተላቆ በተራማጅ ባህሎች እንዲገ

ጥረት ተደርጐአል ፤ እየተደረገም ነው ።

ሆኖም ከአብዮታችን ፍንዳታ ማግስት አንስቶ የተነሱብን ጠላቶቻችን አብዮቱን ለመቀልበስ በፈጠሩት ከፍተኛ ቀውስና አለመረጋጋት አድኃሪያንና ወራሪዎች በከፈቱብን ጦርነት የተነሳ ዛሬም አብዮታችን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች የገጠሙት

ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች

የትምህርት ተሳትፎ	1966	1974
ከጠቅላላው ሕዝብ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ	7%	45%
በአፀደ ሕጻናት የነበሩ ህፃናት ቍጥር	7,573	50,400
የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት	859,831	2,376,897
የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት	101,739	249,424
የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት	81,296	238,722

ምንጭ — የብ· አ· ም· ዘ· ማ·ፕ·ጠ· መምሪያ የአሥር ዓመት መሪ እቅድ አጠቃላይ የትምህርት ግምገማ ዓላማና ስልቶች ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 41

የጤና አገልግሎት	1965	197·4
ከጠቅላላው ሕዝብ ዘመናዊ ሕክምና ያገኝ የነበረው	15%	43%
የሕክምና ትምህርት የጀመሩ የጤና ባለሞያዎች ቍጥር	766	5,721
የክሊኒኮች ብዛት	649	1,829
የጤና ጣቢያዎች ብዛት	93	130
የሆስፒታል አልጋዎች ብዛት	8,624	10,883

ምንጭ — የብ· አ·ም·ዘ·ማ·ፕ·ጠ. መምሪያ የጤና ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ ረቂቅ 1 ፣ ሰኔ 1974 ፣ገጽ 7-8

ነባ ማድረግ ነው ። በዚህም መሠረት ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሕዝባዊ ኢኮኖሚና ባህል ለመገንባት በየአቅጣጫው ከፍተኛ

መሆኑ የማይካድ ነው ። በተለይም በመሐል ሀገር ኢ.ህ.አ.ፓ ፣ ኢ.ዲ.ህና ተገንጣይ ቡድኖች ከውጭ ደግሞ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪ

Digitized by Google

ያሊዝም ያስተባበራቸውና በተስፋፊው የሞቃዲሾ አድኃሪ የገዢ መደብ የተከፈቱብን ጦርነቶች ደረጃ በደረጃ መፈታት ለሚገባቸው ማኅበራዊ ችግሮች መባባስና ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ አይነተኛ ምክንያት ሆነዋል ።

የእርሻውና የኢንዱስትሪው ክፍላተ ኢኮኖሚ ማደግና መበልፀግ ለአጠቃላዩ የማኅበራዊ ችግሮች መፈታት መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ ቢሆንም ፣ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የልማቱ ተግባር የተጠበቀውን ያህል አልተካሄደም ። ይልቁንም የምርት ተግባር መደናቀፍ የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች እንዲቀንሱ አድርጓል። በተለይ በኢንዱስትሪው ረገድ ፣ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ገንጣይ ወንበዴዎች በማምረቻ ፋብሪካዎች ላይ ያደረሱት ጉዳት ፣ በመገናኛና ትራንስፖርት ዘርፍ ተፈጥሮ የቆየው ችግርና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች በብቃት አለመገኘታቸው ከአንዳንድ ፋብሪካዎች እርጅና ጋር ተዳምሮ ለኢንዱስትሪ ምርት አለማደግና መቀነስ ዋንኛ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል ።

ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በተለይም ቀደም ብሎና አሁንም በአንዳንድ ክፍላተ ሀገር በዝናብ እጥረት የደረሰው ድርቅ ብዙዎችን ከኑሮአቸው እንዲፈናቀሉና በልመና ተግባር እንዲሰማሩ አድርጎአቸዋል ። አንዳንዶችም ወደ ከተማ በመኰብለል የቦዘኔውንና የቤተኛ አዳሪዎችን ቁጥር ለማበራከት ምክንያት ሆነዋል ።

ለማኅበራዊ ችግሮቻችን መባባስ እነዚህ ሁኔታዎች ዋንኞቹ ናቸው ቢባልም ፣ ከዚህ በተጨማሪ አሻጥረኛ ነጋዴው ሰው ሠራሽ የእቃዎች እጥረት በመፍጠር ፣ ዋጋን በማናርና ከነጋዴ ገበሬዎች ጋር በመመሳጠር በከተሞችና በገጠር መካከል የረጋ የእቃዎች ልውውጥ እንዳይኖር ያደረገውና የሚያደርገው ጥረት ለማኅበራዊ ችግሮቻችን መባባስ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ተጨማሪ ምክንያቶች አንዱ ነው ።

በተያያዝነው ብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባህል እድገት ዘመቻ ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም፣ የግንባታው እንቅስቃሴ ያሰብነውን ያህል ሊፋጠን አልቻለም። በብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ እንደተገለጸው የኢንቨስትመንት መጠንና አፈጻጸም ዝቅተኛ በመሆኑ ፣ የሥራ ስምሪት እድል ከሥራ ፈላጊው ቁጥር ጋር ሊመጣጠን አለመቻሉ ፣ በነዳጅ፣በጥሬ እቃዎች ፣ በመለዋወጫና በአንዳንድ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች በኩል አገራችን ያለባት የውጭ ጥገኝነት ከፍተኛ መሆን ፣ እንዲሁም በ1973 በደረሰው ከፍተኛ የውጭ ንግድ መዛባት ምክንያት በደረሰው የውጭ ምንዛሪ እጥረት አንዳንድ የልማት ፕሮጀክቶች እንዲሰረዙ ወይም እንዲዘገዩ በመደረጉ የኤኮኖሚያችን እድገት ያሰብነውን ያህል ሊፋጠን አልቻለም ። በሌላም በኩል የማከፋፈያ አውታሮች ደካማ በመሆናቸውና በበቂ ሁኔታ ሊደራጁ ባለመቻላቸው የተነሳ ምርትን በማከፋፈሉ ረገድ ከፍተኛ ችግሮች ይታያሉ ። ምርትን በተደራጀና በተቀላጠፈ መንገድ ለኅብረተሰቡ ለማከፋፈል አለመቻሉ ካሉብን ችግሮችና ድክመቶች አንዱ ነው። ይህም ለማኅበራዊ ችግሮቻችን መባባስ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

ከዚህም በተጨማሪ የመኖሪያ ቤቶችን ሁኔታ በሚመለከት ረገድ ያለው ችግር ከማኅበራዊ የልማት እድገታችን አኳያ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ይህ

ንኑ ጉዳይ አስመልክተው ለኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ«... ዛሬ ከገጠሙን አበይት ችግሮች መካከል አንዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከሚሄደው የከተማ ነዋሪዎች ብዛት ጋር የሚመጣጠን የመኖሪያ ቤቶችና ከዚህም ጋር ተደጋጋፊ የሆኑ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ ሕንፃዎች እጥረት ነው። የቤቶች ግርጀትና አብዛኞቹ ቤቶችም አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን አሟልተው አለመገኘታቸው ችግሩን አባብሶታል » በማለት አስገንዝበው ነበር።

በአጠቃላይ በተወረሰው ኤኮኖሚያዊ ኋላቀርነት ፣ በገጠርና በከተማ መካከል ባለው ሰፊ የኑሮ ልዩነት ፣ እንዲሁም የሰው ኃይል ፍላጐትና ሥርዓተ ትምህርቱ አለመዛመዳቸውና የአነስተኛ እንዱስትሪዎች አለመስፋፋት ፣ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በኢምፔሪያሊስትቶች አማካይነት በዓለም ላይ የተከሰተው ቀውስና ይህም ቀውስ የፈጠረው አሳሳቢ ሁኔታ ለማኅበራዊ ችግሮችን መባባስ ዋንኛ ሁኔታዎች መሆናቸውን ማወቅ ይገባል።

ከላይ በተጠቀሱት አበይት ምክንያቶች በጤናና በትምህርት በኩል ግስጋሴ ለማድረግ፣ ሥራ አጥነትንና ሴተኛ አዳሪነትን ለማስወገድ እንዲሁም አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን፣ አካለ ስንኩላንና ጧሪ ወይም ረዳት የሌላቸውን አረጋውያንን ለመንከባከብና የመኖሪያ ቤቶችን ችግር ለማስወገድ ዛሬም ቢሆን ሙሉ በሙሉ አልተቻለም። እነዚህን ማኅበራዊ ችግሮች ለመቋቋምና ለማስወገድ የረጅም ጊዜ ትግል ይጠይቃል። ይህም ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ኤኮኖሚያዊ እድገት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። አሁን ባለንበት የመሸጋገሪያ ወቅት ካለፈው ሥርዓት የወረስናቸው ማኅበራዊ ችግሮች ሰፊ በመሆናቸውና የሶሻሊስት ስልተምርትም የመመሥረቱ ተግባር የረጅም ጊዜ ትግል የሚጠይቅ በመሆኑ የእነዚህን ማኅበራዊ ችግሮች መወገድ ከሀገሪቱ የምርት ኃይሎች መዳበር ጋር አአብር አያይዞ መመልከት የግድ ነው።

ማኅበራዊ ጠንቆችን ለመከላከልና ለማስወገድ የሚወሰደው እርምጃ ከኢኮኖሚው አጠቃላይ እድገት ተነጥሎ የሚታይ ባይሆንም ለጊዜውና በአጭር ጊዜ ዕቅድ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመቀየስ ችግሩን ለመቀነስ ጥረት መደረግ እንደሚኖርበት ሁኔታዎች ያመለክታሉ። በተለይም ዝሙት አዳሪነትን ፣ ቦዘኔነትንና ወንጀለኝነትን የመሳሰሉትን ማኅበራዊ ጠንቆች ለማስወገድ ከቻሉት ሶሻሊስት አገሮች የሥራ ልምድ በመቅሰምና አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ጠንቆቹን ደረጃ በደረጃ ለመከላከል ከፍተኛ ትግል መደረግ ያለበት መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ።

ለምሳሌም ያህል ኩባ ፣ ከአብዮቱ ማግስት ጀምሮ እርሻና ኢንዱስትሪን በሶሻሊስት መስመር ለመገንባት ያደረገችው ጥረትና ለማኅበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት የሰጠችው ትኩረት ብዙ የሥራ መስኩችን ለመክፈትና የሥራ አጥነትንም ችግር ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ አስችሏታል። በብዙሺህ የሚቆጠሩ በተለይ የሙያ እውቀት ኖሯቸው ሥራ ግን የሌላቸውን በትምህርት ፣ በጤናና በሌሎች የማኅበራዊ መስጫ ተቋሞች ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ መደረጉ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ሊያስገኝ ችሏል። በተጨማሪም አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መከፈታቸውና ከውጭ አገሮች የተገኘውን የነፃ ትምህርት እድል አገሪቷ በሚገባ ለመጠቀም መቻሏ ለብዙ ሥራ አጦች የትምህርት እድል አስገኝቷል።

የቬየትናም ሕዝባዊት ሪፐብሊክም ተመሳሳይ የሆነ ሊጠቀስ የሚገባው ታሪክ አላት።

Digitized by Google

ደቡብ ቬየትናም ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መዳፍ ተላቃ ስትወጣና ለሁለት እንድትከፈል ተደርጋ የነበረችው ቬየትናም አንድ ስትሆን በሳይጎን ከተማ ከግማሽ ሚሊዮን የሚበልጡ ሴተኛ አዳሪዎችና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሥራ አጦች ይገኙ ነበር ። የቬየትናም መንግሥትና ሕዝብ በወሰደው ቆራጥ እርምጃ በተለይ በሴተኛ አዳሪነት ዝቃጭ ኑሮ ይኖሩ ለነበሩት የተሃድሶ ፕሮግራም በማዘጋጀት ፣ የልማት ሥራዎችን ፣ ፋብሪካዎችን ፣ እርሻዎችንና አነስተኛ የእደ ጥበብ ተቋሞችን በማስፋፋት በሥራ ላይ እንዲሰማሩ አድርጉአል ።

ወደ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ በሚደረገው ግስጋሴ እንደ ሥራ አጥነትና ሴተኛ አዳሪነት የመሳሰሉት ማኅበራዊ ችግሮችና ጠንቆች ደረጃ በደረጃ እየተወገዱ የሚሄዱ እንጂ በአንድ ጊዜ የሚጠፉ አይደሉም ። ስለሆነም እነዚህ ችግሮች ዛሬም በአገራችን ጉልተው የሚታዩ አቢይና አሳሳቢ ሁኔታዎች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ለኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ «ማኅበራዊ ችግሮቻችን በምርት ኃይሎች እድገት እየተወገዱ የሚሄዱ ቢሆንም እጅግ አሳሳቢ የሆኑት በተቻለ መጠን የሚቃለሉበትን ሁኔታ መሻት ቸል ሊባል የማይገባው ነው ። ማይምነትን የማስወገዱን ዘመቻ ማጠናከር ፣ በተላላፊ በሽታዎች ላይ መዝመት ፣ ሥራ አጥነትን ለማቃለል ተገቢ ትኩረት መስጠትና የግንባታው ትግላችን ፀር የሆኑትን ለሕዝብና ለመንግሥት ንብረት እንክብካቤ አለማድረግን ፣ ጉቦና ሥርቆትን መዋጋት ፣ በአንጻሩም ቁጠባና ምርታማነት እንዲዳብር ማድረግ በማኅበራዊ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ አበይት ጉዳዮች ናቸው ፤ » ብለዋል ። የመደብ ጠላቶቻችን ግን እንዲህ ያሉትን ችግሮች ሊፈቱ የማይችሉና በሕዝብ ላይ ሆን ተብለው የተጫኑ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ሐቁ ግን ይህ እንዳልሆነ ከሚከናወኑት ተግባራት ማየት ይቻላል ።

አብዮታዊው መንግሥትና ኢሠፓአኮ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮችን ማቃለልና ደረጃ በደረጃ የሚወገዱበትን መሠረት መጣል አንዱ ዓላማቸው ነው ። በዚህም መሠረት ሥራ አጥነትን በሚመለከት ረገድ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኰሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል ።

1. የቀለም ትምህርት ናሯቸው ሥራ ሊያገኙ ያልቻሉትን በኢኮኖሚው ውስጥ እጥረት በሚታይባቸው ልዩ ልዩ ሙያዎች በማሠልጠን ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ፣
2. የደን ሥራ ፣ የእደ ጥበብና የጐጆ ኢንዱስትሪን በማስፋፋት እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማኅበራትና ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማስፋፋትና በማጠናከር የሥራ እድል እንዲፈጠር ፣
3. የተለየ ሙያ የሌላቸው በሰፋፊ ፕሮግራሞች እንዲሁም የገጠሩን ልማት ለማፋጠን በሚረዱ የኮንስትራክሽን ሥራ መስኮች እንዲመደቡ ፣
4. በልዩ ልዩ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች የሚቀይሱት የልማት ፕሮጀክቶች በተቻለ መጠን በሰው ኃይል በይበልጥ የሚጠቀሙና የሥራ እድል የሚያስፋፉ እንዲሆኑ ፣ የሚሉ ናቸው ።

ሥር የሰደዱ ማኅበራዊ ችግሮች ሊወገዱ የሚችሉት በረጅም ጊዜ የግንባታ ሂደት ውስጥ መሆኑ ቀደም ሲል የተገለጸ ሲሆን በተለይ በዝግጅት ላይ ያለው የአሥር ዓመቱ መሪ እቅድ ለዚህ ዓይነተኛነት አለው። የአሥር ዓመቱ መሪ እቅድ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትን በማሳደግ ፣ ማኅበራዊ ችግሮችን በማቃለል ፣ ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ቅድመ ሁኔታ የሆነውን ጠንካራ የማቴሪያልና የቴክኒክ መሠረት በመጣል የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በማገባደዱ ላይ የሚያተኩር ነው ። ይህንኑ በማስመልከት ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በሰጡት ማብራሪያ ይህ የአሥር ዓመቱ መሪ እቅድ ዝግጅት ከፍ

Digitized by Google

ተኛ የሆነውን የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል ከጥቅም ላይ በማዋል ኋላቀር ነታችንንና በዚሁ ሳቢያ የተከሰቱትን ችግሮች ለማስወገድ ፍቱን መፍትሔ መሆኑን አመልክተዋል ።

ሰፊው ሕዝብ በይበልጥ መደራጀትና በመሠረታቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት የሚያደርገው ተሳትፎና እንቅስቃሴ ፣ እንዲሁም እነዚሁ ድርጅቶች ከመንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጉት የሥራ ቅንጅት ለእነዚህ ማኅበራዊ ችግሮች መፈታት አንዱና አቢይ ሁኔታ ነው።ሕዝቡ በጦርነት ምክንያት የተፈጠሩትን አደጋዎችም ሆነ ሌሎች ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከል በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል ። ይህንኑ አስመልክተው ጓድ ሊቀመንበር በኢሠፓአኮ ማእከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር « ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ስለ ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ጠባይና ለሚያስከትሉት ጉዳት ፣ ከአደጋዎች ለመከላከል የሚያስፈልጉትን ዝግጅቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲያውቅ ፣ ጥፋትን ለመቀነስና ለመከላከል በቂ ሆኖ እንዲገኝ የሚያበቃው የሲቪል መከላከል ዝግጅት ነው» ብለዋል ።

የኢንዱስትሪ ግንባታና የሶሻሊስትታዊ የእርሻ እድገት ለሕዝቡ የትምህርትና የቴክኒክ ደረጃ ማደግ ወሳኝ ነው ። በዚህ ሁኔታ እያደገ የሚሄደው ለሶሺያሊዝም ቅድመ ሁኔታዎችን የሚሟላቱ ጥረት የፓርቲን ሚና ከምንጊዜውም በበለጠ ያሳድገዋል ። ፓርቲው የሶሻሊስት ግንባታን በቀጥታ ስለሚመራ በኅብረተሰቡ ውስጥ ጥልቀት ያላቸው የማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ለውጦችእንዲካሄዱ ያደርጋል ። በዚህም ሂደት ሥር የሰደዱ ማኅበራዊ ችግሮች የዘለቄታ መፍትሔ ያገኛሉ ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

1· ብ·አ·የም·ዘ·ማ.ፕ·ጠ. መምሪያ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከያና ማስወገጃ ጥናት ለ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝግጅት የቀረበ ሰኔ 1 ፣ 1974 ገጽ 8 (ያልታተመ)

2· ከገጽ 8 እስከ 9

3· ገጽ 3

4· » 2

5· » 4

6· በአዲስ አበባ ከተሞች ጐልተው የሚታዩ አሳሳቢ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች ግምገማና የመፍትሔ ሃሳቦች ፣ ጥቅምት 1975 ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)

7· የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከያ ማስወገጃ ጥናት ፣ ገጽ 17

8· ብ.አ·ም. ዘመቻና ግ·ፕጠ. መምሪያ፣ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች መከላከያና ማስወገጃ ጥናት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 18 (ያልታተመ)

9· ብ·አ·ም·ዘ·ፕ· ጠ/መምሪያ የጤና ዘርፍ የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ረቂቅ 1 ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 4 (ያልታተመ)

10· ብ·አ·ም·ዘ·ማ·ፕ· ጠ/መምሪያ የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ የአጠቃላይ ትምህርት ግምገማ፣ ዓላማና ስልቶች ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 46 እስከ 49 (ያልታተመ)

11· ብ·አ·ም·ዘ·ማ·ፕ ጠ/መምሪያ የማኅበራዊ ደህንነት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ፣ መጋቢት 1974 ፣ ገጽ 3 (ያልታተመ)

12· ብ·አ·ም·ዘ·ማ·ፕ· ጠ/መምሪያ የሠፈራ እርሻ አዝርዕት ልማት ግምገማና የ10 ዓመት ዓላማና ስልት ፣ ሐምሌ 1974 ፣ ገጽ 80—81 (ያልታተመ)

13· በአዲስ አበባ ከተማ ጐልተው የሚታዩ አሳሳቢ የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች ግምገማና የመፍትሔ ሃሳቦች ፣ ጥቅምት 1975 ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER
1985
INSTITUTION

- አዲሱ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ ሥርዓት
- ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግና ችግሮቹ
- የኤኮኖሚ ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም በአብዮቱ ሂደት
- ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል
- የኋላቀር አገሮች የውጭ ዕዳ ሸክምና የኢምፔሪያሊዝም የፋይናንስ ስትራቴጂ

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 3 ቁጥር
ሰኔ 1975
14

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem No. 14

ET407900 9

መስከረም

ቅጽ 3 ቁጥር 14
ሰኔ 1975

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

- አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት—በፅንሰሃሳቡ ይዘት ላይ አንዳንድ አመለካከቶች 3
  —እምሻ ዳኘው

- የሶሻሊስት የእድገት ፈለግና ችግሮች 15
  —ዶ/ር ታረቀኝ አደቦ

- የኢኮኖሚ እቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም በአብዮቱ ሂደት 34
  —ተክለብርሃን ገ/ሚካኤል
  —ፋሲል ተፈራ

- ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል /ክፍል ሁለት/ 58
  —ኢሳይያስ ደምሴ

- የኋላቀር አገሮች የውጭ እዳ ሸክምና የኢምፔርያሊዝም የፋይናንስ ስትራቴጂ 81

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ኢሠፓአኮ

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት—በጽንሰሃሳቡ ይዘት ላይ አንዳንድ አመለካከቶች

ለአዲሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በይፋ ጥሪ የተደረገው በ1974* ነው ።
ከዚያ በፊት ጥያቄው በተቀናጀ መልኩ ባይቀርብም ፣ በዚህ ጥያቄ ሥር የታቀፉ ነጥ
ቦች በተናጠል በተለያዩ የዓለምአቀፍ ሸንጐዎች ቀርበው ነበር ። ለአዲሱ ዓለምአቀፍ
የኢኮኖሚ ሥርዓት የተደረገው ጥሪ ከላይ በተጠቀሰው ዓመት በተቀናጀ መልኩ እን
ዲቀርብ የተለያዩ ምክንያቶች እንደመንስኤ ሆነው ሊያገለግሉ ቢችሉም ፣ ለጥሪው
ዋናና መሠረታዊ መነሻ የሆነው ኋላቀር አገሮች ተብተቦ በያዛቸው ፣ ለሀብታቸው
መገፈፍና ለገቢአቸው ማነስ ፣ በአጠቃላይ ለዕድገታቸው እንቅፋት በሆነው የካፒታ
ሊስቱ ዓለም በዘረጋው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት መማረራቸው ነው ።

በተለይም ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአዲሱ የዓለምአቀፍ ኢኮኖሚ ሥርዓት
የሚደረገው ትግል እየጐላ እንዲመጣ ያደረጉት ሦስት ሁኔታዎች አሉ ። እነሱም ኋላ
ቀር አገሮች የተጐናጸፉት የፖለቲካ ነፃነት ወደ ዕውነተኛ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ
ነፃነት ሊያመራ አለመቻሉ ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያገለግላል ተብሎ የሚሰጠው ፀር
ዳታ ዕውነተኛ ዕድገት ለማስገኘት ያለመቻሉ ገሃድ መሆንና በተለይም በ1973 የተ
መሠረተው የዘይት ላኪ አገሮች ድርጅት (OPEC) ቀደም ሲል በተለይ ከዳበሩ
ካፒታሊስት አገሮች ጋር የነበረውን የተዛባ የንግድ ግንኙነት በማስተካከል ረገድ
የተቀዳጀው ድል ናቸው ። **

ስለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ምንነት በሚገባ ለመረዳት በተለይ
ከ1970ዎቹ ወዲህ እየተባባሰ ስለመጣውና ለአዲሱ ዓለምአቀፍ ኢኮኖሚ ሥርዓት
ጥያቄ መነሳት መሠረታዊ መንስኤ ስለሆነው ዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ
ቀውስ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

እንደሚታወቀው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለ25 ዓመታት
ያህል ማለትም እስከ 1960ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ድረስ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊ
ዝም ይመራ የነበረው ዓለምአቀፍ ካፒታሊዝም አዳዲስ የምርት አደረጃጀትን በማስ
ተዋወቅም ሆነ ምርታማነትን በማዳበር በካፒታሊዝም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ
የኢኮኖሚ ዕድገት አስገኝቶ ነበር ። ይሁንና ይህ ሁኔታ በሥርዓቱ ውስጥ ቀደም ሲል
ያልታየ የራሱ የሆነ ቀራኔ ፣ መዛባትና ውጥረትን አስከተለ ።

በካፒታሊስት ሥርዓት በሁለት የኢኮኖሚ ቀውሶች መካከል የነበረው ጊዜ ከበፊቱ
በጣም እየተጣበበ መምጣት ፣ ኢኮኖሚው የማገገም ምልክት በሚያሳይበትም ጊዜ

---

* በዝግጅት ገጽ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምሕረቶች ሁሉ እንደአውሮፓውያን
አቆጣጠር ናቸው

** Development and Pace, (Pub. by the Hungarian Peace Council & World Peace Council), Vol. 1, No. 2, 1980, p. 7.

Digitized by Google

ከፍተኛ የሥራ አጥ ቁጥርና የዋጋ መናር መናር ፣ እየተባባሰ የሚሄድ የገንዘብ ፣ የፋይናንስ ፣ የኃይል ፣ የካባቢ አየርና የአካባቢ ተፈጥሮ የመበከል ቀውስ ፣ የዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ሥርዓትን በየጊዜው የሚያገረሽ ቀውስ (Cyclical crisis) ወደ አጠቃላይ ቀውስ እንዲሸጋገር አደረገው ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል ያለው በብዝበዛ ላይ የተመሠረተው የኢንቬስትመንት ፤ የንግድ ፤ የፋይናንስና የቴክኒዎሎጂ ግንኙነት የኋላቀር አገሮችን ዕድገት ጨርሶ ከመግታቱም ባሻገር ፤ ጓድ ፊደል ካስትሮ ለሰባተኛው የገለልተኛ መንግሥታት ጉባኤ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ እንደተጠቀሰው፤ በአሁኑ ጊዜ በኋላቀር አገሮች ውስጥ -

—በረሃብ ላይ ያለው የሰው ብዛት 500 ሚሊዮን መድረሱ ፣
—ምንም ዓይነት የሕክምና አገልግሎት የማያገኘው ሰው ብዛት 1·5 ቢሊዮን መሆኑ፥
—በፍጹም ድኅነት የሚኖረው ከ1 ቢሊዮን በላይ መሆኑ ፣
—በሥራ አጥነት ወይም በስውር ሥራ አጥነት (ሙሉ በሙሉ ሥራላይ ባለመሠማራት) የሚማቀቀው ሕዝብ ከ500 ሚሊዮን በላይ መድረሱ ፣

—በማይምነት ጨለማ የተጋረደው ሕዝብ ብዛት 814 ሚሊዮን መሆኑ ፤
—ትምህርት ለማግኘት ያልቻሉ ሕፃናት ቁጥር ከ200 ሚሊዮን በላይ መድረሱ ፣
—ለመጠጥየሚሆን የተጣራ ውሃ የማያገኘው ሕዝብ ከ2 ቢሊዮን በላይ መሆኑ ወዘተ*...

ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የዘረጋው የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ሥርዓት ኋላቀር አገሮችን ከድጡ ወደማጡ ከመክተት በስተቀር የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ሊያስገኝ ባለመቻሉ ፣ አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ መግባቱ በገሃድ እየታየ ነው ።

ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በኋላቀር አገሮች ላይ የሚነው የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ሥርዓት በአሁኑ ወቀት የደረሰበት ቀውስ ምልክት በኋላቀር አገሮች ሕዝቦች ላይ ያካሄደው ብዝበዛ እጅግ የከፋ ከመሆኑ የተነሳ ፤ ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ረሃብ ፤ እርዛትና ድኅነት ተስፋፍቶ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ሕልውና እራሱ ከፍተኛ አደጋ ላይ ለመውደቅ መቃረቡ ነው ።

ታላላቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ውስጥ በመዋዕለ ነዋይ መልክ ላዋሉት እያንዳንዱ ዶላር ከእጥፍ በላይ የሚሆን ገቢ ወደ አገራቸው ያግዛሉ ። ለምሳሌ የአሜሪካ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ከ1970-1974 ድረስ ባለው ጊዜ ኋላ ቀር አገሮች ውስጥ 11,446 ሚሊዮን ዶላር የመዋዕለ ነዋይ ክምችት አድርገው በዚሁ ጊዜ ውስጥ በትርፍ መልክ ወደውጭ ያጋዙት 48,663 ሚሊዮን ዶላር ነው ። ይህም የአሜሪካ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በተጠቀሰው ጊዜ በኋላቀር አገሮች ውስጥ ላዋሉት አንድ ዶላር 4.25 ዶላር ወደውጭ አግዘዋል ማለት ነው።** ይህ እንግዲህ የካፒታል ኢንቬስትመንትን የሚመለከት ሲሆን በካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል ያለው የውጭ ንግድ ግንኙነትም ከዚህ የባሰ ብዝበዛ የሚካሄድበት መስክ ነው ።

ኋላቀር አገሮች የሚያመርቷቸው ጥሬ ዕቃዎች የሚያስገኙት ዋጋ እየቀነሰ መምጣት ፤ የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች የሚያመርቷቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶች ዋጋ በየጊዜው መጨመር ፣ የነዳጅ ዋጋ መናር ፤ የአነስተኛና የመለስተኛ ኢንዱስትሪ ውጤ

---

* Fidel Castro, *The World Economic and Social Crisis,* (Havana, Publishing Office of the Council of State, 1983), p. 88.

* * *Ibid.*, p. 34.

Digitized by Google

ቶች በሆኑ የኋላቀር አገሮች ምርቶች ላይ ካፒታሊስት አገሮች የሚጥሉት የውጭንግድ ቀረጥ (Tariff) አንድ ላይ ተዳምሮ የኋላቀር አገሮችን የውጭ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ በማዛባት ላይ ይገኛል ። በዚህም ረገድ ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ጋር ባላቸው ያል ተመጣጠነ ንግድ ሳቢያ ኋላቀር አገሮች የሚደርስባቸው ብዝበዛ በጣም ከፍተኛ ነው ። ለምሳሌ ያህል በ1978 ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች 30 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ጥሬ ዕቃ ገዝተው ይህንን ጥሬ ዕቃ ወደተለያየ ሸቀጥ በመለወጥ የተለወ ጠውን ምርት በ200 ቢሊዮን ዶላር መልሰው ሸጠውታል ። * ይህንኑ ሁኔታ በሌላ ምሳሌ ለመግለጽ ያህል—በ1960 አንድ ቶን ቡና 37·3 ቶን ማዳበሪያ ሲገዛ፥ በ1982 አንድ ቶን ቡና ሊገዛ የቻለው 15·8 ቶን ማዳበሪያ ብቻ ነበር ። ** ይህ ሁኔታ እየ ተሻሻለ ሳይሆን እየባሰ በመሄድ ላይ ነው ።

ይህ ያልተመጣጠነ የልውውጥ ሥርዓት ከ1970 ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮ ሰፍና ከሚገኘው የዋጋ ንረት ጋር ተዳምሮ የኋላቀር አገሮችን የንግድ ሚዛን በከፍ ተኛ ደረጃ በማናጋት ላይ ከመሆኑም በላይ በክፍያ ሚዛናቸውም ላይ ይህ ነው የማ ይባል ችግር ፈጥሯል ።

ኢምፔሪያሊዝም የዘረጋውን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ከፍተኛ ቀውስ ላይ የጣለው ሌላው ጉዳይ በኋላቀር አገሮች ላይ የተጫነውና አሁን ባለው ያልተመጣጠነ ንግድና ከፍተኛ የሆነ የወለድ መጣኔ አኳያ ጨርሶ ሊከፈል ያልቻለና ሊከፈልም የማ ይችል ዕዳ መኖር ነው ። እንደሚታወቀው የቀድሞው የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ጭቁን ሕዝቦችና አገሮች ለነፃነት ባካሄዱት ትግል ተንኮታኩቶ በተለይም ከሁለተኛው የዓ ለም ጦርነት ወዲህ ኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓቱን በሰፊው እን ደዘረጋ ፥ ዋንኛው የብዝበዛ ስልት የተትረፈረፈ ካፒታልን በኢንቬስትመንት መልክ ወደኋላቀር አገሮች መላክ ነበር ። ይህ የብዝበዛ ዘዴ በስፋት እስከ 1970 ዎቹ ዓመ ታት መጀመሪያ ድረስ የቀጠለ ሲሆን ፥ ለዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እጅግ ከፍ ተኛ የሆነ ትርፍ ያስገኘ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ይሁንና በተለይ ከ1960 ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ገደማ ጀምሮ ኋላቀር አገሮች ያገኙት የፖለቲካ ነፃነት በቂ አለመሆኑን በመገንዘብ ለኢኮኖሚ ነፃነት ብሎም ለዕው ነተኛ የፖለቲካ ነፃነት ትግል በማካሄድ አንዳንድ የኢምፔሪያሊዝም ድንበር ዘለል ኩባንያዎችን መውረስ በጀመሩበት ጊዜ ፥ ኢምፔሪያሊዝም የታክቲክ ለውጥ አደረገ ። ይኸውም ካፒታልን ወደ ውጭ በኢንቬስትመንት መልክ መላኩን ቀዝቀዝ በማድረግ በባንክ ብድር መልክ ፋይናንስ ካፒታልን በብዛት ወደኋላቀር አገሮች ማስገባት ነው ። በመሆኑም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ ኋላቀር አገሮች በከፍተኛ ደረጃ በመበዝ በዝ ላይ ያሉት የዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የወል እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሣሪ ያዎቹ በሆኑት «ዓለምአቀፍ» የገንዘብና የፋይናንስ ድርጅቶች አማካይነት ነው ። በአ ሁኑ ጊዜ ብዙ ጥናቶች እንደሚጠቁሙትና በጥናቶቹም መሠረት የተጠናቀሩት አኃ ዞች እንደሚያሳዩት፥ ከቀጥተኛ የውጭ ካፒታል ኢንቬስትመንት ይልቅ የወለድና የአ ገልግሎት ክፍያው እየጨመረ የመጣው የባንክ ብድር ለዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት ላይ መሆኑን ነው ። በ1982 ኋላቀር አገሮች ያለባቸው ብድር ከ600 ቢሊዮን ዶላር በላይ ሲሆን በ1990 የብድሩ መጠን ወደ 1,473 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያድግ ጥናቶች ይጠቁማሉ ። *** የሚገርመው ነገር ኋላቀር አገሮች በሚሰጣቸው

* International Affairs, No. 3, 1981, p. 21.

** *The World Economic and Social Crisis*, p. 62.

*** ጓድ ፊደል ካስትሮ ሩዝ ለሰባተኛው የገለልተኛ መንግሥታት ጉባኤ ካቀረ ቡት ሪፖርት ላይ የተወሰደ ፤ ገፅ 31

Digitized by Google

ብድር ላይ የሚከፍሉት ወለድና ዋናውን ብድር በተወሰነ ዓመት ውስጥ ከፍለው ለመ ጨረስ በየጊዜው የሚያደርጉት ክፍያ (amortization) አንድ ላይ ተደምሮ ከዋናው ብድር ከራሱ እየበለጠ መሄዱ ነው ። ለምሳሌ ከዓለም ባንክ የተገኘ አኃዝ እንደሚ ያስረዳው በ1981 ኋላቀር አገሮች ያገኙት ብድር 117 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ፥ በዚሁ ጊዜ ለብድር አገልግሎት (debt Service) ማለትም ዋናውን ብድር ለመጨረስ በየወቅቱ ለሚደረገው የተወሰነ ክፍያና ለወለድ የከፈሉት 99 ቢሊዮን ዶላር ማለትም 85% በመሆኑ ፥ ካገኙት 117 ቢሊዮን ዶላር ላይ በተጣራ ሁኔታ የተጠቀሙበት 18 ቢሊዮን ዶላር ወይም 15% ብቻ ነው ።* በዚህ ዓይነት ሁኔታ በተለይ የዘይት ምርት የሌላቸው አብዛኛዎቹ ኋላቀር አገሮች ከውጭ ንግዳቸው ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ ከ80% በላይ የሆነውን ለብድር አገልግሎት ክፍያ ለማዋል በመገደዳቸው ልማታቸው ሊያድግ ቀርቶ ጨርሶ የተገታበት ሁኔታ ላይ ሊደርስ ችሏል ።

ይህ የኢምፔሪያሊዝም የወቅቱ የእጅ ለዙር የቀኝ አገዛዝ አስተራተጂ ካፒታልን ወደ ምርት ካፒታል ከመለወጥ ይልቅ ከፍተኛ ወለድ የሚያስገኝ የገንዘብ ካፒታል ሆኖ እንዲቀር በማድረግ ላይ ያተኮረ ፥ ሌኒን ኢምፔሪያሊዝም ማለት «ፋይናንስ ካፒ ታል» ነው ያለውን አባባል ዕውነተኛነት የሚያረጋግጥ ነው ።

«ኋላቀር አገሮች ላይ ያለው ይህ የብድር ጫና እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን ተስፋ ጨርሶ ከማጨለሙም ባሻገር ፥ የገቢ ንግድ ከፍተኛ ተፅዕኖ በሚያደርግባቸው አብዛኞቹ ኋላቀር አገሮች ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ዝቅ ተኛ የሆነ የፍጆታ ደረጃ እንኳ ባለበት ለማቆየት አልተቻለም ።» **

የብድሩ ጫና መረን የለቀቀ በመሆኑ ፥ ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ጊዜ በኋላቀር አገር ውስጥ የተወለደ ማናቸውም ሕፃን ገና እንደተወለደ የ260 ዶላር ባለዕዳ ነው ። የብድሩ የዕድገት መጣኔ በኋላቀር አገሮች ውስጥ ከሚታየው አነስተኛ ነው የማይባል የሕዝብ ዕድገት መጣኔ ጋር ሲነፃፀር እንኳ ከፍተኛ በመሆኑ ፥ በ1985 —ከሁለት ዓመት በኋላ ማለት ነው —በኋላቀር ዓለም ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ነዋሪ የ500 ዶላር ባለዕዳ ይሆናል ። ***

ኋላቀር አገሮች በአሁኑ ጊዜ ያለባቸው የብድር ጫና እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ መቻሉ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ባንድ በኩል ብድሩ በምንም ዓይነት ታምር ሊከፈል የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲሆን ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል በኢ ምፔሪያሊዝም አማካኝነት ተዘርግቶ የነበረውና በአሁኑም ወቅት ሰፍኖ የሚገኘው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ጨርሶ ቀጡን ያጣና በቀውስ የተቀሰፈ መሆኑን ነው ።

በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚካሄደውን የኢንዱስትሪ ግንባታና ከዚህም ጋር በተ ያያዘ ሁኔታ በቡርዧ አፈቀላጤዎች አለ እየተባለ የሚነገርለትን «የቴክኒዎሎጂ ሥር ፀትና ሥርጭት» በሚመለከትም ሁኔታው ቀደም ሲል ለማስተላለፍ ከተሞከረው መል ዕክት የተለየ አይደለም ።

---

* *The World Economic and Social Crisis*, p. 90.

** *The World Economic and Social Crisis*, p. 88.

*** *Ibid.*

Digitized by Google

የኢንዱስትሪ ግንባታን በሚመለከት፣ በአሁኑ ጊዜ የኋላቀር አገሮች በአጠቃላይ
ከዓለም የኢንዱስትሪ ውጤት ያላቸው ድርሻ 9% ብቻ ሲሆን፣ እስከ 2000 ሺህ
ዓመተ ምህረት ድረስ ይህ ቁጥር ያድጋል ተብሎ የተገመተው ወደ 13·5% ነው። ይሁ
ንና በዚያን ጊዜ በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሕዝብ ብዛት አሁን ካለበት መጠን በግምት
ከ65% በላይ ስለሚያድግ፣ የኢንዱስትሪው እድገት የሚያሳየው የ4·5% የዕድገት መጣኔ
ከሕዝቡ ዕድገት መጣኔ ጋር ሲነፃፀር አንፃራዊ በሆነ መንገድ እጅግ ዝቅተኛ መሆ
ኑን ያመለክታል ።* ከዚህም በላይ በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎች በአ
ብዛኛው በተላልቀ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ቁጥጥር ሥር ናቸው። ለምሳሌ በ1977
የኢምፔሪያሊስት አገሮች ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ ከተ
መረቱት የፋብሪካ ውጤቶች 76.5%፣ ከብረታ ብረትና ብረት ነክ ካልሆኑ የጥሬ ዕቃ
ምርቶች ውስጥ 80%፣ ከንግድና ከማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ምርት 90.6% ያህ
ሉን ይቆጣጠሩ ነበር። በተጨማሪም ከ1980 ከኋላቀር አገሮች የኢንዱስትሪ ውጤት መካ
ከል 61·4% የሚሆነው በአምስት ከኋላቀር አገሮች ውስጥ የተከማቸ ነበር ።

የቴክኒዎሎጂ ሥርጭትንም በሚመለከት በ1982 ኋላቀር አገሮች ለገዙት ቴክኒ
ዎሎጂ 35 ቢሊዮን ዶላር ከመክፈላቸውም በላይ፣ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከኋላቀር
አገሮች የሚነጥቁት የሠለጠነ የሰው ኃይል በገንዘብ ሲተመን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ
ስለ የሚባለውን «የተክኒዎሎጂ ሥርጭት» ተግባራዊነት በማሰናከል ላይ ይገኛል
ለምሳሌ ያህል የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ድርጅት (UNCTAD) ባካሄ
ደው ጥናት መሠረት፣ ከ1960—1972 ባለው ጊዜ ውስጥ ከኋላቀር አገሮች ወደ አሜሪካ፣
እንግሊዝና ካናዳ ብቻ የኮበለለው የሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ከካፒታል ወጪ አንፃር ሲገ
መገም በኋላቀር አገሮች ላይ የ51 ቢሊዮን ዶላር ኪሣራ እንዳደረሰ ተገምቷል ።**

ከሁሉም በላይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ አገጠ በመምጣቱ እጅግ አሳሳቢ የሆነው በኋ
ላቀር አገሮች ውስጥ ያለው የምግብ እጥረት ሁኔታ ነው ። የምግብ እጥረትን በሚ
መለከት በተለይ የአፍሪካ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል ። የአፍሪካ ኢኮኖሚ
ኮሚሽን ባጠናቀረው ዘገባ መሠረት በ1981 የአፍሪካ አህጉር የምግብ ምርት ያሳየው
ዕድገት 3% ሲሆን፣ ይህም በዚሁ ዓመት አህጉሩ ካስመዘገበው 2·9% የሕዝብ ብዛት
የዕድገት መጣኔ እምብዛም ከፍ የሚል አይደለም ። በተለይ የእርሻ ምርትን የወሰድን
እንደሆነ ደግሞ ሁኔታው ከዚህም የከፋ ነው ። በ1970 ዎቹ ዓመታት የአፍሪካ አህጉር
የእርሻ ምርት ያስመዘገበው ዓመታዊ ዕድገት 1·4% ብቻ ሲሆን፣ ይህም በዚሁ ጊዜ
ውስጥ የሕዝብ ብዛት ከሚያድግበት መጣኔ ከግማሽ በታች መሆኑ ነው ። በአህጉሩ
ውስጥ ለእርሻ ምቹ ከሆነው መሬት ውስጥ 44% ብቻ በመታረስ ላይ ያለና በሥራ
ላይ ከተሰማራው ሕዝብ ከ80% በላይ የሆነው የተሰማራበት መሆኑን ስናገናዝብ፣ በአ
ህጉራችን ውስጥ በአሁኑ ወቀተ ረሃብ፣ ጉስቁልናና ፍጹም ድኅነት ሰፍና መገኘቱ
ግልጽ ይሆናል ። የአፍሪካን ሁኔታ በተለይ ለመጥቀስ የተገደድነው ሁኔታው እጅግ
የከፋና አስቸኳይ የሆነ የጋራ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ለማስገንዘብ ሲሆን፣ በእስ
ያና በላቲን አሜሪካ ያለውም ሁኔታ ቀደም ሲል አፍሪካን በሚመለከት ከተጠቀሰው
እምብዛም የሚለይ አይደለም ።

ከ1980 እስከ ምዕተዓመቱ መገባደጃ ማለትም እስከ 2000 ድረስ ባለው የሐያ ዓመታት
ጊዜ ውስጥ የኋላቀር አገሮች ሕዝብ ብዛት አሁን ካለበት በ1·6 ቢሊዮን ይጨምራል ተብሎ

---

* *Ibid.*, p. 128 & 170.

** *Ibid.*, p. 131.

Digitized by Google

ተገምቷል ። በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለምርት ውጤት ያለው ፍላጐት በ3·4% የሚያድግ ሲሆን፣የምርት መጠን ዕድገት ግን2·6%ብቻ እንደሚያድግ ፣ በተለይ ደግሞ እጅግ በጣም ደሃ በሚባሉት ኋላቀር አገሮች በዚሁ ጊዜ ውስጥ የምርት ዕድገት ከፍላጐት በ25% እንደሚቀንስ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ ። ጥናቶቹ በተጨማሪ እንደሚ ያመለክቱት ያያዝነው ምዕተ ዓመት ሲገባደድ ከአፍሪካ በውጭ ንግድ መልክ ወደ ውጭ የሚላኩ የእርሻ ውጤቶች የሚያስገኙት ገቢ ወደ ውስጥ በገቢ ንግድ መልክ የሚገቡት የእርሻ ምርት ውጤቶች የሚያስወጡትን ወጭ ግማሹን ያህል አይሸፍኑም ።*

በአጠቃላይ በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለው የምግብ ምርት በተለይም የእርሻ ምርት እጥረትና የምርታማነት ማቀልቀል ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ነው ። ይህ ሁኔታ በአብዛ ኞቹ ኋላቀር አገሮች ውስጥ ካለው የለም መሬት መሸርሸር እየተባባሰ መሄድ ፣ የደን ሀብት መመንጠር መጨመር ፣ ከሕዝቡ ብዛት መጨመር አንፃር የእርሻው መሬት ለማካይ መጠን መቀነስ ጋር ሲዳመር ሁኔታውን እጅግ በጣም አሳሳቢ አድርጐታል ።

ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የዘረጋው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ወይም አርጌው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ ባሉ ከ35 በሚበልጡ ዓመታት ቀይታው ለኋላቀር አገሮች ያበረከተው ገጸበረከት ከላይ ባጭሩ ለማሳየት እንደተሞከረው ረሃብን ፣ እርዛትን ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታ ማዛባትንና መናጋትን ፣ የይስሙላ ነፃነትንና አጠቃላይ ቁርቁዝናን ነው ። በኋላቀር አገሮች ላይ የተጣለው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ዓይነተኛ ገጽታ በሆነውና በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በተመሠረተው ፣ የኋላቀር አገሮች ለሚያቀርቡት ማናቸውም የንግድ ፣ የፋይና ንስና የቴክኒዎሎጅ እንዲሁም ሌሎች የግንኙነት ጥያቄዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ባለው አርጌው የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ክልል ሊፈታ አልቻለም ፤ የሚችልም አይ ደለም ።

ይኸም በመሆኑ ለብዙ ጊዜ ታምቆ ሲብለሰል የቀየው የኋላቀር አገሮች ችግርና ብሶት በ1974 በተሰበሰበው ስድስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ ባስተላለፉቸው ውሳኔዎች ቁጥር 3201 እና 3202 ለማካይነት አዲስ ዓለምአቀፍ የኢ ኮኖሚ ሥርዓት ሊመሠረት የሚችልበት መግለጫና (Declaration) የድርጊት ፕሮግራም ተነደፈ ። በዚሁ ዓመት የተሰበሰበው 29ኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የመንግሥታትን የኢኮኖሚ መብቶችና ግዴታዎች ቻርተር አጸደቀ ። ከዚያም በኋላ የ30ኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤዎና ዋና ውሳኔዎች ፣ በ1976 በናይሮቢ የተካሄደው የንግድና የልማት ድርጅት (UNCTAD) አራተኛ ጉባኤ፣ እንዲሁም በ1976 በኮሎምቦ የተካሄደው አምስተኛው የገለልተኛ መንግሥታት ጉባኤ ውሳኔዎች በዚሁ በአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት ላይ ያተኮሩ ነበሩ ።

አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚመለከት የተላለፉት ውሳኔዎች ብዙና ዝርዝር ነገሮችን ያዘሉ ቢሆንም፣የጥያቄው አስኳል «የዓለምን ሀብት ወይንም ምርት ክፍፍል ፣ የኢኮኖሚ ኃይልን ክፍፍልየሚመለከት ነው» ።** ከዚህም በተጨማሪ የው ሳኔዎቹ ይዘት ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲሁ በገበታዊነት ለሚሠሩ የገ በያ ኃይሎች መለቀቅ ያለበት ሳይሆን ፣ በዓለምአቀፍ ደረጃ ሥርዓት ባለው የመንግ ሥታት ግንኙነት መመራት እንዳለበት ይጠቁማል ።

---

* *Ibid., p.* 119.

** *Development and peace, Ibid., p.* 28.

Digitized by Google

የአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የድርጊት ፕሮግራም በመንግሥታት መካከል መኖር የሚገባውን የኢኮኖሚ ግንኙነት በሚመለከት ሦስት ዘርፎችን ያዘለ ነው ። እነሱም፣ 1/ በአሁኑ ወቅት በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላ ቀር አገሮች መካከል ያለው የንግድ ፣ የገንዘብና ፣ የፋይናንስ ግንኙነት የተዛባና የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችን ጥቅም ብቻ የሚያስከብር በመሆኑ ይኸን ሁኔታ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን፤

2/ የኋላቀር አገሮችን የኢኮኖሚ ዕድገት ያፋጥናል ተብሉ ሲሰጥ የቆየው «እርዳታ» የእነዚህን አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን ቀርቶ ጨርሶ በመገታቱ እርዳታ በእርግጥ ለኢኮኖሚ ዕድገት ሊውል የሚችልበትን መንገድ መቀየስ ማስፈለጉ ፤

3/ ነፃ መንግሥታት ያለምንም ተፅዕና በክልላቸው ሥር ያለውን ማናቸውንም የተፈጥሮ ሀብት ለራሳቸው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት በሚያመች መንገድ ሊጠቀሙበት የመቻል መብታቸው እንዲታወቅና በድንበር ዘለል ኩባንያዎች እንቅስቃሴ ላይ ተገቢ ቁጥጥር የማድረግ መብታቸው እንዲረጋገጥ የሚጠቁሙ ናቸው።*

አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚመለከት በብዙ የዓለምአቀፍ ጉባኤዎች ላይ የተላለፉ ውሳኔዎችና ከዚህም ለንፃር ሲካሄድ የቆየው ትግል የኢኮኖሚ ገጽታ ሲጠቃለል ለሁን ያለው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ ኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸውን ለዕድገት አመች በሆነ መንገድ በአዲስ ለማዋቀርና ለስቸኳይ መፍትሔ የሚሹ የረሃብ የድኅነትና ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት አመች ሆና ባለመገኘቱ ፣ ይህን ለጠቃላይ ሁኔታ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። ከዚህ ለንፃር ኋላቀር አገሮች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ሁሉ ትክክልና የሚደገፉም ናቸው ።

ይሁንና ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚካሄደው ትግል የኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ገጽታም ያለው ነው ። በመሠረቱ ለማርክሲስቶች ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት በኋላቀር አገሮች ለማካይነት የሚካሄደው ትግል የተጨቆኑ ሕዝቦች ለአርነት ፣ አገሮች ለዕውነተኛ ነፃነት በሚያካሂዱት የትግል ሂደት ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ነው ። የዚህም አዲስ ምዕራፍ ዓይነተኛ ጠባይ ኋላቀር አገሮች ያገኙት ወይም ያላቸው የፖለቲካ ነፃነት በቂ አለመሆኑን በመገንዘብ አሁን የያዙትን የይስሙላ የፖለቲካ ነፃነት ወደ ዕውነተኛ ነፃነት ለመለወጥ የኢኮኖሚ ነፃነት ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ለመገንዘብ የቻሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ነው ። ይህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊዝም በዓለም ላይ ዘርግቶት የሚገኘውን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በከፍተኛ ቀውስ ላይ የጣለና ከፍተኛ ስጋትም ያሳደረበት ነው ።

ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ፣ ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የሚታገሉ ኋላቀር አገሮች ሁሉ፣ በተለይም ከትግሉ የፖለቲካ ገጽታ አንፃር (በኢኮኖሚ ገጽታው ላይ ሁሉም የሚስማሙ ሲሆኑ) አንድ ዓይነት አመለካከት አላቸው ለማለት አይቻልም፤ ሊኖራቸውም አይችልም ። እንደሚታወቀው በአሁኑ ጊዜ ተወደደም ተጠላም ዓለም በሁለት ታላላቅ ሶሺዮ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች መከፈሏ ተጨባጭ እውነታ ነው ። በኋላቀር አገሮችም መካከል ቢሆን በአንድ በኩል (ጥቂትም ቢሆኑ)

* Eastern Europe and the New International Economic Order, (New York: Pergamon Press, 1980), p. 3.

Digitized by Google

የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመምረጥ ረዥም የሆነውን ጉዞ የተያያዙና በሌላ በኩል ደግሞ የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ላይ የሚገኙ አገሮች መኖራቸው እንዲሁ ተጨባጭ እውነታ ነው። በኋላቀር አገሮች መካከል ሁለት የተለያዩ የፖለቲካ አዝማሚያዎች መኖራቸውም፣ እነዚህ አገሮች ባንድ ላይ ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የሚያካሂዱት ትግል ከፖለቲካ ገጽታው አንፃር የተለየየ እንዲሆን አድርጉታል።

የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሀቀኝነት የሚከተሉ አገሮች በኢኮኖሚና በፖለቲካ ትግል መካከል ካለው ዲያሊክቲካዊ ግንኙነት በመነሳት፣ ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የተጀመረውና በመካሄድ ላይ ያለው ዓለምአቀፍ ትግል ኢምፔሪያሊዝም በዘረጋው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ላይ በመታለም ከፖለቲካ ትግል ጋር እንዲቀናጅ ይሻሉ። ዓለምአቀፋዊ የኢኮኖሚ ግንኙነትን በዲሞክራሲያዊ መሠረት ላይ ለማቀቀር የሚካሄደው ትግል ግቡን ሊመታ የሚችለው ኋላቀር አገሮች በፀረ—ኢምፔሪያሊስት የአንድነት ግንባር ሥር ሲሰለፉና በዚህም ዓይነት ግንባር ሥር ትግላቸውን እስከመጨረሻው ድረስ ሲገፉበት ነው ብለው ያምናሉ።

በአጠቃላይ «ፖለቲካ የኢኮኖሚ የተካተተ ነፀብራቅ ነው» ከሚለው ሌኒናዊ አባባል በመነሳት የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓትን ዲሞክራሲያዊና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ለማድረግ፣ በኋላቀር አገሮች አካማካይነት የሚካሄደው የኢኮኖሚ ትግል የሁሉም ኋላቀር አገሮችን ጥቅም የሚመለከት እንደመሆኑ (ከዚህ አንፃር መላ ኋላቀር አገሮችን የሚያካትተው የአንድነት ግንባር ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ ቢሆንም) ሊሳካ የሚችለው ከዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚደረግ የኢኮኖሚ ድርድር ብቻ ሳይሆን፣ በፖለቲካ ትግል ጭምር መሆኑን ያምናሉ። ኋላቀር አገሮች ኋላቀር ሊሆኑ የቻሉት ዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ሥርዓት ቀደም ሲል በዘረጋው የቅኝ አገዛዝ ቀንበር፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ቀንበር ሥር በመውደቃቸው ስለሆነ፣ ከኋላቀርነት ለመላቀቅ የሚቻለው ከዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ሥርዓትና ይኸም ሥርዓት ከዘረጋው ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል ውጭ በመሆን ነው ብለው ያምናሉ። በአንፃሩ የካፒታሊስቱን የዕድገት ፈለግ የተቀበሉና በብሔራዊ ኢኮኖሚያቸውም ውስጥ የካፒታሊስቱ ይዞታ የበላይነትን ይዞ የሚገኝባቸው ኋላቀር አገሮች ደግሞ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል ያለው የሰፋ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ልዩነት በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነት ክልል፣ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል የንግድን፣ የፋይናንስን፣ የዕርዳታንና የቴክኒዎሎጅ ሥርጭትን በሚመለከት የሚካሄደው ውድድር በሚያስገኘው «ስምምነት» እየተጣበበ ሊመጣ ይችላል ብለው ያምናሉ። በአጭሩ የአዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚመለከት ይኸን ዓይነት አመለካከት የሚያራምዱት አገሮች ለውጡ በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ሥርዓት ክልል፣ በዚህም ክልል ውስጥ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሊከናወን እንደሚችል ይገምታሉ።

ይህ ዓይነት አመለካከት በኋላቀር አገሮች ውስጥ እንዲስፋፋ ከሚገፋፉ የቡርዧው መደብ አፈቀላጤዎች መካከል «የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ፖለቲካ» በሚል ርእስ በቅርቡ መጽሐፍ ጽፎ ያወጣው የአሜሪካው የኢኮኖሚ ተመራማሪ ስይ· ስፒር ይገኝበታል። አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሊመሠረት የሚችለው በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ግንኙነት ክልል፣ በዋና ዋናዎቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮች (አሜሪካ፣ ምዕራብ ጀርመን፣ ፈረንሣይ፣ እንግሊዝና ጃፓን) «የፖለቲካ መሪነት» ለማ

Digitized by Google

ካይነት ለዘጋሚ በሆነ መንገድ እንደሆነ ይኸው የቡርዧ መደብ አፈቀላጤ ሊያሳ ምን ይፈልጋል ።

በሌላ በኩል ይኸንኑ ጉዳይ አስመልክቶ በኋላቀር አገሮች የንዑስ ከበርቴውን የፖለቲካ መስመር በሚያራምዱት አካባቢ የሚሰነዘር ሌላ የተሳሳተ አስተያየት አለ ። ይኸም በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ልዩነት በማስተካከል አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት ወሳኙ ሁኔታ የዓለምአቀፍ ግንኙነትን መለወጥ ነው ከሚል መነሻ ተነስቶ ፥ ኋላቀር አገሮች ኢኮኖሚያቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉት ከተሻሻለ የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት በሚመነጭ የውጭ ዕርዳታ ብቻ ነው ወደሚል መደምደሚያ የደረሰ አስተያየት ነው ።

በመሠረቱ ማናቸውም ማኅበራዊም ሆነ የተፈጥሮ ክስተት ለውጥ ወይም ዕድገትን ሊያሳይ የሚችለው በዚያ ክስተት ውስጥ ባለ ውስጣዊ ቅራኔ ፍጭትና ከፍጭቱም በሚመነጨው ኀይል ሲሆን ፡ ከዚያ ክስተት ውጭ ያለ ነገር ያ ክስተት ለሚያሳየው ለውጥ ወይም ዕድገት ያጋዥነት (ማለትም ለውጥን ፡ ዕድገትን የማፋጠን ወይም የማዘገም) ሚና ይጫወታል እንጂ ፡ ለውጥንና ዕድገትን የመወሰን ኃይል አይኖረውም ። ይኸ አባባል ሁለንታዊ እንደመሆኑ የማናቸውንም አገር የኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ በአገሮች መካከል ያለ የኢኮኖሚ ግንኙነትን ይመለከታል ።

ከዚህ ሳይንሳዊ አባባል ስንነሳ ቀደም ሲል የተጠቀሰው ንዑስ ከበርቴያዊ አስተያየት አንዳንድ ዋና ዋና ድክመቶችን ለዝሎ እናገኘዋለን ። እነሱም ፡

—ዓለምአቀፍ ግንኙነት ቸርነት የተሞላበት የበጐ አድራጐት ሥርዓት ሳይሆን ፡ እንደማናቸውም ማኅበራዊ ክስተት የቅራኔዎችን ትግል ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያቀፈ መሆኑን ባለመገንዘብ ፡ የዓለምአቀፍ ግንኙነትን በዓለምአቀፍ መገባባት (Solidarity) መልክ — ማለትም ጠንካራ አገሮች ደካማ አገሮችን መርዳት ያስፈልጋል የሚል — የሥነምግባር ጥያቄ በማንሳት ይለወጣል ብሎ መጠበቁ ፡

—ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የሚካሄደው ትግል በዓለምአቀፍ ደረጃ ብቻ እንጂ ከእያንዳንዱ ኋላቀር አገር ውስጣዊ ሁኔታ ጋር ፡ ማለትም በእያንዳንዱ ሀገር ውስጥ መከናወን ካለበት ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ለውጥ ጋር መቀናጀት እንደሚገባው ያለመገንዘቡ ወይም ለመገንዘብ ያለመፈለጉ ፡

—የኢኮኖሚ ዕድገትን በሚመለከት የውጭ ዕርዳታ እንደ አጋዥ እንጂ ዋንኛና ወሳኝ እንደሆነ ተደርጐ ሊወሰድ እንደማይገባ ያለመገንዘቡ ፡

—<u>የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረታዊ ጥያቄ ለልማት የሚውል የፋይናንስ ክምችትን የማሰባሰብ ጥያቄ መሆኑን</u> ባይክድም ፡ በተቻለ መጠን የኢኮኖሚ ምርታማነትን በማሳደግ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ለተስፋፋ ዕርባታ ሊጠመድ ከሚችለው በተጨማሪ ፡ ይኸ ክምችት ከመንግሥት መደበኛ በጀት ውስጥ በተቻለ መጠን ኢ—ምርታዊ የሆነው ፍጆታ ሊቀነስ የሚችልበትን ፡ ለልማት የሚውለው ወጭ ሊዳብር የሚችልበትን ሁኔታ ከመፍጠር የሚገኝ መሆኑን ያለመቀበሉ ናቸው ።

Digitized by Google

በአንፃሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ዲሞክራሲያዊና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ለማድረግ፣በእያንዳንዱ ኋላቀር አገር ውስጥ ኋላቀር የሆኑ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ግንኙነቶችን ዲሞክራሲያዊና የብዙኃኑን ሠራተኛ ሕዝብ ጥቅም የሚያስከብሩ እንዲሆኑ ለማድረግ ከሚካሄድ ትግል ጋር ሊቀናጅ ይገባል ። ይህንኑ ጉዳይ በማስመልከት ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እ.ኤ.አ. በሚያዝያ ወር 1974 አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው የሁለተኛው ዓለምአቀፍ«የባለ ብዙ ብሔር ኩባንያዎች ሚናና የልማት ስትራቴጂ» ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር ላይ ሲገልጹ ፣ «. . . የየሀገሮቻችን የኢኮኖሚ ልማት የሕዝቦቻችንን ጥቅም በሚጠብቅ ዘዴ ለማራመድ ከተፈለገ መሠረታዊና ሥር ነቀል የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ለውጥ ማድረግ አማራጭ የሌለው ነው ። ካለበለዚያ ማንኛውም ጥረት እየተናደ በሚሄድ የአሸዋ መሠረት ላይ ድንጋይ እንደመካብ ያህል የሚቆጠር ነው ፤» ብለው ነበር ።

በአጭሩ አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚመለከት የተነሳው ጥያቄ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሲይሆን ፖለቲካዊም ነው ፤ ሊሆንም ይገባል ። ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት የኋላቀር አገሮችን ዕድገት አፍና የያዘው የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ሥርዓት ተፅዕናው የሚከሰተው በኢኮኖሚው መስክ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ፣ በባህልና በአጠቃላይ በመላ የማኅበራዊ ግንኙነቶች መስክ በመሆኑ ነው ። በመሆኑም አዲስ የሆነ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት የሚካሄደው ትግል በብሔራዊ ደረጃ እኩልነት የሰፈነበት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለመመሥረት ከሚደረገ ትግል፣ በዓለምአቀፍ ደረጃም የሁሉንም አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት በመጉተት ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው የጦር መሣሪያ እሽቅድምድምና የጦርነት ዝግጅትን በጥብቅ ከመቃወም ፣ ለሰላምና ለማኅበራዊ ዕድገት ከመታገል ተገንጥሎ ሊታይ አይችልም ፤ ሊታይም አይገባውም ።

በአጭሩ ለአዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚካሄደው ትግል ትክክለኛ አቀጣጫ ሊይዝ የሚችለው ኢኮኖሚን ከፖለቲካ ጋር በማዋሃድ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት አቋሙ እየተጠናከረ የሄደ እንደሆነ ብቻ ነው ። ይህ እንዳይሆን ደግሞ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም ። ለምሳሌ በኅዳር ወር 1981 በሜክሲኮ አገር በካንኩም ከተማ በተካሄደው የዓለምአቀፍ ኅብረትና ዕድገት ስብሰባ ላይ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በሬጋን አማካይነት ኋላቀር አገሮች የሚከተሉትን አምስት ገደታዎች መቀበል እንደሚያስፈልጋቸው በግልፅ አስታውቀ ነበር ። እነሱም ፤ የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነትን በሚመለከት ኋላቀር አገሮች ጥያቄአቸውን ለተባበሩት መንግሥታት ሳይሆን እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደ ዓለም ባንክና ለመሳሰሉት የማቀረብ ፣ ለግል ኢንቬስትመንትና ለድንበር ዘለል ኩባንያዎች በራቸውን መክፈት ፣ የአገር ውስጥ ገበያቸውን ልቅ በማድረግ ለነፃ ንግድ እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ መፍጠር ፣ «የፖለቲካ ሁኔታውን» ለጠረጴዛ ዙሪያ ድርድር የተስማማ እንዲሆን ማድረግ ፣ የአሜሪካ መንግሥት እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ገደታዎች አላሟሉም ብሎ ሲያምን ፣ አላሟሉም በሚላቸው ኋላቀር አገሮች ላይ የመሰለውን ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ቢወስድ መስማማት አለባቸው የሚሉ ናቸው ። ይህ እንግዲህ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በአዲሱ ኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ ያለውን ግልጽ የሆነ የተፃራሪነት አቋም የሚያመለክት ነው ።

Digitized by Google

ለአዲሱ ዓለምአቀፍ ኢኮኖሚ ሥርዓት የሚካሄደው ትግል ትክክለኛ ለቀጣ
ውን ከያዘ የኢምፔሪያሊዝም ሕልውና እራሱ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ስለሚገነዘቡ፣
ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተቻላቸው ሁሉ በዚህ ጥያቄ ላይ የኋላቀር አገሮች አንድ
ነት እየተጠናከረ እንዳይሄድ እርስ በርሳቸው እንዲከፋፈሉ ለማድረግ ከፍተኛ ደባ ይፈ
ጽማሉ ። ይህ ደባቸው በሁለት ገጽታው ይከሰታል ። አንደኛው ፣ ይህ ጥያቄ ያደ
ረሰውን ከፍተኛ ግፊት ለማስታገስ ኋላቀር አገሮች የሚያቀርቡት የኢኮኖሚ ጥያቄ
በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ግንኙነት ክልል ውስጥ በድርድር መፍትሔ ሊያገኝ ይቻ
ላል የሚል ነው ። ለዚህም ድርድር የሚመርጧቸው ሸንጎዎች፣ ሬጋንም በግልጽ እን
ዳስቀመጠው፣ ኋላቀር አገሮች የድምጽ ብልጫ የሚያገኙበትን፣ ሲጀመርም ጥያቄው
የተነሳበትን የተባበሩት መንግሥታትን ሸንጐ ሳይሆን ፣ እነሱ ሊቆጣጠሩአቸው በሚ
ችሏቸው የተለያዩ ተቋሞች (Specialized Agencies) ለምሳሌም እንደ ዓለምአቀፍ
የገንዘብ ድርጅት (IMF)፣ ዓለም ባንክና ወዘተ ... ያሉትን ነው ። በዚህም መሠረት የተ
ወሰኑ ጥሬ ዕቃ የሚያመርቱ ኃላቀር አገሮች ጥሬ ዕቃውን ከሚገዙ የተወሰኑ የዳበሩ
ካፒታሊስት አገሮች ጋር በተናጠል ወይም በቡድን ድርድር እንዲያካሂዱ ይገፋፋሉ ።
በአጠቃላይም ኋላቀር አገሮች ያለባቸውን የከፋ የኢኮኖሚ ችግር በመጠቀም ኢምፔ
ሪያሊስት አገሮች ጠቀለል ብለው በቀረቡ የኢኮኖሚ ዕቅዶች (Economic Packages)
ስም የራሳቸውን ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊና ርዕዮተዓለማዊ ተፅዕና ሊጭኑባቸው ይሞ
ክራሉ ።

ሁለተኛው ደግሞ የሶሻሊስት አገሮች ለኋላቀር አገሮች መበዝበዝ ምክንያት እን
ደሆኑ በማስመሰል ካፒታሊስትና ሶሻያሊስት አገሮችን ሳይለይ ፣ ድርድሩ በአንድ
በኩል «ሰሜን» በሚል አጠራር በተጠቃለሉ፣ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ካፒታሊስትም
ሆነ ሶሻሊስት አገሮች፣በሌላ በኩል ደግሞ «ደቡብ» በሚል መጠሪያ በተጠቃለሉ ኋላ
ቀር አገሮች መካከል እንዲካሄድ የሚደረገው ጥረት ነው ። ይኸም ደባ በኋላቀር አገ
ሮችና በሶሻሊስት አገሮች መካከል ያለውን ታሪካዊ የትግል አንድነት ለማናጋት እን
ደሆነ ግልጽ ነው ። ኋላቀር አገሮች ይኸን የኢምፔሪያሊስቶችን ደባ ማጋለጥ መቻል
አለባቸው ።

አዲሱን ዓለምአቀፍ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት የሚያካሄዱት ትግል ሊሳካ
የሚችለው ኋላቀር አገሮች ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያጠናከሩ እን
ደሆነ ብቻ ነው ። ይህን ሁኔታ በማስመልከት ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማር
ያም ቀደም ሲል በተጠቀሰው «የባለ ብዙ ብሔር ኩባንያዎች ሚናና የልማት እስት
ራቴጂ» ጉባኤ ወቀት ባሰሙት ንግግር ላይ ፣

«...በካፒታሊስቱ ዓለም መካከል ባለው ቀራኔ እየታገዙ፣ ከሶሻሊስቱ ዓለም
ጋር ያለውን ግንኙነት ማጥበቅ ለታዳጊ አገሮች ዕድገት ጠቃሚ መሆኑ የታመነ
ነው ።... የበለጸጉ አገሮች በየደረጃው በሚፈጠሩት መሰናክል ዕውን የመ
ሆን ዕድሉ እየራቀ የሄደው አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓትም
በተግባር እንዲገለጽ በጋራ መታገል ... » እንደሚያሻ አስገንዝበው
ነበር ። በቅርቡ በሕንድ የተካሄደውና ከሞላ ጐደል አብዛኞቹ ኋላቀር አገ
ሮች የታቀፉበት ሰባተኛው የገለልተኛ መንግሥታት ጉባኤ ፣ ማናቸውንም
የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ብዝበዛና ተፅዕና በመቃወም ለፖለ
ቲካና ለኢኮኖሚ ነፃነት ትግል ማድረግ ማስፈለጉን በሚመለከት ያስተላለፉቸው ውሳ

Digitized by Google

ኔዎች አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት በመካሄድ ላይ ላለው ትግል ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው ።

በመጨረሻም ፣ አብዮታዊት ኢትዮጵያ የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመከተል ሥር ነቀል የሆነ አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ ለውጥ በማካሄድ ላይ የምትገኝ አገር እንደመሆኗ ፣ የኢትዮጵያ አብዮትም የዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴ አካል እንደመሆኑ፣ በሰኔ ወር 1976 በበርሊን ከተማ የተካሄደው የአውሮፓ የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ አዲሱን ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት በሚመለከት፣ «ከኢምፔሪያሊዝምና ከእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ነፃ የሆነ ዓለምአቀፍዊ ግንኙነት በመመሥረት በዳበሩና በታዳጊ አገሮች መካከል ያለውን የዕድገት ልዩነት ለማስተካከል፣ የእያንዳንዱን አገር የተሟላ ነፃነት ለማረጋገጥና የሰውን ልጅ ችግሮች ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው ለማስቻል ፣ የዓለምአቀፍ ግንኙነትን ዲሞክራሲያዊ ማድረግና የዓለምአቀፍ ትብብርም በሁሉም ሕዝቦች እኩልነትና የጋራ ጥቅም ላይ እንዲመሠረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው ።»* የሚለው በስብሰባው ሰነድ ውስጥ የሰፈረው መግለጫ ፣ የኢትዮጵያን አብዮት በማዕከልነት የሚመራው የኢሠፓአኮ አቋም መሆኑንም መግለጽ ተገቢ ይሆናል ።

---

* For Peace, Security, Cooperation and Social Progress in Europe, London, 1979, p. 19.

እ ር ም ት

ባለፈው « መስከረም» መጽሔት (ልዩ እትም) ቅጽ 3 ቁጥር 13 ፣

1. ገጽ 27 ፣ 2ኛ ዓምድ ፣ አንቀጽ 2 ፣ 12ኛ መስመር ላይ ማርክስ የሞተበት ዕለት መጋቢት 5 ቀን የተባለው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ስለሆነ ዓመተ ምሕረቱ 1883 ሳይሆን 1875 ተብሎ ይነበብ ።
2. ገጽ 71 ፣ 1ኛ ዓምድ ፣ አንቀጽ 2 ፣ 6ኛ መስመር ላይ « እጅግ በጣም ያነሰ » የሚለው « እጅግ በጣም የበዛ » ተብሎ ይነበብ ።
3. ገጽ 73 ፣ 1ኛ ዓምድ ፣ አንቀጽ 1 ፣ 13ኛ መስመር ላይ « ደህንነት » የሚለው «ድህነት» ተብሎ ይነበብ ።

Digitized by Google

የሶሻሊስት የእድገት ፈለግና ችግሮቹ

ዶ/ር ታረቀኝ አዴቦ

የጽንሰ ሃሣቡ አመጣጥ ፣ ይዘትና ትርጉሙ

ማርክስና ኤንግልስ ባካሔዱት ሰፊና ጥልቅ የኅብረተሰብ ዕድገት ታሪክ ጥናትና ምርምር ሶሲዮ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች እንደሚወራረሱና አሮጌው በአዲስ ዝቅተኛው በከፍተኛው የሚተካበትን ሒደት የሚገዙትን ሕግጋት ይፋ አውጥተዋል ። በዚህም ፊውዳሊዝም ወድቆ በካፒታሊዝም እንደተተካ ሁሉ የካፒታሊዝም መውደቅና በሥፍራው የሶሻሊዝም መተካት የማይቀር የታሪክ ሕግ መሆኑን አስረድተዋል ። የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች በግል ንብረት ፣ በብዝበዛና በጭቆና ላይ የተመሠረተውን የካፒታሊስት ሥርዓት ደምስሶ አዲሱን ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን የሶሻሊስት ኅብረተሰብ መገንባት የወዝአደሩ ታሪካዊ ተልዕኮ መሆኑን በቀመሩት ሳይንስ አረጋግጠዋል ።

የሶሻሊስት አብዮት እውን መሆንና ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ የወዝአደሩ መደብና በሳይንሳዊው ርዕዮተ ዓለም የታጠቀው ፓርቲው ሚና ወሳኝነት ያላቸው መሆኑንና ፣ እንዲሁም የሠራተኛውና የገበሬው የትግል አንድነትና አጋርነት አስፈላጊነትን ማርክስና ኤንግልስ በሳይንሳዊ ጥናታቸውና በትንተናቸው በተደጋጋሚ አስገንዝበዋል ።

ማርክስና ኤንግልስ ያመለከቱት የታሪክ የዕድገት አቅጣጫ ትክክለኛነት በታላቁ የሩሲያ የሶሻሊስት አብዮት በጉልህ በማያጠራጥር አኳኋን ተረጋግጧል ። ታላቁ ሌኒን ሳይንሳዊ ኰምኒዝምን በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ተግባራዊ በሚሆንበት ሁኔታ አዳብሮ ለጭቁንና ምዝብር ሕዝቦች በመማሪያነት በማቅረብና በሩሲያ የወዝአደሩንና ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ከፓሪስ ኮሙን ለጥቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሥልጣን በማብቃት ማርክሲዝምን ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ሊያሸጋግረው በቅቷል ። የጥቅምቱ አብዮት በዋና ይዘቱ ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም የመሸጋገሪያ ዘመን የሆነ

Digitized by Google

አዲስ ዓይነት የታሪክ ምዕራፍ ከፍቷል ። የዚህን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መከፈት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት የዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት መመሥረት ፣ እንዲሁም በቅኝ ግዛትና በከፊል ቅኝ ግዛት አገሮች የአርነት ንቅናቄዎች ድል መጐናጸፍ የበለጠ ግልጽና ጉልህ አድርጐታል ።

በመሠረቱ ለሶሻሊስት ግንባታ አስፈላጊ ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች መሟላት ያለባቸው በካፒታሊዝም ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ ባለንበት ምዕተ ዓመት በግልጽ እንደታየው ከካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ገና ያልደረሱና በአመዛኙ ቅድመ ካፒታሊስት ማኅበራዊ ግንኙነቶች በሚታዩባቸው አገሮች ጭምር ወደሶሻሊስት ሥርዓት ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ ተረጋግጧል ። ለዚህ ክስተት ዋናው ምክንያት የሶሻሊዝምና በአንድ በኋላም በብዙ አገሮች ማሸነፉና የኋላቀር አገሮች የአርነት እንቅስቃሴም አሸናፊ ከሆነው የሶሻሊት አብዮት ግጣመሩ ነው ።

በታዳጊ አገሮች በአጠቃላይ የምርት ኃይሎች ኋላቀር የመሆናቸውን ያህል የመደቦች ማኅበራዊ ክፍፍልና ትራኔም ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ጭቆና ይበልጥ ተጠናክሮ የሚገኘው በእነዚህ አገሮች ነው ። የታዳጊ አገሮች ሕዝቦች ከወደቁበት የረሃብና የጉስቁልና አስከፊ አዘቅት ውስጥ በመውጣት ብሔራዊ ልዕልናቸውን ለመጐናጸፍና የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚችሉት የካፒታሊስታዊውን የዕድገት ጐዳና በመከተል ሳይሆን ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ሂደት ነው የሚል ንድፈ ሐሳብ ቀርቧል ። ይህም ንድፈ ሐሳብ ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ጐዳና ወይም የዚሁ ተመሳሳይ የሆነው ሶሻሊስታዊ የዕድገት ፈለግ (Socialist Orientation) የሚባለው ነው ። ንድፈ ሐሳቡ በሰፊው ውይይት የተደረገበት በ1960 (እ· ኤ· አ·) በሞስኮ በተደረገ የዓለም አቀፍ የኮሚኒስቶችና የሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ሲሆን የግሌ የማኅበራዊ ሳይንስ ሊቃውንትም በሰፊው አጢነውታል ። ከዚህ አንፃር ለብዙ ከቅኝ አገዛዝ ገና ባልተላቀቁ አገሮች የሶሻሊስት የዕድገት ጐዳናና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን ማጽጸም የወቅቱ አብዮታዊ ሂደት የሚጠይቀው ተግባር ሆኖ ቀርቧል ።[1] ስለሆነም የሽግግሩን ወቅት ባሕርያት በትክክል ለመረዳት ሁለቱንም ጽንሰ ሐሳቦች ጠለቅ አድርጐ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል ።

የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ወይም ኢካፒታሊስታዊ ዕድገት የሚባለው ጽንሰ ሐሳብ የሚያመለክተው በኋላ ቀር አገሮች በተለይ «በአፍሪካና በእስያ በቅርብ ጊዜ ነፃ የወጡት አገሮች ወደሶሻሊዝም የሚሸጋገሩበት አጠቃላይ መንገድ ነው» ።[2] ይህ ማለት ገና በአብዛኛው የቅድመ ካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች የሰፈኑባቸው ኅብረተሰቦች ሥርነቀል በሆነ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ አማካይነት ደረጃ በደረጃ ወደ ሶሻሊዝም የሚሸጋገሩበት ጐዳና ነው ማለት ነው ። የዕድገቱ ጐዳና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አካልና «ከቡርዧ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ባሻገር የሚሄድ ነው»።[3] ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ራሱ «በማያጽርጥ ሁሬ ካፒታሊስትና ሶሻሊስት ፈለግ ዝንባሌና ባሕርያት ፣ በመጨረሻም ኢካፒታሊስታዊ በሆነ የሽግግር ወቅት አማካይነት ከቅድመ ካፒታሊስት ማኅበራዊ ግንኙነቶች ወደ ሶሻሊስት ማኅበራዊ ግንኙነት የሚያሸጋግር ነው » ።[4] ይዘቱም አንድ አገር በሚወስዱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርነቀል ለውጦች አማካይነትና ተግባራዊነታቸው በሚያስገኛቸው የወደፊት እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ ወደ ሶሻሊስታዊ ለውጦች የመድረስና ለሶሻሊስታዊ ግንባታም አዲስ መንገድ የመክፈት አዝማሚያ ያለው ነው ። እንዲሁም በሂደቱ ፣ «አብዮታዊ ዲሞክራሲ ደረጃ በደረጃ ወደ ሳንይሳዊ ሶሻሊዝም የሚሸጋገርበት» እንደሆን በዚህ ጉዳይ ምርምር ያካሔዱ ምሁራን ይገልጻሉ ።

Digitized by Google

እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው የሶ
ሻሊስት የዕድገት ፈለግ ወይም ኢ ካፒታ
ሊስትዊ የዕድገት ጉዳና ከሶሺያሊዝም
ግንባታ ጋር አንድ እንዳልሆነ ነው ። የሶ
ሺያሊስት የዕድገት ፈለግ በይዘቱ ቅድመ
ሶሻሊስት የሆነና አብዮታዊ ዲሞክራሲ
ያዊ ለውጥ በሒደት ወደ ሶሻሊዝም የሚ
ያሸጋግርበት ነው ። ለሶሺያሊስት የዕድ
ገት ፈለግ መሳካትም ሕዝባዊ አብዮት
ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው ። [5]

የሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግ ጽንሰሐሳ
ብን በሚመለከት ፥ ከማርክስ ፥ ኤንግል ስና
ሌኒን እንዲሁም ከኮሚንተርን ጊዜ ጀምር
ድል ባደረጉ የወዝአደር- አብዮተኞች በመ
ረዳት የኋላቀር አገር በካፒታሊስት ሥር
ዓት ዕድገት ውስጥ ሳያልፉ በሶሻሊስት የዕ
ድገት ፈለግ አማካይነት ወደ ሶሻሊዝም ሊሸ
ጋገሩ ይችላሉ የሚለውን ትንታኔ ይዘት
ከዚህ ቀጥሎ ለማጤን እንሞክራለን ።

ንድፈ ሐሳባዊ መንደርደሪያዎች

በአጠቃላይ ሶሻሊዝም ካፒታሊዝምን
የሚተካ ሥርዓት ነው ። ይህም ሥርዓት በካ
ፒታሊዝም ውስጥ የተፈራውን ሀብትና የም
ርታማነት ችሎታ ከበዝባዦች እጅ ነጥቆ
ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም ማዋልን ያጠ
ቃልላል ። ሆኖም ይህ ሀቅ እያንዳንዱ ኅብ
ረተሰብ ወደ ሶሻሊስት ሥርዓት ለመሸጋገር
በካፒታሊስት የዕድገት ውስጥ ማለፍን ግዴ
ታ እያደርገውም ። እያንዳንዱ አካባቢም
በታሪክ የታወቁ ሥርዓተ ማኅበሮችን በሙሉ
ማለፍ አይኖርበትም ። በተለያዩ ታሪካዊ
ምክንያቶች አንዳንዱ ሥርዓተ ማኅበር በአ
ንዳንድ አካባቢ ሊታለፍ እንደሚችል ወይ
ንም ሊያጥር እንደሚችል ማርክሳዊ ትን
ተና ያስረዳል ። ለምሳሌ በአንዳንድ አካባ
ቢዎች የባሪያና የዳበረ ፊውዳል ሥርዓተ
ማኅበሮች አልተከሰቱም ። በተለይ ዛሬ የካ
ፒታሊዝም ቀውስና ሶሻሊዝም ዓለም አቀ
ፋዊ ሥርዓት ሆኖ መነሳት ፤ በብዝበዛ ላይ
የተመሠረተው ካፒታሊዝም በኋላቀር አካ
ባቢዎች ገና በጨቅላነቱ እንዲቀጭና እንዲ
ታለፍ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

በአንድ አገር ሆነ በተለያዩ አካባቢዎች
የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች በአንድ ጊዜ
ሊኖሩ እንደሚችሉና አንዱ በሌላው ተፅ
ዕኖ እንደሚያደርግም ግልጽ ነው ። በዚህ
አንፃር ማርክስና ኤንግልስ በ19ነኛው ምዕተ
ዓመት አጋማሽ ሲጽፉ የሚከተለውን ጠቁ
መዋል ። የሶሻሊስት አብዮት በአውሮፓ
ሲያሸንፍ «በተቀሩት የዓለም ክፍሎችም
በሙሉ ከፍ ያለ ተጽዕኖ ያደርጋል ፤ እስከ
ዚያ ያለውን የዕድገታቸውን ሁኔታም ጨ
ርሶ ይለውጠዋል ፤በጣምም ያፋጥነዋል »።[6]
ይህ አነጋገር በማንኛውም የዕድገት ደረጃ
ያሉትን ኅብረተሰቦች ይመለከታል ። «ጨ
ርሶ ይለውጠዋል» የሚለው እስከ ሶሻሊስት
የዕድገት ደረጃ ያለውንም ሂደት ማጠቃለሉ
አያጠራጥርም ።

ማርክስና ኤንግልስ ገበሬ በመደብ ጨቋ
ኞቹ ላይ በመነሳት ለመብቱ በመጣሪያ ሊጋ
ፈጥ የሚችል አብዮታዊ ኃይል መሆኑን [7]
ካለፈው ታሪክና በዘመናቸው ካዩአቸው
ትግሎችም በመጥቀስ ትንተና አድርገዋል።
እንዲሁም በቅኝ አገዛዝ ሥር የሚገኙ የኋላ
ቀር አገሮች ሕዝቦችን የተቃውሞ ትግሎ
ችን ዘርዝረዋል ፤ የነዚህ ሕዝቦች ነፃነትና
ዕድገት ከሶሻሊስት አብዮት ጋር የተያያዘ
መሆኑንም አስረድተዋል ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ድል አድራጊው ወዛ
ደር ከፀረ ፍጹማዊ የፊውዳል አገዛዝ ንቅ
ናቄ ጋር የወዛደር አብዮትም «ከገበሬ ጦር
ነት» [8] ጋር መያያዝ እንዳለበት አመልክ
ተዋል ።

ማርክስ የተነተነው የምዕራብ አውሮፓ
የካፒታሊዝም ዕድገት ሂደት በማንኛውም
አገር የማይቀር የታሪክ ግዴታ እንደሆነ ተደ
ርጎ የቀረበው አስተያየት ትክክል አለ
መሆኑን በማስመልከት ማርክስ ሲገልጽ
ይህ ለምዕራብ አውሮፓ የተደረገው ታሪ
ካዊ ትንተና «በየትኛውም ታሪካዊ ሁኔታ
የሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ ማለፍ ያለባቸው

Digitized by Google

የማይቀር አጠቃላይ ጉዞና የሚገልጽ ታሪካዊ ፍልስፍናዊ ንድፈ ሐሳብ »[9] አለመሆኑን አስገንዝበዋል ። እንዲሁም የካፒታሊዝምን መከሰት እና እድገት «ታሪካዊ ግዴታነት» (በሚመለከት የተሰነዘረው አባባል) በግልጽ ለምዕራብ አውሮፓ አገሮች ብቻ የተወሰነ ነው ። [10]

ኢንግልስም የኋላቀር አካባቢዎች ወደ ሶሻሊዝም የሚሸጋገሩበት «አጠር ያለ የዕድገት ሂደት» ሊኖር እንደሚችል አስገንዝበዋል ። በምዕራብ ድል የተጐናጸፉት ወዛደሮች ንቁ ድጋፍና በዚሁ በምዕራቡ አብዮት ጥሩ ምሳሌነት በማሰብ ፥ «አሁን የካፒታሊስት ምርትን በመጀመር ላይ ያሉትና የነገድ ተቋሞች ወይንም የነርሱ ቅርሶች ገና ባልተነኩባቸው አገሮች ፥ እነኝህን የጋርዮሽ ይዘት ቅርሶችንና ከነሱ ጋር የሚጣጣሙትን ጠቃሚ ባህሎች ወደሶሻሊዝም ለመጓዝ የሚወስድባቸውን ጊዜ ለማሳጠር እንደ መሣሪያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ ። በዚህም በአብዛኛው እኛ በአውሮፓ ውስጥ ማለፍ የነበረብንን ስቃይና ትግል ለማስወገድ ይችላሉ» [11] ብሏል ። ይህም አባባል «ለማንኛውም በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላሉ አገሮች ሁሉ» ተፈጻሚነት ያለው ነው።

የ1917 የጥቅምት አብዮት በሩስያ የወዝአደሩ ትግል ድል መጐናጸፍንና ወደ ሶሻሊስት ሥርዓት የመሸጋገርን አዲስ ዘመን ጉህ መቅደድን አበሰረ ። ይህ በቦልሸቪክ ፓርቲ መሪነት የተካሄደው አብዮትና የተመሠረተው የሶሻሊስት ሥርዓት ፥ ለማርክሳዊ ንድፈሐሳብ ትክክለኛነት ሕያው ነፀብራቅና ለአብዮትና ለተፋጠነ የማኅበራዊ ግሥጋሴም ነጥሪ ምሳሌ ሆነ ። በዚህም ለኋላቀር አገሮች አብዮታዊ ሽግግር ዓለም አቀፋዊው ቅድመ ሁኔታ ተመቻቸ ። ኋላቀር አገሮች ሶሻሊዝምን ከመገንባታቸው በፊት በካፒታሊስት የዕድገት ሂደት ውስጥ ማለፍ የግድ አስፈላጊ ስለመሆኑ ለሚቀርቡለት ጥያቄ የሌኒን መልስ የሚከተለው ነበር ፤

«ድል ያደረገው አብዮታዊው ወዝአደር መበካከላቸው የተቀነባበረ ፕሮፓጋንዳ ካካሄደና የሶቭዬት መንግሥት ባለው አቅም ሁሉ ከረዳቸው ኋላቀር አገሮች የግዴታ በካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ውስጥ ማለፍ አለባቸው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው ።» [12]

ከዚህ ጋር አያይዞ ሌኒን በቅኝ ግዛቶችና በኋላቀር አገሮች ነፃ « ተዋጊ ኮንፍና ፓርቲ » እንዲመሠረት ፥ እንዲሁም የገበሬው ማኅበራት እንዲቋቋሙና የፕሮፓጋንዳ ሥራም እንዲፋፋም አሳስበዋል ። በመሆኑም የማርክስና የኢንግልስን አስተሳሰብ ተከትሎ ለዓለም አቀፍ ኮሚኒስት ሁለተኛ ጉባኤ በ1920 ሌኒን ባቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እንደገለፀው « በለሙት አገሮች ድል የተጐናጸፉት ወዝአደሮች እርዳታ (እማካይነት) ኋላቀር አገሮች በካፒታሊስት የእድገት ደረጃ ውስጥ ሳያልፉ ወደ ሶቭዬት ሥርዓት ከዚያም በተወሰኑ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ በማለፍ ወደ ኮሚኒዝም ሊሸጋገሩ ይችላሉ» [13] ብሏል ።

ሶሻሊስታዊ ሽግግርን ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰነ «የባሕል የዕድገት ደረጃ » ላይ መድረስ አስፈላጊ ስለመሆኑ ለተነሳው ክርክር ሌኒን እንደሚከተለው መልሶ ነበር፤

ሶሻሊዝምን ለመገንባት የተወሰነ የባህል እድገት ደረጃ ይጠይቃል ከተባለ (ያውም በእያንዳንዱ የምዕራብ አውሮፓ ይህ የባህል ደረጃ ስለሚያለያይ የተወሰነ የባህል ደረጃ የሚባለው ይህ ነው ለማለት ማንም ሰውባይችልም) እና ለምን በመጀመሪያ አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለተወሰነ የባህል ደረጃ አስፈላጊ የሆኑትን በቅድሚያ መጨበጥ አንጀምርም? ከዚያ በኋላስ በሠራተኛውና በገበሬው አስተዳደርና በሶቭዬት ሥርዓት አማካይነት ሌሎችን አገሮች ለመቀደም ለምን አንታገልም ? [14]

በ1930ዎቹ አጋማሽ ላይ እንደታየው የሌኒን ቆራጥና አብዮታዊ አስተሳሰብ ፍሬ አሳየ ። በሶቭዬት አስተዳደር አማካይነት የተፋጠነው የኅብረት ሥራ መስፋፋትና የኢንዱስትሪ መዳበር በሶቭዬት ኅብረት

ለሶሻሊዝም አስተማማኝ መሠረት ጣለ ። በዚህም ሌኒን «ለሶሻሊዝም ብቸኛው የኢኮኖሚ መሠረት ከፍተኛ የማሽን ኢንዱስትሪ» ነው ያለው ዕውን ሊሆን ቻለ ።

ኮሚዩኒስት ኢንተርናሽናልም (ኮሚንተርን) በካፒታሊስት የዕድገት ጉዳና ጥያቄ ሌኒናዊ ግንዛቤ ነበረው።በፕሮግራሙ ውስጥ እንዳሰፈረው ገና የወዛደሩ ቁጥር በጣም ጥቂት በሆነበት ወይም ጨርሶ በሌለበት ገና አብዛኛው ሕዝብ በቤተዘመዳዊና በነገዳዊ ሁኔታና ግንኙነት በሚኖርበት፣ ብሔራዊ ቡርዧዥም ጨርሶ በሌለበት ወይም በጣም አነስተኛ በሆነበት፣ ግን ኢምፔሪያሊዝም በወታደራዊ ኃይል ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችን በሚቆጣጠርበት ሁኔታ የብሔራዊ አርነት ጥያቄ ማዕከላዊ ሆኖ ይቀርባል ። በዚህ ሁኔታ የብሔራዊ ንቅናቄ ማሸነፍ የድል አድራጊው ወዛደር ጠቃሚ ዕርዳታ ከታከለበት በሶሺያሊስት የዕድገት ፈለግ አቅጣጫ ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር መንገድ ሊከፍት ይችላል ።[15]

ሌኒንም ሆነ ሌሎቹ የሳይንሳዊ ኮሚዩኒዝም ንድፈሐሳብ መሥራቾች የካፒታሊዝምን የዕድገት ደረጃ በሽግግራዊ ለውጥ ለማለፍ እንደሚቻል ቢናገሩም፣ የሽግግሩን ደረጃዎች፣ የወቅቱን ርዝመት ሆነ የለውጡን መጣኔ አልገለጹም ። ለማሌውያን ንድፈሐሳብ ቀኖና ሳይሆን በእያንዳንዱ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በተግባር የሚተረጐም መመሪያ ነው ። ስለሆነም ነው ሌኒን ስለሽግግሩ ሲናገር፣ «ለዚህ በተግባር ማዋያ መሣሪያዎች ወይም ስልቶች በቅድሚያ ሊጠቀሙ አይችሉም ፤ ምክንያቱም እነዚህ ከተግባራዊ ክንዋኔ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ናቸው »[16] ያለው ።

ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት በኋላ በተጨቆኑ አገሮች ነፃ የሆኑ በቢሊዩን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ለነፃነት የሚያካሂዱት ትግል ኢካታሊስታዊ የዕድገት ንድፈሐሳብ በተግባር የመተርጐምን ጥያቄ ወቅታዊ አደረገው ። በዚህ ወቅት ኢምፔሪያሊዝም ነፃ በመውጣት ላይ የነበሩትን አገሮች በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ክልል ውስጥ እንዲሆኑ ለማድረግ ሴራውን ሲጠነስስ፣ በ1960 (እ. ኤ. አ፡ በሞስኮ የተሰበሰበው የኮሚኒስቶችና የሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ላይ በመመርኮዝ በአዲሱ ዓይነት የሽግግር ወቅት ሊታቀፍ ለሚችለው የሶሻሊስት የዕድገት አቅጣጫ አስፈላጊውን ትኩረት ሰጠ። ስብሰባው በወቅቱ የነበረውን የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም፣ በፊት የነበረውን የማሌቲዎሪ እንደገና በማጤንና ከአንዳንድ ልምዶች በተገኘው ውጤት በመመርኮዝ የሚከተለውን ማጠቃለያ አቀረበ ።

ወዲያውኑ አብዮታዊ ሶሻሊስታዊ ለውጥ ለማድረግ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ባይሟሉምእንኳን፣ሀገሮች ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ፊውዳልና ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ለመቀጠልና ከግብ ለማድረስ፣ ብሉም ደረጃ በደረጃ በሚከናወኑ ዲሞክራሲያዊ ድርጊቶች ወደ ሶሻሊዝም የሚያሸጋግር መንገድ ሊከተሉ ይችላሉ ።[17]

ይህ መደምደሚያ የተገኘው ዝም ብሎ ከአየር አልነበረም ። በአንድ መልኩ ቀደም ያለውን ንድፈሃሣብ መንደርደሪያ ትክክለኛነት የሶብዩት እስያ ሪፑብሊኮች ሽግግራዊ ልምድና የሞንጐልያና የሌሎችም ልምዶች ማስመስከራቸውና በሌላ በኩል የአርነት ንቅናቄዎች ድሎችና በነዚህ አገሮች የነበሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ለንድፈ ሃሣቡ ተግባራዊነት መንገድ መክፈታቸው እንዲሁም የታሪክ አብዮታዊ አቅጣጫ ይህንኑ በማመልከቱ ነበር።

አብዮታዊ መንግሥትና ተግባሩ

ከላይ እንደተጠቀሰው የማሌ ሳይንስ ሊቃውንት ከሶሻሊስት የእድገት ፈለግ ጽንሰ ሃሣብ ጋር ሌላ ለወቅቱ አብዮታዊ ሂደት አንገብጋቢ ጥያቄ አድርገው ያቀረቡት አብዮታዊ ወይም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን የማቋቋም ጉዳይ ነው።

Digitized by Google

አብዮት ራሱ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ እንደሆነ እውቅ ነው ። የፖለቲካ ሥልጣን መሣሪያ መንግሥት እንደመሆኑ ለለውጥና ለግንባታም መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል። የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጡ መደቦች በዚያ መሣሪያነት ፈቃዳቸውን ያስፈጽማሉ ሆኖም የመንግሥት ሥልጣን መደባዊ ይዘት የተጨባጩን ለውጥ ዓይነት ፣ ጥልቀትና አቅጣጫ ይወስናል ። በሌላ አነጋገር በሚደረገው የለውጥ ዓይነት ፣ ጥልቀትና አቅጣጫ የአንድን መንግሥት መደባዊ ባህሪ ለመለየት ይቻላል ። ለሰፊው ሕዝብ ይቁም ወይ ለጥቂት የገዥ መደብ አባላት፣ ዋናመለያ ተግባር ነው ። የሆነ ሆኖ የአብዮት ወቅት የተወሳሰበ የመደብ ትግል የሚካሄድበት እንደመሆኑ ይህንን ሁኔታ በትክክል ለመገንዘብ ጊዜ ይወስዳል ።

የወዝ አደሩ የበላይነት በሰፈነበት አብዮት የመንግሥትን ሥልጣን መደባዊ ባህሪ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል ። ይሁን እንጂ ወዝአደሩ በምርት ኃይሎች ኋላ ቀርነት ሳቢያ በሚኖረው ርዕዮተ ዓለማዊና ድርጅታዊ ኋላቀርነት ምክንያት የበላይነቱን በማይዝበት አብዮት እንደ ሽግግር መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ሌላ የፖለቲካ ቅርጽ ነው ። ስታሩሼንኮ እንደጻፈው «ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሶሻሊስታዊ ዝንባሌ (Socialist oriented) ያለውን እድገት እውን የሚያደርግ ፖለቲካዊ ቅርጽነው።»[18]

ይህ መንግሥት ለሰፊው ሕዝብ የቆመ እንደመሆኑ በኢምፔሪያሊስት ድጋፍ፣ በቡርዧ ፓርቲዎች ከሚመራ፣ የካፒታሊስት የዕድገት አቅጣጫን ከሚከተል ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መንግሥት የተለየ ነው ። የሚቋቋመውም ከአብዮታዊ የመደብ ትግል በኋላ በድል ከሚወጡት ከተራማጅ መደቦችና ቡድኖች ነው ። በአብዮታዊ ፓርቲ ወይም ቡድን አማካይነት ለሰፊው ሕዝብ ብሔራዊ ግንባር አመራር ይሰጣል ።

በአጠቃላይ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ተግባራት ለሶሻሊዝም መገንባት አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት ፤ በኢኮኖሚ ዘርፍም ደረጃ በደረጃ ኢንዱስትሪዎችና ምርታማ የሆነ እርሻን ማስገኘት ነው ። ስለሆነም ማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከት በሶሺያሊስት የእድገት ጉዳና ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገውን ሽግግር በሁለት ደረጃ ይከፍለዋል ። የመጀመሪያው ደረጃ ተግባራት በመሠረቱ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ፣ ፀረ ፊውዳልና ዲሞክራሲያዊ ናቸው። በዚህ ደረጃ በሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅም ላይ የተመሠረቱ ስርነቀል ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ይካሄዳሉ ። በዚህ ሽግግር ወቅት የአብዮታዊው መንግሥት ዋና ዋና ተግባሮች፣ [19]

—የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ነፃነት ማጠናከርና አብዮቱን ከጸረ ህዝቦች መከላከል ፣

—የመሬት ይዞታን ማሻሻልና፣ የፊውዳሊዝምን ቅሪቶች ማስወገድ ፣

—ኢምፔሪያሊዝም ያለውን የኢኮኖሚ የበላይነት ማስወገድ ፣ በውጭ ሞኖፖሊዎች እንቅስቃሴ ላይ ገደብ ማበጀትና በብሔራዊ ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሱትን ትዕዕኖ ማስወገድ ፣

—የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ፣

—ማኅበራዊ ሕይወትን ዲሞክራሲያዊ ማድረግና በመንግሥት አስተዳደር ሕዝባዊ ተሳትፎን ማዳበር ፣

—ብሔራዊ ኢንዱስትሪን ማቋቋም ፣

—ከሶሻሊስት መንግሥታት ጋር ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ትብብርን ማዳበር ፣ ነፃና በሰላም አብሮ በመኖር ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መከተል ናቸው ።

አብዮታውያን አጥበቀው እንደሚያስገነዝቡት እነኝህ ተግባራት እንዲያው በበጎ አሳቢ የፖለቲካ ሰዎች አእምሮ ውስጥ የሚውጠነጠኑ አማራጭ የፖሊሲ መስመሮች አይደሉም ። እነኝህ ተግባራት ለብሔራዊ አርነት እንቅስቃሴ ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ወደ ሶሻሊስታዊ አብዮት ፣ ካል

Digitized by Google

ተሟላ የፖለቲካ ነፃነት ወደተሟላ የፖለቲና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት መሸጋገርና ብሎም በሥር ነቀል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች በማካይነት ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚያስፈልጉ ለዚህ ታሪካዊ ወቅት መገባደድ የግድ የሚያስፈልጉ ክንውኖች ናቸው።

ስለዚህ ስሙ እንደሚያመለክተው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ወይም አብዮታዊ መንግሥት ሳያስልስ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነቱን የማስከበር፣ የአምባገነንነትንና ፀረ ሕዝብ የቢሮክራሲያዊ አስተዳደር ዘይቤዎችን የማስወገድ፣ ለሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲ መብቶችን በየደረጃው የማጐናጸፍ፣ ሕዝቡ በመንግሥት ፖሊሲ ቅየሳ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚድረግና በሥርነቀል ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ የማሻሻል ባሕሪያት ያሉት ነው።

ሁለተኛው የእድገት ደረጃ ዲሞክራሲያዊ ደረጃውን በተገቢ ሁኔታ ጨርሶ የሶሻሊዝምን ግንባታ በወል መያዝን ይመለከታል። በእርግጥ እነዚህ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸው የዲሞክራሲያዊ አብዮት ደረጃ መገባደጃና ሶሻሊስታዊ ጅምር ድንበራቸው ይህ ነው ለማለት አስቸጋሪ ነው። በመጀመሪያ ደረጃም ሶሻሊስታዊ ባህሪ ያላቸው ለውጦች ይከናወናሉ። የሆነ ሆኖ ትክክለኛ ሶሻሊስታዊ ሽግግር የሚከናወነው በካፒታሊስት ጐዳና ለመጓዝ በሚፈልጉና ወደ ሶሻሊስት ግንባታ ለመሸጋገር በሚፈልጉ ኃይሎች መካከል የሚደረገው የተጋጋለ የመደብ ትግል በኋላ በአብዮታዊ ኃይሎችና በሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የበላይነት መስፈን ነው። በትግሉ ሂደት በዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት አብዮቱን ሲደግፉ የነበሩ ብዙዎች ሊያዘቅጡ የሚችሉበት ሲሆን፣ አብዮቱ በግሌ ፓርቲ አማካይነት ሳይንሳዊ አመራር የሚያገኝበት ወቅትነው። ያለግንባር ቀደሙ የሠርቶ አደር ፓርቲ አመራር ሽግግርና ሶሻሊስታዊ ግንባታ አይቻልም። ከዚሁ ጋር መንግሥታዊ አካልም አስፈላጊው አብዮታዊ ለውጥ እንዲያደርግበት ያሻል። በኢኮኖሚው መስክ ሽግግሩ የሚከናወነው የኢንዱስትሪና እርሻ ልማቶች ተስፋፍተው በአብዛኛው ሶሻሊስታዊ ፈር ሲይዙ፣ ብዝበዛን በማጥፋትና «ከእያንዳንዱ እንደ የችሎታው፣ ለእያንዳንዱ እንደሥራው» በሚለው መርህ መሠረት የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የቁሳዊና የባህላዊ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ሲቻል ነው።

የሽግግር ወቅት ውስብስብ ስለሆነ የአመራር አስተዋይነትና ጥንቃቄን ይጠይቃል። አዝጋሚነትና ግራ ቀደምትነት ወደ ስህተት ይጥላሉ፤ ችግሮችን በወቅቱ ያለመረዳት ወይም ተጨባጭ ሁኔታ ከሚፈቅደው ወጪ ለመፍታት መጣር፣ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉትን እቅዶች መተለምና ፕሮፓጋንዳና ተግባርን መነጣጠል የሽግግርን ዓላማ የሚጎዱ መሆናቸውን ግልጽ ሊሆን ይገባል።

አንቀሳቃሽ ኃይሎችና አመራር፣

አንቀሳቃሽ ኃይሎች

በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊው መንግሥት ግንባርነት በአብዮቱ የሚሳተፉ የተለያዩ መደቦችና ማኅበራዊ ቡድኖች አሉ። ተሳትፎአቸውም አብዮቱ የመደብ ጥቅማቸውን በጠበቀላቸውና ወደፊትም እንደሚጠብቅላቸው በሚኖራቸው እምነት መጠን ይወሰናል። በዚህ በሽግግራዊ ሂደት ፍልሚያ ሁለት መደባዊ ትብብሮች እንደሚከሰቱ በአብዮቶች ልምድ የታየ ነው። ከእነዚህም የመጀመሪያው ትብብር የሚገነባው ወዛደሩን፣ ንዑስ ከበርቴውን ማለትም ገበሬውን፣ የእደጥበብ አምራቹን፣ አነስተኛ ነጋዴውን አብዮታዊ ምሁራንን ለአብዮት የቆሙ የቢሮ ሠራተኞችና መለዮ ለባሹን እንዲሁም አገር ወዳድ የሆኑ የብሔራዊ ቡርዧ ግለሰቦችን በማቀፍ ነው። ይህ ትብብር ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ አድሀርትና አብዮቱንም የሚያንቀሳቅስ ኃይል ነው።

ሁለተኛው ትብብር የሚገነባው ለአብዮቱ

Digitized by Google

ተቃራኒ በሆኑና በኢምፔሪያሊዝም በሚደገፉ በፊውዳሎች ፣ በነገድ መሪዎች ፣ በንግድ ቡርዧዎች በቢሮ ከበርቴዎች ነው ።

የአብዮቱ ደጋፊ መደቦችና ቡድኖች በተለይ በዕድገት ወደኋላ በቀሩ አገሮች ጥንካሬያቸው ፣ ሚናቸውና በአብዮቱም እስከ ምን ሊሄዱ እንደሚችሉና እንዲሁም የአብዮቱን የአመራር ጥያቄ በሚመለከት በአጭሩ ማየት ጠቃሚ ይሆናል ።

የወዝአደሩ መደብ

ወዝአደሩ መደብ የሰውን ልጅ ከካፒታሊስት ጭቆና ነፃ የማውጣት ከፍተኛ ተልዕኮ ያለው ግንባር ቀደም አብዮታዊ መደብ ነው ። ተልዕኮውንም ለመወጣት በቁጥሩ በድርጅቱና በመደባዊ ንቃተ ሕሊናው የተጠናከረና የፖለቲካ ሚናውን በትክክል የተገነዘበ መሆን አለበት ።

ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በኋላቀር አገሮች የመደብና የማኅበራዊ ክፍፍል በተለይ የዘመናዊ መደቦች ክፍፍልና ቅራኔ በአብዛኛው በጅምር ላይ ያለ ነው። በነዚህ አገሮች የወዝአደሩን መደብ ተወራራሽነትና ከፊል ገበሬነት ሲገልጽ ብሩቴንትስ የተባለው የሶቪየት ደራሲ « የቤተ ዘመድና የጐሣ ግንኙነቶች ፣ የዘር (ካስት) አስተሳሰቦች ሃይማኖታዊና ሌሎች ኋላቀር አስተሳሰቦች የመደባዊ ግንኙነትን የተሟላ ገጽታ የተድበሰበሰ ያደርጉታል »[20] ብሏል ።

የአፍሪካና የእስያ ጭቁን ሕዝቦች የፖለቲካ ነፃነታቸውን ባገኙበት ጊዜ በጥቂት አገሮች ውስጥ ብቻ ነበር ። የወዝአደሩ መደብ ቅርጽ ይዞ የነበረው ። ልምድ ያለው የኢንዱስትሪው ወዝአደር እምብርት በአመዛኙ «በጣም ደካማና ጥቂት» ነበር ። በአንዳንድ አፍሪካ አገሮች እንዲያውም ጭራሽ የወዝአደር መደብ አልነበረም ። እንደሚባለው በ ዚ ህ በያዝነው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ የኢንዱስትሪ ወዝአደር ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር ከ4—5% ነበር ። ሠራተኞች በአመዛኙ በትንንሽና በተበታተኑ ድርጅቶች ስለሚሠሩና ለገጠር ፣ ለጐሣ ፣ ለቤተሰብና (Patriarchal) ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦች የተጋለጡ በመሆናቸው የቁጥራቸው ማነስ ከድርጅታዊ ከርዕዮተ ዓለማዊ ኋላቀርነት ጋር ተዳምሮ ድካማቸውን የበለጠ አድርጉታል ። ከዚሁም በላይ በሞኖፖሊስቶች በተያዙ ድርጅቶች ውስጥ የወዝአደሩ መደራጀት በልዩ ልዩ የጭካኔ እርምጃዎች ይደናቀፋል ።

ወቅታዊ ግምቶች እንደሚያመለክቱት በአፍሪካና በእስያ የወዝአደሩ መደብ ቁጥር ከደመወዝተኛው ቁጥር ከ20 እስከ 25 በመቶ ሲሆን የደመወዝተኛ ቁጥር ደግሞ ከጠቅላላው ሊሠራ ከሚችለው ሕዝብ ከ5—7% ነው ። በ1970 ዎቹ ማክተሚያ ላይ በሠራተኛ የሙያ ማኅበራት የሚሳተፉ የሠራተኞች ቁጥር 40 ሚሊዮን ሲሆን ከነሱም ውስጥ 3 ሚሊዮን የሚሆኑት ከትሮፒካል የአፍሪካ ክፍል እንደሆኑ ተገምቷል ። ይህም ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው ።

በኢምፔሪያሊስት ሞኖፖሊዎችና በሀገሩ በዝባዦች ርኅራኄ የሌለው ጭቆና የሚፈጸምበትና የሚመዘበረው ወ ዝ አ ደ ር ፍጹም ፀረ ጭቆናና ለሥር ነቀል ለውጥ የሚቆም መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ መደብ ቁጥሩ አነስተኛም ቢሆን የፖለቲካ ነፃነት ጮራ እንዲፈነጥቅ ላደረገው የፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ግብ መምታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በተለይም ከጥቅምቱ አብዮት ወዲህ በተከሰተው የአብዮታዊ ሽግግር ዘመን ወዝአደሩ በጨቅላነት ደረጃ እንኳን ቢሆን ዘላቂነት ያለውን አብዮታዊ ሚና ሊጫወት ይችላል ። የማሌ ሳይንቲስቶች እንዳመለከቱት «ገና በመጀመሪያው የዕድገት ደረጃው እንኳ የራሱ መደባዊ ድርጅቶች ማለትም የኮሚኒስት ፓርቲና አብዮታዊ የሠራተኛ ማኅበር ሊኖሩትና ግንባር ቀደም ታጋዮችም ማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለምን መመሪያቸው

Digitized by Google

ሊያደርጉ ይችላሉ ። እንዲሁም ከዓለም
አቀፍ ወዝአደሮች ፣ ከሶሻሊስት መንግሥ
ታትና ከዓለም የሚኮኒስትና የተራማጅ
የሠራተኛ ማኅበራት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ
ሊያገኝ ይችላል ፡፡ » ። [21]

በኋላ ቀር አገሮች ወዝአደሩ ጨቅላም
ቢሆን ወዝአደራዊ አስተሳሰቦች ግን ከፍ
ተኛ ሚና ተጫውተዋል ። እንዲያውም
ዛሬ ድርጅታዊ ቅርጽም እያገኙ ሄደዋል ።
ስለዚህም ነው ዛሬ በአፍሪካና በእስያ 29
ኮሚኒስትና ቁጥራቸው የማይናቅ የማሌን
ፈለግ የሚከተሉ ፓርቲዎችና ድርጅቶች
ሊፈጠሩ የቻሉት ።

በሽግግሩ ወቅት ይህ እጅግ በጣም አብ
ዮተኛ የሆነው የወዝአደሩ መደብ በትግሉ
ውስጥ እንደአንድ ወሳኝ ኃይል ሆኖ ይሳተ
ፋል ። ወቅቱ በትግል ኋላ ቀደነቱን የሚያ
ስወግድበት ፣ መጠናዊ ፣ ድርጅታዊና ርዕ
ዮተ ዓለማዊ ጥንካሬና ብቃት የሚያገኝበት
ወቅት ነው ። በእርነት ንቅናቄ ከፍተኛ አስ
ተዋጽኦ አድርጓል ። በማኅበራዊና ኢኮኖ
ሚያዊ ትግልም ከአብዮታዊ ኃይሎች ጋር
በቀዳሚነት በመሰለፍ ከፍተኛ ሚና ይጫ
ወታል ። በሶሻሊስት አብዮትም ለመደብ
አጋሮቹ በግንባር ቀደም ፓርቲው አማካ
ይነት አመራር በመስጠት በግንባታ ሂደት
ሶሻሊስታዊና ብሎም ኮሚኒስታዊ ሥርዓ
ትን ያሰፍናል ።

የገበሬ ክፍል

የገበሬ ክፍል በትክክል ከተመራ በአብዮ
ት ሂደት ሊጫወት ስለሚችለው ሚናና ለወ
ዝአደሩም አጋር ለመሆን ስለመቻሉ የማሌ
መሥራቾች አበክረው አስተምረዋል ።
የዚህም ሐቅ በታላቁ የጥቅምት አብዮትና
ከዚያም በኋላ በተካሄዱ አብዮቶች ታይ
ቷል ። በተለይም በኋላቀርና በቅኝ ግዛት
አገሮች በተደረጉ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና
ፀረ ፊውዳል ትግሎች ትልቁ ኃይል ገበሬው
መሆኑ ተደጋግሞ ታይቷል ።

በብዛት በኩል በተለይ አፍሪካንና እስ
ያን ብንወስድ ከሕዝቦቻቸው አብዛኞቹ
ገበሬዎች ናቸው ። በትሮፒካል አፍሪካ
ከ80 እስከ 90 በመቶ ፣ በእስያ ከ60 እስከ
70 በመቶ ይደርሳል ። እርሶ አደሩ የሚኖ
ረው በገጠር ሲሆን በኑሮ ደረጃውም ዝቅ
ተኛውን እርከን ይዞ ይገኛል ።

ገበሬው ከኅብረተሰቡ ክፍሎች ሁሉ
እጅግ በጣም የተጨቆነና የተበዘበዘ ክፍል
ነው ። «በውጭ ካፒታል ፣ በቅኝ ገዥ ባለ
ሥልጣናት ፣ በፊውዳሎች ፣ በነገድ መሪ
ዎች ፣ በባለመሬቶች ፣ በአራጣ አበዳሪዎች
በነጋዴዎች ፣ እንዲሁም ሥር በሰደዱ ሀብ
ታም ገበሬዎች ይበዘበዛል ። » [22]

ይህ ብዛት ያለው የኅብረተሰብ ክፍል
በዚህ ዓይነት በልዩ ልዩ መንገዶች መጨ
ቆኑ ለፀረ ቅኝ አገዛዝ ፣ ለብሔራዊ ዲሞክራ
ሲያዊ አብዮትና በዚህ ጉዳና ለሚካሄዱ
ትግሎች ከፍተኛው ኃይል እንዲሆን አድ
ርጉታል ።

ይሁን እንጂ ገበሬው በመሃይምነት ፣
በኋላቀር እምነት ፣ በተበታተነ ኑሮ፣ በቤተሰ
ባዊ ዝንባሌና በግል ባለንብረትነት የተተ
በተበ በመሆኑ እንደነገ መደባዊ ኃይል ሆኖ
መሳተፍ ይሳነዋል ። ሆኖም ይህ ኃይል በሠ
ራተኛው መደብና በአብዮታዊ ምሑራን
ሊሰባሰብና ሊደራጅ ከቻለ ለአብዮት ጽኑ
ድጋፍ ያለው ኃይል ነው ። በሌላ በኩል ገበ
ሬው ከአድሃሪ ቡርዧዎችና ከንዑስ ከበርቴ
ክንፎች ጐን ሊሰለፍ ይችላል ። ስለሆነም
እርሶ አደሩን በወዛደሩና በአብዮታውያን
ጐን ለማሰለፍ የሚደረገው ፍልሚያ በዘመ
ናችን የአብዮታዊ እንቅስቃሴ ሂደት ከፍ
ተኛ ሥፍራ አለው ። ለአብዮቱ ሂደት የሠ
ራተኛውና የአብዮታውያን ጠንካራ አጋር
እንዲሆን ከተቀሰቀሰ ፣ የፖለቲካ ንቃት
ካገኘና ከተደራጀ ገበሬው የሶሺያሊስቱ የዕ
ድገት ፈለግ ደጋፊ ፣ ከሱም ውስጥ ለሶሻሊ
ስት የምርት ግንኙነት መጠናከርና መስፋ
ፋት የቆመው ግንባር ቀደሙ ክፍል የሶሻሊ
ዝም ገንቢ ኃይል ይሆናል።ለዚህ ግን አስቀ
ድሞ የገበሬውን ኋላቀርነትና ውሱን ማኅበራ
ዊ ስነልቡናውን ማስወገድ፣የባህል ደረጃውን

ከፍ በማድረግ ፣ እንዲሁም በምርት ሂደት የንዑስ ከበርቴያዊ ግለኝነቱን አስወግዶ የሠራተኛነቱንና የኃርዮሽ ባህሪ ዝንባሌዎቹን አዳብሮ ወደ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት የማሸጋገር ውስብስብ ትግል አስፈላጊ ይሆናል ።

የንዑስ ከበርቴ መደብ

ንዑስ ከበርቴ አነስተኛ የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤትነት ያላቸውንና በምርት ሂደት የራሳቸውንና የጥቂት አጋዦቻቸውን ጉልበት የሚጠቀሙ የኅብረተሰብ አባሎች ያቅፋል ። አነስተኛ መሬት ያላቸው ገበሬዎች አነስተኛ ነጋዴዎችና የዕደ ጥበብ ሠራተኞች የዚህ መደብ አካል ናቸው ።በኋላቀር አገሮች ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የሁለቱ ዘመናዊ መደቦች ማለትም የወዝ አደሩና የቡርዧው መደቦች ደካማ መሆን ፣ የንዑስ ከበርቴው መደብና በማህበራዊ ሚናቸው ከዚህ መደብ ጋር የሚመሳሰሉ ማህበራዊ ክፍሎች (ማለትም ወታደር ፣ ምሁር ፣ የቢሮ ሠራተኛ ወዘተ ...) ከፍተኛ የፖለቲካ ሚና እንዲኖራቸው አድርጎታል። ይህ መደብ በተለይ በኋላቀር አገሮች ሕዝባዊ ጥያቄዎችን እንዲነሳ ያደርገዋል ። በሌላ በኩል ትንሽም ብትሆን የግልሀብት ስላለው የመዋለል ባህሪ እንዲኖረው ያደርገዋል ። ብሩቴንትስ እንደ ጻፈው፣ «የንዑስ ከበርቴው የመወላወል አቋም በግልጽ የታወቀ ነው ። አቋሙ ከግል ሀብት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ወደቡርዧው የማዘንበል ባህሪ ይታይበታል ። በሌላ በኩል ደግሞ በሥራ ሂደት ውስጥ በቀጥታ ስለሚሳተፍ ከሠራተኛው መደብ ይቀራረባል ፤ የሠራተኛው መደብም የማኅበራዊ ፣ የፖለቲካዊና የስነ ልቡናዊ ግንኙነቶች ተጽዕኖ ያሳድርበታል።የሠራተኛው መደብ በሚያካሂደው አብዮታዊ መደባዊ ትግልም እንዲሳተፍ ያደርገዋል ።»[23] ከዚህ አንፃር በተለይ ወደ ሶሻሊዝም በሚደረግ የሽግግር ሂደት የንዑስ ከበርቴውን መደብ ወላዋይነት በሚገባ መጠን ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል ።

የምሁራን ክፍል

ይህ ከተለያዩ መደቦችና በተለይ አብዛኛው ከንዑስ ከበርቴው የሚመነጭ ማህበራዊ ክፍል በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሂደት ውስጥ የመሪነት ሚና አለው ። ይህም በግሌ ጽሑፎች አብዮታዊ ዲሞክራት እየተባሉ የሚጠሩ ኃይሎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ፣ እነዚህ ኃይሎች የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የፖለቲካ አመራሩን በመያዝ ቁልፍ የሆነ ሚና የሚጫወቱ ናቸው ።

በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያሉ ምሑራን (ከወታደሩም ሆነ ከሲቪሉ) ማይምነት በተስፋፋበት ሁኔታ ባላቸው የተሻለ የትምህርትና የባህል ደረጃ ምክንያት በፖለቲካ ከፍተኛ ሥፍራ ይኖራቸዋል ። ከሶሻሊስት የዕድገት ጉዳና ልምድ እንደሚታየው የምሑራኑ የፖለቲካ ሚና ይህ ክፍል ባለው አንፃራዊ «የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ነፃነት» ምክንያት የበለጠ ሆኖአል ። የምሑራኑ ክፍል አብዮታዊ ንድፈሐሳቦችን በመቅሰም የማኅበራዊ ዕድገት አቅጣጫን ለመረዳትና ትክክለኛ አዝማሚያዎችን ለመከተል ይችላል ። ከዚሁ ጋር ለንዑስ ከበርቴው ባለው ቅርበት እንደግለኝነት ፣ ወላዋይነትና ብሔረተኝነት የዚሁ መደብን አመለካከቶች ያሉ እንደሚያጠቁት መረዳት ደግሞ አስፈላጊ ነው።

የአብዮታውያን ዲሞክራቶች ሚና በሽግግር ወቅት ብቻ አያበቃም ። በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ጽኑ እምነት ያላቸው እነዚህ አብዮታውያን የወዝአደሩን ርዕዮተ ዓለም በመቀበል ፣ በማስፋፋትና ሠርቶ አደሩን ለሶሻሊስት ግንባታ ለማሰለፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ። በትግል እራሳቸውን እየለወጡ ኅብረተሰቡንም ይለውጣሉ ። ይህን አባባል በመደገፍ አንድ ጸሐፊ እንዳለው ፣ «ታሪክ በአብዮታዊ ትግል ሂደት ውስጥ በተለወጡ በንዑስ ከበርቴ ዲሞክራሲያዊ ግለሰቦች የተሞላ ነው ። በጊዜያቸው ማርክስ ፣ ኤንግልስና ሌኒን ወደሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የመጡት በዚሁ ሂደት ውስጥ ነው ፤ በኩባ ፊደል ካስትሮም እንዲሁ»[24]

Digitized by Google

ብሔራዊ ቡርዧ

በአብዛኛዎቹ ኋላቀር አገሮች በተለይም በአፍሪካ ከፍተኛ ካፒታል ያለው ብሔራዊ ቡርዧ ጥቂት መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህም የመለስተኛ ሸቀጥ ምርት ፣ የኢምፔሪያሊስት ሞኖፖሊ ቁጥጥርና የዓለም የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ተቀጥላነት ባህርያቱ የሆኑት የኢኮኖሚው መሠረት ውጤት ነው። የቅኝና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቁጥጥር ለብሔራዊ ቡርዧ ዕድገት አመቺ ሁኔታ በፍጹም አይፈጥርም ። ለምሳሌ አፍሪካ ለአምስት ምዕተ ዓመታት የባርያ ንግድ ቅኝ አገዛዝና እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተፈራረቀበት በመሆኑ ብሔራዊ ካፒታልና ብሔራዊ ቡርዧ መደብ አላደጉበትም ። ሊያድግ የቻለው አቀባባይና የቢሮ ቡርዧ ነው ።ይህም የኢምፔሪያሊስት ተቀጥላና የፊውዳል አጋዥ ማኅበራዊ ክፍል እንጂ ብሔራዊ ኢኮኖሚን የሚያዳብር አይደለም ።

በዚህ ዓይነት ዛሬ በማደግ ላይ ያለውና በኢምፔሪያሊስቶች ዕድገቱ የታፈነ ብሔራዊ ቡርዧ በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ የተወሰነ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችል አብዮታውያን ያምናሉ ። በተጨማሪም አብዮቱ ጥልቀት እያገኘ ሲሔድ ብሔራዊ ቡርዧ «የሕዝቡን ትግል በመፍራትና ለኢምፔሪያሊስታዊ ድለላ ወይም ማስፈራራት በማጉብደድ በመጀመሪያ ጊዜ የነበረውን ተራማጅ ፖለቲካዊ አመለካከት እርግፍ አድርጐ በመተው ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ወደ መቻቻል»[25] ሊዞር እንደሚችል አብዮታውያን ይገነዘባሉ ።

የአመራር ጉዳይ

የአመራር ጉዳይ በኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ምናልባት በጣም አከራካሪው ገጽታ ነው ። የዚህ የዕድገት ደረጃ ዓይነተኛ ባሕርይ ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር ተፈጻሚነት ማግኘት ነው ። ለዚህም የአመራር ሚና ወሳኝ ነው።

ይህን በሚመለከት ብሩቴንትስ እንደሚከተለው ጽፉዋል፣

አመራሩ፣የወዝአደሩንጥቅሞች ከሚወክሉ የፖለቲካ ኃይላት መካከል ከሆነ፣ አብዮቱ ሕዝባዊ ነው ፤ እንደሕዝባዊ አብዮትም ያድጋል ፤ በቀጥታም ወደሶሻሊስት አብዮት ይሸጋገራል ። አመራሩ የሶሻሊስት ዝንባሌ ካላቸው ወዝአደር ካልሆኑ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሲሆንና አብዛኛውን የሠርተ አደሩን መደብ ጥቅሞች በሚወክሉ ወይም በማርክሳዊ ርዕዮተዓለም በሚጀምሩ ኃይላት ተሳትፎ ሲካሄድ አብዮቱ፣ከጠቃሚ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳል ለውጦች በተጨማሪ ለሶሻሊስት ግንባታ መንገድ ጠራጊ የሆኑ ፀረ ካፒታሊስት ለውጦች በተጨማሪ ለሶሻሊስት ግንባታ መንገድ ጠራጊ የሆኑ ፀረ ካፒታሊስት ለውጦች ሊያስገኝ ይችላል ።[26]

ይህ የአቀራረብ ሁለት ዓይነት የአመራር ዓይነቶችና ሁለት ዓይነት የሽግግር ሂደቶች እንዳሉ ያመለክታል ። በመጀመሪያው አቀራረብ አመራሩ የሚመጣው የወዝአደሩን መደብ ጥቅሞች ከሚወክሉ የፖለቲካ ኃይላት ነው ። ይህም አንድ አብዮት ገና ሲፈነዳ ጀምሮ አመራር የሚሰጥ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሠርቶ አደር ፓርቲ መኖሩን ያመለክታል ። በዚያ ሁኔታ (ለምሳሌ በሰሜን ኮርያና በቪየትናም እንደተደረገው ፣«ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ » አብዮቶች በቀጥታ ወደ ሶሻሊስት አብዮት ያድጋሉ ። ይህ ሲሟላ አብዮት በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ ነው ማለት ነው ።

የሁለተኛው ሁኔታ በአፍሪካና በእስያ በጣም ጉልቶ የሚታየው የወዝአደሩ ግንባር ቀደም ፓርቲ አለመኖር ወይም ቢኖርም እንኳን ደካማ መሆኑ የሚፈጠረው ነው ። በዚህ ሁኔታ አመራሩ አመጣጣቸው ከሲቪልም ከወታደርም በሆነ በአብዮታዊ ዲሞክራቶች እጅ ይገባል ።

እነኚህ ቡድኖች ራሳቸውን በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ወይም በተመሳሳይ የፖለቲካ ድርጅቶች በማደራጀትና

ከላይ የተጠቀሰውን አብዮታዊ መንግሥት በመምራት ለአብዮቱ ሂደት ጥልቀት ማግኘት ይታገላሉ ። የሚወክሉትም የተለያዩ ማኅበራዊ መደቦችን ሲሆኑ ፣ በአብዛኛው ግን ወዝአደሩን ፣ ገበሬውንና በአጠቃላይ የንዑስ ከበርቴውን ጥቅም ነው ። ስለሆነም ቡድኖቹ የተለያዩ ዝንባሌዎችና ተቃራኒ የሆኑ ርዕዮተ ዓለማዊ ግንዛቤዎች ይታዩባቸዋል ።

አብዮቱ ሥር እየሰደደ በሄደ ቁጥር በነኚህ ቡድኖች ውስጥ ባሉ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጥቅም ደጋፊዎችና የቡርዧ ደጋፊዎች መካከል የሚደረገው የመደብ ትግል እየጎላ ይመጣል ። የመደብ ትግሉ እየተፋፋመ አብዮቱ ድል የመጐናጸፍ ወይም የመክሸፍ ወሳኝ ወቅት ላይ ይደርሳል ። በዚህም የግሌ ፓርቲ መከሰት ወይም አለመከሰት ተቀዳሚ ጥያቄ ይሆናል ። ምክንያቱም ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሠራተኛው መደብ የበላይነት መያዝ «የማኅበራዊ ዕድገት ሕግ» ነውና ።

የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ተንታኝ አብዮታውያን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ መድረስ የሚወሰነው ከተጋጋለ የመደብ ትግልና ለውጦች በኋላ ግንባር ቀደሙ አብዮታዊ ኃይል ማለትም መሪ ፓርቲው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን በመቀበሉና በማስፋፋቱ እንደሆነ ይናገራሉ ። የዚህን አባባል ትክክለኛነት ሌኒን ለሞንጎሊያ አብዮታውያን ከተናገረው ለመገንዘብ ይቻላል ። ሌኒን በዚህ ንግግሩ እንዳለው «ዘላኑ ሕዝብ ወደ ወዝአደርነት እስኪለወጥና ምናልባትም በዚህ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲውን ቀስ በቀስ ወደ ኮሚኒስታዊ ፓርቲ ለማሸጋገር እንዲረዳ አብዮታውያን አስቀድመው መንግሥቱን የሚያጠናክሩ ፣ ኢኮኖሚውንና ባህሉን የሚያሳድጉ ልዩ ልዩ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው ።» [27]

አብዮታውያን ግልጽ እንደሚያደርጉት የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ከኢምፔሪስት ሴራና ከሀገር ውስጥ አድኃሪዎች ጋር የሚደረግ የከረረ የመደብ ትግል የሚካሄድበት መድረክ ነው ። አመራር የሚሰጠውም ቡድን የዚህ የተጋጋለ የሁለት መሥመር ትግል አካል ነው ። በአብዮቱ ሂደት ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን የተቀበለውና ለወዝአደሩ ጥቅም የሚታገለው ኃይል ካሸነፈ ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግር ዋስትና ያገኛል ።

በ1960ዎቹ በአፍሪካ ከተከሰቱት ከአንዳንድ የተራማጅ አብዮቶች ቅልበሳ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የሽግግሩ መቃናት በቀላል የሚገኝ አይደለም ። በመሪ ግንባሮች ወይም ፓርቲዎች አስፈላጊ ጥንቃቄ አለመውሰድ ወይም እንቅፋት መሆን ምክንያት የተቀለበሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቶችን ልምድ በመጥቀስ አንድ ጸሐፊ እንደሚከተለው ብሏል፣ «በዚህ አገር በጣም ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር፣ እነኚህ ግንባሮች የሠራተኛ ፓርቲ ሊያደራጁ ወይም እንዲደራጁ ሊፈቀድ ይችላሉ ማለት አስቸጋሪና ምናልባትም የማይታሰብ ነው ።» [28] በእርግጥ በዛ ያሉ የቅልበሳና የዕድገት ጐዳና የመለወጥ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ቢቻልም ፣ ተስፋ አስቆራጭና ትጥቅ አስፈች መደምደሚያ ማቅረብን ታሪካዊ ልምድ አይደግፈውም ።

ሌላው መጤን ያለበት ፓርቲው ከተፈጠረም በኋላ የግሌ መመሪያዎችን ተግባራዊ የማድረጉ ጉዳይ ነው ። በዚህ ረገድ ስታሩሼንኮ የተባለ የሶቪዬት ህብረት የማኅበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ ሲያብራራ ፣ ለውጦች ካልተደረጉ በቀር «እንዲያው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ወይንም ማርክሲዝምን ይፋ መመሪያ አድርጐ ማወጅ አንድን ፓርቲ ማርክሲስት ሌኒኒስት ወይም አንድን አገር ሶሻሊስት አያደርገውም ።» [29] ብሏል ።

ስለተግባራዊ ልምዶችአንዳንድ ነጥቦች

ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ ሆና ስለተገኙ ውጤቶች የአፍሪካ ኮሚኒስት በሚባለው መጽሔት ውስጥ ሌፋም የተባለ ጸሐፊ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፣

Digitized by Google

ከሞንጎልያ ፡ ከሶቭዬት እስያ ሪፑብሊክ በቬይትናም ፡ ከኩርያ ፡ ከቡልጋሪያ ፡ ከኩባና ከቻይና ፡ ቢያንስ እስከ 1960 የተገኙ ልምዶች እንደሚያረጋግጡት ፡ በሶብዬት ኅብረት ሶሻሊዝም በተቃና መንገድ መገንባቱና ከዚያም ጠንካራ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት መመስረቱ ኋላቀር አገሮች በለቀ ራጭ መንገድ ወደ ሶሻሊዝም መድረስን የሚቻል አድርጉታል ፡[30]

በሶብዬት እስያ ዘላን፣ከፊል ዘላን፣ ከብት አርቢዎች ካፒታሊዝምን በመዝለል በአፋጣኝ ሶሻሊዝምን ለመገንባት መቻላቸውና የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ባለቤቶች መሆናቸውን ለዚሁ አቋራጭ የዕድገት ጉዳና ሕያው ምሳሌ ሊሆን ችሏል ፡ ሌሎችም ከሶብዬት ኅብረት ውጪ ያሉ ምሳሌዎች ለመጥቀስ ይቻላል ፡ ይህ ሁኔታ ከአፍሪካ እውነታ ጋር ሲወዳደር ግን በእነዚህ በተጠቀሱት አገሮች አብዮቱ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አመራር ወይንም የሶቭዬት የቅርብ ርዳታ ከመጀመሪያ ያገኘ መሆኑ ለየት እንዲል አድርጉታል የሚል አስተያየትንም ያስከትላል ፡ ይህም ቢሆን ጠንካራ አብዮታውያን ካሉ መልክአ ምድራዊና የሕልናዊ ሁኔታ ችግርችን ተወጥቶ ትግሉን ከዓለም አቀፍ ትግል ጋር በማቀናጀት አብዮቱን ለማራመድ ይችላል ፡

ምንም እንኳን በአፍሪካ ያለው አንዳንድ ሁኔታ ለአብዮቱ ማካሄድ አስቸጋሪነት አለው ቢባልና በአሁኑ በ1960ዎቹ ግልጽ ድክመቶችም የታዩ ቢሆንም ፡ በ1970ዎቹ ዓመታት ግን የታዩት ሁኔታዎች ለአብዮታዊ ለውጦች መሳካት የሚያደፋፍሩ ምሳሌዎችን አፍርተዋል ፡ በኢካፒታሊስታዊ ዕድገት ወይንም በሶሻሊስት አዝማሚያ የዕድገት ፈር አኳያ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ቢያንስ ሦስት ሁኔታዎች ታይተዋል ፡ አንደኛ፣በአንዳንድ አገሮች ለተወሰነ ጊዜ ይካሄድ የነበረው አብዮታዊ ሂደት ተቀልብሷል፡ ሁለተኛ ፡ የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ ነገር ግን ስለሽግግሩ ሁኔታ በተለይ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ስለመከተል አቋማቸው ግልጽ ያልሆነ ጥቂት አገሮች አሉ ፡ ሦስተኛ ፡ በ1970ዎቹ በተፈጠሩት ሁኔታዎች አንዳንድ አብዮታዊ ግንባሮችና ፓርቲዎች ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለማዊ መመሪያቸው አድርገው ተቀብለዋል፡

በአንደኛው ቡድን ለምሳሌነት ጋና፣ግብጽ ማሊ ፡ ሱዳንና ሶማሊያ ይጠቀሳሉ ፡ በሁለተኛው ቡድን ውስጥ አልጄሪያ ፡ ታንዛኒያ፣ ጊኒ፣የማላጋሲ ሪፑብሊክና ጊኒ ቢሳዎ ሲጠቀሱ በሦስተኛው ቡድን ውስጥ አንጐላ ፡ ሞዛምቢክ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኩንጐና ቤኒን ይጠቀሳሉ ፡ ይህ ሲባል አብዮት የተቀለበሰባቸው አገሮች ወደ አብዮት ጐዳና አይመለሱም ማለት አይደለም ፡ ሁኔታዎች በማናቸውም አገሮች ሊለዋወጡ ይችላሉ ፡

ኢካፒታሊስታዊ የዕድገት ጐዳና ስለተቀለበሰባቸው ሁኔታዎች የተደረጉ ጥናቶች በሽግግር ወቅት ስለሚከሰቱ ችግሮች አንዳንድ ጠቃሚ ጥቆማዎችን አቅርበዋል ፡ ችግሮቹ ቀጥሎ እንደምናየው በባሕሪያቸው ውስጣዊና ዓለም አቀፋዊ ናቸው ፡

በፖለቲካ ረገድ በአመራር ላይ የሚወጡ አብዮታውያን ዲሞክራቶች ግልጽ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አለማቅረባቸው ወይንም አዘጋጅተው በተግባር እኔ ዲተረጉም አለማድረጋቸው ፡ ሠርቶ አደሩንና ደሀ ገበሬን የሚያነቁና በሰፊው የሚያሳትፉ አብዮታዊና ተጨባጭ እርምጃዎችን አለመውሰዳቸው ፡ ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ የሠራተኛ ሕጐች አለማውጣትና ገበሬውን ከፊውዳሎችና ሀብታም ገበሬዎች ነፃ የሚያደርግ አዋጅ ዓለማውጣታቸው ፡ ፓርቲና መንግሥታዊ መዋቅሮችን ከአድርባዮች ፡ ከአስመሳዮችና አድሃሪ ቢሮክራቶች አለማጽዳታቸው የሚጠቀሱ ናቸው ፡

Digitized by Google

በርዕዮተ ዓለሙና ድርጅታዊ ጥያቄዎች ረገድ ከንዑስ ከበርቴና ከቡርዧ አመለካከቶች ፀድቶ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን በመመሪያነት አለመቀበል ፣ ቢቀበሉም በትክክል ተግባራዊ አለማድረግ ፣ ለድርጅታዊ ሥራ ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና ፓርቲው በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ሳይሆን በቢሮክራሲያዊ ማዕከላዊነት ተበክሉ ለመንግሥታዊ መዋቅር ትክክለኛ የፓርቲ አመራር ለመስጠት ያለመቻሉ ወይንም ከነአካቴው በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ መዋጡ ሲሆን ፣ በኢኮኖሚ ረገድ ብሔራዊ የኢኮኖሚ አውታሮችን ከሞኖፖሊስቶችና ፊውዳሊስቶች ቁጥጥር ነፃ አለማድረግ ፣ ተስፋፍቶ የሚገኘው ንዑስ ከበርቴያዊው አነስተኛ የሸቀጥ ምርት ይዞታን ለማገደብ አለመቻሉ ለካፒታሊስት እድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

በዓለም አቀፍ መድረክ ኢምፔሪያሊዝም በነዚህ አገሮች የሚካሄደውን አብዮታዊ ሂደት ለመቀልበስ የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም ። የኢኮኖሚ ማእቀብን ያደርጋል፤ አልፎም ከበባንና ወረራን ይፈጽማል ፤ የውስጥና የአካባቢ አድሀርት ኃይሎችን ይደግፋል ፤ አድኃሪ እብሪተኝነትን ያናፍሳል፤ ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ሰላም ፀር የሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያካሂዳል ፤ ወዘተ ... ።

በተለይም የሶሻሊስቱን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች የሚገኘውን ኋላቀርና ውሱን ማኀበራዊ ሥነልቦና በመጠቀም ኢምፔሪያሊዝም የብሔረተኝነት ስሜት በየደረጃውና በየትርጁ ቀፋፍሞ የመደባዊ አንድነት አመለካከት እንዲዋጥ ለማድረግ ብዙ ይጥራል ። በዚህም ሲሻው በጣም ኋላቀርና ውሱን የሆኑ የቤተዘመድ ፣ የጐጣ ፣ የነገድ ፣ የቋንቋ ፣ የሃይማኖትና የአካባቢ ጠባብ አመለካከቶች ፣ ሲሻውም ትምክህተኝነት ፣ ገፋ ሲልም ፋሺስታዊ አመለካከቶች የበላይነት እንዲኖራቸው ይጥራል ።

እነኝህና ሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች የአንድን አብዮት ግስጋሴ መቀልበሻ መሣሪያ ናቸው ። ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ግስጋሴ የሚቻለውና ዋስትና የሚያገኘው ፀረ ፊውዳሊዝም ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊዝምና ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም የሆነ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ባለማወላወል የመደብ ጠላቶችን አሸንፎ በተግባር በማዋልና በማሌ ፓርቲ አመራር ሥር የግንባታውን ሥር እስከመጨረሻው በመቀጠል ነው ።

ስለሃያሲዎች ጥቂት ነጥቦች

ስለሶሻሊስታዊ የዕድገት ፈለግ ሶስት ዋና ዋና የሂስ ምንጮች ለመጥቀስ ይቻላል እነዚህ አንደኛው ምንጭ ለሶሻሊስት ዕድገት ፈለግ ንድፈ ሐሳብ በጐ አስተያየት ያላቸው ግን በዚሁ የዕድገት ጐዳና ላይ አሉ የሚባሉት አገሮች በእርግጥ የዚሁ የዕድገት ጐዳና ጽንሰ ሐሳብ የሚወክለውን ባሕርይ መያዛቸው የሚጠራጠሩ ናቸው ። እነኝህ ሐያሲያን በ1960ዎቹ የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ በተገኙት ልምዶች ላይ በመመርኮዝ በሥልጣን ላይ ያሉት አብዮታዊ ዲሞክራቶች የወዝአደሩን ርዕዮተዓለም ለመቀበል መቻላቸውን ወይንም የወዝአደሩ መደብ የኋላ ኋላ ወደ መሪነት ቦታ እንዲመጣ ማስቻላቸውን ይጠራጠራሉ ። የዚህ ጽንሰ ሐሳብ ትንታኞች የመደብ ትግልን በኩረ ሐሳብ እንደሚዘለል አድርገው ያቀርባሉ ፣ ለመደብ ትግል በቂ ትኩረት አይሰጡትም ይላሉ ። በተጨማሪም ጽንሰሐሳቡ «መንግሥት እንደመደብ መግሪያ ሳይሆን እንደ መደብ ትግል ተቆጣጣሪ አድርጐ ይወስዳል» የሚል አስተያየት አላቸው ።

ይሁን እንጂ ሶሻሊስቱ የዕድገት ፈለግ የሚጽፉ አብዮታውያን ራሳቸው እነኝህን የመሳሰሉትን የዚህ ዕድገት ችግሮች ሳያነሱቸው አላለፉም ። ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው በዚህ ሒደት ውስጥ የሚከሰቱ ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ድክመቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ከትንተናዎቹ መገንዘብ የሚቻል

Digitized by Google

ሲሆን ድክመቶች ግን ከቦታ ቦታ ይለያያሉ ።

ሁለተኛው የሂስ ምንጭ በሽግግር ሂደት ውስጥ የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ሕልውናን ጨርሶ የሚክድ ፥ የ «ግራ» ተስፈንጣሪዎች ቀኖናዊ አመለካከት ነው ። ይህ አመለካከት ከፊል ወዝአደርና ወዝአደር ያልሆኑ የብዙኃንን አብዮታዊ ሚና የሚክድና የሚያንቋሽሽ ነው ። ስለሆነም በአፍሪካና በእስያ የአብዮት መካሄድ መቻልን የሚክድ ነው ። የ «ግራ» ተስፈንጣሪዎች አመለካከት በኋላ ቀር አገሮች የሚካሄድ አብዮት ገና ከጅምሩ የወዝአደሩን መደብ የበላይነት ማግኘት አለበት ይላሉ ። ካልሆነ አብዮቱ ወደ ሶሻሊዝም ሊሸጋገር እንደማይችል አድርገው ይናገራሉ ። ይህ አመለካከት የማሌ ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊነት በአጠቃላይና በኋላ ቀር አገሮች በተለይ በሥራ ላይ ሊውል አይችልም ከሚሉ የቀኝ ኃይሎች ሐሳባዊ አመለካከት ጋር ተመሳሳይነት አለው ።

የሶሻሊስት የዕድገት ጎዳናን በሚመለከት የሚጽፉ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ተከታዮች አብዮታዊ ዲሞክራቶች የሠራተኛውን መደብ ሊተኩ ይችላሉ የሚል አመለካከት በፍጹም የላቸውም ። የዕድገት አቅጣጫውን የሚወስነው የተንታኞቹ ምርጫ ፥ ወይንም አስተሳሰብ ሳይሆን በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለው ተጨባጭና ሕሊናዊ ሁኔታ ነው ። ከዚህ አንፃር የማሌ ምሁራን ሚና ከተቻለ በርግጥ የወዝአደሩ የበላይነት ከመጀመሪያ እንዲመጣ ይደግፋሉ ። በማይቻልበት ቦታ ደግሞ ለወደፊት እንዲቻል አስፈላጊ ሁኔታዎች ስለሚሟሉበት ዘዴ የትግል አቅጣጫውን መቀየስ መሆን አለበት ።

ሶስተኛው ሂስ የሚመለከተው የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ራሱን እንደ ሶሻሊዝም ወይንም እንደ ሶስተኛ አማራጭ ሥርዓት የሚቆጥሩትንና ወይም በብሔራዊ ወይንም በሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በተከለሰ ሶሻሊዝም የሚተኩትን ነው ። እነኚህ ኃይላት ከተለያዩ መንገዶች የአብዮቱን ዕድገት የሚያጨናግፉ ለሠራተኛው መደብ ታሪካዊ ድል እንቅፋት የሚሆኑ አዝጋሚ አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው ።

የኢትዮጵያ አብዮት በሽግግሩ ሂደት

የኢትዮጵያ አብዮት ፀረ ፊውዳል ፥ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ ቢሮክራት ካፒታሊስት ባሕርይ ያለው መሆኑን ሚያዝያ 12 ፥ 1968 የወጣው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በማያወላውል ሁኔታ ያስረዳል ። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይህን አብዮታዊ ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ ለሶሻሊዝም ሽግግር አስፈላጊውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከውስጥና በውጭ የመደብ ጠላቶቹ ጋር ባደረገው የሞትና የሽረት ትግል መሠረታዊና ጥልቀት ያላቸውን ለውጦች አስመዝግቧል ።

በፖለቲካው መስክ የአመራሩ አብዮታዊነት ፥ የርዕዮተ ዓለሙ ገልጽነት ፥ ማለትም የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የይፋ መመሪያ መሆን ፥ የሰፊው ሕዝብ ንቃትና ተሳትፎ ከፍተኛነት ፥ ይህንንም ለማፋፋም ዲሞክራሲያዊ የሠራተኛና የገበሬ ማኅበራት ዓዋጆች መውጣት ፥ በኋላም የኢሠፓአኮ መከሰት ፤ በኢኮኖሚው መስክ ዋና ዋና የምርት መገልገያዎችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያደረገው ዓዋጅ ቁጥር 31/1967 ፥ ቀጥሎም የአምራቾች የአገልግሎትና የኅብረት ሥራ መመሪያዎች መውጣት ፥ በዚህም የምርት ግንኙነት መለወጥና የመደቦች ሹምሽር መደረጉ ፥ በማኅበራዊ መስክም የተገኙ አኩሪ ውጤቶች ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያለማወላወል ከሶሻሊስትና ተራማጅ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ አድኃሮት ትግልን ማፋፋም የኢትዮጵያን አብዮት በሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ግንባር ቀደም ቦታ ሰጥተውታል አብዮቱ ሽግግሩን የሚያመቻቹ ጥልቅ

የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ለውጦችን አስገኝቷል ። የለውጡን ስርነቀልነት ስናጤን ፤ አብዮታዊት ኢትዮጵያን በ1960ዎቹ በአፍሪካ ምድር ከተከሰቱት የሶሻሊስት ፈለግ ምሳሌዎች ጋር ማወዳደር ሙሉ በሙሉ ትክክል አይሆንም ።

በታኅሣሥ 1973 የወጣው የ«መስከረም» መጽሔት የኢትዮጵያ አብዮት በሽግግሩ ሒደት የሚገኝበትን ሥፍራ ሲጠቁም ፤ «አብዮቱ አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ የተገኙት ድሎች ሥር እየሰደዱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከመጠናከር አልፎ ሶሻሊስታዊ ጠባይ እየያዘ በመምጣት ላይ ነው ፤ »[31] ብሎ ነበር ።

በእርግጥ በኢትዮጵያ እስካሁን የተደረጉ ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች፣በእነሱም መንመደርደሪያነት ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የተተመለው ስትራቴጂ የግቡን ጥያቄ ብሩህ ያደርገዋል ። እነዚህ ተጨባጭ ማረጋገጫዎች ስላሏቸው አብዮታውያንና በሰፊው ሕዝብ በድንግዝግዝ ሳይሆን ግልጽ በሆነ ጉዳና፣በጥርጣሬ ሳይሆን በቆራጥነትና በልበ ሙሉነት ወደመጨረሻው ድል በመጓዝ ላይ ናቸው ።

ይሁን እንጂ ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መጠናቀቅና ወደ ሶሻሊስት ግንባታ ለመሸጋገር ዋስትናው የማሌ ፓርቲ መኖር ነው ። በዚህ ሽግግራዊ ሂደት የሕሊናዊ ሁኔታ መሟላት እጅግ ወሳኝ ስለሆነና ፣ በፓርቲ ምሥረታ ጥያቄ አብዮቱ የደረሰበትን ደረጃ ማጤኑ አስፈላጊ ነው ። በዚህ ረገድ በጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቆራጥ አመራር የኢሠፓአኮ መከሰትና እንቅስቃሴ መጀመር ከፍተኛው ድል ነው። የኢትዮጵያ አብዮታውያን ያለማሌ ፓርቲ ሽግግርን አጠናቅቆ የሶሻሊስት ግንባታን እውን ማድረግ እንደማይቻል ስለተገነዘቡ ኢሠፓአኮን መሠረቱ ። ስለዚህ ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ ያለጥርጥር እውን ለማድረግ የኢሠፓአኮ ተልዕኮ መሳካት ወሳኝ እንደመሆኑ ፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴ ዋና ዋና ነጥቦች ማጤኑ ጠቃሚ ነው ።

<u>የኢሠፓአኮ የታወቁ ጥንድ ዓላማዎች</u> [36]

አንደኛ ፤ በሰፊው ሕዝብ መካከል የማሌ ፍልስፍና እንዲሰርጽና እንዲሠራጭ ማድረግና ሁለተኛ ፤ ፊውዳሊዝምን፣ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ደምስሶ ጨርሶ አዲሲቷን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመመሥረት ኅብረተሰቡን ወደሶሻሊዝም ብሎም ወደ ኮሚዩኒዝም የመምራት ተልዕኮ ያለውን በማሌ መርሆች ላይ የተመሠረተ የሠርቶ አደሮች ፓርቲ እንዲመሠረት ማድረግ ነው ።

ኢሠፓአኮ እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ በማድረጉ አኳያ የጉዞ ጉዳናውን የጀመረው በሦስት ምዕራፎች ከፋፍሎ ነበር ። እነዚህም የዝግጅት ወቅት ፤ በአንደኛ ጉባዔው የተጀመረው የእንቅስቃሴ ወቅትና የፓርቲ መዳረሻ ወቅት በተሰኙ የተግባር ክንውኖች የተከፈሉ ናቸው ።

አንደኛው ምዕራፍ ኢሠፓአኮ የውስጥ መመሪያዎችን ያዘጋጀበት ወሳኝ የአመራር አካላትን ያሰየመበት ፣ የየዘርፉን የሥራ ዕቅዶችና አስፈላጊ የመነሻ ሁኔታዎችን በማሟላት ለአንደኛ ጉባኤና እንዲሁም ለዘለቄታው ተግባሩ ወሳኝ ዝግጅት ያደረገበት ነው ።

ሁለተኛው ምዕራፍ የማሌ ርዕዮተ ዓለም በዕቅድና በቅንጅት በተለያዩ ስልቶች እንዲሠራጭ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ፤ የምልመላና የማደራጀት ተግባር የተካሄደበትየአመራር ልምድም የተቀሰመበት ወቅት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ፣ ማለትም ከአንደኛ እስከ ሁለተኛው ጉባኤ ድረስ ኢሠፓአኮ ስድስት መደበኛና አንደኛ ልዩ አስቸኳይ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በማካሄድ አስፈላጊ ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ድርጅታዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስትራተጂና ስልቶች በመቀየስ አመራር የሰጠበት ወቅት ነው ።በዚህ ረገድ የማዕከላዊ ኮሚቴው ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀየሳቸው መሪ ሐሳቦች ታሪ

Digitized by Google

ካዊና ለዘለቄታዊ የግንባታ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው ። [33]

ሦስተኛው ምዕራፍ ገጽ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት እንደተገለጸው «ኢሠፓአኮ ድርጅታዊ አቋሙን በመጠንም ሆነ በጥራት ከፍ በማድረግ ርዕዮተ ዓለማዊና ድርጅታዊ አመራርን ብቃት ባለው ሁኔታ የሚሰጥበት ወቅት ነው ። ይህም ማለት« በሠርቶ አደሩ ሕዝብ መካከል ዘልቆ በመግባት ለፓርቲው ሕልውና መረጋገጥ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን በተግባር የሚያስመሰክርበት የተልዕኮው የመጨረሻ ደረጃ ነው ። » [34]

ከዚህም በላይ በማናቸውም መንግሥታዊ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ አባላት የኢሠፓአኮን አመራር ለማስፈጸም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ያለባቸው ወቅት ነው ።

ይህ የፓርቲው መዳረሻ ወቅት ለሚመጣው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ዕውን መሆን አስፈላጊዎቹ ድርጅታዊና አስተዳዳራዊ ሁኔታዎችን የማመቻቸቱ ተግባር ከፍተኛ ትኩረት ማግኘት ያለበት ወቅት ነው።እንድ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት አመራር ሰጭ የማሌ ፓርቲ ፣ ለአብዮታዊ ግንባታ ምቹ በሆነ ቀልጣፋ መዋቅርና ታማኝ ካድሬዎች የተደራጀ መንግሥታዊ ዘርፍና በዲሞክራሲያዊ መርሆች የተመሠረቱ ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅቶች ያስፈልጉታል። ስለሆነም ኢሠፓአኮ ራሱን በሐቀኛ አብዮታውያን የማደራጀቱን ተግባር በጥልቀት ከመቀጠሉ ጋር ለዓላማው ተፈጻሚነት ወሳኝ መግሪያዎች የሆኑትን መንግሥታዊ አካሎችና ተሳትፎአቸው በየአቅጣጫው እየሰፋ መሔድ ያለበትን ሕዝባዊ ድርጅቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ የመዋቀራቸውን ጉዳይ እንደየቅደም ተከተሉ ማረጋገጥ ይኖርበታል ማለት ነው ።

ይህንኑ በማስመልከት የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ «ለወደፊቱ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ አመራር አመች ሁኔታ እየተፈጠረ እንዲሄድና የተቀላጠፈ መንግሥታዊ አሠራር እንዲሰፍን በመንግሥታዊ አካሎች አስፈላጊዎች የመዋቅርና የአፈጻጸም ለውጦች እንዲደረጉ [35] የሚል ውሳኔ አሳልፎአል ። ይህንን የጉባዔውን ውሳኔ በሥራ መተርጐም ወደሶሻሊዝም ለሚደረገ ሽግግር ወሳኝነት አለው ። የፓርቲን አመራር ለማስፈን በተለይ የአስተዳደሩ ዘርፍ በመዋቅሩና በአሠራሩ በሰው ኃይልም የዓይነት ለውጥ ማድረግን ይጠይቃል ። ለአብዮታዊና ለቀልጣፋ አሠራር የማይበጁ ጉኖችና ቢሮክራሲያዊ ልምዶች እየተወገዱ በሥፍራቸው ቀልጣፋ መዋቅሮችና አብዮታዊ ልምዶች መተካት ይኖርባቸዋል ። ይህም ሊከናወን የሚችለው መዋቅርና አሠራር በመለወጥና በየደረጃው ፓርቲው ዓላማውን ያለማወላወል በተግባር የሚተረጉሙ ቆራጥ ካድሬዎችን በቁልፍ ቦታዎች ሲያስማራ ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነት ካድሬዎች ከአድርባይነት የፀዱ ፣ ድርጅቱ ራሱ በጥራት የኮተኮታቸው ፣ ከነባር ባለሙያዎች በእርግጥ ወደ ማሌ አመለካከት የተሸጋገሩና በተግባር የተፈተኑ መሆን ይኖርባቸዋል ።

ፓርቲውን ዕውን አድርጐ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ ከባድ ትግልን የሚጠይቅ ሥራ ነው ። ስለዚህም አብዮታውያን በየዕድገቱ ደረጃ የመደብ ትግል ይዞ ያለውን ቅርጽና የኃይሎችን አሠላለፍ በትክክል መገምገም ይኖርባቸዋል ። ዛሬ የአብዮታችን ዋነኛ ቅራኔ የተንኮታኮተውን ፊውዳሊዝምን ለመመለስ ወይም ላለማስመለስ የሚደረግ ትግል አይደለም ። በእርግጥ የፊውዳሊዝም ናፋቂዎች ለትግሉ የተለመደውን አድኃሪ አስተዋጽኦ ያድርጉ እንጂ ዋናው ቅራኔ በአንድ በኩል ለካፒታሊስቱ የዕድገት ፈለግና ለግል ጥቅማቸው በቆሙ ፣ (በኢምፔሪያሊዝም ረዳትነት ከቢሮክራሲያዊ አሻጥር ጀምሮ እስከነገንጣይነት ድረስ አብዮቱን በሚፈታተኑና) በሌላው ወገን ደግሞ የእነዚህ ተቃራኒ በሆኑ ለሐቀኛ የማሌ ፓርቲ ምሥረታ ለሶሻሊዝም ልዕልና በቆሙ አብዮታውያን ኃይሎች ማለትም በሠራተኛ ፣

Digitized by Google

በገበሬውና በአብዮታዊ ምሁራን ግንባር መካከል ያለው ትንቅንቅ ነው ።

ትግሉ በአየር ላይ ያለ ሳይሆን በየዕለቱ የሚካሄድ በጥቃቅንና በግዙፍ ፀረ አብዮት ተግባሮች የሚገለጽ ተጨባጭ ሂደት ነው ። ይህንኑ በማስመልከት ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባለፈው የሚይዱይ የፖሊሲ ንግግራቸው የሚከተለውን ብለዋል ፣ «የሥራ ሰዓት አይከበርም ፣ የግል ጥቅም አሳዳጅነትና ሽፍጥ አልተወገደም ፣ ብዙዎች በደምና በላባቸው አገራቸውን ለመለወጥ ሌት ተቀን ሲማስኑ ሌሎቹም ደግሞ እራሳቸውም አልተለወጡም ። አልፎ ተርፎም የአድኃሪውን ርዕዮተዓለም ሸክማቸውን ባላቃለሉት ዘንድ የቀኝ አዝማሚያዎች የሚከሰቱባቸው ሁኔታዎችም ይታያሉ ። » 36

አንድ በኋላቀር ኢኮኖሚውና ባህላዊ ሁኔታ የሚካሄድ አብዮት ዲሞክራሲያዊ ደረጃውን በሚገባ አጠናቆ ወደ ሶሻሊስት ግንባታ እንዲሸጋገር ማድረግ ከባድና እልህ አስጨራሽ የሆነ ትግልን የሚጠይቅ ሂደት ነው ። ኋላቀርነት ብዝበዛና አርጌ ሥርዓቶች በጥላቻ ብቻ አይጠፉም ። ሶሻሊዝምም በመወደድ ብቻ አይከሰትም ። አርጌውን ሥርዓት ገርስሶ አዲሱን ለማምጣት ሳይንሳዊ የግንባታ መርሆችን በቆራጥነትና በከባድ ዲስፕሊን በተግባር ማዋሉን ይጠይቃል ። በየዕድገት ደረጃም የመደብ ትግልን ቅርጾች በማጤን አብዮቱ ወደፊት እንዲገፋ አስፈላጊውን ስዋቶች መቀየስን ይጠይቃል ። በኢትዮጵያ ሁኔታም የኢሠፓአኮ ሁለተኛ ጉባኤ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ሳይዛነፉ ተግባራዊ ለማድረግ ትጥቅን ማጥበቅ ወሳኝነት ያለውና አብዮታውያን በሙሉ መረባረብ ያለባቸው ጉዳይ ነው ።

ማጠቃለያ ፣

ቀደም ሲል እንደተመለከተው ስለሶሻሊስት ፈለግ የዕድገት ጉዳና የቀረቡት ሳይንሳዊ ሥነ ጽሑፎች በማሌ ፍልስፍና መሠረት የሶሻሊዝም ድል የማይቀር የታሪክ ዕድገት ሕግ መሆኑን ያረጋግጣሉ ። ስለሽግግሩ ሁኔታም ሶሻሊዝም ከዳበረ ካፒታሊዝም በቀጥታ እንደሚገነባና ከ«አማካይ» ካፒታሊዝምም በወዝ አደር ፓርቲ አመራር አስፈላጊዎቹ ዲሞክራሲያዊ ለውጦች ታክለው ሶሻሊስታዊ ግንባታ ሊከናወን እንደሚችሉ ያስረዳሉ ።

ከዚህም በተጨማሪ በኋላቀር አገሮች የሶሻሊስት አብዮት ፣ 1/ ከፀረ ኢምፔሪያሊስት ፣ ከዲሞክራሲያዊና ከአርነት ትግል በቀጥታ በማሌ ፓርቲ አመራር ሊጀመርና ሊዳብር እንደሚችል ፣ 2/ የቅድመ ካፒታሊስት ኋላቀርነት በሰፈነበትም ሁኔታ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች አልፎ ሶሻሊዝምን ለመገንባት እንደሚችል ያስረዳል ። ይህም በተለያዩ ምሳሌዎች የተረጋገጠ ነው ።

በኋላቀር አገሮች የሚካሄድ አብዮት የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ወይም የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ ወደ ሶሻሊዝም ሊሸጋገር ይችላል ።

አመራርን በሚመለከት በኋላቀር አገሮች ምሳሌዎች እንደታየው የሽግግር ወቅት በአብዮታዊ ዲሞክራቶች ብሎም በማሌ ፓርቲ ተመርቶ ወደ ድል ሊደርስ ይችላል። በኢኮኖሚውም ዘርፍ በአብዛኛው ኢኮኖሚው ከግል ይዞታ ተላቆ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ወደ ሶሻሊስት ግንባታ የመሸጋገሩ ዓይነተኛ መግለጫ ነው ።

በአጠቃላይ ለሶሻሊስቱ የዕድገት ፈለግ ድል አድራጊነትና ለሶሻሊዝም ግንባታ መጀመር በማሌ ሳይንስ የታነፀ ፣ በወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ የሚመራ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር አስፈላጊነት የማይሻር የማኅበራዊ ዕድገት ሕግ መሆኑን የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ ንድፈ ሐሳብም ሆነ ተግባር ያረጋገጠው ነው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. R. Ulyanovsky, National Liberation, Moscow, (1978), p. 84.
2. Albert Tshume, "The Non-capitalist Road, Africa's Revolutionary way forward", *The African Communist*, No. 52 London, (1972), p. 107.
3. V. G. Solodovnikov, "The Present Stage of the Non-Capitalist Development in Asia and Africa", *Studies on Developing Countries*, No. 74 (Budapest: Center for Afro-Asian Research Of the Hungarian Academy of Sciences 1973), p. 11.
4. *Ibid.*
5. See Ulyanovsky Op. Cit., p. 106.
6. K. Marx ond F. Engels, Selected Works, in three volumes, Vol. 1, (Moscow 1969), p. 92. See also Ulyanovsky, Op. Cit., pp. 88-95.
7. Marx and Engels, Collected Works, Vol. 10, (Moscow: Prog. Pub., 1978), pp. 397-478.
8. Marx and Engels, Selected Correspondence, (Moscow, 1965), p. 111.
9. Marx and Engels, Selected Correspondence, (Moscow: Prog. Pub., 1975), p. 293.
10. *Ibid.*, p. 319.
11. K. Marx and F. Engels, Selected Works in three volumes Vol. 2 (Moscow 1973), p. 404.
12. V. I. Lenin, Selected Works, Vol. 3, (Moscow 1977), p. 408.
13. *Ibid.*
14. V. I. Lenin, Collected Works Vol. 33, (Moscow, 1965), p. 478.
15. The Communist International in Documents (1919-1932), (Moscow, 1932), p. 30 as quoted in Ulyanovsky Op. Cit., p. 97.
16. V. I. Lenin, Selected Works, Vol. 3, p. 408.
17. Gleb Starushenko, Africa Makes a Choice, The Development of Socialist Oriented States, (Moscow: Novosti Press Agency Publishing House 1975), p. 15.
18. *Ibid.*, p. 21.
19. Tshume, Op. Cit., p. 101.
20. K. N. Brutents, National Liberation Revolutions Today, Part One, (Moscow: 1977), p. 72.
21. *Ibid.*, p. 85.
22. *Ibid.*, pp. 89-90.
23. *Ibid.*, pp. 119-120.
24. A. Tshume, "The Non-Capitalist Path in Africa", *The African Communist*, No. 52, (1973), p. 54.
25. Brutents, Op. Cit., p. 259.
26. *Ibid.*, p. 148.
27. V. I. Lenin, Collected Works Vol. 42, (Moscow: 1965), p. 361.
28. Maj Palmberg (ed), Problems of Socialist Orientation in Africa (Uppsada: The Scandinavian Institute of African Studies 1978), p. 31.
29. Starushenko, Op. Cit., p. 116.
30. A. Lerumo, "A Communist Call to Africa", *The African Communist*, No. 75, (1978), pp. 109-110.
31. «የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሶሻሊስት አብዮት አካል ነው» ፣ መስከረም ፣ ቅጽ 1 ፣ ቁ. 2 /1973/ ፣ ገጽ 43
32. የኢሠፓአኮ ማቋቋሚያ አዋጅ ፣ ቁጥር 174 ፣ 1972 ፣ አንቀጽ 5
33. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ፣ የካቲት 1973
34. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ሰነዶችና ውሳኔዎች ፣ ገጽ 8
35. ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 127
36. ሠርቶ አደር ፣ ቅጽ 4 ፣ ቁ. 144 1975 ፣ ገጽ 5

Digitized by Google

የኢኮኖሚ ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም በአብዮቱ ሂደት

— ተክለ ብርሃን ገ/ሚካኤል
— ፋሲል ተፈራ

የኢኮኖሚ«ዕቅድ የኢኮኖሚያዊ ሕጎችን ከቀኔና የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ እድገት በሰዎች ፍላጎት አቅጣጫ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚጠቀም ስልትነው።»[1] ማዕከላዊ ኢኮኖሚያዊ ዕቅድ የሶሻሊዝም ዓይነተኛ ባሕሪ ሲሆን ይህም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ እድገት በግብታዊነት የሚካሔድ አለመሆኑንና እድገቱ እራሱን በአደራጀ ኅብረተሰብንቁ ፍላጎት የሚመራ መሆኑን ይገልጻል ። በመሠረቱ በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ማዕከላዊ ዕቅድ መሠረታዊና እያደጉ የሚሔዱትን የብዙኃኑን የቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የኢኮኖሚ ሀብትን በተቀነባበረ መንገድ ማዕከላዊነት ባለውና ምርትን ለማምረትና ለማሠራጨት አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ እነዚህንም ለእያንዳንዱ የኅብረተሰቡ አባል እንደ ሥራው መጠንና ጥራት ለማከፋፈል ፣ እንዲሁም የብሔራዊ ኢኮኖሚውን የማምረት ዓቅምና ችሎታ በተለይም የማምረቻ መሣሪያዎችን የማምረት ችሎታ ለማዳበር የሚውል የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ልዩ ባሕርይ የሆነ የኢኮኖሚ መምሪያና ማስተዳደሪያ መሣሪያ ነው ።

ለሶሻሊስት ማዕከላዊ የኢኮኖሚ ዕቅድ ምሥረታ በኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ቢያንስ የኢኮኖሚ «መሪ ኃይሎች የሚባሉትን የሚቆጣጠር ሰፊ ሶሻሊስት ይዞታ የመኖርን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ይጠይቃል ።»[2] ስለዚህም የዋና ዋና የምርት መገልገያዎች ሕዝባዊ መሆንና ማዕከላዊ ዕቅድ የሶሻሊዝም ዋነኛ ባሕርያቱ ናቸው ።

ማዕከላዊ ፕላን በሕዝባዊ (መንግሥት) ይዞታ ሥር የዋሉትን የምርት መገልገያዎች በሕዝቡ የማቴሪያልና የባህል ፍላጎቶች ትክክለኛ ቅደም ተከተል መሠረት በማምረት ተግባር ላይ ለማሠማራትና ለማዳበር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር የኢኮኖሚ አስተዳደርና የልማት መሣሪያ ነው ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ምን ይመረታል ? ለማንና በምን ዘዴ

Digitized by Google

ይመረታል? የሚሉት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ምላሻቸውን ሊያገኙ የሚችሉት በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት ነው። ስለዚህም የአንድን አገር ኢኮኖሚ በዕቅድ መምራትና ማስተዳደር ከሶሻሊስት ሥርዓት መፍለቅና መጠናከር ጋር የተያያዘ አዲስ ክስተት ነው።[3]

ይህ ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ የኢኮኖሚ ፕላን መከሰት ከሶሻሊዝም ሥርዓት ምሥረታ ጋር አብሮ የመጣ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፕላን አስፈላጊነት በአያሌ ሳይንሳዊ የምርምር ተቋሞችና ከማርክሲዝም ጨርሰው በራቁ አዝማሚያዎችም ጭምር ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። የበለጸጉት ካፒታሊስት አገሮች ስለኢኮኖሚ እድገት ፕላኖችና ፕሮግራሞች አስፈላጊነት ማውሳት ከጀመሩ ሰንብተዋል። ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በፕላን አማካይነት ለማስወገድ የመሻቱ ጉዳይ የታዳጊ አገሮች ዋነኛ ባሕርያቸው ሆኗል። ዳሩ ግን በተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች የኢኮኖሚ ፕላኖችን በማዘጋጀት በኩል በተወሰኑ ዘዴዎችና ቴክኒካዊ በሆኑ መንገዶች አኳያ ተመሳሳይነት የሚታይ ቢሆንም የእነዚህ ፕላኒንግ ይዘት አንድ አይደለም። በዚህ አቅጣጫ ወሳኝነት ያላቸው ጉዳዮች ዕቅድ የሚካሔድባቸው ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ያለው የፖለቲካ ሥልጣን ባሕሪ ናቸው።

እንደ ማንኛውም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሁሉ የኢኮኖሚ ዕቅድም ሁልጊዜ የመደብ ይዘት አለው። ስለዚህም ፕላኒንግ በማኅበራዊ ሕይወት ማቴሪያላዊ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ሳይሆን በንብረት ግንኙነቶች፣ በልውውጥና በክፍፍል መስኮችም ተፅዕኖ አለው። አብዛኞቹ የካፒታሊስት አገሮች የፕላን ቲዎሪ አዋቂዎች ይህንን የፕላን መሠረታዊ ባሕሪ አያነሱም፤ በፕላኒንግና በአንድ በተወሰነ ሶሺዮ ኢኮኖሚ ሥርዓት መካከል ያለውን የእርስ በርስ መያያዝ አይገልጹም።

የኢኮኖሚ እድገት ፕላን ለማዘጋጀት በአገሩ ውስጥ የሚመረተውን የኢኮኖሚ ምርት መጠንና ዓይነት ለመወሰን መንግሥት በኢኮኖሚ እድገት ሂደትና በብሔራዊ ምርቱ መዋቅር ላይ ተፅእና ማድረግ መቻል ያስፈልገዋል። ይኸውም ለአንድ መንግሥት ፕላን ለማዘጋጀትና የኢኮኖሚ እድገትን ለመምራት ለምሳሌ ብሔራዊ ምርት ለፍጆታና ለከምችት የሚውልበትን መጠን፣ የኢኮኖሚ እድገት መጠንን፣ ኢኮኖሚያዊ ምርት ለማምረቻ መሣሪያና ለፍጆታ ዕቃዎች ምርት የሚውልበትን ሚዛኖች ለመወሰን የሚያስችሉ ነባራዊ መሠረቶች እንዲፈጠሩለት ያስፈልጋል። ይሁንና እነዚህ ሁኔታዎች የሚመሠረቱበት (የሚፈጠሩበት) ቅርጽ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ በምርት ግንኙነቶቹ ጠባይ ይወሰናል።

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚመረተው የምርት ዓይነት የሚወሰነው በገበያ ላይ ባለው በገቢ የተደገፈ ፍላጎት አመልካችነት መሠረት በመሆኑ የምርት አወቃቀር የሚያዘነብለው በቁጥር አነስተኛ ሆኖ ግን ከጠቅላላው ገቢ ከፍተኛ ድርሻ ወደሚያገኘው ወደ ካፒታሊስቱ መደብ ነው። በመሆኑም ለዚሁ ጠባብ ለሆነው የካፒታሊስት መደብ ከሰፊው ወዝአደር መግዛት ኃይል ውጭ የሆኑ በርካታ የቅንጦት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚመረቱ ከመሆናቸውም በላይ፣ የገቢ አደላደሉ እጅግ የተዛባ ከመሆኑ የተነሣ አንዳንዶቹ የኅብረተሰቡ ክፍሎች መሠረታዊ የሆኑ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን እንኳን ለማግኘት የሚያስችል ገቢ አይኖራቸውም። አንዳንድ የካፒታሊስት ሀገሮች ያልተመጣጠነ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ እድገት ሂደት የሚያስከትለውን የዚህ ዓይነቱን እጅግ የተዛባ የገቢ ድልድል በተለይ በመንግሥት ታክስ አማካይነት በጥገና መልክ ለማስተካከል «የደኅንነት» (Welfare) ፖሊሲዎችን ይከተላሉ። ይህ የምጽዋታ ፖሊሲ አነስተኛም ቢሆን የመሸመትን ኃይል የኢኮኖሚ ጉዳት ወደ ደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያሸጋግር መሆኑ ባይካድም፣ ጠባብ በሆነው በካፒታሊስቱ መደብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተው የአመራረት ዘይቤ የሚያስከትለውን

Digitized by Google

ትርፍ የካፒታል የማምረት ዓቅም ሙሉ
በሙሉ በሥራ ለማሠማራትና ሥራ አጥነትን
ጨርሶ ለማስወገድ እንደማያስችል በካፒታ
ሊስት ሀገሮች ያለው ሁኔታ ያሳያል ።

በሶሺያሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ከማ
ኅበራዊ ሥራ የሚመነጨው ፈሰስ ለጥቂት
ግለሰቦች ሳይሆን በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ
ጠቀሜታ የሚውል በመሆኑ (ማለትም የኢ
ኮኖሚ ብዝበዛ ስለማይኖር) ፤ እያንዳንዱ የኅ
ብረተሰቡ አባል የመሥራት መብት ስላለ
ውና በሥራው መጠንና ጥራት መሠረት ስለ
ሚከፈለው ፤ ይህም ክፍያ በአንድ በተወሰነ
ወቅት ቢያንስ ቢያንስ የግለሰቡን መሠረታዊ
ፍላጎቶች ለማርካት የሚያስችለው ስለሆነና
በአጠቃላይም ከሞላ ጐደል የተስተካከለ
የገቢ ድልድል ስለሚኖር ፤ የሚመረተው
የምርትና የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነትና
መጠን የሚወሰነው ገበያ ላይ ባለው «የዶ
ላር ምርጫ» ሳይሆን በማዕከላዊ የኢኮኖሚ
ፕላን አማካይነት በሰፊው ሕዝብ (ማለትም
የፊዚኦሎጂና የመኖሪያ አካባቢ ሁኔታ ፡ ወ
ዘተ ...) መሠረታዊና እያደጉ በሚሔዱ
ተገቢ (Rational) የማቴሪያልና የባህል ፍላ
ጎቶች መሠረት ነው ።

በሌላ በኩል አብዛኞቹ ታዳጊ አገሮች የሚ
ከተሉትን የሶሺዮ ፖለቲካል ፈለግ ከቁጥር
ሳያገቡ የኢኮኖሚ ጥገኝነትን ለማስወገድ ፤
አመራረትን ዘመናዊ ፈር ለማስያዝ ፤ ለሥራ
አጥነት ችግር መፍትሔ ለማስገኘትና እጅግ
ኋላቀር ለሆኑ አካባቢዎች ተመጣጣኝ እድ
ገት ለማስገኘት የታለሙ ብሔራዊ ፕላኖች
ያዘጋጃሉ ። ሆኖም በታዳጊ አገሮች የፕላኒ
ንግ ይዘት ከካፒታሊዝሙም ሆነ ከሶሻሊ
ዝሙ የተለየ ነው ። ልዩነቱም በመሠረቱ
ከዝቅተኛ የምርት ኃይሎች የእድገት ደረ
ጃና ይህም ከፈጠራቸው የተለዩ ሁኔታዎች
የሚመነጭ ነው ። ታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚ
ያዊ ፤ ማኅበራዊ ፤ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ ኋላ
ቀርነታቸውን ለመወጣት በሚያደርጉት
ጥረት የተለያዩ ጠባይ ያሏቸው ችግሮች እን
ደሚያጋጥሟቸው ግልጽ ነው ። ችግሮቹም
የምርት ኃይሎች እድገት ደረጃ ዝቅተኝነት
በብዙዎቹ አገሮች የአገር ውስጥ ከምችት
ምንጭ አነስተኛነት ፤ የገበያ አለመስፋፋትና
በብሔራዊ ኢኮኖሚው የተለያዩ አካባቢዎ
ችና ኢንዱስትሪዎች መካከል ያሉት ኢኮኖ
ሚያዊ ግንኙነቶች ደካማነት ፤ በቴክኒክ ኋላ
ቀር የሆኑና ምርታማነታቸው ዝቅተኛ የሆነ
ኢኮኖሚያዊ ክፍሎች ገነው መገኘት ፤ የሠ
ለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ፤ ከዓለም አቀፍ
ካፒታሊስት ገበያና ሞኖፖሊስቶች ጋር ያለ
ው ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ወዘተ ...
ናቸው ። በዚህም የተነሣ የገበያ ሁኔታ
(market mechanism)ማለትም የማምረ
ትን ሂደት በሚቆጣጠሩ ግብታዊ ኃይሎች
ተፅዕኖ አማካይነት የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድ
ገት የማስገኘት ዓቅም እጅግ ደካማ ሊሆን
ችሏል ። በኢኮኖሚው የተጠናከረና የተደ
ራጀ ብቸኛ መደብ ባለመኖሩም በማኅበራዊ
ምርት ሂደት ውስጥ ለመንግሥት ጣልቃ
ገብነት በር ሊከፈትለት ችሏል ። ስለሆነም
መንግሥት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት
ለመቆጣጠር በኢኮኖሚያዊ ፕላን አማካኝ
ነት የመጠቀም ዕድል ሊፈጥርለት ችሏል ።
ሆኖም የተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገት ለማ
ስገኘት ሲባል በፕላን ላይ ለተመሠረተ እድ
ገት የሚደረገው ሽግግር ባለማቋረጥ የተቀ
ናበረ መልክ ይዞ ሊካሔድ የሚችለው በአር
ጌዎቹ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መዋቅሮች
ላይ የሚካሔደው ለውጥ እየተስፋፋና ሥር
እየሰደደ በሔደ ቁጥር ነው ። እንዲህ ዓይነ
ቱን ሥርነቀል የማኅበራዊና የኢኮኖሚ እድ
ገት አቅጣጫ መከተልና ተግባራዊ ማድረግ
ሶሻሊስት የእድገት ፈለግን የሚከተሉ ታዳጊ
አገሮች የተለየ ባሕሪ ነው ። የፕላኒንግ መር
ሆዎችና ይዘቶች በታዳጊ አገሮች በሰፊው
መስፋፋት የኢኮኖሚና የሶሻል ኋላቀርነት
የመወጣቱን ተግባር ነባራዊ ግዴታ የሚያ
ንፀባርቅ እንጂ የይስሙላ ወይም የአንድ
ሰሞን ፋሺን ሆኖ አይደለም ።

በአሁኑ ጊዜ ሥርነቀል ማኅበራዊና ኢኮ
ኖሚያዊ ለውጦች በሚያካሔዱ ታዳጊ አገ
ሮች ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ለማ

Digitized by Google

ሰኀኘትና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ያለው ብቸኛ ዘዴና መሣሪያ ኢኮኖሚውን በሳይንሳዊ ፕላን አማካይነት መምራት ነው ። ስለሆነም ፕላኒንግ የተመጣጠነና የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገት ማስገኛ ብቁ መሣሪያ እንዲሆን ከተፈለገ የተወሰኑ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩት ይገባል ማለት ነው ። የተሰበጣጠረና የተወገረገረ የኢኮኖሚ መዋቅር ሰፍና በሚገኝበት ሁኔታ የሶሻልና የኢኮኖሚ ፕላን ዝግጅት ቅድመ መሠረቶች የመፍጠሩ ተግባር ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ለውጥ ማለትም ማኅበራዊ መሆን ፥ ከማኅበራዊ ሀብትና ብሔራዊ ገቢ ክፍፍል ለውጦች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ባጭሩ በታዳጊ አገሮች የፕላኒንግ መርሆዎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅድመ ሁኔታዎች የሚፈጠሩት ከሁሉም በላይ በሚከተሉት እርምጃዎች አማካይነት ነው ።አንደኛ ፥ የትላልቅ ካፒታሊስቶች ተቋሞች ማኅበራዊመሆን ወይም ለእንቅስቃሴያቸው የተሟላ የመንግሥት ቁጥጥር መመሥረት ፥ ሁለተኛ ፤ የቁሳዊ ምርትን ሂደት የሚያረጋግጡ ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ የመሠረተ ልማቶችን ዘርፍ መውረስ (nationalization) ፤ ሦስተኛ ፤ የኢኮኖሚውን መሪ አካሎች (Commanding heights) ወደ መንግሥት እጅ ማዞር ፥ ማለትም በባንክ፥ ብድር ሥርዓት ፥ በገንዘብ ልውውጥና በውጭ ንግድ መንግሥታዊ ሞኖፖል መመሥረት ናቸው ። [4]

የተሰበጣጠረ የኢኮኖሚ መዋቅር ባለበት ሁኔታ ፥ የምርት ኃይሎች እድገት ደረጃ ዝቅተኛ በሆነበትና አነስተኛ ሸቀጥ አምራቾችና ከፊል ተፈጥሮአዊ ኢኮኖሚዎች ዋነኛውን ሚና በሚጫወቱበት ፥ የሸቀጥ—ገንዘብ ግንኙነት ባልተስፋፋበት ምርትንና ዝውውርን ማኅበራዊ የማድረጉ ዕድል በጣም የተወሰነ በመሆኑ ፕላኒንግ ብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ ሚዛኖችን (Proportion) ለመመሥረት እንደ ብቸኛ ዘዴ ሊያገለግል አይችልም ። በኢኮኖሚ እድገት ላይ ፕላን የሚኖረውም ተፅዕኖ በሶሻልና በኢኮኖሚ መሠረቶች መኖር ላይ ብቻ የሚመሠረት አይደለም ። ሌሎች እንደ ፕላኑ ዝግጅትና ዓይነት (quality) በፕላን ላይ መንግሥት የሚኖረው አስተያየት ወዘተ . . . የበኩላቸውን ተፅዕኖ ያደርጋሉ ።

የፕላን ዝግጅት ብቃትና ጥራቱ እያደገ የሚሔደው ፕላኑ በብዙኀኑ ሕዝብ ጥቅም ላይ ሲመሠረትና በፕላን ዝግጅትም ሆነ አፈጻጸም በኩል በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሆ ላይ የተመሠረተ ሰፊ ተሳትፎ ሲኖር ነው ።

ከአብዮቱ ወዲህ በኢትዮጵያ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ጽንሰ ሐሳቦችና መርሆዎች የሚያንፀባርቁ እርምጃዎች ተወስደዋል ። መሬትና ከዚህም የሚመነጨው ገቢ ከጥቂት የመሬት ከበርቴዎች ወደ ሰፊው ገበሬ እጅ ተዛውሮአል ። በተመሳሳይ መንገድ መጠኑ አነስተኛም ቢሆን የነበረው ዋና ዋና የግል ካፒታልና ከዚህ የሚገኘው ገቢና ፈሰስ ወደ መንግሥት ተዛውሮአል ። በመንግሥት ለሚቀጠሩ ሠራተኞች የከፍያ መነሻ የተደነገገ ሲሆን ፤ ከዚህ ቀደም የጡረታ መብት የሌላቸው ሠራተኞች ይህ መብታቸው ተከብሮላቸዋል ።በዝቅተኛ የደመወዝ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሠራተኞችም የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎአል ።

ይህ የሀብትና የገቢ አደላደል የጠቅላላ ፍላጎትን ቅርጽ ለውጦታል ። ከቅንጦት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ይልቅ የመሠረታዊ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (ማለትም ምግብና ውሃ፥ልብስ፥ መጠለያ ፥ ማብሰያ፥ ጤና፥ ትምህርት ፥ ወዘተ ...) ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮአል ። በአሁኑ ጊዜ የዚህን ፍላጎት መጠንና ዓይነት እንዲሁም ፍላጎቱን ለማሟላት መፈጠር ያለበትን የማምረት ዓቅም በመገምገም የማምረት ተግባሩንና የልማት ሥራዎችን የሚያካሒዱት ጥቂት ካፒታሊስቶች ሳይሆኑ የምርት መገልገያዎች ባለቤት የሆኑት መንግሥትና ሰፊው ሕዝብ ናቸው።ይህንን ለማድረግ የሰው ኃይልን ፥ ገንዘብንና ማቴሪያልን በአገር አቀፍ ደረጃ በተቀነባበረ

Digitized by Google

መንገድ ማንቀሳቀስና በምርት ተግባርና በልማት ሥራዎች ላይ ማሠማራት ያስፈልጋል። ይህም ሊሆን የሚችለው በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚዘጋጅና በሥራ የሚተረጐም ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው ሁለአቀፍ ማዕከላዊ የኢኮኖሚ ፕላን ሲኖር ብቻ ነው ።

በመሆኑም የዚህ ጽሑፍ ዓቢይ ዓላማ የአብዮቱ ጉልህ ውጤት ስለሆነው የማዕከላዊ ፕላን ጽንሰ ሐሳብ ፣ ዝግጅትና አፈጻጸም በአጠቃላይም በአሁኑ ጊዜ ስለደረሰበት የእድገት ደረጃ አበይት ፍሬ ሐሳቦችን የያዘ ትንተና ማቅረብ ነው ። ጽሑፉ በቅድመ አብዮት ይዘጋጁ የነበሩትን የይስሙላ ፕላኖች ወደኋላ መለስ ብሎ ለማስታወስ ያህል በአጭሩ ከተመለከተ በኋላ ፣ ከአብዮቱ ወዲህ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት ማዕከላዊ ፕላን ማስፈለጉን፣ የተቀየሱትን አበይት የልማት ዓላማዎችንና ስትራቴጂ ፣ የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ ዓላማዎችንና ስልቶችን ፣ የፕላን ድርጅታዊ መዋቅር ፣ የዕቅድ ዝግጅትንና አፈጻጸምን አጠቃላይ መልክ የምርት ዘመቻው ያስገኛቸው ውጤቶችንና የተከሰቱትን ችግሮችና ድክመቶች የአሥር ዓመት ልማት መሪ ዕቅድን ለመመርመር ይሞክራል ። በመጨረሻም የተነሱትን ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን በማጠቃለል በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት ሶሺያሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባት የፓርቲ ምሥረታ የሚኖረውን ወሳኝ ሚና ይጠቁማል ።

ቢቀድሞው ሥርዓት ይዘጋጁ የነበሩት የይስሙላ ፕላኖች

ከአብዮቱ በፊት ይዘጋጁ የነበሩት የወረቀት ፕላኖች በፊውዶ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሕግጋትና ኃይሎች ያዘግም የነበረው የሀገሪቱ ኋላቀር ኢኮኖሚ ያሳየውን አነስተኛ እድገትም ሆነ ወደኋላ ማፈግፈግና መንሸራተት ያሳያሉ ። የሚወጡትን ዕቅዶች በተግባር ለመተርጐም የሚያስችል ምንም ዓይነት በሕግ የተደገፈና ሥርዓት ያለው ድርጅታዊ መዋቅርናአስተዳደርአልነበረም። በአብዛኛውም የወረቀት ፕላኖች ሊባሉ የበቁትም በዚሁ ምክንያት ነው። ለምሳሌ በመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በዓመት በ3.7 በመቶ ብቻ እንዲያድግ ታቅዶ፣ አፈጻጸሙ ግን ከዚህ በታች ሆኖአል።[5] ዕቅድ በማስፈጸም በኩል የነበረውን ደካማና የተዘበራረቀ ድርጅታዊ ሁኔታን በማስመልከት በሁለተኛው የአምስት ዓመት ፕላን ውስጥ የሚከተለው ተገልጦአል፤ «በልዩ ልዩ ሚኒስትሮችና የመንግሥት መ/ቤቶች መካከል የነበረው የሥራ መተባበር ምን ጊዜም አጥጋቢ አልነበረም ።»[6] መጀመሪያውንም ዕቅድ ለማውጣት የታሰበው መሠረታዊ የልማት ለውጥ ለማስገኘትና የሰፊውን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሳይሆን (ይህ በነበረው የሥልጣንና የሀብት ይዞታ ጨርሶ ሊሳካ አይችልም ነበር፤ የውጭ ዕርዳታ (በተለይ ከኢምፔሪያሊስት ሀገሮች) ለማግኘትና በተጨማሪም በታዳጊ ሀገሮች ዘንድ በዚያን ጊዜ የልማት ፕላን መንደፍ የዘመኑ ፈሊጥ ስለነበረ ነው።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ዋና ዋናዎቹ የሀብትና የገቢ ምንጮች በጥቂት ግለሰቦች ይዞታ ስለነበሩና ባለንብረቶቹ የሚያስመርቱት ዕቅዱን ተከትለው ሳይሆን በውጭ ሀገርና በአገር ውስጥ ትርፍን ለማግኘት ስለነበረ ፣ ኢኮኖሚው የሚመራው መንግሥት በሚያወጣቸው ዕቅዶች መሠረት አልነበረም ። እንዲያውም ዕቅዶቹ ለገዢው መደብ ፍላጎቶች ተገዢዎች ነበሩ ማለቱ ይቀላል ። በመሆኑም ለምሳሌ በመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን ከጠቅላላው ኢንቨስትመንት 60 በመቶው በአብዛኛው ከበርቴዎች በከተሞች ውስጥ ሠርተው ለግል ጥቅማቸው ለሚያከራዩአቸው ቤቶችና ቪላዎች የተመደበ ነበር ።[7] በአጠቃላይ ከ15 ዓመታት የይስሙላ ፕላኖች በኋላ ሰፊው ሕዝብ በተለይም የገጠሩ ገበሬ ከረሃብና ከእርዛት ሊላቀቅ አልቻለም ነበር ። በአለፈው ሥርዓት ማክተሚያ ዋዜማም ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሕዝብ

Digitized by Google

በረሃብ አለቀ ። ከ15 ዓመታት የፈጀ ፕላኖች በኋላ ሀገሪቱ ከኋላ ቀርነት ልትላቀቅ የምትችልበት የተስፋ ጭላንጭል እንኳን ለማየት ሳይቻል ቀረ ። ይህ ሁኔታ ይቆይ እንጂ ሊዘልቅ አልቻለም ነበር ። በምዝበራ ላይ ረሃብ ፣ በረሃብ ላይ ምዝበራ የተደራረበበትና የተፈራረቀበት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በእምቢታ በመነሣት አብዮቱን አቀጣጠለ ፤ በአብዮቱም ሂደት ብዙ ድሎችን ተጐናፀፈ ።

ከአብዮቱ ወዲህ ለኢኮኖሚ ግንባታ ማዕከላዊ ፕላን ማስፈለጉ

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የተወሰዱ ልዩ ልዩ አብዮታዊ እርምጃዎች የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በዕቅድ እንዲመራና የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፈር እንዲይዝ ለማድረግ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል ። ከእነኚህ እርምጃዎች ውስጥ መሬት ላራሹ መሰጠቱ ፣ ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ፣ የንግድ ተቋሞች ፣ ባንኮችና የመድን ድርጅቶችና ሌሎች ተቋሞች የመንግሥት ንብረት መደረጋቸው ፣ አዳዲስ የመንግሥት አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች መቋቋማቸው ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ የመኖሪያ ቤቶች የመንግሥት መሆናቸው፣ አነስተኛ ገቢ ለሚያገኙ ሠርቶ አደሮች የደመወዝ ጭማሪ መደረጉ፣ የጡረታ መብታቸው መከበሩ፣ የደመወዝ መነሻ መደንገጉና ሌሎችም ይገኙባቸዋል ።

የሶሺያሊስትን ፈር የሚከተል ኢኮኖሚ በአብዛኛው የሚንቀሳቀሰውና የሚመራው በሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ሕጋጋት መሠረት ነው ። ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አ ብ ዮ ት በሚካሔድበት ሀገር የኢኮኖሚ እድገት አንቀሳቃሽ ኃይልና መሣሪያ ከሆኑት መካከል ማዕከላዊ ፕላን ከፍተኛ ሥፍራ ይዞ ይገኛል።

የሶሺያሊስቱን ፈር በተከተለ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የሶሺያሊስቱ ይዞታ ምርትን የሚያመርተው ፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን የሚያቀርበውና የኢንቬስትመንት ተግባርን የሚያካሂደው በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ እንዳለው ሁኔታ በገበያ ኃይሎች ቀስቃሽነትና ዳኝነት ግላዊ ትርፍን ለማካበት ሳይሆን የብዙኃኑን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት በሚወሰዱ ውሳኔዎችና እነዚህን በተግባር ለመተርጐም በሚደረገው የተቀነባበረ ጥረት ነው ። በመሆኑም ምን ይመረት ? ለማን ይመረት ? እንዴት ይመረት ? የሚሉት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ምላሻቸውን የሚያገኙት በግል ጥቅምና ትርፍ የሚመሩ ግለሰቦች የገበያውን አዝማሚያ በማየት በሚያደርጓቸው ውሳኔዎች መሠረት ሳይሆን ፣ የብዙኃኑ ቀዳሚ ፍላጎቶች ምንድን ናቸው ? እነዚህንስ ፍላጎቶች ለማሟላት ምን ምን ምርቶችና አገልግሎቶች ፣ በምን የጥራት ደረጃ ፣ መጠንና ቅንጅት መመረትና መቅረብ አለባቸው ? እነዚህን ለማምረትስ ሀገሪቱ ያሏት ሀብቶች ምንድን ናቸው? እነዚህ ሀብቶች በምን ዓይነት ቅንጅት በምርት ተግባር ቢሠማሩ ምርታማነትን ፣ የሥራ ስምሪትንና ሌሎች የኢኮኖሚ ዓላማዎችን ሊያሟሉ ይችላሉ ? የሚሉ አበይት ጥያቄዎች በማዕከላዊ ፕላን ድርጅታዊና የአስተዳደር ሥርዓት አማካይነት ከተተነተኑና ከተገመገሙ በኋላ የሚወሰዱትን ውሳኔዎች በተግባር በመተርጐም ነው ።

በኢትዮጵያ ሶሻሊዝምን ለመገንባት በተወሰዱ እርምጃዎች አማካይነት መንግሥት በኢንዱስትሪ ፣ በሀገር ውስጥ ንግድ ፣ በወጭና በገቢ ንግድ ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ ያለው ይዞታ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶአል። አሁን ባለበት የእድገት ደረጃ ሰፊና መሠረታዊ በሆነው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ መንግሥት ያለውን ድርሻ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ አዳጋች ቢሆንም ፣ በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚም ቢሆን መንግሥት ያለው ይዞታ ጨምሮአል ። የማዕድን፣ የኃይልና ውሃ ፣ የባንክና ኢንሹራንስ ፣ የትምህርትና የጤና ዘርፎችና ክፍላተ ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ይዞታ ሥር ናቸው ማለት ይቻላል ። እነዚህ የሀብትና የገቢ ምንጮች የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟ

Digitized by Google

ላት በሰፊው ሕዝብ ስም በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ ናቸው ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ከሕዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች በመነሣት ፣ ሀገሪቱ ያላትንና ወደፊት ሊኖራት የሚችለውን ሀብት በመገምገም ፣ በክፍላተ ኢኮኖሚ መካከል ያለውን ዝምድናና ተደጋጋፊነት በማጤን ሀብትን አንቀሳቅሶ በምርት ተግባር ላይ በማሠማራት በጊዜ ሂደት ውስጥ በክፍላተ ኢኮኖሚና በአካባቢዎች መካከል የተመጣጠነ የኢኮኖሚና የሶሻል እድገት ማስገኘት የሚቻለው በማዕከላዊ ፕላን መሪያነት ብቻ ነው ።

በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት በግል ይዞታ ሥር ያለው የአነስተኛ ሸቀጥ ምርት ይዞታውም የወደፊት እድገት የሚወሰነው በጊዜ ሂደት ውስጥ ይህን ክፍል ከአነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በሚያደርሱ የኅብረተሰብአዊ የአመራረትና የአኗኗር ገጽታዎች በሆኑት በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በማደራጀትና በማጠናከር ፣ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ በማዕከላዊ ፕላኑ እንዲታቀፍና ማዕከላዊና ሥርዓት ያለው አመራር እንዲያገኝ ለማድረግ በሚደረገው ያላሰለሰ ጥረት ነው ።

በአጠቃላይ ዋና ዋና የሀብት ምንጮች የሕዝቡን ፍላጎት በሚወክል አብዮታዊ መንግሥት ይዞታ ሥር እንዲሆኑ ከተደረገ በኋላ የአመራረት ዘይቤው የሚከተለው መርህ «ግላዊ ትርፍን ማካበት» የሚለውን ሳይሆን «ምርት ለሰፊው ሕዝብ ጠቀሜታ» የሚለውን አብዮታዊ መርህ ነው ። ምርት ለሰፊው ሕዝብ ጠቀሜታ የሚለው መርህ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ የሆነው የሶሻሊዝምን ፈለግ በሚከተል ኢኮኖሚ ውስጥ በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት ብቻ ነው ። አብዮታዊ መንግሥትም በኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባት ማዕከላዊ ፕላን አስፈላጊና አማራጭ የሌለው መሆኑን በትክክል በመገንዘብ ነው የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያን በጥቅምት ወር 1971 እንዲቋቋምና ሥራውንም በፍጥነት እንዲጀምር ያደረገው።

ብሔራዊ አብዮታዊ የልማት መመሪያ

ብሔራዊ ኢኮኖሚን በማዕከላዊ ፕላን አማካይነት ለመገንባት መደረግ ካለባቸው ቀዳሚ ተግባሮች መካከል የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ተጨባጭ እውነታ የሚያንፀባርቁ ትክክለኛ ብሔራዊ የልማት መመሪያዎችንና ፖሊሲዎችን ማመንጨት ወሳኝ ሚና አለው ። በዚህ በኩል ከአብዮቱ ወዲህ እንደ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሊወሰዱ የሚችሉት በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ ብሔራዊ ኢኮኖሚውን አስመልክቶ የተጠቀሱት መርሆዎች ፣ የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መግለጫ ፣ የግል ሥራዎችን በሚመለከት የወጣው አዋጅ ፣ በጠ/መምሪያው የተቀየሱት የምርት ዘመቻ ዓላማዎችና ስልቶች በተለይ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በሚመለከት ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ናቸው ።

አብዮቱ ከፈነዳ ከአንድ ዓመት ገደማ በኋላ የሀገሪቱን የወደፊት የልማት ጉዳናና እስትራተጂ ለመንደፍ ጥር 1967 በወጣው የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መመሪያ ውስጥ የሚከተለው አጠቃላይ ዓላማ ሰፍርአል ።

የኢኮኖሚ መመሪያችን የተመሰረተውና የተወሰነው በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ በሚገኘው የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲሆን ፣ ይህም ሁኔታ የሰፊው ሕዝብ ድህነት የሰፈነበት ነው። ሰፊው ሕዝብም ከዚህ ደረጃ ላይ ሊወድቅ የቻለው አንደኛ የሀገሪቱ የማምረቻ ኃይሎች በሚገባ ባለመልማታቸው እና ባለመዳበራቸው ሲሆን ፣ ሁለተኛ ደግሞ የማምረቻ መሣሪያዎች በገዥው መደብ የግል ይዞታ ሥር ከመሆናቸው የተነሳ ባስከተለው የብዝበዛ መዘዝ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብአዊነት /ሶሺያሊዝም/ ግንባር ቀደምና አበይት ዓላማ የማምረቻ ኃይሎችን በማዳበር - የምርት መጠንን በማስፋፋትና የሰፊውን ሕዝብ ብዝበዛ በማስወገድ አገራችንን ከወደቀችበት የድህነት ቀንበር ማላቀቅ ነው።

Digitized by Google

ከዚያም በኋላ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ የሀገሪቱ አበይት የኢኮኖሚ ዓላማዎች በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተጠቃልለው ቀርበዋል ።

የምርት ኃይሉች ተውተብትበው ከታሰሩበት ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም የምርት ግንኙነቶች ጨርሰው ተላቀቀው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲዳብር የሕዝቡም የኑሮ ደረጃ ከፍ እያለ እንዲሄድ ማድረግ፣ ነፃና ጠንካራ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚቻለው የኢንዱስትሪውና የእርሻው ዘርፍ በሚገባ ተቀነባብረው እንዲራመዱ ሲደረግ በመሆኑ፣ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በሶሺያሊዝም ፍልስፍና መሠረት በማጤን የሀገራችንን ዕድገት በተደራጀ መልክ ለቀዶና ለቀናብር በአንድ አጠቃላይ ፕላን መምራት ። ይኸውም የእርሻውን ዘርፍ የብሔራዊው ኢኮኖሚ መሠረት አድርጎ በመውሰድና የሰፊውን ሕዝብ ጊዜያዊ ፍላጉቶች ለማርካት የሚያስፈልጉትን የቀላል ኢንዱስትሪ ዓይነቶች በማስፋፋት በሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት አስፈላጊ የሆነውን ከባድ ኢንዱስትሪ ከአሁኑ በመጀመር ደረጃ በደረጃ ማዳበር።

በጊዜ ሂደት ውስጥ በተለይም ኢሠፓአኮ በሰኔ 1973 ሥራውን በይፋ ከጀመረ ወዲህ ብሔራዊ የልማት ዓላማዎቹና ስትራተጂዎቹ ይበልጥ ጥራት እያገኙ በመምጣት፣ የካቲት 1973 የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ታሪካዊ የኢኮኖሚ ውሳኔዎችን አሳልፎአል ። ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በሚመለከት የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ከፊሎቹ አጠቃላይና ሁል አቀፍ ዓላማዎችን፣ የልማት ቅድሚያዎችን፣ ስትራተጂዎችንና እንዲሁም ሁለገብ የሆኑ ችግሮችን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሔ እርምጃዎችን የሚሸፍኑ ሲሆኑ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ትኩረት ለሚሰጣቸው ክፍላተ ኢኮኖሚ በተመሳሳይ መንገድ ዓላማዎችንና ስልቶችን የሚቀይሱ ናቸው ። በተጨማሪም የውሳኔዎቹ መግለጫ አጠቃላይ ዓላማዎች፣ የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ልማት መርሆዎችን፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚውን አበይት ባሕርይዎችንና የሀገሪቱን የተለዩ የእድገት ዕንቅፋቶች የሚያጠቃልሉ ፖሊሲ አዘል መንደርደሪያዎችን የያዙ ናቸው ።

አጠቃላይ ውሳኔዎቹን በሁለት ዋና አርእስቶች መለየት ይቻላል ። አንዱ ርእስ አጠቃላይ ዓላማዎችን፣ የልማት ቅድሚያዎችንና ስትራተጂዎችን የያዘ ሲሆን፣ ሌላው ለሁለገብ የኢኮኖሚ ችግሮች የመፍትሔ ስልቶችን የሚያጠቃልል ነው ። አጠቃላይ ዓላማዎችን፣ የልማት ቅድሚያዎችን በሚመለከት የተላለፉትን ውሳኔዎች እንደሚከተለው ባጭሩ አጠቃሎ መመልከት ይቻላል ።

በመጀመሪያ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ የሚያስፈልገው የክምችት ምንጭ የግብርናው ኢኮኖሚ በመሆኑ፣ ክፍለ ኢኮኖሚው ይህንን እውን ማድረግ እንዲችል ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥ ፣ የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማስፋፋት የሀገሪቱ የልማት ስልት መሠረት መሆኑን፣ ለዚህም የተጓላ ተግባራዊነት በየጊዜው ለልማት የሚመደበውን መዋዕለ ንዋይ ድርሻ በማሳደግ የተሻሻሉ መሣሪያዎችንና አገልግሎቶችን በማቅረብና አስፈላጊ የሰው ኃይልን በብዛትና በጥራት በማሠልጠኑ በኩል ለአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ተወስኗል ። በሁለተኛ ደረጃ ቅድሚያ የተሰጠው ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ሲሆን ይህም ክፍለ ኢኮኖሚ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ደረጃ በደረጃ በማሳደግ የኢኮኖሚውን የምርት አወቃቀር ለመቀየርና ለከባድ ኢንዱስትሪ መሠረት ለመፍጠር በመነሻው ወቅት የኢንዱስትሪ ልማት ስልቶችን በቀላልና በጎጆ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ላይ እንዲያተኩር ነው ። ቀጥሎም በተከታታይ ለዕደ

ጥበብ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ ት ኩ ረ ት እንዲሰጥ ፣ የምርት ኃይሎችን ለማዳበር ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት በሀገሪቱ ችግሮች ላይ ያተኮሩ በተለይ ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት የሚሰጡ የምርምር ሥራዎች እንዲስፋፉ ፣ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት በሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ሕጎች ላይ መሥርቶ ለመምራት ሶሻሊስት ኅብረተሰብን ለመገንባት በረጅም ጊዜ ዕቅድ መመራት ስለሚያስፈልግ በመዘጋጀት ላይ ያለው የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ በተቀየሰው የልማት ስትራተጂ ላይ እንዲመሠረትና ዝግጅቱ ተጠናቆ ተግባራዊነቱ እንዲፋጠን ፣ የተዘረጋውን የማዕከላዊ ፕላን መዋቅር በየጊዜው በማጠናከርና በማሻሻል በፕላን ዝግጅትም ሆነአፈጻጸም በኩል የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ተግባራዊ እንዲሆንና በመጨረሻም በአሁኑ ጊዜ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የማኔጅሜንት ድክመት ለመወጣትና ለወደፊቱ የግንባታ ሂደት ተገቢውን የማኔጅመንት ድጋፍ ለማስገኘት ምርምር ፣ የአማካሪነት አገልግሎትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን በማቀናጀት የሚካሔድ ተቋም እንዲቋቋም ወስኗል ። [10]

ለሁለገብ የኢኮኖሚ ችግሮች የመፍትሔ ስልቶችን በሚመለከት የተላለፉት ውሳኔዎች ደግሞ የመንግሥትን ገቢና ወጭ በመቀነስ በቁጠባና በቅልጥፍና ማከናወንና እንዲሁም የቁጥጥር ሥራን ማጠናከር ፣ የውጭ ምንዛሪን እጥረት ለመቋቋምና ብሎም ክምችታችንን ለማዳበር የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙልንን ምርቶች መጠን ፣ ዓይነትና ጥራት ማሻሻልና በውጭ ምንዛሪ አጠቃቀማችን ቁጠባን ማጠናከር፣ ሥራ አጥነትን መቀነስ፣ ብኩንነትንና ምዝበራን መዋጋት ፣ የደን ፣ የዱር አራዊትና የተፈጥሮ ሀብታችንን መንከባከብና ማዳበር ፣ የዘላኑን ኅብረተሰብ ኢኮኖሚ ለመለወጥ ፣ የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻልና ለማጠናከር የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚውን ለማልማትና ለማፋጠን፣ የኢነርጂ ክፍለ ኢኮኖሚውን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስችሉ ውሳኔዎች ተላልፈዋል ። [11]

በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መመሪያ ውስጥ የሠፈሩት አጠቃላይ ብሔራዊ የኢኮኖሚ ዓላማዎች ከ1971 ጀምሮ በመዘጋጀትና በመከናወን ላይ ላሉት የአንድ ዓመት የምርት ዘመቻ ዕቅዶች የመመሪያ ፖሊሲዎች ሆነዋል ። በበለጠ ዝርዝር የተላለፉትን የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የኢኮኖሚውሳኔዎች በ1974 እና በ1975 በተዘጋጁት ዓመታዊ የፕላን ዶክሜንቶች ውስጥ የተንፀባረቁ ሲሆን ፣ በመዘጋጀት ላይ ያለውም የ10ዓመት ልማት መሪ ዕቅድ ዓላማዎችና ስልቶች የተመሠረቱት በእነዚህ ውሳኔዎች ላይ ነው ።

ይሁንና ከእነዚህ እስከ አሁን ከተገለጹት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መመሪያዎች መካከል አንዳንዶቹ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ዘርዝር ባለሁኔታ የተነደፉ ሲሆን ፣ (ለምሳሌ የገበሬና የዕደ ጥበብ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መመሪያዎች ፣ የግል ኢኮኖሚው ክፍልና የውጭ ኢንቬስትመንት በኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ የሚኖረው ሚና) አንዳንዶቹ ገና አጠቃላይ የፖሊሲ መመሪያዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ያልተሰጡባቸው (ለምሳሌ የዋጋ ፣ የድጎማ ፣ የደመወዝና የልዩ ልዩ ጥቅሞች ክፍያ) ናቸው ። ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የተጣጣሙ ትክክለኛ ፣ አስተማማኝና ዘለቄታ ያላቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ቀይሶ በሥራ ላይ ማዋል ለኢኮኖሚው ግንባታ የተፋጠነ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መዘንጋት የለበትም ።

በ1971 የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ከተቋቋመ ወዲህ አብዮታዊ መንግሥት የሚቀይሳቸውን አጠቃላይና ብሔራዊ የኢኮኖሚ ዓላማዎችንና ስትራተጂዎችን በቀጥታ በየክፍላተ ኢኮኖሚውና በየዘርፉ በየደረጃው

Digitized by Google

በመመንዘር በድርጊት ፕሮግራሞች እንዲታቀፉ በማድረግ በሥራ መተርጐማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ድርጅታዊ መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ተመሥርቶአል ። በ1971 እስከ 1974 ባለው የአራት ዓመትጊዜ ተዘጋጅተው የተከናወኑት ዓመታዊ የምርት ዘመቻ ዕቅዶች ከመንግሥት የሚመነጩ የኢኮኖሚ መመሪያዎችን በተቀነባበረናማዕከላዊነት ባለው መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ያለውን ልምድና ዕውቀት ይበልጥ አጠናክረውታል ፣ ወደፊትም ሀገሪቱን ለሚጠብቃት ረጅምና ከባድ የኢኮኖሚ ግንባታ ትግል ጠንካራ መሠረት ጥለዋል ።

የብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባህል ዘመቻ ዓላማዎችና ስልቶች ፣ አጠቃላይ ዓላማዎች

የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ በጥቅምት 1971 በአዋጅ ከተቋቋመ ወዲህ በያንዳንዱ ዓመት በተከታታይ የምርት ዘመቻ ዕቅዶች እየተዘጋጁ ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል ። የምርትና የባህል ዘመቻውን ዓላማዎችና ስልቶች ከመመልከታችን በፊት ጠቅላይ መምሪያውን ለማቋቋምና የምርት ዘመቻ ለማካሔድ ለምን አስፈለገ ? የሚለውን ጥያቄ ባጭሩ እንመልከት ።

ባለፈው ክፍል በአጭሩ ለመግለጽ እንደተሞከረው ፣ ሶሺያሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባት ማዕከላዊ ፕላን አማራጭ የሌለው መሣሪያ ነው ። በማዕከላዊ ፕላን የሚመራ የተመጣጠነ ልማት የሶሺያሊዝም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ነው ። ይህንንም ዓቢይ የኅብረተሰብአዊ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሕግ ሂደት ለማጠናከርና ለማፋጠን ማዕከላዊ ፕላን የሚያዘጋጅና የሚያስፈጽም ድርጅታዊ መዋቅር አስፈላጊ ነው ።

በሌላ በኩል የምርት ዕድገት በዘመቻ መልክ እንዲካሄድ ያስገደደው ዋናው ምክንያት በሕዝባዊ አብዮቱና በሀገሪቱ የግዛት አንድነት ላይ በውስጥና በውጭ የአድኅሮት ኃይሎች የተደረገው ጦርነት አሳሳቢና አጣዳፊ የኤኮኖሚ መቃወስ ችግሮችን ፈጥሮ ስለነበር፣ እነዚህን ለማቃለልና ለማስወገድ በአስቸኳይ የመፍትሔ ርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ነው። በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸውን የማምረቻ ተቋሞችንና የፈራረሱ የልማት ሥራዎችን በመጠገንና፣ መልሶ በመገንባት ጦም ያደረ መሬትን በማረስ ምርትን በአጭር ጊዜ ማሳደግ፣ በአሻጥረኞች ሴራ ተዘበራርቆ የነበረውን የንግድ ሥርዓት በማስተካከል ትክክለኛ የሸቀጦች ስርጭት እንዲኖር ማድረግና የውጭ ንግድ ውጤቶችን በተቀላጠፈ መንገድ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝና በመላክ እንዲሁም ምርታቸውን በመጨመር የውጭ ምንዛሪን ማዳበር በአስቸኳይ በዘመቻ መልክ መካሄድ ከነበረባቸው ተግባሮች መካከል ዋናዎቹ ነበሩ።

በአጠቃላይ በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች መሠረት የተስተካከሉት የምርት ዘመቻው ዓላማዎች ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦች የሚከተሉት ሲሆኑ እነሱም የሰፊውን ሕዝብ የኑሮና የባህል ደረጃ ከፍ እንዲል ጥረት ማድረግ፣ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በአጠቃላይም የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነትን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ የክፍላተ ሀገርን ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ተመጣጣኝ ማድረግ ፣ የሥራ ምርታማነትንከፍ ማድረግ ናቸው ። [12]

ስልቶች

እነዚህን ከፍ ሲል የተገለጹትን ዓላማዎች በሥራ ለመተርጐም የተቀየሱትን ስልቶች ደግሞ ለግብርና ቅድሚያ በመስጠት በየክፍላተ ኢኮኖሚው ልማትን ማፋጠን፣ ብሔራዊ ቁጠባን ማሳደግና የኤኮኖሚውን የማምረትና ሥራ የመፍጠር ችሎታ ከፍ ማድረግ፣ ለገበሬዎች ለዕደጥበብ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሥራ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች

Digitized by Google

በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ማሳ
ደግ፣ ወደውጭ የሚላኩ ምርቶችን መጠን፣
ዓይነትና ጥራት ማሻሻል፣ እንዲሁም ገበያን
ማስፋፋት፣ ከውጭ የሚመጡ ዕቃዎችን
በተቻለ መጠን በሀገር ውስጥ ምርት መተ
ካት፣ የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ እንዲኖር ማድ
ረግ፣ የመንግሥታዊ ድርጅቶችን የሥራ አመ
ራር ማሻሻልና ማጠናከር፣ የሰፊውን ሕዝብ
የፖለቲካ ንቃተ ህሊናና ምርታማነት ማዳ
በር፣ በተለያዩ ደረጃዎች ሰፊውን ሕዝብ
በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በተዘረጋው
የማዕከላዊ ፕላን መዋቅር መሰረት ከአሁኑ
የበለጠ ማሳተፍ፥ ስለሶሻሊስት ፕላን ምን
ነት ማሳወቅ፥ በፕላን ሥራ ላይ የተሰማሩ
ትን ባለሙያዎች በፕላኒንግ ጽንሰ ሀሳብና
ቴክኒክ ያላቸውን ዕውቀት ከፍ ማድረግ፥
የኢኮኖሚና የማኅበራዊ የልማት ፕሮጀክ
ቶች በየአካባቢው በተመጣጠነ ሁኔታ እን
ዲሠሩ ማድረግ፥ የልማት ሥራዎች በተቻለ
መጠን በይበልጥ በሰው ኃይል እንዲጠቀሙ
ማድረግ ናቸው ።[13]

የዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ክትትል አጠቃላይ ገፅታ

ሶሻሊዝም የምርት መገልገያዎችን በኅ
ብረተሰቡ ቁጥጥር ስር በማድረግ ለተመጣ
ጠነ የብሔራዊ ኤኮኖሚ ዕድገትና በዚህም
የዕድገት ፕላን አማካኝነት መምራት ነባራዊ
ግዴታን ይፈጥራል ። ብሔራዊ ኤኮኖሚን
በማዕከላዊ ፕላን አማካኝነት መምራት ከሶ
ሻሊዝም ግንባታ ሁለንተናዊ መርሆዎች
መካከል አንዱ ሲሆን የአዘገጃጀቱ መርሆ
ዎችም በሶሻሊዝም ኤኮኖሚያዊ ሕጐች
ላይ ይመረኰዛሉ። የፕላኑ ይዘትና የአዘገጃ
ጀቱ ሥነ ሥርዓት ከመሠረታዊዎቹ የሶሻ
ሊዝም ኤኮኖሚያዊ ሕጐች በሚመነጭ
ሁለት መርሆዎች ይወሰናል ። እነዚህም
ባለማቋረጥ እያደገ የሚሄደውን የኅብረተ
ሰቡን ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ለማሟላት
እንዲቻል ፕላኑ በአንድ በኩል የተመጣጠነ
የማኅበራዊ ምርት ዕድገትን ማረጋገጥ ያለ
በት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በማኅበራዊ
ምርት ውስጥ ምርታማነትን የማሳደግ መር
ሆዎች ናቸው። መርሆዎቹ የምርትና የማኅ
በራዊ ፍላጐቶችን ቀጥተኛ ግንኙነትና እን
ዲሁም በአነስተኛ የማቴሪያል፣ የሰው ኃይ
ልና የገንዘብ ወጭ የፕላን ግቦችን መምታት
አስፈላጊነትን የሚያመለክቱ ናቸው። የኤኮ
ኖሚ ፕላንም ዋነኛ ዓላማ እነዚህን መርሆ
ዎች ተግባራዊ ማድረግ ነው ።

በአጠቃላይ የማዕከላዊ ፕላን ዝግጅት
በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ፣ በትዕዛዝ
መልክ የሚተላለፍ ፕላንና እንደ ዋጋ፥ ገን
ዘብና ትርፍ ያሉትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሣ
ሪያዎች ማጣመርን፥ የተለያዩ የኢኮኖሚው
ዘርፎችን ፕላኖች በአጠቃላይ ፕላን በማቀ
ናበር ማዋሀድን፥ ጠቋሚ ፕላኑንና የአጭር
ጊዜ ፕላንን ማቀነባበርና ከአጠቃላይ የኢ
ኮኖሚው ፍላጐት በመነሳት የአንዱን የተወ
ሰነ ፕላን የዘርፍና የአካባቢ ዝርዝሮች በማ
ቀነባበር መርሆዎችላይ የተመሠረተነው።[14]
ከእነዚህ የፕላን አዘገጃጀት መርሆዎች
መካከል የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ
የዋነኛነቱን ቦታ ይይዛል። ይህም መርህ በብ
ሔራዊ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገትፕላን
ዝግጅት አፈጻጸምና ክትትል ሂደት ውስጥ
የሚኖረውን የማዕከላዊነትና የዲሞክራሲ
ገጽታዎች የአሠራር ጥምረት የሚገልጽ
ነው ።

አንድን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት
ፕላን ማዘጋጀት ዋነኛነት ያለው ተግባር
ይሁን እንጂ የፕላን ዝግጅት የፕላን ሂደት
የመጨረሻ ደረጃ አይደለም። ሌላኛው ዋነኛ
ተግባር የተዘጋጀውን ፕላን በሥራ ላይ የማ
ዋሉ ጥያቄ ነው። በተለይ ደግሞ ይህ የተዘ
ጋጀውን ፕላን በሥራ ላይ የማዋሉ ተግባር
በታዳጊ አገሮች ተጨባጭ ሁኔታ የተለየ
ዋነኛነት አለው ።

ባለፈው ክፍል የዕቅድ አዘገጃጀት በዲ
ሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ ላይ የተ
መሰረተ መሆኑ ተገልጿል ። የዕቅድ አፈጻ
ጸም ክትትል አሠራርም በዚሁ መሠረታዊ

Digitized by Google

መርሆ ላይ የተመሰረተ ነው። ስለሆነም በዕቅድ አፈጻጸምና ቁጥጥር ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች ሁሉ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህበተግባር መገለጽ አለበት ማለት ነው። ይህም በፕላን አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ተግባር ከነባራዊውም ሆነ ከህሊናዊ ሁኔታዎች መንስኤነት ሊከሰቱ ከሚችሉ ችግሮች በመራቅ ትክክለኛውን አቅጣጫ ተከትሎ ንዲካሄድ ያግዛል ።

ወደ ሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር የአሠራር ሥርዓት የሚካሄደው በሚከተለው መልክ ነው። በመንግሥት /በጋራ ስብሰባው/ የጸደቀ የክፍለ ኢኮኖሚና የዘርፍ የምርት ግቦችና የኢንቬስትሚንት ዕቅዶች በሥራእንዲተረጐሙ ተመልሰው ወደ አስፈጻሚ መ/ቤቶች ይላካሉ። ወቅታዊ (Seasonal) የምርት መጠን መለዋወጥን ፣ የጥገና ጊዜንና የመሳሰሉትን ታሳቢ በማድረግ በእርሻ ወይም በፋብሪካ ደረጃ ዓመታዊ የምርት ግቦቹ በሶስት ወር ወይም ወርሀዊ የድርጅት ግቦች ይዘረዘራሉ። በእነዚህም የተግባር የአጭር ጊዜ ፕላኖች መሠረት የምርት ተግባሩ ይካሄዳል፤ የሚመለከታቸውም ክፍሎች አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ ።

ከበድ ያለው ሥራ ያለው የኢንቬስትመንት ፕሮጀክቶች በማስፈጸም በኩል ነው። የኢንቬስትመንት ዕቅዶችን በማስፈጸም በኩል አብዛኛው ሥራ የሚከናወነው በኮርፖሬሽን ደረጃ ነው። የተፈቀዱ የፕሮጀክት ሃሳቦችን ማስጠናት ወይም ከተቻለ ማጥናት፤ ለተጠኑ ፕሮጀክቶች የኮንስትራክሽንና የኢንጂነሪንግ ዲዛይን ማስወጣት፣ ጨረታ ማውጣት፤ ውል መዋዋል፤ የፕሮጀክቶችን የሥራ ሂደት መከታተልና የመሳሰሉት ተግባራዊ ሥራዎች ሁሉ የሚከናወኑት በኮርፖሬሽን ደረጃ ነው።

ትላልቅ ፕሮጀክቶች የሚጠኑትም ሆነ ዲዛይናቸው የሚሠራው በውጭ ሀገር አማካሪዎች ሲሆን ፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በውጭ ሀገር ተቋራጮች ፤ በመንግሥት የኮንስትራክሽን ባለሥልጣኖች ወይም የሀገር ውስጥ የግል ተቋራጮች ይሠራሉ። አንዳንድ ክፍላተ ኢኮኖሚ (ለምሳሌ ትራንስፖርት ፣ መገናኛና ኢንዱስትሪ) በፕሮጀክቶች በኩል ሻል ያለ ድርጅታዊ አቋም (ለምሳሌ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ጥናት ድርጅት ፣ የፕሮጀክት መመሪያ) አላቸው ። ቋሚ የማምረቻ መሜሪያ ተካፋይ ቡድን በየኮርፖሬሽኑ ደግሞ የፕሮጀክት ጽ/ ቤት አሉት ። በየአራት ወር የፕሮጀክት የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርቶች ሚኒስቴሩ ያዘጋጃል ። ይሁንና በሀገር ደረጃ በአጠቃላይ በፕሮጀክት ጥናትና አፈጻጸም በኩል ከፍተኛ ድክመት እንዳለ ተደጋግሞ የተገለጸና የታወቀ ነው ።

በጠ/ መምሪያው ደረጃ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል የሚደረገው በጠ/መምሪያው የኢንስፔክሽን መምሪያ ሲሆን ፤ የዚህም መምሪያ ዓይነተኛ ተግባር በጠ/መምሪያው በተዘጋጁ የዕቅድ መከታተያ ቅጾች አማካይነት ከአስፈጻሚ መ/ ቤቶች በሚላኩለት አንዛዊና ገላጭ መረጃዎች መሠረትና እንዲሁም በቦታው ተገኝቶ የሥራዎችን ሂደት በማየትና ተጨማሪ መረጃዎችን በማጠናቀር የ3 ወር ፤ የ6 ወር ፤ የ9 ወር ና በመጨረሻም ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በቀጥታ ለጠ/ መምሪያው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማቅረብ ነው ። የጋራ ስብሰባው በየወቅቱ እየተሰበሰበ በኢንስፔክሽን ሪፖርት መሠረት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ ለተከሰቱት ችግሮች የመፍትሔ ሀሳቦችንና እንዲሁም መመሪያዎችን ይሰጣል ። የኢንስፔክሽን የዕቅድ አፈጻጸም ዘገባዎች በአጠቃላይ አፈጻጸሙን ከእቅዱ ጋር የሚነጻጽሩ አሀዞችን፣ በአፈጻጸም ጊዜ የደረሱትን ችግሮችንና የተወሰዱ እርምጃዎችንና የመፍትሔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው ። የክፍለ ሀገር ዘመቻ መምሪያዎች የየክፍለ ሀገራቸውን የዕቅድ አፈጻጸም ሁኔታ የሚያሳዩ ዘገባዎች ለጠ/መምሪያው ያቀርባሉ ።

Digitized by Google

ባጠቃላይም የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል
ከላይ በተገለጸው የአሠራር ዘዴ የሚካሄድ
ቢሆንም ፤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በየጊ
ዜው ፕላኑ ጸድቶ በሥራ ላይ በዋለ በ3ኛው
በ6ኛው፣በ9ነኛው ወርና በዓመቱ መጨረሻ፣
ስለፕላናች አፈጻጸም ሁኔታ ገምገሞ መመ
ሪያ የመስጠት ተግባሩን ለማከናወን አል
ቻለም ። ለዚህም ምክንያቱ አስፈጻሚ
መሥሪያ ቤቶች የአፈጻጸም ሪፖርቶችና
የአፈጻጸም መከታተያ ቅጾችን በተሟላ
ሁኔታ ወቅታቸውን ጠብቀው ለጠቅላይ
መምሪያው እንዲደርሱ አለማድረጋቸው
ነው ። በዚህም የተነሣ እስከ ዛሬ ድረስ የ3
ወር የአፈጻጸም ሁኔታ ተገምገሞ የማያ
ውቅ ሲሆን ፤ የ6ኛውና የ9ኛው ወር ግምገ
ማዎችም ቢሆኑ ፤ ወቅታቸውን ጠብቀው
ስለማይካሄዱ ለፕላን አፈጻጸም ችግሮች
ወቅታዊ መፍትሔ መስጠትን አዳጋች ስለ
ሚያደርገ ፤ በአፈጻጸም በኩል ድክመት
አስከትሏል ።

ዘመቻዎቹ ያስገኙት ዋና ዋና ውጤቶችና የተከሰቱ ችግሮች

የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና
የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ከተቋ
ቋመ ወዲህ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋ
ሉት አራት የዘመቻ ፕላኖች ተዳክሞና
ፈራርሶ የነበረውን የኢኮኖሚ ሁኔታ
በማንሠራራትና በማጠናከር ፤ በፕላን
አዘጋገጃጀትና አፈጻጸም ልምድ በኩል
ጠቃሚ የሆኑ ውጤቶችን አስገኝተዋል።
በመሠረቱ የማዕከላዊ ፕላን ሀሳብ ብዙም
ባልተስፋፋበትና ሥራውንም በቅርቡ በተ
ያያዘ አገር ማናቸውም ነገር በተስተካከለ
ሁኔታ ሊከናወን እንደማይችል ግልጽ
ነው ። በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ በተ
ካሄዱት ዘመቻዎች ሂደት ውስጥ ከተለ
ያዩ ማዕዘናች አንፃር ድክመቶች ተከስተ
ዋል ።

እነዚህን ድክመቶች ለይቶ ማወቁ ለወ
ደፊት ችግሮቹን ለማስወገድ የሚያስችሉ
የመፍትሔ ሀሳቦችን ለማመንጨትና ተግባ
ራዊ ለማድረግ ያስችላል ።ስለዚህም ዘመቻ
ዎቹ ያስገኙአቸውን ውጤቶችና የተከሰቱ
ትን ችግሮች መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

በመጀመሪያው ዘመቻ ጠቅላላ የሀገር
ውስጥ ምርት በ5.9% እንደሚያድግ ተገ
ምቶ ፤ በእውን እንዳደገ የተሰላው በ5.3%
ነው ። በሁለተኛውና በሦስተኛው ዘመቻ
ዎች ደግሞ በ7.3 እና በ6.1% /እንደሚ
ያድግ ተገምቶ የነበረው ጠቅላላ የሀገር
ውስጥ ምርት በእርግጥ ያደገው በ5.6%ና
በ3.3% ነው ። በአራተኛው ዘመቻ ታቅዶ
የነበረው የኢኮኖሚ እድገት 4.5% ሲሆን
የተገኘው ውጤት 2.4% ነው ። በሌላ
በኩል በ1972 ታቅዶ የነበረው ጠቅላላ
ኢንቬስትመንት በሥራ ላይ እንደዋለ የተ
ገመተው 65% ሲሆን ፤ በ1973 59%
በ1974 ደግሞ ከ50% በታች ብቻ
ነው ። በአጠቃላይ የምርት እድገቱና ማን
ሰራራቱ ሊገኝ የቻለው ጦም ያደረና ተጨ
ማሪ መሬትን በማረስ ፤ በጦርነት ተሰናክ
ለው የነበሩ ፋብሪካዎችን እንደገና የም
ርት ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ፣
በትርፍ የማምረት ችሎታ በመጠቀም ፤
ትንሽም ቢሆን ፤ በአዳዲስ ኢንቬስትመን
ቶች አማካይነት ተጨማሪ የማምረትችሎታ
በመፍጠርና በመጠኑም ቢሆን የተሻሻሉ
የአሠራር ሥልቶችን በመቀየስና እንዲሁም
ርዕዮተ ዓለማዊ ቅስቀሳ በማድረግ የሠ
ራተኛውን ምርታማነት ለመጨመር ጥረት
በማድረግ ነው ። በተጨማሪም ዘመቻ
ዎቹ የፕላን ፅንሰ ሀሳብን በማስፋፋት ፣ የአ
ሠራር ልምድ በማስገኘት ፣ በሰፊው ሕዝብ
በፕላን አዘገጃጀት ፤ አፈጻጸም ፣ ክት
ትልና ቁጥጥር አኳያ ጠቃሚ የሆኑ ልምዶ
ችን አስገኝተዋል ። ይህም ለተገኘው የም
ርት ዕድገትና ማንሠራራት የበኩሉን አስ
ተዋፅኦ አድርጓል ።

ዘመቻዎቹ ስላስገኙት የምርት እድገ
ትና ልምዶች ስናወሳ አንድ መታወስ
ያለበት ጉዳይ አለ ። ይኸውም በዘመቻ

Digitized by Google

ምቹ አማካኝነት የተገኘው የምርት እድገት መነሻ ዓመቱ ምርት ቀንሶ በነበረበት 1970 መሆኑንና ከዚህም በፊት ዓመታዊ የምርት እድገት በአማካኝ ከዓመታዊ የሕዝብ እድገት በታች በመሆን የነፍስ ወከፍ ምርት እየቀነሰ መጥቶ እንደነበረ ነው ። የምርት ዘመቻው ከተጀመረ ወዲህ የተገኘው የምርት እድገት የነፍስ ወከፍ ምርትን ወደነበረበት ለመመለስና በአጠቃላይም ብሔራዊ ኢኮኖሚው እንዲያንሠራራ ረድቶ አል ።

በዘመቻዎቹ የተከሰቱ ችግሮች

እስከ ዛሬ ድረስ የተካሄዱት የምርትዘመቻዎች የታቀደላቸውን ግቦችና ዓላማዎች ለማሟላት እንቅፋት የሆኑ በርካታና እርበርሳቸው የተወሳሰቡ ችግሮች አጋጥመዋል ። ችግሮቹ በአጠቃላይ ከኢኮኖሚው መዋቅራዊና ድርጅታዊ ኋላቀርነት የመነጩ ቢሆኑም ፣ የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ድክመቶችም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ። ከችግሮቹም መካከል ዋና ዋናዎቹ ፣ ዕቅዱ ሲዘጋጅ ከተጨባጭ ሁኔታው በተለይም ከአለው የማምረት አቅምና ሀብት ጋር የተገናዘበ አለመሆን ፣ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በቂ ሕዝባዊ ተሳትፎና ቅስቀሳ ባለመኖሩ ፕላኑ በሕዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነት የሚፈለገውን ያህል አለመሆን ፣ የፕላን አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ድርጅታዊ ችሎታ ፕላን የሚጠይቀውን የአሠራር ቅልጥፍና ለማሟላት አለመቻሉ ፣ ጉጂ የሆኑ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በተለይም የገቢ ንግድ ዕቃዎች ዋጋ መናርና የወጪ ንግድ ውጤት ዋጋ መቀነስ ፣ ለተጨባ ሁኔታው ተስማሚና ግልጽ የሆኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አለመቀየሳቸው ፣ ያልተጠበቁ የተፈጥሮ አደጋዎችና ሁኔታዎች መፈጠር ፣ በአንዳንዱ አካባቢዎች ፀጥታው የተሟላ አለመሆንና ይህንንም ለማሟላት የሚወጣው ወጪ ከፍተኛ መሆኑና ፕላን ለማዘጋጀትና አፈጻጸምን ለመታተል ያሉት መረጃዎች በቂ አለመሆን ናቸው ።

ቀደም ሲል የተጠቀሱት አጠቃላይ ችግሮች በዝርዝር ሲታዩ በሚከተለው መልክ ተከስተዋል ። ይኸውም ፕላን ለማዘጋጀትና ለማስፈጸም የጊዜ እጥረት መኖር ፣ በወቅቱ አለማረስ ፣ ማዳበሪያ ከውጪ ዘግይቶ መድረስ ፣ የዋጋ መናር ፣ ማዳበሪያ ለገበሬው በወቅቱ ለማደል አለመቻሉ ፣ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዋጋ መጨመር ፣ የገበያ እጦት ፣ ኪሳራ የሚያሳዩ ፋብሪካዎች መኖር ፣ የፕሮጀክት አፈጻጸምና ክትትል ዝቅተኛና ደካማ መሆን ፣ ስለግል ፋብሪካዎችና ዕደጥበባት የተሰበሰቡት መረጃዎች አጥጋቢ አለመሆን ፣ የመሣሪያና የማቴሪያል እጥረት ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ እጥረት ፣ የትራንስፖርት ችግር፣የጸጥታ ችግር ፣ የተሟላ የሥራ ቅንጅትና ክትትል ያለመኖር ፣ ከዕቅድ ውጭ የሚፈጸሙ ሥራዎች መብዛት፣በዕቅድ (በበጀት) የተያዙ የገንዘብ ወጪዎች በታቀደው መሠረት አለመዋል፣ የመረጃዎች እጥረትና አለመቀነባበር ፣የማምረቻ መሣሪያዎች ግርጀት ፣ የጥሬ ዕቃ እጥረት ፣ የቁጥጥር መላላት ፣ የንብረት አያያዝ ድክመት ፣ የብዛትና ጥራት አለመመጣጠን ፣ የኮንስትራክሽን ንድፍ በወቅቱ አለመጠናቀቅ፣ ድርጅታዊ ድክመት ፣ወዘተ ናቸው ።

እነዚህ እስካሁን በተካሄዱት አራት ዘመቻዎች የተከሰቱት ችግሮች በከፊል ከፕላን ዝግጅት ድክመቶች የመጡ ናቸው ። ሌሎች ደግሞ ከአፈጻጸም በኩል የተከሰቱት ችግሮች ሲሆኑ እነሱም ጉጂ ከሆኑ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ፣ ተገቢ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አለመቀየስና ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች መከሰት ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ ሁኔታ መጓደል የሚያስከትለው ወጪና በፕላን ያልታቀፉ ለሥራዎች መበርከት አኳያ የታዩ ችግሮች ናቸው ። በአጠቃላይ ችግሮቹ ከአለፈው ሥርዓት

Digitized by Google

የወረስነው የኢኮኖሚው መዋቅራዊና ድር
ጅታዊ ኋላቀርነት የመነጨ ቢሆኑም ባለ
ፉት አራት ዘመቻዎች ወቅት በዕውቀት
ማነስ ወይም በንቃተ ኅሊና ዝቅተኛ
ነትና ፥ በአመራርና በአስተዳደር ቅንብር
ጉድለት በኩል የታዩት ድክመቶች ለሁኔ
ታው ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በምርት ዘመቻዎቹ ሂደት ውስጥ በፕላን
አዘገጃጀትና አፈጻጸም በኩል የተከሰቱትን
ችግሮች በመገምገም ሆነ መፍትሔዎችን
በመስጠት በኩል ጠቃሚ ጥረቶች ተደርገ
ዋል ። ለምሳሌም ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በፕ
ላን ዝግጅትና የተለያዩት መንግሥታዊና
ሕዝባዊ አካሎች ለፕላን ዲሲፕሊን ተገዥ
የሚሆኑበትን ሁኔታዎችና ሳይንሳዊ የማዕከ
ላዊ ፕላን ፅንሰ ሐሳቦች በሰፊው ሕዝብና
በፕላን ተግባር በተሰማሩ ጓዶች ዘንድ
የማይናቁ ጥረቶች ተካሂደዋል ። ሆኖም
በአጠቃላይ በዘመቻዎቹ ለተከሰቱት ችግ
ሮች የቀረቡት መፍትሔዎች አጥጋቢ ሊባሉ
የሚችሉ አይደሉም ። በዘመቻዎቹ የታዩትን
ችግሮች ከመፍትሔዎቻቸው አንፃር ስንመ
ለከታቸው በአጠቃላይ የአጭርና የረጅም
ጊዜ ጥረቶችን የሚጠይቁ እንደሆኑ እንገነ
ዘባለን ። ችግሮቹ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ
ዕቅዶችን በማውጣት በአጭር ጊዜ ከሚከና
ወኑት ጥረቶች ጋር አቀናብሮ የሚካሔድን
ጥረት ይሻሉ ።

በአሁኑ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ የረጅም ጊዜ
መሪ ዕቅድ ዝግጅት በመካሔድ ላይ ይገኛል።
ስለዚህም እስከዛሬ፤በተካሔዱት ዘመቻዎች
በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ረገድ የተከሰ
ቱትን ድክመቶች በትክክል መመርመሩና
መመዘኑ በመቀየስ ላይ ላለው የአስር ዓመቱ
መሪ ዕቅድ ግብ መምታት መደረግ ያለባ
ቸውን አስፈላጊ ሁኔታዎች ስለሚጠቁሙ
ተገቢው ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ።

ሳይንሳዊ ማዕከላዊ ፕላንን ለማዘጋጀ
ትም ሆነ ተግባራዊ ለማድረግ የሶሻሊስት
ፕላኒንግ ቲዎሪ፣ ቴክኒካዊ ዕውቀትና የማሌ
ርዕዮተ ዓለም ግንዛቤ የሚሻ መሆኑ አጠያ
ያቂ አይደለም። በተለይም በፖለቲካው መስ
ክ የተስተካከለና የተቀነባበረ ማዕከላዊ አመ
ራር መገኘቱ ጥራት ያለው ማዕከላዊ ፕላንን
ለማዘጋጀትም ሆነ ለማስፈጸም የዋነኛነት
ሚና እንደሚኖረው የእስከዛሬው የፕላን
ልምድ ያረጋገጠው ሀቅ ነው ። ስለዚህም ዛሬ
በኢሠፓአኮ ነገ ደግሞ በኢሠፓ አማካኝነት
ይህንን አመራር ማግኘት ሳይንሳዊ የኢኮ
ኖሚ ፕላንን ለማዘጋጀትና አፈጻጸሙንም
በተስተካከለና በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን
የወሳኝነት ሚና ይኖረዋል ።

የአስር ዓመት ልማት መሪ እቅድ ዝግ
ጅት ለምን አስፈለገ ?

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ውስጥ ሶሻሊዝም
ን ለመገንባት የምርት መገልገያዎችን የሕ
ዝብ ንብረት ማድረግ ብቻውን ብቁ እንደማ
ይሆንና ብሔራዊ ኢኮኖሚን በማዕከላዊ ፕላ
ን መምራት ማስፈለጉን ተመልክተናል ።
ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በማዕከላዊ ፕላን
መምራት የሶሻሊዝምን ግንባታ ሁለንተናዊ
ሕግ በመሆኑም የሶሻሊዝምን ፈለግ የተከ
ተሉ ሀገሮች ሁሉ እንደ የሀገሮቻቸው ተጨ
ባጭ ሁኔታ ማዕከላዊ ፕላን መንደፍና
በሥራ ላይ ማዋል ይገባቸዋል ።

የኢትዮጵያ አብዮት ካስመዘገባቸውአብ
ዮታዊ ድሎች መካከል ዋና ዋና የምርት መገ
ልገያዎች በመንግሥትና በሕዝብ ቁጥጥር
ሥር ማዋሉ አንዱ ነው ። ሆኖም ከአብዮቱ
ፍንዳታ ጀምሮ የብሔራዊ አብዮታዊ የም
ርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መም
ሪያ እስከተቋቋመበት ጊዜ ድረስ በተለያዩ
ማዕዘናት ይካሔድ በነበረው ፖለቲካ
ዊና ወታደራዊ ትግል የተነሣ ለሀገሪቱ ኢኮ
ኖሚና ማኅበራዊ እድገት ተገቢው ትኩረት
ሊሰጥ አልቻለም ነበር ። በፖለቲካዊና በወ
ታደራዊ መስኮች ከጊዜ በኋላ አንፃራዊ መረ
ጋጋት በመገኘቱ አብዮቱ ለኢኮኖሚያዊና
ማኅበራዊ መስክ ትኩረት መስጠት እንደጀ
መረ ይታወቃል ። ይሁንና ይህ ትኩረት ከተ
ሰጠም በኋላ በአንድ በኩል የወቅቱን ጉል
ህና አጣዳፊ ችግሮች መቋቋምና የሰፊውን

Digitized by Google

ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል በሌላ በኩል
ደግሞ በረጅሙ ጊዜ ለሚገነባው የሶሻሊ
ዝም ስርዓት አስፈላጊ የሆኑትን የማቴሪ
ያልና የቴክኒክ መሠረቶች የመጣል ተግባር
አስፈላጊ ሆኖ ነበር ። በመሠረቱ እነዚህ
ሁለት የኢኮኖሚ ግንባታ ትግሎች በአንድ
ዓመትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከዳር ሊደርሱ
የሚችሉ ሳይሆኑ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ
ፕላን በማውጣት የረጅም ጊዜ ጥረት የሚ
ያስፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸው ። የመካከለኛ
ውና የረጅም ጊዜ ፕላን ለማዘጋጀት በቂ
ልምድ ፡ ረዘም ያለ ጊዜና የተሟላ ድርጅታዊ
መዋቅር የሚያስፈልግ በመሆኑ ከጠቅላይ
መምሪያው መቋቋም ጋር እነዚህን እቅዶች
ማዘጋጀት አልቻለም ነበር ። ስለሆነም
በጊዜው በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ኑሮ ዘር
ፎች ወቅታዊና አጣዳፊ የነበሩትን ማለትም
እንደ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎችና ገል
ጋሎቶች እጥረት ፡ ሥራአጥነት ፡ የውጭ
ምንዛሪ ማሽቆልቆልና የመሳሰሉትን ችግ
ሮች ለመቋቋም እንዲቻል በየዓመቱ የሚከና
ወን የኢኮኖሚ ፡ የሶሻልና የባህል እድገት
ዘመቻ ማካሔድ ገዴታ ሊሆን ቻለ ። በዚ
ህም መሠረት ከ1971 ጀምሮ አራት ዘመቻ
ዎች የተካሔዱ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ
አምስተኛው በመካሔድ ላይ ይገኛል ።

የአንድ አገር የኢኮኖሚና የሶሻል እድ
ገት በመሠረታዊ የኅብረተሰብ እድገት
ሕጐች አንቀሳቃሽነት የሚካሔድ የረጅም
ጊዜ ሂደት በመሆኑ ማዕከላዊ ፕላን ሶሻሊስት
የምርት ግንኙነትን በማስፋፋትና በማጠ
ናከር በተለይ ከኋላ ቀርነት ወደ ሶሻሊዝም
በሽግግር ላይ ባሉ ሀገሮች የምርት ኃይሎችን
እድገት ለማፋጠን የሚረዳ ዓይነተኛ መሣ
ሪያ ነው ። ስለሆነም ማዕከላዊ ፕላን ተጨ
ባጭና ትልህ ውጤቶችን ለማስገኘት የማያ
ቋርጥ የረጅም ጊዜ ጥረትን ይሻል ። ስለዚህ
ከውጭ በኢምፔሪያሊዝም ጥገኝነትና ጥገ
ኝነቱ ባስከተለው ብዝበዛ ፤ በውስጥ ደግሞ
በምርት ኃይሎች የእድገት ደረጃ ዝቅተኛ
ነት የተነሣ የተፈጠሩት የኢኮኖሚና የኅብ
ረተሰብ ኋላቀርነት መሠረታዊ ችግሮችን
ደረጃ በደረጃ ለማቃለል ስትራቴጂያዊና ሁለ
ገብ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን የሚ
ያስገኙ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት ያስ
ፈልጋል።እነዚህን ለመዘርጋት ደግሞ የረ
ጅምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት እቅድ አው
ጥቶ በሥራ መተርጐምን ይጠይቃል ።በተ
ጨማሪም የአጭር ጊዜ የኢኮኖሚና የሶሻል
ልማት እቅድ በረጅምና በመካከለኛ ጊዜ
የእድገት ጎዳና ትልም ላይ ካልተመሠረተ
አቅጣጫ የለሽ ከመሆኑም በላይ በጊዜያዊ
ምርት ላይ የማተኮር አዝማሚያ ስለሚኖረው
በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በመሠረ
ታዊ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች እጥረት ምክ
ንያት እንቅፋት ይገጥመዋል ። ሌላው ለአ
ስር ዓመቱ የረጅም ጊዜ መሪ እቅድ አስፈ
ላጊነት ምክንያት ሊሆን የቻለው በኢንዱ
ስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የነበረው ትርፍ የማ
ምረት ችሎታ በአብዛኛው በምርት ተግባር
ላይ በመዋሉ ተጨማሪ የማምረት ችሎታን
መፍጠር በማስፈለጉ ነው ። ለማጠቃለል
የአሥር ዓመቱን የልማት መሪ እቅድ እን
ዲዘጋጅ አስፈላጊ ያደረጉት መሠረታዊ ምክ
ንያቶች ።

1ኛ ፡ የሀገሪቱን የሀብት መሠረት ፡ ያለች
በትን የእድገት ደረጃ ፡ ጉልተው የሚ
ታዩትን የኋላቀርነት ገጽታዎች በመ
ካከላቸው ያሉትን የተወሳሰቡ ዝምድ
ናዎች በማጤንና በመገምገም ለተፋ
ጠነ እድገት ተስማሚ የሆነ የረጅም
ጊዜ የልማት ስቀጣጫና እስትራቴጂ
መቀየስ አስፈላጊ መሆኑ ፡

2ኛ ፡ ከፍተኛ የልማት ውጤቶችና መዋቅ
ራዊ ለውጦች ሊገኙ የሚችሉትና በአ
ጠቃላይም የማምረት ችሎታን ማዳ
በር የሚቻለው በረጅም ጊዜ ሂደት ው
ስጥ መሠረታዊ የሶሺዮ ኢኮኖሚ የል
ማት አውታሮችን በመዘርጋት፡ከባድና
ቀላል ኢንዱስትሪዎችንና አገር ኢን
ዱስትሪዎችን በማስፋፋት ፡ በተለያዩ

Digitized by Google

መስኮች የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል ሥልጠና በማካሄድ በመሆኑና እነዚህንም ዓይነት ትላልቅ ፕሮጀክቶችና የሰው ኃይል ሥልጠና ፕሮግራሞች ጀምሮ ለመጨረስ ረጅም ጊዜ ሊፈጅ ስለሚችል ።

3ኛ· ዓመታዊ ፕላኖች በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ፕላኖች ላይ የተመሠረቱ ካልሆኑ የልማት አድማሣቸው ጠባብ ከመሆኑም የተነሣ በጊዜያዊና አጣዳፊ ችግሮች ላይ በቁንጽል የማተኮር አዝማሚያ ስለሚኖራቸው የሀብት መባከንን ከማስከተላቸውም ሌላ ለመሠረታዊ ችግሮች መረታዊ መፍትሂዎችን የማስገኘት ችሎታ ስለማይኖራቸው፣ ለእነዚህ ዓመታዊ እቅዶችና እንዲሁም ለመካከለኛ ጊዜ ፕላን መሠረት የሚሆን የረጅም ጊዜ ፕላን መንደፍ አስፈላጊ መሆኑና፣

4ኛ· የሶሺያሊስት ሥልተምርትን ለማስፋትና ለማጠናከር በተለይም የምርት ኃይሉችን እድገት ለማፋጠንና ለገንባታው ጠንካራ የቴክኒክ ቁሳዊ መሠረት ለመጣል የተቀነባበረ የረጅም፣መካከለኛና የአጭር ጊዜ አመላካከት አስፈላጊ መሆኑ፣ናቸው[15] ።

የአዘገጃጀት ዘዴና ሥርዓት

በመሠረቱ አንድ የኢኮኖሚ ፕላን ምንጊዜም ቢሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ ሦስት ፍሬ ነገሮችን አጠቃሎ ይይዛል ። እነሱም የፕላን ግቦችና መስፈርቶች (Targets and Indices) አስተዳደጋቸው ግብታዊ የሆነውን የማኅበራዊ ክስተቶች ኢኮኖሚያዊ ጥቆማና (Forecasting) የታቀዱትን ግቦችና መስፈርቶች እውን እንዲያደርጉ የሚታለሙ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እርምጃዎችን ማመንጨትና ተግባራዊ ማድረግ ናቸው ። [16] የእነዚህን የፕላን ይዘቶች ቅንጅት የአንደኛው ይዘት ከሌለኛው ይዘት ልቆ መገኘት በፕላኒንግ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ላይ የተመረኮዘ ነው ።

ከዚህ በፊት እንደተገለፀው የሀገራችን የልማት ችግሮች በርካታና እርስ በርሳቸው የተወሳሰቡ ከመሆናቸውም በላይ ችግሮቹ በአንድ ጊዜ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ በረጅም ጊዜ ጥረት የሚቃለሉ ናቸው ። በዚህም የተነሣ ለሀገሪቱ ችግሮች መቃለል የበለጠ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉትን የልማት ሥራዎችና እርምጃዎች በመምረጥ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ አስፈላጊ ይሆናል ። ስለዚህም የአስር ዓመቱ ጠቋሚ እቅድ የብሔራዊ ኢኮኖሚውን የወደፊት ዕድገት ዋና ዋና አቅጣጫዎች እንዲያመለክት ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል ።

የአንድን አገር ኢኮኖሚ የወደፊት እድገት ሁኔታዎች አስቀድሞ በትክክል መተንበይ አስቸጋሪ ተግባር ነው ። ምክንያቱም አስቀድሞ ሊታወቅ ወይም ሊገለጽ የማይችሉ እንደአየር ጠባይ፣ የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ተለዋዋጭነት፣ ሣንይሳዊ ምርምር የሚያስገኛቸው አዳዲስ ውጤቶችና በአኃዝ ሊገለጹ የማይችሉ ክስተቶች . . . ወዘተ ያሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በኢኮኖሚው እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ስለሚኖራቸው የረጅም ጊዜን የኢኮኖሚ ሁኔታ በትክክል የመተንበዩን ተግባር አዳጋች ያደርጉታል ። ይሁንና የሶሻሊስት አገሮች እስከ ዛሬ ባከማቹት ጠቃሚ ልምድና ዛሬ በደረሱበት ከፍተኛ የሳይንሳዊ ምርምር እድገት ውጤቶች የተነሣ የረጅም ዘመን እድገት አቅጣጫዎችን የሚያሳዩ ግምቶች ላይ ለመድረስ አዳጋች አይሆንባቸውም ። ሆኖም ይህ አሠራር አገራችን ዛሬ በምትገኝበት ሁኔታ አንፃር ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል የሚያጠያይቅ አይሆንም ። ስለዚህም የአስር ዓመቱ ጠቋሚ እቅድ በተወሰኑ ክፍላተ ኢኮኖሚና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጐት በከፊል ያሟላሉ በተባሉ ጥቂት ምርቶች ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆን ይኖርበታል ። በዚህም መሠረት ጠቋሚ እቅዱ የአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት በመተንበይና የሕዝቡን ፍላጐት መሠረት በማድረግ ለስድስት መሠረታዊ ምርቶችና ግልጋሎቶች ግቦች በመጣል

Digitized by Google

ላይ ያተኮረ ሆኖ ተነድፏል ፡፡ እነሱም ምግብ፣ ወተት (ለሕፃናት)፣ የመጠጥ ውሀ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ መኖሪያ ቤቶችና ጤና ናቸው ፡፡ [17]

ከላይ በተመለከተው የአሠራር ዘዴ ላይ በመመሥረት የአሥር ዓመቱን ጠቋሚ ዕቅድ አጠቃላይና ክፍላተ ኢኮኖሚ ዓላማ ዎች፣ ሥልቶችና የዕድገት አቅጣጫዎችን የያዘ የመመሪያ ጽሑፍ በ1972 ለሚኒስቴር መ/ቤቶችና መንግሥታዊ ድርጅቶች ተልኮ አስፈጻሚ መ/ቤቶች የየክፍለ ኢኮኖሚያቸ ውንና የዘርፎቻቸውን ዝርዝር ጠቋሚ ፕላ ኖች አዘጋጅተው ለጠ/ መምሪያው አቅ ርበዋል ፡፡ እነዚህንም የተለያዩ ይዘት ያላ ቸውን ዝርዝር ፕላኖች መርምሮ፣ ከልሶ፣ አመሳክሮ፡ አዳብሮ ውስጣዊ ዝምድናዎችን አረጋግጦ የአሥር ዓመቱን ጠቋሚ እቅድ የመጀመሪያ ረቂቅ ለማዘጋጀት ሰፊ ተሳትፎ ያለበት የአሠራር መዋቅር ተዘርግቷል ፡፡ [18]

የፕላን ዝግጅቱም ሥራ የሚከናወነው ከጠ/ መምሪያውና እንዲሁም ከሌሎች መ/ ቤቶች ከፍተኛ ችሎታና ሰፊ የሥራ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች አባልነት በሚቋቋሙት ግብረ ኃይሎች አማካይነት ነው ፡፡ በአጠቃ ላይ 19 ግብረ ኃይሎች የተቋቋሙ ሲሆን እያ ንዳንዱ ግብረ ኃይልም እንደሥራው ጠባይ የተለያዩ ብዛት ያላቸው ንዑስ ግብረ ኃይ ሎች አሉት ፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ግብረ ኃይ ሎች በአራት የሚኒስቴሮች ኮሚቴዎች የሚ መሩ ሆነው ተጠሪነታቸው ለጠቅላይ መም ሪያው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው ፡፡ የፕላን ዝግጅቱ በዚህ አኳኋን መካሄድ የኢኮኖሚ እቅድ አዘገጃጀት ልምድ አነስተኛ በሆነበት ገና ጀማሪ አገር ጠቃሚ የሆኑ ውጤቶች እንደሚኖሩት መገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡ ስለዚህ ይህ አሠራር፣-

በእቅድ ዝግጅት ላይ ሰፋ ያለ ተሳትፎ እንዲኖር አድርጓል፣በእቅዱ ትንተና ወቀት በጠ/መምሪያውና በአስፈጻሚ መ/ቤቶች መካከል ሊኖር የሚችለውን ረዥም የሥራ ግንኙነት ገቦችን ከፍ በማድረግ ወይም በመቀነስ ወዘተ... አሳጥሮታል፣የብዙ ምሁ ራን ውይይት የእቅዱን ይዘት በዓይነትም ሆነ በጥራት ረገድ ያሻሽለዋል፣ የእቅዱ ይዘት ሰፊ ታዋቂነት እንዲኖረው ይረዳል፣ በእቅዱ አውጪው አካልና በአስፈጻሚ መ/ ቤቶች መካከል ያለውን የቀርብ ግንኙነት በማጠናከር እቅዱ ተጨባጭ ሁኔታዎችን እንዲያንፀባርቅና በከፍተኛ ደረጃ ተፈ ጻሚነት እንዲኖረው ያደርጋል ፡፡ [19]

ዋና ዋና ዓላማዎች፣ ሥልቶችና ግቦች

በአጠቃላይ የአሥር ዓመቱ ጠቋሚ እቅድ አጠቃላይ ዓላማዎች በኢኮኖሚው መሠረ ታዊ መዋቅር ለውጥ ለማስገኘት፣ የሕዝ ቡን የኑሮ ደረጃ በሚያስተማምን መንገድ ለማሳደግና የክፍላተ ሀገርን የኢኮኖሚ መተሳሰርና ውህደትን ለማፋጠንና ለማ ጠናከር ነው ፡፡ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባሳለፋቸው ውሳኔ ዎች መሠረት ተሻሽለው የተቀየሱት የ10 ዓመት ልማት መሪ እቅድ የሚከተሉት ዓላ ማዎችና ሥልቶች አሉት፡፡ዓላማዎቹም የሰፊ ውን ሕዝብ የኑሮና የባሕል ደረጃ በሚያስተ ማምን ሁኔታ ደረጃ በደረጃ ማሳደግ፣ የኢ ኮኖሚውን የማምረት ችሎታ በተለይም የግ ንባታ አቅም በማዳበር ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ ጥገኛ ያልሆነ ውስጣዊ ተዛ ምዶውና ተደጋጋፊነቱ ጠንካራ የሆነ ብሔ ራዊ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የሀገሪቱን የተፈ ጥሮ ሀብት መንከባከብ፣ መፈለግ፣ ማወቅ ማልማትና መጠቀም፣ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ቁሳዊ መሠረት መጣል፣ የሰፊውን ሕዝብ የትምህርትና የሙያ ደረጃ ማሳደግ፣ሥራ አጥ ነትን ማስወገድ፡ ማኅበራዊ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ማቃለል፣ የኢኮኖሚና የሰሻል እድገት ፍሬዎችን ለሕዝቡ በየአካባቢው በተስተካከለ መንገድ ማዳረስና የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ውህደት ማጠናከር ሲሆኑ እነ ዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የል ማት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተቀ የሱት ዋና ዋና ሥልቶች አሉ ፡፡

እነኝህ ዋና ዋና ስልቶች የሰፊውን ሕዝብ የምግብ ፍላጐት ማሟላትና በአጠቃላይም

Digitized by Google

በምግብ በኩል ራስን መቻል ፣ መሠረታዊ
የሆኑ የኢንዱስትሪ ፍጆታ ዕቃዎችን በብ
ቃት ማምረት ፣ የንጹሕ ውሀ መጠጥ አገ
ልግሎትን ማስፋፋት ፣ የመኖሪያ ቤቶችና
መጠለያዎች ሥራ ማስፋፋት ፣ መሠረታዊ
የጤና አገልግሎትን ማስፋፋት ፣ ኢንቬስት
መንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለ
ውን ድርሻ ማሳደግ ፣ የኮንስትራክሽን ኢን
ዱስትሪን ማስፋፋትና ማጠናከር ፣ የልማት
ሥራዎችን ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ሀብት
ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ማድረግ ፣ የትራ
ንስፖርትና መገናኛ አገልግሎትን ማስፋፋ
ትና ማጠናከር ፣ ወደውጭ የሚላኩ ውጤቶች
ን በመጠን ፣ በጥራትና በዓይነት ማሳደግና
ከውጭ የሚመጡ ሸቀጦችን በተቻለ መጠን
በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ከሀገሪቱ ተጨ
ባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ ቴክኒሎጂዎችን
የመምረጥ፣ የመጠቀምና የማዳበር አቅምን
መገንባትና ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት
መሠረት መጣል ፣ ምርታማነትን ማሳደግና
ማሻሻል ፣ የመንግሥት አስተዳደር ፣ የል
ማትና የፕላን ድርጅታዊ መዋቅርና የአሠ
ራር ስልት ማሻሻልና ማጠናከር፣በየክፍላተ
ኢኮኖሚው የሚካሔዱትን የልማት ሥራ
ዎች ለማካሔድ የሚያስፈልገውን የኢንቬ
ስት መንት ሀብት ለማመንጨት የብሔራዊ
ቁጠባ መጠንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ የ
ደን ልማት ሥራን በከፍተኛ ደረጃ ማካሄድ።
የማዕድን ምርምር ፣ ፍለጋ ፣ ልማትና ምርት
በከፍተኛ ደረጃ ማካሔድ፣ውሀ ፣ አፈርንና
የዱአራር ዊትን መንከባከብ ፣ የአየርንና
የውሀን መበከልን ማስወገድና መቆጣጠር ፣
የሀገሪቱን የውሀና የመሬት እንፋሎት ሀብት
ለኃይል ምንጭ መጠቀም ፣ የአምራቾች የኅ
ብረት ሥራ ማኅበራትን መንግሥታዊ ድር
ጅቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር ፣ በየደረጃው
የሚሰጠውን ትምህርትና የሰው ኃይለ ሥል
ጠናን በጥራት ማስፋፋት ፣ በቴክኖሎጂ አመ
ራረጥ በኩል ይበልጥ በሰው ጉልበት ለመጠ
ቀም የሚያስችል እንዲሆን በማድረግና በአ
ጠቃላይ ኢንቬስትመንትን በማሳደግ የሀብ
ትና ገቢ ፈጠራ ተግባርን በመፍጠር የሥራ
እድልን ማስፋፋት፣በማኅበራዊና የኑሮ ጠን
ቆች የተጠመዱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን
የሞራል ተሀድሶ በመስጠት አምራች ኃይል
እንዲሆኑ ማድረግ ፣ ሊረዱ ለሚገባቸው የተ
ለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች በመንግሥትና
በሕዝብ ትብብር እንክብካቤ ማድረግ ፣ ጠን
ካራና ቀልጣፋ ክፍለ አህጉራዊ የልማትመዋ
ቅር በመዘርጋትና በየአካባቢው የተፈጥሮ
ሀብት ላይ የተመሠረተ የልማት ሥራዎችን
በተመጣጠነ መንገድ በየክፍለ ሀገሩ ማካሄ
ድና እንዲሁም የዘላኑ ክፍልና በጠረፍ አካባ
ቢ የሚኖረውንሕዝብ ኑሮና እድገት በአጠቃ
ላይ ከሀገሪቱ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት
ጋር ይበልጥ የተሳሰረ እንዲሆን ማድረግ
ናቸው ።

የአሥር ዓመቱ ጠቋሚ እቅድ የሚሸፍ
ነው ዘመን ከ1976 እስከ 1985 ድረስ
ያለውን ጊዜ ሲሆን ለዚህም የረጅም ጊዜ
ዕቅድ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ግቦች ለመጣል
የሚያስችሉ የዕድገት መጠኖች ተመልክተ
ዋል ። የረጅም ጊዜው ጠቋሚ እቅድየእ
ድገት መጠኖች በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ውስጥ
መሠረታዊ የምርት ግንኙነት በማካሔድ
ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በማዕከላዊ ፕላን
ለመምራት የሚችል መዋቅር በመዘርጋቱና
የሀገሪቱ የወደፊት የልማት ስትራቴጂ
ቅደም ተከተል በኢሠፓአኮ አማካኝነት
በይፋ በመውጣቱ ለተፋጠነ ኢኮኖሚ እድ
ገት አመቺ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ መቻላቸውን
በመገለጽ ፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የወደፊት
እድገት እንዳለፈው ጊዜ እጅግ አነስተኛ
በሆነ የእድገት ሁኔታ ላይ መቆየት እንደሌ
ለበት በመገንዘብ የረጅም ጊዜ እቅድ አጠ
ቃላይ ግቦችን ከፍ አድርጎ መጣሉ ያልተቆ
ጠበና ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርግ የሚገፋፋ
ነው በሚል አስተሳሰብ ላይ በመመርኮዝ ፣
ለአሥር ዓመቱ ቋሚ እቅድ ካለፉት ዓመ
ታት አማካይ የእድገት መጠኖች በለጥ ተደ
ርገው ቀርበዋል ። እነዚህ የቀረቡት ግም
ታዊ ግቦች የሚያመለክቱት የብሔራዊ ኢኮ
ኖሚውን አጠቃላይ ዓበይት ክፍሎች

Digitized by Google

ብቻ ነው ። እነዚህም ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ፣ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ፣ ጠቅላላ ፍጆታ ፣ የውጭ ንግድና የገቢ ንግድ ናቸው ።

በአስር ዓመቱ ጠቋሚ እቅድ ውስጥ እነዚህን የብሔራዊ ኢኮኖሚውን አጠቃላይና ዓበይት ክፍሎች አስመልክቶ የቀረቡት ዓመታዊ ግቦች የሚከተሉት ናቸው ። ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርትን በአማካኝ በየዓመቱ በ7·5% ማሳደግ ነው ። ጠቅላላ ኢንቬስትመንት በ1975 ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እስከ 12% ድርሻ እንደሚኖረው ሲገመት ፣ በመጠኑ በየዓመቱ በ15% በማደግ በእቅዱ ዘመን መጨረሻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ወደ 23·6% ከፍ ማለት እንደሚኖርበት ተገምቷል ። በረጅም ጊዜው ጠቋሚ እቅድ ዘመን በጠቅላላ የሚያስፈልገውን ጠቅላላ ኢንቬስትመንት በአሀዝ ደረጃ ስንመለከት በመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት (በ1976-1986) በአማካይ 2·2ቢሊዮን ብር በዓመት የሚደርስ ሲሆን በመጨረሻዎቹ አምስት ዓመታት 1981-1985 ደግሞ4.0 ቢሊዮን ብር በዓመት ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል ። ጠቅላላ ፍጆታ የተሰላው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ላይ የሀገር ውስጥ ቁጠባን በመቀነስ ነው ። በ1972 ጠቅላላ ፍጆታ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የ95% ድርሻ የነበረው በ1976 የእቅዱ መጀመሪያ ዓመት 92.4% ዝቅ እንደሚል ተገምቷል ። በ1985 በእቅዱ ዓመት መጨረሻ ድርሻው ወደ 85%ዝቅ ይላል ። ከዚህ ስሌት በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሀገር ውስጥ ቁጠባ ድርሻ እየጨመረ ሲሄድ በአንፃሩ የጠቅላላ ፍጆታ ድርሻ እየቀነሰ እንደሚሔድ እንገነዘባለን ። ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ቀደም ሲል ከጠቅላላ ሀገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነፃፀር እስከ 11% ድረስ የደረሰ ሲሆን በቅርብ ዓመታት ግን እየቀነሰ በመምጣቱ ወደ 5% ደርሷል ። በአሥር ዓመታት እቅድ የመጨረሻ ዓመት የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ ምርት ውስጥ 15% ማድረስ ሲሆን ፤ በእቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የቁጠባ መጠን በየዓመቱ በአማካይ 16.0% ማደግ እንዳለበት ተገምቷል ። የገቢ ንግድ መጠን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በየዓመቱ የሚኖረው አማካይ ድርሻ 26.4% እንደሚደርስ ተገምቷል ። ይህ መጠን ከ1960 እስከ 1966 ባሉት ዓመታት ውስጥ የነበረው ድርሻ ከ12%ያልበለጠ ሲሆን ከ1966 ወዲህ ግን ፈጣን እድገት እያሣየ መጥቶ በ1972 20% ደርሷል ። በአስሩ ዓመት እቅድ (1975-1985) የገቢ ንግድ አማካይ ዓመታዊ የእድገት መጠን 11·35 % እንደሚሆን ተገምቷል ። በውጭ ንግድ በኩል ከ1966-1973 የታየው ዓመታዊ የእድገት መጠን 4·7% ሲሆን በነዚህ ዓመታት ትይዩ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በዓመት በ0.8% አድጓል።በአስር ዓመቱ ጠቋ ሚ እቅድ የውጭ ንግድ በዓመት በ6·75% እንደሚያድግ ተገምቷል ። [20]

ከላይ ከቀረቡት ግቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ቁጠባን ከመዋዕለ ንዋይ እንዲሁም የገቢ ንግድ ከወጪ ንግድ በከፍተኛ መጠን እንዲበልጥ አድርጎ ማቀድ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በውጪ ሀይሎች ጥገኛ የሚያደርገና ጥገኝነቱን እያደርም እያባባሰው የሚሔድ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ። ይህን አደገኛ አዝማሚያ ለመከላከልና የተጠቀሱትን የዕድገት ግቦች ለመምታት እንዲቻል የወደፊቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ መተንበይና የፕላን ግቦችን መጣሉ በቂ ስለማይሆን ፤ እነዚህን የታቀዱትን ግቦች እውን ሊያደርጉ የሚችሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እርምጃዎችን ማመንጨትና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ። በዚህም መሠረት የታቀዱትን የእድገት መጠኖች በሥራ ለመተርጎም እንዲቻል በሕዝብ ብዛት እድገት ሁኔታ ፣ በምግብ ረገድ ራስን በመቻል ፣ በሀገር ውስጥ ቁጠባ መጠን፣ በውጭ ንግድ፣ በኢንቬስትመንት መጠንና ፖሊሲ ፣ በውጭ ብድርና ርዳታ ፣ በሥራ አጥነት ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋት ፣ በክፍለ ሀገራዊ ልማት ፣ በሶሻሊስት ውድድር ፣ በመኖሪያ

Digitized by Google

ቤት ፣ በተስማሚ ቴክኖሎጂ ፣ በገቢ ድል
ድልና እንዲሁም በትምህርትና ስልጠና
በኩል የፖሊሲ እርምጃዎችን መውሰድ
ያስፈልጋል ።[21] በእነዚህ በተጠቀሱት አቅ
ጣጫዎችና በሌሎችም በኩል ከምንከተ
ለው ርዕዮተ ዓለምና የሀገሪቱ ተጨባጭ
ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ የፖሊሲ እርምጃዎ
ችን መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ ከብሔ
ራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራ ማ
ችን መጠናቀቅና ከሶሺያሊስት ኢኮኖሚ
ግንባታ መጀመር ጋር የተቆራኘ ፣ በቀላሉ
መታየት የሌለበትና በዋና ዋና የሀገራችን
የፖለቲካ የኢኮኖሚና ፣ የማኅበራ ግንኙ
ነት አንፃር ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ የሚ
ኖረው ነው ።

ማጠቃለያ

በተለያዩ የማኅበራዊ የኢኮኖሚያዊ ሥር
ዓቶች ውስጥ የሚገኙ አገሮች ዘንድ ለተመ
ጣጠነና ለተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ትክ
ክለኛውና ቀጥተኛው መንገድ ኢኮኖሚ
ውን በማዕከላዊ ፕላን አማካኝነት መሥ
ራት መሆኑ ሁለንተናዊ ተቀባይነት ካገኘ
ውሉ አድሯል ። ዛሬ የቡርዧ መንግሥ
ታት የኢኮኖሚ ፕሮግራምውን ለማድረግ
የሚያካሂዱት ሙከራ የተመጣጠነ የኢኮ
ኖሚ ዕድገት አስፈላጊነት መቀበላቸውን
የሚያረጋግጥ ሐቅ ነው ። እንደ ዕውነቱ
ከሆነ ግን በጠቅላላ ኅብረተሰቡ ደረጃ
ሁሉን አቀፍ የሆነ አጠቃላይ ፕላን ለማዘ
ጋጀትና ተፈጻሚ ለማድረግ የሚቻለው
የምርት መገልገያዎች ግላዊ ይዞታ በቅድ
ሚያ ሲወገድ ብቻ ነው።የተመጣጠነ የምርት
ዕድገት ሊገኝ የሚችለው በማምረቻ መሣሪ
ያዎች ማኅበራዊ ይዞታ ላይ ተመሥርቶ
በሚዘጋጅና በሚካሄድ ማዕከላዊ ፕላን
አማካኝነት ብቻ ነው ። ይህ ብሔራዊ ኢኮ
ኖሚን በአጠቃላይ ማዕከላዊ ፕላን አማካኝ
ነት የመምራት ተግባር ደግሞ የሶሻሊስት
ሥርዓት የተለየ ባሕሪይ ነው።ስለሆነም የም
ርት መገልገያዎች በግል ይዞታ ሥር እንዳሉ
ሆነው በሥርዓቱ ላይ ምንም ዓይነት ሥር
ነቀል የፖለቲካና የሶሽዮ ኢኮኖሚ ለውጥ
ሳይካሄድ ኢኮኖሚውን በፕላን ለመምራት
የሚደረገው ሙከራ በፕላን አዘገጃጀትም
ሆነ አፈጻጸም ደረጃ አያሌ መሠረታዊ ችግ
ሮች እንደሚኖሩት በማመልከት ከሶሻሊ
ዝም ሌላ የተቀሩት የፕላን ቅርጾች በሙሉ
ሐቀኛና የተሟሉ ፕላኖች ሊሆኑ እንደማይ
ችሉ የተረጋገጠ ነው ።

በኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ፕላን በተለ
ያዩ ቅርጾች የሚካሄድ ቢሆንም በእነዚህ አገ
ሮች ኢኮኖሚውም ሆነ ኅብረተሰቡ እርስ በርስ
ያልተሳሰረና የተውገረገረ መዋቅር ይዞ የሚ
ገኝ በመሆኑ የፕላን ጉዳይ እጅግ የተወሳሰ
በና የተቃረነ ክስተት ይሆናል ። ስለዚህ በእ
ነዚህ አገሮች ለፕላን ዝግጅትም ሆነ አፈጻ
ጸም በቅድሚያ ተበታትነው የሚገኙትን የኢ
ኮኖሚ መዋቅሮች ለማሰባሰብና ለማያያዝ
መዋቅራዊ ለውጥ ማካሄድ ያስፈልጋል ።
ባጠቃላይ በኋላቀር አገሮች ለፕላን ዝግጅ
ትም ሆነ ተግባራዊነት የሚያስፈልጉት ማቴ
ሪያላዊና ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔታዎች መዘ
ጋጀት ይኖርባቸዋል እነዚህ ለፕላን አስፈ
ላጊ የሆኑት ማቴሪያላዊና ማኅበራዊ ሁኔታ
ዎች የሚዘጋጁበት አቅጣጫ ደግሞ በሚመ
ረጠው የዕድገት ፈለግ ላይ ይመሠረታል ።

የእስከዛሬው የፕላን አዘገጃጀትና አፈጻ
ጸም ልምድ እንደሚያሳየው ካፒታሊስት
የዕድገት ፈለግን በሚከተሉ ኋላቀር አገሮች
የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን ተብለው
የተዘጋጁት ፕላኖች የታለመላቸውን ዓላ
ማና ግብ ካለመምታታቸውም በላይ ሊያስ
ወግዷቸው የተነሱት ችግሮች ይበልጥኑ
አባብሰዋቸዋል ። ይኸውም በፕላኑና በተግ
ባራዊ ውጤቱ መካከል ሰፊ ልዩነት ተከስ
ቷል ፣ ፕላኑ ለሕዝቡ በሚሰጠው ተስፋና
በኢኮኖሚው ዕውነታ መካከል ትልቅ ልዩ
ነት ተፈጥሯል።ባጠቃላይ የፕላን ፖሊሲዎቻ
ቸው ድኅነትን ለማጥፋት ፣ የሀብት መበላለ
ጥንና ሥራ አጥነትን ለመቀየስ የሚሹ ይሁኑ
እንጂ በተግባራዊ ውጤቶቻቸው ግን ለእነ
ዚህ ችግሮች መቀጠል አስተዋጽኦ አድርገ
ዋል ።[22]

Digitized by Google

በኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ፕላን ውጤ
ታማ እንዲሆን ከተፈለገ ከፖለቲካዊና ሶሽዮ
ኢኮኖሚ ለውጦች ጋር መዋሃድ ይኖርበ
ታል ። «ለፕላን በብሔር አቀፍ ደረጃ በተ
ሳካ ሁኔታ ተግባራዊ መሆን አስፈላጊ የሆ
ኑትን ማቴሪያላዊና ማኅበራዊ ቅድመ ሁኔ
ታዎች ሊያስገኝ የሚችለው መንገድ የሶሽ
ያሊስቱ የዕድገት ፈለግ ብቻ እንደሆነ ያለ
ፉት ሁለትና ሦስት አሥር ዓመታት አሳይ
ተውታል ። [23] ለዚህም ምክንያት የሆነው
የሶሻሊዝምን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገ
ሮች ሰፊና የማይናቅ ተዕዕና ሊኖረው የሚ
ችል መንግሥታዊና ሕዝባዊ የሀብት ይዞታና
ተራማጅ የሆኑ መንግሥታት በመኖራቸው
የተነሳ ለፕላን አዘገጃጀትም ሆነ አፈጻጸም
ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆኑት ቅድመ ሁኔ
ታዎች ሊፈጠሩ በመቻላቸው ነው ።

በኢትዮጵያ ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ የቀ
ድሞውን አድኃሪ መንግሥት ከሥልጣን ማስ
ወገድ ጋር በማከታተል በተወሰዱት እርም
ጃዎች ለሀገሪቱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድ
ገት አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ። ዋና ዋና የም
ርት መገልገያዎች በመንግሥትና በሕዝብ
ቁጥጥር ሥር ለማዋል በተወሰዱት ሥርነ
ቀል ተራማጅ እርምጃዎች ፣ ከእነዚህም በተ
ጨማሪ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ የሀገሪቱን
የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲ ድርጅታዊ
መዋቅር ሶሻሊስት ፈር ለማስያዝና የሰፊ
ውን ሠርቶ አደር ሕዝብ የኢኮኖሚ ጥቅም
ለማጠናከር ለመጠበቅ እንዲቻል የወጡት
አብዮታዊ አዋጆችን መመሪያዎች የሀገሪ
ቱን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት በተቀ
ነባበረ መልክ በማዕከላዊ ፕላን ለመምራት
የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች ሁነዋል ።
በእነዚህ አመቺ ሁኔታዎች ላይ በመመሥ
ረት የሀገሪቱን ዕድገት በተራማጅ መልክ
አቅዶና በአንድ አጠቃላይ ፕላን በመም
ራት ፣ ፕላኑ በወቅቱ በተግባር መተርጐሙን
በመቆጣጠር ካለፈው ሥርዓት ከተወረሰው
የኢኮኖሚ ኋላቀርነት ለመላቀቅ ተጨባጭ
ጥረቶች ተካሂደዋል ። ለዚህም ሲባል ጥቅ
ምት 1971 የብሔራዊ የምርት ዘመቻና የማ
ዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ በአዋጅ እን
ዲቋቋም ተደርጓል ።

ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በአጠቃላይ ፕላን
የመምራቱ ተግባር የጠቅላይ መምሪያው
አንዱ ዋነኛ ዓላማ ቢሆንም በጊዜው በነበ
ረው የኢትዮጵያ ሁኔታ አጠቃላይ ፕላኖችን
ለማዘጋጀት ከሚያስፈልጉት በቂ ጊዜ ፣ ልም
ድና የተሟላ ድርጅታዊ መዋቅር ችግሮች
ባሻገር በቅድሚያ ጐልተው ለሚታዩት ወቅ
ታዊና አጣዳፊ የኅብረተሰቡ ችግሮች ለመ
ፍትሔ መሻቱ ተገቢ ስለነበር በየዓመቱ በዘ
መቻ መልክ እነዚህን ችግሮች የመፍታቱ
ተግባር ትኩረት ተሰጥቶቷል ። በዚህም መሠ
ረት እስከ ዛሬ ድረስ አራት ዘመቻዎች የተ
ካሄዱ ሲሆን በዚህ ቢያዝነው ዓመት ደግሞ
አምስተኛውን ዘመቻ በማካሄድ ላይ እንገ
ኛለን ። የጠቅላይ መምሪያው መቋቋምና
የዘመቻዎቹ በተከታታይ መካሄድ በኅብረተ
ሰቡ ውስጥ ጐልተው ይታዩ የነበሩት ጊዜ
ያዊና አጣዳፊ ችግሮች በማቃለል በኩል
አስተዋጽኦ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ለማዕ
ከላዊ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም አስፈላጊ
የሆኑ ሁኔታዎችን ማለትም ከቀምሞው የተ
ሻሻለ ድርጅታዊ መዋቅር ፣ በፕላን ሙያ
ተፈላጊነት ያለው የሠለጠነ የሰው ኃይልና
ፕላንን በሥራ ለመተርጐም የሚያስችል
በሕግ የተደነገገ ሰፊና ከፍተኛ የመቆጣጠር
ሥልጣን አስገኝቷል ። ይሁንና የኅብረተሰቡ
ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በጥቂት
ዓመታት ውስጥ የመጨረሻ መፍትሔ ሊገ
ኙላቸው የማይችሉ በመሆናቸው ይህ ጥረት
የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ፕላን በማውጣት
መካሄድ እንዳለበት ዕሙን ነው ። ይሁንና
በአሁኑ ጊዜ ያለው የዘመቻ ጠቅላይ መመ
ሪያ አወቃቀር በወቅቱ በነበረው ተጨባጭ
ሁኔታ አስገዳጅነት የአጭር ጊዜንና (ዘመቻ
የመካከለኛው ጊዜ ግቦችን በተደራራቢነት
እንደሚያከናውን ሆናም ግን ዋናው ትኩ
ረቱ በጣም ጐልተው ለሚታዩ ወቅታዊና
አጣዳፊ የኅብረተሰቡ ችግሮች በአጭር ጊዜ

Digitized by Google

ውስጥ መፍትሔ ለማስገኘት ተገቢውን አመራር እንዲሰጥ ተደርጐ የተዋቀረ በመሆኑ ለዘለቄታው በማዕከላዊ ፕላን አማካኝነት የአገሪቱን የረዥም ጊዜ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት በፕላን ለመምራት ድርጅታዊ አቋሙ ከዚህ ተግባር ጋር ሊጣጣም በሚችልበት መንገድ መሻሻሉ ወቅታዊነቱ ይታያል ።

በሌላ በኩል አንድ የተወሰነየፕላን ሞዴል ጥያቄ ባለው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ ይመሠረታል ። በኢኮኖሚው የተበታተኑ ትናንሽ ከእጅ ወደ አፍ አምራቾች ከፍተኛውን እጅ ይዘው የሚገኙበት ፣ የገንዘብ ልውውጥ የሚካሄድበት ክፍል Monetary Sector እጅግ ጠባብ በሆነ ነበር ፤ በኢንዱስትሪዎች መካከል መኖር የሚገባው ውስጣዊ መያያዝና ትንጅት ዝቅተኛ ፣ አልያም ባዶ በሆነበት ሁኔታ ዝርዝር አኃዛዊ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፕላን ዝግጅት ሆነ ተግባራዊነት ውሱን እንደሚሆን አጠያያቂ አይሆንም ። ስለሆነም በዚህ ደረጃ የፕላን ዝግጅት በኢኮኖሚው የተለያዩ መስኮች ባጠቃላይ ሳይሆን በተወሰኑ የኢኮኖሚው ዋና ዋና ገጽታዎች ላይ መመሥረት ይኖርበታል ። ለምሳሌ ፕላኑ በአጠቃላይ የምርት ዕድገትና ዋና ዋና ይዘቶቹ ላይ ማተኮር ይኖርበታል ። በረጅም ጊዜ ግን የዕድገት አቅጣጫ ከፍተኛ ዝርዝር የፕላን ስልቶችን መጠቀም ይኖርበታል ።

ከላይ በተገለጹት መሠረታዊ ችግሮች የተነሳ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን አጠቃላይና ዝርዝር የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፕላን ማዘጋጀት እንደማይቻል እንረዳለን ። በመሆኑም ያለው አማራጭ የረጅም ጊዜ ጠቋሚ ዕቅድ ማዘጋጀት ሆኗል ። ይህ ጠቋሚ ዕቅድ ግን በካፒታሊዝም ውስጥ ከሚዘጋጁት ጠቋሚ ዕቅዶች መሠረታዊ ዓላማዎችም ሆነ ተግባራዊ በሚሆንበት ዘዴው አኳያ ዓይነተኛ የሆነ ልዩነት አለው ። ፕላኑ ሥርነቀል ከሆነ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር የተያያዘ በመሆኑም በረጅም ጊዜ ወደ አጠቃላይ ሶሻሊስት ዕቅድ (Comprehensive socialist planning) የሚያሸጋግር ነው ።

ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የፕላን ዕፍገት በመረጠችው ኢካፒታሊስታዊ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ዕድገት ፈለግ ላይ የተመሠረተ ነው ። ወደ አጠቃላይ ፕላን ምሥረታ የሚደረገው ሽግግር ከመረጥነው የሶሽዮ ኢኮኖሚ ዕድገት ፈለግ ላይ የተመሠረተ ነው ። ወደ አጠቃላይ ፕላን ምሥረታ የሚደረገው ሽግግር ከመረጥነው የሶሽዮ ኢኮኖሚ ዕድገት መስመር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለዚህ መስመር መጠበቅ ፣ መጠናከርና ለዕድገቱ መፋጠን የግንባር ቀደም አብዮታዊ ፓርቲ ሕልውና ማግኘት አስፈላጊ ነው ። ስለዚህም በኢሠፓአኮ አማካኝነት የሠርቶ አደሩን ፓርቲ ሕልውና ለማስገኘት የሚደረገው ጥረት ዛሬም ሆነ ወደ ፊት በአጠቃላይ ሶሻሊስት ፕላንን ለመምራት ለምናደርገው ጥረት ወሳኝነት አለው ። የዚህ የግንባር ቀደም ፓርቲ አመራር በፕላን ዝግጅትም ሆነ አፈጻጸም በኩል ከተመረጠው የዕድገት ፈለግ አንፃር ትክክለኛውን ፣ ተገቢና ወቅታዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ንቁ የሆነ ሕዝባዊ ተሳትፎና ብቁ ካድሬዎችን በማስገኘት ወዘተ . . . በኩል አስፈላጊ ሚና ይኖረዋል ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. Article by Oscar Lange, "The Role of Planning in Socialist Economy, Memographed, p. 1.
2. *Ibid.*
3. Yu. M. SHVYRKOV, *Centralized Planning of the Economy*, (Moscow: Progress Publishers, 1980), p. 5.
4. USSR Acadamy of Sciences, 'Planning Socio-Economic Progress", *Social Sciences*, Vol. XII, No. 1, 1981, pp. 144-145.
5. *Reading on the Ethiopian Economy*, ed Gerard J. Gill, p. 395.
6. ሁለተኛ የአምስት ዓመት የልማት ፕላን 1955-1959 ፣ ገጽ 61
7. J. Gill, p. 396.
8. የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መመሪያ ፣ አዲስ አበባ ፣ ጥር 30 ፣ ቀን 1967 ፣ ገጽ 3
9. ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም
10. በብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች በሚመለከት ለአኢወግ ማዕከላዊ ኮሚቴ የተዘጋጀ መግለጫ ፣ መጋቢት 1973 ፣ ገጽ 14-24
11. ከላይ የተጠቀሰው
12. የብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ የአራተኛው ዓመት 1974 ዕቅድ ፣ ገጽ 27-29
13. ከላይ የተጠቀሰው
14. L. Ya Berri, ed; Planning a Socialist Economy, Vol. 1, (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 50-51.
15. «የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አጠቃላይ ዓላማዎች ፣ ስልቶችና አበይት የዕድገት አቅጣጫዎች» የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ የካቲት 1974 ፣ ገጽ 2-4
16. Opcit, *Social Sciences*, Vol. XII, 1981, p. 147.
17. የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አጠቃላይ ዓላማዎች ፣ ስልቶችና አበይት የዕድገት አቅጣጫዎች ፣ 1975 ፣ ገጽ 33
18. ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 35
19. የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አዘገጃጀት መዋቅርና የግብረ ኃይሎች የሥራ መመሪያ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ ፣ መጋቢት 1974 ፣ ገጽ 1
20. «የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ አጠቃላይ ዓላማዎች ፣ ስልቶችና አበይት የዕድገት አቅጣጫዎች » ፣ ገጽ 36-43
21. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 44—52
22. Michael P. Todaro, *Economic Development in the Third World*, (London: Longman, 1977), p. 376.
23. Shvyrkov, p. 10.

Digitized by Google

ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው ታሪካዊ ትግል

ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ እስከ 1950ዎቹ *

(ክፍል ሁለት)

—ኢሳይያስ ደምሴ

ኢምፔሪያሊስቶች በ19ኛው ምዕተ ዓመት ማከተሚያ ላይ ዓለምን በቅኝ ለገዛዝ ተከፋፍለው በጨረሱበት ወቅት በትጥቅ ትግል ነፃነቷን አስከብራ ለመኖር የቻለች ብቸኛ አፍሪካዊት አገር ኢትዮጵያ ነበረች ። * *

ኤም ሺ ራይት

በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያው ክፍል /መስከረም ቅጽ 2 ቁጥር 9/ ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ኋላቀር የሆነ የጦር መሣሪያ እየተጠቀመ የአገሩን ነፃነትና አንድነት ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምና ከተቀናቃኞቹ ቅኝ ገዥዎቹ ፈረንሣዮች፣ኢጣሊያኖችና ቱርኮች የተሠነዘሩባትን የማጥቃትም ሆነ የወረራ ሙከራ ሲከላከልና ድል ሲያደርግ መቆየቱን አይተናል ። ከዚሁ ከመከላከል ትግሉም ባካበተው ልምድ የማይናቅ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድሎችን በተንደኞች የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስታዊ አገሮች ላይ በየዘመናቱ ለመቀዳጀት በቅቷል ። በተለይም በ19ነኛው ምዕተ ዓመት ፣ እያሌ የአፍሪካ አገሮች በአውሮፓውያን ግለትም በተንደኞቹ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሣይ ፣ በፖርቱጋል ፣ በቤልጅግ ፣ በጀርመን ፣ በኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ሥር የወደቁበት ዘመን ሆኖ ሳለ ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ግን ምንም እንኳ የውስጥ የመደብ ጠላቶቹ የሆኑት ፊውዳል ገዥዎች ኃይሉን እየከፋፈሉበት አንዳንድ ጊዜ ለቅኝ አገዛዝ አመቺ ሁኔታ የተፈጠረ መስሎ ቢታይም ፣ ደካማ ጎኑን እየሸፈነ በፍጹም ታጋይነትና አልበገሬነት ዳር ድንበሩን ጠብቆና ነፃነቱን አስከብሮ መቆየቱ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዲሰጠው አድርጎታል ። ለድል አድራጊነቱ ዓይነተኛ ምሳሌም በኢጣሊያ ኢምፔሪያሊዝም ላይ በአድዋ የተጎናጸፈው ድል መጥቀሱ በቂ ይሆናል ።

በዚህ ጽሑፍ ክፍል ሁለት የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ከ20ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ጀምሮ 1950ዎቹ መባቻ ላይ በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ እስከተተካበት ድረስ የነበረውን ሚና ለመመርመር እንሞክራለን ።

እንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በዓባይ ሸለቆ

በ19ኛው ምዕተ ዓመት ማከተሚያ ገደማ

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

** A History of Africa 1981-1967 "NAUKA" Pr. Moscow, 1967 p. 324.

Digitized by Google

ኢትዮጵያ ከካፒታሊስት አገሮች ጋር የነበራት ግንኙነት በቅርጽና በይዘቱ ለየት ያለ መልክ እየያዘ መሄድ ጀመረ ። ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ይበልጥ እየተጠናከረ የመጣበት ከመሆኑም በላይ በንግድ ፣ በአገር ጉብኝነት በወንጌላዊነትና በዲፕሎማሲ መልክ የተሠማሩ አያሌ የአውሮፓ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የጀመሩበት ወቅት ነበር ። በተለይም በዲፕሎማሲ መስክ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ፣ ኢጣሊያና ሩሲያ ቀዋሚ ለጋሲዮኖቻቸውን በአዲስ አበባ ውስጥ ከ1896—1906 ባለው ጊዜ ውስጥ በመከፈት ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ሥራ ያካሄዱበት ወቅት ነው ።

በ20ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ላይ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የአሜሪካን የዲፕሎማቲክ ቡድን መርቶ የመጣው እስኪነር እንዳለው ፣ በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ይበልጥ ተስፋፍቶ ይታይ የነበረው የፈረንሣይ ካፒታል ቢሆንም ፣ እንግሊዝም ቅኝ ግዛቷ ከነበረችው ሕንድ ሸቀጥ ወደ ኢትዮጵያ እያስመጣች ንግድዋን ለማስፋፋት ጥረት ታደርግ ነበር ።[6] በያዝነው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይም የእንግሊዝን ጥቅም በመወከል በአዲስ አበባ ከተማ ተቀማጭ የነበረው ጆን ኤልዐሪንግተን በኢትዮጵያ ውስጥ የፈረንሣይን ገበያ ለማጥበብ ፣ የእንግሊዝን ጥቅም ለማስከበርና ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል ።

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ 1902 ስምምነት

ኢትዮጵያ ኢጣሊያን አድዋ ላይ ድል ከመታች በኋላ ኢጣሊያ የኢትዮጵያን ነፃነትና ግዛት አውቃ በመቀበልና ከኢትዮጵያ ቆርጣ የያዘችውንም የባሕረ ነጋሽ ግዛትን ወሰን በመከለል ጥቅምት 1896 አዲስ አበባ ላይ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ስምምነት ስትፈራረም ፈረንሣይም ከኢትዮጵያ ባገኘችው የባቡር ሐዲድ ሥራ ኮንሴስዮን ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ጥቅሟን እያስፋፋች መጣች ። ይህም እንግሊዝን ክፉኛ አሳስቦአት ነበር ።

በሌላም በኩል እንግሊዝ የሱዳን ግዛት የነበረውን አምዱርማንን በ1898 በቁጥጥሯ ሥር ካዋለች በኋላ ነጭ ዓባይንና አብዛኛውን የዲንደርን ፣ የጥቁር አባይን ፣ የጋሽና የአትባራን ሸለቆዎች ወደ ሱዳን ቅኝ ግዛቷ ለመጨመር ወታደሮቿን በኢትዮጵያ ጠረፍ ላይ ማሰፈር ጀመረች ። ኢትዮጵያም በበኩሏ ግዛቷ ቤኒሻንጉልንም እንደሚአጠቃልል ገልጾ ወሰኗን ለማስከበር ተመሳሳይ ርምጃ ወሰደች ።[2] በዚህም መሠረት ከ14 ዲግሪ እስከ 2 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስና በነጭ አባይ መካከል ያለው የራሷ ግዛት መሆኑን ለእንግሊዝ አስታወቀች ።[3] ኢትዮጵያ በ1902 አካባቢም በደቡብ ኬንያንና በምዕራብ ሱዳን የሚያዋስነውን ግዛቷን እያጠናከረች መያዝ በመጀመሯ የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ጉዳዩ አሳሳቢ መልክ እየያዘ መሄዱን በማጤን በዲፕሎማሲ መንገድ መፍትሔ ለመስጠት ይጥሩ ጀመር ። ይህንንም ከፍጻሜ ለማድረስ እንግሊዝ በኢትዮጵያና በሱዳን በኩል ያለውን ወሰን ለመከለልና ኢትዮጵያ ይገባኛል ያለችውን ግዛት ስታገኝ በምትኩ የወርቅ ማዕድን ቁፈራ ኮንሰሲዮን ለእንግሊዝ ከበርቴዎች እንድትፈቅድ ፣[4] የአባይ ወንዝ መጋቢ የሆኑትን ሰባትንና ሌሎችንም ወንዞች እንዳትገድብ አንድ ዓይነት ውል ለመፈረም በመልክተኛዋ በሐሪንግተን በኩል ጥያቄ አቀረበች ።

ኢትዮጵያም በወቅቱ ከነበረው የፖለቲካ አንፃር ሁኔታዎችን አገናዝባ ጥያቄውን በመቀበል በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ወሰን በመከለል ፣ የተባሉትንም ወንዞች ላለመገደብና የእንግሊዙ ሱዳን መንግሥትም በየዓመቱ ለኢትዮጵያ የተወሰነ ገንዘብ/ 10ሺህ ጊኒ - የሱዳን ገንዘብ) እንዲከፍላት ውል በመግባት በ1902 አንድ ስምምነት ተፈራረመች ።[5]

ኢትዮጵያ የ1902 ውልን የፈረመችበትን አንዳንድ ምክንያቶች ከወቅቱ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ነባራዊ ሁኔታ በመ

Digitized by Google

ነግት መጠቆም ይቻላል ። አንደኛ ፣ ኢትዮጵያ ምንም እንኳ በ1896 ከኢጣሊያ ጋር ባደረገችው ጦርነት ድልን ብትጎናጸፍም የጦር ኃይሏ በዓይነትም ሆነ በመጠን ዝቅ ያለ ነበር ። በመሆኑም የጦር ኃይሏ አስተማማኝ ሳይሆን ፣ ከእንግሊዝ ጋር አስፈላጊ ያልሆነ ጦርነት ከማድረግ ይልቅ አንድ ዓይነት ስምምነት ማድረጉ የነበራት አማራጭ ነው ማለት ይቻላል ። ሁለተኛ ፣ ኢጣሊያ ምንም እንኳን በ1896 በአዲስ አበባው ስምምነት መሠረት የኢትዮጵያን ነፃነትና አንድነት አውቃ ብትፈራረም በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በመጠቀም ከእንግሊዝ ጋር ተባብራ በኢትዮጵያ ላይ መልሶ የማጥቃት ዘመቻ ልታካሂድና ልታጠቃ የምትችልበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ መሆኑ ይገመታል ። ሦስተኛ ፣ ኢትዮጵያ በፈረንሣዮች ያስጀመረችው የባቡር ሐዲድ ሥራ ሊፈጠር በሚችለው የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ግጭት እንዳይደናቀፍም ለማድረግ ነው ማለትም ይቻላል ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ ላይ ባለው ከፍተኛ ኢምፔሪያሊስታዊ ጉጉትና በግብፅና በሱዳን ላይ የነበረውን ይዞታ አስተማማኝ ለማድረግ ከነበረው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሣ በየጊዜው የሚያደርጋቸውን ስምምነቶችና ውሎች ሲሰጥና ሲለዋወጥ ታይቷል ። እንግሊዝ በ1902 ከኢትዮጵያ ጋር ያደረገችውን ውል ወደጐን በማለት እንደገና በ1905 ገደማ የዓባይ ውሃ በኢትዮጵያ የዝናብ ወቅት እየበዛ ዝናብ በሌላቸው ወራት ውስጥ ያንሣልና በጣና ባሕር አካባቢ አባይን ገድበን እንደዳስፈላጊነቱ እንጠቀምበት ፣ ወንዙም ሲገደብ በጣና ሃይቅ ውስጥ ያሉትን ደሴቶች እንዳያስጥማቸው መሃንዲስ ልከን እና ስጠናው የሚል ጥያቄ አቀረበች ። በጥያቄው መሠረት ተፈቅዶላት መሃንዲሶችን ልካ ነበር ።

ይሁንና ጊዜው የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ይካሄድ የነበረበት ወቅት ስለነበረ የአውሮፓ የፖለቲካ ሁኔታ የተቀያየረ መጣ። በአውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች መካከል ይካሄድ በነበረው ውድድር ውስጥ ጀርመን የበላይነቱን ለመያዝ አደገኛ በሆነ አጥቂነት ብቅ አለች ። በአፍሪካም ፣ በተለይ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ይደረግ የነበረው የቅኝ ገዥዎች ፉክክር መልኩን ለወጠ ። ከዚህም በቀር በዚሁ ወቅት የጀርመን ከበርቴዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታላቸውን በሥራ ለማዋል ፣ ከሃያ ዓመታት ያላነሰ በአካባቢው ይሯሯጡ የነበሩትን እንግሊዝን ፣ ፈረንሣይንና ኢጣሊያንን ለመቀናቀንና ይዞታቸውንም ለመንጠቅ ሲሉ በ1906 ገደማ በኢትዮጵያ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋት እንዲፈቀድላቸውና ኮንሲሰዩንም እንዲያገኙ ጥያቄ ያቀረቡበት ወቅት ነበር ።

ሶስትዮሽ ስምምነት
(Tripartite Agreement)

ከ1896 እስከ 1906 ድረስ በነበሩት ዓመታት ፣ ኢትዮጵያ አንፃራዊ የሆነ ፋታ የአገኘችበትና ብሔራዊ ግዛቷንና ዳር ድንበሯን ለማስከበር ጥረት ያደረገችበት ወቅት ነበር ። በነዚህ ዓመታት ውስጥም ኢትዮጵያ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ውሎችን ፣ ማለትም ከኢጣሊያ ጋር በጥቅምት 1896 እንዲሁም ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድ ሚያዝያ 28 ፣ 1897 በፈረንሳይ ሶማሌና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰንና ሌሎችም ጉዳዮች የሚመለከት « የነጭ አባይ ኮንቬንሽን » ተብሎ የሚጠራውን ውል ከፈረንሣይ ጋር ስትፈራረም ፣ በእንግሊዝ ሶማሌና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰን ግንቦት 14 ፣ 1887 ፣ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰን ግንቦት 2 ፣ 1902 እና በኬንያና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰን በሚመለከት ረገድ ታኅሣሥ 7 ፣ 1906 ከእንግሊዝ ጋር ፈርማለች ።

Digitized by Google

በኢትዮጵያ ውስጥ የግል ጥቅማቸውን ለማስከበርና ለማስፋፋት ይፎካከሩ የነበሩት እንግሊዝ ፈረንሣይና ኢጣሊያ በመካከላቸው የነበረውን ልዩነትና ፉክክር አቻችለው ኢትዮጵያን በስምምነት ለመቀራመትና አደገኛ ሁኖ የታየቻቸውን ጀርመን በኢትዮጵያ እጅዋን እንዳታስገባ (ምንም እንኳ በውሉ ውስጥ ባይጠቀስም) በጋራ ለመከላከል ሲሉ በለንደን ታኅሣሥ 13 1906 ተሰብስበው «የሶስትዮሽ ስምምነት» የተባለውን ውል ተፈራረሙ ።

ስምምነቱም ፤ 1/ በዓባይ ወንዝና ወደ ርሱ በሚገቡ መጋቢ ወንዞች ላይ እንዲሁም አባይ የወርድበት ሸለቆ እንግሊዝ አለኝ የምትለውን ጥቅምና በምዕራብ ኢትዮጵያ የባቡር ሐዲድ የመዘርጋት ፍላጎትዋ እንዲሟላ ይፈቅዳል ፤ 2/ ፈረንሣይ ቀደም ብላ የጀመረችውን የጂቡቲ አዲስ አበባ የባቡር ሐዲድ ሥራ አጠናቃ ሥራ ላይ እንድታውልና በመንገዱም አካባቢ ያላትንም ልዩ ጥቅም ያስከብርላታል ፤ 3/ ኢጣሊያ የኤርትራንና የኢጣሊያን ሱማሌን ይዞታዋንና በተለይም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ መሀል ለመሀል አልፎ ሁለቱን ቅኝ ግዛቶቿን የሚያገናኝ የባቡር ሐዲድ እንድትዘረጋና አካባቢውንም እንድትቆጣጠር ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነትን አስገኝቶላታል ። ይህ ስምምነት ኢትዮጵያን ሳይጨምር በሦስት አገሮች መካከል ብቻ ኢትዮጵያን ለመቀራመርት የተደረገ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ኢትዮጵያን የሚሸነገሉበት ሀረግም ተጨምሮበታል ። በውሉ አንቀጽ 1 እንደተገለጸው ስምምነቱ በምንም ዓይነት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና የፖለቲካ ነፃነት «የማይነካ» እንደሆነ ይናገራል ።

ይህ ዓይነቱ ስምምነት ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኋላቀር የሆኑ አገሮችን በቁጥጥራቸው ሥር ያዋሉበት ሌላው ዘዴያቸው ነበር ። በንእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ግንባር ቀደምትነት በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን ይህ ዓይን ያወጣ ጣልቃገብነት ግልጽ የሆነ ዕብሪተኛነትና ማንአለብኝነት መሆኑ አያጠራጥርም ። ይህ ነፃ የሆነችዋ ኢትዮጵያ ባልተገኘችበትና ባልተስማማችበት ራስዋን አስመልክቶ በቅኝ ገዥ አገሮች የተደረገ ስምምነት በብሔራዊ ግዛትዋ ውስጥ ገብቶ ግዛቷን እየቆራረሰ የባዕድ ጥቅም ክልል ያደረገ እንደመሆኑ የግዛት አንድነትዋን ለመድፈር የፖለቲካ ነፃነትዋን ም ለመገፈፍ የተቃጣ ስምምነት ነበር ።

ይሁንና ኢትዮጵያ ባልተካፈለችበትና ባልፈቀደችው ስብሰባ የተደረገው ስምምነት በምንም ዓይነት የማትቀበለው መሆንዋን ከመግለጽም በላይ እንዲያውም እንደጣልቃ ገብነትና ወረራ የምትቆጥረው መሆኑን ለሦስቱ መንግሥታትና በአዲስ አበባ ውስጥ ወኪሎች ለነበሯቸው አገሮች ወዲያውኑ አስታውቃለች ።

በመሠረቱ ሦስቱም የውሉ ተፈራራሚ አገሮች በተለይም ኢጣሊያና ፈረንሣይ ፍላጐታቸው ሙሉ በሙሉ ስላልረካ በስምምነቱ አልተደሰቱም ነበር ። ኢጣሊያ ከእንግሊዝ ጋር በ1881 እና በ1884 ያደረገቻቸው ስምምነቶች (ማለት ከአድዋ ጦርነት በፊት) መላዋ ኢትዮጵያ የእርሷ ጥገኛ እንድትሆን ፈቅዶላት ስለነበረ በአዲሱ ስምምነት ላይ የነበራት ቅሬታ በግልጽ ይታይ ነበር ። በዚህም የተነሣ ኢጣሊያን ወክሎ የተፈራረመውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ቲቶኒን የኢጣሊያ ፓርላማ ጠርቶ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ጥቅም አሳንሶ በመፈራረሙ በከፍተኛ ደረጃ ወቅሶታል ። ፈረንሣይም በበኩሏ ከአዲስ አበባ ወደ አባይ ወንዝ የሚያልፍ የባቡር ሐዲድ እንዳትሠራ ስምምነቱን ስለሚያግዳት ደስ አልተሰኘችበትም ።[7]

በ1915 ስምምነት

የ1906 የሦስቱ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ስምምነት ኢትዮጵያን በመከፋፈል ረገድ የጥቅም መበላለጥን በማስከተሉ

Digitized by Google

ፀተፈራራሚዎችም ዘንድ ቅሬታ ነበርና ተግባራዊ አልሆነም ። ከዚህም በቀር የአንደኛው ዓለም ጦርነት ቀስቃሽ የሆነችው ተስፋፊዋ ጀርመን ለሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ሕልውናም ሆነ ከድንበራቸው አልፈው ካፒታላቸውን በቅኝ ግዛቶች ላይ ለማስፋፋት ሲሉ ለሚያደርጉትም ሩጫ አደገኛ እየሆነች መምጣቷ በጉልህ ይታይ ጀመር ።

ተቀናቃኞቹ ኢምፔሪያሊስቶች ከአውሮፓ ውጭ የሚያደርጉትንም ፉክክር ለጊዜው የስምምነት መልክ ባለው ሁኔታ እያካሄዱ ኃይላቸውን አስተባብረው ተቀናቃኝ ሁነው የቀረቡትን ጀርመንና አውስትር ሀንጋሪን ለመውጋት በሚአደርጉት ዝግጅት ኢጣሊያንም የጦር አጋራቸው የሚያደርጉበትን ዘዴ መቀየስ ጀመሩ ። ይሁንና ኢጣሊያ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በ1914 ከተቀሰቀሰ ጀምሮ የአውስትሪያና የጀርመን የጦር ጓደኛ የመሆን ዝንባሌያዋ እያመዘነ ሄደ ። የኢጣሊያንን ዝንባሌ በቅርብ ይከታተሉ የነበሩት እንግሊዝና ፈረንሣይም ኢጣሊያ ከጀርመን ጋር በጦር ጓደኛነት እንዳትተባበር ለማድረግ የሚቻልበትን ዘዴ ለመቀየስ ለንደን ላይ በ1915 የምሥጢር ስብሰባ አደረጉ ። በዚህ ስብሰባ ኢጣሊያ ከአውስትሪያና ከጀርመን ጋር የማትተባበርና በጸረ ጀርመንነት የምትሰለፍ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ዓይነት ጥቅም እንድታገኝ የሚፈቅዱላት መሆኑን በውሳኔአቸው ላይ ሲጠቁሙ ፣ ኢጣሊያም ቅኝ ግዛቶቿን የሆኑትን የኤርትራን ፣ የኢጣሊያን ሱማሌ...ንወሰን አካባቢዎች አስመልክታ ላነሳቻቸው ጥያቄዎች ተመጣጣኝ የሆነ ይዞታ ልታገኝ ትችላለች[8] በሚል ለመደራደር ሙከራ አድርገዋል ። ከዚህ ላይ ምንም እንኳ ሊፈቀድላት የታሰበው ጥቅም በግልጽ ባይጠቀስም ኢጣሊያ ደጋግማ ያነሳችውን ኤርትራንና የኢጣሊያ ሱማሌን የሚአገናኝ የባቡር ሐዲድ የመዘርጋት ጥያቄና በአካባቢው ላይ እንዲኖራት የፈለገችውን የኢኮኖሚ የበላይነት ሳይሆን እንደማይቀር ከሁኔታዎች መገመት ይቻላል ።

በ1915 በእንግሊዝና በፈረንሣይ መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት አሁንም ኢትዮጵያ ሳታውቀውና ሳትፈቅደው ፣ በራሷ ሕልውና ላይ የተዶለተ የሁለቱ አገሮች በተለይም የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ሴራ ነበር ።

የእንግሊዝ ለጣና ባሕር መጓጓት

እንግሊዝ ከሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር ኢትዮጵያን ለመከፋፈል የወጠነችውን በመሻር በፊት አንስታው የነበረውን በጣና ባሕር ላይ ግድብ ለመሥራትና ከእሱም ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ለማከናወን ትችል ዘንድ ኢትዮጵያ እንድትፈቅድላት በ1919 ጥያቄ አቀረበች ። ኢጣሊያ በበኩሏ መልእክተኞች ወዲያውኑ ወደለንደን ልካ እንግሊዝ ያቀረበችውን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ የምትደግፍ መሆኗን ገልጻ ፣ እርሷም ከኤርትራ እስከ ጣሊያን ሱማሌ ድረስ ለመዘርጋት ያቀደችውን የባቡር ሐዲድ ሥራና አካባቢውንም የተፅዕኖ ክልል የማድረጉን ጥያቄ እንግሊዝ በተናጠል ከኢትዮጵያ ጋር በጉዳዩ ላይ ውይይት ጀምራ ስለነበር ፣ ከኢጣሊያ ጋር ግንባር ፈጥሮ መጠየቁ ፣ 1/ ኢትዮጵያ ተንኮል ያለበት መሆኑን ተገንዝባ ጥያቄውን ውድቅ እንድታደርገው ምክንያት ሊሆናት ይችላል ፤ 2/ ኢጣሊያ በመሀል ኢትዮጵያ ላይ የተፅዕኖ ክልል ካገኘች ቀስበቀስ የአባይን ምንጭ ሳይቀር አጠቃሎ በመያዝ ወንዙን ልትገድብ ትችላለች ፤ 3/ እንግሊዝ ከፈረንሣይ ጋር የነበራትን ፉክክር የባሰ ያካርረውና ወቅታዊ ያልሆነ ግጭት ይፈጠራል በማለት የነበራትን ፉክክር ስጋት የኢትዮጵያን ጥያቄ ሳትቀበል ቀረች ። ይሁን እንጂ እንግሊዝ ከኢጣሊያ ለቀረበላት ጥያቄ እምቢታ የሰጠችው ምክንያት ኢጣሊያ የ1906ቱን የሦስቱን መንግሥታት ስምምነት ጥሳለች የሚል ነበር ።[9]

Digitized by Google

እንግሊዝ በ1919 ለኢትዮጵያ ባቀረ
በችው ጥያቄ መሠረት ኢጣሊያንንም ሆነ
ፈረንሣይን ገለል አድርጋ በኢትዮጵያ ላይ
በተለይም በጣና ባሕርና በምዕራብ ኢት
ዮጵያ ላይ የጥቅም ክልል የምታገኝበትን
መንገድ መፈለግ ያዘች ። ባንድ ወገን በቆ
ንሲላዋ በኩል ልዩ መልእክተኛ በምሥ
ጢር በመላክ ፍላጐቷን በውይይት ለማሟ
ላት ስትሞክር ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ኢት
ዮጵያ የምታቀርባቸውን ጥያቄዎች በመቃ
ቃወም በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕና በማድረግ
ጥቅሟን ለማስከበር ጥረት ታደርግ ነበር።
ለምሳሌ ኢትዮጵያም ብሔራዊ ግዛቷ ንለግ
ስጠበቅና ከመንግሥታትም ጋር በሰላም
አብሮ ለመኖር ፤ አብዛኛውን የኢምፔሪያ
ሊስ ፈቃድና ፍላጐት ለማሟላት የተቋቋ
መው የቀድሞው የዓለም መንግሥታት
ማኅበር አባል ለመሆን በ1923 ባለመ
ለከተች ጊዜ የኢትዮጵያን አባልነት ፈረ
ንሳይና ኢጣሊያ እንኳን ሲደግፉ እንግሊዝ
ግን በከፍተኛ ደረጃ ተቃውማለች ። [10] ይህ
ም አድራጐት ኢትዮጵያን በዓለም ማኅ
በር እንዳትሳተፍ በማድረግ ቀስ በቀስ ቅኝ
ግዛቷ ለማድረግ ነበር ።

በሌላም በኩል የእንግሊዝ መንግሥት
ተንኮሉን በወዳጅነት ሸፍና የተነሣበትን
የኢምፔሪያሊስት ዓላማ እውን ለማድረግ
ስለአሰበ ኃይለ ሥላሴ ሰኔ 1924 እንግ
ሊዝን እንዲጐበኙ ጠራው ። ኃይለ ሥላ
ሴም ወደ እንግሊዝ ለጉብኝት የሄደው በመ
ጀመሪያ ፈረንሣይን ጐብኝተና ለፈረንሣ
ይም ወዳጅነቱን አረጋግጦ ስለነበር ፥ ከእ
ንሳግሊዞች ጋር ምን ማድረግ እንደነበረበ
ትና የሚወስደው እርምጃም ፈረንሣይን
ማስቀየም እንደሌለበት ያውቅ ነበር ።በዚህ
መሠረት ኃይለ ሥላሴ 1/ የጦር መሣሪያ
ግዥ እንዲፈቀድለት ፥ 2/ ለኢትዮጵያ የባ
ሕር ወደብ የሚሆን በእንግሊዝ ሱማሌ
በኩል ሕጋዊ ግዛት አድርጋ እንግሊዝ እን
ድትሰጣት የሚሉ ሁለት አበይት ጥያቄዎ
ችን ለእንግሊዝ አቅርቦ ነበር ። ሆኖምጠቅ
ላይ ሚኒስትሩ ኃይለ ሥላሴ ስለጦር መሣ
ሪያ ግዥ ላቀረበው ጥያቄ ከፈረንሣይና ከኢ
ጣሊያ ጋር መምከርና ስለወደቡ ጥያቄም
ቢሆን የእንግሊዝ ምክር ቤት መፍቀድ እን
ዳለበት በመግለጽ እንግሊዝ ፈቃደኛ አለ
መሆንን አሳይቶአል ። በአንፃሩ ግን እንግ
ሊዝ የጣና ባሕርን ገድባ እንድትጠቀምበ
ትና በአካባቢውም ላይ ቁጥጥር እንድታ
ደርግ ኢትዮጵያ ትፈቅድላት ዘንድ ከመ
ጠየቋም በላይ በአጐራባች ቅኝ ግዛቶ
ችና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ወሰን
እንዲከለሉ ግፊት ያለበት ጥያቄ አቅርቦ
ነበር ። [11]

ኃይለ ሥላሴ በበኩሉ እንግሊዝ የጠየቀች
ውን ጥያቄ ማሟላት፥ 1/ከፈረንሣይ ጋር ያለ
ውን ግንኙነት ጨርሶ የሚአደፈርስበትና
አደገኛ ውጥረት ውስጥም የሚከተው መሆ
ኑን ፣ 2/ ይህ ጥቄ ቀደም ብሉ በምኒልክ
ጊዜ የተነሣና በኢትዮጵያ መሪዎች ዘንድ
ተቀባይነት ያላገኘና ጥያቄውን ተቀብሉና
ተዋውሉ ቢመለስ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቃ
ውሞ ሊገጥመው ስለሚችል ፥ 3/ ኢጣሊ
ያና ፈረንሣይም የጣናን ባሕር ለመገደብ
ተመሳሳይ ጥያቄ የነበራቸው የግድቡ ሥራ
ለእንግሊዝ መሰጠቱን ምክንያት በማድ
ረግ ኢትዮጵያን ያጠቁ ይሆናል የሚልም
ፍራቻ ነበረው ። ኃይለ ሥላሴ ለእንግሊዝ
የሰጠው መልስ ኢትዮጵያ ራሷ መሐንዲ
ሶችን ቀጥራ ግድቡን ከአስገደበች በኋላ
ለአንገሉ ኢጂፒሽያን መንግሥት ታከራ
ያለች የሚል ነበር ። በመልሱ ያልተደሰ
ተው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበ
ረው ማክዶናልድም ኃይለ ሥላሴ መሐንዲ
ሶችን ከእንግሊዝ እንዲቀጥር ፣ ይህ ካልሆነ
ግን ከአሜሪካ በስተቀር ከሌላ አገር እንዳ
ይቀጥር በማስገደድ መልክ ተናገሯል ። [12]

ኃይለ ሥላሴም በ1926 መጀመሪያ
ገደማ በአንድ ወታደራዊ መኰንን ፥ በሜ
ጀር ኤል ቢ ሮበርትስ የሚመራ ፥ ኒውዮርክ
ከሚገኘውኖቨርጂ ፣ ዋይት እንጂኒየሪንግ

Digitized by Google

ኮርፖሬሽን » የተላከ የመሐንዲሶች ቡድን አስመጥቶ ወደ ጣና ሂዶ የግድቡን ሥራ እንዲያጠና አድርጐ ነበር። ቡድኑም ጣና ከመድረሱ በፊት ዳንግላ ላይ ከነበረው የእንግሊ ቆንሲላ ከሜጀር አር·ኤ· ችዝማን ጋር ተገናኝቶ አንዳንድ መረጃዎችን ሲአጠና ሰንብቶአል ። [13] ከዚህ ላይ ቡድኑ የተመራው በአንድ ወታደራዊ መኰንን መሆኑን ፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በጐጃምና በጐንደር ክፍላተ ሀገር የስለላ ሥራ ያካሂድ ከነበረው [14] ከሜጀር ችዝማን ጋር ሲወያይ መሰንበቱንና ማከዶናልድም የመሀንዲሱን ቡድን ከአሜሪካ እንዲሆን መፈለጉን ስናገናዝብ በተልዕኮው ውስጥ የስለላ ሥራም እንደነበረበት መገመት ይቻላል ።

እንግሊዝ በግድና በዳንግላ ቆንሲላዎች ያስቀመጠችበት ዋና ዓላማ በምዕራብ ኢትዮጵያ በአባይ ሸለቆና አካባቢ ግዛቶች ላይ ባደረባት ከፍተኛ የቅኝ ግዛት ፍላጐት የተነሳ ነበር ። ይህንንም ዓላማ የተሳካ ለማድረግ ፤ እንግሊዝ በሁለቱ ቆንሲላዎች አማካይነት የስለላ ሥራ ታካሂድ ነበር ። በተለይም በዳንግላ የነበረው አር· ኢ· ቸዝማን በበላያ በረሃ ሳይቀር እየተዘዋወረ ካርታ በማንሳት በካርቱም ለነበሩት እንግሊዛውያን አለቆቹ መረጃዎችን ያስተላልፍ ነበር። [15]

ከዚህ በስተቀር በዳንግላ የቆንሲላው ፀሐፊና አስተርጓሚ የነበረው ኢትዮጵያዊው «እኔ በዚያን ጊዜ እንዳየሁት ፤ እንደተከታተልኩት ... የቆንሲሉ ዓይነተኛ ሥራ በተሾመበት ክፍለ ሀገር ከተማ ለከተማና ገጠር ለገጠር እየተዘዋወረ ከንግድና ከሌላ የኢኮኖሚ ጉዳይ ያልተዛመደውን የፖለቲካና ማናቸውንም ጠቅላላ ሁኔታ እየተከታተለ እያጠና በየጊዜው ለመንግሥቱ ማስታወቅ ነበር ። » [16] ያለውን ማጤኑ ጉዳዩን በይበልጥ ለመረዳት ያስችላል ። ያሉትን ደሴቶችና አካባቢውንም እየተዘዋወረ ከማጥናቱም በላይ በደብረ ታቦርና በደብረ ማርቆስ ከነበሩት የፊውዳሉ ገዥዎች ጋር ሳይቀር ግንኙነቱን አጠናክር በስውር መረጃ ይሰበስብ ነበር ።

እንግሊዝ የፈረንሣይ ካፒታል በኢትዮጵያ ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ መምጣቱን ስታይ ኢትዮጵያን ከፈረንሣይ ኢምፔሪያሊዝም እጅ ነጥቃ የተጽእኖ ክልሏ ለማድረግ ወሰነች ። በዚህም መሠረት ቀደም ሲል ብትጠየቅ አልሰጥም ያለችውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ እንድትጠቀምበትና በአካባቢው 600 እስኩየር ማይልስ ግዛት እንደምትሰጣት ቃል በመግባት ኢትዮጵያን ማግባባት ያዘች ። [17] ሆኖም ይህ አቀራረቧ በምትኩ በጣና ባህር ላይ ያቀረበችውን የግድብ ሥራ ጥያቄ እንደገና ለማንሳት ያቀደችው ተንኮል መሆኑን ኢትዮጵያም ስለተገነዘበች ጥያቄውን አልተቀበለችውም ። ከዚህም በቀር የዘይላን ወደብ በስጦታ መልክ ልትሰጥ የፈለገችው ከዘይላ እስከ ጂቡቲ አዲስ አበባ ድረስ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋትና ቀስ በቀስም የኢትዮጵያን የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ንግድ ለመቆጣጠር እንድትችል የጠነሰሰችው ተንኮል መሆኑ ግልጽ ነበር ።

የ1925 የሮም ስምምነት ፤ — ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ልዩነት እየጐላ በመምጣቱ እንግሊዝ በ1919 አልቀበልም ያለችውን የኢጣሊያን ጥያቄ ተቀበለች ። ሁለቱም አገሮች በ1925 ሮም ላይ ኢትዮጵያን በማስመልከት ፈረንሣይ የሌለችበት ስብሰባ አካሂደው ከስምምነት ደረሱ ። የስምምነቱም ፍሬ ሐሳብ ፤ 1/ በታህሣሥ 13 ቀን 1906 ለንደን ላይ እንግሊዝ ፤ ፈረንሣይና ኢጣሊያ ተሰብስበው የኢትዮጵያን ነፃነት ላለመድፈር (እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ማለቱ ይሻላል) ያደረጉት ስምምነት እንዲከበር ፤ 2/ ኢጣሊያ አባይንም ሆነ የአባይን መጋቢ ወንዞች እንዳትገድብና የግብጽንና የሱዳንን የውሀ ድንብ እንድታከብር፤ 3/ በጣና ሐይቅ ላይ እንግሊዝ ግድብና ከጣና እስከ ሱዳን የሚደርስ የመኪና መንገድ

Digitized by Google

ለመሥራት እንድትችል ከኢትዮጵያ ኮንሲ
ሲዮን ለማግኘት ኢጣሊያ እንድታግዛት ፣
4/ ኢጣሊያ ኤርትራንና የኢጣሊያ ሱማሌን
የሚአገናኝ ከመሀል ኢትዮጵያ አቋርጦ የሚ
አልፍ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋት የነበራ
ትን እቅድና ሐዲዱ የሚአልፍበትም አካ
ባቢ የተጽእኖ ክልሏ እንዲሆን ያላትን ፍላ
ጐት እንግሊዝ አውቃ በመቀበል በኢትዮ
ጵያ ላይ ግፊት በማድረግ እንድትረዳ ፣/ 5
እነዚህን ለኢትዮጵያ የሚአቀርቡአቸውን
ጥያቄዎች በአዲስ አበባ የሚኖሩት የሁለ
ቱም መንግሥታት እንደራሴዎች ባንድ ላይ
ሆነው እንዲአቀርቡ ነገር ግን ያንዱ ተፈ
ቅዶ ያንዱ ሳይፈቀድ እንዳይቀር እስከ መጨ
ረሻው ድረስ እንዲረዳዱ የሚል ነበር ። [18]
ደብዳቤ በመጻፍ በእየእንደራሴዎቻቸው
በኩል ለኢትዮጵያ አቅርበዋል ። ኢትዮጵ
ያም ይህ ስምምነት ብሔራዊ ነፃነቷን የሚ
ደፍር መሆኑን ጠቅሳ ተቃውሞዋን ለቀድ
ሞው የዓለም መንግሥታት ማኅበር አመ
ልክታለች ።

በአጠቃላይ ሶስቱ ኢምፔሪያሊስት አገ
ሮች ኢትዮጵያን አስመልክተው የተጫወ
ቱት የፖለቲካ ሚና ምስቅልቅል ያለ ነው።
ለምሳሌ ፣ በ1906 ሶስቱ መንግሥታት ኢት
ዮጵያን ለመቀራመት ተስማምተው ነበር።
ይሁንና ኢጣሊያ ከስምምነቱ ወዲያውኑ
አፈገፈገች ። ፈረንሳይና እንግሊዝ በ1915
በኢትዮጵያ ላይ ልዩ ጥቅም እንደሚሰጧት
ቃል በመግባት ኢጣሊያን ሊአግባቧት ሞከ
ረዋል። በ1923 ኢትዮጵያ በመንግሥታት ማ
ኅበር ዘንድ ለአባልነት በአመለከተች ጊዜ ፈ
ረንሳይና ኢጣሊያን ባንድነት ሆነው ሃሣቡን
ሲደግፉ እንግሊዝ በብርቱ ተቃውማለች ።
እንደገና በ1925 ኢጣሊያና እንግሊዝ ኢት
ዮጵያ ሳታውቅ ግዛቷን እንደቅርጫ ሥጋ
ለመቀረማመት በምስጢር ዶልተው ተፈ
ራርመዋል ።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት በኢትዮጵያ ላይ
የተቃጣውና የተፈጸመው ደባ የኢትዮጵ
ያን ሰፊ ሕዝብ በአንድ በኩል የሕይወትና
የንብረት መስዋዕትነት ቢጠይቅም በሌላ
በኩል ደግሞ ፀረ—ቅኝ አገዛዝና ፀረ ኢም
ፔሪያሊዝም አቋሙን እንደብረት አጠንክ
ሮታል ። ሴራውና ጥቃቱ የተደጋገመ በመ
ሆኑ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የኢምፔሪያሊ
ዝምን ጀብደኝነትና ተንኮል ይበልጥ እየተ
ረዳው በመምጣቱ ተጋድሎውን ከፍ አድ
ርጐታል ። ይህም በዓለም ጭቁን ሕዝብ
የፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ኢምፔሪያሊዝም የት
ግል ታሪክ ውስጥ ሰፊ አምድ ያለው ሆኖ
አል ። በተለይም ለአፍሪካ ፀረ ቅኝ አገዛዝና
ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግል በምሳሌነቱ አን
ጋፋ ነው ለማለት ያስደፍራል ።

ሦስቱ የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት
ኢትዮጵያን በተጽእኖ ክልላቸው ውስጥ
ለማስገባት በተናጠልም ሆነ በቡድን ያደ
ረጉትን ሙከራ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ
ሰፊ ሕዝብ ትግል ሲአከሽፈው ፣ በሌላ
በኩል ደግሞ «ከሶስቱ አንደኛው መንግ
ሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በውልና
በወዳጅነት ሲተባበር ባዩት ጊዜ ሁለቱ አን
ድነት ሆነው በአንድ ፖለቲካ በኩል እጃቸ
ውን አግብተው የፖለቲካን ቁጥር ይፈቱ
ታል [19] እንደተባለው ኢትዮጵያን በወዳጅ
ነት አታሎ ለመያዝ በሚአደርጉት ፉክክር
የአንዱን ደባ አንዱ ያጋልጠው ነበር። ይህም
የኢምፔሪያሊስቱቶቹ የርስበርስ ፉክክር
ለኢትዮጵያ ነፃነት የበኩሉን አስተዋጽኦ
አበርክቷል ለማለት ይቻላል ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝምና የሙሶለኒ መስፋፋት ዓላማ

በ1929 አካባቢ በካፒታሊስቱ ዓለም በተ
ለይም በአሜሪካና በአውሮፓ ላይ በደረሰው
ታላቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የኢጣ
ሊያ ኢምፔሪያሊዝም በከባድ የሶሲዮ ኢኮ
ኖሚ ችግር ውስጥ እየተዘፈቀ መጣ። በአ
ገሩ ውስጥ የሥራ አጡና የሥራ ፈቱ ብዛት፣
የአርሶ አደሩ ለድኅነት መጋለጥና የሠራተ
ኛው ከሥራ መፈናቀል ከማናቸውም ጊዜ
የበለጠና የከፋ ነበር ። በጣሊያን አገር

Digitized by Google

በታላላቅ ሞኖፖሊስቶች አማካይነት ሥል
ጣን የያዙት ፋሽሽቶች ሌሎች አገሮችን በመ
ውረርና ቅኝ ግዛት በማድረግ ኢጣሊያ የገ
ጠማትን ችግር ለማቃለል ከማናቸውም ጊዜ
የበለጠ ይሯሯጥ ስለነበር ፥ መላ ኢትዮጵ
ያን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ሰበብ አስባብ
እየፈለጉ የጠብ አጫሪነቱን ተግባር አፋ
ፋመ ።

ኢጣሊያ በወቅቱ ቅኝ ግዛቷ ከነበረችው
ሊቢያ ላይ በ1934ና በ1935 በእንግሊዝና
በፈረንሣይ የተወሰነ ግዛት ከተወሰደባት
በኋላ ትኩረቷን በኢትዮጵያ ላይ ማሳረፍ
እንግሊዝን እጅግ አሳስቦአት ነበር ። ከአሳ
ሰቧት ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፥
1/ ኢጣሊያ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ላይ
ይዞታዋን እያጠናከረች ከመጣች ሀ/ በሱዳ
ንና በግብጽ ላይ እንግሊዝ ያላትን ይዞታ
ትጋፋለች ፥ ለ/ የአባይን ውሀ ገድባ በሱዳ
ንና በግብጽ ላይ እንግሊዝ ያላትን ጥቅም
ታስቀራለች ፥ ሐ/ በቀይ ባህርና በሕንድ
ውቅያኖስ በኩል ያለውን የንግድ መስመር
በቁጥጥርዋ ሥር ታውላለች ፥ 2/ እንግሊዝ
መላዋ ኢትዮጵያን የተጽእኖ ክልል ለማድ
ረግ የነበራትን እቅድ ታደናቅፋለች ፥
3/ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በምታካሂደው
ወረራ የተነሳ የሚቀሰቀሰው ጦርነት እንግ
ሊዝ ወደ ያዘቻቸው ጐረቤት ቅኝ ግዛቶች
ሕዝቦች ተዛምቶ ጦርነት ይቀሰቅሳል፥ 4/
ፈረንሣይ ኢጣሊያ የቀሰቀሰችውን ጦርነት
ተጠቅማ ኢትዮጵያን በቁጥጥር ሥር ለማ
ድረግ ጥሩ አጋጣሚ ታገኛለች የሚሉት
ነበሩ ። [20] እነዚህ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊ
ዝም የሥጋት መንስኤዎች ነበሩ ማለት ይቻ
ላል ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም እነዚህንና
ሌሎችንም ጉዳዮች በትክክል ከማጤንና
ከደረሰበትም የ1929ኙ ኢኮኖሚ ቀውስ
ለመውጣት በሚያደርገው ጥረት አኳያ የሚ
ቀይሳቸው ታክቲኮች ኢትዮጵያን በሚመ
ለከት ረገድ ሲለዋወጡ እናያለን ። እርግጥ
የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ከቴዎድሮስ
በኋላ በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ የሆነ ወረራ
አላካሄደም ። ሆኖም ከግልጽ ወረራ ያላነሰ
ሴራ ፈጽሞአል ። ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት
ለማድረግ የተጠቀመባቸው ስልቶች በአ
ንድ ቤት ውስጥ በመስኮት ዘሎ ገብቶ መላ
ውን ቤት በይዞታ ሥር ለማድረግ እንደመ
ቃጣት የሚቆጠሩ ነበሩ ።

የአቀራረቡ ስልት በስተጀርባው ተንኮ
ልና ደባ ያለበት መሆኑ በውል ባለመታወቁ
የብዝበዛ ዓላማውን በቀላሉ ተግባራዊ ለማ
ድረግ አመቺ ሁኔታ አግኝቶ ነበር ። በዚህም
አኳያ ፥ ለእንግሊዝ ከበርቴዎች በኢትዮጵያ
ውስጥ ኮንሲሲዮን ለማግኘት የቋመጡ እን
ግሊዛውያን ምሁራንና ተመራማሪዎች በአ
ገር ጉብኝነት ፥ በተራራ ወጪነት ወዘተ—
ስም መጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደል
ባቸው በመዘዋወር የአገሪቷን ሀብትና ንብ
ረት ማለትም ማዕድናት አጥንተው ለእንግ
ሊዝ መንግሥትም ሆነ ካፒታሊስቶች በቂ
መረጃ ሰጥተዋል ። ከእንደዚህ ያሉት ሰዎች
መካከል አንዱ የሆነው ኢ· ሀይተር ከ1932
በፊት ወደ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በመም
ጣት ጋምቤላ ወርቅ የመላበት አውራጃ መሆ
ኗን ከአጠና በኋላ በኢትዮጵያ አንድ የእን
ግሊዝ ኩባንያ ተቋቁሞ ከፍተኛ የማዕድን
ሀብት አላት ተብላ የተገመተችውን ኢትዮ
ጵያን እንዲበዘብዙ ሐሳብ አቅርቦአል ።
ይህን ሐሳቡን ኃይለ ሥላሴ እንደሚደግፈው
ተናግሮአል ። [21]

እንግሊዝ በእርቅ ስም የፈጸመችው ደባ

ኢጣሊያ በ1934 የወልወልን ግጭት ጭራ
ባደረሰችው የሕይወት መጥፋት እራሷን
ተበዳይ ፥ ኢትዮጵያን በዳይ አስመስላ በማ
ቅረብ ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛቷ ለማድረግ
ፈለገች ። ስለዚህም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን
ለመውረር ሰበብ እንዲሆናት ኢትዮጵያ በወ
ልወል ግጭት በመፍጠሯ ምክንያት
የ20000 ፓውንድ ካሣ እንድትከፍላትና
ለኢጣሊያ ባንዲራ የኢትዮጵያ ጦር ሰላምታ
እንዲሰጥ ጥያቄ አቀረበች ። ኢትዮጵያም
የጉዳዩን እጅግ አሳሳቢነት በመመልከት

Digitized by Google

ጠብ ጫሪዋ ኢጣሊያ መሆኗንና ለደረሰውም የሕይወት ጥፋት ራሷ ጠብ ጫሪዋ ተጠያቂ እንደሆነች በመግለጽ ለዓለም የመንግሥታት ማኅበር ለማመልከት ዝግጅት ጀመረች ። ይህንንም በአዲስ አበባ ተቀማጭ የነበረው የእንግሊዝ መልዕክተኛ ሲድኒ ባርቴን ሲሰማ ጉዳዩን በአስቸኳይ ለእንግሊዝ መንግሥት አሳወቀ ። በወቅቱ የእንግሊዝ ም/የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከነበረው ሮበርት ቫንሲታረት የተሰጠው ትዕዛዝ ኃይለ ሥላሴ ጉዳዩን ለመንግሥታቱ ማኅበር እንዳያመለክት የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንዲያደርግ ነበር ። [22] ይህ ሳይሳካ ቀርቶ ጉዳዩ ለመንግሥታቱ ማኅበር ሲቀርብ እንግሊዝ በአስታራቂነት ጣልቃ በመግባት «ኢትዮጵያ በኦጋዴን በኩል ግዛት ቆርጣ ለኢጣሊያ መንግሥት ካሣ ትስጥ ፤ ኢትዮጵያም ከባህር የምትገናኝበት የዘይላን በር ከእንግሊዝ መንግሥት ታግኝ [23] የሚል ሐሳብ አቀረበች ። በመሠረቱ ይህ ሃሣብ ለኢትዮጵያ ማካካሻ የሚሰጥ መስሎ ቢታይም ሸፍጥ የተመላበትና ሞሶሊኒን ለማስደሰት የተደረገ ነበር ። ምክንያቱም ኢጣሊያ የወልወልን ግጭት ታህሣሥ ፤ 1934 ባነሳችበት ጊዜ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሱማሌ መካከል የነበረውን ወሰን ሊመከለል የእንግሊዝ መልዕክተኞች በዚሁ አካባቢ እንደአጋጣሚ ተገኝተው በዓይን ምስክርነት ያዩት ስለነበር ጠብ ጫሪዋ ኢጣሊያ መሆኗ በግልጽ ይታወቅ ነበርና ፤ [24] ይህ ሐቅ እያለ ፤ ኢትዮጵያ ኦጋዴንን ለኢጣሊያ ትስጥ በማለት እንግሊዝ ያቀረበችው ሐሳብ ፋሽስት ኢጣሊያን በማባበልና በማግባባት የረጅም ጊዜ ጥቅሟን ለማስከበር ያቀደችው ተንኮል እንደነበረ ዓሌ የሚባል አይሆንም ። እንግሊዝ የዘይላን ወደብ ለኢትዮጵያ እሰጣለሁ ያለችውም ከብዙ ጊዜ ጀምራ ታልመው የነበረውን የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ ለመቆጣጠር እንድትችል ነበር ።

ሆኖም እንግሊዝ ያቀረበችው ሐሳብ የራሷን ፍላጐት የሚያሟላ እንጂ ከኢጣሊያ እቅድ ጋር የማይሄድ በመሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች ሞሶሎኒም ሊረካባት አልቻለም ። ይሁን እንጂ ኢጣሊያ የመንግሥታትን ማኅበር ቃል ኪዳን አንቀጽ 12 ጥሳ የድርጅቱ አባል የሆነችውን ኢትዮጵያን በመውረሯ የማኅበሩ አባላት ጥቅምት 7 ፤ 1935 ተሰብስበው በማኅበሩ ቃል ኪዳን አንቀጽ 16 መሠረት በኢጣሊያ ላይ ማዕቀብ እንዲደረግባት ተስማሙ ። [25]

ከማኅበሩ የማዕቀብ ውሳኔ ውጭ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሙኤል ሆርና ፈረንሣዩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ላባል ታህሣሥ 9 ፤ 1935 ተሰብስበው ኢትዮጵያን ለኢጣሊያ ፋሽዝም (ኢፔሪያሊዝም) አሳልፎ የሚሰጥ ሐሳብ በእርቅ መልክ ይዘው ቀረቡ ። በተለይም እንግሊዝ መጀመሪያ ያቀረበችውን ሐሳብ ለውጣና ከቀንደኛ ተፎካካሪዋ ከፈረንሣይ ጋር የነበራትን ልዩነት የአውሮፓውያን ትብብር ማጠናቀር በሚል ሰበብ አቻችላ ከእርሷ ጋር በመሆን ኢትዮጵያ፤ 1/በሰሜን ፤ አክሱምን አስቀርታ ከአድዋ ምዕራብና ምሥራቅ ጀምሮ እስከ ግቤ ወንዝ ድረስ ፤ 2/ በደቡብ ከኢጣሊያ ሱማሌ ወሰን ጀምሮ እስከ ቀራሄ ድረስ ያለውን ግዛትና ፤ 3/ ዳናኪልን ለኢጣሊያ እንድትሰጥ ሲሆን ኢጣሊያም በበኩሏ በፈረንሣይ ሱማሌ ስሜን የሚገኘውን ግዛት ለኢትዮጵያ እንድትሰጥ የሚል ሃሣብ አቀረቡ ። [26]

እንዲሁም ኢትዮጵያ እንግሊዝ አበድራለሁ የምትለውን ገንዘብ ለኢጣሊያ ከፍላ አሰብን እንድታስመልስ የቀረበው የርቅ ሃሣብ እንዲነሳ ሁለቱ ኢምፔሪያሊስት አገሮች የራሳቸውንም ጥቅም ፍላጐት በማንጸባረቅ ፤ የመሃል አገሩንም አስተዳደር በመንግሥታት ማኅበር ስም ሆነው የእንግሊዝ፣ የፈረንሣይና የኢጣሊያ ወኪሎች በበላይነት እንዲቆጣጠሩ የሚል ሐሳብም አስፍረዋል ። [27]

በሌላ በኩል ሆርና ላቫል በታህሣሥ 1935 በምሥጢር ከሞሶሎኒ ጋር ተገናኝተው ኢትዮጵያን በሚቀራመቱበት ዕቅድ ላይ

Digitized by Google

ውይይት አድርገው ነበር ። [28] የአወጡትም
ዕቅድ በኢትዮጵያ ዘንድ ተቀባይነት እንዲ
አገኝ ጥረት በማድረግ ሁለቱ ሴረኞች ታህ
ሣሥ 13 ፥ 1935 ትግሬንና ኦጋዴንን በገ
ዛት ፥ በከፋ ፥ በግጂ ፥ በሲዳሞ ፥ በባሌ፥ በወ
ላሞና በከምባታ የሚገኘውን የኢኮኖሚ
ጥቅም ለኢጣሊያ ሰጥታችሁ ዕርቅ ብታደ
ርጉ ይሻላል [29] በማለት ወደ ኢትዮጵያ ቴሌ
ግራም አስተላልፈው ነበር ።

የእርቁ ሃሳብ ኢትዮጵያን ለፍጹም ቅኝ
ግዛትነት አሳልፎ የሚሰጥ ነበር ። በመሆ
ኑም የቀረበውን ድርድር ባለመቀበል እንግ
ሊዝና ፈረንሳይ በእርቅ ስም የፈጸሙትን
ተንኮል የመንግሥታቱ ማኅበር ውድቅ እን
ዲአደርገው ኢትዮጵያ በመጠየቁ በማኅበሩ
ዘንድ ሽፋፍነው ያቀረቡት ኢምፔሪያሊስ
ታዊ ዓላማቸው ተጋለጠ ። ይሁን እንጂ ማኅ
በሩም ቢሆን በእነርሱ ቁጥጥር ሥር የዋለ
በመሆኑ በኢጣሊያ ላይ ውጤት ያለው ማዕ
ቀብ ማድረግ አልተቻለም ።

ይህ ወቅት ፥ የሁለተኛው የዓለም ጦር
ነት በተለይም በአውሮፓ ላይ ያንዣበበ
በት ጊዜ ስለነበረ በከፍተኛ ውድድርና የጥ
ቅም ግጭት ላይ የነበሩ የአውሮፓ ኢምፔ
ሪያሊስት አገሮች ምንም እንኳ አንዳንድ
ጊዜ በጥቅም ቢለያዩም ጊዜያዊ ግንባር «ፈ
ጥረን» የጋራ ጠላቶቻችን የሆነችውን ጀር
መን ምንአልባት አውሮፓን እወራለሁ ብላ
ብትነሳ ተባብረን እንወጋታለን በማለት ስት
ሬዛ ላይ በ1935 ተሰብስበው አንድ ስምም
ነት ተፈራርመው ነበር ። ኢጣሊያም የዚህ
ስምምነት ፈራሚ አገር ነበረች ። የፈሩት
አልቀረም ፥ የጀርመን አደገኛነትና አውሮ
ፓን የመውረር ፍላጐቷ በግልጽና በተግ
ባር እየታየ ሲመጣ ኢጣሊያ ደግሞ በወል
ወል ግጭት አሳባ ኢትዮጵያን የመውረር
ዝግጅቷና ግፊት እያመዘነ በመሄዱ እንግሊ
ዝና ፈረንሣይ በከፍተኛ ስጋት ላይ ወደቁ።
ጀርመን ነፃነታቸውን ሳይቀር የምትደፍር
ኃይል ሆና ብቅ ስትል ኢጣሊያ ደግሞ በም
ሥራቅና በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ላይ የነ
በራቸውን ቅኝ ግዛታዊ ጥቅም በመጻረር
መተንኮሷን ጀመረች ። በተለይም ኢጣሊያ
የስትሬዛን ውል ጥሳ ከጀርመን ጋር ትተባ
በራለች የሚለው ፍራቻ ስለአስጨነቃቸው
ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ለፋ
ሽስቱ የኢጣሊያ አምባገነን ገዥ ለሆነው
ሞሶሎኒ ቅኝ አገዛዝና ኢሰብአዊ ብዝበዛ
አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ አግራሞ የሌለው
መሆኑ እየታያቸው ሄደ ። ስለዚህም በኢጣ
ሊያ ላይ ማዕቀብ አድርጉ የጀርመን ተባባሪ
እንድትሆን ከመገፋፋት ይልቅ የኢትዮጵ
ያን ሰፊ ሕዝብ ለኢጣሊያ መደለያ ስጥ፡
ከነርሱ ጋር እንድትቆም ማድረጉን እንግሊ
ዝና ፈረንሣይ የአመኑበት መሆኑን መገን
ዘብ ይቻላል ። ይህንን መሰሪ የሆነ የእንግ
ሊዝና የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊዝምን አድ
ራጐት በሚመለከት ረገድ አንድ ጸሐፊ «በ
ኢጣሊያ ላይ ብርቱ ጭቆና ቢደርስባት የስ
ትሬዛን ውል ከማፍረሷም ሌላ ከጀርመን
ጋር መተባበር ወይም ጦርነት ማንሳት ስለ
ምትችል ላንድ ትናንሽና ይልቁንም በሥል
ጣኔ ወደኋላ ለቀረ በአፍሪካ መሀል ለሚገኝ
መንግሥት አንድ ትልቅ ወዳጅ አጥቶ አንድ
ትልቅ ጠላት ከማፍራትና የዚህ ወዳጅ ጠ
ላት መሆን ከፍ ያለውን የፖለቲካ ሚዛን
ስለሚአዛባ የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዲሁ
መተው የተሻለ ነው ከሚል ሐሳብ ላይ ደረሰ
በማለት ሁኔታውን ግልጽ አድርጐ አስ
ቀምጦታል ። [30]

የኢጣሊያ ኢምፔሪያሊዝም ፋሽስታዊ
ዓላማውን ለማርካት ከናዚ ጀርመን ጋር
መሰለፍ እንደሚያስፈልገው ስለተገነዘበ፥
እንግሊዝና ፈረንሣይ ኢትዮጵያን እንደመ
ደለያ ቢያቀርቡለትም እርካታ አልሰጠው
ም ። ስለሆነም የኢጣሊያ ቀደም አድርጋ
የጀመረችውን ፕሮፓጋንዳና ኢትዮጵያን
የምትወርበትን ሰበብ ማለትም «አቢሲኒያ
አልሰለጠነችምና እሰለጥናለሁ ፥ የባሪያን
ንግድ በሰፊው ይካሄድባታልና ይህንን አስ
ቀራለሁ ፥ ወዘተ — » በሚል ሰንካላ ምክ
ንያት በቀድሞው የዓለም መንግሥታት ማኅ

Digitized by Google

በር ዘንድ እያስወራች የወረራ እቅዷን ገፋ
ችበት ።

ኢትዮጵያን በኮሚቴ ለመቆጣጠር

በሌላ በኩል ፥ እንግሊዝ ሙከራዋ ሁሉ
አልሳካላት ሲል ኢጣሊያ ስለኢትዮጵያ የም
ታስገባውን በግጽደቅ የዓለም መንግሥ
ታት ማኅበርን በከፍተኛ ደረጃ በመጉትጐ
ትና የራሷም መሣሪያ በግድረግ አምስት
ሰዎች ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ኢትዮጵያን
እንዲያስተዳድር የሚል ሃሳብ አቀረበች ።
ይህ ሁኔታ በተግባር ሲተረጐም የኢትዮጵ
ያን ብሔራዊ ነፃነት የሚደፍርና ለኢምፔ
ሪያሊስት ብዝበዛም አመቺ ሁኔታን የሚፈ
ጥር ሐሳብ ነበር ። ኢትዮጵያ ያልሰለጠነ
ችና ራሷን ማስተዳደር«የማትችል»አገር ስለ
ሆነች ፤ 1/ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖሊሲ
ንና የፀጥታን ጉዳይ የሚያደራጅ አንድ የ
ውጭ ባለሙያዎች ኮሚሽን እንዲቋቋም ፥
2/ የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ፥ የሥራና የመ
ገናኛ ጉዳይ ፥ የፖስታ ፥ የቴሌግራፍና የስ
ልክ ፥ የገንዘብ ግለትም የአገሪቷን በጀት
የማውጣትና የመንግሥቱን ወጪና ገቢ የ
መቆጣጠር ፥ የፍርድ ፥ የትምህርትና የጤና
ድርጅቶች በውጭ አገር ሰዎች ቁጥጥር ሥር
እንዲካሄድ ፥ 3/ ልዩ የዓለም መንግሥታት
ማኅበር መልዕክተኞችና ከላይ የተጠቀሱ
ትን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚመሩ
አራት አማካሪዎች በዓለም መንግሥታት
ማኅበር እንዲሾሙ ፥ ኢትዮጵያ በእንግሊ
ዝና በፈረንሣይ ሱማሌ ግዛቶች በኩል አል
ፋ ለምታገኘው የወደብ አገልግሎት ምት
ክና የኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ለሆኑት ለኤር
ትራና የኢጣሊያ ሱማሌ ይዞታ ዋስትና ለመ
ስጠት የኦጋዴንና የደንከል ግዛቶች ቆርጣ
ለኢጣሊያ እንድትሰጥ የሚሉ ነጥቦችን ያ
ዘለ ሐሳብ ሲቀርብ በሌላ በኩል ደግሞ የኢ
ትዮጵያ የግዛት አንድነትና ነፃነት የተከበረ
መሆኑን ያወሳል ። [31]

ይህን በእንግሊዝና እንዲሁም በፈረን
ሣይ ገፊት የቀረበውን ሐሳብ በተግባር ቢ
ውል ፥ 1/ ራሷን በራሷ ማስተዳደር የምት
ችል ሙሉ ነፃነት ያላት አገር ናት ፥ ብለው
በግመን በድርጅቱ መርህ መሠረት በአባል
ነት ከተቀበሉአትና በአባልነቷም ለአሥራ
ሁለት ዓመታት ያህል ከቆየች በኋላ ፥ ኢት
ዮጵያ ያልሰለጠነች ፥ ራሷን ማስተዳደር የማ
ትችል ናትና በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ዋነኛ
ተቋሞችን ሁሉ ግለትም የመንግሥቱን
ወጪና የፀጥታ ጉዳይ ሳይቀር የዓለም መን
ግሥታት ማኅበር በሚሾግቸው አማካሪዎ
ችና መልእክተኞች ቁጥጥር ሥር መዋል.
አለባቸው ግለት የአገሪቷን ብሔራዊ ልእ
ልና መዳፈር ከመሆኑ በቀር ሌላ ትርጉም
ሊኖረው አይችልም ። 2/ በዚህ ሁኔታ የኢ
ትዮጵያ የግዛት አንድነትና ነፃነት የተከበረ
ነው የሚለውም ሐረግ ተራ ሽንገላ ይሆ
ናል ። የብሔራዊ ግዛቷ አካላት የሆኑትን
ኦጋዴንና ደንከልን ቆርሳ የቀይ ባህር ጠረፍ
ግዛቷንና ወደቧን በግፍ ሊያዘችባት ፋሺስት
ኢጣሊያ እንድትሰጥ የኢትዮጵያ ከተደረ
ገች የግዛት አንድነቷ የተከበረው ከምኑ
ላይ ነው ?

የቀረበው ሀሳብ ኢትዮጵያን ለመውረ
ርና ፋሽስታዊ ፍላጐታቸውን ለግርካት
በመዘጋጀት ላይ በነበሩት የጣሊያን ፋሽስ
ቶች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ። እንግሊ
ዝና ፈረንሣይም ቢሆኑ ኢጣሊያ እየከዳቻ
ቸው መሄዷን በሙሉ ለኢጣሊያ ለመዳረግ
አይናቸውን ባላሹም ነበር ። የእንግሊዝ ኢም
ፔሪያሊዝም ምንጊዜም ቢሆን የየወቅቱ
ዓይነተኛ ጥቅሙን ለግስከበር ኢትዮጵያን
በተለያየ መልክ ለኢጣሊያ ኢምፔሪያሊ
ዝም መግለጃ ለግቅረብ ያልፈጠረው ምክ
ንያቱና ያላደረገው ጥረት እንዳልነበረ በተ
ደጋጋሚ አይተናል ። ከዚህም በላይ አንድ
ፀሐፊ እንዳለው «እንግሊዝና ፈረንሣይ ከኢ
ትዮጵያ ጋር የነበራቸው ግንኙነት አጠቃ
ላይ ታሪክ የሚያሳየው ለእንግሊዝና ለፈ
ረንሣይ የኢኮኖሚ ፍላጐት አንድ ዓይነት
ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ የኢጣሊያ መንግ
ሥት የኢትዮጵያን ነፃነትና የግዛት አንድ
ነት ለመግሰስ ዝግጁ የነበረውን ያህል የአ

Digitized by Google

ንግሊዝና የፈረንሣይ መንግሥታትም እን ደዚሁ ለማድረስ ዝግጁ እንደነበሩ ነው ።[32]

ኃይለ ሥላሴ ለእንግሊዝ ኢምፔሪያሊ ዝም ያቀረበው የጥገኝነት ጥያቄ

ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን የእንግሊዝ ጥብቅ ወይም ጥገኛ ለማድረግ በአዲስ አበባ የእንግሊዝ መንግሥት ቀዋሚ መልእክተኛ ከነበረው ሲድኒ ባርተን ጋር በምስጢር ውይ ይት ካደረገ በኋላ ጥያቄውን ለእንግሊዝ ንጉሥ እንዲያ ቀርብለት ጠየቀ ።[33] ኃይለ ሥላሳሴ ባርተንን በምስጢር አስጠርቶ ባነ ጋገረበት ወቅት ከሚኒስትሮቹም ሆነ ከአማ ካሪዎቹ አንድም እንኳ ሳይኖር መደበኛ አስ ተርጓሚውንም ሳይጠራ ብቻውን ሆኖ ጥ ቂት የእንግሊዝኛ እውቀት ባለው የግል አሽከሩ አስተርጓሚነት እንደነበረ ተጠቅ ሷል ።[34]

ቆንሲላውም የቀረበለትን ጥያቄና የራሱ ንም አስተያየት ጨምሮ በወቅቱ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበረው አንቶኒ ኢደን የካቲት 20 ቀን 1936 በጣም አስቸኳ ይና ከፍተኛ ምስጢር በማለት አስተላለፈ። የጥያቄውም ዓይነተኛ ይዘት «ተስፋችንና ሐሳባችን አገራችንን ወደከፍተኛ ስልጣኔ ለማድረስና ሁለቱንም አገሮች በሚጠቅም መንገድ በጥገኝነትም ሆነ በጥብቅነት (ስርዝ የፀሐፊው) መልክ ከእንግሊዝ ጋር ለማስተ ባበር ነው ፤ »[35] የሚል ነበር ።

በተጨማሪም ፣ ኃይለ ሥላሴ የጥገኝነት ጥያቄ ማንሳት የጀመረው ገና በ1933 ጀምሮ እንደነበር «በ1933 እና በ1934 ባደረግና ቸው ምስጢራዊ ንግግሮች ሁሉ ከኢጣሊያ ጋር ወደፊት የሚኖረውን ግንኙነት አስተ ማማኝ የሚያደርግ አንድ ዓይነት የእንግ ሊዝ ዋስትና ሲኖር ብቻ መሆኑን ሳያቋርጥ ደጋግሞ ነግሮኛል»[36] ብሎ ቆንሲላው የጻ ፈውን መመልከቱ በቂ ይሆናል ። ከዚያ ላይ ግን መገንዘብ የሚቻለው ኃይለ ሥላሴ «አንድ ዓይነት የእንግሊዝ ዋስትና» ሲል ጥገኝነት ማለቱንና ይህንንም ፍላጐቱን በ1936 በትክክል መግለጡን ነው ። ይሁንና ከአንቶኒ ኢደን ለባርተን በተላከው ቴሌግ ራም የተሰጠው መልስ «የግርማዊ መንግ ሥት (የእንግሊዝ መንግሥት) ኢትዮጵያ የእ ንግሊዝ ጥብቅ ወይም ጥገኛ እንድትሆን የቀረበው ሀሳብ በምን ምዓይነት አይቀበለ ውም »[37] ። የሚል ነበር ።

እንግሊዝ የኃይለ ሥላሴን ጥያቄ አልቀ በልም ያለችበት ምክንያት ግልጽ ይመስ ላል ። እላይ እንደተጠቀሰው እንግሊዝ የራ ሷንና የብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮችን ሕል ውና ያሰጋው የናዚ ጦር አውሮፓን ለመው ረር እየዛተ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ ይህን ጥቃት ለመቋቋም ሁለቱ ቀንደኛ የኢምፔ ሪያሊስት አገሮች ማለትም እንግሊዝና ፈረ ንሣይ የአውሮፓን ኃይል እያሰባሰቡ የነበ ሩበት ወቅት ነበር ። ከዚህም በቀር ኢጣ ሊያ ብዙ ጦሯን በኤርትራና በኢጣሊያ ሱ ማሌ በኩል አሰማርታ ኢትዮጵያን መው ረር ጀምራ ስለነበር በዚህ ወቅት የግንኙነ ቱን ጥያቄ መቀበል ከኢጣሊያ ጋር ወዲያ ውኑ ጦርነት መግጠም ስለሚሆን የሚገጥ ማት ችግር እጅግ ውስብስብ እንደሚሆን ባት እንግሊዝ አስቀድማ ገምግማ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም ። ፈረንሣይም ብት ሆን የኢትዮጵያን ለእንግሊዝ ጥገኛ መሆ ንን እጅዋን አጣጥፋ በመቀመጥ አትመለ ከተውም ።

በፋሺስት ወረራ ወቅት እንግሊዝ የነበራት አቋም

ሞሶሎኒ ግንቦት 1936 « ኢትዮጵያ የኢ ጣሊያ ቅኝ ግዛት ትሆናለች»ብሉ ሲያውጅ በጊዜው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነ በረው ኤስ ባልድዊን «የኢትዮጵያ ጉዳይ እንግዲህ አለቀ ደቀቀ»[38] ብሎ ነበር። በተ ጨማሪም ኢትዮጵያ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቤቱታ አቅርባ ጉዳዩ በመታየት ላይ በነበረበት ጊዜ ሶቭየት ኅብረት ፣ ሜክ ሲኮና ሌሎችም አንዳንድ አገሮች አቤቱ ታዋን በመደገፍ የኢጣሊያን ወራሪነት ሲያ

Digitized by Google

መግዙ እንግሊዝ ከሞሶሎኒ ጐን መቆሟን አሁንም በገሀድ አሳይታለች ። [39] በሌላም በኩል ኃይለ ሥላሴ ፣ አንዳንድ መሳፍንት ንና መኳንንትን እንዲሁም ልጆቹን ሳይቀር ይዞ ከኢትዮጵያ በኮበለለ ጊዜ በጂቡቲ ወ ደብ ላይ ልዩ መርከቧን አቅርባ የተቀበለች ውና በአገሯ ውስጥም ያስተናገደችው እን ግሊዝ ነበረች ። በመሆኑም እንግሊዝ በዚህ ረገድ የተጫወተችው ሚና ከረጅም ጊዜ ጥቅሟ አንፃር እንደሆነ መገመት ይቻላል።

የኢጣሊያ ኢምፔሪያሊዝም የፋሽዝም ባሕርይ በግልጽ በመከሰቱና ነባራዊ ሁኔታ ውም እየፈቀደለት ስለመጣ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር ፈጥሮት የነበረውን ግንባር እያዳከመ ከናዚ ጀርመን ጋር የጥቅም ግን ኙነትን እያጠናከረ ሄደ ። ይህ ሁኔታ የእን ግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም ይበልጥ አደናገ ጠው ፤ ከፍተኛ ስጋትም ላይ ጣለው ። ቢሆ ንም ተስፋ ባለመቁረጥ ኢጣሊያን ከናዚ ጀርመን የጦር ጓደኛነት ለመለየት የኢት ዮጵያን በኢጣሊያ መያዝ ሕጋዊ አድርጐ በ1938 አወቀ ። ከዚህም በላይ የዓለም መን ግሥታት ማኅበር በድርጅቱ ስምም ባይሆን አባላቱ በግል ደረጃ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ግዛት እንዲያውቁ ለማግባባት ጥረት የሚ አደርግ መሆኑን በወቅቱ የእንግሊዝ ጠቅ ላይ ሚኒስትር የነበረው ቻምበርሊን ለሞሶ ሎኒ አረጋገጠለት ። [40] በተጨማሪም ፣ ኢት ዮጵያ በግንቦት 1938 ለተካሄደው የዓለም መንግሥታት ማኅበር ልዩ ስብሰባ በማኅ በሩ ደንብና ቃል ኪዳን መሠረት ኢትዮጵያ ወራሪዋ ፋሽስት ኢጣሊያን ለመከላከል እር ዳታ እንዲደረግላት አመልክታ ጉዳዩ በታየ በት ጊዜ የእንግሊዝ መልዕክተኛ የነበረው ሀሊፋክስ የዓለም መንግሥታት ማኅበር የኢ ትዮጵያና የኢጣሊያን ክርክር አስመልክቶ በተወያየበት ወቅት ኢትዮጵያን በመደገፍ መጋቢት 11 ቀን 1932ና ሐምሌ 4 ቀን 1936 የሰጠው ውሳኔ በአሁኑ ሰዓት ተቀባይ ነት እንደማይኖረው ገልጾ ፣ የእንግሊዝ መን ግሥት የኢትዮጵያን በኢጣሊያ መያዝ ሕ ጋዊ አድርጐ የሚያውቅ መሆኑን ድፍረት በተሞላበት አነጋገር አስታውቆአል። ባደ ረገውም ቅስቀሳና ማግባባት ዘጠኝ አገሮች ሃሳቡን ሲደግፉት ሶቭየት ኅብረት ፣ ቻይና፣ ሜክሲኮና አንዳንድ ሌሎች አገሮች የኢ ጣሊያን ወረራ አውግዘው ከኢትዮጵያ ጐን ቆመዋል ። [41] ይህ የእንግሊዝ ከኢምፔሪ ያሊስታዊ ጥቅሟ አንፃር የወሰደችው አቋ ም ፣ አንድ ፀሐፊ «እንግሊዝ በጣና ላይ ማለ ትም ወደ ሱዳንና ወደ ግብጽ የሚፈሰውን የአባይ ውሀ የመቆጣጠር መብቷ እስከተከ በረ ድረስ መላዋ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ አገ ዛዝ ሥር ብትወድቅ የተሪ ካቢኔ ደንታ የለ ውም» [42] ያለውን የሚያንፀባርቅ ይመስ ላል ። በተጨማሪም ግን በመሠረቱ እንግ ሊዝ በኢትዮጵያ ላይ የነበራት የጥቅም ፍላ ጐት በወቅቱ ከገጠማት ሁለንተናዊ ውጥ ረት አንፃር ካልሆነ በቀር በአባይ ወንዝ ላይ ብቻ ነበር ለማለትም አይቻልም ።

እንግሊዝ የኢትዮጵያ የጦር ጓደኛ የሆነችበት ዓይነተኛ ምክንያት

በአውሮፓ ውስጥ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲስፋፋ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊ ዝም እንደፈራው ሁሉ ናዚ ጀርመን ሰኔ 5 1940 ፈረንሣይን ስትወር ፋሽስቷ ኢጣሊያ ደግሞ ሰኔ 10/1940 በእንግሊዝ ላይ ጦርነት አወጀች ። ይህ ነበር የዓለም መንግሥታት ማኅበርን በቁጥጥራቸው ሥር አውለው የኢ ትዮጵያን ጉዳይ «ጀሮ ዳባ ልበስ» ብለው የነበሩት እንግሊዝና ፈረንሣይ የኢትዮጵ ያን አቤቱታ እንደገና እንዲአጤኑ ያደረ ጋቸው ። በተለይም ፣ እንግሊዝ በምሥ ራቅ አፍሪካ የነበራት ቅኝግዛታዊ ጥቅ ሟን ለማናጋትና ለመንጠቅ ኢጣሊያ በመነሳቷ ኢትዮጵያን በጦር የምትረዳ መስላ ብድግ አለች ። ይህ ነበር የጦር ጓደኛነቱ መሠረታዊ ምክንያት ። ሲልቪያ ፓንከረስት «የእንግሊዝ መንግሥትም በበ ኩሉ ገና ከእየቦታው ሊጠረቃቀም ከሚች ለው ከእንግሊዝ ወታደር በቁጥር የሚአጥ ፉው የኢጣሊያ ሠራዊት የእንግሊዝ ቅኝ

Digitized by Google

ግዛቶች የነበሩትን ሱዳንን ፥ ኬንያንና የእንግሊዝ ሱማሌን ለመውረር ከዚያም በላይ በመካከለኛው ምሥራቅ የነበረውን የእንግሊዝ ይዞታ ከአስጊ ሁኔታ ላይ ለመጣል በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን በማየት የኢትዮጵያ አርበኞች መኖር ከፍተኛ ዋጋ ያለው ድጋፍ እንደሚአበረክት ተገነዘበ ።» [43] በማለት ነገሩን በሚገባ አስቀምጣዋለች ። እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጐን እቆማለሁ ያለችው ፥ 1/ በሰሜን እስከ ምሥራቅ አፍሪካ ያለውን ቅኝ ግዛቷንና በመካከለኛው ምሥራቅ የነበረውን ይዞታዋን ኢጣሊያ በመዳፏ ውስጥ ለማስገባት ጥቃት በመጀመሯ ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፋፍሞ የነበረውን ብሔራዊ የአርበኞች ንቅናቄ በመጠቀም ኢጣሊያን ለመውጋትና 2/ ይህን አጋጣሚ ተጠቅማ ኢትዮጵያንም በቅኝ ግዛትነት በመያዝ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የነበራትን ከኬፕታውን እስከ ካይሮ የተዘረጋ ሰፊ ቅኝ ግዛት ለመመሥረት ታልመው የነበረውን ቅዠቷን እውን ለማድረግ እንደነበር መገመት ይቻላል ። ሃሳቧ ይኸ ለመሆኑ ከጦርነቱ በኋላ ያደረገችው ሴራ የሚመሰክረው ነው ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም እንደፈራውም የኢጣሊያ ፋሽዝም በኢትዮጵያ ላይ ባገኘው ጊዜያዊ ድል በመደፋፈር ኢትዮጵያና ሱማሌ ውስጥ የነበረው ወራሪ ጦሩን በማንቀሳቀስ ከሰላንና የእንግሊዝ ሱማሌን ወረረ ። [44] በዚህን ጊዜ እንግሊዝ ኢትዮጵያን የምትረዳና ከኋላ የቆመች በመምሰል ፋሽስት ኢጣሊያን ለመውጋት መነሳቷን በገሃድ አወጀች ። በዚህም ጊዜ ነበር «እንግሊዞች የኃይለ ሥላሴ መሣሪያነት ምን ያህል ጠቃሚ እየሆነ እንደሚሄድ መገንዘብ የጀመሩት ።» [45]

በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጥላ ስር ተከልሎ የኖረው ኃይለ ሥላሴ እንኳ በዙፋኑ ላይ እንድትቀመጥ እንረዳሃለን ብለው ወደ ካርቱም ያመጡት ለምን እንደሆነ ትዝብቱን ሲናገር « ለዚሁ ሁሉ ጦርነት ቀይ ባህር ከአክሲሶች እጅ ነፃ ካልሆነ ማንኛውም ጦርነት ለእንግሊዝ የማያመች ነበር ፥ ኢትዮጵያንም በሙሉ ጉልበት ለመርዳት የተወሰደው የጦር እርምጃ ፥ ስትራቴጂ ለማግኘት መሆኑ ቢጠቀስም የጊዜው አዝማሚያ ይፈትሻል » [46] ብሎ ነበር ።

እንግሊዝ ከተቻላት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ ፍላጐት እንደነበራት ብዙ መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ታህሣሥ 1940 እንግሊዛዊው ኰሎኔል ብርክሊ ሽርስት ከለንደን አንድ ቡድን መርቶ ካይሮ በመምጣት «በእኔ የሚመራውን ቡድን በደቡብ ኢትዮጵያ በኩል ይዤ ብገባና ሕዝቡንም ከኢጣሊያ ብቻ ሳይሆን ከቀድሞው አገዛዝ ነፃ እናወጣሃለን ብለን ብንሰብከው ከእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ጐን ተሰልፎ ግዳጁን የሚፈጽም ነው ። የንጉሡም ወደ ኢትዮጵያ መግባት ተፈላጊ አይደለም» [47] የሚል ሐሳብ በካይሮ ለነበሩት የእንግሊዝ ከፍተኛ የጦርና የፖለቲካ ባለሥልጣናት አቅርቦ አሳምኖ ነበር ። ሐሳቡም የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ለም የኢትዮጵያን ክፍል «ጋላስ ላንድ (Galla’s land) » ብሎ የእንግሊዝ ግዛት ከነበረው ኦጋዴን ጋር አደባልቆ ለመግዛት ነበር ። ይሁን እንጂ ፥ ኃይለ ሥላሴ እንግሊዞች በቀጥታ በራሱ ላይ እንዳሴሩበት ስለተረዳ ሐሳቡን ተቃወመው ። ጀኔራል ፕላት ኃይለ ሥላሴን እንደምንም ብሎ እንዲአግባባው ዌቬል ትዕዛዝ ሰጥቶት ነበር ። ፕላትም ለማግባባት ከፍተኛ ጥረት አድርጐ ሳይሳካለት ቀርቶአል ። ኃይለ ሥላሴም ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ በጉዞ ላይ እንዳለ በካርቱም የነበሩት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ባለሥልጣናት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለቃ ከወጣች በኋላ ኢትዮጵያ ከጠላት በተማረኩ የቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ስር መተዳደር እንዳለባት የካቲት 1941 ገደማ በካርቱም ሴራ ሲያውጠነጥኑ እንደነበር መስማቱን ገልጾአል ። [48]

ይሁን እንጂ ነገሮችን ከወቅቱ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና እንግሊዝ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት የነፃነት ጉዞ በጐ

Digitized by Google

አመለካከት ያላት አስመስሎ ለማቅረብ በመሞከር የእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው አንቶኒ ኤደን እንግሊዝ የኢትዮጵያን ነፃ መንግሥት እንደገና መቋቋም በደስታ የምትቀበልና በኢትዮጵያ ላይ ምንም አይነት የግዛት ፍላጐት እንደሌላት እና በኢኮኖሚና በፖለቲካ መስክም ሰላም በአካባቢው እንደተገኘ በዓለምአቀፍ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያን «ለመርዳት» ዝግጁ መሆኗን የካቲት 4 ፣ 1941 ለምክር ቤቱ ገልጾ ነበር ። [49]

በተጨማሪም በሱዳንና በጐንደር አካባቢ ለኢትዮጵያ ነፃነት ይታገሉ ከነበሩት አርበኞችና አገር ወዳዶች መካከል የተወሰኑ ቡድኖች የኃይለ ሥላሴን መመለስ አበክረው በመቃወም ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ጋር ውይይት ጀምረው እንደነበር ይታወሳል ። [50] በተለይም በአርማጭሆ ፣ በወልቃይትና ጠገዴ ይዋደቁ የነበሩት አርበኞች ተቃውሞአቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ እንደነበር ተገልጾአል ። [51] እንዲያውም ፣ በአንድ የአርበኞች መሪዎች ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ ወደፊት ሪፐብሊካዊ መንግሥት መመስረት እንዳለባት የሚያሳስብና የ900 ያህል አርበኛ መሪዎችን ፍላጐት ያንጸባረቀ ጽሑፍ ለመንግሥታት ሊግ ለማቅረብ መዘጋጀቱን ግሪንፊልድ የተባለው ፀሐፊ ጠቁሞአል ። ኃይለ ሥላሴም ይህንን እንደሰማ ለደጃዝማች (አሞራው) ውብነህ በጐን ጽፎ የዚህ ዓይነቱ የተቃውሞ ንቅናቄ ባህላዊውን የንጉሥ አገዛዝ የሚቃወም ስለሆነ በጥብቅ መቃወም እንዳለባቸው አስታውቆ ነበር ። [52]

ከጦርነት ጓደኛነት ወደ ዘረፋና የቅኝ ገዥነት ፍላጐት

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በቆራጥ አርበኞቹ ግንባር ቀደም ታጋይነት ድንበሩንና ነፃነቱን በመጣው ደፍር በወራሪው የኢጣሊያ ፋሽዝም ላይ በየአቅጣጫው ድልን እየተቀዳጀ ሲመጣ የጦር ጓደኛ ተብሎ የመጣው የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አጥንቱን የከሰከሰበትንና ክቡር ደሙን ያፈሰሰበትን «የኢጣሊያ ንብረትና ሀብት ነው» እያለ ወደ ጉረቤት ቅኝ ግዛቶች ማሸሽና ማውደም ጀመረ ። የእንግሊዞች አመጣጥ (ለይስሙላ ቃል በገቡበት መሠረት) የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ወግቶ የጠላት ንብረትና ሀብት ነው የተባለውን ለመዘበረው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ማስረከብ መሆኑ ቀርቶ የኢትዮጵያ አርበኞች በግንባር ቀደምትነት እየተዋጉ የሚማርኩትን የጦር መሣሪያና ንብረት እንኳ ሳይቀር እየሰበሰበ በተለያዩ አቅጣጫ ወደ ውጭ መላክ ጀመረ ። ይህንን በመመልከት ፣ በጦር ሸርካነት ይዞአቸው የመጣው ኃይለ ሥላሴ እንኳ «በጠቅላላ የእንግሊዝ ጦር ባለሥልጣኖች — የአገሪቱን ገቢ የገበያና የማዘጋጃ ቤትን ቀረጥ ሁሉ በእጃቸው ይዘው ለሠራተኞቻችን ደመወዝ ለመክፈል እንዳንችል በማድረግ ችግር አድርሰውብን ነበር ፤ ለጦርነት የሚያስፈልግ ነገር ሁሉ አላግባብ መወሰዱ አገሪቱን ከድህነት ላይ እንደሚጥላት እየታወቀ በግዴለሽነት ተመዘበረ፤»[53] በማለት መስክርባቸዋል ። ከዚህም በላይ ፣ ራሱ ኃይለ ሥላሴ እንዳለው የኢትዮጵያ አርበኞች በጅግ ውስጥ መሽጉ የነበረውን የኢጣሊያ ከፍተኛ ጦር ወግተው ድል በማድረግ የማረኩትን የጦር መሣሪያና እንዲሁም ካሚዮኖች እንግሊዞች እኛ ካልወሰድን በማለት አርበኞችን ወግተው ማቁሰላቸው የእንግሊዝ የጦር ጓደኛነት ተልዕኮ አንደኛው ገጽታ ዘረፋና ቅሚያ መሆኑን በትክክል ያመለክታል ። እንግሊዞች በኤርትራ ክፍለ ሀገርም ያደረሱት ጥፋትና ያካሄዱት ዘረፋ እጅግ ከፍተኛ ነው ።

የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም በኤርትራ

እንግሊዝ ለምጽዋ ወደብ ተግባራዊ ሥራና መከላከያ እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ከሰባ አምስት በላይ የሆኑ ልዩ ልዩ ሕንፃዎች ፣

Digitized by Google

የባህር ኃይል ወታደሮችና የሲቪል ባለሥልጣናት መኖሪያ ቤቶች ፣ የሬዲዮ ጣቢያ መሣሪያዎች ፣ የሲሚንቶና የሌሎች ዓይነት ፋብሪካዎች ፣ የመርከብ ማውረጃና መጫኛ መሣሪያዎች ፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ጋኖች ወዘተ… ለተለያዩ አገሮችና የውጭ ድርጅቶች ሸጣለች ፤ አውድማለችም ። [54] እንዲሁም በአብድአልካድር ባህረ ሠላጤ ላይ ተሠርቶ ከአንድ ሺ ሰዎች በላይ ቀጥር ያስተዳድር የነበረውን የጦር መሣሪያ ፋብሪካና ከ500 በላይ አልጋዎች የነበሩትን ሆስፒታል የዘረፈችውን ዘርፋ የቀረውን እንዳልነበረ አድርጋ ደምስሳለች ። [55]

ይህ ድርጊት በምፅዋ ወደብ ብቻ የተወሰነ አልነበረም ። በአቶምሉ ላይ የነበሩትን 500 የነዳጅ ማጠራቀሚያዎችን ዘርፋ ለራሷ ጥቅም አውላለች ። ከዚህም በቀር በፋጥማ ዳሪ ላይ የነበረውን የፖታሽ ፋብሪካም አፈራርሳ እጅግ ውድና ጠቃሚ የነበሩ መሣሪያዎችን ለውጭ አገር ከመሸጧም በላይ በዙላ ከተማ የ400 ፋሽስት ባለሥልጣናት መኖሪያ ቤቶች የነበሩትን በማፈራረስና የሚጠቀሙትን መሣሪያዎችም አስጭና ወስዳለች ። በናኩራ ላይ ፋሽስት ኢጣሊያ ነዳጅ ለመፈለግ ያቋቋመችውን መሣሪያ አንድም ሳይቀር አግዛለች ። ከዚህም ሌላ ከአቆርዳት እስከ ጉንደር ድረስ የባቡር ሐዲድ ለመዘርጋት አስባ ኢጣሊያ ያከማቸችውን ብረትና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ፣ እንዲሁም ከ300 ያላነሱ የባቡር ፉርጐዎች ምንም ዓይነት ይሉኝታ ሳይኖራት እየዘረፈች ለውጭ በመሸጥ ኢምፔሪያሊስታዊ ፍላጐቷን አርክታለች ። [56]

እንግዲህ ፣ እንግሊዝ በኤርትራ ክ/ሀገር ውስጥ ያካሄደችውን ምዝበራ ከብዙ በጥቂቱ ለምሳሌነት አነሳነው እንጂ ይህ የምዝበራውን ጠቅላላ ገጽታ የሚያሳይ አይደለም ። በአጠቃላይ ወራሪነቱን ሳይሆን የጦር ረዳትነቱንና የቃል ኪዳን ጓደኛነቱን ለዓለም መንግሥታት ሊግ ገልጾና አስመዝግቦ የመጣ አባል መንግሥት ይህን አይነቱን ምዝበራና ጥፋት ሊፈጽም አይገባውም ነበር ።

በሌላ በኩል ፣ እንግሊዝ የኤርትራን ክ/ሀገር ሰፊ ሕዝብ ከእናት አገሩ ኢትዮጵያ ገንጥላ ለረጅም ጊዜ ቅኝ አገዛዝ ቀለበት ውስጥ ለማስገባት ስትል በብሔረሰብ ፣ በሃይማኖት ፣ ወዘተ… በመከፋፈል ባከናወነችው ፀረ አንድነት ድርጊት የተነሳ ዛሬ ለሃያ ዓመታት ያህል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ብልፅግና ጠንቅና ጉታች ሆኖ የኖረው የገንጣይ ፋና እንቅስቃሴ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደረገች መሆኗን በመስከረም መጽሔት ቅጽ 2 ፣ ቁ-6 «የኤርትራ ክ/ሀገር በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር ከ1942 እስከ 1952» በሚል ንዑስ ክፍል ስር በስፋት የተዘረዘረ በመሆኑ እዚህ ላይ መድገሙ ተገቢ አይደለም ። [57] በዚያ ጽሑፍ ውስጥ በወቅቱ በኤርትራ «የተለያዩ የሚመስሉ የመገንጠል እንቅስቃሴዎች እንዲፈጠሩ እንግሊዝ ሁኔታዎችን ያመቻቸችው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ብትዋሃድ የማዕከላዊው የፊውዳል መንግሥት የቱን ያህል ደካማና ለማስተዳደር እንደማይችል የዓለምን ሕዝብ አስተያየት ለማስለወጥና ራሷ በሰበብ አስባቡ በአካባቢው በመቆየት ትግራይንና ኤርትራን አንድ ላይ ቅኝ ግዛት አድርጋ በአፍሪካ ቀንድና በቀይ ባህር አካባቢ ጥቅሟን ለማስፋፋት » [58] እንደነበረ ተገልጿል ።

የ1942 እና የ1944ቱ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ስምምነቶች

በተቀሩትም የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛቶች እንግሊዝ በየደረጃው አመቺ በሆነ መጠን ተመሳሳይ ምዝበራ አካሂዳለች ። የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ያደማ ተንኮል ፈጽማለች ። የመሐል ሀገሩን በቁጥጥሯ ሥር ለማዋል ያሳየችው መፍጨርጨር ያልተሳካ መሆኑን ስትገነዘብ ጠረፍ ግዛቶችን በተለይም እንደ ኦጋዴን ባሉት ላይ ይዞታዋን በተለያየ ሰበብ ጠበቅ አድርጋ ወደ ቅኝ ግዛት የምትለውጥበትን መንገድ መቀየስ ጀምራ ነበር ።

Digitized by Google

እንግሊዝ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይካሄድ የነበረበት ወቅት ስለነበረ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ እንደልብ የመዘዋወር መብት ሊኖረኝ ይገባል በሚል ሰበብና በፈረንሳይ ሶማሌ ውስጥም የጀርመኖች እጅ ያለበት አስተዳደር በመኖሩ ኢትዮጵያ የባሕር መውጫ ታጣለች የሚል ምክንያት በመስጠት ጥር 31/ «የ1942 የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ስምምነት» በመባል የታወቀውን ስምምነት ከኃይለ ሥላሴ ጋር ተፈራረመች ።

ስምምነቱ በ12 አንቀጾች የተከፈለ ሲሆን ፍሬ ነገሮቹ 1/ ኢትዮጵያ እንግሊዛውያን አማካሪዎችን በገንዘብ ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ ሥራና የመቆጣጠር ኃላፊነት የሚኖራቸውንና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች ይዘው ሊሠሩ የሚችሉ ባለሙያዎችን እንድትቀጥር ፣ 2/ የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች የኢትዮጵያን ጦርና ፖሊስ ሠራዊት እንዲአደራጁና እንዲአሰለጥኑ ፣ 3/ ኦጋዴንና «የተከለሉ ቦታዎች» የተባሉ አካባቢዎች በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር እንዲውሉ ፣ 4/ የእንግሊዝ የሲቪልና የጦር አውሮፕላኖች ያለምንም ገደብ በኢትዮጵያ ላይ የመብረርና በማንኛውም በኢትዮጵያ በሚገኝ አውሮፕላን ማቢያ የማረፍ መብት እንዲኖራቸው ፣ 5/ እንግሊዝ በጣሊያን ሥር ያሉ ኢትዮጵያውያን ምርኮኞችን እንድታስመልስ የሚሉት ነበሩ ።[59] እንዲሁም ሀ/ በአዲስ አበባ የእንግሊዝ ተቀማጭ መልዕክተኛ ከማንኛውም የውጭ ዲፕሎማሲያዊ መልዕክተኛ በማንኛውም ረገድ ቅድሚያ እንዲሰጠውና ፣ ለ/ እንግሊዝ ሳትስማማ የባዕድ አገር አውሮፕላን በኢትዮጵያ ላይ እንዳይበር ፣[60] ሐ/ ኢትዮጵያም ለእንግሊዝ ወታደሮች መኖሪያና ለጦር ሠፈር የሚውል መሬትና ሕንፃዎች በነፃ እንድትሰጥ የሚሉ ሐሳቦች ይገኙባቸዋል ።

ስምምነቱ የተዘጋጀው በራሷ በእንግሊዝ በመሆኑ እንግሊዝ በኢትዮጵያ ላይ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ጥቅሟን እንድታስከብር ሆኖ ተዘጋጅቶአል ። በስምምነቱ መሠረት በኢትዮጵያ በገንዘብ ፣ በአስተዳደርና የወታደራዊ መዋቅሮች ውስጥ እንግሊዝ እጇዋን እንድታስገባ ሕጋዊ ድጋፍ በማግኘቷ ፣ ሀ/ የእንግሊዝ ከበርቴዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታላቸውን እንዲያውሉና ለ/ እንግሊዝ ከጦር መጣሪያ ጀምሮ ማንኛውንም ሸቀጥ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት እንድትችል አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን፣ በስምምነቱ ላይ የገንዘብ እርዳታ ጉዳይ አልተጠቀሰም ።[61] ሆኖም ፣ በዚህ ወቅት ፣ ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው የወደመባትን ኢኮኖሚዋን መልሳ ለማቋቋም በምታደርገው ጥረት እንግሊዝ የአሥር ሚሊዮን ፓውንድ ስተርሊንግ (እርዳታ እንድታደርግላት ጠይቃ ነበር ። ይሁንና እንግሊዝ ፈቃደኛ ካለመሆኗ የተነሳ ለኢትዮጵያ እርዳታ አደርጋለሁ ብላ ቃል የገባችው ሁለት ሚሊዮን ተኩል እስተርሊንግ ፓውንድ ብቻ ነበር ። ምንአልባትም በስምምነቱ ላይ የገንዘብ እርዳታ ሳይጠቀስ የቀረው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

እንግሊዝ ኢትዮጵያን በራሷ አየር ላይ ያላትን የማዘዝ ሥልጣን እንኳ ሙሉበሙሉ እንዳትጠቀም እንዲያውም በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዳለች አገር ሁሉ በአገሯ ላይ ለሚበሩ የባዕድ አገር አውሮፕላኖች ፈቃድ ለመስጠት እንግሊዝን ማስፈቀድ እንዳለባት በግዴታ ውስጥ ማስገባቷ ኢትዮጵያን ለሁለት ዓመታት ያህል ሙሉበሙሉ በቁጥጥሯ ሥር አድርጋ ቅኝ አገዛዝን የምትዘረጋበትን ፣ ያለበለዚያም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን በአስተማማኝ ሁኔታ የምታጠናክርበትን ስልትን ዘዴ መቀየስ እንዲያስችላት አቅዳ ነበር ለማለት ያስደፍራል ። ከዚህም በቀር፣ በእነዚህ የስምምነት ዓመታት ውስጥ ለአገር ውስጥ እንዱስትሪዎቿ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችንና በ1929 ለደረሰባትና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጅማሬ እያስከተለባት ለመጣው የኢኮኖሚ ድቀት መድኅኒያ የሚሆን ልዩ ልዩ ሀብትም ከኢትዮ

Digitized by Google

ጵያ ለመንጠቅ እንዲአገዛትም አልማ ነበር ማለት ይቻላል ።

በዚህ ከ1942 በኋላ በተፈረመውም የ1944 የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ስምምነት መሠረት እንግሊዝ ኦጋዴንን እስከ 1950 ድረስ በይዞታዋ ሥር ማቆየት ቻለች ።

ይህም ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድና አካባቢውን እንዲሁም ድሬዳዋን ጨምር «የተከለለ አካባቢ» በሚል ስም ይዛ በቁጥጥሯ ሥር እንድታውል አስችሎአት ነበር ። [62]

ይልቁንም ስምምነቱ የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ንግድ መተላለፊያ በር የሆነውን የባቡር ሐዲድና አካባቢ የመቆጣጠር መብት ስጥቶአት ስለነበር አገሪቱን በዚህ ዓይነት ዘዴ እየሸራረፉ መያዝ የተሻለ አማራጭ መስሉ በመታየቱ ጀኔራል ፕላት ጥር 3 ፥ 1942 አዲስ አበባ ፥ አዳማ ፥ ጂማ ፥ አዋሽ ፥ ጐንደር ፥ ዳባት ፤ ሐረር ፤ አዳርቃይ ፤ አድዋ፤ ዶሎ ፤ አዲግራት ፤ ነገሌ ፤ ኩሀ ፤ አዋሽ ፤ ያቤሎ ፤ ኮምቦልቻ ፤ ሜጋ ፤ ሰርዶና ሞጆ የተባሉት ከተሞችና ቦታዎች ተጨማሪ የተከለሉ አካባቢዎች እንደሆኑ በገዛ ሥልጣኑ ማስታወቂያ ለጠፈ ። እነዚህም ቦታዎች «የእንግሊዝ የጦር ሠፈሮች» የሚል ስያሜ ተሰጣቸው ። በእነዚህም ከተሞችና አካባቢዎች ላይ ሕግ የማውጣቱ ፤ የማስፈጸሙና የማስተዳደሩ ኃላፊነት የእንግሊዝ የጦር ዋና አዛዥ የነበረው ጀኔራል ፕላት ወይም እርሱ የወከለው ዋና የፖለቲካ መኰንን የነበረው ሰር ፊልፕ ሚቼል እንዲሆን ገልጾ ነበር ። [63]

ከአዲስ አበባ ከተማ ጀምር በመላ አገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን እስትራቴጂያዊ ከተሞችና አካባቢዎች ምንም ዓይነት የውል መሠረት ሳይኖር የእንግሊዝ የጦር ይዞታዎች ናቸው ብሎ ይፋ ማወጁ የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም የተሰማውን የልብ ልብና ያደረበትን የማን አለብኝነትን ስሜት ከማሳየቱም በላይ ጀግናና በዘመናት ፀረ ቅኝ አገዛዝ አቋሙ በተግባር ፍቱን ለሆነው የኢትዮጵያ ስፊ ሕዝብም የነበረውን ንቀት ያስረዳናል ። ከዚሁም በላይ ከኃይለ ሥላሴ ጋር ባደረጋቸው አንዳንድ ድርድሮች ባገኛቸው የድል አድራጊነት ምልክቶች እየተጽናና ለበለጠ ጥቅምና ብሎም መላዋ ኢትዮጵያን የተፅዕኖ ክልል ለማድረግ መሽቀዳደምና ግፊቱንም መቀጠል እንዳለበት መገንዘቡን ያመለክታል ። በየአቅጣጫውና በየአጋጣሚው በማንኛውም ደረጃ እንግሊዝ የፈጸመቻቸው ድርጊት ሁሉ ለብዙ ጊዜ ኢትዮጵያን በተፅዕኖ ክልል ሥር ለማዋል ታልመው የነበረውን ዕውን ለማድረግ ነበር ።

እንግሊዝ የ1942ቱ የሁለቱ አገሮች የጋራ የስምምነት ጊዜ ሲፈጸም ሌላ « የ1944 የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ስምምነት» የተባለውን ስምምነት ከኢትዮጵያ ጋር ታኅሣሥ 1944 ተፈራረመች ።

ስምምነቱ ከአተኮረባቸው ነጥቦች መካከል፥1ኛ/ ሁለቱ አገሮች የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን ሙሉ ሥልጣን ወደአለው የአምባሳደር ደረጃ ማሳደግ(አንቀጽ 2) ፥ 2ኛ/ ኢትዮጵያ እንግሊዛውያን አማካሪዎችንና ዳኞችን እንደአስፈላጊነቱ መቅጠር(አንቀጽ3)፥ 3ኛ አንድ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለእንግሊዝ ወታደራዊ ዕዝ የሆነ የእንግሊዝ ጦር በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ (አንቀጽ 6) ፤ 4ኛ/ እንግሊዝ የፍራንኮ—ኢትዮጵያ የባቡር ሐዲድ ኩባንያ አስተዳደርንና ቁጥጥርን ለኢትዮጵያ እንድታዛውር፤ ገን በመጓጓዣ ረገድ ለእንግሊዝ ወታደራዊ ሥራና ባለሥልጣናት ኢትዮጵያ በማናቸውም ጊዜ ቅድሚያ እንድትሰጥ (አንቀጽ 5) 5ኛ/ኦጋዴንን የተከለለ አካባቢ የተባለውን ግዛት በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ሥር እንዲቆይ (አንቀጽ 7) ፥ 6ኛ/በእንግሊዝና በእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ሁሉ ዘንድ የተመዘገበ የሲቪል አውሮፕላን በኢትዮጵያ ላይ መብረርም ሆነ ማረፍ እንዲፈቀድለት(አንቀጽ9)የሚሉት ነበሩ።[64]

Digitized by Google

ይሁንና ፣ በዚህ ስምምነት ላይ የኤርት
ራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ወይም በእንግ
ሊዝ እጅ መቆየትና የገንዘብ እርዳታንም
ሆነ ብድርን በሚመለከት ረገድ ምንም የተ
ወሳ ነገር የለም ።

በዚህ በ1944 ስምምነት መሠረት እንግ
ሊዝ በኢትዮጵያ ላይ ከዚህ በፊት ከነበራት
የጥቅምና በአንዳንድ ሁኔታዎች የጣልቃ
ገብነት ይዞታ የሆነ ግሸግሸግ ብታደርግም
አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ የባሕር በሮች
ንና አካባቢ ግዛቶችን በቁጥጥሯ ሥር የአዋ
ለች በመሆኗ በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ላይ
ከፍተኛ ተፅዕና ነበራት ። ይልቁንም የኢት
ዮጵያ የግዛት ወሰን በአብዛኛው በእንግሊዝ
ቅኝ ግዛቶችና ከኢትዮጵያ በተቆረሱ የግዛት
ይዞታዎች (ኤርትራንና ኦጋዴንን ጨምሮ)
የተከበበ ስለነበር አሁንም ቢሆን የኢትዮ
ጵያ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የጥቅሟ
ተገራሪ ሆና ሲገኝ ፈጥና የመቆጣጠር እር
ምጃ ለመውሰድ እንግሊዝ አመቺ መንገድ
ነበራት ማለት ያስደፍራል ።

እንግሊዝ ፣ በ1942ና በ1944 ከኢትዮጵያ
ገዥ መደቦች ጋር ባደረገቻቸው ስምምነቶች
መሠረት የኦጋዴንን ሰፊ ሕዝብ ከቀረው
የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጥላ በመያዝ የስቃይ
ገፈት እንዲቀምስ አድርጋለች ። ይኸውም
1ኛ/ የኦጋዴንን ሕዝብ ሥራዬ ብላ ከአስ
ታጠቀችው የእንግሊዝ ሶማሌ ሕዝብ ጋር ፣
በኦጋዴን ውስጥ የሚገኘውን ውሃና ግጦሽን
በሚመለከት ረገድ ቅድሚያ ለእንግሊዝ
ሶማሌ ሕዝብ መስጠት አለበት እያለች እን
ዲጋጭና እርስ በርሱ እንዲገዳደል አድርጋ
ለች ፣ 2ኛ/ ምክንያትና ሰበብ እየፈለገች የኦ
ጋዴንን ሕዝብ በመግረፍ ፣ በማሰርና በመ
ግደልም አሰቃይታለች ። ይህንንም «ጣሊያ
ያኖችን ተዋግተናል ፤ በጣሊያኖችም ሥር
ተሰቃይተናል ፤ እንደቀሩት ኢትዮጵያውያ
ንም ፣ ለነፃነታችን ተዋግተናል ፣ እኛስ
ለምንድነው ነፃ የማንወጣው ?» [65] በማለት
የኦጋዴን ሰፊ ሕዝብ ወኪሎች ለኢትዮጵያ
መንግሥት ያቀረቡትን አቤቱታ ማጤኑ የደ
ረሰበት ብዝበዛና ጭቆና ምን ያህል መሪር
እንደነበረ ያስገነዝበናል ፣ 3ኛ እንግሊዞች
ኦጋዴንን ያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት
የኦጋዴን ሕዝብ ንብረት የሆነውን ከብት
ገዝተው ገንዘብ ሳይከፍሉ ደረሰኝ ብቻ ሰጥ
ተው በማባረር ፣ ከብቱን ዘርፎ በመው
ሰድ ፣ መንደሮችን በማውደም ፣ ያለፍርድ
በማሰርና በመቅጣት ሕዝቡን በችግር ጠብ
ሰውታል ፤ አሳድውታል ፤ በአጠቃላይ ለስ
ቃይ ዳርገውታል ። [66]

ከዚህም በላይ ፣ ለኢጣሊያ ፋሽስት በም
ንም ዓይነት ሳይነበረከኩ በዱር በገደሉ እየ
ተዘዋወሩ ለአምስት ዓመታት ያህል ይታገ
ሉና ይዋደቁ የነበሩት አርበኞችና ደጀኑ ሰፊ
ሕዝብ የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊዝም የቅኝ
አገዛዝ ፍላጎትና አሻጥር ያለምንም ፍርሃት
በመቃወም በአካባቢው የሚካሄድ ትግል
እየተፋፋመ ሌላ መልክ እየያዘ በመምጣቱ
ለኃይለ ሥላሴም ቢሆን ከእንግሊዝ ጋር እጅ
ና ጓንት መሆኑ ሕዝባዊ ተቃውሞ የሚያስነ
ሳበት ሆነ። ኃይለ ሥላሴ የሕዝቡን ተቃውሞ
በመፍራትና የእንግሊዝ አገዛዝ ለራሱም
ቢሆን ጉዳት ሊያመጣበት እንደሚችል በመ
ገንዘቡ በወሰዳቸው እርምጃዎች በኃይለ
ሥላሴና በእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም መካ
ከል ሊኖር የነበረው የጥቅም መቆራኘትና
ግንኙነት እየፈራረሰ መሄድ ጀመረ ።

ይህንን በሚገባ የተገነዘበውና ምንአልባ
ትም የእንግሊዝንና የኃይለ ሥላሴን መቃ
ቃር መጠቀሚያ አድርጎ እጁን ለማስገባት
የፈለገው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የገፋ
ፋው ኃይለ ሥላሴ በዚህን ጊዜ ነበር ፊቱን
ወደአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መለስ ያደ
ረገው ። ይህን ሁኔታ የተመለከተ አንድ
ጸሐፊ «የኢትዮጵያ መንግሥት የእንግሊ
ዝን ይዞታ ለማዳከም የአሜሪካንን ድጋፍ
ፈለገ ።» [67] በማለት ገልጾታል ። መደባዊ
ጥቅሞችና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ያስገ
ደዱት ኃይለ ሥላሴ በ1951 የወዳጅነትና
የኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም በ1953 የመከ
ላከያ ስምምነቶች ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊ
ዝም ጋር በመፈራረም የእንግሊዞችን ጥቅ

Digitized by Google

ምና ይዞታ አሳንሶ ለአሜሪካ ሞኖፖሊስቶች ሰፊ በር ከፈተላቸው ። [68]

ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለማሳየት የተሞከረው ኢትዮጵያ በተለይ ከ18ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችውን ተጋድሎ ነው ። እንግሊዝ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ለማናጋት የጣና ሐይቅንና የአባይን ሸለቆ በቁጥጥር ሥር በማድረግ ቅኝ ግዛታዊ ፍላጐቷን ለማሟላት ከፈረንሳይ ጋር ታደርገው በነበረው ፉክክር ምሥራቃዊውን የኢትዮጵያ ግዛት የተፅዕና ክልሏ ለማድረግ ያደረገችው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ሙከራ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ከዚህምበቀር የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነት ለመድፈርም ሆነ ኢትዮጵያን በአጠቃላይ የተፅዕና ክልል ለማድረግ እንግሊዝ አንድ ጊዜ ከኢጣሊያ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከፈረንሳይ ጋር ያለበለዚያም ከሁለቱም ጋር አንድ ላይ ሆና ግሴርና ለኢትዮጵያም ጠቀሜታ ያለው ስምምነት አስመስሎ በማቅረብ የተደጋገመ ሙከራ አድርጋለች ።

በተለይም ኢትዮጵያ የአባይን ወንዝና መጋቢ ወንዞችን እንዳትገድብ የሚጠየቀውን የ1902ቱን የእንግሊዝ የኢትዮጵያ ስምምነት ፥ የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ግዛት ሰንጥቆ የሚአልፈውን የሲሺል ሮድን የሐዲድ መዘርጋት ፤ እቅድ ፥ የኢትዮጵያን ግዛት በአብዛኛው ቀራርሶ ለሦስት መንግሥታት ጥቅም የሚያውለውን የ1906 የለንደኑን ሶስትዮሽ ስምምነት ፥ የኢጣሊያ ኢትዮጵያን መያዝ ሕጋዊ አድርጋ ግወቋንና የመንግሥታት ሊግ አባል አገሮችም የኢጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ የነበረውን ግዛት እንዲያውቁ የምትገፋፋ መሆኗን በሚያዝያ 16፤/1938 የገባችውን ቃል ኪዳንና እንዲሁም በ1941 በጦር ጓደኝነት ስም መጥታ ያሳየችውን ቅኝ ግዛታዊ ዝንባሌ ስንመለከት ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ጋር ያካሄደችው ፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግሉ ከነበራት የመከላከልና የጦር መሣሪያ አቅሟ ጋር ሲነፃፀር ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ። ይህ የተጋድሎ ታሪኳም በተከታዩ ትውልድ ዘንድ ሲታወስ የሚኖር ነው ።

የአሁኑም ትውልድ ከዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ፤መማር ከሚችለው አንዱ ፀረ ቅኝ አገዛዝና ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግሉ ምን ያህል መራራ ፥ ውስብስብና ቀራጥ መሥዋዕትነትን የጠየቀ መሆኑንና የዛሬዋ አብዮታዊት ኢትዮጵያም በዚህ መራራ ትግል ውስጥ አልፉ የተገኘች መሆኗን ነው ። ወጣቱ ትውልድ ይህን ኃላፊነቱን ለመቀበልና ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ጭቆና ነፃ የሆነች የተከበረችና የበለፀገች ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመመሥረት በቅርብ ጊዜ ተግባራዊ እንዲሆን የታቀደውን የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ሊያዘጋጁት ከሚችሉት መሣሪያዎች አንዱና እጅግ ተፈላጊው ነው ። በብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት የአሁኑና የወደፊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነት አስከባሪዎች ሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ፤ አገርን መጠበቅ ከምርት ማምረት ጋር በማጣመር የሚካሄድበት ፥ የዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የደረሰበትን የውትድርና ሙያ ዕውቀትን የሚቀስሙበት ፥ ለእናት አገራችን ነፃነት ዋስትና ለመስጠትና የአካባቢያችንንም ሆነ የዓለምን ሰላም ለማስከበር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያዘጋጃቸው ነው ።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ደጋግመው እንዳስገነዘቡት «ምንጊዜም ፍላጐታችንና ዓላማችን ሰላምና ፍትሕ የሰፈነበት ዕድገት ነው ።» ዛሬም የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ተቀዳሚ ዓላማ ጭቆናና ብዝበዛን አስወግዶ ሰላምና እኩልነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ መገንባት ቢሆንም ፥ የውስጥና የውጭ አድኃሪዎች ባላቸው ኃይል ሁሉ ይህን የተከበረ ዓላማ ለማጨናገፍ እየተፍጨረጨሩ ነው ። የዛሬውም ሆነ የጥንት የትግል ታሪካችን የሚያስገነዝበን አንዱ ቁም ነገር ጠላቶቻችን እንደማይተኙልንና ነፃነታችን ሊከበር የቻለውና የሚከበረው በመራራ ትግልና መሥዋዕትነት መሆኑን ነው ። ይህን የታሪክ ሐቅ መገንዘብ ፥ የአሁኑና መጪው የኢትዮጵያ ትውልድ የእናት አገሩን አንድነትና ነፃነት እንዲሁም ፍትሕ፥ ሰላምና ፍጹም ብልጽግናን የሚያስፍንለትን አብዮት የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት የሚጠብቀው መሆኑን በቅድሚያ አውቆና ተረድቶ ለትግሉ የበለጠ እንዲዘጋጅ ይረዳዋል ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. R. P. Skinner, *Abyssinia Today*, E. Arnold, New York. pp. 95-96.
2. H. G. Marcus, *The Life and Times of Menelik II. Ethiopia* 1844-1913, Oxford University Pr., London 1975 pp. 189-190
3. *Ibid.*, p. 190.
4. *Ibid.*, p. 190.
5. ኃይለ ሥላሴ ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅጽ 1 ፣ አዲስ አበባ ፣ 1965 ገጽ 101 ።
6. E. Burns, *Abyssinia and Italia*, V. Collanted, London 1935, p. 37.
7. ተክለጻድቅ መኩሪያ ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፣ አዲስ አበባ ገጾች 144—145።
8. E. Burns, p. 43.
9. *Ibid.*, p. 44.
10. *Ibid.*, p. 46.
11. ኃይለ ሥላሴ ፣ ገጾች 84—85።
12. ከላይ የተጡቀሰው ፣ ገጽ 102 ።
13. ገብረ ሕይወት ጎዳሩ ፣ ያች ቀን ተረሳች ከ1925—1933፣ አዲስ አበባ፣1967 ገጽ 3 ።
14. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 13 ።
15. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 1 ።
16. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 13 ።
17. E. Burns, p. 48.
18. ኃይለ ሥላሴ ፣ ገጾች 143—144 ።
19. ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ፣ ገጾች 143-144
20. E. Burns, pp. 63-64.
21. F. E. Hayter, *Gold of Ethiopia* Paul Coltd, London 1936), pp. 11-13.
22. L. Mosley, *Haile Selassie: The Conquering Lion*, Weiden Field and Nicolson, London 1964, p. 192.
23. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፣ ገጽ 122 ።
24. G. W. Baer, *The Coming of Italian — Ethiopian War*, (Harvard University Pr., Cambridge, Mass, 1967), pp. 53-55.
25. *A History of Africa* 1918-1967, Nauk Pr., Moscow 1967, p. 333.
26. G. W. Baer, p. 245.
27. *A History of Africa* 1918-1967, p. 331.
28. G. W. Baer, pp. 374-375.
29. ገብረወልድ እንግዳ ወርቅ፣ ማይጨው፣ የማይጨው ዘመቻና የጉዞው ታሪክ ፣ አዲስ አበባ 1947፣ ገጽ 36 ።
30. ሞገስ ክፍሌ ፣ የሞሶሎኒ ምስጢር ፣ አዲስ አበባ 1949 ፣ ገጽ 41 ።
31. E. Burns, pp. 59-60.
32. *Ibid.*, p. 62.
33. G. W. Baer, "Haile Selassie's Protectorale Appeal to King Edward VIII" *Cahier's D'Etudes Africanies*, Vol. IX, No. 34 p. 310.
34. *Ibid.*, p. 311.
35. *Ibid.*, p. 310.
36. *Ibid.*, p. 310
37. *Ibid.*, p. 312.
38. *Ibid.*, p. 121.
39. C. Sandford, *Ethiopia Under Haile Selassie*, M. Dent and Sons Ltd., London 1946, pp. 102-103.
40. *Ibid.* pp. 102-103.
41. *Ibid.*, p. 103.
42. L. Mosley, p. 187.
43. E. S. Pankhrust, *Ethiopia and Eritrea, The Last Phase* 1941-1952, Lalibela House, Wood Ford, ESS, 1953, p. 17.
44. C. Sandford, pp. 104-105.
45. Gunther, *Inside Africa*, H. Hamilton, London 1955, p. 264.
46. ኃይለ ሥላሴ ፣ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 220 ።
47. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 253 ።
48. ከላይ የተጠቀሰው ፣ 263 ።
49. C. Sandford, pp. 120-121.

Digitized by Google

50. R. Greenfield, *Ethiopia A New Political History*, Pall Mall Pr., London 1965, p. 247.

51. ገብረሕይወት ጎዳና ፣ ገጾች 216—218

52. R. Greenfield, p. 247.

53. ኃይለ ሥላሴ ፣ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 336 ።

54. E. S. Pankhrust, *Eritrea on The Eve*, New Times and Ethiopian Books, Woodford Green, 1952, pp. 13-14.

55. *Ibid.*, p. 9.

56. *Ibid.*, p. 16.

57. ገርማሜ ገ/ የሱስ ፣ «የኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ–በኤርትራ ክፍለ ሀገር የመገንጠል እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ» መስከረም ቅጽ 2 ፣ ቁ- 6 ፣ 1974 ፣ ገጾች 74—88 ።

58. *Ibid.* p. 76

59. E. S. Pankhrust, *Exitalian Somaliland*, Watt and Co., London 1951, p. 152.

60. Legesse Lemma, *Political Economy of Ethiopia* 1875-1974, Doctrial Dissertation, Unw. Micro Film International, London 1980, pp. 205-206.

61. C. Sandford, p. 129.

62. E. S. Pankhrust, p. 151.

63. *Ibid*, p. 152.

64. Agreement between His Majesty in respect of the United Kingdom and His Imperial Majesty the Emperor of Ethiopia for regulation of mutual relations. Addis Ababa, 1944, Articles, 2, 3, 5, 6, 7 and 9.

65. E. S. Pankhrust, p. 164.

66. *Ibid.*, p. 167.

67. *History of Africa* 1918-1967, p. 338.

68. *Ibid.*, p. 338.

Digitized by Google

የኋላቀር አገሮች የውጭ ዕዳ ሸክምና የኢምፔሪያሊዝም የፋይናንስ ስትራቴጂ*

እየጨመረ የመጣው የኋላቀር አገሮች የውጭ ዕዳና በፋይናንስ ሀብታቸው በኩል የሚፈፀምባቸው ዘረፋ እንዲሁም እየከረረ የመጣው የብድር ተጽዕኖ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ፣ በዓለም ባንክና በሌሎች የባንክ ሞኖፖሊስቶች የተቀየሰ ነው ።

የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲ ኋላቀር አገሮችን በሚመለከት የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስትራቴጂ ዋንኛው የትኩረት መስክ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም በኋላቀር አገሮች ላይ የሚያካሂደውን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ብዝበዛ እንዲቀጥልና እንዲጠናከር ያደረገው ይኸው በአገሮች መካከል ያለው የፋይናንስና የገንዘብ ግንኙነት መሆኑ ግልፅ ነው ።

ዓለም አቀፍ የፋይናንስና ካፒታል የብዝበዛ መረቡን በአገሮች ሁሉ ላይ በመጣል ይህንኑ ብዝበዛ ይበልጥ ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው ። ስለዚህ ኋላቀር አገሮች በአሁኑ ወቅት ያለው የካፒታሊስት ፋይናንስና የገንዘብ ስርዓት መሠረታዊ መሻሻል እንዲደረግበት ያቀረቡትን ትክክለኛ ጥያቄ የዋና ዋናዎቹ ኢምፔሪያሊስት አገሮች መንግሥታት በአንድነት በመሆን ፣ መቃወማቸው ምንም የሚያስገርም አይሆንም ። [1] እንዲያውም የፋይናንስ ብዝበዛቸውን ይበልጥ ለማጠናከር እርምጃ ለመውሰድ እየተዘጋጁ ነው ። የዚህ ሁሉ ጥረት ውጤትም ከ1970ዎቹ ** ዓመታት ወዲህ በኋላቀር አገሮች የዕዳ መጠን ላይ ፈጣን እድገትን ሲያስከትል፣በተለያዩ የዕዳ ዘርፎችና በተለያዩ የክሬዲት ምንጮች የብድር ድርሻም ፣ ላይ ከፍተኛ ለውጥን አምጥቷል።

* ይህ ጽሑፍ የተጻፈው የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ጓዶች በሆኑት ኤሸሌን ኩሉሽ እና ፍሪድፉን ሮዘና ሲሆን ፣ የአማርኛው ትርጉም የተዘጋጀው በመስከረም መጽሔት ዝግጅት ክፍል ነው ።

** በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱ ዓመተ ምህረቶች ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

የኋላቀር አገሮች የፋይናንስ ሁኔታ ማሽቆልቆል

በተፋጠነ ሁኔታ በማደግ ላይ ያለው የኋላቀር አገሮች የውጭ ዕዳ እጅግ አሳሳቢ የኢኮኖሚ ችግራቸው ሆኖ አል። በ1971፣ 85 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የነበረው የኋላ ቀር አገሮች የውጭ ዕዳ በ1981 ወደ 500 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከፍገያለ ሲሆን፣ በ1985 በእጥፍ ያድጋል ተብሎ ይገመታል።

ኋላቀር አገሮች ዕዳቸውን ለማቃለል በ1971፣ 6.1 ቢሊዮን፣ በ1979፣ 44.3 ቢሊዮን ዶላር መክፈል የነበረባቸው ሲሆን በ1981 ግን መክፈል የነበረባቸው ዕዳ ወደ 88 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ብሎ ነበር።[2] የወለድ ክፍያው ድርሻ ደግሞ በ1971፣ 30 በመቶ፣ በ1979 37 በመቶ የነበረ ሲሆን በ1981 ግን ወደ 40 በመቶ ከፍ ብሎአል። ይህም የወለድ ክፍያ ኋላ ቀር አገሮች በጠቅላላ ከወጪ ንግዳቸው ካገኙት ገቢ 80 በመቶ ነበር።[3]

ገና ከ1970ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት ጀምሮ ኋላቀር አገሮች ቀደም ሲል የነበረባቸውን ዕዳና ወለድ ለመክፈል በተደጋጋሚ አዲስ ብድር መጠየቅ ግድ ሆኖባቸው ነበር። ለምሳሌ በ1980 ኋላቀር አገሮች (ዘይትኛው አገሮችንም ጨምሮ) በአጠቃላይ ካገኙት 100 የቢሊዮን ዶላር ብድር ውስጥ 40 ቢሊዮን (ማለትም 40 በመቶውን) ቀድሞ ለነበራቸው ዕዳ ክፍያ ያዋሉ ሲሆን በ1978 ግን ይህ የክፍያ መጠን 25 በመቶ ብቻ ነበር። የተባበሩት መንግሥታት የንግድ የልማት ድርጅት ሪፖርት እንዳመለከተው ኋላቀር አገሮች በ1981 የነበራቸውን ዕዳ ለመክፈል የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ከግል ተበዳሪዎች ካገኙት አዲስ ብድር የሚበልጥ ነበር።[4]

ይህ ሁኔታ ኋላቀር አገሮች የሚያገኙትን ብድር ለተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገትና ለክምችት እንዳያውሉት ዕንቅፋት ሆኖአል። በአንፃሩ ግን እነዚህ ኋላቀር አገሮች ዕዳቸውን ለመክፈል እንዲችሉ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የማበደሩ ተግባር ለብድር ካፒታል ባለቤቶች ከፍተኛ የትርፍ ምንጭ እየሆነ መጥቶአል። ይህም ሌኒን «ከአነስተኛ የአራጣ ካፒታል» ዕድገቱን የሚጀምረው ካፒታሊዝም በግዙፍ የአራጣ ካፒታል ዕድገቱን ያገባድዳል።[5] ያለውን አባባል እውነተኛነት ያረጋግጣል።

የባሰ የፋይናንስ ችግር አዘቅት ውስጥ ከመውደቅ ለመዳን ሲሉ ኋላቀር አገሮች በየዓመቱ የዕዳ መተኪያ ይጠይቃሉ። በ1981 መጨረሻ ላይ 26 ታዳጊ አገሮች የነበረባቸውን የ8 ቢሊዮን ዶላር የዕዳ ክፍያ ያስተላለፉ ሲሆኑ በ1975 ግን የዕዳ ክፍያውን ያስተላለፉት 13 ታዳጊ አገሮች ብቻ ነበሩ። የዕዳቸውም መጠን 1 ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነበር።[6] 1982 እንዲህ ዓይነቱ የዕዳ መተኪያ ብድር መጠን ወደ 30 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከፍ እንደሚል ተገምቷል።

ኋላቀር አገሮች በተለይም ዘይት አምራች ያልሆኑት የገጠማቸውን የክፍያ ሚዛን መዛባት ችግር ከአባባሱት ምክንያቶች መካከል የዓለም አቀፍ የወለድ መጣኔ እየጨመረ መሄድ፣ በኢንዱስትሪ በዳበሩ አገሮች ውስጥ የገበያ ዕድል ማነስ፣ የምርት መጠን ማሽቆልቆልና በካፒታሊስቱ ዓለም የንግድ ግንኙነት ውስጥ የንግድ እገዳዎች መስፋፋት ይገኙበታል። በተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ድርጅት ግምት መሰረት በ1979 45.4፣[7] በ1981 ደግሞ 76.0 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የነበረው የክፍያ ሚዛን መዛባት በ1982 ወደ 92 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል።[8] የዓለምአቀፍ መንግሥታዊ ሞኖፖል የባንክ ሥርዓትና የብድር ካፒታል ገበያ እንዲሁም የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ማለትም ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) የዓለም ባንክና የአካባቢ የልማት ባንኮች የኋላቀር አገሮችን የክፍያ ሚዛን ማስተካከል ስለአለባቸው ከአዳዲስ ችግሮች ጋር በመፋጠጥ ላይ ናቸው። በአበዳሪና በተበዳሪ መካከል ያሉት ግንኙነቶችም በማደግ ላይ ካለው የካፒታሊስቱ የፋይናንስና የገንዘብ አለመረጋጋት ጋር

Digitized by Google

የኋላቀር አገሮች እዳ ሊቋቋሙት የማይችሉት ሸክም ሆኗል



ከፍተኛ የውጭ እዳ ያለባቸው አገሮች

ምንጭ ፡— ካርቱኑና ካርታው «ሳውዝ» (South) ከተሰኘ በእንግሊዝ አገር ከሚታተም መጽሔት የተገኙ ናቸው ።

Digitized by Google

የተቆራኙ ስለሆኑ ብድር በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጫወተው ከፍተኛ ሚና ወደፊትም እንደሚቀጥል አያጠራጥርም ።

በአሁኑ ወቅት በመንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም የገንዘብ ግንኙነት ውስጥ የግያጿርጥ የዋጋ መናር ፣ የገንዘብ ዋጋ መቀነስ፣ የወለድ መጠን ግደግ ፣ የመንግሥት ፋይናንስ ቀውስና አለመረጋጋት ባህርያትን የሚያንፀባርቅ ሆኖአል ። እነዚህም ግንኙነቶች በኢኮኖሚ እድገት በመዋዕለ ንዋይ እንቅስቃሴ በአጠቃላይ በምርት ዕርባታና በካፒታል አጠቃቀም ላይ ያላቸው ቀጥተኛ ተፅዕኖ እየጨመረ የመጣውም ለዚሁ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በካፒታሊስቱ ዓለም የኢኮኖሚ ግንኙነት ላይ በደረሰው ከፍተኛ ቀውስ ሳቢያ የአንዳንድ ኩባንያዎችና ባንኮች ላይ መዘጋትን ያስከተለ ሲሆን በገንዘብ ግንኙነትና በብድር አሰጣጥም በኩል ያለውን አለመረጋጋትም አባብሶታል ። በተጨማሪም በመዋዕለ ንዋይ ሥራና በገንዘብ ካፒታል እንቅስቃሴ አግካኝነት ከፍተኛ ትርፍ ለማጋበስ ሲባል በሞኖፖሎች መካከል የሚደረገው ፉክክር በዓለም አቀፍ የብድር አሰጣጥ መልክና ዘይቤ ላይ ያተኮረ ቢሆንም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሰው ፋይናንስም ሆነ የብድር አሰጣጡ መልክና ዘዴ በመንግሥታዊ ሞኖፖል ቁጥጥርና ተፅዕኖ ሥር የዋለ ነው ።

በግደግ ላይ ያለው የባንክ ዕዳ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የኋላ ቀር አገሮች የክፍያ ሚዛን ጉድለት በአብዛኛው የተስካከለው በግል የባንክ ሞኖፖሎች አግካይነት ነበር ። በ1981 ኋላቀር አገሮች ከነበረባቸው የ500 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ዕዳ ውስጥ 250 ቢሊዮን ግለት 50 በመቶው የግል ባንኮች ኅብረት (ኮንሰርን) መብት ሲሆን በ1971 የግል የባንኮች ኅብረት የነበራቸው ድርሻ ግን 25 በመቶ ብቻ ነበር ።[9] የአውሮፓ ገበያ በተለይም የአውሮፓ የክሬዲት ገበያ (Eurocredit Market) ኋላቀር አገሮች ከባንክ ለሚያገኙት ብድር መሠረታዊ ምንጭ እየሆነ መጥቷል ። ይህ ዓይነቱ ብድር በ1981 44.7 ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን ከ1978 ወዲህ በእጥፍ አድጎና በ1971 ከነበረው ብድር ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 32 ጊዜ ከፍ ብሎ ይታያል ።

ከዓለም አቀፍ የግል ሞኖፖል ክሬዲት ገበያ ከተደረገው የብድር ስምምነት ውስጥ 70 በመቶውን ብድር የወሰዱት 9 ኋላቀር አገሮች ብቻ ሲሆኑ እነዚህም ብራዚል ፣ ሜክሲኮ ፣ አርጀንቲና ፣ ቬንዝዌላ ፣ ኢንዶኔሺያ ፣ ፊሊፒንስና ደቡብ ኮሪያን ይጨምራሉ ። እነዚሁ አገሮች ኋላቀር አገሮች ካለባቸው ጠቅላላ የክፍያ ሚዛን መዛባት 2/3 ኛውን እንዲሁም ከአፍሪካ፣ከእስያና ከላቲን አሜሪካ ኋላቀር አገሮች ጠቅላላ የውጭ ዕዳ ግግሹን የተሸከሙ ናቸው ። በ1980 እና በ1981 ሜክሲኮ ብራዚሊና አርጀንቲና ብቻ የአውሮፓ የክሬዲት ገበያ ከሰጠው ጠቅላላ ብድር ውስጥ ከ1/3 በላይ የሚሆነውን ወስደው ነበር ይህም ከፍተኛ ዕዳ የእነዚህን አገሮች የዕዳ መክፈል ችሎታ (Debt Service Ratio) ዝቅ እንዲል አድርጓል ። ግለትም በአንድ በኩል በዓመታዊ የዕዳ ክፍያ ና ወለድ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ንግድ መጠን መካከል መዛባትን አስከትሏል ።

ስለዚህም በ1979 8% በመቶ የነበረው የኋላቀር አገሮች አግካኝ ዕዳ የመክፈል ችሎታ በ1980 ወደ 22 በመቶ ከፍ ለግለት ችሎአል ።[10] በ1981 ከነበረው የ40 በመቶ አግካኝ የመክፈል ችሎታ ውስጥ የላቲን አሜሪካ አገሮች ኋላቀር አገሮች የበለጠ ድርሻ ነበራቸው ። በዚሁ መሠረት በግል የሞኖፖል ባንኮች ወደውጭ የሚላከው አብዛኛው የብድር ካፒታል የሚዳረሰው ለጥቂት አገሮች ሲሆን እነዚህም አገሮች መግቢያ አገሮች ተብለው የሚጠሩና የመንግሥት ሁለገብ ብድር ተቀዳሚ ተጠቃሚዎችም ናቸው። ወደ ኋላቀር አገሮች በመጉረፍ ላይ ያለው የአውሮፓ ክሬዲትም (Eurocredit)

Digitized by Google

በባንኮች ኅብረትና (ኮንሰርን) በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የቅርብ ትብብር የታገዘ ነው። ተበዳሪ አገሮች ለበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ጠቃሚ የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች በመሆናቸውና በኋላቀር አገሮች ውስጥ የድንበር ዘለል ኩባንያዎች ቅርንጫፎች በመመስረታቸው ለዚህ ትብብር መስፋፋት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል። በተጨማሪም ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በኋላቀር አገሮች ውስጥ የፖለቲካና ወታደራዊ ጥቅም እንዳላቸውም ይታወቃል።

በኋላቀር አገሮች ውስጥ የተመሰረቱት ወይንም የተቋቋሙት የውጭ ባንኮች ቅርንጫፎች ለባለ ብዙ ብሔር ኩባንያዎች ጥቅም የሚውል ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ የገንዘብ ካፒታል ከፍ እንዲል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በተባበሩት መንግሥታት ስታትስቲካዊ መረጃ መሠረት ዓለም አቀፍ ባንኮች በታዳጊ አገሮች ውስጥ ያሏቸው ቅርንጫፎች ቁጥር በ1971 ፥ 968 ሲሆን በ1978 ግን ወደ 1573 ከፍ ብሎአል። [11] ከእነዚህም መካከል አብዛኞቹ የሚገኙት በላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ ነው። በዚሁ መሠረት በብራዚል ብቻ ከ160 በላይ የዓለም አቀፍ ባንኮች ቅርንጫፍ ሲኖሩ ከ50 በላይ የሆኑት ደግሞ በአርጀንቲና በቬንዝዌላና በሜክሲኮ ውስጥ ይገኛሉ።

የአሜሪካ ባንኮችና የጃፓን የገንዘብ ካፒታል የበላይነት ቦታ የያዙበት የደቡብ እስያና የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ማኅበር ASEAN አባል አገሮች ለዓለምአቀፍ ባንኮች ጠቃሚ የሥራ መናኸሪያ ሆነዋል። [12] ከ1970ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮም የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በዚህ አካባቢ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ናቸው።

በታዳጊ አገሮች ውስጥ በመሥራት ላይ የሚገኙት ባንኮች የምርት ተቋሞችን ለመመሥረት የፋይናንስ ድጋፍ ከመስጠታቸውና ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ከመሸጠታቸውም ሌላ ከየሀገሩ የተለያዩ ሁኔታዎች ጋር በሚስማማ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ለገጠማቸው አገሮች የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ከሚጠይቁት በላይ ከፍተኛ ወለድ በማስከፈል ብድር ይሰጣሉ።

ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ የሚሠሩት ለከፍተኛ ትርፍ ሲሆን በእነዚህ አገሮች ሕይወት ውስጥ ወሳኝ የሆነ ሚና ይጫወታሉ። የታዳጊ አገሮች የኢንዱስትሪ ዕድገት ሂደት አሠራር ከዓለም አቀፍ የግል ሞኖፖል ባንኮች በተገኙ ገንዘብ የሚንቀሳቀስ ሲሆን የካፒታል አጠቃቀሙም የዓለም የገንዘብ ካፒታል በሚከተለው የዘረፋ እስትራቴጂ (Ripoff Strategy) መሠረት የሚከናወን ነው። ለብዙ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያለው የንግድ ሥራ በጣም ጠቃሚ እየሆነ መጥቷል። ከነዚህ አገሮች ጋር በመገበያየት የሚያገኙት ትርፍ በጠቅላላው ከሚያገኙት ትርፍ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ስለዚህም የተበዳሪ አገሮች የኢኮኖሚ « ዕድገት » ለድንበር ዘለል ኩባንያዎች «የሞትና የሕይወት » ጉዳይ ይሆናል። [14]

ለታዳጊ አገሮች ከሚሰጠው ጠቅላላ የኤውሮጳ ክሬዲት 1/3 ኛው የሚገኘው ከአሜሪካ ከፍተኛ ባንኮች ሲሆን ይኸም ዋና ዋናዎቹ የአሜሪካ ባንኮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚሠሩበት ክሬዲት ከ20 እስከ 40 በመቶ ይሆናል። ሜክሲኮ ብቻ እንኳን ከ30 እስከ 35 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ የአሜሪካ ባንኮች ዕዳ አለባት። ዘጠኝ የአሜሪካ ትላልቅ ባንኮች በአንድነት 12 ቢሊዮን ዶላር ሜክሲኮ ውስጥ ሥራ ላይ አውለዋል። ከነዚህም ውስጥ በተለይ አሜሪካ ባንክ ተብሎ የሚጠራው ብቻውን የ3 ቢሊዮን ዶላር ድርሻ አለው። [15]

መጠነኛ የኢንዱስትሪ እድገት ወደአላቸው ጥቂት አገሮች የሚላከው ከፍተኛ የብድር ካፒታል በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት የሥራ ክፍፍል ሥርዓት ውስጥ የተከሰተ

Digitized by Google

ውና እያደር በመባባስ ላይ ያለው መዛባት ያስከተለው የገንዘብና የፋይናንስ ቀውስ ነው ። በዓለም አቀፍ ክሬዲት አማካይነት የኢንዱስትሪን ዕድገት የማፋጠን ሂደት ከኋላ ቀር አገሮች የኢኮኖሚ እድገት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ሳይሆን በእነዚህ አገሮች ውስጥ ከሚሠራው ከሞኖፖል ካፒታልና ከተወሰኑ የብሔራዊ የቡርዧው ኃይሎች ፍላጎትና ጥቅም ጋር የተቆራኘ ነው ። ታዳጊ ሀገሮች ከውጭ ክሬዲት ምንጮች የሚያገኙት ብድር የኢኮኖሚ መዋቅራቸውን እያዳከመ በመሔድ ላይ ነው ። ምክንያቱም እነዚህ አገሮች ወደ በለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች የሚልኳቸው ጥሬ ዕቃዎች በአነስተኛ ዋጋ በሚሸጡ ጥቂት የተዘጋጁና (finished) በከፊል የተዘጋጁ (semi-finished) ምርቶች ላይ በማተኮራቸው የውጭ ዕዳቸው በምንም ዓይነት ሊቀንስ አልቻለም ።

በኋላ ቀር አገሮችና በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች መካከል በማደግ ላይ ባለው ኢኮኖሚያዊ ተደጋጋፊነት (economic interdependence) ሳቢያ የኋላ ቀር አገሮች ወደ ውጪ የሚልኩት ዕቃ መጠን በጨመረ ቁጥር የዕዳቸውም መጠን በአንፃሩ እየጨመረ በመሔድ ላይ ይገኛል።ለዚህም ከሚሰጡት መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ውስጥ በቀጥታ ባቋሉት መዋዕለ ንዋይ አማካይነት የሚያገኙትን ከፍተኛ ትርፍ ወደ ሀገራቸው ማሸጋገራቸው ሲሆን የታዳጊ ሀገሮች የወጪ ምርቶች በዝቅተኛ የቴክኖሎጂ መገልገያዎች የተዘጋጁ (in-house processed) መሆናቸውና በትክክለኛ ዋጋ ያለመሸጣቸው ሌላው ምክንያት ነው ። ኋላቀር አገሮች በዚህ መንገድ የሚያወጡት ሀብትከምታቸውንም ከማዳከሙም ሌላ የተፋጠነ የምርት ዕርባታ ዕድገትም እንዲገታ ያደርጋል ። ስለዚህ አሁንም ቢሆን አያሌ ኋላ ቀር አገሮች በፋይናንስ ካፒታል ላይ ያላቸው ጥገኝነት እያደገ በመሄድ ላይ ነው ።

እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በታዳጊ አገሮች ውስጥ የካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ሥር እንዲሰድ ፤ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተውን የካፒታሊስቱን ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ሥርዓት ለማጠናከር ፣ ኋላቀር የሆኑ ማኅበራዊ መዋቅሮችን እንዳሉ ለማቆየትና በታዳጊ አገሮችና በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚያዊ ክፍፍልና ልዩነት ይበልጥ ለማስፋን እንዲችሉ አመች ሁኔታዎችን ፈጥሮላቸዋል ።

አብዛኛዎቹ ኋላቀር አገሮች ክሬዲት የማግኘት ዕድል የሏቸውም

ከጠቅላላ ኋላቀር አገሮች መካከል 2/3ኛ ያህል የሚጠጉት ከግል የሞኖፖል ክሬዲት ምንጮች ብድር ለማግኘት አይችሉም።በዚህ የተነሳም አብዛኛውን ብድር የሚያገኙት ከልማት እርዳታ (Development) መልክ እና ከዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ሞኖፖሎች ነው ። ይሁን እንጂ ከ1970 ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮ እነዚህ አገሮች ከአውሮፓ የክሬዲት ገበያ ብድር መውሰድ ገድ ሆኖባቸዋል ። ለዚሁም መክፈል ያለባቸውም ወለድ ከሌሎች ምንጮች ለሚያገኙት ብድር ከሚከፍሉት ወለድ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ ነው ። ኋላቀር አገሮች በ1979:58 የዚህ ዓይነት ብድሮችን የወሰዱ ሲሆን ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታትግን የዚህ ዓይነቱ ብድር ቁጥርም ሆነ የወለድ ከፍያ መጣኔ እየቀነሰ መጥቷል ። ለዚህም ዋናው ምክንያት አሜሪካ የምትከተለው ከፍተኛ የወለድ ምጣኔ ፖሊስ የሚጠይቀውን ሸክም ኋላቀር አገሮች ሊቋቋሙ ያለመቻላቸው ነው ። በ1979:12% የነበረው የአውሮፓ የገንዘብ (Euro money) እና የአውሮፓ የክሬዲት (Euro credit) ገበያ አማካኝ የወለድ ከፍያ መጣኔ 1981 / 82% ወደ 17 እና 20% መካከል ከፍ ብሏል። እንዲሁም የብድር ስምምነቶች በየጊዜው

Digitized by Google

በሚከሰቱ አዳዲስ የገበያ ሁኔታዎች መሠረት በየስድስት ወሩ የሚታደሱ ሲሆን ይህም ቀደም ሲል ለተወሰዱ ብድሮችም ሆኑ ለአዲስ ብድሮች የሚከፈለው የወለድ መጠን እየናረ መሄዱን ያመለክታል ። በተጨማሪም ከአጠቃላይ የዕዳ ክፍያ ጋር ሲመጣጠን የአጭር ጊዜ ብድሮች የወለድ ክፍያ በከፍተኛ ፍጥነት ማደጉ የብዙ አዳዲስ ተበዳሪ አገሮችን የዕዳ መክፈል አቅም ባለፉት ጥቂት ዓመትታ እጅግ እያዳከመው መጥቷል ። በአሁኑ ጊዜ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የብድር ስምምነቶች ከ12 ወራት በማይበልጥ አጭር ጊዜ ውስጥ መከፈል ያለባቸው ናቸው ።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ካፒታል እያሌ የአፍሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ኋላቀር አገሮች ብድር ለማግኘት ብቃት እንደሌላቸው ያምናል ። ለዚህም ከሚሰጡት ምክንያቶች መካከል የዘይት ሻጭ አገሮች የገመት ገቢ ከመቀነሱ የተነሳ የድንበር ዘለል ባንኮች ኅብረት (Concerns) የብድር ገንዘብ መቀነሱ ፤ ብዙ ባንኮች ኪሳራ ላይ እንዳይወድቁ ያለው ስጋት ወይም የዓለም ክሬዲት ሥርዓት ሊታወስ ይችላል የሚለው ፍራቻ ይገኙባቸዋል ። በማያቋርጥ የኢኮኖሚ ዝቅጠት የተነካ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ለከፍተኛ ችግር ተጋልጦአል ። ከአንድ ዓመት ወዲህ ብዙ አነስተኛና ከፍተኛ ዕዳ ያለባቸው አገሮች ዕዳቸውን በጭራሽ ለመክፈል ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። በዚህ የተነሳም ዓለም አቀፍ የግል ባንክ ሞኖፖሊዎች ሊደርስባቸው የሚችለውን ያልተከፈለ ክሬዲት ኪሳራ ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ አይደሉም ። ። 16

ያም ሆነ ይህ ሀቁ ለዚህ ሁሉ መንስኤው እንደሚባለው ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት አለመሆኑ ነው ። በ1970ዎቹ ዓመታት ውስጥ የአውሮፓ የገንዘብ ገበያ ያለቅጥ መስፋፋት የሚያደርገውም የሚያረጋግጠውም ከዚህ ሁኔታ መኖሩን ነው ። ለምሳሌ የአውሮፓ የገንዘብ ገበያ የተጣራ የገንዘብ መጠን በ1970 እና በ 1981 መካከል ከ10 እጥፍ በላይ አድጓል ። ካባንኮች በውጭ የሚያንቀሳቅሱት ገንዘብ መጠንም ቢሆን በ1979 ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ቲሪሊዮን ዶላር በላይ የደረሰ ሲሆን ይኸ ገንዘብ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ካላቸው ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ በ3 እጅ ይበልጣል ።

በአውሮፓ ገበያ ውስጥ የገንዘብ ካፒታል ያለቅጥ መከማቸት የገንዘብ ዋጋ እየቀነሰ መሄዱን ያንፀባርቃል ። እንዲህ ዓይነቱ የማያቋርጥ የተረፈ ገንዘብ መጠራቀም ደግሞ ገንዘቡን በማያቋርጥ ሁኔታ በሥራ ላይ ማዋልን የግድ ያደርገዋል ። በአውሮፓ ገበያ ውስጥ እጅግ የተስፋፋ ው የባንክ ሞኖፖሎች እንቅስቃሴም የገንዘብ ካፒታልን ዝውውር ከፍ አድርጎታል ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓለም አቀፍ ባንኮችና ድርጅቶች ይሰሩበት የነበረው የተስፋፋ የገንዘብ ክምችት የካፒታሊስቱ የገንዘብና የፋይናንስ ግንኙነት ውስጥ የማያቋርጥ አለመረጋጋትን ከመፍጠሩም ሌላ አብዛኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሀብት በጥቂት ዋና ዋና የባንክና የፋይናንስ ሞኖፖሊስቶች እጅ እንዲገባ በማድረጉ ከፍተኛ የመዋዕለ ንዋይ ትርፍ እንዲያጋብሱ የተለያየ ዕድሎችን ፈጥርላቸዋል ። በ1981 ብቻ በአውሮፓ የክሬዲት ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ ቢያዙ አምስት የአሜሪካ ባንኮች የሚመሩና 131 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ የብድር ካፒታል ያላቸው 20 ዓለም ኣቀፍ የባንክ ሞኖፖሎች ነበሩ ።

በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ የፋይናንስና ምንጮች ላይ ያለው ጥገኝነት በብሔራዊ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየጨመረ በመምጣት ላይ ይገኛል ። ይህም የጥገኝነት መጨመር ሞኖፖሊዎቹ በሚከተሉት የትርፍ ማግኛ ስትራቴጂ ላይ ወሳኝ የሆነ ተፅዕና አስከትሏል ። ለምሳሌ በ1981 የአሜሪካ ሞኖፖሊ ድርጅቶች ብቻ ከአውሮፓ ገበያ የ54 ቢሊዮን ዶላር ብድር የወሰዱ ሲሆን ሲሆን በ1980 ከወሰዱት ብድር በ10 እጅ

Digitized by Google

ከፍ ከማለቱም ሌላ 127 ኋላ ቀር አገሮች በአንድነት ከወሰዱት (አጠቃላይ 44.7 ቢሊዮን ዶላር) ብድር ጋር ሲነፃፀር በ10 ቢሊዮን ዶላር ያህል ይበልጣል ። በሞርጋን ጋራንቲ ትራስት ኩባንያ "Morgan Guaranty Trust Co." አሀዛዊ መረጃ መሰረት ፣ ከብድሩ ሰማንያ በመቶውን (80%) በአሜሪካ ውስጥ ኩባንያዎችን በማዋሀድና በመግዛት ሥራ ላይ አውለውታል ።[17]

ይህም እንደሚያመለክተው ዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ፋይናንስ ሥርዓት ዋነኛው ችግር ትርፍ ለማግኘት ሲባል አንፃራዊ የትርፍ ገንዘብ ክምችትን በተዛባ ሁኔታ ማከፋፈሉ ነው ። በየጊዜው እየጨመረ በመሔድ ላይ የሚገኘው በአጭር ጊዜ የሚከናወነውንና በትርፍ ላይ ያተኮረ የገንዘብ ካፒታል ልውውጥ ከላይ የተጠቀሰውን መዛባት ከማባባሱም ሌላ በተለይም ኋላቀር አገሮች መክፈል ያለባቸውን የወለድ መጠን የናረ ያደርገዋል ። በአንፃሩም የብድር ካቲፒታልን መጠን ይቀንስባቸዋል ።

በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ ባለው ውጥረትና ይህም ሊያስከትል ከሚችለው የፋይናንስ ኪሳራ የተነሳ ካፒታሊስት መንግሥታትና የባንክ ሞኖፖሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የብድር አሰጣጥ ዘይቤ በማናቸውም ሁኔታ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት አሏቸው ። በየውጭ ዕዳ ኋላ ቀር አገሮችንም ሆነ በኢንዱስትሪ የዳበሩትን አገሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ችግር ውስጥ ጥሏቸዋል ። ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ያላቸውን የገንዘብ ሀብት የሚያሟጥጡት ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ በሚናገሩበትና ለባለዕዳ አገሮች አስፈላጊ ብድር የሚሰጥበት ሌላ አማራጭ መንገድ መፈለግ አለበት በሚሉበት በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱ ወገን በራሱ ላይ የደረሰውን ቀውስ ሊያስወግድ የሚችለው ያለበት ዕዳ ለሌሎች በመክፈል ብቻ በመሆኑ ገራ የሚያጋባ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም ።[18]

ሆኖም በዚህ ሂደት ውስጥ የካፒታሊስቱ ፋይናንስና የክሬዲት ሥርዓት የሚከተሉት ቅራኔዎች ውስጥ ገብቷል ። በኋላቀር አገሮች ውስጥ ያሏቸውን የትርፍ ምንጭ ለመጠበቅ ባንኮች ወደውጭ የሚልኩትን የብድር ካፒታል ማሳደግ አለባቸው ። ሆኖም የዓለም አቀፍ የግል ባንኮች እርስ በእርስ የተሳሰሩ በመሆናቸው የውጭ ካፒታላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው ። ስለዚህ ብዙ ከፍተኛ ዕዳ ያለባቸው አገሮች በአንድ ወቅት ዕዳቸውን ለመክፈል ካልቻሉ እንደሰንሰለት የተያያዙት ባንኮች በአንድነት ወደ ውድቀት ሊያመሩ ይችላሉ ። ስለዚህም ጊዜያዊ የዕዳ ችግርችን ለማቃለል የሚቻለው የኢምፔሪያሊዝምን ውስጣዊ ቅራኔዎች በማግባባስ ብቻ ሲሆን ፣ ለዚህም ዋነኛው ኢምፔሪያሊዝም በኋላቀር አገሮች ላይ የሚያካሂደው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ብዝበዛና ቀደም ሲል የተጠቀሱት ቅራኔዎች ናቸው ። ባንኮች በክሬዲት የሚያጋጥማቸውን ችግር ወደ ሁለገብ መንግሥታዊ ሞኖፖል የገንዘብ ድርጅቶች በተለይም ወደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ (World Bank) ለማስተላለፍ ያላቸው አዝማሚያም ይህን ሁኔታ በግልጽ ያመለክታል ።

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) እና የዓለም ባንክ አዳዲስ ችግሮች እየገጠሟቸው ነው

ኋላ ቀር አገሮች ከሚገኙበት አሳሳቢ የፋይናንስ ሁኔታ ለመውጣት ባደረጉት ግፊት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የማበደር ተግባራቸውን እንዲያስፋፉ ተገደዋል ። ከ1970ዎቹ ዓመታት አጋማሽ ጀምሮ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለክፍያ ሚዛን ጉድለት ማካካሻ ልዩ ብድሮችን መድቧል ። በዚሁ መሠረት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች በ1981 ለሰጠው ክሬዲት ወደ 7.5 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ያለ ሲሆን ይህንን ያህል ብድር ከዚህ ቀደም ሰጥቶ አያ

Digitized by Google

ውትም ። ክሬዲቱም ሙሉ በሙሉ ለኋላ ቀር አገሮች ሲሰጥ ይህ የመጀመሪያው ነው ።

የብድር ተፅዕኖ እየጨመረ መሔድ

ሁለገብ የፋይናንስ ተቋሞች በተቻላቸው መጠን ለኋላቀር አገሮች ብድር የመስጠት ተግባራቸውን እንዲያጠናክሩ የካፒታሊስቱ የፋይናንስ ዓለም ተደጋጋሚ ጥሪ እያደረገ ነው ። ዕዳቸውን መክፈል ያቃታቸውና ኋላቀር አገሮች ከችግራቸው ለመውጣት እራሳቸው የመረጡትን እርምጃ እንዲወስዱና በግይቀር የዕዳ ክፍያ ችግር ውስጥ የገቡት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሊያበረታታቸውና ራሳቸውን መልሰው እንዲያቋቁሙ መቀነታቸውን ሸብ አድርገው እንዲገቡ ለማበረታታት ባለ ኃይሉ ሁሉ እነዚህ አገሮች ላይ ሊያተኩር ተገዷል ። ይህንንም ለመፈጸም ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሌላ የተሻለ አበዳሪ ተቋም የለም ። [19]

ኋላቀር አገሮች የክፍያ ሚዛናቸውን ለማስተካከል ተጨማሪ ብድር በሚጠይቁበት ወቅት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚያስገባቸው ውሎች በዓለም አቀፍ የፋይናንስና የክሬዲት ሥርዓት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና እያደገ እንዲሄድ አድርጎታል። ለምሳሌ የማረጋጋት ፕሮግራም (Stabilization Programmes) ተብሎ በሚሠራው አሠራር መሠረት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መንግሥታት ለፍጆታ ዕቃዎች ለምግብና ለማኅበራዊ አገልግሎት የሚያደርጉትን ድጎማ እንዲሠርዙ (ብዙውን ጊዜ ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቁ ስለሆነ) የምንዳ ጭማሪ ጣራ እንዲወስኑ ፣ በኢንዱስትሪ ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ለሚገቡ ዕቃዎች ገበያ እንዲከፍቱ ፣ (የገቢ ንግድን ነፃ እንዲያደርጉ) የግል ክፍለ ኢኮኖሚን እንዲያበረታቱና ለውጭ ሞኖፖሊ መዋዕለ ንዋይ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጥሩ ግዴታ ሊያስገባቸው ይችላል ። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ፔሩ ፣ ግብፅ ፣ ሜክሲኮ ፣ ዛየር ፣ ሱዳን፣ ኢንዶኔዥያ ፣ ጃማይካና ሌሎችም አገሮች እነዚህን የመሳሰሉ ግዴታዎች ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል ። [20]

በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ የዓለም ባንክ የሰጠው የብድር መጠንም እንዲሁ ከፍተኛ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ የዓለም ባንክ ቅርንጫፍ የሆነው ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር (International Development Association) አብሮ ከተወሰደ የዓለም ባንክ በዓለም ውስጥ ከፍተኛው የመንግሥታዊ ሞኖፖል አበዳሪ ድርጅት ነው ። ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር (IDA) በጣም ድሀ ለሆኑ ኋላቀር አገሮች እስከ 50 ዓመታት የሚቆይ ከወለድ ነፃ የሆነ ብድር ይሰጣል ። በ1985 የዓለም ባንክ ያደረገው የ12 ቢሊዮን ዶላር የቅድሚያ የብድር ውል በ1974 ካደረገው የብድር ውል ጋር ሲነጻጸር በ3 እጅ ከፍ ይላል ።

ይህም ሆኖ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የሰጡት ብድር ኋላቀር አገሮች ከአውሮፓ ገበያ ከወሰዱት ብድር ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው ። ለምሳሌ በ1974 እና በ1981 መካከል ዘይት ሻጭ ያልሆኑ ኋላቀር አገሮች የክፍያ ሚዛናቸውን ጉድለት ለማካካስ ከወሰዱት ብድር ውስጥ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ያገኙት አራት በመቶውን ብቻ ነበር ።

የዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ አቋምና እንቅስቃሴ አዲስ መልክ መያዙን የሚያመለክተው የካፒታሊስቱ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት የሚሰጠው የብድር መጠን ሳይሆን ዋነኛው ጉዳይ እንደመንግሥታዊ ሞኖፖል የዓለም አቀፍ የክሬዲት ሀብት አቀናጅና ተቆጣጣሪ ማዕከል በመሆን በሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና ሳቢያ የመነጨው የዓይነት ለውጥ ነው ።

በቅርቡ ባንግላዴሽ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የ217 ቢሊዮን ዶላር ብድር ስትወስድ የገንዘቧን ዋጋ ዝቅ ለማድረግ ፣ ቀረጦችን ለመጨመርና ለውጭ ካፒታሊስቶች መዋዕለ ንዋይ እንቅስቃሴ የተሻለ

Digitized by Google

ሁኔታ ለመፍጠር ግዴታ እንድትገባ ተደርጓል ። ለሕንድ የተሰጠው የ5.8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድርም እንዲሁ ከተወሰኑ ግዴታዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን በዚሁ መሠረት ሕንድ በግል ካፒታል መስፋፋት ላይ የተጣሉትን እገዳዎች እንድታነሣና የገቢ ንግድን ነፃ ለመልቀቅ ግዴታ ገብታለች ። የነዚህ ሁሉ ግዴታዎች ዋነኛ ዓላማም የግል ኢኮኖሚ ዘርፍና የዓለም አቀፍ የሞኖፖል ካፒታልን ተፅዕኖ፤ ማጠናከር ነው ።[21] ዚምባብዌም ብትሆን ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የመካከለኛ ጊዜ ብድር የተሰጣት የዚምባብዌ መንግሥት ለምግብ ሸቀጥ አምራቾች የሚያደርገውን ድጐማ እንዲያነሣ ግዴታ ከገባ በኋላ ነው ።[22]

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ቀደም ሲል የገባውን ቃል በመጣስ ለ15 የድርጅቱ አባል አገሮች ብድር መስጠቱን አቁሟል ። ከእነዚህም መካከል ባንግላዴሽ ፣ ኮስታሪካ ፣ ጉያና ፣ ዛምቢያና ታንዛኒያ ይገኙበታል ። የተከለከለውም የብድር መጠን 5 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ፣ ይህም ከዚህ ቀደም ድርጅቱ ከሰጠው ብድር የላቀና ለ1982 ከደረጋቸው የቅድሚያ የብድር ስምምነቶች 25 በመቶውን የያዘ ነበር ። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንደሚለው ከሆነ እነዚህ አገሮች የተጠየቀውን የማስተካከያ መመዘኛ (Adjestment Criteria) ለማሟላት ተስኖአቸው ነበር ።[23]

የተለያዩ የኮሚኒስትና የሠራተኞች ፓርቲዎች ተወካዮች የሚገኙበት አንድ ዓለም አቀፋዊ የጥናት ቡድን ይህን ተግባር መርምሮ ባቀረበው ሪፖርት የካፒታሊስቱን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የፋይናንስ ሥርዓት ሁኔታ ሲገልጽ ፣ « ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለአድኃሪና ለፀረ—ሕዝብ መንግሥታት የሚሰጠውን የገንዘብ ዕርዳታ ሲያስፋፋ ፣ በእንፃሩ ደግሞ ነፃና ተራማጅ የሆነ የእድገት ፈለግ ለመከተል ለሚሞክሩ አገሮች በሚያመቻቸው ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ብድር እንዳይሰጣቸው ያደርጋሉ ።»[24] ብሏል ።

ኋላ ቀር አገሮች አንድ የተወሰነ መንገድ ብቻ ተከትለው የኢኮኖሚ ግንባታ (Econmic Rehabilitation) እንዲያካሂዱ የሚደረገባቸው ግፊት የነዚህ አገሮች የኢኮኖሚ ችግር በቅድሚያ ከኢኮኖሚ መዋቅራቸው መዛባት የሚመነጭ በመሆኑ ለ«ሦስተኛ ዓለም» አገሮች የኢኮኖሚ ችግር መፍትሔ ሊሆን እንደማይችል የቡርዧዋ የኢኮኖሚ ሊቃውንት እንኳ ሳይቀሩ አምነዋል ። አብዛኞዎቹ ኋላቀር አገሮች በነፃ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩና በምዕራብ አገሮች የሚገኘውን የካፒታሊስት ሥርዓት የተከተሉ እያሌ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ተገደዋል ። አብዛኞዎቹም የአዳዲስ የገንዘብ ሥርዓት መመሪያዎች (Monetarist Formula) መፈተኛ ተደርገዋል ። የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የሚሠሩባቸው የማረጋጊያና ሥርዓት ማስያዣ (Stabilization and disciplining) ፕሮግራሞች የተበዳሪ አገሮችን የኢኮኖሚ መዋቅር መዛባት (ቀውስ) ችግር ለማቃለል አይረዱም ። ምክንያቱም ተቀዳሚ ዓላማቸው እነዚህ አገሮች እንደነባራዊ ሁኔታቸው የምርት ኃይሎቻቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት አይደለም ።[25] ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በ1982 እራሱ የሚከተለው የብድር ፖሊሲ በ23 አገሮች ያስከተለውን ውጤት ከመረመረ በኋላ ፤ «አነስተኛ ውጤት» ያሳየ መሆኑን በይፋ ያመለክታል ።

በዚህም መሠረት የንግድና የክፍያ ሚዛን መሻሻል የታየው ከነዚህ አገሮች በግማሾቹ ብቻ ሲሆን ፤ ከነዚህም አነስተኛም ቢሆን እንኳ የዋጋ መቀነስ የታየው በ12 አገሮች ብቻ ነበር ።[26]

የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት የዓለም ባንክና የባንክ ሞኖፖሊስቶች ኅብረት

እያሌ የግል ባንኮች ለኋላቀር አገሮች ብድር የሚሰጡት በዓለም አቀፍ የገንዘብ

Digitized by Google

ድርጅቶች ውልና ደንብ መሠረት መሆኑ
እያደር መጨመሩ ዓለም አቀፍ የገንዘብ
ድርጅት የዓለም የገንዘብ ካፒታል መቆጣ
ጠሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን የሚጫ
ወተው ሚና ግዴትን በግልጽ ያመለክ
ታል ። [27]

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የብ
ድር ስምምነት የማደስ (Refunding
Negotiations) ሚና እያደር እየጐላ በመ
ሔድ ላይ ነው ። ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድር
ጅት በ1981 ለዛየር ብድር ለመስጠት
የገባውን ውል አገሪቱ ድርጅቱ የጠየቀ
ውን ሁኔታ ለማሟላት ባለመቻሏ ውሉን
ሠርዟል ። ከዚሁ በማከታተልም አበዳሪ
ባንኮች ለዛየር ብድር ለመስጠት ቀደም ሲል
ገብተው የነበረውን ውል ሠርዘዋል ። ሜክ
ሲኮን በሚመለከት ደግሞ የባንክ ሞኖፖ
ሊዎቹ አዲስ ብድር ለመስጠት ፈቃ
ደኛ የሆኑት አገሪቱ ከዓለም አቀፍ ድርጅት
ጋር የማረጋጊያ ፕሮግራም ስምምነት ከተ
ፈራረመች በኋላ ነበር ።

የዓለም ባንክ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ለኋ
ላቀር አገሮች የሚደረገውን ብድር ለማስ
ፋፋት ከንግድ ባንኮች ጋር ለመተባበር
ሙከራ አድርጓል ። የትብብሩም ትኩረት
« በሦስተኛ ዓለም » አገሮች ውስጥ የግል
የመዋዕለ ንዋይ ፕሮጀክቶችን በመገንባት
ላይ ነው ። በ1982 ካንዳ ፣ ቫንኩቨር ከተ
ማ ተደርጎ በነበረው ዓለም አቀፍ የገንዘብ
ጉባኤ ላይ የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ኤ-
ክላውንስን ንግግር ሲያደርጉ እንዲህ ብለው
ነበር ፣ « በዓለም ደረጃ በሰፊው የሚሠ
ሩት የንግድ ባንኮች የኋላቀር አገሮች ዋነኛ
አበዳሪዎች ናቸው ። የዓለም ባንክም ሁለት
መሠረታዊ ዓላማዎች (ማለትም ፕሮጀ
ዎችን ፋይናንስ ማድረግና የፖለቲካ ድር
ድር ማካሄድ) በተለይ በኋላቀር አገሮች
የግል ባንኮች መዋዕለ ንዋይን በሥራ
ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆነውን የረጅም
ጊዜ የተረጋጋ ሁኔታ ለማስገኘትና ለዚ
ህም አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የታ
ቀዱ ናቸው ። [28]

ከ1980ዎቹ ዓመታት ወዲህ ዓለም
አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከሚሰጠው ጠቅ
ላላ ብድር ሁሉ ከሌሎች የባንክ ሞኖፖ
ሎች ጋር በመተባበር በጋራ ለኋላ ቀር አገ
ሮች የሚሰጠው ብድር ከፍተኛ መሆኑ
የዚሁ ድርጅት ስትራተጂ ነጸብራቅ ነው ።
እንዲህ ዓይነቱ ብድር በ1975 ፣ 220 ሚሊ
የን ዶላር ብቻ የነበረ ሲሆን ፣ በ1981-
82 ወደ 3.3 ቢሊዮን ከፍ በማለት በአ
ሁኑ ጊዜ ባንኩ በዓመት ለ240 ፕሮጀክቶች
የሚያወጣውን ገንዘብ የሚሸፍን ነው ። [29]

የዓለም ባንክ ሌላው ቅርንጫፍ በሆነው
በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅትና
(International Finance Corporation)
የባንክ ሞኖፖሎች መካከል ያለው ትብብ
ርም እየተጠናከረ ነው ። የዓለም አቀፍ የፋይ
ናንስ ድርጅት ሙሉ በሙሉ በኋላ ቀር አገ
ሮች የግል መዋዕለ ንዋይን በገንዘብ በማ
ጠናከርና በማበረታታት ሥራ የተሠማራ
ድርጅት ነው ። [30] ይህ ድርጅት በ1981-
82 612 ሚሊዮን ዶላር በማውጣት በ31
አገሮች ውስጥ በ65 ፕሮጀክቶች ተሳትፏል ።
በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ ድርጅቱ
ከዓለም አቀፍ ባንኮች ጋር በመተባበር
የሥራ እንቅስቃሴውን በእጥፍ የማሳደግ
ዕቅድ አለው ። [31]

በአሁኑ ጊዜ የዓለም ባንክ የግል ባን
ኮች ለኋላቀር አገሮች በሚሰጡት ብድር
ሳቢያ የሚደርስባቸውን ኪሣራ ለመከላ
ከል የሚያስችል አጠቃላይ የባንክ ዋስትና
ሥርዓት በመፍጠር ላይ ይገኛል ። ይህም
እጅግ ቢዘገይ በ1983 መጨረሻ ሥራ
ላይ ይውላል ።

እነዚህ ሁሉ ተግባራት ኢምፔሪያሊዝም
መንግሥታዊ ሞኖፖልንና የግል ሞኖፖል
ካፒታልን በተሻለ መንገድ በማቀናጀት
በኋላ ቀር አገሮች ላይ ያለውን ዓላማ
ከግቡ ለማድረስ የሚያደርገውን ጥረት
የሚያግዙ ናቸው ።

Digitized by Google

የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትም የብድር አሰጣጥ ስልታቸውን ለማመሳሰል የሚያደርጉት ጥረትም ከዚሁ አንፃር የሚታይ ነው። በሁለቱ ተቋሞች መካከል ያለው ትብብር ስለ ተበዳሪዎች የመረጃ(የኢንፎርሜሽን) ልውውጥ ማድረግን፤ የብድር ደንቦችና ውሎችን ማቀናጀትና የብድር አሰጣጥ ተግባርን አንድ ዓይነት መልክ መስጠትን ያጠቃልላል። እንግዲህ የዓለም ባንክ ከ1980 አንስቶ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የመዋቅር ማስተካከያ ብድር (Structural Adjustment Loan) ተብሎ በሚጠራውና ለተወሰኑ ኋላቀር አገሮች በተዘጋጀው የ3 የዓመት የማረጋጋት ፕሮግራም ተጨማሪ በሆነው አሠራር መሠረት ብድር እየሰጠ ነው። እስከ አሁን ስምንት አገሮች ማለትም ሊቢያ፣ ኬንያ፤ ቱርክ፣ ሴኔጋል፣ ፊሊፒንስ፣ መውሪሸስ፤ ማላዊና ጉያና የክፍያ ሚዛናቸውን ያሻሽላል ተብሎ የታቀደውን ይህን ዓይነቱን ብድር ተቀብለዋል። ብድሩ ከምንም ዓይነት ፕሮጄዎች ጋር የተያያዘ ባይሆንም፣ የሚከተሉት ግዴታዎች ግን ከብድሩ ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

—ለግል ድርጅቶች የመዋዕለ ንዋይ እርዳታ ማድረግ

—ለትራፊ ያልሆኑትን መንግሥታዊ ድርጅቶች በፋይናንስ ማጠናከር ወይንም ወደ ግል እንዲዛወሩ ማድረግ

—መንግሥታዊ ለሆኑ ድርጅቶች ብድር መከልከል።

ብዙ ኋላቀር አገሮች እነዚህን ግዴታዎች ሊያሟሉ ባለመቻላቸው የዓለም ባንክ የብድር ክፍያውን አገዷል። ለምሳሌ ያህል ጉያናን መጥቀስ ይቻላል።

በ1980/81 የዘርፍ ማስተካከያ ብድር ወደ717 ሚሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር። ይኸውም በተጠቀሰው ዓመት የዓለም ባንክ ለኋላ ቀር አገሮች ከሰጠው ጠቅላላ ብድር 7 በመቶ ያህል ነው። በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የዚህ ዓይነቱ ብድር 10 በመቶ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል።[32]

ከ1960ዎቹ ጀምሮ ዓለምአቀፍ የዕርዳታ ክበቦች (Aid clubs) በመባል የሚታወቁትና ለ24 ኋላቀር አገሮች (ከእነዚህ 21 አገሮች በዓለም ባንክ ሥር ያሉ ናቸው) ብድር የሚሰጡት ተቋሞች በመንግሥታዊ ሞኖፖል የሚተየሰውን የፋይናንስና የብድር ፖሊሲ በኋላቀር አገሮች ተግባራዊ ማድረጊያ ተጨማሪ መግሪያዎች ናቸው። የእነዚህ የዕርዳታ ክበቦች አባላትም የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ተወካዮች፣ የሚመለከተው የአካባቢ ልማት ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ናቸው። የእነዚህ የዕርዳታ ክበቦች ልዩ ባሕሪ የራሳቸው የገቢ ምንጭ የሌላቸው መሆኑ ነው። ዳሩ ግን መስጠት የሚገባውን አጠቃላይ የብድር መጠንና እያንዳንዱ አባል አገር ምን ያህል ብድር ማግኘት እንዳለበት፤ እንዲሁም ለኋላቀር አገሮች የገንዘብ ዕርዳታ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናሉ። የዓለም ባንክ ሰብሳቢ ባልሆነባቸው የዕርዳታ ክበቦች እንኳ(ለምሳሌ በቱርክ የዕርዳታ ክለብ፣ በኔዘርላንድስ በሚመራው የኢንዶኔዥያ የመንግሥታት ትብብር ቡድን) ውሎችንና ደንቦችን የማርቀቁ ተግባር የሚከናወነው በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በዓለም ባንክ ቁጥጥር ሥር ነው። የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በእነዚህ ክበቦች ውስጥ የሚጫወቱት የመሪነት ሚና የኋላቀር አገሮችን ብሔራዊ ሕልውና በማዳከም የዓለም ባንክንና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን አስተያየትና ውሳኔ እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል።[33]

የካፒታሊስቱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ከፍተኛ ቅራኔና ቀውስ ውስጥ በመውደቁ፣ ብዙ ኋላቀር አገሮች የፋይናንስ ችግር ስለገጠማቸውና ዋናዎቹ የካፒታሊስት አገሮች በእስያ፤ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ አገሮች ላይ

Digitized by Google

የኢኮኖሚ ዛቻና (ማስፈራራት) የፋይናንስ ተፅዕኖ ወደሚያደርጉበት አዲስ ዘመን ተሸጋግረዋል ። በቅርቡ በካናዳ ፤ ቶሮንቶ ከተማ ተደርጎ የነበረው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ዓመታዊ ስብሰባ ለኋላቀር አገሮች የብድር ደንቦች ላላ እንዲሉ ፤ ተጨማሪ የክሬዲት ምንጮች እንዲፈልጉ ፤ በተለይም የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የገንዘብ ክምችት እጥፍ እንዲሆን ማለትም 140 ቢሊዮን ዶላር እንዲደርስና የተለየ ገንዘብ እንዲመደብ ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ከዚሁ አንፃር የሚታይ ነው ።[34]

የእንዲህ ዓይነቱ ተፃራሪ ውሳኔ ተቀዳሚ ምክንያት አሜሪካ በሁለቱ የፋይናንስ ተቋሞች አማካይነት በኋላቀር አገሮች ላይ የምታካሂደው የመቆጣጠር ተፅዕኖ እንዲቀጥል የምታደርገው ሙከራ ነው ። ለምሳሌ የአሜሪካ አስተዳደር ከአንድ ዓመት ቀደም ሲል ለዓለም አቀፍ የልማት ዕርዳታ ድርጅት የሚሰጠውን ዕርዳታ መጠንበ 1.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንዲቀንስ የወሰነው ውሳኔ ባለመነሣቱ ዓለም አቀፍ የልማት ዕርዳታ ድርጅት በጣም ድሃ ለሆኑ ኋላ ቀር አገሮች የሚሰጠውን ብድር 30 በመቶ እንዲቀንስ አስገድዶታል ።[35]

በካናዳ ቶሮንቶ ከተማ ተደርጎ በነበረው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ስብሰባ ላይ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የክሬዲት አሠራር ኢምፔሪያሊዝም ኋላቀር አገሮች በቀየሰው የፋይናንስ ስትራቴጂ ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት መሆኑ በገሃድ ሊታይ ችሉአል ። እነዚህ ሁለት የመንግሥታዊ ሞኖፖል የፋይናንስ ተቋሞች የባንክ ሞኖፖሎች በኋላቀር አገሮች ላይ የበለጠ የፋይናንስ ብዝበዛ ለማካሄድ እንዲችሉ አመቺ ሁኔታዎችን በማዘጋጀት ላይ ናቸው ። በመንግሥታዊና በግል ሞኖፖል የፋይናንስ እንቅስቃሴ መካከል የተፈጠረው ከምንጊዜም የቀረበ መደጋገፍና የገንዘብ ካፒታል በኋላቀር አገሮች ላይ ለሚያሳድረው ተፅዕኖ መሠረት ጥሉአል ።

ኋላ ቀር አገሮች በዓለም አቀፍ የካፒታሊስቱ የሥራ ክፍፍል ውስጥ የሚጫወቱትን ዝቅተኛ ሚና እንደተጠበቀ ለማቆየት የፋይናንስና የገንዘብ ግንኙነቶች ወሳኝ ዘዴዎች የሚሆኑትም ለዚሁ ነው ።

ሠንጠረዥ 1 — ኋላ ቀር አገሮች ከአውሮፓ የክሬዲት ገበያ የተበደሩት ብድር
(በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር)

ዓመት	ነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ የሚልኩ ኋላ ቀር አገሮች	ነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ የማይልኩ ኋላ ቀር አገሮች	የኢንዱስትሪ እድገታቸው በማሳየት ላይ የሚገኙ ታዳጊ አገሮች	በጣም ኋላ ቀር የሆኑ አገሮች
1971	0.43	0.55	0.44	—
1975	3.21	8.09	5.18	0.94
1976	4.39	11.13	7. 5	0.02
1977	7.01	11.28	6.18	0.05
1978	10.98	24.21	16.06	0.09
1979	8.99	26.35	18.46	0.19
1980	6.76	22.10	14.27	0.04
1981	11.69	33.07	26.60	—

ምንጭ — UNCTAD, hand book of International Trade and Development Statistics 1979, New York 1979, and sup plement 1980; World Bank, annual report 1981, Washington 1981, World Financial Markets 'Published by Morgan Guaranty Trust Co,/ New York, March 1982.

Digitized by Google

ሠንጠረዥ 2 — **የተወሰኑ ኋላ ቀር አገሮች ዕዳ** (የውጭ ዕዳ በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር)

ዓመት	ሜክሲኮ	ብራዚል	አርጀንቲና	ኢንዶኔዥያ	ፊሊፒንስ	ፔሩ
1970	3.2	3.2	1.9	2.4	0.6	0.9
1979	35.1	28.8	8.7	13.6	5.2	5.9
1980	61.3	50.1	27.5	17.0	11.0	8.5
1981	70.0	80.1[1]	32.0	n. a	15.8	9.0

የዕዳ አገልግሎት ክፍያ መጠኔ በመቶ (%)

1970	13.5	23.6	21.5	6.9	7.5	11.6
1979	34.6	64.1	15.5	13.4	12.6	22.3
1980	61.3	52.0	40.0	9.5	18.0	n. a
1981	64.5	63.0[2]		12.0	19.2	30.0

1. የ1982 የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት
2. የ1982 የቅድሚያ አሃዞች

ምንጭ — World Bank, World Development Report 1981, Washington 1981, Press Items.

ሠንጠረዥ 3 — **በአውሮፓ የክሬዲት ገበያ ውስጥ አበዳሪ ባንኮች** (እ.ኤ.አ. በ1981)

	ጠቅላላ የብድር መጠን (በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር)	የክሬዲት ቁጥሮች
Chase Manhattan	44.2	149
Citycorporation	38.1	143
Morgan Guaranty	31.0	81
Bank of America	26.0	111
Manufactures Hanorerust	24.5	119
National Westminster	22.6	89
Bank of Tokyo	21.0	131
Banque National De Paris	16.2	57
Bankers Trust	16.0	65
Sumitomo Bank	15.4	83

ምንጭ — Neue Zuricher Zeitung, Zurich, 14 January, 1982.

Digitized by Google

ሠንጠረዥ 4— የዓለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅት ክሬዲት/በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር/

	1974	1976	1978	1979	1980	1981
የተሰጡ ብድሮች	4.0	5.0	3.7	1.8	3.7	7.5

ምንጭ፡ International Monetary Fund, Annual Reports, Washington 1980, International Financial Statistics, Year Book 1981 and man 1982, Washington.

ሠንጠረዥ 5 — በዓለም ባንክ የተሰጠ የክሬዲት /ዓለምዓቀፍ የልማት እርዳታ ማኅበር/ /በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር/

	1974	1976	1978	1979	1980	1981
ቅድሚያ ስምምነቶች	4.2	6.5	8.3	9.9	11.4	12.2
የተከፈሉ ክሬዲቶች	2.2	3.6	3.7	4.8	5.7	6.8

ምንጭ ፡ World Bank, Annual Reports, Washington.

የግርጌ ማስታወሻ

1. See also K. Kolloch/W. Luchterhand, Widerspruche zwischen Entwicklungslandern und imperialistischen Staaten in den internationalen Kredit — und Wahrungsbeziehungen (Contradictions between developing and imperialist countries with regard to the international credit and monetary relations), in: IPW-Berichte, Berlin, 4/1980, p. 37 et seq.
2. UNCTAD, Handbook of International Trade and Development Statistics 1979, New York 1979, p. 454; *Ibid.*, Supplement 1980, p. 525; Der Tagesspiegel, West Berlin, 30 May 1982.
3. UNCTAD, TD/B/897, Annex, 10 March 1982, p. 1.
4. See also F. J. Trouvain, Langerfristige Aspekte der Auslandsverschuldung der Entwicklungslander (Long-term aspects of the foreign indebtedness of the developing countries), in: Aussenwirtschaft, Zurich, IV/1981, p. 330; Frankfurter Rundschau, Frankfurt (Main), 6 August 1982.
5. V.I. Lenin, Collected Works, p. 673.

Digitized by Google

6. See also: H. Mayrzedt, Mittel — und langfristige verschuldungsprobleme der Entwicklungslander — wie weiter? (The developing countries' medium — and long-term debt problems — what about their future?), in: Aussenwirtschaft, IV/1981, p. 308.

7. UNCTAD, Trade and Development Report 1981, Geneva 1981, Annex A, p. 15.

8. FrankfurterRundschau, 6 August 1982.

9. See: L. Chudyakova, Trasnational Banks and Developing Countries, in: Mirovaya economica i mezhdunarodnava otnosheniya (MEMO), Moscow 4/1982, p. 132.

10. Calculated from: UNCTAD, Handbook..., Loc. Cit., pp. 250-325.

11. See olso: Transnational Corporations in World Development, a Re-Examination, New York 1978, p. 215.

12. See: L. Chudyakova, Loc. p. 134.

13. See also: Euromoney, London, December 1981, p. 21.

14. Frankfurter Rundschau, 4 February 1982.

15. Frankfurter Allgemeine, Frankfurt (Main), 21 August 1982.

16. AFP on 29 August 1982.

17. Neue Zurcher Zeitung, Zurich, 14 January 1982.

18. Frankfurter Rundschau, 4 February 1982.

19. Die Welt, Bonn, 9 September 1982.

20. See also: E. Kolloch, Loc. Cit., p. 46.

21. See also: National Herald, New Delhi, 2 December 1981.

22. See also: Blick durch die Wirtschaft, Frankfurt (Main), 23 July, 1982.

23. Financial Times, London, 20, April 1982.

24. Team of Authors, Anatomie der Wahrungswiderspruchs (An analysis of monetary contradictions), in: Probleme des Friedens und des Sozialismus, Berlin, 7/1981, p. 968.

25. R. Tetzlaff, Die Weltbank: Machtinstrument der USA oder Hilfe fur die Entwicklungslander? (The World Bank: a power instrument of the USA or aid to the developing countries?), Munich — London 1980, p. 254.

26. See also: IMF Survey, Washington, 5/1982, p. 67.

27. Die Zeit, Hamburg, 21 May 1982.

28. A.W. Clausen, The World Bank and Remarks to the International Monetary Conference, Vancouver, 25, May 1982, p. 8.

29. *Ibid.*, p. 12; Handelsblatt, Dusseldorf, 7 September, 1982.

30. See also: Th. Friendlander, Imperialistischer Kapitolexportin die Entwicklungslander (Imperialist capital export to the developing countries). IPW-Forschungshefte, Berlin, 4/1981, p. 100 et seq.

31. Frankfurter Allgemeine, 25, August 1982.

32. World Bank, Annual Report 1981, Washington 1981, p. 70.

33. R. Tetzlaff, Loc. Cit., p. 220.

34. Handelsblatt, 6, September 1982.

35. See also: E. Kolloch, Jahrestagung des Internationalen Wahrungsfonds und der Weltbank im Zeichen der US-meeting of the Internationall52gDol amerikanischen Hegemoniepolitik (Annual meeting of the International Monetary Fund and the World Bank in the light of the US-American hegemonistic policy), in: IPW-Berichte, 1/1982, p. 32 et seq.

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 071 108 943
Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

B.S.P.P

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

B.S.P.P

Digitized by Google